አበሻው



ደራሲ፡- ጆን ኩሪለተ-ጥ ሩፈን

ተርጓሚ፡- አያሌው ምንተ-ብሩ

አንደኛ እትም ነሐሴ 2003 ዓ.ም.

የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው።
© All Rights Resereved

አበሻው

ደራሲው:- ጆን ክሪስቶፍ ሩፊን

ተርጓሚ:- አያሌው ምትኩ ብሩ

1999 ዓ. ም.

I

ከሞት የተረፈው ሰው ትዕዛዝ

1

በሱዊስ አሥራ አራተኛ የዘይት ቀለም ቅብ ሥዕል የግራ ጉንጭ ላይ፣ በአስፊሪ ግርማ ሞገስ ለፍቶ በተመልካች ዐይን ውስጥ የሚገባ የተሸራረፈ ጥቁር ጠብታ ታይታያል። በሦሥራቁ ዓለም ውስጥ የዘይት ቀለም ቅቦችን እንደቁምጥና በሽታ እየሸራረፈ በመብላት መልካቸውን የሚያበላሽው ነገር፣ ቀስ በቀስ በዚህ ሥዕል ውስጥ በየዕለቱ እየተስፋፋ ነው። የነገ ቡኒ ሽበ የመሰለ፣ ጉልህነት የሌለው አስጠሊታ መስመርም ወደ ጀሮ ግንዱ አቅጣጫ እየተጓበ መሆኑ ይታያል። ቀረብ ብሎ ለሚመረምር ሰው፣ በስዕሉ አካል ላይ ጥቁር አክሰል በተጨማሪ ይመስከታል። በአግር ጣቶቹ ላይ ካሉት ነጠብጣቦች ሌላ፣ የቀረው ሁሉ ሦሚሰቀጥጥ ነው። በአጭሩ የፀሀዩ ንጉሥ ሥዕል ክፉኛ ተበላሽቷል።

ይህ ሥዕል፣ ካይሮ በሚገኘው የፈረንሣይ ቆንሲል መሥሪያ ቤት ላለፉት ሦስት ዓመቶች ተሰቅሎ ቆይቷል። ሥዕሉ ሲሰራ የራሱ የንጉሡ ግላዊ ቁጥጥርና እይታ አልተለየውም ነበር። ሥዕሉን በመጀመሪያ የሣለው ሂያንዝ ሪጋድ ሲሆን ስፍራውም ፖሪስ በሚገኝ የሥዕል ሥራ ቦታ ውስጥ ነበር። ከዚያም በባህር ወደ ካይሮ ይላካል። እንደመጥፎ ሰድል ሆኖ ካይሮ ውስጥም ይሁን በቅርብ ርቀት በሚገኙ የምሥራቅ ሚዲትራኒያን ጣቢያዎች ሊገኝ የሚችል ታዋቂ ሠዓሊ የለም። በዚህ የተነሣ ቆንሲሉ ሙሴ ዴ ማይሌ፣ በማያስደስቱ ሁለት እኩል ምርጫዎች መካከል ውሣኔ ማድረግ ነበረበት። አንደኛው መጥፎ ምርጫ ይህ በንጉሡ ሥዕል ላይ የሚታየው አስቀያሚ ጠባሣ፣ ሕዝብ እያየው እንዲኖር በመሥሪያ ቤቱ ሕንፃ የእንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ ተሰቅሎ እንዲቆይ መፍቀድ ነው። ሁለተኛው የማያስደስት አማራጭ ደግሞ፣ ብቁ ሙያ ለሌላቸው እጆች ምስጢሩን ገልጾ መስጠትና ሥዕሉ ፍፁም እንዲበላሽ የማድረግ ዕድል ነው። እንዲህ አጣብቂኝ ውስጥ የከተተውን ምርጫ ቁርጥ ያለ ውሣኔ ሰጥቶ ከመደመደሙ በፊት ዲፕሎማቱ ሙሴ ማይሌ፣ ጉዳዩን እያብላላው ሰሦስት ወራት አቆየው።

ከሦስት ወራት በኋላ የጥገና ሥራውን ለማከናወን ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ካይሮ ውስጥ የሚኖር አንድ መድሣኒት ቀማሚ ግለሰብን መረጠ። ሰውዬው፣ በወቅቱ ካይሮ ውስጥ ከሚኖሩ ፈረንሣዊ ዝርያ ካላቸው መካከል ሲሆን፣ በአየር ጠባይ ምክንያት የተበላሹ የሸራ ላይ ሥዕሎችን የማደስ ችሎታ አለው ተብሎ የሚነገርለት ነው። ግለሰቡ፣ ረዥምና ጉብጥ ያለ ነው። ፊቱ ጥቅጥቅ ባለው በጥቁር ንብስማ ጢሙ ሣቢያ ወደ ዓይኖቹ ሰርጉድ ብሎ የገባ ይመስላል። የራሱ ፀጉሩ ድብን ብሎ የተጠመዘዘ ጥቅል ይመስላል። ግዙፉን ሰውነቱን በተሸከሙት ረዣዥም ቅልጥሞቹ ሲራመድ፣ ያስጠላል። ይህ ሰው በሥራው ላይ በሚሆንበት ጊዜ ግን የሰውነት እንቅስቃሴው ፍፁም የተስተካከለ ነው። ሌሎች ለምች ሜትር ዝረሚ በሚባለው ስም ያውቁታል። ሜትር ዝረሚ ታማኝ ዜጋ የመሆኑ ዝና ይነገርለታል። ቆንሲል ዴ ማይሌ፣ የንጉሡን መልክ ለአንድ አክራሪ ፕሮቴስታንት አደራ በማለት የመስጠቱ ሃሣብ አልተዋጠለትም። ምክንያቱም ሰውዬው፣ በአንድ በሆነ ሰዓት ላይ የተስፋ መቁረጥ መከራ ሊፈፅም ይችላል። እንዲህ ያለው ባህርይ ደግሞ ቅጥ አምባሩ በጠፋው የካይሮ የውጭ እገር ማህበረሰብ መካከል ብርቅ አይደለም። ነገር ግን ፣ ሙሴ ዴ ማይሌ ሌላ ምርጫ አልነበረውም።

ሜትር ዝረሚ የሥዕሉን ሁኔታ ከተመለከተ በኋላ፣ የማይሱ ሥራ አሥር ቀናት እንደሚፈጅበት ገለፀ። በማግስቱ ከአንድ ኑቢያዊ አገልጋይ ጋር ሰባት ጫማ ከፍታ ባለው የሥራ ክፍል ውስጥ ገባ። ኑቢያዊው ባሪያ፣ ለመድሃኒት መቀመሚያነት የሚውል የእበባ ዘይትና ጥሩ ጠረን የሌለውን የቀለም ማቅጠኛ ቅመም እያደባለቀ እንዲበጠጥለት ተብሎ ከቆንሲሉ ቤት የመጣ ረዳት ነው። እንዲታደስ በተባለው ሥዕል ላይ የአዳሽ ባለሙያ እጅ ባረፈበት ቁጥር በቦታው መገኘት እንዳለበት ቆንሲል ሙሴ ማይሌ፣ አበክሮ ተናግሯል። ከንጋቱ አሥራ አንድ ሰዓት ሲሆንና የቀለም ቅይጡ ተዘጋጅቶ ሲያበቃ አገልጋዮች ቆንሲል ዴ ማይሌን ይጠሩታል። የተበጠበጠው ቀለም የሚያነሳግለው በትኩስነቱ ነው። ሙሴ ማይሌ፣ የሥዕሉን እድሣት በቅርብ ለመቆጣጠር በጅማሮው ሰዓት ላይ ይገኛል። ሙሴ ማይሌ፣ የሥዕሉ እድሣት ገና ሲጀመር በጨርቅ ላይ የተንጠባጠበና በትልሀ የሚታይ ሀምራዊ ቀለም ሲመለከት መተቸት ይጀምራል። በጅማሮው ላይ የቀለሙ ወዝ ገና ሣይቀዘቅዝ ሥራው በጣም የሚያበረታታ ነው። ቀለማቱም ሣይበዙ ቁልጭ ብለው ይወጣሉ። በሸራው ላይ በጊዜ ምክንያት የተፈጠሩ እጥፋቶችም ሙሉ በሙሉ ይወገዳሉ። ይህን ሁሉ ሲመለከት ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ተሰፋው ይለመልማል። ነገር ግን ሜትር ዝረሚ የቀለም ብሩሹን ወደንቡሡ ሥዕል ባቀረበ ቁጥር፣ በጥርስ ሣኪም ወንበር ላይ ተቀምጦ መቆንጠጫ ጉጠቱን በተመለከተ ቁጥር እየተሣቀቀ እንደሚያፋሽግ ሕመምተኛ በማከታተል ያዛጋል። በዚህ ሣቢያ ሥራው ብዙ ጊዜ ይቋረጣል።

በመጨረሻው ላይ የንጉሡን ጉንጭ መዝምዞት የነበረው ነቀርሣ የሚታደስበት ሰዓት ደረሰ። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ቀለል ያለ ነጭ ጋዋኑን ለብሶ በሥዕሉ ፊት እንዲደረግለት ባዘዘው አነስተኛ አግዳሚ ላይ በጭንቀት ተቀምጧል። ባለቤቱ፣ የባሏን እጅት በጡቶቹዋ ላይ ጫን አድርጋ ከአጠገቡ ተቀምጣለች። ሁለቱ ጥንዶች እንደዚያ ተቀምጠው ሲታዩ እጅግ የሚወዳት ሰው ሲሰቀል በጭንቀት እንደሚመለከት የቤተሰብ ቡድን፣ ሽቅብ እየተቁለጨለጨ የሚመለከቱት ይመስላሉ። በወርሃ ግንቦት ከሰዓት በኋላ በሚኖረው አጋማሽ ጊዜ ላይ፣ ከኑቢያ በረሃ የተነሣው ሞቃታማ ነፋስ ከተማዋን ለሦስት ቀናት በደረቅ ሙቀት እያነፈራት ነው። ሜትር ዝረሚ፣ የተደፋ ጀልባ የመሰለ ቆብ ጭንቅላቱ ላይ ካጠለቀ በኋላ አገልጋዩ የማለስለሻ ብሩሽ አቀበለው። ዝረሚ፣ ብሩሹን በባሰግርማ ሞገሱ የንጉሡ ፊት ላይ አነጣጠረ። ይህን ጊዜ ሙሴ ዴ ማይሌ ከአግዳሚው ላይ ብድግ አለ።

«ቆይ!»

መድሃኒት ቀማሚው በመደነቅ ቆመ።

«ይህን ለመሥራት ሙሉ በሙሉ እርግጠኛነቱ . . . ?»

«አዎን፣ ክቡር ሆይ»

ሜትር ዝረሚ በፊቱ ላይ የታየበትን ሁኔታ የሚመስል ስሜት አንፀባረቀ። ቁጣውና ግልፍተኛነቱን ሊያውጣው ሲል አንደምንም ብሎ ራሱን ገታ። ይህ ጥረቱ ግን በፊቱ ላይ ይታወቅበት ነበር። የማጉረምረም ትንፋሽ ሊወጣው፣ በጣም የፈላ የማንቆርቆሪያ ውሃ የሚያሰማው ዓይነት ቀጭን ፉጨት ወጣው። ይህም ቢሆን ፈገድቶ አሳፈተለስም። እጅግ ቢበሣጭም ቀማሚው በጨዋ ትዕግስት አማራሞቱን ገለፀ።

«አሁን ለማድረግ የምከርኩት የላይኛውን ክፍል በስሱ ነካ ለማድረግ ነው። በሩሹ ሸራውን ሰዓመል ያህል መንካቱን ሊያስተውሱ ይችላሉ፣ ክቡር ሆይ» ሲል ቀማሚው ገለፀ።

ሥራውን የመወሰን መብት ለሜትር ዝረሚ ተትቶለት ቢሆን ኖሮ፣ የሉዊስ አሥራ አራተኛን አፍንጫ በደማቅ ቀይ ቀለም ሁለት እጥፍ ያሳድገው ነበር። ጀርምቹንም ከአርቲፊሻል ፀጉሩ ጋር የተጫጫሩ የውሻ ጀርምች ያስመስላቸው ነበር። እንደፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች እርሱና መላው ቤተሰቡ በዚህ ንጉሥ እጅ ሥቃይ ደርሶባቸዋል። እርሱንም ቢሆን ሌሎች ሊገነዘቡት ከሚችሉት በላቀ መልክ በድሎታል። የዕለቱ ፕሮግራም ያለአንዳች ከንሞኔ ቢጠናቀቅም ሁሉንም ሥራ ገሃነም ይግባ ለማለት ሜትር ዝረሚ ለመጀመሪያ ጊዜ ለራሱ ቃል ገብቶ ነበር።

ቆንሲሉ፣ በዚህ ሥዕል አዳሽ ብሩህ እይታ ውስጥ ምናልባት ሊመለከት የቻለው ታላቅ ነገር ስላለ ይመስላል አግዳሚው ወንበር ላይ ተመልሶ ዘጭ ካለ በኋላ «ማድረግ ካለብህ እንግዲያው ቀጥል» ሲል ተናገረ።

ዝረሚ የሁለቱንም እጆቹን ጣቶች በጥርሶቹ መሃል ነክሶ ዐይኖቹን ጭፍን አደረጋቸው።

በዚያው ቅፅበት ከባድ የማንኪኒት ድምፅ በበሩ መዝጊያ ላይ ሁለት ጊዜ ተሰማ። ሠዓሊው ወደኋላው ፈቅ አለ። ሉዳናዊው አገልጋይ ትላልቅ ዐይኖቹን ወደ ሰማይ አቀናቸው። ሙሴ ዴ ማይሌ በስሜት የቀሉትን አይኖቹን በለጠጣቸው። ሥጋትና ጭንቀት የተሞላው ወጥታ በክፍሉ ውስጥ ነገሠ።

በደጋሚ ሦስት ማንኪኒቶች በበሩ ላይ ተሰሙ። አነዚህኞቹ ምቶች ከቅድሙ ይልቅ ከበድ ያሉ ናቸው። ሥዕሉ በሚታደስበት ጊዜ ፊዕሞ ሁከት እንዳይሰማቸው በግልዕና በተደጋጋሚ ቆንሲሉ ራሱ የሰጠውን ጠንካራ መመሪያ ጥሶ ወደ አዳራሹና ወደ ቢሮው የሚያመራውን ትልቁን በር እንዲህ ለማንኪኒት ነፃነቱን የወሰደው ሰው የሚያጠራጥር አይደለም። ዲፕሎማቱ፣ የሰበሰው ጋዋን በሚገባ መቆሰፉን ካረጋገጠ በኋላ ፈጠን ብሎ ዘመራመድ በሩን በርግዶ ከፈተው። በበሩ ፊት ሙሴ ማቹ ቆሟል። በአለቃው የቁጣ አተያይ ሣቢያ ፈጠን ብሎ ከወገቡ ጉንበስ በማለት ታዛዥነቱን ለመግለፅ ሞከረ።

«የጃኒሣሪዎች አጋ ለክቡርነትዎ መልዕክት ልከዋል። አበክረው እንዳስገነዘቡት ከሆነ ጉዳዩ ያልተለመደና አስቸኳይ ነው። በምንም ዓይነት ሁኔታ በዚህ ሥራ ላይ ባሉበት ጊዜ እንዳይረበሹ የሰጡትን ትዕዛዝ መዘንጋት ባይኖርብኝም፣ ሊዘገይ ለማይችል ጉዳይ ቱርኮች የተለየ አገላለፅ ስላላቸው መመሪያዎን ችላ አልኩ።»

ማቹ፣ ፖሪስ ከሚገኘው የምሥራቃውያን ቋንቋዎች ትምህርት ቤት የተመረቀ ሰው ነው። ስለዚህም «የቋንቋ ሰው» በመባል ይታወቃል። የዚህ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ዲፕሎማቸውን ከተቀበሉ በኋላ፣ ዲፕሎማት ከመሆናቸው በፊት ወደ አንድ ኤምባሲ ይላካሉ። ሙሴ ማቹም ያጋጠመው ይኸው ነው። ዋናው ቆንሲል፣ ሰወጣቱ ማቹ የተሰየ አመለካከት አለው። ማቹ፣ ዋናውን ቆንሲል ሊያረካው በሚችል መልክ ደረጃውንና አቅሙን የሚያውቅ ሰው ነው። ሙሴ ማቹ፣ ከጨዋ ቤተሰብ በመወለዱ ሳይሆን በሚያጋጥሙት ጥያቄዎች ሁሉ ላይ የራሱን ገደብና ብልህነቱንም የሚያሣይ ሰው ነው።

«ለመሆኑ አንዳች ደብዳቤ አለ?»

«የለም ክቡር ሆይ። የአጋው መልዕክተኛ ከፈረሱ ላይ እንኳን ሳይወርድ ነው ጌታው፣እርስዎን በቤታቸው ሆነው እየጠበቁዎት መሆናቸውን ብቻ የነገረን።»

«እና እነዚህ ውሾች፣ ስብሰባ እየጠሩኝ መሆኑ ነው፣ አይደል? ለዚህ ጥሩና በቂ ምክንያት ሊኖራቸው እንደሚችል ተስፋ አደርጋለሁ። ይህም ካልሆነ፣ ፓሻው ራሱ ስለሁኔታው መስማቱ አይቀርም» ሲል ድምፁን ዝቅ አድርጎ ሙሴ ማይሌ ተናገረ።

ሙሴ ማቼ፣ በተረከዙ እንደመሽከርከር ብሎ፣ ከቆንሲሉ ጋር ትከሻ ለትከሻ ለመነካካት በሚያስችለው ቅርበት ተጠጋው። ሁለቱ ሰዎች በክፍሉ ውስጥ ለነበሩት ሰዎች ጀርባቸውን ሰጥተው ቆሙ። ወጣቱ ማቼ፣ የመንግስትን ምስጢር በአደባባይ እንደሚያወጅ ዓይነት በማንሾካሾክ ተናገረ። እንዲህ ያለው የዲፕሎማቶች ሥራ የመልካም ሥርዓት መገለጫ ቢመስልም የማታለያ ስለሆነ ሲሰመጽ ተጨማሪ ባህርይ ይሆናል። በዚህ አጉል ባህርይ ቅር በመሰኘት ሚትር ዝረሚ ትከሻውን ሰበቀ።

«አጋው፣ ክቡርነትዎ በፈለጉት ጊዜ ሊጠቀሙበት የሚችሉትን አንድ ፈረንሣዊ ሰው ተናንት ካይሮ ከተማ ውስጥ አስረዋል» ሲል ሙሴ ማቼ አንሾካሾከ።

«ታዲያ ይህም ምክንያት ሆኖ ሥራችንን ማወክና ማቋረጥ አለበት?, ዕድል ፈንታቸውን ለመሞከር ወደዚህ ከሚመጡት አሣዛኝ ምስኪኖች መካከል በየሣምንቱ አንዱን ይይዛሉና፣ ሥራ ያስፈቱናል? ቢሆንስ እኔን ምን የሚመለከተኝ ነው?»

«ብቻ... » በማለት ሙሴ ዴ ማቼ፣ ከበፊቱም ይልቅ በጣም ዝቅ ባለ ድምፅ አጉረመረመ። ቆንሲሉ የሙሴ ዴ ማቼን ንግግር ለመለየት የከንፈሮቹን እንቅስቃሴ መከታተልና ማንበብ ነበረበት። «ሰውዬው ማንም ተራ አስረኛ አይደለም። እንዲያውም አስቸኩን የምንጠብቀው የንጉሡ መልዕክተኛ ነው» ሲል ተናገረ።

ሙሴ ዴ ማይሌ የድንጋጤ ድምፅ አሰማ።

«እንዲህ ነው እንዴ? ጌቶቼ! እንግዲያውማ ጊዜ ማጥፋት የለብንም። የዛሬው ፕሮግራማችን እዚህ ላይ ያበቃል» ሲል ሚትር ዝረሚ እንዲሰማው በማሰብ ጮሳ ባለ ድምፅ ተናገረ

ቆንሲሉ፣ ከፍሱን ለቅቆ ሲወጣ የተደበላለቀ ስሜት በፊቱ ላይ ይነበብበት ነበር። የክብርና ያለመደሰት ስሜቶች ይታዩበት ነበር። በውስጣዊ ስሜቱ ግን ሲገዋመው ከሚችለው ሥቃይ የሚገላግለው ማንኛውም ነገር ቢሆን የተሻለ እንደሆነ እርግጠኛ ነበር።

ሚትር ዝረሚ፣ ከወጣቱ አገልጋይ ጋር በመሆን እየማለና እየተገዘተ የሥዕል ቡሩሹን ወደ ብልቃጡ ውስጥ ወረወረው። በዚህን ጊዜ ለንጉሡ የሥዕል ጉንጭ ሲባል ከተዘጋጀው ውድ ሣምራዊ ቀለም ውስጥ ብዙ ፍንጥቅጣቂዎች በጥቁሩ ልጅ ጥቁር ግንባር ላይ ተረጨበት።

በዚያን ዘመን፣ ጥሩ ገስጋሽ የካይሮን ከተማ በሰዓት ሰዓታት ውስጥ መዞር ይችላል። ከተማዋ ገና ትንሽ ብትሆንም፣ አገር ጐብኚዎች ግን በደምግሣው አስቀያሚ፣ ጮስቋላና የማትማርክ የሚሏት ነበረች።ጠባቦቹን መንገዶችዋን ተከትሎ ወደ ከተማዋ እምብርት ዘልቆ

የሚገባ ሰው እይታውን የሚጋርድበት ባለሁለት ፎቅ ድርድሮች ይገጥሙታል። በጮዳናዎቹ አናት ላይ እንግዳ ተንገሮችን የሚያስፈሩ ባለቀይ ቀለም ሹል ቅጠሎች ካሉዋቸው ረዣዥም ቅርንጫፎች በስተቀር የተጊያጊያጠ ነገር አይታይም። በከተማዋ ውስጥ ጮሳ ብለው የሚታዩት ሕንፃዎች የቤዮች ቤተመንግስት፣ በአንድ አቅጣጫ ወደሩማይላ አደባባይ ሲል ክፍት ከሆነው የፈርአኖች መኖሪያ ከነበረው ግንብና ከብዙ መስጊዶች በስተቀር የለም። በዚህ ምስቅልቅል ውስጥ ሁሉም ነገር ለዓይን አይሞላም። ከተማዋ ውበትን ሁሉ ገፍትራ ስሜት የማትሰጠ ናት። ደስታና ፍቅርም ከአናጆቹ የሕንፃ ግድግዳዎችዋና ከጥቋቁሮቹ የመግቢያ በሮችዋ በስተጀርባ የቀሩ ይመስላል። ከአጮራብች የባሳገር መንደሮች የሚመጡ ነጋዴዎች በስተቀር በሞና ዋና ጮዳናዎችዋ ውስጥ የሚዘዋወሩ ሰዎች ጥቂቶች ናቸው።

እንግዳ ሰው፣ በካይሮ ነባር ሰፈሮች ውስጥ እምብዛም ደፍር አይጓዝም። በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ በአቶማን ቱርክ፣ ሡልጣን በነበረው በካየር አድ ዲን ባርባሮሣና በፈረንሣይ መካከል ስምምነት ተደርሷል። ይህ ስምምነት ከድል በኋላ የተደረገ ነበር። በስምምነቱ መሠረት አውሮፖውያን በነፃነት የመነገድና የተወሰኑ መብቶችን አግኝተዋል። ይሁን እንጂ ክርስቲያኖች ስጋት እንደገባቸው ይኖራሉ። በሴላ በኩል ግብሣውያኑ ባለማቋረጥ እርስ በርሣቸው እንደተጣሉ ናቸው። ስምምነቱና ግቡቡነቱ የተገላቢጦሽ ካልሆነ በስተቀር፣ ፓሻው በራሱ ታጣቂ ሚሊሺያዎች ወደመቃብሩ ይወርዳል። የክብር ዘበኞች ከአገረ ገዥዎች ጋር ፀበኞች ናቸው። አገረ ገዥዎች ከኢማሞች ጋር አይስማሙም። ኢማሞች ከፓሻዎች ጋር አይጣጣሙም። በዚህ ስምምነት ሳቢያ ፈረንሣውያን ነፃ ቢሆኑም በተቻለ መጠን ከተወሰነላቸው አካባቢ እንዳይርቁ አጥብቀው ይጠነቀቃሉ።

በዚያን እለት፣ ያ ወጣት በዝዚያ ጠባብ የካይሮ ጮዳናዎች እንደዚያ ተዝናንቶ የመጓዙ ነገር በጣም የሚገርም ነበር። ወጣቱ፣ ከአንድ ተራ የአረብ ቤት ሲወጣ ደካማውን የማንቃ በር ወደ ኋላው ወርውሮ በመዝጋት ነበር ወደ ጮዳናው ውስጥ የገባው። መውጫውና መግቢያው በሚይታወቀው በካይሮ ውስብስብ ጮዳና ውስጥ አቅጣጫውን ይዞ ሲጓዝ እንደአገሬው ሰው ሣያጣደፍ ነው። ይህም ሆኖ ፈረንሳዊነቱ በግልፅ ያስታውቃል። እርሱም ቢሆን ባዕድነቱን ለመደበቅ አልተጨነቀም። ከማለዳው ጀምሮ ከሃምሲን ተብሎ የሚጠራው ነፋስ፣ የአሸዋ አቧራ ትንፋሹን ከበረሃው ወደ ከተማው ይረጫል። ወጣቱ ኩሌታው ክፍት የሆነ ከናይለንና ከጥጥ ቅያሳ የተሠራ ቀሳል ሽሚዝ ለብሷል። ሱሪውም ከጥጥ ፊኔርቅ የተሠራ ጥብሁለት ሆኖ ንብድና በቀሳሱ የሚተጣጠፍ ጫማ ተጫምታል። በጭንቅላቱ ላይ ግን ምንም አላደረገም። የባህር ሃይል የሱፍ ጃኬቱን በክንዱ ላይ አንጠልጥሏል። እየተንዘ ግለ፣ ከሐሰን መስጊድ ፊት ለፊት ሁለት አረቦች መንገድ እያቋረጡ ገጠሙት። ወዳጅነትና ፈገግታ የተሞላበት ሠላምታ ሰጠት። እርሱም አፀፋውን በአረብኛ ቋንቋ በአንድ ቃል መልሶላቸው መንገዱን ቀጠለ። ይህ ሙሳት ቱርክዊ ባለመሆኑ በምንም መልኩ ባለሥልጣን አይደለም። ነገር ግን በከተማው ውስጥ የሚኖር እያንዳንዱ ሰው፣ ይህ ወጣት፣ ጆን ባፕቲስት ፖንሴ የሚባል መሆኑንና በፓሻው ጠንካራ የመኖሪያ ምሽግ ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ እንዳለው ያውቃል።

ጆን ባፕቲስት ፖንሴ ጥሰቅ ያለ፣ ወንዳ ወንድና ጠንካራ ሰውነት ያለው ነው። ቁመናው መለሎ፣ ደረቱ ሰፊና ጫንቃውም ደንደሣም ነው። ይህን እርሱም ያውቃል። እንዲያውም በዚህ ቁመናው ሳቢያ የአርባ ቀን ዕድሉ ለምን በፀሃዩ ንጉሥ አጠገብ ለጀልባቸው ቀዛፊነት እንዲመለመል እንዳላደረገው ራሱን ይጠይቃል። የራስ ቅሉ በጠንካራው ደንደሱ ላይ በማያሰመት ሁኔታ የተተከለና ረዘም ብሎ ጥሩ ቅርፅ ያለው ነው። የፊቱ ገፅታም ቢሆን

ስለሰለስ ያለና ወጣትነት የሚታይበት ነው። ጥቁሩ የራስ ወገሩ ፊቱን እንደክፈፍ ይከበዋል። ዛጉልማ ዓይኖቹ ከመሀል ሆነው ብርሃን የሚፈልቅባቸው ይመስላሉ። ነገር ግን የፊቱ ገፅታ ተስተካክሎ ያልተሰራ መሆኑን ማስተዋል አያቅትም። የአንደኛው አገጩ አጥንት ከሌላኛው ይልቅ በመጠኑ ከፍ ያለ ነው። የዓይኖቹ አቀማመጥ ለማስደንገጥ ሲባል የተቀመጡ ይመስላሉ። በዚህም ለአተያዩ ግርማ ይሰጡታል። እነዚህ ወጥነት የሌላቸው ቅርጾቹ በዚያ ቁመናው ላይ አንዳች ምስጢራዊ ሃይል ያለው ያስመስሉታል።

በግንቦት ወር ላይ ሃያ ስምንተኛ ዓመቱን የሚይዘው ጆን ባፕቲስት ፖንሴ፣ ካይሮ በቆየባቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ እጅግ በጣም የታወቀ ሃኪም ሆኗል።

በጐዳናው መሃል ሲጓዝ፣ በአጁ የያዛትን አንዲት ትንሽ ሣጥን ወደ ፊትና ወደ ኋላ ያወዛውዛታል። ሣጥኗ፣ በሽርከኛው ርዳታ ራሱ ቀምሞ ባዘጋጃቸው ልዩ ልዩ መድሃኒቶች የተሞላች ነች። በሣጥኗ ውስጥ ያሉት የመድሃኒት ብልቃጦች ርስበርሣቸው ሲጋጋ የታፈነ ቅጭልጭልታ ያሰማሉ። የእርምጃውን እንቅስቃሴ ተከትለው ከነዚያ የመስታወት ብልቃጦች ወጥተው እንዲሰሙ በሚያደርጋቸው ዜማዊ ቅጭልጭልታዎች፣ ወጣቱ ፖንሴ ደስተኛ ነው። ምንም እንኳ ከየመስኩቶቻቸው መጋረጃና ከእንጨት ርብራብ ሣንቃዎቻቸው ጀርባ ተከልለው የሚከታተሉት ሰዎች እንዳሉ ቢያውቅም፣ በዚህ ሣይረበሽ በፈገግታና በሰላማዊ ስሜት ወደፊት እየተመለከተ ይራመዳል። ከነዚህ ቤቶች መካከል ብዙዎቹን ያውቃቸዋል። በብዙዎቹ ቤቶች ውስጥ የህክምና አገልግሎቱን ሰጥቷል፣ ወይም ለሻይና ለእራት ግብዣ ተጠርቶ ተስተናግዶባቸዋል። የከተማዋን ሰፊ አካል ጥቂት፣ የትንሹን አካልዋን ደግሞ ብዙ ሚስጥሮችን በሚገባ ያውቃል። አጠቃላይ ነገሮችን ለማወቅ ባለው ከፍተኛ ጉጉት የተነሣ ቡተለይም የወሲብ ፍላጐት ስሜትና ሴራ፣ በጨለማው ውስጥ የሚነሣሱበትንና የሚነግሰብትን የሴቶች ጉዳይ ያውቃል። እንዲህ ያሉ ጉዳዮችን በፍቅር ስሜትም ይሁን በግብዝነት ሣይደነቅ የተቀበላቸው ናቸው። በውስጣቸውም ጭልጥ ብሎ በመግባቱ ወይም የርሱ ባህርይ ስለሆነ ያለይሉኝታ ቀጥሎባቸዋል። ድርጊቱ ሁሉ አገርና አካባቢን የማያውቅ፣ የሚቃብዝ እንሰሳ የሚያደርገው ይመስላል። እንዲህ ባለ ተንከራታች እንሰሳ ላይ የብዙ ሺህ ስልጡን አዳኞች አይኖች፣ እያንዳንዷን እንቅስቃሴውንና ዱካውን እንደማከታተሉ ያውቃል። ይህም ሆኖ ቀጥሎባቸዋል።

ጉዞውን በመቀጠል በአንድ የሸቶ ሱቅ አጠገብ አልፎ በመጨረሻው ክሣሊኛ ወይም የካይሮ ቦይ በተባለው ጻርቻ ደረሰ። የትንሿን ምንጭ የፍሰት አቅጣጫ ተከትሎ ለጥቂት ጊዜ ሽቅብ ተንዘ። ይህ ቦታ በዚህ ወቅት ደረቅ ነው። ማዕበል ሲጀምር ግን ሊያነፍር የሚችል ሃያል ትንፋሽን ይለቀዋል። ፖንሴ፣ በዝግታ ተጠማገዘ ድልድዩን ለማቋረጥ ተንዘ። ቦታው ሁልጊዜም በሰዎች እንደተሞላ ነው። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ አንድም በአካባቢው ያሉት ሱቆችና ቤቶች ድልድዩን ተከትለው የተሰሩ ስለሆነ ነው። ሌላው ምክንያት ደግሞ በአርጌው ካይሮና በአረቦች መኖሪያ መካከል ያለው ብቸኛው መተላለፊያ መስመር ይኸው በመሆኑ ነው። በዚህ ዕለት ግን የሕዝቡ ብዛት ከወትሮው እጅግ ይልቃል። ጆን ባፕቲስት ፖንሴ በመከራ እየተጋፋ ይጓዛል። ድልድዩ መካከል ሲደርስ ግን፣ አንዳች ያልተለመደ ክስተት አንዳለ ተገነዘበ። ከቤቶቹ መካከል ከአንዱ ውስጥ ወፍራም ጥቁር ደመና እየተግተለተለ ይወጣል። እሣቱ፣ ከአንድ የጨርቃ ጨርቅ ነጋዴ ሱቅ ውስጥ የነበረ የሸክላ ምድጃ ሲደፋ፣ የተያያዘው ከሰል በመረጨቱ እንደተቀጣጠለ ሲያወሩ ሰማ። ብዛት ያላቸው ግብፃውያን በቅርባቸው ከሚገኝ የጉድጓድ ውሃ በባልዲ በመቅዳት እየሮጡና እየተጣደፉ በእሣቱና በሚጨሰው ቤት ላይ

ይረጫሉ። እሣቱ በቁጥጥር ሥር በመዋሉ የከፋ ጉዳት አላደረሰም። ይሁን እንጂ እንዲህ ባለ መንደር አንዳች ትንሽ ነገር በተከሰተ ቁጥር ሰዎች ከየአቅጣጫው እየጉረፉ ለመመልከት ስለሚሰባሰቡ መጨናነቁ የግድ ነው። በዚህ የተነሣ በድልድዩ ማዶ መሄድ አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን ጆን ባፕቲስት ፖንሴ እየተጋፋ ወደፊት ይራመዳል። ራቅ ብሎ፣ እርሱ ከመባበት አቅጣጫ ወደ ድልድዩ መግቢያ ላይ በጭንቅንቁ መካከል በሁለት ፊረሶች የሚሣብ ጋሪ ከጉዞው ተገትሯል። ሊመለከተው የፊረንሣይ ቆንሲል ምልክት ያረፈበት ጋሪ መሆኑን ለየ። ይህን ጊዜ፣ ትዕይንቱን እንደ ጅል ፈዝዘው የሚመለከቱትን ሰዎች እባካችሁ አሣልፉኝ ብሎ እየጠየቀና እየለመነ ከመቆየት ይልቅ በትክሻው እየሰቀሰቀና በጉልበቱ እየተጋፋ ቀረበ።

ምንም እንኳ በመድሃኒት አዋቂነት የተመዘገበ ቢሆንም፣ ፖንሴ ምንም ዓይነት የህክምና መታ ዲፕሎማ አልነበረውም። በዚህ ሣቢያ የህክምና ተግባሩ ሁሉ ህገወጥ ነው። በጉዳዩ ላይ ቱርኮች ምንም ዓይነት ተቃውሞ አያነሱም። የሚቃወመውና በተጠያቂነት የሚወነጅሉት የራሱ አገር ሰዎች ናቸው። በተለይም መታየዊ የምሥክር ወረቀት ያለው ሃኪም በመሣከላቸው ከተገኘማ አያላውሰትም። እንደዕድል ሆኖ በዚህ ወቅት ካይሮ ውስጥ ሌላ ሐኪም አልነበረም። የራሱ አገር ሰዎች በተደጋጋሚ ስሙን ሊያጠፉ ሞክረዋል። እርሱም ይህን በመፍራት ከዚህ ቀደም ሁለት ክተሞችን ሰቅቶ ለመውጣት ተገዷል። ከሕግ አስከባሪ ሃይሎች ጎደን መራቅ ማለት በራሱ አርቆ አስተዋይነት መሆኑን ይረዳል። ሕጉ፣ ፈረንሣውያንን በተመለከተ ከሆነ ሃላፊው ቆንሲሉ ነው።

ጋሪውን በማሰፍ ላይ እያለ ጭንቅላቱን ወደ ትክሻው ዘንበል በማድረጉ ፊቱ በክፊል ይታያል። በመሃሉ አንድ በኩራትና በልበሙሉነት አቢት እንዲል የሚያስገድደው ድምፅ በጥሪ ገተው። «ጌታው እባክህ . . . ጥቂት ጊዜህን ልትሰጠን ትችላለህ?»

ጆን ባፕቲስት፣ ቆንሲሉ ቢሆን በማለት ፊርቶ ነበር። ነገር ግን እንደ አደል ሆኖ የጠራውና የገታው ድምፅ የሴት ነበር። ጋሪው ዘንድ ሲደርስ አንዲት እመቤት በጋሪው መስኮት በኩል ጭንቅላቷን ዝቅ አድርጋ አወጣች። መስኮቶቹ ሁሉ በተዘጉበት ጋሪ ውስጥ በነበረው ሙቀት ሳቢያ በላብ ተጠምቃለች። ሳቢ ቁልቁል በመፍሰሱ ጉንጮችዋን የተቀባችው ቅባት ታጥባል። በዚህ የተነሣ ፊቷ አሰቦ በመምሰል መሸብሸብ ጀምሯል። ይሁንና የጊዜን ሂዝመት ለመደበቅ ራሷን በራሷ እየካካሰች የተጌያጌያጠችባቸውና የሰዎችን ዓይኖች የሞታታልልባቸው ጌጦችዋ ፊቷን ይበልጥ አጥምቀውታል። እየተንጠባጠበ ያለውን የፊትዋን ቅባት በመጥረግ ፈገግታ አቀረበች።

«ሠረገላችን እንዳይፈጥን ያደረገው ጉዳይ ምን እንደሆነ ልትነግረን ትችላለህ? ለመሆኑ በአየ ውስጥ ነን እንዴ?»

ጆን ባፕቲስት፣ የቆንሲሉን ባለቤት በአንድ ጊዜ ለይቶ አወቃት። ከዚህ ቀደም አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ያህል በፊረንሣይ ለጋሲዮን የአትክልት ሥፍራ አይታታል።

«ተመልካቾችን የሰበሰባቸው ከቤቶቹ አንዱ በእሣት ተያይዞ ነው። ሆኖም ሁሉም ነገር በእሞር ጊዜ ውስጥ ወደ ተለመደው ሠላማዊ ሁኔታ ይመለሣል»

የቆንሲሉ ባለቤት እፎይታ ማግኘቷን ገልፃ፣ ጆን ባፕቲስትን አመስግና፣ ጭንቅላቷን መልሳ ወደ ጋሪው ውስጥ በማስገባት በተደላደለው መክዳ ላይ ተዝናንታ ተቀመጠች። ወዲያውም የንፋስ ማራገቢያውን ማወዛወዝ ቀጠለች። በዚህን ጊዜ ሴትየዋ ብቻዋን እንዳልሆነች ጆን ባፕቲስት ተገነዘበ። ክሴትዮዋ ጮን በዳር በኩል፣ በክሃሊጁ ወይም በካይሮ በይ ሣቢያ አግድሞሽ በመጣው በፀሃይ ብርሃን ጨረር ደምቃ የምትታይ ወጣት ልጃገረድ ሠረገላው ውስጥ ተቀምጣለች።

የአንዱ እንክን የሌላውን ዐጋና ውበት ይደብቀዋል ቢባል ማጋነን አይሆንም። ሁለቱ ሴቶች ሲታዩ ፍፁም ተቃራኒዎች ነበሩ። በአሮጊቷ እመቤት ፊት ላይ የተጋገረው የክሰሞቲክስ ቅራፊ፣ በወጣቷ ፊት ላይ ከሚታየው ፅዱ ገፅ ጋር በተነፃፃሪነት የሚታይ ነው። የአሮጊቷ ቁንጥንጥ ስጋት ከወጣቷ ርጋታና ዘና ማለት ጋር ተቃራኒ ነው። ጆን ባፕቲስት እንዲገልፃት ቢጠየቅ ምን ብሎ እንደሚጀምር አያውቅም። ወጣቷ የተንጠለጠለውን ፀጉርዋን በሰማያዊ የሃር ሪቨን ቋጥራዋለች። ጆን ባፕቲስት፣ ወጣቷን ቆንጆ በመደነቅ ተመለከታት። ምንም እንኳን በሳሪው ረጋ ያለ ቢሆንም በዚህ አድናቆቱ ራሱን ማረጋጋት ተሳነው። ጋሪ ነጅው አለንጋውን ሲያጮኸው ሠረገላው ወደፊት ተንቀሣቀሠ። በሁለቱም ዓይኖች ውስጥ የክረው የፀጥታና የዝምታ ንግግር ተቋረጠ። ጆን ባፕቲስት መናገር ተስኖት፣ ግራ ገብቶት፣ ግን ደስ ብሎት ብቻውን ድልድዩ ላይ ቆሞ ቀረ።

«ያበሳጫል! እንዲህች ያለች ሴት ካይሮ ውስጥ ከዚህ በፊት አይቼ አላውቅም» ሲል ለራሱ ተናገረ።

2

ሙሴ ዴ ማይሌ የተወለደው፣ ዝቅተኛ ከሆነ አንድ የመሣፍንት ወገን በምሥራቅ ፈረንሣይ ዉስጥ ነው። ቤተሰቡ በርግጥ አሁንም እንጥፍጣፊ ሃብት አለው። በአጠቃላይ ከመጀመሪያውኑ መነሻ ሃብት ስላልነበራቸው ጨርሶ ድህነት ውስጥ ገብተዋል ብሎ መደምደሙ ተገቢ አይሆንም። በአንድ በኩል እያደገ በመጣው የከበርቴው መደብ፣ በሌላው በኩል በከበርቴ ገበሬዎች እየተከበበ ያለው ይህ የመኳንንት ቤተሰብ አንዳችም የሚሠራው ወይም በይዘታነት ያለው ምንም ባይኖረውም ተደሣች ነው። ከሌላው ጋር ራሣቸውን እንዳያወዳድሩና ዝቅ እንዳይሉ ያደረጋቸው እነርሱ የመሣፍንት ወኖች መሆናቸው ነው። ከዚህ ሁሉ እንደሚወጡና አንድ ቀን ደህንነት እንደሚመጣ ቅንጣት አይጠራጠሩም። ምን ያህል የትውልድ ሃረግ ርቀት ይኑራቸው፣ ብቻ ከዘራቸው አንዱ ከፍ ካለ ደረጃ ከደረሰ /ይህ ደግሞ አንድ ቀን ይሆናል/፣ እነርሱ ሁሉ ከወደቁበት ቀና ይላሉ። ይሁን እንጂ ይህን ተስፋቸውን እውን የሚያደርግ ተአምር ወዲያውኑ አልታየም። ነገር ግን የእናታቸው የመጀመሪያው የአጦት ልጅ የሆነው ሱዊስ ፖንቻርትሬይን፣ የፀሃዩ ንጉሥ ሚኒስቴርና በኋላም ጠቅላይ ሚኒስቴር ሲሆን ለረዥም ጊዜ ሲጠብቁት የነበረው ሁኔታ እውን ሆነላቸው። ማንም ሰው በራሱ ችሎታም እንኳ ቢሆን አገኘው ቢባል፣ እዚህ ደረጃ ለመድረስ ግን ያለደጋፊ አይሆንለትም። ፖንቻርትሬይን እዚህ ደረጃ ሊደርስ የቻለው የርሱ የሆኑ ብዙ ሰዎች በየቦታው ስለነበሩት ነው። እነዚህን ሰዎች በየቦታው ያስቀመጣቸውና የሚጠብቃቸው እርሱ ነበር። በዚህም ሣቢያ በእንደ አጋጣሚ እነርሱም ውለታውን ይክፍሉታል። ፖንቻርትሬይን ይህን ስለሚያውቅ ቤተሰቡን መጥቀምን አልዘነጋውም።

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ በአክራሪ ሃይማኖተኛነት ውስጥ የተገኘ፣ ከመካህፍትም ሆነ ከሕይወት ተሞክሮ ምንም የሚያውቀው ያልነበረው ወጣት ነበር። ከዚህ ባዶነቱ በማዳን ካይሮ ውስጥ የቆንሲልነት ሥራ ያገኘለት ጠንካራው አጎቱ ነበር።

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ የአጐቱ ውለታ ቢኖርበትም ቅሉ፣ እርሱም ስለመጭው ጊዜ ብርቱ ፍርሃት ነበረው። የአጐቱን ውለታ በራሱ ጥረት ብቻ ሊከፍል እንደማይችል ያውቃል። ይህ ታላቅ ሥልጣን ያለው አጐቱ፣ ምናልባት አንድ ቀን በተራው ውለታ ይጠይቀው ይሆናል። አጐቱ የሚጠይቀው ውለታ፣ ምናልባት ሙሴ ዴ ማይሌ ራሱን ለአደጋ ማያጋልጥ የማይገኝ ይሆን ይሆናል።

ካይሮ የሚገኘው የቆንሲላ ጽሕፈት ቤት፣ በምሥራቅ ሜዲቴራኒያን ውስጥ ካሉት ሁሉ የሚያስቀና ቦታ ነው። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ተጠሪነቱና ሪፖርት የሚያደርገው ኮንስታንቲኖፕል ለሚገኘው የፈረንሣይ ኤምባሲ ነው። ይህ ደግሞ ትንሽ ራቅ የሚል ሥፍራ ነው። የቆንሲል ጽሕፈት ቤቱ የሚያከናውነው ተግባር በካይሮ የውጭ አገር ነዋሪዎች መንደር ውስጥ ችግር ፈጣሪ የሆኑ ጥቂት ነጋዴዎችንና ጀብደኞችን በተመለከተ ሕግጋትን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ማውጣትና ተቀባይነት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። እነዚህ ሰዎች ባልተለመዱ ተከታታይ ሁኔታዎች ሳቢያ ያለ ዕርዳታና ድጋፍ መውጫው ጠፍጂቸው

ወደአገራቸው መመለስ ባለመቻላቸው እንደወጡ የቀሩ ናቸው። በድፍረት የሚሠሩትን እንደ ፀጋ ይቆጥሩታል። ገንዘብን እንደ ሃይል ምንጭ ያስቡታል። በስደት የቆዩበትን የዘመን ርዝማኔ እንደ ክብር ይመለከቱታል። እንዲህ ካለው አስተሳሰባቸው እንዲታቀቡ ሊያስታውሣቸው የሚችለው ደግሞ ሙሴ ዴ ማይሌ ነው። ከዚህ በተረፈ ዋናውና ዐብዩ ተግባር፣ ፖንቻርትሬይን ደግሞና ደጋግሞ ሁል ጊዜም ሳይሰለች የሚናገረው በወቅቱ ካሉት የቱርክ ሃይሎች ጋር መግባባት ነው። በሌላም በኩል ስምምነቱ ሕዝባዊ ሥርዓት እንዲከበር ይረዳል። ይህ ካልሆነና ከፈረንሣይ ቆንሲል በኩል አንዳች የራስ መነቅነቅ እምቢታ ቢታይ ቱርኮች ችግር ፈጣሪ የሚሉትን የውጭ አገር ዜጋ ያባርሩታል። ስለዚህ የፈረንሣይ ማህበረሰቦችን በሰላም ማሰንበት የቻለው ይህ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ የሚጠቀሱ ጥቅሞችም አሉ። በካይሮ የሚገኘው ቆንሲል ምንም ዓይነት ኪራይ አይከፍልም። እንዲያውም በየዓመቱ አራት ሺህ ሊቭሬ ይቀበላል። በተጨማሪም ለጽሕፈት ቤቱና ለቤት አገልጋዮቹ በሚል ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሊቭሬ ያገኛል። በዓመት አንድ መቶ በርሜል የወይን ጠጅ ለማስገባት መብት ሲኖረው በአንድ በርሜል የሚከፈለው ቀረጥም ሁለት ተኩል ፒያስትሬ ነው። ከዚህ የሚገኘው ትርፍ የትና የት ነው። እነዚህ ጥቅማ ጥቅሞች ሙሴ ዴ ማይሌን ሃብታም አድርገውታል። የዚህ ሁሉ ማጠንጠኛው በውስጡ ታላቅ ውስታ እንዳለበት እንዲሰማው ያደርገው ጀመር። ለጠባቂውና ለተከላካዩ ለፖንቻርትሬይን በፈረንሣይ የምሥራቅ ሕንድ ኩባንያ መርከቦች ተጉዞ፣ አሌክሣንደርያ ወደብ ሰንብቶ የሚሄድ ደብዳቤ መላፉን ተያያዘው። በነዚህ ረዣዥም ደብዳቤዎች ውስጥ የሚበዛውና ዋናው ቅመም፣ ማንም እንደሚገምተው ውዳሴና ምስጋና ነው። ቢሆንም ግን እነዚህ እንደማር የሚጣፍጡ የውዳሴና የምሥጋና ቃላት ምናልባት አንድ ቀን ፖንቻርትሬይን ያቅለሸልሹትና ያስጠሱት ይሆናል የሚል ስጋት አለው። ስለዚህም ቆንሲል ዴ ማይሌ፣ እነዚህን የታላቅነት የሙገሣ ቃላት የአካባቢውን ሁኔታ ከሚገልፅባቸው የተለያዩ ጉዳዮች ጋር እያዋዛ ማለዘብ ጀመረ። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ፅሁፉ ከጭብጡ ወጣ ይል ጀመር። የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩን ምላሽ ባያውቅም፣ በገደብ የሰሸ አገላለፁም ይከራ ጠቅሷል።

ሙሴ ዴ ፖንቻርትሬይን፣ ለደብዳቤዎቹ ሁሉ መልስ ይሰጣል። እንዲያውም አስተያየቶችንና አንዳንዴም በፖለቲካው ጉዳዩ ላይ ጥቂት ማስታወሻዎችን ያክልባቸዋል። አሁን ወር በሞላውና በመጨረሻው በተላከው ደብዳቤ ላይ ግን ለመጀመሪያ ጊዜ የቀጥታ ትዕዛዝ ያለበት የሚመስል ፅሁፍ ላክ። በደብዳቤው ላይ ክቨርሣይለስ ቤተመንግስት ተነስቶ በርም አድርጉ አንድ የጀስዊት ቄስ ተልኮ ስለሚመጣ ቆንሲሉ እንዲጠብቀው፣ይህ ወንጌላዊ ቄስ ይዞት ከሚመጣው ከማንኛውም ዓይነት ትዕዛዝ ጋር በቅን መንፈስ እንዲተባበር የሚጠይቅ ነው። የደብዳቤው መንፈስ የራሱንና የንጉሥ ሉዊስ 14ኛን ምኞቶች እንደያዙ እንዲገምት የሚጠይቅ ነበር።

በፅሁፍ ሰፍሮ የሚተላለፍን መልዕክት ሊደጋገም የሚችለውን አደጋ ለማስወገድ ሲባል፣ አንድ መልዕክተኛ መልዕክቱን በቃል ይዞ እንዲሄድ ማድረግ፣ በላኪውና በተቀባዩ መካከል የሚኖረውን ምስጢር በጣም ጥብቅ ያደርገዋል። የደብዳቤው መንፈስና ሊከተል

የሚችለው የሥራ ጉዳይ ሙሴ ዴ ማይሌን አሳሰበው። ውሎ ሲያድርና ጊዜም እያለፈ ሲሄድ ግን የተባለው የጀስዊት ቄስ ብቅ ሳይል ቆየ። የነገሥታት ፖሊሲዎች የሚጨበጡ አይደሉም። በየጊዜውና ሣያቋርጡ መልካቸውን ይለዋወጣሉ። ምናልባት የተባለውን የጀስዊት ቄስ ሌሎች ዲፕሎማቶች በሌላ አቅጣጫ ለአጣዳፊ ጉዳይ ወስደውት ይሆናል። ይህ ካልሆነ ቄሱ በጉዞው ላይ ደብዛው ጠፍቶ ቀርቷል። ሙሴ ዴ ማይሌ የአዕምሮ ዕረፍት አገኘ።

አሁን ግን ይህ ተንኛር መሆኑ የሚያጠራጥር ሰው ብቅ አለ። ሲደርስ ደግሞ በአጋው የክብር ዘቦች እጅ እስረኛና ግማሽ አካሉ እርቃኑን ሆኖ ነው። አጋው፣በራሱ ፅውቀትና ተሞክሮ ቆንሲሉ ምን ጊዜም ትክክለኛ ነው ብሎ የሚያምን ሰው ስለሆነ፣ ይህን ምርኮኛ ለመልቀቅ አላመነታም። በአንዳሩ የቄሱ ጉዳይ በሰዎች መካከል ከፍተኛ ጉጉት ቀስቅሷል። ይህ የተባለው የፀሃዩ ንጉሥ መልዕክተኛ መሳው አካሉ በጥቃ ተሰውሶ፣ ነገር ግን ለአንድ ግለሰብም ይሁን እዚያ ለሚገኙ ሁሉ የፖለቲካ መልዕክት ይዞ መምጣቱን ለመግለፅ ፍፁም ድፍረት የነበረው ሰው ስለሆነ፣ ፖሻውና በከተማው ውስጥ የሚገኙ ሌሎች የውጭ ሃይሎች የዚህ ምርኮኛ ምስጢር በሚገባ እስካልተገለፀ ድረስ ጉዳዩ እንዲጸዳን አይሹም።

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ በእንግዳ መቀበያው አዳራሽ ውስጥ እየተንጉራደደ እነዚህን ሃሳቦች በአዕምሮው ያመላልሣቸው ጀመር። እንግዳውና እርሱ ለብቻቸውም እራት የሚበሉበት ቦታ እንዲዘጋጅላቸው ትዕዛዝ ሰጠ። ሁለቱ ሰዎች ለብቻቸው መነጋገር ከመጀመራቸው በፊት የቆንሲሉ ባለቤትና ሴት ልጁ፣ ለክህኑ የአቀባበል ለሳምታ አቅርበው ክፍሉን ሰቅቀው ወጡ። ኑቢያዊው የቆንሲሉ አልባሽ፣ ተጓዥ እንግዳ የሚታጠበውበትን ቀዝቃዛ ዐሃ በባልዲ ይዞ በደረጃው ላይ እየተጣደፈ ሲራመድ ይሰማል። በሁሉም መልክ ሲታይ የቀድሞው ምርኮኛ እፎይታ ያገኙ ይመስላሉ። ሙሴ ዴ ማይሌ ግን ትዕግስት በማጣት በእንግዳው ላይ የቁጣና የብስጭት ስሜት ይሰማው ጀመር። በአዳራሹ ውስጥ መንጉራደዱን አቋረጠና እንዲታደስ ሲያደርገው በነበረው ሥዕል አንባር በሚገኝ አግዳሚ ላይ ተቀመጠ። የተመለከተው ነገር አቅሱን እንዲስት አደረገው። የንጉሡ ፊት አንዳችም ስም የሚያስነሣ ስህተት የለበትም። የቆሸሸው ሁሉ ተወግዶ የንጉሡ የፊት ቆዳ ገፅታ ወደቀድሞው ዕዱነቱ ተመልሷል። ይሁን እንጂ በጣም በቅርበትና በክፍተኛ ጥንቃቄ ሲመረመር፣ በተፈጥሮ በነበረው ሽታ ላይ በስሱ የተሳ ቦታ ይታያል። ይህ ዓይነት ቀለም በሀዛን ልጅ ፊት ላይ ቢሆን ኖሮ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት በደረሰ የጥፊ ምት ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችል ነበር። ግርማ ሞገስ ባለው የንጉሡ ፊት ላይ ሲሆን ግን፣ ያለልክ የተቀባ የጉንጭ ቀለም መስሎ ንጉሡም በመልካም ጤንነት ላይ የሚገኝና ህዝቡም ባለብሩህ ተስፋ መሆናቸውን የሚያመላክት ይሆናል።

«ሜትር ዝረሚ ነገ ማለዳ ከማንኛውም ሥራው በፊት እዚህ እንዲገኝ ንገረው» ሲል በበር ጠባቂው ላይ አምባረቀበት።

ያ ባለጌ መናፍቅ፣ ሙሴ ዴ ማይሌ ተጠርቶ እንደወጣ ሥዕሉን ለማደስ ደፍሯል። ውጤቱም የተሳካ ነበር። ይህ በራሱ "ተመስገን አምላኬ!" ያሰኛል። ግን ምን ድንገተኛ መቅሰፍት ደርሶ ይሆን? ሥራው በርግጥ የተዋጣለት ነው። ክፍያም የሚገባው ነው። ስለክፍያው አስቀድሞ ስምምነት ተደርጓል። በእንግሩ ግን የሰውዬው አልታዘዝ ባይነት የሚያስቀጣው ነው። እንዲህ ባለው ወሮበላ ላይ ሥልጣንን ለማሣየት ከዚህ የተሻለ ዘዴ የለም። በዚህ መሠረት ቆንሲሉ ለዚህ ባለጌና ደፋር መድሃኒት ቀማሚ ሁለት ምርጫዎችን

ያቀርብለታል። አንደኛው የአንድ ሳምንት እስር ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን ከክፍያው ላይ የሚቀነስ የገንዘብ ቅጣት ነው። ሜትር ዝረሚ ደግሞ ከነዚህ ሁለት አማራጮች መካከል የገንዘብ ቅጣቱን እንደሚመርጥ ቆንሲሉ ቅንጣት ታህል አይጠራጠርም። የሥዕሉ መልክ ዕድሣት በስኬት ተከናውኗል። ይህ ማለት ከሙሉ የእጅ ዋጋ ከፍያ ላይ ቅናሽ በሚያስከትል ድል አድራጊነት ጣፍጠ የታጀበ ነው። አባ ቬርሣው ለአራት ሲመጡ፣ ቆንሲሉ እጅግ ደስ በሚል ተቀበላቸው።

«ወዳጄ ሆይ!» አሉ የጀስዊቱ ቄስ፣ የቆንሲሉን ሁለት እጆች በእጆቻቸው ውስጥ ይዘው። «ባንተ ውብ አቀባበል ከእስራ ተፈታሁ። እንዲያውም ወደ ሕይወት የተመለስኩ ያህል ነው። መታጠቢያው፣ ንፁሆቹ ልብሶች፣ ያማረው ባለሥነስርዓት ቤት ሁሉ ነፃ አድርገውኛል። እንዲህ ያሉ ነገሮችን ለማግኘት ምን ያህል ጓጉቼ እንደነበረ ብታውቅ ትደነቃለህ»

የምስጋና አምባዎች የቄሱን ዐይኖች ሞሏቸው። ማኪያቬሊ የተናገረው እውነት ከሆነ፣ ሴሎችን የምንወዳቸው ባደረግንላቸው መልካም ነገር ከሆነ፣ ቆንሲሉም ለአባ ቬርሣው ያደረገላቸው ሞቀ ያለ የርህራሄ ና ከመጠን በላይ የሆነው እንክብካቤና አትኩረት ምንም መደነቅን ሊፈጥር አይችልም።

«ክብርት ማዳም ዴ ማይሌን በመተላለፊያው ላይ ሣገኛት አክብሮቴን ገልጫለሁ። በእራት ገበታ ላይም አብራን እንደማትሆን ተረድቻለሁ። የቤትህን የውስጥ ሥነስርዓት በምንም ዓይነት ልጥሰው አልፈልግም» አሉ አባ ቬርሳው።

«የሰም በፍፁም፣ በፍፁም። ሰብቾችን የምንወያይባቸው ጉዳዮች አሉን። እነዚህን የሥራ ጉዳዮች ለመነጋገር የሚያመቸውን የአራት ሰዓት መጠቀም ይኖርብናል»

«እውነት ነው። ሴት ልጅህን፣ ማዳሞዜል ዴ ማይሌንም፣ በድንገት አግኝቻት ነበር። ስለውበቷና ስለጠንቃቃው ሥነ-ምግባርዋ ምስጋና ይገባሃል። አስተማሪዎችና ትምህርት ቤቶች በሌሉበት እንዲህ ባለ የባዕድ አገር እንዴት አድርገህ ልታስተምራት ብትችል ነው?»

«እስከ አሥራ አራት ዓመት ዕድሜዋ ፈረንሣይ ውስጥ ነበረች። አብራን እንድትሆን ያደረግነው ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ነው»

ሁለቱ ሰዎች ከዚህ በፊት ጨርሶ አይተዋወቁም። አሁን የጀመሩት ጭውውት ግን እንደ ረዥም ጊዜ ጓደኛሞች ቀጥሏል። በጨዋታቸው መሃል። «እንዲህ ባለ ርጥበት አዘል የአየር ጠባይ ባለበት አገር፣ በሚደነቅ ሁኔታ የተጠበቀ ነው» ሲሉ ቄሱ የንጉሡን ሥዕል አደነቁ። በመቀጠልም የቆንሲሉን ጤንነትና በያዘው የሥራ ደረጃ ላይ ያሰበትን ሃላፊነት በሚመለከት ጥቂት ጥያቄዎችን ጠየቁት። በመጨረሻም ገበታ ላይ ሲቀመጡ ጭውውታቸው ወደ ክስታራ ጉዳዮች ተለወጠ።

«አባቴ? የገብያን ዝርዝር ጉዳይ ለማወቅ አፈልጋለሁ። ሁሉንም ነገር። የተሣፈሩበት መርከብ ተሰባብሮ ሲወድቅ እንደጠፋብሞ ገልፀውልኛ ነበር?»

«በጣም መጥፎ መሰባበርና መስጠም ነበር። የእግዚአብሔር ቸርነት ባይሆን ኖሮ ይኼኔ ሞቼ ቀርቼ ነበር»

በመቀጠልም፣ ከሮማ ከተማ እንዴት እንደሰቀቀ ረዥም ታሪካቸውን ማውጋት ቀጠሉ። መርከቡ ተሰባብሮ የወደቀው ከቆጵሮስ ደሴት አይታ ማይሰወር ነበር። እነሀ ጀስዊት ቄስ አደጋ እንደማይቀር ሲገነዘቡ፣ በመርከቡ ላይ ከሚገኙ ጀልባዎች አንዱ እንዲወርድላቸው አዘዘው ከሌሎች ጥቂት ሰዎች ጋር ይሣፈራሉ። የባህሩ ሞገድ ከአንድ ማዕበል ከበጣጠሰው የጠረፍ ቋጥኝ ጋር ያጋጫቸዋል። ያች ለአንድ ሰው ብቻ የምታገለግል ጀልባቸው ጥልቀት ባልነበረው ቦታ ላይ ብትንትኗ ይወጣል። ግን ልክ በአንድ ከማይፈልጉት ውሃማ መቃብር ላይ እንደተጣሉና ይህ እየጉደለ ፣ ሁሉም እንደሚያውቀው ከምዕዓት ፍርድ በኋላ ከሞት እንደገና እንደወጡ ያህል አባ ቬርሣው የቅሬታ ውጋት ተሰማቸው። ችግራቸውን፣ ህይወታቸውንና የተቀበሉትን ትዕዛዝ ለእግዚአብሔር በመተው በመሞታቸው አምነው ነበር። በመጨረሻው ሰዓት ላይ ትዝ የሚላቸው፣ በቀዝቃዛ፣ ጥቁርና በሚናወጥ ውሃ ውስጥ ሰምጠው የመሞታቸው ጉዳይ ነበር። ከዚህ ቀጥሎ የሚያስታውሱት በአንዲት ትንሽ ጅረት አጠገብ ባለ አሸዋ ላይ እጆቻቸው ከርሣቸው ጋር ከባህሩ ቡተፋ በአንድ ምሰሶ ላይ ታስረው መንቃታቸውን ነው። በዚያን ሰዓት ብቻቸውን፣ እርቃናቸውን፣ በፍርሃት እየተንዘፈዘፉ፣ በቆፈን ተይዘው ልክ አዳም በተፈጠረበት ዕለት እንደነበረው መስለው ነበር። ይሁንና እግዚአብሔር አልተዋቸውም። በዙሪያው ነዋሪ የሆኑ አሣ አስጋሪዎች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ከሞት አትርፈዋቸው በሚችሉት አቅም አልብሰዋቸው፣ እንደለመዱት መረቦቻቸውን በሚጥሉባቸው የግብፅ ጠረፍ ከሁለት ቀናት በኋላ አደረሷቸው። በርሣቸው ጥያቄ አሌክሣንደሪያ አጠገብ ባለ የባህር ዳርቻ አወረዷቸው። ጥሩ መተላለፊያ በሌለበት የአቶማን ግዛት ውስጥ መሆናቸውን ሲረዱ ከተማውን መሸሽ ቀጠሉ። ከዚያም በአሌክሣንደሪያ ዙሪያ ጥምጥም ባሰው በረሃ ተንከው ወደ ደቡብ ራቅ ብለው ተጓዙ። ለጀልባ ቀዛፊዎች የሚከፍሉት አንዳችም ሰባራ ሳንቲም እንደሌላቸው በመናገርና በመደራደር ወደ ካይሮ የሚያደርሣቸውን መንገድ በመጠየቅ አባይ ወንዝ ደረሱ።

«የቀረው የምታውቀው ነው» ሲሉ በትህትና ተናገሩ።

ቄሱ ታሪካቸውን በሚናገሩበት ወቅት፣ ሙሴ ዴ ማይሌ አንድ ሺህ ጊዜ ያህል የማዳነቅና ተስፋ የመቁረጥ ድምፅ ያሰማ ነበር።

«ያጋጠመኝ መከራና ስቃይ፣ እዚህ የመድረሴንና አንተ ስታገኘኝ የነበርኩበትን ሁኔታ ማስረዳት ከቻለ በቂ ነው። ዋናውና አብዩ ጉዳይ ግን ሴላ ነው» ሲሉ የጀስዊቱ ቄስ ይበልጥ ክስተር ባለ ድምፀት ተናገሩ።

«አ! እውነት ነው። የንጉሡን መልዕክት ማለትም ነው» አሰ ሙሴ ዴ ማይሌ።

አባ ቬርሣው ወንበራቸው ላይ ተስተካክለው ተቀመጡ። አንዴ ወይም ሁለቱ ዓይኖቻቸውን በዝግታ አርገበገቡና ትህትና ባልተለየው ሁኔታ ውይይቱን ቀጠሉ። ሙሴ ማይሌ፣ የንጉሡን ሥዕል መልክት ሊያደርግ ራሱ ንጉሡ ከበላያቸው መገኙቱን ያበሰረው መሰለው።

1/25/10

«አትጨነን ለመናገር ምንም መልዕክት ይዤ አልመጣሁም» አሉ የጀስዊቱ ቄስ።

«ነገር ግን ሲናገሩ እኮ . . . »

ጥቁር የሰበሱት ቄስ፣ ዴ ማይሌ ዝም እንዲልና ይህ ጉዳይ ጊዜ የሚወስድ ነው ለማለት ፈልገው እጃቸውን ከፍ አደረጉ።

«ምንም መልዕክት የለም ስልህ፣ በዕውፍ መልክ ያመጣሁት የለም ለማለት ነው። በሌላ አነጋገር ንጉሣችን ራሣቸው በቀጥታ የፃፉት ወይም የገለፁት ነገርም የለም። ወደፊት ልታደንቀው እንደምትችለው የዚህ ምስጢር መጠበቅ በሁሉም መልኩ እጅግ አስፈላጊ ነው። እንዲጋጠሙኝ አደጋ ሁሉ ላደርሰው የማልችለውን መልዕክት ብቀበል ኖሮም ጥፋትና ነውር ይሆንብኝ ነበር።»

«በዚህ እስማማለሁ» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ

«ምንም ዓይነት መልዕክት የለም ብልህም፣ በንጉሡ መንፈሣዊ አባት በኩል ራሣቸው ንጉሡ የሚለማቸውን የገለፁበት ጉዳይ አለ»

«የንሰሃ አባታቸው፣ አባ ዴ ላ ቾይስ ናቸው?»

የጀስዊቱ ቄስ የአይን ቆባቸውን አጨማደዱ። ሙሴ ማይሌ፣ በደረት እቅፉ ሙሉ እጅግ ብዙ ሃብት የታቀፈ ሕፃን ይመስል በሚያምር ስልት ይመለከታቸዋል።

«እንደምታውቀው የጀስዊት ሥርዓትን የሚከተሉት እኒህ ቅዱስ ሰው፣ የንጉሡን ምስጢር የሚናገሩት እጅግ በጣም ለሚቀርቧቸውና ለሚተማመኑባቸው፣ ለምሣሌ በቬርሣይለስ ቤተመንግስት የሃይማኖትን ጉዳይ በቀናኢነትና ያለዕረፍት በሚያስቡት እንደ ማዳም ዴ ሣይንቴኖ፣ እንደ ዋናው መሪ ቄሣችን እንደ ሙሴ ፖንቻርትሬይን፣ በምሥራቅ ሚዲቴራኒያን ለሚገኙት የአየሱስ ማህበረሰቦች መሪ እንደሆኑት ረዳታቸውና ተወካያቸው እንደ አባ ፍሌሪአው እና አሁን ደግሞ እንዳንተ ላላችሁት ብቻ ነው።»

ሙሴ ማይሌ፣ ለዚህ ጠንካራ ለሆነው ሃይል ፍላጐት እጅ በመስጠትና በተደረገለትም አክብሮት የተነሣ በዓይኖቹ ግጥም ያለውን እምባ ለመደበቅ ሲል ራሱን ደፋ።

«ጉዳዩን በጥቂት ቃላት ጠቅለል ማድረግ ይቻላል። እንደምታውቀው በአሁኑ ጊዜ የክርስትና እምነት ክበላቶቻዋ ጋር በጦርነት ላይ ነች። የአቶማን ቱርክ መስፋፋትም ለጊዜው ተገትቷል። የሚቀጥለው እርምጃ ጊዜ ይወስዳል እንጂ ዳግም በድል መንቀሣቀስ ይኖራል። ነገር ግን በክርስቶስ እየሱስ አምነው ለመኖር በሚሹ ወገኖች መካከል እጅግ ከባድ አደጋ ተቀስቅሷል። ይህ የሃይማኖት ተሃድሶ የሚባለው አስቀያሚ የአፍ ቁስል የሆነው ነገር፣ የአግዚአብሔርን የእጁን ሥራ በውስጥ ባሉ ብሳቶች ለማፈራረስ እደጋ እያሴረ ነው። እንዲህ ያለው ራሱን ቀና የሚያደርገውን ለይጣናዊ እንቅስቃሴ፣ የፊረንሣይ ንጉሥ ራሣቸው ተቃውመውታል። ለምሣሌ በፐሮቴስታንትነት ላይ የሚደረገውን ተቃውሞ በራሣቸው ፈቃድ በናንቴስ አዋጅ ሰርዘውታል። አውሮፖም ውስጥ አሌጋቸውን ከአደጋ ለመጠበቅ ጠላቶቻቸውን

ፊት ለፊት ተጋጥመዋቸዋል። ዊልሄልም የሚባለው የኦራንጅ ግዛቱ ከሃዲ የፐሮቴስታንት መስፍን ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ነው። ትግሉ ግን በሜዲተራንያንና በሚያዋስኑት አገሮች ብቻ የተወሰነ አይደለም። ዛሬ ዓለም ሁሉ በዚህ ውጊያ ውስጥ ገብቷል። የክርስቶስ አየሱስ መልዕክት የሰው ዘር በማያውቃቸው በታምች ሁሉ ላይ መድረስ ይኖርበታል። በአረማውያንም ዘንድ እንዲስፋፋ መደረግ ይገባዋል። ከዚህም በተጨማሪ በሚገባ ባልታወቁና ባለፉት ሁሉት ነፍሶ ዘመኖች ለክርስትና እምነት የፍልሚያ ሜዳዎች መሆን ወደጀመሩት አሜሪካ፣ ኤንዲስ፣ ሩቅ ምስራቅ ወደሚባሉት አዲሶቹ በታምችም መስፋፋት ይኖርበታል። በየጊዜው ተመሣሣይ ጉዳዮች ይገጥሙናል። በመጀመሪያ አንተበላችሁም የሚሉን ኩትክክሰኛው አምነት ውሎ መኖርን የለመዱት ህዝቦቹ ራሣቸው ናቸው። እነዚህ ሕዝቦች ለዘለዓለሙ ውጦ ሊያስቀራቸው የሚችለውን የሞራል አደጋ መገንዘብ አይችሉም። በሁለተኛ ደረጃ ይህ ተሃድሶ የሚባለው ተፎካካሪ ሃይልም ከኛ ጋር ተፋጥጦ ይገኛል። በርግጥ የዚህ ዲያብሎሳዊ ሙከራ፣ የእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል እጅግ ከሚያሰፈልጋቸው ሰዎች እንዳይደርስ የሚያደርግ ሙከራ ነው።»

እንደ እውነቱ ከሆነ ውይይቱ ወደ ኮስታራ የፖለቲካና የሃይማኖት ጉዳይ ፀቅፅበት ሲለወጥ፣ የኒህ ደነማ ቄስ ችሎታና አንደበተ-ርቁዕነት በእጅጉ አስደንቆታል።

«የፈረንሣይ ንጉሥ በረዥም የዘውድ አገዛዝ ዘመናቸው ብዙ ጉዳዮችን ተምረዋል» በማለት ቄሱ ንግግራቸውን ቀጠሉ። «በታሪክ አጋጣሚ ከሆኑት ይልቅ አርቀው የማየት ችሎታ ያላቸው ናቸው። የንስሃ አባታቸውን ድንትና አስገራሚ ችሎታ በትክክል የተረዱ ናቸው። ለደረሱበት ታላቅ ዓለማዊ ሥልጣን የበቁበትን ቁም ነገር የተሞላበት ትግል የተረዱ ናቸው። በዚህ ዓለም ውስጥ በእውነተኛው አምልኮና አሁንም በጨለማ ውስጥ በሚጻዝሩ ሃይሎች መካከል ያለው ፉክክር ነፍስና ስጋቸው የሚፐንቱባቸው ሰው ናቸው። እስከ መጨረሻዋ ሀቅታቸው ድረስ ለዚህ ለመታገል ቆርጠው ያሉ ናቸው። ምንም እንኳ ትግል የማሸ ብዙ ጉዳዮች ቢኖሩም አንዳንዶቹ ከሌሎች ቅድሚያ የሚጠይቁ ናቸው። ቱርኮች በጊዜ ሃደት ዋጋቸውን ያገኛሉ። እኛ አሁን በጥሩ እድል ላይ እንገኛለን። እሳቱ እንዳይጠፋ እዚህ የሚገኙትን ጥቂት ክርስቲያኖች እናግዛቸዋለን። አስቸጋሪው የኦቶማን ሃይል መሰነጣጠቅ ሲጀምር፣ መከላከያዩ ነው ብሎ በሚተማመንበት በያንዳንዱ ጉድባው ሰርስረን እንገባለን። በርግጥ አሁን ሰዓቱ አይደለም። ነገር ግን በቅርብ ያሰች ርዳታችንን የምትፈልግ አገር እየጠራችን ነው። ልንቆጣጠረው ለማንችለው የታሪክ መዘውርና ለድንቅ የተራራ ሰንሰለቶችዋ ምስጋና ይግባቸውና ተለይታን የምትገኝ ትልቅ አገር አለች። ይህች አገር አሁንም በጨለማ ውስጥ ነች። ለማለት ያህል ለበለው እንጂ ይህቺ አገር በኛ ደረጃ ከመሆን ያለፈ የምትፈልገው የላትም። አገረቷ የክርስቲያኖች አገር ነች። ይሁንና እምነቷ ባልተገባ መስመር የተገነባ በመሆኑ ዝበርቅርቅ ብሎ ያደገ ነው»

«አቢሲኒያ ነች!» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ እንደ መፍዝዝ ብሎ።

«አቢሲኒያ። አምን፣ ይህች በቅጡ ያልታወቀች ነገር ግን በእጅጉ የአማንያን አገር የሆነች፣ ሊያሪሱሩዋት የቃጡትን ሁሉ ውጣ ያስቀረች፣ ነገር ግን አሁንም የኛን ድጋፍ የምትሻ አገር ናት»

ጀስዊቱ ቁስ፣ የሙሴ ዴ ማይሌን እጅ ለመያዝ ትርፍራፊ ባለበት ሣህን ላይ በመሣብ ጮንበስ አሉ።

በዚያች አገር አንድ የኤምባሲ ተግባር እንድታከናውን ሃላፊነቱን ዋስውበሃል»«የፈረንሣይ ንጉሥ ይህችን አገር መልሰው ወደ ቤተክርስቲያናቸው በመቀላቀል ክብራቸውን ከፍ ማድረግ ይፈልጋሉ። ግርማዊነታቸው

3

ጆን ባፕቲስት ፖንሲና ሚትር ዝረሚ በመድሃኒት ቅመማና ሽያጭ ንግድ ሥራ ላይ በሽርክና በመሠማራታቸው፣ በአንድ ቤት ውስጥ በጋራ መኖር ጀመሩ። ቤቱ እንደ አስቱዲዮም ያገለግላቸዋል። ይህ ቤት በፈረንሣውያን ማህበረሰቦች መኖሪያ የመጨረሻው ዳር፣ ሰላምና ሁሃታ በነገሠበት ጉዳና ላይ በመሆኑ ብቻቸውን ሆነው ሲያከናውኑት ለሚችሉት ሥራ አመች ነው።

«ሃሎ! አንተ አስማተኛ ሽማግሌ፣ ለመሆኑ አለህ እንዴ?» በማለት ጉላ ባለ ድምፅ እየተናገረ ጆን ባፕቲስት ምስቅልቅል ያለውን የወንደላጤ ቤታቸውን በር በርግዶ ገባ።

በላይኛው ፎቅ ላይ፣ በቅጥር ግቢው ውስጥ ያለውን አፀድ እንደልብ ለማየት የሚያስችል ሰፊ በረንዳ አለ። መስኮቶች ሁሉ መጋረጃዎቻቸው ወርደዋል። ሌሎች ብዙ መስኮቶች በሸክላ ጡብ ድፍን ተደርገው ተዘግተዋል። ፖንሴ ሲደርስ፣ ጓደኛው ጮራዴ ይዞ ፋዝዝ ብሎ በበረንዳው መደገፊያ ላይ ደገፍ ብሎ አገኘው።

«ይህን መሣሪያ ጨብጠህ እዚህ ብቻህን ምን እየሠራህ ነው?»

«ቆንሲሉን አሁን ገደልኩት» አለ ዝረሚ

«እውነትህን ነው?»

ጆን ባፕቲስት ጓደኛውን አንዳች ነገር እንዳወከውና እንዳበሣጨው አወቀ።

«እውነቴን ነው የምልህ። አሥራ ሁለት ጊዜ ነው የገደልኩት። ማየት ትፈልጋለህ፣ ተመልከት» ይህን ተናግሮ፣ የገደል ስባሪ የሚያክለው ሚትር ዝረሚ፣ ስላሰፈው ሣጣብ ረዥሙን እንዳልሆነና ከባላጋራው ጋር በጮራዴ እንደሚፋለም ሰው ወደ ፊቱ ዘልሎ ወረደ። ግድግዳው ዘንድ ሲደርስ በብዙ ጥረት ጮራዴውን በባላጋራው ሰውነት ውስጥ ሰንዝሮ ሲመነዠርና ሲለነጥቀው የሚያሰማውን ዓይነት ዝቅ ያለ የበቀል ድምፅ አሰማ። የጮራዴው

ሜፍ፣ የግድግዳውን ልስን ዘልቆ ሲወጋው፣ አንድ ትንሽ ሽራፊ ነገር ተቀርፎ ሲወድቅ የሁለት የጡብ ሽክላዎች ቀይ መልካቸው ተጋለጠ።

«ብራቮ፣ በውነት መሞት ይገባዋል» በማለት ጀን ባፕቲስት

አጨበጨበ። «ለመሆኑ ከዚያ በኋላ እርይታ ተሰማህ?»

«እጅግ በጣም ነዋ!»

«መልካም አሁን እንግዲህ ተረጋግተሃል። አስቲ አጠቃላይ ሁኔታውን አስረዳኝ»

ጀን ባፕትስት ወንበር ስቦ ተቀመጠ። ጓደኛው ወደፊትና ወደኋላ እየተንጐራደደ በያዘው ጉራዴ እግሩን ይጠቦጥባል።

«የዚህ ቆንሲል አስር መርሮኛል። በዚህ የተነሣ መልኩን ሳየው ግደለው! ግደለው! የሚል ይመጣብኛል።»

«ይህማ እንግዳ ጉዳይ አይደለም» አለ ጀን ባፕቲስት ፈገግ አያለ። «እንደሚመስለኝ ይህን ሥራ እንዳትቀበል ከመጀመሪያም የወንድምነት ምክሬን አካፍዬህ ነበር»

«እንዳልቀበለው! አስገድዶ ሊጠራኝስ?»

«እኔን በግዳጅ ጠርቶኝ ቢሆን ኖሮ አልሄድለትም ነበር» አለ ጀን ባፕቲስት

«እንደዚያ ነው እንዴ? ልንገርህ። አየህ፣ አንተ የኝሮቴስታንት ተከታይ አይደለህም። ስለዚህ ከኔ ይልቅ በጣም በተሻለ ሰላምና ደህንነት እዚህ መኖር ትችላለህ። ከዚህም በላይ ፖሻው ያማክርሃል። የግል ሃኪሙ ያህልም ያከብርሃል። እኔን ግን ከአንድ ምስኪን የዕፅዋት ቀማሚነት ሌላ ማንም አይደለህም። በርግጥ ጥያቄው ይህ አይደለም። ማይሌ አስገድዶ ጠራኝ። እኔም አሺ ብዬ ፣ ሥራውንም ሠርቼ ጨረስኩ»

«እና ታዲያ ተሳክልህ?» ሲል ጀን ባፕቲስት ጠየቀው

«በትክክል አምናለሁ!»

«እንግዲያውማ ሁሉም ነገር ጥሩ ነው»

«አይምሰልህ። አንተ ቆንሲሉን አታውቀውም። ጠባቂዎቹ ባሻቸው ሰዓት መጥተው ወደ አስር ቤት እንደሚከቱኝ አስባለሁ። አስካሁንም አንዳች ነገር ሳያስተውል የቆየው ምናልባት በሥራ ተወጥሮ ቢሆን ነው።»

«ቢሆንስ ምን ሊያደርግ ይችላል። የተመደብክበትን ሥራ ማከናወን ወንጀል አይደለም»

«በርግጥ አይደለም። ክቡር ቆንሲሉ ግን ከዚህ ባሻገር መሆን የሚፈልግ ሰው ነው። የግድ ተግስተሃል የሚል ሰው ነው። ሕግ አስከባሪውም፣ ዳኛውም አርሱ ራሱ ነው። ስለዚህ ከራሱ ጋር ክርክር አይገጥምም። ይህ ስስታም ሽማግሌ የገንዘብ መቀጫ ይጥልብኝና ከማገኘው ከፋሪያ ላይ ይቆርጥብኛል»

«ክፈላ! በዚህ ካበቃልህም የታሪኩ ፍፃሜ ይሆንልሃል»

«አላደርገውም። ከዚህ ይልቅ አርሱን ገድዬ ወደ ሌላ አገር አከበልላለሁ»

ገንዘብን በተመለከተ ሜትር ዝረሚ መሉ በመሉ የፐቲስታንት የውሃኔ ስሜት አሰጠ። ሌላው ቀርቶ በትክክልና በተገቢ መንገድ ያላገኘውን ሰባራ ሣንቲም እንኳ የማይቀበል ሰው ነው። እንዲሁም ደግሞ ሊከፈለው ከሚገባው ውሰጥ አንዲት ሣንቲም ብትጐድልም አይቀበልም።

«ዝረሚ፣ አስቲ ረጋ በል። በቅጣት ማቢያ ተጠያቂ አድርጐ ሊይዝህ መብት የለውም። በኛ ደረጃ ቆንሲሉ ሊያደርግ የሚችለው የገንዘብ መቀጮ ወይም የእሥር ጊዜን በአማራጭነት ማቅረብ ነው። ለዚህ ደግሞ የሳበህን ዋጋ ከሚበላብህ መታሰሩን ምረጥ። ተቆልፎብህ የምትቀየው ለሁለት ቀን ያህል ነው። ከዚያ በኋላ ዳግመኛ ከርሱ ጋር አንዳችም ነገር አትሠራም። ይህ ማለት ባላደረግሁት ኖሮ እያለ እድሜ ልኩን ሲንገበገብበት የሚኖርበት ጉዳይ ይሆናል»

ቆንሲሉን ከረዥም ጊዜ በፊት ድምጥማጡን ሊያጠፋው ይችል በነበረው በጓደኛው ጣፋጭ ምክር ሜትር ዝረጣ ረካ። የጓደኛውን ጥበብ የተሞላበት ብልጠትም አደነቀ።

ለእፍታ ያህል ሁለቱም በፀጥታ ቆሙ። ጆን ባፕቲስት፣ ወደ ጓዳ ገብቶ ሁለት ሽሩቤ ብርሌዎችንና የሚጠጣ ይዞ መጣ። ሁለቱም ጠጡ።

«ከጥቂት ጊዜ በፊት በከሃሊጅ ድልድይ አጠገብ የእግት ቃጠሎ ደርሶ ነበር። ለአጭር ጊዜም ቢሆን ሽብር ፈጥሮ ነበር። የቆንሲሉ ሚስትም የነበረችበት ጋሪ ቡተሰበሰበው ሕዝብ ምክንያት ከመንቀሣቀስ ተገትቶ ነበር።

ምንም የተሰየ ስሜት ስላላዘለት ሜትር ዝረሚ «እሀ» አለ።

«በነገራችን ላይ» ሲል ጆን ባፕቲስት ሌላ መጠጥ ሰራሱ እንደገና እየቀዳ «በቆንስላው ውስጥ በቆየህባቸው ረዥም ጊዜያት ውስጥ . . . »

ጓደኛው ትከሻውን አነቃነቀ።

«ለመሆኑ ከማዳም ዴ ማይሌ ጋር አብራ ያለችውን ወጣት ልጃገረድ ታውቃታለህ?»

«ምን ትመስላለች?»

ጆን ባፕቲስት፣ የማስታውሰው በልጃገረዲቷ ፀጉር ላይ የነበረውን ረቨን ነው በማለት ራሱን ማጋለጥ አልፈለገም።

«በደንብ አድርጌ ላያት አልቻልኩም።»

«ለመሆኑ ፈዛዛ ቢጫ ፀጉር፣ ትላልቅ ሰማያዊ አይኖች ያሏትና ያዘነች የምትመስል ናት?»

«ይመስለኛል፣ አገላለፅህ ትክክል ነው» ሲል ወጣቱ ሰው በፍጥነት መለሰ

«አሏማ የዚያ የበስባሳ ቆንሲላችን ልጅ ነች

«ተፈጥሮ ይቅር ለማለት ፈጣን ነች» አለ ጆን ባፕቲስት

«አይቻታለሁ ብትል የማይመስል ነገር ነው። ወጣቲ ልጅ በሰላማዊ መልክ የትም ወጥታ አታውቅም። እዚህ በቆየህባቸው ሁለት ዓመቶች ውስጥ፣ አንድም ሰው፣ በመሠረቱ አንድም ሰው አይቷት አያውቅም። እኔ እንኳን በጨረፍታ ያየኋት በአዳራሹ ውስጥ ባለው መተላለፊያ ማዕዘን በኩል እጥፍ ስትል ነው። በርግጥ ዛሬ የኢንጢቆስቤ የበዓል ዕለት ነው። ሁለቱ ሴቶችም በቪሲታንዲን የአመምኔቶች ገዳም ቅዳሴ ላይ ለመገኘት ስላቀዱ ነው ያየሃቸው። በታላላቅ በዓላት ጉዞ ካልሆነ በስተቀር አዛታ እንደሃብት በቤቱ ውስጥ ደብቆ ነው ያስተመጣት»

«እንደዚያ ከሆነ ትክክል ነው። መደበቅና መጠበቅ ያለባት ነች» አለ ጆን ባፕቲስት።

«ቆንሲሉ አኮ ጭራቅ ነው» ሲል ሜትር ዝረሚ መለሰ።

ከሆደ ባሻ የድምፅ ቅላጼው በመነሣት ዝረሚ ቂሙን እያመነዠከ ይመስላል።

ጆን ባፕቲስት በመከዳው ግንብ ላይ እግሮቹን አመሣቅሎ ወንበሩ ላይ ተዘርግቶ ተቀምጧል። ከጣሪያው በላይ፣ ከበረንዳው መቀመጫ አናት በላይ ያለው ሰማይ፣ ሃምራዊ እየመሰለና በመጥለቅ ላይ ያለችው ፀሃይ እንደ ሃረግ የተንሻፈረገገውን ደመና እያቀላችው ነው።

ከርሱ መኖሪያ ሠፈር በላይ ያለችው ወጣት ልጃገረድ ያጋጣሚ አንፅብራቂ፣ ትውስታውን ወደ ቬኔስ፣ ወደ ፖርማና ወደ ሊዝቦን ወሰደበት። በርግጥ በነዚህ ከተሞች ውስጥ ማንኛውም ነገር ይኖካ ነበር።

ጆን ባፕቲስት፣ ከዙሪት ሕይወት የሚገኘውን መልካም ነገር መያዝ የጀመረው ገና ከመሠባትነቱ ጊዜ ጀምሮ ነው። ከአንድ የተለየ የህብረተሰብ ክፍል የመደብና የሥልጣን እርከን ውጭ በመሆኑ ይህ ተጓዥ ነፃ ሰው ነው። ስለሆነም ከማንም ጋር በእኩልነት የመነጋገር ፅድል ያለው ነው። መነሻ ምንጩ ምንም ይሁን ምን፣ አንድ ዘዋሪ ሰው ብልህ ከሆነ የልዑል ኅሊና ወይም የልዕልት ፍቅረኛ ሊሆን ይችላል። ሌላው ቢቀር ይህ ሊሆን እንደሚችል በዓይነ ህሊናው ሊመለከት ይችላል። ፖንሴ ግን፣ ሎሌነትና ሊሆን ይችላል ብሎ የወደፊቱን ነገር

የማሰብ ጉዳይ ይጉድለዋል። እነዚህ ከዚህ በላይ የተነገሩት ሁሉ እርሱ በኖረባቸው ክተሞች በተደጋጋሚ እውነት መሆናቸውን አረጋግጧል።

ፖንሴ ወደ አገሩ ባህልና ሥርዓት ውስጥ ተመልሶ ሲገባ፣ ተገቢ ቦታውን ይይዛል። ልክ እዚህ ካይሮ በሚገኘው የፈረንሣይ ማህበረሰብ ውስጥ እንዳሰው ዘር ማንዘሩን ለመደበቅ ቢሞክርም፣ የአንዲት አገልጋይና የአንድ ማንኑ የማይታወቅ ሰው ልጅ ከመሆኑ ሌላ ማንም አይደለም። በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው የልዩነት ቦታ አዲጋች እንቅፋት ነው። እንዲህ ያለው እንቅፋት ደስታን ይገፍፋል። ዛሬ ያየውን የተለየ እንግዳ ፍጡር ይቅርና ህልሙም እንኳ የርሱ እንዳይሆን ይገፍፍበታል።

«ይህ ኩተማ እየሰለችህ አልመጣም?» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቀ።

«በሌላ ልለውጠው ብችል ደስታውን አልችለውም ነበር» በማለት በተመማሃይ ሃሣብ ውስጥ ነጉዶ የነበረው ሜቅር ዝረሚ መለሰለትና «ማን የት መሄድ እንችላለን?» ሲል አከለ።

በምሥራቃዊው የሜዲተራኒያን አገሮች ሁሉ፣ ሁሉም እንደሚያውቁት እዚህ ያጋጠማቸውን ዓይነት ቅሬታ ይጥምማቸው ነበር። ይህ የሚሆነው አካባቢው ባዕድ ስለሚሆንባቸው ሣይሆን፣ የራሣቸው አገር ተወካዮቻቸው በዚያ አካባቢ መገኘታቸው ሲበዛ የርኅ ዝንቦችና ግዲለሾች ስለሚሆኑባቸው ነው። ለዚህ ሁሉ መፍትሄው ወደ አውሮፖ መመለስ ነበር። እዚያ በርግጥ ያለ አንዳች የሥራ ፈቃድ፣ እዚህ የጀመሩትን የእጅ ሥራ ጥበብ መያቸውን፣ በማያቋርጥ የሕግ ክትትል ሥር ሆነው መሥራት አይችሉም።

«ይበልጥ በራሣችን የምንተማመን አንድነሆን ደፍረን ወደ አዲሱ ዓለም መሄድ ይኖርብናል» አሰ ጆን ባፕቲስት።

ይህ ድንቅ ሃሣብ ይመስላል። ስለሆነም ረጋ ባለና በሰከነ መንፈስ በሚገባ ለመነጋገር እንዲችሉ፣ በጠመዘማዛው ጉዳና አድርገው ወደ አሮጌው ካይሮ ክፍል ደስ አያላቸው

የጀስዊቱ ቄስ፣ ወደ ክፍላቸው ሂደው ፅረፍት ለማድረግ እንዲችሉ እንዲፈቀድላቸው ጠየቁ። ሙሴ ዲ ማይሌ፣ ክርናቸን ጠረጴዛው ላይ አስደግፎ፣ ውስጡ በሃሴት ተሞልቶ፣ ብቻውን ቀረ። የኤምባሲ መክፈትን ጉዳይ ከጠቀሱበት በኋላ ሙሴ ማይሌ ፣ የቄሱን ሴሎች ማብራሪያዎች ማዳመጥ ትቶ ነበር።

ይህ የኤምባሲ መክፈት ጉዳይ በቆንሲል ዲ ማይሌ ላይ ያልታሰበ ድንጋጤ ፈጥሮበታል። ነገር ግን ስሜቱ እንዳይነበብበት በከፍተኛ ጥረት ሊደብቀው ሞክሯል። በከፍሱ ውስጥ ብቻውን ለመቆየት እንዲችል በማለት ጠባቂውን አሰናብቶ፣ በውስጡ የታፈነውን እምባውን ሰቀቀው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ አስተናጋጁ መጥቶ በአንድ ትልቅ አልጋ ላይ ለመተኛት እንዲችል ረዳው። ይሁን እንጂ ሀሊናውን ስቶ እንደተኛ ቀረ።

ይህ ሁሉ ሲሆን የዲፕሎማቱ ባለቤትና ሴት ልጁ ወደ ቪሲታንዳይን የአመምኔቶች ገዳም ካደረጉት ጉዞ ገና መመለሳቸው ነበር። የተከፋውን ቆንሲል እንደተመለከቱ ዙሪያውን ፈጥነው ከበቡት።

ማዳም ዲ ማይሌ፣ ከቤት የምትወጣው ከስንት አንዴ ነው። በቤቱ ውስጥ ካሉት ክኖሎች አንዱ፣ ሙሉ በሙሉ ሰርስዋ አገልግሎት ብቻ እንዲውል ተደርጓል። የዚህን ክፍል አንድ ጥግ የፀሎት ቦታ አድርጋዋለች። የተለያዩ የሴት ፅቃዎችዋንና የልብስ መስፊያ መኪናዋን በሌላው ጥግ አስቀምጣቸዋለች። በነዚህ ቦታዎች ላይ ተራ በተራ እየተገኘች የሚሰማትን ቅሬታ፣ ጥያቄም ሆነ ምሥጋና ትናገራለች። ባሏን በፍፁም ታማኝነት ታመልከዋለች። ይህ ባህርይ ዳብሮባት የወደፊቱን ሕይወት በጨለምተኝነት እንድታስበው አድርጓታል። ይህች ምስኪን ሴት፣ ተራና የማይረቡ የቆንስላውን ችግሮችና ኑሮ እንደአስደንጋጭ አደጋ ማሰብና መገመት ጀምራለች። እንዲህ ያለው አስተሣሰብ ያደረባት፣ ሙሴ ዲ ማይሌ ራሱ የሚያጋጥመውን ማንኛውንም ዓለማዊና የሥራ ግጭት ሁሉ እያጋነነና እያስፈራራ ይነግራት ስለነበረ ነው። እንዲህ ባለው ሕይወት ውስጥ ስለኖረች፣ የሚነገራት ሁሉ፣ እንዲህ እንደዛሬው አንድ ቀን ባለቤቷ ዝርግት እንዳለ እንደሚቀር እንድትገምት ያደርጋት ነበር። ይህ እንደሚደርስ ብትገምትም፣ ከሆነ በኋላ እርሷ ልታከናውነው ስለሚገባት ጉዳያም እንዲሁ አንድ ቀን እንኳ ሳታሰላስል ቀርታ አታውቅም። አሁን ግን ባጋጠማት ድንጋጤ አልጋው እየዘረች ማልቀስዋን ቀጠለች። ወጣቷ ልጅ ግን አዕምሮዋን ሰብስባ፣ አለንጋ የመሰሉ ጣቶችዋን በመጠቀም በአባቷ አንገት ላይ የታሰረውን ክራቫት ለማላላት ሞከረች።

ሙሴ ማቹ ዱካው ሳይሰማ መካከላቸው ከች አለ። የቆንሲሉን ሁኔታ ከተመለከተ በኋላ ሃኪም እንዲጠራ ሃሣብ አቀረበ። ሁለቱም ሴቶች ሃሣቡን ተቀበሉት።

«ይሁን፣ ግን ማን አለ?» ስትል ወጣቷ ማዳሞዜል ዲ ማይሌ እየፈራች ጠየቀች።

«ፐሳኩስ?» በማለት ሙሴ ማቹ ዝቅ ባለ ድምፅ ጠቆመ።

ቆንሲሉ፣ በርግሎ ብድግ ብሎ ተቀመጠ።

«አሱ አይሆንም! » ክሴኮንዶች በኋላ ፍፁም እንደዳነ በመግለፅ በአንድ መክዳ ላይ ተቀመጠ።

የአንድ ሰው ስም ምን ያህል አስደንጋጭና አስፈሪ እንደሆነ ከዚህ መረዳት ይቻላል። ዶክተር ፖሳኩ፣ የአንድ የመርከብ ላይ የቀዶ ጥገና ሃኪም ነበረ። በዚሁ ጊዜ ከአንዲት ተዋናይት ፍቅር ይዞት ተከትሏት ይመጣል። ተዋናይቷ ወይዘሮ በሞት ስትለይ፣ እርሱ ካይሮ ውስጥ ያለረዳት ይቀራል። የካይሮ ሰዎች በሙሉ የሚያውቁት፣ የመጨረሻው እውነተኛ ሐኪም ከአራት አመት በፊት አነሩን ለቅቆ ከሄደ በኋላ ለፈረንሣውያን ማህበረሰብ አባላት የህክምና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ የተፈቀደለት ባለሙያ ዶክተር ፖሳኩ ብቻ ነበር። እንዳለመታደል ሆኖ ስለመድሃኒቱ ያለው አስተሳሰብ ጊዜ ያለፈበት ነበር። ዕውቀቱም የተስተካከለ አልነበረም። የሕክምና ዘዴውም ጭካኔ ያለበት ነበር። በነዚህ ምክንያቶች የተነሣ፣ ማንም ሰው ስለህክምና ሲያማክረው ፍቃደኛ አልነበረም። ምንም አይነት የጤና መታወክ ሲደርስ፣ ሐኪሙ ዶክተር ፖሳኩ ነው ከተባለ፣ ልክ አንድ ሰው የራሱን ትንፋሽ ዋጥ ሲያደርግ እንደማይታፈነው ሁሉ፣ የፈረንሣውያን ማህበረሰብ አባላትም በርሱ ላለመታከም ሕመማቸውን ዋጥ አድርገው ይችሉት ነበር። ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ነጋዴዎችና ተራ ሰዎች፣ ሌሎች ፈዋሾችን መፈለግ ጀመሩ። ለአይሁዳውያንና ቱርካውያን አስመሣዮች፣ ዝነኛው መድሃኒት ቀማሚ ጆን ባፕቲስት ፖንሴ ሆነ። ይሁን እንጂ ህክምናን በተመለከተ እነዚህን ህገወጥ ሰዎች ማንም አንዳይጠይቃቸው ቆንሲሉ በግልፅ ከልክሏል። በዚህ ግዚያ፣ ከእንግዲህ በኋላ፣ ካይሮ በሚቆይባቸው ጥቂት ዓመታት፣ ለሌሎች ምግቤ ሆኖ ለመገኘት ሲል ህመሙን ሊያስታግሱለት የሚችሉ እንኪን ቢሆኑ ወደነርሱ ድርሽ ላለማለት ወስኗል።

በቆንሲሉ የማገገም ፅድለኛነት፣ እዚያ የነበረው ሁሉ የእፎይታ ትንፋሽ ተነፈሰ። የክፍሉም ድባብ ሰላም ሰፈነበት። ማዳም ዴ ማይሌ ቡና እንዲቀርብ አዘዘች።

አራቱም ሠዎች ቡና ይዘው ክብ ሠርተው ተቀመጡ።

«ይህን ያህል የሚያስከትለው መዘዝ የለውም። ምግቤን ትንሽ ከበድ ይል ነበር። የአየሩም ጠባይ ምንም አይልም። ወይነ ጠጁ ግን . . . » ሲል ቆንሲሉ አስረዳ

ከዚህ የበለጠስ ምን ሊናገር ኖሯል? ለርሱ የተነገረውን ታላቅ ምስጢር ለነዚህ ለፍላፊ ሴቶች መንገር እንደሆነ አስቸጋሪ ነው። ቢነገር እንኳ ምናልባት ለማቼ ነው። አምን፣ ማቼ ይህን ምስጢር ማወቅ ይገባዋል። በመጪው ጊዜ ውስጥ ይህ ሁሉ ውርስ፣ ብዙ ጥረት ይጠይቅ ይሆናል። ለዚህ ደግሞ ረዳት ያስፈልጋል። የጀስዊቱ ቂስ ይህን በርግጥ ይረዳሉ። ማቼ፣ ያለ አንዳች ገደብ ሲያገለግል የኖረና ፍፁም ታማኝ ሰው ነው። ከወጣቷ ሴት ልጁ ጋር ማቼ ሊነጋገር የተመለከተው ቆንሲል፣ ተደፈርኩ በሚል ሁኔታውን አልወደደውም። ለምሣሌ፣ እዚህ እፊቱ እንኳ፣ ይሽው አንዳቸው ወደ ሌላኛው ፊታቸውን አዙረው፣ የቡና ሲኒዎቻቸውን ሙጭጭ አድርገው ይዘው ይታያሉ። በርግጥ ምስኪን ሕፃን ስለሆነች እንዲህ ባለው ጉዳይ ላይ አንዳችም ስህተትና ጥፋት አይታያትም። ማቼ ግን ማድረግ ከሚገባው በላይ አጥብቆ እየተመለከታት መሆኑን ምሎ መናገር ይቻላል።

ከማዳሞዜል ዴ ማይሌ ጋር ለቅርብ የፍቅር ግንኙነት ማይሆን፣ ለጉርብትናው ሲባል ግንኙነት እንዲኖረው የተፈቀደለት ወጣት፣ ሙሴ ማቼ ብቻ ነበር። ምንም እንኳ ከእንቅልፉ ሲነቃ ደስ የማይል ጠረኑን ትቶ ቢሄዛና ሲበዛ አስቀያሚ ሆኖ ብታገኘውም፣ ወጣቷ ልጃገረድ ከርሱ ጋር መጫወትን ትደሰትበታለች። ማቼ የተለየ ሰው ነው። ሲያዳምጣት በከፍተኛ ፍላጐት ነው። አሁን ግን እርስዋ ተገልላ በምትገኝበት ሁኔታ ላይ ጭውውትን ውብ ሊያደርግላት ስለሚችል ይህ በእውነቱ በቂ ነው። ሙሴ ማቼን በተመለከተ ግን እርሱ የራሱን የሕይወት ጉዳና በሚስማማው መልክ መርጧል። ያጋጠመውን የማዕረግ ዕድገት ዕድልም፣ አባቷ በእጁ ውስጥ ይዞባት ላለች አንዲት ወጣት ሴት ሲል ሊያባክንና ለድርድር ሊያቀርብ አይሻም። ይሁንና፣ በጣም አልፎ አልፎ፣ በርሱ በኩል የግድ መከናወን ያለበት ጉዳይ ሲኖር፣ ልዩ በሆነው ውበቷ፣ አቋሟና ወጣትነትዋ ሳቢያ ስትመጣበት ጥውልግልግ ይልላታል። እርሱ ከውስጡ ባይሆንም በጥልቀት ይመለከታታል። እርሷም ከውስጣ ባይሆንም ምላሹን በደስታ ትሰጠዋለች። እንዲህ ያለው ሁኔታ በአባቷ ዓይኖች ውስጥ ከወንጀል ያነሰ አይደለም።

«ከሙሴ ማቼ ጋር ለብቻችን የአፍታ ቆይታ እንዲኖረን ይፈቀድልናል?» ሲል ቆንሲሉ ጠጠር በሚል ድምፅ ጠየቀ።

«ማቼ! ስለባህሪህ ልናገራቸው የምችላቸው ብዙ ነገሮች አሉኝ። ነገር ግን አሁን ጊዜው አይደለም።»

ቆንሲሉ ንግግሩን በቀጣ ጀመረው። «ማቼ! ልብ ብለህ አስተውል። በችግር ጊዜ እንደሚኖሣ እንጂ አንዳችም ችሎታህን በማሰብ እንዳልሆነ፣ እደግመዋለሁ፣ በችግር ምክንያት ስለሆነ እጅግ ከበድ ያለ የፖለቲካ ምስጢር ላከናልህ ነው። ለዚህ ደግሞ ብታት ያለህ መሆንህን ማሣየት ይጠበቅብሃል። ይህ ካልሆነ ደግሞ ከካድከው ሰው አስፈሪ ቁጣ የሚሸሸግህና የምትድንበት አንዳችም ጉድጓድ በምድር ላይ አይኖርህም።»

ይህን ተናግሮ፣ ቆንሲሉ፣ አመልካች ጣቱን ወደ ሉዊስ አሥራ አራተኛ ሥዕል ቀሰረ። ወጣቱ ማቼ፣ አፍንጫው ጉልበቶቹን እስኪነካ ድረስ በተቀመጠበት ሆኖ ዝቅ በማለት ታዛዥነቱን አረጋገጠ።

4

«አሁን በነፃነት ልገልፀው በማልችለው ምክንያት ንጉሡ ወደ ኢትዮጵያ አንድ ኤምባሲ ለመላክ ወስነዋል» ሲል ሙሴ ማይሌ፣ ዝቅ ባለና በጮሪነነ ድምፅ ንግግሩን ጀመረ።

«ይህን በተመለከተ ክቡርነትዎ ስምና አንድ ደብዳቤ ልከው ነበር» አለ ሙሴ ማቼ

«ትክክል ነህ። ወደዚያ አገር ዘልቀን መግባት የምንችልባቸውን የተለያዩ ዘዴዎች ሚኒስትሩ ጠይቀውኝ ነበር። በእግርጥ ጉዳዩ አሁን በቤተመንግስቱ ተቀባይነትን አግኝቷል። ያን ጊዜ ደርሼበት የነበረውን የድምዳሜ ሃሳብ ለመሆኑ ታስታውሰዋለህ?»

«ሁለት መንገዶችን ጠቁመው ነበር። አንደኛው፣ በጂዳ በኩል ጠረፉን ተከትሎ በባህር ላይ ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን በሲናር ንጉሣዊ ግዛትና በተራሮች ተጉዞ፣ በየብስ ላይ የሚል ነበር»

«ብዙ መረጃዎችን ደህና ታስታውሣለህ ማቼ። በነዚህ ሁለት አማራጭ መስመሮች ላይ የነበረኝን የወደፊት ምልከታስ ታስታውሣለህ በባህር ከተባለ፣ ወደ አገሩቱ የሚያስገባው መስመር ከቱርኮች ጋር ስምምነት ባለው የመሰሊም ገዥ የተያዘ ነው። የዚህ ገዥ አብይ ሥራው ወደዚያች አገር አንድም አውሮፖዊ ክርስቲያን በተለይም ካቶሊካዊ ዘልቆ እንዳይገባ ማገድ ነው። ባለፉት ሃምሣ አመቶች ይህን እንቅፋት ያስወገደው የለም። እንደለማሁት፣ መከራ ያደረጉት የመጨረሻዎቹ ቀሣውስት እንዲገደሉ፣ አንገታቸው ተቆርጦና ራሣቸውም ተሳጭቶ ለኢትዮጵያው ንጉሥ በአገልግል እንዲላክ ትዕዛዝ ሰጥቷል።»

ሙሴ ማቼ ፊቱን በጥላቻ አጨማድዶ ሲያበቃ፣ ከኪሱ ውስጥ መሃረቡን አውጥቶ አፍንጫውን ለአጭር ጊዜ ሜን አድርጉ ያዘ።

«የየብሱም መስመር እንደዚሁ ፍፁም መጥፎና የሚሰቀጥጥ መሆኑ ተረጋግጧል። በመከራ አቋርጦ ወደዚያ አገር የገባው ከስንት አንድ አውሮፖዊ ግን፣ ሕዝቡ ንጉሥ እያለ የሚጠራውን ንገሠ ነገስት በቀጥታና ፊት ለፊት ለማግኘት ችሏል። ሆኖም ይህ የተሣካላቸው

ሰዎች ቀሪውን ዘመናቸውን በንጉሠ ነገስቱ ቤተመንግስት ውስጥ እስረኛ ሆነው ያሣልፋሉ። ከዚህ ሌላ፣ በጣም ብዙውን ጊዜ ካቶሊካውያን መሆናቸው ሲረጋገጥ በአመፅ በሚነሣው ሕዝብ በድንጋይ ተወግረው ይገደላሉ»

«ያለ ጀስዊቶች ይህ ሊሆን የሚችል አይደለም» በማለት ሙሴ ማቼ እያዘነ ተናገረ

«አሸሸሽ» አለ ቆንሲሉ ፊቱ ፍም እየመሰለ።

ማንም ሰው ለአዳራሹ ውስጥ የሚነገረውን እንደማይሰማ አይቶ ለማረጋገጥ፣ በዝግታ ተራመዶ በሩን ከፈተው።

«አሁን እዚህ ያሉን እንግዳ ከነርሱ አንዱ እንደሆኑ በሚገባ የምታውቅ ይመስለኛል። ከዚህም በላይ እኒህ ቄስ፣ ከንጉሡ የንስሃ አባት ጋር የቅርብ ዝምድና አላቸው»

«ይህም ቢሆን ያው ነው። እዚያ ምን እንደተፈፀመ ሁሉም ማወቅ ይገባቸዋል»። ሲል ሙሴ ማቼ ዝቅ ባለ ድምፅ ተቃወመ።

«ያ ከሃምሣ አመት በፊት ነው»

«ይህም ቢሆን ብልህነትና ግዴለሽነት የተቀያየጡበት ያልተለመደ አሠራር ነው። በርግጥ ንጉሡን አግምነው፣ ሃይማኖቱን አስለውጠውትና አገራቱንም በሙሉ አሸንፈው፣ እንዲገዟቸውም አድርገው ነበር። ነገር ግን በዚህ ግቢያ ተሳድደው ወጥተው ለዘለአለመ· የደረሱበት ሳይታወቅ ቀርቷል። የሄደቱ ወይም የነገሩ ፍፃሜ የሆነው አንድም ካቶሊክ እንዳችም ዓይነት ሰበብ ሰጥቶ ወደ አቢሲኒያ እንዲገባ አለመፈቀዱ ነበር። አሁን በዚህ ቤት በንብኝት ላይ የሚገኙት ካህን፣ ወደዚያ እንመለስና እንሞክር ይሆናል የሚል የጅል ሃሣብ ያቀርባሉ ብለው ክቡርነትዎ እንደማይነግሩኝ ተስፉ አለኝ»

«የለም፣ ማቼ፣ ካህኑ ብቻቸውን ወደዚያ ለመሄድ አላቀዱም፣ የርሣቸው ፅቅድ አንተ ልታስበው ከምትችለው በላይ እጅግ አስገራሚና አስደንጋጭም ነው»

የቆንሲሉ የታችኛው ከንፈር በትንሹ መንቀጥቀጥ ጀመረ። ቀደም ሲል ታውክ የነበረው ጤንነቱ እንዳየነረሽበት በመፍራት እጁን በጠረጴዛው ላይ አሣረፈ።

«አሁን እኔን ሊልኩኝ አሰቡ።»

«እርስዎን፣ ክቡር ሆይ? ይህ ፍፁም ሊሆን የማይችል ነው።» ሲል ሙሴ ማቼ ከተቀመጠበት ሥፍራ ዘሎ በልሎ ተነሣ።

ሁሉቱ ሰዎች፣ ፊቶቻቸው ቀልተው፣ ለጥቂት ጊዜ እንቅስቃሴ አቋርጠው እርስ በርሣቸው ተሩጥጠው ቆሙ። ከማዳሞዜል ዱ ማይሌ ጋር በዙና ሰዓት ያለጥንቃቄና እንደልቡ የመሆኑ ጉዳይ ያስቆጣው ቆንሲል፣ አሁን ባልታሠበ አጋጣሚ ወደ ስላማዊና የተረጋጋ መንፈስ ተሰወጠ።

«የጤንነትም ጉዳይ . . . » በማለት እጆቹን አንዲት የቢራቢሮ ነፍሣትን በአየር ውስጥ ለመያዝ እንደሚሞክሩ አይነት እያወናጨፈ ተናገረ

«አዎን፣ አዎን ጤንነቴ ጉዞውን ፈፅሞ መቋቋም የሚችል አይደለም» ሲል ቆንሲሉ ፈጥኖ አረጋገጠ። «የአየር ጠባዩ ደግሞ ያባብሰዋል። በዚያም ላይ ማቋረጥ የሚገቡኝ እጅግ ብዙና ሠፋፊ በረሃዎች አሉ»

ፊቱ በቅፅበት ጠቆረ።

«ነገር ግን ይህን ፊፅሞ አያምኑልኝም። ክቬርሣይለስ አካያ ሆኖ ሱተመለከተው በክይሮና በሱዳን የአሸዋ ምድር መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት የለም»

«ሁሉም ተመሣሣይና አንድ . . . » አለ ሙሴ ማቼ። አዕምሮው አሁንም ያለዕረፍት ይጋልባል።

«ቱርኮች!» ሲል ቆንሲሉ ከፍ ባለ ድምፅ ተናገረ። «የኦቶማን ባለሥልጣኖች እንዲህ ያለውን ተልዕኮ አይፈቅዱም። ስለክርስትና ሃይማኖት መስበክ እዚህ የተከለከለ ነው። በዚህ ላይ ደግሞ የኦቶማን ቱርክ ፖሊሲ፣ አቢሲኒያ በሙስሊም ጉሪቤቶች ምንጊዜም ተከብባ

እንድትቀር የሚል ነው። ካቶሊኮች ከጀርባቸው የሚያደርጉትን ስምምነት ያህል ቱርኮችን የሚያስፈራቸው ሌላ ነገር የለም»

«እርግጥ ነው። ኤምባሲ እንዲከፈት ካስፈለገ ፍፁም በምስጢር መጠበቅና በማይታወቅ ሰው የሚመራ መሆን ይገባዋል» አለ ሙሴ ማቼ

«ከዚህም በላይ አደጋውም ቀላል ነው። ክፍያ እስከተደረገ ድረስ ከአቶማኖች ጋር ማንኛውም ነገር ማደራጀት ይቻላል። ይሁንና ፖሻው፣ የአስፈፃሚነት ደረጃ ያለው የቆንሲል ጽህፈት ቤትን ለመክፈትና ኤምባሲ ሆኖ ለሚንገዝ ሰው ለመፍቀድ ከፍተኛ ገንዘብ ይጠይቃል» በማለት ቀደም ሲል የገለፀውን የራሱን አስተሣሰብ እንደሚቃረን ሳያመዛዝን ተናገረ።

«በአያንዳንዱ የአቋም ለውጥ ላይ መደለያው ብዙ ገንዘብ የሚያስወጣ ሊሆን የግድ ነው»

ሁሉቱ ሰዎች ስሜቶቻቸው በደስታ ጋሉ። ሙቀቱ ሳንቃውን በመክፈቱ መስኮቶች በክፈል ተከፍተዋል። ቆንሲሉ በቃል እየነገረው፣ አንድ አጠር ያለ ማስታወሻ ለመሣፍ ሙሴ ማቼ ብዕርና ወረቀት አነሣ። የማስታወሻው ይዘት በስርዓት የተቀነባበረ መክራከሪያ ነጥቦችን የያዘ ነው። ከነዚህ ሁሉ ዐብይ የሆነው ነጥብ ግን፣ ዲፕሎማቱ ወደ አቢሲኒያ የሚያደርጉት ጉዞ የወደፊቱን ሁኔታ የሚያሰናክልና አሁንም ሱተፈፃሚነቱ እርግጠኛነት የማይኖርበት መሆኑን የሚገልጽ ነው። ማስታወሻውን ደግመው በደስታ አነበቡት። ሙሴ ማይሌ ሁለት ትናንሽ ብርጭቆዎች አምጥቶ፣ የደረቀ ወይንጠጅ ቀድቶ ስለጤንነታቸው ጠጡ።

ወይነጠጁ የመረረው ያህል ፊቱን ኮሶ አስመስሎ፣ ብርጭቆውን ጠረጴዛው ላይ እያስቀመጠ «አልሸሹም ዞር አሉ። በዚያም አልን በዚህ ሁሉም ንጉሡን አለመታዘዝ ነው!» አለ ቆንሲሉ

«አለመታዘዝ አይደለም፣ ክቡር ሆይ! ንጉሡ፣ አቢሲኒያ ውስጥ ኤምባሲ እንዲከፈት ይፈልጋሉ። እርስዎ ይህን ተልዕኮ ሲመሩ አለመቻልዎን ብቻ ያሣያሉ»

«እንግዲያው አንድ ሌላ ተተኪ ማግኘት ይኖርብናል?»

ቆንሲሉ፣ ምናልባት ምርጫውን በኔ ላይ ያሣርፍ ይሆናል በሚል ሃሣብ፣ ማቼ ሲቃ ያዘው። ሠላማዊ ርጋታ የተሞላበት ብሩህ የሕይወት መስመር እየጠበቀው፣ ወደ ሞቱ ለመሄድ የሚፈልግበት አንዳችም ምክንያት እንደሌለው ተሰማው።

ፈጥኖ አስተዋለውና «የምንፈልገው ሰው ጥሩ የስኬት ዕድል ሊኖረው የሚችል መሆን አለበት። ንጉሡ ኤምባሲ ለማቋቋም ብቻ የሚፈልጉ አይመስለኝም። ምላሹንም ይሻሉ። አንድ ዲፕሎማት ለዚህ ጉዳይ ቢመረጥ በጣም ትኩረት ስለሚስብ ከግብፃውያን ወሰን ከቶም ማለፍ አይችልም»

«ትክክል! በመጀመሪያው ደብዳቤያችን ላይ ለሚኒስትሩ የፃፍንላቸውም ይህንኑ ነው» ሲል ቆንሲሉ አረጋገጠ።

ሁለቱ ሰዎች በዘመታ ማሰባቸውን ቀጠሉ። በወንበሩ መደገፊያ ሥር ሲመለከቱት በላብ የወረዛው የሙሴ ማቼ የጥጥ ጃኬት ከብብቱ ሥር ጠቁሯል። ቆንሲሉ ይህን ስለተመለከተ ለአፍታ በጥላቻ ተሞላ። እንደ እውነቱ ከሆነ ልብሱን ወዲያውኑ ሊለውጥ ይገባዋል ሲልም አሰበ።

ቀደም ሲል ሲያውጠነጥነው በነበረው የሃሣብ ፈረስ ላይ ሊጋልብ ቢሞክርም፣ በመካከሉ ሃሣቡን በሠረቀበት ጉዳይ የአስተሣሰቡ አቅጣጫ ስለተቀየረበት፣ «በእውነቱ የምንፈልገው የተግባር ሰው ነው» ሲል በድንገት ጮኸ።

በራሱ ሃሣብ የተገረመው ሙሴ ማይሌ፣ ነገሩን ሣይጨርስ አቋረጠ። የዚህን ሃሣብ አውነተኛነት በመገንዘብ መሴ ማቼም እንደዚያው ግርም አለው።

«እርግጥ ነው። ክቡር ሆይ፣ በጣም ትክክል ነዎት። ንጉሡ የሚፈልጉትን ነገር ሊያቀርብላቸው የሚችል ሰው ይፈልጋሉ»

«ነጋዴ ነዋ!»

የሙሴ ማቼ ፊት በደስታ ፈካ። «ጌታዬ! እንደሚያስታውሱት አንድ የነጋዴ ቅፍለት ከኢትዮጵያ ተነስቶ ካይሮ እንደሚገባ መረጃ ደርሶን ነበር። ይሁንና ይህ ቅፍለት አሁን የት

እንደደረሰ ፋናው አልታወቀም። ምናልባት ከከተማው በስተደቡብ ሲል ተበታትኖ ይሆናል። የዚህ ቅፍለት መሪ ደግሞ በተደጋጋሚ ወደ አቢሲኒያ የተመላለሰ የሙስሊም ነጋዴ ነው»

«ታውቀዋለህ እንዴ?»

«አንድ ጊዜ ካይሮ ውስጥ ሰዎች ለይተው አሳይተውኛል። ቁመናውና አተያዩ ትህትና የተሞላው፣ ሲያዩት ለማኝ የሚመስል ነው። እንደነገሩኝ በመጨረሻው ካደረገው ጉዞው ሲመለስ፣ አምስት መቶ ሺህ ኢኩ ሲያወጣ የሚችል የወርቅ ዳቁት፣ የጥሪኝ ዝባድ፣ የአምበርግሪስ ማዕድን አምጥቷል። ይህን ያገኘው ንጉሡ ባዘዘው ሽቀጥ ልዋጭ ነው።»

ሙሴ ማይሌ ስሜቱ ተነሣስቶበት በክፍሉ ውስጥ ወደ ፊትና ወደ ኋላ መንጐራደድ ጀመረ።

«ለመሆኑ አሁን ካይሮ ውስጥ ይገኝ ይሆን?»

«ይህን አላውቅም። በአጠቃላይ እዚህ የሚገኝ አይመስልም። ነገር ግን እርግጡን ማን ይናገራል። ሰውዬው ንግዱን የሚያከናውነው በክፍተኛ ምስጢር ነው። አቢሲኒያን በተመለከተ መረጃ ሊሰጠን ቀርቶ ሊያነጋግረን እንኳ ፈቃደኛ መሆኑንም ርግጠኛ መሆን አልችልም።»

«ቀስ! ጉዳዮችን ተራ በተራ እናንሣቸው። መጀመሪያ ፈልገህ አግኘው፣ ከዚያ በኋላ እንዴት ሊተባበረን እንደሚገባ እናውቅበታለን?» ሲል ምላሽ የማይሻ ትዕዛዝ ሰጠ።

ቆንሲሉ ቁርጥ ያለ ውሣኔ ላይ ደርሷል። ሙሴ ማቼን ወደ በሩ ይዞት

«በል ወጥተህ ይህን ሰው አሁኑኑ ፈልገህ አግኘው»

በቆንሲሉ ድንገተኛ ጥድፊያ ሀሐፊው ተደናገረ።

«ፈረሴ ያውልህ፣ ተከታይ ዘበኛ፣ ገንዘብና ሌላም የሚያስፈልግህን ያዝ። ሰውዬው በከተማው ውስጥ ካለ አይጡ ገብተህ አምጣው። በነገራችን ላይ ስሙ ማን ይባላል?»

«አረቦች፣ ሃጂ አሊ ይሉታል»

«በል ወዳጄ፣ ሃጂ አሊን ለማግኘት እግዜር ይርዳህ፣ ይቅናህ»

በመጨረሻ ላይ የተነገረውን የቅርበት ቃል ሲሰማ ማቹ ልቡ በኩራት ተሞላ። ቡተልዕኮው ተስፋ ቢቆርጥም ወደ ቅጥር ግቢው ፈጥኖ ። ከአሥር ደቂቃዎች በኋላ ከተማው ውስጥ ገብቶ ሰመጠ።

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ዝግጅት በሌለው አቀራረብ ሃማብ ገብቶት፣ ከሙሴ ማቹ ጋር በመሆን የባፋትን ማስታወሻ አውጥቶ ያብራራለት ጀመር። የጀስዊቱ ቄስ፣ በንቃት ተቀምጠው ተረጋግተው ያዳምጣሉ።

ጥቂት ከተወያዩ በኋላ፣ ወደ አቢሲኒያ የሚሄደውን የኤምባሲ ቡድን፣ ሙሴ ዴ ማይሌ ራሱ እንዳይመራው የሚለውን የቆንሲሉን ሃሣብ አባ ቬርሣው ደገፉ። ይህ አቋም ለቆንሲሉ እፎይታን ሰጠው።

«እውነቱን ለመናገር አንተ ወደዚያ እንዳለብህ ያሰበም አልነበረም» ሲሉ ቄሱ ንግግራቸውን ደመደሙ።

ይህን አስቸጋሪ ጉዳይ በተመለከተ ከቄሱ የቀረበው አስተያየት መልሶ በጠበጠው። ምናልባት ፈርቷል ብለው ጠርጥረውት ይሆን? አንዳንድ ጊዜ፣ እውነተኛ ጀግንነት ስድብን በፀጋ እስከመቀበል ይደርሣልና እርሱም እንደዚያ ታስቦ ከሆነ ለመቃወም ተዘጋጅቶ ነበር። ነገር ግን ጥርሱን ነክሶ ዝም አለ።

«ሌላ ምን አማራጭ ሃሣብ ትሰጠናለህ?» ሲሉ ቄሱ በጥሞና ጠየቁ።

«እንደሚታየኝ ከሆነ ከታላቁ ንጉሣችን ግርማዊ ሉዊስ 14ኛ፣ ይህ ከዚያው ከበቀለበት አገር ሌላ ለማያውቀው ባለዘውድ የኢትዮጵያ መሪ፣ ምንም ዓይነት የአቤቱታ አቀራረብ መልክ እንዳይኖር ነው። እንደነዚህ ካሉ ሰዎች ጋር ግንኙነት ሲጀመር ምን እንደሚጠብቁ የሚያውቅ

የለም። ባለፈው ምዕተ ዓመት የፖርቹጋልን ኤምባሲ እንዳጋጠመው ዓይነት የኛም ኤምባሲ ምርኮኛ ቢደረግ፣ በግርማዊነታቸው ላይ የሚደርሰውን ውርደት ያስቡት። የኤምባሲው መሪ የነበረው ፔድሮ ዴ ክቪልሃም ተይዞ፣ ለአርባ ዓመት እዚያው ታሥሮ ቆየ። በመጨሻም እዚያው ሞተ። ይህን ሁሉ ግስብ እኛ ክምንልከው መልዕክተኛ ይልቅ እኛን የላከን ባለሥልጣን ታሳቅ ነው።»

«አስተማሰብህ ጥልቅ ነው። እኛ ባሰብነው መንገድ ግን አሁን አውተኛውን ኤምባሲ መላክ ማለት የአቢሲኒያ ገዥም በተመሳሳይ ደረጃ እንደምንፈልገው ምላሽ እንዲሰጠን ያገሳል የሚል ነው። ይሁንና የምንሻው የመጨረሻ የውጤት ደረጃ ላይ ሊያደርሱን የሚችሉ ሌሎች ዘዴዎች ካሉህም . . . »

ውይይቱ እየተካሄደ ያለው ሰአባ ቬርሣው በተመደበው በሁለተኛው ፎቅ ላይ በሚገኘው ሰፊ ክፍል ፊት ለፊት ባለው ሰገነት ላይ ነው። ከዚህ ከፍታ ላይ ሆነው ሁለቱ ሰዎች የፈረንሣይ ማህበረሰቦች መኖሪያዎች እጅብ ብለው የሚገኙበትን ዋና ጉዳና ይቃኛሉ።

«እኔ እንደሚታየኝ ኢትዮጵያ ከግብፅ ጋር ጠብቃቸው ያሱንት መደበኛ ግንኙቶች ሰኛ በሚጠቅም መልክ መጠቀም ነው» ሲል ሙሴ ዴ ማይሌ በልበ ሙሉነት ተናገረ።

«እነዚህ የምትላቸው ግንኙቶች ምን አይነት ናቸው?»

«ሁለት ዓይነት ናቸው። በየጊዜው የአቢሲኒያው ንጉሠ ነገስት፣ የአሌክሣንደሪያ ኮፕቲክ ቤተክርስቲያን ፖትሪያርክ አንድ አዲስ አቡን መርጠው እንዲልኩለት መልዕክተኛ ይልካል። ይህ ዓይነቱ ልማድ ዘመናት ያስቆጠረ ነው። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የበላይ መሪ፣ አቡን ይሰላል። ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የበላይ አባት ሆኖ የሚላክው፣ ግብፃዊ ኮፕቲክ ነው። በዚህም ይህ ዕድል ቡጣም አስተኛና ልንተማመንበት የማንችልበት ነው።»

«ሌላው ዕድልስ?»

«ነጋዴዎች ናቸው። በአንዳንድ ዓመት ላይ ከአቢሲኒያ ተነስቶ ሽቀጦችን ካይሮ ውስጥና እግሬመንገዱንም ባሉ ቦታዎች ለመለዋወጥ የሚመጣ ቅፍለት አለ»

«ንጉሡ ከሙስሊሞች ጋር በጦርነት ላይ የሚኖር ነፀር የሚመስለን»

«እኛም ብንሆን ከቱርኮች ጋር በጦርነት ላይ ነው ያለነው። ያም ሆኖ ይኸው እርስ‌ምና እኔ በዚህ ሰገነት ላይ በሰላም ተቀምጠን እንጫወታለን። ግለሰቦች ሲያከናውኗቸው ለሚሳካሯቸው ጉዳዩች መንግሥታት ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል። አንዳንድ ግንኙነቶች ደግሞ ጨርሶ የማይበጠሱ ናቸው አባቴ»

«ክቡር ሆይ» አሉ ቄሱ። በዲፕሎማቱ ላይ ያላቸውን ሙሉ እምነት በሚያረጋግጥ አስተዋይ ፈገግታ፣ «የንጉሡን እቅድ ወደፊት ሊያራምድ የሚችል መፍትሄ እንድትጠቁም ሁሉንም ነገር ባንተ ትከሻ ላይ ጥያለሁ።»

ቆንሲሉ ራሱን ዝቅ አድርጉ እጅ ነሣ። ውስጡ ግን በትህትና ኩራት ተሞላ።

❧

ሙሴ ማቼ ወደ አሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ ተመለሰ። ከመጠን በላይ ስላላበው ፀጉሩ በራሱ ላይ ተጣብቆ፣ እርሱም በላብ ተጠምቆና የደረቀው የላብ ጨው በጉንጩ ላይ መስመር አበጅቶ፣ ይቅርታ በመጠየቅ ወደ ቆንሲሉ ጽህፈት ቤት ዘሎ ገባ።

«አገኘሁት» ሲል በደስታ ምስጢሩን ገለፀ

«ነጋዴዎችንን?»

«አምን፣ ሃጂ አሊን ራሱን?»

አንድ አጁን በልቡ ላይ ጫን አድርጉ፣ ቀስ በቀስ ትንፋሹ መለስ አለለት።

«ከተማዋን በሙሉ አለክኪት። ሁሉም ሰው ሲለኝ ነፀር። እንዲያው አንደዕድል ሆኖ አንዱ መረጃ አቀባዩ ትናንት አይቶት ኖሮ ነገረኝ»

«አሁን የት አለ? » ሲል ቆንሲሉ ክፍተር ብሎ ጠየቀው።

«በእንግዳ መቀበያው ክፍል እየጠበቀ ነው። አስቀድሜ ግን ልገልፅም የምፈልገው ነገር አለኝ . . .» ማቼ ንግግሩን አረመና «ክቡር ሆይ! አለ» አለ። ትንፋሹ መለስ ሲልለት ወደሚታወቀው ሥነ-ሥርዓታዊ ባህርይውም ተመለሰ። በምንም ዓይነት ሁኔታ የበታቾች ነፃ እንዲሆኑ መሴ ዴ ማይሌ አይፈቅድም።

«ወስላታና ብልጣብልጥ ቀበሮ አይነት ነው።» ሲል መሴ ማቼ ተጠለ። «ስለ አቢሲኒያ አንዳችም ቃል እንድተነፍስ አልፈቀደልኝምና ቃል ገብቼለታለሁ»

«እና ታዲያስ?»

«አንድ መቶ ኤኩስ»

«እውነት?» ቆንሲሉ እንዲቀጥል አደረገው።

«ይህን ያህል ካገኘ ይናገራል»

«አንድ መቶ ኤኩስ ሊያወጣ የሚችል ምን ሊነግረን ይችላል?»

«ክቡር ሆይ፣ የተሰማማሁበትን ጉዳይ እንዲያከብሩልኝ እማፀናለሁ። ይህ ካልሆነ ከሞት የከፋ ውርደት ይጥመኛል»

«እሺ ይሁን፣ እክፍላለሁ፣ ግን ምን አለ?»

«አስከ አሁን አልተነፈሰም»

«አየቀለድክ ነው!» አለ መሴ ዴ ማይሌ ክፍሉን ለቅቆ የሚወጣ እየመሰለ።

«ክቡር ሆይ! እባክዎን ይናገራል። ንጉሡ ምን እንደሚፈልግ ይነግረናል» ሙሴ ማይሌ ለእፍታ አመነታ።

«እሺ እንግዲያው ምን ትጠብቃለህ? አስገባው!» አለ በቁጣ

ሃጂ አሊ፣ የጉሣ ምንጫቸው ይህ ነው ተብሎ ሊነገርባቸው ከማይችሉት ሰዎች አንዱ ነው። ማንም ሊገምተው ከሚችሰው በላይ ቀጭን ነው። አጥንትና ቆዳ ክሆኑ እጀቹ፣ ጉድጓድ ከመስሉት ጉንጮቹ ጋር ሲመሰክቱት የሚሰበር ነገር ይመስላል። አፍንጫው መንበቀ ሲመስል፣ የአይኖቹ ቆቦች ትላልቅ ናቸው። የሰውነቱም ቀሰም መዳብ መሰል በመሆኑ የመን ውስጥ የመናዊ፣ ግብፅ ውስጥ አረባዊ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ አበሻና ሌላው ቀርቶ ህንድ ውስጥ ህንዳዊ ያስመስለዋል። ከዚህም ባሻገር፣ በሐሩር ፀሃይ ቆዳው የጠቆረበት ሰው ነው ተብሎ፣ አውሮፖዊም መባል የሚችል ነው። አረቦች የሚለብሱትን የተሰየና ሰማያዊ የወታደር ሸሚት ለብሷል። አረንጓዴ ገምባሌ ያለው ጫማ ተጫምቷል። የቀኝ ጆሮው ተበስቶ የወርቅ ቀሰበት ጉትቻ አለበት። የቀንሲሉን እጅ በሁለት እጀቹ መሃል ተቀብሎ በርግቶ ያዛቸውና ሦስት እጥፍ የሚሆን የታዛችነትና የአክብሮት ሁኔታ ካሣየ በኋላ፣ የቀኝ እጁን በራሱ ልብ ላይ አሣርፎ ሲያበቃ ጣቶቹን በመሣም ሠላምታውን ፈፀመ።

መሉ ማይሌ፣ እንዲህ ያሉትን የተሰያዩ የሰላምታ አቀራረቦች የመቀበል ልምድ ቢኖረውም፣ ሁልጊዜም አሰልቺ የሆኑትን የሰላምታ አቀራረቦች ላለመቀበል ሳይገልፅ አያልፍም።

መሉ ማቼ፣ ስሁለቱም እያስተረጉመላቸው ውይይቱ በዝግታ ጀመረ። ሃጂ አሊ፣ የቀንሰላውን ጽሕፈት ቤት ማሸብረቅ ከሥዕሉ በመነሣት ሲፈርጀው፣ የንጉሡን ውብ ቁመናና የተጋበዘውን ከቆንጆር አበባ የተቀመመ ጣፋጭ መጠጥ አደነቀ። ምንም ያህል የበዛ ሃብት ቢኖረውም፣ ተቀምጦ የሚውል ሰው፣ በሚተኛበት ጊዜ ክበላዩ ሆነው በጓደኝነት ለሚጠብቁት ከዋክብት ካሣ መክፈል አለበት በማለት አስተያየቱን ቋጨ። መሉ ዴ ማይሌ፣ አስተያየቱን በትህትና ተቀበለው። ይህም ሆኖ ውይይቱ ሊሣካ አልቻለም።

ከመሉ ማቼ በተሰጠው ምልክት ቆንሲሉ በጥግ በኩል ካለው ባለግጣም ሣጥን አንድ የቆዳ ቦርሣ አወጣ። ቦርሣው ቃል የገባውን ገንዘብ መጠን ይዟል። መሉ ዴ ማይሌ፣ ለግመል ነጂው ሰጠው። ተቀባዩም ወዲያውኑ ሰወረው። ከዚህ በኋላ፣ ሃጂ አሊ ስለንጉሡ ማውራት ጀመረ። በአሁኑ ጊዜ ዘውድ ጭኖ ያለው ንጉሠ ነገስት፣ አያሱ ይባላል። ይህ

የርሱ መጠሪያው ነው። ዕድሜው አርባ ዓመት ይሆናል። ሃይለኛ ጦረኛ ነው። ብዙ ታላላቅ ጦርነቶችን ተዋግቷል። አሁን ግዛቱ ሰላም ነው።

«ኢትዮጵያውያን የሚፈልጉት አንዳችም ነገር የለም። አገራቸው የሚፈልጉትን ሁሉ ታቀርብላቸዋለች» ሲል ቀደም ብሎ መሉ ማቼ ላቀረበው ጥያቄ ሃጂ አሊ መለሰ።

«ይሁን እንጂ ተመልሰህ የሆኑ ነገሮችን እንድታመጣለት ንገሠ ሳይዋዋልህ እንዳልቀረ ይገባኛል» አለ ቆንሲሉ ሆን ብሎ

የሃጂ አሊ መልሱ አጭር ነበር።

«እንደሚለው፣ እቃዎች አይደለም» ሲል መሉ ማይሌ አስተረጉመ።

«ምን ማለቱ ነው ዕቃዎች አይደለም ሲል? ታድያ ምንድነው?»

«ይህን እኔ አላውቅም ክቡር ሆይ፣ ምናልባት እንስሳት ይሆኑ?»

«አርሱት ጠይቀው»

መሉ ማቼ ጥያቄውን ተርጉሞ ነገረው። በዚህን ጊዜ ነጋዴው ጭንቅላቱን ወደ ኋላ ወጥሮ ተንከተከተ።

«የዚህን ደስታ ምክንያት ማወቅ እንችላለን?»

«በግልፅ ለመናገር ምንጩ ጥያቄህ ነው» አለ መሉ ማቼ

«ንጉሡም ምንም እንደማይፈልግ ነገርኳችሁ። እናንተ ግን እንሰሳት ይሆኑ? ትላላችሁ። ይህ በርግጥ አስቂኝ ነው» አለና ስርቅ አያለው ሃጂ አሊ መሳቁን ቀጠለ።

«ጌታዬ» አለ መሉ ዴ ማይሌ፣ ተበሣጭቶ። «የጨዋታ ስሜትህን መሉ በመሉ እንፈሰሰሁ። ይሁን እንጂ ማወቅ የምፈልገው፣ ወደ ኢትዮጵያ ስትመለስ ዕቃዎች ወይም

እንሰሳት ካልሆኑ ምን ልትወስድ እንዳሰብክ እንድትነግረን ነው። ይህን ልትነግረን ተዋውለናል?»

ሃጂ አሊ ተመልሶ ፍርጥም አለ። «ሰው እየፈለግሁ ነው»

ሙሴ ዴ ማይሌና ሙሴ ማቹ ፈጣን የአይን አይታ ተሰዋወጡ። «ደህና! ምን ዓይነት ሰው ነው?»

«ይህማ የመንግስት ምስጢር ነው። በነፍሴም ቢመጣ የማልናገረው ነው» ሲል ነጋዴው እንዳችም ክርክር በማያሻው ቅላጼ ተናገረ።

ረዘም ያለ ዝምታ ሠፈነ። ከዚህ በኋላ ቆንሲሉ ሌላ ቦርሣ ለማምጣት ወደ ሣጥኑ እንዲሄድ፣ ሙሴ ማቹ ምልክት ሰጠው። ሆኖም ግን፣ ሙሴ ዴ ማይሌ በዝምታና በንዴት ሳይቀበሰው ቀረ። በመጨረሻም ፉክክሩ አድክሞትና ግቡም

ሩቅ እንደሆነ በማመዛዘን ቆንሲሉ ተሸነፈ። እንደመጀመሪያው ሁሉ ይህኛውም ቦርሣ በነጋዴው ጃኬት ውስጥ ሰምጦ ጠፋ።

ሃጂ አሊም ቦርሣውን ከተቀበለ በኋላ ለተግባር ተነሣሣ። «ባለፈው ዓመት ታምሜ ነበረ»

የአጀማመሩ ሁኔታ ቆንሲሉን ተስፋ አስቆረጠው «በቀጥታ ወደ ፍሬ ነገሩ ግባ»

የግመል ነጂው በራሱ ስልት ርዕሰ ጉዳዩን እንዲቀጥል በማሰብ፣ ይህን የቃለአጋኖ ንግግር ሙሴ ማቹ ላለመተርጉም ብልህ ውሣኔ አደረገ።

«ታምሜ ስለነበረ ወደ ካይሮ ለሕክምና መጣሁ። የአረብ ሃኪሞች መድሃኒት ሊያገኙልኝ አልቻሉም። እነርሱን በምንም መልኩ አላምናቸውም። ሁልጊዜም ሣስበው ፈረንሣውያን ሃኪሞች የበለጡ አዋቂዎች ናቸው። በናንተ ማህበረሰብ ውስጥ ሣፈላልግ የሆነ ሰው የአንድ መኳሪ ስም ሰጠኝ። የተባለውን ሰው ሳገኘው ሂድኩ። የሰበሰው የኔ አገር ሰዎች የሚሰብሱትን ዓይነት ቢሆንም፣ ካባው ግን ቡኒ ሆኖ ወገቡን በገመድ ታጥቋል።»

«ካፑቺን ነው?» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ ትዕግስት አጥቶ ጣልቃ በመግባት

«ሊሆን ይችላል። እዚህ አገር እነርሱ ብዙ ናቸው። እኔ የምለው ሰው ግን ሽማግሌና ዐይነ-ሥውር ሲሆን የተቃረበ ነበር። በመሃመድ የሚያምኑትን ለማክም ይፈቅድ እንደሆነ ጠየቅሁት። አምን አለ። በርግጥም አክሞ አዳነኝ»

«ይህን ሁሉ በማወቁ በጣም ደስ ብሎኛል። የርሱ የጤንነት ጉዳይ እኛን የሚመለከተን አለመሆኑን ንገረውና ይህ የሚነግረን ታሪክ ከኛ ጉዳይ ጋር ምን አግባብነት እንዳለው ጠይቀው»

«በመስክረሙ ቅፍለት ወደ አቢሲኒያ ተመለስክ። ደርሼ ሳልሰነብት ንጉሡ ጠራኝ። ባልተሰመደ አኳኋን ሰብቻ እንዳነጋግረው ጠየቀኝ። በጭውውታችን ጊዜ እርሱ ራሱ መታመሙን ነገረኝ። ሕመሙ እኔ የታመምኩትንና በፈረንሣዊው መነኩሴ ታክሜ የዳንኩት ዓይነት ነበር»

«እና አንድ ዶክተር ለመውሰድ ወደ ካይሮ ተመለስክ?» አለ ሙሴ ማይሌ፣ ፊቱ ሣምባ መስሎ።

ሃጂ አሊ ጥያቄውን በአምንታ መመለሱን ለመግለፅ በአክብሮት ዝቅ አለ።

«አግኝተኸው ወይም አላገኘኸውም እንደሆነ ብትነግረን?» ሲል ቆንሲሉ ጠየቀ።

«እንዳለመታደል ሆኖ» ሲል ሃጂ አለ ሃዘኑን አጉልቶ ሊገልፅለት በሚችል የድምፅ ቃና ተናገረ። «እኔን ያዳነኝ ሽማግሌ ከመሆኑም በላይ ልቡ . . . »

«ታድያ ምን ለማድረግ ወሰንክ?» ሲል ቆንሲሉ ጠየቀ

«አጠብቃለሁ! ማንም ሰው እምነት ካለው አላህ የሚያስፈልገውን ይሰጠዋል»

«እምነትህ የሚመስገን ነው። አሁን የምንነጋገረው ግን ይህ ስራችን በዓለማዊው እሣቤ እንዴት ሊሆን ይችላል የሚል ነው»

«እኔን ያዳነኝን የሚመስል ሌላ ዶክተር በቅርቡ እንደሚመጣ ሌሎች ፈረንሣውያን መነኩሴዎች ቃል ገብተውልኛል። ይህ የነርሱ እምነት አባል የሆነ ሰው ከእየሩሳሌም ስለሚመጣ እየጠበቅሁት ነው። ሰውዬው በማዳን ችሎታው ስሙ የገነነ ነው። እስክአሁን አሌክሣንደሪያ አካባቢ መጠጋት ይችላል። ቢበዛ በአሥር ቀናት ውስጥ እዚህ ይደርሣል።»

«ምን ዓይነት መታደል ነው» አለ ሙሴ ዲ ማይሌ።

«ይህ ሰው በመምጣቱ በጣም ደስተኛ ነኝ። ምክንያቱም የበፊቱ ዶክተር የሰጠኝ መከላከያ እያለቀ ስለሆነ አዲስ እፈልጋለሁ።»

«ይህ የምትሰው ህመም ምን እንደሆነ ማወቅ ይቻላል?» ሲል ቆንሲሉ ሙሴ ማቼን ጠየቀው። ጥያቄው ለነጋዴው በዙሪያ ጥምጥም እየተነገረው ቢሆንም በተቻለ መጠን ተተርጉሞ ተነገረው።

«ሕመሜ ምስጢር አይደለም። እንደምታውቁት ንጉሡም የሚለቃየው በዚሁ በሽታ ነው። ንጉሡን ካልካደኩ በስተቀር የበሽታውን ባህርይ መግለፅ አይገባኝም። ልትገነዘቡት የሚገባችሁ በሽታው ገዳይ በሽታ አይደለም። ግን የአዕምሮ ሰላምና ምቾትን ይነሣል። ፀባይንም ብስጩ ያደርጋል። እንዲህ ያለው ህመም በአገር መሪ ላይ ሲሆን አለመታደል ነው»

በሚቀጥለው ዕለት እንደገና ለመገናኘት በመወሰን፣ በአሥራ ሁለት ሰዓት አካባቢ ሙሴ ማቼ፣ ነጋዴውን ወደ ማረፊያው ወሰደው።

ሙሴ ዲ ማይሌ፣ ሊገመት ከሚችለው በላይ ተደሰተ። እንኳን ደስ አለህ በማለት ሊያሞቀው፣ ፀሐፊውም ከጀርባው ዝቅ በማለት ተቀበለው። አንዳችም የማጥላላት ነገር ሳይጨመርበት የሙሴ ዲ ማይሌን ሕይወት ለማዳን የእምባሲውን እቅድ መልሰው ለማሻሻል ቻሉ። የንጉሡን ችግርና ከዚሁ ጋር ተያይዞ አንድ መልዕክተኛ እንዴት ሊደርሰው እንደሚችልም አውቀዋል። ከዚህም በላይ መልዕክተኛው የካቶሊክ መነኩሴ መሆን አለበት። ይህ ሉዊስ 14ኛን ያስደስተዋል። ሁለቱም ሰዎች ለዲፕሎማቲክ ችሎታው በጣም ከፍተኛ ነጥብ ሰጡ። ከዚህ በኋላ የሚፈልጉት ቢኖር ይህን መልካም ዜና ለጀስዊቱ ቁስ ሸፋፍነው ማቅረብ ብቻ ነው።

«በነገራችን ላይ፣ ህመሙ ምን ይሆናል ብለህ ትገምታለህ?» ሲል ሙሴ ዲ ማይሌ ጠየቀው

«በኔ አስተሣሰብ ሃኪ አሊ የቆዳ ሕመም ችግር አለበት። ያለጥርጥር እንዳስተዋልኩት፣ ባለማቋረጥ የቀኝ ጉኑን ያክክ ነበር። ሻዩን ለማንሣት እጁን ሲዘረጋ፣ በክርኑ አካባቢ በአገራችን ደኖች ውስጥ በዛፎች ቅርፊት ላይ ያለውን የአንጨት ሸበት የመሰለ ሽፍታ ያስተዋልኩ ይመስለኛል።»

«ይሁና! ለማንኛውም የለውነት ቆዳውም ይሁን ሌላ የሰውነቱ ክፍል ብዙም ልዩነት አያመጣም» አለ ቆንሲሉ

ወዲያውኑ ተነስተው ለአባ ቬርማው ለመንገር ወደ ፎቅ ወጡ። ቄሱ፣ እጆቻቸውን በሆዳቸው ላይ አጣምደው የሚነግሯቸውን መግለጫ በትህትና አዳመጡ። ሙሴ ዲ ማይሌ፣ የፈረንሣዩን ሃኪም ጉዳይ የሚገልጹበት ደረጃ ሲደርስ ደቃቃው ሽማግሌ የሚጥል በሽታ እንዳለበት ሰው ፈርተው ዘለሉ። በመጀመሪያ ላይ በጣም ያስደነቃቸው ነገር እንዲያ ያለ ደካማ ሰውነት ያንን የመሰለ ማዕከላዊ ቁጣ ከውስጡ ማመንጨት መቻሉ ነበር። በኋላ ላይ ግን እንዲህ ያለ ቁጣ የሚያደርግ ምላሽ የሚፈጥር ነገር ምን እንደሆነ ለማወቅ ማውጠንጠን ተጠሉ። ይህ ሁሉ የጀመረው ሙሴ ማይሌ ከአፉ «ካፑቺን» የሚለው ቃል እንደወጣ መሆኑን አስታወሰ።

5

ካፑቺኖዎች በራሣቸውና በትክሻቸው ላይ ጣል በሚያደርጉት የአንገት ልብስ ተለይተው ይታወቃሉ። በኢጣሊያንኛ ካፑቺኖ ሲባሉ፣ ከፍራንሲስካውያን ተከታይነት በተሃድሶ ተለይተው የተመሰረቱ መነኮሣት ናቸው። በቅድስት አገር በተፈፀመ ችግር ተተብትበው በመያዛቸው፣ በግብፅ አገር የሚገኙ ካፑቺኖዎች በቁጥርም፣ በፖለቲካ አቅማቸውም በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ በጣም ቀንሰዋል። ይህ ጉዳይ በሙሴ ማይሌ ዘንድ ይታወቃል። ከአገሪቱ ፍውም ተጠርገው እንዳይጠፉ በመስጋት፣ ካፑቺኖዎች ጥሩ ያልሆነ የማምለጫ ብልሃት መፍጠራቸውንም ያውቃል። ሮም ድረስ በመጓዝ ጳጳሱ በግል እንዲያግልዷቸውም ጠይቀዋል። በሺህዎች የሚቆጠሩ አቢሲኒያውያን ካቶሊኮች፣ ከሃምሣ ዓመት በፊት የጀስዊት ተከታይ ሆነው ነበር። ነገር ግን፣ የኢየሱስ ማህበረሰቦችን ንጉሡ ከአገር ካስወጣ በኋላ አማንያኑንም እያሰቃያቸው ስለሆነ ከሃገራቸው እየተሰደዱ ናቸው በማለት እነዚሁ ወንኖች ጳጳሱን ለማሣመን ችለው ነበር። እንደ ካፑቺኖዎች አገላለጽ፣ እነዚህ በጀስዊት እምነት ሳቢያ ሰለባ ሆንን የሚሉ ሰዎችና የአትዮጵያ መናፍቃን የጭካኔ ሥራ፣ ለመኖር ሲባል የተደረገ ስልት ነው። በዚህ ሣቢያ ለኑሮ አመችነት በሌለው ከግብፅ በስተደቡብ በሲናር ምድርና በአቢሲኒያ ድንበር አካባቢ ተበትነዋል። እነዚህን ሰዎች ሌላ ማንም ያያቸው ባይኖርም፣ መነኮሣቱ ግን መኖራቸውን ስላረጋገጡ፣ ካፑቺኖዎች እነዚህን የተበተኑ ካቶሊካውያን ለመታደግ ጥያቄ አነሱ። ለዚህ ተልዕኮአቸው፣ ጳጳሱ በአፊሌል ሥልጣን እንዲሰጧቸውም አቤቱታ አቀረቡ። የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ጳጳስ አቡነ ኢኖሴንት 12ኛ፣ እነዚህን በትምህርታቸው ያልገፉ መነኮሣት በጥሩ መንፈስ ሰላዩዋቸውና ብዙዎችም ማስተዋል ያሰባቸው ኢጣሊያውያን ስለሆኑ፣ አቤቱታቸውን ተቀብለው ፈቀዱላቸው። ከዚያም ወደ ደቡብ በማቅናት በላይኛው ግብፅ አካባቢ አንድ የእንግዳ ማረፊያ ቤት ይከፍታሉ። በአንድ ወቅት በአገሪቷ ውስጥ ፍፁም እንዳልነበሩ ሁሉ፣ ዛሬ ደግሞ ከመቸውም በበለጠ ሃይል ተጠናክረው ተመልሰዋል።

እምብዛም ክብደት አይሰጠው እንጂ፣ የካፑቺኖዎች እቅድ እዚያ ላይ እንደሚያበቃም ሙሴ ዴ ማይሌ ያውቃል። ዋናው ግባቸው በስደት ላይ የሚገኙትን አቢሲኒያውያን ለመርዳትና ለመታደግ ሣይሆን፣ አቢሲኒያን ራሷን ወደ ካቶሊክነት ለመለወጥ ነው። ጳጳሱም፣ ይህን እቅዳቸውን በመደገፍ ስላበረታቷቸው፣ ወደ አቢሲኒያ ለሚጓዙ የካፑቺኖ ሚሲዮናውያን ፍላጐት የሚያግዝ፣ ያልተቋረጠ የገንዘብ ድጋፍ እንዲደረግለት መላ ፈጥረዋል። ይህ እንቅስቃሴያቸው ደግሞ ከጀስዊቶች ጋር ቀጥታ ፉክክር ውስጥ ያስገባቸዋል። ጀስዊቶች በበኩላቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የገጠማቸውን ሽንፈት ፈፅሞ ባለመቀበል አንድ ቀን እንመለሣለን ብለው የሚያምኑ ናቸው።

በግብፅ ውስጥ የሚኖሩ ጀስዊቶች ጥቂቶች ነበሩ። አነዚህ ሰዎች በዙሪያቸው ካሉት ሁሉ ጋር በሰላምና በግልፅ በሚታወቅ ወዳጅነት ይኖራሉ። ከሌሎች የሃይማኖቱ ቅርንጫፎች ጋር ይህን ያህል የጠነከረ ፉክክር፣ ቢያንስ በከፍተኞቹ የሥልጣን አካላት መካከል ይኖራል ብሎ ቆንሲሉ ገምቶ አያውቅም። «ካፑቺን» የሚለው ቃል ሲጠቀስ፣ በአባ ቬርሣው ላይ የታየው የቁጣ ስሜት ግን፣ ሙሴ ማይሌ ስለ ፉክክሩ የነበረው ግንዛቤ ምን ያህል የተሣሣተ እንደነበረ በግልፅ የሚያሣውቀው ሆነ።

«የፊረንሣይ ንጉሥ መልዕክት፣ በኢጣሊያውያን በኩል ይተላለፋል የሚለው ጉዳይ ከኖያቂ ውጭ ነው። ከዚህም በላይ ተልዕኮው የኛና የኛ ሃይማኖት ቅርንጫፍ ሃላፊነት ብቻ ነው። በዚህ ነጥብ ላይ የንጉሡ መመሪያ አንዳችም ስህተት የለበትም። የተፈጥሮ ጉዳይ ሆኖ ስለራሴና ስለተግባሬ ያለመግለፅ ሁኔታ ስላለብኝ እንጂ፣ በርም በኩል አቋርጬ ወደዚህ ስመጣ ብዙዕ ወቅዱስ የሮማን ጳጳስ በአካል አግኝቻቸው ነበር» ሲሉ ቁሱ ሃይል በተቀላቀለበት አነጋገር አስገነዘቡ።

አስቀድሞ ሲታሰብ ይሆናል ለማለት ቢያስቸግርም፣ አሁን የተገለፀው እውነታ የጀስዊቶች ክብር ከፍ ያለ መሆኑን በሙሴ ዴ ማይሌ ዓይን እንዲታይ አደረገው። ቆንሲሉ፣ መላ አካሉን አድናቆት ቢሞላውም፣ የልምድ ማነስ የፈጠረበት ሃፍረትም ስሜቱን አሣመመው። ከዚህ በኋላ የኒህን የጀስዊት ቁስ ቃላት፣ በሙሉ መንፈሣዊ ምርኮኝነት ለመስማት ተዘጋጀ።

«የፈረንሣይን ንጉሥ በመወከል በመቅረቤ፣ ጳጳሱ መስማማታቸውን አረጋግጠዋል። ከዚህም ባሻገር፣ አቢሲኒያ፣ ባለመታደል ከሰመጠችበት የመናፍቅነት መከራ ሊያድኗት፣ የኢየሱስ ማህበረሰቦች ለሚወስዱት አርምጃ ቡራኬአቸውን ሰጥተዋል»

በሐሩር አውራጃ አገሮች ምሽት ፈጥኖ ይደርሣል። ክፍሉን የሞላው ድንግዝግዝ ያለ ብርሃን፣ ሰቁሱ ቃላት ይበልጥ ክብደት አከሰበት።

የዚህ ሁሉ እውነታ ማጠንጠኛው፣ ሕዝብን በመንፈሣዊ ሥርዓት ውስጥ ለማምጣት የሚደረግ ዳግም ጥረት፣ እንደ ሃቀኛ እምነት እንዲቀጥል ማድረግ የሚቻለው፣ ከምድራዊው ፍላጐት በላይ በሆነውና ተፎካካሪ በሌለው ሃይል ፈቃድ ሲሆን ነው። ይህ ዓይነቱ ሃይልና አቅም ያላቸው ሳያዳሉ ዕቅዱን ማሣካት የሚችሉት በዘመናችን ታላቁ የካቶሊክ ንጉሠ ነገሥት የሆኑት የፈረንሣዩ ንጉሥ ብቻ ናቸው። ሌላው ነገር ሁሉ የሚመነጨው ከዚህ ታላቅ እምነት ነው። ብፁዕነታቸው ይህን የተቀደሰ ነው ብለው ተቀብለውታል። የኛ ቅርንጫፍ ደግሞ በታላቅ ትህትና ይተገብረዋል፣ ሲሉ ጠንካራ ሃይማኖተኝነታቸውን በሚያሣይ መልክ ገለፁ።

ቁሱ፣ ለአፍታ ያህል ንግግራቸውን ገታ ካደረጉ በኃላ፣ በድምፃቸው ውስጥ አለመደሰታቸውን ሊያመለክት በሚችል ቅላፄ «ክታች በማይማን ቀሣውስትና በደከማ መንግስት ዜጐች እየተመራ እንዲንቀሣቀስ የሚደረግ አዲስና ልዩ ዕቅድ፣ ሲበዛ ሰብዓዊ በሆኑ ምክንያቶች የሚሰራ ስለሆነ ምንም ልትረዳው አትችልም»

የመጨረሻውን ዓረፍተ ነገር ሲደመድሙ ቁሱ ቁና ተነፈሱ። ሙሴ ዴ ማይሌ ትንፋሹን ውጦ ፍውም ተረበሸ።

«ሥራህ ተሰፋ በሚሰጥ መልክ ቀጥሏል» ሲሉ የጀስዊቱ ቁስ ክፍ ባለና ተመልሶ ወዳሸዊ በሆነ ቃና ንግግራቸውን ቀጠሉ። «ከዚህ ነጋዴ ጋር ተጉዳኝቶ በሚሄድ ሃኪም ትክሻ ኤምባሲያችንን ማድረጉ እጅግ ድንቅ ሃሣብ ነው። ይሁንና ሃኪሙ ፈረንሣዊ መሆን ሲኖርበት የኛ እምነት ተከታይም አብሮት ሊሄድ ይገባል።»

አገልጋዮች የፋና መብራት ይዘው በመግባታቸው የሁሉቱ ሰዎች ውይይት ተደናቀፈ። ንግግራቸው እዚህ ላይ ሲቋረጥ ርዕስ ጉዳዩም ተዘጋ።

እራት በታላቅ ክብር ቀረበ። ቁሱ ስላደረጓቸው ጉዞዎች ብዙ ታሪኮችን አወጉ። ሴት ወይዛዝርት ስለ ቤርሣይስና ስለ ሮም ይጠይቃሉ። ቁሱ፣ ትኩረታቸውን ይበልጥ ወደ ማዳሞዜል ዴ ማይሌ በማድረግ ብልህነታቸውን አስመሰከሩ። የልጃገረዲቱ አባት፣ በቁሱ ላይ የአገራዊ ስሜት ዝንባሌ እንዳለ ስለተረዳና በዚህ ነፃ የሃይማኖት ሥርዓት ገለፃ፣ የወጣቶችን ነፍስ ለመምራት በመቻላቸው ስሜቱ ተደሰተ።

ቬርሣው፣ በዚያን ጊዜ ካይሮ ውስጥ ሊገኙ እንደሚችሉ የሚያውቋቸውን ሁለት ጀስዊቶች ለማየት መጓጓታቸውን አባ ገለፁ። ምናልባት በማግስቱ ያኟቸው ይሆን? ሙሴ ማቹ፣ የቁሱን መልዕክት ለዚህ ለሚጠበቁ ጀስዊቶች ለማድረስ ቃል ገባ። ግብዣው በጊዜ ተጠናቀቀ። ቆንሲሉም በቢሮው ውስጥ ብቻውን ቀረ። በአዕምሮውም ውስጥ አስፈሪ የሆነውን እውነታ ለረሻም ጊዜ አውጠነጠነ። ይህን እውነታ ከዚህ በፊት አምኖ ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበረም። ጀስዊቶች ወደ አቢሲኒያ ኤምባሲ ሲላክ የሚያጋጥመውን የሚታወቅ አደጋ ቸሰል የሚሉ ብቻ ሣይሆን፣ አገር ሁሉ ጠልቷቸው እያሰም ራሣቸው ወደዚያው ለመሄድ ይፈልጋሉ። ይህ ሁሉ ይቅርና፣ ሙሴ ዴ ማይሌን አሁን የገጠመው መጥፎ ጣጣ፣ በፈረንሣውያን ማህበረሰብ ውስጥ አንድ ፈረንሣዊ ዶክተር የማግኘት ጉዳይ ነው። በርግጥ ደግሞ አንድም የለም።

ከማለዳው አንድ ሰዓት ሲሆን የሰሊቱ ቅዝቃዜ ቀስ እያለ ሲወገድ፣ ከተማዋ በሞቃት ብርሃን ተሞላች። በፈረንሣውያን መኖሪያ አካባቢ በሚገኙ ትላልቅ ሣፎች ላይ የሰፈሩ ወፎች፣ በመገፈፍ ላይ ባሉ ጥላዎች ሥር ባለማቋረጥ ይዘምራሉ። ምንም እንኳ የአገር እርምጃ ያንተግቀሰው በአየር ውስጥ ተንሣፍፎ ቢቀርም፣ ገና ከመሬት ላይ አልተነሣም።

ሜትር ዝርሚ፣ በአሸዋማው የመንገዱ ጠርዝ አጠገብ በሚገኙና ዝርግት ባሉ ሣፎች ጥላ ሥር አቋርጦ፣ የፀሃይ ብርሃን በሣፎች ቅርንጫፎችና ቅጠሎች ተቀራርጦ በሚታይባቸው ቦታዎች ላይ ወዲያና ወዲህ ይራመዳል። በቀዝቃዛ የውቅያኖስ ውሃና በሞቃት አየር መካከል እንደሚቦርቅ ዶልፊን ደስተኛ ነው። ምንም ዜማዊ ቃና የሌለው ፉጨት ይሰጫል። አንዲት

ትንሽ የልብስ ከረጢት ይዟል። የቆንሲሉ አሽቃባጮች እንደተተነበየው ቆንስላው ጽሕፈት ቤት እንዲገኝ የሚያዝዘውን መጥሪያ ይዘው ትናንት ማታ መጥተው ነበር።

በመጨረሻው ሰዓት ላይ ሜትር ዝረሚ የጓደኛውን የጀን ባፕቲስትን ብልሀ ምክር ተተብሷል። በአንድ አነስተኛ ከረጢት ውስጥ የንፅህና ዕቃዎችን፣ ንፁህ ሸሚዝና የኪስ መፅሃፍ ቅዱስ በመያዝ ከሰዓት በኋላ በግዴለሽነት አሣ ስማጥመድ እንደሚሄድ ሰው፣ እርሱም ወደ እሥሩ ተዘጋጀ።

በቆንስላው መግቢያ ላይ አንድ አገልጋይ መጥቶ በክብር ወሰደው። አስቀድሞ ወደ ሁለተኛው ፎቅ መራው። ከዚያም በላይኛው አዳራሽ ውስጥ ባለ አጭርና ስውር በር አልፈው አንዲት ትንሽ ክፍል ውስጥ ገቡ። ክፍሉ ቅዝቃዜ ያለው ነው። በክፍሉ መሃል ላይ ሰፊውን ቦታ ይዞ የሚገኝ የምግብ ገበታ የሚሆን ጠረጴዛ አለ። ዙሪያውን፣ ማይሴ በሚል ጉትጎ ጥልፍ ያጌጠ ነጭ የጠረጴዛ ልብስ ለብሷል። የሚያብረቀርቁ የመስተዋት ብርጭቆዎች፣ የፍራፍሬ ጭማቂ የያዘ ብሩህ የመስታወት ጀግ፣ ሁለት የሸክላ ስኒዎችና ትኩስ ዳቦ ተቀምጧል። የታዘዘውን ለመፈፀም ዝግጁ የሆነው አገልጋይ ወንበር ስቦ ሜትር ዝረሚ እንዲቀመጥ ጋበዘው። ነገር ግን መድሃኒት ቀማሚው እምቢ አለ። አንዳች የተፈጠረ ስህተት ስላለ በአስቸኳይ መታወቅ ይኖርበታል። ክፍሉና የሚታየው ዝግጅት ስህተት እንደሆነና እርሱ ወደመታሠሪያው መሄድ እንደሚፈልግ መናገር ሲጀምር አገልጋዩ ልጅ ከአጠገቡ ፈጥኖ ሄደ።

ቆንሲሉ ብዙም ሣይቆይ ደረሰ። ሲያዩት ጤናው ጥሩ አይመስልም። ዓይኖቹ ቀልተዋል። መሆን ከሚገባው በላይ ፊቱ ተኳኩሏል። ስሜቱ በተለየ ደስተኛ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም።

«ሜትር ዝረሚ! ስላገኘሁህ በጣም ደስ ብሎኛል። ታዲያ ምነው መቀመጫ አልተሰጠህ? አባክህ ቁጭ በል!»

ደነገጠ። አለማመኑን ሙሉ በሙሉ ሣይተው፣ ባለመድሃኒቱ ረዥም አካሉን በሚያስደስት አኳኋን አጣጥፎ ወንበር ላይ ተቀመጠ። ቆንሲሉ፣ መዓዛው ውብ የሆነ የሚጋት ሻይ አዘዘ፣ እንግዳውን ከመጠን በላይ መጎክባበብ ሞከረ። ወተት፣ ስኳርና የማማሰያ ማንኪያ ሰጠው። የፍራፍሬ ጭማቂውንም በሁሉም ብርጭቆዎች ውስጥ በራሱ እጅ ቀዳ። ያችን ቀጭን ሽል ጉራዴውን ባለመያዙ ሜትር ዝረሚ አዘነ። እርሷን ይዞ ቢሆን ኖሮ ይህን ሁሉ ሢልት በአንድ ውግ ክፍፋሜ ያደርሰው ነበር።

«እኔ በሌለሁበት የተሰራ ቢሆንም ያከናወንከው ተግባር እጅግ በጣም ድንቅ ነው» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ ቅንድቡን ከፍ አድርጎ።

ሜትር ዝረሚ የሚሰጠውን መልስ አላወቀም። ሰራሱ እርጋታ እንዲሰጠው በማሰብ የቀረበለትን ብስኩት በአፉ ሙሉ ጉረሰና ጠበቀ። ምን ይከተል ይሆን በሚል ስጋት አፉን ዘጋ።

«ሥራህ ትልቅ ችሎታ የሚጠይቅ ነበር። የተለያዩ ዕፅዋትን አዋህዶ የተለያዩ ማጣዘቂያዎች /መጫዎች/ እንዲሆኑ ማድረግ፣ መቀባትና መወልወል በእውነቱ ትልቅ ክህሎትን የሚጠይቅ ነው»

ሜትር ዝረሚ ጭንቅላቱን አንዴ ወደ ቀኝ፣ አንዴ ወደ ግራ እያጋደለና ትከሻውን እየነቀነቀ ማላመጡን ቀጠለ።

ምን እንደሆነ እንጃ እንጂ፣ በቆንሲሉ አዕምሮ ውስጥ አንድ ነገር አለ። ዲፕሎማቱ፣ በአንድ ትልቅ ስኒ ውስጥ የተቀዳውን ቡና በአንድ ትንሹ ሲጨልጠው፣ መድሃኒት ቀማሚው በበኩሉ የተጠራበት ጉዳይ ከዚህ በኋላ እንደሚቀጥል በልቡ አሰበ።

«አንዚህን ቅይጦች ለብዙ ጉዳዮች እንዲጠቅሙ ማድረግ ይቻላል። በዚህም ላይ ሌላው ቀርቶ መድሃኒት እንደምትቀምምም ስትናገር ጆሮዬ ውስጥ ጥልቅ ብሎ ነበር። ተሣሣትኩ?»

እንግዲህ ጀመርን ማለት ነው፣ ሲል ሜትር ዝረሚ አሰበ።

ከኋላዋ የሚገኝ ቁጥቋጦ ድንገት የተተረማመሰባት መስሏት የበረገገች ድኩላ ይመስል፣ ቁና ቁና መተንፈስ ጀመረ።

በአገልግሎት ብዛት የወየበች አንዲት ትንሽ መሃረብ ከኪሱ አውጥቶ አፉን እየጠረገባት «አይዞህ አትፍራ!» አለው ቆንሲሱ። «ከኔ በፊት የነበሩት ሃላፊዎች፣ ተገቢው ቅድመ ፈቃድ ሣይኖራቸው በመድሃኒት ቅመማና ንግድ ወይም በሕክምና ሥራ ላይ ተሰማርተው የነበሩትን አንዳንድ ባልደረቦችን በተመለከተ በጣም ይቆጣጠሩ ነበር። እኔ ራሴም ብሆን ጠንቃቃ ልሁን እንጂ በዚህ ሁኔታ ላይ በዙሪያችን ብዙ አስመሣዮች ስላሉ ሃላፊነታችንን በትክክል መረዳት ይኖራል ብዬ አስባለሁ። አንተስ ምን ትላለህ?»

ሜትር ዣረሚ ቅንድቦቹን ሁለት ጊዜ አርገበገባቸው። ይህ ማለት በሃሣቡ መስማማቱ ነው ሲል ሙሴ ዴ ማይሌ አሰበ።

«አንተን በሥራ ላይ ነው ያየሁህ። ያውም በሥዕል ቅብ ሥራ ላይ። ይህ እውነት ነው። ከዚያ ወዲህ አዕምሮዬ ወሰነ። ስላንተ ያገኘሁት መረጃም በጣም ትክክል ነበር። ከዕፅዋት የፈውስ መድሃኒቶችን መቀመምህን ብታረጋግጥልኝ ሙሉ ድጋፌ እንደማይለይህ ላረጋግጥልህ እወዳለሁ። ቃሌንም የማከብር ሰው ነኝ። ይህንንስ ታውቃለህ?»

«አምን፣ ክቡር ሆይ» አለ ሜትር ዣረሚ በብዙ ጥረት።

«እንግዲያው በግልፅ አነጋግረኝ። በስፋት እንደሚነገረው በርግጥ አዕዋትን ለመድሃኒትነት በማሣደግና የነዚሁኑ መድሃኒቶች አዘገጃጀትና ጠቀሜታ ልምዱ አለህ?»

«እንደዚያ ብዬ አምናለሁ» አለ ቀማሚው

«እንደዚያ ያምናል! ምን ዓይነት ትህትና ነው። ከሚታየው በበለጠ እንደሆንክም ሰምቻለሁ። ማህበረሰቡ ከሚኖርባቸው ከተሰያዩ ቦታዎች እየመጡ የሚጐበኙህ ሰዎች፣ ሌላው ቀርቶ ፖሻው ምክር እንደሚጠይቅህ ሰምቻለሁ።»

ሜትር ዣረሚ መሬት መሬት ማየት ጀመረ።

«በዚህ ቅር አትሰኝ። ይህ ድንቅ ነው። በጣም ድንቅ ነው። እንዲህ ያለ ችሎታ አለህ ብዬ ጨርሶ አልጠረጠርኩም ነበር። ትህትናህ የሚደነቅ ነው። ትናንትና ማታ መጠነኛ

የጤና መታወክ ደርሶብኝ ነበር። ስለመድሃኒት ስንነጋገር ባለቤቱ ማዳም ዴ ማይሌ፣ እኔ ሣላውቀው ከስድስት ወራት በፊት ጠርታህ አድነሃት እንደነበረ ነገረችኝ»

በአንገዳው ፊት ላይ የሥጋት ሁኔታ ስላየበት ቆንሲሱ በጣም በተረጋጋ ቅላፄ መናገር ጀመረ።

«እውነቱን ነው። አትፍራ! እንዴት ላግዝህ እንደምችል ግራ ይገባኛል። የምሥራች ብዬ መልካም ምኞቴን አቀርባለሁ። ከዚህ በተረፈ በዚሁ እንድትቀጥልበት አደፋፍርሃለሁ።»

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ከመቀመጫው ብድግ በማለት ወደ መስኩቱ ከተራመደ በኋላ ዞር ብሎ፣ «ለምሣሌ ጥቁር ሰዎችን የሚያጠቃውን እንደቁምጥና ዓይነት ያለውን የቆዳ በሽታ የማዳን ችሎታ አለህ?»

«እንዴት ልገልፅም እችላለሁ? ይህን ነገር የምንሰራው ሁለት ሆነን ነው፣ ክቡር ሆይ።» ሲል ሜትር ዣረሚ በመጨረሻ አንተመተመ።

«ምን ማለትህ ነው?»

«ሽሪክ ጓደኛ አለኝ።»

«ጥሩ። ገባኝ፣ጥያቄዬን በትዕግስት መልስልኝ»

«ነጥቡ ክቡር ሆይ! የመድሃኒት ዕውቀቱ ያለው ጓደኛዬ ነው። እርሱ ስህመምተኞች መድሃኒት ያገዛል። እኔ መድሃኒቱን አቀምማለሁ። ለምሣሌ ማዳም ማይሌን በተመለከተ ችግሩን ገለፅኩለት። እርሱ የሚያስፈልጋቸውን ነገረኝ። ቅባቱን አዘጋጅቼ አመጣሁላቸው። የኔ የተሣትፎ መጠን ይህን ያህል ነው።»

ቆንሲሱ ወደ ጠረጴዛው ተመልሶ ወንበሩ ላይ ተቀመጠ።

«ገባኝ። እንዲህ ከሆነ ይህን ሽሪክህን ማነጋገር ይኖርብኛል ማለት ነው?»

«ልገልፅም እሞክር የነበረውም ይህንኑ ነው፣ ክቡር ሆይ» ሙሴ ዴ ማይሌ ከውይይቱ ያተረፈው የጋለ ስሜት በአንድ ጊዜ ቀዘቀዘ።

«ስሙ ማን ይባላል?»

«ፖንሴ ይባላል፣ ክቡር ሆይ። ጀን ባፕቲስት ፖንሴ»

«ታዲያ የት ነው ላገኘው የምችለው?»

«ደባሎች ነን። እርሱ በላይኛው ፎቅ ላይ ሲኖር፣ እኔ በታችኛው ወለል ላይ እኖራለሁ።»

«ቤተ-መከራችሁስ?»

«አ! ክቡር ሆይ! በሕይወታችንና በሥራችን ላይ ያለውን ለያይቼ ለመግለፅ እጅግ ይከብደኛል። ይህን ልገልፅም ይከብደኛል . . . »

ቆንሲሉ ሰረዝም ጊዜ በሃሣብ ውስጥ ሰመጠ።

«ለመሆኑ ይህ ጓደኛህ፣ ረዥም ጉዞ ለማድረግ ፈቃደኛ የሚሆን ይመስልሃል?»

«ክቡር ሆይ፣ ይህንንማ እርሱን መጠየቅ ይገባል። እርሱ . . . የተለየ ዓይነት ሰው ነው። ሽረኩ ባልሆን ኖሮ . . . ብቻ የተለየ ተሰጥኦ ያለው ሰው ነው።»

«የተለየ ተሰጥኦ! አትሰኝም!»

እነዚህ የጀብድ ሰዎች እኮ ስለምንም ነገር አይጨነቁም ሲል ሙሴ ማይሌ አሰበ።

«ልታመጣው ትችላለህ?»

«እርስም ክጠየቁ ይቻላል። እኛ እኮ የንጉሠ ነገስታችን ተገዥዎች ነን። እርስም ደግሞ የንጉሠ ነገስታችን ሹመኛ እንደራሴ ነዎት»

አንዳችም የሚያስኬትሰው ውጤት ከሌለውና የራሱን ልብ ሳያሞቅ፣ ይህን የመሰለ የሙያ ታማኝነት ሊሰማ አይችልም። ታዲያም ይህን የመሰለ ታማኝነቱን በግልፅ ላቀረበ ሰው ፈፅሞ ውለታ ቢስ መሆን አይገባም። እንግዲህ ንጉሣዊ አገዛዙን አፅንቶና አስማምቶ ማኖር

የሚቻለው፣ አስደሳች ባለሥልጣን በአመስጋኝ ሕዝብ ላይ ሲኖር ነው፣ ሲል ሙሴ ዴ ማይሌ አሰበ።

«እንዲህ ከሆነ ሽሪክህን እዚህ በአምስት ሰዓት ላይ እንደምጠብቀው ንገረው» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ።

«እንደክቡርነትዎ ፈቃድ እሺ። እና ግን . . . »

ሚትር ዠሪሚ አቅማማ። ቆንሲሉ ተንኮል ያሰበ አይመስልም። የጀን ባፕቲስትን እውነተኛ የሙያ ምስጢር ማዋየቱ አንዳችም አሉታዊ ገፅታ የለውም። ችግሮችን የመቀስቀስ ሁኔታ የሚፈጠረው በተለይ በዓደኛው ባህርይ ሣቢያ ነው። «እኔን ቢጠራኝ ኖሮ አልሄድም ነበር» በማለት ጀን ባፕቲስት ከትናንት በስቲያ ማታ ባይናገር ኖሮ ጥሩ ነበር።

«እና ግን?» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ ትዕግስት በማጣት

«እና ግን ዓደኛዬን ፖንሴን ደህና አድርጌ ስለማውቀው ሌላ ዘዴ ባቀርብስ?»

«ምን ዓይነት?»

«ክቡርነትም፣ ወደ ቤታችን፣ ማለቴ ሁለታችን ወደምንኖርበት ቤት፣ እርስም በሚፈልጉት ጊዜ እንዲገኝ ካዘዙት አለቅዋ ባለውለታም ስለሚሆን አንዳችም ነገር እምቢ አይልምትም»

«እንግዲያው አዘጋጅለሁ። ሲፈልግ ተመልከችና አድማጭ ተፈቅዶለታል»

አንዳችም አለማለት እርቆ አለማሰብ ነው፣ ሲል ዠሪሚ ገመተ።

ይህ ድንቅ ነው። የማይመስልና እንዲያውም የሚያምፅ ዓይነት ነው። ነገር ግን ይህ ጉዳይ ድንገተኛ ስለሆነና ሰውዬውም የአሸናፊነት ሚና ስላለው፣ እርሱ በመረጠውና ለአጭር ጊዜም ቢሆን የሚንቁትን መቀበል ግዴታ የሚሆንበት ጊዜም አለ። ሲል ቆንሲሉ አሰበ።

«በአንድ ሰዓት ጊዜ ውስጥ ሊደርስ ይችል ይሆን?» ሲል ቡጢውን አጠንክሮ ሙሴ ዴ ማይሌ ጠየቀ።

6

ሰረገላው፣ በግቢው ውስጥ በተነጠፈው የጣውላ ሜንቃ ላይ ቆሞ ይጠብቃል። በጣም ግሩም ሠረገላ ነው። ቆንሲሉ፣ ሠረገላውን የሚጠቀመው በክተማው ውስጥ ይፋዊ ጉብኝት ሲያደርግ ነው። በዚህ በመጠቀሙ በቱርክኛ መነክለ ከፍተኛ ባለስልጣን ያስመስለዋል። ሙሴ ዲ ማይሌ፣ እርሱ ለራሱ ሆን ብሎ የወሰነው ሰዓት ሲያበቃ፣ ወደ ዶክተሩ ቤት በሠረገላው ለመሄድ ወሰነ። የብዙ ሰዎችን አትኩረት ለማስቀረት፣ ቆንሲሉ በሠረገላው ላይ ሆኖ መውጣትና አንዳንድ ጊዜ ከሚጉበኛቸው ታዋቂ ነጋዴዎች ሱቅ አጠገብ ቆም ማለት፣ ከዚያም ጉብኝት ለማድረግ እንደወጣ በማስመሰል መድሃኒት ቀማሚውና ሽርክ ወደሚኖሩበት አቅጣጫ መንገዱን ይዞ በመጓዝ ሌላ ምንም ፍላጐት እንደሌለው ማዘናጋት የተሻለ ነው። ቆንሲሉ፣ ስለዚህ ሃሣቡ ሙሴ ማቼን አስተያየት እንዲሰጠው ጠየቀው። ሃሣቡና እምነቱ በሙሴ ማቼ ሲረጋገጥለት ሁለቱም ተያይዘው ከጠዋቱ አራት ሰዓት ሲሆን ጉዞ ጀመሩ።

አወጣጡ ሠላማዊና የተረጋጋ እንዲመስል፣ ሠረገላ ነጅው፣ በየት በየት እያደረገ እንደሚሄድ ቆንሲሉ ትዕዛዝ ሰጠው። «ከፈረንሣውያን ማህበረሰቦች መኖሪያ አካባቢ ውጭ፣ በክተማው ዙሪያ ተጉዘህ ትመለስና በክተማው ውስጥ በሚገኘው በሙሴ ቢ ቤት ፊት ለፊት ስትደርስ ትቆማለህ»

«አይደለም እንዴ ማቼ። ለመሆኑ ልንጉበኛቸው የምንሄድባቸውን ታላላቅ ሰዎች በተመለከተ በማህደሮቻቸው ውስጥ ምን አገኘህ?»

«ምንም አላገኘሁም ማለት ይቻላል፣ ክቡር ሆይ። ሰውዬው ሰላማዊ ነዋሪ ነው። ሌላው ቀርቶ፣ ፖንሴ እውነተኛ ስሙ መሆኑንም እናውቅም። እዚህ የመጣው ከሦስት አመት በፊት ነው። ከቬነስ ለቅቆ ከመጣ በኋላ አሌክሣንደሪያ ውስጥ ለስድስት ወሮች ተቀምጧል። ብዙ ጊዜ ማርሴይ፣ ቢዩካሬና ከዚያም በፊት ኢጣሊያ ውስጥ የመድሃኒት ቅመማ ሥራ ማከናወኑን በጉራ ይናገራል። የያዘው የሙያ ማስረጃ የተጭበረበረ ነው ለማለት በቂ ምክንያት አለን። የልደት ሠርተፊኬቱ የወጣለት ከግሬናብል ነው። ይህ ማለት ያ በጣም የተሰየ ችሎታ ኖሮት፣ የሃሰት ሰነድ እያዘጋጀ ሲሰጥ ተደርሶበት ተይዞ፣ አምና የታሠረው

ያፈረሰ መነኩሴ ከነበረበት ቦታ ማለት ነው። በወቅቱ ይህን እውነታ አውቀው ጉዳዩን እንዲጠነቀቁበት ቢቀርብልሥ ምንም አንኳ ስለትውልድ ቦታው ዕለትና ሁኔታ ማወቅ ባንችልም፣ ከቡርኑትም በቸርኑትም፣ ሙሴ ፖንሴ፣ የፈረንሣይ ጥበቃ እንዳይቋረጥበት አዘዘ»

«ትውልዱ ምን የሚፈይደው ነገር አለ?» ሲል ሙሴ ዲ ማይሌ ሃሳቡን አለመውደዱን በሚገልፅ መልክ ተናገረ።

በቆንሲሉ እምነት የትውልድ ቦታ ያለው ሰው፣ በስሙ የሚጠራበት ቦታ ያለው፣ ሰዎችንና ነፍሣቸውን የሚያኖርበት ሥፍራም ያለው መኳንንት ብቻ ነው። ሌሎቹ ሰዎች ባሻቸው ሥፍራ የተወለዱ ናቸው። አሁን የተገለፀው ግን ተረት ተረት ነው ሲል አሰበ።

«ሰውዬው ከአገር አገር የሚንከራተትበትን ምክንያት ለመሆኑ በትክክል እናውቃለን። ምናልባት ይህ ፖንሴ የሚባለው እንደ ሽሪኩ ጓደኛው ፕራቴስታንት ይሆን ይሆን?» ሲል ጠየቀ።

«ከቦታ ቦታ መዘዋወሩ በስም ማጥፋት ሰበብ ይመስለኛል። የመድሃኒት ቅመማና ሽያጭ ስራ የሚያከናወነው ምንም ዓይነት ፈቃድ ሳይኖረው ነው። ሃይማኖቱን በተመለከተ ግን የተጠመቀ የሮማ ካቶሊካዊ ክርስቲያን እንደሆነ ፍፁም ርግጠኞች ነን»

«ቢሆንም በፀሎት ቤት ጨርሶ አይቼው አላውቅም»

ይህን የጠቀሰው ከቆንስላው ግቢ ጋር ተያይዛ ያለችውንና የፈረንሣይ ማህበረሰብ በየእሁዱ የሚሰበሰብባትን አነስተኛ ቤተክርስቲያን ለመግለፅ ሲል ነው።

«መቼም ከማህበረሰባችን ሩብ ያህሉ ክርሱ የበለጡ አክባሪዎች

አይደሉም።»

«ይገባኛል፣ ግን አንድ ቀን አንድ መፍትሔ ማግኘት ይገባናል»

«ቁሱ እንደተናገሩት ሰውዬው እዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ከደረሰበት ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ ከቤተክርስቲያን ሥነ - ስርዓት በኋላ ሁልጊዜም ወጥቶ ይሄድ ነበር። በግልፅ እንደሚታወቀው አበባዎችንም ወደ ቤተክርስቲያን አምጥቶ ያውቃል።»

«ለመሆኑ የንስሃ ቃል ወጥቶት ያውቃል?»

«ብዙውን»

ቆንሲሉ፣ ትክሻውን ነቀነቀና ተዕግስት በማጣት በመስኮት ወደ ውጭ ተመለከተ።

መሌ ማቼ፣ ጭኑ ላይ ያስቀመጣቸውን የወየቡ ወረቀቶች ያገላብጣል። በተከፈተው መስኮት በኩል ከአረብ ከተማ የሚነፍሰው ሞቃት አየር በሠረገላው ውስጥ ሲያልፍ፣ የቡናና የደረቅ ቅመማ ቅመም መዓዛ ይዞ ይገባል። በጠባቡ ጉዳና ላይ ያለው ሕዝብ ለመተላለፍ ሲል አልፎ አልፎ ከሠረገላው ጋር ይጋፋል። ሕዛናት የቀልድ ማሾፊያ ቃል ይናገሩና ይሮጣሉ። ሁልጊዜም በቡድን ተሰብስበው የሚጓዙት ሴቶች፣ በሠረገላው ውስጥ ያለውን ለማወቅ በዓይነ ርግባቸው ሥር አሙልቀው ይመለከታሉ።

«በዙም የሚጠቀስ የለም» ሲል ፀሐፊው ቀጠለ። «እሱና ጓደኛው ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ነገር ለማክበር ብለው ይወጣሉ። በሁለቱ ሰዎች መካከል የከረረ ፀብ ተፈጥሮ ሰላም አያፍርሰዋል የሚል መረጃ ቀርቧል። ነገር ግን ሲጣራ ለቀልድ ብለው ሻምላዎቻቸውን ስላፏጯቸው መሆኑ ይታወቃል። ፖንሴ፣ ቱርኮች ዘንድ በብዛት ይመላለሳል። የካይሮ ዋናው ቃዲ ዘንድም ገባ ወጣ ይላል። ብዙ ነጋዴዎች ዘንድም ይመላለሳል . . »

ጉዳዩ ለቆንሲሉ እንዲህ እየተንሸራተተ የሚያስቸግረውም ለዚሁ ነው። ይህ መድሃኒት ቀማሚ፣ ከቱርክ ባለሥልጣናት ዘንድ ያገኘው ድጋፍ ከፍተኛ ነባነት ሰጥቶታል። በማይረባ ግጭት ሰዎችን ማስቆጣት የአገሬውን ሕዝብ የጥላቻ ስሜት ሊቀሰቅሰና የዲፕሎማሲያዊ አተካሮ ሊፈጥሩ የሚችሉ አደጋዎች እንደሚሆኑ ቆንሲሉ ከተሞክሮው ያውቃል። ፖንሴም ይህንን ያለጥርጥር ያውቃል። በዚህ ማቢያ ሰውዬው መርዛም ባህርይውን በከፍተኛ ብልግና ቆንሲሉ ላይ ሊያሣይ ማይሞክር አይቀርም።

ምንም እንኳ በእዘቦቱ ጊዜ በውጭ አገር ማህበረሰቦች ላይ ሰፋ ያለ መረጃ ስለመያዝ ክብደት ባይሰጥም «ማህደር ሲበዛ ባዶ ነው፣ ለዚህ ደግሞ የምሥራች አትባልበትም» አለ ቆንሲሉ በአብሪት።

ሰረገላው የሚዞርበትን መስመር አጠናቅቆ በአንድ የግል ቤት ፊት ለፊት ሊደርስ ቆመ። ሁበታሙ ባለቤት፣ በእድናቆትና በደስታ እንግዳውን ለመቀበል ሽርጉድ እያለ ወጣ። እንዲህ ያለው ሁኔታ ጥንቃቄውን ሊጉዳበት ስለሚችል ሞንቅላታሙን ነጋዴ ሊመለከት ዲፕሎማቱም የደስታውን አፀፋ ሊመልስ አለመቻሉን ጠቅሶ መንገዱን እንደሚያቋርጥ ነገረው። ከዚህ በኋላ የሙሴ ማቼን ክንድ ይዞ፣ ጉዳናውን በመጀነንና በክብር አቋረጠ።

ፖንሴና ሚትር ዝረሚ ተዳብለውበት የሚኖሩበት ቤት ከፊት ለፊት ከሚታየው ይልቅ የባለ ደካማ ነው። እርስ በርሣቸው እንዲያያዙ ከተደረጉት ባለሁለት ፎቅ ሕንፃዎች በስተቀር ሌላ የለውም። ሙሉ በሙሉ የጣውላ እንጨት ባይለበጥበት ኖሮ፣ ወደ መንገዱ ሲል ያለው የሕንፃው ግደግዳ አጥር ይሆን ነበር። በጉዳናው የውሃ ልክ እኩል በተሠራው ባለጉበን የሰገነት መወጣጫ ስር አድርገው አንድ ሰው በጥላ ውስጥ ሊንዝ ይችላል። ከበላይ ያለው ፎቅ ከበስተኋላ የሚገኙትን ክፍሎች ቀዝቃዛ እንዲያደርጋቸው ሲባል እንደ ፀሐይ መከላከያ ያገለግላል። የሁለቱ መድሃኒት ቀማሚዎች መኖሪያ፣ በዙሪያቸው ካሉት አጠቃላይ ወጥ ሕንፃዎች አንድ አካል እንጂ ተለይቶ የሚገኝ አይደለም። በውጫዊው መልኩ ከሌሎች ጋር አንድ ነው። ይህ ጥቂት ጉረቤታሞች ያሉበት ሕንፃ ከማህበረሰቡ ውስጥ ዝቅተኛ ኑሮ ያላቸው፣ አዲስ እንግዳ ደራሾች፣ የከሰሩ ሰዎች፣ ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች፣ የታወቀ ሥልጣን የሌላቸው የቅይጥ ዘር ልጆች፣ አንዳንድ ጊዜ ቆንሲሉ ባለው ርህራሄ በማህበረሰቡ ውስጥ ታግሷቸው የሚኖሩ አባላት ተፋፍገውና ንፅህናው ባልተጠበቀ ቅርርብ የሚኖሩበት ነው።

ወደ መድሃኒት ቀማሚው ቤት የሚያስገባው በር ወለል ብሎ እንደተከፈተ ነው። በመንገዱ ላይ መቆም ጥርጣሬን እንዳያስከትል በማሰብ፣ ዲፕሎማቱ፣ ይግቡ የሚል ግብዣ ወይም ፈቃድ ሳይጠብቅ ዘው አለ። ሚትር ዝረሚ ሊያስተናግዳቸው ሲል ፈጠን ብሎ ወደ ቤቱ በሚያደርሰው ጠባብ መተላለፊያ ላይ ቀደማቸው። ክፍሉ፣ የምድር ቤቱን ወለል ሙሉ በሙሉ የሚይዝ፣ ሰፊና ጨለማ የዋጠው ነው። የሥፍራውን ምስቅልቅልነት ለመግለፅ የሚያስቸግር ነው። ለዕይታ ስሜት የሚሰጥ አንዳይሆን፣ ሲበዛ የተለያዩ ነገሮች የተከማቹበት

ነው። በመጀመሪያ ዕይታ፣ በቢጫ ነፀብራቁ ሞላንጭል እየፈጠረ ዐይንን የሚስበው የነሃስ መቀጫ ይስተዋላል። አንገተ ረዣዥም የሸክላ እንስራዎች በጋሰ የከሰል ምድጃ ላይ ተጥደው፣ እንደምሰሶ የተጉተረ ጭስ ከውስጣቸው ወደውጭ ይተፋሉ። ጭሱ ግን፣ በአንዳች ምስጢራዊና ከባድ ነገር ጫና እንደተደረገበት ያህል ተመልሶ አግድም በግድግዳዎች መሃል ይሰምጣል። በአንድ ጥግ በኩል፣ በአንድ የገለባ ፍራሽ ላይ ያለቀ አንሶላ ተነጥፏል። ኮርኒሱ ዝቅ ያለ ሲሆን በጥቀርሻ ብዛት ጠቁሯል። በዚያ ላይ መቶ ወይም ሁለት መቶ የሚሆኑ የቀርቀሃ ቅርጫቶች በውስጣቸው የደረቁ ዕፅዋትን፣ የጠወላሰጉ ፍራፍሬዎችን፣ በአይጦች የተተፈተፉ የዳቦ ቅራፊዎችን ይዘው ተንጠልጥለዋል።

በረኸሙና ሰፊው ቁመናው የኮርኒሱን አውታር እየቦረሸ «ወደ ቤተሙከራችን እንኳን ደህና መጡ ስል ታላቅ ክብር ይሰማኛል፣ ክቡር ሆይ»

«ሽሪክህስ እውስጥ አሰ አንዴ?»

«ፎቅ ላይ ነው»

በደብዛዛው ክፍል ውስጥ ቀጭን ብርሃን ከፎቁ ወደ ምድር ቤቱ ይወርዳል። በዚያ ክፍተት በኩል የሚያስወጣ የጣውላ ደረጃ አለ። ቆንሲሱና ሙሴ ማቹ እየተንተቱ ደረጃውን ወጡ።

ከላይ ያለው ክፍል እንደታችኛው የጨለመ ሣይሆን ብርሃን የሞላበት ነው። ዙሪያውን ባሉት አራት መስኮቶች የሚገባው ብርሃን ክፍሉን ወለል አድርጉታል። መስኮቶቹ ወደ ጐዳናው ሲል ወደ ሚገኘው በረንዳና በጉን ወደ ሚገኘው ሰገነት ይከፈታሉ። የዚህ ክፍል ኮርኒስ አንድም ተክኒል ወይም ጨርሶም አልነበረውም። በዚህም የተነሣ የጣሪያው ወራጅና ግራጫ የሆነው የጣሪያው ክዳን ጡብ፣ ወለል ብሎው ይታያሉ።

ቦታው ሙሉ በሙሉ በቅጠሎች የተሞላ ነው። ሙሉ እድገታቸው ላይ የሚገኙና ከነሥራቸው በትልቅ የእንጨት ገንዳ ውስጥ ተተክለው ብርሃንና የርጥበት መቀት ለማግኘት ሽቅብ አድገው የተመዘዙ ዛፎች ይታያሉ። አንድ እጅግ ግዙፍ የቁልቋል ዛፍ በፎቁ ጣሪያ ላይ ከተተከሉት ዕፅዋት ጋር በቁመት ተስተካክሏል። በድምቀት የሚያብረቀርቁ፣ ግንዳቸው በፀጉር የተሸፈነ የሚመስሉ ሌሎቹ በእሾህ የተከበቡና ቅርንጫፎቻቸው የተንዘረፈፉባቸው ትላልቅ

ተክሎች አሉ። በግዙፎቹ ተክሎች መካከል በሚገኙት ባዶ ቦታዎች ላይ ብዛት ያላቸው የተለያዩ ትናንሽ ዕፅዋት አሉ። የዚህ ክፍል ወለል ወደ አትክልቱ ስፍራ በሚወስደው በረንዳና ሌላው ጐዳናውን ሊያሳይ ወደሚችለው ሰገነት የሚወስዱ ቀጫጭን መተላለፊያዎች በስተቀር ሙሉ በሙሉ በትናንሽ ማሰሮዎች የተሞላ ነው። መሣሀፍት የተከመሩበት አንድ ጠረጴዛና ጨለማ ከሚለው ጥግ በቀር አንድ አነስተኛ ቁም ሣጥንም አለ። በመካከለኛ ቁመት ክፍታ፣ በግድግዳው ላይ ካሉ የነሃስ ወይም የቆርቆሮ ማንጠልጠያዎች ላይ የተሰቀሉ ወይም ከጣሪያው ርብራብ ላይ በተቋጠሩ ሲባጎዎች ታስረው የተንጠለጠሉ በደርዘኖች የሚቆጠሩ ግንዶቻቸውና ቅጠሎቻቸው ወፍራም ሆነው በተፈጥሯቸው ብዙ ውሃ የሚይዙ ተክሎች፣ የእንጨት ወይም የድንጋይ ሽበት የሚታዩባቸው፣ ውብ መዓዛ ያላቸው ትላልቅ አበቦችና ሌሎችም ፋፍተውና ዳብረው ይታያሉ።

ቆንሲሱና ፀሐፊው ለጥቂት ጊዜ በዝምታ ተዋጡ። እንዲህ ፍፁም ልዩ በሆነ የአረንጓዴ ዕፅዋት ማሣደጊያና ማራቢያ ቤት ውስጥ፣ ማንም ሰው የትናንሽ ወፎችን ክንፎች መርገብገብና ጫጫታቸውንም መስማት ይችላል። ሜትር ገረሚ ወደ ፎቁ አልወጣም። ሁለቱም ጉብኝ ዎች በዚህ ምድራዊ ገነት በሆነ ቦታ ሌላ የሰው ፍጡር ይኖራል ብለው አላሰቡም።

«ግቡ፣ ግቡ ጌቶቼ» ሲል ከላይኛው የክፍሉ አካል ከአንድ ቦታ የተላከ ድምፅ ጋበዛቸው።

ዲፕሎማቶቹ አንድ ሁለቴ ወደፊት ራመድ አሉ። የወለሉ ንጣፍ ጣውላ ባልተቋረጠ ሁኔታ ውሃ ስለሚፈስበት ሲረግጡት ይንሳጠጣል። በክፍሉ በስተጀርባ በሰው ቁመት ልክ በሚሆን ከፍታ ላይ፣ ከመረብ የተሰራ ባዶ ተወዛዋዥ አልጋ ይታያል።

«ይህን አስቸጋሪ የማዳቀል ሥራ እንደጨረስኩ አመጣለሁ። አስከዚያው ድረስ እባክችሁ ተቀመጡ። ጠረጴዛው አጠገብ ሁለት በርጮማዎች አሉላችሁ።» አለ ድምፁ።

ዐይኖቹ አጥርተው የማያዩለት ሙሴ ማቹ፣ በረኸሙ ዛፍ ላይ የተደገፈውን መሰላል ቆንሲሱ እንዲመለከት አቅጣጫውን በእንቅስቃሴ መራው። በመሰላሉ የመጨረሻው የመርገጫ ማዣር ላይ የሚተጣጠፍ የቆዳ ቦት ጫማ የተጫመ ሁለት እግሮች ይታያሉ።

«ደህና፣ ደህና፣ ሥራህን ስትጨርስ ትደርሳለህ» አለ ቆንሲሉ ንዴቱን በትንሹ በሚገልፅ ቃና ጮክ ብሎ።

ቆንሲሉ፣ በእንቅስቃሴ ሙሴ ማቼን አመሰከተው። ሁሉቱም ድምፁ ወዳዘዛቸው ቦታ ለመድረስ በየማሰሮው ላይ እየተራመዱ፣ የማይሰተዋሉ የቆንጥር አሻሆች የእግር ሹራቦቻቸውን እየያዙባቸው በዝግታ ወደ ጠረጴዛው አምርተው ተቀመጡ።

«እነዚህ ቁርጥራጮች ሊፀድቁበት የሚችሉበት ወቅት ከእንግዲህ አጭር ነው። የኛ ሙያ ተስፋ የሚያደርገው በማዳቀል ሥራ ላይ ነው። በተፈጥሮ የምናገኘው ዕፅ ጥሬ ሃብታችን ነው። ወይኔ! ወይኔ! ወይኔ፣ ይህች ትንሽ ሸቦ ድጋሚ ተሰብራ ወደቀች። እባካችሁ ይቅርታ አድርጉልኝ» ሲል ከመሰላሉ በላይ ያለው ድምፅ ተናገረ።

ቆንሲሉ፣ ቁጣውን ሊደብቅ የሚችልበት ትዕግስት ከዚህ በኋላ አይኖርም ከሚል ፍርሃት «ይገባናል» ሲል ሙሴ ማቼ መሰሰለት

«እንዳልኩት የተፈጥሮው ተክል ጥሬ ሃብት ነው። ይህን በማዳቀል አንዱ ሌላውን እንዲደግፍ ማድረግ ያስፈልገናል። ለኛ የነገሮች መነሻ ምንጊዜም ተፈጥሮ ነች። ቅመሞቹ ሁሉ በእጃችን ውስጥ ናቸው። የምንመረምረው እነዚህን ቅመሞች እንዴት እናስተባብራቸዋለን የሚለው ነው»

በጠረጴዛው ላይ መጠናቸው የተለያዩ ወረቀቶች ተቆልለዋል። ቆንሲሉ፣ በድንጋጤ ያንሳጠጣቸው ጀመር። በአዝዕርትና ዕፅዋት ሣይንስ ላይ የተፃፉ የሆራስ ግጥሞችና ትልልቅ መጠን ባሏቸው ብዙ ወረቀቶች ላይ በአረቢኛ የተፃፉ ቅፆች ናቸው።

ለሻቦላ ግጥሚያ የሚያስፈልጉ ሁሰት ሻምላዎች በመጠቅለያ ተደርገው በአንድ ወፍራምና ጠንካራ ግንድ ላይ ተንጠልጥሰዋል። ወለሉ ላይ የእጅ ጓንቶች፣ የደረት መክላከያዎችና የፊት ጭምብሎች ወድቀዋል።

«የሥራችንን ሁኔታ በተመለከተ ውይይታችንን ለመጀመር እንድንችል እንኳን ደህና መጣችሁ አላለሁ። ጆን ባፕቲስት ፖንሴ እባላለሁ። አንድ ነገር ልትነግሩኝ እንደመጣችሁ አስባለሁ።»

«ጌታው» አለ ቆንሲሉ ከመቀመጫው ላይ እየተነሣ።

«የመጣሁበት ጉዳይ እጅግ በጣም አስቸኳይ እንደሆነ ርግጠኛ ልትሆን ይገባሃል። ይህ ባይሆን ኖሮ ወደዚህ ልገብኝህ አልመጣም ነበር። ምኞቴ ሁሉ በእውነት አንተን ለማግኘት ነበር። እርስ በርሣችን ልንደማመጥና ልንግባባ እስከቻልን ድረስ ሁሉም መልካም ነው»

«እውነት ነው» አለ ጆን ባፕቲስት ቢጋለና ከልብ በመነጨ ድምፅ። «የጀመርኩትን ሥራ ከፍፃሜ እንዳደርስ ስለፈቀዳችሁልኝ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ያ ባይሆን ኖሮ የደስምክብት ሁሉ መና ይቀር ነበር»

«ሙሴ ፖንሴ» አለ ቆንሲሉ በድንገት ተነስቶ ቆሞ፣ ጣሪያ ጣሪያውን እያየ። «ለመሆኑ የመድሃኒት ቅመማ ሥራ ማከናወንህ እውነት ነው?»

«አዎ፣ ይህ ዓይነቱ ጊዜ እንደሚመጣ ሁልግዜም አጠበቅ ነበር፣ ክፉር ሆይ። ከዚህ በኋላ እውነቱን ልንደብቅም አንችልም። ስለዚህ ጉዳይ ቀደም ብሰን ባለመናገራችን የቅሬታ መነሻ እንደሚሆን ይሰማኛል። በርግጥ ለሁሉም መልካም የሆነን ጉዳይና ሥራ በመደበቅ ደስታ እንደሌለም አውቃለሁ። እርስም ይህን ሥራ እንደሚጠሉትም አውቃለሁ። አሁንኑ አዘሁ እያሉ ናሙናዎችን አሣይዎታለሁ።

«ስማ ፖንሴ፣ ጥያቄዬ ቀላልና ቀጥተኛ ነው። የሥራ ፈቃድ የመክልከል ሃሣብ በውስጤ የለም። እንዲያውም የተገላቢጦሹ ነው። በድጋሚ አጠይቅሃለሁ። አንተም በቀላሉ እንድትመልስልኝ አፈልጋለሁ። የመድሃኒት ቅመማ ሥራ ታከናውናለህ?»

«አዎን?»

«ለምሣሌ በአገሬው ሰዎች ላይ የሚታየውን ቁምጥና መሰል የቆዳ በሽታ ፈንገስ ማከም ትችላለህ?»

«እንዲህ በቀላሉ የምመልሰው ጥያቄ አይደለም። ይህ ማለት መፍትሔ የለውም ማለቴ ግን አይደለም። በሕክምና ላይ እያንዳንዱ ሕመም በየግሉ ነው የሚታየው»

«በዚህ ነጥብ ላይ ይህ በቂ ነው» ሲል ቆንሲሉ አቋረጠውና «ሴላ ጥያቄ ላቅርብልህ? እዚህ የመጣሁት ታላቅ ክብደት ያለውን አንድ የዲፕሎማሲያዊ ተልዕኮ እንድትቀበል በክብር ልጠይቅህ ነው»

«ዝረሚ! ይህ ሽቦ፣ ይህ ሽቦ!» በመስላሉ ላይ ያለው ሰው ጮኸ

«ሰምተኸኛል?» ሲል ቆንሲሉ ጠየቀው

«አዎን፣ አዎን፣ ይቀጥሉ»

«የፈረንሣይ ንጉሠ ነገስትን መልዕክት ተቀብለህ ለማድረስ ትፈቅዳለህ?»

«ምን አይነት?» ሲል ፖንሴ ሞንቅላቱን ወደ ፎቁ ብቅ እያደረገ በከፍተኛ ድምፅ ጠየቀ።

«ይህ የመዳብ ሽቦ፣ እባክህ አዲስ ጥቅል ልታመጣልኝ ትችላለህ? ጓደኛዬ፣ ይህ እዚህ ያለው ይበጣጠሳል»

«ሙሴ ፖንሲ፣ የማነጋግርህ እጅግ በጣም ታላቅ በሆነ ጉዳይ ላይ ነው። ከዚያ ዛፍ ላይ ወርደህ ሁለት ደቂቃ ያህል እንኳ ልትሰጠኝ አትችልም እንዴ?» ሲል ቆንሲሉ በለስነ እርጋታ ጠየቀው።

«ጨርሻለሁ፣ ሁለት ወይም ሦስት ቋጠሮዎች ቢቀሩኝ ነው። እንዳለ ከተውኩት ሁሉም ነገር ይወድማል። አይዞም አይስጉ። የተናገሩትን ሁሉ ሰምቻለሁ። ለንጉሠ ነገስቱ የዲፕሎማቲክ መልዕክት . . . »

«የክርስትና እምነት ታላቅ መሣሪያ ሊያደርግህ የሚችል ፣የብፁዕ ሊቀ ጳጳሱ አኩሪ መሣሪያ ሊያደርግህ የሚችል ተልዕኮ ነዎ»

«ነገርኩዎት ክቡር ሆይ። ጥያቄዎን ሊያረካና እርስዎን ሊያስደስት የሚችል ማንኛ ውንም ነገር አለራለሁ። ነገር ግን ለነዚህ ይፋ ለሆኑ ጉዳዮች እምብዛም ደስታ የለኝም» ሲል አንዳችም የጉጉት ስሜት በሌለበት ድምፅ ፖንሴ ተናገረ።

«ይህን ጉዳይ በሌላ መልክ ላቅርብልህ። ጥያቄው ለአንድ የነፃ አገር መሪ ሕክምና የመስጠት ጉዳይ ቢሆንስ?»

«ለንጉሰ ነገስት ሉዊስ 14ኛ?»

«አይደለም። ነገር ግን የፈረንሣይ ንጉሠ ነገስት ሊልኩህ ወደሚፈልጉት ነፃ የአገር መሪ ነው። ይገባሃል? የአንድ ታላቅ ንጉሥን ሰውነት በማከም መደነቅና ክብር አለ። አይመስልህም?» ሲል ቆንሲሉ፣ በዚህ የሕይወት ተሞክሮው አነስተኛ በሆነ ገራገር ሰው ሁኔታ ትዕግስት በማጣት ተናገረ።

«አዩ ጌቶች! እኛ ሐኪሞች የሰውን አካል ስንመለከት አንዳችም ንጉሠ ነገስትነት የሚባል ነገር የለም።»

ሙሴ ማቼ ቀና ብሎ ቆንሲሉን ሲመለከተው፣በርሱ ውስጥ የተፈጠረውን ዓይነት ተስፋ አስቆራጭ አዝማሚያ አነበበበት። ይህ ስሜት ደግሞ በማንኛውም ጊዜ የአፍ አላፊ ዘለፋና ስድብ ሊያስከትል ወይም ወደ ልቅሶ ሊለውጥ ይችላል።

«እንግዲህ፣ ክቡር ቆንሲል፣ እዚህ ድረስ የመጡት እኔን ፈልገው ስለሆነ ሃሣቤን እለውጣለሁ። ሕክምና የሚሻው ንጉሥ ቢሆንም ባይሆንም እርስዎ እኔ እንዳከመው የሚፈልጉት ሰው እስከሆነ ድረስ ስርስዎ ስል እየርገሞለሁ። ተስፋ የማደርገው ግን ቦታው ከዚህ እጅግ እንደማይርቅ ነው። ምክንያቱም አሁን የያዝኩት እጅግ ብዙ ሥራ ስላለኝ፣ ለረዥም ጊዜ ልቀይ አልችልም»

«እንዲህ ከሆነ እስከአሁን ስንነጋገር የነበረው ሁሉ እርባና የሌለው ነው ማለት ነው።» በማለት ተናግሮ ቆንሲሉ ወንበሩ ላይ ተመልሶ ዘጭ አለ።

«ይቀጥሉ፣ አስቲ ልወቀው»

«እንደእውነቱ ከሆነ ይህ ሥራ ለአጭር ጊዜ የሚደረግ የቤት ውስጥ ደርሶ መልስ ጉብኝት አይደለም። እንደምገምተው የሕመምተኛውን አልጋ ለመድረስ በትንሹ ከስድስት ሰዎች በላይ ይወስድብሃል ብዬ እገምታለሁ።»

«ስድስት ወሮች፣ እንዴት ሊሆን ይችላል ይላሉ?»

«የአበሻውን ንጉሥ በራሱ ቤተመንግስት ውስጥ ለማከም ነው?» አለ ቆንሲሉ። በዛፉ ቅርንጫፎች ውስጥ ረዥም ፀጥታ ሆነ። ከዚህ በኋላ መሰላሉ ሲንቀጠቀጥና ሁለት እግሮች በመወጣጫው ላይ ቁልቁል ሲወርዱ ጉብኝዎቹ ተመለከቱ።

ጀን ባፕቲስት ፈጥኖ ወለሉ ላይ ደረሰ። በሸሚዙና በወጉሩ ላይ የተጣበቁትን ትንንሽ ቅጠሎች አራግፎ ወደ ዲፕሎማቶቹ በዝግታ አመራ።

ምናልባት በሕዝብ አዕምሮ ውስጥ፣ አንድ ሐኪም እንደ አንድ ብልህ ሊቅ ሰው፣ ሽምገል ያለ ይመስላል ከሚለው ጠንካራ አስተሳሰብ በመነሣት ሲያስበው እንደነበረው ሣይሆን፣ ሙሴ ዴ ማይሌ ከገመተው ይልቅ ፖንሴ በጣም ወጣት ሆኖ አገኘው።

ከዚህም ባሻገር፣ ቆንሲሉ አሁን ከፊት ለፊቱ ስለሚመለከተው ሰው አካላዊ ቁመና ብዙም አላስተዋለም። ቆንሲሉ አስቀድሞ ያስተዋለው ስላላስደሰተው ባህርይው ነበር። በፀሎት ሥነ-ሥርዐት ላይ ያለውን ትህትና፣ ገና የመጀመሪያውን እንቅስቅሴ ሲመለከት፣ ተገድዶ ለማስመሰል የሚያደርገው ዓይነት ነገር የለበትም። እንኪንስ ሊቅለሰለስ የአክብሮት ምልክት አይታይበትም። ግልፅና ተፈጥሮአዊ ቢሆንም ስሜቱን ስለሚነኩ ጉዳዮች አንዳችም የሚታወቅ ነገር የለም። ሁለቱ ጉብኚዎች አመዳቸው ቡን አሉ። ቀጥሎም ላብ አዘፈቃቸው። የባለሥልጣንነት አቋማቸውን ለማረጋገጥ ጨነቃቸው። የውይይታቸው ተካፋይ የሆነው ሰው ለማንኛውም ሰው እንደሚሆነው ሁሉ ጠንካራ የማወቅ ፍላጐት ያለው፣ ግልፅና የርህራሄ ስሜት ያለው ቢሆንም ለእነርሱ ግን የብልግና ቁንጮ መሪ መስላቸው። እንዲህ ካለ እንግዳ ባህርይ ጋር የተፋጠጠው ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ከመቼውም በበለጠ ራሱን ተቆጣጥሮ ፀጥ አለ። ሙሴ ማቹ፣ ሰውነቱን ሁሉ ወዲያውኑ ጥላቻ ሲወርረው ተሰማው።

ቆንሲሉና ፀሐፊው ነፃነትን ወዲያውኑ ጠሏት። ምክንያቱም በእንደኛቸው አስተሳሰብ ነፃነት እጅ እንድትሰጥ የምትደረግ አይደለችም። በሌላኛው አስተሳሰብ ደግሞ ነፃነቱን እሸሩሩ ላይላት በመኖሩ ተፀፅታል። ሁለቱም በየምክንያቶቻቸው ነፃነትን ጠሏት። ይሁንና ሁለቱም እዚሁ ፊት ለፊታቸው በመገለፅዋ የግዳቸውን አወቋት። ከአፍታ ፀጥታ በኋላ፣ ጀን ባፕቲስት የመፈኪያውን እርምጃ ወደፊት ተራምዶ አጠገባቸው ከደረሰ በኋላ ፊገግታ በተሞላበት

«የአበሻው ንጉሥ! ይህ ከሆነ ጌቶቼ። ይህ በቁም ነገር የምንጋገርበት ጉዳይ ነው» አላቸው።

7

ማዳም ዴ ማይሌ፣ በመጀመሪያው ደረጃ ላይ ቆማ ባለቤቷን ትጠብቀዋለች። ትንፋሽን በሚያጠፋው ሙቀት ውስጥ በቻይናውያን ዕጌረዳዎች የተጊያጊያጠውን የወረቀት ማራገቢያ በፍጥነት ታወዛውዘዋለች። ሰረገላው በአምስት ሰዓት ላይ ተመለሰ። ቆንሲሉ ከረዳቱ ጋር ወረዱ። ማዳም ዴ ማይሌ ወደ ባሏ ሮጠች።

«ውዴ ሆይ! እባክህ ጥቂት ዕረፍት እንድታደርግ አለምንሃለሁ። ዕረፍት እኮ አጣህ። የአየር ጠባዩም በጣም አደገኛ ነው። ልብህም . . . »

«ስለኔ ስጋት አይደርብሽ። ይልቅስ በክባድ ችግር ውስጥ ስላለው ስለመንግሥት ጉዳይ ተጨነቂ። አሁን ግን አባ ቬርግውን በዚህ ሰዓት የት ላገኛቸው እንደምችል ንገሪኝ» አላት ቆንሲሉ

«ዛሬ ሧት ሊጉበኟቸው ከመጡ ሁለት የጀስዊት ቀሣውስት ጋር ከአንድ ሰዓት በላይ ለሚሆን ጊዜ ክፍላቸው ውስጥ ዘግተው ነው ያሉት»

ቆንሲሉ፣ ለሙሴ ማቹ፣ እንዲንቀሳቀስ ምልክት በመስጠት ወደሁለተኛው ፎቅ ጉዞ ጀመረ።

ለጀስዊቱ ቄስ የተወሰነላቸው በጣም ሰፊ ክፍል በጓሮ በኩል ዝቅ ያለ ጣሪያ ወዳለው የጽሕፈት ቤት ያመራል። ቀሣውስቱ በዚህ ክፍል ውስጥ ኮሚቴ ጀምረው ቆይተዋል። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ሲያንኳኳና እንዲገባ ሲፈቀድለት ዘው አለ። ሙሴ ማቹም ተከትሎት ገባ። ጥቁር ካባ ለብሰው በጠረጴዛው አጠገብ ከተቀመጡት ሦስት ካህናት ዘንድ ተቀመጡ።

«ከምታውቋቸው ከአባ ጋቦሪ እና አስክአሁን አይናችሁን እንዳላሳረፋችሁባቸው ተሰፋ ከሚደርግባቸው ከአባ ዴ ብሪቬዳንት ጋር እንዳስተዋውቃችሁ ፍቀዱልኝ» አሉ አባ ቬርግው

ዲፕሎማቶቹ ለሁለቱ ካህናት ሠላምታ አቀረቡ። አባ ጋበሪ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ቢያንስ ለአሥራ አምስት ዓመታት ኖረዋል። አራት ማዕዘን ቅርፅ ያላቸው፣ ወፍራም፣

የእጆቻቸው ቅላት ከፊታቸው ጋር የሚመሣሰል ናቸው። የፈረንሣውያን ማህበረሰብ ልጆችን ያስተምራሉ። በሁሉም አቅጣጫ በቅሎ ምስቅልቅል ያለው ወጣ ገባ የላይኛው ጥርሣቸው፣ ከታችኛው ጥርሣቸው ጋር ሣያስተግራቸው በእኩልነት ገጥሞ እንዴት እንደሚዘጋላቸው ብዙ የሕፃናት ትውልድ ሰመረዳት ሙከራ ያደርጋል። ይሁን እንጂ እኚህ መልካም አባት ንግግራቸውን ሲያቆሙ ተአምረኛው ጥርሣቸው ተመልሶ ያው ነው። የአውሬ የሚመስለው አስፈሪው አፋቸውም እንዲሁ በርጋታ ይከደናል። የዚህ የመንጋጋቸው መሻሸፍ ዋናው ሰበብ፣ በሌላው ሁሉ ሪገድ እንከን የለሽ ቢሆኑም ለፈሣሽ ነገሮች የተለየ ዝንባሌ ያላቸው መሆናቸው ነው። ቀደም ሲል እንደገለፅነው ቆንሲሉ በወይን ጠጅ ንግድ ላይ የሞኖፖል አቅም ቢኖረውም፣ የአልኮል መጠጦችን ለህፃናት በዋጋው በማቅረብ በኩል ቸር ነው። በደረቡት ካባና በጫኑት ቆብ መሠረት ፍጆታቸውን በተወሰነ ገደብ ውስጥ ካደረጉ፣ ቆንሲሉ የለመደውን ትርፍ ቀነስ ያደርግላቸዋል። ይህን ዓይነት ሥርዓት የሚጥሱት አባ ጋበሪ ብቻ ነበሩ። ሙሴ ዲ ማይሌ፣ ቁሱን ቅድስና የሌላቸው ለካራም ናቸው ሲላቸው፣ ቁሱም፣ እርሱን ተራ ሌባ ነው ማለታቸው አልቀረም።

ሌላኛው የጀስዊት ቁስ በሁለመናቸው ተቃራኒ ናቸው። ቁመተ ረዥም ሆነው እግረ ስባራ ናቸው። ቀጭን ናቸው ባይባልም አጠቃላይ አኳኋናቸው ለስላሣና ደካማ ነው። በሸምበራ አፍንጫቸው ላይ የመዳብ ፍሬም ያለው የአይን መነጽር ሰክተዋል። መንማናው የፊታቸው ክፍል በአጭሩ ከተቆረጠው ፀጉራቸው አፈንግጠው የሚታዩትን ግንባራቸውን፣ አፋቸውንና አገጫቸውን ያጉሊቸዋል። እነዚህ ወደውጭ በጣም አፈንግጠው የወጡት የፊታቸው ክፍሎች ደግሞ ከአጥንት ይልቅ የሥጋ ክፃሮች ይመስላሉ። ወፍራሙ ከንፈራቸው በቀላሉ አይከደንም። የአንገታቸው ቆዳ ወደ አገጫቸው መንጠልጠል ጀምሯል። እኒህ ጉባጣ ሽማግሌ የግንባራቸው ወጣ ወጣ ማለት፣ መነፅር ማድረጋቸው፣ አጥንትና ቆዳ የሆኑት እጆቻቸው፣ የወየቡ የወረቀት ገፆችን የማገላበጥ ልማዳቸው ተዳምረው ድንገት ሲታዩ ምሁር ያስመስሏቸዋል።

«በጣም ትክክል ነዎት፣ አባ ዴ ብሬቤደንትን አላውቃቸውም» አለ ቆንሲሉ እጅ እየነሣ

«ከመጡ ገና ሁለት ወራቸው ነው። እንደምታውቀው ቱርኮች በጣም ያስቸግሩናል። በአፊሴል እዚህ ቋሚ ኗሪ ሲኖረን የሚችለው አንድ አባላችን ብቻ ነው። ሌሎች ተራ ጉብኝ ሦች ናቸው። ስለዚህ ባለሥልጣናቱን በተመለከተ አባ ዴ ብሬቤደንት ተራ ጉብኚ ናቸው»

አባ ዴ ብሬቤደንት በፍርሃት ፈገግ አሉና ጭንቅላታቸውን ሙሉ በሙሉ ሣያዞሩ ቆንሲሉን በዐይናቸው ቁጥ አዩት።

«እና ሆኖም ግን፣ ሊሆን የሚችል መልዕክተኛ አገኘህ?» አሉ አባ ቬርሣው

«አዎን አባቴ፣ ቀላል ባይሆንም አንድ አግኝቻለሁ። ሰውዬው በወሰጡ ጠንካራ የተፈጥሮ የጀብደ ስሜት ያለበት፣ የህክምና ባለሞያና የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ፈረንሣዊ ነው»

«ይህ በርግጥ እግዚአብሔር ፀሎታችንን ስምቶ የሰጠን መልስ ነው» በማለት የጀስዊቱ ቁስ ንግግራቸውን እንዲያፀድቁላቸው ዙሪያቸውን ቃኙ «ሙሉ በሙሉ ተቀበለ?»

«እንዴት ልበል . . . ከምሣ በኋላ እዚህ ይደርሣል። ውሣኔው ገና አልተቋጨም። እንደሚመስለኝ ግፊት ባናደርግበት ጥሩ ነው። የተልዕኮውን ዝርዝር እርስዎ በቀጥታ እንዲገልፁለት ዕድሉ ይኖርዎታል። እርስዎ ይፍቀዱት እንጂ ቃል ኪዳኑን ሲያጠናክርለት በሚችለው በስልጠናው ላይ ሁላችንም እንገኛለን»

ሙሴ ዲ ማይሌ፣ ወዲያውኑ ስለተባለው ሰው ዝርዝር መግለጫ ሰጠ። የሰውዬውን ባህሪይ እያደነቀና ግራ የሚያጋባም መሆኑን እያስረዳ፣ የአረማመዱን ጥበብ ለማሣየት ጥንቃቄ የተሞላበት እርምጃ አከናወነ። ስለዕፆው በግልፅ የሚገመት የዕድሜ መጠን ለአባ ቬርሣው መግለፅ አስተዋይነት እንደሆነም ገመተ።

«ሊያዩት ወጣት ነው። ነገር ግን በእጃችን የሚገኝ የፖሊስ መረጃ፣ ሰውዬው ሊያዩት እንደሚመስለው ሣይሆን ጠና ያለ ነው።»

ቆንሲሉ እየሣቀ «ምናልባት በተክሎች ላይ ከልቡ የሚያከናውነው ሙከራ በትክክል መሥራቱን ለማረጋገጥ በራሱ ላይ ስለሚፈትሽ የዚያ ውጤት ይሆናል»

«ወጣት መድሃኒት ቀማሽ?» ሲሉ አባ ቬርሣው ጠየቁ። አባ ቬርሣው ዕድሚአቸውን ሙሉ መጠኑ የተወሰነ የእትክልት ጭማቂ እንደመድሃኒት ይወስዱ ነበርና ትንሽ ተግሳቱላቸዋል።

«እንደዚያ ሣይሆን አይቀርም ብዬ አስባለሁ። አለበለዚያ ያልተለመደውን ዓይነት የተክሎች አጠባበቁን ሁኔታ ለመግለፅ አዳጋች ነው»

ማጻም ዴ ማይሌ፣ የምሣ ገበታ መዘጋጀቱን ለመግለፅ አንድ ተላላኪ እስክ ላከችበት ጊዜ ድረስ ሁሉንም ዓይነት በሽታ ማዳን ይችላል ስለሚባል መድሃኒት፣ ቀሣውስቱና ሙሴ ዴ ማይሌ ለጥቂት ጊዜ ሲወያዩ ቆዩ። ከዚህ በኋላ ሁሉም ወደምድር ቤት ወረዱ።

ማጻም ዴ ማይሌ፣ በምሣ ገበታው ላይ ተካፋይ ሆነች። በንጉሠ-ነገስት ሉዊስ 14ኛ ትዕዛዝ ወደ ኢትዮጵያ የሚደረገውን ተልዕኮ ለማደፋፈርና መልዕክተኛው እንዲቀበለው ለማደረግ፣ አባ ቬርሣው ማንኛውንም ዝርዝር መግለጫ እጅግ በማጣፊጥ በውይይቱ ላይ አቀረቡ። ቆንሲሉ፣ የተልዕኮው አጠቃላይ ምስጢር መገለፁ ግብዝነት እንደሆነና ምናልባትም ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ተሰማው። ይህን አብይ ጉዳይ በተመለከተ ፍፁም ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ መያዝ እንዳለበት ዛሬ ማታ ለሴት ልጁ ለመንገር ለራሱ ቃል ገባ። በዚህ ሁሉ መካከል የቀረበው ምግብ ግሩም ነበር። አባ ቬርሣው፣ ስለአበሻ ነገሥታት የሚታወቀውን ሁሉና በክፍለ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ በጀስዊቶች ሃይማኖቱን ስለለወጠውም ንጉሠ ነገስት ጭምር ተናገሩ። ጀስዊቶች፣ ሲታሰቡ የሚኖሩባቸውን ታሪኮች በኢትዮጵያ ውስጥ መሥርተው እንደነበር፣ በተጓዳኝ ደግሞ ከአገር እንዲወጡ ታላቅ ሃይማኖታዊ ጥቃት በካቶሊካዊያን ላይ እንደተፈፀመባቸውም አስረዱ። ከዚህ በመቀጠል ተልዕኮው ሊያጋጥመው የሚችለውን አደጋ፣ የአየር ጠባዩንና በጉዞው መስመር ላይ የሚገኙ ሕዝቦችን እጅግ አስቃቂና ጭካኔ ያለባቸው መሆናቸውን ገለፀ። ምሣ ሲጠናቀቅ ሁሉም ተጋባዥ በደስታና በፈንጠዚያ ስጋዊ ስሜቱ አመዝኖበት ይታይ ነበር። ምንም እንኳ የውይይቱ ርዕስ ኮስተር ያለ ጉዳይ የያዘ ቢሆንም፣ አንዲህ ያለ ታላቅ ደስታና የጋለ ስሜት በዚህ ቤት ውስጥ የማይታወቅ

መሆኑን ቆንሲሉ አመነ። ሁሉቱ እንግዳ ጀስዊቶች፣ በንፅፅር ሲታይ ጥሩ ሁኔታ ላይ አልነበሩም። አንደኛው፣ ቡተለይም አባ ብራቬዳንት፣ ስለሚፀፅታቸው ጉዳይ የሚናገሩትን አሳቋርጥ አሉ። ሌላኛው፣ ከበፊቱ ይልቅ እያስተሱና በርበሬ እየመሰሉ ከሦስተኛው ብርጭቆ ወይን በኋላ በተቀመጡበት ማንኮላጀት ጀመሩ።

ጋባዦችና ተጋባዦች ምሣቸውን አጠናቅቀው ገበታው ከፍ በሚልበት ጊዜ፣ አስተናጋጁ ተርሆ ሙሴ ፖንሴ መምጣቱን ተናገረ። ሴቶቹ ወዲያውኑ ወጡ። የቀሩት የንጉሠ ነገስቱ ሥዕል ባለበት የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ቡና እየጠጡ ሲቀበሉት ወሰኑ።

ፖንሴ ወደ አዳራሹ ገባ። ልብሶቹን ለመቀየር አልተጨነቀም። ጥቁር ስማዮዊ ጃኬቱን ሳያቆልፈው በሸሚዙ ላይ ደርቧል። ባርኔጣ የለውም። እጅጌዎቹ ቁልፎች የሏቸውም። ከዘራም አልያዘም። ዞር ሲል፣ ጥቁር ጥምልምል ፀጉሩ በነፋነት ይዘናፈላል። ሲገባ፣ እርሱን የሚመለከተው ጭውውት ወደ ደስታ ስለተለወጠ፣ አረንጓዴ ምልክት የሚታይባቸውን ቀሚሳቸን እጆቹን እያወዛወዘ በአየር ውስጥ የሚንሣፈፍ ይመስል ወደፊት ተራመደ። ቆንሲሉና ሦስቱንም ቀሣውስት፣ እያንዳንዳቸውን አይኖቻቸው ውስጥ እየተመለከታቸው ሰላምታ አቀረበላቸው። ቆንሲሉ የመግቢያውን ንግግር አደረገ።

በቀጥታ ከንጉሠ ነገስቱ ሥዕል ሥር በባለመደገፊያ ትልቅ ወንበር ላይ የተቀመጡት አባ ቬርሣው በግርማ ሞገስ ተናገሩ።

«ሙሴ ጆን ባፕቲስት ፖንሴ» ሲል በትህትና ጀመረ። «ወደ አበሻ ንጉሥ በሚደረገው ጉዞ ተካፋይ በመሆን የፈረንሣዩን ንጉሠ ነገስት መልዕክት ለማድረስ መስማማትህን በይፋ ቀናግረህ ልታረጋግጥልን ትችላለህ?»

የፖንሴ ፊት በደስታ ፈካ።

«ጌቶች፣ በአንድ የሚያሳድፍ ጉዳይ ላይ ያላችሁ ይመስለኛል» አለ እየሣቀ። «እስከአሁን ከፊት ለፊታችሁ እንደተገተርኩ አለሁ። ከሰዓት በፊት፣ ሙሉውን ጊዜ ስሰራ ነው የዋልኩት። ሙቀቱ ሌሎቹን ሰዎች ከመንቀሣቀስ ባገደበት በዚህ ሰዓት ወደዚህ የመጣሁት

ሞር ባለው ጉዳና ብቻዬን ተጉዤ ነው። ከዚህም በላይ ቡናና ብስኩቶችም አመለከታለሁ። . . . »

«ትክክል ነህ» አለ የጥድፊያ ጉዳይ ስላለበት ማድረግ ይገባው የነበረውን ያላከናወነው ቆንሲል። «እባክህ ተቀመጥ? ምን እናቅርብ? ማቹ፣ እባክህ ጣዕም ያለው አንድ ስኒ ቡና፣ ሰሙሴ ፖንሴ . . . »

ወጣቱ ሰው የሚፈልገውን ወዲያውኑ አገኘ። ቡናውን ቀስ እያለ ጠጣው። የሞውውቱን ርዕስ ወደ ንጉሠ ነገስቱ ሥዕል በመቀየር፣ የታደሰበትን ዘዴ፣ በግቢው ሲገባ በቆንስላው የአትክልት ሥፍራ ስላያቸው ዛፎች ተናገረ። ሞውውቱ እየሞቀ ሲሄድ ሌሎችም በዘይው ርዕስ ላይ የበኩላቸውን ሲያክሰብት በድንገት ርዕሱን ለውጦ አሁን በጀመሩት ጉዳይ ላይ አደረገው።

«ክቡራን ሆይ! እንንዲህ የነገስታትን ንጉስ እንዳከም ልትልኩኝ ትፈልጋላችሁ? በእውነት እምልላችኋለሁ ሃሣቡ ግሩም ነው። እንዲያውም እጅግ በጣም ግሩም ነው። ስለጉዳዩ በጥልቀት ሣስብ፣ ወደዚያች አገር ሲገባ ወዲያውኑ የማይገደል ሰው ቢኖር፣ ሐኪም ብቻ ሊሆን እንደሚችል በግልፅ ማየት ትችላላችሁ። ነገር ግን አሁን በዙፋኑ ላይ ያለው ንጉሠ ነገስት የኔን አገልግሎት መሻቱን እንድታስቡ ያደረጋችሁ ምክንያት ምንድነው?»

«ንጉሡ ራሱ የህክምና ባለሞያ ፈልጐ ለዚሁ ሲል ሰው ልኳል። በዚህ ሰዓት፣ ሃላፊነት የተሰጠው አንድ መልዕክተኛ፣ ሐኪም ይዞለት ለመሄድ እዚሁ ካይሮ ውስጥ ይገኛል። ይህን መረጃ በጣም ከሚታመን ምንጭ ያገኘነው ነው። ስለዚህ አንተ አብረኸው ትጓዛለህ»

«ንጉሡ እኔ ሳልደርስ በፊት ካልሞተ መልካም ነው።»

«በማንኛውም መልኩ ግን ሙከራ መደረግ አለበት» ሲል ቆንሲሉ አከለ።

«ከሥራችን ዘርፎች አንዱ የሕክምና ጥያቄ ጉደይ ነው» በማለት በጣም በተለመደ ቅላፄ ጣልቃ ገብተው አባ ቬርሣው ተናገሩ። «ሆኖም ግን አንተም እንድታመጣልን የምንፈልገው መልዕክት አለ»

«ምን እንደሆነ በትክክል ቢነገሩኝ?» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቀ

«ደህና» አሉ አባ ቬርሣው፣ ሞውውቱ ወደተፈለገው ጉዳይ በመለወጡ ተደስተው። «ከዚህ በኋላ የግርማዊ ንጉሠ ነገስት ሉዊስ 14ኛ መልዕክተኛ መሆንህንም በትህትና ታስታውቃለህ። የፈረንሣይ ንጉሠ ነገስት፣ በአበሻ የክርስቲያን ግዛተ ዘውድ ላይ ታላቅ ስሜት እንዳላቸውም ታስረዳለህ። የፈረንሣይን ንጉሠ ነገስት በኃያልነት፣ በታላቅነት፣ በቅድስና ደረጃ የሚመጣጠናቸው እንደሌለ በተቻለህ መጠን ታስረዳለህ። የአበሻው ንጉሥ፣ እስከመጨረሻው ድረስ፣ የምዕራቡ ዓለም ንጉሥ ምን እንዳለው እንዲረዳ በማድረግ፣ የፈረንሣይን ንጉሥ ለመጉብኘት እንዲፈቀድለት እንዲጠይቅ ማድረግ ይገባል። ከዚህም በላይ የኢትዮጵያው ንጉሥ ወደዚህ ደማቅ ብርሃን ፊቱን የመመለስ ፍላጐት የራሱ ነው።»

«ባማረ ሁኔታ የተገለፀ ነው። እንበልና እኔ መልዕክቱን በሚገባ ላስተላልፍ። ነገር ግን ከዚህ ሁሉ ጥረት እናንተ ምን ተጨባጭ ውጤት ይታያችኋል?» አለ ፖንሴ

«የምንሻው፣ የአበሻው ንጉሥ በአፀፋው ወደ ቬርሣይለስ መልዕክተኛ እንዲልክ ነው። የሚላከው የኤምባሲ ጓድ በጣም ብልህና አስተዋይ መሆን ይኖርበታል። የሚመራውም የንጉሡን ሙሉ እምነት ባገኘና በከፍተኛ መሪነትና መሣፍንት አደብ ውስጥ ሊነተት በሚችል ሰው መሆን ይኖርበታል። በመጨረሻም አንድ በጣም ወሳኝና እጅግ ከፍተኛ ጉዳይ አለ። ኤምባሲው፣ ፖሪስ በሚገኘው በታላቁ የሉዊስ የቅደመ ዝግጅት ትምህርት ቤት ገብተው ለማሩ የሚችሉ ብዙ ወጣት ኢትዮጵያውያንን ያካተተ መሆን ይኖርበታል። እነዚህ ወጣቶች በቋንቋችን፣ በባህላችንና በሣይንሣችን በዓለም ሁሉ ላይ የተቀዳጀናቸውን ክብር ይመለከሩልናል» ሲሉ አባ ቬርሣው ቀጠሉ

«ስለተፈፃሚነቱስ የምትሰጡኝ ደብዳቤ አለ?» ሲል ፖንሴ ጠየቀ።

«አስፈላጊ የሆኑ ማህተሞችና ጥብጣቦች የተለጠፉበት አፈሴል ደብዳቤ» ሲል ቆንሲሉ ጣልቃ ገብቶ ተናገረ።

«ሆኖም እንዳይከብህ ደብቀህ ልትይዘው ግድ ነው። መልዕክቱ የሚሰጠው ለንጉሡ ለራሱ ብቻ ነው» ሲሉ አባ ቬርሳው ቀጠሉ።

«ገብቶኛል። ሊያጋጥም የሚችለውን ችግር ከኔ አንባር ሆናችሁ ልትመለከቱት ብትችሉ፣ እንደሚመስለኝ ዲፕሎማሲያዊው ተልዕኮ ተጨማሪ ሥራ ነው ማለት እንችላለን» አለ ጆን ባፕቲስት

ያልገባው ይመስል ተደንቆ «ተጨማሪ?» በማለት ቆንሲሉ ተናገረ።

«አዎን ተጨማሪ ነው። ሁላችሁም እንደምታውቁት እኔ መጀመሪያ ነገር በሙያዬ ዲፕሎማት አይደለሁም። ወደዚያ የምሄድ ከሆነ የምገነዘው ንጉሠ ነገስቱን ከሕመሙ ለማዳን ነው። መነጋገር ያለብንም ይህንኑ ነው»

«ምንድነው የምንነጋገረው። በቀላሉ አዎን ወይም አይሆንም ብለህ ትነግረናለህ። ጉዳዩም በዚህ ላይ ይቋጫል» ሲል ቆንሲሉ ጠየቀ።

«ይቅርታ ክቡር ሆይ። አውንም ሊታሰብባቸው የሚገቡ ዝርዝር ጉዳዮች አሉ። የመጀመሪያው በክፍያ መልክ ምን ማግኘት እንደምችል ማወቅ አፈልጋለሁ።» አለ ጆን ባፕቲስት።

«ክፍያ አሉ?!» ሲሉ አባ ቬርሳው በመደነቅ ደገሙ። «የንጉሰ ነገስቱን ፍላጐት እንድታደርስ ነው የተጠየቅከው። ክብሩ . . . »

«እያንዳንዱ ሰው የሌለውን ይሻል።» ሲል ፖንሴ በትንሹ እንደማሣል አድርጐ አቋረጣቸው። «እኔ የሌለኝ ደግሞ ገንዘብ ነው።»

ቆንሲሉ በድንጋጤ አተያይ አባ ቬርሳውን ተመለከታቸው።

«ባለፀጋ የማይከፍል ከሆነ ድሃውን እንዴት በነፃ ላክመው እችላለሁ?» አለ ጆን ባፕቲስት በክበበው ትልቅ ዝምታ ያልተረበሸ በመምሰል።

«ጌታዬ» አሉ አባ ቬርሳው በመጨረሻ። «ንጉሠ ነገስቱ ሃኪም ይፈልጋል። ስለዚህ የህክምናውን ወጭ እርሱ ራሱ ይከፍልሃል። የኛ ድርሻ የንጉህን ወጭ ብቻ የሚመለከት ይሆናል»

«አስተሳሰብህን አቀበላለሁ» አለ ፖንሴ የቀረፋ ብስኩቱን እየነከሰ።

«ስለክፍያው ለንጉሰ ነገስቱ አመለክታለሁ። ሆኖም ግን አሰቲ ወጭውን እንመርምረው»

ከዚህ በኋላ ሁሉንም ሰው ያሣተፈ ውይይት ቀጠለ። በዚህ መካከል፣ ቆንሲሉ በፅሁፍ ሊሠፍር ይገባዋል ያለውን ቃል ኪዳን ዶክተሩ አንጥሮ አወጣው። በዚህ መሠረት የዕቃ ማንሢጣ ወጭውን፣ ባለመኖሩ ምክንያት ከሥራውና ከደንበኞች ሊያገኝ ሲገባው የሚያጣውን ሂሣብ ለመተካት የሚሉት በፅሁፍ ይጠቀሣሉ። ያመጣቸው የህክምና መገልገያ ቁሣቁሶች ዋጋ፣ መሣሪያዎቹ ከአገልግሎት ውጭ እንዲሆኑ ሲደረጉ አስቀድሞ ይከፈልባቸዋል። በዚህም ላይ መቀት የሚሰጡ ልብሶችና መሣሪያም እንዲታከልለት አጥብቆ ጠይቆ ነበር። በተጨማሪም ለንዛው የሚሆኑ የኮርቻ የጋማ ከብቶች ሂሣብ፣ እያንዳንዱ መስፍን ግዛቱን የሚያቋርጡ ሁሉ ሊከፍሉት የሚገባውን የቀረጥ ሂሣብ በሚታሰበው ወጭ ላይ መደመር ነበረበት።

ቆንሲሉ በወጭው መናር ቢደነግጥም በተጠቀሱት ነገሮች ሁሉ ተስማማ። በዚሁ መሠረት በዚያኑ ዕለት ለዘመዱ ለሙሴ ፖንቻርትሬይን ወጭው እንዲፀድቅ የሚጠይቅ ደብዳቤ ለመፃፍ ወሰኑ።

«እሺ እንግዲህ፣ ጥያቄውን ተቀብያለሁ። እናንተ በፈለጋችሁበት ጊዜ ወደ አበሻ አገር እንነሣለሁ» አለ ጆን ባፕቲስት በመጨረሻ

በክፍሉ ውስጥ በጉልህ የሚታይ እፎይታ ሰፈነ።

ስምምነቱ እንድም ነገር ሳይሰተዋል እንዳይተላለፍ መከናወን ስላለበት «እንዲያው አንዣት ነገር ማከል አፈልጋለሁ» አሉ አባ ቬርሳው።

እጃቸውን ወደ ሥራ ባልደረባቸው በመዘርጋት «አይበውህ የሚሄዱት አባ ብሬቬዳንት እኒሁና»

«የጀስዊት አማኝ ወደ አበሻ አገር ሊሄድ? የአበሻው ንጉሠ ነገስት ላለፉት ሃምሣ ዓመቶች እንደጠላት ሲያወግዛቸው ነበር። አባቴ፣ ይህን አይነት አደጋ ያለበት ሁኔታ ማንም ሰው እንዲቀበለው በበኩሌ አልጠይቅም» አለ ፖንሴ።

«አንተ እንዲቀበሉ እየጠየቅሃቸው አይደለም። እኛ የታዘዝነው በንጉሠ ነገስታችን ነው። አሁን ቡትክል እንደጠቀስከው ጉዳዩ የተፈፀመው ከሃምሣ ዓመት በፊት ነው። መቼም ነገሮች ይለዋወጣሉ። አባ ብሬቬዳንትንም ጀስዊት አስመስለህ አትወስዳቸውም። በዚህ ረገድ ጥያቄ እንደማይኖር ርግጠኛ ልትሆን ትችላለህ። እዚህ አሣቸውን የሚያውቃቸው አንድም ሰው የለም። በአጭሩ ተራ አገር ጉብኚና ሂሪ ናቸው። እዚያ ስትደርሱ ደግሞ እንበልና አገልጋይህ ይሆናሉ»

ፖንሴ፣ ለአፍታ ያህል የመከላከያ ምሽግ እንዳገኘ ተዋጊ ሰው በመደሰት ከአባ ዴ ብሬቬደንት ጋር ዓይን ለዓይን ተያየ።

«እርሳቸው ከፈቀዱና ከተስማሙ እሺ፣ አገልጋይ ናቸው» አለ ፖንሴ

ከዚህ በኋላ ወደ ጀስዊቱ ቄስ ዞር ብሎ «ከእንግዲህ በኋላ ዮሴፍ ብለን እንጠራዎታለን። ይህን ስም ይስማማዎታል አባቴ?»

አባ ብሬቬደንት ወደ መሬት አቀረቀሩ።

«ይህን የጉዞ ዘመቻ አስከመረጥን ድረስ እኔ አንዳችም ነገር ያለርሱ ላከናውን የማልችለው ሽሪክ አለኝ። ይህ ሰው አብሮን ሊጓዝ የሚችልበት ሁኔታ ካለ . . . » አለ ጀን ባፕቲስት

«ሁንኖቹን?» ሲል ቆንሲሉ በድንገት በከፍተኛ ድምፅ ተናገረ። /ሁንኖቶች የፊረንሣይ የካልቪኒስት ፕሮቴስታንት አባላት ሲሆኑ በ16ኛውና በ17ኛው ክፍለ ዘመን በተከታታይ ከብዙኃኑ ካቶሊኮች ጋር የርስ በርስ ጦርነት ያካሄዱ አማኞች ናቸው/

ይህን እንደተነገረ አባ ቬርግው ከመቀመጫቸው ላይ ብድግ አሉ።

«ጌታዬ፣ ጥያቄህን ሁሉ እንደተቀበልን አምናለሁ። በሌለህ መብት ላይ ብዙ አታስቸግረን። ንጉሠ ነገስታችንና ቤተክርስቲያናችንን በእጅጉ በሚመለከት ጉዳይ ላይ አንድ የፖለቲካ ስደተኛን መጨመር ከቶም ሊታሰብ የሚችል አይደለም። ይህን በቀላሉ መረዳት ትችላለህ። ስለዚህ ጉዳይ ከእንግዲህ በኋላ አናነሣም»

ስለ ጉዞው ሜትር ዣረሚን ያላማከረው ፖንሴ፣ ርዕሰ ጉዳዩን አጥብቆ መያዝ ዋጋ እንደሌለው ስለተረዳ እዚሁ ላይ እንዲቆይ ወሰነ።

ሁለቱም ወገኖች ስምምነታቸውን በክብር አፀደቁት። ቆንሲሉ፣ ፖንሴን እስከ አዳራሹ ፊት ድረስ ሸኘው። ሲመለስ በክፍሉ ውስጥ በነበሩ ሰዎች ፊት ላይ የሚታይ ርካታ ነበር። የምስጋና መዝሙር ሲደረግ ቆንሲሉም ተካፈለ። ማቼ፣ በተለመደው ዘዴው ጉዳዩን በሰላም ለመጨረስ እንዲቻል አሳሰበ።

«እንግዲህ ሃጂ አሊ፣ ከካፑቺኖች ጋር የገባውን ስምምነት እንዲሰርዝ ማግባባት ብቻ ነው ያለብን» አለ በቁጣና በማስፈራራት ዓይነት።

ጀን ባፕቲስት፣ በቆንስላው ዕሕፊት ቤት በረንዳ ደረጃዎች ላይ ቆሞ በረኻሙ አየር ግበ። በአቅራቢያው ከሚገኘው ከአዝባኪያ መናፈሻ ለአፍንጫው የደረሰው የጥድ ባፍ፡ ሽታ፣ በሞቃቱ አየር ውስጥ እየተግለበለበ አወደው። ነገር ግን ከበረሃ ገኑቶች ጠረን ባሻገር፣ ከበረሃው መነሀ ማዶ የሚገኘውን አገር፣ እንዲያስሰው፣ እንዲያጠናውና እንዲመረምረው የተሳከበትን ሥዩር ለይቶ ያወቀው መሰለው። አየራት ከሚመነገበት ከደጋማዎቹ ምድር ማህፀን ፈልቆ፣ የታሳቱን ጅረት የፍስት አቅጣጫ ተከትሎ፣ ከተራሮች ቁልቁል ወርደው የደረሱትን የእጣንና የቅመሣጣ ሽታ መነሻ ያገኘ መሰለው። የአበሻን ምድር . . . ያልመው ነበር። ቬነስ በነበረበት ጊዜ ጓደኛው ባርባሪ፣ ስለ ጀአ ቤርሙዲዝ ታላቅ የጀብድ ጉዞ ነገሮት ነበር። ባርባሪ፣ የዘርስቶፈር ዳጋማ አማሽ ሠራዊት አባል ነበር። ክርስቶፈር ዳጋማ፣ የቫስኮ ዳጋማ ልጅ ነው። ዘርስቶፈር ዳጋማ ማለት፣ ከአንድ ክፍለ ዘመን በፊት የሙስሊሞች ወረራ ኢትዮጵያን

ባሊጋበት ጊዜ ለድጋፍ የተላከ ሰው ነበር። ጆን ባፕቲስት ወደዚህ አገር ቆርጦና ተዳፍሮ ለመጓዝ አይቃጣም ነበር። ወደ አዲስ ምድር፣ ወደ አበሻ ምድር የመጓዙ ነገርም ሀልም ብቻ ሆኖ ይቀርበት ነበር። አሁን ግን ሁልጊዜም በርግጠኝነት የሚያምነበት፣ የራሱ መልካም ዕድል ወደዚህች አገር የሚሄድበትን ሁኔታ አስገኝለት። ዕድሜውን ሙሉ አዲስ ዓለም ለማየት ይጓጓ ነበር። እንደ አፈታሪክ ስትነገር ከነበረች፣ ዝነኛና ሊደረስባት ከቶም አስቸጋሪ ከሆነች አገር የበለጠስ፣ ምን ዓለም አዲስ ሊሆን ይችላል? የአበሻ አገር፣ ጭር ያለችና የማትታወቅ ብትሆንም በወርቅና በታሪክ ክምችት ሀብታምና የበለፀገች ስለሆነች የሚመጿት አገር ነች።

ፊረንሣይ ውስጥ በነበረው የፍሮንድ አማፅያን ዘመን፣ በመከራና በችግር ጊዜ ቢወለድም፣ አንዳችም ሀብትና መጠጊያ እንኳ ባይኖሩትም፣ ሃዘንና ተስፋ ቢስነት የሚት ዕድሉ ቢሆኑም፣ እንደዚህ ላሉ ስሜቶች ላለመሸነፍና እጁን ላለመስጠት ከረዥም ጊዜ በፊት ወስኖ ነበር። ጆን ባፕቲስት ፖንሴ፣ ያሣለፋቸውን የተድላና የደስታ ወቅቶች ወይም ደግሞ በአስገዳጅ ውጫዊ ሃይል ሥር ያልወደቀበትን ጊዜ ማሰብ አስቸጋሪ ይሆናል። አሁን የሚኖርባትን ከተማ በሚገባ አበጥሮ ካወቃትና እየሰለቸችው መምጣቷንም መገንዘብ ከጀመረበት ቅፅበት ጀምሮ፣ ዕድሉ - ያ መልካም ገዳ ጣልቃ ገብቶ፣ በአረቦች ወግ ውስጥ እንደሚጠቀሰው ዓይነት፣ ሕልሙ እውን ሊሆን ወደሚመኘው አገር ወሰደው።

የነገሮች እንዲህ አዲስ የታሪክ አቅጣጫ መያዝ እየገረመውና እያስደነቀው፣ ጆን ባፕቲስት የቆንሲላውን ደረጃዎች ብዝግታ ተራምዶ ወረዳቸው። በቆንስላው ግቢ ውስጥ በምትገኘው አነስተኛ የአትክልት ሥፍራ ፊት አዘውትሮ ቢመላለስም እንዲህ ወደ ውስጥ ገብቼ አያለሁ የሚል ቅድመ ሃሣብ ጨርሶ አልነበረውም። አሁን ግን ቆም ብሎ በሚገባ ተመለከታት። በስተቀኝ ባለችው ጠባብ የጠጠር መንገድ በኩል ጉድጓዳ ግሀን የመሰለ አረንጓዴ መስክ ሲናር መሃሉ ላይ ከድንጋይ ውስጥ እየፈለቀ የሚንቦርቀቀው ምንጭ አለ። ወደ ምንፖ ሄደ ። ከምንፖ በስተኋላ ከዚህ በፊት አይቶ የማያውቀው አንድ ትንሽ ዛፍ ተመለከተ። በራሱ የሕልም ዓለም ሃሣብ ቢጨነቅም፣ ጆን ባፕቲስት ዓለምን በአዝርዕትና ዕፅዋት ተመራማሪ ዓይን አያት። በዛፉ ቁጥቋጦ አጠገብ ተንበርክኮ፣ ክብ ቅጠሎቿን መረመራቸው። ቀጥሎም፣ አንድም ምን የሚባል ዕፅ እንደሆነ በመፅሐፎቹ ውስጥ ለይቶ ሊያውቀውና ሁለተኛም የዕለቱ ማስታወሻ እንዲሆነው በማለት የእንጨት እጀታ ያለውን ቢላዋ

ከኪሱ አውጥቶ ትንሽ ቅርንጫፍ ቆርጦ ለመውሰድ አሰበ። በመጀመሪያ፣ በዙሪያው የሚመስከተው ማንም ሰው እንደሌለ ለማረጋገጥ ዐይኖቹ አማተሩ። ወዲያውኑ እነዚያ ድንጉጥ አይኖቹ በሁለተኛው ፎቅ ላይ ቆማ አግሮጀን በደፋ ላይ ካሳረፈችው ከማዳሞዜል ዲ ማይሉ አይኖች ጋር ተጋጥ። እንደርሱው ሙሉ በሙሉ ተገርማ ስለነበር ዓይኖቹን ይነቅላል ብላ አልገመተችም።

ጆን ባፕቲስት፣ አሁን ባለበት ጥሩ መንፈስ ውስጥ ሆኖ ይህን የሁለተኛ ጊዜ ግንኙነት ሰብዘ ቀናት እንደአስደማች ምልክት ሲተረጉመው ቆየ። በዚህም የራሱ ትርጓሜም ፈገግ ይላል። እርሷ አሁንም እነዚያን ሰማያዊ ጥብጣቦች ሸብ አድርጋቸዋለች። ይህን የተለመደ ጉልቶ የሚታይ ነገር ክሩቅ ስላየ ጆን ባፕቲስት የወጣቷን ሰልክክ ያለ ሰማላጋ ቁመና ሆን ብሎ በበለጠ ነፃነት ለማየት አሰበ። አፍንጫዋ አጭር ቢሆንም ቀጥ ያለ ነው። ኩል ከመሰሉት የገረጠ ዓይኖችዋ ለርሱ ፈገግታ ምላሽ በምትሰጥበት ጊዜ የሰበት ሃይላቸው ሁሉ ተሟጦ ይጠፋል። ነገር ግን አፍታም ሳትቆይ እነዚያን በሰልፍ የተሰደሩትን ነጫጭ ጥርሶችዋን ገልጣ አሣያታው፣ የርሱን እይታም አቀጣጥላ ምልስ አለች። ጆን ባፕቲስት፣ በመስኩ ላይ ተንበርክኮ ለጥቂት ጊዜ ከቆየ በኋላ ተመልሣ ብቅ እስክትል ድረስ ለመጠበቅ ሲል ብድግ አለ። መስኩ እንደተከፈተ ቀርቷል። በዝግታ ወደ ጠባቧ መንገድ አምርቶ ጉዳናው ውስጥ ገባ። ከዚያም ጊዜውን ለማገባደድ ወደ ቤቱ ተንዘ።

ይህ የቀረበለት ያልተለመደና እንግዳ የሆነ የጉዞ ሃሣብ ዳግመኛ ተመልሶ ሀሊናውን ያዘው። የማዳሞዜል ዲ ማይሌ በድንገት ብቅ ማለት፣ ትናንትና በሃዘንና በትካዜ ውስጥ ጥሎት የነበረው፣ ዛሬ ደስታውን ጨመረለት። ሁሉም ነገር እንደገና ሊሆን የሚችል ሆነ። ከዚህ በፊት በቬኔስ፣ በፖርማና በሊዝቦን እንደነበረባቸው ጊዜያት ሁሉ እንደገና እግር ተወርች ያልታሠረ ነፃ ተንቫ መሆኑ ተሰማው። ይህን ማሰቡ በራሱ ደስታን እንዲያስከው አደረገው። የሚፈልገው፣ የሚሻውና የሚጠይቀውም ይህንኑ ነበር።

8

የአሥራ አራት ዓመት ኮረዳ እስክትሆን ድረስ፡ አሊስ ዴ ማይሌ መልክ ጥፉ ሕፃን ነበረች። ወላጆችዋ ውጭ አገር ለመኖር ከሄዱ በኋላ፣ ያደጎችው ቺኖን አጠገብ በሚገኝ የአመምኔቶች ገዳም ውስጥ ነበር። በውፍረቷና በርበሬ በሚመስሉት ጉንጩችዋ ምክያት የሚያስቁ የቅፅል ስሞች ነበሩዋት። እርስዋ ከምታስታውሣቸው መነክስ ሁለቱ «በርበሬ ጉንጭ» እና «ዱባ ፊት» የሚሉት ይገኙባቸዋል። ምንም እንኳ በተፈጥሮዋ መልክ ጥፉ ብትሆንም፣ አንዳንዶች የሚጠሯት ለራሣቸው ለመደሰትና እርስዋን ለማብሸቅ በሚል ነው። የሚፈራት ወይም የሚቀናባት አልነበረም። በርስዋ መልከጥፉነት ማቢያ ሌሎች ገሸሽ ሲያደርጓቸው፣ እርሷ ደግሞ ፍቅራቸውን ትቸር ነበር። የሰውነትዋ መጠን የተለየ መሻሻል ባይታይበትም አካሏ የራሱን የዕድገት ለውጥ ማሣየቱን ቀጠለ። በስድስት ዓመቷ መልክ ጥፉ ሆና የገባችበትን የእመምኔቶች ገዳም፣ በአሥራ አራት ዓመትዋ ግብፅ የሚገኙትን ወላጆችዋን ለመቀላቀል ስትሰቅቀው መልክ ጥፉ እንደሆነች ቆይታለች።

ከዚህ በኋላ ግን አንዳች የትኩሣት ህመም በሰው ፊት ላይ እንደሚፈጥረው ድንገተኛ ሽፍታ፣ ሲገለፅ የማይችለው ድንቅ ውበትዋ መፍነስ ጀመረ። ቁመቷ ረዥምና ሽንቃጣ ሆነ። መልክ ጥፉ ያደረጋት የውፍረት ክምችት ሁሉ ቀልጦ ሽቅብ እንድትመዘዝ አደረጋት። በርበሬ ይመስሉ የነበሩ ጉንጩችዋ ገርጣ ማለት ጀመሩ። የፊትዋ ፀዳል ያልተለመደ አዲስነት፣ የሚያበራና በእጅ ቢነኩት የሚቆሸሽ መስለ። ወደ ኋላ ተስቦ ሲታሰር ወይም ከሀዛንትዋ ጀምሮ በሹርባ ሲጎነጉን የነበረው ወፍራም ፈዛዛ ቢጫ ፀጉርዋ፣ መልኩን ወደ ጥቁር ሃርነት በመቀየር ላይ ሲሆን ፊትዋ ለቅቃዋለች። እንዳለመታደል ሆኖ፣ ይህ ውበት በርስዋ ላይ መፍሰስ የጀመረው ማንም ከውጭው ዓለም ይህን ትመስያለሽ የሚል ማረጋገጫ ሊሰጣት በማይችልበት የብቸኝነት ጊዜዋ ነበር። የወላጆችዋ ዕይታ ለርስዋ የሚገልፅላት አንዳችም ሚዛን የለውም። የመልኪንና የአካሏን ሁኔታ ልትገልፅላት የምትችል የሌት ጓደኛም አልነበረቻትም። ዘወትር የምትጠቀመው መስተዋትም፣ ብቻውን የሚነግራት አንዳችም የለውም። አካላዊ ለውጡ በመሻሻል ላይ መሆኑ ቢሰማትም፣ ራሷን በተመለከተች ቁጥር ሊያጋጥም የሚችል አደጋም ይታሰባታና ይታያት ጀመር። በብቸኝነት የቆየችበት አስፈሪ ጊዜም

ስሜቷን እንዳያዛባባት ስጋት አደረባት። ካይሮ በሚገኘው ውብ የወላጆችዋ መኖሪያ ውስጥ አንድም ሰው አይታ አታውቀም። ወይም በሌላ አገላለፅ እንደም ሰው አይቷት አያውቅም።

ወደ ካይሮ እንደመጣች፣ ከጥቂት የቀድሞ የትምህርት ቤት ጓደኞችዋ ጋር የልጃገረድነት ደብዳቤ ልውውጦችን ታደረግ ነበር። ይሁን እንጂ ምንም ዓይነት የመልስ ደብዳቤ ሳይደርሣት ሲቀር ወይም ቢመጣላትም እንኳ ከረዥም ጊዜ በኋላ ሲሆንባት ከሌሎች ሰዎች ደብዳቤ መጠበቋን ተወችው። እርስዋም መፃፏን አቋረጠች። በካይሮ ቆይታዋ ጥቂት የፒያኖ ትምህርቶችን ቀስማለች። ነገር ግን የዚህ መኖሪያ መምህርቷ፣ ከዕለታት አንድ ቀን ወደ ቆንሰላው ግቢ ስታመራ ድንገት በመንገድ ላይ በመውደቋ ለአሥር ቀናት ያህል ራሷን ስታ ቆይታ ሞተች። አባ ጋዕሪ ደግሞ የላቲን ቋንቋ ሊያስተምሯት ሞክረው ነበር። እንደ እውነቱ ከርሣቸው ይልቅ እርስዋ ቋንቋውን በተሻለ ታውቀዋለች። በአመምኔቶች ገዳም ትምህርት ቤት ቆይታዋ፣ በላቲን ቋንቋና ባትወደውም እንኳ በሂሣብ ትምህርት ጉበዝ ተማሪ ነበረች። የላቲን ትምህርቱን እንዲቀረጥ አባቷን አጥብቃ ለመነችው። ከዚህ በኋላ የቀራት ነገር ማንበብ ብቻ ነበር። የቆንሰላው ቤተመፃሕፍት በበቂ መጠን የተሟላ ነው። የተፈጥሮ ሣይንሶችና የጥንታዊ ትራጀዲ መፃሕፍት ያስደስቷታል። የሚያነቃቁ መፃህፍት በጣም ያበረታቷታል። ከነዚህ መነክስ የላፎንቴይን እና የፈኔሎን ቴሌማክ መፃህፍት ተጠቃሾች ናቸው። አባቷ እንዳታነብባቸው የሚያወግዛቸውን፣ እርሱ ራሱም ያላነበባቸውንና ሌላም ሰው እንዳያነብባቸው፣ ግን ሣይሸሽጋቸው ያሉትን የተለያየ አቀራረብ ያላቸውን ረዣዥም ልብወለዶችን በራስዋ ጥረት ማግኘት ቻለች። ጀግናይቱ ሴት በፍቅር የተጨቆነችበት ላፓሪንሲስ ዴ ክልቬስ የተሰኘው መጽሃፍ፣ አዲስ ዓለምን አሣያት። ይህን መፅሀፍ ዳግመኛ ከእጇ ሳትጥለው አቆየችው። ሕልም ለማለም ማንም ቢሆን ቆንጆ መሆን አይጠበቅበትም የሚለውን ከሀዛንትዋ ጀምሮ ያረጋጠችው እውነታ ነው። በዚህ ዓለም ህይወት ውስጥ፣ ደስታን የማስገኙት ዕድል ይሰጥ እንደሆነ በሚል ሰተወሰነ ጊዜ የአካልዋ ጉዳይ በሃሣብ ውስጥ ከትታቷት ነበር። በመጨረሻ ግን እርግጠኛነት ወደሌለውና ወደራስ አለመተማመን መራት። በዚህ ግቢያ የራስዋን ስሜት በሚቀሰቅስና ደስታን በሚሰጣት ዓለም ውስጥ ተመልሣ ገባች። በዚህም፣ ቢያንስ ከሁሉም ይልቅ አመዛዛኝ ስለሆነች በሁሉም ዙሪያ አድናቆትን አገኘች።

ከጀስዊት ቀሣውስት ጋር ምሣ ከበላች በኋላ፣ ይህች ወጣት በመኝታ ቤትዋ መስኮት አጠገብ ተቀምጣ በቆንሰላው የአትክልት ሥፍራ ውስጥ የሚገኙትን የዛፎች ቅጠሎች

ታስተውል ጀመር። ከጥቂት ጊዜ በፊት ሲነገር ስለነበረው ስለአበሻ አገር ማሰብና ማሰላሰል ጀመረች። በዙሪያዋ ያለው ዓለምና የአበሻ አገር እጅግ በጣም ቅርቧ ናቸው። ሆኖም ግን በቀላሉ አይደረስባቸውም። ሌሎች ልጆገረዶች ይህን ጊዜ ስለነዚህ አገሮች ያልሙ ይሆናል። በአንፃሩ በዚህ ቦታ እርስዋ ልትወለድበትም ትችል ነበር። ቀሰሜ ጥቁር ቢሆን ኖሮ ብላ መቃዠትም ጀመረች። እንደ ወተት አረፋ በሚነጣው ክንዷ ላይ የሚገኘውን አምባሯን ተመለከተችውና ይሽው ብጫና አብረቅራቂ አምባር፣ በጥቁር መደብ ላይ ቢሆን ኖሮ ምን ሊመስል እንደሚችል ብላ አሰባ ተደነቀች። ክንዶችዋን በመስኮቱ ላይ እንዳሣረፈች በዙሪያዋ የሚገኙትን ቁሣቁሶች ሁሉ ዘንግታ ጨናማ በሆነው የራስዋ ተመስጦ ውስጥ ሰመጠች። የጊዜው መንኮድ ሣይታወቃት ሦሣን ከእንዱ ርዕስ ወደሌላው እያቀያየረች ጭልጥ አለች።

ክርስዋ በታች በሚገኘው ፎቅ የፊት ለፊት ደረጃ ላይ በድንገት ድምፅ ሰማች። ድምፁ በበሩ አጠገብ ሰው የተመለከተው የአባቷ ድምፅ ነበር። ሰውዬው ከፎቁ ሲወርድ በአይኖችዋ ተከታተለችው። ከኋላ ስትመለከተው ቀጭን፣ ባርኔጣ ያላደረገ፣ የራስ ቅሉ በሚዘናፈል ፀጉር የተሸፈነ፣ የቆዳ ቦት ጫማ ያጠለቀ ሰው ነው። በጠባቡ መንገድ ላይ ሊሄድ ቆም አለ። እርስዋም መከታተልዋን ቀጠለች። እርሱ ግን ከመንገዱ ፈንጠር ብሎ በመውጣት በመስኮ ላይ ተራመደ። እርስዋ ራሷ አስተውላው በነበረውና ከሌሎች ተራ አፅዋት ጋር ከማይመሣሰለው ትንሽ ዛፍ አጠገብ ሲደርስ ተንበረከከ።

የጐብኚውን ሰው ቅርፅ መለየት ቻለች። ሰውዬው፣ ከትናንት በስትያ በክሣሊጅ ድልድይ ላይ ያየችውና እስዋን በተለየ ሁኔታ ሊመለከታት የነበረው ነው። ተክለ ሰውነቱ ቁፍጥን ብሎ፣ማራኪ ቁመና ያለውን ነው። እንዴት ተዝናንቶ በርክክ እንዳለና እንዴትስ አድርጐ ቢላዋውን ከኪሱ ውስጥ እንዳወጣው፣ ቅርንጫፉንም እንዴት በቀላሉ እንደጨበጠው አስተዋለች። በቀንሰላው ውስጥ ያጋጠሟት ጥቂት ሰዎች ሁሉት ፍፁም ተባራሪ የሚመስሉ ዓይነቶች ናቸው። አንዳንዶቹ የአጋጣሚ ዓይነት ምሁራን፣ ትሁቶች፣ ስራሣቸው ሙሉ ክብር የሚሰጡ፣ ግትሮች፣ በጣም የሚከበሩ፣ በተለይም በሚተገበር ጉዳይ ላይ ተፈጥሯዊ እንቅቃሴን ማከናወን የማይችሉ አስመሣዮች ናቸው። ሌላኛዎቹ ዓይነቶች ሕዝባውያን፣ ሁሉንም ተግባር የሚያከናውኑ ነገር ግን ከምንም የማይቆጠሩ ናቸው። ምግብ አዘጋጆች ይሁኑ፣ ጋሪ ነጂዎች ይሁኑ፣ ዘበኞች ይሁኑ እንደ ጠበብት ክችች ያሉ ናቸው። በዚህ ሣቢያ፣ ማንም ቢሆን ፀጥ፣ረጭ ብለው ተደብቀው ቢቆዩለት ይመርጣል። ከፊት ለፊትዋ የሚታየው ወጣት ግን

የሁለቱንም የህብረተሰብ ክፍሎች በጋራ አጣምሮ የያዘ ቅይጥ ይመስላል። ተክለ ሰውነቱ የጌታ ነው። ትዕግስቱ የአጃቢ ነው።

እንዲህ እየተከታተለችው እያለች ምናልባት በድንገት አታይ ይሆን? የሚል ስጋት አልተሰማትም። በርስዋ ፍልስፍና በእንቅልፍ ላይ ያለ ሰው ከቶም እንደማይጋለጥ ሁሉ፣አሊስ አሁንም በህልም ዓለም ውስጥ ነች። ሆኖም ግን ይህ ወጣት ሰው ዓይኖቹን ወደርስዋ ወረወራቸው። በማህበረሰቡ መካከል፣ በማይታወቅ ሰው እየተመረመሩ ለሚኖሩ ሁሉ በጣም ጤነኛ የሆነው ይህ ልዩ ስሜት ኩተሰማት ምን ያህል ጊዜ ይሆን ይሆን? በርግጥ ከህፃንነት ካለፈች በኋላ ምናልባት አንዳንድ ጊዜ አባቷ ራት ከሚጋብዛቸው ሽማግሌ ቀሣውስት በስተቀር እንዲህ ያለ ስሜት አንድም ጊዜ ተሰምቷት አያውቅም። ነገር ግን ራሱን ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ ሰመፈተሽ ያቀረበ፣ ተፈጥሯዊ አቋሙን የጠበቀና ግልፅ መደነቁን የሚገልፅ ሰው አይታ አታውቅም። እንዲህ ባለ ግራ መጋባት ውስጥ ሆና፣ ለርሱ ፈገግታ፣ የፈገግታ መልስ ሰጠች። ከመፍራቷ የተነሣ ከመስኮቱ ሦስት እርምጀ ወደኋላ ተራመደችና ወዲያውኑ ተወፀቸች። እጆችዋን ጀርባዋ ላይ አጣምራ፣ የመኝታ ክፍሏን የአንፀሬት በር እየዳበሰች፣ በሣይል እየተነፈሰች፣ ስሜቷ ታውኮባት ለረዥም ጊዜ ፀጥ ብላ ቆመች። በነዚያ ዐይኖች ውስጥ የነበረው የጋለ ስሜት ግን አመለጣት። ስሜታዊ መልስዋ ግን፣ አንድ ሀሣን በጣም የሚያስደስት ገጠመኝን ተመልክቶ እንደመቦረቅ ፈንታ አደጋ ይናራል ብሎ ሊያስብ እንደሚሮጥ ዓይነት ነው የሆነችው።

ለምንስ ወደኋላ ተራመድኩ? ስትል ራስዋን ጠየቀች። ያ ወጣት የሚያስፈራ አይደለም። እኔም አልፈራሁም። አልፈራሁም። ከዚህም በላይ ፍፁም ታማኝና ትሁት ይመስላል። ይህ ባይሆን ኖሮ አባቴ በፍፁም ወደዚህ አይጋብዘውም ነበር። በመስኮቱ ወደ ውጭ ማየቴ ምን ጥፋት ነው? አንድ ጐብኚ ከቆንስላው ግቢ ሲወጣ መመልከትስ ምን የሚያስነውር ነገር አለበት?

ለረዥም ጊዜ ከራሷ ጋር ተከራከረች። በመጨረሻም አንደኛው ሦሣብ አመዝኖ የክርክሩ ትግል ሲቋረጥ ተመልሣ ወደ መስኮቱ ሮጠች። እንግዳው ሰው ግን የለም።

ጠበቀችው። ሰውዬው ግን አልተመለሰም። በመጨረሻም ራቲን ወደ ክፍሉ መሰሰች። በዜቱ ውስጥ ያለው መቀት ማቃጠል ጀምሯል። ከውጭ፣ ረጋ ባለው ነፋስ የሚወዛወዙት

ሣፎች ጥቂት እርይታን ቢያስገኙም በቤቱ ውስጥ ግን አንዳችም የለም። አረንጓዴ የአልጋ ልብስ የተነጠፈበትን አልጋ፣ የስሚ የመጀመሪያ ፊደል የተጠለፈበትን ትራስዋን፣ ወፍራም አረንጓዴ ጨርቅ የለበሰውን ትንሽ ጠረጴዛ፣ ተጣጣፊውን ወንበር፣ መፃህፍቶችና፣ ጥቂት የሸክላ አሻንጉሊቶችን ተመለከተቻቸው። እነዚህ የተለመዱ ዕቃዎች ብዙ ቀን ያፅናኑዋት ቢሆኑም፣ እንዳታመልጥ አስረው ያስቀመጧት ናቸው። የሰውዬው አይታ እነዚህን ዕቃዎች እርቃናቸውን አስቀርቶ አጋለጣቸው። ከነዚህ እቃዎች አንዳችም የመፅናኛ ነገር ሳታገኝባቸው ፊትዋን በእጆችዋ ውስጥ ሸፍና ቆማ አነባች።

❧

«አረንጓዴ!» አለ ቆንሲሉ፣ ቁርጥ ባለ ድምፅ «በትክክል ስምተሸኛል። ከሁለት ቀናት አስፈሪ ስቃይ በኋላ እንደበሰበሰ ፍሬ ወደቀ»

«ክቡር ሆይ፣ እንዳስተረጉም ጥቂት ጊዜ ይስጡኝ» አለ ሙሴ ማቹ እጆቹን እያወራጨ

ሃጂ አሊ፣ በፊቱ ላይ አስፈሪና ስሜት የሚነካ ሁኔታ እየታየበት በጀርባው ተንጋልሏል።

«ሕመምተኛው ሞቶ እንደሆነ ማወቅ ይፈልጋል» ሲል ፀሐፊው አስተረጉመ

«የለም። አስከአሁኗ ሰዓት ድረስ በርግጥ አልሞተም። ለረኽም ጊዜ ያህል ግን ተሰቃይቷል። እንዲያውም ከስቃዩ እንዲገላገል በመፈለግ እንዲገድሱት ሁሉ ተማፅኗል። ይሁን እንጂ እኛ ክርስቲያኖች ነፍስ ማጥፋት በእምነታችን አይፈቀድልንም» አለ ሙሴ ማይሴ እንደ ምሁር።

ሀጂ ግንባሩን በእጅጌው ጠረገና ወደ ዳፕሎማቱ ዞሮ፣ ሙሉ በሙሉ ዓይኖቹ ውስጥ አየው።

«ለመሆኑ በትክክል የሆነውን ነው በእርግጠኝነት እየነገርከን ያለኸው?» ሲል ጠየቀው።

«እርግጠኛ ነኝ። ዜናውን ያገኘሁት እየሩሣሌም ከሚገኙት የተከበሩ የሥራ ባልደረባዬ ነው። ሰውዬው፣ ቁስጥንጢንያ ለሚገኙት አምባሣደር ሙሴ ዴ ፌሪዩል በራሣቸው እጅ ነው የፃፉላቸው። ለአምባሣደሩ ደግሞ አስቸኳይ መልዕክት በሚያደርስ ሰው በኩል ይህንኑ ገለውልኝ። እንዲያውም ፈረሰ አስከአሁን ነጭ ላብ እያላበው መሆኑን በፈረሰቹ ጋጣ ውስጥ ሊያዩት ይችላሉ»

ማቹ አስተረጉመ።

«አንድ የካቦቺን መነኩሴ ነው» ካለ በኋላ አስቸጋሪ ትምህርት ወደቤቱ ይዞ የሚገዝ ተማሪ ይመስል ዝግ ባለና በግልፅ አነጋገር «እንዲያውም ራሱን የሕክምና ዶክተር እንደሆነ በማስመሰል በቅርቡ ከእየሩሣሌም ሰቅቆ ወደ አሌክሣንደሪያና ካይሮ በሚመጣ ጀልባ ላይ የተሣፈረ ነው። ይኸው የሚባለው ሰው መሆን አለበት። አይደለም?»

«መሆን አለበት» አለ ሃጂ።

«በቁምጥና ሕመማቸው ላይ እርሱ አከሚአቸዋለሁ ያሳቸው ሦስት በሽተኞች፣ እርሱ ከሰቀቀ በኋላ ወደ ቆንስላው መጥተው ነበር። የሥራ ባልደረባዬ አንዱን በሕይወት አግኝቶታል። የቀሩት ሁለቱ ሞተዋል። የሁለቱ ሰዎች እጆቻቸው ወደ አረንጓዴነት ሲለወጡ አንደኛው ግን እጆቹን አንዳሉ አጥቷቸዋል።»

ሊያስመልሰው ሲቃጣው አፉን በክርኖቹ መካከል ወሽቆ «ይበቃል። ሁሉንም ነገር ይገባሜ እንዳትነግሩኝ» በማለት ሃጂ አሊ በከፍተኛ ድምፅ ጮሆ ተናገረ።

«ደግሜ የተናገርኩት አንተ ለመስማት ፈቃደኛ ስላልሆክ ብቻ ነው። ታሪኩን አሁንም አላመንክውም»

«ያላመንኩትማ ሌሎች ካቦቺኖች ስላሉና ምናልባት እነሱ እንዳይሆኑ በማለት . . . »

«ይህን ርዕሰ ጉዳይ በዚህ ላይ እናብቃው። እንዲያውም ላስጠንቅቅህ፣ ለንጉሡ፣ የሆነ አለመሣይ ሐኪም ይዘህለት የመጌድ ሣኅብ ካለህ ውሣኔው ያንተ ነው። ይህ ሚና እኔን መቹም አይመለከተኝም» አለ ሙሴ ዴ ማይሴ ተነስቶ እየቆመ።

«ይህን ካፑቺን ካልወሰድኩት ሌላ ምን አማራጭ አለኝ»

«በፊረንሣይ ማህበረሰብ ውስጥ መቶ በመቶ ብቃት ያለው ፈረንሣዊ ዶክተር አለ።»

«እርግጥ ነው? ለመሆኑ ማነው?» አለ ሃጂ አሊ ፊቱ በአድናቆት እያበራ

«ፓሻውን ራሱን የሚያክም አንድ መድሃኒት ቀማሚ ነው»

«አ አምን፣ አምን፣ ስለርሱ ሰውዬ ሰምቻለሁ። ግን እኮ ሁሉም ያው ነው። ፈረንሣውያን ደግሞ ከቱርኮች ያሰችግር ምስክርነት ያገኛሉ። ታድያ ይህ ትንሽ አያስቸግርም?»

«የቱርኮች ምስክርነት ስትል ምን ማለትህ ነው። የኔ ምስክርነትስ? የለም፣ የለም፣ የዚህን ሰው ብቁ መሆን በይፋ የምመሰክር እኔው ነኝ። የራሴን ባለቤት አክሞ የፈወሳት ሰው ነው»

ሃጂ አሊ የተጠራጠረ መሰለ።

«ካፑቺኖዎች ከዚህ ሰው እንድጠነቀቅ ነግረውኛል» አለ በመጨረሻ

«በምን ምክንያት? ቅር ባትሰኝብኝ እዝህ ሰዎች በስም ማጥፋት ዘመቻ ላይ ተሰማርተዋል ማለት ይሆን?»

«ሃይማኖተኛ አይደለም»

«ሃይማኖተኛ እንኳን አይደለም?!» ሲል ሙሴ ዬ ማይሌ በመደነቅ ተናገረ። «በመጀመሪያ ነገር ይህ ሐሰት ነው። ሰውዬው ቤተክርስቲያን ይሄዳል፣ ይሣለማል። ሁለተኛ ው ነገር፣ የሃይማኖት ጉዳይ ከተነሣው ጥያቄ ጋር ምን ግንኙት አለው? ሰውዬው ጥሩ ሐኪም ከሆነ ሌላው ጉዳይ ምን ይፈይዳል»

«በዚህ ጉዳይ ላይ እግዚአብሔር ካልተጨመረበት በስተቀር ምንም የሚሆን አይደለም።» አለ ግመል ነጂው ራሱን እየነቀነቀ

«እስቲ አንተ ራስህ ምን ይሰማሃል? አንተ ሞሃመዳዊ ነህ። ሐኪሙ ካቶሊካዊ ነው። ንኩሙ ደግሞ ሺሮቴስታንት ነው። በዚህ ላይ ምን ዓይነት እግዚአብሔር ነው ሊታሰብ የሚችለው?»

«እግዚአብሔርማ እግዚአብሔር ነው» አለ ሃጂ አሊ። ጣቶቹን ከንፈሮቹ ላይ አሳረፈና ሽቅብ ወደ ሰማይ እየተመለከተ።

«አንግዲያው የአሌክሣንደሪያውን የክፕቲክ ፖትሪያርክ ይዘሃቸው ሂድና እስቲ አባክህ አባቱ ተአምር ያሳዩ ብለህ ጠይቃቸው» ሲል ቆንሲሉ ጮኸ።

ሙሴ ዬ ማይሌ አሁን እየተገነዘበ ያለው፣ ሰውዬው በእግዚአብሔር የማያምነውንና እርሱ መርጦ ያቀረበውን ውሰደው ይሰኛል ወደሚል አገዛማሚያ እየገፋው መሆኑን ነው። በዚህም ሳቢያ ፀጥ አለ። ነጋዴውም ሰረቻም ጊዜ በራሱ ሃሣብ ተውጦ ቀረ።

ከአየሩሣሌም መጣ ስለተባለው መልዕክተኛ ታሪክ ሰማሙን ወይም ላለማመን ሃጂ አሊ ግራ ተጋባ። የርሱ ዓለም የበረሃ ዓለም ነው። በርሱ ዓለም ውስጥ የማይመስሉ የሚባሉ ነገሮች እምብዛም አውነት አይባሉም። ሃጂ አሊ በጣም እርግጠኛ ሆኖ ያወቀው ጉዳይ ግን፣ የቆንሲሉ ፍላጉት፣ እርሱ ከካፑቺኖ መነኮሳት ጋር ያለው ግንኙነት እንዲቋረጥ፣ በነርሱ ፈንታ ይህን ፈረንሣዊ ሃኪም እንዲወስድ ጠንካራና ጥያቄ የማይቀርብበት ፍላጉት እንዳለው ነው። ሃጂ አሊ፣ ሊያገኝ የሚችለውን ጥቅም በፍጥነት አሰላና ሰባኪዎቹ ለዚህ ሃላፊነት እንደማይናርባቸው ወይም እንደማይወቀሱ ተገነዘበ። አንደኛ፣ ሰባኪዎች የገቡለት ምንም ቃል ኪዳን የለም። እንዲያውም እንቅስቃሴያቸውን ሁሉ ለርሱ ውለታ እንደሚውሉለት ዓይነት እያስመሰሉት ነው። ከዚህም በላይ መነኮሳቱ ቅፍለቱን አደጋ ላይ የሚጥሉ ናቸው። በነርሱ ሣዚያ ቱርኮች ብቻ ሣይሆኑ በጉዞው መስመር ላይ የሚገኙ ተወላጅ ሃይሎች ሳይቀሩ ድንጋጤ ሙሶዮ ሊገቡ ይችላሉ። በእንግሩ ለፈረንሣዊው ሃኪም የሚኖረው ጥርጣሬ ግን እንኩተኛ ነው የሚሆነው። ይልቁንም ይህ ሐኪም እንዲሄድ የራሱ መንግስት የሚፈልግ ከሆነ በክፍያው ላይ ሊደራደሩ ይችላሉ።

ሃጂ አሊ በአግባቡና አስቸጋሪው ሁኔታ ምክንያት አርር ኩርምት ብሎ አለቀሰ።

«ለምን እንደሚያለቅስ አስቲ በቅን መንፈስ ጠይቀው» አለ ቆንሲሉ፣ ሙሴ ማቹን እየተቆጣው።

«አቅዱን ለውጦ ሌላ ሐኪም ሲወስድ የሚያጋጥመውን ከፍተኛ ወጭ በማሰብ እንደሆነ ነው የሚናገረው»

ምስጋና ይግባህ አምላኬ፣ በመጨረሻው ከምንፈልገው ላይ ደረስን በማለት፣ ቆንሲሉ ለራሱ ተነፈሰ።

ውይይቱ ለተጨማሪ ግማሽ ሰዓት ቀጠለ። ሙሴ ዴ ማይሌ ወደትንሽ ሣጥን ሦስት ጊዜ መመላለስ ግድ ነበረበት። ግመሎች መቀየር አለባቸው፣ መልዕክተኞች አስቀድመው መላክ ይኖርባቸዋል። የምሥጋና ፀሎትም ለእግዚአብሔር መቅረብ ይገባዋል። በከፍተኛ አትኩሮት ሲከናወን የነበረው ጉዳይ በሁለቱም መካከል በመተማመን ተቋጨ። እያንዳንዳቸው ረክተው ተለያዩ።

የድርድሩ ውጤት በመልካም ሁኔታ መቋጨቱን ሲያውቁ፣ አባ ቬርማው በማግስቱ እንደሚሄዱ አስታወቁ። የጉዟቸው አቅጣጫ ሌላ ሥራ ወደሚጠብቃቸው ወደ ደማስቆ ነው። እራት በፍጥነትና በፀጥታ ተበላ። አባ ብሬቬዳንት፣ የአለቃቸውን የመጨረሻ መመሪያ ለመቀበል ከዕኩለ ለሊት በኋላ መጡ። ሁለቱ ቀሣውስት ውይይታቸውን በሁለተኛው ፎቅ ላይ አደረጉ።

ሙሴ ዴ ማይሌ በሥራ ብዛት ስለደከመው በጊዜ ተለያቸው።

ከማህበረሰቡ ሰፈር በማይርቅ በአንድ የመጨረሻው ትንሽ መንገድ ላይ ጆን ባፕቲስትና ሜትር ዝረሚ የሚወዱትን አንድ ጠርሙስ የወይን ጠጅ በደስታ ጨለጡ። አሥር ሰዓት ሲሆን ወደ በረንዳው ወጡ። ከባድ የአሸዋ አቧራ የተሸከመው ነፋስ የምሽት ከዋክብቶችን ሸፈናቸው። በአየር ውስጥ የነበረውን የቀን ሙቀት አንቆ የያዘው የጋብቻ ወራት ገና በመጨረሻዎቹ ሣምንቶች ላይ ስለሆነ፣ ከአረቦች መንደሮች ሁሉ የአታሞዎችና የዕልልታ ድምፆች ያስተጋቡ ጀመር።

«የለም፣ የለም፣ በዚህ ጉዳይ ላይ የኔ መከፈል ጨርሶ ጥያቄ የሚነሣበት አይደለም» አለ ሜትር ዝረሚ ውይይታቸውን በመቀጠል።

«ቢሆንም ቆንሲሉ ጨርሶ ሊያውቀው አይገባም። እኔ አንዳችም ቃል አልተነፍስም። እኔና አንልጋዬ ከተማውን ለቅተን እንወጣለን። አንተ መንገዱን ወርደህ ትንሽ ራቅ ብለህ እናግኝህ»

ዝረሚ፣ የአርሳስና የቆርቆሮ ቅይጥ የሆነውን ዋጋጫ በአንድ እጁ ይዞ ሌላውን እጁን በባለሥልጣን አነጋገር ጅመልክ ከፍ አደረገው።

«አርባና የለውም! መልሱ አይሆንም ነው»

«እንዲያ ከሆነ የየራሣችንን የተለያየ መንገድ እንሄዳለን?»

ለመጀመሪያ ጊዜ ከአምስት ዓመት በፊት የተገናኙት ቬኔስ ውስጥ ነበር። ጆን ባፕቲስት፣ የሻምላ ውጊያ መምህር ይፈልግ ነበር። በፖለቲካ ምክንያት ከአገሩ ወጥቶ አንዳች ታላቅ ነገር ይሸ የነበረና በሌላ ስም የሚታወቀውን፣በቀላሉ የሚበሣጭ፣ ባልጥቁር ፀጉር ፈረንሣዊ ስደተኛ አገኘው። ተማሪዎቹ ሜትር ዝረሚ በሚባል ስም ያውቁታል።

«እና እንዲህ መሆኑ ነው» አለ ፕሮቴስታንቱ እንደመተከዝ ብሎ።

የጦር መሣሪያ ባለሙያነት ላይ ከመሠማራቱ በፊት፣ ዝረሚ ከፀሐይ በታች በሚገኙ የተለያዩ የአጅ ሥራዎች ላይ ተሰማርቶ ነበር። ከነዚህ ሁሉ ይልቅ ይበልጥ ፍቅርና ዝንባሌ የነበረው በመድሃኒት ቅመማ ዝግጅት ላይ እንደሆነ ያስታውሣል። ይህ የሆነው፣ ጆን ባፕቲስት ቁሶች በውስጣቸው ምን እንደያዙ የሚያስገነዝበውን የመክራ ሥራ ሰላሰኮማረው ነዘር። በዚህ ትምህርት ግቢያ የጦራዴ ውጊያውን ሙያ ተወው። የሁለቱም ጓደኝነት ተጠናክሮ፣ ሽርክች መሆን ችለው ወደ ምሥራቃዊ ሜዲቴራኒያን ተሰደዱ።

«ይህች ዓለም!» ሲል ዝረሚ በሰገነቱ ላይ ከሚኘው መደገፊያ በድንገት ተስፈንጥሮ ወደ ኋላው ተራመደ። በኋላም «ይህ ሁሉ የእኔ ጥፋት ነው» አለና ተንሰትሰቶ አለቀሰ።

በረንዳው ላይ ሁለት ጊዜ ሃይል የታከለባቸው እርምጃዎች ከተራመደ በኋላ ወደ ሸረሁ መለሰ አለ።

«የምንለያየው፣ እኔ ለመቅረት ስለፈግሁ ሣይሆን አንተ ለአንድ ወገን ብቻ የሚያደላ የሥራ ስምምነት በችኮላ በመቀበልህ ነው» አሰው።

«ካይሮን ትቼ ወደ አዲሱ ዓለም መሄድ እፈልጋለሁ ስትል የነበረው ትናንት አይደል እንዴ?» አለ ጆን ባፕቲስት ራሱን በመከላከል።

«አዲሱ ዓለም! እና ይህ ማለት እኮ በዚያ ቆንሲል ትዕዛዝ ማለት አይደለም። ሰው ወዳልደረሰበት ምድር እንኳ የምሄድ ብሆን፣ እመነኝ ከጀስዊቶች ጋር ስንተት አልሄድም»

«ወይ ጉድ፣ ጀስዊቶች? እነሱ እኮ ማስመሰያዎች እንጂ፣ ምንም አይደሉም። ለመሆኑ ለዚህ ተልዕኮ እኔ ጠቀሜታ ያለኝ ይመስልሃል? ለኤምባሲያቸውና ለንጉሡ አገልግሎት ደንታ የለኝም። ነገር ግን ፈረሰኛ፣ ትጥቅና መሣሪያዎች ሰጥተውኝ ሊያጃጅሉኝ ቢሞክሩ፣ እኔ የባስ ጅል ሆኜ ስጦታውን አልቀበልም ልበል እንዴ?»

«ምንም ልዩነት የለውም። አሁንም ታስረሃል።»

«ታስረሃል? ትቀልዳለህ። እነሱ ከኔ የሚጠብቁትን መፈፀም እንዳለብኝ የተሣፈ ነገር የለም። አንዳች ቦታ ቀልቤን ከሣበው እዚያው እቀራለሁ፣ ወይም አንዳች የሚመራኝ መንገድ ካገኘሁ እከተለዋለሁ። ኤምባሲያቸው ቢሻው ራሱን ያንጠልጥል። የአበሻን አገር ለማየት ከፍተኛ ጉጉት አለኝ። የምሄድበትም ብቸኛው ምክንያት ይኸው ነው። ከዚህ በላይ አገሩ የሚስማማኝ ከሆነ በዚያው እቀር ይሆናል»

ለረዥም ጊዜ ዝም ተባባሉ። ሜትር ገ/ሚ ምንም ሳይተነፍስ ቆይቶ፣ ሻማ ይበራበት ወደ ነበረው ቤት ገባ። ሁለት ሻምላዎችን አነሣ፣ ከተሰፋ ቆዳ የተዘጋጁትን ሁለት የደረት መከላከያዎችንም ያዘ። ወደ መድሃኒት ቅመማው ሙያ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ የሻበላ ግጥሚያ በበጋው ወራት ምሽቶች የጊዜ ማሣለፊያቸው ነበር።

«በል ተነስ፣ ይህና አድርጌ አውቅሃለሁ። ትሄዳታለህ» አለው ጆን ባፕቲስት፣ ሻምላቸውን ሣያገናኙ በፊት።

«የለም፣ አላደርገውም። ሣጫን ልታስለውጠኝ አትችልም። ቢሆንም መልካምና ለላማዊ ጉዞን እመኝልሃለሁ» አለ ሜትር ገ/ሚ

ሁለቱ ሻምላዎቻቸው እንደተጋጩ፣ ሊጫናቸው አስፍስፎ የነበረው ትካዜ ብትን አለ።

9

ወደ አቢሲኒያ ለሚደረገው ቅኝስት፣ ዝግጅት መደረግ ነበረበት። የቅኝስቱ መሪ ሃጂ አሊ ሲሆን፣ ፖንሴና ወንድ አገልጋዩ ዮሴፍን ያካትታል። የቱርኮችን ጥርጣሬ ላለመቀስቀስ ሁሉም ነገር በተቻለ መጠን ሰላማዊ መምሰል ነበረበት። በዚህ የተነሣ፣ ቆንሲሉ በቅኝስቱ ውስጥ አንዳችም ተሳትፎ አይኖረውም። ጆን ባፕቲስትም ቢሆን ምንም ዓይነት የመነሣሣት ፍላጉት ማሣየት የለበትም። ግመሎቹንና በቅሎዎቹን፣ ኮርቻዎቻቸውን፣ ልጓሞቻቸውንና የጭነት ዕቃዎቻቸውን ሁሉ የገዛው ሃጂ አሊ ነበር። ለጉዞው ለሚያስፈልጉ የልብስ ዓይነቶች ኀጋዩው የሚጠራውን ምንም ዓይነት ዋጋ የሚሸፍነው፣ ሙሴ ዲ ማይሌ እንዲሆን ታቅዶ ነበር። ይህ ስምምነት ሃጂ አሊ ተጨማሪ ትርፍ እንዲያገኝና በዚህም የሚችለውን ያህል ሸቀጣሸቀጥ በስብቶቹ ላይ ለመጫን ያስችለዋል። ይህ ነገር አቢሲኒያ ደርሶ፣ ሽቀጦቹ በወርቅና በጥሪኝ ዝባድ ከተሰወጡ የኀጋዩውን የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት በአሥር እጥፍ ያሣድግለታል።

ቆንሲሉ፣ አፈሴል ደብዳቤ አዘጋጅቶ ለአበሻው ንጉሥ ሣፈ። ጽሁፉ በሙሴ ማቹ አማካይነት ወደ አረብኛ እንዲተረጎም አደረገ። ይበልጥ ጥንቃቄ ለማድረግም ሊል ትርጉሙን በአረቦች መኖሪያ የሚኖሩት ሶሪያዊ ምሁር መነኩሴ፣ ወንድም ፍራንሲስ እንዲያጣሩት አደረገ። ይህ ተከናውኖ ሲያበቃ፣ በደብዳቤው ላይ የፈረንሣይን ማህተም አሳርፎበት ለፖንሴ ተሰጠው። ከዚህ በተረፈ ቅኝስቱ ለሚያልፍባቸው አገሮች ገዢዎች የሚሰጡ ገፀ በረከቶች መሰብሰብ ነበረባቸው። የቀረዋ ክፍያውም ጥበቅ በሆነ የጉዞ ሰዓት የተወሰነ ነው። ይህ ዓይነቱ አሠራር ከጥንት ጀምሮ ሲተገበር የነበረ ነው።

ጆን ባፕቲስት በበኩሉ ሊገመት የሚችለውን ማንኛውንም ድንገተኛ አደጋ ለማከም የሚያስፈልጉትን የሕክምና መሣሪያዎች በመሰብሰብ ተወጥሯል። መድሃኒቶቹን የሚያስቀምጥበትን አዲስና ሰፊ የጠርሙስ ሣጥን፣ ሙሴ ዲ ማይሌ ሰጥቶታል። የዘመቻውን መሣሪያም፣ ጆን ባፕቲስት መርጧል። አንድ ትልቅ መስኩቶ ጠመንጃ በየሲፍ ኮርቻ ላይ ሲሣን፣ ባሩዱና እርሣሶቹ ግን በፖንሴ ጥበቃ ውስጥ ሆነዋል። ከጥንድ ጐራዴዎች ሌላ፣ ለጆን ባፕቲስት ሁለት ሽጉጦችም ተገዝተውለት በኮርቻው ኮሮጆዎች ውስጥ ሞኗቸዋል።

ዝግጅቱ እየተካሄደ ነበለ፣ ቆንስላው የእንቅስቃሴው ጠቅላይ መምሪያ መሰለ። የቅፍለቱ አባላት የየዕለቱን እርምጃ ለመወያየት በየምሽቱ ልክ ከእራት በኋላ ይገናኛሉ። የወንድ አገልጋይ የተባሉት የሴፍ ጥርጣሬ እንዳያድርባቸው ሲባል የጀስዊት አለባበሳቸውን ተዉ። የቆንሲሉ የራሱ አገልጋዮች ምናልባትም አንዳንዶቹ ለላዮችም ስለሆኑ ፊጥነው ሲጠረጥሯቸው ስለሚችሉ አልባሽ የተባሉትንም ማሣመቻ አስካሁን አልተዋሃዱትም። አሊ፣ ፖንሴና ጉብውን የማይከፈለው ነገር ግን በዝግጅቱ ላይ ድጋፍ የሚያደርገው ዝርሚ መግባታቸውና መውጣታቸው ሣይጠቀስ ወደ ቆንስላው ይመላለሳሉ። እንዲህ ያለው እንቅስቃሴ ከአጭር ጊዜ በኋላ እንደሚያከትም ስለሚያውቅ የመግባትና መውጣቱን ነፃነት የፈቀደው ሙሴ ዲ ማይሴ ነው።

ሽርጉዱ ማዳም ዲ ማይሴን ቢያደክማትም፣ ልጇ አሊስ፣ በቤታቸው ዙሪያ ጥቂት ጉብኚዎችን በማየት መዳስ ርካታን ሰጥቷታል። ከሁሉም በላይ ግን በአትክልቱ ሥፍራ ውስጥ ብዙ ጊዜና በቅርብ ርቀት ያስደነገጠችውን ወጣት ለው በሚገባ ለመለየትና ማን መሆኑን ለማወቅ ዕድሉን አገኘች። እርሱ ግን በቀጥታ ጠርቶ እንዳያሸኩረምማት ብርቱ ጥንቃቄ ያደርጋል። ይሁን እንጂ፣ አሊስ በርግጥ ፊት ለፊት የሚነጋገሩ የሚመስላትን አስገራሚና አስደሳች ስሜት በውስጧ ፈጥራለች።

ይህን የመሰለው ስሜት የተፈጠረባት ሰዎቹ፣ ክባዱን ጭነት መሸከም ያለባቸው ግመሎች ናቸው? ወይስ በቅሎዎች? በሚል ረዥም ክርክር ባደረጉበት ዕለት ነበር። ከተሰመደው ዕውቀት በተቃራኒው ግመሎች ከበቅሎዎች ያነሰ ጭነት ይሸከማሉ በሚል ጆን ባፕቲስት ሙዝዝ አለ። እርሱና ሃጂ አሊ ሲከራከሩ፣ ቆንሲሉ፣ ሙሴ ማቹና አባ ብሬቬዳንት የየራሣቸውን አስተያየት አሰሙ። በሮች ሁሉ ክፍት ሆነው በቆንስላው ውስጥ አዲስ ስሜት ስፍኖ ባለበት ውይይት መካከል አሊስ ገባች። ወደ አንድ ወገን ፈቅ ብላ፣ በአነስተኛ ብርኩማ ላይ ተቀምጣ፣ ጥልፏን እየሰራች እንግዶቹን ማጤን ጀመረች። ወዲያውኑ፣ ያ ወጣት ለው ለራሱ እንጂ ለሌሎች እንደማያወራ ተሰማት። ይህ ስሜቷ በጣም እንግዳ ነው። የጆን ባፕቲስት ቃላት፣ ከፊት ለፊቱ ሆነው የሚመለከቱት ሰዎች ጠጣር አካል ላይ ነጥሮ የሚመለስና ክሰዎቹ በስተጀርባም ብርሃን የሚታይ መሰላት። ቃላቱ በጣም ልስልስ ብለውና በወራጅ ወንዝ ውስጥ እንዳሉ ክብ ጠጠሮች፣ ቀለሞቻቸው የማይነበሩና ዋናው ትርጉማቸው የተፋቀ ሆነው ደረሷት። በአጭሩ ለርስዋ የተረፋት እንድትደሰትበት ተብሎ የተላከላትና

በትክክልም ግቡን የመታ ሙዚቃ ነበር። ሁለቱ ብቻቸውን ወይይት ቢያደርጉ ኖሮ፣ ስለቃላቱ ትርጉሚ ይበልጥ አትኩረት ትሰጣቸው ነበር። ነገር ግን ይህ የዝምታ ሣጣብ መለዋወጥ ከንፁህ ስሜት የመነጨ ነው።

ወጣቱ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደርስዋ አቅጣጫ ይመለከታል። ዓይኖቹ ከመስኩቱ ባሸገር ባለ ነጥብ ላይ ያነጣጠሩ ይመስላሉ። ሌሎች ሰዎች አንዲህ ያለውን አተያይ፣ ሣጣቡን ለመሰብሰብ የሚጥር ተናጋሪ የሚያደርገው ዓይነት ነው ብለው አስበው ይሆናል። እርስዋ ግን፣ አተያዩ ሁሉ ሙሉ በሙሉ በርስዋ ላይ ማረፉን በርግጠኝነት ተሰምቷታል። ከፊትዋና ከፈላዛ ቢጫው ፀጉርዋ የሚወረወረው የብርሃን ፀዳል መልዕክቷን ተሸክሞ፣ እርስዋነትዋን ታዝሎ፣ ወደ ጥልቁ የዓይኖቹ ውሣዎች ውስጥ፣ ወደ ምስጠራዊው ልቡ ውስጥ እንደዘለቀ አወቀች። ዓይን ወርወር የማድረግና የዕይታ ጨዋታ ስሜትን ካቀጣጠለ፣ የሚቀሰቅሰውን ውስጣዊ ስሜት ሊያባብሰው አይችልም። አሊስ፣ ወጣቱን ሰው ለመቅረብ ያላትን ስሜት ከማቀዘቀዝ ይልቅ እነዚህ አስቸጋሪ ምልክቶች ጭራሹኑ አባባሱት። እርሱ በበኩሉ በመሳክላቸው ያለውን የመለያየ ርቀት ለማገናኘት አልጣረም። እርስዋ ደግሞ ይህን ልዩነት እንዳታስወግደው ያለችበት ስፍራና ያታዋ የማይፈቅዱላት ሆነ።

ከዕለታት አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ፣ አሊስ፣ ሊደርስባት ከሚችል የሞራል ውንጀላ ለመጠንቀቅ፣ እናቷን መከላከያ አድርጋ ወጣቱ ሰው ወደ ቆንስላው ሲገባ እንደማንም ልታነጋግረው ቻለች። ሁለቱ እመቤቶች በትንሿ የመናፈሻ ሥፍራ ይንሸራሸሩ ነበር። ጆን ባፕቲስት፣ በነርሱ ቁመት ልክ ባለችው ጠባብ መንገድ ሲደርስ፣ እርሱ እንዲሰማት ጮክ ብላ፣ እርሱን ተንበርክኮ ያየችበትን ትንሽ ቁጥቋጦ እያመለከተች፡-

«እማዬ ይህ ሰው ስለዕፅዋት ብዙ ያውቃል። ትናንት ያየውና ለኛ የተለመደ ሥልሠነውን የዚህ ቁጥቋጦ ስም ለምን አትጠይቂውም?»

ጆን ባፕቲስት ቆም ብሎ፣ ከወገቡ ጉንበስ አለና ባልተረበሸ ድምፅ መልስ ሰጣቸው።

«አዎም እንደናንተው አስተውዬዋለሁ። ምንነቱን ለማወቅም ጓጉቼ ነበር። ግን ተክሉ አዘውሮፓ ውስጥ የማይታወቅ ዝርያ ነው። ሌላው ቀርቶ፣ ጆን ሬይ በዕፅዋት ስም ዝርዝሩ ውስጥ አላካተተውም። ስለዚህ ዕፅ የተጠቀሰ ነገር ያገኘሁት በአንድ የግብፃውያን መፅሃፍ ላይ ነው። ዝርያው ራቅ ብሎ ወደ ደቡብ በጣም የተለመደና ተራ ነው። ተክሉ አሁን ከሚታየው በላይ ቁመቱ አያድግም። በሕይወት ዘመኑም የሚያብበው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። አንዳንድ

ለምች፣ በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተጠቀሰው አስብላቢት ቁጥቋጦ መገለጫ ትርጓሜ ነው ይላሉ»

እነዚህን የመጨረሻዎችን ቃላት ሲናገራቸው በቀጥታ በወጣቷ ልጅገረድ ዓይኖች ውስጥ እየተመለከተ ነበር። ወዲያውኑም ቀለጠች። ሴትነትዋ በረታ። ጉንጮችዋ ፋሙ። እርሱም ዝቅ ብሎ ስላምታ ሰጥቷቸው ተለያቸው።

የልጅዋን ግራ መጋባት ያላጤነችው ማዳም ዩ ማይሌ፣ ስለመፅሀፍ ቅዱስ ትርጓሜ የተገለፀውን በተደጋጋሚ እያሰበች ተደሰተች። በሚቀጥለው ሳምንት ታሪኩን ለንስሃ አባቷ ስትነግራቸው፣ እንዲህ ያሉ የመፅሀፍ ቅዱስን መልዕክት በምሳሌያዊና በሃይንግዊ ማብራሪያዎች የሚገልፀ በድብቅ ሥልጣን ለመያዝ የሚሯሯጡ አድመኞችና የፍልስፍና ሰዎች እንደሆኑና እነርሱም ፀረ ሃይማኖት አቋም እንዳላቸው ተገነዘበች።

በቅፍለቱ ጉዞ ዋዜማ ላይ እነዚህ አስደሣች ትርምሶች ሁሉ ማብቂያቸው መድረሱን አሊስ በድንገት ስትገነዘብና ያንን ወጣት ሰው በቀጥታ እንዳላነጋገረችው ስትረዳ፣ በዚህ አደገኛ ጉዞ ላይ ይሞትም ይሆናል ስትል አሰበች። ልታደርገው የምትችለውስ ነገር ይኖር ይሆን? እንደተለመደው ከሀልም ዓለሚ የሚመልሣት ነጥብ ላይ ስትደርስ አሊስ አቅማሚች። ስለእውነተኛው ህይወት ምን ያህል ተገንዝባ ተሰናዶ እንዳላት ተሰማት። ስሜቶችዋ ሁሉ፣ ፅይታዋ ሁሉ፣ የወጣቱ ሰው እሆናለሁ ብላ ስታስበው የነበረው ሃሳብ ሁሉ ምናልባት ከራስዋ የመነጨ እንደሆነ ስትል ለራስዋ ነገረች። ከዚህም ባሻገር፣ ለመሆኑ ሰውዬው ራሱ ሊያነጋግራት ሞክሯል? ወይም ደግሞ የፍቅር ደብዳቤስ ልኮላታል? የመጀመሪያውን አስተያየት ወይም ጥያቄ አርስዋ ብታቀርብለት በርግጥ ስህተቷን ይገልፅላታል። ዱብዬ ምን ትፈልጊያለሽ? እነዚህ በርበሬ ጉንጮች የት ያደርሷት ይሆን? ለዚህ ማረጋገጫ እስካሳገኘች ድረስ ተናቅሁ ብላ አትበሣጭም። እንዲህ ከሆነ ባለፉት ጥቂት የደስታ ዕለቶች አጠረቃቅማ ያከማቸቻቸውን ጣዕረ ሞቶችና ጣፋጭ ህልሞች ሳይበላሹ ትጠብቃቸዋለች። ስለ ምን ተስፋ ልታደርግ ትችላለች?

ግራ በመጋባት፣ ጆን ባፕቲስት የባለ ነው። ሊመኘው የነበረውንና ጥልቅ ስሜት ያሣዳረበትን ጉዞ ሊጀምረው ነው። ይህ ደግሞ ለደብዱና ለአሰሳ ላለው አምሮት የሚመች ነው። ለዚህም በጋለ ስሜት በዝግጅት ላይ ተጠምዷል። አሁን ግን ይህችን ወጣት ሴት

ከተዋወቀበት ጊዜ ጀምሮ የጥርጣሬ ስሜት አድሮበታል። የተሟላና ትክክለኛ በነበረው ደስታው ላይ ጥላ አጥልቶበታል።

ለመጀመሪያ ጊዜ በክሃሊጅ ድልድይ ላይ በድንገት ሲገናኙና በቆንስላው ግቢ ለሁለተኛ ጊዜ ሲተያዩ ከነበረው የልበ ሙሉነት ትምክህት በኋላ፣ ተከታታይ የሆኑ ጉብኝቶችና መተያየቶች ተከስተዋል። ጆን ባፕቲስት፣ ይህችን ወጣት ለመጀመሪያ ጊዜ ሊያያት ብልጭ ያለበትን ስሜት፣ በቅርብ ሆኖ ሊያስተውላትና ሊያስላስላት ትርፍ ጊዜ ነበረው። በመሆኑም አሁን ስሟን ማወቅ ችሏል። ባለፉት ጥቂት ቀናት ያደረጓቸው ቅርርቦሾች፣ ሲጀመር የነበረውን ስሜቱን እያበለፀጉለትና በጉልህ የሚታይ በማድረግ፣ በአዕምሮው ውስጥ የተቀረፀው የመጀመሪያው ውበቷና ምስጢራዊነቷ ሳይበታተኑበት፣አካል ቁመናዋ ሕልሙን ፈታሉት። እንዲያውም፣ ባሳያት ጊዜ፣ ያጣት ያህል የሚሰማው ስሜት ላይ ደረሱ።

በማህበራዊ መደባቸው መካከል ያለው ልዩነት በመጀመሪያ ከፉኛ ይሰማው ነበር። እያደር ግን ችላ ሊባል እንደሚችልም ሲያስብ፣ ተዝቀዝ ቢልለትም አሁን ደግሞ እንደገና ብቅ ማለት ጀመረ። በመካከላቸው የተጋረደው ግዳንዳ የማይገፋ ቢሆንም፣ ዓይኖቻቸው ግን እየጣሱት ይንከራተታሉ። ጆን ባፕቲስት ተስፋ መቁረጥ ጀመረ።

ዝግጅቱና የየዕለቱ ግንኙነት የለነበተው ለጥቂት ሣምንት ነበር። ብዙው ነገር በቅፍለቱ እንቅስቃሴ ስለተሸፈነ፣ ጆን ባፕቲስት የራሱን ስሜት እንኳ ለማጤን ጊዜ አላገኘም። ከዚህም ባሻገር ምስጢሩን ለማን ያካፍል? ሜትር ዝረሚ እንዲህ ካሉ ጉዳዮች እንደሚሸሽና በዝምተኛ ፕሮቴስታንት ስጋት፣ በሻካራ ቋንቋ ሌሎች ላይ በሚደነፋ መካከል፣ መሃል ሥፍራ እንደሌለም ያውቃል። ጆን ባፕቲስት፣ የካይሮን ምስጢሮች ሁሉ ያገኛል። እርሱ ግን እህ ብሎ የሚያዳምጠው አንድም ሰው የለውም። ይህን ሁሉ በድንገት ሲያስበው ፍፁም ብቸኛውና ደስታ ቢስ ሰው የመሆን አዲስ ስሜት ይመጣበታል። ይሣካልኛል፣ ይሆንልኛል፣ ብሎ በታላቅ ስሜት በሚጀምረው ድንቅ ጉዞ ላይ ደንቃራ ይሆንበታል። ርሀራሄን ለራስ በመስጠት፣ ውጤት ላይ የሚኖረውን ተፃራሪ የሆነ ጥፍጥና ለመጀመሪያ ጊዜ ተሰማው። በመነሻው ዋዜማ ሰለት ፀሐይ እንዳቆለቆለች ወደ አረቦች መንደር አመራ።

የሚያውቃቸውን ሁሉ ትቶ የሚሄድ ሰው አስቀድሞ በጥሞና ለማሰብ የሚችለው፣ ግንዛቻቸው ዘርጣጣ የሆኑ ዘንባባዎች ባሉበት፣ ቅርንጫፎቻቸው የተጥመለመሉባቸው እጅግ

ትላልቅ የማንጐ ዛፎች በሞሉበት፣ ሻካራና ክቸች ያሉ ግራሮች በተጠቀጠቁበት፣ ለወይራ ተራራ ጥሩ አቻ ይሆናል ተብሎ የሚገመተውን የካይሮ ሰፈር ነው።

ስተስፋ መቁረጥ ምንም ተሰጥኦ የሌለው መሆኑ የተሰማው ጆን ባፕቲስት፣ ወደዚህ ብቸኛ ቦታ ድርሽ ብሎ አያውቅም ነበር። የመናፈሻው ሰምሰም ተክሎች፣ ዘይታማ ሽታቸውን በፀሃይ ግለት ከምድር እየለቀቀ በሚነሣው አየር ውስጥ ይተነፍሣሉ። በትካዜ ውስጥ ሆነው በባዶ እግራቸው ያሉ ሽማግሌ አትክልተኞች የለጋ ችግኞችን ሥር ውሃ ያጠጣሉ። በደረቁ መሬት ላይ የሚፈስሰው ውሃ ለስላሣና ውብ ድምፅ ይፈጥራል። ቀኑ ረዥም ነው። ፀሐይ የጠለቀች ቢሆንም፣ ሐምራዊ ጥላ የመሰለው ብርሃንዋ እስከምሽቱ ይዘልቃል። ጆን ባፕቲስት በአንድ አግዳሚ ላይ አረፍ አለ። በስሀተት ምክንያት ባጣው ነገር ሃዘንና ትካዜ ስለገባው፣ ይህን ሁሉ ሰዓት እንደቅጣት በመክፈሉ በራሱ ድድብና ሣቀ። ዳግም ግን እንዲህ ላያደርግ ማለ።

በተቻለው መጠን ሁኔታውን በርጋታና በፀጥታ ሊመረምረው አሰበ። በመጀመሪያ ምንም ዓይነት ተሞክሮ የሌለው መሆኑን አመነ። ከረዥም ጊዜ በፊት ጀምሮ፣ የሴቶችን ስጦታ ያለድካም ይደሰትበት የነበረ ቢሆንም፣ ፍቅርን እርሱ በሌሎች ውስጥ ሊቀሰቅሰው እንጂ ፣አያውቀውም ነበር። እንዲህ ካለ አድሏዊ ስሜት የተማረው፣ ከቁጡ ቀናተኛ ባል እንዴት እንደሚያመልጥ ብቻ ነበር። አንድ ጊዜ፣ አንድ ግልፍተኛ ባል በአደገኛ ሁኔታ ከቪኔስ እንዲሰቅቅ አስገድዶት ነበር። ካይሮ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ግን፣ አንዳችም አደጋ እንዳይደርስበት ከቆነጃጅትና ፍላጐታቸው እያየሰባቸው ጠልፈው ሊያስገቡት ከሚከጅሉት የአቶማን ወይዛዝርቶች ሁሉ በጥንቃቄ ራሱን ለማላቀቅ ችሏል። ከቤዮች አንዱ፣ ከተወዳጀው በኋላ ትልቋን ልጁን ሊጋብቻ ሰጥቶት ነበር። ይህ ጉዳይ በርግጥ አንዳች ግዴታ ታክሎበት ነበር። ይኸውም ጆን ባፕቲስት የእስልምናን እምነት መቀበል ነበረበት።

እንደዕድል ሆኖ፣ መቃበጦችንና ጊዜ ማሣለፊያዎችን ለፍቅር ሲል እንደማይወስዳቸው በጣም ግልፅ ነበር። እንዲህ ያለ ስሜትም እንደሌለው ያውቃል። ይህ ታዳያ ሃዘን ወይም ቅሬታ የሚፈጥርበት ሣይሆን ደረት አውነታ ነው። በመሆኑም እንዲተም ሴት ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ወይም አብሮ የሚኖር፣ ሽብርና ቅበጥብጥነትን የምትፈጥርበት፣ አዕምሮውን የመግዛት ሃይል ያላት፣ ፍቅርን ሊገልፅ የሚችለውን የልብንና የስሜት ህዋሣትን የማሸነፍ ስሜት የፈጠረችበት የለችም። እስከዛሬ የገጠሙትን ብሩህ አውነታዎች በመለማመዱና

በመደሰቱ፣ በነፃነቱ ላይ ገደብ የሚጥልበት ፍቅር አግኝቶት አያውቅም። ታላቅ የጀብዱ ተግባር ለመፈፀም ለጉዞ ሲነሣ፣ እጅግ የሚማሣስት፣ ጥንቃቄ የሚሻውና ጭንቀት ውስጥ የሚከትተው የማዳሞዜል ዲ ማይሌ ሃሣብ፣ በቁርጠኝነት ሊከተላትና ሊያገኛት እንደሚገባው በውስጡ የተፈጠረበት የመጀመሪያው ትግል፣ ደስታ አልሰጠውም።

በአህያው ጀርባ ላይ ተንጋድዶ የተቀመጠ አንድ ሽማግሌ ሰው፣ በመንገዱ ላይ በዝግታ ያመጣል። አስካሁን ፀጥ - ረጭ ባለው ምሽት፣ የሽማግሌው ሰውዬ የድፍረት ማሽካኸትና ለዚህ ምላሽ ደግሞ የታፋነ ድምፅ የሚመስለው የአህያው ኮቴ ዜማዊ ቅላፄ ይሰማል። በአህያው ጐን የተንጠለጠሉት ኮሮጆዎች አሾሃማ ፍሬ ተሞልተዋል። ሰውዬው ቀረብ ሲል፣ ጆን ባፕቲስት ምልክት አሳየው። በመቀጠልም ሣንቲም ሰጥቶት አራት ፍሬዎችን ተቀበለ።

በፍቅር ወጥመድ በመያዙ ፀፀት አልሰማህ አሰው። ምክንያቱም አሁን የያዝው በርግጥ ፍቅር ነው። ነገር ግን ምን ሊያደረግ ይችላል? በአዕምሮው የሚመጣለት ብቸኛው መፍትሔም እርባና ቢስ ነው። ካይሮ ውስጥ ቢቆይ ቆንሲሉ እጅግ በጣም ይቆጣል። ሊያጠቃው እና ምናልባትም ዳግመኛ እንዲሰደድ ሊያስገድደው ይችላል። በዚህ መልክ የቆንሲሉን ሴት ልጅ ማሰብ በራሱ የማይመስል ነገር ነው። ልጅቱ በርግጥ ምላሽዋን ሰጥታዋለች። ይህን ያደረገችው በብቸኝነት ስለኖረች ቢሆንም፣ ከሌሎች ሰዎች ይልቅ በሁሉም ነገር ከፍ ከሚል ቤተሰብ የተገኘች ወጣት ሴት ነች። በተለይም አሁን በርስዋ ዓለም ደረጃ ሊሰጥ የሚችለውን አጭር የዲፕሎማሲያዊ ተልዕኮ የማይቀበለው ከሆነ፣ እርሱን የመሰለ ሰው፣ እርስዋን የመሰለች ሴት ለማስደሰት የሚያስችል ሣጣ እንኳ ሊኖረው አይችልም። በሌላ በኩል ይህን ተልዕኮ የማይቀበለው ከሆነ፣ እርስዋንም እስከነአካቴው ዳግመኛ ላያያት ይችላል። ምናልባት ደግሞ ይህ የተሻለው መፍትሔ ይሆናል። በዚህ መልክ ሁሉም ነገር ያልፋል። ጉዞ ደግሞ ትዝታን ያስቀራል። መጥፎውን ከደህናው፣ ምናልባት ጥቂት አዲስ ግምትን በነርሱ ላይ በማሣደር ያልፋል።

ሆኖም ግን ሊታረቁ የማችሉ የማይመስሉትን ሁለቱን መስመሮች ሊያገናኛቸው እንደሚችል አንዳች ነገር ነገረው። አንዱም አቢሲኒያን የማየቱና ከዚያም ራሱን ታዋቂ አደርጐ ማቅረቡን ፈፅሞ ክዶ ይተወዋል። ወይም ደግሞ የማይደረስባትን አሊስ ዲ ማይሌን፣ በሁሉም የርሱነቱ የደም ሥር ሥሪት፣ እርሱን ለማስደሰትና ስርሱ ብቻ የተፈጠረች መሆንዋን ማመኑን ይክዳል።

አሾሃማው ፍሬ፣ ውሃ የሞላውና ጣፋጭ ነበር። በትንሹ ፍሬ ውስጥ ባለው ጠንካራ ዘርና የሚገመጠው ለስላሳ ሥጋው መካከል ያለው ንፅፅር አስደስተው። አሾሁ ጨርሶ ተልጦ ስላልተወገደ ወጋው። የወጋው ደግሞ ፍሬው ጣፋጭ ስለሆነ ነው ሲል አሰበ።

አንዳንድ ጊዜ አንዳችም ፍች የሌላቸው ዐረፍተ ነገሮች በሃሣብ ባቡር ውስጥ ሥፍራ ይይዛሉ። ሊገልፀው ይገባው የነበረው፣ የበለሱ አሾህ፣ ጣፋጮን ፍሬ ከሚመኙት አንስሳት የሚከላከል ነው የሚል መሆን ነበረበት። ይሁን እንጂ አዕምሮውን አስጨንቆ የያዘው ፕሮብሌም ስላጃጃለው፣ ይሆን እርስ በርሱ የሚጋጭ ሃሳብ እርሱ በሚገኝበት ሁኔታ ላይ አገልባብጦ እንዲያስበው አደረገው። በቀጥታ ራዕይ የታየው መስሎት ተደነቀ። ፍሬዎቹን ወረወራቸውና በትክክል ይኸው ነው ሲል አሰበ። በኔና በርስዋ መካከል ያልተሰመደ ዓይነት እንቅፋት አለ። ይሀን ማሸነፍና ድል ማድረግ የሚችለው ደግሞ ያልተለመደ ሁኔታ ነው። ካይሮ ውስጥ የምቀር ብሆን ኖሮ ፍፁም ላያት አልችልም ነበር፣ ፍፁም ላነጋግራትም አልችልም ነበር። በሁለታችንም መካከል አንዳችም ነገር ስኬታማ ሊሆን ከቶም አይችልም ነበር። ነገር ግን በሃላፊነት የተጣለብኝ ተልዕኮ፣ በታላቅ አደጋ ውስጥ የሚያቆየኝ ቢሆንም ምናልባት ታላቅ ድል አድራጊነትንም ያጐናፅፈኝ ይሆናል። እንደታሰበው ወደ አቦሸ አገር እሄዳለሁ። ንጉሡን ክብሸታው አክሜ አድነዋለሁ። እንደተጠየቅሁትም ከአቢሲኒያ ኤምባሲ ጋር ተከትዬ እመለሳለሁ። እስክ ቬርሣይለስም አጀቤው እሄዳለሁ። ሉዊስ 14ኛም የክብር ዘቦቹው ያደርጉኛል። ያን ጊዜ ሴት ልጄን ብጠይቀው፣ ቆንሲሉ ፊፅሞ አምቢ አይለኝም። ይኸው ነው። የዛሬ ተዋጊ አሾህ፣ ይዋጋል። ነገ ደግሞ ይመስገነው ለፈጣሪ፣ ጣፋጭ መዓዛው ይገኛ ል።

ወጣቱ ለው ተነስቶ ቆመ። ለራሱ አንዳች ነገር አጉተመተመና ወደ አትክልት ሥፍራው መግቢያ በር በፍጥነት ተንደረደረ። በአዕምሮው ውስጥ የተፀነሰው ሰፊ ንድፍ መሠረት ስለያዘ ቀሪው ጉዳይ ያለብዙ ድካም መፃጣት ይችላል። የተግባር እንቅስቃሴ ለማድረግ እቅድ አወጣ። በተለያዩ አቅጣጫዎች ገምግሞ በጣም ጥሩ መሆኑን አረጋገጠ። እስከ ፍፃሜውም ይህንኑ ሊያከናውን ማለ።

ሁሉም ነገር፣ በተለይም ሃላፊነት የተሰጠው ዲፕሎማሲያዊ ተልዕኮ በአዲስ መልክ ብሩህ ሆኖ ታየው። በመጀመሪያ ይህ ሁሉ ተግባር የፈረንሣዩን ንጉሥና የጳጳሱን ፍላጐት ብቻ ለማሟላት ነው ሲል አስቦ ነበር። እየዋለ እያደረ ግን የርስንም ደስታ አውን ሊያደርግ እንደሚችል ተገነዘበ። ቀሪው ተግባርና ሥራ ሁሉ የምር መሆን ጀመረ።

10

በአባይ ወንዝ ላይ በምትገኘው ቡላክ በተባለች የአይሮ ወደብ የሚገኙትን ጀልባ ቀዛፊዎች ሙሴ ማቼ ሲጠይቃቸው፣ ሁለት የካፑቺን መነኮሣት ከደለሱ ምድር ተነስተው በአንድ በተበላሸች ጀልባ ላይ ተሣፍረው ሽቅብ እየተጓዙ መሆናቸውን ተረዳ። እነዚህ ሰዎች አሁንም ከከተማዋ የሦስት ቀን ርቀት ላይ ናቸው። የመድረሣቸው ዜና አደጋ ያለበት ስለሆነ ከወዲሁ ዝግጅት እንዲከናወን የሚያነሣሣ ነበር። ቅፍለቱ ከሠላት ቀናት በኋላ በዕለተ ሰኞ እንዲንቀሣቀስ ተወስኗል። አንድ ቀን ቀደም ብሎ ሣምንታዊውን የቅዳሴ ፀሎት ሥርዓት አባ ዩ ብሬቨደንት ራሣቸው በቆንስላው ውስጥ ለማከናወን እንዲችሉ ቆንሲሉን ጠይቀውታል። እነሆን ካህን ሁልጊዜም እንደሠራተኛ መገመቱ በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ ቆንሲሉ የግል ስሜቱን እያንፀባረቀ ፈቀደ። ዋናውን የፀሎት ቤት ቢጠቀሙ የማህበሩ አባላት በሙሉ ሶክፊሉት የሚችሉበት ይሆናል። ይህ ደግሞ በምስጢር ሊጠበቅ የነበረውን አንቅስቃሴ ሁሉ ማወጅ ይሆናል። ስለዚህ ለተንገቦቹ የሚደረገው የፀሎት ሥነ-ስርዓት የንጉሡ የቅብ ስዕል ባለበት የአንገዳ መቀበያው ክፍል ውስጥ ይሆናል። ከሙሴ ዩ ማይሉ ቤተሰብ ሌላ በዚህ ሥነ-ሥርዓት ላይ የተገኙት አባ ጋበሪ፣ ሙሴ ማቼ፣ ሙሴ ፍሪሌንቲና ጀን ባፕቲስት ነበሩ። እንደተሰመደው ጀን ባፕቲስት ለወጣቷ አሊስ ምንም ምልክት አልሰጣትም። ግን በጣም ረኸም ጊዜ የቀየ የመጨረሻ መተያየት አደረጉ። በዚህም ጊዜ ውስጥ አነበበችው፣ እርስዋኑ አስክደንቃት ድረስ ውስጧ ተደሰተ።

ቆንሲሉ፣ ስለ ወጣቱ ሐኪም ባህርይ ግዴለሽ ቢሆንም፣ በጣም መሠረታዊ ስለሆነው የቤተክርስቲያን ሥርዓት ግን ምንም ዕውቀት እንደሌለው አስተውሎታል። ይህ አነስተኛ ማስረሻ፣ ግለሰቡ አማፋሪ የሃይማኖት ክህደት በውስጡ እንዳለው አረጋገጠለት።

ሥነሥርዓቱ ከተከናወነ በኋላ ቀጥሎ በሚገኘው የሣሉን ክፍል ውስጥ ቀላል ቁርስ ቀረበ። እንኒን ደስ አለን! የምስራች! ተባባሉ። በዚህ ሰዓት ጀን ባፕቲስት፣ ቆንሲሉን ለመጨረሻ ጊዜ የግል ጉዳዩን በተመለከተ ሊያነጋግረው ፈቃድ ጠየቀው።

«በል እንግዲህ ንገረኝ። ምንድነው?» አለው ቆንሲሉ ብቻቸውን በሆኑበት ጊዜ፣ ትዕግስት በማጣት

«ክቡር ሆይ፣ እኔ ከዚህ ከወጣሁ በኋላ ዓደኛዬ ካይሮ ውስጥ ሊቀር እንደማይችል አውቃለሁ። እርሱ የሚያዘጋጃቸው ፍቱን መድሃኒቶች ሁሉ የሚቀመሙት በኔ መመሪያ መሠረት ብቻ ነው። ብቻውን አንዳችም ነገር መሥራት አይችልም። ስለዚህ፣ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን አብሮት እንዲሰራ የሚፈልግ አንድ መድሃኒት አዋቂ፣ ወደ አሌክሣንደሪያ እንዲመለስ ጠይቆታል።»

«ደህና፣ እኔ ደግሞ ልጠይቅህ፣ ይህ ጉዳይ እኔን ምን ይመለከተኛል?» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ

«ወደዚያው እያመራሁ ነው። የዚህ የሥራ ባልደረባዬ ወደ አሌክሣንደሪያ መሄድ ጊዜያዊ ነው። እኔ ከአቢሲኒያ ስመለስ . . . »

ቆንሲሉ አይኖቹን ሰበራቸው

«. . . አምን» ሲል ጀን ባፕቲስት ንግግሩን በቁርጠኛ ድምፅ ቀጠለ። «እኔ ከአቢሲኒያ ስመለስ፣ ሜትር ገረሚ ወደ ካይሮ ተመልሶ ሥራችንን በጋራ እንቀጥላለን»

«ድንቅ ሃሳብ ነው»

«የዚህ ውጤቱ . . . »

«የዚህ ውጤቱ?»

«መኖሪያችንን እንዳለ ትተነው ነው የምንሄደው»

«በዚህ ላይ ምንም ችግር አይታየኝም። ስለኪራዩም ከሆነ ራስህን አታስጨንቅ» አለ ቆንሲሉ፣ ፖንሴ ወዴት እያመራ መሆኑን በሚገባ ሊያውቅ።

«ባቀረብኩት የወጭ ዝርዝር ውስጥ የአንድ ዓመት ኪራይ አስቤ ነው የሠራሁት። እኔ የምለው ጉዳይ ግን ሌላ ነው»

«ታዲያ ሁሉም ነገር ተከናውኗል?»

«የለም» አለ ፖንሴ፣ ሁለት ጊዜ በትንሿ ክፍል ውስጥ ዞር ዞር አለና በማስፈራራት መልክ፣ በቆንሲሉ ላይ እንደሚከመርበት ዓይነት ፊት ለፊቱ አፍጥጦ ቆመ። ፖንሴ፣ ከአንገቱ በላይ ከቆንሲሉ ይረዝማል «ቤቱ ምንም ማለት አይደለም። በውስጡ የያዛቸው ዕቃዎች ግን እጅግ በጣም ጠቃሚዎች ናቸው። በርግጥ ብዙ አይደሉም እንጂ እቃዎቻችን በሙሉ እዚያው ናቸው። ነገር ግን ጨርሶ በዋጋ ሊተመኑ የማይችሉ እጅግ ከፍተኛ ትዕግስትና ጥንቃቄ ወስደን ባለፉት ዓመታት ያዳቀልናቸው ብዙ ልዩ ልዩ ዕፅዋት አሉ። እነርሱ መጥፋት የለባቸውም»

«አሽከሮቼ ውሃ እንዲያጠጧቸው ትዕዛዝ መስጠት የሚኖርብኝ ይመስለኛል»

«ውሃ እንዲያጠጧቸው! አሽከሮችም! ስለነዚህ ነገሮች ስመሆኑ ምን ያህል ያውቃሉ ጊታቱ!» አለ ፖንሴ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ በልጦጠ እያንከባለላቸው። «እንዲያው ያስቡት፣ ማንም አላዋቂ ሰው በማንኛውም አሣቻ ሰዓት እየመጣ ጥቂት ውሃ እያፈሰሰና እየረጨባቸው፣ እነዚህን የመሰሉ ሃብቶችን በርግጥ በሕይወት ያቆያቸዋል ብለው ያምናሉ?»

«ስገምተው አምን፣ እንደዚያ ብዬ አምናለሁ» ሲል ቆንሲሉ ተንተባተበ

«የለም፣ እንደዚህስ አይደለም» ሲል ፖንሴ በሃይል ተናገረ። «አዩ የሚከፈሰንም በዚሁ መጠን ነው። ምክንያቱም ስለዚህ አስገራሚ የዕፅዋትና የአዝርዕት ዓለም ሁሉንም ነገር በሚገባ ማወቅ ይኖርብናል። ከዚህ ቀጥሎ ያለው የሰው ልጆች ተንኮል፣ በጣቅ የሚታሰፍ ቀፋ ነገር ነው። እነዚህን ዕፅዋት በተገቢው ሥርዓት ለማልማትና ለማሣደግ የነበረውን የትዕግስት መጠን፣ ጥልቀትና የስሜት ብርታት የሚገነዘቡ አይመስለኝም። ዕፅዋቱ በተፈጥሮ እንዳ ለሌላኛው ጠላት ነው»

በአንድ ትምህርታዊ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተመስጦ ሊይዝ እንደሚያደርገው ሁሉ፣ ጀን ባፕቲስት ቃላቱን አበክሮ ሲናገራቸው፣ እጆቹን በሃይል ያወናጭፋቸዋል።

«ለምሣሌ አንድ የዕፅ ዘር፣ የሙቀት መጠኑ በጥቂት ዲግሪዎች ከፍ ቢል ሊሞት ይችላል። ይህን ሲያውቁ መስክት በመክፈት ችግሩን የሚፈቱት ይመስልዎታል? ነገር ግን አይደለም። ይልቁንም መቅሰፍት ነው የሚሆንበት። ተክሉ በነፋስ ከተመታ በኋላ በማግስቱ ደርሰው ቢያዩት ጠውልጐና ሞቶ ያገኙታል»

የድምፁ ቃና የዕፅዋቱ ጉዳይ ምን ያህል አሣዛኝ እንደሆነ እንዲሰማ ሆኖ ተሰቀቀ። ሙሴ ማይሴ፣ አይኖቹን በድንጋጤ በሰጠጣቸው።

«ሌላም አለ» ሲል ጀን ባፐቲስት፣ የቆንሲሉ ውስጣዊ ስሜት እንዲቀሰቀስ ለማድረግ ሲል ቀጠለ። «ዕፁ የሚሰጡትን ውሃ በሙሉ ይመጥጣል። በዚህም ሳቢያ በውሃ ብዛት ቁንጣን ይይዘዋል። ቅጠሎቹ ያብጣሉ፣ ይፋፋሉ፣ ይወድቃሉ። ከዚያም እስከ አፍ ጢሙ የሞላ የፍየል ስልቻ ይመስላሉ። በየዕለቱ አንዳንድ ባልዲ ውሃ ይደፋበታል። እርስዎ ከመንቃትዎና ከማወቅዎ በፊት ተክሉ ውሃ የማይሸበት ወይም በድርቅ መቆየት የሚገባው ደረጃ ላይ ይደርሣል። ይህን የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ውጫዊ ምልክት የለም። በርግጥ ዓይን የማይገቡ ምልክቶች አሉ። ይህን ለማወቅ የተክሎችና ዕፅዋት ጥናት ባለሙያዎች ለዘመናት ደክመዋል። ከቀን ወደ ቀን፣ አንድ ብርጭቆ ውሃ በተክሉ ሥር ማፍሰስ ዕውን ሙሉ በሙሉ ያበሰብሰዋል።ከዚህም ሌላ፣ ፈሰሞ የማይጣጣሙና አብረው መኖር የማይችሉ ዕፅዋት አሉ።እነዚህ ተለይተውና ተራርቀው መጠበቅ ይኖርባቸዋል። አለበለዚያ አንዱ ሌላውን በቅርንጫፎቹ ሃይል እያነቀው በመግደል ይበላዋል። ሰው ሲያስበው . . . »

«ንብቶኛል ብዬ አምናለሁ» ሲል ቆንሲሉ፣ ሌሎቹን ሰዎች ለመቀላቀል ካለው ፍላጐት በመነጨ አቋረጠው። «ይህን ሃላፊነት ማን ቢወስደው ትወዳለህ?»

«የተማረና በሚገባ ማንበብ የሚችል ሰው ቢሆን አሻለሁ። ምክንያቱም ሁሉንም ነገር ጽፈን አስቀምጠናል። እያንዳንዱን የዕፅ ዘር ከነሁኔታው፣ ከነመሠረቱ፣ ሀመሙን፣ ረሃቡን፣ ጥማቱንና አተነፋፈሱን የሚገልፁ ማስታወሻዎች አሉን። ነገር ግን ይህ ብቻውን በቂ አያደለም። አንድን ተክል ሳይገድሉት የማይነኩት አንዳንድ ምሁራን አሉ። ምንም እንኳ ዕፅዋትን ለማወቅና ለመገንዘብ እኛ እጅግ ብዙ ጥረት ብናደርግም፣ እነርሱ ግን በተፈጥሮአቸው ገና ስንጠጋቸው ያውቁናል። ለምሣሌ፣ ማቼን በዚህ ሃላፊነት ላይ ቢያስቀምጡት ቤታችን በአንድ ማምሻት ውስጥ መቃብር ይሆናል»

«እና ማን ይሁን?» ሲል ቆንሲሉ ጠየቀ። የሚያቀርበውን ተመራጭ አልቀበልህም ሲሰውና ሲሸማቀቅ ለማየት ጓጉቶ።

«አስቀድሜ እንደተናገርኩት ዕፅዋት አንዳንድ ሰዎች በሚያስተላልፏቸው ምልክቶች የሚስማማቸው መሆናቸውን የመለየት ሃይል አላቸው። እንዲህ ያሉ ሰዎችን እኛ የዕፅዋት ጥናት ተመራማሪዎችም ለይተን እናውቃቸዋለን። እዚህ፣ ተፈጥሮ ለዚህ ስትል መርጣ ያስተመጠችው አንድ ሰው ብቻ አለ»

«መልካም፣ ቢያንስ አንድ ሰው መኖሩም ጥሩ ነው» አለ ጉዳዩን መቋጨት ያልቻለው ቆንሲል ትዕግስት እያጣ። «ስሙን ንገረኝና አሁኑኑ አዲሱን ሥራውን ላስታውቀው»

«ማዳሞዜል ዲ ማይሴ፣ የርስም ልጅ»

ይህን ፈንጂ ካቀበለው በኋላ፣ ፖንሴ ሁለት እርምጃ ወደ ኋላ ተራምዶ ጠበቀ። ቆንሲሉ መናገር ተሣነው።

«የኔ ልጅ?» ሲል ክብሩን በመቀማቱ የተሰማውን ብስጭት በሚገልፅ ቃና «እሷ ማ፣ ዘጠሬሻሞ እንዲህ ካለ ሥራ ፍፁም በላይ ነች»

«ያሁን እንጂ ተፈጥሮ ይህን ችሎታ የሰጠችው ለርስዋ ነው»

«ከዘረተሰብ አስካልፈቀደው ድረስ ተፈጥሮ የሚፈቅደው ነገር ውጤቱ ደካማ ነው፣ ይልቁንስ ይህን ሣጣበህን ተወውና ሌላ ሰው እንድትፈልግ እጠይቅሃለሁ።»

«ለዚህ የሚሆኑ ሰዎች ጨርሶውንም የሉም»

«ይህ ካልሆነ ተክሎችህ ይሞታሉ፣ እኛም ዋጋቸውን እንተካልሃለን»

«የገንዘብ ጉዳይ አይደለም» አለ ጀን ባፕቲስት ክስተር ብሎ፣ ሰላማዊ በሆነና ያመሰፈፈኒት በሌለበት አኳኋን ወደ ቆንሲሉ ቀረብ ብሎ

«አቡቲ እጅግ በጣም አሣሣቢ ስላልሆነ ነገር የተጠየቁ አድርገው ያስቡ። እኔና ሸሪኬ ሄሎኒ ጆሞሮ እንሄዳለን። ቤቱ አናውን ይቀራል። ልጅም፣ በትልቁ መደርደሪያ ላይ ሁለት

ትላልቅ የማስታወሻ ደብተሮች ታገኛለች። በዚያ ውስጥ ሁሉም ነገር በላቲንኛ ተፅፏል። ዕፅዋት የሚፈልጉትን ርሀብና አስደሣች ባህርይ በርስዋ ውስጥ በደመነፍስ ያገኙታል። ሌላው ሁሉ ከዚያ በኋላ ስለራሱ ይጨነቃል።»

«ጥያቄው ተዘግቷል ብዬ ስናገር፣ በዚያው ላይ ሙጭጭ እያልክ መሆንህ ይታየኛል። ልጄ ግን በምንም ሁኔታ አትሄድም»

«ይህ ከሆነ» ብሎ ጆን ባፕቲስት ቱማ አለ። «እኔም አልሄድም፣ በንጉሡ ደዌ ዙሪያ የሚያነፈንፍ ሌላ ሰው ሊፈልጉ ይችላሉ»

«ጌታው! እንዳች አክብሮት ቢኖርህ ይሻላል። የምትናገረው ስለ ንጉሠ ነገሥት ነው»

«አዎን፣ ስለ ንጉሠ ነገስቱና ስለ በሽታቸው፣ ስለመልካም መስተንግዶዎ ስል የተቀበልኩት አደራ ነው»

ጆን ባፕቲስት ከአንገቱ ገበቅ ካለ በኋላ በሩን ከፈተው።

«ፖንሴ» አለ ቆንሲሉ «ይበቃል፣ ሊያዛም ማር ይመራል። ማስፈራራትህ ከመጠን እያለፈ ነው። በሩን ዝጋውና አዳምጠኝ»

ሐኪሙ ከበር ላይ አልተነቀሣቀሰም

«ለአንድ ሣምንት ሙሉ፣ እያንዳንዱን ፍላጐትህን እንድናሟላልህ ግራ ስታጋባን ቆይተሃል። ሁሉም ነገር ደግሞ መጠን አለው። እንዲያው ከልቤ ልንገርህና፣ ካቀረብክልኝ ሃሣብ በስተቀር፣ ስለቤትህ የምትሻውን ዓይነት ማደራጀት ማድረግ ትችላለህ። ያ ሃሣብህ ግን የማይሆን ነው። ከዚህ በኋላ ወደ አቪሲኒያ ትንቀሣቀሣለህ። አለበለዚያ . . . »

«አለበለዚያ ምን?»

«አለበለዚያ አሁኑኑ እንድትታሰር አደርግሃለሁ። በዚህ ከተማ ውስጥ በሚገኙ የአገራችን ዜጐች ላይ ያለኝ ሥልጣን ፍፁም ነው። ይህን ስጠቀም ደግሞ አንዳችም ርህራሄ አላደርግም»

«ታዲያ ስምን አሁኑኑ እንድታሰር አያደርጉም?»

«አትገፋፋኝ!» ሲል ቆንሲሉ ጮኸ

ፖንሴ፣ እጆቹን ለካቴናው እንደዘረጋቸው ናቸው

«ምንድነው የሚጠብቁት?»

የክርክራቸው ድምፅ፣ ሙሴ ማቼንና አባ ዴ ብሪቨይንትን ስላሳሰባቸው፣ ጣልቃ ገብተው ሁለቱንም አቀዘቀዟቸው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፖንሴ ወደ ቤቱ ሄደ። ያቀረበው ሃሣብ የፀና መሆኑንና ዲፕሎማቱ ግን ለሊቱን ሙሉ ሲያስቡበት ሲያድሩ እንደሚችሉ ከመሰናበቱ በፊት ነገረው።

ሙሴ ዴ ማይሴ፣ በዚህ የመጨረሻ ግጭት ተፈታ። ያጋጠመውን ችግር ለፀሃፊው ወይም ለጀስዊቱ ወርውሮላቸው ወደ ክፍሉ ሄደ። ዕረፍት ለማድረግም አሻፈረኝ አለ። ባለቤቱ ወዲያውኑ ደረሰችና አልጋው ላይ ተንጋልሎ፣ ጭንቅላቱ በሁለት ትራሶች ተደግፎ፣ ተዘግሞቶ ስታየው ታጨነቀች። ትንሽ እፎይታ ሲያገኝ፣ ወጣቱ ሰው ያቀረበው ሃሣብ ለንግሥቱ ሰበብ እንደሆነ ተነፈሰላት።

ማዳም ዴ ማይሴ፣ የክብር ወይዘሮ መሆንዋ አጠራጣሪ አይደለም። ከታላቅ ቤተሰብ መወለዷን ልክ ባለቤታ የሚከራበትን ያህል አርሷም ትከራበታለች። ይሁን እንጂ በጣም አስፈላጊ ከሆነውና ተጨማሪ ከሆነው የቱ እንደሚሻል በመለየት ረገድ ሴቶች ከወንዶች ብዙውን ጊዜ የተሻሉ ናቸው። በእርጋታና በብዙ ብልሃት፣ የፖንሴን የመጨረሻውን ጥያቄ ከመቀበልም ይልቅ ቢስማማና ቢቀበለው ፍላጐቱ ብዙም እንደማይጐዳ ነገረችው። መድሃኒት ቀማሚው የማይሄድ ከሆነ ቆንሲሉን እቤቱ ድረስ እየመጣ መፈለጉ ግን አይቀርም። ይህን ተከትሎ የሚመጣው ውስብስብ ሁኔታ የቆንሲሉን ጤንነት ያቃውሰዋል። ሆኖም ግን፣ ሙሴ ማይሴ ሃሣቡን ቢቀበለው ችግሩ በጣም አነስተኛ ይሆናል ወይም እስከነአካቴውም ይጠፋል።

«በርግጥ በዕፅዋትና በመዛፍት የተሞላ መሆኑን ማንም ቢያውቀውም ቤቱ ባዶ ይሆናል። አሊስን ከአባ ጋቦሪ ጋር ወደ ቦታው እየላክናት፣ ዕፅዋት አጥኚ እንደሆነች

በቅድሚያ ቢነገር ሌላ ነገር የሚያስብ ሰው የለም። ለልጃችንም፣ ትንሽ ትንሽ ወጣ ማለት ይጠቅማታል። በዚያውም አካላዊ እንቅስቃሴ ታደርጋለች»

«ይህ እርኩሱ፣ እንዲያውስ በመጀመሪያ ደረጃ እንዴት ሊያስተውሳት ቻለ?» አለ ድንገት ከተኛበት ደንብሮ በመቀመጥ። «በዚህ ቤት ውስጥ ምስጢራዊ ግንኙነት ፈፅመው ሊሆን ይችላል?»

«እንግዲህ ይህን ስታመነዥክ አትዋል። ምን ጣጣ ነው? ልጃችን ጠንካራ ተፈጥሮአዊ ትህትና እንዳላት እኔ እናቷ እመሰክርላታለሁ። ሰውዬው ያነጋገራት አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ለዚያውም እኔ በቦታው ነበርኩ።»

በትንሿ የአትክልት ሥፍራ የነበረውን ሁኔታ በአጭሩ አስታወሰችው።

«እናም» ስትል ማዳም ዴ ማይሌ ቀጠለች። «ስለፅፅዋት አበቀቃቀል ያሳትን ዝንባሌ ያወቀው ያን ጊዜ ነው። ሰውዬው ትክክል መሆኑን ሳረጋግጥልህ እችላለሁ። በአትክልት ማብቀያ ውስጥ ከማበቅላቸው ትንንሽ ዕፅዋት መካከል በሙቀት ወይም በድርቁ ምክንያት ሽምድምድ የሚል ካለ ሁሉም ለአሊስ እሰጣታለሁ። ወደ ክፍሏ ትወስደውና ከጥቂት ቀናት በኋላ አረንጓዴና ጤነኛ ሆኖ መልሳ ትሰጠኛለች።»

ማዳም ዴ ማይሌ፣ በጥሩ ሁኔታ ተከራክራ ባሏን አሳመነችው። ፖንሴ፣ ከጉዞው የመመለስ እድል አይኖረውም ሲል ለራሱ አሰበ። የሰውዬው ሃሣብ ክብር የጐደለውና ሕገወጥ ዕቅድ ቢሆንም፣ ይህን ለማስፈፀም ግን ለምንጊዜውም ዕድሉ አይኖረውም። ይህን የመጨረሻ እንቅፋት በድል በመወጣቱ ሰላምና እርካታ አገኘ። ምንም እንኳ ለዚህ ሁሉ የርሱ ድርሻ ቢኖርበትም፣ ቆንሲሉ፣ ነቢያዊ አሸክሩን በጣም ተራ ማስታወሻ አስይዞ ላከው። «ልጄ፣ ከአባ ጋዕሪ ጋር ሆና ሁልጊዜ ማለዳ በቤትህ ተገኝታ እፅዋትህን ታጠናለች። አሁን ሂድ»

2

ጉዞ ወደ አበሻ ሃገር

በቅድሚያ ቢነገር ሌላ ነገር የሚያስብ ሰው የለም። ለልጃችንም፣ ትንሽ ትንሽ ወጣ ማለት ይጠቅማታል። በዚያውም አካላዊ እንቅስቃሴ ታደርጋለች»

«ይህ እርስዱ፣ እንዲያውስ በመጀመሪያ ደረጃ እንዴት ሲያስተውሳት ቻለ?» አለ ድንገት ከተኛበት ደንብሮ በመቀመጥ። «በዚህ ቤት ውስጥ ምስጢራዊ ግንኙነት ፈፅመው ሊሆን ይችላል?»

«እንግዲህ ይህን ስታመነዥክ አትዋል። ምን ጣጣ ነው? ልጃችን ጠንክራ ተፈጥሮአዊ ትህትና እንዳላት እኔ እናቷ እመሰክርላታለሁ። ሰውዬው ያነጋገራት አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ለዚያውም እኔ በቦታው ነበርኩ።»

በትንሿ የአትክልት ሥፍራ የነበረውን ሁኔታ በአጭሩ አስታወሰችው።

«እናም» ስትል ማዳም ዴ ማይሌ ቀጠለች። «ስለዕፅዋት አበቀቃቀል ያላትን ዝንባሌ ያወቀው ያን ጊዜ ነው። ሰውዬው ትክክል መሆኑን ላረጋግጥልህ እችላለሁ። በአትክልት ማብቀያ ውስጥ ከማበቅላቸው ትንንሽ ዕፅዋት መካከል በሙቀት ወይም በድርቁ ምክንያት ሽምድምድ የሚል ካለ ሁሌም ለአሊስ አሰጣታለሁ። ወደ ክፍሏ ትወሰደውና ከጥቂት ቀናት በኋላ አረንጓዴና ጤነኛ ሆኖ መልሳ ትሰጠኛለች።»

ማዳም ዴ ማይሌ፣ ቦጥሩ ሁኔታ ተከራክራ ባሏን አሳመነችው። ፖንሴ፣ ከንብረቱ የመመለስ እድል አይኖረውም ስል ሰራሱ አሰበ። የሰውዬው ሃኒብ ክብር የጉደለውና ሕገወጥ ዕቅድ ቢሆንም፣ ይህን ለማስፈፀም ግን ለምንጊዜውም ዕድሉ አይኖረውም። ይህን የመጨረሻ እንቅፋት በድል በመወጣቱ ሰላምና እርካታ አገኘ። ምንም እንኳ ለዚህ ሁሉ የርሱ ድርሻ ቢኖርበትም፣ ቆንሲሉ፣ ነብያዊ አሽከሩን በጣም ተራ ማስታወሻ አስይዞ ላከው። «ልጄ፣ ከአባ ጋቦሪ ጋር ሆነ ሁልጊዜ ማለዳ በቤትህ ተገኝታ እፅዋትህን ታጠናለች። አሁን ሂድ»

2

ጉዞ ወደ አበሻ ሃገር

1

ወደ አበሻ አገር የሚጓዘው የፀሐዩ ንጉሥ የመልዕክተኞች ቡድን፣ ሰኞ ከንጋቱ በአሥራ አንድ ሰዓት ላይ ተንቀሣቀሰ። ሃጂ አሊ፣ በመሪው ግመል ላይ ተቀምጧል። ጭንቅላቱን በአዲስ ሻሽ ጠምጥሟል። እርሱን የተከተለው ጆን ባፕቲስት ነው። ጆን ባፕቲስት፣ በአንድ ቁንጥንጥ ፈረስ ላይ ጉብ ብሏል። ነጭ ላባ ያለበት ሰፊ ነጭ ባርኔጣ አድርጓል። በመጨረሻ ያሉት የውሸቱ አሽከር፣ ነገር ግን እውነተኛው ጀስዊት ዮሴፍ፣ ናቸው። ዮሴፍ ከገለባ በተሠራ ባርኔጣ ፊታቸውን ደብቀው፣ በከተማው መግቢያ በር አጠገብ በቅሎአቸው ላይ ተቀምጠው ሲጠብቋቸው አገኟቸው። ከኋላ አምስት የጭነት አጋሰሶች ተከትለዋል። ግመሎችና በቅሎዎች ተደባልቀው ዓዝ ተጭነው፣ ቦጥቂት ነብያውያን ባሮች ይነዷሉ።

ለጥንቃቄ ሲባል ባለፈው ምሽት በቆንስላው ቤት ከተደረገው ሥነስርዓት በስተቀር የመሰነባበቻ ነገር አልተከናወነም። ከሌሎች ጋር ለመገናኘት ሲመጣ ከለሲቱ ዘጠኝ ሰዓት ከመሆኑ ጥቂት ቀደም ብሎ ጆን ባፕቲስት፣ በሰጋሲዮኑ አጥር ሥር አልፏል። ሙሴ ዴ ማይሌና ባለቤቱ ሰገነቱ ላይ ሆነው ምልክት ሰጥተውታል። ይህን ምስኪን ልጅ ሲያዩት እጅግ አዘኑ። ዕጣ ፈንታው ሆኖ፣ በሁሉም መልክ ሲታሰብ ዳግመኛ የማይመለሰው ልጅ፣ በታላቅ ትህትና እንደሚጨነቅላቸውና እንደሚያስባቸው በሚያመላክት መልክ፣ ዓይኖቹ በምሥጋና እምባዎች ተሞልተው ሰላምታ አቀረበላቸው። እውነቱ ግን፣ ጆን ባፕቲስት ሰሁለቱ አላውንት ሸርጣኖች ተጨንቆላቸው ሣይሆን፣ ተስፋ ለሚያደርጋትና ከበስተኋላቸው በሁለተኛው ፎቅ ባለው በእንደኛው በረንዳ ላይ ሆና ለምትመለከተው ለአሊስ ነበረ።

ቀጥሎ የተከናወነው፣ ለቱርክኛ የሚያቀርቡት ረዥምና ሞቅ ያለ የደህና ሁኑ ሰላምታ ነው። ቅፍለቱ አስፈላጊውን የጥበቃ ሁኔታ እንዲያገኝ ያደረገው ፓሻ፣ የግል ሐኪሙ ሰትቶ ሲሄድ አሰቀሰ። ፓሻው፣ ሁልጊዜም የሐኪሙን ትዕዛዝ እንዳከበረ ነው። በዚህም ይደሰታል። ምንም እንኳን በተወሰነ ጊዜ ውስጥ መከታተል የሚገባው ሕክምና መረር የሚል ቢሆንም የአሣራሹ ሥራውን ለማከናወን ድጋሚ ስምምነት አድርሟ ነበር። ሁሴይን የሚባለው ፓሻ ዕድሜው ሃምሣ ዓመት ይሆናል። በነዚህ ዘመናት፣ በእኩል ክባድ መከራና መጠን ያሰፈ የአስረሽ ምችው ሕይወት ውስጥ ዕድሜውን ያገባደደ ሰው ነው። ለርሱ ግብዕ ማለት ደስ

የማትልና ለአንዛዝ የማትመች አገር ነች። በወታደራዊ አንጻዎችና በአገረ ገዥዎች መካከል መቋጫ የሌለው ውስብስብ ችግር እንዳደከመው ነው። ግዴለሽ ሆኖ ሲለነብት የአመፁ መጠን ያድጋል። ባላንጣዎቹ በብልጣብልጥነት ተግባር ሲያታክቱት ጥቂት ደርዘን የሚሆኑት አንገታቸው እንዲቀላ ይወስናል። ለፖንሴ መልካም መሥሪያ ቤት ምስጋና ይግባውና በነዚህ ሁለት ተቃራኒ ሃይሎች መካከል የሚወዛወዘው ችግር ተቀብሯል። በቅርቡ የነበሩት መከሳሳቶችና የሞት ቅጣቶችም ጥቂቶች ነበሩ። እንግዲህ ፖንሴ ለቅቆ ሲሄድ በድጋሚ ይከሰቱ ይሆናል። ይህን ሁሉ ዕድል ፈንታው የወሰነው ስለሆነ ሃላፊነቱ ለማስቆም ሃላፊ የለውም።

የጆን ባፕቲስት ደንበኞች የሆኑ ሃብታም ቱርኮችና አረቦች ገንዘብ አዋጥተው እየሰጡት በቶሉ እንዲመለስላቸው ይፀልያሉ። ድሆችን ለመርዳት አንድም ጊዜ አሻፈረኝ ብሎ አያውቅምና፣ የካይሮ ተራ ነዋሪዎችም በሐኪሙ መሄድ ተጨንቀዋል። አነስ ስንኩላን ለማኞችና ትውት ቤተሰቦች፣ የሃኪሙን መልቀቅ ዜና በመስማታቸው ተስብስበው፣ በጠባቦቹ መንገዶች ላይ ዘሚገኙ የዛፍ ጥላዎች ሥር የተኙትን እስካም ውሾች በመቀስቀስ በፍርሃቷ እየጮሁ ከፊት ለፊታቸው እንዲሮጡ በማድረግ አጀበውት ይዝላሉ። ፊቶቻቸውን በዓይነርግብ የሸፈኑ ሴቶች፣ እንደነገሩ ገለጥ አድርገው ያያሉ። ጆን ባፕቲስት እንደሚመስሉ ቃል ይገባላቸዋል። በመጨረሻ ላይ ግን፣ እግሮቹን አንቀው የያዙት ሰዎች እንዲለቅቁትና ፈጠን ብሎ መንገዱ እንዲችል ይገስፃቸዋል።

በዚህ ስሜታዊ ሁኔታ ብዙ ጠመዝማዛ ጉዳናዎችን በማለፍ መንገደኞቹ ከተማዋን አቋርጠው ወጡ። አስከምሽጉ ግዳግዳ ድረስ በፈረስ ላይ ተቀምጦ የነበረው ሜትር ዝረሚ ለቅፍለቱ በሙሉ ረጋ ያለ የደህና ሁኑ ሰላምታ ሰጠ። ዝግጅት ይደረግ በነበረበት በእያንዳንዱ ቀን ጆን ባፕቲስት፣ ጓደኛው ሃሣቡን ቀይሮ አብሮት ለመጓዝ ወስኖ እንደሆነ ሲጠይቀው፣ ባዚያው በእያንዳንዱ ቀን ዝረሚ በበኩሉ ስለርሱ ከቶውንም እንዳያስብ ይነግረው ነበር። ሆነም ቀረም፣ ሁለቱም ሕይወትን ለተወሰነ ጊዜ እያታለሉ በጋራ እንዲሰሩ ያገናኝቻቸው ሲሆኑ፣ አሁን ደግሞ የየግላቸውን መንገድ ይጓዛሉ። ለዚህም ዕጣ ፈንታ ሲሉ፣ ሌላውን ይለቅቃሉ። ሜትር ዝረሚ የአሣማ ወርች በሚያክለው እጁ፣ የጆን ባፕቲስትን እጅ ለመጨረሻ ጊዜ ሲጨብጠው ያሣየው ስሜት አነስተኛ ነበር። ምናልባት ተጨባብጠው እያሉ፣

እጆቹን የወዘወዘበት ጊዜ ከተሰመደው ይልቅ ረዘም ያለ ሊሆን ቢችልም፣ ሊለቅቀው ግን ቃል አልተነፈሰም።

አነስተኛው ጓድ ከተማዋን ለቅቆ የወጣው በሥጋጃ ሠረዎች በር ነው። የሴፍን በፈርኦኖች የውሃ መውረጃ ቦይ ግንብ ሥር አድፍጦ አገኙት። ይህ ሲሆን ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ይሆናል። ፀሐይዋ ቢጫ ቀለማቷ በድንጋዮች ላይ እያበራች ነው። ቀስ በቀስ ወደ ምዕራብ በተንዘሙ ቁጥር የሰውነታቸው ጥላ ከበስተኋላቸው ባለው መሬት ላይ እየረዘመ፣ እየረዘመ ይሄዳል። የአባይን ወንዝ ከወጣቸው በላይ ራቁታቸውን በሆኑ ሰዎች ቀዛፊነት፣ በሁለት ትላልቅ ጀልባዎች ላይ ተሣፍረው ተሻገሩ። ግመሎቹ ፈርተው ከቃጫ የተሠራውን ለከአቸውን ይጮትቱታል። ብርሃን እየሸሸ ሲሄድና የውሃው መልክም ቀለም መምሰል ሲጀምር፣ መንገደኞቹ ገና ወንዙ መሃል ናቸው። በዚያ ቦታ ሆነው፣ የካይሮን ግራጫ ግዝፈትና የአቶማኖችን የፀሎት መጥሪያ ግንብ፣ በርቀት በወንዙ አንድ ጉን ሲመለከቱት፣ ከበስተኋላቸው ደግሞ በጥቁር አረንጓዴቹ የዘንባባ ዛፎች መጋረጃ ውስጥ፣ አስፊሪውን የፐራሚድ ቁልል ይመለከታሉ። በምሽት ጊዜ መንደር ደረሱ። በጠባቦቹና መግቢያ መውጫቸው በማይታወቁ የሸክላ ቤቶች ውስጥ የዘይት መብራቶች ቢጫ ብርሃናቸው ይፍጫል።

የሃጂ አሊ የአጐት ልጅ፣ በግራር ዛፍ ጥላ ወደ ተዋበውና ወደ ተነጠፈው ግቢው እንዲገቡ ፈቀደላቸው። መኝታቸውንም በቤቱ ጣሪያ ላይ ባለው አርከን እንዲያደርጉም ጋበዛቸው። ካይሮ ከዚህ ቦታ በጣም ሩቅ ነው። ምሽቱም ይበልጥ ጨለማ፣ ቀዝቃዛና ጠፍ ጨረቃ ነበር። በርግጥ ጥሩ እንቅልፍ ወሰዳቸው።

በማግስቱ ከማለዳው ቀደም ብሎ ለቀቁ። በወንዙ ዳርቻ እጅግ ሰፊ፣ እንደሃር ለስላሣና የሚያብረቀርቅ ሜዳ፣ እዚህም እዚያም ጥቁር አራት ማዕዘን እራፊ ጨርቅ የተሰጠፈበት አረንጓዴ ልብስ መስሎ ተዘርግቷል። በሺህዎች የሚቆጠሩ ገበሬዎች ሰብቾ፣ ወይም ጥቂት ደስ የተሰኙ ቡድኖች በነዚህ አዲስ በታረሱ ማሣዎች ላይ በተጋት ይሰራሉ። ሌሎቹ መንገዱን ተከትለው በሬዎቻቸውን ከፊት ለፊት እየነዱ የእርሻ መሣሪያዎቻቸውን በትከሻዎቻቸው ላይ አድርገው ይጓዛሉ። አነስተኛው ቅፍለት፣ ይህን ረዥም ሰም መሬት አቋርጦ በፒራሚዶቹ ጥግ ወዳለው በረሃ ዘለቀ። የማለዳውን ሙቀትና ፀጥታ እየተዝናኑበት፣ የፐራሚዱን ግርጌ በዝግታ አለፉት። ጆን ባፕቲስት፣ ካይሮ ውስጥ በኖረባቸው ዓመታት እዚህ ቦታ አዘውትሮ የመጣው በሃሣብ ለመናወዝ ሲል ነው። የቺዮፕስን ፒራሚድ፣ ከንጋት በፊት ፀሐይ

ከተራሮች ጫፍ ላይ ስትላቀቅ ለማየት ሁለት ጊዜ ወጥቶታል። ስፊኒክስ /አካሉ የአንበሳ፣ ሞንቅላቱ የሰው/ የተባለውን ሲቃረቡ፣ ጆን ባፕቲስት፣ ከቅፍለቱ ሹልክ ብሎ ተሰይቶ በመሄድ፣ ይህን ታላቅና ማራኪ የአሸዋ ድንጋይ ሃውልት ዞረው። ከሐውልቱ አናት ላይ ሲደርስ ፊት ለፊቱ ቆሞ፣ አረቦች እቡ አል ሁልል፣ ወይም የሽብር አባት በማለት የሞት ያህል የሚፈሩት መሆናቸውን አስታወሰ። ጥላ ያጠሳባቸውን የሃውልቱን ዓይኖች ተመልክቶ፦

«ዳግም እንደምንገናኝ ምዬ አረጋግጣለሁ»

ከዚህ በኋላ ቅፍለቱን ለመቀላቀል ጋለበ።

በሚቀጥለው ዕለት ከዋክብትን ጣሪያቸው አድርገው፣ በረሃው፣ ከታረሰው ለም መሬት ጋር በሚዋሰንበት ቦታ ላይ ስልጆቻቸውን ሰብስበው አውላላ ሜዳ ላይ ሲንከባለሉ አደሩ። በሚቀጥሉት ሁለት ሣምንታት የአባይን ሸለቆ ይዘው ወደ ማንፋሉት መንደር ቀስ እያሉ ሲወጡ፣ የተሰመደውን የቅፍለት የጉዞ እንቅስቃሴ ሥርዓት ተከተሉ። ማለዳ፣ ፀሐይ ስትወጣ ይነሣሉ። እግት ላይ የፈላ በጣም ጣፋጭ ሻይ ይጠጣሉ። ጓዛቸውን በእንስሳቱ ላይ ይጭናሉ። ሁመመን ውስጥ ያሉ በሚመስል ሁኔታ ፀጥ ብለው ይጓዛሉ። የሚሠፍሩበትን ቦታ ይመርጣሉ። ሞነት ያራግፋሉ። እራት ይበላሉ፣ ይተኛሉ።

ከአሥራ አራት ቀናት የእግር ጉዞ በኋላ፣ ማንፋሉት ከተማ ደረሱ። ከተማዋ ትልቅ ብትሆንም ከጥርብ ድንጋይ የተሠሩት ቤቶችዋ በጣም አጫጭሮች ስለሆኑና ከመሬት በላይ ከፍ ስለማይሉ፣ የበረሃው ሃ°ድር አካል ይመስላሉ። ማንፋሉት ከተማ ከገቡ በኋላ ግን፣ ተሰፋ አድርገው የሚፈልጉትን ምኞት ያገኛሉ። የቤቱን የሳይኖውን አካል ለተጓዦች ከሚያከራይ አንድ አይሁዳዊ ነጋዴ ላይ ማረፊያ የሚሆናቸውን ቤት ተከራዩ።

አብረውት በመቀላቀል አስከ ነቢያ ድረስ ሊጓዙ የሚችሉትን ትልቅ ቅፍለት ማግኘት የሚችሉት እዚህ ነው። ትልቁ ቅፍለት በቅርብ ጊዜ ውስጥ እንደሚንቀሣቀስ ሃጂ አሊ ያውቃል። ነገር ግን በበረሃ ውስጥ «በቅርብ» የሚለው ቃል ክብዙ ጊዜ ከሚለው አገላለፅ የሚያንሰው በትንሹ ነው። ቀናት አለፉ። ከዛሬ ነገ የሚለው ጥበቃቸውም በዚህ መቀቱ በሚያቃጥል ሐሩር መንደር በዝግታ ቀጠለ።

ከፊት ለፊቱ ሊገጥመው ከሚችለው አደጋ ይልቅ፣ በዚህ ረዥም ጉዞ ላይ የሚያገኛቸው ተጓዳኞቹ ጉዳይ፣ ጆን ባፕቲስትን ይበልጥ አሣሰበው። ሃጂ አሊ፣ እንደግመሉቹ ሁሉ ጭውውት ያበዛል። በአንዲት ትንሽ ሹል ስንጥር እንጨት ጥቁሩን ጥርሱን ሲጮረጥር ሰዓታት ይፈጃል። አንዲት ትንሽ የአሀል ትራፊ ጮርጮሮ ማውጣት ክቻለ አስደንጋጭ የመምጠጥ ድምፅ ያሰማል። ፖንሴ ለሚያቀርብሰት ጥያቄ ሁሉ፣ ይህ የቅፍለት መሪ፣ እግዚአብሔር ሲፈቅድ ይገለፃል፣ እያለ ይመልሣል። ስለጉዞው፣ ስለአበሻ አገር ወይም ስለንጉሠ ነገስቱ አንዳችም መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆን አለ። የኒጋዴው ሁኔታ፣ ጆን ባፕቲስትን ሐኪም ነው ብሎ ባለማመኑ እንደሆነ አረጋገጠ። ፖንሴን ለመውሰድ የተስማማው ቆንስሉ አጥብቆ ማፊት ስላደረገበትና መስማማቱም ጥሩ ምክንያት ስላለው ነው። ይህም ሆኖ ነጋዴው ፖንሴን የሚፈትንበትን አጋጣሚ እየጠበቀ ይመስላል።

ጆን ባፕቲስት፣ ከአባ ብሬቬደንት ጋር ያላቸው ግቡኝነት በመጠኑም ቢሆን አስደሣች እንደሆነ አወቀ። በሃጂ አሊ ፊት የሚሰጣቸው ትዕዛዞች አጫጭሮች ናቸው። ይህንንም ቢሆን ዐይናቹን ማይሰብራቸው ፈፅሞ አያደርገውም። ማንፋሉት ከተማ ውስጥ በሰነበቱባቸውና ብቻቸውን መሆን ሲገደዱ፣ቁሱ ዕፅዋትን እንዲያዩ በማለት ወደ ባላገር ይዟቸው ይወጣል። አንዳንድ ጊዜ በድፍረት ወደ አባይና ወደ ቆላው የደለል ምድር በመሄድ አዳዲስ የሰንበሌጥ ዝርያዎች፣ በየቦዩ ውስጥ ንፁህ የውሃ አረንጓዴዎችን ያገኛሉ። አንዳንድ ጊዜም ወደ በረሃው በመዝለቅ ውሃ የሞላቸው ጣፋጭ ተክሎችን ይሰበስባሉ። እንዲሁም ጊንጦች ርስ በርሳቸው ሲፋለሙ ይመከለታሉ። አባ ዴ ብሬቬደንት፣ በሣይንሱ መስክ ጠንካራ መሠረት እንዳሳቸው ወዲያውኑ መገለፅ ጀመረ። ጆን ባፕቲስት፣ ከአንድ ቱርካዊ ታካሚ የተሰጠውን ከነሃስ የተሠራ ትንሽ የአቅጣጫ ጠቋሚ መሣሪያ በሞነቱ ውስጥ ሸጉጦ አስቀምጧል። እንዲት መጠቀም እንደሚችል ጀስዊቱ አስተምረውታል። ወዲያውኑ፣ በይቅርታ አጠያየቅ ዓይነት ተግባራዊውን ሠርቶ ማሣየት የሥነ ከዋክብት ጭውውታቸውን በምሁራዊ አገላለፅ ጨረሱት። ርስ በርሣቸው የተዋወቁ ሲመስላቸው፣ ሁልጊዜም እንደሚጠቀመብት፣ እጅግ በጣም ትህትና በዘዛበት ሁኔታቸው፦

«ገና ወጣት ሆኜ፣ ከረዥም ዓመታት በፊት፣ የማያቋርጥ እንቅስቃሴ የሚያደርግ አንድ መሣሪያ ፈልስፌ ነበር። አትጣቅ! ነገሩ ትልቅ አልነበረም። ነገር ግን የተፈጥሮ ሣይንስ

ፊላስፎችን ሲበዛ አስደንቋቸው ነበር። ሴላው ቀርቶ የዚህን የመሣሪያ ዓይነት ከአንጨትና ከብረታብረት ሠርቼ ነበር»

ጆን ባፕቲስት የመጓጓት ድምፅ አሰማና ዝርዝሩን እንዲያወጡት ገፋፋቸው።

«ከረዥም ጊዜ በፊት ይመስለኛል። ደህና አድርጌ እንኳ አላስታውሰውም» ሲሉ ቁሱ መለሰ። በመቀጠልም እንደማፈር አሉና።«የሣይንስ አካዳሚ ጋዜጣ ዕቅዶቹን በማተም ክብር አንዳገኝ አድርጐኛል»

እነሀ ሃዘንና ተጣዚ አድቅቋቸው፣ የሥነ-ፊለክ ጥናት ከንቱ ሥራ ነው ብለው ከሚያስቡ የጀስዊት ቄስ ይልቅ፣ ሴላ የተሻለ የጉዞ ጓደኛ ሊታሰብ ይችል ነበር። ነገር ግን በዚህ ሁኔታ ላይ፣ ያለውን መጠቀም ይመረጣል። ያለወዳጅ መኖር የማይችለው ጆን ባፕቲስት፣ ለአባ ብሬቬደንት የራሱን ታሪክ ዘረገፈላቸው። ደንገዝገዝ ሲል የልብ ጓደኛሞች ሆነው፣ ሽሚዞቻቸው በላብ ረዋበው፣ ያገኙትን ዕፅዋትና ነፍሳት በትርጫት ሞልተው ጉን ሰጉን ሆነው ሲመለሱ ይታያሉ። በአንደኛው ትከሻቸው ላይ ባዶ የፍየል ቆዳ ስልቻ አንጠልጥለዋል። ይህ፣ ቀትር ላይ ሁለቱም የሚጠጡትን ውሃ የሚይዙበት ነው። ተመልሰው ሲመጡና ክሎግዋ በዓይን ርቀት ላይ ስትሆን የጌታና የሎሌ ሚናቸውን ይጀምራሉ።

ጆን ባፕቲስት፣ የአባ ብሬቬደንትን የአዕምሮ ብስለትና ችሎታ አወቀ። እነሀ አደጋ የማይችሉ፣ ጨዋ፣ የጤናቸው ሁኔታም ደከማ የሆኑ ሰው፣ ወደ ጉድጓድ ውሃው እየተቻኩሉ የሚሄዱና የሚመለሱ፣ በባልዲው ውሃ ክብደት የተነሣ ቁና ቁና የሚተነፍሱ፣ እንደትል ለሚመለከታቸው ለሃጂ አሊ፣ ወገባቸው እስኪንቋቋ የሚያሥነብሱትን ሲመለከት ይበልጥ ማፈር ጀመረ። ይህን ዓይነት ውርደት እንዴት እንደሚቀበሉም ይገርመዋል። አዕምሮውን ለዘመናት በነፃነት ሲጠቀምበት ለኖረው ሰው ይህ ድርጊታቸው ይበልጥ ያሣፍራል።

ይደርሣል የተባለው ትልቁ ቅፍለት የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ። የገባውን ምክንያት ጨርሶ ሊዘነጋው ስለማይችል፣ ፖንሴ ይበልጥ መስጋት ጀመረ። ይህ ደግሞ እጅግ መጥፎ ውጤት ይኖረዋል።

በሜራሽ ሳይታሰብ በድንገት የተጣለባት አምነት፣ ተግባርና ሃላፊነት፣ አሊስ ዴ ማይሌን እጅግ በጣም አስደነቃት። አባቷ ሁሉንም ነገር በዝርዝር ነገራት። እንዴት ሊሆን ይችላል በሚል ስረዥም ጊዜ ልትረዳው ግትችል ብትቆይም፣ የኋላ ኋላ በደስታ ተሞላች። በማግስቱ፣ የማለዳውን ጊዜ በሙሉ፣ የእጅ መሣሪያዎችዋ የሆኑትን ማኑዋሎችን በማፀዳዳት በየመልካቸው ስትደረድራቸው ቆየች። አንድ ተልዕኮ ይጠበቃታል። ራሷን ችላ አንዳች ነገር አንድታከናውን፣ አንድ ሰው ሃላፊነት ሲሰጣት በምድር ላይ ይህ የመጀመሪያዋ ነው። ፀሎትዋ ሁሉ ተሰምቶላታል። በጠባቡ ክፍሉ ውስጥ እያንዳንዷን እርምጃ ደጋግሞ እንደተመላለሰባት አስረኛ ከምታውቀው ከዚህ የወላጆችዋ ቤት፣ በመጨረሻው ላይ ልትወጣ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ቦታው በማንም ያልተያዘ ስለሆነ የመምራት ዕድልም ይኖራታል። ቦታው እንደ ደን፣ ሥርዓት ባጣ ሁኔታ ውስብስብ ያለ መሆኑን አባቷ ገልያላታል። ይህ ገለፃ የማወቅ ፍላጐትዋን ይበልጥ ነፍስ ዘራበት። ከዚህ ደስታዋ ጋር በርግጥ ፍርሃትም ተሰምቷታል። ተልዕኮዋን በአሸናፊነት ትወጣዋለች? ጠላትነት ካላቸው፣ አጠቃላይ ካልሆኑና ራሣቸውን ለመግደል ዝግጁ ከሚሆኑት ዕፅዋት በስተቀር ከሌሎች ዕቃዎችና ሕይወት ያላቸው ነገሮች ጋር አትፋጠጥም ይሆን? ሊያጋጥማት የሚችለው አደጋ ብዙ እንደሚሆን ስግታ ብትሸበርም፣ በመጨረሻ ግን ልበሙሉነት ተሰማት። ከዚህም ባሻገር ቦታው ሙሉ በሙሉ እንግዳና ባዕድ አይሆንባትም። ቤቱ የጆን ባፕቲስት ፖንሴ ነው። እርሱ በኖረበት ግቢ ውስጥ ልትገባ ነው። በዝምታውና በመሄዱ ቅር ብትሰኝም፣ ትውስታዋ እውነት ሆኖ ከቤቱ ባለቤት ጋር በነበረችበት ጊዜ ይሰማት እንደነበረው፣ አሁንም በተመሣሣይ ስሜት ውስጥ እንደምትሆን ገመተች።

አባ ጋቦሪ፣ በዚህ ሥራ ውስጥ ሣይደለቱ ገቡበት። ቅፍለቱ ካይሮን በለቀቀ ማግስት፣ አሊስን ሄደው አመጧት። ዕፅዋቱ ከዚህ በላይ ጥንቃቄ ሣይደረግላቸው ሲተው አይቻልም። ኮፈኗ ወደ ኋላ የምትተጣጠፈዋን መኪናውን፣ ቆንሲሉ ፈቀደላቸው። ሁለቱም፣ ለጥቂት ደቂቃዎች ንብ ወጡ። በዚያኑ ማለዳ ሙሉ ዴ ማይሌ፣ ሴት ልጁ ከዚህ በኋላ ከአባ ጋቦሪ ጋር በመሆን በመድሣኒት ቀማሚው ሰው አሮጌ ቤት ውስጥ ዕፅዋትና ተክሎችን እንደምትንከባከብ፣ እንግዶችና ጉብኚዎቻቸው ሁሉ እንዲያውቁለት አደረገ። ጉዳዩ ይፋ እንዲሆንና እንክን የሌለው አሠራር ሆኖ እንዲታይ ፈለገ። ፖንሴ ቤት መግቢያ በር ላይ ሲደርሱ ጀስዊቱ፣

መኪናው እንዲቆም አደረጉ። ቁልፍ በእጃቸው ስላለ እውነታውን፣ ምስጢር ማድረግ አልፈለጉም። ወደ መጀመሪያው ክፍል የሚያመራውን በር ሲከፍቱ፣ ሜትር ዝርጋጊ፣ ደህንነቱ የሚጠበቅበት የነበረውን የብቸኝነት ክፍሉን አገኙ። ፕሮቴስታንቱ፣ ክፍሉን ለቅቆ ከመሄዱ በፊት የአልጋ ልብሶቹን አንስቷቸዋል። በየቦታው የተዝረከረኩትን ማህኖችም ወደ አንድ ጐን ሰብስቧቸዋል። በተቻለው መጠን ክፍሉን አዕድቶታል። በክፍሉ መሃል በሚገኝ ጠረጴዛ ላይ፣ አድራሻው ለአባ ጋቦሪ የሆነ ደብዳቤ አገኙ። በክፍሉ ውስጥ ያለው ብርሃን፣ ለደካማው አይናቸው በጣም ደብዛዛ ስለሆነባቸው፣ ደብዳቤውን ልጅቱ እንድታነብላቸው ጠየቋት። ጀስዊቱ፣ በሕይወት ዘመናቸው አንድ ጊዜ ወጣት እንደነበሩ፣ ዛሬ ግን አይደሉምና ወደ ሁለተኛው ፎቅ ለመሄድ ደረጃውን በመውጣት ራሣቸውን እንዳያደክሙ ሃሣብ የሚሰጣቸው ደብዳቤ ነው። ስርሣቸው የሚሆንና ሊፈልጉ ጋደም ሊሉበት የሚችሉበት ረዥም ፎቴ፣ እዚሁ ክፍል ውስጥ የተዘጋጀላቸው መሆኑን ሁሉቱም በአንድ ጥግ በኩል ተመለከቱ። ጥንቃቄና ብልህነት በሚታይበት መልክ፣ ህመምተኛው ቁስ የሚፈልጉበትን፣ በተለይ ያዘጋጁትና መድሃኒት የተሞላበት፣ ከሥሩ የቢንጎ መክፈቻና መዝጊያ የተገጠመለት ትልቅ ደምበኛን አለ። በላይኛው ፎቅ ላይ ለዕፅዋቱ የሚያስፈልጓቸው ጥንቃቄዎችን በተመለከቱ መመሪያዎች የተመዘገቡባቸው ሁለት ትላልቅ መዝገቦችን ማዳሞዚል ታንኛቸዋለች።

ቁስ፣ መድሃኒቱን ቀመስ አድርገው ፈታቸውን ከፊገማታ ጋር አኮሣተሩ።

«ኮምጣጣ ነው እንዴ?» ስትል አሲስ ጠየቀች

«ልጄ ሆይ፣ መድሃኒት ስለሆነ መቀበል ያለብንም እንደመድሃኒትነቱ ነው»

መድሃኒቱ በፈሲም የታዘዘ ባይሆን ኖሮ፣ አባ ጋቦሪ፣ መጠጡ፣ አልኮሆል ነው ብለው ይምሉ ነበር። አንድ ሙሉ ብርጭቆቸውን ከጨለጡ በኋላ በረኽሙ ፎቴ ላይ ጋደም አሉና ተማሪያቸው፣ በላይኛው ፎቅ ላይ ሥራዋን በትጋት እንድትቀጥል መመሪያ ሰጧት።

ከጥቂት ቀናት በፊት፣ አባቷ እንዳዳረገው፣ ደረጃዎቹን ወጥታ ስትጨርስ፣ ጥቅጥቅ ያለ የተክሎች ክምችት ያለበትንና የማይታሰበውን የዕፅዋት ማሣደጊያ ቤት አገኘች። ተክሎቹ፣ እርጥበት አዘሉን ትንፋሻቸውን በለሊት ተንፍሰዋል። በክፍሉ ውስጥ ያለው አየር፣ ሞቃት

ሆኖ ርጥበት ያለው ሲሆን፣ የእንጨት ብስባሽና የደን አበባዎች ሽታ አለው። በጣሪያው ላይ በበቀሉት ዛፎች ውስጥ ያረፉት ወፎች፣ ዒው ዒው የሚሰውን ድምፃቸውን ያሰማሉ።

ወጣቷ ልጃገረድ፣ በየእንጨቱ ቅርንጫፍ ላይ ጣቶችዋን በዝግታ እያሣረፈች፣ በማሠሮች ውስጥ በበቀሉት ዕፅዋት መካከል ባሉት ጠባብ መተላለፊያዎች በዝግታ ተራመደች። በአንድ ጠረጴዛ አጠገብ ደርሣ ከበርፖማዎቹ በአንዱ ላይ ተቀመጠች። ቦታው በርግጥም የተለየ፣ በዙሪያዋ ያለ መስሏት ከሚታሰባትና ከፈጠረው ውጣት ሰው ባህርይና ሁኔታ ጋር የማይመሣሰል ነው። ጣፋጭ በሆነ የቀን ህልም ውስጥ በሰመመን ስትንዝ፣ ጠረጴዛው ላይ ሁለት ወፍራም መዝገቦችን ተመልክታ ነቃች። መዝገቦቹ ተግባሯን አስታወሷት። የመጀመያውን ቅፅ ገለፀችው። ከሃያ ዓመታት በፊት ሆላንድ ውስጥ የታተመና በዕፅዋት አበቃቀል ጥናት ላይ የተደረገ ጥብቅ ስምምነት ያሰበት መፅሃፍ ነው። የመፅሃፉ ውፍረት ሃሞቷን አፈሰሰው። ሙሉ በሙሉ አንብባ እስክትተረጉመው ድረስ ዕፅዋቱ ሞተው ይረግፉ። ይሁን እንጂ የመጀመሪያዎቹን ገፆች ገለጥ፣ ገለጥ ስታደርቻው፣ የገፅ ማስታወሻ ምልክት የመሰሰች ቁራጭ ወረቀት በጠርዝ በኩል ታየቻት። በዚያች ወረቀት ላይ የተፃፈው እንዲህ ይላል። «ሰትልልቆቹ ተክሎች፣ በየቀኑ አንዳንድ ባልዲ ውሃ ስጫቸው። ለትንንሾቹ አንዳንድ ብርጭቆና ግንዶቻቸው ወይም ቅጠሎቻቸው ብዙ ውሃ ሰሚያከማቹት ሁሉ በሣምንት ገማሽ ብርጭቆ አጠጫቸው። ቀን ቀን መስኮቶቹን ሁሉ ክፈቻቸው። ወደ ቤት ስትመለሺ ግን ዝጊያቸው። ሰቀሪዎቹ ዕፅዋት፣ አንቺ ጥሩ ነው የምትይውን ፈፅሚላቸው። ከሁሉም በላይ ግን ልክ ለኔ እንደምታወሪኝ ሁሉ አፅዋቱን አነጋግሪያቸው . . . ጀን ባፕቲስት»

አንብባ ስትጨርስ፣ አሲስ ሣቋን ለቀቀቸው። ይሁን እንጂ፣ የቁሱን ስሜት እንዳትስብ ሰግታ አፏን በእጆቿ ዘጋቸው። ከታችኛው ፎቅ የሚሰማው አንድ አይነት አተነፋፈስ ብቻ ነው። ይህ ማለት፣ አባ ጋቦሪ ተኝተዋል ማለት ነው። ትንሿን ወረቀት አጣጥፋ መደርደሪያው ላይ በሚገኙ ሁለት መፅሀፍት መካከል ደበቀቻቸውና ከፊትዋ የተደቀነውን፣ ቀላሉንና የሚስማማትን ሥራ ከግቡ ለማድረስ በደስታ ጀመረች።

2

የመልዕክተኛው ቡድን ከሄደ ከሁለት ቀን በኋላ፣ ሙሴ ጄ ማይሌ፣ እስክ ቆንሲላው ጽህፈት ቤት ድረስ የመጣ እንግዳ ተቀበለ። ሰውዬው የተለመደ ዓይነት መልክ የሌለው ሲሆን፣ ወንድም ፖስኒል እባላለሁ ብሎ ራሱን አስተዋወቀ።

ወደ ቢሮው ሲገባና ሰውዬውን ሲመለከተው፣ ቆንሲሉ ተንቀጠቀጠ። ሰውዬው፣ ያለጥርጥር የካቦቺን መነኩሴ ነው። በወገቡ ላይ የታጠቀው ገመድና ጀርባው ላይ የተንጠለጠለው ቆብ፣ የካቦቺን መነኩሴነቱን ማያሳስቱ ይናገሩበታል። በለፊው ካባው ውስጥ በመሆኑ፣ ቅርፁን መናገር ቢያቅትም፣ በተከሻው ስፋት፣ በቁመቱ ርዝመትና እጁ ላይ የሚታየው ቅርፊት የመሰለ ቆዳው፣ ለውዬው ለሥራ እንዲንቀሣቀስ የታዘዘ ዛፍ ቆራጭ ያስመስሉታል። በአስፈሪው ቁመናው፣ አራት ማዕዘን በሆነው የራስ ቅሉ ቅርፅ ፣ በሚጠቀለለው ጥቁር ፂሙና የሚያንፀባርቁ ትናንሽ አይኖቹ የተሟላ ሰው ነው። የንግግር ቅላፄው ጫን ያለ የኢጣሊያንኛ ዘዬ ነው። የ«ረ» ን ፊደል ድምፅ ሲያወጣት፣ በአፉ ውስጥ እያንከባለላት ነው። የሱካንዳ ነጋዴ፣ ፎማና ቀይ ሥጋን ለመለየት ሲል በቢላዋው እንደሚቆራርጥና እንደሚሰነጣጥቅ ቃላቱንም በጭካኔ ያወጣቸዋል።

«የማህበረሰባችን መሪ ነኝ» ሲል ለቆንሲሉ ዝቅ ብሎ እጅ እየነሣ ተናገረ።

እንግዳው መነኩሴ፣ ወደ ኢትዮጵያ ንጉስ የተላከውን ኤምባሲ መርቶ እንዲሄድ፣ ሙሴ ጄ ማይሌ የሾመውን ሰው ለማግኘት እንደሚፈልግ ገለፀ።

ቆንሲሉ፣ ስለዚህ ጉዳይ የሚያውቀው አንዳችም ነገር እንደሌለ ለመካድ ሞከረ። መነኩሴው ግን፣ ካባው ውስጥ እጁን ሰድዶ አንድ ወረቀት አወጣና ቆንሲሉ ለፖፑሴ የሰጠውን፣ የፈረንሣይ ግዛተ ዘውድ ማህተም ያረፈበትን የምስጢር ደብዳቤ አንድ አንቀፅ አነበበ። ይህ ውይይት በሚካሄድበት ጊዜ በቦታው የነበረው ሙሴ ማቼ፣ የአለቃው ፊት እንደሞት ሲጠቁር ተመልክቶ፣ ቆንሲሉ ሀሊናውን ሊስት ነው ብሎ አሰበ። ይሁን እንጂ፣ ቆንሲሉ ራሱን ተቆጣጥሮ መነኩሴው ይህን መረጃ ከየት እንዳገኘው ለመጠየቅ ብርታት አገኘ።

«እርስዎ ነምት ቆንሲል፣ እርስዎ ነምት የላኩልን» አለ ካፑቺኑ ያሰቁ ጥርሶቹን በፊገግታ እያሣየ

«እንዲህ ያለ ነገር ጨርሶ ልከላችሁ አላውቅም»

«ፀሐፊው ይመስለኛል። ትርጉሙ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ለአንድ ወንድማችን አመጣው። የለም? ለወንድም ፍራንሲስ ነው። ያውቁት ይሆናል?»

ቆንሲሉ፣ ወደ ማቼ ዞር አሉና በእይታው ገላመጠው። ሊመታው ቢችል ኖሮ፣ ያለማመንታት ያደርገው ነበር። ያጠፋው ጥፋት ይቅርታም የማያሰጥ ነው። ይህን ጥፋተኛ ነብን ሙሉ በሙሉ ሊደመስስለት የሚችል ቅጣት ስለመኖሩም ተጠራጠረ። ቆንሲሉ የደብዳቤው ትርጉም እንዲረጋገጥለት የፈለገው በጀንቲ ችሎታቸው ዕውቅ ናቸው በሚባሉትና ከከተማው በስተኋላ ባለው ቂራ አጠገብ በሚኖሩት የሚሮናይት እምነት ተከታይ መነኩሴ፣ በወንድም ፍራንሲስ ነበር፣ ነገር ግን ይህ ብቃት የሌለው፣ ይህ ጅል ፀሐፊ፣ ጉዳት ለማያስከትለው ሶሪያዊ መነኩሴ ማይሆን ላልተባለው፣ ያውም ለካፑቺን መነኩሴ ነው ደብዳቤውን ያሣየው።

ደስ ባይለውም፣ በመጨረሻው ላይ ሙሴ ማቼ በበኩሉ አመነ። በጳፓሎማሲያዊ ምስጢር አጠባበቁ ረገድም፣ በመሠረታዊነት ያሰበውን ጉዳይ ገለፀ። ቆንሲሉ፣ ለንጉሡ የሚፈውን አፈሲል ደብዳቤ፣ ማይወድ በገድ ከንዛው እንዲተሩ ሳደረጋቸው ለነዚህ ካፑቺኖች መግለጽ ይገባዋል። ሙሴ ጄ ማይሌ፣ የተከናወነውን አማፋሪ አውነታ ተረዳ።

በዚህ መነሸል ሙሴ ማይሌ፣ አሰምሮው ተረጋጋ። አለመግባባቱን ለማስወገድም ቢሆን ወደፊት ጊዜ ይኖራል። አሁን ግን፣ ይህ ባለጌ መነኩሴ የያዘውን ወረቀት እንዲህ አጠንክሮ ወየሮ የሚከራክር ምን ቢፈልግ ይሆን? አውጥቶና አውርዶ ሲያበቃ፣ የፈረንሣይ ንጉሠ ነገሥት፣ ለአበሻው ንጉሥ በዓፉት ደብዳቤ ላይ ጀስዊቶችን አለመጥቀሣቸውን አስታወሰ ገለፀ።

«ይህ ኤምባሲ የተባለው ጉዳይ በጣም ሣሩም ሃሣብ ነው» ሲሉ ወንድም ፖስኒል ቀጠሉ። «የመጣሁት ሊረዳችሁ የሚችል ሃሣብ ይዤ ነው። የእምነታችን ተከታዮች የሆኑት ወንዮሞች፣ በላይኛው ግብፅና ኑቢያም ውስጥ አሉን። ከዚህ በኋላ፣ መነኩሴው፣ ኢትዮጵያን በሚመለከት የርሣቸው የሃይማኖት ማህበር በቀጥታ ምን እንደሚመለከተው ወደ ማስረዳቱ

ገቡ። ጳጳሱ ራሳቸው፣ ካፑቺኖዎች፣ ኢትዮጵያን እንዲለውጡና እንዲያሣምኑ፣ ቅዱስ የሃላፊነት ተልዕኮ ሰጥተዋቸዋል። በርግጥ ከሁለት ሣምንት ከማይበልጥ ጊዜ አካባቢ፣ ቅዱስ አባታችን፣ የፍራንሲስካን ሃይማኖት ማህበር የርሣቸው መልዕክተኛ በመሆን ወደ አቢሲኒያ ደብዳቤ ይዘው እንዲሄዱ በይፋ ሰይመዋቸዋል። በዚህም፣ የጳጳሱን የኢኖሴንት ፲ኛን፣ ለአብነት የሚያበቃ አስመሣይነት፣ ቆንሲሉ ተገነዘቡ። በፈረንሣይ ንጉስ ነገስት ስሚደረገው የጀስዊት ሚሲዮናዊ ጓድ ቡራኬያቸውን ከሰጡ በኋላ፣ በዚያኑ ጊዜ በጮሌያዊ ማጭበርበር ከጀስዊቶች ጋር በቀጥታ ፉክክር ውስጥ ያሉትን የሃይማኖት ማህበር መሪ፣ የራሣቸውን የጳጳስ መልዕክተኛ በማለት ሰይመዋቸዋል። በሌላ አነጋገር፣ ጳጳሱ፣ በመካከላቸው ፍቅር የሌላቸውን ሁለት የሰባኪያን ጓዶች በአንድ አቅጣጫ ልከዋል ማለት ነው።

ይሁን እንጂ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ለመወያየት ጊዜ የለም። ቆንሲሉ፣ ከዚህ በኋላ ሊከተል የሚችለው አደጋ ስለተሰማው ወዲያውኑ ልዩ አፀፋዊ ምላሽ ሰጠ።

«በሰማይ ያለኸው ሃያሉ አምላኬ! ወንድም ፖስኳል፣ ምን ዓይነት አለመታደል ነው! በእርግጥ አቅዳችንን በፀሃፊዬ በኩል አስታውቄዎት ነበር። ነገር ግን ወንድም ፍራንሲስ ምንም ዓይነት መልስ ሣይሰጡን ሲቀሩ፣ በበኩላችንም ስለኤምባሲያችን እውቀና እንጂ ሌላ ምንም ነገር የለም በሚል እንደቀላል ነገር ወሰድነው። በዚህ ኤምባሲ ውስጥ መሣተፍ የምትፈልጉ መሆናችሁን የሚያመላክት አንዳችም ነገር አልነበረም። ሰዎቹ ከሄዱ ሦስት ቀን አለፋቸው። ከዚህ በኋላ እነርሱ ላይ ልንደርስ የምንችልበት አንዳችም ዘዴ የለንም።»

«አዎን፣ አለመታደል ነው» አሉ ወንድም ፖስኳል፣ ጭንቅላታቸውን እየነቀነቁ። «በጥቂት ቀናት ውስጥ ሁለት ዕድሎች አመለጡን። ከአንድ አረባዊ ነጋዴ ጋር አብረው ሊጓዙ ዝግጁ የነበሩ ሁለት ወንድሞች ነበሩን። ነጋዴው ወደዚህ የመጣው፣ ለእሸው ንጉሥ ሐኪሞችን ሊወስድለት በማለት ነበር። አሁን ግን ደብዛው ጠፍቷል።»

«እንዴት ሊሆን ይችላል?» ሙሴ ዴ ማይሌ፣ በሰውነቱ ቀዳዳዎች ሁሉ ላብ እያመነጨ በመደነቅ ጠየቃቸው። «በእርግጥ ቅሬታም ይገባኛል» ቆንሲሉ የማዕናናት ቃላቱን ቀጠለ። የካፑቺኑ መነኩሴ፣የሚናገሩት ጠፍቷቸው፣ እንደነገሩ ጉንበስ በማለት ሠላምታ ሰጥተው፣ ወጥተው ሄዱ።

ሕይወት እንደሆነች በአጋጣሚዎች የተሞላች መሆንዋን ለመቀበል፣ ወንድም ፖስኳል ዝግጁ ነበሩ። ከዚህም ባሻገር፣ በያንዳንዱ የመጨረሻ ሁኔታ በሌሎች ሰዎች የግል ሀይወት ጣልቃ በመግባት ማሣዘን ተገቢ እለመሆኑን የምሥራቅውያንን ባህል ስለሚገነዘቡ ያውቁታል። ይሁንና የመልዕክተኞች ቡድን፣ እጅግ በጥድፊያ ከከተማው የሰቀቀ ይመስላል። ቆንሲሉም፣ በመልካም ታማኝነት ተግባሩን በሚወጣው ሰው ሳቢያ በጣም የታወከና የተረበሸ ይመስላል። የካፑቺኑ መነኩሴ ምርመራቸውን ለመቀጠል ወደ አረቦች መኖሪያ አቀኑ።

መነኩሴው እንደወጡ፣ ሙሴ ማይሌ ወረቀቱን በጫጭቆ ጣለው። ፊቱ በላብ ተበምቆ፣ ሙሴ ማቺ ላይ ሆረበት። ነገር ግን በቁሱ ላይ ሊፈፅመው የማይችለውን እልሁን ሊወጣበት ከመነሳቱ በፊት፣ ፀሐፊው፣ ተሰብሮ እንደሚወድቅ የለውዝ ሽፋን ዓይነት፣ በሣንቃው ወለል ላይ በጉልበቱ ወድቆ ተነጠፈ። ቆንሲሉን፣ በሕይወት ዘመኑ እንዲህ ወድቆ ይቅርታውን የለመነው ሰው የለም። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ የፀሐፊውን የሁለት ወር ደመወዙን ለመያዝ ወሰነ።

በመጨረሻ፣ ትልቁ ቅፍለት ማንፋሱት ደረሰ። ገና ስማይና መሬት ሣይላቀቅ፣ ከተማዋ በእንትልፍ ላይ እያለች ክትት አሉ። ባለፈው ምሽት፣ ትልቁ የገበያ ቦታ፣ ሣራጫ አሸዋ የተበራበትና ጥቂት አጥንታቸው ያገጠጠ ውሾች የሚልከሰከሱበት አና መሬት ነበር። ዛሬ ግሰዳ ደግሞ፣ ከዳር እስከዳር በጠባቂዎቻቸው ሥር ባሉ ግመሎች፣ በገመድ ተቀርቅበው በተሰሩ ጭነቶችና በመጠለያነት እንዲያገለግሉ ሲባል በእንጨት አጠናዎች ላይ በተወጠሩ የጨርቅ ጣቃዎች ምድሩ ተሸፍኗል። ስማያዊ የወታደር ሸኬት የለበሱ፣ በጭንቅላታቸው ላይ ጭምብሣም ያሰሩና የጥምጣሙም ጫፍ እንደ አንገት ልብስ በትከሻቸው ላይ የተለቀቀ ሰዎች፣ እጅግ ብዛው እየተንጫጫ ከቦታ ቦታ ይንቀሣቀሣሉ። የሻይ ማንቆርቆሪያዎች በእሣቱ ላይ ቀጥደዋል። የበግ ጠቦቶች ሥጋ ከሚጠበስበት ምድጃ፣ በቅባቱ ሳቢያ ስማያዊ የሚመስል ጭሣፊም ጭስ፣ በሰው ጭንቅላት ልክ ቡልል ይላል።

ሃሰን አል ቢልቤሲ የሚባለውን የዚህን ትልቅ ቅፍለት መሪ፣ ሃጂ አሊ በሚገባ አውቀዋል። በዚህ ጠንካራ ግንኙነታቸው ሳቢያም አንዳንድ ጉዳዮችን በቶሎ ለመፈፀም

ይችላል። ስለሆነም አምስቱን በቅሎዎቹን በሁለት ግመሎች ሰወጠ። የዚህ ምክንያቱ አንደኛ የግመሎቹ ዋጋ ክካይሮ ይልቅ እዚህ በመጠኑ ስለሚቀንስ፣ ሁለተኛም በቅርቡ ለሚያቋርጣቸው በረሃዎችም ግመሎቹ የተሻሉ ምርጫዎች ስለሆኑ ነው። ይሁን እንጂ፣ እንዳለመታደል ሆኖ ሁለቱ ግመሎች በአምስቱ በቅሎዎች ላይ ያለውን ጭነት ለመሸከም የሚችሉ አይደሉም። ይህን ችግር ለመቋጨት የሚያስችለውን አማራጭ ሃጂ አሊ በአስቀያሚው ፈገግታው አስረዳቸው። ዮሴፍ፣ የሚጓዝበት የጋማ ከብት ከአንግዲህ አይኖረውም። በበረሃው አሸዋ ላይ የመጓዝ ልምድ እንዳላቸው እንደነብያውያኑ፣ እርሱም ከጭነት ከብቶቹ ጋር በእግሩ መራመድ ይኖርበታል።

አባ ብራቬደንት፣ ይህን እጅግ የከፋ ውርደት በትህትና ተቀበሉት። እንዲያውም፣ የጉዞ ጓደኛቸው አንድም ዓይነት ተቃውሞ እንዳያነሣና ጥርጣሬ እንዳይፈጠር፣ ጥንቃቄ ማስፈለጉን በማስገንዘብ እሺ እንዲል አደረጉት። የጀስዊቱ ቄስ፣ ገደብ የለሽ ሽንፈትን ለመቀበል ፈቃደኛና ደስተኛ መሆናቸውን አስተዋለ። በዚህም የተነሣ፣ ሰውዬው ቁም ነገረኛ ናቸው በሚል ሰርግቸው በመጀመሪያ የነበረው የርህራሄ ስሜቱ ተነነበት። ካህኑ ትጋታቸውን በማስመሰልና በትህትና ደባልቀው የያዙ ናቸው። ብራቬደንት፣ ሁልጊዜም ጥንቃቄ የተሞላበት አቋም ይይዛሉ። ከጆን ባፕቲስት ጋር በሚያደርጉት ንግ የሚያገኙት ደስታ ከፍተኛ መሆኑን ቢገልፀም፣ ብዙም ሣይቆይ ገሸሽ እያደረጉት መሆናቸው መታወቅ ጀመረ። ሰውዬው፣ በርግጥ ሊሠሩት የፈለጉት ከእሸሃማ ፍራንታቸው በስተጀርባ ሆነው እምነታቸውን የሚያጠነክርላቸውን መንፈሣዊ እንቅስቃሴ ማከናወን ነው።

የሁለቱ ሰዎች ፊዕሞ አለመመሣሰል ከዕለታት አንድ ቀን በቤት ውስጥ ቡተነግ ጭውውት ላይ ተገለፀ። ጆን ባፕቲስት፣ አሁን ዮሴፍ የተባሉትን ሰው፣ ወደ ክህነት ተግባር እንዴት እንደገቡ ጠየቃቸው። ካህኑም፣ በገራገር የራስ መተማመን ስሜት መልስ ሰጡ።

«በጣም ቀላል ነው። የተወለድኩት ክሃብታምና ሁሉም በእጁ፣ ሁሉም በደጁ ከሆነ ቤተሰብ ነው። ለኔ፣ ሁሉም ነገር በጣም ቀላል ነበር። ማወቅ የቻልኩት ያስተማሩኝን ብቻ ነበር። ሳይንስ በሚባለው ቋንቋ፣ የአፈጣጠር ፍቃድ ያለችግር ተዘጋጅቶ ቀርቦልኝ፣ እግዚአብሔርም፣ ቅዱስ ፈቃዱን በኔ ላይ አዘነበ። ሁሉንም ነገር እርሱ ሰጠኝ። እኔም፣ ሁሉንም ነገር መልሸ ልሰጠው ፈለግሁ»

«እኔ ደግሞ» አለ ጆን ባፕቲስት «በተቃራኒው አቅጣጫ ነኝ። የተወለድኩበት፣ ቤተሰብ አልባ ከሆነና ከድሃ ነው። በስድስት ዓመቴ፣ ለአንድ መድሃኒት ቀማሚ እንዳገለግል ተላክሁ። አንድ ውሻ መንክባልን እንዲማር እንደሚያደርጉት ሁሉ፣ የዚህ የመድሃኒት ቀማሚ ሴት ልጅም ፊደል አስተማሪችኝ። ያገኘሁት ዕውቀት ይኸው ብቻ ነበር። የቀረውን ሁሉ በራሴ ጥረት ተማርኩ። በምችለው ዘዴ ሁሉ መማር ቻልኩ። የርስጆን አባባል ብኩል፣ እግዚአብሔር ምንም አልሰጠኝምና ፅዳ የለብኝም»

ሕግ የጣሰን ተማሪ የሚመስክት ሌላ ተማሪ፣ ቅጣቱን ትጋራለህ ቢባል የሚሰማውን ዓይነት ፍርሃት፣ ጀስዊቱ በመሸበር ስሜት ተመለከቱት። ምንም እንኳ ፖንሴ አውነተኛው ጳያብለሰ ባይሆንም፣ ክመልዕክተኞቹ አንዱ እንደሆነ ገመቱት። ክመጀመሪያ ጀምሮ፣ አባ ዜርግውና ቆንሲሉ፣ ማለቂያ የሌለው ሃይማኖታዊ ማስጠንቀቂያ በጀሮአቸው ውስጥ ሲያንቆቀቁላቸው ስለነበረ፣ መሠረት የሌለው ጥላቻ ተክለውባቸዋል። በዚያኑ ዕለት፣ ጆን ባፕ ተስት ብቻውን መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ ተገነዘበ። ሜትር ዝረሚን እጅግ በጣም ነው ያጣው። ንደኝነቱን፣ ግብዞችን ሁሉ ከአገር እንዲጠፉ የሚያደርገውን ለእውነት ሚቸነቱን፣ ጥርነቱንና እንደልብ የማይጥፍውን የጨዋታ ስዛውን በርግጥ አጥቷቸዋል።

ከሁለት ቀናት በኋላ፣ ቅፍለቱ ማንፋሉትን ሰቀቀ። የጋማ ከብቶቹ ወደ አንድ ሙቶ ሃምሣ ይደርሣሉ። ጉዛው ቀጥ ያለና ረዥም ሠልፍ ሲሆን ሃጂ አሊ፣ ፖንሴና ዮሴፍ በጉዛው መሃል ላይ ናቸው። ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ አንድ አሥር ኪሎ ሜትር ያህል ከተንዙ በኋላ፣ አልነንታራ በተባለ መንደር ሊደርሱ ሠፈሩ። ከዚህ በኋላ የአባይ ቅርንጫፍ ነው የሚባል አነድ ጠባብ የድንጋይ ድልድይ ያለበት የወንዝ ቦይ አቋረጡና፣ በበረሃው ውስጥ ጭንቅላቱና ሆዱ አነባበ በመሸርሸር የተጉዳ፣ የተቀመጠ ፊርኦንን ይወክላል የተባለ ትልቅ የአግርና የመጫሚያው ፍራሽ ያለበት ሃውልት አጠገብ ሠፈሩ። ሰቅፈሰቱ መሪ ውሰታ ምስጋና ይግባውና፣ ሃጂ አሊና ፖንሴ በሃውልቱ የአውራ ጣቶች መካከል ሁለት ውብ ቦታዎችን የኔነው የኔ ነው፣ ለማለት ችለው ነበር። በዚህ እጅግ ታላቅ በሆነው የድንጋይ ክምር መካከል ያለው ገላ ያለ ቦታ ዋሻ መሰል ስለሆነ ከለሲቱ ቅዝቃዜ ይከላከላቸዋል።

ዮሴፍ፣ ለጌቶቻቸው ራታቸውን አዘጋጁላቸው። ሾርባውን እያማሰሉ ባለበት ጊዜ፣ ፖንሴ ከምድጃው አጠገብ ሆኖ አገዛቸው። የጀስዊቱ ካህን ከመቼውም ይልቅ የተጨነቁ ሆነው አገኟቸው።

«ግመል ነጂዎቹን ቀደም ብዬ ነበር የተቀላቀልኳቸው፣ እናም ጥቂቱ ወይይታቸው ጀሮዬ ጥልቅ አለ» አሉ ቁሱ።

«እሺ፣ ምን ነበር የሚሉት?»

«በቅፋስቱ ውስጥ ሌላ ፈረንሣዊ አለ ይላሉ»

«ይህ ታዲያ መልካም ነው» አለ ፖንሴ ላይቆጣና ላይረበሽ። «አውሮፖውያን ነጋዴዎች ወደላይኛው ግብፅ ብዙ ጊዜና እንዲያውም ኑቢያ ድረስ ይጓዛሉ»

የጀስዊቱ ቁስ የባህርይ ሁኔታ ይረብሸው ጀምር። የሚታይባቸው የጥፋተኛነት ስሜት ሁኔታ፣ ባልተቋረጠ መልክ የመጨነቃቸውና ለዛ ማጣታቸው ሁሉ ያበሣጭት ጀመር። ጆን ባፕቲስት በበኩሉም፣ ሰውዬውን በአሽሙር መጮሻምና ግልፅ ማድረግ ጀመረ።

«እንዲህ ባለ ትልቅ ቅፍለት ውስጥ ብቻህን እንደሆንክ አስብ፣ እናም በተንገጮች መካከል ሁለት ሌሎች ክርስቲያኖች እንዳሉ አወቅህ እንበል። ይህ መቼም ተራ ግንዛቤ ነው። ታዲያ ፈጥነህ ልታገኛቸው አትሻም?» ሲሉ አባ ብሬቬደንት አያትረመረሙ ጠየቁት።

«ወደ ምስራቁ ዓለም፣ ማንነታቸው በራሣቸው አገር ሰው እንኳ ላይታወቅ የሚገዙ ዘዋሪዎች ብዙ ናቸው» አለ ጆን ባፕቲስት ትዕግስቱ እያለቀበት

«እንግዲያውስ ይህን የሚባለውን ሰው ሄደን እንፈልገው፣ በዚህም ከኛ ይሸሽ እንደሆነ ወይም የሚደብቀው ነገር እንዳለ እናውቃለን»

በመጨረሻ ላይ ጆን ባፕቲስት ተሸነፈ። መከራከሩ ሰልችቶታል። የእኒህ እርጉም ቁስ ጉተታም፣ እያሸነፈው መጣ። በሠፈሩ ዙሪያ ዞሮ ለማየት ተስማማ። ዮሴፍ፣ ማማሰያ ማንኪያውን ለኑቢያው ሰጡትና እንዳያቃጥለው አስጠነቀቁት። ምሽቱ ከመጋመሱ በፊት

የቀራቸው ጊዜ አጭር በመሆኑ፣ ቅፍለቱም ትልቅ ስለሆነ የሥራ ክፍፍል አደረጉ። ካህኑ፣ በትልቁ የድንጋይ ሃውልት በአንድ ጉን ሲሄዱ፣ ፖንሴ በሌላው ጉን ሄደ። ጨለማው ፈጠነ። ከአድማስ ላይ የተንጠለጠለችው ፀሐይ፣ ቀይ ኪስ መምሰልና በጥቁሩ የበረሃው ክብ የመሬት ቅርፅ ላይ መዘርጋት ጀምራለች። እየሸሸ የሚሄደው ብርሃን፣ ከሰፈሩ በተነሣው አሳራ ሳቢያ፣ የተለያዩ የቀስተ ደመና ቀለሞች ስለተፈጠሩ፣ ወዲያና ወዲህ የሚንቀሣቀሱትን ሰዎች፣ ጭጋጋማ ብርሃን ዙሪያቸውን ከብቧቸዋል። ሁለቱ ሰዎች፣ ጨለማው ለዓይን እስኪስለክል ድረስ ብዙ ቡድኖችን ለመመርመር ቢሞክሩም፣ ፊረንሣዊ የሚመስል ሰው ማግኘት ግን አልቻሉም። አባ ቬርሣው፣ በካፑቼኖች ላይ የሚቃጣ ሴራ እንደሚኖር ስላስጠነቀቋቸውና የነዚህም ሴረኞች ጠረን በዚህም ምስጢራዊ ጉዞ ውስጥ ስለሚሸትት ፈልገው በማጣታቸው ውጤት ላይ እርግጠኛ አልሆኑም።

የሚቀጥሉት ቀናት በጣም አስቸጋሪዎች ነበሩ። አንድም የውሃ ጉድጓድ ሳያገኙ ድንጋያማ በረሃ ማቋረጥ ነበረባቸው። የዮሴፍን ሁኔታ ለተመለከተው የሚሰቀጥጥ ነበር። በከባዱ ሙቀት ሳቢያ እየተንጠራወዙ በያንዳንዱ ዕረፍት በሚደረግበት ቦታ ላይ የተሰነጣጠቁትን ከንፈሮቻቸውን ለማርጠብ በፖንሴ ኮርቻ ሥር ወደተንጠለጠለው የፍየል ቆዳ ስልቻ ያመራሉ። በሁለተኛው ቀን፣ ባለዘለሰቡቱ ጫማቸው ተገንጥሎ በመውደቁ፣ በሚያቃጥለው መንገድ ላይ በባዶ እግራቸው መንገዝ ተገደዱ። በዚህም የተነሣ በአንድ ቀን የውስጥ እግራቸው ከባድ ውሃ ቋጠረ። ፖንሴ ፣ መድሃኒቶቹን የቀረቀረበትን የቆዳ ሻንጣ ከፍቶ፣ የምስኪኑን ሰው እግሮች በመቀባት እብጠቱ እንዲቀንስላቸው፣ ቁስሉቱ እንዲደርቅላቸውና ከሕመማቸውም እፎይታን እንዲያገኙ አደረጋቸው። በማግስቱ፣ ከመኝታቸው ነቅተው መራመድ ሲሞክሩ፣ ገርጥተውና ነፍሣቸውን ስተው ነበር። ይህን የተመለከተው ጆን ባፕቲስት፣ የራሱን ግመል እንዲቀመጡበት ቢጠይቃቸውም፣ ዮሴፍ አንዳቸውም ነገር ሳይሰማቸው አፋቸውን ዘግተው መንገዱን ሁሉ ተጓዙ።

እኒህ ሰው ለታዛዥነት እውነተኛ ፍቅር አላቸው። ሆኖም ግን፣ የነፍሳትን ያህል የሚፈሩት ሌላ ምንም ነገር የለም ሲል ጆን ባፕቲስት አሰበ።

እንደ ዕድል ሆኖ በሚቀጥሉት ጥቂት ሰዓታት ውስጥ ለማየ ደመነ። መቀቱም መለስ አለ። በዚያ አካባቢ ያለው የምድረበዳው ቦታ በደቃቅ አሣራ የተሸፈነ ነው። ይህ ደግሞ ለባዶ እግር ቀለል ይላል። በዚያን ዕለት ምሽት፣ ሃጂ አሊ፣ አሰፈሩበት ቦታ ድረስ መጥቶ፣ ከአንድ ቀን ጉዞ በኋላ አንድ ትልቅ የበረሃ ገነት የሆነ መንደር እንደሚደርሱ፣ በዚያም ብዙ ቀናትን እንደሚስነብቱ ነገራቸው። ከዚህ በኋላ፣ ወደ ቅፍስቱ መሪ ወደ ሃሰን አል ቢልቤሲ ሄደ። ሃሰን አል ቢልቤሲ፣ አንድ የተጐዳ ግመል አርዶ፣ ሥጋው በትልቅ እሣት ላይ እየተቀቀለ ነው።

የሚቀጥለውም ቀን እንዲሁ እጅግ ሞቃት ነበር። ዮሴፍም፣ በድጋሚ እጅግ በጣም ተሰቀዩ። በዚህ ዕለት ምሽት ላይ ጥንታውያኑ፣ ፖርባ የበረሃ ገነት የሚሉት፣ አረቦች ደግሞ

አልዋህ ብለው ከሚጠሩት በታላላቅ የቴምር ዛፎች ተሞልቶ ደን ከሚመስለው መንደር ደረሱ። ይህ ቦታ፣ ግብፅ ግዛት ውስጥ የሚገኝ የመጨረሻው ሩቅ ቦታ ነው። ትንንሽ የቴምር ዛፍ ደኖች አርስ በርሳቸው በቀጫጭን የተክሎች ገመድ እንደ ደሴት ተያይዘውና ተበታትነው፣ በዚህ ደረቅ የአሸት ባህር ላይ ይታያሉ። ቦታው በሙሉ አንድ ትልቅ ከተማን ያክላል። ከጥቁሩ አፈር ውስጥ፣ ብዙ ምንጮች ኩልል ብለው በመፍሰቅ ረዣዥም የሰብል ተክሎችንና ጥቅጥቅ ያሉ ሣሮችን ያጠጣሉ። በአጫጭር የድንጋይ አጥሮች የተከበቡና አይነ ምድር እንዲደርቅ ማድረግ የሚችሉ ሰብሎች፣ የተዘሩባቸው አርሻዎች አሉ። ሃጂ አሊ፣ በባህሉ መሠረት ቋሚ ደንበኛው ወደሆነች አንዲት የአካባቢው ሴት ዘንድ ሄዶ ሰንበተ። ፖንሴ በበኩሉ የሰሌን ክዳንና አልጋ ላይቀር ያለው ጦጀ አገኘ። ግመሎቻቸውን ከአንዲት አነስተኛ ኩሬ አጠጥተው እንዲግጡ ለቀቋቸው። ጀን ባፕቲስት፣ አልጋውን ለሶሴፍ ለቅቆላቸው አርሱ ተንጠልጣዩን አልጋውን በሁለት የተምር ዛፎች ላይ አሠረ።

3

በበረሃው ገነት ውስጥ በነበሩባቸው ሁለት ቀናት መሣል፣ ሃጂ አሊ፣ ከጀን ባፕቲስት ጐን ተቀምጦ ሻይ ሊያፈላለት መፈለጉን ገለፀለት። ረዘም ላለ ጊዜ ሲሳሳቁ ከቆዩ በኋላ፣ ኒጋይሔ፣ ለስፍታ ያህል ወደ ገለባው ጦጀ እንዲመጣ ፈረንሳዊውን ጠየቀው።

ጦጀው ውስጥ ከገቡ በኋላ «እስቲ ተመልከተው» አለ አጂ አሊ።

ከሰፊው ጀኩቱ እጅጌ ውስጥ አንድ ክንዱን አወጣና ክንዱን፣ ተከሻውንና የጀርባውን የላይኛውን ክፍል የበላውን የቆዳውን ቁስል ሊያሣየው ልብሱን ወደ ኋላው አወለቀው።

«ይህን አይነት ህመም ከያዘህ ምን ያህል ጊዜ ይሆንሃል?» ሲል ፖንሴ ጠየቀው።

«ሦስት ዓመት ያህል ይሆነኛል። ህመሙ አንዴ ይጠፋል፣ ደግሞ ይመለሣል»

«ለመሆኑ ታክመዋለህ?»

«ቀንና ማታ፣ ሳላቋርጥ ነዋ። ከዚህ ሊያድኑኝ የሚችሉት ነብዩ ብቻ ናቸው። ነገር ግን የርሣቸውም ዐይኖች ወደ ሌላ መመልከት ሲጀምሩ እኔም እስኪደማ ድረስ እጐደፍረዋለሁ።»

ልብሱን እንዲለብስ ፖንሴ ነገረው። ከጦጀው እንደወጡ፣ ሃጂ አሊ፣ በሻዩ ማንቆርቆሪያ አጠገብ ባለው መቀመጫ ላይ ቦታውን ያዘ። ሃኪሙ፣ በጦጀው በር አጠገብ ወደተከመረው ሻንጣው ሄደና በቡሽ የተከደነ ብልቃጥ አመጣ።

«ሁልጊዜም ጠዋትና ማታ በቁስልህ ላይ ይህን ቀባው። ከሦስት ቀን በኋላ እንደገና እንነጋገርበታለን»

ሃጂ አሊ፣ የሐኪሙን እጆች ማማቸውና ብልቃጡን በጥንቃቄ ተቀብሎ ደስታና ሥራ ተደበላልቀውበት፣ አልባሹ፣ መድሃኒቱን እንዲቀባው ለማድረግ ሄደ።

ትዕይንቱን ክርቀት ሲመለከቱ የነበሩት አባ ብራቬደንት፣ ጆን ባፕቲስት አጠገብ ለመቀመጥ መጡ። ካህኑ ከጥቂት ቀናት በፊት ካጋጠማቸው ሥቃይ ቢያገግሙም፣ ሁኔታቸው ግን አሁንም የሚያጠራጥርና አስፈሪ ነው።

«ይህን ያህል ጊዜ ለምን ቆየ? ከመነሣታችን በፊት ሁኔታውን ሊያሣየን ይችል ነበር» ሲሉ የግመሎችን ጌታ በመጠራጠር እየተመለከቱ አጉረመረሙ።

«መሆን አልነበረበትም። ካይሮን ከመልቀቃችን በፊት የኔ ህክምና ውጤት አልባ ቢሆን ኖሮ፣ ምን ሊሆን እንደሚችል አስቲ ያስቡ። ንጉሡንም ማዳን አይችልም፣ ተብዬ በድፍረት ተነግሮብኝ ገብተውም ይሰረዝ ነበር። አሁን ባለንበት ደረጃ ላይ ግን ፣ ሄጂ አሊ፣ ከፍለነው ራሣችንንም በርሱ ሥር አድርገናል። እዚህ ቢተወን፣ ጥቅመ በአመዛኙ የርሱ ነው?»

ሁለቱም ዝም አሉ። የካህኑ አዕምሮ ከመቼውም በበለጠ በፈጨምተኛ አስተሣሰቦች እንደተወጠረ፣ ጆን ባፕቲስት ገመቱ።

እንደ እውነቱ ከሆነ አባ ዴ ብራቬደንትም ቢሆኑ፣ በጆን ባፕቲስት የሕክምና ችሎታ ላይ እምነት የላቸውም። ዕፅዋትን ለማየት በተዘዙባቸው ጊዜያት የመድሃኒት አዋቂው ችሎታ ምን ያህል ትንሽ እንደሆነ እንዲያዩ አስችሏቸዋል። ጆን ባፕቲስት ግን፣ በምንም ዓይነት የሚወናበድ ሰው አይደለም። «የሥነ-ዕፅዋት ዕውቀት ከመድሃኒት ጋር አንድ ዓይነት ነገር አይደለም። በሕክምና ጥናት የሚፈለገው ትጋት፣ የተፈጥሮ አስተዋይነት፣ ሕይወት ባላቸው ነገሮች መካከል ያለውን የስሜት ቅርርብ መገንዘብ ቋው። በሕክምና ጥናት የሚፈለገው፣ በሕመምተኛው ሰውና እርሱን ሊፈውስ በሚችለው ዕፅ መካከል ያለውን አስፈላጊ ስምምነት ማግኘት የመቻል ጉዳይ ነው»

አኒሀን ጅላጅል ብራቬደንትን በተመለከተ ከሆነ፣ እንደ አስማት አንድ ዘርፍ አድርገው ያስባሉ። እነዚህ በሦስቱ ያሉ ግን እውነት ያልሆኑ ጉዳዮች ዛሬ በሄጂ አሊ ላይ፣ እና ሄ ደግሞ በንጉሡ ላይ ምን ያህል ከባድ ጉዳት እንደሚኖራቸው አያውቁም። ይህን በተመለከተ ወደ ኋላ መመለስ በጣም የዘገየ ጉዳይ ነው። የጂስዊቱ ካህንም ዕጣ ፈንታቸው፣ ለልማት ወይም ለጥፋት ቢሆን ከዚህ እንግዳ ከሆነ የዕፅ ሃኪም ጋር አስተሳስረውታል።

የውይይቱን ርዕስ ለመለወጥና ድባቡም ቀለል እንዲል ለማድረግ በማሰብ፣ ጆን ባፕቲስት፣ ጭውውቱን አል-ዋህ በተባለው በዚህ የበረሃ ንጉት የሆነ መንደር ስም ላይ እንዲያተኩር አደረገ።

«ሥሙ የመጣው አል-ሃዊህ ማለት አየር ከሚለው ይመስለኛል። ስሙ በአካባቢው ካለው ቅዝቃዜና የተምር ቅጠሎች ያለዕረፍት እየተንሻሹ ከሚፈጥሩት ትንፋሽ ሊሆን ይችላል»

ብራቬደንት፣ በሌላ በኩል፣ ሃላዋ ማለት ጣፋጭ ማለት ነው ወደሚለው ትርጉሚ ይበልጥ አደሉ። በቋንቋው ዕድገትና ታሪክ ላይ ያላቸውን ልዩነት አንድ ተወላጅ ሰው እንዲጻፍቸው ወሰኑ።በመጀመሪያ ያገኙዋቸው አንድ ሽማግሌ ሰው ሁለት አሀዮችን ይነዱ ነበር። ቅርጫቶቻቸው በተምር የተሞሉ ሲሆን፣ ከከብቶቹ ጉን እየተራመዱ በትንሽ ዘንግ እንስሳቱን ወጋ ወጋ ያደርጓቸዋል።

አረቦች ቋንቋቸውን ይወድዳሉ። ቋንቋን በሚመለከት፣ በቃላት ላይ የሚነሱ አለመግባባቶችን ሁልጊዜም ያስተናግዳሉ። ሽማግሌው፣ ሁለቱን ተጓዦች እንዳገኟቸው ጭርምትምት ያለው ፊታቸው በታሳቅ ፈገግታ ተዘረጋጋ። ሁለቱ ፈረንሣዊያን፣ የየራሣቸውን አስተያየት በአጭሩ ገለፀላቸው። ሽማግሌው፣ በያዙት ዘንግ የሻምላ ስንዘራን እንደማክሸፍ ዓይነት የብራቬዳንትን ደረት ወጋ አደረጉና

«አይደለም!»

ቀጥለውም ወደ ፖንሴ ዞሩና እርሱም ላይ እንደዚያው ካደረጉ በኋላ «አል-ዋህ» አሉ። ቃሉን በተወላጆች ቅላፄ ተናገሩና እንዲከተሏቸው በዓይናቸው ጠቀሷቸው።

ሽማግሌው እየመሯቸው፣ ጆን ባፕቲስትና ብራቬደንት እየተከተሏቸው፣ ሁለቱ አሀዮች ከኋላ እየተጐተቱ መስኩ በተመነጠረበት ቦታ አቋረጠው አይነ ምድር እንዲደርቅ የሚያደርገው ሰብል ያለበትን ማሣ አልፈው በመታረስ ላይ ያለውን ቦታ አቋርጠው ጥቅጥቅ ያለ ጥቁር አረንጓዴ ቅጠል ያለባቸው የቁጥቋጦዎች ጥሻ ውስጥ ገቡ። ወደ ትንንሾቹ ዛፎች በጠራቸው እያመለከቱ ሦስት ጊዜ ተናገሩ።

«አል-ዋህ!»

ዕው፣ልስልስና አንፀባራቂ ጥቁር አረንጓዴ ቅጠሎች ከጥቂት አሾሆች ጋር ያለው ነው።

«የሙሴ በትር-አልዋህ» አሉ ሽማግሌው

ቀጥሎም ወደ ቁጥቋጦው አመለከቱ

«የካሊድ ኢብን አልዋሊድ በትር-አልዋህ!»

«ኢብን አልዋሊድ ማነው?» ሲሉ አባ ብሬቬደንት በትህትና ጠየቁ።

የቀረበው ጥያቄ፣ የማያረካና የማይምነት መገለጫ በመሆኑ ሽማግሌው ግንባራቸውን ቋጠሩ።

«ታላቅ ጀነራል ነው። ክርስቲያኖችን ደምሳሽ የነበረ» አሉ።

«እውነት?» አሉ ቁሱ ቅር እያላቸው።

«ጥንት እዚህ ቦታ የነበረው ውሃ መራራ ነበር። ካሊድ ኢብን አልዋሊድ በበትሩ ምንጮቹን መታቸው። ከዚያም ውሃው የጠራና ንፁህ ሆነ። አልዋህ!»

ሽማግሌውን አመስግነው ወደ ጉጆው በዝምታ ተመለሱ።

«እና አሁንስ?» አሉ አባ ዴ ብሬቬደንት፣ አጃቢያቸው በሃሣብ ጭልጥ ብሎ መንዙን ሊመለከቱ። «ለመሆኑ ይህች ፕላኔት ምን መሰኪታዊ መልዕክት ታመላክትሳለች?»

ጀን ባፕቲቲስት፣ ግልፅ ያልሆነ ምልክት አሣየ።

ቁጥቋጦው ብቻውን ጠፍቶ፣ ብቻውን እድገ፣ በቆንሲሉ የእትክልት ቦታ ያለው ዓይነት መሆኑን እርግጠኛ ሆነ። ከዚያ ዛፍ ላይ ትንሽ ቅርንጫፍ ቆርጦ ሊወስድ ቀና በማለቱ አሊስን ያገኛት ትዝ ስላለው በሃሣብ ዋለሰ።

ለሁለት ሣምንት ያህል፣ አሊስ በየቀኑ በሣጣቡ ውስጥ ትመጣ ነበር። ሌሎች ሁኔታዎች ሁሉ መልካም የየዕለት ልማዶች መሆን ጀምረዋል። አባ ጋበሪ፣ ጣፋጩን መድሃኒታቸውን ከወሰዱ በኋላ በረኽሙ ሃሩ ላይ ተኝተዋል። አሊስ፣ ከወፎቹና ከዕፅዋቱ ጋር ለማውራት ወደ ፎቁ ወጥታለች። ጀን ባፕቲስት እንደተነበየው፣ እያንዳንዱ ተክል ምን እንደሚፈልግ፣ ትንንሾቹን አይዟችሁ ማለትና የአሸናፊነት ስሜት ያላቸውን የትልልቆቹን ቅርንጫፎች በደመነፍስ ስሜት እየነረዘች ወደኋላ መለስ ታደርጋቸዋለች። የመፃህፍቱን ገፆች ለመገላለጥና በቅርንጫፎቹ ላይ ተንጠልጥለው ያሉትን ሻምላዎች እያመነታችም ቢሆን ለመጨበጥ ጊዜው ነበራት። በተንጠልጣዩ አልጋ ላይ ወጥታ ዝርግትግት ለማለትም አስከመድፈር ደርሣ ነበር። ይሁንና፣ ሁሉም ነገር አለመኖርን የሚናገር ነው። አንዳንድ ጊዜ፣ የጀን ባፕቲስት ዱካ ባለበት ሁሉ በስሜትዋ አርሱ ያለ ይመስላት ነበር። በሌላ ጊዜ ደግሞ ጭንቅላቱ ተቆርጦበት እንደተወሰደበት በድን አካል ክፉኛ ታጣዋለች።

ከቡቱ ጋር ከተሰማመደች ከሁለት ሣምንታት በኋላ፣ በውስጠኛው አደባባይ በሚገኘው አርክን ላይ ሙከራ ማድረግ ጀመረች። ምንም እንኳ መጋረጃዎቹ ሁሉ የተዘጉ ቢሆኑም፣ ሥናልባት ከመስኮቶቹ በስተጀረባ ሆኖ የሚመለከት ሰው ቢኖርና የሆነ አሰቃቂታ ከአባቷ ጀሮ ቢደረስ በማለ ፈራች።

በመጀመሪያ ከአርክኑ ላይ ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ቆየች። ፊት ለፊት ባሉት መስኮቶች በስተጀርባ አንዳችም የሚንሣቀሣቀስ ነገር የሌለ መሰላት። ቀስ በቀስ ድፍረት እያገኘች ስትመጣ፣ በመጨረሻ ላይ ወንበር አውጥታ ማማሹን የማለዳ ሰዓት በደጅ ማሣለፍ ቻለች።

ቅፍለቱ ከሄደ ከአምስተኛው ቀን በኋላ፣ ከመጋረጃዎቹ በአንደኛው በስተጀርባ በኩል አንድ አነስተኛ ድምፅ ስትሰማ እዚያው ነበረች። በፍርሃት ራደች። በኋላም ደነዘዘች። መስኮቱን የሚቧጥጠው ድምፅ እንደነና ተመለሰ። ድምፁ የሚመጣው ከርስዋ ከሦስት ጫማ በላይ ከፍ ከሚለውና ለአርክኑ ቅርብ ከሆነው መስኮት ነው። በቅፅበት መጋረጃዎቹ ሁሉ ግልጥልጥ አሉና አንዲት ሴት ታየች። የደነገጠችው ወጣት፣ አርዳታ ለማግኘት፣ እሪታዋን ልታቀልጠው ስትል፣ ሴትየዋ ጣቶችዋን ከንፈሮችዋ ላይ በማድረግ፣ አሊስ ምንም ዓይነት

ድምፅ እንዳታሰማ አስጠነቀቀቻት። አሊስ፣ ራሷን አረጋጋችና ሁለቱም ሴቶች በዝምታ ርስ በርሳቸው ተያዩ። በመስኮት የታየችው ሴት፣ በዕድሜ በሰል ያለች ነበረች። ሴትዮዋ፣ በርቀት ከሚነኝ የሕይወት ጫፍ የወረደችና በርስዋ ዕድሜ ማንም ሊደርስባት የማይችል መስለሸች። ከአርባ ዓመት በላይ ይሆናታል። ጠንካራና ውብ የገበሬ ሴት ቁመና ያላትና ፊትዋ ሙልት ያለ ነች። ዐይኖችዋ፣ ፈገግታ የተሞሉና ጮላ ጮላ ያሉ ናቸው። ወዲያውኑ፣ በአንድነት መንፈስ ስሜት እንዳየቻት፣ በድሃ ኩራት የአይኖችዋን ብርሃን ሰቀቀችባቸው። ተራ የሆነ ጥቁር ቡኒ የአገልጋይ ልብስ ስለለበሰች፣ ድቡልቡሎቹ ክንዶችዋ፣ ጠንካራዎቹ ትከሻዎችዋና ፍርጥም ያሉት ጡቶችዋ ከቅርጫት ውስጥ ሞልቶ የሚፈስስ ፍሬ ይመስላሉ።

«አይዞሽ ጓደኛሽ ነኝ፣ ጓደኛሽ ነኝ» እያለች በአንድ እጅዋ ምልክት በመስጠት ስታንሾካሽክላት ሌላው እጅዋ ከንፈሮችዋ ላይ እንደተቀመጠ ነበር።

አሊስ፣ አቅሷ መመለሱን ስትመለክት፣ አሁንም ዝት ባለ ድምፅ «ሂጂና ቂሱ ተኝተው እንደሆነ ተመልከቻቸው» አለቻት።

ወጣቲ ልጃገረድም የተነገራትን ፈፀመች።

ወደ ታችኛው ፎቅ ስትወርድ ስለቂሱ እንዴት ማወቅ ቻለች? ስትል በመገረም ራሷን አወዛወዘች።

አባ ጋበሪ በሰላም ያንኮራፋሉ።

«እኩው ወደታች፣ እመጣለሁ» ስትል ሴትዮዋ ተናገረች።

በዚህ ላይ ወጣቲ ልጃገረድ ልትጨቃጨቅ አልፈለገችም። ይልቁንስ፣ ይህች ጠንካራ ሴት በመስኮቱ ላይ በሚያስደንቅ ቅልጥፍና ወጥታ፣ ዱካዋ እንደማይሰማ ድመት አርከኑ ላይ ስትዘልል ተመለከተቻት። ተከረዝ የለሽ ለንደል ጫማ ብታደርግም፣ አሊስ ትረዝማለች። የተጨማደደውን ቀሚስዋን በእጇ መዳፍ አንድ ሁለት ጊዜ ሳብ፣ ሳብ አድርጋ ካስተካከለች በኋላ፣ ወጣቲ ልጃገረድ አጠገብ ደረሰች። የአሊስን ሁለት እጆች በወዳጃዊ ስሜት በመያዝና ወደ ራስዋ ሳብ በማድረግ፣ በአድናቆት ከላይ እስከታች ቃኘቻት።

«እንደተባለውም በርግጥም ቆንጆ ነሽ» አለቻት

አሊስ በንግግሩ አፈረች። እንዲያውም ቀይ ወፍራም አበባ የሆነች መሰላት።

«እርሱ ከተናገረውም የበለጠ ቆንጆ ነሽ» ስትል አከለች።

በሴትዮዋ ፊት ላይ አንዳች የርህራሄና የማዕናናት ሁኔታ ይነበባል። ፈገግታዋ፣ በዓይኖችዋና በከንፈሮችዋ ዙሪያ የሚታዩት የፊት መሸብሸቦች፣ እንባና የመከራ ዘመናት አብረዋት እንደዘለቁ ያመለክታሉ። እንዲህ ንፁህ በሆነው ደስታዋ ላይ እነዚህ ነገሮች ጥልቅ የኅዘቅር ስበት ኃይልን ይጨምራሉ።

«ማነው እሱ?» ስትል ጠየቀች

«ዝረሚ ነዋ! ሌላ ማን ይሆናል» አለች ሴትዮዋ እየሣቀች

ማዳሞዜል ዱ ማይሌ፣ በፊትዋ ላይ የሚነበበውን ቅሬታ መደበት አልቻለችም።

«ሰለዚህ ጉዳይ የነገረችም እርሱ ነው» ስትል ግልፅ ባልሆነ ሁኔታ አከላ ተናገረች።

የአሊስን እጅ ይዛ ወደ አንድ ወንበር ወስዳት እንድትቀመጥ አደረገቻት። እርስዋ ግን ወደ ፎቅ መውጫው ላይ ባለው የደረጃ መደገፊያ ላይ ተደገፈች።

«ባለፉት ሁለት ሣምንታት ስከታተልሽ ነበር። ስለአንቺ ሁሉንም ነገር አውቃለሁ። ስምሽን አውቃለሁ። ከማን ጋር ፍቅር እንደያዘሽም አውቃለሁ። በርግጥ ይህ ንግግሬ ተገቢ አይደለም። ስለራሴ ጥቂት ነገሮችን ልንገርሽ። ስሜ፣ ፍራንቾይዝ ይባላል። የምኖረው እዚህ ቤት ውስጥ ነው። ሁለቱ ጌቶች፣ እዚህ ቤት በነበሩ ጊዜ በየዕለቱ እየመጣሁ ምግባቸውን አዘጋጅላቸው ነበር። ይህ ማረጋገጫ ሊሆንሽ ይችላል?»

«አዎን . . . የለም . . . እኔ እንኳ አላውቅም» አለች አሊስ ግራ ገብቷት።

«በርግጥ ከቀናት በፊት ሳነጋግርሽ ይገባኝ ነበር። ታዲያ ፋይዳ ያለው ሥራ ሳላከናውን፣ እዚሁ ከአስር ጫማ በላይ በማይርቅ ቦታ ሆኜ፣ አንቺን ማየት የሚያስደስተኝ መሰለሽ?»

የፍራንቾይዝ ሃር የመሰለው ጥቁር የፀጉር ክምር በግራና ቀኝ ግንባርዋ ሲወድቅ፣ አንገትዋን መትታ ወደ ቦታው መለሰችው። እጆችዋ በክብድ ሥራ ምክንያት መቅላታቸውን፣ የጣት ጥፍሮችዋ በአጫጭሩ የተቆረጡና የተሰባበሩ መሆናቸውን፣ አሊስ ተመለከተች። ይሁን እንጂ እነዚህ እጆች የሴት እጆች ናቸው። የእጆችዋ ቆዳ፣ የደም ስር ጅማቶችዋን ሙሉ በሙሉ በውበት በመሸፈናቸው፣ ለስላሳና ደስ የሚያሰኙ ናቸው።

«አየሽ፣ ልትረጂኝ ይገባሻል። እኔ እንደሆንኩ የተቀበልኩት ትዕዛዝ አለ። መቼም . . . አንቺ ሁልጊዜም ትዕዛዝ ሳትቀበይ ትችያለሽ። እኔ ግን ቃል ገብቻለሁ።»

«ቃል ገብቻለሁ? ምን ብለሽ ነው ቃል የገባሽው? ደግሞስ ለማን ነው ቃል የገባሽው?» ስትል አሊስ ጠየቀች

«ለዝረሚ ነዋ። እዚህ አርፈሽ መቀመጥ አስክትችይ ድረስ ልጠብቅሽ፣ ቁሱም ፈጥነው ማንቀላፋታቸውን በየቀኑ ለማረጋገጥ፣ ምዬለታለሁ። በነገራችን ላይ ያዘጋጁላቸው መጠጥ አሁንም በበቂ መጠን አለ እንዴ?»

«ግማሽ ያምበጃን ይሆናል አላለሁ»

«ሲያልቅ ሲል መልሼ እንድሞላው አስታውሺኝ»

«በብዛት አለሽ እንዴ?» ስትል የመጠጡ የማለቅ ሁኔታ ለብዙ ቀናት ሲያስጨንቃት የነበረችው አሊስ ጠየቀቻት።

«እስክዘለዓለም ብትፈልጊውም ሞልቷል። ቆንሲሉ አባትሽ፣ በሃያ ፔያስትሪ የሚሸጡልን ዓይነት ተራና መናኛ መጠጥ ነው!»

ፍራንቾይዝ፣ ጭንቅላትዋን ወደ ኋላ ጣል አድርጋ በለሆሣስ ሣቀች። ጥርሶችዋ፣ ችምችም ያሉ፣ እንደሉል የነጡና ሙሉ ናቸው። ወዲያውኑ ኮስተር አለች።

«ይህን ሁሉና እንዲያውም ደብዳቤውንም የምሰጥሽ ከዚህ በኋላ ነው ብዬ ለዝረሚ ቃል ገብቼለታለሁ።»

«ደብዳቤ!» አሊስ በሣቅ ፈነዳች

ምኑንም ነገር ልትረዳ አልቻለችም። ዝረሚ? ደብዳቤ? እንዲያውም ፍርሃት፣ ፍርሃት ይላት ጀመር።

በታችኛው ፎቅ ውስጥ ከተኙት ለው የሚመጣ ድምፅ እንዳለ ለማዳመጥ እንዲችሉ፣ ዝም እንድትል ፍራንቾይዝ አደረገቻት። የሚያዳምጡት ምንም ነገር ባለመኖሩ፣ ልጃገረዲቱም በመጓጓት የምትጠብቀው ነገር መኖሩን በመረዳት፣ ፍራንቾይዝ አጀችዋን ወደ ቀሚሷ ውስጥ ከትታ አንድ ፖስታ አወጣች።

«ምን ያህል ጓጉተሻል? አንቺው! እዚህ ቦታ ላለፉት ሁለት ሣምንቶች በትዕግስት ስትጠብቂ ሰንብተሻል። ከእንግዲህ በኋላ ጥቂት ተጨማሪ ጊዜያትን ማቆየት የሚበዛም ይመስለኛል! አንቺ ተቀበይኝ»

አሊስ፣ ደብዳቤውን እንደመንጠቅ ዓይነት አድርጋ ወደሰችውና አነበበችው። «ለማዳም ሞዜል ዴ ማይሌ፣» ከመጀመሪያው ዕለት አንስቶ ደጋግማ፣ ደጋግማ ስታነብበው የነበረውን የጀን ባፕቲስትን ማስታወሻ ዓይነት የብዕር አጣጣል ነው።

4

ከሦስት ቀን በኋላ ረሻሙ የቅፍለት ሰልፍ እንደገና በዝግታ ጀመረ። ራቅ እያለ ወደ ደቡብ በተዘረጉት ምድሮች ባሉት አገሮች የቀኑ ሐሩር ከባድ ነው። በዚህ ወቀት፣ ጨረቃ በምድረበዳው ላይ የሰሊት ተረኛ መሆን ስለጀመረች በለሊት ለመንዝ ውሣኔ ተደረገ። ቅፍለቱ ንዛውን የሚጀምረው ከሰዓት በኋላ ፀሐይ መጥለቅ ስትጀምር ይሆናል። የውሃ ጉድጓዶች መጠንም እጅግ ስለሚቀንስ የውሃ ዕደላውም ሊያንስ ይችላል። ለስምንት ቀናት የሚበቃቸውን ምግብ ይይዛሉ። ግመሎቹ የመጨረሻውን የጭነት ክብደት ስለተሸከሙ፣ በመጨረሻ ላይ ዮሴፍ አንድ ጀንያ እንዲሸከሙ ተሰጣቸው።

ሃጂ አሊ፣ በግልፅ የማያስታውቅ አስተያየት ጀመረ። ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየተመላለሰ የቅፍለቱን ጭነቶች ይመለከታል። ትዕዛዞችን እየጮኸ ያስተላላፋል፣ በአለንጋው ሾጥ ያደርጋል። በቀጥታ በፖንሴ ፊት ብዙ ጊዜ ቢመላለስም ሰቁስሉ የተሰጠው ህክምና መሥራት አለመሥራቱን ግን የመግለፅ አዝማሚያ አላሣየም። ፊረንሣዊው ሰው ግን፣ የተባለው ሦስት ቀን ሣያልፍ በፊት አንዳችም ጥያቄ ላለማቅረብ ታቀበ።

ቅፍለቱ እንቅስቃሴውን ጀመረ። ለስለስ ባለው የምሽት አየር በዝግታ መንዝ ቀጠለ። ጨረቃ የብርሃን ብናኟን በነገሮች ሁሉ ላይ እያሣረፈች ጨለማውን ስለምትገፍፍ፣ እፎይታን ትሰጣለች። የሚወዛወዙት ግመሎች፣ በዝምታ ተመስጠው የሚራመዱት ሰዎች፣ በአሸዋው ላይ የሚሰሙት በመቶዎች የሚቆጠሩ የታፊኑ የእግር ዱካ ድምፆች ስሜትን በሚያሳጉ መልክ ያባብሳሉ። በአጠቃላይ በእንቅልፍ ላለመውደቅ ከባድ ጥረትን ይጠይቃሉ።

ጉጋት ላይ፣ በስተግራቸው ያለው ሰማይ በሣምራዊ ብርሃን መሞላት ሲጀምር፣ የመጀመሪያውን የውሀ ጉድጓድ ቦታ ደረሱና ጭነቶችን አራግፈው ሰፈሩ። ይህ ቦታ የበረሃ ገኖት ሣይሆን፣ ጥቂት ዛፎች ያሉበት፣ በብርማ አብረቅራቂ ሰፈፍ ተሸፍኖ፣ ክፉኛ የሚሸት የጉድጓድ ውሃ ያለበት ነው። ሰፈፉ ተገፍፎ የሚነሣበት የተበከለ ነገር ያለበት ሲሆን ጣዕሙም የሚቀፍፍ ነው። ሰዎቹ፣ ጭንቅላቶቻቸውንና ፊቶቻቸውን በዚሁ ውሃ አቀዘቀዙ። በአዕምሮው ውስጥ ራሱን ለማጥፋት ለረዥም ጊዜ ሲያሰላስል የኖረ ሰው ካልሆነ በስተቀር፣ በውሃ ጥማት ምክንያት ይህንን ጠጥቶ ለመሞት የሚፈልግ ሰው አይኖርም።

ሃጂ አሊ፣ ሕክምና ካገኘ ሦስተኛውን ቀን እንዳይደርስ የለምና ደረሰ። ደርሶም አለፈ። ሠፈር ከተቆረቆረ በኋላ ሃጂ አሊ፣ በጥልቅ ስሜትና ኦስተር ባለ ሁኔታ በፖንሴ ፊት አልፎ ከማለዳው ፀሎት በፊት ፊቶቻቸውንና እጆቻቸውን ሰመታጠብ በጉድጓድ ውሃ አጠገብ ከተሰበሰቡት ሰዎች ጋር ተደባለቀ። ሰዎቹ፣ ደረቶቻቸውና ጭንቅላቶቻቸው እርቃናቸውን ናቸው። ሃጂ አሊ፣ በቀስታ እንደ ሰዎቹ አደረገ። ሰፊውን ሱሪውን እንደለበሰ ቢሆንም ጫማዎቹን ግን አወለቃቸው። ውሃ ቀድቶ በራሱ ላይ ከለበሰ። ለውኑን አሻሽና ምራቁን ተፋ። ጃኬቱንና ጥምጣሙን በአንድ እጁ፣ ጫማዎቹን በሌላው ይዘ ፖንሴ ፊት ቀረበ። ሕክምና የተደረገበት ቦታ በሙሉ መዳኑንና በጥቂት ቀናት ውስጥ ጨርሶ ሊጠፋ የሚችል ትንሽ ቅርፊት መሰል ነገር መኖሩን ዶክተሩ ተመለከተ። በሽታው ጠፍቷል። ሃጂ አሊ፣ በአክብሮት ለጆን ባፕቲስት ዝቅ ብሎ ሰላምታ አቀረበና ጃኬቱን አጥልቆ ፀጥ ያለ ቦታ በመምረጥ የመስገጃ ምንጣፉን ዘረጋ።

ሁሉንም ድርጊት ሲመለከቱ የነበሩት ዮሴፍ፣ በድብቅ በመስቀል ምልክት ሠርተው አማተቡ።

«ሃያሉ አምላክ! ይህ ተአምር ነው!»

የተሰበሰው አስተያየት ችሎታውን ዝቅ ያደረገበት ስለመሰለው ጆን ባፕቲስት ቅር ተሰኘ።

«ሥልጣን ሰመያዝ ሲሉ በምስጢር የሚደራጁ ጥቂት ቡድኖች ምን እንደሚሉ ያውቃሉ? በተአምራት የሚያምን ጅል ነው ይላሉ» ሲል ተናገረ።

አባ ብሬዘደንት፣ መራት መራት አዩ። «የማያምን ደግሞ ከሃዲ ነው። ዛሬ ማታ መንገዳችንን እንደገና ስንቀጥል በዚህ ጉዳይ ላይ በተመስጠ ሊያስቡበት ይችላሉ» አለችው

የሚቀጥሉት ቀኖችና ምሽቶችም በተመሣሣይ ሁኔታ አለፉ። የበረሃው መርከብ፣ ጭር ያለውን ምድረ በዳ ፈጥኖ ለማቋረጥ መነሳስ ጀመረ። በዚያ ቅልጥጥ ባለ የምድር ገፅ መሃል ከመሰረታቸው የቆዳ ድንኳኖች ሌላ አንዳችም መጠለያ ሣይኖራቸው ብዙ ጊዜ ተኝተው አሳርፈዋል። በጨርቅ ድንኳኖች ውስጥ ያለው መሞቱ የምድኃ ያህል ነው። በማነፃፀር ከታየ፣ ንዛዛው ጉና ሊጀምርና በእንቅስቃሴ ላይ ሊኖን ካለው ጊዜ ይልቅ፣ አሁን የዕረፍቱ ሰዓት ይበልጥ የሚለሰተጥጥ ነው። ምክንያቱም፣ ቢያንስ፣ ቢያንስ፣ በምሽቱ ጊዜ የምሽቱን ቅዝቃዜ

ይረከብታል። ንፁህና ጥሩ የሆነ ሌላ የውሃ ጉድጓድ ዘንድ ሲደርሱ የስልቻ ቀርበታቸውን ሞሉ።

የጆን ባፕቲስትን የሕክምና ችሎታ ከፈተነና ካረጋገጠ በኋላ፣ ሃጂ፣ ይበልጥ ያከብረው ጀመር። አሁንም ቢሆን ሰፍላፊና ወሬኛ የጉዞ ጓደኛ ባይሆንም፣ ፈረንሣዊው ስውዱ ለሚያቀርብለት ጥያቄ ሁሉ በፈቃደኝነት መልስ መስጠትና እንዲያውም ይጠቅመው ይሆናል በሚልም የሚገምታቸውን መረጃዎች ይነግረው ጀመር። ከዕለታት አንድ ቀን፣ የዕለቱን ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት ሃጂ አሊ ወደ ፖንሴ ዘንድ መጣ።

«እስከ አል-ዋህ ድረስ ሌላ ፈረንሣዊ በቅፍለቱ ውስጥ ነበረ። ለመሆኑ ይህን ታውቅ ኖሯል?»

«ሊወራ ሰምተናል እንጂ አላየነውም፣ ለመሆኑ ማን ነበር?»

«አላወቅነውም። አሁንም ከኛ ሁለት ቀን ቀድሞን ሄዷል»

«ከማን ጋር ነው የሚጓዘው?»

«በግመል ላይ ተቀምጦ ነው የሚጓዘው። አንድ ሰው ተከትሎታል። ሰውዬው ብቻውን ነው»

ግመል ነጅው እንደሄደ፣ ዮሴፍ ስለዜናው ለመጠየቅ መጡ። በከፊል በአዘኔታ፣ በከፊል ደግሞ የጀስዊቱን ተስፋ መቁረጥ ለማስወገድ በማሰብ፣ ጆን ባፕቲስት፣ ሁሉም ነገር መልካም መሆኑን ነገራቸው።

አድካሚ የሆኑ ብዙ የዕረፍት ቀናት ቀጠሉ። ለአይን በምታጥበረበረው ሙሉ ደማቅ ጨረቃ ውስጥ፣ ዝምተኛና አሰልቺ የጉዞ ምሽቶችም ቀጠሉ። በመጨረሻም የምድረ በዳውን ደጋማና ሚጻማ ምድር ወጡ። ይህን ሰፊ ምድር ከወጡ በኋላ ክበስተግርጌአቸው በምሽት ከምድሩ ላይ በተነሣው የጭጋግ ሻሽ የተጀቦነውን የአባይን ሸለቆ ፀሐይ ስትወጣ አገኙት። ወንዙ በሚጠማዘዝበት ቦታ ላይ አንድ ትልቅ ከተማ አለ። አሜጭር ሆነው ችምችም ያሉት የሸክላ ቤቶች ፣ አረንጓዴ በለበሱ አደባባዮችና በታላላቅ የፀሎት መጥሪያ ግንቦቹ የተሞላ ነው። በታችኛው ግብፅ ከሚታየው ጦር መሰል ሾጣጣ የአቶማን ግንብ ይልቅ ይህ ፈፅሞ የተለየ

ነው። የደረሱበት ከተማ ዶንጉሱ የሚባልና በሲናር ግዛት ዘውድ ውስጥ የሚገኝ የመጀመሪያው ከተማ ነው። ቅፍለቱ ከከተማው መግቢያ ውጭ ቆመ። ሃጂ አሲና ፖንሴ በቀትር ላይ ወደ ከተማው ዘለቁ። የዶክተሩ አሽከር በሰዓት እርምጃ ወደ ኋላ ቀርቶ ይከተሳቸዋል። በሲናር ንጉስ ስም፣ ከተማውን በመግዛት ላይ ለሚገኘው ሃላፊ ያመጡትን የድጋፍ ደብዳቤና ስጦታ አቀረቡ።

በብሩህ ጨርቅ በተሠራው ዘፋኑ ላይ የተቀመጠው ሰዕይታ የማይሞላ አጭርና ለንቋሣ ሰው ነው። አንግዶቹን በጋሰ ስሜት ከተቀበላቸው ቦኋላ ፖንሴ መልካም ፈቃዱ ሆኖ ዓይነስውር በመሆን ላይ የምትገኘውን የአሥራ አንድ ዓመት ሴት ልጁን ያክምለት እንደሆነ ጠየቀው። ወጣቷ ልዕልት ተጠርታ ስትመጣ፣ የትም ቦታ ተከትላት የምትሠር የሴት አገልጋይዋን እጅ ይዛ ነበር። የህፃንዋ ዐይኖች ደስ በማይል በዚጫ ነገር ተጣብቆ የተሸፈነ ነበር። አንዳንድ ጊዜ በተሰይም ሌሊት የህፃንዋ እጆች ወደ ኋላ ታስረው ማደር ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም፣ የዓይኖችዋን ቅንድቦች ስትነካቸው ይህ የሚፈስሰው ቢጫ መግል ይፋስስበታል፣ ሲል አገረ ገሸው አብራራ። ጆን ባፕቲስት፣ የመድሃኒት ሻንጣውን እንዲያመጡለት ዮሴፍን አዘዞቸው። ሻንጣው ሲመጣለት፣ ቀይ ዱቄት አወጣና ይህ በተወሰነ ንፁህ ውሃ ውስጥ ተበጥብጦ የልጅቱ ዓይኖች፣ በቀን ሦስት ጊዜ በዚሁ መድሃኒት እንዲታጠቡና ሌሊት ግን የኖኖ ባዙቶ እንዲመጠው እንዲያስሩላት አዘዘ።

በሚቀጥለው ማለዳ የልጅቱ ዓይኖች ደረቅ ሆኑ። ከሰባት ቀናት በኋላ ዓይኖችዋን ያለችግር ልትገልጣቸው ስለቻለች ብርሃኗ ተመለሰላት። አገረ-ገሸው በደስታ የሚያደርገው ጠፋው። ለፖንሴም፣ እርሱ ጠይቆት የማይፈቅድለት ምንም ነገር እንደሌለ ነገረው። ፖንሴ በዘዙሉ የአገረ-ገሸውን ጥበቃ ብቻ እንደሚፈልግ መለሰ። ደንጉሱ በቆዩበት አንድ ሣምንት ጊዜ ውስጥ፣ ቤታላቅ ክብር፣ መስተንግዶና በቤተመንግሥቱ ውስጥ ማረፊያ ተሰጥቷቸው ነው። የድኩላ የኋላ እግርና የአልዋዲጊሣ ፍርምባ ተጋብዘዋል። ወቅቱ ባለመሆኑ ንጉሡ አያዘነ፣ የጉማሬ ጉንጭም ተሰጥቷቸዋል።

ፖንሴ፣ ከታላላቆቹ መሣፍንትና ቤተሰቦቻቸው የመጡ ብዙ ህመምተኞችን እንዲያክም ተጋብዶ ነበር። አገረ-ገሸው፣ ለርሱ ፈረስ፣ ለአሽከሩ ደግሞ አህያ እንዲገዝራቸው አቅርባላቸው በዚህ ሳቢያ ሁለቱ ፈረንሣውያን ይህን በተለየ ሰም የሆነውን የሸለቆ ክፍል

ለማየትና ለማድነቅ ቻሉ። በዚህ አካባቢ የወንዙ ጻርቻ መሬት ከውሃው ወለል በላይ ከሁለትና ከሶስት ጫማ የበለጠ አይረዝምም። መሬቱም በግብፅ እንደሚሆነው በየዓመቱ በጉርፍ አይጥለቀለቅም። ሰዎች በሰሩት የማያቋርጥ መዘውር በግድቦቻቸውና በቦዮቻቸው ተጠቅመው ሰብሎቻቸው በመስኖ ይለማሉ። ወደ ቤተመንግስት እንደተመለሱ አገረ ገዥው በግብርና ላይ ስላለው እቅድና አውራጃውን በትክክል በማስተዳዳሩ መደነቁን በማከል ፖንሴ ገለፀ።

«ከተማዋን ልትንከባከባት ከፈለግህ ያንተው ናት። እዚህ ሃኪም ሆነህ መኖር ትችላለህ። ነገውኑ ሸለቆው ውስጥ ሃያ ኤከር መሬትና በዚያ ላይ የሚሠሩ ሰላሣ ቤተሰቦችን እሰጥሃለሁ። ከተማው ውስጥም ቤት፣ በግመሎችና በአረብ ፈረሶች የተሞላ ጋጣም ይኖርሃል። እመነኝ ደስተኛ ትሆናለህ።»

ሃጂ አሊ፣ ጠቃሚ ሰው መሆኑን በድጋሚ አስመሰከረ። በትህትና፣ ለአገረ ገዥው፣ ይህ ፈረንሣዊ የአበሻውን ንጉስ ሊጉበኝ እንደሚጓዝ ገልፆ ለተደረገላቸው ታላቅ መስተንግዶና ስጦታ ሊመሰሱ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ገለፀ። የአባይ ሰዎች አበሻዎችን የውሃ ጌቶች አድርገው ያስቧቸዋል። የውሃውን መነሻ ስለሚቆጣጠሩት የፍስት አቅጣጫውን ሊለውጡት ወይም አስከናካቴው ሊያደርቁት ይችላሉ ብለው ይገምታሉ። «የውሃዎችን አባት» ማበቃጣት የሚታሰብ ነገር አይደለም። ስለዚህም አገረ-ገዥው ዝቅ ብሎ እጅ ነሣ።

በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ፣ ከፖንሴ ታካሚዎች የሚሰማው ዜና እጅግ በጣም ጥሩ ነበር። ቤያንዳንዱ ቀን የማይታመን ማገገምና መዳን ይሰማል። እባ ብሬቬደንት እያጉረመረሙም ቢሆን፣ ምንፖ ምንም ይሁን ምን፣ ይህ ውጣት የማዳን አቅም እንዳለው አምነው ተቀበሉ። የሌሎችን ሰዎች ስቃይ በጥንቃቄ ለመመርመርና ለመፈተሽ፣ ብሎም ለመፈወስ ችሎታው አለው። ከሰዎች ጋር ያለው መግባባትና መቀራረብም ፍፁም ንፁህ መልክ ያለው ነው። ህፃን ልጅን ሊመለከት፣ በልጁ ውስጥ ፈገግታ ይጫራል። እንስሳት ላይቀሩ፣ የርሱ በዙሪያቸው መኖሩት ርጋታን የሚሰጣቸው ይመስላል። በመንገድ ላይ የሚወጡና ሰዎችን በሩቅ የሚሸሹ አሰቀያሚና አስፈሪ እከካም ውሾች፣ መግቢቸውም ባያውቅ በደመነፍስ ከተማው ውስጥ ይከተሉታል። እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ሁሉ ጋር ያለው ንብበኑትና ስምምነት ከጥብቁና ከክባዱ ብሎ ካለው ቅዱስ አግናጢዮስ ይልቅ ከሞኖሞሮች የቅዱስ ፍራንሲስካ ተከታዮቹ አስተሳሰብ ጋር እጅግ ይመሣሰላል። ጀስዊቶች፣ እንዲህ ያለውን የልጅ ቂላቂልነት በርግጥ

አያደንቁም። በሌላ በኩል የፖንሴ ስጦታዎች እንደ አካባቢው ቋንቋዎችና እምነቶች አንዳችም ዓለማን እንደማያገለግል የእውነተኛውን እምነት ምክንያቶች ግን በምስጢር ለማሣከት የሚጠቅም ዓይነት ነው። ፖንሴ፣ ወደ አቢሲኒያ የሚያስገባውን እጅግ ድንቅ ፖስፖርት አስገኝቷል። ብሬቬደንት ደግሞ ከዚህ የሚገኘውን ጥቅም በሚገባ መጠቀም ይኖርባቸዋል።

በመጨረሻ የሚለቅቁበትና የሚሄዱበት ሁኔታ ተስተካክሎ ተዘጋጀ። ለመጨረሻው ስንበት በአንድ ቦታ ላይ ለምሽት ግብዣ ተጠሩ። ቅፍለቱ እስሚቀጥለው ማለዳ አይንቀሳቀስም። ምክንያቱም በአጐራባች አገሮች ሊገጥማቸው የሚችለውን አደጋ በመፍራት፣ ጉዟቸው በቀን እንዲሆን ወስነዋል።

በበሩ ላይ የመሏጠጥ አይነት ድምፅ በሚሰማበት ጊዜ ፖንሴ በክፍሉ ውስጥ ዕረፍት ላይ ነበር። ምናልባት ከተማ ውስጥ አንድ የታመመን ሰው እንዲመለከት ሊሰምነው መልዕክተኛ መጥቶ ይሆናል። ማን እንደሆነ ለመለየት ብቅ ሲል ፀጉሩን የተላጨ በአፍንጫው ላይ ንፍጡ የሚወርድበት፣ ግማሽ ሰውነቱ እርቃኑን የሆነ አንድ ደካማ፣ ትንሽ ጥቁር ልጅ የማስታወሻ ወረቀት አውጥቶ ሰጠው። ደብዳቤውን ፖንሴ ከፈተው። የተፃፈው በፈረንሳይኛ ነበር።

«መጥተህ እንድንገናኝ። ይህ ህፃን ያሳይሃል»

የእጅ ፅሁፉ አጣጣል እንዳይለይ ቃላቱ የተፃፉት በትልልቅ ፊደላት ነው። በዚያም ላይ መልዕክቱ አልተፈረመበትም።

ፖንሴ በምድር ቤቱ ውስጥ የተችትን አባ ብሬቬደንትን ቀስቅሶ፣ አብረውት እንዲሄዱ ሊጠይቃቸው ወሰነ። ተጥሶም የተዘጋጀውና ይዞት የሚሄደውን ሻንጣውን ተመለከተ። ከዚያ ውስጥ አንድ ጉራዴ መዝዞ ታጠቀ። ሌላ አንድ ትልቅ ፖቤ አውጥቶ፣ በፍርሃት ሰሚንቀጠቀጡት ጀስዊት ሰጣቸው። ጭለማው እየበረታ፣ ለአይን ያዝ ማድረግ በጀመረበት ሰዓት ትንሽ ልጅ እየመራቸው ወሰዳቸው። የከተማው መሣል በሰዎች የተሞላ ነው። ቀኑን ሙሉ ከዚታቸው ውስጥ የሚቆዩት የከተማው ነዋሪዎች፣ ከመስኮት የለሹ ቤታቸው ቀስ እያሉ በመውጣት ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው እያወሩ ይመላለሳሉ።

ጆን ባፕቲስት፣ የሚጓዙበትን አቅጣጫ ካርታ በአእምሮው ለመመዝገብ ሞክሮ ተወው። በመጨረሻም ሦስት ጠባብ መንገዶች የሚገናኙበት አንድ አነስተኛ አደባባይ ዘንድ ደረሱ። በአደባባዩ አንድ ወገን በመካከለኛው ምስራቅ ውስጥ እንደሚገኙት ሁሉ ሁለት ካሬ ሜትር የሚሆኑት መስኮቶች በብረት ግሪል እንደሚሸፈኑባቸው ያለ ሻይ ቤት አለ። ወደ ውስጥ ዘልቀው ሲገቡ ቤቱ ሰው የለበትም። ወለሉና ግድግዳው፣ ዙሪያን ከአፈር የተሰሩት የመደብ መቀመጫዎች ቡትት ያሉ ቀይና ለማያዊ ሲጋቻዎች ለብሰዋል። አንዲት ትንሽ የዘይት ፋኖስ፣ በአንድ የመዳብ ሣህን ላይ ተቀምጣ ሞቃት ግለቷን ታሠራጫለች። በክፍሉ ጀርባ፣ ጨለማ ውስጥ ተተምሮ የነበረው ሰው አነርሱ ሲገቡ ብድግ አለ። ፖንሴም በትልጥፍና እጁን ወገቡ ላይ በታጠቀው የጉራዴ እጀታ ላይ አሣረፈ።

«ወዳጄ» አለ ሰውዬው

ፖንሴ፣ በረዶ ሆነ። በጨለማው ውስጥ በአስፈሪ ሁኔታ የሚንቀሳቀሰውን ረዥም ሰው ተመለከተው።

«ይህን ድምፅ አውቀዋለሁ . . . »

እንግዳው ቀርቦ፣ በጭንቅላቱ ላይ የነበረውን ፈትቶ፣ በጠረጴዛው ላይ ባለው ብርሃን እንዲታይ ሲል ቆመ።

«ሜትር ዣረሚ!» አሉ ጀስዊቱ

የኃያኛውን ድምፅ ወዲያውኑ የለየው ጆን ባፕቲስት፣ ዘሎ ክንዶቹን አቅፍ አደረጋቸው። በደስታ ፖኸት አሰሙ።

ፖንሴ፣ ከጥንት ጓደኛው ጋር ዳግም በመገናኘቱ እጅግ ተደሰተ። የሴፍ፣ እምብዛም ጓደኛ ሊሆኑ ስለማይችሉ ከእንግዲህ በኋላ ብቸኛ አይሆንም። ሜትር ዣረሚ፣ ለሁሉም ቡና አዘዘና ሲጨርሱ፣ ከኪሱ ውስጥ የያዛትን አነስተኛ ጠርሙስ አውጥቶ ነጣ ያለ ፈሳሽ ቀዳላቸው። ዳግም በመገናኘታቸው ስለጤንነታቸው ጠየቁ።

«ግመል ጋላቢው የተባልከው ፈረንሣዊ ለካ አንተ ነበርክ ስትከተለን የነበርከው?» አለ ጆን ባፕቲስት

«ግበፅ ውስጥ እስካለን ድረስ ራሴን ማሣወቅ አልችልም። ሣልፈልግ ቀርቼ እንዳልሆነ ግን እመነኝ»

ዐይኖቻቸው ደኅማውን የፋኖስ መብራት ስለተሰማመደ፣ ፖንሴ በኃደኛው ላይ የሚስተዋለውን የመልክ ለውጥ ተመለከተ። ፊቱ በጣም ከስቷል፣ አይኖቹም ጉድጓዳቸው ገብተዋል።

«እዚህ ከደረስኩ በኋላ አንተ ከስገረ ግሸው ጋር ጉዳይህን እንድትፈፅምና ከዚያ በኋላ ከመልቀቅህ በፊት ራሴን ላጋልጥ ፈለግሁ። እናም ምን ታስባለህ? ቅፍስቱን መቀላቀል ያስቸግረኝ ይሆን?»

«አስቲ አየዋለሁ። አሁን ዳግም ተገናኘን፣ እንግዲህ መለያየት የለብንም» አለ ፖንሴ።

ሁሉም የራሣቸውን አስደሣች ገጠመኞቻቸውንና ምሬቶቻቸውን ተጨዋወቱ። ሜትር ዣረሚ፣ ብርቁ ወዳጆቻቸውን ለሁለተኛ ጊዜ ሞላው። የተቀዳላቸውን በአንድ ትንፋሽ ጨልጠው፣ መሣቅና መቃለድ ቀጠሉ።

«ስለገዛህ ሁሉ ልትነግረኝ ይገባሃል? ለመሆኑ ተከትለኸኝ ለመምጣት የወሰንክው መቼ ነው? ከዚያም በላይ እንዴት መደበቅና መቆየት ቻልክ?»

ሜትር ዣረሚ ከመጠጡ በዛ አድርጉ ሣበና ሰቀረበው ጥያቄ ፈጥኖ መልስ እንደሚሰጥ እጁን በማወዛወዝ ገለፀ። ነገር ግን እስክአሁን ፀጥ ብለው የነበሩት ጀስዊት፣ ከፍተኛ ድምፅ በማሰማት በደንገት ጣልቃ ገቡ።

«ይቅርታ አድርግልኝና የዚህ ሰው ከኛ ጋር መገኘት ክስምምነታችን ጋር የሚጣጣም አንዳልሆነ አምናለሁ»

የተለመደው የአዛዥነት ቅላፄያቸው የተመለሰ ይመስላል። እስክአሁን ድረስ እንደታዛዥ አሽከር ያከናወኑ እንደነበር አይደሉም። ሜትር ዣረሚ የሰውዬውን መኖር የተገነዘበው ይሄኔ ነበር።

«ይህ አሮጌ ቁራ፣ ከኛ ምን ይፈልጋል?» ሲል አባ ብራቬደንትን በግልፅ ጥላቻ እየተመለከተ ተናገረ።

«አዚህ ያለው» ቁሱ ቀጠሉ «በንኑሁ ትዕዛዝና በቅድስተ ቅዱሳን ሊቀጳጳሱ አመራር ነው። ይህ ተልዕኮ የኛና የኛ ብቻ ሃላፊነት ነው። ከመነሣታችን በፊትም፣ ቆንሲሉ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ተናግረዋል። ኤምባሲያችንን ሌላ . . . ማንኑቱ . . . የሚደባለቅበት አንዳችም ጥያቄ እንደማይኖር . . . »

ሜትር ዠረሚ ፊቱ እጅግ አስፈሪ አስተያየት በማንፀባረቁ፣ ጀስዊቱ የጀመሩትን ዐረፍተ ነገር የመጨረስ ብርታት አጡ።

«አቶን እንዲዘጋ ንገረው። አሰበሰዚያ ሞንቅላቱን ነው የምፈክስለት» ሲል ሜትር ዠረሚ በነኮድንድ ድምፅ አምባርቆ የመደቡን ጠረጴዛ ደጋግሞ በሃይል መታው። ድምፁ እንደብረት ሣህን መሰባበር ዓይነት በመሆኑ፣ የሻይ ቤቱን ባለቤት ሮጦ እንዲመጣ አደረገው።

ጀስዊቱ፣ እስከአሁን በርጋታ ባለውና ቆይቶ ለጉዳዩ ውሳኔ በሚሰጠው ጆን ባፕቲስት ላይ ጥቃታቸውን ከፈቱ።

«ሙሴ ፖንሴ፣ አክብረህ ልትጠብቀው የሚገባህ ግዴታ ገብተሃል። ምንም ያህል ርቀት የተጓዝን ብንሆንም፣ በመጨረሻው መመሰሳችን አይቀርም። ስለዚህ፣ የምንሰራቸውን ሁሉ በኋላ ላይ ማሣመን መቻል ይኖርብናል። ይህን ሰው ከኛ ጋር ይዘነው ብንሄድ፣ አንተ ማታውቀው እንደተቀላቀለን አድርጎ ማን ያምንሃል። እንዲያውም፣ አንተ ያቀድከው ነው ብለው ይናገሩብሃል» ሜትር ዠረሚ ጮኸና ጉራዴውን መዘዘ።

«ይህንን አይኖ ሁለት ቦታ አስነየቀዋለሁ» ሲል አጓርቶ ወደ ጀስዊቱ ተንደረደረ።

ፖንሴ በሁለቱ መካከል ገባ። ፖኸቱ ቀለጠ። በሁለቱ ፈረንሣውያን መካከል የተፈጠረውን ያልተሰመደ የፀብ ትዕይንት ለመመልከት አላፊ አግዳሚው ወደ መስኩቱ መከልከል ጀመረ። ጆን ባፕቲስት፣ ፀቡን ለማብረድና ከጓደኛው እጅ መሣሪያውን ለመውሰድ ቻለ። ጓደኛውን ወደ ክፍሉ መጨረሻ ገፍቶ ከወሰደው በኋላ ወደ አባ ብራቬደንት ዞረ።

«ዙሪያ ገባው ሁሉ ገደል የሆነበት ዓደኛዬን ልተወው አንዳችም ቃል አልገባሁም። ከዚህ ሰው እዚህ መምጣት ጋር እኔ አንዳችም ጉዳይ እንደሌለኝ ሊያወቁት ይገባል። ነገር ግን፣ ከእንግዲህ በኋላ ይህ ሰው ከኛ ጋር የመቆየቱን ሃላፊት እኔ እወስደዋለሁ።»

ሜትር ዠረሚን እጁን ይዞ እየጐተተው፣ ዮሴፍንም ከፊት ሰፊቱ አስቀድሞ እየገፋቸው፣ ጆን ባፕቲስት ወደበሩ አመራ።

«በሉ፣ አስፈላጊ የሆኑ ወረቀቶችን ለማዘጋጀት፣ አሁኑኑ ወደ አገረ ገዢው ዘንድ እንሂድ?» አላቸው።

የተሰበሰበውን ሕዝብ፣ በሻይ ቤቱ በር ላይ ከሁለት ከፍለው ጨለማ በዋጠው መንገድ፣ በቅድመ ትንሽ መልዕክተኛ ልጅ መሪነት ወደመጠባበቅ ተመለሱ።

ፖንሴ፣ ትንሿን ሴት ልጁን ስለአዳነለት አገረ ገዥው ውለታ አለበትና ለዚህ ፈረንሣዊ ውለታ መመለስን እምቢ አይልም። በዚህ መሠረት ሜርት ዠረሚን ብቁ መሆኑን በመመስከር፣ ለሊናር ንኮሥና ለኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ደብዳቤ ፃፈለት። ሁለቱ ፈረንሣውያን፣ በሌላ ሦስተኛ አካል እንደገና መጠናከራቸውን ሃጂ አሊ ደስ ሳይለው ቢከታተለውም፣ በዚህ ላይ ቅራኔ መፍጠር ከንቱ መሆኑን ተረዳ። አባ ብራቬዳንትን በተመለከተ እንደገና ተመልሰው ዮሴፍ ስለሆኑ አንዳችም ምክር መለገሳቸውን አቆመ። የታችኛው ከንፈራቸው መውደቅና የአገጫቸው እንደገና መርገብ የተለመደውን የትካዜ መልካቸውን አወጡባቸው። ከበፊቱ ይልቅ በጣም ዝምተኛም ሆኑ። ጀስዊቱ፣ ከዚህ በፊት ካሣዩት አነስተኛ ግቡዝነት ባሻገር፣ ለውዱው ሁለቱ ጓደኞሞች እንደገና በመገናኘታቸው ብቻ ቅናት ያለባቸው አልመሰል አለው።

በማንኛውም ደረጃ፣ እኒህ አገልጋይ፣ ፕሮቴስታንቱ ቅፍለቱን በመደባለቁ ተጠቅመዋል። ዠረሚ ያመጣቸው ሁለት ግመሎች አሉ። ለአገረ ገዥውም ያቀረቡት ስጦታ ከጭነቱ ላይ ተቀንሷል። ስለዚህ እርሣቸው ከዚህ በኋላ በእግር አይጓዙም።

የሜትር ዠረሚ መድረስ ለራሱ ለፖንሴና ለጓደኛው ጥቅም ሲባል የተሠራ ትያትር እንደሆነ ቁሱ ማመናቸውን ቀጠሉ። በርግጥ እውነቱን መደበቅ አይቻልም። ቅፍለቱ በአዝጋሚ ጉዞው ወደፊት በሚንቀረፈፍበት ጊዜ ሁለቱ ጓደኞሞች በቅርብ የነበራቸውን

አያንዳንዱን ተግባራቸውን ያወሩ ነበር። ሜትር ዣረሚ፣ ጓደኛው ብቻውን ብዙ ችግሮችን እንዲጋፈጥ ስለተወው ፀፀት ተሰምቶታል። በዚህም ሳቢያ ቅፍለቱን ለመደባለቅ ከጅምሩ ላይ ወስኖ ነበር። ነገር ግን፣ ከቆንሲሉ ጋር ነገሮች እንዳይወሳሰቡና ችግር እንዳይፈጠር ለመከላከል፣ ጆን ባፕቲስትም ሃሰት እንዳይናገር ለመጠበቅ በማሰት ሜትር ዣረሚ፣ ድርጊቱን አጥብቆ ቢጠላውም፣ አንዳችም ነገር ሣይተነፍስ፣ ዘማቹ ግብፅን ሲያልፍ ሲቀሳቀል ወሰነ።

ጆን ባፕቲስት በበኩሉ፣ ከመጀመሪያው ጀምሮ በቅርባቸው ተደብቆ ስለነበረው አስገራሚ ፈረንሣዊ ፍንጭ ቢኖረውም፣ እስከመጨረሻዋ ሰዓት ድረስ ግን በርግጠኝነት ማን መሆኑን አያውቅም ነበር።

ጓደኛው፣ ጉዞ ከጀመረ በኋላ፣ ሜትር ዣረሚ አንድ ቀን አድሮ ስለነበረ፣ ስለሳይሮ አወሩ። ቤቱን ለቅቆ የወጣው፣ ጋሪው አሲስንና አባ ጋቦሪን አድርሶ፣ ተመልሶ ዋናው መንገድ ውስጥ ሲገባ መሆኑን ነገረው።

«ደብዳቤዬን እንደተቀበለች እርግጠኛ ነህ?» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቀው።

5

ከዚህ በኋላ ለመነክሴው የታዘዘላቸው መድሃኒት ምን እንደሆነ አወቁት። አባ ጋቦሪ፣ መጠኑን ከፍ እንዲያደርጉ ለመገፋፋትም ፈጠነች። በዚህ ዕሰት በመድሃኒት መቀመሚያው ቤት ከመድረሣቸው፣ አንድ ትልቅ ብርጭቆ ሙሉ በአንድ ትንፋሽ እንዲጨልጡ አደረገቻቸው። ቁሱ፣ አምስት ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ እንትልፍ ወሰዳቸው። በመጀመሪያው ማንኮራፋት፣ ዘልላ ወደ እርከኑ በመሄድ በተዘጋው መስኮት በኩል ተጣራች።

«ፍራንቾይዝ መምጣት ትችያለሽ!»

መጋረጃዎቹ በፍጥነት ተከፍተው፣ ፍራንቾይዝ እርከኑ ላይ ወዳለችው ልጃገረድ ወርዳ መጣች። በጥግ በኩል ሁለት ወንበሮች አድርገው ጉን ለጉን ተቀመጡ።

«እና?» ስትል ፍራንቾይዝ ጠየቀቻት። «ትናንት የሰጠሁሽ ደብዳቤ አስደሰተሽ?»

አሊስ አፈረች። እንዲህ በርህራሄ የምትመለከታትን ሴት የማታውቃት ቢሆንም፣ በደመነፍስ ብቻ አመነቻች። የማለዳው ሰዓቶች ማብቂያ የሌላቸው ይመስላሉ። እንዲህ ልትረዳት ለምትችል ሴት ምስጢሯን ሁሉ ጮልጮላ ለመናገር ትዕግስት አጥታ ተቃጠለች።

«ይኸውልሽ» አለቻት ወረቀቱን ለጓደኛዋ እያሳየቻት። «ራስሽ አንብቢው።» ጆን ባፕቲስት የአጅ ዕሁፍ የተሞሉትን ሁለት ገፆች ፍራንቾይዝ ተቀብላ የሚከተለውን አነበበች።

ለተወዳጇ አሊስ፣

የምፅፍልሽ በጣም እየተቻኮልኩና በአንድ ሻንጣ ላይ ተቀምጬ ነው። ኢቃሙቺ ሁሉ በዙሪያዬ ብትንትን እንዳሉ ናቸው። አዕምሮዬ፣ ለጉዞው በሚያስፈልጉ አንድ ሺህ ትንንሽ ጥንቃቄዎች ሞነት ተሞልቷል። በርግጥ፣ ውሰጣዊ ስሜቴን ይህ ሊገልፅልኝ አይችልም። ይሁንና፣ በዚህ ሰዓት፣ የኔ የሆኑት ሁሉ በግልፅ ይታወቁኛል። በነዚህ የኔዎች በምላቸው ነገሮች ምክንያት ያቀድኩትም በጣም ትክክል ነው። እነዚህን ነገሮች ስወሰናቸው ሊሣራ አልጠብቅም። እነዚህን ውሳኔዎች ለመሰማት ባልተዘጋጀሽባቸው

ለዓቶች እንዲነገሩ በማቅረቤ በጣም ፈርቻለሁ። በዚህ ምክንያት ይህ ደብዳቤ ጥቂት ዘግይቶ እንዲደርስሽ ጥንቃቄ ወስጃለሁ። ለዚህም፣ እባክሽ ይቅር በይኝ። እነዚህን መስመሮች ስታነቢ እቤቴ መጥተሽ፣ እንደ ቤትሽ እየተሰማሽ ነው። የምወዳቸው ተክሎቼ በዙሪያሽ ናቸው። ፍራንቹይዝንም አግኝተሻታል። እርሷ በአንች ላይ ከፍተኛ እምነት አሳት። ይህም ይገባታል። እነዚህ ሁሉ አንድ ላይ ሆነው፣ አለንቺ ጋር መነጋገሩን ቀለል ያደርጉልኛል። ምንም እንኳ አንድ ላይ ባንሆንም፣ አንድ ቦታን እንጋራለን። እንድንገናኝ ሊረዱን የሚችሉ ወዳጆች አሉን። በጣም ቅርብ ለቅርብ በነበርንበት ጊዜ፣ እንዳንነናኝ ከሚያራርቁን ነገሮች አሁን በርግጥ የቦታ ርቀት ነፃ ሰላደረገን፣ ከመቼውም በበለጠ አንዳችን ለአንዳችን ቅርብ ነን።

በርቀት መገኘቴ እንደመከላከያ ስለሚሆነኝ ምን እንደሚሰማኝ ለመናገር ብዙም አልፈራም። ባለፉት ጊዜያት ይህን ለማድረግና ለመዳፈር አልፈለግሁም። ሁኔታ ሠች ሁሉ አላመቹኝም ነበር። ይሁን እንጂ ለሌሎች በምናገርና በምመልስበት ጊዜ የማናግረው አንችን ነበር። ሌሎችን የማያቸው በምመለከትበት ጊዜ የምመለከተው አንችን ነበር። በሁለመናዬና በሃሳቤ ውስጥ አንች ነበርሽ።

ሁሉንም ደረጃ እንዳናስታውስ እርስ በርሳችን ከተዋወቅን በጣም አጭር ጊዜ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ በዘሃሊጅ ድልድይ ላይ ካየሁሽ ቅፅበት ጀምሮ በወብትሽና በተከለ ሰውነትሽ ተማርኬያለሁ። ቀርቤ ላይሽ ከቻልክብትና የአይን ዕይታ ከተለዋወጥንበት ጊዜ ጀምሮ ያ የመጀመሪያው ስሜቱ ይበልጥ መጠንከር ጀመረ። ራሴን በደስታ ከማስማረኩ በፊት እንዲህ ያለ ጠንካራ ስሜት ኖሮኝ ስለማላውቅ በመጀመሪያው ላይ ተፈኔንቂ ነበር። እንዲያውም ተናድጀ ነበር። ባንች ላይ ያለውን የደስደስ ሁሉ ለመግለፅ በቂ ጊዜ በኖረኝ ምንኛ በተደሰትኩ። ገለፃዬንም የወረቀቶች ክምርም ቢሆን ሊሸከመው አይችልም። እያንዳንዱን ያንችን ጥራት ለመግለፅ ትርፍ ጊዜ ስለሌለኝ ንቁ የተውኒቸው እንዳይመስልሽ፣ ምንም ላለማለት መረጥኩ። ውድ አሊስ፣ አንችንና ያየሁብሽን ሁሉ አመልካለሁ። እስካሁን ሸሽገሽው በብርታት የያዝሽውንና በቅርቡ የሚኮየውን ጥንካሬሽን በፍቅር እንደምወደው አገልፅልሻለሁ።

ርቀሽ በመሄድ ላይ እያለሁ ይህን ሁሉ ለምን እነግርሻለሁ? ስሜቶቼ በርግጥ ጠንካሮች ቢሆኑ ኖሮ፣ ካንች የማልለይበትን ምክንያት ለምን አይሰጡንም ነበር? መሄዴን የመግለፄስ ጥሩነቱ ምኑ ላይ ነው? ባለፉት ቀናት በአዕምሮዬ የሚገላለጡ ጥያቄዎች እነዚህ ናቸው። እነዚህ ደግሞ ይበልጥ ያበሳጋ ናል። ምክንያቱም፣ በህይወቴ ውስጥ ለዛዘንና ለትክዜ አንዲት ቅንጣት ቦታ ለመስጠት ፈቃደኛ አይደለሁም። እያንዳንዱን ነገር በአዕምሮዬ ውስጥ ያለፍርሃት ሳመላለስ፣ ሁኔታውን በተለየ መልክ ለማየት ቻልኩ። በዚህም የተነሣ መለየቴ ጥሩ አጋጣሚ ይመስለኛል። አምን፣ አሊስ፣ በትክክል አንብበሽኛል፣ እኔም ላሳምንሽ እሻለሁ። ይህ ጉዞ ለሁለታችንም ታላቅ እድላችን ነው። ካይሮ የምቆይ ብሆን ኖሮ፣ በሁለታችንም መካከል አንዳችም የሚሆን ነገር አይኖርም ነበር። ከፊት ለፊቴ የሚደቀንብኝ ፈተና ቢኖርና እኔም የሚሣክልኝ ቢሆን ተስፋ የማላደርገው ነገር አይኖርም ነበር። ድሉ ወደ አንቺ አንለርኝ፣ ሊሆን ያደርሠኖ ል። ፈቃድሽ ከሆነ ነፃና እኩል አድርጊኝ። ይህን ተልዕኮ ለማሣካት ቃልኪዳን የገባሁት ላንችና ለአንች ብቻ ነው። በኔና በዓላማዬ መካከል ሊመጣ የሚችለውን ማንኛውንም እንቅፋት ድል ለማድረግ ብርታት ይሰማኛል። ካንቺ እያራቀ የሚወስደኝ እያንዳንዱ እርምጃ ይበልጥ ወደ አንቺ ያስጠጋኛል። ተስማምቼ የተቀበልኩት ሃላፊነት ስለሚያስከትለው ውጤት ምንም ጥርጣሬ የለኝም። እመለሳለሁ። ብቸኛው ተስፋዬ ግን፣ ልትጠብቂኝ የሚያስችልሽ በቂ ትዕግስት ይኖርሻል የሚል ነው። አሊስ! ይህን ደብዳቤ እያነበብሽ ባለሽበት ጊዜ አሁን በምንዝባቸው አገሮች ውስጥ ሆኜ ከኔ ጋር መገናኘት ካልቻልሽ፣ ልትታይኝ አለመቻልሽን ማወቅ ይኖርብሻል። አሁንም አደበሽኝ ያለሽ እየመሰለኝ ያልተቋረጠ ደስታ ይሰማኛል።

እዚህ ህግ በማይገዛቸው በምድረበዳው ጉዳናዎች ውስጥ ሙጭጭ አድርጌ እየሣምኩሽ ነው።

«ደግ!» አለች አሊስ ደብዳቤውን አንበባ ስትጨርስ

«በዙ ግራ የሚያጋባ፣ ረዥምና ሊሆን ከሚገባው በላይ የተወሳሰበ ቢሆንም፣ እንደሚያፈቅርሽ የሚገልፅ ነው»

«ግን» አለች ልጃገረዲቷ ተረብሻ «ይህ ሰው እምብዛም አግኝቶኝ አያውቅም። ጭራሽ አልተገናኘንም . . . »

«እንዳንቺ ከሆነ ታዲያ ሰዎች እንዴት ነው በፍቅር የሚወድቁት? ከማይወዱት ጋር በየዕለቱ ብዙ ሰዓቶችን አብረው መቆየት ነው?»

«የለም በእርግጥ እንደዚያ አይደለም። ነገር ግን ከልቡ መሆኑን እንዴት ማወቅ ትችያለሽ?»

አሊስ ከባለፈው ምሽት በፊት የተጋፈጠችውን ሃሣብ አውጥታ ለመናገር፣ የሚያስታወቅ ጥረት ታደርጋለች።

«አገር ለቅቆ በጉዞ ላይ የሚገኝ ሰው፣ እንዲህ ያለ ውሸት ለመናገር ምክንያት አይኖረውም» አለች ፍራንቾይዝ

«ምናልባት ደብዳቤውን የላፈው የኔን ፍላጐት ለመቀስቀስ ይሆናል ወይም ትዝታ ይዞት ይሆናል። ወይም ለጉራም ይሆናል። ሆነም ቀረም እንድጠብቀው መጠየቁ ምንም አይጐዳውም»

«ለአፍታ እንኳ ይህን ታምኛለሽ?» ፍራንቾይዝ ጠየቀች

ወጣቷ ልጃገረድ ዓይኖቿን ሰበረችና ከስተር ብላ በጥንቃቄ አሰበች። የእንባ ዘለላዎች ጉንጮችዋ ላይ ቁልቁል ወረዱ።

«በእርግጥ አላምንም» አለች «ራሴን በተቃራኒው ለማላመን እየሞከርኩ ነው እንጅ እያንዳንዱ እኔነቴ ልክ እኔ እንደማፈቅረው እርሱም እንደሚያፈቅረኝ ይነግረኛል።»

«በቀላሉ ይህን መቀበል መጥፎ ይሆናል?»

«ጉዳዩ እንዲህ ከሆነ» አለች ወጣቷ ልጃገረድ ሃሳቧ ውሣኔ ላይ እንዲደርስ እየሞከረች።«የፈለገው ቢሆን እንኳ አዝናለሁ»

«ይህስ ቢሆን ሰምን ይሆናል» አለች ፍራንቾይዝ

«እስቲ አስቢው» አለች አሊስ ጮሳ ባለ ድምፅ፣እንባ የቋጠሩ ዓይኖችዋን ወደ ጓደኛዋ መልሳ። «ከጉዞው ሣይመለስ ቢቀር ለዘላለም ልቤ እንደተሰበረ ሲቀር ነው። ከተመለሠ ደግሞ . . . »

«ከሁለት አንዱ ሊሆን ይችላል። እርሱም ያሰው ይህንኑ ነው»

«አባቴን አታውቂውም አይደል?!»

ምን አይነት ልጅ ነች! ስትል ፍራንቾይዝ አሰበችና ተንቀሳቀሰች «ገና እሩቅ ያለ ነገር ትመለከቻለሽ?» አለቻት ረጋ ብላ። «እስኪመለስ ድረስ ብቻ ጠብቂው። ሰሌላው ነገር ሁሉ እመኚው። የማይታወቅን ግዛተ ዘውድ በሮች ለማስከፈት የሚችል፣ የአካባቢውን ተወላጅ መሣፍንት አመኔታ የሚያገኝ፣ የፈረንሣይን ንጉስና የርዕሰ ሊቃነ ጳጳሱን ዓላማዎች ከዳር ለማድረስ የሚችል ሰው፣ አንድን መንቻካ አባት ማግባባትና ማሣመን የሚችል ሊሆን ይችላል።»

ልንሰማው የምንፈልገውን በታማኝነት ለሚገልፁልን ሰዎች ፣ ቆጥበን እንደምናቆይላቸው ፍቅርና የእምቢተኝነት ስሜት፣አሊስ፣ ድብልቅልቅ ባለ ርህራሄ ተመለከተቻት።

«በየዕለቱ ሚት ሚት ነይና እንጫወታለን። ጊዜውም ፈጥኖ ያልፋል» አለች ፍራንቾይዝ።

ከዚህ በኋላ ወጣቷን ልጃገረድ በክንዶችዋ ውስጥ ይዛት ፀጉሯን በማሻሸት ትንሽ እንድታለቅስ አደረገቻት።

ሲናር እስኪደርሱ ድረስ ሁሉም ነገር በሰላም ተካሂዷል። ቅፍለቱ፣ ከተማ የደረሰው በባዩዓ ምድረበዳ አስር ቀን ሙሉ ከተጓዘ በኋላ ነው። ጉዟቸው ወደ ደቡብ አቅጣጫ በቀጠለ

ቁጥር ቀስ በቀስ ጣር ቅጠል መታየት ጀመረ። አረቦች፣ ራህማት አላህ «የእግዚአብሔር ምህረት» እያሉ የሚጠሩት አገር ገብተዋል። የእግዚአብሔር ምህረት፣ በዚህ ቦታ ላይ መቀመጡ የሚታየው፣ እንደ ዶንኮሎ ሰዎች መሬታቸውን በመስኖ ማልማት የሰባቸውም። መሬቱ የሚለማው በዝናብ ነው። በየትኛውም አቅጣጫ አረንጓዴ የግጦሽ መስኩች፣ መካከለኛ ቁመት ያላቸው ዛፎችና እንዲያውም በአንዳንድ ቦታዎች ደን ይታያል። ለመለከታዊው ችሮታው ምስጋና ይግባውና፣ ገበሬዎች የተወለነ ትርፍ ጊዜ ኖሯቸው ከአሀዮቻቸው ጐን እየዘመሩና እየዘፈኑ ይንዛሉ።

ዋና ከተማዋ ሲናር፣ በጥቁር አባይ ዳር የተመሠረተች ናት። ጥቁር አባይ፣ ከአቢሲኒያ ተራሮች ቁልቁል ሲምዘገዘግ፣ ውሃው በደቃቅ አፈር ደፍርሶና ከብዶ ነው። ሲናር፣ ታላቅ የንግድና የግብርና ከተማ ስትሆን፣ በደማቅ የባዛር ትርኢቶች፣ በውብ መስጊዶችና ሰንጉሥና ለቤተመንግስቱ በቋሚ መኖሪያነት በሚያገለግል ድንቅ ቤተመንግስት የተዋበች ነች። ሁለመናዋ በድንጋይ የታነፀ ሲሆን፣ በቀይ ሸክላ ተሰስናለች።

በምድረ በዳው የመጨረሻ ክፍል ላይ ጉዞው ያላንዳች ግጭት አልፏል። ዳግም ሲገናኙ ከተፈጠረው ደስታ በኋላ፣ ሚትር ዝረሚ ወደተለመደው ጋግርታምነቱና ብስጮነቱ ገብቷል። ከጀስዊቱ ጋር የመሳሪያ ፍልሚያ ላለማድረግ ተስማምተዋል። አንዳቸው ሌላቸውን ለመሸሽ ሲሉ የሚናገሩት ሁሉ ለፖንሴ ብቻ ነው። ፖንሴ ደግሞ ሁለቱን ሰዎች ለመሸምገልና ለማስታረቅ በማያመቸው ሁኔታ ላይ ሆነ። የየሴፍን ሁኔታ እንቀበለው ካልን ከሁሉም ይልቅ ፍፁም ደስ የማይል ነበር። በሌላ በኩል፣ ጠላቱ፣ ራሱን እንደ ጌታ እዩኝ እያለ ነው። እርሱ ደግሞ የትሁት አሽከርን ሚና በማከናወን፣ በመጫን፣ በማራገፍ፣ በያንዳንዱ ማረፊያ ምግብ በማዘጋጀትና የውሃ መያዣ ቀርበታዎችን መመላት ይገደዳል። ከዚህም በላይ ሃጅ አሊም ትዕዛዞችን ይሰጠው ጀመር። ትዕዛዝ እንዳይሰጥ ፖንሴ ጠይቆት ነበር። ነገር ግን፣ በዚህ ጊዜ በባዕድ አገር ውስጥ በመሆናቸው፣ ግመል ነጂው፣ ለፈረንሣውያኑ የነበረውን ፍርሃት ሁሉ ርግፍ አድርጐ ጥሎታል። ለጀን ባፕቲስት ካለው ግልፅ አክብሮት ባሻገር፣ በየአጋጣሚው ሁሉ ትንሽ ገንዘብ እያስከፈለው፣ በመጨረሻ ላይ ትልቅ ወጭ አቋዲሆን አድርጓል። በባዕድ ምድረ በዳ መሃል ላይ ለአፍታ ቆም እንዳሉ፣ ሃጅ አሊ፣ በአዲስ አይነት ዘዴ አስፈራርቶ ገንዘብ ሊቀበል ሞከረ። አሸዋ ያቀላውን ዓይኑን ብቻ ማማየት እንዲችል በማድረግ፣ ፊቱን በጥምጣሙ ግጥም አድርጐ ከሸፈነው ከሃሰን አልቢል ቤሲ ጋር መጣ።

«በሁለት ቀን ውስጥ፣ ጉራዕ፣ የፈንጣጣ ምርመራ የሚደረገበት ቦታ እንደርሳለን።» አለ ሃጂ አሊ።

በሽታን አጥብቆ የሚፈራው የሲናር ንጉስ፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ በሽተኛ ተጓዦችን ላለማስገባት በድንበሩ ላይ የተገለለ ቦታ አዘጋጅቷል። ሲል ገለፀ።

«ሃሰን የኬላውን አዛዥ እንደሚያውቀው ይናገራል፣ ይህ ሰው አረቦችን እንዲያልፉ ይፈቅድላቸዋል። እናንተን ግን ማግለሉን ይጠራጠራል። በዚህ የተነሣ እናንተን እዚያው ትተናችሁ ልንገዝ ነው። በስተቀር . . . » ሲል ሃጂ ቀጠለ

«በስተቀር ምን?»

«በስተቀር፣ የዚህን ነገር ሠሪ አስተማሰብ፣ የሚለውን ነገር ካልሰጣችሁን» ሃጅ አሊ ከመጠን በላይ የሆነ ገንዘብ ጠራ። ይህን ከተናገረ በኋላ ግመል ነጂው አፀፋዊውን ሃሣብ በዘፈንና በዳንስ ዘዬ ለሃሰን አል ቢልቢሲ አስረዳው። ሃሰን አል ቢልቤሲ፣ በበኩሉ በግትር እምቢተኛነት አለመስማማቱን ጭንቅላቱን በመነቅነቅ ይገልጽለታል። ብሎ ብሎ ዋጋው ዝቅ አለ። ይህን ለመክፈል ግድ ሆነባቸው። ከሁለት ቀናት በኋላ በወሰን ኬላው ላይ ሲደርሱ፣ ቦታውን እና ሆኖ አገኙት። የወረርሽኝ ፍርሃት በግልፅ በመወንዱ፣ የተገለለው ቦታ ተነስቷል። ሃጂ አሊና ሃሰን ገንዘቡን ተካፍለው ስለነበር ሊመልሱ አልቻሉም።

ሲናር ላይ ነገሮች በመልካም ሁኔታ ተጀመሩ። ለንጉሡ ደብዳቤአቸውንና ገፀ በረከታቸውን ለማቅረብ በቀጥታ ወደ ቤተመንግስት ሄዱ። ልክ ደንኮሎ እንደሆነው ሁሉ፣ የጆን ባፕቲስትን ሐኪም መሆን ንጉሡ ስላወቀ፣ አንድ ዘመዱን እንዲያክሙለት ጠየቀው። ከዚህ በኋላ ነገሮች ሁሉ መበላሸት ጀመሩ።

ንጉሡ፣ ከዙፋን ክፍሉ በስተጀርባ በምትገኝ ክፍል ውስጥ፣ ፖንሴንና የድጋፍ ደብዳቤው መድሃኒት ቀማሚ መሆኑን የሚመሰክርለትን ሚትር ዝረሚን ጠራቸው። አዬው፣ ቀጭንና ተልባሩ ነው። ቆዳው፣ እንደ ከሰል አመድማ ነው። ብዙ አሠቃቂ ተግባር እንዲፈፅሙ ያዘዘና እንዲያውም እርሱ በፈለገበት በማንኛውም ጊዜ እጅግ የከፋ ዘግናኝ ቅጣት እንዲፈፅም የሚያዝዙ ትንንሽዋ ዓይኖቹ ጭካኔ የተሞሉና ዕረፍት የለሽ ናቸው። ለምክክሩ ሃጅ አሊ አልተጠራም። ንጉሡ፣ ሁኔታውን ፖንሴና ዝረሚ በሚገዙ በሚረዱት አረበኛ ያስረዳቸዋል።

አንድ በብ፣ ምናልባት ከአስራ አራት ዓመት የማይበልጠው፣ ቁመቱ ግን ከሁለቱም ፈረንሣውያን የሚረዝም ጉረምሣ፣ አስከትሎ ገባ። በንጉሡ ትዕዛዝ ይህ ወጣት በሽተኛ፣ በወርቅ የተዘመዘመውን ጥቁር ጃኬቱን አውልቆ፣ እጅግ ያልተለመደ ቀጭን ሰውነቱን አሣየ። የማርሽ ጥርሶቹ እንደሚታይበት መሣሪያ፣ የዚህም ልጅ ጡንቻዎች በስሱ የቆዳው ሽፋን ስር ይታያሉ። ሆዱ ክፉኛ ተወጥሮ፣ እምብርቱ በሃይል ወደ ውጭ ወጥቶ፣ አንገቱ የጫፖት አንገት ይመስላል። በጣም የሚገርመው፣ ልጁ ከሚገባው በላይ ከመቅጠኑ በስተቀር በጥሩ ጤንነት ላይ ይመስላል።

«ይህ የሶስተኛዋ ሚስቱ ልጅ ነው። ምን እንዳለበት አናውቅም። የበላው ሁሉ እንዳለ ይወጣል። ነጭ ማሽላ ቢበላ ነጭ ማሽላ ይወጣል። ቀይ ማሽላ ቢበላ፣ ቀይ ማሽላ ይወጣል። ሥጋ ቢበላ፣ ሥጋ ይወጣል» አለ ንጉሱ

ሐኪሞቹ የሚሰጡትን አስተያየት ለመስማት ጠበቁ።

«ምን ይመስልሃል?» ሲል ፖንሴ ጓደኛውን ጠየቀው።

በዚያን ማለዳ ከዮሴፍ ጋር የተጨቃጨቀው ሚትር ዠረሚ ግልፍቱ አልበረደለትም ነበር።

«ቀላል ነው» አለ «ሲፈልገው አበት ይብላ»

ጀን ባፕቲስት እንዲህ ያለ መልስ እሰማለሁ ብሎ አልተዘጋጀም ነበርና ማቁን ሰቀቀው። የሠራውን ስህተት ወዲያውኑ ቢያርምም፣ ጥፋቱ ግን ተፈፅሟል። ንጉሡ፣ እነዚህ ሁለቱ፣ በልጁ ወይም በርሱ ላይ የሚቀልዱ መስሎ ታሰበው። መድሃኒት ቀማሚው፣ ምን እንዳለ ፖንሴ ትርጉሙን እንዲነግረው ንጉሱ ጠየቀው። ፖንሴ፣ ይህ ምንም እንደማያስፈልግ ገልፆ ሌላ ታሪክ ተናገረ። ንጉሡ ግን ቅር እንዳለው ቆየ።

ፖንሴ፣ የንጉሡን ልጅ በጥንቃቄ ተከታተለው። እርሱ ያዘዘለት መድሃኒት ልጁ የበላውን ምግብ እስከሚቀጥለው ዕለት ሳይቀር አቆየለት። ነገር ግን ልክ እንደተሠላጠቀ፣ ግን ጨርሶ እንዳልተሰበረ አንድ ሳህን ያህል ንጉሡ ለነርሱ የነበረው እምነት በመሠረታዊነት ስለተበላሸ ይህን መልሶ የመገንባት ተስፋ ጨርሶ ጠፋ።

በማንኛውም ተራና አዘቦት ጊዜ እምብዛም ጉዳይ የማይባል ነገር ተከሰተ። መሠንጠቁ የማይታይን ነገር ስብራቱ አስካለበት ቦታ ድረስ ለማስፋት ተሞከረ። አባ ብሬቬደንት እደጋውን አፋጠኑት።

ማንነታቸውን የሚጋርደው ፈረንሣዊ መታወቅ ሲጀምር፣ ጀስዊቱ የሆነ እርይታ ይሠማቸው ጀመር። ምንም እንኳን ካፑቺን ባይሆንም፣ አሁን ድረስ ከፕሮቴስታንት ጋር መጓዛቸው ያስጨንቃቸዋል። ካፑቺኖችንም ሃፈታተረው ለመጣል በመቻላቸው፣ ፈጥነው ከካይሮ ለመልቀቃቸው ምስጋና ይግባውና ከተፎካካሪ የሃይማኖት መስመር ሊገጥማቸው ይችል የነበረው አደጋ ማለፉን ራሣቸውን ለማሣመን ችለዋል።

አባ ብሬቬደንት ልበ ሙሉ ስለነበሩ፣ ሲናር ላይ ለሚገኙት ጥቂት መነኩሳት፣ ማህበረሰባቸው ለካፑቺኖች የሠራውን ቤት ለመጐበኘት ሃሳብ አደረባቸው። ፖንሴ፣ አብሯቸው የሚሄድ ከሆነ እንደ ጌታና አሽከር ሆነው ለመሄድ ፈለጉ። በዚህም፣ ሁለቱ ስለአካባቢው መረጃ ለመሠባሠብና መነኩሣቱም፣ አቢሲኒያን በሚመለከት ምን መላ እያዘጋጁ እንደሆነ ለመረዳት ይችላሉ። ፖንሴ ተስማማ። ሁለቱ ሰዎች ወደ ገዳሙ በአግር ጉዞ ሊጀምሩ፣ ሜርት ዠረሚ፣ ከተማው ውስጥ ሃጂ አሊ በተከራየላቸው ቤት ቆየ።

የሙስሊም መንግስት ንጉስ፣ ለካቶሊኮች የሚሆን የአንግዳ ማረፊያ በዋና ከተማ ውስጥ ይፈቅዳል ማለት የሚገርም ቢሆንም፣ መልሱ ግን ቀላል ነው። የንጉሡን ፈቃድ ሲያገኙ ካፑቺኖች ከጳጳሱ ጋር ያደረጓቸውን ክርክሮች ፍፁም ተቃራኒውን ተጠቅመዋል። ሮም በነበሩበት ጊዜ፣ ተልዕኮአቸው፣ ከጀስዊቶች መባረር በኋላ ተሠድደው ሲናር ጥገኝነት የጠየቁትን የካቶሊክ ስደተኞችን ማዳን ነው። ሲናር ውስጥ ግን፣ ሁሉም በሚገባ እንደሚያውቀው፣ ንጉሱም በተለይ እንደሚረዳው፣ እንዲህ ያሉ የካቶሊክ ስደተኞች የሉም። ጀስዊቶች፣ አቢሲኒያ ውስጥ ከንጉሡ በስተቀር ይህም እንኳ ለአጭር ጊዜ ነው፣ አንድም ሰው በደረጓቸው የሃይማኖት መስመር አልለወጠም። አቢሲኒያ ሲደርሱ እንደነበረው፣ ሲለቅቁም ብቻቸውን ነበሩ። ሲናር ውስጥ ካቶሊኮች ቢኖሩ ኖሮ፣ ሕዝባዊ እንቅስቃሴን በመፍራት፣ የሥልጣን ጉዳይ ነውና ንጉሱ ሮማዊ ቄስ እንዲመራቸው አይፈቀድላቸውም ነበር።

ስለዚህ አንድም ካቶሊክ ባለመኖሩና ያሉትም ቢሆኑ የሥቃይ ቅጣት እንዳይጥሣቸው እንድም ሙስሊም ሐይማኖቱን ላለማስለወጥ መሃላ ጉበተው ነው የሚኖሩት። ታዲያ፣ እነዚህ አኅጉን ለማይሞሉ ለማዊ የውጭ ዜጐች መኖሪያ መፍቀድ ምንም ጉዳት የለውም። ለህፃናት የሚሆን ትምህርት ቤት ከፍተዋል። ለታመመት ይጠነቀቃሉ። የጳጳሱም ጀሮ ስለማይርቃቸው፣ የሲናር ንጉሥ ከአውሮፖ ጋር ግንኙነት እንዲኖረው ይረዳሉ።

ፖንሴ፣ ዮሴፍ ተስትሰውት የገዳሙን የእንጨት በር አልፈው ሰፊ አደባባይ ውስጥ ገቡ። የተገረዙ የብርቱካን ዛፎች በተልቅ ክብ ቱቦዎች ውስጥ ተተክለው በአሊራማው ቀይ መሬት ላይ ተሰድረዋል። እንኳን ደህና መጣችሁ ያሏቸው ካፑቺን፣ በጉብኝታቸው ትንሽም መደነቅ አላሣዩም። እንደሌሎቹ ሁሉ አደባባዩን ቁልጭ አድርጉ ወደሚያሣየው መስኮት የሰሽ ክፍል መሯቸው። በአጫጭር የጠፍር መቀመጫዎች ላይ አረፍ እንዲሉም ጋበዟቸው። ከዚህ ቀጥሎ አራት መነኮሣት ተደባለቁቸው። እንደትዱስ ፍራንሲስ ይሰብሱ የነበረው ልማዳቸው ቀርቶ እዚህ የለበሱት የአረቦችን አሰባበስ ይመስላል። የጠቆረውን ፊታቸውን፣ ጥቁር ፂማቸውንና ከአበሩዚ የመጡ ገበሬዎች የሚያስመስላቸው አጭርና ወፍራም ቁመናቸው ሲታይ፣ በአንገታቸው ዙሪያ ያጠለቁት መስቀል ባይኖር ኖሮ፣ የዚህ የኑቢያ ግዛተ ዘውድ ተወላጅ ናቸው ቢባል በቀላሉ ተቀባይ ያገኙ ነበር።

ከመነኮሣቱ አንዱ ራሣቸውን የበላይ አድርገው አስተዋወቁ። ስማቸውም ራይሞንድ ይባላል። እንደርሣቸው ተራና የማይማርክ ልብስ የለበሱትን ጓደኞቻቸውንም አስተዋወቁ። በመቀጠልም ትንሽ ወደኋላ ራቅ ብለው ፖንሴን በጥርጣሬ አይን የሚመለከቱ መነኮሣትን አመለከቷቸው።

«እነዚህ ሁለት ወንድሞች ጐብኚዎች ናቸው። ትናንት ጧት ነው ከካይሮ እዚህ የደረሱት።»

«ትናንት ጧት!» አለ ፖንሴ። «በየት በኩል ነው የመጡት? ደንቡሎ ላይ ልናያቸው ይገባን ነበር»

«ወደዚህች ከተማ ከአንድ ቅፍለት በላይ ይጓዛል» አሉ ወንድም ራይሞንድ። «እነርሱ የአባይን ሸለቆ ተከትለው እስከ ሁለተኛው ፏፏቴ ድረስ በመጣጣት ከኛ በስተሰሜን ያለውን የአሸዋ ምድረ በዳ አቋረጡ»

«ይህ ይበልጥ ረጅም መንገድ ነው።» አለ ፖንሴ

«እንደወቅቱ ይለያያል። አባይ ዐማይጐርፍበት ጊዜ አንድ ጋላቢ በሸለቆው ውስጥ መንገዝ ይችላል።»

ካይሮን መቼ እንደለቀቁ ጆን ባፕቲስት ጠየቃቸው። ከርሱ በኋላ አስር ቀን ቆይተው መነሣታቸውን አሠሳ።

6

ከገዳሙ፣ በሲናር ጥላማ ጐዳናዎች ውስጥ ሊመሰሱ ዮሴፍ የተባሉት ሠው ራሣቸውን ከፍተኛ ሹብር ውስጥ ከትተው ነበር። ጉዞ ከመጀመራቸው አንድ ቀን ቀደም ብሎ፣ አባ ቬርሣው የሰጡት ከፍተኛ ማስጠንቀቂያ፣ በተደጋጋሚ ያደረጉት ቅስቀሣ፣ የካፑቺኖች ተንኰልና ትን ያልሆነ ሴራ፣ ባልታሰበ መንገድ አሁን አውን እየሆነ መምጣቱን ያሣያል። ሞቃቱ ለሊት ሊገለፅ በማይችል ስጋት ተዋጠ። ጀስዊቱ፣ ወደዚህ አገር የመራቸውን ዕለትና ወደዚህ አገር የጀመሩትን የጉዞ ዕለት ማሰብ ጀመሩ። እነዚህ ሁሉ በርሣቸውና በብርሃን መካከል እጅግ ብዙ ክብደት ያለው ጥቁር ድንጋይ የተጫነባቸው መሰላቸው። ፈረንሣዮች ሊጮሁ፣ አሪ ሊሉና ሊያሰቅሉ ይችላሉ። ወይም ሊሞቱ ይችላሉ። ታዲያ ማንም ሊያድናቸው አይመጣላቸውም። ይህ ክፉ ሣጣብ በአምሮአቸው ውስጥ እየተሸከረከረ ሣለ፣ ጀስዊቱ፣ እንደአሣነሪ በክፍተኛ ድምፅ ትንፋሻቸውን ለቀቁ። ጆን ባፕቲስት፣ በጣም ስለተበሳጨ፣ ይሆን ሊሰማ ወደማይችልበት ራቅ ያለ ቦታ በፍጥነት ሄደ። ወጣቱ ሰው፣ በካፑቺኖች ማስፈራራት ሳቢያ የተፈጠረበትን የቁጣ ስሜት ሳያገናዝብ ትክክለኛነት በሌለው ሁኔታ ሁሉንም ነገር በብሬቪደንት ላይ ይከምርባቸዋል። በዚህ አይነት ሁኔታ አንዳቸው አውጋሽ በመሆን ሌላኛው ተስፋ በመቁረጥ ሜትር ዝረሚ ወደሚጠብቃቸው ቤት በእግር ተጓዙ።

በቅጥር ግቢው ውስጥ ከስፈት በተሠራ የቅርጫት ክምር ላይ ተቀምጠ፣ ጭልጭል በምትል የፋናስ ብርሃን መፅሐፍ ያነብ ነበር። ፖንሴና ዮሴፍ ከፊት ሰፊቱ ባለው ግንዲላ ላይ ተቀመጡ።

«ካፑቺኖች ሁሉንም ነገር አውቀዋል» አለ ጆን ባፕቲስት

አባ ብሬቪደንት አይናቻቸውን አዙዘው መሬት መሬት ያያሉ።

«ስትል . . . »

ሜትር ዝረሚ፣ የጀስዊቱን ቂስ ማለቱ እንደሆነ በሚል አይናቹ ከጆን ባፕቲስት ላይ ሳይነቀሉ በእገፖ አመለከተ

«አይደለም፣ እንደመታደል ሆኖ የማያውቁት የሚመስለው አንድ ነገር ይህ ነው»

«ታዲያ ምን አለ?»

«ዋናው ነገር እኛ ለፈረንሣይ ኤምባሲ ሆነን መንዛችን ነው»

«ዝም፣ ዐጥ እንዲሉ ልንጠይቃቸው ይገባል» አለ

ሜትር ዠረሚ፣ ከተደላደለው መቀመጫው ላይ እየተጉተተ ተነሣ። ቅጥር ግቢውን የሚያካልሉት ከጭቃ የተሠሩት ግድግዳዎች ቁመታቸው በሰው ራስ ልክ ነው። በርቀት ያሉ ጭውውቶችን፣ የህፃናት ልጆችን እሪታዎች፣ በቅርብ ያሉ ማጉረምረሞችን፣ የውሾችን ፖሽትና የኮቴ ድምፆችን ይሰማሉ። ለሊቱ ጠፍ ጨረቃ ነው። ከላይ፣ በጥልቁ ሰማይ ውስጥ ከዋክብት ከብደው አሸብርቀዋል፣ ከባድ ነፋስም ያፏጫል።

«በትክክል ምን ይፈልጋሉ?» ሲል ሜትር ዠረሚ ሳይንቀሳቀስ፣ እንደቆመ ጠየቀ።

«ሁለቱ መነኮሳቶቻቸው አብረውን እንዲገዙ ይፈልጋሉ። እኛ ገብ ከጀመርን ከጥቂት ጊዜ በኋላ ካይሮ ውስጥ ቆንሲሉን አነጋግረው ነበርና አሁንም ከሃጅ አለ ተልዕኮ ጥቂት የማትረፍ ተስፋ አላቸው።»

«አሻፈረን ብንላቸውስ?»

«ለሲናር ንጉስ ሁሉንም ነገር ይነግራሉ። ይህ ደግሞ ምን ማለት እንደሆነ አስብ። ንጉሡ ሙስሊም ነው። ለአቢሲኒያ ንጉስ የራሱን አገር አቋርጦ ሐኪም እንዲሄድለት ሊፈቅድ ይችላል። ክፉርስቲያን ንጉስ የተላከ ኤምባሲ ግን ከቶውንም አይሆንም»

«እናስ?»

«ከሁሉም አስቀድሞ ምናልባት እንታሰር ይሆናል። ጉዳዩ በዚህ እንደማያበቃ ካፑቺኖች ፍንጭ ሰጥተዋል። በተለይም ሌሎች የውጭ ዜጐችን በሚመለከት መጥፎ አስባልታዎችን በማሠራጨት ረገድ ተራው ህዝብ በጣም ያምናቸዋል። እንዲያውም አስማተኞች እንደሆንን ሊነግሯቸው ይችላሉ። ይህን ደግሞ በሣጥኔ ውስጥ ያሉት ብልቃጦች ደጋፊ ማስረጃ ይሆኗቸዋል። ህዝባዊ ቁጣው አንገታችን እንዲቀላ ሊጠይቅ ይችላል። ንጉሡ ደግሞ በፈቃደኛ ነት ይፈፅምላቸዋል።»

«እንተስ ምን ነገርካቸው?» ሲል ሜትር ዠረሚ ጠየቀው

«እኔማ ነገሮችን ሁሉ ከሃጅ አለ ጋር ሆነን ማቀነባበር ይገባናል። ለዚህ ደግሞ ሁለት ቀናት ያስፈልጉናል አልኳቸው»

«ብራቮ፣ ታዲያ በነዚህ ሁለት ቀናት ምን ማድረግ እንችላለን?» ሲል ሜትር ዠረሚ ጠየቀ።

ምንም ዓይነት ሣጥን እንደሌለው ለማስታወቅ ፖንሴ ቅንድቡን ሸቅብ ገፋው። ሊሆን የሚገባውን ሣጥን በዝምታ ማውጣትና ማውረድ ጀመሩ። ሁኔታው አግባቢ ቢሆንም፣ ጀን ባፕቲስት፣ በርግጥ ስጋት አልተሰማውም። በዚህ ጊዜ ጉዞአቸው ፍፁም ድርድር ውስጥ በመግባቱና ዕቅዳቸው መሰናክል ስለገጠመው ቢበሳጭም፣ በስተመጨረሻው ግን ጉዟቸው እንደሚሣካ ርግጠኛ ነበር። በዚህ ልበሙሉነት ውስጥ የሣጡን እምብርት የያዘው የአሊስ ጉዳይ ነው።

«አንድ ካፑቺን ይዘን እንሂድ» አለ ሜትር ዠረሚ፣ ፍፁም ክስተር ብሎ «እናም ከዚህ አካባቢ በቀ ርቀት ላይ ስንደርስ ቀነጣጥሰን እንጣለው»

አባ ብሬቬደንት በድንጋጤ ዘለሉ። እንደተሰመደው፣ ንግግራቸው ለፐርቴስታንቱ ከማድረግ ይልቅ ለፖንሴ ነገሩት።

«የነዚህ ተሣድሶ ፍራንሲስካውያን በኛ ተልዕኮ ውስጥ መካተት ከተልኳችን መሰረታዊ ሁል ጋር በቀጥታ የሚጣረር ነው። ቀሣውስቱን የመግደሉ ጉዳይ ከሆነ፣ ሣጡ የሚመነጨው ሳቡም ፀረ ሣይማኖት ከሆነ አፅምሮ ብቻ ነው።»

«ሴላ የመፍትሔ ሣጥን እንዲያቀርብ ንገረው» አለ ሜትር ዠረሚ።

ፖንሴ ከመቀመጫው ላይ ተነስቶ በትንሿ ግቢ ውስጥ ብርሃን እስካለበት ጠርዝ ድረስ ጥቂት እርምጃዎች ተራምዶ ተመልሶ ወደ ጓደኞቹ መጣ። ፊት ሰፊታቸው ግትር ብሎ አንዛአ አላቸው።

«ዛሬ ሌሊት ለቅቀን መሄድ አለብን»

«ሰቅቀን?» አሉ ሁለቱም ሰመጀመሪያ ጊዜ በአንድ ላይ

«አዎ ሰቅቀን። ይህ ማለት ሁለት ቀንና ሁለት ለሊት እናገኛለን ማለት ነው። የካፑቺኖች ሰላዮች፣ እኛ ከተማው ውስጥ መሆናችንን እንዲያስቡ የሚያደርግ ማሳሳቻ ዘዴ ግን ማግኘት አለብን። ይህ እስኪሆን ድረስ እኛም በነርሱ ላይ ብልጫ ልናገኝባቸው የምንችላቸውን ጉዳዮች ማሰብ ይገባናል።»

«ስለ አገሩ አንዳችም ዕውቀት የለንም» አሉ አባ ብሬቬደንት

«ቅፍለቱም እስከ አንድ ሳምንት አይንቀሳቀስም» ሲል ሚትር ዠረሚ አከለ።

«ቅፍለቱን እንጠብቅም። ሃጅ አሊ መንገድ መሪያችን ይሆናል»

አንድ የቃለ ምልልስ የሚያደርግና ሰማሰብ የተጨነቀ ሰው፣ ትክክለኛውን መልስ ሲሰጥ ሰራሱ እንደሚሰማው ዓይነት፣ ፖንሴም በተናገረ ቁጥር መልሶቹ ይመጡለት ጀመር።

«እዚህ ቆይታችሁ የግል እቅምቾችሁን አዘጋጁ። በተቻለ መጠን ባዶ ይሁን። እኔ ሃጅ ዓሊን ለማግኘት እሄዳለሁ።»

እነርሱ ቃል ከመተንፈሣቸው በፊት እርሱ ተፈተለከ። በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ በየጥላው ላይ እየነጠረ፣ በተነጠፈው ቀጭን የድንጋይ መንገድ ላይ እየተደነቃቀፈ ሄደ። እንደ እድል ሆኖ፣ ቅፍለቱ፣ ከተማ ሲገቡ ሲሉ የሚሠፍሩበት ቦታ፣ ትልቁ የመዝናኛ አሸዋ ሜዳ በቀጥታ ከፊት ለፊቱ ነው። ችምችም ብለው ከተተከሉት ድንኳኖች መሃል ወደ ሃሰን አል ቢልቤሲ ድንኳን የሚያደርሰውን መንገድ መረጠ። እንደገመተው፣ ሃጂ አሊ ከቅፍለቱ መሪና ከሌሎች ብዙ ነጋዴዎች ጋር መሬት ላይ በተዘረጉ ምንጣፎች ላይ ተቀምጦ አገኘው። ሁሉንም ዙሮ ሰላም አላቸው። ትግስቱ እስከፈቀደለት ድረስ ቀስ ብሎ የሚጠጣውን ሻይ ፉት እያለ ከጨረሰ በኋላ፣ ሃጅ አሊን ለአስፈላጊ ቁም ነገር እንደሚፈልገው ገልፆ ጠየቀ። ግመል ነጅው ከጓደኞቹ ተነጥሎ ለመሄድ ከመወሰኑ በፊት ጥቂት ጊዜ ወሰደ። በኋላ ግን ፈቅዶ እንደወጣ ፖንሴ በቀጥታ ወደ ቤቱ አመራ።

«እንዲህ በድንገት ምን የሚያስጨንቅ ነገር ገጠመህ?» ሲል ሃጅ አሊ በደረቅ ቀልድ ጠየቀው።

«ዛሬ ሌሊት መንቀሣቀስ አለብን» አለ ፖንሴ

ሃጅ ዓሊ የተሰባበሩ ባዶ ጥርሶቹን በምፀት ፈገግታ ገለጣቸው

«ዛሬ ሌሊት?» ሲል ጠየቀው

«እየቀለድክ አይደለም»

«አለመታደል ነው» አለ ሃጂ አሊ እያፈዘ

«እና ብቻህን ልትንዝ ነው?»

«አይደለም ከአንተ ጋር»

«ድንቅ ነው። መጠኖ በሰው አዕምሮ ውስጥ ፍፁም ያልተለመደ ሃሣብ ስለሚፈጥር፣ ነብዩ የአልኮል መጠጥ እንዳይጠጣ በመከልከላቸው እናመሰግናቸዋለን።»

«አንዳችም የሚያሰክር መጠጥ አልቀመስኩም» አለ ጆን ባፕቲስት «እና የምነግርህን በጥንቃቄ እንድታዳምጠኝ አፈልጋለሁ። አለበለዚያ ነገ ጀርባህን ተተልትለህ አስር ቤት ነው የምትወረወረው።»

«ጀርባህን ተተልትለህ? በማን?»

«በንጉሡ»

ሃጂ አሊ ደነገጠ

«ካይሮ የሚገኘው የፈረንሳይ ቆንሲል፣ ከካፑቺኖች ጋር ወደ አቢሲኒያ እንዳትንዝ መፈለጉን ታስታውሳለህ?»

«ደህና አድርጌ አስታውሳለሁ»

«ቆንሲሉ ልክ ነበር። የተናገረውም ዕውነት ነው። እነርሱ ጥበቅ ሰዎች ናቸው። አንተን እንደተከታተሉህና የበቀል ዕርምጃ ሊወስዱብህ ሁለት ሰዎቻቸውን ልከዋል። አሁን ደግሞ አግኝተውሃል»

«እዚህ?»

«አዎን እዚህ። ቀግውስቱ እዚህ ከተማ ውስጥ ቤት አላቸው። ንጉሥ፣ እነሱን በጥሩ ሁኔታ ስለሚመለከቷቸው በማንኛውም ረገድ ከሰላ ይሰጧቸዋል።»

ሃጂ አሊ የፍርሃት ጅማሮ ተሠማው። ሰውነቱ ሲሸማቀቅ ያስታውቃል። ፊቱም ቀስ በቀስ የሚያዛዝን ገፅታ እየተነበበት ምህረት ለመለመን የተዘጋጀ መሰለ።

«በኔ ላይ ምን ወንጀል ሊያቀርቡብኝ ይችላሉ?» ሲል ጠየቀ

«በሁላችንም ላይ የያዙት ወንጀል ስላለ እዚህ ሊገቱን ይፈልጋሉ። ነገ ጧት ዶክተሮች ሳንሆን አስመሳዮች መሆናችንን ለንጉሡ ይነግሯቸዋል። ንጉሱም ያምኗቸዋል። የፊረንሣዩ ንጉስ ሉዊስ አስራ አራተኛ መልዕክተኞች መሆናችንን ይነግሯቸዋል። እናም ወደ ወህኒ እንጣላለን።»

ኧረ! ኧረ! በማለት ከጠቅላላው ድርሻው የሚያጣውን አጠቃላይ እድል በፍጥነት ሲያሰላ ሃጂ አሊ አቃሰተ።

«እናም ለንጉሡ ፊረንሣውያን ዶክተሮች መሆናችንን በሃሰት ተናግረህ ስላቀረብከን ተንርፈህ ወደ ወህኒ ትወርዳለህ»

«ግን» አለ የግመል ነጅው «አላወቅም ነበር አላለህ»

«ካፑቺኖች፣ ካይሮ ውስጥ ከቆንሲሉ ጋር ተነጋግረዋል። ሁሉንም ነገር እንደምታውቅ እነርሱም ያውቃሉ።»

በሃጅ አሊ ላይ ጠንከር ብሎ አፈጠጠበት

«እነርሱም ምንም ባይናገሩ፣ እውነቱን የምናፍረጠርጠው እኛው እንሆናለን። እነርሱ ምንም ባይናገሩ እኛ እንጠቅሠዋለን»

ምንም እንኳን በፊቱ ላይ ይቅርታ የለሽ ጭካኔ ያለበት መስሎ አረፍተ ነገሮችን ቢናገራቸውም፣ ጆን ባፕቲስት የሚያሣምን አልነበረም። ሃጅ አሊ የሠዎችን ባህርይ በማንበብ የሰለጠነ ነው። በዚህም ሳቢያ ፖንሴ መጨረሻው መጥፎ ጠላቱ ላይ እንኳ ቢሆን እንዲህ ያለ ነገር አያፈፅምም። የማስፈራራቱ ዓላማ በተዘዋዋሪ ዘዴ ግቡን መታ። የግመል ነጅው አስመታመን በፊቱ ላይ ጭንቀቱን ሲያጋልጥበት፣ የጆን ባፕቲስት የእውነት መንፈስ ደግሞ በንግግሩ ላይ ይታወቅ ነበር። ሃጅ ዓሊ፣ ሶስቱ ፈረንሣውያን በርግጥ በአደጋ ላይ መሆናቸውን አምኖ፣ የራሱ ጥቅም ምን ላይ ሊሆን እንደሚችል ገመተ። እነዚህ ሰዎች ጠፍተው ቢቀሩ አንዳችም ጥቅም እንደማይተርፈው ለመገንዘብ ብዙ ጊዜ አልወሰደበትም። እንዲህ ያለ ችግር በምድረ በዳው መካከል አጋጥሞት ቢሆን ኖሮ ቢያንስ የነርሱን ንብረት በሙሉ ይወስድ ነበር። አሁን ግን የሲናር ንጉስ ካሠራቸው ቀጣዩ ተግባር በነርሱ ሃብት ላይ እጃቸውን መጫን ነው።

አይሆንም! ቢል የርሱ ጠቀሜታ ሰዎቹን ንጉሡ ዘንድ በማቅረብ ላይ የሚመሠረት መሆኑን አረጋገጠ። የአቢሲኒያን ንጉስ፣ ፖንሴ በማግኘቱ በመደሰት ይበርቅና፣ ሃጅ አሊን ደስ በሚያሰኝ መጠን ሽልማት ይሠጠዋል። ከዚህም ሌላ ይህ ነጋዴ፣ ካይሮ የሚገኙትን ፈረንሣውያን ምስጋና ያገኛል። በነዚህ ግልፅ ምክንያቶች ጥቅሙ ተጓጉቶን በማዳን ላይ ይሆናል። በተጨማሪም ደግሞ፣ ፈረንሳውያኑ ከሲናር በግድ መሸሽ አሰባቸው። ስለዚህ የተወሰነውን ሻንጣቸውን እንዲሁ መተው ይገደዳሉ። ከዚህም ሃጅ አሊ፣ ትርፍራፊ አያገኝም። ስለዚህም ሳያቅማማ ውሳኔ ላይ ደረሰ። ይህን ሲፈፅም አስፈሪ መስዋዕትነት እየከፈለ መሆኑንም መግለፅ ይኖርበታል። በመሆኑም ፖንሴ በሚችለው መጠን በነፃነት ካሣ ይከፍለዋል።

ሃጅ አሊ ማቃሠት ጀመረ። የግርፋትና የእስራት ወሬ በተጀመረበት ጊዜ በፊቱ ላይ የፈነሠሠውን ላቡን ጠረገና የገዝዘብን ነገር ጠቀሰ። ከአስራ አምስት ደቂቃዎች በኋላ ስምፅኑት ላይ ተደረሰ። አራቱም፣ ማለትም ሶስቱ ፈረንሳውያንና ሃጂ አሊ በአንድነት ይንቀሳቀሳሉ። አምስት ግመሎችንና በጣም ጥቂት ሙነት ይይዛሉ። አያንዳንዱ ተጓዥ የግል ንብረቱንና መሳሪያውን በራሱ ግመል ላይ ይጭናል። የጭነቱ ግመል ሰንጉሱ የሚቀርበውን ገፀ-በረከትና የመድሃኒት ሻንጣውን ይሸከማል። ከዚህ የሚቀረው ሌላው ነገር ሁሉ ማለትም ሣይንሣዊ

መሣሪያዎቻቸው፣ ለየአካባቢው አስተዳዳሪዎች የሚሰጡ ገፀበረከቶችና የነርሱ የቀያሬ ልብሶች በዚያኑ ዕለት ምሽት ሃጅ አሊ ወደሚያውቃትና በሲናር ውስጥ በሚያልፍባቸው ጊዜያት በተለምዶ ሲያዕናናት የነበረች ባሏ የሞተባት ሴት ቤት ይመጣል። እርሱ እስኪመለስም ድረስ እነዚህን ትርፍ ንብረቶቻቸውን በጥንቃቄ ደብቃ ታቆየዋለች። በመጨረሻም ከዚህ አለት ጀምሮ ግመሎቹ የርሱ ንብረቶች እንደሚሆኑ ሃጅ አሊ መጭጭ አሉ። ፈረንሣውያን ስለጥቅሙ ሲሉ ከፍተኛ የኮሣ ግንዘብ ይከፍሉታል።

በአፀፋው፣ ሃጅ አሊ ካጋጠመው ጊዜያዊ ችግር ነፃ ለመውጣት ተስማማ። ሌላው ቀርቶ የነርሱን መጥፋት ሃሰን አል ቢልቤሲ ከለላ እንዲሰጠው ያደርጋል። ማንም ሰው ስለፈረንሣውያኑ ቢጠይቀው በወንዙ ዳር ያሉትን ዕፅዋት ለመመርመር ሄደዋል፣ ይላል። ሃጅ አሊም ሃይለኛ የራስ ምታት ስለያዘው በህመም ውስጥ ራሱን አግልሎ ተኝቷል። ሁሉንም ነገር በኋላ ያዩታል።

አንዳቸውም እንኳ ፅንቅልፍ ባይዛቸውም፣ አራቱም ዕረፍት ለማድረግ ጋደም አሉ። ከሃሰን አል ቢልቤሲ ጋር ለመመነክር የሄደው ሃጅ አሊ፣ በስምንት ሰዓት ላይ አንድ ግመል ይዞ መጣና ሁለቱን ሻንጣዎች በኮርቻው ላይ ጫነበት። የየግላቸውን ኮርቻ ተሸከሙና ግመል ሃጅውን በመከተል፣ ሦስቱ ፈረንሣውያን መንገዱ ውስጥ ሹልክ ብለው ገቡ። ከቅፍለቱ ጥቂት ርቀት ላይ ታስረው የነበሩትን ግመሎቻቸውን ጥቁር ቀለም በሚመስለው ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ አቻኩሏቸው። ደግነቱ፣ ሃጅ አሊ መንገዱን ደህና አድርጉ ያውቀዋል። እንደ ሽሽት የሚያፅናና ስለሌለ የፍርሃት ስሜት የለባቸውም። ለብዙ ሰዓታት በጥንቃቄ ተጓዙ። ከዚህ በኋላ ከተማው ከነርሱ ብዙ ርቀት ወደኋላ ነው። የውሾች ፖኸትም አይሰማም። ወንዙ ካለበት በስተግራ በኩል ርጥበት አዘል ነፋስ ሽው ይላል። የጥቁር አባይን አቅጣጫ ተከትለው ሽቅብ እንደሚጓዙ ገመቱ። የማለዳው የንጋት ብርሃን ሲፈነጥቅ ፊት ለፊታቸው ከሽንብቆ ደን አጠገብ የጭቃ ጉጆዎች ብቅ ብቅ ሲሉ፣ በወንዙ ዳር ሆነው የሌሊቱን ቅዝቃዜ ለማባረር ሲሉ ደንግጠው የሚጫጫሁ መንጋዎች ተመለከቱ። በዚህ አካባቢ የአባይን ወንዝ ከዳር እስከዳር የሚያቋርጠው የእንጨት ድልድይ አለ። ይህን በሠላም ካቋረጡ በኋላ የተቀመጡባቸውን እንስሳት ወደ ሃምራዊው የምስራቅ ብርሃን እንዲጋልቡ ኮረኮሯቸው።

አሲስና ፍራንቾይዝ በመድሃኒት ቀማሚው ቤት በረንዳ ላይ በየዕለቱ ማለዳ የሰመዱት የተደጋገመ ምስጢራዊ ግንኙነት እነርሱ ከገመቱት ቀደም ብሎ ስጋት ያንጣባበበት ጀመር። ሰላማዊውና ህክምናቸውን ሳይቃወሙ በመቀበል እንዳችም ችግር ያልፈጠሩባቸው አባ ጋበሪ በድንገት ታመሙ።

ከእለታት አንድ ቀን በተለመደው ሰዓት ላይ አሊሰ ልታያቸው ስትመጣ፣ ግማሽ ሰውነታቸው ከተኙበት ረዥም ሶፋ ላይ ወርዶ፣ አንድ እጃቸው ከመቀመጫው ላይ ቁልቁል ተንጠልጥሎ፣ አንዱ አይናቸው ብልጥጥ ብሎና አፋቸው ተጣምሞ አገኙቸው።

ሽማግሌው ሰው በህይወት ቢሆኑም፣ መንቀሳቀስም ሆነ መናገር አይችሉም ነበር። የርሳቸው መጥፋት ማለት ገና በጅምር ላይ ያለውን፣ ለጋውን የወይዛዝርት ንደኝነትም እንዲያከትም የሚያደርግ ነው። ቆንሲሉ ይህንን መነሻ ሰበብ አድርጉ ስለ እዕዋቱ ሲባል ልጁ የምታደርገውን ወጣ ወጣ ማለት በአስቀያሚ ግዴታ ሊያዝዝ እና እንዲያበቃ ሊያደርግ ነው። ልጁ ግን ለስለስ ባለ ገሰፃ «ለዚህ ቤተ ሙከራ ባለቤት» ቃል መግባታቸውን አስታወሰች። አባቷ ትክሻውን ነቀነቀ። ለጥንድ ሌቦች እነዚህ ጥሩ ውሎች ነበሩ። ጉዳዩ፣ አሲስ ባልተገመተ ሞንካራ የአባቷን ምኞት ተቃውማ ጭቅጭቅ ተነሣ። በመጨረሻም፣ ከዚህ በኋላ በእናቷ በማዳም ዴ ማይሌ አጃቢነት በዚያ የሙከራ ቦታ ያለውን ተግባሯን እንድትቀጥል አግባባችው። እናቷ አጅባት በመጣችበት በመጀመሪያው አለት የዕፅዋቱን ሁኔታ በተመለከተ ዝርዝር ማብራሪያ እንድትሰማ አደረገቻት። በእርግጥም ሌላ ሰው የሌለበትን የራሷን ግኝቶች ለዚሁ ዕለት ሲባል እንዲካተቱ ብዙ የላቲን ቃላትን በመጨመር አብራራች። በየአንዳንዱ ሲጋ ተክል አጠገብ ለረዥም ሰዓት በመቆም በድንገት አንድ ፍፁም ልዩ የሆነ ዝርያ ዘንድ ደረሰች። ምስክሷ እናት በጣም በከባዱ ተሰላቸችና የራስ ምታትና የእግር ቁርጥማት እያመማት ወደ ቤት ተመለሰች። ልጇን አጅባ ወደ መድሃኒት ቀማሚው ቤት ለሁለተኛ ጊዜ ስመሄድ ሰራሷ ቃል ብትገባም ይህ የመጨረሻዋ ሆነ። በእዕዋቱ ማሳደጊያ ቤት ውስጥ ያለው አየር ለጤንነትዋ መጥፎ መሆኑን ብታስታውቅም፣ ለልጅዋ ግን ከፍተኛ ጥቅም እንዳገኘላት መቀበሏን ገለፀች።

አሊስ ለእዕዋት ያላት ፍቅር ጉዳት የሌለው ነው። እንዲያውም ይህን ፍቅሯን በማርካት ፋንታ መቃወሙ ሌላ ስጋት ሊፈጥር እንደሚችል፣ ማዳም ዴ ማይሌ ባሏን አግባባችው። ቆንሲሉም ለማመን ፈቃደኛ ሆነ። የሴት ልጁን ጉብኝት በተመለከተ ከውጭ ዜጐች ማህበረሰብ አንዳችም ያለመስማማት ሽክሽክታ አልደረሰም። እንዲያውም የአንድ የሆነ ነጋዴ ወንድ ልጅ፣ የራሱን ደርቀው የሚቀመጡ እዕዋት የማቆየት ስራ መጀመሩን እያመሰገኑ ይነግሩት ጀመር። አሊስ፣ ይህንን ጉብኝቷን ፍፁም እንዳታቋርጥ ወይም በቅርብ የሚደረግባትን አጀብ ፈርታ ነበር። ከዚህ ይልቅ አባቷ ብቻዋን እንድትሄድ ስለፈቀደላት ፍራቻይዝን ያስተቆጣጣሪ ማግኘት ቻለች።

ጊዜው የደስታ ወቅት ነበር። ወጣቷ ልጃገረድም ፍፁም የመለወጥ ስሜት አደረባት። የመጀመሪያው ምልክት ይህን ጉዳይ በመምራት ረገድ በጥንካሬና በቆራጥነት አባቷን መጋፈጧ ነበር።

በመጀመሪያ ላይ ሁሉም ላይ ላዩን ባሉ ሁኔታዎች ተመስጠው ነበር። ጓደኛ እጅግ ያስፈልጋት በነበረበት ዕድሜዋ ላይ፣ አሊስ ጓደኛ ተለለለች። አሁንም ምኞት የሚነሣትን የአካሏን ውበትና አዲሱን ቁመናዋን፣ አንዳች ከፍተኛ የመንፈስ ሃይል ጥንካሬ ቢያስፈራራትም በክብር ልትጠብቀው ፈለገች።

አዲስ የፀጉር አሠራር ዘዴ ለመሞከር ጊዜው ስለነበር፣ አሊስ ወደቤት ከመመለስዋ በፊት ቀትር ላይ ነባሩን አሠራር በችኮላ ፈታችው። የናቷን ቆንጆ፣ ቆንጆ ሙሉ ልብሶች በድብቅ በክረጢት ይዛ ከቆንስሳው እየወጣች ታመጣለች። በብርቱካን ዛፎች ስር፣ ጥላ በጣለበት እርከን ላይ እየለበሰች ለጓደኛዋ እያሣየችና እየሳቀች ትራመዳለች። ወጣቷ ልጃገረድ አጠቃላይ የሆነ የውበትና የቁንጅና አስተሳሰብን ብቻ ሳይሆን፣ እያንዳንዱን ዝርዝር እንደምን ዋጋ ልትሰጠውና የሚገባውን ሙሉ ድርሻ አንዳታሳንስበት ፍራንቾይዝ ታስተምራታለች። አሊስ እያበበች ነበር።

ይህን ዘመን ወደኋላ መለስ ብላ ስትመለከተው፣ ራሷን ለማግኘት በሞኛ ሞኝ ስሜት ተውጣ በነበረበት ጊዜ፣ ፍራንቾይዝ ያን ያህል ትዕግስትና ደስታ ስላላየቻት ፍፁም የማይረሣ ውለታ አለባት።

ቀስ በቀስ ይህ ነው በማይባል ጉዳይ ውስጥ ገቡ። አሊስ ስለንብረቶችዋ ጠንቃቃ የነበረች ቢሆንም ልካቸውን ስለምታውቅ መጨነቋን ትታለች። ከዚያ ጊዜ ወዲህ አዲስ ሰላም ሰራሏ ፈጠረች። ጥልቅ የሆነ የራስ መተማመን አዳበረች። እነዚህን ሁሉ በንግግራና በባህሪዋ ትህትና ሸፍና ለማቆየት ብልህነቱ ነበራት። በተለመደው ሁኔታ እናቷ ምንም አዲስ ነገር አታስተውልም። ምንም እንኳ እናቷ ባለመቅረቧ ብታዝንም ምስኪኗ ሴት ያስተማረቻት ነገር አለመኖሩን ተገንዘበች። ታሳቅ ልብወለድ ሊነፍበት ከሚችለው የፍራንቾይዝ ሕይወት ጋር የሰማይና የመሬት ያህል ልዩነት አላት።

የተወለደችው ግሬኖብል ውስጥ ሲሆን፣ አባቷ ሞልቶ የተረፈው የእህል ነጋዴ ነበር። ወላጆችዋ አምብዛም ስለማይከታተሏት ብድሯን ለመመለስ በአድሚው ሠላሣ አመት ከማበልጣት ጋር ፍራንቾይዝ ከበለጸች። ሰውዬው የንግድ ስራ ላይ ቢለማራም ጠበቅ አድርጉ አልያዘውም። ሃብታምም ባይሆን ገንዘብ ያለን ነበር። ይህ ደግሞ ከፍራንቾይዝ አባት ባህርይ ጋር ፍፁም ተቃራኒ ነበር። ይህ ፍቅረኛዋ፣ ንግግር አዋቂ፣ ምስራቃዊውን ዓለምና ኢጣሊያንን የሚያውቅ ነበር። ሰውዬው ይዟት ዜደ። ይህ ማለቂያ የሌለው የጀብዱ ሕይወታቸውን የጀመሩበት ጊዜ ነበር። ፍራንቾይዝ፣ ያንን ወቅት እንደ አንድ ሺህ አንድ ለሊት ተረቶች፣ በትንሽ በትንሹ ትተርከዋለች። በክብለላ ተጀመረ። ሃብት ተገኘ። ዙሪት ተጀመረ። በድህነት ተደመደመ። ሁሉቱ የጠፉ ፍቅር ነበራቸው። በኋላ ግን ለስደት ተዳረጉ። ትዋለት ተጀመረ። ቁማር ተለመደ። የከፋ ድህነት ሰተት ብሎ ገባ። ካይሮ ከደረሱ በኋላ ዳግመኛ አይን ላይን አልተያዩም። የሚቀጥለው ምዕራፍ ከደጡ ወደ ማጡ እንዲሉ፣ ከገደል ወደ አዘቅት ወረደ። ሰውዬው በቆሻሻ የአረቦች መኖሪያ ብቻውን ኖሮ ሊሞት ምዕራፉም ተዘጋ። ከዚህ የማይታመን የአኗኗር ታሪክ፣ ፍራንቾይዝ የሰጠችን ስዕል ትሰላለች። ታሪኩንን ትጽፋለች። ጥቂት ስለ ወባይ ትገልፃለች። እርሷ ልትጠቀምባቸው ባትችልም ምክሮችዋን ትሰጣለች። ትንታግነቷ በዕድሜና በግዴለሽነት ሳቢያ ጠፍተውባታል። ፍራንቾይዝ በመደሃኒት ቀማሚዎች ስለተቀጠረችበት ባወራች ቁጥር፣ ሜትር ዝረሚን ያለስሜት ዘቅጣው እንደማታውቅ አሊስ ልብ ብላች።

«ታፈቅሪዋለሽ?» ስትል ወጣቷ ልጃገረድ ጠየቀቻት

«ግልፅ እንድትሆኚ ጠይቂኝ ነበርና እኔም በግልፅ እነግርሻለሁ።» አሰቻት ፍራንቾይዝ «ሞኩና ወኔ ያለው ሰው ነው። አምን፣ አፈቅረዋለሁ ብዙ አምናለሁ»

«ነግረሽው ታውቃያለሽ?»

«ኦ! በርግጥ አታውቂውም ማለት ነው። አኩራፊና ግልፍተኛ ሰው ነው። ልንገረው እያልኩ ከዛሃ ጊዜ በላይ አስቤያለሁ። ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ በአይኔ ሣይዞር ምን እንደምናገር አስባለሁ። እንዳይነጋ የሰም፣ ሲነጋ እዚሁ እደርሣለሁ። በነዚያ ጨፍጋጋ አይኖቹ ሲያየኝ፣ ወኔዬም ድራሹ ይጠፋል። አየሽ፣ የዚህ አለም ሴት እንደሆንኩ አስመስላለሁ እንጅ፣ ያንቺ ያህል እንኳ ላከናውን የምችል አይደለሁም. . .»

ይህች አነስተኛ እውነት፣ ፍራንቾይዝ በነገረቻት ሁሉ ላይ የሚታከሰውን ግምት ከፍ ያደርግላታል። በልጅነት ዘመኗ የፈፀመችውን አደገኛ ሁኔታ ስትናገራቸውና የውድቀት ጊዜያቶቿን ስትነግላቸው፣ ፍፃሜውን ለማሣወቅ የተከተለችው ስልትና ገና ደፍራ ያልገለፀቻቸውን ሁሉ የምታስረዳው በንፁህ መንፈስ ነው።

አሊስ ታደንቃታለች። ይህን አይነት ስሜት በአንድ አገልጋይ ላይ ማሣደር፣ አባቷን ያስቀይመው ነበር። ነገር ግን አሊስ በተሰየ መልክ ተመክሰተችው። ፍራንቾይዝ ነፃ ሴት ነበረች። ነፃነቷን ለማግኘት እጅግ ከፍተኛ ዋጋ ከፍላለች። የደረሰባትን ሁሉ ፈፅሞ አዝናበት አታውቅም ።

እስከዚህች ሰዓት ድረስ አሊስ የምታስበው፣ የአንዲት ሴት ምርጫ ሽንፈት ብቻ ይመስላት ነበር። የፍራንቾይዝ ሕይወት ግን አማራጮን አቀረበላት። በዚህች የዕድሜ ባለፀጋ ሴት ማነሣሣት የአሊስ ሕልሞች ይበልጥ ለጀብዱና ለምስቅልቅልነት ተዘጋጁ። አሊስ የራሷን ነፃነት እንደቅዠት ስታስበው፣ ከጆን ዣፕቲስት ጉን ፈረስ ስትጋልብ ይታያታል። በመጀመሪያ ነገር በርስዋ ዙሪያ እርሱን ልታወዳድረው የምትችለው ሰው ስለሌለ ይመስላት ነበር። ነገር ግን ፍራንቾይዝ በተለየ መልክ አማባቿት።

«ሕልሞችሽን ፍፁም አጠንክሮ የሚይዝብሽ ወንድ ካለ፣ እንዲህ በቀላሉ የሚለቀቅ አይደለም» አለቾት ራሷን እየነቀነቀች።

7

ለዛያ አንድ ቀናት በእግራቸው ተጓዙ። ሽሽት በጀመሩባቸው የመጀመሪያ ሰሞን፣ በሲናር ንጉስና በሰራዊቱ ክትትል እየተደረገባቸው እንደሆነ እርግጠኞች ነበሩ። ካደረባቸው ፍርሃት በመነጨ ንጉሡ ካሳቸው ስልጣን በላይ የትም ቦታ የሃያልነታቸውን ምልክት እንደሚያዩ ይገምቱ ነበር። ክትትል እንደማይደረግባቸው ራሣቸውን ለማሣመን የአንድ ሣምንት ጊዜ ወስዶባቸዋል። ክንፍ አላቸው ብለው በሚያስቧቸው በንጉሱ ምስጉን ወኪሎች ተቀድመው እንዳይሆን ሁሉ ይሰጉ ነበር። እውነታው ግን፣ በሰፊው የምድረበዳ ግዛት ውስጥ እነርሱ ራሣቸው ጠፍተዋል። እውነተኛው ጠላታቸው፣ የማይታየው ገዥ ወይም ቅንነት የሌላቸው ካፑቺኖች ሣይሆኑ፣ ውሃ፣ ምግብና ፅሪፍት ሳያገኙ የሚያቋርጡት አገር ነው።

ምድሩ ሰጥ ያለ ሜዳ ነው። አልፎ አልፎ በሚታይ፣ ፀሐይ የጋገረችው የሚመስል የቋጥኝ ነጠብጣብና የአሸዋ ወንዝ ሸለቆዎች እየተፈራረቁ ያሉበት እጅግ ሰፊ የሆነ ደረቅ አገር ነው። በዚህ ሸለቆ ውሃ የሚወርደው በዓመት አንድ ጊዜ ታሳት ጉርፍ ሆኖ ነው። ነገር ግን ይህ ጉርፍ ከሌሎች የውሃ መስመሮች ጋር ከመቀላቀሱ በፊት አፈሩ መጥቦ ያስቀረዋል። በዚህ አንግዳ በሆነ ሸለቆ ውስጥ ያለው ሣር ቅጠል በሽመል፣ በመታ፣ በማዙብ ላይ ባሉ የቆንጥር አሾሆች፣ ብዙ ውሃ በሚይዙ ሹል ወፍራም ቅጠል ባላቸው ተክሎችና በግራር ዛፎች የተሞላ ነው። የነሸሸላ ቁጥቋጦና የቀንጠፋ እሾት በምድሩ ላይ ወፍራም ምንጣፍ ሆነው በዘያ ቦታ መቆየትን አስቸጋሪ ከማድረጋቸውም በላይ አንዳንድ ጊዜ ጉዟቸውንም ይጉቱባቸው ነበር።

ሞነታቸውን እጅግ በጣም ቀንሰው ስለነበር፣ ኩበሳሞቹ መከላከያ የሚሆናቸው ድንኳን ወይም ተንጠልጣይ የጨርቅ አልጋ ወይም ብርድልብስ አልነበራቸውም። መሬት ላይ ይተኙ ሉ። በምድረ በዳው ውስጥ ከናዝራ፣ ከጊንጥና ከመርዘኛ እባቦች መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል። ሣር ቅጠሉ ጥቅጥቅ ባለበት ቦታ መንገድ እየጣሱ ሲንዙ በጣም ትልቅ ዘንዶ አጋጥሟቸው ነበር። ከዚህም በላይ የሰው ልጅ ምንም ያህል ቢፈራቸውም፣ ፈጣሪ የፈጠራቸውና ለውን ዘመናሪያ ጫካቸው ውስጥ አማድያው ወደ መሠሎቹ እንዲዜድ የሚያባርሩት ትንሾችና ሌሎች ሣያነቶች የተባይ ዘሮች ነበሩ። ከሲናር በሽሹ በመጀመሪያው ሰሞን አንድ ቀን አባ ዲ ብሪዘኤያንት ቁርጭምጭሚታቸው ላይ በአንድ ትልቅ ናዝራ ተነድፈው ነበር። ሕመሙን

ለማስታገስ ፖንሴ መድሃኒት ቢሠጣቸውም፣ እብጠቱ በእግራቸው ሁሉ ላይ በመሠራፈጡ ትኩሣት ፈጥሮባቸው ነበር። በዚህ ግዚያ ጉዞው ፍፁም የስቃይ ሆነባቸው። ሆኖም ቀስ በቀስ ሀመሙ እየቀነሠና እየተሻላቸው ቢመጣም ከዚያ ወዲህ እየደከሙ፣ እየደከሙ መጡ።

እየተሣደዱ መሆናቸውን ባሰቡ ቁጥር፣ መንደሮችን ለዚያውም ጥቂት የከብት አርቢዎች ጐጆዎች ያሉባቸውን ሰፈሮች መተው ጀመሩ። የውሃ ቀርበታዎቻቸውን ለመሙላት ወደ ጉድጓዶች የሚሄዱት በሌሊት ሆነ። ክሲናር የያዙት አንድ ጀንያ ደረቅ ባቄላ ሳያልቅባቸው፣ ከመንጋዋ ተነጥላ የጠፋች ጥጃ አግኝተው ይይዛሉ። ሃጅ አሊ በአምነቱ ስርዓት ካሪዳት በኋላ የሴፍ እንዲገፍፉት አዘዛቸው። ሙስሊም አርዲት፣ ካቶሊክ በልቷትና ፕሮቴስታንት ተመግቧት ያበቃቸውን ጥጃ የአይሁድ ራባይ አጥንቶችዋን እንዲቆረጣጥም ካልተጋበዘ በስተቀር፣ ሌላ የክርስትና መስመር ተከታይ አይገኝም። ያልተበላውን ቀሪ ክፍል በኮርቻቸው ላይ ጫኑ። እንደአሰመቃደል ሆኖ አንድ እረኛ አይቷቸው ስለነበር የማስጠንቀቂያ ምልክት አሰማ። ወዲያውኑም ጦርና አጫጭር የነሃስ ጉራዴ የያዙ የጥቋቁር ሰዎች ሠራዊት ወረራቸው። ፖንሴ፣ የቁጥራቸውን ሙበዛት አይቶ መሸሽ የሚሻል መሆኑን ሲገምት ሜትር ዝረሚ ዘልሱ ጉራዴውን ያዘና ጮኸ።

«ኑ ወደኔ ጌቶቼ!»

ጆን ባፕቲስትም መሣሪያውን አፈፍ አድርጐ ጓደኛውን ለመከላከል ገባ። አስቀድመው የደረሱባቸውን ሁለት የአካባቢው ተወላጆችን አጠቋቸው። እጅግ ፈጣን በሆነው ለአይን በማይታየው የረዥም ስለታምና ሹል ጉራዴ የእንቅስቃሴ ፍጥነት፣ ሁለት አጥቂዎች አይኖቻቸውን ጐልጉለው፣ ሰውነታቸው እንዲወጋ የፈቀዱ ያህል ዘለው ገብተው ተወግተው ወደቁ። በዚህን ጊዜ ሁለት ሌሎች አጥቂዎች ተኳቸው። በተግባር፣ ቁጥር ውስጥ ሲገቡ በማይችሉ ተጋጣሚዎቻቸው እንቅስቃሴ ተደነቁ። የጉራዴዎች መፈጨት አሸበራቸው። ሌሎች የአካባቢው ተወላጆች አንድ በዓል የሚያከብሩ ይመስል እነዚህን ነጠላ ውጊያዎች ከብበው ይመለከቱ ጀመር። ሁለቱ እንግዶች እንደ የውሃ ተርብ ክንፎች በሚርገበገቡት በረዣዥም የብረት ዘንጐቻቸው ላይ አካላዊ ብርታታቸውን ተጠቀሙ። ተቃዋሚዎቻቸው የሚደርስባቸውን ሞት ለመከላከል ከባድ ጦሮቻቸውን ተጠቀሙ። አንዳንዶቹ የቆዳ ጋሻ አንግበዋል። አንድ ምት ሊያርፍባቸው፣ በሁለት ሌሎች ይተካሉ። የቆሙት ጥቂቆሮቹ ሰዎች ቁጥራቸው ከሁለት መቶ በላይ ስለሚሆን ውጤቱ የሚያጠራጥር አይደለም።

መራቱን እየደመደሙ በእግራቸው ቁርጭምጭሚት ላይ ያለሯቸው አምባሮች እንዲንቃጨሉ ያደርጋሉ። ፖንሴና ጓደኛውን እየከበበ ያለው መስመር ፍፁም ጠበበ። ድካም ሲያሸንፋቸው አጥቂዎቻቸው በቀላሉ አንገቶቻቸውን እያነቁ መሳሪያዎቻቸውን በመማረክ ሲጥ ያደርጓቸዋል። በዘቡ መካከል ፖንሴ በሲጋጣሚ ዮሴፍን ተመለከታቸው። ሕዝቡ እርሳቸውን አልከበባቸውም። እጃቸውን በጉናቸው ላይ እያወዛወዙና ምን ማድረግ እንዳለባቸው መወሰን ሳይችሉ ከግመሎቻቸው አጠገብ ቆመዋል።

«ሽጉጡን» ሲል ፖንሴ ጮኸባቸው

ጀስዊቱ ግራ የተጋቡ ይመስላሉ

«ኮርቻዬ ቦርሣ ውስጥ የተቀባበለ ስላለ ይተኩሱ!»

ክቡ በዝግታ ግጥም አለ። ቅላፄ ካለው የእግር እርገጫ ስር እርቃናቸውን ያሉ፣ ሰቁጥር የሚያታክቱ ቀጫጭን እግሮች ከሚያነሱት አቧራ በስተቀር ፖንሴ ሌላ ማየት አቃተው።

በድንገት ሁለት የተኩስ ድምፅ ምድሩን አናወጠው። የአካባቢው ተወላጆች በያሉበት ፀጥ አሉ። ለሠላሣ ሴኮንዶች ያህል ሁሉም ነገር ዐኖ አለ። ከዚያ በኋላ ቁስለኞቻቸውና መሣሪያዎቻቸውን ጥለው እግሬ አውጭኝ አሉ።

ከአፈሙዛቸ እየበለለ የሚወጣውን ጭስ እየተመለከቱ ጀስዊቱ በፍርሃት ሽጉጦችን እንደያዙ ናቸው።

«ደግ» አለ ዝረሚ ወደ የውሽቱ ዮሴፍ እየተራመደ «ይህን ድል አድራጊነት ብለህ ልትጠራው ትችላለህ። በሁለቱ ሽጉጦች እዚህ ለራስህ ግዛተ ዘውድ መመስረት ትችላለህ»

ለጀስዊቱ ፈገግ አለላቸው።

«እርግጠኛ ነኝ፣ በቀላል መግባባት ሁሉም ወደ ካቶሊክነት ሊለወጡ ይችላሉ።።»

ጀስዊቱ ትከሻቸውን ነቀነቁ። ግጭቱን በርቀት ለመመልከት የወሰነውን ሃጅ አሊን በአንድ እሾሃማ ቁጥቋጦ ስር ሆኖ አገኙት። ብዙና ጠለቅ ብሎ የተቦጫጨረውን ሰውነቱን

እንዲያክምለት ፖንሲን ለመነውና የቁስል መጥረጊያውን እንደ ሀማዕት ተቋቋመው። ከአራቱ ተንገሮች መካከል ከዚህ አጭርና የድል አድራጊነት ተጋድሎ በኋላ ቆስሎ የተገኘው እርሱ ብቻ ነው።

የንጉሱ ብቀላ ሊደርስባቸው ከሚችለው እጅግ እርቀው መገኘታቸውን በመገመት፣ በየመንደሩ ጥጋጥግ እያንዣበቡ መጎዝ የአካባቢውን ተወላጆች ጥርጣሬ ከሚያስፈልገው በላይ ስለሚቀሰቅስ፣ እንደ ሰላማዊ ተንገሮች በግልፅ መሄድ እንደሚሻል ጆን ባፕቲስት ገለፀ። ከዚህ በኋላ ሕይወታቸውም ይበልጥ የተመቻቸ ሆነ። የሚያገኟቸው ጉሳዎች፣ ጥቃት የሌለበት መስተንግዶ ያደርጉላቸዋል። ክርቀት ቦታዎችም፣ ነፖን ቆዳቸውን ሰማየት ይመጡ ጀመር። አንዳንዶችም እየፈሩ ይነኳቸዋል። የአካባቢው ተወላጆች ሞቅ ያለ አቀባበል ያደርጉላቸው ጀመር። የተጣሏቸው ጉሣዎች የተጋጫቸው፣ ንብረታቸው በድብቅ በመወሰዱ ተቆጥተው ነው። በወዳጃዊ ስሜት ከተጠየቁ ያላቸውን ለመስጠት ወደ ኋላ የማያሉ ናቸው። ለተንገቦቹ የማሽላ ቂጣዎችና አፍሪካውያን ከፍተኛ ጥራት ያለው የሚሉትን ትኩስ የላም ደም ተደባልቆበት የተመታ ትልቅ ወጪት ውተት ይሰጧቸዋል። እንደ ቀላል የመልካም አቀባበል ማረጋገጫ ከዘመዶቻቸው ውብ የሆኑ ኮረዳዎችንም ያቀርቡላቸዋል። ፖንሲና ሜትር ዝረሚ ለረዥም ሰዓታት በኮርቻ ላይ ስለሚውሉ አልጋ ላይ ከወደቁ በኋላ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ከመተኛት ሌላ የሚያስቡት የለም። የተመረጡላቸው ሴቶች ከጉናቸው እንዲተኙ ቢጋብዙም፣ ጥቂትም ሣየቆዩ ማንኮራፋት ይጀምራሉ። ከማንቀላፋታቸው በፊት ግን ተንዳኞቻቸው ሙሉ አካላዊ ክፍላቸውን ያሳዩዋቸዋል። በኋላ እንደገለፁላቸው ከዚን እነዚህ አብረዋቸው እንዲያድሩ የሚደረጉት ወጣት ሴቶች አብይ ተግባራቸው፣ በሚቀጥለው ቀን ለማህበረሰብ በሞላ የነዚህ የተንገቦች ፍፀም የግላቸው የሆነው የአካል ክፍላቸው ምን አይነት ቀለም እንዳለው ሪፖርት ማቅረብ ነው። ለእነዚህ ተወላጆች ይህ እንግዳ የሆነው ነጭ የቆዳ ቀለም ከባዕዳኑ ሰውነት ላይ፣ ከላይ እስከታች ድረስ መገለፁን የአይን ምስክር ሆኖ የሚያረጋግጥላቸው ስለሌለ ለማሣመን አስቸጋሪ ነበር።

አባ ብሬቪዩን የሚደረግላቸውን ክብር በምንም መልክ እምቢ እንዳይሉና እነርሱ የሚያርጉትን እንዲከተሉ ጓደኞቻቸው መክረዋቸው ነበር። እርሳቸውም፣ ለዘንዶ እንዳይጣሉ በመፍራት ሌሊቱን ሙሉ የፀፀት ፀሎት ሲፀልዩ ያድራሉ። በእግራቸው ላይ ካለው እብጠት፣ ዘለፋል ቢድኑም፣ ባጋጠማቸው መከራ ቢደክሙም፣ የተራቸውን የጤንነት ጉዳይ ይበልጥ

አባባሉት። ሜትር ዝረሚ እያሾፉ ክብረ ንፅህናን መጠበቅ አስፈላጊ እንዳልሆነ የቅዱስ አግናጢዮስን ትዕዛዝ በመውሰድ፣ እንደራሣ መሆን ነውና ጥቅም የለውም ይላል።

ሃጅ አሊ፣ እንዲህ ባሉ ትክክለኛውን ነገር በመፈፀም ጉዳይ ራሱን አያስጨንቅም። እርሱ አሁን እየተጨነቀ ያለው በወጉት አሾሆች ሲሆን ለአመል ሊነኩት ይሙሃል። የሚያደርገው ቢኖር የነዚህን ያልሰለጠኑ ሰዎች ባህል ማንኳሰስና እስልምና እስካሁን እነርሱን ባለማሰልጠኑ በማዘን የሚሰጠው አስተያየት ነው።

በዚህ አይነት ሁኔታ ከአንዱ መንደር ወደ ሌላው ለአምስት ቀናት ከተንዙ በኋላ፣ ገረፊም ከተባለ ትልቅ ከተማ ደረሱ። ገረፊም፣ በዘንባባ ዛፎች የተከበበች፣ በንዋባ፣ በሮማን፣ በአቦካዶና በብርቱካን አበባዎችና ፍሬዎች የተዋበች ነች። በቀቀኖችና ሌሎች ብሩህ ቀለማት ያሏቸው አዕዋፋት በየዛፎቹ ውስጥ አርፈው ሲታዩ ለበዙ ቀናት የተንገቦቹ ብቸኛ አጃቢዎች ሆነው በሰማይ ላይ ይታዩ ከነበሩት ጥንብ አንሣዎች ይልቅ ተስማሚ ሰውጦች ናቸው።

አሁንም ረዥሙንና ሰሙን የሰሜን ሽለቆ እስኪደርሱ ወደ ሰርክ የሚወስዳቸው ገና የሁለት ቀናት አጫጭር የምድረበዳ ጉዞ ይቀራቸዋል። የጥጥ ተክል በስበሱ ነጫጭ ኮረብታዎች ዙሪያዋን የተከበበችው ከተማ፣ ትልቅ የንግድ ቦታ ነች። በከተማዋ መካከል እረፍት የሰሸ ገበያ አለ። ከአካባቢው በሚጐርፈው የስራ ውጤት የሚያማምሩት ደማቅ የጥጥ ልብሶች፣ በከተማው ውስጥ ተሸምነው በጥሬ ማቅለሚያዎች፣ በክርሚን፣ በጥቁር ሰማያዊ፣ በብርቱካንማ ቀለማት ተሰርተው ይታያሉ። የቅመም መዓዛ በገበያው አየር ውስጥ ይንሣፈፋል። በየመደብሩ፣ ውብ ሽታ ያላቸው የኢትዮጵያ ሽቀጦች ይታያሉ። ከተማዋ፣ የመሻገሪያ ድልድይ ባላት በአንዲት ቀጭን ምንጭ አጠገብ የተመሠረተች ናት። በርቀት ያለችው አገር አቢሲኒያ ነች። የረዣዥም ተራራዎች ምድሮች ቅርፅ በአቢራማው እይታ ውስጥ ሲጠፋ ይታያል።

ድልድዩን እኩለ ሰሊት በስድስት ሰዓት ላይ አቋረጡት። በዙሪያቸው ከነበረው አንዳችም የተሰወረ ነገር ባይኖርም ከወንዙ ማዶ እግራቸው መሬቱን ሲረግጥ መንፈሣቸው ተነሳስቶ

በደስታ ጮኹ። ፖንሴ፣ የመድሃኒት ሻንጣውን ከፍቶ በተለይ ለዚህ ልዩ ወቅት ሲል ያስቀመጠውን ልዩ ፋሽኮ ጠርሙስ አወጣ። በአንድ ሥሩ ላይ፣ ባለ ሦስት ማዕዘን የሻርክ ክንፍ ቅርፅ ኖሮት የአጅና የጀርባ መደገፊያ ያለው ዛፍ ሥር ተቀመጠ። ጆን ባፕቲስት ጠርሙሱን ከፈተውና አቢሲኒያ ሰለመድረሳቸው ሰጨንነታቸው ጠጡ። ጆን ባፕቲስት፣ አንድ ጉንጭ ሙሉ በአንድ ጊዜ ሳበና ጠርሙሱን ለዣረሚ ሰጠው። እርሱም በተመሣሣይ አንድ ጉንጭ ሙሉ ሣበ። መጠጡ፣ አባ ጋቦሪን በዚያ ረዥም ፎቱ ላይ በደስታ እንዲጋደሙ የሚያደርጋቸው ዓይነት ነው። በዚህ ወንዶች ባላባት በሆኑባት በክርስቲያን ምድር ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ብዙም ስለሣይማኖቱ ያልተጨነቀው ሃጅ አሊ፣ ሁለት ጊዜ ተጮነጨ። የሴፍ ለመጠጣት እምቢ አለ። እነርሱ ግን አደፋፈሩዋቸው። ከአስር ደቂቃዎች በኋላ ደም አስታወካቸው። የከሀኑ ሁኔታ በጣም ያስጨነቀው ፖንሴ፣ ህመምተኛውን ሰው አረፍ አድርጉ፣ ሊያይ የሚችልበት ትልቅ ዛፍ ወይም ከተቻለ የመኖሪያ ጉጀ ሊያገኙ የሚችሉበትና በአቢሲኒያ አገር ውስጥ የሚገኘው የመጀመሪያው ከተማ ምን ያህል እንደሚርቅ ግመል ነጂውን ጠየቀው።

በቅርቡ ምንም መንደር እንደሌለ፣ የሚሻለው መንገዱን መከተልና ከዋናው ከተማ ብዙም እንደማይርቁ ሃጅ አሊ ነገራቸው። ነጋዴው፣ የነህ አገልጋይ ሕይወት እጅግ በጣም ጠቃሚ ባይሆንም፣ ጉሟቸውን እንዳያዘገይባቸው በማሰብ በተቻለ መጠን በፍጥነት ከተማ ለመድረስ ይፈልጋል።

ሕመማቸውን ቀላል በማስመሰል ጀስዊቱ ተስማሙ።

«ከዚህ ቡኋላ ወደ ዲጋው አገር ልንወጣ ነው። አዚህ ከሚያነድደን የምድር በዳ ሐሩር ይልቅ ላይ ያለው ቀዝቃዛ አየር ሣይሻል አይቀርም» አሰ

ከአንድ ሰዓት ጉዞ በኋላ ከተራራው ግርጌ ደረሱ። በለምለም የቀርከሃና የጥቁር እንጨት ጫተ የተሞላውን ሸለቆ ተከትሰውም መንገዝ ቀጠሉ። ቀጭኑን የአግር መንገድ ይዘው ሲጓዙ የሳቃዋቱ መጠን ይበልጥ ጫካና ደን እየሆነ ይመጣል። ጀምበር ስትጠልቅ በመንገዱ ዳር ባለ ጎላ ቦታ ላይ አረፉ። እኩለ ሌሊት ሲሆን እጅግ አስፈሪ የሆነ ግሣትና ከፍተኛ ድምፅ ያለው ፖዝት ከእንቅልፋቸው ቀሰቀሣቸው። ጨረቃዋ ስለጠለቀችና ምሽቱም ድቅድቅ ያለ ስለሆነ፣ ለደህንነታቸው መልካም የሚሆነው አብረው በመቆየት የሆነውን ሁሉ ጧት መመልከት

እንደሚሻል ወሰኑ። ንጋቱ ላይ ሁለቱ ግመሎቻቸው እንደሌሉ አወቁ። አንደኛው፣ ከአንበሣ ጋር ታግሎ መቦላቱን የሚያሣይ እጅግ ብዙ የሆነ የደም ነጠብጣብ አዩ። ሌላኛው ግመል በአንዘሮቹ ጥቃት ፍርሃት የታሰረበትን የገመድ ለኮ በጥሶ ከርሱ በታች በመቶዎች የሚቆጠሩ ርምጃዎች ራቅ ብሉ ተገኘ።

ሌላም ግመል ስለጠፋባቸው ከተጓዦቹ አንዱ የግድ በአግሩ ሊጓዝ ነው። ጀስዊቱ ለዚህ ፈቃደኛ ሆኑ። ፖንሴ ድርቅ ብሎ አይደረግም አለ። ሰውዬው፣ ክስት ጥቁር ብለው ትኩሣታቸው ተነስቶባቸው እግራቸውም ማበጥ ጀምሯል።

«አባክህ ፍቀድልኝ» አሉ አባ ብራቬደንት «ምንም አይነት አድልዎ አታድርግልኝ። አሽከር መሆኔን አስታውስ። በተሰየ መልክ ከታየሁኝ ጥርጣሬን ትቀሰቅሳለህ።»

በዚህ ጊዜ ማናቸውም ንግግራቸውን አልተቀበሏቸውም። ሚትር ዝረሚ፣ ካሁኑ በራሱ ኮርቻ ላይ አስቀመጣቸውና እርሱ ከቅፍሰቱ ጋር በአግሩ መጓዝ ጀመረ።

በሸለቆው ውስጥ ሰቀጣይ ብዙ ቀናት ተጓዙ። ሣር ቅጠሉ ይበልጥ ጥቅጥቅ እያለ ሲመጣ አንዳንዴ አስር ጫማ ያህል አጠር ያለ ዋርካ ያጋጥማቸዋል። ሲመሽ ሽንጣቸውን አቀባብለው ይይዙና ግመሎቹ ከታሰሩበት ጥቂት ጫማ ፊቅ ብለው በአሳቱ አጠገብ በመቀመጥ፣ በተራ መጠበቅ ጀመሩ። ከሸለቆው የመጨረሻ አናት ላይ ከበፊተኛው የሚተልቅና ቀጣይ የሆነ ትልቅ ሸለቆ አገኙ። የመሬቱ ከፍታ፣ አየሩን በማለዳ ቀዝቀዝ ያሰና ተስማሚ እንዲሆን ሲያደርገው ምሽቱ ግን ቀዝቃዛና ርጥበት አዘል ነው። አንዱን ሸለቆ ከሌላው የሚከፍለውን ትንሽ የክረብታ ከፍታ፣ መሰስ ብለው ሲመለከቱት እጅግ ድንቅ የሆነ የመሬት አቀማመጥ መመልከት ቻሉ። በአረንጓዴ መቀነት የተጠቀለለው የተራራው ምድር እነርሱ የተጓዘበትን የእግር መንገድ መልሶ የሚያሣይ በረዥምና ወዝቡን የሚጠመጥም ሌላ ጠባሣ ዓይነት ምልክት ይታይበታል። አሁን ካሉበት እጅግ ከፍ ካለው መሬት ላይ ሆነው በዙሪያቸው ያለውን የቋጥኝና የዛፍ ክምችት ሲመለከቱት በአሸዋማ የባህር ዳርቻ ላይ እንደሚጋጭ ሞገድ ተጠቅልሶ፣ አንዱ በሌላው ላይ ጉባ ብሎ፣ በግራጫው የት እየለሉ ምድረበዳ ላይ የተንጠለጠለ ያስመስለዋል። በርቀት የሚታዩት እዚህም እዚያም የተበታተኑ የዘንባባ ዛፎችና እራፊ ጨርቅ የሚመሣስሉ ጥቂት ነጫጭ የአርሻ ማሣዎች፣ በሣር ቅጠሉ የርጭት ሞገድ የተወረወሩና ሞገዱ ወኋላው ሲመለስ የተበተኑ ይመስላሉ።

በአዲሱ ሽለቆ ግራና ቀኝ በብዛት የሚታዩት የጥድና የዱር ወይራ ዛፎች ናቸው። በአየር ውስጥ እየበረሩ የሚዘምሩ ወፎች፣ የቁራ ዘሮችና ግንደቆርቁሮች በዛፎች መካከል ይሰማሉ፣ ይታያሉም። የእግር መንገዱ በጣም ዳገታማና ወዲያው ወዲያው የሚጠማዘዝ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ሁለቱ ወይም ሶስቱ ከበላያቸው የተሸነቆረ ይመስላቸውና ያዩታል። የአበሻን ምድር እግራቸው ከረገጠበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ አንድም የሠፈራ ቦታ አላለፉም። ከአንዳንድ ፀጉራቸውን እጦፍረው፣ ግማሽ ርቃናቸውን ሆነው ከሠል የተሞላባቸው ጀንያዎችን ተሸክመው በመንገድ ላይ ኩስ፣ ኩስ ከሚሉ ምስኪን ሰዎች በስተቀር ሌላ ሰው አላጋጠማቸውም።

የዱር አውሬዎች አስፈሪነት የቀነሰ ቢመስልም፣ ሌሊት የጥበቃ ተራቸውን ተግባር ቀጥለዋል። ቀን ቀን የሚያዩዋቸው እንስሳት ትላልቅ፣ ጥቋቁር፣ ሠውነታቸው ቀጭን፣ እጆቻቸው የእግሮቻቸውን ያህል የሚረዝሙ የዝንጀሮ መንጋዎች ብቻ ሲሆኑ፣ ዝንጀሮዎቹ በእጆቻቸውና በእግሮቻቸው ቀልጣፎች ይመስላሉ። በመጨረሻም ጫካውን ጨርሰው፣ የቢጫ አበባዎች ምንጣፍ በለበሠ ግራጫ የሣር ምድር ውስጥ ገቡ። እዚህ ቦታ ጥቂት ቅጠሰ ቀጫጭንና የባሕባብ ድንክዬ ዛፎች እዚህም እዚያም የበቀሉበት ነው። ከፍ ብሎ፣ ሻሮው ያሰውና እንደግርግዳ ቀጥ ያለው ገደል ወደ ተርተሩ ያመራል። ይህ የከፍተኛው የደጋ ምድር ሜዳ ጠርዝ ነው። እየቀረቡ ሲሄዱ፣ ይህ ጥቁር አጥር ከበላያቸው እንደምሽግ ግድግዳ ከእንድ ጥግ እስከሌላው ጥግ ይዘልቃል። ከዚህ ግዳግዳ መሠረት ላይ ተፈልጠው የተንከባለሱና የቆሙ የጥቁር ድንጋይ ቋጥኞች ይታያሉ። በጣም ንፁህ ቀዝቃዛ ምንጭ፣ በቡናማው ቋጥኝ ላይ ይቋጠርና ወዲያውኑ ቀጥሎ ባሉት ሰምለም ሣሮች ውስጥ ይንቆረቆራል። በዚህ አረንጓዴ የሚዳ ላይ ትያትር ቤት ለክፍተኛው የደጋ ሚዳማ አገር እንደዘርፍ የሆነው የባልፖት ድንጋይ ቀለበት ሙሌት አቀማመጥ፣ ለነፍስ ሄሴትን የሚፈጥር ነው። በለስላሳው ሣር ላይ ተጋድመው፣ ንፁሁን ውሃ ተጉነጭተው፣ የፀሐይዋን ግለት ሞቀው፣ ለስለስ ባለው ነፋስ ቀዝቅዘው፣ ቀኑን ሙሉ በሃሣብ አርቀው እየተመለከቱ በክፊል እንደመተኛት እያደረጋቸው ዋሉ። እስከዚያች ሰዓት ድረስ ሃሣባቸው ሁሉ በህይወት ስለመኖራቸው ነበርና አይኖቻቸው ከፊት ለፊታቸው ባለው መሬት ላይ ተተክሎ ነበር። አሁን ግን ሰማየ ሰማያትን በማድነቅ ተውጠዋል።

ጆን ባፕቲስት፣ እያንዳንዳቸው በፀሎት ላይ ያሉ መሰለው። በተለይ ደግሞ ሃጅ አሊ ፊቱን ወደ መካ መልሶ ተንበርክኩ ስላየው ትክክል ነው። አባ ብሬቬደንት፣ አይኖቻቸውን በከፊል ጨፍነው፣ በሃያሉና በተመስጋኙ ፈጣሪ አጠገብ ስለክብሩ የሚዘምሩትን የምስጋና መዝሙሮች፣ የእምቢልታና የመሰከት ድምፆችን ተስተጋብት የሚያዳምጡ ይመስላሉ። ከደማቁ የቤተክርስቲያን የፀሎት ስነስርዓት የተሰየው አርሱ ብቻ ይሆን በብቸኝነት የሚባክን ጊዜ ሲላመደው አልቻለም።

ሜትር ዝረሚ በአንድ ትልቅ ቋጥኝ ላይ ተቀምጦ፣ ሰማይ ሰማዩን እየተመለከተ በክባድ ተመስጦ ጭንቅላቱን ያወዛውላል፣ ከንፈሮቹን ያነቃንቃል። ይህ የርሱ የፀሎት ዘይቤው መሆኑን ፖንሴ በሚገባ ያውቃል። ዝረሚ በበኩሉ አርሱ ምንጊዜም በእግዚአብሔር እይታ ውስጥ መሆኑን ያምናል። ፀሎት፣ አሱና እግዚአብሔር የሚነጋገሩበት የተሰየ ጉዳይ ያለበት ወቅት ነው። ፕሮቴስታንቶችም የርሱን ቃላቶች ጨርሶ አይሰነጥቋቸውም። አርሱ እንደሚለው ፈጣሪ ሰፊጠራቸው ነገሮች ሁሉ ብዙ ሃላፊነቶች አሱበት ወይም የበለጠ ያስብሏቸዋል ይልና «ከሁሉም በፊት አርሱ ጀመረው።» ይላል። ምንጊዜም በደል መፈፀሙን ካመነ፣ ሜትር ዝረሚ የራሱን የመራከሪያ ሃሣብ እያቀረበ እግዚአብሔርን ይገስፃል፣ ወይም ሰፊጠረው አምላክ ትዕዛዝ እስክ መስጠትም ይደርሳል።

ጆን ባፕቲስት በበኩሉ፣ ስማቸውንና መልካቸውን ለማያውቃቸው የሠማይና የምድር፣ የማይታዩ ሃይሎች ለአንዱና ለመጨረሻ ጊዜ እየተናዘዘ ምስጋናውን ያቀርብላቸዋል። ለረዥም ጊዜ መንገዱ ፍፁም ወደርስዋ እንዳመጣው በማሠላሠል አሊስን በሚያስደስት ስሜት ያስባታል።

8

በጎርሱና በከፍተኛው ደጋማ ሜዳ መሃል ያለውን ያንጠጠውን የመጨረሻውን አለት ከመጋፈጣቸው በፊት፣ ሦስቱ ፈረንሣውያን የለበሷቸውን የተቀዳደዱትንና የቆሸሹትን ሱሪዎቻቸውን፣ ከመቶ ጊዜ በላይ በየውሃ ጉድጓዱ፣ በየኩሬውና በየተራራው ምንጮች ውስጥ እየተነከሩ በእድፍ የወፈሩትን አውሮፖዊ ልብሶቻቸውን አወለቁ። ሦስቱም፣ ረዣዥም ሰማያዊ ጃኬቶችንና የጭንቅላት ጥምጣም የአረብ ልብሶችን ለበሱ። ሃጅ አሊ፣ ሦስቱንም እንደተራ ግመል ነጂዎች አድርጐ እንደሚያስተዋውቃቸውም አስጠነቀቃቸው። እንዲህ ያለውን ቅፍለት የሚያውቁት አበሾች በሰላም ያልፏቸዋል።

ከሁለት ሰዓት ጉዞ በኋላ እንደምሰሶ በተገተረ የጥቁር ድንጋይ ግድግዳ መሬት ሥር ደረሱ። በዚህ ቦታ የመተንፈሻ ቀዳዳ የመሰለ የአጥር መውጣጫና መንጠላጠያ ደረጃ እስኪያገኙ ስር ስሩን ተንዘፍ። ከዚህ እጅግ ቀጥ ካለው አቀበታማ መንገድ መጨረሻ ላይ፣ በጥቁሩ ድንጋይ መሳከል እንደ እባብ እየተጠማዘዘ የሚሄድ መተላለፊያ አግኝተው፣ በደጋማው መሬት የመጨረሻ ጠርዝ ላይ እንደ ቆጥ የተንጠለጠሉት መንደር አገኙ።

ከዚህ በጣም አስቸጋሪ ከሆነው ምድር በላይ አስቀድመው ያዩት፣ በጦር መሠል ጣሪያው ላይ መስቀል ያለበት ባለስምንት ማዕዘን ቅርፅ ቤተክርስቲያን ነበር። እነርሱ ሲያልፉ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ስርዓተ ፀሎት ይካሄድ ነበር። በዚህ ፀጥና ረጭ ባለው ንፁህ አየር ውስጥ ከፍተኛ የሆነው መዝሙረ ዳዊት ሲዘመር የመዚቃው ድምፅ የገደል ማሚቶው ይስተጋባል።

ከተማዋ ባሮችና ከብት ጠባቂ ነዋሪዎች ያሉባት ትልቅ የገበያ ማዕከል ከመሆን የበለጠች አይደለችም። ተወላጆቹ፣ በትከሻቸው ላይ ደበሎ ጣል አድርገው፣ በወገባቸው ዙሪያ የነጭ ጥጥ ጨርቅ አገልድመው፣ ጭንቅላታቸው ላይ ምንም ሳይሰጡ የሚንዙ ናቸው። እስካሁን ካዩዋቸው ጥቋቁር ሰዎች ይልቅ የነዚህኞቹ የቆዳ ቀለም ፈካ ያለ ነው።

ሊናር የክርስቲያን አገር በነበረችበት በጥንት ዘመን ይህች ከተማ በሁሉቱ አገሮች መካከል የጉምሩክ አገልግሎት የምትሰጥ ነበረች። ወደ ከተማዋ ለመግባት ሲሉ ያቋረጡት የግንብ ግድግዳ ይህን ያረጋግጣል። ሃጅ አሊ ቀደም ሲል ወደሚያውቀው ፀጥ ያለ የነጋዴ ቤት

ወሰዳቸው። ባለቤቱም፣ የአድመኛ ሹክሹክታ በመሠለ አነጋገር ሰላምታ ሰጣቸው። በአረቦች አሰባበስ ስለቆዩ ደንገዝገዝ እስኪል ድረስ ማንም እንኳን አላስተዋላቸውም። በከተማዋ ውስጥ የሚታወቀው ሃጅ አሊ ማንነቱ እንዲታወቅ ለማድረግ ፊቱን ላለማሸፈን ጥንቃቄ አድርጓል።

ከእንግዲህ በኋላ የሚያቋርጡት ምድረ በዳ ስለሌለ ያስተናግዳቸው ነጋዴ በሚቀጥለው አሰት ግመሎቻቸውን በበቅሎ ሊለውጥላቸው ሁኔታዎችን አመቻቹ። ልውውጡ እነርሱ በሚጨምሩት መጠነኛ ገንዘብ ስምምነት ተቋጨ። አባ ብራቬደንት፣ በነጋዴው ቅጥር ግቢ ውስጥ ከቃጫ ገመድ በተሠራ አልጋ ላይ አዳራቸውን ከዋክብት እያዩ ውብ ሴቲት በማግለፋቸው ይሁን ወይም በቤተክርስቲያኑ ጉልላት ላይ መስቀል በማየታቸው፣ በማግስቱ ሟች በጣም የተሻላቸው መስለው ታዩ። ሃጅ አሊ፣ ንጉሱን በመወከል የኬላ ቀረጥ ለሚቀበለው ሠራተኛ ለመክፈል ፈጠን ብሎ ሄደ። እንደተመለሰ በጣም በማለዳ መንገዳቸውን እንደገና ተያያዙት።

በአጀማመራቸው ላይ፣ ዝግ እያለ የሚያድግ፣ በሃምራዊና ነጭ አበቦች፣ በወፍ ዘራሽ አጃና ሌሎች አረሞች በተሸፈነ ኮረብታ ላይ ተንዘፉ። ከዚያ በመቀጠል ነፋስ እንደልብ በሚያልፍበት ልክ አማንያን እንደሚቀመጡበት የካቴድራል ረዥም መቀመጫ ያለው በሚመስል ለውበት ሲባል እንደተሠራ ወጋግራ፣ በዛፎች ግንዶች፣ በተዋቀረና በቀስት ቅርፅ ከፍ ብሎ በቅርንጫፎች በተሠራ ጣሪያ መሠል የጥድ ጫካ ውስጥ መግባታቸውን አወቁ። ግራ የተጋባውና ደካማ ከሚመስለው የግመሎች መንቀራፈፍ ይልቅ በቅሎዎቹ ሳይጣደፉ በዝግታ ያሰግራሉ። ቀጥታ ሃያሏን በምታሣርፈው ፀሐይ ውስጥ አየሩ ሞቃት ቢሆንም፣ ከበረሃው አሣራማ ሙቀት ይልቅ የሚያነቃቃና የሚያስደስት ነው። አንዳንድ ጊዜ በዛፍ ስር ሲያልፉ ወይም በሠማይ ላይ የሚንቀሣቀስ ደመና ጥላውን ሲያሣርፍባቸው ያልጠበቁት አዲስነት በውስጣቸው ሲፈጠርባቸው አውሮፖን ያስታውሳቸዋል። ይሁንና ይህ የአካባቢያዊ ባህርይ ለውጥ ውጤት፣ ለተጓዦቹ የሚስማማ አልነበረም። በምድረበዳው እጅግ አስቀያሚ የአየር ጠባይና ድርቀት ሰውነታቸው ክፉኛ ተጉድቶ ስለነበር፣ አሁን ደግሞ በአንፃራዊነት የተረጋጋና ተዝቀዝ ያለ ሲሆን በሴናቸው ላይ ሲደርስባቸው የነበረው ጉዳት ሁሉ መውጣት ጀመረ። በመጀመሪያው ቀን ሌሊት ጥቂት ጉጀዎች ባሉበት አንድ መንደር አረፍት ለማድረግ ሲሉ ሰፈሩ። ሜትር ዝረሚ፣ ፖንሴን ጠርቶት እግሩን ገልጦ አሳየው። ከቁርጭምጭሚቱ ከፍ ብሎ ሊሠረጉድ የሚፈልግ የመሰለ የቀላ ቆዳው ላይ የሊኒ ትል እንደ ነጭ ክር ጫፍ ጭንትላቱ

ብቅ ብሏል። ጆን ባፕቲስት፣ የዶሮ ላባ እንዲመጣለት ካደረገ በኋላ፣ የዚህን ደም መጣጭ ትል የመጀመሪያ አካል በዝግታ ጠቅልሎ አነሣውና ሁሉንም ነገር በዕቃው አድርጐ ጠቅልሎ አሠረው።

ጆን ባፕቲስት ራሱም ቢሆን በጥሩ ሁኔታ ላይ አልነበረም። ያንቀጠቅጠዋል። መጣጠሚያዎቹን ይቆረጣጥመዋል፣ ራሱንም ያመዋል። ሴሊቱን ሙሉ ጥርሶቹን ሲያንጫነጫቸው ነበር ያደረው። ማለዳ ላይ የጀስዊቱ ሁኔታ ጭራሽ እንደባሰበት አዩ። ከንፈሮቻቸው ደርቀው፣ ደረቅ ሣል እያሣላቸው፣ ግንባራቸው በላብ ተዘፍቆ ተመለከቱ። ሌላው ቀርቶ ለዚህ አይነት ጉዞ ልምድ ያለው ሄጅ አሲ ሣይቀር፣ ለሆድ ሕመም መድሀኒት እንዲሰጠው ፖንሴን ጠየቀው።

በዚህ መንደር የሚቆዩበት ጊዜ የላቸውም። ደህንነታቸው የሚረጋገጠው የአምስት ቀን ጉዞ በሚቀራቸው በዋናው ከተማ ጐንደር ሲደርሱ ብቻ ነው። በከፊል ብቻ ንቁ ሆነው፣ ስሜታቸው በትኩሣት ተጐድቶ፣ በድንዛዜ ተውጠው፣ የአንሩ ድንቅ ባህሪያት ብቻ አጀባቸው የጉዟቸውን የመጨረሻ ክፍል እጠናቀቁ። በትውስታቸው ውስጥ ያለው፣ ከአስተሳሰባቸው ጋር ተምታትቶ ደብዝዘ እያጠፋባቸው፣ በሠውነታቸው ውስጥ የሚሠማቸው ህመም የፈጠረባቸው፣ የስሜት ስሜቱ ጠፍቶባቸው የምድሩ መልክ ብቻ ጠንካራ አሻራውን አሣረፈባቸው።

ከፍያለው፣ እያደገ የሚሄደውና የሚጓዙበት ኮረብታ በከባር ዳርቻ እንደሚገኝ ተራና ግልፅ የትያትር ቦታ፣ የመሬት የተፈጥሮ መሠረታ ይመስላል። እየተከተሉት የሚሄዱበት የእግር መንገድ ወደ ኮረበታው የመጨረሻ ጠርዝ ሲያደርሣቸው፣ ቁልቁል የሚመለከቱት ሸለቆ የአቢራና የውሃ እንፋሎት ጭጋግ ሸቅብ የሚነሣበት፣ የነርሱን የት እየለሌ ከፍታ የሚገልፅ ላይሆን በተቃራኒው በሚጨለፀው የመሬት የውስጥ አካል ላይ አፉን የከፈተ ጭራቅ መስሎ ይታያል። ሰቅፅበት ያህል መንገዱ ከገደሉ ከንፈር ትንሽ ለወጥ ብሎ ቢሄድ ከራሱ ከደጋማው ምድር ላይ ሸቅብ የሚነሣ፣ ግርጌው በተለያየ ሣር ቅጠሎች የተሣላ፣ ጫፉ ግን አንዳች ነገር የሌለበት ደራቂቅ፣ ቀዝቃዛና ሕይወት አልባ የቋጥኝ ተራራ ያያሉ። አንዳንድ ዐታዎች ላይ እነዚህ የተራራ ጫፎች ግዙፍ የቋጥኝ መጠን፣ ከውስጣቸው ሊወድቅ የተቃረበ የግራጫ ድንጋይ ሃውልት ይመስላሉ።

አልፎ አልፎ፣ ሁለት ጉዳዮች በአንድ ጊዜ ያጋጥማሉ። የመንገዱ አንደኛው ጠርዝ ተንዶ አልም ያለ ገደል ሲፈጠርበት፣ ሌላኛው ጐኑ ደግሞ ብቻውን የተመዘዘ የቡግር ድንጋይ ተራራ ይሆናል።

ባለፈው ምሽት ባረፉበት በገበሬው ጐጆ ውስጥ ካየዋቸው ሰዎች ሌላ አንድም ሰው በመንገድ ላይ አልተመለከቱም። ከአናታቸው ላይ ቀኑን ሙሉ ጥንድ ንስር አሞራዎች ሲያንዣብቡባቸው ዋሉ። ምንም እንኳ እንስሳውን ባያዩትም የገዘፈን ፋንድያ ተመለከቱ። ከእሰታት አንድ ቀን ደግሞ በአበሻዎቹ ዘንድ እጅግ ጣፋጭ ናቸው ተብለው የሚገመቱ አጋዘን የሚባሉ የዱር ፍየሎች መንጋ አጋጠማቸው። ሄጅ አሲ፣ ከነዚህ የዱር ፍየሎች አንዱን በሽጉጥ እንዲገድልላቸው ፖንሴን አጥብቆ ቢጠይቀውም፣ ፈረንሣዊው ሰው ይህን ለመሞከር የሚዘገንን ጉዳይ ሆነበት።

በመጨረሻም ከጐንደር የግማሽ ቀን የአግር ጉዞ ርቀት ላይ ከምትገኘው ከባርካ ከተማ ደረሱ። በዚህ ወቅት ንጉሰ ነገስቱ በገዛታቸው ውስጥ ከተቀሰቀሰባቸው አመፅ አንዱን ለመደምሰስ ከዋና ከተማዋ መውጣታቸውን ሄጅ አሲ አወቁ።

«ቀደም ብለን ጐንደር ለመድረስ የምንጣደፍበት ምክንያት የለም። ንጉሱ እስኪመለሱ እዚህ ሆናችሁ ብትጠብቁ የተሻለ ነው። ወዳጀ የሆነ ሰው ከቤቱ ደብቆ ያቆያችኋል። እኔ ወደ ከተማ እሄድና ጊዜው ሲደርስ ልወስዳችሁ እመጣለሁ» አለ ሄጅ አሊ

የግመል ነጂውን አነጋገር ፖንሴ እምብዛም አላመነም። ያላቸውን ሁሉ በማጭበርበር ስለወሰደባቸው ይቅር ሊለው አይችልም። ለንጉሰ ነገስቱ ካመጡላቸው የእጅ መንሻ በስተቀር ሁሉም ንብረታቸው በነጋዴው እጅ ወድቋል። ሌላው ቀርቶ አሁን የለበሷቸው የአረብ ሸሚዞች ሳይቀሩ የርሱ እንደሆኑና ንጉሱ የመጀመሪያውን ወርቅ ሲከፍሏቸው እንደሚመልሱለት ሲያስታውሳቸው አላፈረም። ሄጅ አሲ ጭራሹኑ ትቷቸው እንዳይቀር እየሰጋ፣ ጆን ባፕቲስት እያዘነ፣ ሲሄድ ግን ዝም ብሎ ተመለከተው።

እንደ አድል ሆኖ ጤንነታቸው መሻሻል ጀመረ። በሜትር ዝረሚ እግር ላይ ወጥቶ የነበረው የጊኒ ትል ዕለት በዕለት ትንሽ በትንሽ እየተጠቀለለ ይወጣል። በዚህ የተነሣ በቅርቡ ይድናል። የጀስዊቱ ሁኔታ ግን በጣም አሣሰባቸው። ሄጅ አሲ ያገኟቸው ቤት ከእንጨት

ተሠርቶ፣ በሞቃ፣ በጥድና በክብት እበት ድብልቅ የተመረገ ነው። ወለሉ በቆሻሻ የተሞላ ነበር። በአጠቃላይ አንድን በሽተኛ ሰው ለማስታመም የሚሆን አመች ቦታ አልነበረም። ጊዜያዊ በሆነችው ጠባብ አልጋቸው ላይ የተኙት ምስኪኑ ዮሴፍ፣ ዕለት በዕለት ይበልጥ ወደ መቃብራቸው ይጠጉ ጀመር። ስውዬው ብርታታቸውን ከሚገባው በላይ ገምተው ነበር። ለተልዕኳቸው የነበራቸው ፍፁም ታዛዥነት፣ እንደርሳቸው ያለ ፀጥ ያለ የቤተመላሕፍት ምቾትን የለመደ ምሁር፣ በዚህ እጅግ አስቸጋሪ ጉዞ ላይ የሚገጥማቸውን ፈተና በሰንሰለት ተቆራኝተው እንደተፈረደባቸው ሰዎች በፅናት እንደሚወጡት አንዲያምኑ አድርጓቸዋል። ነገር ግን እያደር የሚጨምረው ድቀታቸው ሰውነታቸውን ለበሽታ ስላጋለጣቸው፣ የጥድ እንጨት እሣት ቀኑን ሙሉ እንዲነድና እንዲሞቃቸው ግድ ሆነ። ጀስዊቱ በርግጥ በሚያሣዝን ሁኔታ ላይ ነበሩ። ረኻሙና ግዙፉ ሰውነታቸው እንደሃረገ ጥምልምል አለ። የሚተነፍሱት በአፋቸው ስለሆነ ከራሳቸው ሰውነት የሚመጨነው የትኩሣት ሙቀት ከንፈሮቻቸውን አደረቀባቸው። ጆን ባፕቲስትና ሜትር ዝረሚ በካህኑ አልጋ አጠገብ ተራ በተራ መቀመጥ ጀመሩ። በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ ፕሮቴስታንቱ ሲያደርግላቸው የነበረው ርህራሄ እየተዘነጋቸው፣ ይህ መናፍቅ አጠገባቸው መሆኑን ሀሊናቸው መለስ ሲል ሲያውቁ፣ ፍፁም የጥላቻ ርግማናቸውን ይገልፃሉ። ጤናቸው እንደሚመለስና እንደሚድኑም ስለሚያምኑ ተልዕኳቸውን እንደሚፈፅሙ ያምናሉ። አንዳንድ ጊዜ በሚያስደስት ቅላፄ ከውስጥ፣ ከአንጀታቸው መንጭቶ አቢሲኒያን እንደምን የሃይማኖታቸው መስመር ተከታይ እንደሚያደርጓት ታላቁን አቅዳቸውን ለረኻም ሰዓት ያብራራሉ።

«አስቀድሞ የምንፈልገው የአቢሲኒያን ህዝቦች ባህል፣ ጠባይና ቋንቋ መገንዘብ ነው። አዎን፣ ቋንቋቸውን ማወቅ ነው። አዚያ እንደደረስን እኔ ቋንቋውን ማጥናት እጀምራለሁ። ስለቋንቋው ፈረንሣይ ውስጥ መጠነኛ ነገር ተምሬአለሁ። በርግጥ የሚናገረው ሰው የለም። ሰዎችን ለማግባባት የሚያስችለው ጉዳና ቋንቋ ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ እምነታቸው . . . አስቀድመህ ግን በትክክል ልታውቃቸው ይገባሃል። ትልቁ ምስጢርም ይኸው ነው። አውሮፖ ውስጥ እምነት ያልነበራቸውን አረማውያን ባህላዊ ክብረ በዓላት፣ ቀናቱ፣ ቦታዎቹና አስተሣሰቦቹ ተመሣሣይ ሆነው የቤተክርስቲያን ስርዓቶች ተከተዋቸዋል።»

አንዳንድ ጊዜ በአልጋቸው አጠገብ ያለው ማንም ይሁን ማን ጨበጥ ያደርጋሉ። በመጨረሻም ፖንሴ አየመሠላቸው በስህተት ከሜትር ዝረሚ ጋር ሣይቀር ያወሩ ነበር።

«በአያት ቅድመ አያቶቻችን የተፈፀሙትን ስህተቶች እንደግማቸውም። ልክ አይደለም እንዴ? አስቀድመን ሕዝቡንና ካህናቱን ሳንለውጥ በፊት ንጉሡ ሃይማኖቱን እንዲለውጥ መደረግ የለበትም. . . »

ጀስዊቱ በጣዕረሞት ተይዘው ሣሉ እንኳ፣ ውርደትን በትህትና ለመቀበል የነበራቸው ፈቃደኝነት፣ ይህም የታላቅ ክብራቸው መገለጫ መሆኑን ያሣዩ ነበር። የሃይማኖት ማህበራቸውን ደንብ በፍፁም ታዛዥነት ሲቀበሉ ሁሉንም አይነት ግላዊ ምኞቶች ይክንናሉ። ይህን የሚያደርጉት ሥልጣንን በሙሉ ሃይል ለመጠቀም ከዘመናት በፊት የታቀደውን የተጠራቀመ ጉጉት ለማገልገል ሲሉ ነበር። አንድን ንጉስና ግዛቱን ለመግዛት አስቀድሞ በውሣ ቀጅነት ማገልገልን የሚመርጠው ሰው ነበሩ። ጆን ባፕቲስት፣ ለካህኑ አኳኋን፣ ጥንካሬና ብስለት አትኩረት ቢሠጥም፣ የጀስዊቱ ህመም እየጠናባቸው መጣ። ቂሰም በቅርብ እንደሚሞቱ አውቀ። የመሞታቸውን ሁኔታ ሲረዱ የታዛዥነት ፍቅራቸው አዲስ መስመር አበጀ። ለቅዱስ ተልዕኳቸው ፍላጐት ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ቢያስገዙም፣ የአግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈፀም የሚለውን ሣጣብ ተቀበሉ። ራሣቸውን ሙሉ በሙሉ በህመማቸው ስር በመጣል፣ የተወሰነው ዕጣ ፈንታቸው ለዚህ እንደላካቸው መግለፅ ጀመሩ። ከዚህ በኋላ ቀጣይ ህክምና መስጠት ጥቅም አልነበረውም። ሃጅ አሊ እያምባረቀባቸው ትዕዛዝ ይሠጣቸው እንደነበረው ሁሉ ለሞት ጥሪም ታዛዥ ሆነው ከሦስት ቀን በኋላ አረፉ።

ፖንሴና ዝረሚ በግቢው ውስጥ ያለው የግራር ዛፍ ባጠላበት ቦታ ቁሱን ለመቅበር ፈለጉ። ይሁን እንጂ ያረፉበት ቤት ባለቤት፣ ቤቱን የሠራው ቅድመ አያቱ እጅግ ክፉኛ ታመው ሲሞቱ የተቀበሩበት ቦታ በመሆኑ አይሆንም አሳቸው። ይህንን መጥፎ የጉዞ ጓደኛ አስከሬን በዚያ ውስጥ በመጨመር፣ መቃብሩን ለዘላለም ማርከስ ከጥያቄ ውጭ ነው ሲል ባለቤቱ ተቃወመ።

በዚያን እለት ማታ ወደ ባቄላ ማሣ በሚወስደው ጠባብ መንገድ፣ ጠፍ በሆነ መሬት ዳርቻ ላይ ጠለት ያለ ጉድባ ቆፍረው የጀስዊቱን አስክሬን ቀበሩ። የተከፈኑት በለበሱትና ሃጅ አሊ ሁጊዜም እየተቅጨለ በሚያወራበት የአረብ ሽሚዛቸው ነው። መፅሃፍ ቅዱስን በመጥቀስ ሜትር ዝረሚ አጠር ያለ ፍትሃት ሲያደርግ፣ በዚያ ቦታ የነበረው ብቸኛው ካቶሊክ ፖንሴ፣ እንዲህ ላለው ሥነ-ስርዓት ልምድ የሌለው በመሆኑና ምን ማድረግ እንዳለበትም ስለማያውቅ

ሚትር ዣረሚ የጀመረውን መዝሙር ሳይጨርስ በፊት በእጁ አፉር መመለስ ጀመረ። ዣረሚ ለረዥም ሣምንታት መከራቸውን ሲጋራቸው ቢሰነብትም፣ አሁን ግን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በመቃብር ውስጥ ሲጠልቁ ተመለከተ። ወዳጅነቱን ሲሰጣቸው የነበረው ጆን ባፕቲስትም፣ ይህ ውሰታው ፍፁም እንደማይረሣበት ርግጠኛ ሲሆን አልቻለም።

መፅሐፍ ቅዱሱን ካጠፈው በኋላ «ክነሣነት ለመሸሽ የዚህን ያህል ርቆ የተጓዘ ሰው የለም» አለ ሚትር ዣረሚ። ይህ መግለጫ በምስኪኑ ቄስ መቃብር ላይ የሚሣፍ ታሪክ መሆኑ ነው።

ሁለቱ ጓደኛሞች ወደ ቤት ሲመለሱ ስለምስጢራዊው አሀጉር፣ ስለጠፋው ህፃን፣ ስለሞቱ ተስፋጮችና ስለተረሱት ያለፉ ዘመናት በሃሣብ ተውጠው ነበር። ምንም እንኳን በቁሱ ሞት ክልብ ቢያዝኑም፣ አጣናቸው የሚል ስሜት አልነበራቸውም። እንደገና መነጋገር ሲጀምሩ፣ የቁሱ ህይወት ከዕረፍታቸው የባሰ አሣዛኝ እንደነበረ ተስማሙ።

በሚቀጥለው ቀን ስለቁሱ የነበራቸው ሁኔታ በሙሉ ተወግዶላቸው ነበር። ይልቁንም ክእንግዲህ በኋላ እንዳያመልጣቸው አጥብቀው የሚይዙት አዲስ የፍስሃ ስሜት በመሣከላቸው ተፀነሠ። ሃጅ አሊ ከሄደ ከሶስት ቀናት በኋላ ተመለሠ። በአበሻዎች የአሰባበስ ዘይቤ ብሩህ ቀለም ባላቸው ክሮች የተጠለፈ ነጭ ቀሚስ ለብሶ፣ ሽቶ ተቀብቶ፣ ፀጉሩን ወደ ኋላ ሰቅቆትና ሌላ ሰው መስሎ ተመለሰ። የዮሴፍን ዜና እረፍት ሲነግሩት ልክ አንድ በቅሎ የጠፋው ያህል ስሜት አሣየ። ምንም አይነት አስተያየት ሳይሰጥ በቀጥታ የሚያነጋግራቸውን ጉዳይ ጀመረ።

«ንጉስ ነገስቱ ዛሬ ጉንደር ይገባሉ። ስለዚህም ሕዝቡ እንዲሰበሰብ መጠየቅ ይኖርብናል።» ሲል ጀመረ

«በስንት ሰዓት?» ሲል ፖንሴ በፍጥነት የመልቀቅ ሃሣብ በውስጡ ተፈጥሮ በደስታ ጠየቀ።

«ይህ የሰዓታት ጥያቄ ሳይሆን የቀናት ነው»

«የቀናት? ንጉሱ ለመታከም ጉጉት የላቸውም?»

«በርግጥ አሳቸው። ነገር ግን ፈረንሣውያን ሃኪሞች እንዲመጡላቸው ማድረጋቸውን ከመግለፃቸው በፊት የሸማምንቶቻቸውን አሰምሮ ዝግጁ ማድረግ ይኖርባቸዋል። እስከ ዛሬ ድረስ እናከምዎታለን እያሉ ሲያታልሏቸው የነበሩትንና ያልተሳካላቸውን ሰዎች ማረጋገጥም ይኖርባቸዋል።»

«እኛ ይህን ሁሉ መንገድ ተጉዘን ልናድናቸው ወይም ልንገድላቸው መጥተን እስክንደርስ ድረስ እነዚህ የተባሉት ሰዎች ረዥም ጊዜ ነበራቸው» አለ ጆን ባፕቲስት

«ምን አልባት» ሲል ሃጅ አሊ ከአዲሱ አኒኋኑ ጋር መረጋጋትን ለመጠበቅ ሲል መልሱን ጀመረ። «ተመልሼ ወደዚህ አገር መምጣቴንና የተሠማራሁበትንም ተልዕኮ አውቀዋል። የንግስቲቱ ደንዝጠሮችና አሻቢዎች፣ ለፈረንሣውያን ጥላቻ ስላላቸው አንድ የመጨረሻ ሙከራ ለማድረግ ወስነዋል። ቀሣውስትና ትንቢት ተናጋሪዎች ነን የሚሉት እነዚህ ቡድኖች፣ ንጉሡ ላደረሱባቸው ውርደት ብቀላ እንደሚፈልጉ ማወቅ አለባችሁ። የመጨረሻውን ወታደራዊ ዘመቻቸውን ለማድረግ ሊንቀሣቀሱ ሲሉ ኩተሰመደው የበሏጠ ብሩህ የሆነና እጅግ በጣም ረዥም ጅራት የነበረው ተወርዋሪ ኮከብ ታይቶ ነበር። ትንቢት ተናጋሪዎቹ፣ ንጉሡ እንደሚሸነፉና ጭራሽንም እንደማይመለሱ ተንብየው ነበር። ይሁን እንጅ ድል አድርገው ተመለሱ። አሁን ደግሞ የርሳቸውን ፍቅርና ድጋፍ መልሰው ለማግኘት ሌላ ዘዴ እየፈለጉ ናቸው።»

«እና አሁን ደግሞ ምን ዘዴ ሊጠቀሙ ነው ያቀዱት?»

«ባለፈው ሣምንት አንድ ታላቅ ቅዱስ ሰው ከሳሊበላ በሰልፍ ታጅበው እንዲመጡ አቅደው ነበር። ሰውዬው ላለፉት ሃያ ዓመታት ምግብ ሳይበሉና ውሃ ሳይጠጡ የኖሩ መነኩሴ ናቸው»

«ሃያ አመት!» አሉ ጆን ባፕቲስትና ሜትር ዣረሚ፣ ቅዱስነታቸው ላይ በሚቀለድ የድምፅ ቅላፄ

«ይህ የሚቀለድበት አይደለም፣ ሙሉ በሙሉ እውነት ነው። ቅዱሱ ሰው በማንም ሊታዩ የማይችሉ ናቸው። በአንድ አጉበር ውስጥ ተኝተው ነው ያሉት። ታሪዛቸውን የሚሸከሙ

አራት መኳሣት ናቸው። ከፊት ለፊታቸው ፖትርያርኩና ረዥም የወርቅ መስቀል በመያዝ እየዘመሩ የሚራመዱ ደርዘን የሚሞሉ መነኮሳት ከብበዋቸው ይጓዛሉ። ከኋላቸው ደግሞ በባዶ እግራቸው የሚጓዙ ሠላሣ ወጣት ተዋጊዎች ተከትለዋቸዋል።»

«እናም የጠጅ በርሜሎችን የተጫኑ ደርዘን በቅሎዎችም አሉ?» አለ ሜትር ዝረሚ በማሸሚጠጥ ሣቅ።

«መነኩሴው እዚህ ከደረሱበት ጊዜ ጀምሮ በፀሎት ላይ ናቸው?» በማለት አተካሮውን ወደጉን በሙተው ሃጅ አሊ ቀጠለ «ዛሬ በጠዋት ንጉሱን አይተዋቸው፣ የድንግል ማርያምን ምስል ጭነውባቸው ነበር። ነገ ተመልሰው የእግዚአብሔር ቃል የተደገመበትን ፀበል እንዲጠጡ ይሰጧቸዋል»

«እንዲጠጡ በምን መልክ» ሲል ጆን ባፕቲስት ኮስተር ብሎ ጠየቀ።

«ጉዳዩ በምስጢር ተሸፍኖና ተደብቆ ነው የሚከናወነው። መነኩሴው ሌላ ሰው ሊይዛቸው የማይችላቸውን ብዙ ቃላት ያዥጉዳጉዳሉ። የምስጢሩ እምብርትም ይህ መሆን አለበት፣ አለበለዚያማ ድርጊቶቻቸው ቀላልና የሚታወቁ ናቸው። ንጉሡ የሚበሉትንና የሚጠጡትን ለመቆጣጠር ሃላፊነት ያለባቸው መኮንኖች ሥርዓቱን በሚገባ አይተው ነው የገለፁልኝ። ቅዱስ መነኩሴ፣ የእርሣስና የቀርቀሮ ቅይጥ በሆነ ክታብ ላይ ባህርይውና ምንነቱ ምስጢር ሆኖ የሚቀር አንድ ቃል ይፅፉበታል። ከዚያ በኋላ ይህን ብርቱ ቃል ፀበል በያዘ ጉድጓዳ ሣህን ውስጥ ይከቱትና በሰሀፍ ላይ ያለው ቀለም ይሟሟበታል። ከዚያም ውሃውን ንጉሡ ይጠጡታል።»

«ይህን አይነት ተግባር ለምን ያህል ጊዜ ነው ተደጋግሞ የሚከናወነው?» ሲል ጆን ባፕቲስት ለስለስ ብሎ ጠየቀ

«ሁለት ጊዜ ብቻ»

«ለውጥ ማሣየት ከመቻሉ በፊት ምን ያህል ቀናት ነው በዚህ ላይ የሚሰነብቱት?»

«በአንድ ሣምንት ውስጥ የማይሻላቸው ከሆነ ንጉሡ ያሣውቁኝና እናንተ እንድታክሚያቸው ይጠሯችኋል»

«በሆነ መልካም ዕድል ቢድኑስ?»

«በሆነ መልካም ዕድል ቢድኑስ?» አለ ሜትር ዝረሚ። «በእርግጥ ይሆናል አይባልም፣ ሕክምና ነው። በአንድ ጊዜ የማይሠራ ከሆነ መጠኑን ከፍ ለማድረግ መላውን መፅሃፍ ቅዱስ በአንድ ኩባያ በጥበጠ እንደመጠጥ ማድረግ ሊያስፈልጋቸው ነው»

«ከዳኑ ግን እኛ እንመለሳለን» አለ ሃጂ አሊ

«ሣናያቸው»

«ምንም እንኳን እናንተ እንድትመጡላቸው የላኩት ንጉሱ ራሣቸው መሆናቸውን ህዝቡ ቢያውቅም፣ እናንተን ለማየት ግን ሊገጥማቸው የሚችል ክፉድ አደጋ ሊኖር እንደሚችል ልትረዱ ይገባል። በእያታቸው ዘመን፣ ጀስዊቶች አገሪቱ ሃይማኖተዋን እንድትሰውጥ ካደረጉት ሙከራ በኋላ ንጉሦቹ ሙሉ በሙሉ ነፃ አይደሉም። ካህናቱና ካቶሊካዊነትን የሚቃወሙ ሁሉ በጥብቅ ይከታተሏቸዋል። አንዲት እጅግ አነስተኛ የስህተት እርምጃ ካዩ፣ ከንጉሡ የብረት እጅ ራሣቸውን ነፃ ለማድረግ ማንኛውንም ዓይነት ሴራቸውን ያድማሉ። ፈረንሣውያን ቀሣውስት አሁንም ቢሆን አግባብነት ባለውም ይህን በተንኮል ወደ አገሪቱ ለመግባት ተሰፋ እያደረጉ መሆናቸውን አያንዳንዱ ስለሚያውቅ ይጠነቀቃሉ። የአገራቸውን የውስጥ ሰላም ለማስጠበቅ ሲሉ ንጉሡ የህክምና ክትትል እየተደረገላቸው ነው የሚል የይቅርታ መጠየቂያም ሣያስፈልጋቸው ሊያባርሯችሁ ይችላሉ።»

ይህን የሚረብሽ ዜና ከነገራቸው በኋላ፣ ሃጅ አሊ ወደ ቤተመንግስት ለመመለስ ትጉቸው ሄደ። እነርሱም ብቻቸውን ቀሩ። በራስ መተማመናቸው አሁንም ጥብቅ ቢሆንም፣ በአጥር ግቢያቸው ውስጥ ተዘግተባቸው በመቀመጣቸው አልተደሰቱም።

ክአስተናጋጃቸው ልጆች አንዱ፣ ወደ ገበያ ወጥቶ እዚያ ከሚሸጠው ከያንዳንዱ የእፅዋት ዝርያ ናሙና አመጣላቸው። ሁለቱ ጓደኛሞች በክፍተኛ ትጋት በምድር ላይ እንደዚህ ያለ ጠንካራና ውብ መዓዛ ያላቸው ዝርያዎች፣ ጥሩ ሽታ ያላቸው መድሃኒቶች፣ ማቅለሚያዎችና

ቀመሞች ያሉት አንድም አገር የሌለውን እነዚህን አፅዋቶች በየወገናቸው መለየትና ማስቀመጥ ጀመሩ። መውቀጫቸውንና ማጣሪያዎችን አሻሽለው በሠሩት አንተተ ረዥም ጠርሙስ በመጠቀም ሜትር ዝረሚ የጓደኛውን የፖንሲን አመራር እየተከተለ ይወቅጣል፣ ያነጥራል፣ የሚበጠበጥና የሚደባለቀውን ሁሉ ይሠራል። ጉዟቸው በጣም የጨረሰባቸውን መድሃኒት በከፊል የመጠባበቂያ ክምችት ሣጥናቸው ውስጥ ያስቀምጣሉ። ንጉሡን ግያዩዋቸው በዚሁ የሚመለሱ ከሆነ እነዚህን ያተክልትና የአዝዕርት ዝርያዎች ማግኘታቸውን ብቻ ይዘው ይመለሳሉ።

ሃጅ አሊ ኪያቸው ከሶስት ቀናት በኋላ፣ ያረፉበት ቤት ነጋዴ በዚያኑ ዕለት ምሽት ወደ አዲስ ቤት መዛወር እንዳለባቸው ሲነግራቸው መጣ። ሲመሽም ማንነታቸው እንዳይታወቅ ረዥሙን የአረብ ቀሚሳቸውን ለብሰው ከዋናው ከተማ የሚለያቸውን ርቀት ተጓዙ። አነስተኛ ውን ጭነት የተሸከሙት በቅሎዎቻቸውም ከኋላቸው ተከተሏቸው። ጉንደር ውስጥ በአረቦች ሰፈር ነዋሪ የሆነ ሌላ መሰሊም ተቀበላቸው። ለማረፊያነትም በጥሩ ሁኔታ የተጌጡ፣ መስኮቶቻቸው በጥልፍልፍ ብረት ተሠርተው ወደ ጠባቡ መንገድ የሚያሣዩ ሁለት ክፍሎች ተሰጧቸው። ባለቤቱ ራሱ ምግብ ይዘላቸው በመምጣት ትዕግስት እንዲኖራቸው መከራቸው።

ከአንድ ሣምንት ጥብቅ ቆይታ በኋላ ሃጅ አሊ ፊልጓቸው መጣ። ከአንድ ቀን በፊት የአበሻ ልብሶችን እንዲለብሱ በማለት ከነጭ ናይለን የተሰሩ አጫጭር ቀሚሶችና በትከሻዎቻቸው ላይ የሚደርቧቸው በጥጥ የተሰሩ ካባዎችን ልኮላቸው ነበር። በማግስቱ ጧት፣ ሃጅ አሊ፣ የከርቻ እቃው በትላልቅ ላባና የሱፍ ኪሶች በቁንጠኛነት በተጌጠ አጭር ዳማ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ብቅ አለ። ለኮ የጠለቀላቸውን ሁለት ፈረሶች እየመሩ የሚመጡ ባሪያዎችም ተከትለውት ነበር።

በሃጅ አሊ አመራር መሠረት ፖንሲና ሜትር ዝረሚ የአበሾችን ልብስ ለብሰው ተራ በተራ በፈረሶቹ ላይ ወጥተው በሰያፍ የዝግታ ሰግሪያ ወደ ቁስቋም ቤተመንግስት ተጓዙ።

9

«ቀጥል» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ በብስጭት። «ደብዳቤው በሚቀጥለው የፖስታ ጉዞ አሌክሣንደሪያ መድረስ ካለበት ዛሬውኑ መጠናቀቅ እንዳለበት አትርሣ»

ሙሴ ማቹ ብዕሩን ይዞ ጠረጴዛው አጠገብ ተቀመጠ። ባሣለፈው መጥፎ ሰሊት ምክንያት አይኖቹ ደመና እንደለበሱ ናቸው። በጨዋታ ለዛ ያፈለበሱት የለቅሶ እምባ በበጋው ወቅት ከተማዋን ለወረራት የትንኝ መንጋ፣ ጥሩ የምግብ ፍላጐታቸውን የሚቀሰቅስላቸው ነበር። ወንዶችም ሴቶችም አጠገቡ እንዳይደርሱ ሊደረግ ነፍሣቶቹ ግን እየተሣቡ ይመጡበት ነበር። እንዳለመታደል ሆኖ የተለመደውን ቅነሳ ባለማድረጉ የራሱን ግላዊ የጤና አጠባበቅ ዘዴም ለወጠው።

«ቆይ! ቆይ! እንይ» አለ ማንበብ ያቋረጠበትን ቦታ እየፈለገ «እዚህ ላይ ግን . . . ለክቡርነትዎ ልናዘዝና . . . እኒህ ባለፈው ጊዜ ከኤምባሲያችን ጋር የርሳቸውን የሄይማኖት ማህበረሰብ አባል መነኩሴ አብሬ እንድልክላቸው የጠየቁኝ ካቮቺን አባት፣ ትናንትና ከኔ ጋር ለመገናኘት ችለው ነው።»

«የለም፣ ይህ የዲፕሎማቲክ ቋንቋ አይደለም፣ አንድ ቆንሲል ለአንድ ቄስ አይናዘዝም»

«እንዲህ ብንለውስ፣ ክቡርነትዎ ሊያውቀው እንደሚችለው . . . »

«መጠነኛ ማሻሻል ነው። ቀጥል»

«ክቡርነትዎ ሊያውቀው እንደሚችለው ቃለ ምልልሳችን ምንም አይነት ትህትና አልነበረበትም። ምንም እንኳ አባ ፖስኳል ስለ እራሳቸው ብቻ በመናገር ትህትናና አክብሮትን የሚጠይቁ ውይይቶችን ብዙ ጊዜ ቢጥሱም፣ ሳዳምጣቸውና ሳግባባቸው ሞክራለሁ።»

«ይህ መጥፎ የሚባል አይደለም» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ አንድ እግሩን እየዘረጋ፣ በደብዳቤው መንፈስ ተደስቶና በዚያውም አሁን በቅርቡ ከፈረንሣይ በጀልባ የመጣለትን አዲስ አረንጓዴ የሐር የእግር ሹራቡን እያደነቀ።

«የመጨረሻውን ቃለ ምልልሳችን ተከትሎ የመልዕክተኞቻችንን ቅፍለት የሚከታተሉ ሰዎችን ላክ። ካፑቺኖች የኛን መልዕክተኞች ሊናር ላይ ደርሰውባቸው ጥያቄዎቻቸውን ደጋግመው ነለው። መልዕክተኞቻችን የጠፍ ጨረቃ ለሊት አግዟቸው ሸሹ። ይህም ሆኖ እነርሱን ለማግኘት ሁሉም አይነት ሙከራ ቢደረግም ዱካቸው ሊገኝ ማይችል ቀርቷል»

«ለመሆኑ ነጠላ ቁጥር ነው እየተጠቀምክ ያለኸው?»

«ይቅርታ ክቡር ሆይ፣ አልሰማሁዎትም»

«ዱካ የሚለው «ቃል» »

«አዎን እንደዚያ ነው የፃፍኩት ፣ክቡር ሆይ»

«የብዙ ቁጥር አድርገው። በጉዟቸው ላይ በአንዳንድ እግራቸው ጡብ ጡብ እያሉ በአንድ ነጠላ ዱካ ላይ የሚሄዱ ይመስል ዱካ በማለት የማስረዳት ችግር አለ መሰለኝ»

«. . . እነርሱን ለማግኘት ሁሉም አይነት ሙከራ ቢደረግም ዱካዎቻቸው ሊገኙ ላይችሉ ቀርተዋል።» በማለት «ዎቻቸውን ጨመርኩበት»

«ግሩም ድንቅ»

«የፈረንሣይ የልዑካን ቡድን በደንብት በመሸሹ የነቁት ካፑቺኖች ምርመራቸውን በመቀጠል አሽከር የተባለውን የዮሴፍን ማንነት ለማረጋገጥ ቻሉ። ጉዳዩን ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ እንዲያውቁት ይደረጋል ሲሉ አባ ፖስኳል አረጋግጠውሰኛል።»

«የኒያን ጅላጅል ሰው ስም አሁንም አሁንም ባንጠቅስ ጥሩ ነው። በቀላሉ . . . ይደረጋል ሲሉ ካፑቺኖቹ አረጋግጠውልኛል በለው»

ሙሴ ማቹ የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሣብ በማስታወሻው ያዘ

«ይህን ያልታደለ ጉዳይ በተመለከተ ክቡርነትዎ ሊመዝኑ የሚችሏቸው ሁለት የማጠቃለያ ሃሣቦችን ባቀርብ። አንደኛው መልክተኞቻችን አስካለፈው አንድ ወር ድረስ

በህይወትና በጥሩ ጤንነት ላይ ሊናር ውስጥ እንደነበሩ መግለፅ በዚያን ፅለት የት እንደነበሩ ተስፋ ማድረጋችንን ያስረዳል።»

ሙሴ ዲ ማይሌ እየተንጐራደደ ወደ መስኩቱ ዜዶ ውጭ ወደ አትክልቱ ውስጥ ተመለከተ።

«እናም ሁለተኛ፣ ምንም እንኳን በጣም ደካማና ሊቀየሩ የሚችሉ ቢሆኑም እነዚህ የዛይማኖት ጥያቄዎች በዲፕሎማሲያዊ ተግባራችን ውስጥ ውስብስብ ነገሮችን ማስከተል ጀምረዋል። በሁለቱ የዛይማኖት ማህበራት መካከል ያለው ፉክክርና አበሾች ለካቶሊክ ካህናት ያላቸው ግልፅ የሆነ ጥላቻ፣ ተልዕኳችንን ያውም የራሱ ችግሮች እያሉበት፣ በአደጋ ላይ እንዲወድቅ የሚያደርጉ ናቸው። በሌላ አነጋገር በጣም ቁልጭ አድርጌ ባስቀምጠው፣ ይህን ፕላን በራሣቸው ጥረት የተጠቀሙበት ጀስዊቶቹ ዛሬ ተመልሰው ይደራደሩበታል። በበኩሌ፣ ግርማዊነታቸው ይህን ተልዕኮ ሊያዝዙ ለመላው የክርስትና እምነት ጥቅም እንዲሰራ ተመኝተው ይመስለኛል።»

ካለፈው ምሽት ወዲህ ይህን ደብዳቤ ሲያነብቡት አራተኛ ጊዜያቸው ነው። ቆንሲሉ ይህንን ድፍረት የተሞላበትና ወደፊት ሊደርስ እንደሚችል የሚያምንበትን የደብዳቤውን ፖለቲካዊ ክፍል ለመስማት አልሰለቸም። በዚያን ሰዓት፣ ሴት ልጁ በቆንስላው ጽሕፈት ቤት ለአጭር ጊዜ ብቅ በማለቷ ሃሣቡ ተበታተነበት። ጊዜ ጠልቶትና በቃህ ብሎት ለዘላለም ሊያስወግደው እንደታስታወሰው ማድረግ እንዲቻል የአባቷን ብልህነትና አርቆ አስተዋይነት አሰምሮዋ ትከክለኛውን ምስል ቀርፆ እንዲያስቀምጥላት፣ ይህን ዓይነት ድንቅ ዲፕሎማቲክ ሥራ ከርሷ ጋር ቢጋራው ምን ያህል ደስ ባለው።

«ስለዚህም የፈረንሣይ ንጉስ በዚህ ጉዳይ ላይ ከካቶሊክ እምነት ጋር እንደሚስማሙ ማሳራት ግዴታችን ይሆናል» ሲል ሙሴ ማቹ ቀጠሉ። «የምንጠብቀው ኤምባሲ እንደተመለሰ እንሄት መቀጠል እንደሚገባኝ ከክቡርነትዎ ለማወቅ አማክርዎታለሁ። የመንግስትን ጉዳይ ከሃይማኖት ጋር መደባለቃችንን እንቀጥልበት? ወይስ ዲፕሎማሲያዊና ሌላው ቀርቶ የንግድ ቁርኝቶች እንኳ ሚዛናቸውን ጠብቀው እንደሚተገበሩ እኛም ግርማዊነታቸውን ሙሉ በሙሉ በመወከልና ለግዛቱ ዘውዳቸው ቀዳማይ ጥቅም ስንል እንስራ?»

«አሁን በጣም ትክክል እንደሆነ አምናለሁ» አለ ሙሴ ዴ ማይሴ በመመሣጀቅ ዓይነት «አርማቶቹን ካስገባህ በኋላ እንደገና አንድ ጊዜ እናነበውና ከዚያ በኋላ ይላካል።»

ሙሴ ማቼ ብድግ አለና እንደ ፅሕፈት ቤት ወደምታገለግለውና ወደምታፍነው የእቃ ማስቀመጫ ክፍሉ አመራ።

ቆንሲሉ፣ ከወፍራሙ የመስኮት መጋረጃ በስተኋላ ትንሽ ፈቅ ብሎ ልጁ በመኖሪያ ቤቱ ያሉትን እፅዋት ልትንከባከባቸው ስትሄድ በስስት ተመለከታት። የደስደስ ያለውን ቁመናዋን፣ ረጋ ያለ አረማመዷንና ከሕፃንነት ወጥታ ከስተር የማለቷን ሁኔታ አደነቀ።

ጋብቻ እንድትፈፅም መወሰን ያለብኝ ጊዜ ነው።

ፍ

«ይህች አውሬ የምትችለውን ሁሉ በማድረግ ልትጥለኝ ትፈልጋለች»

ሜትር ዠረሚ ትንሿን ፈረስ ለመቆጣጠር ከብደቱን ሁሉ ተጠቀመ። ፈረሷ ግን በፍርሃት ዓይኖች ዘለለች። ሃጅ አሊ አንዱን አገልጋይ ሲያመለክተው ወዲያውኑ ለክንውን ያዘ።

«አሁን የመዝናናትና ግዴለሽ የሚሆንበት ጊዜ አይደለም።» አለ ጆን ባፕቲስት ልጓሙን በሁለት እጆቹ ጨብጦና ፈረሱ እንድትራመድ ጥረት በማድረግ ሲሳካለት።

ከአረቦች መኖሪያ ወጥተው፣መንደሩን ከዋናው ከተማ የሚለየውን አነስተኛ ምንጭ ተሻገሩ። ከዚህ በኋላ በሙስሊም ጥምጣም መሸፈናቸው ቀርቶ፣ ለሁሉም ሰው አውሮፖውያን መሆናቸውን በግልፅ ማሣየት ጀመሩ። በጠቦቹ የከተማው መንገዶች ውስጥ የሚጮርፈው ህዝብ እነርሱን በተመለከተ አንዳችም ጉጉት ሣያሣይ ረጋ ያለ ነበር። ለዚህ ደግሞ ብዙ ምክንያቶችም ነበሩ። በመጀመሪያ ደረጃ ለምድረ በዳው የፀሐይ ቃጠሎ ስረዥም ጊዜ ተጋልጠ የነበረው የሁለቱ ፈረንሣውያን ቆዳ ጠቆር ስላለ፣ ይህ ቀለም ከአቢሲኒያ ክርስቲያኖች ጋር ይቀራረባል። ሁለተኛ፣ ጐንደር ውስጥ በቁጥር ብዙ የውጭ ዜጐች ስለሚኖሩ ሕዝቡ የመልኩን ቀለምና ትርፅ ለምዶታል። ብዙዎቹ ግሪካውያንና አርመናውያን ሲሆኑ ጥቂት

ደቡባዊ እስላሮች አሉባቸው። እነዚህ ሠዎች የአቶማንን የአገዛዝ ቀንበር ሲሸሹ፣ በአበሻው ንጉስ ጥገኝነት የተሠጣቸውና ጥበቃም የሚደረግላቸው ናቸው። በመጨረሻም እንግዶቹ ቀስ በቀስ የሚያውቁት አንድ ነገር አለ። አቢሲኒያውያን ስሚታቸውን ወይም አስተሣሠባቸውን በግልፅ ማሣወቅ አይወድዱም። በዚያም አለ በዚህ፣ ሁለቱ ጓደኛሞች ስለነዚህ ጉዳዮች ምንም ሳያስተውሉ ለረዥም ጊዜ ሲያልሟት የነበረችውን የዚህችን የተረት ተረት ያህል የምትታወቅ አገር አካል መሆናቸውን በደስታ እያሰላሰሉ ጉዟቸውን ቀጠሉ። ጥቅጥቅ ያለውና ግራጫ መሆን ያጀመረው የሜትር ዠረሚ ፂም፣ የብልህና የአዋቂ ሞገስ ሲሰጠው፣ የጆን ባፕቲስት በጣም ጥቁርና የተጥመለመለው ፀጉሩ፣ ትኩስ ቁመናው፣ ግርማ ሞገስ ያለው ዛሳውና፣የመንገትና በደስታ የመሞላት ስሜቱ ጉን ለጉን ሊገዙ ወጣት ሃብታም አስመስሎታል።

ወደ ቤተመንግስቱ በዝግታ እየወጡ ሳሉ፣ የተሠበሠበው ሕዝብ በመሃል እንዲያልፉ መንገድ ይለትቁላቸው ነበር። ወንዶችም ሌቶችም አንድ አይነት ተራ ካባ፣ አንድ ወጥ በሚመስለው ቀጭን ትከሻቸው ላይ ሰብሰዋል። ምጥጥ ያለው፣ የታወቀ ቅርፅና መጠን ያላቸው ትልልቅ አይኖቻቸውና ቀጥ ያለው ቁመናቸው፣ ጀንን ባላባቶች ያስመሰላቸዋል። ድል ከተመቱ አገሮች የመጡ ባሮች ፊታቸው ሻከርና ጉብጦ አርስ በአርሳቸው እየተሰፋፉ ሲገዙ መለየት በጣም ቀላል ነው።

ከተማው አሁንም ቢሆን ጦራቸውን፣ የቆዳ ጋሻቸውንና በቅርቡ በተደረገው ዘመቻ የተያዙ እስረኞችን ይዘው በመንገዶች መሃል በሚንቀሣቀሱ የታጠቁ ወታደሮች እንደተሞላ ነው። አንድ ገለጥ ያለ፣ ከዚያም ሣር የሸፈነው አካባቢ ምናልባትም የሰልፍ ወይም የሰብሰባ ቦታ ሣይሆን የማይቀር ሲያልፉ ሜትር ዠረሚ ወደ ጆን ባፕቲስት ዞር አለ።

«ከትናንት ወዲያ ስለሠማነው ጉዳይ መግለጫው ይኸውና»

በቅርቡ ንጉሡ ድል ያደረጓቸው አንድ ሃያ ምርኮኛ ተዋጊዎች፣ አደባባዩ ውስጥ ያቃስቱ ነበር። ጥቂቶች ስብርባሪ ድንጋዮች ላይ ተቀምጠዋል። ሌሎች ደግሞ ክንዶቻቸውን ዘርግተው ቆመዋል። አምስት ወይም ስድስት የሚሆኑ ደግሞ ጭንቅላቶታቸውን በእጆቻቸው ሸፍነው መሬት ላይ ተጋድመዋል። ሁሉም በዝቢያ ጥቁቁር ፊቶቻቸው መሃል ሁለት የደም ምልክቶች በአይኖቻቸው ላይ ነበሩባቸው።

«የከሃዲዎች ቅጣት ነው» አለ ሃጅ አሊ

በድል አድራጊው ሰራዊት ተይዞ የመጣው የአማፂያን መሪ ተከስሶ በከፍተኛ ፍርድ ሰጪ አካል ሁለት አይኖቹ እንዲታወሩ ተፈርዶበት ቅጣቱ ከሁለት ቀናት በፊት ተፈፅሟል። አስረኞቹ አይኖቻቸው እንዲጠፉ ሲደረጉ፣ አሪታቸው በከተማው ሁሉ ውስጥና ሌላው ቀርቶ ሁለቱ ተጓዦች እንዲቆዩ እስከተደረጉበት ቤት ድረስ ይሰማ ነበር።

ንፂቸውን ወደ ቤተመንግስት ቀጠሉ። ጆን ባፕቲስት በኮርቻው ላይ ሆኖ ብዙ ጊዜ እየተጠማዘዘ ይህን አስደንጋጭ ትርዒት ሲመለከት፣ የተሰበሰበው ሕዝብ ግን ሰተጉጆ ሰለባዎች ምንም ቁብ የሌሰው ለማስመሰል ሲሞክር አስተዋለ። አንድ አስረኛ በጨለማው ውስጥ ሲንዘዛ፣ በዳበሳም ቢሆን ወደ አንድ አበሻ ለመድረስ ቢሞክር ወይም እርምጃውን በመንገድ ላይ ለማድረግ ቢጥር አላፊ አግዳሚው፣ ውሃ በቂጠረ መንገድ ላይም ቢሆን ይዘላል ወይም መንገዱን ስቶ ለመጣ እንሰሳ ጉዳናውን በመልቀቅ ምንም እንደማይመለከተው ሁሉ ሸሸሽ በማለት ይተወዋል።

ቤተመንግስቱ፣ ዙሪያውን ድንኳኖችና ጊዜያዊ ሕንፃዎች ግዳግዳውን ተጠግተው ስለሚከቡት፣ የሚታይ ያህል አይደለም። በጥርብ ድንጋይ የተሠራ ግዙፍ ሕንፃ ሲሆን ጉንና ጉኑ አራት ማዕዘን ቅርፅ ያላቸው ባስጉልላት ግንቦች አሉት። ሃጅ አሊ እየመራቸው ትልቁን ባለቀስት ቅርፅ የመተላለፊያ ጣሪያ ከጠባቂ ዘቦች ጋር ቃል ሳይለዋወጡ ከፈረሶቻቸው ወርደው፣ ፈረሶቻቸውን ለጠባቂዎች ሰጥተው፣ በእንድ ጨለም ባለ መተላለፊያ በኩል ሄዱ። በጣም ቀዝቃዛ የሆነና እምክ እምክ በሚሸት የእንግዳ መቀበያ ክፍል ለአጭር ጊዜ ከጠበቁ በኋላ፣ ሁለት ትላልቅ መስኮቶቹ ክታች ወደሚታየው ሳቢ የሚክፈቱ፣ ትልቅ የህዝብ መሠብሠቢያ አዳራሽ ውስጥ ይዘዋቸው ገቡ። ደርዝን የሚሆኑ ሰዎች በግድግዳው ዙሪያ ተሰልፈው የነርሱን መምጣት ይጠባበቃሉ። ሃጅ አሊ በጣም ጉንበስ ሲል፣ ጓደኞቹም እርሱን ሙሉ በሙሉ በመከረጅ ተመሣሣዩን አደረጉ።

ከቡድኑ መሃል አንድ ሰው ተነጥሰው ወጡ። ሰውዬው፣ ከሌሎቹ ትንሽ ቀደም ብሰው ቆሙ። በወርቀ ዘቦ የተጠለፈ ጥቁር ካባ ለብሠዋል። የወርቅ ሃብልም አጥልቀዋል። ፊታቸው ክብ ነው። ፀጉራቸው ጥምዝ ሆኖ በአጭሩ የተከረከመ፣ ፂማቸውም እንዲሁ በአጭሩ የተቆረጠ፣

ነው። የሜትር ዝረሚን ያህል ባይረዝሙም በእድሜ እኩያ ሳይሆኑ አይቀሩም። ሰሰምች ከፍ ባለ ድምፅ ተናገሩ።

«ይጠይቋችኋል» አለ ሃጂ አሊ «በእርግጥ ፈረንሳውያን ናችሁ?»

«ለመሆኑ ማን ናቸው?» ሲል መልስ ከመስጠቱ በፊት ጆን ባፕቲስት በሹክሹክታ ጠየቀው።

«ራስ ዮሐንስ ናቸው። የግዛቱ አፖ ጀኔራል ሲሆኑ፣ ከንጉሠ ነገስቱ በመቀጠል እጅግ ከፍተኛው ባለስልጣን ናቸው።»

«ፈረንሣውያን ሲሉ፣ ካቶሊኮች ማለትዎ ከሆነ መልሣችን አይደለም ነው። ክቡር ሆይ፣ እኛ የታላቁ ንጉስ የሉዊስ አስራ አራተኛ ህዝቦች እንጅ የሮማ ቤተክርስቲያን ጳጳስ ሰዎች አይደለንም»

ባለፉት ረዥም የቆይታ ቀናት ጆን ባፕቲስትና ሜትር ዝረሚ ሊቀርቡ ይችላሉ ብለው በጣም በገመቷቸው ጥያቄዎችና በመልሶቻቸውም ላይ በስፋት ተወያይተዋል። አባ ዴ ብራቬደንት ስለሌሉ ማንም ጥቃት ሊሰነዝርባቸው አይችልም። እንዲያውም በካቶሊክነት ላይ የሌሎች ሰዎችን አስተያየት ከቁም ነገር ሳያስገቡ ጭራሹን ጠላትነት እንዳላቸውና ራሳቸውን ከጀስዊቶች ማራቅን እንደሚመርጡ ለመግለፅ መሰኑ። ይህ አደገኛ ጨዋታ ቢሆንም የተሻለ አማራጭ አልነበራቸውም።

ከጥቂት ቁዘማ በኋላ፣ ራሱ ወይም ዋናው ባላባት «መጣንበት የምትሉት አገር የት ነው?» ሲሉ ጠየቁ። ሃጅ አሊ እንደተረጐመው የእንግዶቹ የመጀመሪያ መልስ ትንሽ ያደናገራቸው ይመስላል።

«ከሲናር፣ ከግብፅ ማዶ፣ ከታላቁ ባህር ሌላኛው ዳር ላይ ነው ክቡር ሆይ»

የአቢሲኒያውያን የጂአግራፊ ዕውቀት እስከነዚህ ሁለት አገሮች ብቻ እንደሆነ ጆን ባፕቲስት ያውቃል። በርግጥ ሌሎች ሕዝቦች ስለመኖራቸው፣ ስለፖርቹጋሎችና ስለኢጣሊያን ሲወራ ያውቃሉ። ነገር ግን የነዚህ ሕዝቦች አገሮች የት እንደሚገኙ ምንም ሃሣብ የላቸውም።

«በነዚህ ምድሮች ውስጥ ራሱን የክርስቲያኖች አለቃ ብሎ በሚጠራው ሰው አገዛዝ ሥር ያልሆኑ መሬቶች አሉ?»

ክሃምሳ አመታት በፊት ጀስዊቶች የጳጳሱን ትልቅ ሥልጣን በምዕራቡ ላይ ለመመስረት ሲሉ ያሰራጮትን ፕሮፖጋንዳ ጆን ባፕቲስት አስታወሰው።

«ክቡርነትዎ በርግጥ እንደሚያውቀው እንደ እድል ሆኖ ብዙ አሉ። ጳጳሱ የሰውን ነፍስ እገዛለሁ ይላሉ። ስለዚህም እነዚህን አገሮች አይገዙም። ነገስታት ግን፣ ከነዚህም መካከል አንዱ የኛ ናቸው፣ ብዙ ዓይነት ሕዝቦች በግዛታቸው ወስጥ ስላሉ ሌላው ቀርቶ እንደኛ የጳጳሱን ስልጣን አናውቅም የሚሉትን እንኳ ይጠበቁቸዋል።»

ቀደም ሲል በጦር ሰለባዎች ላይ የተፈፀመውን የሥቃይ ቅጣት ስላዩ ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት የውይይቱን አስፈሪ አደጋ በመስጋት ሜርት ዝረሚ አሁንም አሁንም አይኖቹን ያሻሸ ጀመር።

«እንዲህ ከሆነ በክርስቶስ አታምኑም ማለት ነው» ሲሉ ሌላው ሰው በድንገት ጠየቁ። ጥያቄው የመጣው ከራስ ዮሐንስ በስተግራ ከቆሙና ፀጉራቸውን በቀይ ሃር ካስጉነጉኑ አንድ ረዥም ሽማግሌ ሰው ነው።

«በርሱ እናምናለን፣ በትምህርቱም እናመልካለን» አለ ጆን ባፕቲስት «ይህን የምናደርገው በራሳችን ሥርዓት እንጅ በጳጳሱ አይደለም። በዚህ ግቢያ የናንተው እንደተከነከነው ሁሉ የኛም እምነት በጳጳሱ ተከንኖብናል።»

በተሰበሰቡት ባለስልጣኖች መካከል አንዳች ስሜት ተሰራጭቶ ጉምጉምታ ተሠማ። የአቋማቸውን ግርማ በማሰብ ራሳቸውን ከገዙ በኋላ እነዚህ ባለሥልጣኖች ርስ በርሳቸው ተያዩ። ከዚህ በኋላ ማንሾካሾክ ተጀመረ።

«ለመሆኑ ቀሣውስት ናቸው?» ሲሉ እኒያው አዛውንት ጠየቁ

«በጭራሽ፣ አይደለንም»

«ጉዳቱን እንፈውሣለን ትላላችሁ፣ ሲባልም እንሰማለን»

«በፍጥረት ጊዜ እግዚአብሔር ለሠዎች ልጆች መልካም ጠቀሜታ በማለት ያስቀመጣቸውን የእፅዋትንና የእንስሣት ቅመሞች ሰው ለሆነ ወገናችን በመስጠት እናገለግለዋለን እንላለን»

«እንዲህ ከሆነ ያለፀሎት መፈወስ ይቻላል ብላችሁ ታምናላችሁ»

«ፀሎት፣ ተአምራት እንዲፈጠር መለመን ነው። እኛ ይህን እናደርግም»

«በተአምራት አታምኑም?»

ጆን ባፕቲስት ቀደም ሲል ለኒያ ጀስዊት የሰጠውን ዓይነት መልስ ለመስጠት ከቃጣ በኋላ የተሻለ አሰበ።

«በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተመዘገበውን ተአምራት እናምናለን። በእግዚአብሔር ልጅ የተፈፀመውንም እናምናለን። ሌላ ተአምራት አናውቅም»

«ታላላት ቅዱሣን ተአምራት ሠርተዋል» አሉ ራስ ዮሐንስ

«ይህ ምናልባት የኛን የእምነት እውቀት ውስንነት ያመለክት ይሆናል» አለ ጆን ባፕቲስት «ክርስቶስ የተናገራቸውን ሁሉና በአራቱም ወንጌሎች ላይ የተፃፉትን በጥብቅ እንከታተላለን። ነገር ግን ሚች የሆነ የሰው ልጆች ሁሉ የተናገሩትን ፍፁም ትክክል ነው ብለን አንስማማም። ለምሣሌ አንድ ጊዜ አንድ ቅዱስ ሰው ሰይጣንን አማኝ አደረገው የሚለውን አይነት፣ ወይም አንድ የታመመና የተራበ መነኩሴ በፀሎት ኃይል ብቻ መሶቡ የተጠበሰ የቆቅ ስጋ ዘንበ ተሞላለት በሚሉት አናምንም»

እነዚህን ሁለቱን ምሣሌዎች ከአቢሲኒያ ተባረው ከወጡ ጀስዊቶች ከንፈሮች መስማታቸውን አስታውሰው ለጆን ባፕቲስት የነገሩት አባ ዴ ብሬቬደንት ነበሩ። በሰይጣን አለቃ በሱሲፈር ላይ ድል የተጐናፀፈው ቅዱስና የቆቅ ስጋ እንዲዘንብ ያደረገው መነኩሴ ታሪክ በኮፕቲክ ካህናት መካከል ውዝግብ ያስከተሉ ነጥቦች ናቸው። በዚህ ጊዜ በግልፅ የሚስተዋል ሁከት በተሠበሠቡት ባለሥልጣናት መካከል ተቀሰቀሰ። ጆን ባፕቲስት፣ እዚያ ከተሠበሠቡት መካከልም ቢሆን በጣም ጥልቅ አለመግባባት ያለባቸውን ሃይለኛ ነጥብ ስለነካው ይመስላል

ራስ ዮሐንስ በክፍሉ ውስጥ ፀጥታ እንዲሰፍን አዘዙ። ሰዎችም ፀጥ አሉ። ከዚያም አንድ አጭር ሰው ክባስልጣናቱ መካከል ወጥተው ወደፊት ተራመዱ። ቢጫ ብርቱካንማ የመነኩሴ ልብስ ለብሠዋል። ያበጡት አይኖቻቸው አጥርተው አያዩላቸውምና በዙሪያቸው የሚገኘውን በጭጋግ ውስጥ የሚያዩ ይመስላቸዋል።

«ክርስቶስ ስንት ባህርያት አሉት?» ሲሉ እንደቃጭል በቀጠነ ድምፅ ጠየቁ።

የጥያቄዎቹ ሁሉ እምብርት ይህ ነው። ጀስዊቶች ለረዥም ጊዜ የተፋጠበት ጥያቄ ነው። ነጥቡ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና የሮማ ቤተክርስቲያን ከአስራ ሁለት ክፍለ ዘመናት በፊት እንዲለያዩና በየራሣቸው መንገድ እንዲጓዙ ያደረጋቸውና ሊገለፅ ያልቻለ ውስብስብ የመንፈሣዊ ትምህርት ጉዳይ ነው። ሁለቱ መንገደኞች ቀደም ሲል ባደረጉት መሠናዶ ውስጥ እንዲህ ያሉ ጥያቄዎች ይነሣሉ ብለው ዝግጅት አላደረጉም ነበር። በጣም በግልፅ እንደሚታወቀው እንዲህ ያለ ክባድ ሃሣብ ይነሣል ብሎ የተጨነቀም ሰው አልነበረም። ሜትር ዠረሚ ወደ ጆን ባፕቲስት ሲመለከት ጥልቅ የመደነቅ ስሜት በፊቱ ላይ አስተዋለበት።

10

«ክርስቶስ ስንት ባህርያት አሉት?» ሲሉ መነኩሴው ለሁለተኛ ጊዜ ጠየቁ።

ክባድ ዝምታ በክፍሉ ሁሉ ላይ ሰፈነ። ሁሉም ዓይኖች ምንም ወደማይናገረው ወደ ጆን ባፕቲስት ዞሩ። ከዚያም በድንገት እንዳች መንፈስ አነሣሣውና ተበረታታ።

«ክርስቶስ ስንት፣ ስንት ባህርያት አሉት የሚለውንማ ጥያቄ አባቶቼ እኔ እናንተን የምጠይቀው ነው።»

ሃጂ አሲ ቃላቱን እንዲተርጉም ጊዜ ሠጠውና ቀጠለ።

«እያንዳንዳችን መናገር የሚገባን በራሣችን የሙያ አውቀት ዙሪያ ያለውን ነው። በበኩሌ እኔ ሐኪም ነኝ። ጓደኛዬም መድሃኒት በመቀመምና በማዘጋጀት ባለሙያ ነው። ከዚህ ውጭ የምናውቀው በጉናችን ታጥቀናቸው ያሉትና አያያዛቸውንም የምናውቅባቸውን ጉራዴዎቻችንን ነው። እፅዋትንና መሣሪያዎቻችን በተመለከተ፣ አባቶቻችን፣ ደስ ያላችሁን ጠይቁንና በተቻለን መጠን የሚያረኩ መልሶች እንሰጣችኋለን። ነገር ግን አሁን የጠየቃችሁን ጥያቄ በርግጥ እናንተን የመሰለ የመንፈሣዊ ትምህርት ሊቃውንትን የሚመለከት ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ለመማር ደግሞ ዝግጁ ነን።»

ጆን ባፕቲስት በክብር ዝቅ በማለት መልሱን አጠናቀቀ። ነጭ ካባውን እንደለበሰ አንድ እጁን በልቡ ላይ አሣርፎ ወደ ራስና እዚያ ወደ ተሰባሰቡት ጓደኞቻቸው ትጥቅ በማስፈታት ታማኝነት መልክ ተመለከታቸው።

በአንድ ገደል ጥግ፣ በሁለቱም ጉኑ ስለ መድረሻ ባለው ጠባብ መንገድ ላይ የሚራመድ መስሎት ውስጡ ተሰቃየ። ልቡ ዘለለች። ቀዝቃዛ ላብ በጀርባው ቁልቁል ወረደ። ይሁንና ይህን ሁሉ ላለማሣየት ራሱን አበረታ።

ረዘም ያለ ፀጥታ ተከተለ። የሚሰማ ድምፅ ቢኖር በግቢው ውስጥ የተነሣው የሴቶችና የወንዶች የተደባለቀ የቅሬታ ድምፅ ብቻ ነበር።

«ንጉሰ ነገስቱን ለማየት ተዚጋጃ» አሉ ራስ ዮሐንስ በመጨረሻ በፈጠዋ ቅላፄ። «ልትፈውሣቸው የሚያስችልህ እውቀት እንዳለህ በመግለፅህና ግርማዊነታቸውም የህክምና ትዕዛዝህን እንደሚፈፅሙ በመግለፃቸው፣ ከፊታቸው እንድትቀርብ ይደረጋል። ይሁንና ላስታውቅህ የሚገባኝ፣ ንጉሰ ነገስታችን ከማንም ጋር በቀጥታ ግንኙነት አይጀምሩም። ይህ በውጭ ሰዎችም ላይ ይለራል። አትነካቸውም ወይም አትጠጋቸውም። ነገር ግን ታያቸዋለህ። በእንደራሴያቸው በኩልም የሚናገሩትን ትሰማለህ»

«ነገር ግን ይህ የሚቻል አይደለም። እርስዎም ቢሆኑ ይህ እንዴት ሊሆን . . .»

«አካሄዱ ይኸው ነው። ልትፈውሣቸው ችሎታው አለህ ወይስ የለህም?»

በቀረበለት አስገዳጅ ቃል ጆን ባፕቲስት ተስፋ ቆረጠ። ምክንያቱም ሃጅ አሊ የገለፀለትን የንጉሡን ህመም የማከሙን ሁኔታ ይጉዳበታል። ከዚህም ባሻገር የዲፖሎማቲክ ተልዕኮውንም ይጉዳበታል። ታዲያ ለንጉሰ ነገስቱ መልዕክቱን እንዴት ያስተላልፍላቸዋል? ይህንን ያህል ግልፅ ስለሆነ፣ ራስ ምንም ተቃውሞ አይፈቅዱም። ፖንሴም የቀረበውን ቃል እንደተባለው ተቀበለ። ባለሥልጣኖችም ከከፍተ በለልፍ ለቀቁ ። ሦስቱ ተጓዦች ተመልካቻቸውን እንዲጠብቁ ከዚያው ቀሩ።

«እነዚህን ዝርዝር ነገሮች በሞራሽ አልገለፅካቸውም» አለ ጆን ባፕቲስት፣ ለሃጅ አሊ በቁጣ «ንጉሡን ልናነጋግራቸው እንችልም»

«በህዝብ ፊት፣ ሰው የማይደርስባቸው ናቸው» አለ ግመል ነጂው። «ይህ ደንብ ነው። ሌላው ቀርቶ መሬቱን እንኳ እንዲነኩ አይፈቀድላቸውም። ዙፋናቸው ላይ ሲቀመጡ ሲሉ መጀመሪያ በበቅሎ ጀርባ ላይ ሆነው ይመጡና ሲወርዱ፣ እግራቸው መሬት የሚያርፈው ዙፋኑ የተቀመጠበት ምንጣፍ ላይ ሲደርሱ ብቻ ነው። በቅሎዋ ምንጣፉ ላይ ስትወጣ ሁልጊዜም በዚያ የፋርስ ጌጥ መሀሉ ላይ ፋንድያዋን ትጥላለች። ሁሉም የለመደው ነገር ስለሆነ ለውጥ አያመጣም። እንደእውነቱ ከሆነ እናንተ እድለኞች ናችሁ። ነገሮች በጣም ተሰዋውጠዋል። በቀድሞ ጊዜ ንጉሠ ነገስቱን በፍፁም አታያቸውም። የኒህኛው አያት ለህዝብ የሚታዩት በአመት ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ ብቻ ነበር። ከዚህ በተረፈ ከሚያምረው መጋረጃ ጀርባ ነበር የሚኖሩት»

«ንጉሡ ለምንድን ነው የማይናገሩት?»

«ልማዱ ይኸው ነው። አያንዳንዱን ተግባር የሚያከናውንላቸው አንዳንድ ሃላፊ አላቸው። ለምሳሌ የንጉሱ አይን የሚባል አለ። ይህ ሃላፊ በቤተመንግስቱ የሚያየውን ሁሉ ሪፖርት ያደርግላቸዋል። የንጉሥ ጆሮ የሚባልም አለ። እንደራሴያቸው ሆኖ ስለራሳቸው ይሠማል። የቀኝ እጃቸው እና የግራ እጃቸው አዛዦች የሆኑና ሠራዊታቸውን የሚቆጣጠሩላቸው አሏቸው። ሌላው ስማ በለው ይባላል። የንጉሡን ቃሎች በከፍተኛ ድምፅ ጮሆ ያሰማል።»

«ለመሆኑ ልጆቻቸውን የሚያሣድጓቸው ራሣቸው ናቸው?» ሲል ሜትር ዝረሚ አጉተመተመ።

«ቀልዱን ተወውና ወደ ቁምነገሩ እንመለስ። ብዙ ጊዜም የሰንም» አለ ፖንሴ «ለመሆኑ ለአለፉት ሃምሣ አመታት ምንም ሣይበሉ የኖሩት ቅዱስ ምን አጋጠማቸው? ደግሞስ እኛ ከእርሣቸው ጋር ውድድር ውስጥ ነው ያለነው ወይስ እሳቸው ዓዛቸውን እንዲጠቀሉ ተደርገዋል?»

«ሃያ አመቶች» አለ ሃጅ አሊ ጠንቀቅ ብሎ «ሃያ አመት ሙሉ ምንም አልቀመሡም። አቤቱ ነብይ! እንዲህ ያለውንስ ቀልድ አይቁጠሩበት . . . »

የጣቶቹን ጫፎች ሳማቸውና ዓይናቸን ወደ ሠማይ አቀናቸው

«ንጉሰ ነገስቱ?» ሲል ቀጠለ «ቅዱሱን ሰው ከእንግዲህ በኋላ አምነው ምስጢራቸውን አያዋዩዋቸውም»

«እግርጠኛ ነህ? እንጀራቸውን አንነጥቃቸውም» ሲል ሜትር ዝረሚ ጠይቀ።

ፖንሴ በቁጣ ገሳመጠው።

«ይቅርታ» አለ ዝረሚ «ረዥሙ ቆይታችን አበሳጭቶኝ ነው»

«ቀልደህን፣አይኖቻችንን ስሚያወጡበት ጊዜ አቶየው» አለ ጆን ባፕቲስት ትህትና በጐደለው መልክ። እንደ እውነቱ እርሱ ራሱ ክንደኛው በባለ ጨሳል።

ወዲያውኑ ሁለት ዘበኞች ሊመሯቸው መጡ። ሦስቱም ሰዎች ተከታታይነት ባላቸው ትናንሽ ጨለማ፣ ቀዝቃዛና አና ክፍሎች በኩል ተከትለዋቸው ሄዱ። ተጠቃልለው እስኪደርሱ ጠበቁና ወደ እንግዳ መቀበያው አዳራሽ ገቡ። አዳራሹ በጣም ሠፊ ክፍል ሲሆን፣ በአንድ አብይ ዋልታ ላይ የተዋቀረ ባለ ሦስት ቀስት ጫፍ ጣሪያው በአምስት ክብና ወፋፍራም ምሰሶዎች ላይ በመሃልና በጐንና ጐን በኩል አርፏል። ከቤተ መንግስቱ ባለሟሎች አብዛኛዎቹ ከኋላ በኩል ቆመዋል። ወደ ንጉሡ ቀረብ እየተባለ ሲመጣ ባለው ሬድፍ ላይ ብዙ ሰዎች ተቀምጠው ይታያሉ። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ሁሉም በንጉሱ እይታ ውስጥ ስላልሆኑና በባህሉም ንጉሡ ሊያዩዋቸው የሚገቧቸው ሁሉ፣ ስብሰባው ለሰዓታት እንኳ ቢቀጥል ቆመው መታየት ስለሚኖርባቸው ነው።

አዜው ጓዳ በመሠለ ቦታ፣ በምንጣፍ ላይ በተደረገ ዙፋን ላይ ከወደ ጥግ ተቀምጠዋል። በቅሎይቱ እንደተለመደው ፋንድያዋን ጥላለች። የአዜው አቀማመጥ ከፊት ለፊት ከተቀመጡት የአጃቢዎች መስመር ብዙ እርምጃዎች ራቅ ብሎ ነው። እነዚያ የውጭ ዜጐች በፀጥታ እየተመሩ ወደፊት ተወሰዱ። በዚህን ጊዜ ግቢው ውስጥ አንበሶች ሲያገሱም ሰሙ። በእነዚህ ተይዘውና ታስረው በሚገኙ አንበሶች የተነሣ ንጉሠ ነገስቱ ዝና አግኝተዋል። በአዳራሹ ሌላኛው ጠርዝ ቀደም ሲል ከራስ ዮሐንስ ጋር ቃለ ምልልስ ሲያደርጉ በነበረበት ጊዜ ያደመጡትን ዓይነት የሀዘን ዜማዎች ሰሙ።

ቀደም ሲል በተሰማሙት መሠረት ፖንሴና ጓደኛው፣ ሃጅ አሊ የሚያደርገውን እያንዳንዱን አነስተኛ እንቅስቃሴ በመከተል ይኮርጃሉ። ከንጉሡ ፊት ሲደርሱ ግመል ነጅው ተንበረከከ፣ ከዚያም ክንዶቹን ወደፊት እንደመዘርጋት አድርጐ በድንጋያማው ወለል ላይ ሙሉ በሙሉ የመዘርጋት ያህል ለጥ አለ። ሌሎች ሁለቱ በትክክል ይህንኑ ፈፀሙ። እንዳሰመታደል ሆኖ ሜትር ዝረሚ ተንበርክኮ በጣም ወደፊት ስለተሳበ እጆቹ የቤተመንግስቱን ምንጣፍ ነኩ። ሁለት ባለስልጣኖች ወደ ኋላ ገፈተሩት። ሶስቱ ሰዎች፣ አዜው ከፊታቸው እንዲቀርቡ መፍቀዳቸውን «አፈ ንጉሱ» እስኪያስታውቋቸው ድረስ እስኪደክማቸው ቆሙ። ከዚያ በኋላ አዜውን ለማየት ቻሉ።

የአቢሲኒያው ንጉሰ ነገስት አፄ እያሱ፣ የሀንዳውያንን ጨርቅ ለብሰው ከፍ ካለ ቦታ በተቀመጠው ወርቃማው የእንጨት ዙፋናቸው ላይ ሆነው ይታያሉ። የአዜው ሰውነትም ይሁን ፊታቸው በትልቅ ደማቅ ቀይ ልብስ ስለተሸፈነ ሦስቱ ሰዎች በግልፅ ሊያዩዋቸው አልቻሉም። ረዥሙ ፀጉራቸው፣ በቀጭን የጥጥ ጨርቅ ሻሽ ከማጅራታቸው ላይ ታስሮ በግራና ቀኝ አገጫቸው በኩል ወርዷል። በሚገባ የሚታየው ቀጠን ያለው ትልቅ እፍንጫቸው፣ የሚያበራውና ፈዘዝ ብሎ የሚመስለተው ዓይናቸው ነው። እፋቸው፣ በእንገታቸው ዙሪያ በተጠመጠመላቸው የታጠፈ ቢጫ የሃር ፎጣ ላላ ተደርጐ ተሸፍኖላቸዋል።

ሲናገሩ ድምፃቸው አይሰማም። ስለዚህም የንጉሠ ነገስቱ ፈቃድ የሚሠማው፣ ለዚሁ ሲባል ሃላፊነት የተሰጠው ባለሥልጣን ግልፅና ከፍ ባለ ድምፅ መልሶ ሲናገረው ነው። በንግግሩ መሃል፣ ሃጅ አሊ ማስተርጉም ማቆሙን ጆን ባፕቲስት አስተዋለ። ከአፈንጉሡ በስተቀኝ የቆመ አንድ አቢሲኒያዊ ተርጓሚ በይፋ የሚሰጡትን መግለጫዎች በሙሉ በአረብኛ ይነግራቸዋል። ከንጉሰ ነገስቱ ጋር የተደረገው ይህ ይፋ ስብሰባ በጣም አጭር ነበር። ንጉሠ፣ በሠውነታቸው ላይ ስላለው ህመም ከውጭ አገር ሰዎች ምክር እንደሚሹ ከማረጋገጣቸው ባሻገር ዝርዝር ነገር አልተነገረም። ፖንሴ፣ ከግብፅ ፓሻ የመጣውን የፅሁፍ መልዕክት «ለቀኛዝማች» አቀረበላቸው። ንጉሰ ነገስቱ፣ እንደሀ ካለው ገዥ ጋር በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን የንግድ ሁኔታ አስመልክቶና ግብፅ፣ የአሌክሳንደርያው ፖትርያርክ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የምትተማመንበትን አቡን እንዲልኩ በመፍቀድ ጉዳይ ላይ መልካም ግን ጉንቱ እንዲቀጥል እንደሚወድዱ መልስ ሰጡ።

የፓሻው ደብዳቤ በአረብኛ አስተርጓሚው ተነበበ። ደብዳቤው አጭርና በምስጋና የተሞላ ነው። በዚህ ውስጥ የፖንሴ ሐኪም መሆን በተለየ አፅንኦት ተገልጿል። በፓሻው ስላልተጠቀሰው ሜትር ዝረሚ ደግሞ ፖንሴ ሃላፊ ሆነ። ስንጉሠ ነገስቱ ያመጡላቸውን ገፀ በረክት ደግሞ ፕሮቴስታንቱ ሰሌላ ባለስልጣን አስረከበ። እንደግለሰብነታቸው መድሃኒት ቀማሚዎች ድንቅ ገፀ በረክት እንዲያቀርቡ አይጠበቅባቸውም። በሃጅ አሊ ምክር መሠረት በገዘሆን ጥርስ የተሰሩ እጀታዎች ያሏቸው አንድ ሣጥን ምላጮችን ሦስት ሜትር በአምስት ሜትር የሆነ አንድ ቡተረት ውስጥ የሚታወቅ አጭር ሰው፣ አጋዘን ሲያድን የሚያሣይ ስዕል ያለበት ጨርቅ ነበር ያቀረቡት። ስጦታው በንጻ ፀኩል ወዲያውኑ ተሰወረ።

ንጉሱ፣ ምንም ዓይነት ምስጋና ሳያቀርቡላቸው አሰናበቷቸው። የተናገሩት ቢኖር በሚቀጥለው ዕለት የህክምና ትዕዛዛቸውን እንደሚጠብቁ ብቻ ነበር። በዙፋኑ አጠገብ ቦታቸውን የያዙት ራስ ዮሐንስ፣ ዛቻ ያለበት በሚመስል አነጋገር፣ መድሃኒቱ መጀመሪያ በሶስት ባሪያዎች ላይ፣ ቀጥሎ በሁለት ባለስልጣኖች ላይ ተሞክሮ እንደሚፈተንና ንጉሰ ነገስቱ ከዚያ በኋላ እንደሚሰጣቸው አክለው ተናገሩ። በዚህ ሂደት ውስጥ በየትኛውም ደረጃ ላይ አደጋ ቢከሰት በሁለቱ ባዕዳን ላይ ውጤቱ የከፋ ይሆናል። በመጨረሻም በከተማውና በገጠሩ እንደልባቸው ሰመዘዋወር ነፃ መሆናቸውን ነገሯቸው። ከሚፈልጉት ማንኛውም ሰው ጋር መነጋገር ይችላሉ። ነገር ግን የካቶሊክን እምነት የሚሰብክ የሚመስል አንድ ቃል ቢተነፍሱ ፈጣንና ተገቢው ቅጣት ይፈፅምባቸዋል።

እንግዶች ለሁለተኛ ጊዜ ብዙ በመቆማቸው ከደከሙ በኋላ፣ ሲደበደቡ የቆዩ ይመስል ክፉኛ እየተንቀጠቀጡ የስብሰባውን አዳራሽ ለቅቀው ወጡ።

ወደ ሃጅ አሊ የሙስሊም ጓደኛ ቤታቸው በመመለስ ላይ ሳሉ አንድ እንደነገሩ የለበሰ አግረኛ መልዕክተኛ ሲሮጥ ደረሰባቸው። ሁለቱ ባዕዳን ሣጥኖቻቸውን ቀርቅበው በፈረሶቻቸው ላይ እንዲጭኑና እንዲከተሉት ነገራቸው። ሃጅ አሊ ብዙውን ነገር ስለዘረፋቸው የመጫን ስራው የሚወስድባቸው ጥቂት ጊዜ ነው። ከቀሯቸው ጥቂት ቁሣቁሶች ውስጥ ያረጁ የአውሮፖውያን ልብሶቻቸውን፣ አረቡ ሊያነብባቸው የማይችላቸውን መፃህፍቶቻቸውን፣ የመድሃኒት ሻንጣቸውንና በጨርቅ ውስጥ ሆነው በኮርቻ ስር ያሉትን የሚወዷቸውን ጉራዴዎቻቸውን በጆንያ ውስጥ ከተቱ። መልዕክተኛው ቀደም ሲል ከጹበት ጉን በተቃራኒው ባለ ከቤተመንግስቱ ግድግዳ ቀጥሎ በሚገኝ የድንጋይ ቤት አስገባቸው። ለዘበኛ ተብሎ የተሠራ ቤት ይመስላል። መግቢያው ወደ አንድ ረዥም የመወጣጫ ደረጃ የሚያመራ ጠባብ የመተላለፊያ ቦታ ነው። በክፍሉ ቁልፍ ተቸንክሮ የነበረውን ከባድ መዝጊያ በትግል ከከፈተው በኋላ ይህንኑ መልዕክተኛ ተከትለው ደረጃዎቹን ወጡ። መጠነኛ ስፋት ያለው ክፍል አሳያቸው። ወደ ማስዳው ፀሐይ አቅጣጫ በሚከፈት መስኮት ብርሃን ይገባል። በክፍሉ ውስጥ ሁለት የጠፍር አልጋዎች፣ ሁለት የእንጨት በርፖሣዎች፣ አንድ ጠረጴዛና ለጋራ የሚያገለግል መስታወት አለ።

በፖንሴና በጓደኛው አዕምሮ ውስጥ የሚመላለሰው ጥያቄ ግዙፉ ቁልፍ ምን እንደሚሆን ነበር። ለነርሱው ተሰጥኦቸው ይህ ከእንግዲህ ቤታችን ነው ብለው እንዲያስቡ ያደርጋቸው

ይሆን? መልዕክተኛው ግን ቁልፉን በበሩ ላይ ተወው። ይህ ሰው አረብኛ አያውቅም ነበርና ከርሱ አንዳችም ነገር ማወቅ አልቻሉም።

ሁለቱ ጓደኛሞች ብቻቸውን ከቀሩ በኋላ ለረዥም ሰዓታት በየአልጋቸው ላይ በፀጥታ ተጋድመው ቆዩ።

«እንደ ዮናስ በአሳነባሪ ሆድ ውስጥ የሆንክና በህይወት የምትውጣበት ምንም ዕድል እንደሌለህ ታስባለህ?» ሲል ዠሪሚ በመጨረሻው ጠየቀው።

«በአንድ ጊዜ አንድ ነገር ላይ እናተኩር» አለ ጆን ባፕቲስት እየተንጠራራ። «እስከአሁን ድረስ ጥቂት መሰናክሎችን አልፈናል። ከአንግዲህ ቀጣዮቹን ማየት ይገባል። ዛሬ ማታ ለንጉሡ ባሪያ መድሃኒት እናዘጋጅለታለን። ሃጅ አሊ እንዳረጋገጠልን፣ ንጉሱ ያለባቸው ሕመም ልክ እርሱ ላይ እንዳለው ደዌ ነው። ከዚያ በኋላ የሚሆነውን እናያለን።»

ይህን ተናግሮ ጆን ባፕቲስት እንቅልፍ ወሰደው። ሜትር ዠሪሚ በደስታ የጓደኛውን ፈለግ ተከተሰ።

በሩ ላይ በተፈጠረ አነስተኛ መንኳኳት ነቁ። በውጭ ያለው የፀሐይ ብርሃን ቀነስ ያለ ሲሆን፣ ስማያዊ ጥላ ከወደ መንገዱ በኩል እየዘለቀ ነው። ጊዜው ከቀትር በኋላ ዘግይቶ ነው። ወደ ክፍላቸው የዘለቀው ወጣት ሰው ሃያ አመት የሚሆነው አጭርና በጣም ቀጭን ነው። ፊቱ በፈንጣጣ የተላላጠ ስለሆነ ሕመሙ ቆዳውን አደድርታል። ፊቱ ሸካራ ሲሆን አፍንጫው በተለይ አጭርና እንደካስ ኩበ ነው። ጥቋቁር አይኖቹ ብልህነትና ለዛ የተሞሉ ናቸው። በክንፈርቹ ላይ ፈገግታ ሲያንዣብብባቸው አጪቃላይ እንቅስቃሴው ስዛ ያለው ነው። እነዚህ ምልክቶች ከጥቁርና ከርዳዳው ፀጉሩ ጋር ሲታይ፣ ለጆን ባፕቲስት እንዳልታደለ ወንድሙ ያህል ነው።

«ስሜ ዲሚጥሮስ ነው» አለ በአረብኛ

አረብኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ መናገሩ በግልፅ ያስታውቃል። አፍ የፈታበትን ግሪክኛንም እንደሚናገር ነገራቸው። አነርሱ ግን ይህን ቋንቋ አያውቁትም። ጣሊያንኛን ግን

ሁለቱም ፈረንሣውያን ቪኔስ ውስጥ ተምረው ነበር። ውይይታቸው የቀጠለው በዚህ ቋንቋ ነበረ።

ዲሚጥሮስ፣ የንጉሠ ነገስቱ የግል አሽከራቸው መሆኑን ራሱን አስተዋወቀ። ሃጅ አሲ በጣም ስራ ስለሚበዛበትና በተከታታይ አብሯቸው ሲሆን ስለማይችል እነርሱ በፈለጉት ጊዜ ዲሚጥሮስ ሊያጅባቸው ይችላል። ከማንም ባይሠሙም ዲሚጥሮስ አዲሱ የእስር ጠባቂያቸው መሆኑን ተገነዘቡ። ነገር ግን የዚህ ወጣት ፍልቅልቅና ደስተኛ መሆን ንግግሩንም እንዳስ ቧቸስታ እንዲቀበሉት አደረጋቸው።

«ከተማውን መጐብኘት ትፈልጋላችሁ? እራት ለመብላት ይዣችሁ ልወጣ እችላለሁ። ወይም ምግባችሁ እዚህ እንዲመጣላችሁ ልናደርግ እንችላለን»

ጊዜው ገና ስላልመሸና ስለዋና ከተማውም እስክ ዛሬ ምንም ስላላዩ ከተማውን እየተመሩ ለማየት ተስማሙ።

ሦስቱም ተመሣሣይ የጥጥ ልብሶችን ለብሠው በእግራቸው መንገዝ ጀመሩ። ሁለቱ ፈረንሣውያን እነርሱን በሚመስል ሕዝብ መሃል በነፃነት መንቀሣቀስ የሚችሉና ከእንግዲህ በኋላም እንግዶች እንዳልሆኑ የተነገረው ሃሣብ አስደሰታቸው። ዲሚጥሮስ እንደሁልጊዜው ፈገግታው፣ በባለማወቅና በድንገት አስተሣሰባቸውን ያርመዋል።

«እኔ አብራአችሁ እስካለሁ ድረስ አንዳችም ነገር አያስፈራችሁም። ቀሣውስቱም ሊገድሏችሁ አይደፍሩም» አላቸው።

እነዚህ ቃላት ከተነገሩ በኋላ ሁለቱ ባዕዳን እያንዳንዱን አላፊ አግዳሚ በጥርጣሬ ማየት ጀመሩ። አቢሲኒያውያን ያለልዩነት ግደሰሾች መሰሏቸው። እነርሱ በሚያልፉበት ጊዜ ወደነሱ ዓይኖቹን ዞር የሚያደርግ ወይም አፍጥጦ የሚያያቸው የለም። በመሆኑም መኖራቸውን እንኳ ልብ የሚለው የለም ብሎ ምሎ የሚወራረድ ይኖራል።

ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚዝቡበት አነስተኛ መንገድ ወደ ዋና ጐዳና ያድጋል። ከነዚህ መንገዶች በአንደኛው ረዥም ሰልፍ ሲመጣ ሊያሳልፉት በማሰት ቆሙ። ሰልፉ ደማቅ ቀይ፣ ዘርፋፋ ካባና በወርቅ የተጠለፉ ቆቦች በለበሱ ቀሣውስት የሚመራ ነው። ክበድ ያሉ ነገሮችን፣

ስርዓት ያላቸው ቀዳዳ የተበጀባቸውን መስቀሎች በቅርዕ ላይ ተሸክመዋል። የመስቀሉ ንድፍ አለቅጥ የተደጋገመና መልክ እንዲኖረው በመሠራቱ ሊገጣጠም መልሶ መስቀል የሚሆን ነው። በመሆኑም ብረቱ ሃያልና መሠረታዊ በሆነ ቅርዕ ላይ እንደ አመዳይ የረጋ አብረቅራቂ መስተዋት መስሏል። ከቀሳውስቱ በስተኋላ ጦሮችን፣ የጠቋቋሩ ጋሻዎችንና ወገባቸው ላይ ፖቤአቸውን የታጠቁ ተዋጊዎች ተከትለዋል። ጥቂቶቹ በክንዶቻቸው ላይ ቀጫጭን የቀይ ጨርቅ ጥምጣሞችን ቋጥረዋል። ይህ የክብር ምልክት መሆኑንና እያንዳንዱ ጥቁጣብ የተገደለውን ጠላት ቁጥር እንደሚያመለክት ዲሚጥሮስ አብራራላቸው። በሰልፉ መሃል ላይ፣ ኮስተርና ፀጥ ያሉ ወታደሮች አሉ። እነዚህ ምናልባት የሰልፉ ዓብይ ክፍል ሣይሆኑ አይቀሩም። በረዥም ጦር ጫፍ ላይ የእንጨት መስቀል ተሠርቶበት ከራሱ በላይ ከሁሉም ሰው ሙሉ በሙሉ በሚበልጥ ረዥምና ጠንካራ በሆነው አቢሲኒያዊ ተይዟል። በአንድ መንበቀ ባለው እንጨት ላይ ከጥቁር ሃር ጨርቅ የተሠራ ጃኬት የመሰለ ነገር ተሰቅሏል። ይህ ነገር ሁለት እጀጌዎች ሲኖሩት ጭራው ላይ ሁለት የተበጣጠሱ የመስመር ምልክቶች አሉበት። ልብሱ በልዩ ልዩ ቀለማት የተሸፐራረረ የኔ ብጤ ልብስ ይመስላል። ከዚህ እንግዳ ነገር ከሆነ ምልክት ቀላ ያለ ፊላሽ ይንጠባጠባል።

«ኦ እንደምትበሳፖ እገምታለሁ» አለ ዲሚጥሮስ እነርሱን በጭንቀት እየተመለከተ።

«ቆዳ ይመስላል» አለ ሜትር ዝረሚ አይኖቹን ብልጥጥ አድርጐ ክፍቶ በፍርሃት

«የዚህችን አገር ህግ ለማድነቅና ልትጨብጧቸው የሚገቧችሁ፣ በመጠኑ ለየት ያሉ በመሆናቸውም ሰመገንዘብ የሚያስቸግሩ ግን አስፈላጊ ነገሮች አሉ።» አለ ዲሚጥሮስ። «የተለያዩ የቅጣት አይነቶች አሉ አሁን የምታዩት አይነት ቅጣት ብዙም አይፈፀምም። እንደ እድል ሆኖ በዚህ የሚያስቀጣውም ወንጀል እንደሁ አይሠራም። ለጠላት ያደሩ ክሃዲዎች ዓይኖቻቸው እንዲወጡ ይደረጋል።»

«ያንን አይተናል»

«አዎ፣ ወዳጅ ሆኖ፣ የራሣችን የጦር ሠፈር ሰው ሆኖ፣ የራሣችን ቤተሰብ ሆኖ ልክ አሁን እንደተደረገው ከህይወቱ ቆዳው ይገፈፋል።»

ይህ ሊነገር፣ ጆን ባፕቲስትና ጓደኛው ይህ በነፋስ የሚውለበለብ አስደንጋጭና በሞራልም ረገድ መጥፎ የሆነውን ቆዳ ሲመለከቱ አጥወለወላቸው። ከሰልፉ በስተመጨረሻ ያሉት ፈገግ የሚሉ ሴቶችና ሕፃናት ሲሆኑ በፀጥታ ያጨበጭባሉ።

ሦስቱ ሰዎች ጉዟቸውን ቀጠሉ። ሁለቱ ባዕዳን ባዩት ነገር ክፉኛ እንደሚጉዱ ዲሚጥሮስ ይሰማዋል።

«አትበሳ፫» አላቸው። «የደረሳችሁት ድል አድራጊ ወታደራዊ ሠራዊት ከዘመቻው በተመለሠበት መጨረሻ ላይ ነው። አስረኞቹ እየተቀጡ፣ ከሃዲዎች እየተጋሰጡ፣ ጀግኖች እየተሸለሙ ነው። ሕይወት ሁል ጊዜም አስደሳች አይደለም»

«በመስማታችን ደስ ይለናል።» አለ ሜትር ዣረሚ «የኛም ቆዳ በጉዳናዎች መሃል በሰልፍ የሚያልፍበት ጊዜ እስኪመጣ ለህዝቡ የምንሠጠው አዝናኝ ነገር እምብዛም አይኖረንም። ይህን በማወቃችን እንፅናናለን።»

«የናንተ ቆዳ በጉዳናዎች መሃል መቼም በሰልፍ አያልፍም» አለ ዲሚጥሮስ በሳቅ እየተንከተከተ። «ይህ ሙሉ በሙሉ ሊሆን የማይችል ነገር ነው።»

«መድሃኒታችን ውጤት ባይሰጥስ ምን ይሆናል?» ሲል ፖንሴ ጠየቀ

«ያን የመሰለ ቅጣት በናንተ ላይ አይፈፀምም። እናንተ የንጉሠ ነገሥቱ እንግዶች ናችሁ»

«ጀስዊቶችስ? የንጉሠ ነገስቱ እንግዶች አልነበሩም እንዴ?» አለ ሜትር ዣረሚ

«አ! ቆይ እስኪ» አለ ዲሚጥሮስ አመልካች ጣቱን አውጥቶ «እኔ እስከማውቀው ድረስ ጀስዊቶች ከነ ህይወታቸው ቆዳቸው አልተገፈፈም። አነርሱን በተመለከተ ሕጉ በጥብቅ ነው የተፈፀመው»

«ማለት?»

«ማለትማ በድንጋይ ተወግረው ተገደሉ። ወደታች ተመልሰን ስንሄድ፣ በአደባባዩ መካከል ላይ ሁለት የድንጋይ ክምሮችን ታያላችሁ። የመጨረሻዎቹ በሞት የተቀጡት ጀስዊቶች የተቀበሩበት እዚሁ ነው። እነዚህን የድንጋይ ቁልሎች ደግሞ ማንም እንዲነካቸው አይፈቀድለትም»

«ስለዚህ እኛም የመገፈፍ አደጋ ውስጥ ነን ማለት ነው?» አለ ፖንሴ፣ ከዚህ ቅን፣ በግልፅና በትህትና ከሚናገር ልጅ ጋር መጨዋወቱ ደስታን እየፈጠረለት።

«ኑ፣ ኑ፣ እናንተ ምንም አይነት አደጋ ውስጥ አይደላችሁም» አለ ዲሚጥሮስ። ሁለቱንም ክንዶቻቸውን ይዞ፣ ከርሱ ጐን እንዲራመዱ እያደረጋቸው። «ንጉሠ ነገስቱ ይጠብቋችኋል። እኔ ደግሞ አሸከራቸው ነኝ። ከዚህ በኋላ አዲስ ርዕስ ላይ እንነጋገራለን። ይህች አገር ሌሎች ብዙ ደስታዎችን እንደምትሰጣችሁ ታያላችሁ»

11

ከመንገዱ ከፍታ በመጠኑ ዝቅ በሚል አንድ ትልቅ ክፍል ውስጥ እራታቸውን በሉ። በአንድ አጭር በር አልፈው ሲገቡ፣ መካከለኛ እድሜ ያላት ረዥምና በተለያዩ ቀለማት የተጠለፈ የጥጥ ቀሚስ የለበሰች ሴት ተቀበለቻቸው። ሴትዮዋ፣ የተለመደው የነገስታት ዝርያ ያላት መሆንዋን የሚያረጋግጥ ጠለቅ ያለ የውበት ምልክት ይታይባታል። ከሌሎች ክፍሎች በቀጭን የጥጥ ጨርቅ መጋረጃ ወደተለየና ጠባብ ጓዳ ወደሚመስል ቦታ መራቻቸው። ከመጋረጃው በስተጀርባ ደብዘዝ ያሉ ቅርፆች ሲንቀሳቀሱ ይታያል። በአቢሲኒያውያን ባህል በህዝብ ፊት ምግብ አይበላም። ምክንያቱም የአንግዳ ሰው ዓይኖች በምግቡ ላይ ክፉ መንፈስ በማሣረፍ በምግቡ አማካይነት ወደተመጋቢው አካል ይገባል የሚል ፍርሃት አለና ነው። ስለዚህ በምግብ ሰዓት፣ ምግብ ቤቱ በጥጥ ጨርቆች ወደተከፋፈሉ ተያያዥ የሆኑ ብዙ ትንንሽ ክፍሎች ተለውጦ ተመጋቢዎቹ ከውጭ ተመልካች አይን እንዲከለሉ ይደረጋል። ምግብ ካበቃና ገበታ ከፍ ካለ በኋላ፣ ዓይነ ርግብ የመሰሉት ስስ መጋረጃዎች በሙሉ ወደ ጮን ሲሰበሰቡ ክፍሉ በሙሉ ወለል ብሎ ይታያል። ተመጋቢ የነበሩትም ሰዎች በቀለማት ባሸበረቁ የቀርከሃ ጠረጴዛዎች ዙሪያ በበርፖማዎች ወይም በምንጣፎች ላይ ተቀምጠው ይታያል። መንገደኞቹ አንድ ክንድ ያህል ስፋት ያለው ከክ መሰል ምግብ ተመገቡ። ይህ ምግብ የሚዘጋጀው በአቢሲኒያ ከፍተኛ ምድሮች ላይ ሲሆን ከመጋገሩ በፊት እስኪመጥጥ ድረስ ይቦካል። ይህ ምግብ ሲቀርብ መላው በክባድ ቅመማት በተሠራ ወጥ ይሸፈናል። መጠጥ የሚቀርበው በባለረዥም አንገት ብርሌ ነው። መጠጡ ከማርና ከውሃ ተበጥብጦ የሚዘጋጅ፣ ጉዳት የሌለው የሚመስልና ከጠጡት በኋላ ግን ግራ መጋባትና በትክክል ማሰብ የሚከለክል አስካሪ ነው። መጋረጃዎች ሲሰበሰቡና ሌሎች ተመጋቢዎች መታየት ሲጀምሩ፣ ፖንሴና ጓደኛው በዙሪያቸው ውብ ፊቶች ያሏቸውን ወንዶችና ሴቶች ተመልክተው ተደነቁ። እንደ እውነቱ ሌሎች ተመጋቢዎችን በስሜት ሲመረምሩ ለሴቶች የተለየ ዝንባሌ እንደነበራቸው አተያያቸው በግልፅ ያስታውቅ ነበር።

«ጠንቀቅ በሉ» አለ ዲሚጥሮስ። «እዚህ ባሉ ፍፁም ቀላል ነው። እነዚህ ሰዎች አመንዝራነትን እንደሃጢያት አይቆጥሩም። ነገር ግን በምንም መልኩ በግልፅ የሚጠበቁትና

የሚጠነቀቁት ስለክብራቸው ነው። ሁልጊዜም ሴቶችን ትንሽ እንኳ ሳታንቋሽሹ ከፍ ባለ አክብሮት ተመልከቷቸው። አይኖቻችሁ ሴቶችን ከመመልከት ይቆጠቡ። ይህ እንርሱ እናንተን እንዳያስተውሏችሁ አያደርጋቸውም። ማንም ሰው ባይመለከታችሁም ሁሉም ሰው እንደሚያያችሁ እወቁ። የተሰጠኝን የስራ ሃላፊነት ካላከበዳችሁብኝ በስተቀር ልታስታውሱት የሚገባችሁ ነገር አለ። በዚህች አገር ውስጥ ትልቁ አደጋ የአንድ ወጉረ ልውጥ አተያይ ነው። በዚህች አገር ውስጥ ከአንዲ ጋር ብቻችሁን ብትገኙ፣ ያገባች ትሁን ወይም በደሚ የመሣፍንት ወገን ትሁን፣ በልባችሁ ፍላጐት እንኳ ሊያድርባችሁ ቢችል፣ ከሁሉም በፊት ወደርስዋ ፊፅሞ አትመልከቱ።»

የተገፈፈው የሰው ቆዳ በሁሉቱ መንገደኞች ላይ ቀርፆ ያስቀረው ስሜት ገና ብርቱ ስለነበረ፣ ዲሚጥሮስ የነገራቸውን ክለሙ በኋላ በዙሪያቸው ያለውን መመልከት አቆሙ። ሌላው እንዲያወቅላቸው ጆሮአቸውን ሁሉ ወደ ዲሚጥሮስ አቀኑ።

ወጣቱ ዲሚጥሮስ፣ ኢጣሊያንኛን አቀላጥፎ ይናገራል። ቋንቋውን፣ ግሪካዊ ከሆነችው እናቱ እንደተማረ ገልፆ፣ ሴት አያቱ ግን ቺቺሊያዊት እንደነበረች ገለፀላቸው። እንደሌሎች የነጋዴ ቤተሰቦች የርሱዎቹም የመጡት ቀይ ባህርን አቋርጠው ሲሆን በሁኔታዎች አስገዳጅነት እዚሁ የቀሩ ናቸው። እናቱ፣ አምስት ልጆች ሲኖሯት ከነዚህ ሁሉቱ የሚወለዱት ከአበሻ አባት ነው። ዲሚጥሮስ ከነዚህ ዲቃላ ልጆች አንዱ ነው።

«ሰረዝም ጊዜ ያህል በከተማው ውስጥ በጣም ቆንጆው ህፃን እኔ ነበርኩ» በማለት በጥልቀት በተበሳሳው ፊቱ እየተመለከታቸው «ከዚያ በኋላ ወረርሽኝ ገባ። ብዙ ሰዎች ሞቱ። እኔ ግን ሕይወቴ ተረፈ። አሁን የሚያሣስበኝም ይኸው ብቻ ነው። ከወላጆቼ ሞት በኋላ፣ ንጉሡ እንዳገለግላቸው ወሰዱኝ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ደግነታቸው አልተለየኝም። ገባችሁ?» ሲል ገራገር የሆነ የአክብሮት ፍርሃት በፊቱ ላይ እየታወቀበት ተናገረና «እርሳቸው ከሌሎች በጣም የተለዩ ርህሩህ ንጉስ ናቸው» አለ።

«ይህን ባህሪያቸውን የሚያረጋግጥልን ጥቂት አሣማኝ ነገር ስላየን አምናለሁ» አለ ጆን ጥንቲስት

«ምን?» አለ ወጣቱ ሰው «እነዚህ ቀደም ሲል የተፈፀሙ አጋጣሚዎችን እስከአሁን እያሰባችኋቸው ነው? ያ በእውነቱ ትክክል አይደለም። አንድ ንጉሠ ነገስት እንደዚህ ባሉ ጥቃቅን ዝርዝር ጉዳዮች መፈረጅ የለበትም። አፄ አያሱ፣ እኔ እስከማረጋግጠው ድረስ ምናልባት ኢትዮጵያ በብዙ ዘመናት ውስጥ ያገኘቻቸው ድንቅ ንጉስ ናቸው። ሰዚህ የሚሆን ምሣሌ ትፈልጋላችሁ? በዚህች አገር ውስጥ አንድ ንጉስ ዙፋን ሲይዝ፣ ወንድሞቹና አህቶቹ ወይም የሥልጣኑ ተቀናቃኝ ይሆናሉ የሚባሉ አምባ ላይ ይታሰሩ ነበር። ከደጋው አገር ሜዳ ላይ ሽቅብ የሚያድጉትንና የማይወጣበትውን ኮረብታዎች አይታችኋቸዋል። እነዚህ ሰዎች በዚህ ቦታ እድሜአቸውን ሙሉ ታስረው ይኖሩ ነበር። ቢያመልጡ እንኳ አካላቸው እንዲጐድል ያደርጋል። ምክንያቱም መግዛት የሚገባው ሙሉ አካል ያለው ሰው ነው የሚል የተሣፈ ሕግ አለ። እናም አያሱ ንጉሠ ነገስት መሆናቸው ሲታወጅ፣ የመጀመሪያ የነበረው ተግባራቸው፣ ልዑሎቹና ልዕልቶቹ ወደታሰሩበት ወደ አምባ ዋሽን ግርጌ ድረስ በአግር ለመሄድ ሰልፍ ማድረግ ነበር። እንደደረሱም፣ እንዲሰቀቁ አዘዙና ሰዎቹ እስኪመጡ ጠበቁ። ሰዎቹ ሲመጡ ምን ይመስሉ እንደነበረ ማሰብ አትችሉም። ከተራራው ላይ እንዲወርዱ የተደረጉት ሰዎች ፍፁም የሚያሣዝን ሁኔታ ላይ ነበሩ። እንደ እሮብ በቅማል የተወረረ ቡትቶ የለበሱ ሽማግሌዎች ነበሩ። አነዚህ ከአፄ ኢያሱ በፊት ከነበረው ሦስተኛው ትውልድ የደም ትስስር የነበራቸው ልዑላን ነበሩ። ሕፃናትም ነበሩ። ከነርሱም መካከል አንዱ ጀሮው የተቆረጠበት ነው። ይህ የሆነው አንዲት ባሪያ ልጇ በጣም ስለራራ ሕፃኑ እንዲያመልጥ ለመርዳት በቀሚሷ ውስጥ ትደብቀዋለች። እነዚህ ሰዎች በርግጥ ሊያሣዝኑን ይገባል። ምክንያቱም ይህ የሚፈፀምባቸው ልዑላን ስለሆኑ እንጅ፣ ከሃዲዎች ወይም ወንጀለኞች ሆነው አይደለም። ባህሉ ተዝኪ እንዳልሆነና አደገኛነቱንም አፄ አያሱ በትክክል ተገንዝበውት ነበር። ከእስረኞች መካከል በጣም ጀግኖች የሚባሉ፣ ለንጉሡ ጥላቻ ያላቸውና ከዙፋኑ ሊያወርዱት የሚፈልጉ እንጅ፣ በልባቸው ምንም የሌላቸው ናቸው። ይህን እስር ቤት ለመያዝ የሚችል የጠላት ሃይል ቢኖር ለዙፋኑ ሕጋዊ ወራሽ ሊሆኑ የሚችሉና ለበቀል የተዘጋጁ ብዙ ሰዎችን ለማግኘት ይችላል። ይህ ሁሉ ባለፉት ዘመናት የሆነ ነው። ታዲያ አፄ አያሱ ለአፍታም ሳያቅማሙ ሁሉንም ነፃ አድርገው ፈቷቸው። ልብስና ምግብ እንዲሰጣቸው አዘዙ። ለሁለት ቀናት የደስታና የምስጋና አምባ ሲረጭ ውሎ አደረ»

ጠጁ፣ የተናጋሪውን ምላስ እየያዘው ስለሆነ አድማጮቹ በትክክል እንዳያዳምጡት ይደነቃቅፍ ጀመር። በወፍራም ስጋጃ ላይ በምቾት ተቀምጠው፣ አንድ ሽማግሌ በሚጫወተው የክራር ዜማ ተመስጠው፣ ሁለቱ ፊረንሣውያን የዲሚጥሮስን አስመስሎ የመቀስድ ችሎውን እያደነቁ ቀዩ።

«ለመሆኑ እነዚህ ልዑላን የደስታ እንባቸውን ብዙም ሣይቆዩ አሳደረቁትም። ደግሞስ፣ ቅናትና ጉትትስ እውን ከልባቸው ሙሉ በሙሉ ተፍቆ ወጥቷል?» ሲል ፖንሴ ጠየቀ።

«አዎን፣ ፍፁም ወጥቷል። ንጉሳችን ከነዚህ የቤተሰብ አባላት መደበኛውን የእጅ መንሣት ከመቀበል በስተቀር ሌላ ግንኙነት የላቸውም። አመፅ አስነስቶ የነበረ አንደ የወንድም ልጅ ብቻ ነበር?»

«እናም በቁም ቆዳው ተገፈፈ።» አለ ሜትር ዝ'ረሚ።

«እንግዲያውስ ታሪኩን ታውቀዋለሃ?» አለ ዲሚጥሮስ በመደነቅ አይነት

«መቋጫውን ነው?»

ወጣቱ ሰው ከት ብሎ ሣቀ።

«በዚህች ትልቅ አገር ውስጥ የንጉሡን ስልጣን የሚቀናቀነው ቤተሰቡ ብቻ አይደለም። ባላባቶች፣ መኪንንቶች፣ መሣፍንት፣ ልዑላን፣ ገዥዎች፣ ጐሣዎችና አያንጸንጹ ይቀናቀናል። በጣም አነስተኛውን ችግር ይፈጥሩብናል የምንላቸው ሙስሊም ጐረቤቶቻችን ናቸው። እነርሱ ከአለም እንድንነጠል ሊያደርጉ ቢችሉም፣ በአሁኑ ጊዜ ከኛ ጋር በጦርነት ላይ አይደሉም። ንጉሣችን ግን አረፍት የላቸውም። ይህ የሁሉም ነገስታት ሥራ ቢሆንም፣ አሁን ያሉት ንጉሥ ግን ሃያል ጥንካሬና ብርታት ስላሳዩ፣ ለረዥም ዘመናት ከነበሩት ሁሉ ታላቁ ንጉሰ ነገስት ናቸው። ልዑላኑን አግባብተዋቸዋል። ጐሣዎችን አረጋግተዋቸዋል። ሰሙስሊሞች ክብር ሰጥተዋል። የስራ ክንውናቸው እጅግ ከፍተኛና አስደናቂ ነው»

«ስለርዓቱ ውጭ ብሆንብህ ይቅርታ ታደርግልኛለህ» አለው ፖንሴ የማይረባ ጥያቄ የሚያቀርብ መስሎ «እኒህ ዛፊ ሚት በህይወት ያገኘናቸው ሃውልት የመሰሉ ንጉሥ፣ እንዴት

ይህን ሁሉ ሊያከናውኑ ይችላሉ ብለህ ትናገራለህ? እንዲያውስ ሙሉ በሙሉ በሌፍቴናንት ጀኔራላቸውና በተሣውስቱ መዳፍ ውስጥ አይደሉም እንዴ?»

«ንጉሠ ነገስቱ?» አለ ዲሚጥሮስ «አታስቀኝ። አነርሱ እርሳቸውን ይፈሯቸዋል። በጣም ስልጣናቸውን ስለወሰዱባቸው ይጠሏቸዋል። ከፍተኞቹ ካህናት በጠንካራ የቤተመንግስት ቁጥጥር ስር አይደሉም። ንጉሡ፣ በመንፈሣዊ ትምህርት ላይ ያላቸው ስሜት እምብዛም ነው። ሆኖም ስልጣናቸውን ማስከበር ስለሚፈልጉ፣ ይህም የሚሆነው የቤተክርስቲያንን አንድነት በመጠበቅ ላይ ሲመሠረት መሆኑን ያውቃሉ። በካህናቱና በባሳባቶች መካከል መከፋፈልን አስቀርተው፣ ሁሉንም ከጫማቻው በታች አድርገዋቸዋል። በታላቅ ስብሰባ ላይ ሕይወት ያለው ሐውልት መስለው ቢታዩ ካህናቱን፣ ልዑላኑና መሣፍንቱ ከፊታቸው ሆነው እንዲመለክቱ ስማድረግ ነው። እንዲያችሁት ሁላቸውም ደክመው ሊወድቁ ነበር»

«ከዚያ ሁሉ ክምችት ውስጥ ከሌሎቹ ይበልጥ ተስሚነት ያለውና አንድ መልዕክት በቀጥታ ሊያደርስላቸው የሚችል የለም?» ሲል ክቆንሲሉ ተቀብሎ የያዘውን የዲፕሎማሲያዊ ተልዕኮ አስቦ፣ ጆን ባፕቲስት ጠየቀው።

«ከነዚያ ካያችኋቸው ውስጥ? የለም፣ አንድም እንኳ የለም። ነገር ግን ሌሎች መንገዶች አሉ»

«ለምሳሌ ባንተ በኩል?» ሲል ጆን ባፕቲስት፣ ዲሚጥሮስን እየተመለከተው ጠየቀው።

«አንዲህ ያለ ነገር ስታስቡ ለኔ እጅግ ከፍተኛ ክብር ነው»

በጨለማው ጦዳና ውስጥ እየተንገዳገዱ ወደ ቤት ተመለሱ። ዲሚጥሮስ፣ እስክበራቸው ድረስ በዓይኑ ተከተላቸው። ጆን ባፕቲስት ከመተኛቱ በፊት የመድሃኒት ቅመሞችንና መጠናቸውን የፃፈበትን ደብተሩን በመድሃኒት ሣጥኑ ውስጥ ፈለገ። አንዲት አነስተኛ የመፃፊያ እርሳስ በአንድ ኪሱ፣ የማስታወሻውን ደብተር በሌላ ኪሱ አስቀመጠ።

«ነገ ደግሞ ማስታወሻ መውሰድ እጀምራለሁ።» አለ ሙሉ ልብሱን እንደለበሰ እየተጋደመ

«ለምን?» አለ ሚትር ዝረሚ መንጋጭላው እስኪላቀቅ ድረስ አፉን ከፍቶ እያዛጋ።

«በመጀመሪያ ደረጃ አስደናቂና አስደሳች ነው። ሁለተኛ ነገር ከዚህ አገር የምንወጣበትን ዘዴ የምናገኝበት ስለሚሆን ነው»

ገና ድቅድቅ ጨለማ እያለ በመዝሊያው ጓንጓቸር ውስጥ የመክፈቻው ቁልፍ ሲተሻሸ ጆን ባፕቲት ሰማ።

በአልጋው ስር የደበቀውን ጉራዴ አፈፍ አደረገው። በሩ በዝግታ ተከፈተ። አንድ ሰው አጭር ጣፍ በሸክላ መቅረዝ ላይ ይዞ ቆሟል።

ጆን ባፕቲስት ዘልሎ ሲነሣ፣ ተረጋግቶ ጠበቀ። ወዲያውኑ፣ ግዙፉ የሚትር ዝረሚ ጥላ ድምፁን አጥፍቶ ወደ በሩ ዘልሎ ሲወረወር የጉራዴውን ብርቅርቅታ ተመለከተ። ፕሮቴስታንቱ፣ በቅፅበት የጉራዴውን ሹል ጫፍ በሰርጉ ገቡ ሰው ደረት ላይ አሳረፈው። እንግዳው፣ እጃቹን በመማረክ ብድግ ሲያደርግ የያዘው የጣፍ መብራት በፊቱ ላይ አበራበት። ዲሚጥሮስ ነበር።

«በዚህ ውድቀት ሌሊት ምን ትፈልጋለህ?» ሲል ሚትር ዝረሚ ከፍ ባለ ድምፅ ተናገረ።

«አህ! እባካችሁ ምንም ድምፅ አታሰሙ። ጉራዴያችሁንም አስቀምጡ» አለ ዲሚጥሮስ በሹክሹክታ።

ሚትር ዝረሚ ፈንጠር ብሎ ሲቆም ዲሚጥሮስ ወደ ክፍሉ ውስጥ ዘለቀ።

«ልብሣችሁን ልበሱ» አለ ዲሚጥሮስ በርጋታ

«እንደለበስን ነን»

«እንግዲያውስ ተከተሉኝ። አንዳችም የሚያስፈራችሁ ነገር የለም»

ሁለቱ ጓደኞሞች ለአፍታ ያህል ርስ በርሳቸው ተያዩ። ጉራዴያቸውን አስቀምጠው ወጣቱን ሰው ተከተሉት። ከቤቱ ውስጥ ሳይወጣ ቀደም ሲል አይተውት እንደነበረና ወደ ጣሪያው የሚአስወጣ ሳይሆን እንደማይቀር በገመቱት በር በኩል ሄደ። ይህ በር ወደ ጣሪያው የሚያደርስ ሳይሆን ወደ አንድ ጠባብ የመተላለፊያ ቦታ ያመራል። ሁለት ሌሎች በሮችን ሲያልፉ፣ ግድግዳው የተሠራበትን የድንጋይ ቅርፅና መጠን ሲገነዘቡ በቤተመንግስቱ ውስጥ እንደሆኑ አወቁ። ዲሚጥሮስ ከፊት ከፊታቸው እየተራመደ በአንድ በሚጠማዘዝ ደረጃ ላይ ሲወጡ፣ በጠባቡ ሳንቃ መሰከት በኩል ቀዝቃዛ ነፋስ ከውጭ ይገባል። በመጨረሻም የመተከሻ ቀዳዳ ያሰውና የቤተመንግስቱን ምሽጐች ሁሉ መመልከት የሚያስችል የግንብ አናት ላይ ወጡ። ስማዩ ደመና የሌለበት ንፁህ ነበር። ከተማ ውስጥ፣ በቃፊር ጣቢያዎችና በጥበቃ ቦታዎች ከሚታዩት የእሣት ፍሞች ሌላ የሰም። ሰማዩ ጣሪያ ሆኖ ከዳር እስከዳር ምድሪቱን ሲሸፍን፣ ልክ የሃር ጨርቅ በመልኩና በፈርሱ
ብቻ እኩል የተረጨበት ሆኖ የሚያንፀባርቅ ይመስላል። በአቢሲኒያውያን ደጋ ምድር ከደረሱበት ጊዜ ጀምሮ እነዚህ ተጓገሮች ከአገራቸው እጅግ ርቀው መኖራቸውን በትግስት ቢያስቡትም፣ ሰማዩ ግን ሁልጊዜም ያስታውሣቸዋል። በቆሙበት ቦታ ላይ ባሉበት የመታከሻ ቀዳዳዎች በደቡባዊ በኩል ያለውን መስቀል ይመለከታሉ።

የግንቡን እያንዳንዱን ማዕዘን ከሚያመለክቱት ጉልላቶች አንዱ ላይ ጐንበስ ብሎ እስኪያልፍ ድረስ፣ ዲሚጥሮስ አንደ ሕፃን መራቸው። ጉልላቱ፣ እንዲት እኩል አራት ማዕዘን ለሆነች ክፍል ጣሪያ ነው። ክፍሏ በአንድ የእንጨት ጠረጴዛና በአራት በርፖማዎች ተሟጣለች። በአንደኛው ላይ አንድ ሰው ተቀምጧል። ሰውዬው፣ በወገቡ ላይ የጥልፍ ቀበቶ ያለበት ቀላል ነጭ ሻኬት ለብሷል። አንድ ክርኑን ጠረጴዛ ላይ አሣርፎ፣ ወደ ጣፋ ጐንበስ ብሎ ተቀምጦ ቢቆይም እነርሱ ሲደርሱ ቀና አለ። ከአይኖቹና ክአፍንጫው ቅርፅ ሀይወት ያለው ሐውልት፣ ረጋ ያለ ጣአት ይመስላል። አውነቱ ግን በዘያኑ አለት ጣት ከፊት ለፊታቸው ቀርበው የሰገዱላቸው ንጉሠ ነገስቱ እንደሆኑ አወቁ። ፖንሴ፣ ለአፍታ ያህል አመነታ። እንዲህ ባለች ጠባብ ክፍል ውስጥ ሙሉ በሙሉ ወለሉ ላይ መዘርጋት ይኖርባቸዋል? ይህ ምኞት የሌለው ጉዳይ ነው። ጆን ባፕቲስት ስለሠውነት ቆዳው ባይጨነቅ ኖሮ፣ ፊቱን በመሣቀቅ ክፉኛ ሊያጨማድደው ነበር። ነገር ግን ንጉሡ በሁለቱም ጉናቸው ያሉትን በርፖማዎች አመልክቷቸውና ትንሽም እንኳ እፍረት ሳይሠማቸው በሁለቱም ምንጣፎች ላይ ተንጋዶ ወድቆ የነበረውን ሌላውን በርፖማ አቃኑት።

ሁለቱ ፈረንሣዮች በትንሹ ከአንገታቸው ዝቅ አሉና ከንጉሡ ጐን ተቀመጡ። ከሁኔታው ጋር በመያያዙ እንጂ፣ ንጉሠ ነገስቱ ከሌሎች ዜጐቻቸው ይህን ያህል የሚጋነን የበለጠ ግርማ አልነበራቸውም። አቢሲኒያውያን ላይ የሚታየው አይነት የረጋና የጨዋ መልክ ቢታይባቸውም፣ንጉሠ ነገስቱ ፊታቸው ዕረፍት ሲያገኝ የሐዘንና የመሳቀቅ ነገር በግልፅ ይታይባቸው ነበር። ሁለቱን ባዕዳን ሰዎች እንደተመለከቱ ሞቅ ያለ ፈገግታ አሳዩዋቸውና ወዲያውኑ ደግሞ ያ የቀድሞው የድካም አተያያቸው ተተካ። በሰውነት አቋማቸው ሲታዩ፣ በነገስታት ዝርያ አኳያ አነስ ያሉና ሊበዛ ቀጭን ሰው ናቸው። እድሜአቸው አርባ አመት የሚሞላቸው ሲመስሉ በመጠኑ ከትከሻቸው ጐበጥ ይላሉ። በአይኖቻቸው ላይ የጭካኔ እሳት የሚተፋና ድንጋይ ልብ መሆናቸውን የሚያመለክት ነገር የለባቸውም። ከአንድ ቀን በፊት በአሰፈሪው የስቃይ ቅጣት ማዘናቸውን የማያውቅ፣ አዝናላቸው፣ እኒህ ይልቁንስ የደከሙ ሰንቋሳ ሰው ናቸው ይላቸው ነበር።

«ስላየኋችሁ ደስ ብሎኛል» አሉ ለስለስ ባለ ድምፅ

ዲሚጥሮስ ቃላቶቻቸውን ወደ ኢጣሊያንኛ ተረጐማቸው

«ግርማዊነትዎ ታላቅ አክብሮት አድርጐልናል . . . » ሲል ጆን ባፕቲስት ጀመረ።

ንጉሡ፣ የዲማጥሮስን አስተርጓሚነት አቋረጡ

«አትቸገሩ» አሉ «ይህ ዋጋ የለውም □□ እነርሱም የሉም»

ፖንሴ መናገር አቃተው።

«ሰካሀናቱ ደህና አድርገህ ነው መልስ የሰጠሃቸው» ሲሉ ንጉሡ አስተያየታቸው ግዴለሽ በሚመስል መልክ ቀጠሉ።

ባለማቋረጥም በክንዳቸውና በሆዳቸው አካባቢ እንደሚያክኩ አስተዋሉ።

«አምን፣ ያሳችኋቸው ቃላት ሁሉ ተነግረውኛል። እነሱ ጥበበኞች ናቸው። እኔም እንደናንተው ከአንግዲህ በኋላ እነርሱ በሚያወሩት ተአምር አላምንም። የነርሱ ተአምሮች ትኩሣትን አንኳ ሲያድኑ አይታወቅም። ከመንፈሣዊው አለም በምናገኘው ምልክት ስለመጭው

ዘመን ማወቅ እንችላለን የሚለው ሥነ ስራታቸው ሁሉ ማታለል ነው። አንድ በራሪ ኮከብ በታየበት ጊዜ ስለኔ መሸነፍ አስቀደሙው መናገራቸውን ስምታችሁ ይሆናል። ይህ መቼም ሁል ጊዜ የሚደረግ ነው። ውድቀቴን በእጅጉ ስለሚፈለጉ ፣ከዋክብት ብርታቱን እንዲሰጧቸው እንደለመኑ ናቸው። ይሁን እንጅ እናንተ ካቶሊክ ካልሆናችሁ የኛንም አይነት ካልሆናችሁ ሃይማኖታችሁ ምንድን ነው?»

«ግርማዊ ሆይ፣ የተሃድሶ ቤተክርስቲያን ይባላል» አለ ፖንሴ

«ጀስዊቶች እዚህ በነበሩበት ጊዜ ስለዚህ ቤተክርስቲያን ፍፁም ተናግረው አያውቁም።»

«ጥሩ ምክንያት አላቸውና ነው። እነርሱ እጅግ መጥፎዎች ጠላቶቻችን ናቸው።»

«አምናችኋለሁ።» አሉ ንጉሠ ነገስቱ

ቀጠል በማድረግ ድክም ያለውን አመለካከታቸውን ወደ ሜትር ዠረሚ መለሰ በማድረግ በዝግታ ቀጠሉ።

«ይሁንና ይህ ሰው ከነርሱ አንዱ ነው ብዬ እምል ነበር።»

«ጀስዊት!» አለ ፖንሴ

ሜትር ዠረሚ አመዱ ቡን አለ

«አምን፣ ወይም የነርሱን ዘዴ ለማቆየት የሚጥር ቂስ ነገር ይሆናል ብዬ ነበር» በማለት ጀን ባፕቲስትን በድጋሜ እያጠኑት ተናገሩ «አንተ ዶክተር መሆንህን አውቃለሁ። እርሱ ግን ሲራራውን የተቀላቀለው እንደ ሴባ ወይም እንደ ቂስ በኋላ ነው»

ሜትር ዠረሚ ዘልሎ ሊነሳ ነበር። ፖንሴ ክንዱን አጥብቆ ይዞ አቆየው።

«ደግነቱ ሃጅ አሊ ሁሉንም ታሪክ ነግሮኛል። ይህ ሰው የስራ ሽሪክህ እንደሆነና ፈረንሳዮቹ ግን ሲራራውን እንዳይቀላቀል መቃወማቸውን ተገንዝቤአለሁ። አትፍሩ፣

አምናችኋለሁ። ስለመድሃኒት ችሎታው እንዳላችሁ በግልፅ ይታወቃል። የኔ ፍላጐት ደግሞ ይሽው ብቻ ነው። ያሰን ጊዜ አጭር ስለሆነ ሕመሜን ሳሣያችሁ።»

የሚፍ ነበልባሎች በድንጋዩ ጉልላት ላይ ጥላቸውን አጥልተዋል። በጣም ከፍ ያለውና ባለጉልላቱ ጣሪያ ዋሻ ይመስላል። ሰማይና መሬት እየተላቀቀ ሲሆን፣ ከበላያቸው ባለው ጨለማ ውስጥ በአንድ ወደ ምሥራቅ በሚከፈት ጠባብ መስኮት ሰማያዊውን ሰማይ መለየት ችለዋል።

ንጉሠ ነገስቱ ቀበቶአቸውን ፈትተው ቆሙ። በቀልጣፋ እንቅስቃሴ ጃኬታቸውን አወለቁ። ፖንሴ ተረብ ብሎ በዝምታ መረመራቸው።

«ልትነካው ትችላለህ።» አሉት ንጉሠ፣የደክተሩን ማቅማማት ተመልክተው።

ሜትር ዠረሚ ጣፉን ከፍ አድርጐ እንዲይዝለት ጠይቆት፣ ፖንሴ የተጐዳውን አካባቢ መረመረ። ይህን ጉዳት ለማየት በመቻሉ የታደልኩኝ ነኝ ሲል አሰበ። ይህ ቁስል፣ ከሃጅ አሊ ቁስል ጋር አንዳችም መመሣሰል የለውም። ከወገባቸው በላይና ከሆዳቸው አካባቢ ንጉሠ ትልቅና በተሠነጣጠቁት ቦታዎች መግል የሚያዥበት ነው። ዶክተሩ ሌላም የተጐዳ ቦታ እንዳለ ቢፈልግ ማግኘት አልቻለም። ሕመምተኛውን ወደዚህና ወደዚያ እያዟዟራቸው ብዙ ጊዜ አያቸው። ማንም ሰው ይህን ቡድን ከቅርብ ርቀት ሆኖ ቢመለከተው በጣም የሚያስገርም ትርዒት ማየት ይችላል። እርቃናቸውን የቆሙት ጉባጣው የነገስታት ንጉስ ያንን ጭራሮ አካላቸውንና ሰፋፊ ቁስል ሁሉም እንዲያየው በትህትና ገልጠውታል። በጉናቸው የተዋጊ ቅርፅ ያለው ግዙፉ ሜትር ዠረሚ ጣፉን በፀጥታ ይዞ ቆሟል። ጀን ባፕቲስት ሕመምተኛውን በእርጋታ ይነካቸውና የህመማቸውን ምንነት ለመረዳት ጥረት ያደርጋል። አንድን ንጉስ በታዛዥነት ከማገልገል ይልቅ፣ ወንድማዊ ተግባሩን ማከናወኑን መመልከት በራሱ ትርዒት ነው።

«ለመሆኑ የሕመም ስቃይ አለው?» ሲል ፖንሴ ጠየቀ።

«አምን» አሉ ንጉሠ ነገስቱ «ሆኖም የህመሙ ስቃይ ምንም አልነበረም። ማሣከክ ነው የከፋው።»

ዶክተሩ ምልክት ሲሰጣቸው ልብሦቻቸውን ለበሱ።

«ብዙ ሰዓት የፈጀውን ያንን ስብሰባ አስቡት» ሲሉ ንጉሱ ቀጠሉ «በጥፍሮቼ ስጋዬን እንዳልቆፍረው ፍርሃት ነበረኝ። ሆኖም መንቀሣቀስ አልነበረብኝም። ያለተራቸው እንደዚያ የሚለፈልፉት እነዚያ ውሾች መታመሜን ያውቃሉ።ሊያውቁ የሚችሉትም ይህንን ብቻ ነው።በህመሜ ስሰቃይ እንዲያዩኝ አልፈልግም ፣ወይም የህመሜ ሲቃይ አስገድዶኝ በፊቴ ላይ የሚነበበውን ስሜት እንዲያውቁ አልፈልግም። መንፈሴ ሳይለበር መታየት አስፀያት። ይህ ካልሆነ ቦሚሞቀው ይጥሉኛል»

በጠረጴዛው ዙሪያ ተመልሰው ተቀመጡ።

«ለመሆኑ ህክምና ወስደው ነበር?» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቃቸው።

«ጥቂት ነገሮችን ሞክሬአለሁ። ጎላ መታጠብን፣ በሞቃ ቁስሉን መድፈን፣ የእናቴ አዋላጅ የነበረችና ጥቂት የመድሃኒት እውቀት አለኝ የምትል አሮጊት ሴት፣ የሆነ ዱቄት ሰጥታኝ ነበር።»

«እናስ?»

«እየባሰ፣ እየባሰ መጣ»

«እንትንህ፣ እንትንህ . . . » ፖንሴ አቅማማ። « . . ሰሃያ አመታት ምንም ሳይቀምሱ የኖሩት ታላቁ ቅዱስ?»

«ምን? ሰምቻለሁ እንዳትለኝ? ቀንና ማታ እንዲጠበቁ አደረግሁ። በመጡ በማግስቱ ገና ሰማይና መሬት ሳይላቀቁ በአራት እግራቸው እየዳሁ ማድ ቤት በወይራ ፍሬ ቁንጣን ይዟቸው ተገኙ። ከነሆዳቸው ወደ ገዳማቸው እንዲመለሱ አዘዝኩ»

አራቱም ሣቁ

«ግርማዊ ሆይ» አለ ፖንሴ «ለህመምም የሚሆን ቅባት እናዘጋጅልዎታለን። ሆኖም ግን መድሃኒቱ አስቀድሞ በአንድ ባሪያዎ ላይ ይሞክር?»

«አይደረግም። ለካህናቱ የፈለጋችሁትን የማይጐዳ መድሃኒት ስጧቸው። ለኔ ግን የመድሃኒት ማዘዣችሁን በቀጥታ በዲሚጥሮስ በኩል ላኩልኝ። እንዴት እንደምጠቀመው ለርሱ መንገራችሁን አትርሱ»

«የኛን መድሃኒት ሲወስዱ ሌሎች ህክምናዎችን ሁሉ የግድ ማቋረጥ ይኖርብዎታል።»

«አትስጉ»

«የህክምናችንን ውጤት ለመወሰን በሁለት ቀናት ውስጥ በድጋሚ ልናይዎ አስፈላጊ ይሆናል»

«ስብሰባዎቻችን አደገኞች ናቸው። ስለስብሰባዎቻችን ማንም ሰው ሊያውቅ አይገባውም። እኛም ከሚያሰፈልገው ቦላይ ልንገናኝ አይገባንም። ከዛሬ ጀምሮ ለሁለት ቀናት ሁኔታዎችን ለማስተካከል እሞክራለሁ። እናንተ ግን ትዕግስት አትጡ። ይህን ደግሞ በፍፁም ትንፍሽ ማለት እንደሌለባችሁ እወቁ»

ንጋት ተቃረበ። ፈቶቻቸውን ግራጫና አመዳም የሚያስመስል ሰማያዊ ብርሃን ክፍሉን ሞላው። ንጉሠ ነገስቱ በአንዲት ጠባብ በር በኩል ትተዋቸው ወጡ። በምሽጉ ግዳግዳ በኩል ተመልሰው ቤታቸው ገቡ።

«ህመማቸው ምን እንደሆነ አውቀሃል?» ሲል ዲሚጥሮስ ወጥቶ ሲሄድ ሜትር ዣረሚ ጠየቀው።

«አውቄዋለሁ ለማለት አልደፍርም። ሕመሙ ግን ከባድ ነው»

ኮስተር ብሎ ተጀምሮ በደስታ ከታጀበው ከመጀመሪያው ምስጢራቸውና ተከትሎት ከመጣው ጥልቅ ወደጅነታቸው በኋላ፣ አሊስና ፍራንቾይዝ የዕለት ተዕለት ወደ ሆነው

አሰልቺው የጆን ባፕቲስት እፅዋት እንክብካቤ ጥልቅ ብለው ገቡ። ውይይታቸው ሁሉ የሚገመት እቅጣጫ እየያዘና መልካሟ ጊዜ ይመጣል ብለው የሚያስቡትን ሁኔታ ማንፀባረቅ ጀመረ። ሁልጊዜም በዚያ ቦታ ተወስነው መቅረታቸውና የሚጠብቋቸውን ሰዎች በእርግጠኝነት ያስገኝላቸዋል የተባለው ቤት፣ ቀስ በቀስ ስቃይ የበዛበት የተራዘመ አለመገኘትን የሚያሣያቸው ሆነ። አንዳቸውም ራሳቸውን በትክክል መቆጣጠር አልቻሉም። ምንም እንኳ ሰላም ወዲያውኑ ቢወርድም፣ በማይሆን ነገር ላይ ሁለትና ሶስት ገዜ ተጣልተዋል። ይህ ደግሞ ግንኙነታቸውን ያለ አንዳች ዓይነት ለውጥ ለረዥም ጊዜ ሊዘልቅ እንደማይችል የሚያስጠነቅቃቸው ነበር። በዚህ የተጎሣ አሊስ አንድ ሣጥብ አመጣች።

«አንቺ አንድታገለግያት፣ እናቱን ባግባባት ምን ይመስልሻል?» ስትል ፍራንቾይዝን ጠየቀቻት። «እየተመላለስሽ ስትሰሪ በቆንስላው ውስጥ ልንተያይ እንችላለን። በበኩሌ ላንቺ የጠለቀ ወዳጅነት እንዳለኝ በማሣየት ጓደኛዬ ተደርገሽ እንድትመደቢልኝ እደርጋለሁ። ለሽርሽር አብረን እንወጣለን። እዚህም ቢሆን ልንመጣ እንችላለን። ነገር ግን ሁልጊዜም እዚህ ቦታ ብቻ ለመገናኘት መገደድ አይኖርብንም»

ፍራንቾይዝ ለሣጣኑ አጨበጨበች። ከዚህ በኋላ ማዳም ዴ ማይሌን የሚያግባቡበትን ዘዴ መሻት ይኖርባቸዋል። እቅዱ ገና ፍሬ ሳያፈራ በህይወታቸው ውስጥ የጋለ ስሜት እጫረባቸው።

አሊስ፣ የአንዲት የጠፋች ፈረንሣዊት ሴት ልጅ ሁኔታ ስሜቷን እንደነካው ለእናቷ መንገር ጀመረች። በመድሃኒት ዕፅዋቱ ማሣደጊያ አጠገብ በደሣሣ ጉጆ ውስጥ የምትኖር ምስኪን ሴት ተክሎቹን በመንከባከብና ውሃ በማመላለስ ትረዳታለች። ቀደም ሲል ውጣ ወይዘሪት፣ ምስኪኗ ሴት ስላደረገችላት ዕርዳታ ጥቂት ሣንቲሞችን ልትከፍላት እንድትችል እናቷን ጠየቀቻት። ቀጠል አድርጋ የዚህችን ምስኪን እድለቢስነቷን ማስረዳት ቀጠለች። በጨዋታቸው መሃል፣ ይህች ምስኪን በጠባይዋ መጥፎ እንዳልሆነችና የአርባ ቀን እድሏ በዚህ ጨካኝ ከተማ ውስጥ ቤሳ ቤስቲን የሌላት ምስኪን አድርጉ እንዳስቀራት ነገር ጣል ታደርጋለች። እናትና ልጅ፣ የዚህ አለም ሃዘን እርር ኩምትር ያደረጋቸውን ምስኪኖች ያስባሉ። ማዳም ዴ ማይሌ ደግሞ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ካለ የማታ እራት የማጣት ጊዜ ጠብቆ ስላቀያቸው ታመሰግናለች። ሁሉቱ የሚወያዩባቸው ርዕሶች አልነበራቸውም። አሁን ግን

ፍራንቾይዝ ሰውይይታቸው ተመራጭ ርዕሣቸው ሆነች። ከአለታት አንድ ቀን ማዳም ዴ ማይሌ፣ ስለዜጮቻቸው ተመፅዋችነት ወሬ ስትጠይቃት ጉዳዩን አፍረጥርጣ ለመናገር የቆረጠችው አሊስ በተስተካከለ ድምፅ

«አዕምሮዋ ፍፁም ስላማዊ ነው። ሴትዮዋ ውሳኔ ላይ ደርሣለች።»

«የምን ውሣኔ?»

«ነገሬሽ ካልሆነ ረስቼዋለሁ። በጣም ሃብታም የሆነ ቱርካዊ ሰው ሊያገባት ጠይቋት ነበር። ይህ ጋብቻ ለሕይወትዋ ዋስትና ይሰጠው ነበር። በርግጥ ለመወሰንና ላለመወሰን ስታወላውል ረዥም ጊዜ ትቀያለች። ሰውዬው ሽማግሌና አስቀያሚ ነበር። ቢያገባት እርሷ እራተኛ ሚስቱ ትሆንና የጋብቻውን አላመቺነት ከቀሩት ሦስት ሚስቶች ጋር መጋራት ሊኖርባት ሆነ።»

«ያስፈራል» አለች ማዳም ዴ ማይሌ «የክርስቲያን እምነቷንም ለመተው ቃል መግባት ግድ ሊሆንባት ነው?»

«የማመንታቷ ዋናው ምክንያትም ይኸው ነው። በጣም ሃይማኖተኛ ስለሆነች ክርስትናን መካድ ሰርሷ ፍፁም ሞት ነበር»

«እሺ እና በመጨረሻ ምን ወሰነች?» ስትል የአሊስ እናት ጠየቀች።

«ቱርካዊው ሰውዬ፣ አስልምናን መቀበል ከባድ ሽክም አይሆንም፣ ዝም ብለሽ ላኢላሐኢለሏህ ማለት አላህ ማለት ነው፣ መሃመድም የአላህ ነብይ ናቸው ትያለሽ። የምታደርጊውም ይህን ብቻ ነው። ሙስሊሞች ክርስቶስን እንደ ቅዱስ ሰዎች ሁሉ ተቀብለውታል። ከመሃመድም ይቀድማል። ስርሱ ልትፀልይ ይፈቀድልሻል ይላታል። በአጭሩ ቱርካዊው ሃይማኖቷን ብትለውጥ ምንም እንደማታጣ፣ በአኳያው ግን ቢያንስ በየሰቱ ሆዷን ልታ ልትበላ እንደምትችል ያሣምናታል።»

«ልጀ» አለች ማዳም ዴ ማይሌ፣ አይኖቿን በስጋት በልጥጣ «ይህች ምስኪን ሴት ብፍታ ትቀር ነበር። እነዚህ አረመኔዎች የሚናገሯቸውን፣ ሰው መስማት የለበትም። ቅድስት ቤተክርስቲያኖችን በመቆጣጠር በሺህ የሚቆጠሩ ቤተክርስቲያኖችን አወደሙ። ቁጥራቸው በውል

ያልታወቀ ክርስቲያኖችን ገደሉ። የሚከፈለውን ከፍለን ቱርካዊ እንዳትሆን በተቻለን መክላ ይኖርብናል። ከሠማሁት ተነስቼ የተገነዘብኩት እነዚህ በሚስቶቻቸው ላይ ሲበዛ ባለጌዎ የሆኑ ሰዎች መሆናቸውን ነው። ሴትዮዋ እንዲህ ያለውን ሰው ብታገባው በምድር ሪ መሞቷ ብቻ ሳይሆን ለዘላለምም ነፍሷን ለሲኦል ሰጥታው ትቀራለች።»

ሁለቱ ሴቶች፣ ይህን አስፈሪ ውጤት ያለውን ዊውውት ለማስወገድ ሌላ ዘዴ ፈለገ በመጨረሻም ፍራንቾይዝ እነርሱን ለማገልገል እንድትገባ አሊስ ሃሣብ አቀረበች። እናቷ ሃሣቡን በቁም ነገር ተቀበለችው።

«አምን አስቤበታለሁ። ልብስ አጣቢያችን ወደ ፈረንሳይ ከተመለሰችበት ጊዜ ጀም ሙሴ ዴ ማይሌ፣ እርሷን በሌላ እንዲተካልኝ ስጠይቀው ነበር። እርሱ ግን ይህን ቦታ ሊሸፍ የሚችል ብቃት ያለው ሰው በፈረንሣይ ማህበረሰብ ውስጥ የለም እያለ ሁልጊዜም ይመልስል ል። እንደሚመስለኝ እርሱ በኢኮኖሚው የሚገፋፋ ነው። የአገሪቱን ገንዘብ ወጭ የማድረ ጉዳይ በተነሣ ቁጥር አባትሽ ሁልጊዜም ሲበዛ የመመጠን ነገር ያሣያል።»

«ይህ የተሳሳተ የኢኮኖሚ አስተሣሰብ ይመስለኛል። የልብስ አጠባውን ተግባ የተረከቡት ሁለቱ ኑቢያውያን ባሪያዎች የብዙ ልብሶችን ቀለማት አበላሽተዋል። የናይል ልብሶችንም ሲበዛ የማጠቢያ ሶዳ እየተጠቀሙ እያቃጠሏቸው ነው።» ስትል ሃሳ ያልተዋጠላት አሊስ ተናገረች።

«ልብስ ሲተኩሱ ያለውን ትተን፣ በርግጥ ጥፋት ነበር። ይሁንና እንደአለመታደ ሆኖ አባትሽ ለዚህ አይነት ጉዳይ ቁብ አልነበረውም። ልብሶቹን በተመለከተ ቅሬታው የሰማሁት ከጥቂት ወራት በፊት አረንጓዴ የሣር ካልሲዎቹ፣ ከኔ ባርኔጣዎች ጋር አብረው ተነክረው ቀይ ሸክላ መስለው ሲወጡ የተናገረው ብቻ ነው።»

«ይኸውልሽ፣ አየሽ? ከትርፉ ይልቅ አውነተኛ ልብስ አጣቢ በማግኘት የሚገኘውን ጠቀሜታ እንዲገነዘበው ልናደርገው እንደምንችል እርግጠኛ ነኝ። አባቴ፣ ለስራው ፅፖ ለማግኘ ት ጊዜ የለኝም ይላል። እስከ አሁን ያለው ቢቀር አንድ ማግኘታችን ራሱ ጥሩ ነገር ነው»

አሊስ ጥሩ አድርጋ ተከራክራ ስለአሳመነቻት፣ እናቷም ጉዳዩን ለሙሴ ዴ ማይሌ ልታቀርብለት ተስማማች። ምንም እንኳ የሰው ህይወት በእግዚአብሔር እጅ ያለ በመሆኑ ለማዳን ምንም ማድረግ ባትችልም፣ የኃይማኖተኛዋ ሴት ነፍስ ከትክክለኛው መስመር ወጥታ ስትጠፋ ከማየት ይልቅ ልታድነው ፈቃደኛ ሆነች።

«ጉዳዩን ለአባቴ እንዴት አድርገሽ ነው የምታቀርቢለት?» ስትል አሊስ ጠየቀቻት።

«ደህና አድርጌ አውቀዋለሁ። ነገሮችን መደባበቅ ጥሩ አይደለም። አንቺ እንደነገርሽኝ እኔም ሁሉንም ሐቅ እነግረዋለሁ።»

ፈገግ ላለማለት አሊስ ራሷን ተቀጣጠረች። ነገር ግን የእናቷን ቃላት ሰፍራንቾይዝ በሌላ ጊዜ ስትነግራት ሁለቱም ክት ብለው ስቀዋል።

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ አቋሙን አለሣልሶ፣ የልብስ አጠባውን ጉዳይ ለሁለት ሣምንታት የሙከራ ጊዜ ብቻ ለመጠቀም ለባለቤቱ ፈቀደላት። የቤት ውስጥ ጉዳዮችን እንዳይረዳ ሥራ ለሚበዛበት፣ ፍራንቾይዝ በአጭሩ እንድትተዋወቅ በመደረጉ፣ የባለቤቱ የማዳም ዴ ማይሌን ልብ ማሸነፍ ቻለ። ከመጀመሪያው ዕለት ጀምሮ አዲሷ ልብስ አጣቢ በጥንካሬ መስራት ጀመረች። ምንም እንኳ ቸልተኛ ቢሆንም፣ ከሁለት ሣምንት በኋላ ቤቱ መለወጡን ቆንሲሉ አረጋገጠ። ልብሶቹ እንደበፊቱ ማብረቅረቅ ጀመሩ። በፖንሴ ቤት ከሚገኙት ዕፀዋት በቀመመቻቸው ማጠቢያዎች ፍራንቾይዝ የተበላሹትን የቆንሲሉን የእግር ሹራቦች የጀመሪያው ቀለማቸው እንዲመለስ ለማድረግ ቻለች። ሴቶቹ ሽሮ የመሰለ የወየበ ልብስ ከመልበስ ይልቅ ነጭ መልበስ ቻሉ። ከሁሉም በላይ ፍራንቾይዝ በጣም የቀሸሹትን የቆንሲሉን ሁለት ሙሉ ልብሶች ተራ በተራ በእርጋታና በእርግጠኝነት በጥንቃቄ ያዘቻቸው። ከአስታት አንድ ቀን ማለዳ፣ ፀሐፊው የወረቀት ክምር ይዞ ወደ ፅሕፈት ቤቱ ሲገባ፣ አንድ ነገር እንዳጐደለ ቆንሲሉ ተገነዘበ። የክፍሉን ዙሪያ ቢቃኝም፣ ከተለመደው ውጭ የሆነ ነገር ማግኘት አቃተው። ነገር ግን ከፊት ለፊቱ የቆመውን ሙሴ ማቼን ሲመለከተው ፀሐፊው አንዳችም አፍንጫ የሚወጋ ጠረን እንደሌለው ተገነዘበ። ስለዚህ ለዚህ ሁሉ ፍራንቾይዝ ተቀጥራለች።

እንደታቀደው፣ አሊስና ፍራንቾይዝ ጓደኝነታቸው በቆንስላው ውስጥ ቀጠለ። ወጣቷ ልጃገረድ በየዕለቱ ማለዳ ዕዕዋቱን ለመንከባከብ ትሄዳለች። አሊስ ብቻዋን ትሄድና ከበፊቱ

ይልቅ አጭር ጊዜ ብቻ ትቆያለች። ክዚያም ትመለስና በቤቱ ውስጥ ወዲያና ወዲህ ትላለች። ሙሴ ዴ ማይሌ የያዛቸው የቤቱ ክፍሎች፣ የክብረ በዓል ክፍል ማለትም የንጉሡ ሥዕል ያለበትና ጥቂት የሚዋለኑ ክፍሎች፣ ብዙ ጊዜ ባዶ የሚሆኑት በሁለተኛው ፎቅ ላይ ለጉብኚ ባለስልጣናት የሚሆኑ አፖርታማዎች ናቸው። ማዳም ዴ ማይሌ በበኩልዋ ከክፍሏ አምብዛም አትወጣም። የተቀረው የቤቱ ክፍል ለምሳሌ የመፀዳጃ ክፍሎች፣ የመተላለፊያ ክፍሎች፣ የአሲስ መኝታ ክፍል፣ የመልበሻ ክፍሎች፣ የምግብ ማዘጋጃ ክፍሎች፣ ጓዳዎች፣ የልብስ ማጠቢያ ክፍሎች ሁሉ፣ ለሁለቱ ጓደኛሞች መገናኘት ምቹ ቦታዎችን ሰጧቸው። የተለያዩት አካባቢዎች ግብረ አበርነታቸውን በውበት አደሱላቸው። ጥንቃቄአቸውንም የሚያጓጉ አደረጉላቸው። ሁለቱም ሁሌም ጥንቃቄ ቢያደርጉም በዚያ ሰፊ ቤት ውስጥ ለመወያየት አንድ ሺህ እድል ሰጣቸው።

12

ያልተጠበቀውን ውይይት ከንጉሠ ነገስቱ ጋር ባደረጉ በሚቀጥለው ማለዳ፣ ጆን ባፕቲስትና ሜትር ዠሪሚ ሁለት መድሃኒቶችን በማዘጋጀት ራሣቸውን በሥራ ወጥረው ነበር። ከመድሃኒቶቹ አንዱ፣ ለንጉሡ የሚሄድላቸው ሲሆን ሁለተኛው ካህናቱ እንዲመረምሩት ይላክላቸዋል።

በዚያኑ ዕለት ከሰዓት በኋላ፣ በየአመቱ የገዝር ድግስ በሚደረግበትና በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ወደሚሠበሰብበት ከከተማው ወጣ ብሎ ወደሚገኝ ትልቅ ቤተክርስቲያን፣ ጳሚጥሮስ ይዟቸው ሄዱ። ፀሐይ ደማቅ ብርሃኗን ታበራለች። በያንዳንዳቸው አዕምሮ ውስጥ የነበረው የመጨረሻው ነገር የስቃይ ቅጣቱ ነበር። ዐይኖቻቸው ሊያዩ እስከሚችሉበት ርቀት ድረስ ሲመለከቱ፣ ነጭ የለበሱ ሴቶችና ህፃናት፣ ጥቋቁር ዣንጥላዎቻቸውን ዘርግተው፣ በትናንሽ አህያዎች ላይ ሆነው ይሰግራሉ። ሽማግሌ ወንዶች፣ ረዣዥም የእረኛ ዘንጎቻቸውን እየተመረኮዙ ይጓዛሉ። ደማቅ ቀለማት ያሏቸውን ካባዎች የደረቡ ብዙ ካህናትና መነኮሳት፣ መስቀሎቻቸውን በሰልፍ ሰድረው አለፉ። ከፍተኛ ባለስልጣናትን ከፀሐይዋ ቃጠሎ ለማዳን ሁሪያ ክረፋቸው ላይ የሚቅጨለጨሉ የብር ደወሎች ያሉባቸው ትላልቅ፣ ቀያይና ጥቋቁር ኧንጥላዎች፣ በወጣት ባሪያዎቻቸው ተዘርግቶ ተይዘላቸዋል። ሁሉም ሰው ወደ አንድ የጥድ ዛፎች ጫካ ያመራል። የነዚህ ዛፎች የታችኞቹ ቅርንጫፎቻቸው ወደ መሬት እየተጠማዘዙ ስለወረዱ ሕፃናት እየተንጠለጠሉባቸው ዥዋዥዌ ይጫወታሉ። ቤተክርስቲያኑ እምብዛም አይታይም። ስምንት ማዕዘን የሆነው ክብ የግር ክጻን ጣሪያው፣ ተስተካክለው በተቆረጡና ከቤተክርስቲያኑ ግድግዳ ስምንት ጫማ ያህል ርቀው በበቀሉ ትላልቅ የጥድ ዛፎች ግንድ ላይ አርፏል። በነዚህ የዛፍ ግንዶችና በቤተክርስቲያኑ መካከል የጊንዲላ ወለሎችን በመጨመር ይህ ተፈጥሮአዊ ምሰሶ ወደ ክብ ሰገነትነት ተሰውጧል።

ጳሚጥሮስ ጫማዎቹን ሲያወልቅ፣ መንገደኞችም በተመሣሣይ ፈፀሙ። የመጀመሪያውን የቤተክርስቲያኑን ክልል ጥሰው ለማለፍ ከቻሉ በኋላ፣ የተለያዩ የእድሜ ዘመናት ያሳቸውን የዛድቃንና ስማዕታት ሥነ ሥዕሎች ተመለከቱ። አንዳንዶቹ የባዘንታይን የአሣሣል ጥበብ ተፅዕኖ ያለባቸው ሲመስሉ፣ ብዙዎቹ ግን፣ በተለይ የአቢሲኒያውያን አሻራና

ይልቅ አጭር ጊዜ ብቻ ትቆያለች። ከዚያም ትመለስና በቤቱ ውስጥ ወዲያና ወዲህ ትላለች። ሙሴ ዴ ማይሌ የያዛቸው የቤቱ ክፍሎች፣ የክብረ በዓል ክፍል ማለትም የንጉሡ ሥዕል ያለበትና ጥቂት የሚዋለኑ ክፍሎች፣ ብዙ ጊዜ ባዶ የሚሆኑት በሁለተኛው ፎቅ ላይ ለጉብኚ ባለሰልጣናት የሚሆኑ አፖርታማዎች ናቸው። ማዳም ዴ ማይሌ በበኩልዋ ከክፍሏ እምብዛም አትወጣም። የተቀረው የቤቱ ክፍል ለምሣሌ የመፀዳጃ ክፍሎች፣ የመተላለፊያ ክፍሎች፣ የአሲስ መኝታ ክፍል፣ የመልበሻ ክፍሎች፣ የምግብ ማዘጋጃ ክፍሎች፣ ጓዳዎች፣ የልብስ ማጠቢያ ክፍሎች ሁሉ፣ ለሁለቱ ጓደኛሞች መገናኘት ምቹ ቦታዎችን ሰጧቸው። የተለያዩት አካባቢዎች ግብረ አበርነታቸውን በውበት አደሰላቸው። ጥንቃቄአቸውንም የሚያጓጉ አደረጉላቸው። ሁለቱም ሁሌም ጥንቃቄ ቢያደርጉም በዚያ ሰፊ ቤት ውስጥ ለመወያየት አንድ ሺህ አድል ሰጣቸው።

12

ያልተጠበቀውን ውይይት ከንጉሠ ነገስቱ ጋር ባደረጉ በሚቀጥለው ማለዳ፣ ጀን ባፕቲስትና ሜትር ዣረሚ ሁለት መድሃኒቶችን በማዘጋጀት ራሣቸውን በሥራ ወጥረው ነበር። ከመድሃኒቶቹ አንዱ፣ ለንጉሡ የሚሄድላቸው ሲሆን ሁለተኛው ካህናቱ እንዲመረምሩት ያላክላቸዋል።

በዚያኑ ዕለት ከሰዓት በኋላ፣ በየአመቱ የዝክር ድግስ በሚደረግበትና በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ወደሚሠበሰብበት ክልተማው ወጣ ብሎ ወደሚገኝ ትልቅ ቤተክርስቲያን፣ ጻሚጥሮስ ይዟቸው ሄዱ። ፀሐይ ደማቅ ብርሃኗን ታበራለች። በያንዳንዳቸው አዕምሮ ውስጥ የነበረው የመጨረሻው ነገር የስቃይ ቅጣቱ ነበር። ዐይኖቻቸው ሲያዩ አስከሚችሉበት ርቀት ድረስ ሲመለከቱ፣ ነጭ የለበሱ ሴቶችና ህፃናት፣ ጥቋቁር ዣንጥላዎቻቸውን ዘርግተው፣ በትናንሽ አህያዎች ላይ ሆነው ይሰግራሉ። ሽማግሌ ወንዶች፣ ረዣዥም የእረኛ ዘንጎቻቸውን እየተመረኮዙ ይጓዛሉ። ደማቅ ቀለማት ያሏቸውን ካባዎች የደረቡ ብዙ ካህናትና መነኮሳት፣ መስቀሎቻቸውን በሰልፍ ሰድረው አለፉ። ከፍተኛ ባለስልጣኖችን ከፀሐይዋ ቃጠሎ ለማዳን ዙሪያ ከፈፋቸው ላይ የሚቅጨለጨሉ የብር ደወሎች ያሉባቸው ትላልቅ፣ ቀያይና ጥቋቁር ጃንጥላዎች፣ በወጣት ባሪያዎቻቸው ተዘርግቶ ተይዘላቸዋል። ሁሉም ሰው ወደ አንድ የጥድ ዛፎች ጫካ ያመራል። የነዚህ ዛፎች የታችኞቹ ቅርንጫፎቻቸው ወደ መሬት እየተጠማዘዙ ስለወረዱ ሕፃናት እየተንጠለጠሉባቸው ዥዋዥዌ ይጫወታሉ። ቤተክርስቲያኑ እምብዛም አይታይም። ስምንት ማዕዘን የሆነው ኩብ የሣር ክዳን ጣሪያው፣ ተሰተካክለው በተቆረጡና ከቤተክርስቲያኑ ግድግዳ ስምንት ጫማ ያህል ርቀው በበቀሉ ትላልቅ የጥድ ዛፎች ግንድ ላይ አርፏል። በነዚህ የዛፍ ግንዶችና በቤተክርስቲያኑ መክከል የጊንዲላ ወለሎችን በመጨመር ይህ ተፈጥሮአዊ ምሰሶ ወደ ኩብ ሰገነትነት ተለውጧል።

ጻሚጥሮስ ጫማዎቹን ሲያወልቅ፣ መንገደኞችም በተመሣሣይ ፈፀሙ። የመጀመሪያውን የቤተክርስቲያኑን ክልል ጥሰው ለማለፍ ከቻሉ በኋላ፣ የተለያዩ የአድሜ ዘመናት ያላቸውን የፂድቃንና ሰማዕታት ሥነ ሥዕሎች ተመለከቱ። አንዳንዶቹ የባዘንታይን የአሣሣል ጥበብ ተፅዕኖ ያለባቸው ሲመስሉ፣ ብዙዎቹ ግን፣ በተለይ የአቢሲኒያውያን አሻራና

ዘዴ ያሰባቸው ናቸው። የስዕሉቹ አይኖች ሙሉ በሙሉ ከሚቆጣጠሯቸው ፊቶቻቸው ነፃ ሆነው የራሣቸው ሕይወት ያላቸው ይመስላሉ። የፃድቃኑና የሰማዕታቱ አካላት የተሣሉት በብሩህ ቀለም ነው። የቅድስናና የተአምራት መለያ የሆኑ የተከበሩ ምልክቶች ለፀሎት እንደሚያነሳግለው የሞተ ቋንቋ፣ በብሩህ ቀለማት ተገልፀዋል። ይሁን እንጅ ማምሳያዎቹ የተወሰዱት ከአገራዊ ሞዴል ነው። ስለዚህም ከበድ ያለውና የበላይነት የሚታይበት የክርስቶስና የናቱ ምስሎች፣ የተራ ሴትና የሕፃን መልክ ያላቸው ናቸው።

ወደዋናው ከተማ ከተመለሱ በኋላ፣ ዲሚጥሮስ፣ ቤተመንግስቱን እንዲጎበኙ ወሠዳቸው። ከንጉሡ ጋር ወደተገናኙበት የክብር ቦታ ሲሄዱ ያረፉበትን ግቢ አላያቸው። ወጣቱ ሰው በለጠው ምልክት የተነሣ፣ የንጉሱ አራት አንበሶች ወደተኙበት ጉዞ እንዲያልፉ ዘበኞቹ ፈቀዱላቸው። ከእንስሳቱ አንዱ ወንድ፣ ሦስቱ ግን ሴቶች ሲሆኑ፣ አንዷ በጣም ወጣት ስለሆነች በወፍራም የብረት አጥር ውስጥ ታስራለች። ዲሚጥሮስ፣ እንስሳቱ የተከተቱበትን አንዳች የሰቃይ ቅጣትና የመስዋዕት ታሪክ ሲነግራቸው እንዳቀደ በማሰብ፣ ፖንሴ ለአፍታ ያህል ተጨነቀ። ይሁን እንጅ አውሬዎቹ፣ የንጉሡ የግላቸውና የግላቸው ብቻ መሆናቸውን፣ ሁልጊዜ ማለዳም እንድ ባሪያ እርሳቸው ባሉበት፣ ሥጋ ወደ ጉጆአቸው እየወረወረላቸው እንደሚመግቢቸው፣ ምንም አይነት ነገር ዕረፍታቸውን እንዲረብሽባቸው እንደማይፈቀድ ነገራቸው። ይህን ሲሰሙ መንገደኞቹ እፎይታ ተሰማቸው።

በመጨረሻም፣ ዲሚጥሮስ፣ በከተማዋ ውስጥ በሚገኙ መሣፍንቶች ቤቶች ብዙ የመታያ የአራት ግብጣ ጥሪዎችን ከሰዓት በኋላ አመጣላቸው። ለዚያን ዕለት አንዱን ብቻ ተቀበሉ። አስተናጋጃቸውም ለክብራቸው ሲባል የሚገመተውን ሁሉ አቅርበዋል። ጣፋጭ ምግቦችን፣ በቂ የጠጅ መጠጥ፣ እንዲሁም አነስተኛ ቡድን የሆኑ የሙዚቃ ተጫዋቾችንና ዘፋኞችን አቅርበዋል። በዚያን እለት ከሰዓት በኋላ፣ ብዙ ማስታወሻዎችን የፃፈው ፖንሴ፣ የአገሩን ባህል አይቶ ለመክተብ ቻለ። ካስተዋለው ውስጥ ወንዶች በባህሉ ምግብ ወደአፋቸው ለማድረግ ብዙም እንደማይደፍሩና በአኳያው ግን የሴት ጓደኞቸው አንድ፣ አንድ፣ ጉርሻ የሚሆን እያዘጋጁ እንደሚያጉርሷቸው፣ አቢሲኒውያን ሹካና ማንኪያ እንደማይጠቀሙና በጣቶቻቸው እንደሚያጉርሷቸው አስተዋሉ። ፖንሴ የተቀመጠው፣ በሰል ያለ እድሜ ካላት ረጋ ያለች ግዙፍ ሴት ወይዘሮ ቀጥሎ ነበር። የወይዘሮዋ ወፍራም ቅርፅ፣ የሚፈስስ በሚመስለው በጥልፍ ያጌጠ የጥጥ ቀሚስ ውስጥ ተሰይቶ ይታወቃል። አንዲት ወጣት ባሪያ፣ ሰፊውን

አንጀራና ወጡን ከጠረጴዛው ላይ ስታስቀምጥና አጠገቡ የተቀመጠችው ሴት በረዣዥሞቹና የመርቅ ቀለበት ባጠለቀችባቸው ጣቶችዋ፣ ግማሹን በወጭት ውስጥ ስትፈተፍተው ከቀናነት በመነጨ ስጋት ተመለከታት። ከዚህ በኋላ ሴትየዋ በሚያቃጥል በርበሬ በተሠራው ከቀይ መረቅ ውስጥ ካስዋኘችው በኋላ ሁሉንም ጠቅልላ ጀን ባፕቲስትን አጉረሰችው። በዚህ ጊዜ ወዲያውኑ ከገጠመው የሚያቃጥል ስሜት በስተቀር፣ መቃወም እርባና አልነበረውም። ሁለተኛውን ጉርሻ ዓይኖቹ በፅንባ ተሞልተው ተቀበሉ። ሜትር ዠረሚም በስተቀኙ ካለች ለግላጋ ወጣት ሴት እጅ ተመሣሣይ መስተንግዶ ተደረገለት። ሌሎች ወንዶች እንዲህ ያለ እይን ያወጣ ተግባር ሲፈፀም አንዳችም የመደናገጥ ስሜት አልታየባቸውም። ይልቁንስ ፖንሴና ሃደኛው ይህን አስገዳጅ ጉርሻ ለማስቆምና እንደልባቸው ለመናገር ሲጥሩ፣ ሰዎቹ በበኩላቸው ደግሞ ከበድ ባለ ሁኔታ የጉርሻውን ተገቢነት ያረጋግጡ ነበር።

ሁለቱ ሰዎች እስኪጠግቡ ድረስ በልተዋል በሚል አጉራሾቻቸው ስለወሰኑ ይሁን፣ ወይም ደግሞ ባለፈው ተሞክሮ ላይ በመመስረት ይሁን ወይም ሴቶች የሚጠይቁት ዋጋ ይወድቅብናል ብለው ይሁን ብቻ የስቃዩ ጉዳይ ቀጠለ። ፈረንሣውያኑ በጠጅ ጉርፍ ውስጥ ኖኙ። ውሰጣቸውም ነደደ። ሙሉ በሙሉ ጋሉ። በቤቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ቀስ በቀስ መውጣት ጀመሩ። ጥቂቶች በጨረቃዋ ብርሃን ውስጥ ቡና ለመጠጣት ወደ በረንዳው ወጡ። የፖንሴ ኮስታራ አጃቢ እንዲከተላት ጠቀሰችው። ሜትር ዠረሚም እንዲሁ በሌላ አቅጣጫ ከራሱ አጃቢ ጋር ጠፋ።

ዓይኖቻቸው በእንባ ስለበዙ፣ ከንፈሮቻቸውም በጠንካራ ቅመሞች ስለነደዱ፣ ፊቶቻቸው ላይ ውሃ በመርጨት ሰማቀዝቀዝ እንዲችሉ ወደ መታጠቢያ ክፍል የሚመሯቸው መስሏቸው ነበር። ከዚህ ይልቅ ሰጋጃ ተነጥፎባቸው፣ ትራሶች ተደርድረውባቸው ባሉ ጨለማ ክፍሎች ውስጥ ራሳቸውን አገኙ። አስተናጋጆቻቸው በፀጥታ ልብሶቻቸውን ቦማውሰቅ የዝሀን መንገደኞች የምግብ ፍላጐት ሃላፊነት እንደወሰዱ ሁሉ ሌላውንም ፍላጐታቸውን ፈፀሙላቸው። እጭር የእምቢታ መቋቋም ካደረጉ በኋላ፣ የባለስልጣን አስተያየትን የመቀበል ያህል የማኪያቤሊን ቴልህ ዘዴ መቀበል እንዳለባቸው አመኑ። ሊያስወግዱት የማይቻልን ነገር በትጋት ማከናወን ተገቢ ነው። እውነታው ሲገለጥላቸው፣ ለተጀመረው ሥራ ድጋፋቸውን ለጠ። በምድረበዳው ውስጥ ባላለፏቸው ረዥም ቀናት፣ የወሲብ ግን ኑነትን ፈፅመው

ረስተው ነበርና እንዲህ ባልተገመተ ሁኔታ ሲያገኙት ቢደነቁም አልተቆጣበትም። ጥቂት ቆይቶ ወደ እንግዳ ክፍሉ ሲመለሱ ሌሎች እንግዶች ፈንጠርጠር ብለዋል።

ዲሚጥሮስ፣ ሁለቱን ፈረንሳውያን ወደቤታቸው አጅቦ ሊወስዳቸው ጠየቃቸው። የአስተናጋጆቻቸው ባሎች፣ ከነዚሁ ፈንጠርጠር ብለው ከተቀመጡት መካከል ሣይሆኑ እንደማይቀሩ ባያጠራጥርም፣ ደስ ያላቸው የሚመስሉትን ሰዎች ፖንሴና ሜትር ዝረሚ እጅ ነሱ። ቀጥለውም ታዛዥነታቸውን በከፍተኛ ክብር የተቀበሉትን ሌቶች እጅ ነሱ።

ሁለቱ ሰዎች ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ይበልጥ ግራ ተጋብተው ተኙ። ከጆን ባፕቲስት አዕምሮ ውስጥ አልጠፋ ያለችውን አሲስን ሲያስብ ይህ የስጋ ፈቃድ እርሷን በስልት እንዳጣት መሰለው። ካጋጠመው ልዩ ሁኔታ ጋር ስሜቱ ተደበላልቆበት የወጣቷ ትዝታ ተቀሰቅሰበት፣ ሌሊቱን በውብ የደስታ ስሜት እያለማት አሣለፈው።

በማግስቱ ዘግይተው ከእንቅልፋቸው ተነስተው ወደ ቅመማ ቅመም ገበያ ሰጉብኝት ሄዱ። በዚያም፣ ባርካ ውስጥ ላስተናገዳቸው መስሲም ምስጋና ይግባውና፣ እርሱ ያሣያቸውን ናሙናዎችና ብዛት ያላቸው እንደልብ የማይገኙ ሌሎች ዕፅዋት ለዕይታ ተደረድረው ተመለከቱ። ከነጋዴዎች ጋር ተነጋገሩ። እንዲያውም፣ ሥራቸው እነዚህን ድንቅ መዓዛና የመድሃኒትነት ጠባይ ያላቸውን ዕፅዋት ከሩቅና ከማይደረስባቸው ቦታዎች እየሰበሰቡ የሚያመጡ ሁለት ሰዎችን አገኙ። ስለተለያዩ ፍሬዎችና ቅጠላ ቅጠሎች አጠቃቀም ሲጠይቋቸው፣ በዚህች አገር ላይ በሚገባ የተጠናው የመድሃኒት ቅመማ ጉዳይ በመርዞች ላይ እንደሆነ ፖንሴና ሜትር ዝረሚ በድንጋጤ አረጋገጡ። በአውሮፖ ደህና አድርገው የሚያውቁት፣ ከጥንት ጀምሮ ትክክለኛና በተግባር የተፈተኑትን የሞት ውጤት የሚያስከትሉትን ሲሆን፣ የነዚህ ዕፅዋት ደካማ ዝርያዎቻቸው የሆኑ መድሃኒቶች ግን በማምት እንደቀሩ፣ ብዙ እንደሚያወግቡና እንዲያውም አንዳንዶች ጠቀሜታው ዝቅተኛ የሆነ ሣይንስ የሚሉት እንደሆነም ተገነዘቡ።

የዚያን ዕለት፣ ለዕራት ወደ ሌላ ቤት ሄዱ። የባለፈው ዕለት ተሞክሯቸውን ስለሚያውቁ ምግባቸውን ራሣቸው መጥነው እንደሚጐርሱ ሙጭጭ ብለው፣ ከመጠጡም ትንሽ ጠጡ። የምግብ ፍላጐታቸውን ሁኔታ ካወቀች በኋላ ጣልቃ መግባቱ እንደማይረባ አስተናጋጇ ተረዳች። ሁለቱ ሰዎች ሲበቃቸው አቆሙ። ከምግቡ በኋላ ቡና ያፈላችላቸውን

ባርያ ልጃገረድ ተጠግተው በአቢሲኒያውያን ስነፅሁፍ ላይ ጐረቤቶቻቸውን በጥያቄዎች አዋከቧቸው። እንደማዘናጊያ ሆኖ ወደ አንስቶች ብዙም እንዳያስቡ ያደረጋቸው ከነርሱ ሞራሉት ያልገመቱት ፣ነገር ግን አቢሲኒያውያን ለስነግጥም ታላቅ ፍቅር እንዳላቸው አወቁ።

አጫጭሮቹና እንዲሠሟቸው ተብለው የሚነገሩትን ግጥሞች ወደ ኢጣሊያንኛ ለመተርጐም ዲሚጥሮስ ፈተና ሆነበት። የነዚህ ግጥሞች ውበት ኢትዮጵያውያን ስምና ወርቅ ብለው በሚያነዓፅሩት መካከል መሆኑን ዲሚጥሮስ አብራራላቸው። ሰም፣ የወርቁ እንቁ የሚፈስስበት ቅርፅ ማውጫው ነገር ነው። የቅርፁ ማውጫ መልክ ተራ ቢሆንም ውስጡ መሠረት አለው። ይህ ቅርፅ ማወጫ ሲሰበር፣ በውስጡ ያለው ሃብት ይወጣል። በግጥሞቹ ቃላት በመጀመሪያ ላይ ሰዛ ቢስ አሳላች ሲመስሉ፣ በጮሌ የአትኩሮት አጨዋወት ውጫዊው ትርጉማቸው ይጠፋና ሌላ ውስጣዊ ድንቅና ብልህ ትርጉማቸው ይገለጣል። የዲሚጥሮስ ትርጉም፣ ይህን ትርጓሜ የመለወጥ ሂደት፣ ሊገልፀው አልቻለም። ጆን ባፕቲስትና ጓደኛው እንግዶቻቸው ግጥሞቹን እንደገና በመጀመሪያ በስም ቅርፃቸው ሲናገሩ፣ የመሰልቾትና የመተከዝ መመሳሰል ተመለከቱባቸው። ከዚያም ብዙም ግልፅ የማይሆን የቅላፄና የትርጉም ልዩነት ያከሰብታል። ይህን ጊዜ የወርቁን ሃረግ ተናገረ ማለት ነው። ያን ጊዜ ደግም ፊታቸው በአድናቆትና በጣም በሚገርም ደስታ ያበራል።

ሁሉም ሰው ተደስቶ ወደ ቤቱ ሄደ። ጆን ባፕቲስትና ጓደኛው ወደቤታቸው ሲሄዱ፣ ከልብ በመወያየታቸው ለሌሎች ሁሉ የግጥምን ደስታ በመመኘት እኳን ደስ ያለን ሲሉ ለራሣቸው ተመኙ። ይህ ሁኔታ ቀደም ብሎው እንዲሰቀቁና አዕምሮአቸውንም ነፃ እንዲያደርጉ ረዳቸው። ወደ መኝታ ከማምራታቸው በፊት፣ ከንጉሠ ነገስቱ ጋር እንዴት እንደሚሆኑ የመጨረሻ ውይይት አደረጉ። ጆን ባፕቲስት፣ ስለነገሮች ላይ ላዩን ብቻ እንዲመለከቱና የንጉሡን የህመም ምልክቶች ብቻ እንዲነጋገሩባቸው ለጓደኛው ሣጣብ አቀረበ። ሆኖም ግን፣ ለእውነት ቁርጠኛ ፍቅር ያለው ሜትር ዝረሚ፣ ጓደኛው ይበልጥ ሃቀኛ እንዲሆንና ንጉሡ ሕመማቸው በጣም ከባድ መሆኑን እንዲገነዘቡት እንዲያደርጋቸው የሚል ሣጣብ ሠነዘረ። ስም ወይም ወርቅ ሁልጊዜም ወደ አንድ ነገር ይመለሳል። ቀጣዩ ተግባራቸው ላይ ከውሳኔ ላይደርሱ እንቅልፍ ወሠዳቸው።

ንጋት ላይ እንደገመቱት ዲሚጥሮስ ቀስቅሷቸው፣ ንጉሰ ነገስቱን በግንባቸው ውስጥ ሊያዩዋቸው ሄዱ።

ንጉሡን በተሸበረ ስሜት ውስጥ ሆነው አገኟቸው። ወዲያው እንደገቡ ሞቅ ባለ ፈገግታ፣ እያሱ እንዲህ አሏቸው።

«አድናችሁኛል»

ጀን ባፕቲስትና ሜትር ዠረሚ ደንዝዘው ቀሩ።

«ማላከኩ ትቶኛል። ሊገድለኝ የሚጀምረኝ ህመም ጠፍቷል። ትልቁ ቁስል ተቀርፎ ሊወድቅ የሚያዠት ቦታዎች መድረቅ ጀምረዋል። የራሴን እምነት ባላተኩርበት፣የናንተንም ተአምር ፈጥሯል ማለት እችላለሁ። ተመልከቱ።»

ቀበቶአቸው እንደታሠረ አያለ፣ ክንዳቸውን ተራ በተራ ከእጅጌአቸው ሰማውጣት ረዥሙን ቀሚሳቸውን እንደሸሚዝ ሊያወልቁት ቃጣቸው።

ፖንሴ ቁስሉን መረመረ።

«በጣም የተሻለ ሁኔታ ላይ ነው» ሲል አመነ።

« በጣም ስሜትህን የነካው አይመስለኝም» አሉ ንጉሡ « ይገባኛል፣ ጠንቃቃ ነህ። ውጤቱ ጥቂት ሊቆይ የሚችል መሆኑን እርግጠኛ ለመሆን ትፈልጋለህ። ትክክል ነህ፣ ነገር ግን ልንገርህ፣ እፎይታው ጊዜያዊ እንኳ ቢሆን ላንተ ፍፁም ውለታ አለብኝ፣ ከብዙ የማይቻል ስቃይ በኋላ የሰዓታት ሰላም ሰጥተኸኛል።»

«ግርማዊ ሆይ» አለ ፖንሴ «አሁን የምናየው የሚያበረታታን ነው። አሁን በተደረገልዎ ሕክምና ሕመምዎ ምላሽ በማግኘቱ ለማመን በቂ ምክንያት አለን። በሚቀጥሉት ቀናትም በጣም የመሻሻል ለውጦች እናያለን። ነገር ግን . . . »

እዚህ ላይ በጣም አለቃቂ በሆነ ታልዕኮ ላይ እንደሚለማራ ወታደር፣ ፖንሴ ወደ ዠረሚ ተመለከተ።

« . . . ሊያውቋቸው የሚገቡ አንዳንድ ነገሮች አሉ» ሲል ቀጠለ።

«አለማሃለሁ»

«በሚያለቃይም ህመም ላይ የነበረዎ ቅሬታ ቀንሶ ይሆናል። ጉዳቱ ለረዥም ጊዜም ቢሆን ሊቀንስ ይችል ይሆናል እንጂ ፍፁም አይድንም። ህመሙ እንደና ሊመለስ ይችላል። እርስዎም ከህመሙ ጋር መኖር መቻሉን ሊቀበሉ ይገባል። ያለጥርጥር ግን . . . »

አፍታ ጊዜ በፀጥታ እንዲያልፍ አደረገ። ንጉሡ አይናቸውን ሣያርገበግቡ ፍጥጥ ብለው ተመለከቱ። ጀን ባፕቲስት የራሱን አረፍተ ነገር የመጨረሻውን ሲናገር ራሱን ሰማና ራሱ ተገረመ።

« . . . በዚሁ ጠንቅ ሊሞቱ»

ዲሚጥሮስ እነዚህ ቃላት ከተረጐማቸው በኋላ፣ ንጉሡ መልስ እንዲሰጡ ተመለከታቸው። መልሱ ወዲያውኑ አልተሠጠም። ንጉሡ ተነስተው ቆሙና ወደ ክፍሉ ማዕዘን በመራመድ በጭለማው ውስጥ ከተሠወሩ በኋላ ተመልሰው ወደነርሱ መጡ።

«የምትነግረኝን ባልወደውም፣ ቋንቋህ ያስደሰተኛል። ንግግሩ የአስመሣዮችና የሸንጋዮች አይደለም። እኔ ለማዳመጥ መቻሌን በማሰብህም ትክክል ነህ።»

ሰጥቂት ጊዜ ዝም ብለው የጢፉን ክልባል ተመለከቱ። እንደገና የጀን ባፕቲስት ዓይኖች ውስጥ ትኩር ብለው አዩ።

«ከዚህ ሕመም ጋር ለምን ያህል ጊዜ ልኖር እችላለሁ?»

«አላውቅም» አለ ፖንሴ

«እውነት አይደለም» አሉ ንጉሡ፣ ጮሳ ባለ የቁጣና የባለስልጣን የድምፅ ቅላፄ

ጀን ባፕቲስት ግራ ተጋባ።

«ከዚህ ዓይነት በሽታ ተለክፎ የሚሠቃይ ሰው ከሁለት ዓመት በላይ በህይወት መኖሩን የማውቀው ማስረጃ የለኝም።»

ንጉሡ፣ ዐረፍተ ነገሩ በትክክል መነገሩን ሰሙ። ቀና ብለው ፀጥታውን ሰበሩት።

«ለኔ በግሌ ከሆነ ሞት ምንም አይደለም። ነገ ልሞት እችላለሁ። ለዚህ ዝግጁ ነኝ»

የንግግራቸውን ሞገስ ቀዝቀዝ ለማድረግ ተመልሰው ተቀመጡ።

«ነገር ግን» ሲሉ ቀጠሉ «የማከናውነው ጉዳይ አለኝ። ትልቁ ልጄ»ሲሉ ቀጠሉ «ገና አስራ አምስት አመቱ ነው። አሁንም ገና ለጋና በቀላሉ ሊጠመዘዝ የሚችል ነው። እኔ ባልነበርኩባቸው ረዥም ጊዜያት ከካናቱና ከቤተመንግስቱ ስላገኘው ትምህርት ይጨንቀኛል። ዙፋኑን ስርሱ እንዲፀናለት ማድረግ ችዬ ሀይወቴ ቢያልፍ ደስ ይሰኛል። ይህ ካልሆነ ሦስት የንስታት ትውልድ አንዳችም ሳይፈይድ ይቀራል።»

የቀለጠው ሰም ቁልቁል ሲፈስስ፣ ሚፉን ትክ ብለው ተመለከቱት

«ሁለት ዓመት?» አሉ

ብድግ ብለው በገበብት በር አጠገብ ወዳለ ወንበር ሄዱ። በወንበሩ ላይ በአራት ማዕዘን ቅርፅ የታጠፈ ነጭ የአንገት ልብስ አለ። የአንገት ልብሱን ትከሻቸው ላይ ወርወር አደረጉና ራሳቸውን ጠበቅ አድርገው ጠቀለሉበት።

«አያቴ ዙፋኑን ሲወርስ» ሲሉ ቀጠሉ «ይህች አገር ሙሉ በሙሉ በሥርዓተ አልበኝነት ውስጥ ነበረች። ጠላቶቻችን ፍፁም አወደሟት፣ ሉሌዎቻችን ነፃነቶቻቸውን መልሰው አገኙ። ካህናቱም በንጉሡ ላይ ፍላጐታቸውን ጫነባቸው። በአገር ቤት ህዝቡ በርሃብ ያልቅ ነበር።»

ዞር አሉና ወደነርሱ ተራመዱ

«የራሳቸውን መታኖች የበሉ ገበሬዎች ነበሩ»

ፖንሴ አይኖቹን ሰበራቸው። ሜትር ዝረሚ በጨለማው ላይ አፈጠጠ።

«የዚህች አገር ሁኔታ ይህን ይመስል ነበር። ሁሉም ነገር ገና መሠራት ይኖርበታል። ንጉሣዊ ሥልጣን በሚገባ መረጋገጥ ይገባዋል። ጠላቶቻችን ወደኋላ መባረር ይኖርባቸዋል። መኳንንቶቹ እጅ መስጠትን ነው ያመጡልን፣ ካህናቱ የእንቅስቃሴው ተቆጣጣሪዎች ሆኑ። ቅድመ አያቴ ፋሲለደስ፣ ሂደቱን በድምቀት ጀምሮ ይህች በዙሪያችን የምትገኘውን የጐንደርን ከተማ ቆረቆረ። ለዘመናት ቤተመንግስቱን ይዛ የኖረችውን አክሱምን ካወደማት መስከና በተለየ መልኩ፣ ጐንደርን አዲሲቱ ዋና ከተማ አደረጋት። ከዚያ በኋላ የመጣው የርሱ ልጅ፣ የኔ አባት ነው። አባቴም ለአገሩ እንደ አያቴ ታማኝ፣ ታላቅና ቁርጠኛ ነበር። የአባቴን አልጋ ስወርስ፣ ረዥም

ዘመን ሰመንግስ፣ የታሪካችንን ቅርስ ጠብቄ ለማቆየትና እንዲያፈራም ለማድረግ ጥሩ እድል ነበረኝ። ለህዝቡ የግብር መጠን ቀንሻለሁ። አገሪቱን ወደተበጣጠቀችና ተሰያይቶ ወደሚኖር ቦታ የለወጧትን የቀማኞችንና የዘራፊዎችን የኪላ ቀረጥ አስወግጃለሁ። ከሁሉም የበለጠ የሕግ የበላይነትን ተግባራዊ አድርጌአለሁ። ሕጉ ጥብቅ ነው። ይሁን እንጅ በህግ ፊት ሁላችንም እኩል መሆናችንን እያንዳንዳችን የምናውቀው የአባቶቻችን ሕግ መሆኑ አያጠራጥርም።»

ቀስ በቀስ ንጋት ደረሠ። ሀምራዊ የደመና ቀለም በመስኩቱ ውስጥ ሰንጥቆ ሲገባ ክበላዩ ጨለማ ሌሊት፣ ከስሩ ደግሞ ግራጫ ፈላሽ ይታያል።

«ይህን ሁሉ ብቻችንን ማከናወናችንን ታውቃለህ። ብቻችንን። ከጦረቤቶቻችን እርዳታ መጠበቁን የተውነው ከረዥም ጊዜ በፊት ነው። እነርሱ ይጠሉናል። ከዚህም ሌላ ከርቀት ሆነው ወዳጆቻችንና ወንድሞቻችን አድርገን ከምንቆጥራቸው የባህር ማዶ ካቶሊኮች ራሳችንን መጠበቅ ይኖርብናል። ከአንድ ክፍለ ዘመን በፊት ቱርኮች ይህችን አገር ሊወሩ፣ በጊዜው ነግሶ የነበረው ንጉስ፣ የፖርቹጋሎችን እርዳታ መጥራት ፈልጐ ነበር። የታላቁ የቫስኮ ልጅ ክርስቶፈር ዳጋማ ሕይወቱን ላይቀር አሣልፎ ሰጥቶናል። ያዳኑን ግን ከአደጋው በኋላ ጀስዊቶቻቸውን ሊልኩልን ብለው ነው። ካህናቱ እንደመጡ ግን መሆናቸውን እንኳ ያወቀ አልነበረም። አያቶቻችን እጆቻቸውን ዘርግተው ተቀበሏቸው። በክርስቶስ ወንድሞቻችን አይደሉ? ጳጳሱን እንድንታዘዛቸውና ከካቶሊኮች ጋር እንደገና እንድንቀላቀል ሲጠይቁን ተቃውሞ አላደረግንም። እስቲ አስቡው። ክሌላው አለም ተገልለን በመቅረታችን እጅግ ተጐድተናል። የዳግም ቅልቅሉ ሦስቱ አያስደስትም? ይሁን እንጅ፣ የነርሱ የወንጌል ትርጉም ከኛ ትርጓሜ የሚበልጥበትን መንፈሣዊ የመከራከሪያ ነጥብ አቅርበው እንዲያረጋግጡ ጠየቅናቸው። ይህ በርግጥ ተገቢና ትሁት ጥያቄ ነበር። የኛ ካህናት ንቱርኩ ውስጥ ሦስቱ ሰፊ ሆነው ገቡ። ሆኖም ግን በንባብና በጥናት ያገ ኙትን ታላቅ ፅውቀት አመጡት። በራሣቸው ጠባም እርግጠኞች የነበሩት ጀስዊቶች ስጥያቄዎቻችን መልሶችን እንደሚያውቁ መናዘዝ ነበረባቸው። ወደሮም ተዋርደው ተመለሱ።

«ጳጳሱ በጣም የተማሩና ይሉኝታ የለሽ የሆኑ ሌሎች ቀሣውስትን ላኩ። እኛ አሁንም፣ እንደወንድሞቻችን ተቀበልናቸው። የነርሱ ተግባር ግን የጠላት ዓይነት ሆነ። በዚያ ጊዜ ትልቁ ደክመታችን ንጉሡ ነበሩ። ምስኪኑ ሰው በቀላሉ ሃሣባቸውን ተቀበሏቸው። በጀስዊቶች

ዥውጣዋ ውስጥ ሆነው ብዙ መጥፎ ውሳኔዎችን ፈፀሙ። በመጨረሻም ባላቸው ሙሉ ሥልጣን ሁሉም በጅምላና አገሪቱም ወደ ካቶሊክነት እንዲለወጡ አዘዙ። በጣም ዘግይቶም ቢሆን፣ ከወሰን ድንበራችን ባሻገር ካሉት ሌላ፣ ሌሎች ክፉዎች መኖራቸውን አወቅን። እነርሱም ወዳጆቻችን መስለው የማንፈልገውን እንድንቀበል ያደረጉን ናቸው። ዝርዝሩን ለሌላ ጊዜ አቆይሃለሁ። ነገር ግን የፈረንሣውያኑ ካህናት የጠንቅ መዘዞች፣ አፅምሯችንን አሸንፈው፣እንድንታዘዛቸው ሊያደርጉን የሚያበቃቸው አዲስ እምነት በግድ ሊጭኑብን የሚያስችላቸው፣ በመሃከላችን አለመግባባትና ጠብ ፈጥረን ሸባ እንድንሆን በመፈለግ፣በሽፍጥ ሊገዙን የሚያግዟቸው ለቁጥር የሚያታክቱ ማስረጃዎች ነበሩ። አገራችን እጅግ የከፋ የርስ በርስ ጦርነት ያየችው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው። የከፋ ውጥረት በነበረበት ጊዜ እንኳ ተጠብቆ መኖር የቻለው የንጉሠ ነገስቱ ሥልጣን እንክትክት አለ። ይህ ሁሉ የሆነው ንጉሡ በቅፅበታዊ ድክመታቸው የነዚህን እንግዶች እምነት ለመቀበል በመሞከራቸው ነው። ያን ጊዜ ሊከራከሯቸው ባይችሉም በቀሳውስቱ ዙሪያ ጥገኝነት ፈለጉ። ጠላቶቻችን በውስጣችን የተቀሰቀሰውን ግርግር ለራሣቸው ጠቀሜታ አዋሉት። ይህንን የተከተለው ሶስት ትውልድ፣ ሊፍቀውና ሊያስተካክለው የጣረው የገለፅኩልህን ትርምስ ነው።

አየተረጋጉ ይበልጥ ለስለስ ብለው ቀጠሉ።

«አየህ ነገሮች ሁሉ ይህን በመሰለ ደረጃ ላይ ናቸው። እኔም ጊዜ የፈለግሁት ለዚሁ ነው።»

በዚህ ጊዜ ነግቶባቸው ነበር። ንጉሡ ወደ ፖንሴ ተጠግተው እጃቸውን በትከሻው ላይ አሳረፉ። እጃቸው ክችች ያለ ደካማና ክብደት ያልነበረው ነበር።

«አንተን የመሠለ ሰው ስመለከት ከምዕራብ የሚመጣልንን ሁሉ ላለመቀበል የምናደርገው ጥረት ትልቅ ሃፍረት ሆኖ ይሠማኛል። ጎረቤቶቻችን ድንገተኛ ወረራቸውን ከምድረበዳው ከመጀመራቸው በፊት የናንተና የኛ ሥልጣኔ አንድ ነበር። በአያቶቼ ቤተመንግስት ግሪክኛ ይነገር ነበር። አሁንም ቢሆን በራችንን እነዚህ ወንድሞች ለሚባሉት እንዳንከፍትላቸው፣ እንዳንሰበር ስጋት አለን። ሁላችንም ደህና አድርገን እንደምናውቀው፣ አሁንም ሃይማኖታችንን ሊያስለውጡን እየሠሩ ናቸው። የሚያደርጉት ነገር የሚያጠፋን መሆኑን አልተረዱም»

እጃቸውን አነሱና ወደበሩ መራመድ ቀጠሉ።

«አመሰግንሀለሁ» አሉ በደስታ። «ህይወቴ አሁን ተስፋ አለው። ማከናወን የሚገባኝን አውቃለሁ። ይህን ለመፈፀም ምን ያህል ጊዜ እንደቀረኝም አውቄአለሁ።»

ንጉሡ ወጥተው ሄዱ። ጉብኝዎቻቸው አዝነውና ተከዘው በዝምታ ቀሩ። የቀን ብርሃን እያየለ ወደ ክፍሉ መዝለቁ የረበሸው ዲሚጥሮስ፣ ወደቤታቸው እጅጊቸው ተመለሠ። ልብሶቻቸውን ሊቀይሩ፣ ወጣቱን ከሁለት ሰዓት በኋላ ለማግኘት ተስማምተው ብቻቸው እንዲተዋቸው ጠየቁት።

በሩ እንደተዘጋ ሚትር ዠረሚ ዘልሎ ጆን ባፕቲስት ላይ ተከመረበት።

«አብደሃል እንዴ? ምን ሰክፈሀ? ተስፋቸውን እያለመለምክ፣ ረዥም የህመም ዘመን እንዲኖራቸው የሚያደርግ መድሃኒት እንደምታዘጋጅላቸው ተስማምተን ነበር። ታዲያ ባደረግኸው ነገር የምታዝንበት ምን ተገኘ? ሕመሙ እየበረታ ስለመሄዱ ምን ማምት ተፈጠረብህ?

«አውቃለሁ» አለ ጆን ባፕቲስት። ሞንቅላቱን በሁለት እጆቹ መሃል ቀብሮ «ሰውዬውን ስመለከታቸው . . . ራሴን ለመዋሸት አልቻልኩም።»

«ውሸት አንድ ነገር ነው። ነገር ግን እውነቱን ሁሉ ለምን ትነግራቸዋለህ?»

«ሁሉንም ነገር እንድዘረግፈው ያደረገኝ በሰውዬው ውስጥ ያለ አንዳች አስገዳጅ ሃይል ነው።»

«ብርሃታቸው ውስጥ ሣይሆን ባንተ ውስጥ ነው» አለ ዠረሚ «ላንድ ንጉስ እጣ ፈንታውን መንገር! ምን ዓይነት እብደት ነው። ወዳጄ፣ ራስህን ፈጣሪ ነው ያደረግኸው። ነገሩ በጣም ቀላል ነው። ይህ ሁሉ ሌላ ሳይሆን ትምክህት ነው። እያበጠ የመጣ ትልቅ ትምህክት»

«አይመስለኝም» አለ ፖንሴ ዝቅ ባለ ድምፅ። «እኔ የማስበው ተቃራኒውን ነበር። ሣነጋግራቸው ንጉሥ ሆነውብኝ አይደለም። ልክ ለ . . . ወንድም እንደምናገረው ነው።»

«ወንድምህን ነዋ ስሜቱን የወጋኸው»

ንግግሩን ሣይጨርስ በሩ ላይ ሦስት ጊዜ ማንኳኳት ተሰማ። ፕሮቴስታንቱ ሊከፍት ሄደ። ሁለት የጥበቃ መኮንኖች ሊይዟቸው መጡ።

13

ዘበኞች የተቆጡ ይመስላሉ። የሚናገሩትም የራሣቸውን ቋንቋ ብቻ ነው። ፖንሲና ሚትር ገሪሚን ሌሊት በተጠቀሙት የምስጢር በር በኩል ሣይሆን፣ የቤተመንግስቱን ግድግዳ ሙሉ በሙሉ ሦረው በዋናው የክብር በር በኩል ወሰዷቸው።

ጠባቡን የእንግዳ መቀበያ ክፍል አቋርጠው መጀመሪያ ከራስና ከቀሣውስቱ ጥያቄዎች የተዥጐደጐዱላቸው የእንግዳ መቀበያ አዳራሽ ውስጥ ገቡ። በቦታው ላይ እነዚያው ባለስልጣናት ነበሩ። በመካከላቸው ባለው የድንጋይ ወለል ላይ በእንሶላ የተሸፈኑ ሶስት ሰዎች ተጋድመዋል። አንድ ካህን ሊናገሩ፣ ከንጉሡ ጋር ይፋዊ የሆነውን የመጀመሪያ ንግግር ሊያደርጉ፣ በአሪብኛ ሊያስተረጉም የነበረው ቱርጅማን ወደፊት ቀረበ።

«በአጃችሁ የተዘጋጀ መድሃኒት ሰጣችሁን። ይህም ለንጉሡ የሚጠቅም እንደሆነ ታስቦ ነው። ባሮች ቀመሱት። እናም ሁሉም ሞቱ» አሉ

ጆን ባፕቲስት በእጅጉ አፍይ አለ። የባሰ መጥፎ ይጥመኛል ብሎ ፈርቶ ነበር። «ይፋ» የተባለው መድሃኒት ከውሃ፣ ከዱቄትና እንዲያቀልመው ሲባል ከቀይ ስር ጭማቂ ተደባልቆ በዲሚጥሮስ ፊት የተዘጋጀ ነበር።

«ለክፉራት እንዲህ በል» አለው ጆን ባፕቲስት። «ያዘጋጀነው መድሃኒት በጣም ቀላል ነው። ናሙናችንን ከመላክችን በፊትም እኩል መጠን ያለውን ለንጉሠ ነገስቱ አገልጋይ ሰጌታ ዲሚጥሮስ ሰጥተነው ነበር።»

የዲሚጥሮስ ሰም ሲጠቀስ፣ ቱርጅማኑ ገና ማስተርጐም ሣይጀምር በአዳራሹ ውስጥ ኃመሰ ጀመረ። ወጣቱ ግሪካዊ እንዲመጣ እንደተላከበት፣ ሁለቱ መድሃኒት ቀማሚዎች ተረዱ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ አንዲት ትንሽ ሣጥን ይዞ እያላበው ደረሰ። በዚያች ሣጥን ውስጥ ለቀሣውስቱ የተሰጠው ነገር ግማሹ ነበረበት።

ወጣቱ ረዘም ያለ ንግግር አደረገ። ምንም እንኳ ፈረንሣውያኑ ምን እንደሚል ሣይረዱትም፣ የቅሳፄውን ሞቅ ማለት ለራሳቸው እንደሚስማማቸው ተረጐሙት።

እንቅስቃሴውን ከቃላቱ ጋር እያስማማ፣ ዲሚጥሮስ ሳጥኗን ከፈታት። ከተዘጋጀው ውስጥ የላቆጠች ፍሬ ጠልፎ አወጣና በይፋ እየበላ አሣያቸው። ከዚያም በዙሪያው ላሉት ሁሉ አደላቸው። ቀሣውስቱ የማስመሰል ጥላቻ አሣዩና ከአጭር ውይይት በኋላ ስብሰባው ተበተነ። ወዲያውኑ አዳራሹ ባዶ ሆኖ በሩ ተዘጋ። ጫጫታ ያለበት ወሬ ግን ይሰማ ነበር።

ግጭቱ መቋጨቱን ዲሚጥሮስ በፈገግታ ገለፀ

«እነዚህን ሦስት ያልታደሉ ሰዎች በመመረዛቸው፣ ንጉሡ የሞት ቅጣት ይፈርዱባቸዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ» አሰ ጆን ባፕቲስት

ጥቂት ወታደሮች በፀጥታ ወደ አዳራሹ ገብተው፣ የአስከሬኖቹን ቁርጭምጭሚቶች ይዘው ጐተቷቸው።

«አንድ ሰው የሚፈረድበት፣ ሰው ሲገድል ብቻ ነው። ባሮች ደግሞ ሰዎች አይደሉም» አለ ዲሚጥሮስ ክስተር ብሎ።

ከዚህ በኋላ ሁለቱ ሃኪሞችና መንገድ መሪያቸው ክፍሉን ለቅቀው ወጡ። የሌሎችን መከራ መቀበል፣ በተለይም መላው ህብረተሰብ ያፀደቀው ከሆነ ለመልመድ በጣም ቀላል ነው። በነዚህ ለለባዎች ላይ የተፈፀመውን የፖለቲካ ሤራ ወዲያውኑ ረስተው በድርጊቱ ጀልነት ብቻ ሣቁ።

የዚህ አይነቱ ተግባር፣ ንጉሡ በምን ዓይነት ብዙ አደጋዎች መሃል ሥልጣናቸውን እንደሚጠቀሙበት እንዲገነዘቡ ረዳቸው። ንጉሡ ነገስቱ የሚተማመኑባቸውም እንደ ዲሚጥሮስና ሃጅ አሲ የመሰሉ ከውጭ አገር በመጡ ሰዎች ላይ ብቻ ነበር። ከነዚህ ሰዎች አንዳንዶቹ በወታደራዊ ወረራ ወይም ዘመቻ ጊዜ የተማረኩና የታሠሩ ናቸው። ቱርካውያን አፍነው የሚወስዷቸውን ወጣት ክርስቲያኖች በማሰለም፣ የሱልጣኑ ጠባቂ ወታደራዊ ጓድ እንደሚያደርጓቸው ዓይነት፣ ንጉሡም ወጣት ሙስሊሞችን ክርስትና በማንሣት አገልጋያቸው ሲያደርጓቸው፣ እነርሱ ፍፁም ታማኝነታቸውን ያረጋግጡላቸዋል። ከአገራቸው ውጭ ለሚደረጉት ምስጢራዊ ተልዕኮዎች እንደ ሃጅ አሲ ያሉትን ከፍተኛ ውለታ ያላቸውን ሰዎች ወይም አርመናውያንና የአቶማን ከሲፋ ዜጋ የሆኑ የምስራቅ ሜዲተራኒያን ክርስቲያኖችን ይጠቀማሉ።

ፖንሴና ጓደኛው፣ ጐንደር በኖሩበት ጊዜ የንጉሡን ምስጢራዊ ጠባቂ፣ የርሱንም ጥላ ከለላ መለየት ቻሉ። ከዲሚጥሮስ በተጨማሪ በጣም ጠንቃቃና ማንነታቸው ተሰይቶ የማይታወቁ ምስክሮች፣በሚጓዙባቸው ጉዳናዎች፣ ምግብ በሚበሉባቸው ቤቶች ፣ እዕዋት በሚሰበስቡባቸው የባላገር አካባቢዎች ሁሉ ከጐናቸው ይኖራሉ። የማያስቀይመውን የገበሬዎች፣ የወሮበሎችን ወይም የኒጋዴዎችን ሁኔታ በማየት ንጉሡ በፈረንሣውያን ላይ ያላቸውን ሃያልነት ይቀበላሉ።

እነዚህ ተጓዦች በዋናው ከተማ ውስጥ የሰነበቱባቸው ሣምንታት፣ የየዕለቱን ሕይወት ትዕይንት የአይን ምስክር ሆነው እንዲያረጋግጡ ዕድሉን ሰጥቷቸዋል። የአገሬውን እንግዳ ባህል ተመልክተዋል። ምንም እንኳ በዚህኛው መስመር ቁጥብ መሆናቸው መጥፎ ስም ቢያሰጣቸውም፣ ጥቂት የሰጋ ፈቃድ ግንኙነትንም አድርገዋል። ከዚህም ባሻገር ብዙ ቤተክርስቲያናትን ጐብኝተዋል። አገራዊውን ባህላዊ የስዕል ቅብ ተመልክተዋል፣ በመጀመሪያ ላይ አልጭማቸው ያላቸውን የአገሪቱን ሙዚቃ አድንቀዋል። በተለይም ሙዚቃው በውዝዋዜ ታጅቦ ትዕይንትና ድጋፍ ሲኖረው ውበቱን በተሻለ መረዳት ችለዋል።

ብዙ ነገሮች ከምን እንደተሠሩ፣ ከእንጨት ይሁን ከመዳብ ወይም ከቀርከሃ ፈጥነው ለማወቅ ቻሉ። የእጅ ስራዎቻቸው ዓይነት፣ መለያየትና መብዛት፣ በንጉሠ ነገስቱ ግዛት ውስጥ ብዙ የተለያዩ ባህሎች አብረው መኖራቸውን ያንፀባርቁላቸዋል። ፖንሴ፣የማስታወሻ ደብተሩን በሙንጭርጭር ፅሁፍ ሞላው። ለዘዴኛው ዲሚጥሮስ ምስጋና ይግባውና ሌላም ገዛ። አቢሲኒያውያን ወረቀት ስለማያውቁ የሚፅፉት በብራና ላይ ነው።

ጥርጣሬ ላለመቀሰቀስ፣ እንደመጀመሪያው ቶሎ ቶሎ ባይሆንም ንጉሡን ማየታቸውን ቀጠሉ። የሕመማቸውን ሣይሆን የምልክቱን ቀስ በቀስ መክሰምና መለወጥ መዘገብ ቻሉ። ንጉሡ ስለህመማቸው መባርታት ወይም መሻል ፊዕሞ ደግመው አልጠየቋቸውም። በሌላ በኩል ለቁጥር የሚያታክቱ ስለ ባህል፣ ስለላይንስና ስለምዕራባውያን አገሮች ፖለቲካ ይጠይቋቸው ነበር።

ንጉሡ እንደገና ለወታደራዊ ዘመቻ እንደሚንቀሣቀሱ ዲሚጥሮስ የሚያረዳቸው ዕለት ደረሰ። የሲናር ንጉስ፣ በድንበር አካባቢ የተፈጠረውን አነስተኛ ግጭት ሰበብ በማድረግ

በአቢሲኒያ ላይ ጦርነት አውጇል። ጐንደር ከመሰንበት ይልቅ ንጉሡን ተከትሎ መሄዱ አደጋው አነስተኛ እንደሚሆን ውጣቱ ግሪካዊ ነገራቸው። የንጉሡን ድጋፍ ለማግኘት በአደገኛ ሁኔታና በብልጣብልጥ አካሄድ የመድረሳቸው ጭምጭምታ በሚናፈስባቸው በሁለቱ ባዕዳን ላይ፣ የቤተመንግስቱ ባለስልጣናት በሚያገኙት ተነፃፃሪ ነፃነት ሌላ ሴራ ለመጠንሰስና ለመፈልፈል ዕድል ይኖራቸው ይሆናል። የፈረንሣውያን ሐኪሞችን ባለስልጣናቱ በይፋ ያስተላለፉላቸውን መመሪያ በመጣስ በአደገኛ ሁኔታ ወደ ንጉሡ ቀርበዋል። ያዘጋጁላቸውንም መድሀኒት የወሰዱና የዳኑ በማስመሰል በመግለፅ፣ ሕመማቸው እንደተሻላቸውና በመጨረሻም ንጉሡ መዳናቸውን ሁሉም እንዲያውቁት በማድረግ አስወሩ። ንጉሡም ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ብዙ ስጦታዎች ለሁለቱ ባዕዳን ሸለሟቸው። ከዚህም ባሻገር፣ በከተማዋ ውስጥ ከሚገኙ ሴሎች ሕመማንም ገንዘብ ያገኙ ነበር። በጊዜ ብዛት ጆን ባፕቲስትና ሽሪኩ ጓደኛው ከሁሉም ዓይነት ደረጃ ከሚመጡ ሰዎች ጋር እንዲገናኙ ጥሪ ይጐርፍላቸው ጀመር። ይልቁንም ንግስቲቱ የሚማረሩበትን ህመማቸውን እንዲያከሙ በይፋ በመጠራታቸውና በተሣካ ሁኔታ በመፈፀማቸው ክህናቱ በርግጥ ተቆጥተዋል።

ንጉሡን በወታደራዊ ዘመቻቸው ላይ የማጀቡ ጥያቄ ሲመጣ፣ እውነቱ መገለፅ ያለበት ጊዜ መድረሱን ጆን ባፕቲስት ወሰነ። አቢሲኒያ ውስጥ መቆየቱ ምንም ያህል ደስታ ይሰጠው እንጅ፣ የጉዞው እውነተኛ ምክንያትና እርሱም በይሁንታ ለመቀበል የተገደደበትን አይዘነጋውም። አንድ የአቢሲኒያን ኤምባሲ ይዞ መመለስ ይኖርበታል።

ኤምባሲ ይዞ የመመለስ እድሉ ደግሞ የተረጋገጠ አይደለም። ንጉሡ፣ ጀስዊቶችንና ምዕራባውያን ሃይሎችን ያላመኑበትን ምክንያት ፈረንሣውያኑ ተገንዝበዋል። ንጉሠ ነገስቱም አገራቸው በሯን የምትክፍትበት ጊዜ ገና መሆኑን ነግረዋቸዋል።

የኤምባሲ ሃሣብ ጉዳይ የፖለቲካ መሰናክል ቢሆንም፣ ሌላ የግል የሆነ ችግርም አለ። እስከ አሁን ድረስ ፈረንሣውያኑ፣ ንጉሠ ነገስቱ ዘንድ ለመድረስ የነበራቸውን የረዥም ጊዜ ዕቅድ ጥቅም ብቻ ነው ያገኙትና አሁን ግን የዚህን ዕቅድ ጉዳትም ማሽተት ጀምረዋል። የንጉሡን አመኔታና ወዳጅነት ለማግኘት ያደረጉት ጥረት፣ እነርሱ ከመጀመሪያውኑ ተስፋ ካደረጉት ይልቅ በጣም ተሳክቶላቸዋል። ከሁሉም የበለጠ የሆኑት ንጉሠ ነገስት ወድደዋቸዋል። ከነርሱ ጋር በመተማመንና በፍቅር ተሣስረዋል። ለዚህ ደግሞ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የማያጨቃጭቅ ማረጋገጫ ሰጥተዋል። እነርሱ ያከናወኑት ጨዋታ ግን እደጋ

አልነበረውም ማለት አይደለም። ከንጉሠ ነገስቱ ጋር የፈጠሩት ወዳጅነት፣ ንጉሡ፣ አነርሱ ለኤምባሲ ያላቸውን ጉጉት እንዲቀበሉ ያደርጋቸው ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ ሊሆን የሚችለው ከነርሱ በፊት ሌሎች ብዙ ተጓጉች ላይ እንደተፈፀመው ከርሣቸው እንዳይለዩ እድሜአቸውን ሙሉ አስረው ሊያስቀሯቸው መቻላቸው ነው። ጆን ባፕቲስት በሚቀጥለው ውይይት ጊዜ ለንጉሠ ነገስቱ ሊነግራቸው ወሰነ። ቀኑን ሙሉ ካይሮን፣ ካይሮ የሚገኘውን ቤቱንና ማዳሞዜል ዴ ማይሌን ሲያስብ ዋለ። የራሱን ሃሣብ እየመላለሰ በማባባስ፣ የመመለስ ናፍቆቱ በጣም ስለአየለበት፣ ሌላው ቀርቶ ሃሣቡን የማይለውጥ ተቃዋሚንም ቢሆን ለማሣመን በውስጡ ሃይል ተሰማው።

ንጉሡ ሁልጊዜም ጉልላት ባለው የቤተመንግስቱ ክፍል ውስጥ አይቀበሏቸውም። ብዙ ጊዜ ዲሚጥሮስ ይመጣና ንጉሠ ነገስቱ በአንድ ደን ዳርቻ ነብርና አንበሣ ለማሣደድ ቀን ቀን በሚያርፉበት የአደን ድንኳናቸው ድረስ ይወስዳቸዋል።

አሁን አሁን በተሰመዱ ጉዳዮች ላይ ማውራት ጀምረዋል። ይሁን እንጅ፣ ንጉሡ የክብራቸውን ደረጃና ተፈጥሮአዊ ግርማ ሞገሣቸውን ፈፅሞ ዝቅ አላደረጉላቸውም። በዚያን ዕለት ማታ ለክብራቸው ክባለስልጠኖቻቸው ጋር የእራት ግብዣ አደረጉላቸው። ሶስቱም ሰዎች በእንጀራው ላይ ወደ ፈሠሠው ወጥ እጃቸውን እየሰደዱ ያጠቅሣሉ። ዲሚጥሮስ፣ ዜኖችን ለሚገዛው ሀግ ተገዥ ነው። ስለቀጣዩ ዘመቻና ስለንጉሡ መሄድ ተወያዩ። ምግቡ ካበቃ በኋላ አንድ ወታደር በጣሣ ውሃና ገበቴ አቅርቦ ጣቶቻቸውን ታጠቡበት።

«ግርማዊ ሆይ» አለ ጆን ባፕቲስት ብቻቸውን ሲሆኑ «አሁን ስለንዞዎ ተነጋገርን። ነገር ግን ስለኛ ደግሞ እንድናገር ይፍቀዱልኝ»

ቃላቱ አሻሚ ናቸው። የንጉሠ ነገስቱ ዓይኖች ሲያርፉበት፣ በተመግሣይ አቅጣጫ ስለመዓዛቸው ፖንሴ እንዳልተናገረ ገባው።

«ግርማዊነትዎ ጠርተውን መነኮተናል። እኛም በአቅማችን ልክ መስራት የሚገባንን ፈፅመናል። ከመጀመሪያው ጀምሮ ሃጅ ዓሊን ከሃሣባችን ውጭ አድርገነው ነበር። አሁን ግን ወደመጣንበት አገር የመመለሻ ጊዜአችን ነው።»

አንድ አገልጋይ በትናንሽ ስኒዎች ቡና አመጣ። ንጉሡ ለእንግዶቻቸው በራሣቸው እጅ አቀረቡ። አቢሲኒያውያን «ጤና አዳም» ከሚሉት ውብ መዐዛ ካለው ተክል ላይ ጥቂት ቅጠሎችን እየበጠሱ ወደ ቡናቸው ውስጥ እየጨመሩ ሰመናገር ጊዜ ወሠዱ።

«በጣም የሚገርም ነው። እዚህ ኗሪ የምትሆነብትን ሁኔታ ዛሬ ማታ ላዋያችሁ ነበር። ለዘመናት ያሰን አስገዳጅ ሕግ በጣም ጥብቅ ነው። እንግዶች ሁል ጊዜም እንኳን ደህና መጣችሁ ቢባሉም፣ አገራችን ውስጥ መቆየት ይኖርባቸዋል። ችግሩን ታውቁታላችሁ። ከዚህ ስንስርዓታችን ለቀን በወጣን ጊዜ ሁሉ ሲከተለን የነበረውን አሣዛኝ ጉዳይም ሳይቀር ታውቁታላችሁ። እኔም ሕጉን ለመጠበቅ አስባለሁ።»

ፖንሴ ወደ ዓደኛው ዞር ብሎ፣ ቀጥሎ ምን ሊገጥም እንደሚችል እያሰበ ሲመለክት፣ በፕሮቴስታንቱ አይኖች ውስጥ አለምንም የሚል ስሜት አነበበ።

«በቁጥጥር ስር ላደርጋችሁ ሃሣቡ የለኝም። ወይም ደግሞ በጣም ሊያስቸግራችሁ የሚችለውንና እኔም የምረዳውን ተገልሎ የመኖር ሕይወት ኑሩ አልልም። ስለዚህ ሃሣቤ በይፋ ሹመት ሰጥቻችሁ፣ ቤተመንግስቱም እንዲያፀድቀው አድርጌ፣ እኔ የምገምተውን የናንተን ከፍ ያለ ዋጋ ልከፍል የሚችል ዳረጐት እየተሰጣችሁ እንድትኖሩ ነው።» ሲሉ ንጉሡ ተናገሩ።

«ግርማዊ ሆይ» አለ ፖንሴ፣ ደስ በሚል ወዳጃዊ ቁርጠኛ አገላለፅ፣ «በበኩሌ እዝናለሁ። ልንቀበልም አንችልም። ከመጀመሪያ ጀምሮ ወደ ካይሮ መመለስ እንዳለብን ነግረንዎታል።

«እውነት ነው» አሉ ንጉሠ ነገስቱ «ይህንንስ ነግራችሁኖል። የካይሮ ፓሻም በአወዳሽ ደብዳቤው ውስጥ ይህንኑ ገልጿል። ያ አንድ ነገር ነው። የገለፅከላችሁን ሥነስርዓት ለመጣስ ምናልባት ይህ አንድና ብቸኛው ሁኔታ ይሆናል። የካይሮውን ፓሻ እንደ ጠላቴ ነው የምቆጥረው። በሌላ በኩል እኛ ስራ አብረናቸው ከምንሰራቸውም ጋር ጠላት ነው። እኔ በአባይ ላይ ባለኝ ሃይል ምክንያት ይፈራኛል። እኔ ደግሞ እነርሱን የምፈልግበት ጉዳይ አለኝ። እዚህ ያሉት ጳጳስ ሲሞቱ፣ አዲስ ፖትርያርክ እንዲሳክልን ይፈቅዳል። በባህላችን የኛን ቋንቋ የሚይናገር፣ እዚህ ከመምጣቱ በፊት ግብፅ ውስጥ ከሚገኘው ገዳሙ ወጥቶ የማያውቅ መነኩሴ፣ እዚህ እኔ ፊት እየተንቀጠቀጠ በመቆም የቤተክርስቲያናችን የበላይ መሆን

ከመቸውም ጊዜ በበለጠ አሁን በጣም ጠቃሚ ነው። ስለዚህ ለግብፅ ፓሻ በገባሁስት ቃል መሠረት እንድትሄዱ ልፈቅድላችሁ እችላለሁ።»

« ለግርማዊነትዎ እጅግ ትልቅ ውለታ አለብን።»

«እኔም እንድ ተመሣሣይ ጥያቄ እንዳቀርብላችሁ ፍቀዱልኝ» አሉ ንጉሡ

ፖንሴ ጭንቀላቱን ዝቅ አደረገ። የበላይ ገዝው ፍላጮታቸውን በሃይል ለመጫን ባይፈልጉም አግባብተው ሊያቆዩዋቸው የመሞከር ጥረታቸውን ግን አልተዉትም።

«ምንም አይነት ፍቅር ሊነፍጋችሁ ከማይችለው ከአንድ ክርስቲያናዊ ልውል ይልቅ ይህን አንዳችም ምስጋና ምን ጊዜም አሣይታችሁ ለማያውቀው ለዚህ ቱርካዊ ለማገልገል ለምን መረጣችሁ?»

«ግርማዊ ሆይ የምንመለሰው ለካይሮው ፓሻ ስንል አይደለም» አለ ፖንሴ።

«ታዲያ ለምንድነው?»

ወጣቱ ሄኪም ወዲያውኑ አለበ። እንግዲህ ተቃርበናል። ቡናውን ፉት አለና ቀጠለ።

«እንደሚያውቁት ሜትር ዣረሚና እኔ ሽሪኮች ነን። አሉ እኔን ይከተሰኛል። እርግጡን ግን ወደቤት መሄድ የምፈልገው እኔ ነኝ።

«እንግዲያው ደህና፣ እኔም ጥያቄውን ያቀረብኩት ሳንተ ለጆን ባፕቲስት ነው» አሉ ንጉሡ

«ይኸውልዎ ግርማዊ ሆይ፣ ከአንዲት ወጣት ሴት ጋር ፍቅር ይዞኛል» አለ ፖንሴ።

ንጉሡ ሣቁ። እንዲህ ሲስቁ ሲያዩ የመጀመሪያቸው ነበር። ድምፅ አውጥተው በጣም ሲስቁ፣ ጭንቅላታቸውን ወደ ኋላ ጣል አድርገው ነው። ጭውውቱ እንደገና እንዲቀጥል ዲሚፕሮስ በአክብሮት ጠበቀ።

«ደህና» አሉ ከሁሉም የበላይ የሆኑት ንጉስ። «በኔ ቤተመንግስት ውስጥ ሙሉ በሙሉ በወርቅ በተሸፈነ መኖሪያ ቤት ለመኖር እጅግ እንደምትደሰት አስባለሁ። እንደሠማሁት ካይሮ

በጣም ይሞቃል። ሴቶች ደግሞ የኛን ያየር ጠባይ ይመርጣሉ። ሚስትህ ጉንደር መጥታ አብራህ እንድትኖር አድርግ»

«ሚስቴ አይደለችም።» አለ ጆን ባፕቲስት

«አዚሁ ልታገባት ትችላለህ»

«እውነቱን ለመናገር፣ ግርማዊ ሆይ . . . እዚህ ደረጃም ላይ ገና አልደረስንም።»

ንጉሡ፣ ያን አስደናቂ አሣሣቃቸውን እንደገና ሣቁ።

«ታዲያ ምን ደረጃ ላይ ነው የደረስኸው?»

«ግርማዊ ሆይ፣ ይህች ወጣት የማህበረሰብ ደረጃዋ ከኔ እጅግ ከፍ ያለ ነው። አባቷ፣ በመንግስታችን ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ አላቸው፣ እኔና እርስዋ እንፋቀራለን»

ይህን እንደተናገረ ምናልባት ዕድሉን ሊሞክር እንዳሰበ መስሎት ጆን ባፕቲስት ለአጭር ጊዜ መጥፎ ስሜት ተሠማው። በአፍቃሪ ላይ በሚነገር አጉል እምነት የተነሣ፣ በዚህ በተለየ ነጥብ ላይ ስለ ዕጣ ፈንታ ከሌላው ሁሉ ነገር በበለጠ ፈራ።

«አሁንም ቢሆን ቤተሰቦችዋን ማላመን መቻል ይኖርብኛል። ይህ ደግሞ ቀላል የሚሆን አይደለም።»

«እንግዲያው በአንድ ታላቅ ንጉስ አጠገብ እንደምትኖርና አንተም ከከፍተኛ መኮንኖቹ አንዱ እንደምትሆን ንገራቸው።»

«አቤት! ግርማዊ ሆይ፣ እርስም ሰዎችን በተሻለ ያውቋቸዋል። ሰዎች አርቀው አያዩም። ምንም ነገር ይሁን በቀጥታ በአይናቸው ስር ካልሆነ የለም የሚሉ ናቸው። ለግርማዊነትም የማገልገል ሹመት፣ የብዙ ማዕረጉች ክብረት እንዳለውና የታላላቅ ቤተሰቦቻችንን ልጆች በኩራት እንደሚሞላቸው በሚገባና ሙሉ በሙሉ አውቃለሁ። ነገር ግን ያፈቀርኳትን ልጅ አባት ለማሣመን ይህ በቂ አይሆንም»

ዲሚጥሮስ ተርጉሞ እስኪጨርስ ለጥቂት ጊዜ አቋረጠ። ከዚያም ድምፁን ከፍ አድርጉና እያንዳንዱ ሃሣብ በአምሮው ውስጥ እንዳመጣለት አስቦ እንዲነግረው ሞንቅላቱን ግራና ቀኝ በማወዛወዝ ቀጠሰ።

«ግርማዊነትም እኔን ለመርዳት የሚቻለውን ሁሉ እያደረገልኝ መሆኑ ይታየኛል። ለዚህም ባለውለታ ነኝ። እንደ እውነቱ ሌላም ነገር አለ . . .»

«ምንድን ነው? ተናገረው»

«ብናገረው ድፍረት ይሆንብኛል። ምክንያቱም አስተሣሰቦቼ እርስዎ አጥብቀው ከሚይዙት የፀና እምነትዎ ጋር በተቃራኒው የሚሄድ ነው»

«ቀጥል፣ ተናገር። የምከለክልህ ከሆነ፣ ቢያንስ ከሁለት አንዳችን፣ መሞከር ሲገባን ያላደረግነው አለን ብለን እንፀፀታለን።»

«እንግዲያው እንዲህ ነው» አለ ጆን ባፐቲስት በመጨረሻ። ልክ አንድ ሠው ሞነቱን ከትከሻው ላይ አነቃንቆ እንደሚጥለው አይነት ቃላቱ በጥድፊያ ይወጡ ጀመር። «የፍቅረኛዬ አባት ዲፕሎማት ናቸው። ለርሣቸው ደረጃ ተመሣሣይ በሆነ ማህበረሰባዊ ቦታ ለመድረስ ብችል በደስታ ይቀበሉኛል። እኩል መሆኔንም ያረጋግጣሉ። ወይም የተመሣሣይ አለም አባል መሆኔን ይቀበላሉ። ይህ ሊሆን የሚችለው ግርማዊነትም እኔ በአቢሲኒያ የፈረንሣይ ንጉስ፣ የግርማዊ ሉዊስ አስራ አራተኛ፣ ቋሚ አምባሣደር፣ እንድሆን እርስዎ ሃሣብ ቢያቀርቡ ነው። ከዚያ በኋላ ወደዚህ ልመለስና የደረጃዬን አንፀባራቂነት ለማፈቅራት ሌት አረጋግጣለታለሁ። ግርማዊነትም በዙፋንም አጠገብ የሚሰጡኝን ደረጃ የፍቅረኛዬ አባት ሊረዱት የሚችሉት ካልሆነ ዝቅ አድርገው ይንሙቱታል ብዬ አፈራለሁ»

«ኤምባሲ ነው?» አሉ ንጉሡ

በዚያን ቅፅበት፣ በንጉሣዊ ድንኳን ስር የገባው ድንገተኛ ነፋስ፣ የአሸዋ አውሎ ነፋስ ከወለል ላይ በማስነሣቱ ውይይቱ ቆም አለ።

«አየህ፣ ይህ የኛ ባህል አይደለም» አሉ የሁሉም የበላይ «ለጉብኝቶቻችን መንገር የሚገባን ጉዳይ ካለ በተቻለ መጠን በነጋዴዎች፣ ቅዱሣን ቦታዎችን ለመሣለም በሚጓዙ

ሰዎችና አንዳንዴም በለማኞች ሣይቀር በቀጥታ መልዕክቶቻችንን እንልካለን። የየመንግስታቸው ይፋ ባለስልጣናች ተደርገው ሰዎች ሊላኩልን፣ ሰሞሌ በቀድሞ ጊዜ ከፖርቹጋል እንደተላኩት አይነት እብሪታቸው ደማችንን ያፈላውና አገራችንን ለቅቀው ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ አንፈቅድላቸውም ነበር»

«አውቃለሁ» አለ ፖንሴ

ንጉሡ በጠረጴዛቸው ዙሪያ እጃቸውን በሹካው የድንኳን ጨርቅ ላይ ምንም እንደማያስብ ወይም እንደማያዳምጥ ሰው አሣርፈው ወዲያና ወዲህ አሉ።

«ከዚህም በተጨማሪ፣ አናንተ ጀስዊቶች የምትሏቸው ካህናትና ሌሎችም እንዲሁ አሉ። የአረቦችን ልብስ እየለበሱ በድንበሮቻችን አካባቢ በማንገዋበብ፣ ወደ አገራችን ለመግባት አመቺ የሚሆናቸውን አነስተኛ ሰበብ ሁሉ አፈፍ ያደርጋሉ። ሕፃን እያለሁ፣ ልክ እኔ፣ አንተ እንድትመጣልኝ እንደላክሁት፣ አባቴም፣ ከካይሮ ሃኪም እንዲመጣለት ላክ። ሁለት መነኩሣት መጡ። ጥቂት ቢጠራጠርም፣ በወዳጃዊ ሁኔታ ተቀብሎ አስተናገዳቸውና ሐኪሙ ማንኛቸው እንደሆነ ጠየቃቸው። ዶክተሩ ከነሱ ጋር ጉዞ ሊጀምር እንዳልቻለና እነርሱ ግን ቀድመው መምጣታቸውን በጥሞና ተናገሩ።

«እና ምን ሆኑ?» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቀ

«የፈረንሣይ ካህናት ተመልሰው መምጣታቸውን ህዝቡ ሲሰማ፣ መሠብሠብ ጀመረ። የኛ ካህናትና መሣፍንት ደግሞ፣ ከዚህ በፊት እንዳጋጠመን መጥፎ ዕድል፣ ንጉሡ ሃይማኖቱን ይለውጥ ይሆናል በሚል ፍርሃት፣ በተገለለ ቦታ አስቀመጡት። በማንኛውም ሰዓት የርስበርስ ጦርነት ሊፈነዳ የሚያስጋ ነገር ነበር። ንጉሡ አባቴ፣ ፈፅሞ አላመነታም። ሁሉቱንም እንግዶች በቁጣ ለወጣው ሕዝብ አሣልፎ ሰጣቸውና በቤተመንግስቱ ፊት ሰፊት በድንጋይ ተወግረው ሞቱ። ይህን ያነሣሁልህ፣ እኛ ባንፈልጋቸውም እንኳ እዚህች አገር ለመግባት ምንም ነገር እንዲያቆማቸው የማይፈልጉ አክራሪዎችን ኤምባሲው ከመነሻው ይዞ ቢመጣ የሚል ስጋት መኖሩን ልገልፅልህ ነው።»

«ትክክል ነው» አለ ጀን ባፕቲስት፣ እንደተከዘ ቆይቶ። ወዲያውኑ የመጣለትን ሃሣብ ስመናገር እንደከደለ ሆኖ ቀጠለ። «ግርማዊነትዎ በሚገባ የሚያውቁትን፣ ስካናቱ ያለምትን ጥላቻ የሚያውቅና እነርሱን ወደዚህች አገር ፊፅሞ ላለማምጣት ቃል የሚገባልዎትን እምባሣደር ይሹመ። ይህ አሠራር ጉዳዩን ሁሉ ፍፁም በአዲስና ጠንካራ መሠረት ላይ ይጀምረዋል። እኔ እንደማስበው፣ ግርማዊነትም በእውነት የሚያስፈራም እምብዛም ነው። በተቃራኒው ግን፣ በአገርዎ ያለውን ሁኔታ ከሚያውቁት የፈረንሣይ ንጉስ መልዕክተኛ መቀበል፣ ጉን ለጉንም የጀስዊቶችን የብልጣብልጥ እንቅስቃሴ ማወቅዎና ቀሣውስቱ የሚፈፅሙትን የመጀመሪያ አዲስ የዘመቻ እንቅስቃሴ ምልክት ለሁሉም የበላይ ንጥላችን ሪፖርት እንዲያደርጉ ይረዳዎታል። ንጉሰ ነገስት ሉዊስ አሰራ አራተኛ፣ ከጳጳሱ ጋር ከፍተኛ ግቡቡነት ስላላቸው የሃይማኖታቸው ማህበር ያለውን ከፍተኛ ጉጉት እንዲገታው ሊጠይቋቸው ይችላሉ። ብዙ ነገሮች የሚሆኑት እርስዎና አገርዎ በኛ አገር በሚገባ ለመታወቃችሁ ነው። ፕሮፖጋንዳ በማይምነት ውስጥ ስር ይሰድዳል። ግልፅ በመሆኔ ይቅር ይበሉኝ። ስናገረው ያሳፍረኛል እንጅ፣ ጀስዊቶች፣ ይህች አገር በማይምነትና በጭካኔ የተሞላች የአረማውያን ምሣሌ ነች አያሉ መናገር ችለዋል። ይህ ደግሞ፣ የእምነትን ብርሃን እንዲያስገቡ ለማስቻል ለነርሱ ክብርና ዝና ይሠጣቸውና ባለውለታ ያደርጋቸዋል። እኔ ያለውን እውነተኛ ሁኔታ ለንጉሣችን በትክክል ማስረዳት ብችል እርሣቸው ይረዱኛል። በሁለቱም አቅጣጫ ልረዳዎት እችላለሁ። በጋራ መከባበር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ባላቸው፣ አንዱ በምዕራብ ሌላው በምስራቅ በሚገኙ ሁለት የክርስቲያን ንጉሦች መካከል እንዲናር ልረዳዎት እችላለሁ። ይህ አካሄድ የንጉሠ ነገስት ግዛትዎን ሰላም በማናጋት ስልጣንና ዘለዓለማዊውን ነፍስ ለመንጠቅ የሚጥሩትን የሰርጉዝቦችን ምንጭ ከመነሻው ይገድበዋል።»

ቀስ በቀስ እያደገና እየጋለ፣ ሌሎችን ሊያሄስ የቆየበት ረዥምና ቁጣ የተሞላበት ንግግሩ ሊያበቃ፣ ድንገተኛ የሆነ መደነቅና የመውደድ ስሜት ስላሳደረበት፣ ጀን ባፕቲስት ዓይናቹን በንጉሡ ላይ ተከለ። ንጉሡ መንቀሣቀስ የማይችሉ መስለው ለረዥም ጊዜ ቆዩ። ከዚያም ዘበኛውን ጠሩት። በአንድ እጁ አለንጋ፣ በቀበቶው ላይ ጉራዴ የታጠቀ ረዥምና በጣም ቀጭን ወጣት መጣ።

«ፈጥነህ ሰው ወደ ከተማ ላክ። ሙራድ አዚህ እንዲመጣ አድርግ» አሉት።

14

ሰው ምንም ያህል ዋሾ ቢሆን፣ ሴባም ቢሆን፣ ቃሉን የማይጠብቅና ከሃዲም ቢሆን እንኳ፣ እድሜውን በሰላም ስመጨረስና ለተባረከ ረዥም ዘመን የሚበቃው ጠንካራ እምነት ሲኖረው ብቻ ነው። ቅንጣት ታህል እምነት ያለው፣ የዕምነት ዕናቱ ፍፁም የሆነ፣ በሆነ ባልሆነው ጉዳይ ዕምነቱ የማይዛባበት ሰው፣ ከክፉ ነገር ሁሉ ይጠበቃል። ሙራድ እንዲያ ያለ ሰው ነው። ይህ አርመናዊ፣ በክውካሰስ ሕዝቦች ላይ ብቻ የሚታየውን ዓይነት የማይገመት ዕድሜ ኖሯል። የካውካሰስ ሕዝቦች በሂሳብ ጉብዞች ቢሆኑም፣ የዕድሜ ጉዳይ ሲነሣ ስለሚጸጽ ይምታታባቸውና ፣ የታላላቆቻቸውን ዘመን እንኳ መናገር ያቅታቸዋል። የሙራድ ረዥም እድሜ በሁለት ክፍሎች ብቻ ሊከፈል ይችላል። የመጀመሪያው የልጅነት ጊዜው ነው። በቫን ሐይቅ አጠገብ በምትገኝ መንደር ውስጥ የሕፃንነት ዘመኑን ያሣለፈው ሙራድ፣ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ከነጋዴ አባቱ ጋር ነው። ከአስራ አምስት አመቱ ጀምሮ፣ ባልተቋረጠና ባልተናጋ አራት የአቢሲኒያ ነገስታት ዘመን አገልግሏል። የኢትዮጵያን የቅርብ ጊዜ ታሪክ በሙሉ በዓይኑ ያየ ሰው ነው። የጀስዊቶችን ተልዕኮ፣ ከአገር መባረራቸውን፣ ከዚያም የተከተለውን የስርዓት አልበኝነት ጊዜ፣ የፋሲለደስ ወደስልጣን ዳግም መመለስና መንግስት መቆጣጠር፣ የልጅ ልጁ እያሱ ያከናወናቸውን ሁሉ አይቷል። ቋንቋዎችን በማወቁ፣ በዲፕሎማሲ ጥበቡ፣ ሰዎችን ፈጥኖ በመፈረጅ ችሎታው፣ በተለይም ወደሀገድና ባሊ ወደሚገኘው የደች ተጠሪ፣ የነገስታቱ ተመራጭ የመንግስት መልዕክተኛ እንዲሆን አድርጦታል። ለረዥም ጊዜ በቆየው ዝናው ሳቢያ፣ አሁን በቅርቡ ከተመለሰበት ተልዕኮ ባታቢያውያን ስለአድናቆታቸው የሰጡትን ብዙ የነሐስ ደወል ይዞ መጥቷል።

ጀን ባፕቲስት፣ ጉንደር ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ሙራድን ብዙ ጊዜ አግኝቶታል። በመጀመሪያ እንደተገናኙ ሙራድን ዕድሜው መከላከያ ያልሆነለትን ሕመም አክሞለታል። ነገር ግን በዕድሜው ምክንያት እንኳ ሊደክም ባልቻለው የፍትወት ብርታቱ ይህ ሕመም እርሱ እንዳለው «ለሃያ አራትኛ ጊዜ» ይዞታል። የፖንሴ ሕክምና ውጤታማ ነበር። ሽማግሌው፣ ሃያ አምስተኛውን የመለከፍ ዕጣ ለመቀበል፣ ከዕለታት አንድ ምሽት ላይ አንዲት ያለተዳረች ውብ ድንግል ወጣት ሴት አስከትሎ ሲንቀሳቀስ ድንገተኛ በሆነ የአንጉል ውስጥ ደም መፍሰስ ግማሽ ሰውነቱን በድን አደረገበት። ጀን ባፕቲስት ላደረገለት እንክብካቤና ጥንቃቄ ምስጋና ይግባውና የተጉዳው ጉኑ ቀስ በቀስ ወደ ሕይወት ተመለሰለት። ሆኖም ግን፣ አንዱ እጁ አሁንም

ሊሰንፍበት ከንፈሮቹም የወደቁ ናቸው። አዕምሮው ግን ጉዳት አላገኘውም። ንጉሡ የራሣቸውን አስተያየት ሁልጊዜም ያለአድልም በማድነቅ በሚመለከተው ሰው ሃሣብ ላይ መጨመራቸው ውጣቱን ሃኪም ፖንሴን እፎይ አሰኘው።

ሽማግሌው ከአንድ ሰዓት ቆይታ በኋላ ደረሠ። ሲያዩት እንቅልፉን ሳይጨርስ አስቀድሞ እንደተነሣ ሰው ቅር መሠኘትና የመበሳጨት መልክ ይታይበታል። ሙራድ ትንሽ እንደሚተኛና ለዚያውም ጥሩ እንቅልፍ እንደማይወስደው፣ አለመደሰቱን የሚያሣየው መቃጣትም ለማስመሰል እንደሆነ ጆን ባፕቲስት አውቋል። ይህ ገፅታው፣ ገና ምክክር በሚደረግበት ጉዳይ ላይ የሽማግሌውን ዕርካታ የሚደብቅለት ዘዴ ነው። ሽማግሌው፣ አታላይ ነጋዴ ስለሆነ፣ ይህ የቅሬታና የብስጭት መልክ ለድካሙ፣ ለጥረቱና ለሚከፍለው መስዋዕትነት የሚጠይቀውን ዋጋና የሚጠብቀውን ማካካሻ ከፍ ያደርግለታል።

ሙራድ እንደመጣ፣ ንጉሡ፣ የጆን ባፕቲስትን የኤምባሲ ስራ ሙሉ በሙሉና በቀላሉ እንዲገነዘበው አደረጉ። በርግጥ የፍቅርን ጉዳይ አላነሱም። ይህን አስቸኳይ ጉዳይ ለመቀበልና ለመፈፀም ያለውን ዝግጁነትም ጠየቁት።

ሽማግሌው፣ በክፈል የንጉሠ ነገስቱ የአደን እቃ በሆነውና አንፀባራቂ ሱል ኩተስበጠ ወንበር ላይ ተቀምጦ አዳመጠ። አቀማመጡ በጉን ሆኖ፣ ክርኑ ላይ ተደግፎ፣ አይኖቹን በክፈል ጨፍኖ ነበር። በዚህ ጊዜ ከታችኛው ቅንድቡ በስተጀርባ ባሉት የነጡ አይኖቹ አጮልቆ ሲመለከት፣ በራሱና በንጉሡ መካከል ልዩ ንቃት ኖሯቸው፣ ወደ ኋላና ወደፊት እንዲንከባለሉ እያደረገ መሆኑን ጆን ባፕቲስት ተሰማው። ውጣቱ ሰው ግን፣ ንጉሡ እየገለፁት ያሉት ጉዳይ አንዳችም ማስመሠል የሌለበት እጅግ ከፍተኛና ጠቃሚ ጉዳያቸው መሆኑን ለመግለፅ ተቁነጠነጠ። የንጉሡ ንግግር ቀዝቀዝ እያለ ሲመጣ፣ ሙራድ በተቆራረጠ የሕመም ስሜት ድምፅ ተናገረ።

«ግርማዊ ሆይ! ይህ ድንቅ ሃሣብ ነው። ነገር ግን ሄሮደቱስ እንደተናገረው የማሰንቆ መምቻ እንደተጠቃሚው ነው። ሊያስፈልግ የመቂቃ መሣሪያ ይሆናል። አለበለዚያ የጦር መሣሪያ ይሆናል። በተመሣሣይ መልክ ይህ እጅግ ታላቅ የሆነ አዲስና አስቸጋሪ እቅድም በአተገባበሩ ላይ ተመስርቶ በጭራሽ የተለየ ውጤት ያስገኝ ይሆናል።»

ይህ የሙራድ የተለመደ የአነጋገር ስልት ነው። አንድ ጠረኛ ሊመታው የሚፈልገውን ሰው፣ ከጋሻው በስተጀርባ ራሱን ደብቆ እንደሚቀርብ ሁሉ፣ ሙራድም እውነት ይሁን የፈጠራ

የግሪክ ፈላስፎችን ምሣሌ እንደሸፋን ሳይጠቅስ የራሱን አስተያየት ጨርሶ ስጥቶ አያውቅም። ንጉሱ ቀሪውን ለመስማት ጠበቁ።

«በመጀመሪያ» አለ ሙራድ፣ ፍፁም በደከመ አኳኋን፣ «ግርማዊነትዎ በፅሁፍ አንዳችም ነገር ማስፈር የለብዎትም። በምዕራባውያን ዋና ከተማና በዚህ መካከል ያለው መንገድ ረዥም ነው። ደብዳቤዎ ባልሆነ ሰው እጅ ወድቆ ያለአግባብ ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ዕድልም በጣም ሰፊ ነው። ሌላው ቀርቶ እዚሁ አገር ውስጥ፣ እርስዎ ከፈረንሣይ ንጉስ ጋር ኤምባሲ መጠየቅዎን ቀሣውስቱ ቢያውቁ፣ ሊፈጥሩ የሚችሉት ትልቅ ችግር ይኖራል። ወይም ደግሞ በጉዞው ላይ ደብዳቤው ቢጠፋና በማይገባው ሰው እጅ ቢወድቅ፣ ቱርኮች በርስዎ ሃሣብ ላይ መጠንቀቅ ይጀምራሉ። ሰር ፖንሴም፣ ርስዎ ፈላጭ ቆራጮ የሆኑበት ፍጡርዎ ተደርጉ ይገለፃል። በመጨረሻም መታሰብ ያለበት የፈረንሣይ ቤተመንግስት አለ። ጀስዊቶችን፣ ብልጣብልጥ ክርክራቸውን፣ አንድን ሰው እውነት ያልሆነውን ነገር እውነት ነው ብሎ እንዲቀበል የማድረግ ችሎታቸውን፣ ቅንነት የጐደለውንና ሽፍጥ የተሞላውን አስተሣሰባቸውንም እርስዎም ያውቃሉ። በርስዎ ግምት ፍፁም ጉዳት የላትም የምትባል አንዲት ቃል፣ በነርሱ ተጠምዝዛ የነርሱን መገኘት የምትጠይቅ ሊያደርጓት ይችላሉ። ወይም ደግሞ ለርሶ የታማኝነት መግለጫ ያደርጓታል። ወይም ማንኛውንም እነርሱ የሚፈልጉትን ያደርጉታል። በአጭሩ አንዳችም ነገር በፅሁፍ አያስቀምጡ»

«እንግዲያው እንዴት መቀጠል እችላለሁ?» ሲሉ ይህን ሁሉ ቆመው ሲሰሙ የነበሩት ንጉሱ እጃቸውን ወገባቸው ላይ ወደኋላ አሣርፈው ጠየቁ።

«አባትዎና አያትዎ እንዳደረጉት፣ እርስዎ ራስዎም ብዙ ጊዜ ሲያደርጉ እንደነበረው»

«ሰር ፖንሴን እጅዎ የሚሄድልኝ መልዕክተኛ» አሉ የሁሉም የበላይ። «አንተ ያልከውን ዘዴ ለመከተል ፈልጌአለሁ። ግን ማን ይሁን? አንተው ሙራድ?»

«ግርማዊነትዎ ይህን የሚጠይቀኝ ስደንቡ ቢሆንም፣ ይህ ለእኔ ታላቅ ክብር ስለሆነ አመሰግንዎታለሁ። ግን እንደሚያውቁት ሞት በከፈል መትቶኛል። ትዕግስት ስለነበረኝ ሞትን አጐንብሼ አሣለፍኩትና አመሰጥኩት። ሆኖም ግን በድጋሚ የሚመታኝ ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን አስባለሁ። ይህም ለመጨረሻ ጊዜ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ።»

«እንግዲያው ማን ይሁን?» ሲሉ ንጉሡ ጠየቁ። «ሃጅ አሊ ንቃቱንና ጠንቃቃነቱ በመሃመዳውያን መካከል ነው። እንዲህ ያለውን ተልዕኮ መወጣት አይችልም»

ከተገቢው በላይ የንዘብ ዋጋ ከሚጠይቀው ከሀጅ አሊ ጋር ተመልሶ እንደማይገዝ ሲያውቅ፣ ፖንሴ እፎይታ አገኘ። ዞር ብሎ ሜትር ዝረሚን ተመለከተው። ከድንኳኑ በስተኋላ በፀጥታ ከተቀመጠበት ሆኖ አጠገቡ እንዲመጣ ጆን ባፕቲስት ጠራው።

«ማይሌ ወጣት አቢሲኒያውያን መሣፍንቶችን እንደሚፈልግ ሪሣህ እንዴ?» አለ ፕሮቴስታንቱ ዝቅ ባለ ድምፅ።

«ለዚህ የሚሆን ቅንጣት ዕድል እንኳ የለም። ቢሆንም እጠይቃለሁ።»

ጆን ባፕቲስት ወደ ንጉሡ አጠገብ ተመለሰ

«ከጨዋ ቤተሰብ የሆኑ ብዙ ወጣት ኢትዮጵያውያን ቢካተቱ ግርማዊነትዎ ምን ይላሉ። እነዚህ ወጣቶች ከጉዞው ብዙ ነገር ሊጠቀሙ፣ ፊረንሣይ ውስጥ ሲማሩ፣ ቋንቋችንንም እንዲሁ ተምረው የርስዎንም ቋንቋ ለኛ ሆነው ሊያስተምሩ ይችላሉ።»

«አብደሃል እንዴ» አሉ እያሱ «በጉረቤቶቻችን ሣይገደል ይህችን አገር ለቅቆ መሄድ የሚችል አቢሲኒያዊ ክርስቲያን የለም። ደግሞም ጉዳዩ በምስጢር የሚያዝ መሆኑን አትርሣ»

አርሱም ልሞክር ብሎ ያቀረበው ጥያቄ ነበርና ይህን ክርክር ፖንሴ በቅፅበት ተቀበለው።

እንደገና በዝምታ ሣሣብ ውስጥ ለጥቂት ጊዜ ቆዩ።

«ዲሚጥሮስ?» አሉ ንጉሡ በፍጥነት፣ አስተርጓሚያቸውን ተመልክተው

«የለም፣ የለም፣ እርሱ እዚህ እጅግ ጠቃሚ ሰው ነው» ሊል ሙራድ ተቃወመ።

መልሱን ትንሽ በትንሽ በፍጥነት ቢለቅቀውም የድካም መንፈስ እንዳለበት ይታወቃል። ሽማግሌው ሰውዬ ዕፆ አድርጉ ሊያቀርበው የፈለገው ሰው እንዳለውና፣ ንጉሰ ነገስቱንም ቀስ በቀስ ወደዚያው ሊያመላክታቸው እንዳሰበ ጆን ባፕቲስት ተረዳ።

የሁለት ወይም የሦስት ሰዎች ስም እንዲጠቀስ፣ ሙራድ ጊዜ ሰጠ። ይሁንና የተጠሩት ሁሉ ወዲያውኑ ተሰረዙ። በመጨረሻም ሆነ ተብሎ ፀጥ ከተባለ በኋላ፣ አርመናዊው እንደማፈር ብሎ ጉሮሮውን አጠራ።

«መቼም ሁል ጊዜም የእህታችን ልጅ አለ . . .?

«ምን አይነት የእህት ልጅ ነው የምትለው? እህትህ ብዙ ልጆች እንዳሏት አውቃለሁ። ሁሉም ሌቶች ይመስሉኛል»

«ወንድ ልጅም አላት። እንደኔው ስሙ ሙራድ ነው። ይህ ብዙም እንደማይስማማ ይገባኛል። ምንም እንኳ አርባ አመት ቢሆነውም እርስዎን ደስ ካለዎት፣ ሙራድ ወጣቱ ብለን እንጠራዋለን። ያደገው አሌፖ ውስጥ ነው። ግርማዊነትዎ ምናልባት ያውቁ እንደሆነ፣ ዋርሣዬ

በዚያ አገር ለጥቂት ጊዜ ሲነግድ ነበር። የርሱ ሚስት፣ የእኔ እህት፣ ከአስራ አምስት አመት በፊት ወደዚህ ተመለሰች። ከባሏ ጋር በጭራሽ ልትስማማ ስላልቻለች ነው። በዘላኖችን መሠረት አባትዬው ልጁን ከራሱ ጋር አቆየው። ወይ ጉድ! ልጁ ካለው ድንቅ ችሎታ ሌላ ለመናገር ፈልጌ አይደለም። ግርማዊነትም ሣሣቡን የሚተበሱኝ ከሆነ ልጁ ምግብ አዘጋጅ ሆነ።»

«እና ታላቁን ንጉሰ እንዲጠይቅ የምትልከው ይህን ሙራድ ነው?»

«ግርማዊነትዎም በሚገባ እንደሚያውቁው፣ ተመራጭ መልዕክተኞች ትሁቶች ናቸው። ምክንያቱም ማንም ሳያስተውላቸው ያልፋሉ። በርግጥ በጣም የሚያስፈልገው ፈጣን አሣቢ መሆንን ነው። ዋርሣዬ ደግሞ በምንም መልኩ ዘገምተኛ አይደለም። እንደሚታወቀው ዓይነት ተራ ምግብ አዘጋጅ አይደለም። ለአንድ ታላቅ ክርስቲያን ነጋዴም አገልግሏል። ጥቂት ቋንቋዎችን ተምሯል። ከነዚህ መካከል የፈረንሣይኛን መሠረተዊ ነገሮች ማወቁን አምናለሁ። ባለፈው ዓመት ተመልሶ ሊመጣ በጣም ተሻሽሎ ስላገኘሁት ደንቆኝ ነበር። ግርማዊነትዎ ራስዎ እርሱን የማየት ዕድል ስለሚኖርዎ እኔ ብዙ ባልናገር ይሻላል። ከሁለት ቀናት በፊት ጣና ሃይቅ ላይ አሣ ሊያጠምድ ሄዷል። አሣ ማጥመድን በጣም የሚወደው ሲሆን አበሣሥሉንም በሚገባ ያውቅበታል . . . አልክበትና ነገ ይሄዉ አመጣለሁ።»

«በጣም ጥሩ» አሉ እያሱ ያለንጉት፣ «አቀበለዋለሁ።»

ሽማግሌው መልዕክተኛ ትርፍ የሚያገኝበት መስሎት ስለገመተው፣ የራሱ ቤተሰብ አባል የሆነ ሰው በዚህ ተልዕኮ ላይ እንዲመደብ መፈለጉን ንጉሡ ተረድተዋል። ይህ ደግሞ ደንብ ነው። የንጉሡ አማካሪዎችም ትርፍ የሚያስገኝላቸው ካልሆነ በስተቀር ምንም አልፈየዱም። ይህንንም በደንብ ያውቃሉ። ከዚህም ባሻገር የራሣቸውን ፍላጐት ሲከታተሉ በንጉሡ ፍላጐት ላይ ሚዛናዊነት የሌለው ተግባር ለመፈፀም ወደኋላ የማይሉ ናቸው። እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ልክ እንደጀልባ ነው። የጀልባዋን አገልግሎት የተዋዋለው ሰው ጥቅም ሲያመዝን፣ ጀልባዋ ወደርሱ በኩል ታዘነብላለች። ጀልባዋን የሚያንቀሣቅሳት ሰው ጥቅም ሲያመዝን ደግሞ፣ ወደ ሌላው አቅጣጫ ተጋድላለች። ስለዚህ እንዳትሰምጥ በሁሉም አቅጣጫ ሚዛኗ እኩል መጠበቅ አለበት።

«መልዕክተኛ የማግኘት ችግር አሁኑኑ መፍትሔ የምንሻለት ጉዳይ ነው። ነገር ግን ይህ መልዕክተኛ ይዞት በሚሄደው መልዕክት ላይ ግርማዊነትዎ ወሰኗልን?»

«በርግጥ» አሉ ንጉሡ፣ እንደገና በራስ መተማመን እየታየባቸው። በዚህ ርዕስ ላይ የሽማግሌውን ይሁንታ እንጅ ምክሩን አይፈልጉም። «ለንጉሡ ሰላምታዬን ያደርስላቸዋል። ይህ ሰላምታ አንድ ዜጋ ወይም ሎሌ የሚልከው ዓይነት ሳይሆን፣ አንድ ንጉሰ እንደማዕረጉ

ለሌላ ንጉስ የሚልከው ቡራኬና ምስጋና ይሆናል። እኩያ ለእኩያ የሚልከው ዓይነት ይሆናል። ስለኔህ ስለሱዊስ ያወቅሁት ሃያል መሆናቸውን ነው። አልጋቸውና ዙፋናቸው በሰላም ተጠብቆ፣ ግዛታቸው በሰዎች ላይ እንዲስፋፋ እመኝላቸዋለሁ። በተጨማሪም፣ እድሜአቸው በሽምግልናው ውስጥ ቢሆንም መልካም ጤንነትንም እመኝላቸዋለሁ። ፍቅርና ደስታንም እመኝላቸዋለሁ። እነዚህን ምኞቶች መልዕክተኛው ሲገልፃቸው የእኩልነት ደረጃችንን በግልፅ ማሳወቅ ይኖርበታል። መልዕክተኛው፣ የንጉስ ሰለሞንና የንግስት ሣባ ልጅ፣ የምኒልክ ተወላጅ፣ የነገስታት ንጉስ፣ የላይኛው ኢትዮጵያና የታላላቅ ንጉሦች ንጉስ፣ የታላላቅ አገሮችና ግዛቶች፣ የሸዋ ንጉስ፣ የክፋ ንጉስ፣ የጋፋት ንጉስ ፣የአንጮት ንጉስ ወዘተ. . . መልዕክተኛ መሆኑን ይናገራል። መልዕክተኛው ከዚህ ከመልቀቁ በፊት እነዚህን ሁሉ አንድም እንኳ ሳይሰት፣ ክብራቸውንና ማዕረጋቸውን ማወቁን እኔው ራሴ እነግረዋለሁ። ከዚህ በኋላ ሰላማችንን የሚያደፈርሱ ካህናት ከእንግዲህ በኋላ ከርም እንዲመጡብን እንደማንፈልግ ለንጉስ ሱዊስ ይናገራል። በዚሁ ጊዜ እኛ ለነዚህ ካህናት በመርህ ደረጃ ምንም ዓይነት ጥላቻ እንደሌለን፣ እንዲያውም በቅድሚያ እጀቻችንን ዘርግተን በደስታ እንደተቀበልናቸውና እነርሱ ግን መስተንግዶችንንና እምነታችንን እንዳዋረዱብን፣ ንጉሡ እንዲያውቁ አድርጉ ይናገራል። በርሳቸው በኩል የእጅ ባለሙያተኞችንና ሠራተኞችን እንዲልኩልን፣ ምክንያቱም የርሳቸው አገር ባለእጆች በጣም ጥሩ ጥበበኞች ስለሆኑ፣ ሠዓሊው ብራንካሊዩን በቀድሞው ጊዜ ዘወድ በመድፋት ላይ ለነበረው ንጉስ ክብር ሲል ቤተክርስቲያኖቻችንን እንዳስጌጠልን ሁሉ፣ ዋና ከተማችንን ያስጌጡልናል። በመጨረሻም ታማኝ ዜጋቸው የሆነውን የፖንሴን ልጅ፣ ሰር ጀን ባፕቲስትን በመንግስቴ ውስጥ የርሳቸው አምባሣደር አድርገው ቢያስቀምጡልኝ በአገሬ ውስጥ ያለውን ሥልጣኔንና አድገት ስርዓታቸው ሊያሣውቅ፣ በርሳቸውም አገር ያለውን እንዲሁ ለኔ በየጊዜው ሊያሣውቀኝ እንደሚችል ይናገራል። መልዕክቱ ይኸው ነው። ይህ የአቤቱታ አቀራረብ ሳይሆን አንድ የሁሉም የበላይ የሆነ እኩያውና ወንድሙ ለሆነ የበላይ የሚልከው ሰላምታ ነው። በዚህ ውስጥ አንድም የሃይማኖት ጉዳይ አይጠቀስም። ምክንያቱም ማንም እንደሚያውቀው ሁሉታችንም በክርስቶስ እናምናለን። ይህ እውነታ ደግሞ ሊያስተባብረን እንጂ ሊከፋፍለን አይገባም። ከዚህም በላይ ከነዚህ መንፈሣዊ ፀቦች የምናተርፈው አለመኖሩ ብቻ ላይሆን ይህ ጉዳይ የነገስታት ጉዳይ እንዳልሆነ አምናለሁ።

«እና ምን ገፀ በረከት ይልኩላቸዋል?» ሲል ሙራድ ጠየቀ

«ገፀ በረከት? በዚህ ሁኔታ ውስጥ ጠቀሜታ አላቸው?»

«ግርማዊ ሆይ፣ እንደ እኩያ አነጋግራቸዋለሁ ብለው በእንደበትዎ የነገሩን እርስዎ ነዎት። እንድ ታላቅ መስፍን፣ በራሱ ግዛት ውስጥ ላለ ሌላ መስፍን ሰላምታ ሲልክ ምን ያደርጋል? ታላቅነቱንና ክብሩን የሚያሣዩለት ስጦታዎችን በማድረግ እርሱ ግን ምንም እንደማይሻ ያሣየዋል።»

«ትክክል ነህ ሙራድ» አሉ ንጉሡ። «ለኛ አለም ልውሳን የምንሰጣቸውን ዓይነት ገፀበረከቶች አዘጋጁ። ፖንሴ በጣም በትንሹ በምናውቀው በምዕራቡ ዓለም ይበልጥና በተለይ የሚወደደው ምን እንደሆነ ንገረን፣ ይህ ያንተ ሥራ ነው»

እነዚህን ተናግረው፣ ንጉሡ እንግዶቻቸውን አሰናበቱ። ሙራድ በእጁ ሊያተርፍበት የሚችለውን ስምምነት በተሣካ መልኩ ስለፈፀመው፣ የተፈጠረበትን የደስታ ስሜት ለመደበቅ ሲል እያቃለተ ወደ አልጋው ተመለሰ።

ከሁለት ቀናት በኋላ ሙራድና ወጣቱ ሙራድ መጡ። አጐቱ ብቻ ባለበት፣ ከንጉሡ ጋር በምስጢር ተገናኙ። ከዚህ በኋላ ራሱን ከፖንሴና ከሜትር ዠረሚ ጋር አስተዋወቀ። ሰውዬው፣ ግዙፍ ቦርጫም ሲሆን፣ ጉንጮቹ በተሰየ መልክ ፍም ስለሚመስሉ፣በሃይል በጥሬ የተመታና ምልክቱ ሣይጠፋ የቆየበት ይመስላል። የኩርዶችን ወይም የፋርሳውያንን የአለባበስ ዘዴ ተከትሎ ለብሷል። ረዥሙ እጀ ጠባቡ ቁርጭምጭሚቱ ላይ ሲደርስ በጣም እየጠበበ የመጣውን ባጊ ሱሪውን ሸፍኖበታል። ስፋት ያለው የጨርቅ ቀበቶ ወገቡ ላይ ጠምጥሟል። በተላጨው ራሱ ላይ ቢጫ የሃር ጥምጣም አድርጓል። እነዚህ ሁሉ ጨርቆች ግን የዘይት ጠብታዎች ነጠብጣብ አሰባቸው። ይህ ማለት፣ ሰውዬው ንፅህና የሌለው ነው ማለት አይደለም። ነገር ግን በጣም ከመንገብገቡ የተነሣ፣ ልብሱን እንኳ እስኪለውጥ ስለአላስቻለው ምግቡን መንጭቆ እየተስገበገበ ሲውጥ፣ ዘይት በልብሱ ላይ ስለተንጠባጠበበት ነው። ሙራድና ወጣቱ ሙራድ በአለባበሱ ላይ የወሰዱት ጥንቃቄ፣ ምግብ በሞራሽ የተረፋቸው አያስመሰሳቸውም። ምንም ነገር ሰማከናወን ሌላው ቀርቶ መሃረቡን ዘርግቶ እንኳ ከንፈሮቹን ለመጥረግ አልሞከረም።

የአለባበሱ እንከን፣ አሰታዊ ስሜትን ይናገራል። ይሁን እንጅ ማራኪ ፊት አለው። ከረዥም ዘመን በፊት የነበረው የልጅነት የደስደስ ፊቱ፣ በወፍራሙ ፊቱ ውስጥ ተጠብቆ የቆየ ይመስላል። የፊት መሸብሸብም በፋፋው ሥጋው ላይ ምንም መስመር አልሠራም። ጢሙን እንዲያድግ ቢተወውም በሰርጓዳ ጉንጮቹ ላይ ሁሰት የመጠባበቂያ ፂሞች መስለው ይታያሉ። ፈረንሣውያኑ ከመጀመሪያውኑ በዚህ ሰው ላይ አንድ የሚጠቅም ነገር አዩበት። አሁን

በሚታየው ዓይነት ሙራድ ወጣቱ፣ የትም ቦታ ቢሆን ትኩረት ሳይሰብ ሊሄድ ይችላል። የሚናገረው በትክክል ፈረንሳይኛ ሳይሆን በምስራቅ ሚዲትራኒያን የሚገኙ ነጋዴዎች የሚጠቀመብትን መሰል የለሽ ቅይጥ ቋንቋ ነው። ሌላ የተሻለ አማባሣደር በርግጥ ማሰብ ይቻላል። ይሁን እንጅ ይህኛው ጥሩ የንዛ ጓደኛ፣ ምስጠር ጠባቂና ጥሩ ምግብ አብሣይ ሊሆን ይችላል።

ጆን ባፕቲስት ከሁሉም በላይ የሚያሣስበው ጉዳይ በማንኛውም መልኩ ፈጥኖ መልቀቅ ነው። በመንገዳቸው ላይ ዋናዎቹን መሰናክሎች ሁሉ አልፈዋቸዋል። በመመለስ ላይ የሚኖረው ችግር እምብዛም አሳሳስበውም። ይህን ጊዜ ካይሮ በሆነኩ ብሎ አሊስን ባለማቋረጥ ያስባታል። አዕምሮው ውሣ በማያሳልፈው ጓዳው እርሷን ብቻ በማሰብ ተወጥሯል። በጉዞው ጊዜ በጣም ርቀት ላይ በመሆኑ ተስፋ ሳስመቁረጥ በመወሰን፣ ስለርሷ አብዝቶ ላለማሰብ ተጠንቅቆ ነበር። አሁን ግን መልኳና ቁመናዋ በአዕምሮው ውስጥ በግልፅ ይታዩት ጀመር። ዳግመኛም በቅርቡ እንደሚያያትና ታሳቋን የኤምባሲ ዜና ሲያበስራት ታየው። ጆን ባፕቲስት ይህን ሁሉ የሚያልመው ለመመለስ ጉዞው እየተዘጋጀ ሣለ ነው። ችግሮች፣ እርግጠኛ ያለመሆን ሁኔታዎችና አንድ ሺህ አንድ የሚሆኑ ብዙ ሥራዎችና ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች፣ እርሱ በትዕግስት እንደሚጠብቃት ሁሉ እርሷም መመለሱን በናፍቆት እንደምትጠባበቅ ለአፍታ እንኳ አይጠራጠርም። በፍቅር መጀመሪያ ላይ ምንም ነገር እርምጃውን ቢያዘገየው ይመግበዋል። ምንም ነገር በተቃውሞ ቢነሣበት ወኔና ብርታት ይሰጠዋል። እነዚህን ሁለት ፍቅረኛሞች ሰጥቂት ቀናት ከተገናኙ በኋላ እንዲለያዩ ካደረጋቸው አስገዳጅ ሁኔታ ሌላ ተቃራኒ ነገር ማሰብ ይከብዳል። ተሳራሪ የሚመስለው የሁለቱን ስሜት እንዲህ እንዲጠነክር ለማድረግና ጥርጣሬን አሽቀንጥሮ ለመጣል፣ ሌላ ነገር ይህን ያህል አይሠራም ነበር።

ወደ ቤት የመመለስ ሃሣብ አጥብቆ ስሜታቸውን ያነሣሣው ጆን ባፕቲስትና ሜትር ዠረሚ፣ ንጉስ ነስቱ ሰዘመቻ ሊወጡ በተዘጋጁበት ጊዜ እነርሱም ዝግጅታቸውን አጠናቅቀው ቅፍለታቸውን ሰብስበው አደራጁ። ከነርሱና ከወጣቱ ሙራድ ሌላ አስር አቢሲኒያውያን ባሮች ነበሩ። ንጉሡ፣ ለወጣቱ ሙራድ ብዙ ዓይነት ዕቃዎችንና ትጥቆችን ሰጥተውት ነበር። ከነዚህም መካከል የክብረ በዓል ልብሶች ሲገኙባቸው፣ በአጠቃላይ ሁለት ሻንጣ ሙሉ ሰጥተውታል። አስሩ ጥቋቁር ሰዎች ግማሽ ሰውነታቸውን እርቃናቸውን የነበሩ፣ፀጉራቸውን በዛጐል ሹሩባ የተሠሩ፣ ሁሉም በጦርነት የተያዙ፣ ስድስት ወንዶችና አራት ሴቶት ነበሩ።

ወጣቱ ሙራድ፣ የተልዕኳው ዝርዝር የሌለበት፣ በአጭቱ ተዘጋጅቶ በንጉሠ ነገስቱ የተፈረመና ብዙ የመንግስት ማህተሞች ያረፉበት፣ ተለይቶ የተገለፀ ተቀባይ ያልታወቀበት፣ በአጭሩ አርመናዊው የንጉሡ የመንግስት መልዕክተኛ መሆኑን የሚገልፅ እጥር ምጥን ያለ ደብዳቤ ይዟል። ለፈረንሣዩ ንጉስ የሚያቀርበውን መልዕክት ግን በጥንቃቄ ከልቡ አጥንቷል። ባሮቹ በጉዞው ላይ መንገደኞቹን ያገለግላሉ። በጉዞው መጨረሻ ላይ፣ ሉዊስ ለሚባለው ለንጉስ ሉዊስ አስራ አራተኛ ልጅ በስጦታ ይቀርባሉ። ሌሎች ስጦታዎችም እንዲሁ ነበሩ። ከነዚህም መካከል አምስት ፈረሶችና በከባድ ሰንሰለት እንዲቆራኙ የተደረጉ ሁለት ኮርማ ዝሆኖችም ነበሩ። ሦስት ሣጥን ሙሉ የጥርኝ ዝባድ፣ ትንባሆና የወርቅ አፈር ከስጦታዎች መካከል ነበሩ።

ፈረንሣውያኑ ሐኪሞች በበኩላቸው፣በቆይታቸው ጊዜ የሰበሰቧቸውን ወርቅ፣ የከበሩ ድንጋዮች፣ ቆዳ፣ የገዘቦን ጥርስ እና ሌሎችም ታካሚዎቻቸው፣ ከነዚህም መካከል የንጉሠ ነገስቱ የልፍኝ አስከልካይ በክፍያ መልክ እንዲቀበሏቸው የሰመኗቸውን፣ ዕቃዎች የሚጭኑባቸው ሁለት ፈረሶች ያስፈልጓቸው ነበር። በቆይታቸው ወቅት የሰበሰቧቸውን የደረቁ ዕፅዋት፣ ሥራስሮችና ፍሬዎች ሰፊና በጣም ቀላል በሆነ ሰልቻ ውስጥ አድርገው የሚጭኑበት አንድ አህያ ነበራቸው። ለንጉሡ የሚያገለግል ብዙ ብልቃጥ መድሃኒት፣ ከነሕክምና መመሪያው ለዲሚጥሮስ አስቀመጡለት። ምንም እንኳን ንጉሠ ነገስቱ ለጊዜው የዳኑ ቢሆኑም ሕመሙ ግን ተመልሶ መምጣቱ አያጠራጥርም።

በቆይታቸው ወቅት በከተማዋ ከሚኖሩ ብዙ ሰዎች ጋር ተዋውቀው ስለነበር፣ ተሠነባብተው እስኪነሱ ሦስት ቀናት ፈጀባቸው። ጆን ባፕቲስት፣ ሃሣቡ ሁሉ በሚወዳት ልጅ ላይ ስለነበረ ከተዋሸማቸው ሴቶች የቀረቡለትን ስጦታዎች በተቻለ የትህትና መጠን ሣይቀበል ቀረ። በተለይም በመጨረሻው ምሽት ይህን ዓይነቱ ስጦታ በጣም ብዙ ነበር። ስለዚህም ሜትር ዠረሚ ሁለቱንም ወክሎ ሲሰራ ነበር።

መድረሱ አይቀርምና የመጨረሻው ዕለት ደረሰ። የበጋው ወቅት እየተገባደደ ስለነበር የደመና ቁልል በምሽት ሰማይ ላይ ያንጎባባል። ተጓዦቹ፣ ከንጉሡ ጋር መጀመሪያ በተገናኘ ብት የቤተመንግስቱ አናት ዘብ ክፍል ውስጥ ለመጨረሻ ጊዜ ሊወያዩ ተገናኙ። ንጉሡ፣ እንደ ወንድሞቻቸው አቅፈዋቸው አለቀሱ። ሁልጊዜም እግዚአብሔር እንዲጠብቃቸውና በፍጥነት መልሶ እንዲያመጣቸው እንደሚለምኑትም ነገሯቸው።

«እንካችሁ» አሉ ለእያንዳንዳቸው የእጅ መጻፍ የሚያክልና የይሁዳ አንበሣ ምስል መሀሉ ላይ የታተመበት የወርቅ ሜዳሊያ እየሰጧቸው። «እንደማታምኑበት አውቃለሁ። ነገር ግን በነዚህ ውስጥ ከቁሣዊ ሃብትነታቸው ይበልጥ ጥቂት ነገሮች አሉባቸው»

ንጉሡ የወርቁን ሰንሰለት ቢጀን ባፕቲስት አንገት ላይ በራሣቸው እጅ ካጠለቁለት በኋላ አቀፉት። በተመሣሣይ መልክ ለሜትር ዝረሚም አደረጉና ወዲያውኑ ተለዩዋቸው።

የዚያኑ ዕለት በርቀት በህዝባዊ ስብሰባ ላይ እንደገና ንጉሡን አዩዋቸው። እንደቀሣውስቱና መሣፍንቱን ከሆነ፣ ተጓገቹ ንጉሡን በግል ማየት አይፈቀድላቸውም። ይሁን እንጅ ውስጠ ምስጢርነቱን ሁሉም ያውቃሉ።

ሁለቱም ፈረንሣውያን ዙፋኑ ወደተዘጋጀበት የቤተመንግስት ግቢ ተወሰዱ። ከንጉሰ ነገስቱ ጥቂት እርምጃዎች ፈቀቅ ብለው አራት አንበሶች በጉጆአቸው ውስጥ ሆነው ያቃስታሉ። እንደሁልጊዜውም፣ ንጉሠ ነገስቱ ንቅንቅ ሳይሉ በአፈ ንጉሣቸው በኩል ይናገራሉ። ፖንሴና ሜትር ዝረሚ በግንባራቸው መሬት ላይ ተደፍተው ሰገዱ። ግንባራቸውን የገጨኔው በመንገዱ ላይ የተነጠፈው ጉርበጥባጣ ድንጋይ መጀመሪያ ሊመጡ በጣም ቀዝቃዛ ከነበረው ቢለይም ተመሣሣይ ስሜት ነበረው። ልዩነቱ እምብዛም በማይታወቅበት ምድር፣ ከሠማይ በታች ተቀራርቦ የተነጠፈው ጥቁር ድንጋይ፣አፈሩ ወይም ድንጋዩ ከእንግዲህ በኋላ ዐስፈልም ቢሆን የነርሱ ነው። ከንጉሠ ነገስቱ ዘንድ የቀረቡበት ጊዜ ትንሽ ረዘም ሲል፣ ቀሣውስቱም፣ ተጓገቹ ረዘም ላለ ጊዜ እንደሰገዱ ቢቆዩ ጥሩ እንደሚሆን አሰቡ። ሲነሱ ግን ሁለቱም ሰዎች እያንዳንዳቸው መሬቱን በስሙም ቢሆን እንዳወረዙት ይህም በእንባቸው እንደሆነ አስተዋሉ።

ሠላሣ ፈረሰኛ ወታደሮች ከከተማው ጀምሮ የአምስት ቀን ጉዞ እስከወሰደባቸው አክሱም ድረስ አጅበዋቸው ተጓዙ። እንደደረሱም፣ ከውጣቱ ሙራድና ከቀሪው ቅፍለት እንዲሁም ዝሆኖች ጋር ተቀላቀሉ። እስከ ንጉሠ ነገስቱ ግዛት ወሰን ድረስ በቁጥር ሰባት ወንዶች ያሉበት ቀላል አሻቢ ኃይል ይሣቸው ሄደ። ከዚያም አክሱምን ለቅቀው ወደ ቀይ ባህር ጠረፍ ተጓዙ።

3

የሹመት ደብዳቤው

1

ዲፕሎማሲ ጥበብ ነው። ጥበብ ሲባልም ርጋታን የሚጠይቅ ጥበብ ነው። ሁልጊዜም ያልተቋረጠ ክብር የሚጠይቅ ጥበብ ነው። ለአረማመድ እንኳ ግርማ ሞገስ የሚሻ ጥበብ ነው። ስለዚህ ከጥሪት ጋር፣ ከድካም ጋር፣ ከጥድፊያ ጋር የሚጣጣም አይደለም። በአጭሩ ወይም በሌላ አባባል ከስራ ጋር የሚስማማ አይደለም።

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ አንዳችም የሚሠራው ነገር ባልነበረውና ራሱን ሙሉ በሙሉ ለስራ ማዋል ይችል በነበረበት እንደነዚያ ጊዜያት ሳይሆን፣ እንደአሁኑ አስተዋይ ዲፕሎማት ሆኖ ሥራውን አከናውኖ አያውቅም። ማንም ሰው፣ ወኔ ኖሮት ስለዚያ ጊዜው ሀይወቱ ሊጠይቀው ቢችል በምስጢር ተሸፍኖ፣ በማጣት ሽትቶ ይኖር ከነበረበት ደረጃ ተነስቶ፣ ራሱን የመንግስት ባለሟል ማድረግ የቻለ ሰው መሆኑን ይረዳል። የመልዕክተኞቹ ቡድን ወደ አቢሲኒያ ከሄደና ከካሀናቱ መጥፎ ሴራ በኋላ፣ ቆንሲሉ የተለመደውን የመንግስት አገልግሎቱን ቀጠለ። ጥቂት ዘግይተው በደረሱት ጋዜጦች ላይ፣ ከሥራ አቻዎቹ አንዳንዶቹ አዲስ የስልጣን ደረጃ እንዳገኙ ያነበበውን ወደጉን በመተው የራሱንም ህጋዊ የጉጉት አቅጣጫ ማመላከት የሚችልበትን ዘዴ መፈለግ ጀመረ። በመጨረሻም፣ ከርሱ በፊት ተወስኖ በነበረ ትዕዛዝ መሠረት ብዙ የቱርክና የአረብ ሰዎችን ጉበኘ። ለነዚህ ሰዎች የሚነግራቸው አልነበረውም፣ ከነርሱም ምላሽ ሰመስማት ደንታ አልነበረውም። ውይይቱ፣ ልክ የምስራቃውያን የቀረፃ ጥራት የብዙ ሺህ ተጓጉችን አይኖች እየማረኩ ግን አንዲትም ቅርፃቅርፅ ወይም መልክ ወይም ምልክት እንደማይቸሩ፣ እንዲሁ ያለ አንዳች ፋይዳ ይቋጫሉ።

ይህም በስምምነት የዘለቀ ቆይታ፣ ፖንሴና ሄጅ አሊ ጉዞ ከጀመሩ በኋላ፣ በ1700 ግንቦት ወር መጀመሪያ ላይ ክፉኛ መሰናክል ገጥሞት ነበር። ይህ ሁሉ የሆነው በሁለት ሣምንት ለደሚ ውስጥ ነው። በመጀመሪያ የክቡር ዴ ፖንቻርትሬይን ደብዳቤ የያዘ ፖስታ ከአሌክሣንደርያ ይመጣል። ቆንሲሉ ሳይረበሽ ለማንበብ ቢሮውን ቆልፎ ተቀመጠ። ደብዳቤው፣ በመደበኛው የሰላምታ አቀራረብ ጀምሮ ወደ ሌሎች ጥቃቅን ጉዳዮች ይሸጋገራል። ከዚህ በኋላ ሚኒስትሩ ርዕሱን ኢትዮጵያን ወደ ሚመለከት ጉዳይ ይቀለብሱታል። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ከደብዳቤው ውስጥ የሚከተሉትን አስደንጋጭ ዐረፍተ ነገሮች ያነኛል።

ወደ ኢትዮጵያ የጀመረኸውን የመንግስት መልዕክተኞች ሥራ በተመለከተ የንጉሡን ሃሣብ የዘነጡልህ መልካሞቹ ደስዊቶች፣ ምንም እንኳ ተመሣሣሮች ባይሆኑም ከራሣቸው ሃሣቦች ጋር ያምታቱት ይመስለኛል።

አቢሲኒያ፣ የቅዱስ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሥርዓት ውስጥ በተመሰጋገኞቹ የየሰሰ ማህበረሰቦች ጥረት መግባቷን ሲያውቁ፣ ግርማዊነታቸው ደስታቸውን መግለፃቸውን በጀርዌ የሰማሁት ሐቅ ነው። ነገር ግን፣ ቬርሣይለስ ውስጥ የአቢሲኒያን ንጉሰ መቀበል አልፈቀዱም ነበር። ከግርማዊነታቸው ጋር ዛሬ በድጋሚ ተመካክርን። እንዲህ ያለውን ኤምባሲ ለመቀበል ደስተኛ እንዳልሆኑ ላረጋግጥልህ እወዳለሁ። ምክንያቱም፣ ይህ አይነት ተግባር አሁን ያለውን የአውሮፖ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ከመቸውም በበለጠ ጥሩ ግንኙቱን ጠብቆ ማቆየት ሲገባ፣ የአቶማን ሡልጣንን የሚያስቆጣ ሲሆን አይችልም ማለት አይቻልም። ከደብዳቤህ እንደተረዳሁት መልዕክተኞችህ በሰላም ስለመመለሳቸው ልበ ሙሉ አይደለህም። ነገር ግን፣ እዚህ መልዕክተኞችህ ወደ ካይሮ የሚመለሱ ከሆነና ከኢትዮጵያው ንጉሰ መልዕክተኞች ጋር ታጀበው የመምጣት ዕድል ካላቸው፣ እዝህን ባለሙሉ ሥልጣን አምባሣደር የሆኑ ስምኦን ወደ ቬርሣይለስ እንዲይዙ አዚያው እንድታቆያቸው የራሴን አሰተያየት አሰግስሃለሁ። ለጥቂት ጊዜ አጠገብህ አቆይቸውና የሚያቀርቡትንም ምሲጋና ተቀበል። ከዚያ በኋላ ከብዙ የምሲጋና ቋንት ጋር ወደ ጌታቸው መልሰህ ሳካቸው። ከዚህ ሌላ አይደረግም።

እነዚህ አዳዲስ መመሪያዎች አንዳች ክፉ ነገር እንደሚመጣ የሚጠቁሙ ናቸው። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ በገፀታ ላይ እንኳ ትካዜና ሃዘብ ገብቶት ሲውል በተከታታይ ቀኖች በጉዳዩ ላይ ከሙሴ ማቼ ጋር ሲመካከር ስነበተ። የዕቃ ማስቀመጫ በሆነችው ትንሽ ክፍል ውስጥ የሚሠራው ፀሐፊ፣ አሁንም፣ አሁንም በመጠራቱ ደስታ እየተሰማው ነው። በሚቀጥለው ሣምንት ደግሞ ሌላ አስደናቂ ሁኔታ ተከሠተ። አንድ አረባዊ ፈረሰኛ በፈጣን ግልቢያ እስከፈረንሣውያን ማሕበረሰብ መኖሪያ ድረስ ሽምጥ እየጋለበ ይመጣል። ያደረገው ቀይ ባርኔጣ በነፋስ ውሰጥ እየተውለበለበ፣ ቆንሲሉው ግቢ ፊት ለፊት ሲደርስ ከፈረሱ ላይ ዱብ ብሎ ወርዶ፣ ለፈረንሣይ ተወካይ ደብዳቤ መያዙን ያስታውቃል። ቆንሲሉ በፖስታው ላይ አጥብቆ በተጠየቀው መሠረት፣ ደብዳቤውን ከመልዕክተኛ እጅ ላይ ራሱ ተቀበለ። ጥቂት ጥያቄዎች ካቀረበለት በኋላ፣ ደብዳቤውን ያመጣው መልዕክተኛ ሦስት ደረጃዎችን አልፎ በአረቢያን የባህር

ወሽመጥ በኩል ከጅዳ የመጣ መሆኑን አወቀ። መልዕክተኛው እንደደረሰ ሊከፈለው ይገባ ነበርና፣ በዋጋው ላይ እንዲከራከር ሙሴ ዴ ማይሌ ሃላፊነቱን ለፀሐፊው ሰጠው።

አዲሱ ደብዳቤ ዲፕሎማቱን ከመጀመሪያው የበለጠ መንፈሱን ረበሸው። በቤቱ ውስጥ ያለው አጠቃላይ እንቅስቃሴም ግራ ተጋባ። ስንፍናን ዱቄት ለማድረግ በሚገባ ተሟሽቶ የሰለጠነው የቆንሲሉ ጭንቅላት፣ ዛሬ እፍኝ በማትሞላ የመታወክ ፍሬ መንሣጠጥና ማቃስት ጀመረ። ማዳም ዴ ማይሌ፣ ባሏ እንደገና ጤናውን አደጋ ላይ እየጣለ መስሏት ተጨነቀች።

ከሁሉም ይልቅ የተጨነቀችውና ዜናውን የተራበችው በርግጥም አሊስ ነበረች። በነዚህ ሁሉ ረዥም ወራት ሁሉንም የስሜት ደረጃዎች በማቋረጥ፣ ከተስፋ ወደ መጨነቅ፣ ከዚያም መጥፎ ነገር ይደርሣል በሚል መሰቃየትና በመጨረሻም ገና ያልተከሰተ አስፈሪ ሁኔታ ይኖራል በሚል ተሰቃየች። በአሁኑ ጊዜ እጅግ አደገኛና ወደ ሞት ሊያደርስ ወደሚችል ደረጃ ራሷን እያደረሰችው ነው።

የሁለቱ መልዕክተኞች መድረስ፣ የአሊስ ትዕግስት የማጣት እና የጉጉቷን መጠን እንደአሣት የሚያቃጥል ትኩሣት ሰቀቀባት። ሙሴ ዴ ማይሌ ግን አዕምሮውን የያዘውን ምስጢር ጉዳይ ሰቤተሰቡ ላለመግለፅ ወስኗል። የመልዕክተኛው ቡድን ወደ አቢሲኒያ ሲንቀሣቀስ አድሮበት በነበረው ከመጠን ያለፈ በራስ መተማመን ሳቢያ፣ በቤቱ ውስጥ ተፈጥሮበት የነበረውን ምስቅልቅል ሁኔታ በሚገባ ያስታውሰዋል። በዙሪያው ያሉት ሰዎች ያቀረቡሰትን የመጀመሪያ ጥያቄ ተከትሎ ምስቅልቅል ነገሮች ስላሉ፣ እንደ አይሰተር አሣ ዝም፣ ዝግት ብሎ ያጉረመርማል።

በር ስር ተሰጥፈው ለማዳመጥ ከፍተኛ ጥረት ከማድረጋቸው በስተቀር፣ አሊስና ፍሪንችይዝ የተሻለ ነገር ማወቅ አልቻሉም። በዚህም ሣቢያ መሳምቶችን መደርደር ጀመሩ። አሊስ፣ መንገትና ፍቅር ስላለባት፣ የታሰባትና በርግጥም ያለማጋነን ያጋጠማት፣ በጀን ባፕቲስትና በተልዕኮው ላይ አንዳች አሰቃቂ ነገር ደርሷል የሚል ነው። ፍራንችይዝ በመጨረሻ ላይ አንድ ሃሣብ እስክታመጣ ድረስ ተስፋ በመቁረጥ ምንም አይነት ዜና ላለመስማት ወስና ነበር።

«ቆንሲሉ ይህን በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሚያከናውኑት ስላልሆነ፣ ያለው ብቸኛ ነገር ምንነቱን መፈተሽ ነው» አለች

«ወደ ቢሮው መግባት? ይህ ፈፅሞ የማይሆን ነገር ነው» አለች አሊስ።

በፍራንቾይዝ ሥር ሆና በመቆየትዋ ወኔ ያላት ወጣት ሴት መሆን ብትችልም፣ ትዕዛዝ የመጣሱ ሃሣብ ግን በእጅጉ አስፈራት።

«ይህ በጣም አስቸጋሪ አይደለም። በምሽት ወረቀቶቻቸውን ሁሉ ጠረጴዛው ላይ በትነው ነው የሚተውት። በሩም ቢሆን እይቆለፍም። ይህን፣ የመስኩቶችን መጋረጃ የሚለቅቀው ትንሹ ኑቢያዊ ነግሮኛል» አለች ፍራንቾይዝ

«ወደ ቢሮው መድረስ የሚቻለው በእንግዳ መቀበያው በኩል እንደሆነና ጠባቂው ደግሞ እዚያ ውስጥ እንደሚተኛ ረስተኻል ማለት ነው።»

«ታውቂያለሽ» አለች ፍራንቾይዝ በማታለል። «ወደ ቤታቸው መጀመሪያ በመጣሽ ጊዜ ለአባ ጋበሪ የሰጠናቸው መጠጥ፣ ምናልባት ሙሉ በሙሉ አያስተኛቸውም ይሆናል በማለት ሜትር ዠረሚ ፊርቶ ነበር»

«እናስ?»

«እናማ ሌላ ጠርሙስ እኔ ዘንድ አስቀመጠ። ከዚህ ውስጥ ጥቂት ጠብታዎች በማንኛውም ፈሣሽ ውስጥ ቢጨመር፣ ምስኪኑ ሰው ቄልጥ ያለ እንቅልፍ ውስጥ ስለሚገባ፣ አጠገቡ ቆመን እንኳ ድምፃችንን ዝቅ ሣናደርግ ብናወራ ሊያጸምጠን አይችልም። ያንን በቁሱ ላይ መጠቀም አልነበረብንምና አልተጠቀምንም። ይሁንና ጠርሙሱ አሁንም እኔ ዘንድ አለ።»

በማግስቱ ሚት ጠባቂው ዘበኛ የተቀሰቀሰው፣ አንድ ጣሣ ውሃ በሸሚዙ ላይ ከተቸለሰበት በኋላ ነበር። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ የአገሬው አገልጋዮች ጠፍ በመሆናቸው ከማማረር ሌላ ያለው አልነበረም።

እንደከ ትላንት በስቲያ ማታ በአምስት ሰዓት ድረስ ዘበኛው መተኛቱን እርግጠኛ ስትሆን፣ ፍራንቾይዝ በበሩ አጠገብ ሆና ስትጠብቅ፣ አሊስ ወደ አባቷ ቢሮ እየዳሸች በጠረጴዛው ላይ በተቀመጠው ቀይ የቆዳ ማህደር ላይ የሚኒስትሩን የዴ ፖንቻርትሬይን ደብዳቤ ሰይታ አወቀች። የስም ማህተሞቹና በወረቀቱ ላይ ጉላ ብለው ሲታዩ በውሃ ቀለም የተፃፉት ደብዳቤዎች አያሣስቱም። የወረቀቶቹን ቅደም ተከተል ለማስታወስ እየሞከረች በጥንቃቄ አነሣችው። ለማንበብ እንኳ ስትሞክር፣ ዋናው ጉዳይ የሚገኘው ሌላ ቦታ ነው በሚል ወደጉን አስቀመጠችው። በጣም ርግጠኛ ሆና ሌላ ትንሽ ደብዳቤ ከስሩ አገኘች።

የመጀመሪያው ደብዳቤ ከሌሎቹ ደብዳቤዎች ሁሉ ጉላ ብሎና በግርማ ሲታይ፣ ይህኛው ግን ጉስቁልቁል በማለቱ ተጨማድዶ፣ ቁዘዜ አወይቦትና በቆሻሻ ጣቶች ምልክት የተበላሸ ነበር። አሊስ በጥንቃቄ አነሣችው። የተላከው ከጂዳ ሲሆን የፅሁፉ አጣጣል የጆን ባፕቲስት ነው። ወረቀቱን ወደ ደረቷ በሃይል አስጠግታ አቀፈችው። ለማንበብ ስትጓጓ ደረቷ ላይ ይዛው አቆየችው። ወረቀቱን ደረቷ ላይ አትፋ ማቆየትዋ ጆን ባፕቲስትም ይህችኑ ወረቀት እንዲሁ እንዳደረጋት መስሏት፣ እርሷም በሮሱ እጆች ላይ የራስዋን ያስቀመጠች መሰላት። በመጨረሻም ልታነብበው ተበራታች። መጥፎ ሁኔታ ላይ ተኩኖ በመቃ ብዕር ስለተፃፈ፣ በደብዳቤው ብዙ ቦታዎች ላይ የቀለም ነጠብጣቦች ቢኖሩበትም አጭርና በሚገባ ሊነበብ የሚችል ጽሁፍ ነው። የፅሁፉ አጣጣል ሽቅብ ወደ ቀኝ ዘመም ያለ ነው።

ክቡር ሆይ

በአሁኑ ጊዜ ወደ ካይሮ በመመለስ ጉዞ ላይ እኖራለሁ። አባ ብራቪዳንት፣ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ሳይደርሱ በመሞታቸው ሐዘን ቢሰማኝም፣ ወደ አቢሲኒያ የተደረገው ተልዕኮ ሙሉ በሙሉ የተሣካ ነበር። ከኔ ጋር ከንጉሡ የተላኩ አምባሣደር ይሸ እየመጣሁ ነው። ሰውዬው ለጥቂት ጊዜ ምዕዋ ላይ ቢዘገይም፣ በአሁኑ ሰዓት ቀይ ባህርን እያቋረጡ ናቸው። ንጉሡ ነበሱ፣ ሰፈረንሣይ ንጉስ የምናቀርባቸውን ልዩ ልዩ ገፀ በረከቶች ሰጥተውናል። በዚህ መሠረት አስር አቢሲኒያውያን ባሮች፣ ፈረሶች፣ ሁለት የዝሆን ጥርሶችና ሌሎችም ብዙ አሉ። ቡድናችን ተመልሶ ሲሰባሰብና የመጓጓዣ መርከቡን ስናገኝ ወደ ፖርት ሳይድ የምናደርገው ጉዞ ይጠብቀናል። ሁሉም ነገር በሰላም ከተከናወነ፣ በአንድ ወር ውስጥ ካይሮ እንደርሣለን። ለክቡርነትዎ ጤንነት እፀልያለሁ።

«በአንድ ወር ውስጥ!» አለች አሊስ

በወረቀቱ አናት ላይ ቀኑ የተጫጫረበትን ቦታ ተመልክታ በፍጥነት አሰላችው። ልክ ከዛሬ ዘጠኝ ቀናት በፊት የተፃፈ ነው።

የጆን ባፕቲስትን ደብዳቤ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠችና የሚኒስትሩን በላዩ ላይ አኖረች። ልታውቅ የፈለገችውን ስላወቀች ከዚህ የበለጠ ማንበብ አያስፈልጋትም።

2

ካምፖቸው ካለበት ከፍተኛ ቦታ ላይ ሆነው፣ ጆን ባፕቲስትና ጓደኞቹ መላዋን የስዊስ ከተማ ማየት ይችላሉ። ከተማዋ፣ ጥቂት የአቶማን ሕንፃዎችና ከቀይ ሸክላ የተሠሩና የሮማውያን የጣሪያ ክዳን ሸክላ የለበሱ ብዛት ያላቸው ባህላዊ ቤቶች በዝቅተኞቹ አረቦች መኖሪያ ሠፈሮች ውስጥ እዚህም፣ እዚያም ተንጠባጥበው የሚታዩባት ናት። በሁለት ረድፍ፣ በረዥም ቦታ ላይ የተተከሉትና ጠርዛቸው የነተበ የሚመስሉት የቴምር ዛፎች አረንጓዴ ቅጠሎች፣ ከባህር ወሽመጡ ውስጥ በሚመጣው ነፋስ ይርገበገባሉ። ሶስት ማዕዘን ቅርፅ ያላቸው የጠረፍ ነጋዴዎች ጀልባዎችም፣ እስከ ምድረበዳው መዳረሻ በሚዘረጉት የሰማያዊው ባህር፣ቀጭን ጣት በሚመስለው ውሃ ላይ በረዥም ሰልፍ ይንሳፈፋሉ። መንገደኞቹ የሲናን ባህረገብ ገደል ወደኋላቸው ትተው፣ የግብፅን ለጥ ያለ የጠረፍ ምድር ደርሰዋል።

ስዊዝ ማለት፣ የውሃ ሕልም የሚያበቃባት የሃዘንና የትካዜ ቦታ ናት። በሕንድ ውቅያኖስ ውስጥ ዳብሮ የሚጀምረው ውሃ፣ በቀይ ባህር ረዥም ክንድ ውስጥ እየተንከባለለ ቀጥሎ በዚያው ባለው አሸዋ ውስጥ ሲቋረጥ፣ የሜዲቴራኒያን የማይበገርና የማይነቃነቅ ምድር፣ ሰቀይ ባህር ጥሪ ጀር ዳባ ልበስ ያለ ይመስላል። ለቁጥር የሚያታክቱ የሲራራ ነጋዴዎች የሰፈር ምልክቶች ወይም ዱካዎቻቸው ሁለቱንም የባህር አካሎች በሚከፍለው የአሸዋ ቀበቶ ሁሉ ላይ መስመራቸው ተዘርግቷል።

ጊዜው የዝናቡ ወቅት ማብቂያ ነበር። የመጨረሻዎቹ ዝናብ ያዘሉ ጥቋቁር ደመናዎች ከባዱንና ቀዝቃዛውን ዝናብ በምድር ላይ ሊያዘንቡ በዝግታ ይሰባሰባሉ። ባሮች፣ የወዳደቁ እንጨቶችን ለብስበው በሚያነዱበት እሣት አጠገብ ጥቂት የተንሹ ቡድኖች ተቀምጠው ይመለከታሉ። ጊዜው ፈጥኖ እየመሸ ነው። በሰማይ ውስጥ የሚታዩት ቀለማት ማራኪ ሀብር ፈጥረዋል። ጥላው የምድሩን አቀማመጥ አጉልቶ ስላውጣው ንፅፅሩን ያሣምረዋል። ይህ አስደናቂ ነገር እያለ፣ ተንገርቹ እርስ በርሣቸው ሳይተያዩ የየራሣቸው ምስኪን ሁኔታ ሁሉ ይሰማቸዋል። በዚህ ሰዓት ሁሉም የሚሰማቸውን ዓይነት ስሜት ያልተሰማው፣ ሙራድን ብቻ ነበር። ሙራድ በዚህን ጊዜ ሙሉ በሙሉ የሚያስበው ስለምግባቸው ጥራት ብቻ ነበር።

የሚቀቀለው ምግብ፣ ቀለሙ ቀይሮና አምሮ እንደሆነ በማለት አሁንም አሁንም እየተንተከተከ ያለውን የቶፋውን መግላሲት ያነሣል።

ጐንደርን በኩራት ከለቀቀው ሰልፍ የቀረው ጥቂት ነው። የሙራድ ፈረስ፣ ገና ከተራራው እንደወረዱ በቆላ ዝንብ ተነድፎ ሞተ። ሌላ ፈረስ ለማግኘት አርመናዊው ወደ ንጉሠ ነገስቱ ዘንድ መልዕክት መላክ ነበረበት። አምስት ፈረሶች ወዲያውኑ ተላኩለት። ሆኖም ግን፣ እነዚህም በፍጥነት ሞተው አለቁ። የሁለቱ ፈረንሣውያን ፈረሶች ግን ትንሽ እንኳ ባለመታመማቸው ጥርጣሬ አስከተለ። መዘግየቱ ያስቆጣው ፖንሴ፣ ሜትር ዝረሚን ይዞ ሰቆንሲሉ መልዕክት መላክ ወደሚችልበት ወደ ጅዳ በጀልባ ተጓዘ። በመጨረሻም በሣጥኖች የነበሩትን ብዙዎቹን ነገሮች ከሠዋ በኋላ፣ ሙራድ የቀረውን በአህዮችና በሁለት በቅሎዎች ላይ ጫነ። ፖንሴ ግን፣ ሙራድ የቀሩትን ሁሉ ምዕዋ ላይ አትርፎ ሣይሸጥ እንዳልቀረ ጠረጠረ። በጊዜው ዝግጅቱ ይህን ይመስል ነበር። ዝሆኖቹ ረዥም ዕድሜ አላገኙም። እንደኛው ጠረፍ ላይ በነበረው ሙቀት ሳቢያ ሞተ። ጠንካራ የሚመስለው ሌላኛው ዝሆን ግን በእንድ አነስተኛ ጀልባ ላይ ሙሉውን ወሰል ይዞ ተጫነ። ይህን ዝሆን በሰንሰለት አስሮ ጀልባው ላይ ሰመጫን አስር ሰዎች አስፈልገው ነበር። ዝሆኑ በጀልባው ላይ ተጭኖ እንዲያ ሲንሳፈፍ ሲመለከተው ሙራድ ኮራ። ከዚህ በኋላ ቀሪዎቹን አጃቢዎቹን አስከትሎ እርሱም በፈንታው ዝሆኑ የተጫነበትን ጀልባ ለማጀብ በትልቅ ጀልባ ላይ ተሣፈረ። በእንሰሳቱ አዕምሮ ውስጥ ምን እንደተፈጠረ ምስጢር ሆኖ ይቀራል። ነገር ግን የዝሆኑ ጥጃ ዙሪያውን በውሃ በመከበቡ ፍርሃት ዋጠው። ጀሮዎቹን እያራገበና በሚያስፈራ ሁኔታ ጡርምባ መሰል ድምፁን እያሠማ፣ የታሠረባቸውን ሁለት ሰንሰለቶች በጥሶ ወሰሉን ረጋግጦ አደቀቀው። የጀልባዋ ነጅ ግን ውጤት ባያመጣም ዝሆኑን ለማረጋጋት ተሯሩጧል። ነገር ግን እርሱም ባለመቻሉ፣ ዝሆኑ የታሰረበት ጀልባ ተገልብጦ የባሀሩ ውሀ በላያቸው ላይ ተደፋ። በዚህ አደጋ አምስት የጀልባ ሠራተኞችም ሰጠሙ።

ሙራድ፣ ምንም ዝሆን ሣይዝ ደረሰ። አስቀድሞ መሬት ላይ የሞተውን ዝሆን ጀሮዎች ግን አስቦበት በማስቆረጥ በሚገባ በሚሰማር በታሸገ በእንጨት ሳጥን ውስጥ አስቀምጧቸዋል። እነዚህ የሚያማምሩ ትላላቅ ጀሮዎች የአፍሪካ ዝሆኖችን ጀሮዎች ያክላሉ። የንጉሰ ነገስቱን እፀብ ድንቅ ሰጦታ ምልክት ለማስቀረት አስቦ ስላከናወነው ሥራ፣ ጆን ባፕቲስት፣ አርመናዊውን አሞገሰው። በዚህ ማስረጃ ለተጠራጣሪዎች ሊያሣዩት የሚችሉት ይኖራቸዋል። የጆን ባፕቲስትን ሙገሣ፣ ሙራድ በትህትና ተቀበለው። ነገር ግን፣ በርሱ አዕምሮ ውስጥ

የዝሆኑን ጀሮዎች አስቀርጦ ያስቀመጠበት ምክንያት ፍፁም የተለየ ነበር። ከዚህ በፊት እንደሰማው የዝሆን ጀሮ በሚገባ ተጠብቆ እንዲደርቅ ቢደረግ ተወዳዳሪ የሌለው ልስላሴ ይወጣዋል።

የባሮችም ሁኔታ የተለየ አልነበረም። ሱቱርካዊው ሱልጣን ምስጋና ይግባውና እርሱ በሳክለት ጠመንጃ ተኳሽ፣ በትንንሽ ደሴቶች ላይ የነገሠው የምፅዋ መስፍን፣ መንገደኞቹ ሣይረበሹ እንዲያልፉ የሚጠይቀውን የንጉሡን መልዕክት ለማክበር ሙሉ በሙሉ ዝግጁ ነበር። ናኢቡ፣ ሃያላኑ ጦረቤቶቹ በርሱ በኩል መልዕክተኞቻቸው እንዲያቋርጡ ሲጠይቁት እጅግ ያመሰግናል። ይሁን እንጂ በንጉሠ ነገስቱ መልዕክት ውስጥ የባሮች ነገር ስላልተጠቀሠ፣ ናኢቡ አራቱን ሴቶች ለራሱ ጥቅም ሲል አስቀራቸው። ከሙራድ ሰዎች አንዱ በዝሆኑ ሣጥን ውስጥ አብሮ ሞተ። አራቱ ግን ጅዳ ደረሱ። የአንበሳቱ ሞነት ተሰል ይልላቸዋል በሚል ለመካው ሽሪፍ ታስቦ የነበረውን ስጦታ፣ አርመናዊው፣ ምፅዋ ላይ ሸጣቸዋል። በምትኩ ግን የቀረበለት የጥርኝ ዝባድና ሁለት ክረጢት የወርቅ አፈር፣ ለሽሪፉ አነስተኛ ካሣ ሆነለት። ከቀሩት አቢሲኒያውያን ባሮች ይበልጥ ፈርጣማ ጡንቻ ባላቸው በሁለቱ ላይ አይኑን የጣለው ሽሪፍ፣ እነዚህ የርሱ ንብረቶች መሆናቸውን አሳወቀ። በዚህ ላይ ፖንሴ ተቃውሞ ሲያነሣ፣ ሽሪፉ አንዱን ብቻ ለመውሰድ ተስማማ። ከዚህ በኋላ የተረፉት ሦስት ብቻ ሆኑ። ከነዚህም ውስጥ አንዱ አማረ ቆልማማ ሲሆን፣ ሁለቱ የአስራ አንድና የአስራ አራት ዓመት ሕፃናት ናቸው። እነዚህ ልጆች በዚያን ዕለት ምሽት በስዊዝ ኮረብታዎች ላይ እራታቸውን በሉ።

ሁለቱ ፈረንሣውያን አስክሁን ያለውን ታሪካዊ ሂደት ሊያሻሽሉት አልቻሉም። ፖንሴ፣ በአረቢያ ውስጥና በቀይ ባህር ጉዞ ላይ ክፉኛ ከመታመሙ በስተቀር ፈረሶቻቸውና ብዙው ጓዛቸው አሁንም ድረስ መኖራቸው ርግጥ ነው። ቀደም ሲል ምፅዋ ውስጥ ሜትር ዝረሚ ታምሞ ነበር። ከአንድ ዓመት ጉዞ በኋላ ሰውነታቸው መንምኖ፣ በትኩሣትም ደክሞ፣ በጀልባ ላይ ከወጡም በኋላ እግሮቻቸው ቆስለው፣ የሚታጠቡበት የጨው ውሃ አሳብጦባቸው፣ አሸዋውም አበቃ ሲባል ይባስ እያበሳጫቸው ነው። ክብራቸውንና ማዕረጋቸውን ሊመልስላቸው የሚችለው ጅዳ ውስጥ ተሰፋ አድርገው የገዟቸው አዳዲስ ቦላሌዎች፣ ባለማሰሪያ ኮሌታ ያሳቸው ከጥጥ የተሰሩ ሸሚዞችና ቀያይ ሰደሪያዎች ናቸው። የገዙትም እንዲህ ነው። ጥቂት የባህር ላይ ወንበዴዎች እነዚህን ልብሶች ከአውሮፖውያን የሸልማት መርከብ ላይ በምርኮ የወሰዷቸው ናቸው። ወንበዴዎቹም ልብሶቹን በመዉሸኛ የወርቅ መጠን ሊለውጧቸው

ይስማሙዋቸዋል። ልብሶቹን ከገዙ በኋላ በጥንቃቄ አጣጥፈው በቆዳ ሻንጣዎቻቸው ውስጥ ይደብቋቸዋል። ከዚህ በኋላ የተነሣው ጥያቄ እነዚህን ልብሶች እንዴት ሊጠቀሚችው እንደሚችሉ ነው። ከዚህም በተረፈ ዘማቹ ጓድ፣ ካይሮ መግባቱ አይቀርምና እንዴት ሊገለፅ ነው የሚሰው ሌላው ጥያቄ ነበር።

«ከካይሮ የሶስት ቀናት ጉዞ ርቀት ላይ ነን» አለ ጆን ባፕቲስት «ከዚህ በኋላ ከነዚህ ከሁለቱ ጋር አብረን እንንዛለን። በመጨረሻው ሠፈራችን ላይ፣ ዝረሚ ፈረስህን ለኛ ትተህ በቅሎ በመያዝ ወደ ሰሜን ትሄዳለህ። ከሁለት ቀናት በኋላ በአባይ ዳር ካለችው ቤንና መንደር ትደርስና ከአንድ ቀን በኋላ ከአሌክሳንደሪያ ካይሮ ትገባለህ። ምክንያቱም ሄጂል የተባልከው አሌክሳንደሪያ ስለሆነ ነው።»

ምንም እንኳ ይህ ሰው የጉዞውን መከራ ሁሉ አብሮ የተጋራ ቢሆንም፣ በመልሱ ላይ አንዳችም ክብር ላያገኝ ነው። ይሁን እንጅ ይህን ትሁት ድርሻ፣ ይህ ልምድ ያለው የጥንት ወታደር በዝምታ መቀበሉን ፖንሴ ያውቃል።

«ሁሉታችንስ፣ አብረን እንቆያለን?» ሲል ሙራድ በመጓጓት ጆን ባፕቲስትን ጠየቀው።

«አዎን፣ ግን ለሁለት ቀናት ብቻ። ከዚያም ዝረሚ የሚለየን ቦታ ላይ ትቆያላችሁ። እኔ ቀድሜ እሄዳለሁ።»

«ምን?» አለ ሙራድ «ብቻዬን በምድረ በዳ መካከል ልቆይ ነው?»

«ብቻህንማ አትሆንም። ባሮቹ አሉልህ» ሲል ሜትር ዝረሚ አጉረመረመ

«ቅር የሚልህ ነገር አለ? ለመሆኑ አይተሃቸዋል?»

«ደህንነቱ በሚያስተማምን የሊራራ ነጋዴ ሰፈር እናርፋለን። እዚያም ለሚጠብቃችሁ ሰው እኔ እስፍላለሁ።» አለ ፖንሴ ክስተር ብሎ

«እናም አንተ ቀድመህ ትሄዳለህ?» አለ ሙራድ ጠንካራ እምነት ላይኖረው።

«የናንተን መድረስ አስቀድሜ ወሬው እንዲነዛ አደርጋለሁ። በሚቀጥለው ቀን እኩለ ቀን ላይ፣ በተቻላችሁ መጠን በጨዋነትና በክራት ትመጣላችሁ። ከባሮቹ አንዱ፣ በዕድሜ ጠና

ያለው፣ የአግሩን ሽባነት ለመደበቅ ቁርጥራጭ ጨርቆችን እንጠመጥምበትና በሌላው በቅሎ ላይ ሆኖ ይከተልሃል። ሁሰቱ ህፃናት በእህቶች ላይ ሆነው ከኋላ ይከተላሉ።»

ሙራድ ጭንቅላቱን አነቃነቀ።

«ለመሆኑ ሣጥንህ ውስጥ ስንት ልብሶች አሉህ?» አለ ፖንሴ

«አንድ»

«በመጠባበቂያነት ያዝው። በይፋ የምትታይበት ቦታ ስትደርስ ቀይረው። ወደ ከተማዋ መግቢያ ላይ ስትደርስ ሰላምታ ሊያቀርቡልህ የሚመጡትን ሰዎች እጅግ ረዥም፣ አስቸጋሪና አደገኛ ጉዞ አድርጉ የሚመጣውን ሰው እባካችሁ ተጪት በላቸው።»

ከዚህ በኋላ በጥቂት ተጨማሪ ጉዳዮች ላይ ተወያይተው ከተስማሙ በኋላ፣ ጊዜው ስለመሸ በእሣቱ ዳር በየጆንያዎቻቸው ላይ ተጠቅልለው ተኙ ። ጆን ባፕቲስት፣ ታላቅ ፍንደቃ ተሰማው። መላ አካሉ፣ አንድ ሺህ አንድ የድካምና የሕመም ስሜት ለቀቀበት። ላለፈው አንድ አመት ከስራቸው ሆኖ ያደረባቸውንና በቅርቡ የሚለያቸውን የከዋክብት እይታም አሰበ። በቅርብ ያለችውን ካይሮና የአሊስ ልዩ ስሜት አዕምሮውን ሞላው። ሁሉም ነገር ተስፋ የሚያስቆርጥ ቢሆንም እንኳ አንድ ተጓዥ በጉዞ ጀማሮው ላይ ትዕግስት አያጣም። ስለሆነም በጉዞው መሃል ላይ የነበረው ትዝ አለው። ታዲያ አሁን በመመለሻው ሰዓት ላይ መዘግየቱ ለምንድን ነው?። ደቂቃዎች እንዲህ እየተንቀራፈፉ የሚያዘግሙት ለምንድን ነው? በተለይም ሰላም በሚያገኝበትና ሁሉንም በመጨረሻው ላይ በሚያውቅበት ሰዓት ለምንድን ነው ጥቂቶች እንቅፋት የሚሆኑት? ሲል ይጠይቃል።

የመመለሱን ሃሣብ ጆን ባፕቲስት ለረዥም ወራት በውስጡ ሲያሣድገው ቆይቷል። አሊስን፣ ፍቅሯንና እስከ ዘለዓለም የሚጣመሩበትንም ሁኔታ አስቧል። ነገር ግን የሚወድዳትን ሴት፣ በዓይኖቹ ሥር የሚያኖርበትን፣ ራሱንም ለታላቅ ደረጃ ለማብቃት፣ ድንጋይ በድንጋይ ላይ በመገንባት መላውን ሕንፃ እንዴት እንደሚሰራው በቅፅበት አሰበ። በመካከላቸው ያለው ርቀትና ልዩነት ምንም ያህል የሰፋ ቢሆንም፣ ከተለያዩና ግራ ከሚያጋቡ ደካማ ተስፋዎች የተሠራ የሃሣብ ሕንፃ ቢሆንም፣ ትዝታውን ይጠግንለታል። ጥቂት ረዘም ካሉ ያለፉ ቀናት የተሰበሰቡ ያልተሟሉ የዕይታና የድምፅ መረጃዎችን ይዞ፣ በመሠረቱ አይታው የማታውቀው

ሴት ታፈቅረኛለች ብሎ ማሰቡን፣ በሚገባ የማታውቀው ሴት ትጠብቀኛለች ብሎ በጭፍን የሚወራረድ መሆኑን፣ ይህ ሁሉ ሃሣብ እንዴት በሚከዳ በአሸዋ ላይ የተገነባ ሕንፃ እንደሆነ ተገንዘበ። ይህን እያሰላሰለ ረዥም ቦታን ሰረዥም ጊዜ ተጓዘ። ይህ ታዲያ ከራሱ ፍላጐት ሌላ ሊሆን ይችል ይሆን? ያንን ሌሊት በነዚያ ስለታም የምድረ በዳ ድንጋዮች ላይ ሳይመቸው አረፍ ብሎ፣ ጆን ባፕቲስት፣ አሊስ ታፈቅረው እንደሆነ ብቻ ሳይሆን፣ ኩቶውንም እርሷ በዚህ ዓለም ላይ በርግጥ ኖራ ይሆን ሲል ራሱን ጠየቀ።

በመጨረሻም ይህን የመጨረሻ ሠፈር እኩለ ለሊት ላይ ለመልቀቅ ወሰነ። ባለፈው ቀን ሁሉም ነገር እንደታቀደው ተከናውኗል። ሜትር ዣረሚ፣ እንደልማዱ እያጉረመረመ በአሌክሣንደሪያ አቅጣጫ ሄዷል። በጣም እንቅስቃሴ በሚበዛበት የሲራራ ነጋዴዎች ማረፊያ ስለሠፈሩ፣ ሙራድ ተፅናንቷል። በዚህም ላይ ሁለት ሚሊሺያ ወታደሮች ሰሊቱን እዚያ ለማሣሰፍ ወስነዋል። ሁሉም ሰው ስለደከመው በጊዜ ተኛ። ሙራድም ወዲያውኑ በከፍተኛ ድምፅ ማንኮራፋት ጀመረ። ጆን ባፕትስት በበኩሉ እንቅልፍ እንደማይወስደው አውቋል። በፀጥታ ፈረሱን ጫነው። አህያውንና ሌላውን መሣሪያውን ሁሉ በሚቀጥለው ቀን ወደ ከተማ እንደሚደርሱ ስላወቀ ከቀረው ዓዝ ጋር ተወው። ሲነሳ ግን፣ ንፁህ ሸሚዙን፣ ቦላሌውንና ኮቱን ለብሶ ብቻውን ወጣ። በምዕራብ በኩል ትልቅ ነጭ ጨረቃ መንገዱን እንደ ክረምት ፀሐይ ወገግ አድርጋ፣ በማብራቷ ታሣያለች። ቀኑ የሚያንገበግብ ሙቀት በመሆኑ ከአንዳንድ ኪስ ቦታዎች ላይ ባሉ መንገዶች ሞቃት አየር ይጋረፋል። ብቸኛው ሰው እንደ ብዙ የሃር ኮቶች መውሰብሰብ ብቅ ጥልቅ እያለ ይጋልባል። በምድረ በዳው መሬት ላይ የፈረሱ የኮቴ ምት እንደ ብዙ የልብ ትርታዎች የገደል ማሚቶ ፈጥሮ ይሰማል።

ጆን ባፕቲስት፣ በፕቶሎሚ ቤተመቅደስ ፍርስራሽ ስር ሲያልፍ፣ ዓለም ገና በጨለማው ውስጥ እንደጠለቀች ነች። የጊዜውን ማጠር ማስላሰል አልፈለገም። ይልቁንም፣ እርሱ በተቃራኒው፣ የእያንዳንዷን ሴኮንድ ዘለዓለማዊነትና ክቤቱ ተለይቶ የቆየበትን ማብቂያ የሌለውን የጊዜ አዝጋሚነት ያስባል። ሰማይና መሬት ሲላቀቁ ካይሮ ደረሰ። ዘበኞቹ ሁሉ ተኝተዋል። በሮችም ዝግ ነበሩ። ውብ ልብስ የለበሰና ምንም መሣሪያ ያልታጠቀውን ፈረንሣዊ ከተመለከቱ በኋላ ምንም ጥያቄ ሳያቀርቡለት እንዲገባ ፈቀዱለት። እንደግራጫ ጥላ ከወዲያና ከወዲህ በመዋከብ ላይ ከሚገኙት ለማኞች በስተቀር፣ ከተማዋ አሁንም በእንቅልፍ

ላይ ነች። ከፀሐይዋ ጋር ቀዝቃዛ የነፋስ ሽውታ አብሮ መጣ። ወፎች በፈጣን በረራቸው ከአናት በላይ ሽው ሽው እያሉ ይዘምራሉ።

ሽማግሌው የፈረንሣውያን ማህበረሰብ ሰፈር ጠባቂ፣ ፖንሴን ገና ሲጋልብ እንዳየው የመስኬቶ ጠመንጃውን ሊተኩሱበት ነበር። ነገር ግን ወዲያውኑ ለየውና የደስታ ፖኸቱን ለቀቀው። ጆን ባፕቲስት ግን ዝም እንዲል ገሰፀው።

በመጨረሻም ወደ ዋናው ጉዳና ሲገባ፣ የቆንሲላው ግቢ ግማሽ መንገድ ያህል ዝቅ ብሎ በነፖ ሜዳ ላይ ባንዲራው ሲውለበለብ ተመለከተ። በረዥም መንገድ ስግሪያው የተነሣ ፈረሱ አረፋ ደፍቆ፣ ሳይመሩት ይራመዳል። ጋላቢውም፣ መኮርኮሩንና ማጣደፉን በመተው ለኮውን ቀዳማዩ ላይ አሳርፎታል። ጆን ባፕቲስት ቀና ብሎ፣ የአሊስን መስኮት ተመለከተ። መስኮቱ ክፍት ነው። ቢሆንም መጋረጃዎቹ ወርደዋል። በዚህ ሰዓት ከዚህ ንድፉ የተገላቢጦሽ ታትሞ ከሚታየው ሰማያዊ የጥጥ ጨርቅ በስተቀር በርሱና በርስዋ መካከል ሌላ መስናክል የለም። ሊለያቸው የሚችል ምድረበዳ ወይም ተራራ ወይም የዱር አውሬ የለም። አሁንም ቢሆን፣ ሁለቱን የለያያቸው የፍቅር ጉዳይ በተነሣ ቁጥር፣ የመረዳዳትና የመደጋገፍ ጥያቄ በተወሣ ቁጥር፣ ለምች በመሳከላቸው ያበጁት ደካማ፣ ነገር ግን ለጊዜው ጠንካራ ግርዶሽ ብቻ ነው። ጆን ባፕቲስት ከማስተዋሉ በፊት ፈረሱ ቆመ።

በአትክልቱ ስፍራ ውስጥ የሚንቃጨል ድምፅ ተሰማ። ምናልባትም ጠባቂው፣ ይህ እንግዳ ሰው ምን እንደሚፈልግ ለማየት ሲቀርበው ይሆናል። ሆኖም፣ ቅጭልጭልታው ጆን ባፕቲስትን ከቀን ህልሙ አነቃው። ፈረሱን እንዲራመድ አደረገው። በመጀመሪያው መንገድ ተጠምዝዞ የሰመደውን ግን የረሣውን ቁልቁለት መንገድ አግኝቶ ወደ ቤቱ ሄደ። ከፈረሱ ላይ ወርዶ፣ በመሺለኪያው ላይ ባለ የቀለበት መቀርቀሪያ ላይ ካሠረው በኋላ ወደ ቤቱ በር አቀና። ቁልፉ እንደተሰመደው በተሸፈፈው ግድግዳ ውስጥ ባለው ጉድጓድ ተደብቋል። በሩን ከፍቶ ገባ። የታችኛው ቤት ወለል አሁንም ጨለማ ሲሆን፣ በፎቁ ላይ የሚገኘው የርሱ ክፍል ግን ብሩህ ቀን ሆኗል። በክፍሉ ውስጥ አንዳችም የተለወጠ ነገር የለም። በዓለም ውስጥ ወዳለ ሩቅ ቦታ ሄዶ ስለነበር፣ ሌላው ቀርቶ ራሱ ያለፈበትን ዱካ እንኳ አጥቶ ነበር። እንደተረት ተረት ከሚታሰቡና በቀላሉ ከማይደርስባቸው ሰዎችም ጋር ተነጋግሯል። በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ ሊገደልም ነበር። በውሃ ውስጥም ሊሰምጥ ነበር። ረሃብም ሊገድለው ነበር። ልክ እንደሀልም፣ እውነት በማይመስሉት ተንጠልጣይ የፋሺያ ተክል፣ ሃምራዊው አበባ እያደጎ ነው።

የአጋቬው ዕፅ፣ በህይወት ዘመኑ አንዴ የሚያብበውን አበባውን፣ በረዥሙ ዘንጋማ ሽካራ ግንዱ ላይ ያወዛውዘዋል። አራውካሪያው መቅሳት ጀምሯል። የብርቱካን ዛፎች ፍሬ አበጅተዋል። የተክሎቹ አዝጋሚ ታዛዥነት፣ በተጨነቀችው ህይወቱ ውስጥ ያለፈው ሳይቋረጥ፣ ወደ አሁኑ ማለፍ የሚያስችለውን የመተላለፊያ መስመር አበጅተዋል።

የተክሎች ተፈጥሮአዊ እድገት፣ የሰውን ልጅ እጆች በማፍቀራቸው ምን ያህል በቁጥጥር ስር እንደሆኑ፣ ምን ያህል እየተመሩ እንደሆነ ቁምር፣ ጆን ባፕቲስት ተመለከተ። ጥቂት ወንበሮች በበረንዳው ላይ እዚያና እዚያ ከመታየታቸው በስተቀር፣ አርሱ አስከሚያስታውሰው ሁሉም ነገሮች ባኖራቸው ሥፍራ ላይ ናቸው። መከራ የማይችለው ስብስብ፣ ብርታቱንና ሥርዓቱን፣ ምርታማነቱንና መጠኑን ጠብቆ ሊያየው ያልተቋረጠና ከመጠን በላይ የሆነ ክትትል እንደተደረገለት አወቀ። በአዕዋቱ መካከል ያለው ስላምና ርጋታ የተጠበቀው፣ በሚቀናቀኑትና በሚበጣበጡ ተክሎች መካከል ሚዛናቸው ተጠብቆ እንዲቆዩ ያደረገው የተንከባካቢያቸው ብልሀነት አለ። ከመጀመሪያ ዕይታው ጀምሮ እንዳልተዋቸው ተረዳ።

ይህንን ካረጋገጠ በኋላ ከባድ ድካም በሰውነቱ ሁሉ አረፈ። ሙሉ ልብሱን እንደለበሰ፣ የፈረስ መኮርኮሪያው ከጫማው ጋር እንደታሰረ፣ ወደተንጠልጣዩ አልጋው ሄዶ ተጋደመ። ጉዞው የፈጠረበት የመንፈስ ጭንቀት፣ ባለማቋረጥ የቆየበት ጥንቃቄና አመቱን ሙሉ የንበረው ሙሉ ንቃት በአንድ ጊዜ ከላዩ ላይ ወረዱ። በድካም ላይ ያነማው ብርታት፣ በጥቂት ክሮች ብቻ ተይዞ የነበረው የውቅያኖስ ማዕበል ድካም፣ አሁን ብጥስጥሱ ወጣ። ዓይኖቹን ጨፍኖ ወደ እንቅልፍ አለሙ ሄደ።

ጆን ባፕቲስት፣ በሃይለኛው ህልም ላቢያ ነቃ። በአትክልቶቹ አጠገብ አንድ እጇ አፏን አፍና፣ አይኖችዋ በፍርሃት ፈጥጠው፣ ፍራንቾይዝ ቆማለች። ማንነቱን ስታውቅ ፊትዋ ተለወጠ።

«አ! በመጮኤ አዝናለሁ። ሙሴ ጆን ባፕቲስት፣ ሙሴ ጆን ባፕቲስት፣ በርግጥ አንተ ነህ? እንዴት ማወቅ እችላለሁ? አምላኬ ! እንዴት ተሰወጠሃል?»

ተንጠልጣዩ አልጋ አጠገብ ደርሳ፣ የወጣቱን ሰው እጅ ያዘችና ሣመችው።

«አምላኬ ! በጣም ከስተሃል። ያ ጉንጭህን ይሞላው የነበረው ዒምህም ይበልጥ ጉድጉዷል! ፀጉርህ በጣም አድጓል!»

አይናችዋ እንባ እንዳዘሉ ታየው ጀመር። አርሱ በበኩሉ ስሜቱ በጣም ስለተነካ ቃል መተንፈስ አልቻለም።

«እንዴት ያሉ ውብ ልብሶች ናቸው?» አለች፣ ልዩ ልዩ ጥልፍ የተሰራበትን ወፍራም የቀይ ኮት ጨርቁን እየነካች።

በባህር ላይ ዘራፊዎች ተይዛ የነበረችው መርከብ ከፍተኛ ዋጋ ነበራት ማለት ነው። ጆዳ ውስጥ ስለጉዳዩ እምብዛም አትከሮት ያልተሰማው ጆን ባፕቲስት፣ እንደጨዋ ሰው መልበሱን እሁን ተገነዘበ።

«ርቦሃል?» ስትል ፍራንቾይዝ ጠየቀችው። ራሷን ስትገዛ «ጠምቶሃል?» ቆይ ከቤት የሆነ ነገር አገኛለሁ።

«የለም» አለ ጆን ባፕቲስት «አትቸገሪ፣ ይደርሳል፣ በኋላ፣ በኋላ፣ ብቻ የት እንዳለች ንገሪኝ»

«አ! ሙሴ ጆን ባፕቲስት፣ ስትጠይቃት መስማቴ ለኔ ደስታ ነው። ይህ ማለት ደግሞ አልረሃሃትም ማለት ነው። በጣም ሩቅ አገር በመሄድህ ምክንያት ፍርሃት ነበረብኝ። ለርሷ ግን ሁልጊዜም በተሰፋ እንድትጠብቅህ እነግራት ነበር። በህይወት መንገድ ውስጥ ብዙ ነገሮች ሊያጋጥሙና የልብ ስሜትም ሊለወጥ ይችላል»

ጆን ባፕቲስት ተነስቶ፣ እግሮቹን ከአልጋው ልብሶች ውስጥ አውጥቶ ቀጥ ብሎ ተቀመጠ።

«ሊለወጥ ይችላል? የኔ ግን በምንም ምክንያት አይለወጥም። የሆነው ሆኖ እባክሽ የት እንዳለች ንገሪኝ? ስመሆኑ ሃሣቢስ እንዴት ነው?»

«ሃሣቢ ሁሉ አንተኑ የማፍቀር ነገር ነው። ከዚህ ከሜድክበት ዕለት ጀምሮ ካንተ በስተቀር ሌላ አስባ አታውቅም።»

«አ! ፍራንቾይዝ» አለ ጆን ባፕቲስት በክንዶቹ እያቀፋት ወይም እናቱ የሆነች መስሎት በርሷ ክንዶች ውስጥ እየገባ።

ከዚህ በኋላ የፍራንቾይዝን ትልልቅ እጆች በእጆቹ ውስጥ ይዞ ወደ ኋላ ራመድ አለ።

«ወደዚህ ትመጣለች?»

«በየዕለቱ»

«መቼ?»

«አ . . . » አለች ፍራንቾይዝ እየውጣች ያለችውን ፀሐይ በመስኮት በኩል እያየች «በዚሁ ሰዓት አካባቢ»

በጉጉት ስሜት፣ ጆን ባፕቲስት ዘሎ ተነሣ

«መምጣት የለባትም . . . » አለ። «ሂጅና እንዳትመጣ አድርጊያት። መመለሴን ንገሪያት። ነገር ግን በዚህ መልክ ሆኜ ልታየኝ አይገባትም። ለመሆኑ ማኑኤል እስካሁን እዚሁ ነው?»

ማኑኤል በዚህ ግቢ ውስጥ ለረዥም ጊዜ የኖረ ሽማግሌ አገልጋይ ነው። የቀድሞው ጌታው ወደ ፈረንሣይ ከመመለሱ በፊት፣ ጥቂት የጡረታ ገንዘብ ተቶለታል። ምንም እንኳ ዲዳ ቢሆንም፣ እስካሁን ድረስ ጠንካራ ሰው ስለሆነ፣ ፖንሴና ሽሪኩ በየጊዜው ሥራ ይሰጡት ነበር።

«አቤት ነው ያለው» አለች ፍራንቾይዝ

«ጥሪው። በገንዳው ውስጥ ውሃ እንዲሞላልኝና ሣሙናም እንዲያመጣልኝ ንገሪው። በተጨማሪም ፀጉሬንና ጢሜን እንዲያስተካክልልኝ እፈልጋለሁ። አንቺም ፍራንቾይዝ፣ ልትንከባከቢኝ ይገባል።»

«ቆስሰሃል እንዴ?»

«እግዚአብሔር ይመስገነው ውስጤ ሴናማ ነው። ነገር ግን ውጫዊው አካሌ ብጥስጥስ ብሏል።»

ፍራንቾይዝ ሥራዋን ወዲያውኑ ጀመረች። በዚህ ጊዜ ውስጥ፣ የጆን ባፕቲስት አዕምሮ ግን በሥራ ላይ ነበር።

«ከአጭር ጊዜ በኋላ በቆንስላው ፅሀፊት ቤት መገኘት ይኖርብኛል። መመለሴ አንድ ጊዜ ከታወቀ ወደዚህ ሰዉብኘት መምጣት አትችልም። ታዲያ እንዴት አድርገን ነው መተያየት የምንችለው?»

«አትጨነቅ፣ አንተ እዚህ ባልነበርክባቸው ጊዜያት ውስጥ ብዙ ነገሮች ተፈፅመዋል። በአሁኑ ጊዜ አኔም፣ ለማጸም ዴ ማይሌ በማገልገል ላይ ነኝ። ወደ ቆንስላው ደስ እንዳለኝ እገባለሁ። አወጣለሁ። ቤቱ ግን እዚሁ ነው። ለማንኛውም አስፈላጊውን ሁሉ እናዘጋጃለን።»

«ፍራንቾይዝ! » አለ ጆን ባፕቲስት እጆችዋን እየሳማቸው።

ሮማ ለመሄድ የተዘጋጀች መስለች። የፎቱን መውጫ የመጀመሪያውን ደረጃ እንደደረሰች በተቻላት መጠን በጣም በተለመደ ድምፅ ተናገረች። ምናልባትም ተቀባይነት ያለውን አንድ ጉዳይ ለማንሣት ፈልጋ ይመስላል።

«ሽሪክህ ሚትር ዝረሚ መቼም አብሮህ አይደለም?»

«አይደለም» አለ ጆን ባፕቲስት ከዋያቁው እንዳች ነገር ለማንበብ ሳይችል ቀርቶ። «አሌክሳንደሪያ መሄዱን ታውቂ የለም እንዴ?»

«ጀመርክ እንግዲህ፣ ከእኔ ጋር መቃለዱን ተወው። ዘመቻህን መቀላቀሱን በትክክል አውቃለሁ።»

ካይሮን ለቅቆ ሲወጣ፣ ሚትር ዝረሚ፣ ለፍራንቾይዝ መመሪያ ሰጥቷታል። ምስጢራዊውን እቅዱንም ነግሯታል። ምስኪኗ ሴትም፣ ከተራ ምስጢርነት ባሻገር ነበር የተቀበለችው። ይህንንም ምስጢር ብርቅ ምስቢር አድርጋ፣ ከአሊስ ሣይቀር ደብቃ አቀይታዋለች። በርግጥም ደግሞ ከለውዱው ጋር የተጋራችው ነገር ቢኖር ይህን ብቻ ነው።

«በይ እንግዲህ ሌሎች ሁሉ የሚያምኑትን አንችም እመኚ። እርሱ የሄደው ወደ አሌክሣንደሪያ ነው። ነገር ግን» ፖንሴ ንግግሩን ቀጠለ «በሚቀጥሉት ሁለት ቀናት ውስጥ እዚህ እንደሚመጣ አንዳች ነገር ሊነግረኝ ይሰማኛል»

3

ጆን ባፕቲስት፣ ካይሮ ውስጥ ባልነበረበት ጊዜ ምንም ነገር አልተለወጠም ብሎ ማሰቡ ትክክል አልነበረም። ሆኖም ይህን ያረጋገጠው ቆንሲላው ግቢ ሲገባ ነበር። ጉዳዩን በስፋት ከተመለከተው በኋላ፣ ቆንሲሉ፣ በትልቁ የእንግዳ መቀበያ ውስጥ ያለውን ጠረጴዛውን ከአንድ ጥግ ወደ ሌላው አሟዙሮታል። በዚህም መሠረት ጠረጴዛው እንደ ቀድሞው በመስኮቱ አጠገብ ሳይሆን በቀጥታ በንጉሡ ሥዕል ስር ያለውን ቦታ ይዟል። ቆንሲሉ ከንፁህ አየር ሊያገኘው ያልቻለውን ግርማ ተጐናፅፏል። ጥንቃቄ በተሞላውና በልዩ ሁኔታ፣ ጥቁር፣ ሰው ሰራሽ ፀጉሩን አጥልቋል። ጥብቅ ያሰና ሲከፈት የፎሊየር የሐር ሰደሪያውን የሚያሣይ ባለወርቅ ዝምዝማት የቁልፍ ቀዳዳዎች ያሉት ጥቁር ለማያዊ ልብሰ ለብሷል። ከዚህ ቀደሙ ጊዜ ይበልጥ ቢያልበውም፣ በተሰመደው ብርታቱ ዋጥ አድርጐ ችሎታል። ከሰዓት በኋላ፣ አስር ለወት አካባቢ ፖንሴን ተቀበለው።

ከነሃስ የተሠራ የተንቆጠቆጠ የቀለም ብልቃጥ መደረደሪያ በስተቀር ሌላ ከሌለበት ትልቅ የተስፋ ቆዳ ከለበሠው ጠረጴዛ በስተጀርባ ተቀምጠ፣ ሙሴ ዴ ማይሌ፣ እንግዳው እንዲቀመጥ እንኳ ሳይጋብዘው፣ የሚነግረውን መግለጫ ያዳምጣል። ጆን ባፕቲስት ፂሙን ተላጭቶና ፀድቶ፣ ፀጉሩን ተስተካክሎ ቢታይም፣ አሁንም እንደደከመ ሲሆን፣ ነጭና ጥቁር በሆነው የወለል ምንጣፍ ላይ እንደ ቼዝ ጠጠር ተንትሮ ቀረ። ዲፕሎማቱ፣ ውይይቶችን አጭር ከሚያደርግባቸው አነስተኛ ታክቲኮች አንዱ ይህ ነው። ሌላው፣ አሁን እንደሚያደርገው መጥፎ ቁጣን በግልፅ ማሳየት ነው።

ቆንሲሉ፣ የመድሃኒት ቀማሚው ተልዕኮ ማብቃቱን ግልፅ ለማድረግ ፈልጐ ነበር። ከዚህም በላይ፣ ሰውዬው ገና ሲደርስ ከቀረበለት አጭር የእንኳን ደስ ያለህ መግለጫ ባሻገር፣ ሌላ እንዳይጠብቅ የሚልም ነበር። ፖንሴ፣ ጅዳ ሆኖ የላከው ፖስታ ከአንድ ሣምንት በፊት በመድረሱ፣ ቆንሲሉ ይሠማውና ያስበው የነበረውን ጉዳይ የሚሰውጥበት ምክንያት በፖንሴ መምጣት ተክስቶ ይሆናል። በአሁኑ ገዜ እጅግ አሣሣቢው ነገር በተሰይም የቆንስሉ ብቸኛው ሞንቀት፣ የንጉሡን መልዕክተኛ እንኳን ደህና መጣህ የማሰቱ ነገር ነው። ይህ መድሃኒት አዋቂ ለጥቂት ጊዜ መልዕክታቸውን በማድረስ ጠቃሚ የነበረ ቢሆንም፣ በአሁኑ ጊዜ ጉዳዩ

አለምን በሚያተራምሷት ዲፕሎማቶች እጅ ስለሚገባ አንድ ተራ፣ አግሪኖና የልምድ መድሃኒት አዋቂ፣ ሣይሣለቁበት አድገት ሊመኝ እንደማይችል ሊረዳው ይገባዋል። ለኢትዮጵያ ኤምባሲ ተዝዚውን አቀባበል ለማድረግ፣ ሙሴ ዴ ማይሌ አግባብነት ያላቸው ጥያቄዎችን ጠየቀ። የመልዕክተኛውን ስም፣ የክብር ተከታዮቹን ብዛት፣ የተጓዘበትን አቅጣጫና እዚህ ሊደርስ የሚችልበትን ሰዓት ግምት ጠየቀ። ወጣቱን ሰው፣ በጉዞው ላይ ስለነበረው ጀብዱ ላለማሞገስ፣ ቆንሲሉ ጥሩ ጥንቃቄ አድርጐ አለፈው። ተጓዡም በዚህ ነጥብ ዙሪያ ፍንጭ ሲያሣየው፣ እንዲህ ያሉትን ዝርዝር ጉዳዮች በርሱ ደረጃ ያለ ሃላፊ ሊሰማው እንደማይገባ ግልፅ አደረገ። ስለነዚህ የጉዞ አጋጣሚዎች ሁሉ፣ ቆንሲሉ ጆሮውን ቢሰጥ ሊበዛ ጅልነት ይሆናል። ሰውዬውም፣ እነዚህ ጀብዱዎች ለክብሩ ብቸኛዎቹ መሠረቶች ስለሆኑ ለራሱ ጠቀሜታ ሊያስተካክላቸው እንደሚጥር እርግጠኛ ነበር።

ጆን ባፕቲስት ፍፁም ደክሞታል። ወደ ቆንስላው ግቢ ሲገባም ሞልቶት የነበረው ጥልቅ ስሜትና አሊስን በድንገት የማግኘት ተስፋው ሁሉ፣ ስርዓተ ቢስነቱን በመመገብ ሊጠቅመው የሚችለውን የወኔ ሃይሉን፣ ተስፋ አስቆራጭ ወደሆነ መልክ ለውጦታል። ያጋጠመው የእንኳን ደህና መጣህ አቀባበል፣ ከቆንሲሉ የሚጠብቀው አይነት እንደሆነ አውቋል። ይሁን እንጅ፣ ከምሩ፣ ምናልባትም ይህንኑ ተስፋ አድርጐ ነበር። ሆኖም እጅግ ጥልቅ የቅሬታ ስሜት አደረበት።

«መስናበት እንድችል የቆንሲሉን ፈቃድ ባገኝ?» ሲል ወደ በሩ እየተራመደ ጆን ባፕቲስት ጠየቀ።

«አመሰግናለሁ» አለ። ለመልካም ተግባር የሚገባውን ሽልማት በሚገባ የሚያውቀው ሙሴ ዴ ማይሌ።

«ደህና ሁን ሙሴ ፖንሴ»

ወጣቱ ሰው ወጥቶ ሄደ። በውይይቱ ወቅት በእንድ ጨለማ ጥግ ቆይቶ የነበረው ማቼ፣ ወደ ቆንሲሉ ጠረጴዛ በመቅረብ ወደፊት ጐንበስ በማለት በተጣደፈና ዝቅ ባለ ድምፅ ተናገረ።

«ክቡር ሆይ፣ ኤምባሲውን ለመገናኘት የሚሄደውን የመልዕክተኞች ቡድን ይህ ሰው እንዲያጅብ ቢደረግ ተገቢነት የለውም ማለት አይቻልም»

«እሱን? እና በምን ሚና?» ሲል ሙሴ ዴ ማይሌ ጠየቀ።

«እንደሚመስለኝ . . . የንጉሡ መልዕክተኞችና ይህ መድሃኒት ቀማሚ ርስ በርስ ይተዋወቃሉ። ቢያንስ ቢያንስ፣ ከርሱ ጋር የሚኖረን የመጀመሪያ ግንኙነት ቀላል ይሆናል። አምባሣደሩም፣ የንጉ ንደኞቹ የት እንዳሉ ይጠይቅ ይሆናል . . »

«ልክ ነህ። አሁንም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ወጣ ብለህ በመንገድ ላይ እንዳለ ተመልከተውና፣ መገኘት እንደሚገባው ንገረው» አለው ቆንሲሉ።

ልብስ አጣቢዋ፣ ጥሩ መዓዛ ያለውን ትኩስ ሽቶ በተፈጥሮ በሚያመነጨው ጠረኑ ፋንታ ልብሱ ላይ ስለረጨችበት፣ ሙሴ ማቼ ወደ በሩ ሲንደረደር ሽታው በክፍሉ ውስጥ ቀረ።

አዳራሹን አቋርጦ ደረጃው ላይ ፈጥኖ ደረሰ። በዚያም ሳይታሰብ በመንገዱ ላይ ራቅ ብሎ አገኘዋለሁ ብሎ ከሚያስበው ፖንሴ ጋር ተሳተመ። የቀርከሃ ቅርጫት በክንዷ ስር ይዛ የነበረችው ፍራንቾይዝ፣ ከመድሃኒት ቀማሚው ጋር በመወያየት ላይ እንደነበረች አመነ። እርስዋ ግን ፀሐፊውን እንዳየችው አንዳችም ነገር ላያቋርጣት፣ ከልትክልቱ ሥፍራ በቀጥታ እንደመጣች አስመስላ ወደ ቤት ገባች። ምንም ነገር የማይዘነጋው ሙሴ ማቼ፣ በተለይም አብራርቶ ሲገልፀው የማይችለውን ነገር የማይዘነጋው ሙሴ ማቼ፣ በርቀት ከዝና በሚያቆይበት፣ ነገር ግን በሚገባ ሰይቶ ሊያውቀው በሚችልበት የአዕምሮው ክፍል ውስጥ፣ «ጠርጥር» የሚለውን ግምታዊ ሃሣቡን መዘገበ። ምንም እንዳላስተዋለ ሆኖ፣ ጆን ባፕቲስትን አናገረው።

«ነገ ጠዋት፣ ለአምባሳደሩ ሰላምታ ለማቅረብ ከሚጓቀሣቀሰው የመልዕክተኞች ቡድን ጋር ተቀላቅለህ ለመሄድ ራስህን አዘጋጅ። በሰዓቱ ላይ አስክ አሁን ያልወሰንን ቢሆንም፣ ጊዜው ሲደርስ በተረኛው ወታደር በኩል መልዕክት እንልክብሃለን።»

ሙሴ ማቼ እንደማቅማማት ብሎ፣ ሙሉ በሙሉ የግሉን ምክር እንደሚለግስ ሰው፣ ዝቅ ባለ ድምፅ «እናም ተስማሚ ልብስ ልበስ። እዚህ የምንነጋገረው ወደ ንጉሡ ከሚሄደው ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ጋር ነው።»

ጆን ባፕቲስት በመገረም ተመለከተው። በጭንቅላቱ ውስጥ፣ አንዳች ድምፅ በሰውዬው ላይ ጮክ ብሰህ ማቅበት የሚል ሲሰማ፣ ሌላው ድምፅ ደግሞ ይህን አስቂኝ ሰው ሽቅብ ተቀልብሦ የታሰረውን ከሴታውን በመያዝ አንተኸው ጭንቅላቱን ከግድግዳው ጋር አጋጨው ይሰዋል። ሆኖም እነዚህን ሁሉ አልሰማቸውም። የሃዘንና የፍሬቢስነት ስሜት ስለተሰማው ይህን ሁሉ የሚያስወግድለት እንቅልፍ እንደሚሆን አሰበ። በተረከዙ ላይ እንደመሽከርከር ብሎ ዞሮ፣ ማንንም ሳይገናኝ ወደ ቤቱ ሄደ።

በቆንስላው ጽህፈት ቤት በር ላይ እንዳገኘችው፣ ፍራንቾይዝ ጥቂት ቃላትን ብቻ ልትተነፍስለት ነበር። የቻለችው

«ዛሬ ልታይህ አትችልም»

ጆን ባፕቲስት እነዚህን ቃላት አሰላሰላቸው። እቤት እንደደረሰም በጥልቅ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሰጠመ። ይህ አይነቱ ተስፋ መቁረጥ፣ በአንዳች ድራማዊ ክንዋኔ የተነሣ የተፈጠረ ሳይሆን ይልቁንም በዙሪያህ ያለው ሁሉም ነገር የሚቻል የሚሆነው፣ አንድ ሰው ሲኖርህ፣ ወይም አለኝ ብለህ ተስፋ ስታደርግ የሚመጣ አሳዛኝ ክንዋኔ ነው። ይሁን እንጅ፣ ይህ አንድ ሰው፣ ባሆነ መልኩ ጉድ ቢያደርግህ፣ ከዚያ በኋላ፣ አስደሳች የነበረችው ዓለም ወደ ፍርስራሽነት ትለወጣለች። በውስጧ ያሉት ሰዎች ሁሉ መርዛም፣ ከሃዲዎችና የሚያበሳጉ ይሆናሉ።

ፍ

አሊስ፣ አሁንም በአልጋዋ ውስጥ ብትሆንም መንፈሷ አልተረጋጋም። በትልቅ ተስፋና ሁልጊዜም እየታሰበ የነበረው የጆን ባፕቲስት መመለስ አሁን ከሆነ ነገሮች አንዳንድ ጊዜ እንደሚሆኑት፣ ሳይታሰቡ ልውጥውጥ የሚሉና፣ እርሷንም ማስተዋል ተስኗት የተተበተበች መሰላት። ለዕለቱ የአፅዋት እንክብካቤ ሥራዋ ለመሄድ ስትዘጋጅ ፍራንቾይዝ በመድረስዋ እፎይታ አገኘች። በአይነ ህሊናዋ በግልፅ የሚታይዋት ችግሮች የፈጠሩባትን ድንገተኛ ድንጋጤ ዋጥ አደረገቻቸው።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጆን ባፕቲስትን ታየዋለች። አንዳችም እቅድ እንዳትነድፍ ሃሣቧ ሁሉ የተመሰቃቀለ ነበር። ፍራንቾይዝ ሁሉንም ነገር በጥንቃቄ ትጠብቃለች። አሊስ፣ ራሷን ዝግጁ

ማድረግ ብቻ ይኖርባታል። አዎን፣ ልክ ነው፣ መዘጋጀት ብቻ ነው ያለብኝ ስትል፣ ወጣት ልጃገረድ አሰበች። ፍራንቾይዝ ወጥታ ሄደች። በመጋጌጫ ጠረጴዛዋ አጠገብ ስትቀመጥ አቅሟ ሁሉ ከዳት።

ባለፈው አንድ ዓመት ውስጥ የኮመራውና በራስዋ ውበት የነበራት ኩራት ሁሉ ተጠርጐ ጠፋ። ፊትዋ ያበጠ፣ መልኳም አስቀያሚ፣ የፀጉርዋ ቀለምም አስጠሊታ መሰላት፣ ተፈጥሮአዊውን ፀጋዋን እንድትገነዘበው ያደረጋት የጆን ባፕቲስት የመጀመሪያ እይታ ነበር። አሁን ግን፣ ሙሉ በሙሉ በርሱ ሰመፈተሽ ስትዘጋጅ ሁሉም ነገር ጠፋባት። እንዳፈቀረችና በምላሹም እንደተፈቀረች እርግጠኛ በነበረችበት ጣፋጭ ሕልም ውስጥ ኖራለች። በተሰመዱ ሁኔታዎች ውስጥ እንዲህ ያሉ የህሊና ትስስሮች ከእውነታው ጋር ድርና ማግ ሆነው በቅርበት የተያያዙ ይሆናሉ። በዚህም መሠረት አንዳችው ሌላኛውን፣ ማንም እንደሚያውቀው በተፈጥሮ ያጠናክረዋል። ድንኳኑም በእውነታና በዓይነህሊና፣ በተግባርና በፈጠራ፣ በትዝታና በምኞት እኩል ይሠራል። ሆኖም፣ እዚህ ግን፣ በተለመደው መለያየታቸው ምክንያት ፍቅር የሸመነው፣ አስፈላጊ ያልሆነው ለስላሣውንና ውብ ቀለሙን ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ገና ሲነካ እንደሚረግፈው የቢራቢሮ ክንፍ ወድቆ ትቢያ ይሆናል።

ተዘጋጅታ እንደምታገኛት በመተማመን ፍራንቾይዝ ወደ አሊስ ክፍል መጣች።

«ምን ነካሽ፣ ፈጠን በይና ተዘጋጅ እንጅ?» አለቻት

«መዘጋጀት አልፈልግም»

«ቆይ፣ ቆይ፣ ምንድን ነው ነገሩ?»

«አስቲ ተመልከችው ይህንን፣ በአፍንጫዬ ዳር ላይ ያለውን»

ፍራንቾይዝ አይኖቿን አንሸዋርራ ቀረብ አለች።

«የፈጠርከኝ ጌታ፣ ምንም ነገር አይታየኝም»

«በርግጥ ርህሩህ ነሽ፣ ነገር ግን የምትዋሺበት ምክንያት የለም። ትልቅ ቡጉር አለበት። እኔ ይሰማኛል። ደግሞም በግልፅ የሚታይ ነው» ቀጠል አድርጋም በቁርጠኛ ቅላፄ

«እንዲህ መሰዬ መታየት አልፈልግም»

«ጀን ባፕቲስት በማንኛውም ሰዓት እዚህ ሊደርስ ይችላል። እንደሚመስለኝ ለእፍታ አየት የማድረግ ጉዳይ ነው። የሚመጣውም ላንቺ ሲል ነው። የሚፈልገው ደግሞ አንቺ እስካሁን እዚሁ መኖርሽንና የምትጠብቂው መሆንሽን ለማየት ነው። መዘጋጀት ያለብሽ ራቅ ያለ ቦታ መሄድ ስለሚያስፈልግሽ ጉዳይ አይደለም። ብቻ ይይሽ። አንችም ታይዋለሽ። ሁለታችሁም፣ እንደሰሜቶታችሁ ትፅናናላችሁ። ወደፊት ደግሞ ረዘም ያለ ጊዜ አብራችሁ ማሳለፍ ትችላላችሁ።»

«ፍራንቾይዝ፣ አይሆንም! ይህ በጉር በጣም አስጠሊታ ነው። እንዲህ ሆኜ እንዲያየኝ አልፈልግም።»

ሰፊ ልምድና ተሞክሮ ያላት ሴት በመሆኑዋ ከዚህ የበለጠ መሎትጉት ጥቅም እንደሌለው ፍራንቾይዝ ተገነዘበች። አሊስ፣ የቡጉሩ ጉዳይ በእውነት ያስጨነቃት ግብዝ አይደለችም። ይህ ሁሉ፣ የፍቅር ጥቃት የደረሰባቸው ሰዎች ላይ የሚታይና የፈለጉትን እንዳያደርጉ ነፃነታቸውን የሚገድብባቸውና ባህርያቸውን አፍኖ የሚይዝባቸው ምልክት ነው። ፍቅር በህዋ ውስጥ የሚጋልብበት ወይም በህልም ውስጥ በነፃነት የሚከንፍባቸውና አያንዳንዱ ተፈቃሪ እንዲፈላለግ ወይም እንዲሸሽ የሚያደርግበት ጊዜያት አሉት። በሌላ በኩል፣ ፍቅር ገና መታወቅ ሲጀምር፣ አንዳች አነስተኛ እንቅስቃሴ፣ ሴላው ቀርቶ ደካማ የአፅ ወይም የከንደ እንቅስቃሴ፣ ሙሉውን ባሪያዎችን ብቻ ከሚጭን መርከብ ላይ ሰንሰለቶችን ለመበጣጠስ ከሚጠይቀው ጥረት የበለጠ ሃይል የሚጠይቅበት ሁኔታ አለ። ይህም ሆኖ ከመጠበቅ በስተቀር ምንም ማድረግ አይቻልም። ፍራንቾይዝ፣ ወጣቱ ሰው ይህን እንዲያውቅ ለማድረግ በአጻራሹ ውስጥ እንደሚተላለፍ ሆና ሄደች። አሊስ፣ በክፍሏ ውስጥ ብቻዋን ሆና ጣቶችዋን ነከሰች።

ፍ

ካይሮ የሚገኘው የፈረንሣውያን ማህበረሰብ፣ የአውሮፖ አገራት ሕዝቦችን ሁሉ የሚያቅፍ ነው። የፈረንሣይ፣ የጣሊያንና የእንግሊዝ እንዲሁም የሌሎች አገሮች ተወላጆችን የሚያቅፍ ነው። አጠቃላይ ቁጥራቸው በብዙ መቶ ከሚሆኑት ከነዚህ ሕዝቦች መካከል

ብዙዎቹ ነጋዴዎች ናቸው። ከአውሮፖውያን አገሮች መካከል ተወካይ ያላቸው ሁለት ብቻ ሲሆኑ፣ እነርሱም እንግሊዝና ፈረንሣይ ናቸው። ይሁን እንጅ፣ በዚህ ወቅት ላይ የእንግሊዝ ልዑካን ቁጥር እንደተሰመደው ፍፁም ስለቀነሰ፣ ቆንሲል የለውም። ስለዚህም ላቅ ያለውን ቦታ የያዘው የፈረንሣውያኑ ነው።

የፈረንሣይ ቆንስላ፣ በአስተዳደሩ ጥላ ሥር የሚገኙ ፈረንሣውያን ላይ ቀጥተኛ ባለሙሉ ሥልጣን ሲሆን፣ በሌሎች አገሮች ዜጋዎች ላይ ግን ሥልጣኑ ቀጥተኛ አይደለም። እነዚህ ሰዎች፣ በቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑና ራሣቸውንም መከላከል የማይችሉ እንደ ማሮናይት ክርስቲያኖች ያሉ ስለሆኑ ፈረንሣይ ትጠብቃቸዋለች። በሌላ በኩል፣ ካይሮ ውስጥ ለጋሊዮን ለሌለው አገር ፈረንሣይ ለነዚህ ዜጐች የመንግስትነት ሚና እንዳላት አድርጋ ትገምታለች።

በነዚህ ማህበረሰብ አባላት ውስጥ ያለት ሰዎች፣ የቆንሲሉን ስልጣን፣ ሁሉም እኩል አይቀበሉም። በምስራቅ ሜዲትራኒያን የአውሮፖውያንን ማህበረሰብ ቁጥር ከፍ የሚያደርጉት ነጋዴዎች፣ ለቆንሲሉ ሥልጣን ያላቸው ክብር የማያስደስትና ፈቃደኞነትም የማይታይበት ነው። ይሁንና ሴላ ምርጫ አልነበራቸውም። በቆንሲሉ ሥልጣን ሥር እንዲሆኑ ያደረጋቸው፣ ቱርኮች፣ በእስላማዊ አገር ውስጥ ለመኖርና ለመነገድ የሚችሉት በዚህ መልክ ሲሆን ብቻ እንደሆነ ስለፈቀዱ ነው። ነጋዴዎቹ፣ ለቆንሲሉ ሥልጣን ተመጣጣኝ የሆነ አቅም እንዲኖራቸውና የነርሱንም አቤቱታ የመቀበል ፅድል ከፍ ለማድረግ ሲሉ የማህበረሰባቸውን ተወካይ እንደራሴ ይመርጣሉ። የቆንስላው ባለስልጣኖችም፣ ፈረንሳውያንን የሚመለከት ማንኛውንም ጉዳይ ለመቀበልና ለመስማት ግዴታ ይኖርባቸዋል። ቀደም ባሉት ጊዜያት፣ ቆንሲሎቹ ሥልጣናቸውን በተወካይ እንደራሴው ላይ ለመጫን ይሞክሩ ነበር። ይህ ድርጊት ግን፣ ውጤቱ መጥፎ ነበር። ሙሴ ማይሌ ሥራውን ለመጀመር ሲመጣ፣ ማህበረሰቡ ያደረገለት አቀባበል ቀዝቃዛ ነበር። ከርሱ በፊት የነበሩት ቆንሲሎች ተመርጠው የወጡት ከራሱ ከማህበረሰቡ ውስጥ ሲሆን የርሱ ሹመት የመጣው ግን ከቬርሣይለስ ነው። ስለዚህ፣ ከመነሻው ሙሴ ዴ ማይሌ፣ የተወካይ እንደራሴውን የግል ድጋፍ ለማግኘት ደፋ ቀና በማለት ጥረት አድርጓል። በዚያን ጊዜ ተወካይ የነበረው ግለሠብ ብሬሎት ይባላል። ይህ ወፍራም ነጋዴ፣ ካይሮ ውስጥ ከሚኖሩደው የሃር ንግድ ተካፋይ የነበረና ሥራውን የጀመረውም ሊዬንስ በምትባለዋ የፈረንሣይ የሃር ከተማ ውስጥ ነበር። ሃብታም ቢሆንም፣ የሚያስፈልገውን ነገር በተመለከተ ሲበዛ ቆጣቢ ነው። እንደሚወራው ከሆነ፣ የወለዳቸው ልጆቹ፣ በቤት ውስጥ ለማኝ

እንኳ የሚጠየፋቸውን የተበሣሱና የተቀዳደዱ ልብሶችን ይለብሣሉ። ቅንጦትን በተመለከተ ደግሞ፣ ፍፁም አባካኝ ሰው ነበር። ሊያስከብረውና ከፍ ከፍ ሊያስደርገው ከቻለ፣ የሃብቱን መጠን ማሣወቅ ውድ አይሆንበትም ነበር። በተለይም ከፍ ማሉቱንና ክብሩን ሊሠጠው በሚችለው ካይሮ ውስጥ በሚገኘው አንድ እውቅ ሰው ዘንድ ከሆነ ችግር የለበትም። ይህም ሰው ቆንሲሉ ነው።

ስለዚህም፣ ሙሴ ማይሌ፣ በሚቀጥለው ቀን የኢትዮጵያን አምባሳደር ለመቀበል በነበረው ዝግጅት ፊቱን ወደ ብሬሎት መለስ ማድረጉ፣ ሙሉ በሙሉ ተገቢ ነበር። እያደገ የሚታየውን እውቅናውን ከፍ ከፍ ከሚያደርጉለት መገልገያዎች አንዱ፣ ዳሚየታ ከተማ ውስጥ፣ ብሬሎት፣ ከአንድ የባንክ ሰራተኛ የገዛትና ጣሪያዋ ወደ ኋላ ሊታጠፍ የምትችል ውብ የእንግሊዝ መኪና ነች። ምስኪኑ እንግሊዛዊ፣ ኪሣራ ሲገጥመው ወደ ማርሴይ ሊያደርሰው በሚችል መርከብ ላይ ለመሣፈር አንባ በአይኖቹ እንደሞላ መኪናዋን ባልሆነ ዋጋ ሸጣት።

ብሬሎት፣ ለምክክር በሚል ወደ ቆንሳላው ጽህፈት ቤት ከሰዓት በኋላ በተደጋጋሚ ተጠርቶ ተመላለሰ። ምሽት ላይ የተቀባዮች ስም ዝርዝር ተጠናቀቀ። ከፍተኛ ሰው መምጣቱን የሚያናፍሰው ወሬ በማህበረሰቡ መንደር ውስጥ ተሠራጨ። ጥቂቶቹ ፖንሴ መመለሱን ያወራሉ። ብዙ ነጋዴዎች፣ አልመለስን አለ በሚል አኳኋን በቆንሳላው ዙሪያ ማንገርገብ ጀመሩ። ነገር ግን፣ በሚቀጥለው ዕለት አንድ ከፍተኛ ባለስልጣን ለመቀበል ሙሴ ዴ ማይሌ እየተዘጋጀ ስለሆነ፣ ሁላቸውም በየቤቶቻቸው እንዲቆዩ፣ በመንገድም ላይ አንዳችም መንፈስ የሚረብሽ ነገር እንዳይፈፅሙ፣ የተባለውን አምባሣደር ለመቀበል አንድ ጓድ በመኪና እንደሚወጣ፣ በዚህም ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉት በዝርዝር የተመዘገቡት ብቻ እንደሚሆኑ ሙሴ ማቼ ወጥቶ ማሣሰቢያ ሰጠ።

በሚቀጥለው ዕለት ጧት፣ ጆን ባፕቲስት በሚያስደስት ስሜት፣ ሌሊቱን ሙሉ ባገኘው ሰላማዊ ዕንቅልፍ ይበልጥ ተጠናክሮና ብቁ ሆኖ ነቃ። ያለፈውን ዕለት ሁኔታዎች መልሶ መላልሶ ፈተሻቸው። አሊስንም በጥድፊያ አለማየቱ ለበጐ ሣይሆን አይቀርምና ፍራንቾይዝ ያመጣችለት ዜና ድንቅ እንደነበረ ደመደመ። ቆንሲሉ ያደረገለትን አቀባበል በተመለከተም፣ ይጠብቀው የነበረው ነውና እቅዱ ግቡን መትቷል። ከዚህ በኋላ አቀባበል ከሚያደርገው ሠልፈኛ ጋር በትህትና ሄዶ አምባሣደር ሙራድን ይቀበላል። ከዚያም አርመናዊውን፣ አስቀድሞ በነደፈለት መንገድ እየመራ ይወስደዋል። ቆንጆ ቀይ ሙሉ ልብሱን፣ ትናንሽ

ቀዳዳዎች ያሉበት የሚመስል ንድፍ ባረፈበት ለስላሣ ሽሚዝ ላይ ለብሷል። በቁም ሣጥኑ ውስጥ አስቀምጦት የነበረውን ባርኔጣውን አራግፎ አጠለቀ። ጐራዴውን በጉኑ ላይ ታጠቀና ፈረሱን ሊጭን ወጣ።

አርሱ ቆንስላው ግቢ ሲደርስ፣ ተቀባዩ እድምተኛ ተሰብስቦ ቆይቷል። ከበላይ የሚታየው የፈረንሣይ ቆንሲላ ግቢ ሃላፊ የሆነው፣ ሙሴ ፍሌሃው ነበር። ምንም እንኳ ከሙሴ ዴ ማይሌ ጋር ተመሣሣይ የሆነ ዲኘሎማሲያዊ መደብ አባል ቢሆንም፣ በጣም ዝቅ ባለ ደረጃ የሚሠሩ ተራ የሂሣብ ሥራና ደብዳቤዎችን ከመላክ ሌላ ሲሠራ፣ ጆን ባፕቲስት አይቶት አያውቅም። ሰውዬው፣ ጥልፍ ያለበት ሙሉ ልብስ ለብሶና ላባ የተሠካበት ባርኔጣ አድርጓል። በህይወቱ እንዲህ አምሮ አያውቅም። በስተቀኙ፣ የቆንሲሉ ዋና አስተርጓሚ፣ ሙሴ ፍሬሴቲ አለ። አስተርጓሚው፣ሙያውን በከተማው ውስጥ በመለማመድ፣ የንግድ ሥራ ትርጉሞችን እየሠራ የመኖሪያ ገቢውን ያገኛል። አንዳንድ ጊዜ፣ ቆንሲሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሻ የትርጉም ስራ እየሠጠው በርሱና በአቶማን ባለስልጣኖች መካከል የሚተላለፉ አፊሴል ደብዳቤዎችን እንዲተረጉም ሾሞታል። ከሙሴ ፊሌሃው በስተግራ፣ ለንጉሡ ተብሎ ቀሚስ በለበሰ ፈረስ ላይ፣ ብሬሎት ተቀምጧል። ብሬሎትን በፈረሱ ላይ ለማስቀመጥ ብዙ ሰዎች ተሸክመውታል። የብሬሎት ግዝፈት የሙጣው፣ የሠውነት መገጣጠሚያዎችን በሚያሣብጥ በሽታ ነው። ይሁን እንጅ፣ በቡኒው ረዥም ሠው ሠራሽ ፀጉሩና በሠብቱ ምክንያት በለበሠው ሙሉ የሃር ልብስ የተኘሣ፣ የመጡ ልኬት ጥሩ ነው። እርሱን ተከትሎ መኪናዋ አለች። ከመኪናው ውስጥ ከነጅው በስተቀር ሌላ ተሣፋሪ የለበትም። በመልስ ጉዞ ላይ ብሬሎት ከአምባሣደሩ ጐን የመቀመጥ ክብር ይኖረዋል። በመጨረሻም፣ ዝቅተኛ ጥራት ባላቸው ፈረሶች ላይ፣ በሁለት ተርታ የተቀመጡ ነጋዴዎች አሉ። የነዚህ ነጋዴዎች ምርጫ ረዥም ድርድር ተደርጉበታል። ሁለቱ ቬኔሲያውያን በዚህ አጀብ ውስጥ የመሣተፍ እድል ያገኙት አልፍኝ ታዳራሽ የሆነውን ቤታቸውን ለአቢሲኒያው ባለስልጣን ማረፊያነት ስለሠጡ ነው። የፐሮቶኮል ደረጃን በተመለከተ በተደረጉት ውይይቶች፣ አንድ ነጥብ ግን ያለምንም ጭቅጭቅ ተቀባይነት አግኝቷል። ፖንሴ የመጨረሻውን ስፍራ ይይዛል። አርሱም ይህን ቦታ በፈቃደኝነት ተቀብሎታል። ይህ አነስተኛ ቁጥር ያለው ሰራዊት በአራት ሰዓት ላይ ተንቀሣቀሰ። ብዙም ሣይቆይ የመልዕክተኛውን ዓዝ ያገኛሉ። ወዲያውም ተቀባዮቹ አጀቡት፣ በቆንስላው ሠገነት ሥር በማለፍ ወደ ማህበረሰቡ ሰፈር ይመለሣሉ። ሙሴ ዴ ማይሌ መልዕክተኛውን የሚቀበለው እዚያ ነው። ዲፕሎማቱ፣ የሹመት ደብዳቤውን አቅርቦ እስኪያስረክብ ድረስ ምንም ዓይነት የቅርበት ንክኪ ማድረግ

ክልክል ነው። አምባሣደሩም፣ ጣሊያኖች በሚኖሩበት የፈረንሣውያን ማህበረሰብ መኖሪያ ውስጥ «የቬኒስ ወረዳ» እያሉ ወደሚጠሩት ቤት ያመራል።

የቱርኮችን አትኩረት ሳስመሣብ ሰልፈኛው አሮጌ ካይሮን ትቶ በመክላክያ ምሽጉ ግድግዳ አቋርጦ ተጓዘ። ምክንያታቸውን ባያውቁም ደማቅ ሰልፎች ሲደረጉ፣ ቱርኮች ሁልጊዜም ይጠራጠራሉ። ሠራዊቱ የድመት በር በሚባለው መውጫ አድርጐ በአቅራቢያው ወዳለው ቀበሌ ሲደርስ፣ በምድረበዳ ውስጥ እየተጓዘ መሆኑን አወቀ። ከከተማው አጥሮች አንድ ማይል ከአሩብ ያህል ርቀት ከተጓዙ በኋላ ቆሙ። ይህ ሥፍራ ፖንሴ ኮትናንት በስቲያ በጨረቃ ብርሃን በፈረስ ላይ ሆኖ የተጓዘበት የቤተመቅደስ ቦታ ነው። ቀኑ ሞቃት ነበር። ከምድረበዳው የሚመጣው ነፋስ የአቧራ ደመና ስላስነሣ አይኖቻቸውን ይቆረቁራቸው ጀመር። ብዙም በተንተን ሣይሉ፣ የአድምተኛው አባላት ጥላ በመፈለግ መዝናናት ጀመሩ። የአገሩ እይታ ያልተለመደ ዓይነት ነው። ከወደምድረ በዳው በኩል በነፋስ እየተጠረጉ የተፈጠሩ ታላላቅ የግሪክ ምስሶዎች ሽቅብ አስግገው ይታያሉ። ከበስተኋላቸው ደግሞ በፈረሶቻቸው ላይ በፀጥታ የተቀመጡና እንቅስቃሴ አልባ የሆኑ ፈረሰኞች፣ በሃብታም ልብሶቻቸውና በረዣዥም ሰው ሰራሽ ፀጉሮቻቸው ሥር በላብ ተዘፍቀው ይታያሉ። ጥቂቶቹ አድማሱን ባለማቋረጥ ይመለከታሉ። ሌሎች ደግሞ ራሱ ላይ ጥምጣም ያደረገ ሽማግሌ እረኛ ያለ ዓላማ የሚነዳቸው በጉች ያንጠባጠቧቸውን ጥቋቁር በጠቦች በመቁጠር ትኩረታቸውን በዚያ ላይ አድርገዋል።

ጥበቃው በመቀጠሉ፣ ምናልባት አስቸጋሪ ጥያቄዎች ያቀርቡ ይሆናል በሚል፣ ፖንሴ ስለተጨነቀ ከፊት ለፊት ያለውን መንገድ ለመቃኘት አንዲቻል ሃሣብ አቀረበ። ፈረሱን ኮርኩሮ ለአንድ ሰዓት ያህል ጋለበና ምንም ሳያይ ቀስ እያለ እየሰገረ ተመለሰ።

የዕለቱ ከሰዓት በኋላ፣ በሰላም እየተገባደደ ነው። ባለስልጣናቹ ከፈረሶቻቸው ወርደው የደረቧቸውን ኮቶቻቸውንና ጃኬቶቻቸውን አውልቀው በሽሚዞቻቸው ሆነው፣ በውሃ ጥም ተቃጥለውና ቁጣቸውን ሊሰነዝሩበት ተዘጋጅተው አገኛቸው።

«ሊገባኝ አልቻለም፣አንዳች አስቸጋሪ ነገር አጋጥሞ መሆን አለበት።» አለ።

በዚህ ጊዜ ሌሎች፣ ሌላው ቀርቶ አምባሣደር የተባለው ሰው ከቶውንም ስለመኖሩ መጠራጠር መጀመራቸውን ተረዳ። እነርሱ ሰውዬውን ስለማያውቁት ቢጨነቁም፣ ፖንሴ ግን ስለሚያውቀው በሌላ ምክንያት የሙራድ አጣ ፊንታ አሣሰበው።

«አሁን አሥር ሰዓት ሆነ፣ ወደ ቤት እንድንመለስ ሃሣብ አቀርባለሁ። ምናልባት መልዕክተኛው በምሽት የሚደርስም ከሆነ ጠብቀው እንዲያሣውቁን ሁለት ጠባቂዎችን እንልካለን» አለ ጀን ባፕቲስት።

ባለው ሁኔታ ምላሹ ጥሩ እንደማይሆን ስለተረዳ ላቀረበው ሃሣብ የሚሰጠውን ምላሽ ሳይጠብቅ ፈረሱን ኮርኩሮ ወደ ካይሮ ነጐደ።

4

በተሰይ በዚያን ዕለት፣ የድመት በር የሚባለውን የሚጠብቁት ሁለቱ ተረኛ ሽማግሌ የአረብ ዘቦች፣ ሰውነታቸው ሁሉ በክብር ምልክቶች ተሞልቶ፣ በጣም ተደስተው ነበር። የሚሊሺያዎች አዛዥ፣ ለወታደራዊ ጀግንነታቸው ምስጋናውን ለማሳወቅ፣ በዚህ ዕለማዊ ጣቢያ ላይ ሕይወታቸውን ሙሉ እንዲቆዩ ፈቅዶላቸዋል። በዚህ ጊዜ፣ ካይሮ ከውጭ ከሚያጋጥማት ወረራ ይልቅ የውስጥ የሕዝብ አመፅ ይበልጥ ያስፈራት ነበር። በየበሩ ያሉት ዘበኞች ዋናው ሃላፊነታቸው፣ በምሽት፣ ጅቦችና ሌሎችም አራዊት ከምድረበዳው ተነስተው ወደ ከተማ እንዳይገቡ በሮችን መዝጋት ነው። ቀን ሲሆን ግን፣ ሁለቱ ሽማግሌዎች ከመሬት በታች ባለው ጥላ ቦታ ላይ ምንጣፋቸውን ዘርግተው፣ እግሮቻቸውን አመሣቅለው በመቀመጥ ቼዝ ሲጫወቱና በቅርባቸው ካለ ሱቅ አንዲት ባዶ እግሯን የሆነች ትንሽ ልጅ የምታመጣላቸውን ሻይ እየጠጡ ይውላሉ። ከጧቱ ሦስት ሰዓት ሲሆን በሕዝብ ትርምስ መሃል ሰፊ ቦላሌና እንደ ኩርዶች አለባበስ ሰፋ ያለ የወገብ መታጠቂያ የለበሰ ሰው ወደ ከተማዋ ሲገባ ያያሉ። ሰውዬው ሥጋው የደለበና በምስኪኗ በቅሎው ላይ ከባድ ጭነት ነበር። እንሰሳይቱ፣ ወደ በሩ ከሚያመራው መውጫና መውረጃ መሃል ስትደርስ ቀጥ ብላ በመቆም አንዲት እጥቅ እንኳ ላለመንቀሳቀስ አሻፈረኝ አለች። ሰውዬው፣ በፍጥነት ተንቀሣቅሶ ብዙ ቦታ ስብርባር ባለና በቅሎይቱን ሊያስገድዳት በማይችል በደካማ አርፖሜ ይገርፋት ጀመረ። ግንም ሰው ኑብያዊ ናቸው ሊል የሚችላቸው፣ነገር ግን ቅርፃቸው ለየት ያለ፣ ሦስት ጥቋቁር ሰዎችም የበቅሎይቱን ውዴላ ይዘው ቢገፏትም እንሰሳይቱ በቁጣ እነርሱ ላይ ተሸክርክራ ዞረችባቸው። የመጨረሻው ጥረታቸው ግን እንሰሳይቱ እስክነአካቴው እንዳትተናነቸባቸው መጠበቅ ሆነ። በዚያው መስመር ፈንጠር ብሎ በሰላም አብረው የተቆራኙ ሦስት አሆኖች እምቢነገር ተጭኖባቸዋል። ሌላ አንድ በቅሎም እንደሁ በመንገዱ ዳር ባሉት ድንጋዮች መሃል ብቅ፣ ብቅ ያሉትን ስለታም ሣሮች ትመለከታለች።

በመጨረሻም ሰውዬው ከበቅሎይቱ ላይ ወረደና ወደ በር ጠባቂዎቹ ተራምዶ ፊት ለፊታቸው ሲደርስ ቆመ። ከበቅሎው ወርዶ አስር አርምጃዎች በመራመዱ ቁና ቁና ይተነፍሣል።

«አ! ውድ ወዳጆች፣ ወንድሞች» አለ እያለከለከ «ይህች በቅሎ እዚህ ድረስ እንድትራመድልኝ ልትረዱኝ ትችላላችሁ። ዕድሜዋን ሙሉ በከተማ መግቢያ በር አልፋ የማታውቅ እንሰላ ነች። በጣም ስለፈራች ምንም ዓይነት ምክንያት ማዳመጥ አትፈልግም»

ሰውዬው የሚናገረው አረብኛ የሶርያ ዘዬ ነው

«እንዲያው ሰመሆኑ እናንተ ከወዴት ናችሁ? በከተማችሁ መግቢያ፣ በሮች የሏችሁም?» ሲል አንዱ ዘበኛ ጠየቀ።

«እኔ የመጣሁት፣ አናቶሊያ ከሚገኘው ከቫን ከተማ ነው። በዚያም ብዙ በሮች አሉን። ነገር ግን እኔና በቅሎዬ ሁለት የተለያየን ነገሮች ነን። ይህችን በቅሎ የገዛኋት አረቢያ ከሚገኘው ፊሊክስ፣ ከአንድ ባላገር ላይ ነው።»

«አሃ! እንግዲያውስ ማንበብ የማትችለው በቅሎይቱ ነች ማለት ነው!» አለ ሽማግሌው በሣቅ እየተንከተከተ

ሁለተኛው ሽማግሌ፣ የተሰጠው አስተያየት ምን አስቂኝ ነገር እንዳለበት እርግጠኛ ባይሆንም፣ በጓደኛው በሣቅ መንከትከት ተሸንፎ አብሮት መንከትከት ጀመረ። መንገደኛው፣ ሁለቱም ሰዎች ሲስቁ ተመልክቶ፣ እርሱም አብሯቸው ቢስቅ መልካም እንደሚሆን አሰበ፣ የሣር ጥምጣሙ ከጭንቅላቱ ላይ እስኪወድቅ ድረስ ክልቡ ፍርስ አለ።

«ከዚህች ማንበብ ከማትችል እንሰላ ጋር እንግዲያውስ ወዴት ነው የሚሄዱት?» ሲል የመጀመሪያው ሽማግሌ ጠየቀ። ሣቁ ጣሪያ የሚደርስ ስለነበረ በአካባቢው የነበሩ ተላላፊዎች ቀልዱን ለመካፈል ተሰበሰቡ።

«ወደ ፈረንሣውያን ቆንሲል» አለ መንገደኛው

«አሃ! ምናልባት በቅሎዎ ላቲንኛ ማንበብ መቻልዋን ለማወቅ ፈልገው ነው!» አለ ሌላኛው ሽማግሌ። በዚህም ሁለተኛ ዙር ሣቅ ሊቀጥል፣ ባለ በቅሎውም በደስታ የሣቃቸው ተካፋይ ሆነ።

ፀጥታ እስኪሰፍን ድረስ ሁለት ወይም ሶስት የተለያዩ ጉዳዮች በዚህ ዙሪያ ሊያጫውቷቸው ቆዩ። በር ጠባቂ ዘበኞችም በተጨማደዱ አይኖቻቸው ላይ የተጠራቀሙትን

እምባዎች ጠራረጉ። አንዳችም የጥቃት እርምጃ ለመለንዘር ሣይቃጣ፣ ይህን ያህል የመሣቅ ዕድል እንዲያገኙ ላደረጋቸው ለዚህ አስደሳች እንግዳ ሰው ርህራሄ ተሰማቸው።

«ስምሥ ግን ማን ይባላል ወንድም?» አለ ከዘበኞች አንዱ

«ሙራድ ነው፣ ወዳጄ»

«ጥሩ እንግዲያው ሙራድ። እኛ በቅሎዎን መቼም አንነብልዎትም። አነዚህን እንሰላት አውቃቸዋለሁ። ጥሩ አይደሉም። ይልቅስ ከዚህ በጣም የተሻለ ልናደርግ እንችላለን። ምክር ልንሰዋዎ እንፈልጋለን። ጥሩ ምክር እንሰጥዎታለን። እሺ?»

«ጆሮዎቼ ያዳምጣሉ» አለ ሙራድ በመበሳጨት ስሜት

«በዚህ መግቢያ በር ካለፉ ከተማዋን በሞላ ማቋረጥ ይኖርብዎታል። ከዚህ ይልቅ፣ በትናንሽ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች በኩል ባለቅስት መግቢያዎች አሉ። ማንበብ የማትችለው በቅሎዎ እነዚያ በሮች መግቢያዎች እንደሆኑ ታውቅና ትሄድልዎታለች። ስለዚህ ጥሩው ነገር በቀጥታ ወደ ቀኝ ታጥፎ ዞሮ መሄድ ነው። ከዚህ ከመውጣጫው በታች እሾሃማ የፍሬ ዛፍ ይታይዎታል?»

«አዎን አየዋለሁ»

«እዚያ ሲደርሱ ወዲያውኑ ትንሽ እልፍ ብለው ወደ ቀኝ ይታጠፉና፣ በከተማው ዙሪያ የምትዞረውን የእግር መንገድ ይያዙ። ሌሎች መግቢያዎችን በርቀት ያያሉ። ስድስት ያህሉን ከቆጠሩ በኋላ ሰባተኛው አጠገብ ሲደርሱ ወደዚያው ያምሩ። መግቢያው እንደዚህኛው ሳይሆን ትልቅ የብረት ፍርግርግ በር ስለሆነ፣ በቅሎዎን አያስፈራራብዎትም። በዚያ በኩል ይለፉና አንድ መቶ ያርድ ያህል ከተጓዙ በኋላ፣ በግራ በኩል የፈረንሣውያንን መኖሪያ ያኖሉ»

ሙራድ፣ ለሁሉቱ ሽማግሌ ዘበኞች ሞቅ ያለ ምስጋና ካቀረበ በኋላ የሰጡትን አስተያየት ተቀብሎ ባሰቡት አቅጣጫ ጉዞውን ጀመረ። በዚህ ጊዜ በቅሎይቱም ሙሉ ትብብርዋን አሣየች።

በድመት በሩ ስር ተሸብሸቦ የነበረው ሕዝብም ቀስ በቀስ ተበተነ። የበሩ ጠባቂ ዘበኞች ሁኔታውን እያስተዋሉ በመሣቅ ላይ ሳሉ፣ ከአንድ ሰዓት በኋላ የፈረንሣይ ፈረሰኞች በአስደሣች

የሶምሶማ እርምጃ ሲያልፉ ተመለከቱ። ፈረሰኞቹ ባለቀለማት ጃኬቶችና ሰው ሰራሽ ፀጉሮችን ለብሰዋል። ውድ ዕቃዎችን በተጫኑት ፈረሶች መካከል አንፀባራቂ ቀለም የተቀባችና የተወለወለች ጥቁር መኪና አለች። በግንቡ በኩል ቁልቁል ወጥተው ከከተማዋ ፈጥነው ራቁ።

ሰቆንስላው አትክልተኛ፣ ወደ ዋናው ሕንፃ መግቢት ፍፁም የተለየ ነገር ነው። ሽማግሌው ሰውዬ፣ የካይሮ ተወላጅ የሆነ ቅብጣዊ ክርስቲያን ሲሆን ታማኝ አሽከር ነው። ምሽት ጀምሮ እኩለ ለሊት ድረስ፣ በደካማ አቅሙ፣ በዝግታና በፀጥታ በቀጫጭኖቹ ማቋረጫዎች ላይ እየተንዘዘ፣ ከነሃስ የተሠራውን የውሃ ማጠጫ ይዞ፣ በደረቁ ቅጠሎች ላይ ውሃ እንደዝናብ ሲያፈስስባቸው ከሚሰማው የማጉረምረም ድምፅ በስተቀር፣ አንዳችም ኮሽታ አይሰማም። በዚህ ቀን ግን ይህ አትክልተኛ ዕድል አልነበረውም። የቆንስላው ግቢ ባዶ ነበር። የሙሴ ዴ ማይሌ ሾፌር፣ የቀንና የሌሊት ጠባቂና ሁለቱ ወንድ አሽከሮች ሁሉ ኤምባሲውን ለመቀበል ከወጣው መልዕክተኛ ጋር ተከትለው ሄደዋል። ከራሱ ከሽማግሌው አትክልተኛ ከገብርኤል በስተቀር፣ ማንም ሰው በቤቱ ውስጥ አልቀረም። መልዕክቱን ሊቀበለው የሚችለው ሰው በማጣቱ፣ ከበር በር እየሄደ፣ በመጨረሻም እጅግ እያቅማማ ከቆንሲሉ ጽህፈት ቤት በር ደረሰ። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ሰው ሰራሽ ፀጉሩንና አንፀባራቂውን የሃር ጃኬቱን በእንጨት መስቀያ ላይ አስቀምጧል። እርሱ ግን ወንፊት የመሰለ ሽሚዝና የሃር ቦላሌ ለብሶ ወደፊትና ወደኋላ እየተንጐራደደ ቅንድቡን በመሃረብ ይጠርጋል። ሙሴ ማቼ፣ በአንድ ወንበር ላይ ኩርምት ብሎ፣ ትዕዛዝ ወይም የውይይት ርዕስ ሊሆን የሚችል ቃል እንዲተነፈስ ይጠብቃል። የእትክልተኛውን የፈራ ተባ አገባብ አስቀድሞ ያስተዋለውም እርሱ ነበር።

«እና ይህ ደግሞ ምን ይፈልጋል?» ሲል ቆንሲሉም በተራው እንዳስተዋለ ጠየቀ።

ሙሴ ማቼም፣ አረቢኛ ብቻ የሚያውቀውን ሽማግሌ በቋንቋው ጠየቀው።

«እንደሚሰው አንድ ሰው ሊያይዎት ይፈልጋል። ክቡር ሆይ»

«አንድ ሰው!» አለ ቆንሲሉ በለበጣ ፈረግታ። «እንዴት ያለ የሚገርም ነገር ነው። አንድ ሰው ከማሉት ይልቅ ለምን ዱባ ወይም አይነ ትልልቅ ዝንጀሮ አይሆንም? ለዚህ ጅል፣ ከሁሉም በላይ ስለሚያብቡት ተክሎቻችን ብቻ ጥንቃቄ እንዲወስድና ሌላውን እንዲተው ንገረው።

እናም ጳግመኛ እዚህ ላየው አልሻም። አንድ ሰው እኔን የሚጠይቅ ከሆነም በአጭሩ ስራ ላይ ነው ይበሰው።»

የቆንሲሱ መልስ ተተርጉሞለት ከለማ በኋላ የሽማግለው ሰው ፊት በንዴት ልውጥውጥ አለ።

«ሄዶ እንደሚነግራቸው፣ ግን የሚሰጣቸው መልስ ሰምቼን ከርሱ መስኩት ፈቅ እንዲሉ ያደርጋቸው እንደሆነ እንደሚጠራጠር ነው ሚናገረው።

«እንደሚነግራቸው? ለመሆኑ ስንት ናቸው?» አለ ቆንሲሱ።

«አራት ናቸው። ጭነት ያለባቸው አህዮችና በቅሎዎች አሉ» አለ ሽማግሌው ሰው።

«ለመሆኑ ምን ይመስላሉ? ቅፍለት ይሆን?» ሲል ሙሴ ዴ ማይሌ ጠየቀ።

«አዎን፣ ከፈለጉ ቅፍለት ነው። ይሁን እንጂ በዚህ አካባቢ እንዲህ ያለ ነገር አይቼ አላውቅም»

«ለመሆኑ፣ ወደ ማህበረሰቡ ሰፈር በሚያስገባው በር ላይ የሚገኘው ዘብ ለምንድን ነው እንዲገቡ የፈቀደው?»

«ምናልባት ሰውዬው ለኔ የነገሩትን ለዘቡም ነግረውት ይሆን ይሆናል»

«ምን ነበር የተናገረው?»

«የአቢሲኒያውያን ንጉሥ አምባሣደር መሆናቸውን ነው» አለ አትክልተኛው በአክብሮት ፈገግታ

ሙሴ ማቼ አመዱ ቡን አሰና የሽማግሌውን ቃሎች ተረጐማቸው።

«ቸሩ ጌታዬ!» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ

ለአፍታ ያህል ዲፕሎማቶቹ መናገር ተስኗቸው ቆዩ። ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግ ወደ መስኩቱ ተራመዱ። ተራ በተራ ወደውጭ ተመለከቱና በቅፅበት ምልስ አሉ።

«ሊሆን የሚችል ነው እንዴ?» አሉ ሁለቱም በጋራ

በድጋሜ በመስኩቱ በኩል ተመለከተ። በታች በኩል በሚገኘው ማዕከላዊ መንገድ ዳር፣ በመደዳ በተተከሉት ዛፎች ሥር መከረኞቹ የክብር ዘበኞች ቆመዋል። ሰውነታቸው የተጉጣጠበና የተመላለሱ፣ ጫንቃቸው የቆሳሰለ ስለሆነ ትናንሽ ወፎች የሚያነቁሩት፣

እንዲሁም ካይሮ ውስጥ ዝቅተኛው ውሃ አመላላሽ የማይፈልጋቸው በቅሎዎች ይታያሉ። እነዚህ ምስኪን እንስሳት መጠናቸው ትልልቅ የሆኑ ጭነቶችን ተሸክመዋል። ጭነቶቹ በጀርባቸው ላይ በቃጫ ገመድ ጥፍር ተደርገው ሲጫኑ፣ በጣም በቆሰለው አካላቸው ላይ እራፊ ጨርቅ ተደርገዋታል። ከጥጥ የተሰራው የሰበሱት ሽሚዝ የበረሃውን አፈር የመሰለ ሦስት ጥቋቁር ወንዶች መናገር ተስኗቸው ይጠብቃሉ። አንድ ዛፍ ተደግፎ መሬት ላይ የተቀመጠው ሙራድ ጫማውን አውልቆ የእግሩን መዳፍ በሃይል ያክላል።

«ማቼ» አለ፣ ሌሎችን ለማዘዝ የተፈጠረውና ሳይታሰብ ድንገት ቢጠራ የማይበሣጨው ቆንሲል። «ውረድና የቆንሲሉን አክብሮት ግለፅለት። ከዚያም ሁኔታውን አስረድተኸው ወደተዘጋጀለት የቬኒስ ወረዳ ውሰደው።»

ፀሐፊው ወዲያውኑ ወጣ። አትክልተኛው እየመራው ሄዶ ሹልክ ብሎ ጠፋ። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ብቻውን ቀረ። ቀና ብሎ የንጉሱን ሥዕል በዓይኖቹ ቀረፀና፣ ወዲያውኑ፣ የሁሉም የበላይ ለሆኑት ንጉሠ ነገስትና ለዋናው ሚኒስትር ለፖንቻርትሬይን ብልህነት ያለው ታላቅ አክብሮት መንፈሱን ሞላው። ዋናው ሚኒስትር በቅርቡ የላኩለትን ደብዳቤ በምስጋና እምባ አስታወሰ።

በዚህ መሃል፣ ማቼ፣ እስከዚህ ጊዜ ድረስ እግሩን ያክክ ወደነበረው ወደ ሙራድ ዘንድ ደረሰ። አትኩሪቱን ለመማብ ሲል እንደማሳል አደረገ።

«ሎ ጓደኛ አገኘን ማለት ነው» አለ፣ አርመናዊው ጫማውን መልሶ እያጠለቀና ተነስቶ እየቆመ

ሙሴ ማቼን ለመጨበጥ የእርግ ጣቶቹን ሲያክክበት የነበረውን እጁን ዘረጋ

«ሙራድ እባላለሁ። ከኢትዮጵያ የመጣሁ አምባሳደር ነኝ»

«አጅግ ሞገስ ያለው እንኳን ደህና መጡ።» አለ፣ ፀሐፊው የእጅ መጨባበጡን ለመከላከል ከወገቡ በመጠኑ ዝቅ ብሎ።

«እሺ፣ እሺ፣ ተነሱ» አለ ሙራድ በመጨነቅ። «አራሜችሁን እየጐዳችሁ ነው። ተነሱ ተነሱ፣ እሺ እባክህን ይንገሩኝ፣ እርስዎ በርግጥ ቆንሲሉ ነዎት?»

«አይደለሁም፣ የተከበሩ፣ ክቡር ቆንሱሉ ክቡርነትዎን እንኳን ደህና መጡ እንድልዎትና አክብሮታቸውንም እንድገልፅልዎ ልከውኝ ነው። ኦፊሴላዊ የሆነ የሚቀበልዎ የመልዕክተኛ ቡድን ልከንልዎ ነበር። ነገር ግን ሳያገኝዎት ቀርቶ ነው»

«በዚህች ደደብ በቅሎ ምክንያት ነው» አለ ሙራድ፣ ፍንክች የማትለዋን እንሰላ እየረገጣት። «ምንም ነገር የምትሰማ አይደለችም። በዚህም የተነሣ በግንቡ ዙሪያ መጓዝና በብረት በሩ በኩል ዞሬ ማስፍ ነበረብኝ። ምን ይደረግ! መድረሱን እንኳ ደርሰናል፣ መንገዱም ደግሞ አታምነኝም በጣም ረዥም ነው። ለመሆኑ ፖንሴ የት ነው?»

«አርሱም ከተቀባይ እድምተኞች ጋር ነው»

«ከእድምተኞች! ታዲያ እንዴት ላደርግ ነው? ይህን ከተማ በጭራሽ አላውቅውም። ማንም ሰው ቢሆን ማረፊያ ሲሰጠኝ አይችልም»

«ማረፊያ አይሰጠኝም? ይህማ ለክቡርነትዎ ተዘጋጅቷል። እኔን ብቻ ይከተሉኝ»

«እውነት ነው? በል፣ ይህ ጥሩ ዜና ነው። እና የምመገበውም ትሰጠኛለህ?»

«የሚበላ፣ የሚጠጣ፣ ክቡርነትዎ የሚሻውን» አለ ሙሴ ማቼ ይበልጥ እየተደነቀ።

«እግዚአብሔር ታሳቅ ነው። በል እሺ እከተልሃለሁ። እናንተ ሦስታችሁ። ወዲህ ኑ። እነርሱ አቢሲኒያውያን ናቸው። በተፈጥሯቸው ጠንካራ ሀዝቦች ናቸው። ነገር ግን ለኔ የተሰጡኝ ሶሶት ሰነፎች ይመስሉኛል። ኑ ተከተሉን፣ ተከተሉን»

በቅሉዎችንና አህዮችን አንቀሣቅሰው፣ የማህበረሰቡን ሰፊር በሙሉ አቋረጡ። ቆንሲሉ፣ በዚያን ዕለት በመንገድ ላይ የሕዝብ እንቅስቃሴን በመከልከላቸው፣ ማቼ፣ ራሱን በራሱ እንኳን ደስ ያለኝ ይላል። ምንም እንኳ በነበሩት ጥቂት ምስክሮች ይህን ያህል ባይሰጋም፣ ክርሱ በፊት የነበረው ሰው ግን ከዕለታት አንድ ቀን «አ አምን፣ ማቼ፣ የኢትየጵያን አምባሣደር ሁለት አህዮችን ሲነዳ ያየሁት መሆኔን አታውሣለሁ» ብሎ ታሪክን ያበላሽበት ይሆናል።

በመንገዱ ዳር ከተተከሉት በአንደኛው ዛፍ አጠገብ አረፍ ለማለት ሙራድ ቆመ። ይሁን እንጂ፣ በጉረሮው ውስጥ እርሱ ራሱ የፈጠረው ድምፅ ይህ ዕፎይታው የሚሰጠውን ደስታ ያበላሽበታል።

በመጨረሻም ወደ ቬኑሲያውያኑ ቤት ደረሱ። የምድር ቤቱ የተወለነው ለኤምባሲው ነበር። ቤቱ የእንጨት ቢሆንም፣ ሁለተኛው ፎቅ ግን ውብና ማራኪ በሆኑ ባለሦስት ማዕዘን

ወጋግራዎች ድጋፍ ቆሟል። በቤቱና በጕዳናው መሣከል በደንብ የተጠበቀች ትንሽ የአትክልት ቦታ አለች። አንድ አነስተኛ የጣውላ አጥር፣ የቬነስ ሪፐብሊክ ግዛት የት ድረስ እንደሆነ ለማመልከት ተስተካክሎ ታጥሯል። በዚህም ውስጥ አረንጓዴ በአረንጓዴ ላይ የሆነ፣ በመስኩ መሣል ላይ የተዘጋጀ፣ የቤተሰቡ መለያ ቢጋሻ ላይ ተነድፎ ተቀምጣል። እንሰላቱ ሁሉ ሥነታቸው ከተራገፈላቸው በኋላ ወደ መስኩ እንዲገቡና እንዳሻቸው በነፃነት እንዲንቀሣቀሱ፣ ሙራድ ሙጭጭ ብሎ ለአቢሲኒያውያኑ መመሪያ ሰጠ።

አርመናዊው ወደቤት ሲገባ፣ ጫማዎቹን አወለቀና በመጀመሪያው ሶፋ ላይ ሄዶ እንዘጭ በማለት ዳግመኛ ላለመነሣት ይምል ጀመር።

ሙሴ ማቼ ሃላፊነቱን ለመወጣት ቀዝቃዛ መጠጦች እንዲመጡ መልዕክት መላኩን ገልፆ ተሰናበተ

«እና የሚበላ ነገርም ጭምር!» ሲል ሙራድ ጮክ በማለት ማቼ ከአይታ ሳይሰወር በፊት ተናገረ።

ፀሐፊው ከተመለሰ በኋላ ስለአምባሳደሩ ያልተለመደ ባህርይ ለቆንሲሉ ማብራሪያ ሰጠ። ሙሴ ዴ ማይሌም፣ አንድ በባዕድ አገር ውሰጥ ሆኖ ራሱን በአድናቆት ስሜት ውስጥ እንዲገባ የሚያደርግ ዲፕሎማት፣ በጦርነት መሣል የራስ ቁሩን እንደሚያኮሣ ተዋጊ ነው ሲል ነገረው።

«ከሁሉም በላይ ጥቂት ቸርነትን ልናሣየው ይገባናል። ከየት እንደመጣም አስተውል»

የእንኳን ደህና መጡ አቀባበል ከሚያደርጉ መልዕክተኞች ጋር ስማቸው ያልተጠቀሱትን ነጋዴዎች በሙሉ ለሌላ የክብር ሥራ፣ በተለይም ለአምባሣደሩ ቀሰል ያሉ ምግቦችና ለስላሣ መጠጦችን እንዲያቀርቡ በሚል ለሁለተኛ ጊዜ ዝርዝር ተዘጋጀ።

«ምንም እንኳ . . . ልገልፀው» ሲል ሙሴ ማቼ ጠየቀ

«በደንብ ነዋ» አለ ቆንሲሉ። «ከነዚህ ከተከበሩ ሰዎች ለመጀመሪያው ቢሮውን እንዲያሰናዳ ንገረው»

ከሰዓት በኋላ ያለውን ጊዜ በሙሉ፣ ክብር ያላቸው ሃብታም ነጋዴዎች፣ ባልተቋረጠ መልክ በሰልፍ የገቡት አሽከሮቻቸው የፍራፍሬ ቅርጫቶችን፣ የብስኩት ሣህኖችንና ጣፋጭ ምግቦችን ተሸክመው፣ የቬኒሲያውያኑን ቤት ሞሉት። የኢትዮጵያውን አምባሳደር በክብር ለመቀበል የከፈሉት ዋጋ ይህ ነው። በኋላ ላይ ሁሉም ነጋዴዎች ወደ ሙሴ ዴ ማይሌ

በመምጣት እንዲህ ያለ ነገር ዳግመኛ እንዲያከናውኑ እንዳይገደዱ ሲነግሩት ተጣደፉ። የተቀበላቸውና ያስተናገዳቸው እንዲህ ያለ ቀርፋፋና ባለጌ የንጉሡ ባለሥልጣን መሆኑ ሊያምኑት ከሚችሉት በላይ ነው። ቆንሲሉ ላይ አንዳችም የመከነን ነገር ሣያሣርፉ፣ ፖንሴን የማጭበርበር ስራ ሰርቷል በሚል ከሰሱት። ይህን አይነት አስደንጋጭ ትዕይንት እየተከናወነ ሣለ፣ የብሬሎት ተወካዮች ተመሰሱና ሁሉም በፖንሴ ላይ ቁጣቸውን አወረዱበት። ምን እንዳጋጠመ ከተረዱ በኋላ የሌሰን መልዕክተኛ እንዲጠብቁ ያደረጋቸውን መድሃኒት ተማሚውን መክሰሳቸውን አቁመው፣ ቅሬታቸውን የሚያስተካክልላቸውን መዝናኛ ተቀሳቀሱ። በወቅቱ ሰፍኖ የነበረውን ትርምስ በመጠቀም ጆን ባፕቲስት ከቆንስላው ሾልኮ ወጣ።

«ክቡራን፣ ፀጥታ» አለ፣ ቆንሲሉ፣ ከፍ ባለ ድምፅ። «ከዚህ በኋላ ከድካማችሁ አረፍ እንድትሉ አጠይቃለሁ። በተጨማሪም ለድጋፋችሁ አመሰግናችኋለሁ»

ሌላ የተቃውሞ ጫጫታ ተቀሰቀሰ። ቆንሲሉ በአካላዊ እንቅስቃሴው አበረዳቸው።

«ይህ ሰው የአንድ ታላቅ ንጉስ መልዕክተኛ ነው። በርግጥ ንጉሡ ሰብዙ ዘመናት ከስልጣኔ ተቆራርጦ ኖሯል። ቸርነታችንንም ማሣየት ያለብንም ለዚሁ ነው። ከሁሉም ነገር በላይ የዚህ መልዕክተኛ አዚህ መድረስ በራሱ ትልቅ በዓል ነው። መልዕክተኛው በማንኛውም መልኩ ከያዝው መልዕክት በታች የሚገመት ነው። የአቢሲኒያው ንጉሥ ምን እንደሚነግሩን ነገ እንሰማለን። »

ቆንስላውን ከለቀቀ በኋላ፣ ፖንሴ፣ በቀጥታ ወደ ሼክስ ወረዳ ሙራድን ለማየት ሄደ። የሼክስያውያን የእንግዳ መቀበያ ክፍል መቀመጫዎች በሙሉ በግድግዳው የውጭ አካል በኩል በሙራድ ትዕዛዝ እንዲከመሩ ተደርጓል። በነጋዴው የእንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ የቀሩት፣ ምንጣፎችና ከባለመደገፊያው ወንበር ላይ ወርደው ወለሉ ላይ የተበታተኑት ትራሶች ናቸው። ሙራድ፣ እግሮቹን አጣምሮ፣ በመስተዋት ጪሌ በተጌጠው በትልቁ መብራት ሥር፣ ብዛት ባላቸው የብር ትሪዎች፣ አብረቅራቂ ጉድጓዳ ማሀኖች፣ ከፍተኛ ዋጋ ባላቸው ማንቆርቆሪያዎች ተከብቦ ተቀምጧል።

ጆን ባፕቲስት፣ የበቅሎዋን ባህርይና ባልታሰበ መንገድ የመጣበትን ታሪክ እንዲያወጋው ጠየቀው። የፈረንሳውያን ማህበረሰብ እንዴት እንደተቀበለው የሙራድን ሃተታ ሰማ። ሁሉም ኮንዲዎች አስነዋሪ ብልግና ያሣዩት መሆኑን አርመናዊው ይገምታል። ከእንግዲህ በኋላ እቤቱ ዳሰ አድርጉ እንዲገምትና ስጦታዎችንም ካበረከተለት በኋላ ሁለቱም ያንን ማንጓጠጥና

ብልግና ሊያረግቡና ይህን ንብረት እንዴት እንደሚጠቀምበት ተወያዩ። ምንም ነገር እንደሚፈልጉት አልነበረም። በአትክልቱ ሥፍራ ያሉት በቅሎዎች ወይም ከክፍሉ የተነሣው የቤት ውስጥ ቁሳቁስ፣ ወይም በአቢሲኒያውያን ስልት ፊት ለፊት ባለው መድረክ ላይ በሚገባ በተቀጣጠለው እሣት ላይ የፈላው ቡና እንደሚፈልጉት አልነበረም።

የሙራድን ቁጣ ባባባሰው በዚህ ታሪክ ክልብ ከሣቀ በኋላ፣ በፀባዩ ላይ አንዳችም ነገር እንዳይለውጥ ጆን ባፕቲስት ነገረው። በሚቀጥለው ቀን ከቆንስላው የሚመጣ ሰው አማኙቶት ስለሹመት ደብዳቤው ቢጠይቀው፣ ምን ማለትና ማድረግ እንደሚገባው በጣም ግልፅና ትክክለኛ የሆነ መመሪያ ሰጠው።

ከዚህ በኋላ፣ ጆን ባፕቲስት ወደ ቤቱ ፈጥኖ ሄደ። ከአሊስ፣ በአንድ ወይም በሌላ መልክ መልዕክቷን ይጠብቅ ነበር። ከትናንት በስትያ ጀምሮ ስላላያት፣ የሚያስበውም ይህን ብቻ ስለነበረ በጣም ጓጉቷል።

ፎቁን በጨለማው ውስጥ ወጣውና ሻማውን አበራው። እንደገመተውና እንደጠበቀውም አራት ቦታ የታጠፈ መልዕክት በሻማው ሥር አገኘ። መልዕክቱ ከፍራንቸይዝ የተላከ ማስታወሻ አልነበረም። ማስታወሻው የቤተክርስቲያኑ ደወል ሁለት ጊዜ እንደተደወለ በማሀበረሰቡ ዋና መንገድ መጨረሻ ላይ ባለው የአትክልት ሥፍራ እንዲያገኛቸው የሚያዘዝ ነበር።

5

አሊስ፣ በጨለማው ክፍሏ ውስጥ ቆማ የቀጠሮውን ሰዓት ትጠብቃለች። በዚያ ምሽት፣ ብርማዋ ጨረቃ ፣አልፎ አልፎ በከባድ ደመና እየተጋረደች አለች። እንዲህ ባለ ድቅድቅ ጨለማ ሌሊት እስከመናፈሻው ድረስ በመንገዶች ላይ መጓዝ እንደማያሰፈልግ ፍራንቾይዝ አስበች። በዚህም፣ ከቆንስላውና ከሰላዮቹ ቢያንስ ትንሽ ራቅ ይላሉ። ገና አመሻሽ ሲጀምር፣ ውጣቷ ልጃገረድ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለማድረግ ከበቂ በላይ ጊዜ ስለነበራት፣ ወደዚያ ወደተባለው መገናኛ መሄድ የጅል አስተሣሰብ እንደሆነና ክብሯንም ዝቅ እንደሚያደርግባት ለራሷ ስትነግር ቆየች። ሰዓታት እያለፉ ሲሄዱ ግን አርሷም ይህን ሃሣቢን ልክ አንድ ሴባ ሊያጠቃህ ሲመጣ ገፍትረህ ግርግዳ ላይ እንደምትወረውረው ሁሉ አሽቀንጥራ ጣለችው። ለራሷም እንዲህ አለች። ለመሆኑ በሙሉ ልቤ አሳፈቅረውም?

ከዚህ ውሳኔዋ በኋላ፣ ቀጠሮውን አፈርሣለሁ ከሚለው ሃሳቧ ይልቅ፣ አክብረዋለሁ፣ በሚለው ውሣኔዋ ርግጠኛ ነበረች። በአሁኑ ጊዜ በአዕምሮዋ ውስጥ የሚመላለስባት የክርክር ነጥብ፣ የጥንቱ የዕድገትዋ ጉዳይ ሣይሆን፣ ባለፈው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ራሷ ያገኘችው የአሁኑ አዲሱ ዕኑ እምነትዋ ነበር። ከፍራንቾይዝ ጋር በተጨዋወተችባቸው ረጅም ወራት ውስጥ፣ በጥቅም ሣይሆን በጥልቅ የስሜት ፍቅር የሚመራውን የአውነተኛ ፍቅርን ክብር ተገንዝባዋለች። ክብርን በተመለከተ ከሆነ፣ በሚገባ ልትጠብቀው የቻለችው እናትዋ ጥሩ ምሣሌ ናት። እርሷ ግን፣ እንደራሱ የግል ንብረት ሳደረጋት ሰው ባሪያው ካልሆነች ምን ልትሆን ነው? ልብሷን እየለበሰች ይህን የመሰሉ አደገኛ ሃሣቦች፣ በአሊስ አዕምሮ ውስጥ አሰፉ። ይህ ሁሉ ግን በፍራንቾይዝ የማነሣሣት ተፅዕኖ የመጣባት ሃሣብ ነው ብሎ ማሰቡ ትክክል አይሆንም። ሁለቱ፣ በማድቤቱ መግቢያ በኩል ተሸልከው ከወጡና በመንገዱ ላይ ካለው ጭለማ ጋር የራሣቸውን ጥላ ካመሣሰሉ በኋላ፣ አሊስ የደስታ እንቅጥቃጤ ተሰማት። ይህ መንቀጥቀጥ የተፈጠረባት እያደረገችው ባለው ነገር ሃሣብ አልነበረም። ይልቁንም በጉዳዩ ላይ ያለው ጥልቁ የተግባር ዕውቀት፣ አሁን እያከናወነችው ያለው ተግባር፣ አደጋ፣ ምናልባትም የመስዋዕትነት መልክ ያለው አደጋ፣ ፍፁም እውነተኛ የሆነና በሥልጣኔ ቅንጣት ታህል ያልተሸፈነ፣ በአጭሩ፣ የርስዋ እውነተኛ ባህሪ የፈጠረባት ነው።

መገናኛውን እየጠበቀ፣ ጆን ባፕቲስት በትውስታ ወደ ኋላ ተመለሰ። ሁልጊዜም ቀላልና ብልጭ ብሎ የሚያልፍ የፍቅር ግንኙነቶች እንደነበሩት ትዝ አለው። ከነዚህ ውስጥ የመጀመሪያ ግንኙነቱ እንደሚታወቀው ሁልጊዜም የመጨረሻ ይሆናል። የውድድር ዓይነት ቅርፅ ነበረው። የውድድሩ ተሣታፊዎች እያንዳንዳቸው ግልፅ የሆነ ለማሸነፍ ወይም ለመቋቋም ያለመፈለግ ቅዝቃዜ ይታይባቸው ነበር። በመሆኑም ጨዋታው የተቻለውን ያህል ለረዥም ጊዜ ከመደባበቅ ባለፈ እውነተኛው ሃሣብ ሣይገለጥበት ቀረ። ይህ ከሆነ በኋላ እያንዳንዱ በጥልቀት ያለውንና ሌላኛው ሰው ምን እንደሚሰማው ማወቅ ቻሉ። የማሸነፍ ወይም የመተው ጥያቄ አልነበረም። መደረግ የነበረበት በውስጣቸው ተፀንሰ የነበረውንና ለረዥም ጊዜ አውግዘውት የነበረውን ፍቅር፣ ለዓለም ግልፅ ማድረግ ነበር። መደረግ የነበረበት፣ቃላትና የሰውነት እንቅስቃሴዎች የሚያስተጋቡትን ፍቅር ፍንትው አድርገው በአየር ውስጥ በግልፅ ማሣየት ነበር። ይህን የማድረጉ ሃላፊነት ገልጃጃ እንዳደረገው ተሰማው።

ሰዓቱ በጭለማው ውስጥ ሁለት ጊዜ እንደደወለ፣ ሁለቱም ፍቅረኛሞች ወደመገናኛው አቀኑ። አሊስና ፍራንቾይዝ፣ ከመግቢያው በስተግራ በኩል ሲደርሱ፣ በአትክልት ስፍራው በስተጀርባ ተሸሽጉ የነበረው ጆን ባፕቲስት፣ ከውስጥ በኩል ብቅ አለ። ሁለቱም እንኩት በሚልና ሊጠገን በማይችል ውድ ሁኔታ ውስጥ የሚኖሩ መስሉ ተሰማቸው። ይህ ደግሞ የተገነባውን ቃል ኪዳን በማመልከቱ አይደለም። ምክንያቱም፣ ቃልኪዳኑ ከረዥም ጊዜ በፊት የተፈፀመ ነው። ነገር ግን ዳግመኛ አይፈፀምም የሚል ሰጋት ስላላቸው ነው። እያንዳንዳቸው በየበኩላቸው፣ ይህ ጊዜ በተቻለ መጠን ረዥም እንዲሆን ለማድረግ፣ ልክ ዳግመኛ ልታዩት የማትችሉትን ሰው መልክ በህሊናችሁ ቀርፃችሁ ለማኖር እንደምትሞክሩ፣ እነርሱም በትዝታ ዓዳቸው ውስጥ መስርተው ሊያኖሩት ቁርጠኞች ነበሩ። በአጭሩ፣ ግንኙታቸውን በመጣደፍ ሊያሣጥሩት አልፈለጉም። ይሁን እንጂ አካላዊ ጥላዎቻቸው እርስ በእርስ መቀራረባቸውን ሲመለከቱ፣ ሁለቱም ብቻቸውን በነበሩበት ጊዜ ውሣኔአቸው ትታቸው ጠፋ። ተለያይተው የቆዩበት ጊዜ ረዥም ነበር። ጭለማውና ሰው በሌለበት ቦታ ያደረጉት ግንኙነት ጉጉታቸውን ጨመረው። ፍላጉት አጠጋጋቸው። ወዲያውኑ ተቃቀፉ። እርስ በርሣቸውም በመሣሣም ተሸፋፈኑ።

«ምን ያህል ደስ እንዳለኝ» አሉ፣ ተራ በተራ።

የያንዳንዳቸውን ከንፈሮች አጣጣሙ። ትዕግስት በሌለው ሁኔታ፣ በርግጥ እንደኛው አብሮት መኖሩን ለማረጋገጥ በሰቀቀን ሥጋቸውን አነካኩ። በዚህም ደስታን ሸመቱበት።

ሁሉም ነገር ጠፍቶ፣ በፍቅር መድረክ ላይ ሁለቱ ብቻ ነበሩ። ስለዚህም ጥቂት ቃላት አስፈለጓቸው። መቀራረባቸው በራሱ በቂ ነበር። ነገር ግን በፍርግርጉ የብረት በር በኩል ጥበቃ ስታደርግላቸው የነበረችው ፍራንቾይዝ መጥታ፣ ብዙ ጊዜ እንደሌላቸው ነገረቻቸው። ንግግሩ፣ በመንገዳቸው ላይ ጥንቃቄ ስለሚያስፈልገው መሰናክልና ወደ አውኑ ዓለም መልሟቸው።

«አባቴን እንዴት ልታግባባው ትችላለህ?» አለች አሊስ፣ ቀጭኑን ጥላውን ብቻ የምታየውን ፍቅረኛዋን እየተመለከተች «ደግሞና ደጋግሞ እንደሚድረኝ ነው የሚያወራው»

«ለጊዜው ምንም አንሃገራቸውም። እርሳቸውም፣ አንዳችም ነገር እንዲጠረጥሩ አናደርግም። ከዚህ በኋላ ግን መተያየታችን ይቀጥላል። አንቺን በክንዶቼ ውስጥ ካልያዝኩሽ በስተቀር መኖር አልችልም። ይኸው አሁን በመጨረሻ ላይ አብረን ሆነናል። እኔ አቅዴን ወደ ተግባር አስክለውጥ ድረስ አንድም ሰው እንዳያውቅ ይሁን። ሆኖም ግን አስቀድሞ ወደ ቬርሣይለስ እሄዳለሁ»

«ምን?» አለች አሊስ፣ በፍርሃት ወደርሱ ሽጉጥ በማሰት። «እዚህ የደረስክው እኮ በብዙ ውጣ ውረድ ነው። ይህ እያለ አሁንም ስመሄድ ትፈልጋለህ?»

«ፈጋ ብለሽ ብታስቢው፣ ያሰው ብቸኛ መፍትሔ ይኸው እንደሆነ ታያለሽ። ንጉሱ፣ ኤምባሲ ይፈልጋሉ። ታዲያ፣ እኔ እንድ አመጣሁላቸው። የምፈልገውን ውለታ ሊከፍሉኝ የሚችሉት እርሳቸው ብቻ ናቸው። ስመለስ ከብር ያለው ሰው ሆኜ እመለሣለሁ። ያን ጊዜ አባትሽ የሚከለክሉኝ ነገር አይኖራቸውም»

የምታፈቅረው ሰው የሚነግራትን ማንኛንም ነገር ለመቀበል፣ አሊስ ዝግጁ ነበረች። ነገር ግን እቅዱ እንደገና እንዲለያዩ የሚያደርጋቸው ስለሆነ አልተደሰተችበትም። በሌላ በኩል ግን ይህ እቅድ የተሻለው ዘዴ እንደሆነና እርስዋም ጀን ባፕቲስትን፣ በርስዋ አቅምና ችሎታ ሥር ባለ ነገር ሁሉ እንደምትረዳው ማለች።

«ልትረዚኝ የምትችይው አንዱ መንገድ እኔን አለመርሣትሽ ነው።»

በኩርፊያ ቁጣ፣ ተቃውሞዋን ስትሰነዝር፣ በረዥም መሣም ታፈኑ።

በመጨረሻም ፍራንቾይዝ ተመልሣ በመምጣት፣ የዕለቱ ተረኛ ተዘዋዋሪ ዘበኞች የሚመጡበት ሰዓት ስለሆነ እንዲላቀቁ ለመነቻቸው። ተላቀቁና መልሰው በፈጣን እርምጃ ለአንድ ጊዜ ተቃቀፉ። በመጨረሻም ሁለቱም በሞቃቱ ምሽት በተለያየ አቅጣጫ ተጓዙ። ከበላያቸው፣ የዘንባባ ዛፎች በነፋሱ እየተወዛወዙ ይንሳጠጣሉ።

ሙራድ፣ በጀን ባፕቲስት ላይ ሙሉ እምነት አለው። ንጉሡ ራሣቸው፣ ለዚህ እንግዳ፣ የተለየ ፍቅር አሣይተውት አልነበረም? በዚህ ምክንያት፣ ሐኪሙ የሚጠይቀውን ማንኛውንም ነገር ለመፈፀም ፈቃደኛ ሆነ። ይሆን ሁሉ እንዲህ ቀላል ያደረገው ሌሎች የፈረንሣውያን ማህበረሰብ ነዋሪዎች ሊማርኩት ስላልቻሉ ነው። እነዚህ ሲበዛ ሃብታምና ሲበዛ ፍልቅልቅ የሆኑ ነጋዴዎች፣ አሌፖ ውስጥ የነበረውን የጥንቱን ጌታውን አስታወሱት። ያ የጥንት ጌታው፣ ሁልጊዜም በመልካም ቃላት እየሸረደደ በክፍተኛ ግብዝነት የሚሠራ ነው። ብዙ ጊዜ በጥንቃቄ የተሠራውን ምግብ በቀጣሪው ሰው ፊት ላይ ለመወርወር ይቃጣም እንደነበር አስታወሰ። አሁን ቢሆን ሊያደርገው ይችላል። በተቀባይ ጫፍ ያሉት ምንም ካላደረጉት ሲበዛ መጥፎ ነው።

«ምን ማለትህ ነው፣ የሹመት ደብዳቤዬን ስትል?» አለው ሙራድ በኩራት፣ ሙሴ ማቹ ስለደብዳቤው ሊጠይቀው በመጣ ጊዜ። «ማን የሆንኩ ነው የመሰለህ? እኔ እኮ የንጉሡ መልዕክተኛ ነኝ። የነገስታት ንጉስ፣ ከዚህ የበለጠ ምን አለ?»

እንደሐፃን ልጅ የፋፋትን እጆቹን፣ በነሃስ ቀለበት የተጌጠውን ትንሽ ጣቱን ተመለከተና ተጠለ።

«ግርማዊነታቸው በጥብቅ ያሣሰቡኝ፣ ደብዳቤአቸውን ለማንም ሰው ሳይሆን፣ ለፈረንሣይ ንጉሥ በእጃቸው እንድሰጣቸው ነው። ደብዳቤዎቹን ለመስጠት ወደ ቬርሣይለስ መሄድ ይኖርብኛል።»

ሙሴ ማቹ ሙጭጭ አለ። አርመናዊውም ከአቋሙ ፍንክች አልል አለ። በመጨረሻም ግን ፈረንሣዊውን አዋርዶ አባረረው። ፀሐፊው፣ ወደ ቆንስላው በፍርሃት ተሞልቶ ተመለሰና የነበረውን ውይይት በቅሬታ አገላለፅ ለሙሴ ዴ ማይሴ ተረከለት።

«አህ! እንዲህ ነው እንዴ!» አለ ዲፕሎማቱ።

«ደብዳቤውን ማሣየት አይፈልግም! ግን ምን የይለፍ ይሂል። መሬት ላይ ተቀምጦ መላውን ማህበረሰብ እንዲሰድብ እንፈቅዳለን? ነገር ግን እጅግ ቢያንስ በሕጉ መሠረት ራሱን ማሣወቅ ይገባዋል።»

«ምናልባትም ለርስዎ . . . » ሲል ሙሴ ማቹ ሃሳብ ሰነዘረ

ቆንሲሉ ባለበት ረጋና፣ ምስኪን ፀሐፊውን ጥላቻ በተሞላው እይታ አተኮረበት

«እኔ የፈረንሣይን ንጉሥ የምወክል፣ የሹመት ደብዳቤውን የማያሣየውን ሰው ማነጋገር እንደምችል መገመትህ የሚያጠራጥር አይደለም»

«አይደለም፣ በእውነት» አለ ሙሴ ማቹ በመለማመጥ

«መልካም። ሊያገለግለው የሚችል ሌላ መልዕክተኛ እንልክበታለን»

«ወደዚያ ተመልሶ ለመሄድ አንድም ነጋዴ ፈቃደኛ አይሆንም»

«እንግዲያው ራስህ ትሄዳለህ።» አለ ሙሴ ዴ ማይሴ «እናም የሹመት ደብዳቤውን ከነገ በፊት ባያቀርብ ከማህበረሰቡ ሰፈር እንደሚባረር ትነግረዋለህ። ከዚያም በአሮጌው ካይሮ ሠፈሮች ውስጥ የሚስማማውን መስፈሪያ ሊፈልግ ይችላል»

ማቹ፣ መልዕክቱን ለማድረስ ሄዶ፣ ጀሮ ግንዱ ላይ አምባረቀበት። መራድ፣ የብልግናውን ደረጃ ከፍ በማድረግ ዘይት የጠገበውን የባቅላቫ ቁራጭ አስቀድሞ ትንሽ ከገመጠ ;;ኋላ፣ ማቹ ጭንቅላት ላይ ወረወረ።

«ይህ አክስተኛ ቀልድ እዚህ ላይ ያከትማል» አለ ሙሴ ዴ ማይሴ፣ በርጋታና በቆራጥነት። «የዚህን የደብዳቤ ሥረ መሠረት እንዴት ማግኘት እንደምችል አውቃለሁ።

እናም አመነኝ፣ አንድም ደብዳቤ አለመያዙ ከተረጋገጠ ይህን ሸካራ ፀባዩን እንደያዘ፣ እርሱን፣ ከብቶቹን፣ ባሮቹንና ቁርጥራጭ ጨርቆቹን መንገድ ላይ ለመወርወር ጥሩ ምክንያት ይኖረኛል።»

ይህን ከተናገረ በኋላ፣ ቆንሲሉ፣ ጋሪው እንዲዘጋጅለትና፣ ፓሻው ዘንድ፣ ሊቀር የማይችል ጉብኝት እንደሚኖረው ለስቀድሞ እንዲያሣውቁለት ተናገረ።

ከስብሰባው ሲመለስ ስለራሱ በጣም ተደስቶ ስለነበረ፣ ያን ሌሊት በጥሩ ሁኔታ ተኝቶ አደረ። በማግስቱ ወደ ቢሮው ሲገባ ግን አባ ፕላንቴይን መምጣታቸው ተገለፀለት።

ጀስዊቱ፣ ካይሮ የደረሱት፣ አባ ብሬቬደንት ወደ ኢትዮጵያ ከሄዱ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነበር። አባ ጋቦሪን የአልጋ ቁራኛ ያደረጋቸው ሕመም፣ እነሀን አዲስ መጪ ካህን በይፋ እንዲታዩ አደረጋቸው። በጥቂት ሣምንታት ውስጥም አባ ፕላንቴይን በዚህ ጣቢያ ላለው የምስራቅ ሚዲቴራኒያን ሕጋዊ ተወካይ ሆኑ።

ዕድሜአቸው አርባ ዓመት ይሁል ይሆናል። ሰውነታቸው በሚገባ የተገነባ ነው። ይህ ደግሞ፣ እንደአውነቱ ከሆነ ቤተሰባቸው በቀንድ ከብቶች ኢንዱስትሪ ፈረንሣይ ውስጥ፣ በቻሮሌ አካባቢ ለዘመናት መስራቱ ነው። ረዣዥም አለንጋ የመሰሉ ጣቶች ሲኖሯቸው፣ ቀስ እያሉ እጃቸውን ይጨብጧቸዋል፣ ይዘረጓቸዋል። እጆቻቸውን በፍቅር ሲመለከታቸው፣ የቀንድ ከብቶች እረኝነት መሠረት እንዳላቸው ብቻ የሚያጋልጠብቸው አይደሉም። ጭንቅላታቸው፣ ክብ አለት ከመሰለው ከትልቁ ግራጫ የራስ ቅላቸው በታች፣ ጠፍጣፋ ሆኖ በአይኖቻቸው ላይ ወደፊት አብጦ የወጣ ነው። ግንባራቸው ትልቅ ነው። ቀደም ባለው ጊዜ ይህ የብልህነት መለያ የነበረ ቢሆንም፣ አሁን ግን ልክ ክብደቱ በመላው ፊታቸውና መላ አካላቸው ላይ ቁልቁል የተጫነው ይመስል፣ አንዳች የዘገምተኝነት ስሜት ሰጥቶታል። የተፈጥሮ ቅርፃቸውን ብቻ ብንወሰደው፣ በቀላሉ ድንጋይ ጠራቢ ወይም ሙዚቀኛ ሊሆኑ ይችሉ ነበር። ለመማር ጥሩ ጭንቅላት ቢኖራቸውም፣ አሁንም በመማር ላይ ያሉ ግን ምንም ልምድ የሌላቸው ናቸው። ካይሮ ከደረሱበት ጊዜ ጀምሮ፣ ሰቆንሲሉ ብዙ ወዳጃዊ ጥርጣሬአቸውንና በሌሬ ተግባር ለመሰማራት ማቀዳቸውን ነግረውታል። በመጀመሪያ ላይ፣ ቁሱ ቀላልና ፊት ለፊት ናቸው ሲል፣ ሙሴ ዴ ማይሴ አሰበ። ውሎ አድሮ፣ የአታላይነት ባህሪይ ሲያይባቸው ስህተቱን ተገነዘበ። ከዚያ ወዲህ፣ ለጀስዊቱ የአታላይነት ባህርይ ዕድል ነፈገው።

«እርስዎን ማየት ደስታ ነው አባቴ!» አለ ቆንሲሉ፣ ጥቁር ካባ የለበሱት ሰው በቤቱ በር ደርሰው ሲያያቸው። ይህ ሁሉ ሲሆን፣ ዲፕሎማቱ፣ አንድ ሰው መርዘኛ እንስሳን በትንሽ የጭራሮ ጫፍ ለማንሣት ሲል የሚያደርገውን ጥንቃቄ ያህል ራሱን ጠንቀቅ አድርጐ ነበር።

አባ ፕላንቴን፣ ቢያንስ ለማንልገል ፈቃደኛ አልነበሩም። አጭበርባሪነታቸው በማስመሰል በጀግንነት የተሸፋፈነ ነበር። ስላምታቸውን ጮክ በማለት «ክቡርነትዎ!» በማለት ትዕዛዝ ለመቀበል እንደተዘጋጀ ሰው በተጠንቀቅ ቆሙ።

«ማስታወሻዎን ተቀብያለሁ፣ ክቡር ሆይ አመሰግንዎታለሁ። እጅግ ድንቅ ዜና ነው። ምስኪኑ አባ ዱ ብሬቪደንት ጉዞውን በሕይወት አለማጠናቀቃቸውን ከግምንት በፊት አውቀን ነበር። ከዚህ መጥፎ እድል በስተቀር ሁሉም መልካም ነበር። አምባሣደራችንም መጥቷል» አሉ ጀስዊቱ

ወደ አቢሲኒያ ተልኮ የነበረው የመልዕክተኞች ጓድ መመለሱን፣ ቆንሲሉ፣ ለእየሱስ ማህበረሰብ[6] ተወካዮች አስታውቋቸው ነበር። ወደ ኋላ መለስ ብለው ሲያዩት፣ ይህ ከርህራሄ የመነጨ ሊመስል ቢችልም፣ ቅፍለቱን ለመቀበል ከተንቀሣቀሰው ጓድ ጋር እንዲቀላቀሉ ካዘኑን አልጋበዛቸውም።

«እንደሚመስለኝ» አሉ ቄሱ። «እርስዎ ያረጋጠጡልኛል እንጂ፣ የተመለሱት ከሦስት አቢሲኒያውያን ተወላጆች ጋር ነው»

«አኔም እንደዚያ ነው የሰማሁት»

«እርስዎም አላየኋቸውም ነው የሚሉኝ?»

«በጨረፍታ ብቻ ነው»

የሹመት ደብዳቤውን ጉዳይ በማንሣት ከኢህ ችግር ፈጣሪ ጋር ለመወያየት፣ ሙሴ ዴ ማይሌ ፍላጐት አልነበረውም።

«ገና መድረሣቸው መሆኑንማ አይዘንጉ እንጂ» አላቸው ሙሴ ዴ ማይሌ በየዋህነት

ጥቁር የለበሱት ሰው፣ የተሸከሙት ክብደት፣ አካላዊ እንቅስቃሴአቸውን ያሰቃየው መሆኑን በሚመስክር መልኩ ጭንቅላታቸውን ደጋግመው አነቃነቁ።

«ሰምሥራቅ ተማሪዎች በተያዙ መቀመጫዎች ላይ ሦስት አቢሲኒያውያን በታላቁ የሉዊስ ትምህርት ቤት ሊገቡ ነው።» አሉ ጀስዊቱ አይናቻቸውን እያቁለጨለጩ። «ይህ ደግሞ ታሳቅ ዱላ ይሆንብናል። ክቡር ሆይ! ለመሆኑ እርስዎ ይህ እንደሚሆን አውቀው ነበር» ሲሉ ቄሱ ወደፊት ዘንበል ብለው ንግራራቸውን ቀጠሉ። «ማለቴ በቅርቡ በኢትዮጵያና በሲናር ንጉስ መካከል በተደረገው ጦርነት ላይ፣ ካፑቺኖች ሰባቱን እንደያዟቸው ያውቁ ነበር? እስቲ ያስቡ። እነዚህ ሰዎች በቀጥታ ወደ ሮም ሊያመሩ ነው . . . »

ወደ ቆንሲሉ ይበልጥ ጐንበስ ብለውና ድምፃቸውንም በጣም ዝቅ አድርገው

« . . . ለዚያውም ቱርኮች እንዲማፈሩ የሚፈቅዱላቸው ከሆነ።»

እነዚህን ቃላት በፈገግታ አጀበው የተናገሩት ቄስ፣ በሁኔታዎች ሂደት ውስጥ ጣልቃ ለመግባት ማሰባቸው አያጠራጥርም

«እኛም ተመሣሣዩ ችግር ይኖርብናል።» ሲል ቆንሲሉ ጀመረ። ወዲያውኑ ግን ተፀፅቶ «በተሰይ ከአገራቸው ወጥተው ወደኛ ዘንድ የመጡትን አቢሲኒያውያን በመሳካችን ችግር ይኖርብናል»

«እ! ክቡር ሆይ» አሉ ጀስዊቱ፣ ራሣቸውን በግርማ ሞገስ ቀና እያደረጉ። «የፈረንሣይ ንጉሥ የሚሹት ጉዳይ፣ እዚህም ቢሆን ክብደቱ ተመሣሣይ ነው። ቱርኮች እኛ የምንላቸውን እንደሚሰሙን አምናለሁ። በርግጥ ፋታ ላልሰጥዎና ተራ ላልጠብቅ እያወራሁ ነው። እርስዎ ዲፕሎማት ስለሆኑ እነዚህን ጉዳዮች ከኔ በተሻለ ያውቋቸዋል።»

ሙሴ ዴ ማይሌ ፣እንደ አሮጊት ልብስ አጣቢ፣ አንዳች የጥላቻ መግለጫቸውን ፍንጭ የሰጡትን እኒህን እንደ አለት የጠነከሩ የሚመስሉ ሰው ሸፍጥ አደነቁ።

«አባ፣ እርስዎ እንደገለፁት የዲፕሎማቲክ ሥራዎች በጣም ውስብስብ ናቸው። እንደመጣልኝ ልናገረውና የዲፕሎማቲክ ሥራዎች ምናልባትም እርስዎ ከሚገምቱትም በላይ ነው። ዋናው ሃላፊነትም፣ ሁሉም ነገር ተራ በሆነና በተለመደው መልክ መከናወን የሚገባው

መሆኑ ነው። እርስዎ የክርስትናን እምነት እያገለገሉ ነዎት። እንቅስቃሴ በማደንዘዣ ስለመተላለፉና የመንፈስ ቅዱስ ብርሃን በሰው ልጅ ነፍስ ላይ ስለመውረዱ ልምድ አለዎት። እኛ ደግሞ በሌላው ወገን የምንሠራው በዚህ ዓለም ገፅ ላይ ነው። ፖለቲካ የሚከናወነው በሰዎች እንቅስቃሴ ላይ ነው። ለዚህም መጣደፍ የለበትም»

የዚህን አነስተኛ ንግግር ምንነት ጀስዊቱ በጭራሽ አልተረዱም። ከአመታት በፊት፣ አባታቸው አታላይ ነው ብለው የሚያስቡትን አንድ ውብና የደለበ እንሰሳ እንደሚመለከቱት አይነት፣ ቁሱም ቆንሲሉን በጥልቀት በተሸበሸበት አይናቸው ቂጥ ተመለከቱት። ቆንሲሉ፣ አንዳች ከፍተኛ ጉዳይ እየደበቃቸው እንደሆነ አምነዋል። ጭውውቱ ለተጨማሪ አስር ደቂቃዎች ቢቀጥልም ቁሱ ምንም ያወቁት ነገር አልነበራቸውም።

ጀስዊቱ ወጥተው በመሄድ በመንገዱ ላይ እያመነቱ ሲጓዙ ቆይተው፣ ወደ ፖንሴ ቤት አቀኑ። እንደደረሱ በሩን ቢያንኳኩም ጆን ባፕቲስት በቤቱ ውስጥ አልነበረም። ከዚያ በኋላ ወደ ቬኔስያዊው ቤት ሄዱ። ከአትክልቱ መግቢያ በር ላይ ዝርግት ብሎ የነበረው አንድ ሽማግሌ ቱርካዊ፣ የተከበሩት የኢትዮጵያ አምባሣደር ማንንም እንደማይቀበሉ ለአባ ፕላንቴይን ነገራቸው።

ጀስዊቱ፣ ግራ ተጋብተው ወደ ቤታቸው ሄዱ።

ሜትር ዝረሚ፣ ጥንቃቄ በተሞላው ሁኔታ በቆንሳላው ግቢ በምሽት፣ በየጭለማው ጥላ ውስጥ እያደባ ወደ ማህበረሰቡ ሰፈር ተመለሰ። እቤት ሲደርስም፣ ከፖንሴ ጋር ለመጨረሻ ገዜ የተያዩት ከሁለት ወራት በፊት እንደነበረ ሁሉ ፖንሴ እርሱን በማየቱ ሲደሰት አገኘው።

ባለፈው ቀን የነበረውን ሁኔታ ጆን ባፕቲስት ነግሮት ካበቃ በኋላ፣ ፕሮቴስታንቱ በመቀጠል፣ «መቼም አዚህ ስትደርስ የጀግና አቀባበል እንዳደረጉልህ፣ አንተም ጀብዱህን በአድናቆት ለሚያወሩ ወይዛዝርት ስትናገር እንደቆየህ እገምታለሁ።» አለው

«ይህ የሚያመለክተው የማህበረሰቡን ሠፈር ምን ያህል እንደምታውቀው ነው። ፈሪዎች ስለሆኑ እርስ በርሣቸው ይሰላለላሉ። እኔ እንደሆንኩ በየሄድኩበት ቦታ እንኳን ደህና መጣህ አልባልም። ሊያዩኝ የሚፈልጉኝ ሰዎች ደግሞ እኔ ልርቃቸው የምፈልጋቸው፣ ለምሳሌ ዛሬ ከሰዓት በኋላ እንደመጡት ጀስዊት ያሉ ሲያነጋግሩኝ እንደሚፈልጉኝና ጉረቤቱ ሁሉ ይህን እንዲያውቅላቸው የሚሹ ናቸው። ጉዞው ገና አለመገባደዱን እመነኝ። ባለፉት ሁለት ቀኖች ምድረበዳውን ስናቋርጥ ከነበርንበት ሁኔታ ይልቅ ብቸኝነት ተሰምቶኛል።

«ሙራድስ?»

«በርግጥ እርሱን አገኘዋለሁ። የመሣፍንት መኖሪያ ቢሰጡትም፣ ቆንሲሉ አስካሁን ሊያገኘው አልተስማማም። ቆንሲሉ የሹመት ደብዳቤውን ሊያይበት ይፈልጋል። እኔ ደግሞ፣ ሙራድ ደብዳቤውን እንዳይሰጠው ቃል አስገብቼዋለሁ። እንዲያውም፣ ተልዕኮው አስክ ቬርሣይለስ እንደሚቀጥል ከመግለፅ ሌላ ትንፍሽ አላለም።»

«እና ፍቅረኛህስ?»

«ዳግመኛ መቼ እንደማያት አላውቅም። ትናንት ምሽት ላይ . . . ለመሆኑ ምግብ ቀምሰሃል?»

«አስካሁን ገና ነኝ»

«እንግዲያውስ ከዛሰን መስጊድ ባሻገር ወዳለው፣ ወደ ዩሱፍ ቤት እንሂድ። እዚያ በሰላም መጫወት እንችላለን»

ሁለቱም ደስ ብሏቸው ወደ አሮጌው ካይሮ ተያይዘው በእግራቸው ተጓዙ።

ፖንሴና ሽሪኩ እኩለ ለሊት ላይ ወደ ቤት ተመለሱ። ልክ በራቸው ሲደርሱ ከጨለማው ውስጥ አንድ ጥላ ወደነርሱ ዘልሎ ወጣ። ሚትር ዝረሚ ጉራዴውን መዘዘ።

«ይትር፧» አለ፣ ጥላው። «አኔ ነኝ»

«ሙራድ! በዚህ ውድቀት ሌሊት እዚህ ምን ታደርጋለህ?»

ወደ ቤቱ ውስጥ ገፍተው አስገቡት። ፖንሴ ጧፍ አበራ። አርመናዊው በላብ ተዘፍቆ ቁና ቁና ይተነፍሣል።

«ተኝቼ እያለሁ ከጥቂት ጊዜ በፊት አንድ ሃያ የሚሆኑ ሰዎች ገቡ» አለ ሙራድ እያለከለከ

«ሃያ ሰዎች? እነማን ናቸው? ወታደሮች ናቸው ወይንስ ነጋዴዎች?»

«ወታደሮች ናቸው። ቱርኮች ናቸው። ሙሉ በሙሉ ያበዱ ሰዎች ነበሩ። ዘልለው ያዙኝና ትልቅ ጉራዴአቸውን መዝዘው አንገቴ ስር በመወደር አንድማረክላቸው አፈጠጡብኝ፣ እዩት»

አገጯ ስር የተንጠለጠለውን ወፍራም ቆዳውን አሣያቸው።

«እና ከዚያስ?»

«ከዚያማ ሁሉንም ነገር ፈተሹ፣ ሁለንም ነገር እየገለባበጡ አመሰቃቀሉ፣ ሁሉንም ነገር ከፋፈቱ። ቤቱን በሙሉ፣ የሳዩን ወደታች የታቹን ወደ ላይ ካደረጉት በኋላ፣ ነገ ጧት ፓሻው ዘንድ እንደምቀርብ ብቻ ነገሩኝ።

«ምንድን ነበር የፈለጉት?» ሲል ፖንሴ ጠየቀ

«ምንስ ወሰዱ?» ሲል ሜትር ዠሪሚ አከለ

«ምንም»

«እንዴት፣ ምንም?»

«ምንም፣ ወርቅ አልወሰዱም፣ ገፀ በረከቶችን አልወሰዱም፣ ልብሶችንም አልወሰዱም»

«ምንም ነገር አልወሰዱም?»

«የንጉሡን ደብዳቤ ብቻ» አለ ሙራድ አይኖቹን ሰብሮ

6

ፖንሴ ባልነበረባቸው ረዥም ጊዜያት ውስጥ ታማኝ ታካሚው የነበረው የካይሮ ፓሻ ሁሳይኒ፣ ከፈረስ ላይ ከፋኖ ወድቆ እግሩን ተሰብሮ ነበር። የሕክምናው ዕውቀትና ችሎታ የሌላቸው አታላዮች እንዲያከሙት ይጠራሉ። እነዚህ አጭበርባሪዎች በሕክምናቸው የፓሻውን የእግር ቆዳ በመጥፎ ሁኔታ በማሸት ስብራቱን በድጋሚ ያናጉታል። የሕዝብ አመፅም ይሁን፣ ወይም መርዝም ይሁን፣ ወይም ደግሞ ብልግና የተሞላበት ሀክምናም ይሁን፣ ያከናወኑት ጉዳይ ብቻ በአንድ የወሰን ምልክት ድንጋይ ማደናቀፍ ላይ ተሳክቦ ቀረ። ሁሳይን ከፋኖ ተሰቃይቶ ሞተ።

ሁሳይኒን እንዲተካው በከፍተኛው ባለሥልጣን ተሹሞ የተላከው ሰው ደግሞ፣ ፍፁም የተለየ ነበር። ስሙ መሃመት ቤይ፣ ሊሰኝ፣ ፍፁም ጦረኛ ነበር። በሃንጋሪ ውስጥ የቱርክ ወራሪ ሃይል ፊታውራሪ በመሆን ሲያገለግል፣ ለክርስትና ፍፁም ጥላቻ ያለው ሆኖ ተገንጥሎ ወጣ። ይሁን እንጂ፣ ይህ ሰው፣ አንዱን ሕዝብ ከሌላው መለየት ስለሚችል ፈረንሣውያንን በሚገባ ለይቶ ያውቃቸዋል። እንዲህ ያለውን አስቸጋሪ ሥራ የሚያከናውኑት ጥቂት ቱርካውያን ናቸው። ከፈረንሣውያን ጋር በቀጥታ አልተዋጋም። ይሁን እንጂ፣ ፈረንሣውያኑ በሃፕስበርጐች ላይ ከከፍተኛው ባለሥልጣን ጋር ብዙ ልዩ ልዩ ምስጢራዊ ንብረቶችንና ስምምነቶችን ማድረጋቸውን ያውቃል። ዕድሜ እያሸነፈው ሲመጣ፣ መሃመት ቤይ፣ በሊማሞችና በሙፍቲዎች እጅ ወደቀ። እነዚህ ቅዱሣን ሰዎች በጥበብና በዘዴ፣ ራሣቸውን የፓሻው መንፈሳዊ መሪዎች አደረጉ። ይህም፣ ይህ ጠንቃቃ፣ ነገር ግን ማይም የሆነ ሰው ከቀደሙት መሪዎች ይልቅ በእስልምና ጠላቶች ላይ ያለው መረጋጋት ቀዝቀዝ ያለ መሆኑን ተስፋ ቡማድረጋቸው ነው።

ሙራድ፣ ከፓሻው ፊት ተክሰስ በቀረበ ጊዜ፣ መሃመት ቤይ በመጀመሪያ የብስጭት ቁጣውን ለቀቀው። አርመናዊው የሚቀርብለትን ቃለመጠይቅ በማሰብ በጣም ከመፍራቱ የተነሣ፣ እስከ ከተማው ጠባቂ ድረስ ራሱን አረጋግቶ በበቅሎው ላይ ሆኖ ደረሰ። እንደ አድል ሆኖ የከተማውን የጥበቃ በር በበቅሎ ላይ ሆኖ የመግባት መብት በአገሮችና ቋንቋዎጊንያ በሚገኘው ከፍተኛው ባለሥልጣን መካከል በተደረሰ ስምምነት መሠረት ለክርስቲያን

አምባሣደሮች የተወሰነ ነበር። ጠባቂዎቹ፣ ሙራድን በሚዘገንን ሁኔታ ከበቅሎው ላይ እንዲወርድ አድርገው በፓሻው ፊት ጉተቱት።

«ለመሆኑ ማን የሆንክ ይመስልሃል?» ሲል ወርቅማ ጥብጣብ የሚከብበውን የራስ ጥምጣሙን አጥልቆ፣ የቱርኮችን ቀይ ዩኒፎርም ለብሶ፣ በእብሪት ተውጥሮ የቆመው መሃመት ቤይ ጠየቀ። «ሆናም ግን አስቀድመህ ዝቅ ብለህ ስገድ! ሡልጣኑን ላለማክበር ሃሣቡ አለህ?»

«እኔ . . . እኔማ አከብራቸዋለሁም። የሚገባቸውንም ክብር አቀርባለሁ» አለ ሙራድ ተንበርክኮና የድንጋይ ንጣፍ ወለል ላይ አፍንጫው ተጣብቆ እየተንቀጠቀጠ።

«ከዚህም በላይ» አለ መሃመት ቤይ፣ ከፊቱ ሰግዶ ባለው ሰው ዙሪያ እየተራመደ፣ «አንተ ቱርካዊ አይደለህም።የአክብሮት ነገር በጣም ከማጣትህ በስተቀር ቋንቋችንን ትናገራለህ፣ ባህላችንንም ትጋራለህ። መቼም ሃይማኖትህን የካድክ አትሆንም፣ ከደህ ይሆን?»

«በጭራሽ፣ በጭራሽ፣» አለ፣ አሁን ድረስ አፍንጫው መሬት ላይ ተጣብቆ ያለው ሙራድ። ቆሞ ቢሆን ኖሮ የክህደት እርምጃ ለመፈፀም ቃጥቶ የነበረው ሙራድ እውነቱን እየተናገረ። «እኔ አርመናዊ ነኝ። ሃይማኖቴም ከአባቴና ከታላቁ ሰው፣ ከቱርካዊው ሱልጣን በርህራሄና ጥበብ ከተሞላው የወረስኩት ሲሆን ሃይማኖቴን ጠብቄ እንድቆይ ያደርገኛል»

« እኛ የፈረንሣይ ውሾችን ስንዋጋ፣ አናንተ ከጀርባ ሆናችሁ ስትወጉን ሱልጣኑ፣ ለክርስቲያኖች እጅግ ታላቅ ርህራሄ ያሣያችኋል። መቼም የዚህች ዓለም ጉዳይ እንዲህ አይደል? . . . »

ተነስ! እስቲ ይህን ከሃዲውን ፊትህን አሣየኝ»

ሙራድ ቀና ቢልም፣ በእንብርክኩ ላይ ቆየ። ወፍራሙ ፊቱ፣ ለረዥም ሰዓታት ተዘቅዝቆ በመቆየቱ ቀልቶና አብጦ ይታያል። ፓሻው አንዱን ጠባቂውን ሊጠቅሰው፣ የብር ትሬውን ይዘለት ቀረበ። ከዚያም ላይ ፓሻው የንጉሡን ደብዳቤ አነሣ።

«የኑብዩን ትዕዛዞች ሣትቀበል፣ በመሬታቸው ላይ መኖርህ ብቻ ሣይሆን፣ እኔ እስከሚታዮኝ ድረስ አንተ እስልምናን በፅናት ከሚከላከሉና እንዲያውም ከሚወጉት ጋር የተባበርክ ነህ»

ሙራድ አቅሱ ከተመለሰለትና ከተበረታታ በኋላ፣ ወኔውን ሞልቶ ምን ማለት እንደሚገባው ፖንሴ የመከረውን ለማስታወስ ሞከረ።

«ክቡር ሆይ፣ እኔ ነጋዴ ነኝ» ሲል በደካማ ድምፅ አሳዘነ። «መኖሪያዬን የማገኘው የምችለውን ሁሉ አድርጌ ነው። ወደቀይ ባህር የወሰደኝ ዕድል ፈንታ ነው። ለአጭር ጊዜ ያህል ለምዕዋው ናኢብ አገልግዬ ነበር። እርሣቸው ጥሩ ሙስሊም ናቸው። አንድም ጊዜ በኔ ላይ ቅሬታ አልነበራቸውም። ይህን ሊጠይቋቸው ይችላሉ። ከዕለታት አንድ ቀን ለኢትዮጵያውያን ንጉስ የማደርሰው መልዕክት ሰጡኝ»

«ለዚያ ቀበሮ ደብዳቤ የሚልክለት ለምንድን ነው?»

«ክቡር ሆይ፣ በቀድሞው ጊዜ አቢሲኒያውያን ውሃውንና እህሉን ሁሉ አቋርጠውባቸው ነበር። ናኢቡ፣ መሬታቸው ከርሣቸው በላይ በተራራው ላይ ከሚገኙት ከጐረቤታቸው ጋር ከመስማማት በስተቀር ሌላ ዕድል አልነበራቸውም።»

መሃመት ቤይ፣ የሙራድ ንግግር አእምሮውን ዘልቆ የገባው መሆኑን በሚያመላክት ሁኔታ አይኖቹን በትንሹ አንሸዋረራቸው። ከጠጣሩ ጭንቅላቱ ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ምናልባትም እርሱን በሚመለከት ከሆነ፣ ከስንት አንድ ጊዜ ቢባል የተሻለ ይሆናል፣ እውነታ አብረቅርቆ፣ ሃሣብ የሚባለውን የሚያበሳጭ ነገር ሰርስሮ ይገባዋል።

«እንዲህ ከሆነ ንጉሡ በርግጥ ውሃ ወደ አገራችን እንዳይፈስስ መከልከል ይችላል ብለህ ታስባለህ? ይህ ከሆነ ደግሞ ይህን ያህል ከልቡ የሚጠላን ከሆነ ለምን እስከዛሬ አላደረገውም ነበር?»

«ይህንን በባህረ ገፁ ምዕዋ ላይ ፈፅሟል። ላሳነሰ ጊዜ ምዕዋን ሁሉንም ነገር ነፍገዋት ነበር»

«ይሁንና እኛን በተመለከተ፣ እዚህ ግብፅ ውስጥ በአባይ ወንዝ ላይ ሕይወታችን የተመሠረተውን?»

«ክቡር ሆይ፣ እኔ ከማውቀው ከሁሉም በበለጠ፣ ንጉሡ አንድም የመከልከያ ዘዴው የላቸውም ወይም ለሙስሊሞች የሕይወታቸው መሠረት የሆነውን ውሃ የመንፈግ ምክንያት

የላቸውም። ነገር ግን ሊታሰብ የሚገባው ንጉሡ የአባይን የላይኛውን ፍሰት፣ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ የሚፈሰሰውን እንብልና ወደ ምስራቅ አቅጣጫ ቢሰውጡት፣ የግብፅን ፍፁም መውደም ብቻ የሚያመለክት ሣይሆን፣ ነገር ግን. . . »

«ነገር ግን ምን?»

« . . . ነገር ግን በተመሣሣይ መልኩ እንደርስም ሙስሊም ሰሆኑት ሰሶማሊያውያን ብልፅግናን ያስገኙላቸዋል»

ፓሻው እነዚህን ቃላት መዘገባቸው። ቃላቱ በአዕምሮው ጥልቅ ሞሰማ ጓዳ ውስጥ ተጉዘው፣ በመጨረሻ ላይ አርሱ ራሱን በሣቅ አፈነዱት። ሣቁ ደግሞ፣ በታላቁ አዳራሽ ዙሪያ በጥበቃ ላይ ባሱ ዘበኞች ተቀባይነት በቀላሱ የገደል ማሚቶ ፈጠረ።

«አግዚአብሔር ወደ ምድር የሚልከው ውሃ» አለ ፓሻው «አስቀድሞ በርሱ ለሚያምኑትና የርሱንም ኾብይ ለሚከተሱት የታደላቸው ነው። ጌታህ፣ ዝናቡ በመጀመሪያ ከርሱ ጠቃሚነት በሌላቸው ትራሮቹ ላይ በመዝነቡ፣ ሃይል ያለው መስሎት ካሰበ ተሳስቷል። እና ይህንን መልዕክት እንድታደርስልኝ ነው እንዴ፣ ወደ እኔ የላከህ?»

«አይደለም፣ክቡር ሆይ»

«እኔም፣ አንተንም ሰዚህ ብለህ መጥተሃል ብዬ አሳስብም። ይሁን እንጂ፣ እዚህ ከደረስክበት ጊዜ ጀምሮ የሱልጣኑ ዜጋ እስከሆንክ ድረስ አክብሮትህን ልትገልፅላቸው ወይም ለኔ ልትገልፅልኝ እንደሚገባህ አሳሰብክበትም»

«ክቡር ሆይ፣ ሙሉ በሙሉ አቅጄ ነበር። ነገር ግን ጊዜ . . . »

«አትቅጠፍ፣ እውነቱ የሚታወቅ ነው። ንጉሡ ከፈረንሣውያን ጋር ወዳጅነት እንድትመሠርትና ይህም የሕብረት ወዳጅነት በርግጥም በኛ ላይ እንዲሆን ታስቦ ነው የላከህ። ይህ ደግሞ እንግዳ ተቀባይነታችንን ባለማቋረጥ የሚሣደቡት የነዚያ የካቶሊክ ቀሣውስት ክፉ የእጅ ሥራ እንደሆነ እገምታለሁ»

ጥቁር ቀሚስና ነጭ ጥምጣም በመልበሣቸው ተሰይተው የሚታወቁት መፍቲዎች፣ በስብሰባው አዳራሽ አንድ ጠርዝ ላይ እጅብ ብለው ተቀምጠዋል። ፓሻው ከተናገረ በኋላ የማዳነቅና የመስማማት ዓይነት መንሸካሸክ ጀመሩ። በፓሻው ፅናትም ተደሰቱ።

«ክቡር ሆይ፣ ንጉሡ የላኩኝ የተወሰኑ ነገሮችን እንደ ጠላ ነው»

«ምን?» አለ መሃመት ቤይ፣ ነጐድጓድ በሆነ ድመፅ። «ተጨማሪ ውሸት! ብትጠነቀቅ ይሻልሃል። ከዚህ አታላይ ባህርይህ ሊያድንህ የሚችለውን ግርፋት አልሰጥህም። አንተንና አንተን በመሰሉት ላይ ከረዥም ጊዜ በፊት ማከናወን ይገባኝ የነበረውን ነው የምፈፅመው»

ሙራድ እንደመጀመሪያው ጊዜ አንጥቱን ደፋ።

«ክቡር ሆይ፣ ርህራሄዎን ያሣዩ?»

«የማውቀውን ሁሉ ለእንዲና ለመጨረሻ ጊዜ ልግለፅላችሁ። በግልፅና በተደጋጋሚ ወደ ንጉሥ ሉዊስ 14ኛ የተላከህ የንጉሡ መልዕክተኛ መሆንህን ራስህ ተናግረሃል። በወታደሮች ፍተሻ ከሽንጣህ ውስጥ የተገኘው ደብዳቤ የሚገልፀው የአቢሲኒያውያን ንጉሥ በአንድ ተልዕኮ ላይ የሾመህ መሆኑን ነው። ያ ተልዕኮ ምንድን ነው?»

«የአቢሲኒያዊ ንጉስ ወደ ፈረንሣይ እንድሄድ መፈለጋቸው እውነት ነው»

«ኛ በአውሮፓ ላይ ጦርነት ስናነሣ ከጀርባችን ልትወጉን። ከዚያ መንግስት ጋር ሽፍጠኛ ስምምነት ላይ ለመድረስ እንደሆነ አያጠራጥርም »

«አይደለም፣ ክቡር ሆይ» አለ ሙራድ ቀና ብሎ በመታነቅ አይነት ድምፅ

«እንግዲያው ለምን?»

«በአጭሩ ግርማዊ የፈረንሣይ ንጉስ፣ ነፍላቸውን ስለታደጉት ለማመስገን ነው»

«ነፍሱን ስለታደጋት?»

«እምን፣ ክቡር ሆይ፤ ጉዳዩ ቀላል ነው። ንጉሡ እጅግ ክፉኛ ይታመማሉ። በአገራቸውም ውስጥ አንዳችም መፍትሔ ያጣሉ። ስለዚህም ከፈረንሣይ ዕርዳታ ይጠይቃሉ። የፈረንሣይ ቆንሲል፣ የንጉሣዊውን የቤተመንግስት ቆንሲል፣ ስለሁኔታው ካስረዳው በኋላ፣ ለንጉሡ አንድ ፈረንሣዊ ሃኪም ላክላቸውና ይኸው ሃኪም አዳናቸው። ከምሥጋናው ጋር እማረ መንገዴንም ለንጉሥ ሉዊስ ጥቂት ገፀበረከቶችን በማቅረብ ውለታቸውን እንድገልፅላቸው ነው።»

«ይህ ፈረንሣዊ ሃኪም የት ነው ያለው? ለመሆኑ አቢሲኒያ ሄዶ በዚያው ቀርቷል?»

«አይደለም፤ ክቡር ሆይ፣ ከኔው ጋር ወደዚሁ ተመልሷል። በዚህ በአሁኑ ሰዓት እዚሁ ካይሮ ውስጥ ነው»

መሃመት ቤይ ስለዚህ ጉዳይ የሚያውቀው አንዳችም ነገር የለውም። ይሁን እንጂ ስለዚህ ሐኪም፣ ክርሱ በፊት የነበረው ባለስልጣን አቻቢዎች ሲያወሩ ሰምቷል። ከአካላዊ ጤንነት ጉዳይ ጋር በተዛመዱ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ እምነት ስላላቸው፣ ከዚህ መረጃ በኋላ፣ ፓሻው በእስልምና ዶክተሮች ላይ ላለው ጭፍን እምነት ወሰን አበጀለት። በሮር ሜዳዎችም ቢሆን፣ ክርስቲያኖች በሙሮች ላይ መድሃኒትን በተመለከተ የበላይነት እንዳላቸው ብዙ ጊዜ አስተውሏል። ከዚህም በላይ የመድሃኒትን ጥበብ የሚያከናውኑት ብዙዎቹ ሙሉ በሙሉ ሃይማኖተ ቢሶች ናቸው። እነዚህን ሰዎች ደግሞ ሙያቸውን በስኬት ከማከናወን የሚያግዳቸው ነገር እንደሌለም ያውቃል። በዚህም የተነሣ፣ የተነሣው ርዕሰ ጉዳይ ሃይማኖታዊ ስላልሆነ በዚህ ረገድ ያለውን አቋሙን ማለዘብ እንደሚሻለው ወሰነ። ባለፉት ዓመቶች ጉልበቶቹንና የመገጣጠሚያ አካላቱን እያዛበጠ በሚያሳምመው በሽታ፣ ጠንክር ባለ ሁኔታ ይሰቃይ ስለነበረ፣ በተጠቀሰው ፈረንሣዊ ሃኪም ላይ ይበልጥ ስሜቱ ጠነከረ። አርመናዊው በተጥታ የንጉሡን ሕመምና ፖንሴ የተጠቀማቸውን ዘዴዎች ለመግለፅ ፈቃደኛ ባይሆንም፣ ፓሻው ብዙ ጥያቄዎችን ጠየቀው። ከሙራድ ጋር ከረር ባለ ሁኔታ ለመቀጠል ፈልጉ የነበረው ፓሻ፣ ሙራድ ስለጉዞው በሰጠው ምክንያት ስሜቱ በረድ ያለ መሰለ። በመጨረሻም አሰናበተው።

«የመንግስት መልዕክተኛ፣ እዚህ ያለኸው እኔ ወድጀ በሰጠሁት ፈቃድ እንዳልሆነ እንዳትዘነጋ። በማንኛውም ሰዓት ግን፣ እዚህ ቀርበህ ትዕዛዜን ልሰጥህ ስለምችል ትመጣለህ። የያዝከው መልዕክት የተሰየ መብት አያሰጥህም። ለብልግናህም ማስረጃ ሊሆንህ አይችልም።

አሁን በቀጥታ ወደ ፈረንሣዮች ዘንድ ሂድ። ነገር ግን፣ ከነርሱ ካህናት ጋር እያሴርክ መሆንህን እንዳውቅ አታድርገኝ። ሰምተኸኛል?»

«ክቡር ሆይ» አለ ሙራድ ከመጨረሻው እምብርክክ በኋላ። «ሁሉንም ነገር አረዳለሁ። ከኔ የበለጠ ታማኝ አገልጋይ ፈፅሞ ሊኖርዎ አይችልም»

«እንዲሆን እግዚአብሔርን እለምነዋለሁ» አለ ፓሻው

አርመናዊው ሰላምታ አቅርቦ፣ ከአዳራሹ ሲወጣ ጉንበስ ብሎ፣ ወደ ኋላው ተራመደ። ወዲያውኑ ግን ቆመና

«ክቡር ሆይ! ደብዳቤዎስ!»

«አንተም ዲፕሎማት ነኝ ብለህ ማሰመሰል በመቻልህና ንጉሡም ለፈረንሣይ ወዳጅነት ይዘህ እንድትቀርብ ስለሾመህ ደብዳቤህን ፈረንሣይ ቆንሲል ውስጥ ታገኘዋለህ»

ይህ የተሰጠው መልስ፣ ወደፊት ሁኔታዎችን እንደሚያውሳስብ ታየው። ነገር ግን ስንብቱ በጣም ስላስደሰተው፣ ሞንቅላቱን ትከሻው ላይ ዘለስ እንዳደረገ፣ በቅሎውንም ረስቶ የሩጫ ያህል ወጥቶ ሄደ።

ሙሴ ዴ ማይሊም መልዕክተኛውን ለማየት የተዘጋጀ መሆኑን የሚገልፅ መልዕክት ላክ። የዚያኑ ዕለት ከሰዓት በኋላ፣ የንጉሠ ነገስቱ መልዕክተኛ ፈረንሣይ ቆንሲል ውስጥ ተገኘ።

ሙራድ፣ ከፓሻው ጋር የነበረውን ውይይት አጠናቅቆ ሲወጣ በጣም ደንግጦ ነበር። ካይሮ ሲደርስ ይሰማው የነበረው ደንታ ቢስነትም ጨርሶ ጠፍቶበታል። በአቋሙ ጸንቶ ሆኖ እንዲቆይ ፖንሴ የሰጠው ምክር ቢኖርም፣ አርመናዊው፣ ከፈረንሣውያኑ ጋር የነበረው በቀላሉ የመዛመድና የመቀላቀል ስሜቱን ፈፅሞ ተወው። ቆንሲሉን የሚያስደንቁት ነገሮች ማብቂያም የላቸውም። ሙራድ ወደ ቢሮው ሲገባ፣ ፓሻው ዘንድ እንዳደረገው በጉልበቱ ተንበረከከ። ሙሴ ማቹ እንዲቆም አደረገው። ቆንሲሉ ግን፣ አንዲት ባሏ የሞተባትን የመስፍን ሚስት፣ ነፋስ

በድንገት ቀሚሷን ቢገልብባት የሚያሣየውን ትህትና ዓይነት በማቅረብ ምንም እንዳላስተዋለ አስመሰለ።

«ውድ ጌታዬ» አለ ቆንሲሉ፣ ሁሉም ተደላድለው ከተቀመጡ በኋላ። «የቱርካውያኑ ፓሻ፣ አንተ እዚህ ከደረስክበት ጊዜ ጀምሮ ሲናፈስ በነበረው ወሬ በጣም ስለተደናገጠ፣ ስለማንነትህ እርግጠኛ መሆን እንዳለበት አሰበ። እንዲህ ካለ የወዳጅነት ጥሰት ባህርይ ጋር ግንኙነት እንደሌለኝ ስነግርህ አመነኝ። እኔ፣ ሁሉንም አይነት የሃይል ሁከት እጠላለሁ። ነገር ግን ቱርካውያን ለራሣቸው የተወሰኑ መብቶችን ስለሰጡ፣ በባዕድ አገር ያለው የኛ ኑሮ ዕጣ ፈንታው ይኸው ነው። የዚህ ሁሉ ሥራ አንዱ ፍፃሜ የሆነው ከቤትህ ተበርብሮ የተወሰደውን ደብዳቤ ፣ ፓሻው፣ በእኔ እጅ እንዲደርስ ማድረጉ ነው። እዚህ አገር ከገባህበት ጊዜ ጀምሮ እንድታሣየኝ በከንቱ ስታደክመኝ የነበረው ደብዳቤ ይኸው አሁን በኔ ቁጥጥር ሥር ሆነ። በርግጥ እጅግ መጥፎ ይሆንብህ የነበረውን ሁኔታ ሁሉ ያስቀረልህ አንድ የዕድል ውጤት አለ። ይኸውም፣ አንተ ከጥርጣሬ ባሻገር፣ የንጉሡን እውቅና ያገኘህ መልዕክተኛቸው መሆንህንና ይህ ሠነድም እውነተኛውን የንጉሠ ነገስቱን ማህተም የያዘ መሆኑን ማወቅ ችያለሁ። ስለዚህም አክብሮቴን ልገልፅልህና የእቪሊኒያው ንጉሠ ነገስት መልዕክተኛ አድርጌ ስቀበልህ ክብር የሰማኝ ል»

ሙራድ በአክብሮት ጭንቅላቱን ጎንበስ አደረገ። ወዲያውኑ ገልመጥ ብሎ፣ ከዚህ ከሚሰማው መልካም ዜና ጋር ተጉዳኝቶ ያልተጠበቀ ውርደት ይገጥመኝ ይሆናል በሚል ሁሪያውን ቃኘ።

«የሹመት ደብዳቤው» ሲል ሙሉ ዴ ማይሉ ቀጠለ። «በማያወላዳ ሁኔታ ሕጋዊነትን ሊያረጋግጥ፣ ንጉሡ የቬርሣይለስ ቤተመንግስትን እንድትጎበኝ መመኘታቸውን የሚጠቅስ ነገር የለውም። ፈቃደኛ ከሆንክ በሚከተሉት ላይ እንስማማ። በካይሮ ቆይታህ ወቅት ስቤተሰብህ ጭምር፣ እንደሚመስለኝ ሦስት ናቸው፣ ያውጣኸቸውን ወጭዎች እንተካልሃለን»

ሙራድ ጭንቅላቱን ነቀነቀ

«በፈለግኸው ጊዜ ልትጠቀምበት የምትችለው፣ ከቆንስላው ሂሣብ ላይ የሚከፈል አምስት አቡኪል በየወሩ እናስቀምጥልሃለን። ተልዕኮህ ግቡን መምታቱን እርግጠኛ በምትሆንበት ጊዜና ወደ አቪሊኒያ ስትመለስ፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ እናደርግልሃለን።»

«ነገር ግን» አለ ሙራድ እየፈራ፣ የፖንሴን ምክር አስታውሶ፣ «ከሹመት ደብዳቤዬ በተጨማሪ ለንጉስም የማደርሰውን የግል መልዕክትም ይዣለሁ»

«ነገርከህ እኮ» አለ ቆንሲሉ፣ የተዘጋጀለትን ሾርባ ለመመገብ ከማይችል ሕመምተኛ ጋር የሚያወራ ይመስል ረጋ ባለ አንደበት፣ «ደብዳቤው እኮ መልዕክቱን አንተው ማድረስ አለብህ አይልም።»

«ይህም ሆኖ . . . » አለ ሙራድ ድክም ብሎ

«ውድ ጌታዬ» አለ ቆንሲሉ መረር ባለ መልክ። «ጉዳዩ እኮ ሙሉ በሙሉ ቀላል ነው። በዚህ ላይ ምንም ውስብስብ ነገር ባንጨምርበት። ለንጉሡ መልዕክት አለህ። መልካም። እንግዲያው ለኔ አስረክበኝ። የተባረ ከሆነ እኔ አልከዋለሁ። ነገር ግን ፓሻው ባደረገው ፍተሻ፣ እኔ አስከማውቀው ድረስ እንዲህ ያለ ነገር አላገኘም። በቃል የተላከ ከሆነም፣ ይፋዊ በሆነ መልዕክት እኔው በታማኝነት አስተላልፈዋለሁ። ምናልባት መልዕክቱ ከስጦታ ጋር አብሮ መቅረብ ያለበት ከሆነም በራሣችን መርከብ እንልከውና ወደታቀደለት ቦታ በሰላም እንዲደርስ እናደርጋለን።»

«ነገር ግን ፣ ንጉሡ፣ ራሴ ሄጄ ለማድረስ ርግጠኛ እንድሆን ነግረውኛል»

«ስማ» አለው ቆንሲሉ «ፈጥነህ መልስ ለመስጠት አትጣደፍ። ዝግ ብለህ አስብበት። ከዚህ ከተማ ባህል ጋር ራስህን እስክታለማምድና እዚህ ያለህን ተልዕኮ እስክትረዳ ጊዜ እንደምትፈልግ ይገባኛል»

ከሁሉም ነገር በላይ፣ ሙራድ፣ በጊዜ ርዝመት ውስጥ የርሱ ሁኔታ የማያስተማምን መሆኑን እንደሚረዳና የተሻለው ምርጫ ምን ሊሆን እንደሚችል እንደሚገነዘብ፣ ሙሉ ዴ ማይሉ ያምናል። ከዚህ በኋላ፣ ከቆንሲሉ ጋር ለፊ ክርክር ተደረገ።

«መልዕክቱን አንተው በግንባር ባለማቅረብህ ንጉሡ እንደጥፋት አይቆጥሩብህም። እውነቱ ደግሞ ጉዳዩ ቀላል መሆኑ ነው። በመጀመሪያ፣ አንተ በአፊሴል ወደ አውሮፓ መሄድህን ይቃወማሉ። በመካከላችን ላለው መልካም ግንኙነት ምስጋና ይግባውና እዚህ ሊጋሊዮኑ ውስጥ መገኘትህን ይቀበላሉ። ነገር ግን ወደፈረንሣይ በመጓዝ በመርከብ ላይ እንድትሣፈር በምንም አይነት አይፈቅዱልህም። ሰመሆኑ ራሴን ግልፅ አድርጌአለሁ?»

ሙራድም ከዚህ የተለየ ነገር እንደማይኖር ስላወቀ ተስማማ። በሰማው ዜናም ሰራሱ እየተደነቀ አፎይታ አገኘ። በልቡ፣ ከነፋሱና ከምገዱ ጋር እየተላተመ፣ ንጉሥ ሉዊስ 14ኛን ለመጉብኘት ምኞቱም የሰውም። የንጉሡ ሥዕል ከላይ ወደ ታች በቆንሲሉ ላይ እንዲታይ በመደረጉ፣ ቆንሲሉን፣ ከፓሻው ይልቅ አስፈሪ አድርጐታል። ከሙሴ ዴ ማይሌ ጋር ያደረገውን ውይይት በደስታ አጠናቅቆ፣ በዘጠኝ ሰዓቷ ፀሐይ ኃይል እያላበው፣ አስደናቂውን ዜና ለፖንሴ ሪፖርት ለማድረግ ተመለሰ።

በአየር ጠባዩ ላይ በተፈጠረ ያልተለመደ ምክንያት፣ ግብፅ ውስጥ ያደጉ የዝሆኖች ላባ፣ ዋጋ ቢሶች ናቸው። አውሮፓ ውስጥ እንደሚገኙት የዝሆኖች ላባ፣ ወረቀት ላይ ሲያርፉ ጠንካራና ቀጥ ያሉ በመሆን ፈንታ ሲበዛ ደካማና እጥፍጥፍ የሚሉ፣ ቀለም ውስጥ ሲነከሩ የበለጠ የሚለሰልሱ ይሆናል። ስለዚህም ለሙሴ ማይሌ እነዚህ ላባዎች የተላኩለት ከፈረንሣይ ነው። የቆንስላው ተቀጣሪዎች መፃፍ የሚገደዱት በአገር ውስጥ ውጤቶች ሲሆን፤ ጥሩዎቹን ላባዎች ክስንት አንድ ጊዜ በራሱ የእጅ ጽሁፍ ለሚያዘጋጃቸው ደብዳቤዎች መግፊያ ያስቀምጣቸዋል። በዚያን ዕለት ምሽት፣ ለሙሴ ዴ ፖንቻርትሬይን፣ በራሱ እጅ ለመፃፍ ቆረጠ። በሰዓት ማሰሪያው ላይ ተደጋግሞ በመመላለስ የሚሰማው ህመም ቢሰማውም፣ ሥቃዩን ፈርቶ ሃሣቡን ለሚኒስትሩ በራሱ እጅ ከማስፈር አያግደውም። ረዥምና ጋደድ የሚለው የብዕር አጣጣሉ በፋናሱ ብርሃን ስር ያበራል።

ለንጉሡ መልዕክተኛ፣ ቱርኮች የርሱን ወደ ፈረንሣይ መጓዝ እንደሚቃወሙ አመልክቼዋለሁ። የምር ከተናገርኩ እውነቱ በትክክል ይህ አይደለም። በካይሮ የሚገኘው ፓሻ እኛ አስተያየት ስፋፍን እንደሀ ዓይነቱን ተልዕኮ ለመከለከል ሥልጣን የሰውም። ይሁንና የአቢሲኒያውያን ኤምባሲ፣ ለረዥም ጊዜ ባለን ጥሩ ግንኙነት ላይ መጥፎ ስሜት ማሣደሩና ከፍተኛውን ባለሥልጣን ማስከፋቱ እንደማይቀር እውነት ነው። ይህ አባባሌ በተዘዋዋሪ መንገድ እውነት ሲሆን፣ ቱርኮችም እንዲህ ዓይነቱን ጉዞ በርግጥ ሊያደናቅፉ አይችሉም። በዚህ ጉዳይ ላይ ጠበቅ አድርጌ ልገልፀው የምሻውና ይህንንም እንዳምን

የሚያደርገኝ ነጥብ አለ። ይኸውም የንስታትን ንጉሥ መክሱ እዚህ የሚገኘው ሰው ለዚህ ሃሣብ ተቃውሞ እንደማያስነሣ ነው።

የሃሣቤን ስመክንዮ ሠፋ አድርጌ እንዳብራ ይፍቀዱልኝ። አቢሲኒያውያን በመልክም ሁኔታ የጀመሩት ሃሣብ የኛን ፍላጐት ወደፊት ሊያራምደው የሚችል ምልክት ሆኖ ሊያድግ ካልቻለ ትልቅ ሃፍረት ይሆናል ብዬ አፈራለሁ። በዚህም ላቢያ፣ ሥራውን ከጀነዊቶች እጅ በመውሰድ፣ በኛ አይታ መሠረት እኛው እንድናከናውነው ሃሣብ አቀርባለሁ። ለመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ የጀነዊቶች ፍላጐት ምን ነበር? የአገሪቱን ሃይማኖት ለመለወጥ ነው? ይህን እንዳያደርጉት፣ በአባ ብሬዚደንት ያለጊዜአቸው መሞት ተሰናክሎባቸዋል። ይሁን እንጂ፣ ይህን ሁሉ ርቀት ከመንግስት መልዕክተኛው ከሙራድ ጋር ተጉዘው ከመጡት ሦስቱ አቢሲኒያውያን ጋር ወደ ፈረንሣይ መጓዝ ቢችሉ፣ ጉዛው የተሣካ ነበር ብለው ያስባሉ። እነዚህ ሰዎች፣ በጥሩ የአባቶች ትምህርት ቤት በሚገባ በትምህርት ታንፀው ወደ ሃገራቸው እንዲመለሱ ቢደረጉ የአገራቸውን ሕዝብ ከባዕድ ሰው ይልቅ ለማሳመን ትልቅ ዕድል ይኖራቸዋል። የአየሱሳውያንን ማህበረሰብ የሚያሳስባቸውም ይኸው ነው። በኔ አስተሣሰብ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ሙሉ በሙሉ መደሰት ይገባቸዋል። በስኬታቸው ተደፋፍረውና፣ አዲሶቹን አቢሲኒያውያን ተረጂዎቻቸውን በማዘጋጀት ሥራ ላይ ተመሰጠው፣ ይህም የወደፊቱን የመንግስት መልዕክተኛ ይጨምራል፣ የጀሰዊት አባቶች ቢያንስ ለጊዜውም ቢሆን እንኳ፣ ወደ ንጉሡ ኤምባሲ በመላክ ጉዳይ ላይ ክአንግዲህ በኋላ ፍላጐት አይኖራቸውም። በተቃራኒው፣ እኛ በነፃነት ለብቻችን ብንንቀሣቀስ እነርሱን ስማርካታችንም በላይ ሰፊ ጊዜ እንዲኖረን እናደርጋለን። በዚህ ላይ፣ ይህን ዕድል በመጠቀም በተቻለ ፍጥነት ከመንግስት መልዕክተኛው ከሙራድ ጋር ሊጓዝ የሚችል የራሣችንን ኤምባሲ ወደ ንጉሡ እንድንልክ ሃሣብ አቀርባለሁ። ከሙራድም ጋር ቢሆን፣ ራሣችንን በማራቅ በመጨረሻ ስሙን የራሣችን እናደርጋለን።

ለሽልማት የሚያበቃው የጉዛው መሪ መልዕክተኛችን፣ የፖንሴ ተግባር፣ ጉዛው የሚቻል እንደሆነ ከማሣየቱም በላይ አደናቸነቱም ማንም ከሚያስበው በታች መሆኑን ነው። እውነተኛ ኤምባሲ በመላክም፣ ዳግመኛ ድንገቴ በሆነ በመድሃኒት ቀማሚ ፍላጐትና አምሮት ላይ እምነት አንጥልም። ከዚህም ጋር አጠቃላዩ ተልዕኳችን አነስም በዛም፣ ፍላጐታቸው በጥልቁ ውስጣቸው ውስጥ በስልት ተሸፍኖ ካሉ ድብቅ ቀሣውስት ጋር

ይደራደራል ብለን አንፈራም። እንዲህ ያለው ኤምባሲም ቢኖውንተኛ ዲፕሎማ ከተመራ፣ ከኢትዮጵያ ንጉሥ ጋር በጠንካራ መሠረት ላይ የሚገነባ የፖለቲካ ግንኙነ ለመመሰረት ይችል ይሆናል። ከዚሁ ጋር በተንዳኛ በፈረንሣይ የምሥራቅ አንድ ኩባን ስም ከፍተኛ ተሰፋ ያለውን የንግድ ሽርክናም ያዳብራል። በዚህች አገር ውስጥ ወረ በብዛት እንዳለ እናውቃለን። የተፈጥሮ ሃብቷም ቢሆን ገና ያልተነካ ነው። አገሪ በአሁኑ ጊዜ ከፉክክር ሙሉ በሙሉ ነፃ ሆና ያለችና ወደ ሩቅ ምስራቅ ለመድረስ መነ መሆን የምትችል ናት።

ይህን የመሰለውን ተልዕኮ ማን ሊመራው ይችላል ብለው ይጠይቁ ይሆናል ምንም እንኳ ጠልቁ ባላውቀውም፣ በቅርቡ በላኩልኝ ደብዳቤ ላይ መምጣቱን የገለፀልን በኔ ሥር በሚገኘው፣ ዳሚየታ ውስጥ የምትል ቆንሲልነትን ሃላፊነት ማሟላ የሚችለውና ለዚህ አይነቱ ሥራ አስፈላጊው ብቃት ሁሉ ያለው፣ ምስጉኑ የንጉሠ ነገስ ባለሟል ፈረሰኛ፣ ሌ ናይር ዱ ሮውሌ ነው።

ሙሉ ሌ ናይር ዱ ሮውሌን ለመምረጥ ዕድሉን እንዳገኝ ላደረጉኝ ቤተሰቤ ያለኝ የፍቅር አክብሮት እገልፃለሁ። በዚህ ባቀረብኩት ሃሣብ የራሴን ፍላጐት ከንጉሠ በላ አድርጌ እንደማላስቀምጥ እንደማረጋግጥ ተሰፋ አለኝ። በድፍረት ተሰፋ የማደርገዉ ሁለቱም እንደሚገጣጠሙና ሙሉ ሌ ናይሬ ዱ ሮውሌም፣ ሳቀርብለት በምችለው ክብር ሃብት እንደሚያንፀባርቅ፣ከሁሉም በላይ ከሴት ልጀ ጋር ተጋብቶ ቤተሰቤን በማኩራ ተክክለኛው አቻ እንደሚሆን በማሰብ ነው።

7

ጆን ባፕቲስት፣ የሙራድን ዜና ከሰማ በኋላ፣ ጨዋታው ማብቃቱንና ከዚህ በኋላ የስኬት ነገር እንደማይቻል ተገነዘበ። በቆንሲሉና በፓሻው መካከል ተራ የሆነ የፍላጐት መገጣጠም ይሁን ወይም ቅን ስምምነት የፈጠረው ሀብረት፣ ከኤምባሲው ጋር እስከ ሽርሣይለስ የመጓዙን ዕድል አጠፋው። ሙራድ፣ መልዕክቱን ለቆንሲሉ ለመስጠት ቢስማማ፣ ዲፕሎማቱ ለንጉሡ ከማድረሱ በፊት ለራሱ ዓላማ በሚያመች መልክ ይቀይሰዋል። በዚህም የተነሣ እየናቀው እንዳለው፣ የፖንሴን ፍላጐት ለማሣካት የሚያስችለው ቅንጣት ታህል ዕድል አይኖረውም።

ያ ሁሉ ጥረት፣ ማብቂያ ያልነበራቸው የሚመስሉት የጉዞ ቀናት፣ መከራውና ችግሩ ሁሉ መና ቀረ። ሁለት መልክም ዜናዎች በተከታታይ ሣይደርሱት ቀደም ብሎ፣ ጆን ባፕቲስት በተሰፋ መቁረጥ ውስጥ የሚሰጥምበት ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። እነዚህ ሁለት መልካም ዜናዎች የወደፊቱን አተያዩን በምንም መልኩ ሳይለውጡ ተሰፋ ያለበትን ቅፅበታዊ ደስታ አላበሱት።

በቀዝቃዛው ጥላማ በረንዳ ላይ ከሚትር ዝረሚ ጋር በመሆን እየተወያዩና ርዕሰ ጉዳዩን በሁሉም አቅጣጫ ሲመለከቱት ወደ ቬርሣይለስ የሚደረገው ጉዞ በፍፀም ድርድር እንደተደረገበት እርግጠኛ በሆኑበት ጊዜ፣ አንድ ዘበኛ ከቆንስላው ጽህፈት ቤት ሙሴ ዴ ማይሌ የላከለትን ማስታወሻ ሊሰጠው መጣ። ቆንሲሉ፣ «ሙሴ ፖንሴ» በሚቀጥለው ቀን «በግርማዊ የአቢሲኒያ ንጉሥ ክቡር ተወካይ» እዚህ መድረስ ክብር ሲባል በሚደረገው የዕራት ግብዣ ላይ እንዲገኝ ይጋብዘዋል። ጆን ባፕቲስትን ያስደሰተው ግን በዝርዝሩ ውስጥ «ክቡር የፈረንሣይ ቆንሲል፣ ማዳም ዴ ማይሌ እና ሌት ልጃቸው» የሚለው ብቻ ነበር።

ከዚህ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ፍራንቾይዝ በቤትዋ መስኮት በኩል ብቅ አለችና ዘልላ በረንዳው ላይ በመውጣት፣ ከእራት ግብዣው በዓል በኋላ፣ አሊስን ለብቻዋ ሊያገኛትና ሊያያት ከፈለገ ሊከተለው የሚገባውን እያንዳንዱን ዝርዝር አትድ አብራራችለት። መልዕክቱን ካጠናቀቀች በኋላ በመድሃኒት ቀማሚው ቤት ውስጥ ሽርጉድ በማለት ምንም እንዳልጠፋባቸው

ስማየት በማለት እንደሆነ ተናገረች። የምታደርገውን ፍተሻ ሜትር ዝረሚ መድሃኒት የማቀላቀሉን ዝግጅት ለማድረግ ወደሄደበት እስክ ምድር ቤቱ ድረስ አዘሰቀችው። እርሱም በማጉረምረም ስለተቀበላት ምስኪኗ ሴት በመመለስ፣ በስሜት ውስጥ የነበረውን ፖንሴን በማለፍ ቀደም ሲል በገባችበት በኩል ሾልካ ተሰወረች።

በሚቀጥለው ዕለት ከዕራት በፊት ያሉት ሰዓቶች እንዲገባደዱለት በማለት፣ ፖንስ በቤቱ ውስጥ ተደብቆ ቆየ። ቀትር ላይ ግን ሙራድን ለማየት ሾልኮ ወጣ። በዚህ ዕለት ማታ፣ በቆንስላው ውስጥ የመንግስት መልዕክተኛው ሊያሣየው የሚገባውን ፀባይ በዝርዝር ገለፀለት። የሙራድ የመጀመሪያው የማህበራዊ አቀራረብ መልኩ፣ ወደ ፈረንሣይ ቤተመንግስት እዳይሄድ፣ ቆንሲሉ እንዲከለክለው ምክንያት ሊሆነው ይችላል የሚል ሥጋት ፖንሴ ነበረው። ከዚያ በኋላም ወደ ቤት ተመለሰና እዚያም ማንኛውንም ጉብኚ ሰላም እንኳ ላለማለት ከመቸውም ጊዜ ይልቅ ዝረሚን አኩርፎ አገኘው። በነጋዴዎች አካባቢ እያንዳንዱ ሰው የፖንሴን የጉዞ ታሪክ ከሌላው ቀድሞ ለማወቅ ጠንክር ያለ ጉጉት አድሮበት ነበር። መድሃኒት ቀማሚው እስክ አሁን ድረስ ታሪኩን ለማንም ሰው ስላልተናገረ፣ የተሰጠው ግምትም ዕለት ተዕለት እየጨመረ ነበር። አባ ፕላንቱይንም ሶስት ጊዜ ያክል መጥተው ነበር። ይሁን እንጂ ሜትር ዝረሚ በሩን እንዳያልፉ ስለተጋረጥባቸው፣ ጀስዊቱ፣ በኘሮቴስታንቱ ትከሻ ላይ አሻግረው በቤቱ ውስጥ ምን የተደበቀ ምስጢር እንዳለ ለማየት ወዲያና ወዲህ ተሣሣሩ። ሙራድም እንዲሁ ማንንም ስለማይቀበል አባ ፕላንቱይን ክፉኛ ቅሬታ ያሰማሉ። እርግቸው፣ የአባ ብሬቬደንትን የአሟሟት ታሪክ እንዲሁ ለመስማት ይፈልጋሉ። ሜትር ዝረሚ፣ እኒህን ጀስዊት ወደ መንገዱ ላይ ገፍትሮ ከመወርወር ራሱን ገትቶ፣ የምሬት ቅሬታቸውን በትዕግስት ቢያዳምጥም፣ ከቀመበት ሥፍራ ግን አንዲት ጋት እንኳ ፈቀቅ አላሰላቸውም።

በመጨረሻ የእራት ሰዓት ደረሰ። ጀን ባፕቲስትም በጥንቃቄ ልብሱን ለበሰ። ክባሀር ላይ ወንበዴዎች የገዛቸው ልብሶች፣ በሰላማዊ ጉዳዮች ላይ ክለስፈላጊው በላይ የሚያሸበርቁ ቢሆኑም፣ ለዛሬ ምሽት ሁኔታ ግን ፍፁም ተስማሚ ነበሩ። እፁብ ድንቅ መሆኑን ጓደኛው ሜትር ዝረሚ አረጋገጠ። ፖንሴ በበኩሉ በጓደኛው ዐይኖች ውስጥ የቅሬታ ሁኔታዎችን አነበበ። ይህ ቅሬታ ብዙም ጉጉት ባላሳደረበት ክዛሬው ምሽት በዓል ውጭ በመሆኑ ሳይሆን፣ ሁሉም ሥራ፣ አደጋውና የወራት ጉዞ ድላቸው፣ የማይቀበሉትና የጥፋት እውነቶች ሆነው፣

አረሱ የዋህ እምነቱን በታማኝነት ይዞ እንዳቆየው እንዲደበቁና በምስጢር ደረጃ ገዝቶ በማለታቸው ነው።

ወደ ቆንስላው እየተጓዘ ሣለ፣ መልካም ስሙን ለመጠበቅ፣ ክፍተኛው አስተዋፅኦ የሚትር ዝረሚ ስለሆነ፣ ውሰታውን ለመመለስ፣ ክፈረንሣይ ሆኖ በተሻለ ብቃት መስራት እንደሚችል ማሰላሰል ጀመረ። ይህም ወደ ቬርሣይለስ ኤምባሲውን መርቶ ለመሄድ አንድ ተጨማሪ ምክንያት ይሆነዋል። ሆኖም የዚህ ዓላማ የስኬት ዕድል ይበልጥ እየራቀ ነው።

እራት በታሳቅ ሥርዓት እንዲቀርብ ሙሴ ደ ማይሌ አዘዘ። የንጉሡን መልዕክተኛ እንኳን ደህና መጣህ ሊለውና ባጋጠመውም ተሰፋ አስቆራጭ ሁኔታ ላይ ሊከሠው ፈለገ። በዘኾቹ፣ በድል አድራጊ ወታደር ባህል ዓይነት በዋናው የመግቢያ ደረጃ ላይ አሸሚጣጭ ጉራዴአቸውን በግራና ቡጎኝ ከፍ አድርገው በማናኘት፣ ለሚመጣው እንግዳ ማለፊያ ቅስት ሠርተው በተጠንቀቅ ቆመዋል። በተትረፈረፈ መጠን የተዘጋጁ መብራቶች በባለጌጥ አቃፊዎች ላይ ተቀምጠው የአዳራሹን መግቢያና ታሳቁን የእንግዳ መቀበያ ክፍል ፍፁም አንዲያሸበርቁ አድርገዋል። ከዚህም በላይ በወርቃማ የስዕል ፍሬሞች፣ በተወለወለው የወለል ጣውላና ለላው ቀርቶ በአስናጋጆች ልብሶች ላይ ባሉት የነሃስ ቁልፎች ላይ ብሩህ አንፀባራቂ ብርሃን ፈንጥቀውባቸዋል። ይህ ከፍተኛ ብርሃን ፊቶቻቸውን በአብረቅራቂው ሃይሉ አጥለቅልቆትና ከመጠን በላይ አጋንኖባቸው ስለነበረ፣ ሴቶቹ በዚህ ሰው ሠራሽ ብርሃን በደስታ ተሞሉ። በፈረንሣውያን ማህበረሰብ መንደር ውስጥ የሚኖሩት ሴቶች፣ ምንም እንኳ በአብዛኛው ጦናቸው ክብር የሚገባቸው የነጋዴዎች ሚስቶች ቢሆኑም፣ አሁን ባለው ሕይወታቸው ውስጥ ረግተው ከመኖራቸው በፊት፣ እጅግ ምስቅልቅልነት የበዛበት ሕይወት ነበራቸው። የመጀመሪያውና በአጠቃላይ ለረዥም ጊዜ የነበረው ሕይወታቸው የንግድ ሱቅ ላይ ያተኮረና ወይም እንዲያውም በጉዞ መዝናኛዎች ላይ መሥራት ነበረ። ጀብደኛ የትዳር ጓደኞቻቸው በመጨረሻ ላይ ካይሮ ውስጥ ሃብት ሲያገኙ፣ እነዚህም ሴቶች ገደብ የለሹን ፍላጐታቸውን ለማርካት ስለቻሉ ወደመከበሩ ደረሱ። የአልማዝ ጌጦቻቸውን በሕገወጥ መንገድ ወደ አገር ውስጥ ከሚገቡ የአይሁድ ነጋዴዎች በመግዛት፣ የእጅ ዋጋዋን ሊከፍሏት ላልቻሏት የአሥራ ሁለት ዓመት ልምድ ላላት የአረብ ልብስ ሰፊ ሴት በመስጠት፣ በወቅቱ በፖሪስ ውስጥ ያለውን ፋሽን ኮፒ እንድታደርግላቸው ያደርጋሉ። እነዚህ አርቲፊሻል ጌጣጌጦችንና መዋቢያዎች፣ ቁመናቸውን ለማስዋብ የበቁት፣ ሥራና ወሲባዊ ፍላጐታቸው፣ የአበባ ጊዜያቸውን በእጅጉ

ከሸረሸሩት በኋላ ዘግይተው ነው። ቢሆንም ግን፣ እነዚህ የቅንጦት ባህርያት ናቸው። የማስፈለጋቸው ምክንያት ደግሞ የተገዙት ጌጣጌጦች ጥራት፣ ስለባለቤቱ ማንነቱን የሚገልፁ ናቸው። የሰውነቱ መገጣጠሚያዎች ያባበጡበትና፣ በከተማ ውስጥ በዘመነኛ ባለ አንድ ፊረስ ሠረገላው ሲዞር የሚውል ሰው፣ ለፈረሶቹ ደህንነት በእጅጉ ሲጠነቀቅ፣በምሽት ሰኣት ወጣትነትዋ የሸሻት ሴት አዲስ፣ ደማቅና የሰበሰችውን ለስላሣ ጨርቅ ያለሃፍረት በወንዶች እግር ላይ ስታሻሸው ሲመለከት ለአይን አስደሳች ትሆንበታለች።

በመጨረሻ ከደረሱት ሁለት ተጋባዦች አንዱ የሆነው ጆን ባፕቲስት፣ ለቆንሲሉ ያለውን አክብሮት ገለፀ። በዚያን ጊዜ ቆንሲሉ በአዳራሹ መግቢያ ላይ ለእንግዶቹ ሰላምታ በመስጠት ይቀበላቸው ነበር። በኋላም፣ ቆንሲሉ፣ ሣር በለበሱ፣ በሱልና በሚያንፀባርቁ የከበሩ ድንጋዮች ባጌጡ፣ ሴቶች መካከል በርሱ ዓይን ለሽልማት የምትብቃዋን ለማግኘት በሰዎች ውስጥ ሰጠመ። በዚህ ታላቅ በዓል ጊዜ የምድር ቤቱ ክፍሎች በሙሉ ተከፍተዋል። የእንግዳ መቀበያው ክፍል አሁንም የፀሃዩ ንጉሥ ሥዕል ሲታይበት፣ የቆንሲሉ ወንበር ግን ተነስቷል። ከበስተጀርባ የሚገኘው ሌላው በኢኮኖሚ ምክንያት በአዘቦቱ ጊዜ ተዘግቶ የሚኖር ክፍል ለዛሬው ምሽት የአራት ግብዣ ሲባል ጠረጴዛዎች ንብተውበታል። በዚህ ቦታ አሊስ አልነበረችም። በመጨረሻም፣ ጆን ባፕቲስት ባልጠበቀው ክፍል ውስጥ አገኛት። ክፍሉ፣ ሴቶች በምሽት ሲደክማቸው የሚያርፉበት የሙዚቃ ክፍል ነው። በጓሮ በኩል ወዳለው መስኮት አጠገብ፣ በቀላል ውበት የተጌጠ አረንጓዴ ፒያኖ ግድግዳውን ተደግፎ ቆሟል። አሊስ፣ በእግት ማንደጃው ምድጃ ላይ ከተቀመጠው ትልቅና ረዥም መስተዋት አጠገብ ቆማለች። ጆን ባፕቲስት ወደዚህ ክፍል በድንገት ሲገባና ከኋላ በኩል ሲያያት ደነገጠ። ክፍሏ ትንሽ ነች። ድንገት ፊት ለፊት መገጣጠማቸው ሁለቱንም በመጠኑ አደነጋገራቸው። ይሁንና በዙሪያቸው ያለው ትዕይንት ሲበዛ የተሟሟቀ፣ በሣቅና ሁካታ የተሞላ፣ ማጋነን የሚሰማበትና ጮክ ያለ የለላምታ ልውውጥ የነበረበት ስለነበረ፣ እንዲህ ያለውን ዝርዝር ሁኔታ ማንም ልብ ብሎ አይመለከተውም።

ምንም እንኳ በአለባበስዋና በደረበቻቸው ማላበሻዎቿ ክፍተኛ ጥንቃቄ ብታደርግም፣ ልብ ያለ ተመልካች ሊለያት ይችል ነበር። በአንዳሩ፣ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ማራኪነትዋን አልተጠቀመችበትም ነበር። አሁን ግን፣ እንዲህ ተነቃቅታ ስትታይ ማንዘባረቅ ጀምራለች። ውበቷ፣ ልክ አንድ የነፋስ ማራገቢያ ተዘርግቶ ሲታይ ወይም የጣምስ ወፍ የጭራ ላባዎችዋን ዘርግታ ወይም በራቢሮ ክንፎችዋን ዘርግታ ስትታይ ያለውን ማራኪ ውበት ይመስላል።

ትጠብቀው የነበረው ለስላሣ የነፋስ ሽውታ ሲደርስና ወደዚያው ክፍታ ስትወጣ፣ ቁንጅናዋ እንደ ጀልባ አንሣፍፎ ወሰደው። ጆን ባፕቲስት፣ ሣንባው ጉረሮው ላይ ተወትፎበት፣ ለአፍታ ያህል ፀጥ ብሎ ቆመ። ከዚያ በኋላ ሁለት ርምጃ ወደፊት ተንቀሣቀሰ። ወዲያውኑም ሁሉም ጥይት በርሱ ላይ ያነጣጠረበት መሆኑን እንደተገነዘበ ወታደር፣ በእምስት ወይም ስድስት ሴቶች ተከበበ። ሴቶቹ፣ ስለዚህ ወጣት የጀብዱ ሥራ ስምተው ስለነበረ፣ ወደ ቤታቸው ሊጋብዙት እንዲችሉ ባሉቻቸውን በየዕለቱ ይለምኗቸው ነበር። ብርማ ጉንጉን ያለበትን ቀይ ሰደሪያውን ለብሶ፣ አምሮና ተውቦ፣ ፀጉሩ በነፃነት ተዘናፍሱ፣ክራቫት ሣያስርና፣ከተፈጥሮአዊ ቁመናው ጋር ሲያዩት፣ የራሣቸውን ውስጣዊ ፍላጐት በርሱ ታሪክ ውስጥ እያደባለቁ ይሰውታል። አንዳንዴ በውስጣቸው የሚዳብረው ስሜት፣ በተንቆጠቆጠው ልብሣቸው ውስጥ አሁንም ሊቋቋሙት የማይችሉትን ምስጢራዊ የቁም ቅዥት ያጉላባቸዋል።

በድንገተኛው ጥቃት ውስጥ ሊሰምጥ ጥቂት ሲቀረው፣ ከዚያች አነስተኛ የመዚቃ ክፍል ውስጥ የአምባሣደሩ መምጣት ሲነገር ተጣድፎ ሊወጣ፣ በተፈጠረው አጠቃላይ እንቅስቃሴ ተረፈ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን የውሸት ጥንቃቄ ነበር። ቆንሲሉ፣ ሠረገላውን ለሙራድ ቢልክለትም፣ አርመናዊው አልተዘጋጀም ነበርና ምናልባት ቆንሲሉ ሠረገላውን ይፈልገው ይሆናል በሚል ግራ በተጋባ ስሜት ይመልሳል። በዚህም የተነሣ ሦስቱን ባሮቹን ከተጓዡ ጋር ቀድመው እንዲሄዱና እርሱ በአሞር ጊዜ ውስጥ በእግር ተጉዞ እንደሚደርስ እንዲናገሩ አዝዞ ይልካቸዋል። ሠረገላው እየተሸከረከረ በቆንሲላው ግቢ ደርሶ ሲቆም፣ ቆንሲሉ ራሱ በሩን ለመክፈት ተሽቀዳድሞ ነበር። ነገር ግን በአድምተኞቹ ኮስተር ያለ አይታ ተገርሞ ሊመለከት፣ ሠረገላው ሦስት በባዶ እግራቸው ያሉ፣ ሰውነታቸው በአራፊ የጥጥ ጨርቅ የተሸፈነና በፍርሃት አይኖቻቸው ቁልጭልጭ የሚሉባቸው የአገሬውን ተወላጆች አየ። ከአንድ አሥር ደቂቃዎች በኋላ፣ ሙራድ ቁና ቁና እየተነፈሰ፣ በሩ ዘንድ ደረሰ። መጀመሪያ ላይ፣ በጨለማው ውስጥ ሲለየው ባለመቻሉ ዘበኛው በአስነዋሪ ሁኔታ እንዳይገባ ከልክሎት ነበር።

በዚህ የእጋጣሚ መጥፎ መዘግየት የተነሣ፣ የአራት ግብዣውም ዘግይቶ በመጀመሩ የእንግዶቹን ደስታ አቀዘቀዘው። ብዙዎቹ ተጋባዦች እንዲህ ላለ ኦፊሴላዊ በአል በአክብሮት ተጋብዘው አያውቁም። በመጨረሻ ላይ እንግዶቹ በሁለት ረዣዥም ጠረጴዛዎች ዙሪያ መቀመጫዎቻቸውን ያዙ። አምባሳደር ሙራድ፣ በመጀመሪያው ጠረጴዛ አጠገብ ከቆንሲሉ አንዣር ተቀመጡ። ሁለተኛው ጠረጴዛ በበላይነት የሚመራው፣ በቅኝ ግዛት ተወካይ በሰር

ብራሱት ነበር። ስር ብራሱት፣ ሙራድን ለመቀበል ወጥቶ የነበረውንና ነገር ግን ሳያገኘው የተመለሰውን የመልዕክተኞች ጓድ መርቶ የነበረ ሲሆን፣ ሙሴ ዴ ማይሌ በአሁኑ አቀራረቡ ሊያባብለው የፈለገ ይመስላል። ክርሱ ትይዩ ያለው ቦታ በቆንስላው ውሰጥ ቀዳሚ አስተርጓሚ ስሆነው ሰፍሪሴቲ ተሰጠ። ፖንሴ፣ አሜዛኝ መሆናቸውን ወዲያውኑ በተገነዘበላቸው ሁለት ሴቶች መካከል በሁለተኛው ጠረጴዛ ዙሪያ ሲቀመጥ፣ በስተቀኙ በኩል በቅርብ የተቀመጠው ወንድ፣ ፀሐፊው ማቼ ነበር።

አሊስ የተቀመጠችበትን ቦታ ሰማየት ሲል፣ ጆን ባፕቲስት ክፍሱን ቃኘው። በመጀመሪያ ላይ ሊያያት ባለመቻሉ አንዳች የብስጭት ውጋት ተሰምቶት ነበር። እርስዋም ተገቢ ወዳልነበረ ቦታ ሄዳ ስለነበረ፣ በመጨረሻ ላይ ከፍሪሴቲ በስተቀኝ ተቀመጠች። ይህ ደግሞ በቀጥታ ከፍትቅረኛዋ ፊት ለፊት ካለው ቦታ ባሻገር አድርጓታል። ቀደም ሲል ከተገናኙ በኋላ እንዲህ በሕዝብ ፊት ሲቀራረቡ ይህ የመጀመሪያ ጊዜያቸው ነበር። በደማቁ ብርሃን ውስጥ ሁለቱም የቤቱ አባወራና እማወራ የሆኑ ያህል የቁም ቅዠት ተሰማቸው።

ጆን ባፕቲስት ስሜቱ ጠንካራ ስለሆነ፣ ይህንኑ ሰዎች ከፊቱ ላይ እንዳያነብቡበት በመስጋት ወደ አሊስ አቅጣጫ አብዝቶ መመልከቱን ተወ። እንግዶቹ በሙሉ በየመቅመጫቸው ላይ ከሆኑ በኋላ አጠቃላይ ጫጫታው ስከነ። ስርዓት ባለው ሁኔታ እራት አንድ ጊዜ በአንድ በኩል፣ በሌላ ጊዜ በሌላ በኩል ሲቀርብ ጨዋታው ደራ።

«ውድ ሙሴ ፖንሴ፣ እንግዲህ አሁን ወደ አቢሲኒያ ያደረግሽውን ጀብዱአዊ ጉዞ በርግጥ ትነግረናለህ?»

ጥያቄው የቀረበው ከሙሴ ማቼ ቢሆንም፣ በጠረጴዛው ዙሪያ ያሉትን ሰዎች ፍላጐትም የሚያንፀባርቅ ነበር።

«እንዲህ ከሆነ ጥያቄዎችን ልትጠይቀኝ ይገባሃል።» አለው ጆን ባፕቲስት። «አቢሲኒያ የምትገኘው በእጅግ ርቀት ቦታ ላይ ነው። በእያንዳንዱ ዕለት ያጋጠመኝ ሁኔታ ደግሞ በራሱ መጠን አንድ የመፅሃፍ ምዕራፍ የሚወጣው ነው»

«ከገዛው ከራሱ ጀምር። አዚያ አገር ለመድረስ በርግጥ አደገኛ ነበር?» አለ ማቼ

የፀሐፊው ጥያቄ በአቀራረቡ ሁሉ ከእውነት የመነጨ ፈጣን አቀራረብ ቢሆንም፣ እውነቱ ግን እንደሁልጊዜውም ትዕዛዝ የሚከተል ነው። ቆንሲሉ፣ ከዚህ በኋላ አንድ ኦፊሴል ኤምባሲ ለመሳክ ወስኖ በትጋት እያቀደ ባለበት ጊዜ ሊያጋጥም የሚችለውን አደጋም ለማወቅ ይፈልጋል። በዚህ ረገድ መረጃ ለመስጠት፣ የሙራድ እርዳታ አነስተኛ ነው። ስለዚህ የተሻለው ዘዴ ፖንሴ የራሱን የጉዞ ታሪክ እንዲናገር ማድረግ ነው። በዚህ ላይ ቆንሲሉ ራሱ በቀጥታ ሊጠይቀው ፈቃደኛ አይደለም፣ ወይም ደግሞ መድሃኒት ቀማሚው በርሱ ላይ ዝንባሌ እንዳለው ተረድቶ ክብር እንዲሰማው አልፈለገም።

የእራት ግብዣው ሲታቀድ፣ ሙሴ ዴ ማይሌ ፣ ፖንሴን የማጋነንና የማሞካሸት ሃሣብ ነበረው። ስለዚህ የተለየ አትኩሮት እንዳለደረገበት በማስመሰል፣ በሕዝብ ፊት እንዲናዘዝ ሃደቱን ጀመረው። በተቻለ መጠን፣ ፖንሴ ብዙ እንዲናገር እንዲያደርገው፣ ሙሴ ማቼ መመሪያ ተቀብሏል። የትረካውን አቅጣጫም ብልህነት በተሞላው ጥያቄ በመምራት፣ ፖንሴ የሚላትንም ሁሏንም ነገር በአስገራሚዋ የማስታወስ ችሎታው ውስጥ ይከትባታል። የአሊስ አይኖች በርሱ ላይ ማተኮራቸው ሲሰማው ጆን ባፕቲስት ሽሽት ጀመረ። በጠረጴዛው ዙሪያ ሰተቀመጡት ቂላቂል ከበርቴዎች፣ የገለባ ያህል አልተጨነቀላቸውም። ይልቁንስ የጉዞውን ውኔ የተሞላበት መግለጫ፣ አደጋ፣ መከራና ያጋጠመውንም ደስታ የሚተርከው ለሚያፈቅራት ሴት ብቻ ሲል እንደሚሰጥና እርሷም እነዚህን ሁሉ እውነታዎች ከሰማች በኋላ ስሜቱን የምትጋራው ይሆናል በሚል ተናገረ።

የተንገቡን ትረካ ወደ ተግባራዊ ጉዳዮች በማስተላለፍ ረገድ፣ ማቼ ትልቅ ችግር ነበረበት። ፖንሴም፣ ባለማቋረጥ ከርዕሱ ወጣ እያለ ዝርዝር ውስጥ ስለሚገባ፣ ይህ ደግሞ ወሃፊውን ከመጠን ባለፈ ስሜቱን ይይዘዋል። ለምሣሌ ፖንሴ ማሰቂያ ወደሌለው የአቢሲኒያውያን የቡና ሥነስርዐት ይሸጋገራል። ማቼ፣ ወደ ሲናር ንጉስ ወይም እስከ ጣና ሐይቅ ድረስ ስላለው ጉዞ ሰማወቅ ተራኪውን ወደ ኋላ ሊመልሰው ሲሞክር፣ ወይዛዝርቱ ግን ግልፅ የሆነ ስሜታቸውን በነዚህ ጉዳዮች ላይ በማሣየት፣ የሙሴ ማቼን ጥረት ያከሽፉበታል። ከዚህ በኋላ፣ ተስፋ በመቁረጥ፣ ፖንሴ ምንም አርባና የሌላቸውን ጥያቄዎች መመለስ እንዲችል ተወው።

ከአራት በኋላ፣ ጣፋጭ ምግብ ሊቀርብ ሲል፣ በመጠጥ ምቅ ያሳት የአንድ ነጋዴ ሚስት የሆነች ባለትልቅ ዳሌ ሴት ውይይቱን ለመካፈል ተደፋፈረች። በዚህም የተነሣ ለአሣ ሻጭነት ስትለማመድ የኖረች መሆንዋን በሚያጋልጥ ድምፅ፣ ጆን ባፕቲስትን አነጋገረችው።

«ጌታው፣ ሰዎች አቢሲኒያውያን ሴቶች ሲበዛ ቆንጆዎች ናቸው ይላሉ። ለመሆኑ አንዲት ሴት ይዘህ አልተመለስክም?»

ሁሉም ሰው ፖንሴን ተመለከተው

«ሴት?» አለ አይኖቹን ሰበር አድርጉ።

አጠቃላይ የሆነ የአፍታ ዝምታ ነገሠ። ጆን ባፕቲስት አይኖቹን ቀና አድርጉ ለአጭር ጊዜ ወደ አሊስ ተመለከተ። በዚህ እይታም ውስጥ የፍቅራቸው ሃይል ሁሉ በመካከላቸው ተሳለፈ።

«አውነቱ፣ እመቤቴ» አለ ጥያቄውን ወዳቀረበችው ሴት አንዳችም ትኩረት ሣያደርግ «ጉዛውን የተቀበልኩትም አንዲት ሴት ለማግኘት ስል ነበረ። እናም እንዳገኘኋት አምናለሁ።»

ከአንደበቱ የወጡት ቃላት፣ ኩስተር ብለው በመነገራቸው፣ ረዘም ላሉ ሴከንዶች የቆየ ግራ የሚያጋባ ዝምታ ተከተለ።

«አያጃጃለን ነው!» አለ የወንድ ሰው ድምፅ በመጨረሻ ላይ። ውጥረቱ ፈጥኖ በመላላቱ ብዙ ሰዎች ሳቁ።

«አየቀለድክ ነው፣ አይደል?» አለው፣ ከአጠገቡ የተቀመጠው ሰው ወደርሱ ዘንበል ብሎ።

«የተጋነነ ነገር የለበትም»

ለአፍታ ያህል ሁሉም በመደነቅ «እምም» የሚል ድምፅ ካሰማ በኋላ፣ ጭውውቱ እንደቀድሞው ተሟሟቀ። ሙሴ ማቼ፣ የማዳሞዜል ዴ ማይሌን ውበት ሣያደንቅ በቀጥታ እንዳይመለከታት ራሱን ቢቆጣጠርም፣ እርሷ ከጆን ባፕቲስት ጋር የተለዋወጠቻቸውን የጨረፍታ እይታዎች በማስተዋል ትክክለኛ ትርጓሜውን ተረድቷል። ከዚህ በኋላ፣ ሁለቱንም

በሚገባ በመከታተል እያስተዋላቸውና ለበኋለኛ ጊዜው እንዲጠቅመው፣ ማስታወሻውን በአዕምሮው ውስጥ መመዝገብ ቀጠለ።

አራት አበቃ። ተጋባዦቹም፣ በእንግዳ መቀበያው ክፍል ውስጥ በሚገኘው በንጉስ ሉዊስ አሥራ አራተኛ ሥዕል ስር ሆነው ቡና ለመጠጣት ከየተቀመጡበት ተነሱ። ፖንሴ በነበረበት ጠረጴዛ ዙሪያ የተመገቡት ሁሉ በጣም ተደስተውና በትረካው ተደንቀው ነበር። በመጀመሪያው፣ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው የተመገቡት ደግሞ ፊታቸው የከፋውና ያኮረፈ ነበር። በግልፅ ስሜት፣ የአቢሲኒያውን ንጉሠ ነገስት ባለሙሉ ሥልጣን አምባሣደርን አሣፋሪ ባህሪ በሃሜት ሲበጭቀት ነበር። የአምባሣደሩ አበላል በእጆቹ በመሆኑ፣ እንግዳና ያልተለመደ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ በአጠገቡ ያሉ ሰዎች ከአንድ ምግብ አብሣይ ጋር አራት እየተጋሩ እንደሆነ አስኪመስላቸው ድረስ፣ በእንዲት የዶሮ ብልት ላይ፣ ይህን ለማዘጋጀት ስለተጠቀሙት ዘዴ፣ ወጡ ውስጥ ስለተጨመረው የቅቤ መጠን ጥያቄዎችን ያቀርብ ነበር። በወይን ጠጅ ሞቅታ ሣቢያ አጠገቡ በተቀመጠች ሴት ቀሚስ ላይ ጣቶቹን ለመጥረግ ደርሶ ነበር። የባህሪው መጥፎነት ያለጥርጥር የታየው አንድ ብርጭቆ ጣፋጭ መጠጥ ከተጎነጨ በኋላ፣ ከጐኑ በተቀመጠችውና በፈረንሣይ ማህበረሰብ ውስጥ ሃብታሙ ባለባንክ የሆነውን ሰው ሚስት አንገቷ ሥር ሊስማት ማስመሰሉ ነበር። በፈረንሳይ ማህበረሰቡ ውስጥ የመጨረሻው ወሳኝ ዳኛ የሆነውና እያንዳንዱ አባልም ባህርይውን ሰርሰ በሚስማማ መልክ እንዲያርቅ የሚያደርገው ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ጉረሮውን የታነቀ በማስመሰል የሰዎችን ስሜት ለመቀየር ባይችል ኖሮ፣ ሁኔታው መጥፎ መልክ ይይዝ ነበር።

በክፍሉ ውስጥ እንዲህ የመሰሉ ታሪኮች ሲከናወኑና በአንዱ ጠረጴዛ ዙሪያ የሚረብሹ ትዕይንቶች በመኖራቸው እንግዶቹ ቅፌታዎቻቸውን ሲሰዋወጡና በሌላው ጠረጴዛ አካባቢ በሚነገረው ትረካ ሲበሳጉ፣ አለስ ክፉ የራስ ምታት እንደጀመራት ለመንገር ወደ እናቷ ሄደች። አስቀድሞ አምቢ ብላ የነበረ ቢሆንም፣ ይህን የአራት ግብዣ ለማዘጋጀት ልጅዋ ያደረገችውን ጥረት ማዳም ዴ ማይሌ ታውቃለች። ግንባሯ ላይ ከሣመቻት በኋላ፣ መልካም ሊሊት ብላ አሰናበተቻት። ጆን ባፕቲስት ግን ወጥቶ ለመሄድ እጅግ ተቸገረ። ሃያ ሌቶች ባለማቋረጥ ጨቀጨቁት። የምርጫው ሁኔታ ደከም ያለ ቢሆንም፣ ለአራት ግብዣቸው እንደሚመጣ ለአሥራ ዘጠኙ ቃል በመግባቱ እጅግ አስደሰታቸው። ሃያኛዋ ግን ምንም አለመጠየቅ ብልሀነት እንደሆነ ብትገምትም፣ ወዲያውኑ፣ በሌሎች ላይ ቅናት አደረባት።

ጆን ባፕቲስት ለቆንሲሉ ምስጋናውንና አክብሮቱን ለመግለፅ ቀረበ። ቆንሲሉም፣ ለአንደበተ ርቱዕነቱና ስለደስተኛ ስሜቱ እንኳን ደስ ያለህ አለው። በጠረጴዛው ዙሪያ የሚገኙ ተጋባዦችም ተጨማሪ ምስጋናቸውን አከሉ። ከዚህ በማስከተል ይህ አቢሲኒያዊ መልዕክተኛ፣ ቀደም ብሎ የመውጣት ልማድ ስላለው፣ እጅቦት ወደ ቤቱ ሊሄድ ይችል እንደሆነ መድሃኒት ቀማሚው ጠየቀ። ቆንሲሉ፣ ከዚህ ባለማቋረጥ ከሚያሣፍር ሰው ለመላቀቅ ሲል ሣጣቡን ወዲያውኑ ተቀበለ። ሠረገላውን እንዲጠቀሙበት ቢፈቅድም፣ አላስገደዳቸውም። በእንግዳ መቀበያው ክፍል፣ ሰው በለቀቀው አንድ ጥግ በኩል፣ አርመናዊው ባለመደገፊያ ወንበር ላይ እጥፍጥፍ ብሏል። የሰበሰው ሻኬት በጥብስ ቅባት ተበክሏል። ምግብ በጣቶቹ ስለሚያነሣ እጆቹ በቅባት ወርዝተዋል። በዚህ ሁሉ የተነሣ አዲሱና ሃር መሣይ ለማያዊ የመደገፊያ ትራስ ሊነገር ከሚችለው በላይ ተበላሽቷል። ፖንሴ፣ በአግር መንዙ የተሻለ እንደሚሆን ገልፆ፣ አምባሣደሩን ጉትቶ ሊያነሣው፣ ሰውዬው በሁሉም አቅጣጫ እየተጥመለመለበት ያልተያያዘ ማንመትመት አሰማ። በማዕድ ቤት ውስጥ አራታቸውን የበሉትን ሦስቱን አቢሲኒያውያን በመግቢያው በር ደረጃ ላይ አገኟቸው።

«ሰተከበሩ አምባሣደር ባትሪ አምጠሳቸው» ሲል፣ ሙሴ ዲ ማይሉ አዘዘ።

«በዚህ ትዕይንት ውስጥ ከሚያስፈልገው በላይ መብራት አለማብራት የተሻለ ይሆናል» ሲል፣ ጆን ባፕቲስት ሣጣቡ አቀረበ።

ቆንሲሉም፣ የዚህን አስተያየት ትክክለኛነት በመገንዘብ ብሸሽት ላይ እንደሚገኝ አንድ አስተኛ ጦሣ በጭለማ እንዲሄዱ ፈቀደላቸው።

መንገድ ውስጥ ከገቡ በኋላ ለአንድ ሁለት መቶ ሜትሮች ያህል አብረው ተጓዙ። ከዚያ በኋላ ፖንሴ፣ የሙራድን ክንድ፣ ጠንካራ ለሆነውና አረቢኛ ለሚናገረው አቢሲኒያዊ ካስያዘው በኋላ ወደ ቬኒስያውያን ቤት ይዞት እንዲሄድ አዘዘው። ጆን ባፕቲስት በፀኩሉ ወደ ግራ ታጥፎ በሰፈው የቆንስላው መሬት ዙሪያ ተጉዞ፣ በሁሉም ጐናቸው መስኮት በሌላቸው ቤቶች መሃል በሚገኝ አነስተኛ መንገድ ውስጥ ገባ። ከነዚህ ቤቶች አንዱ የሌጋሲዮኑን የማዕድ ቤት ግቢ የሚለይና ለቁሣቁስ አቅራቢዎች መግቢያ በር ያለው ነው። በዚያ ቦታ ፍራንቾይዝ ስትጠብቀው አገኛት።

8

ፖንሴ፣ አምክ አምክ በሚሸትት ቀጭን የንሮ ደረጃ፣ ፍራንቾይዝን ተከትሏት ወጣ። ከዚያ በኋላ ብቻውን ወደ አንድ ጨለማ የመልበሻ ክፍል አመራ። ቀጥሎም መስኮቱ የሌሊቱን ከዋክብት በብዛት እንዲያሣይ ተብሎ በስፋት ወደተከፈተ የመኝታ ክፍል ገባ። ቀለል ያለ የሰሜን ነፋስ ከከተማው ዝቅ ብሎ ከሚገኘው የደለል ሥፍራ የአፈር ሽታ ተሸክሞ ያመጣል። ከምድር ቤቱ በኩል፣ ግራ የተጋቡት የአራት ግብዣው እንግዶች ውካታና ጫጫታ ይሰማል። ብዙዎቹ እስከዚህ ሰዓት ድረስ በሣቅ እያውካኩ ቆይተዋል። ጭል፣ ጭል የሚለው ሻማ፣ ከመቅረዙ ላይ ሆኖ፣ ቢጫ ብርሃኑን ፍቅረኛዋን በምትጠብቀው አሊስ ላይ ይረጫል። ጆን ባፕቲስት፣ በዝግታ ወደርስዋ ተራመደ፣ በእቅፎቹ ውስጥ አስገባት። ልብሶችዋን አልቀየረቻቸውም ነበርና፣ ጆን ባፕቲስት ያንን እንግዳ ፀጉር፣ ጌጣጌጥና ቡተሊይም ያንን በቅርቡ በአዕምሮው ውስጥ አትሞ ያቆየውን ውበት፣ ቀለሙንና የውበቱን ውህደት አጣምሮ የያዘውን አንፀባራቂ መልክ፣ በታላቁ የእንግዳ መቀበያ አዳራሽ ግዙፍ የመብራት ብርሃን ስር ተመለከተ። በአጭሩ፣ ሁለቱ ፍቅረኛሞች አንዳቸው ለሌላኛው በሕይወት ቆይተው ፣ይጓጉለት ለነበረው ጊዜ መድረሳቸውን በደስታ ለመገንዘብ ችለው ነበር። እዚህ ደረጃ ለመድረስ ብዙ መሰናክሎች ተደንቅረውባቸው ስለነበረ፣ በአሁኑ ጊዜ ያገኙትን ደስታ ለአመል ያህል እንኳ የሚያደናቅፍባቸው ነገር ቢኖር የማይቀበሉት ነው። ሁለቱም በሰሜት ተውጠው በረዥም መሣሣም ውስጥ ቀለጡ። በጨለማ ውስጥ በቆየው የኦፔራ አዳራሽ፣ ትዕይንቱ ሊያልቅ ሲል፣ ውብ ጥንዶች በመድረክ ላይ ዳግመኛ ሲገናኙ የሚሰማውን የድጋፍ እልልታ ዓይነት ድምፅ ከምድር ቤቱ በኩል ይሰማል።

ከአጠገባቸው አንድ አልጋ አለ። ብቸኝነታቸው፣ ከማንኛውም ዓይነት ሁከት ነፃ ሆነው፣ ምስጢራቸውም ፍፁም የግላቸውና የተሟላ ነበር። ይሁን እንጂ በዚህ የፍቅር ደረጃ ላይ እርስ በርማቸው የመፈላለጋቸው ነገር፣ እጅ እንዲሰጡና እንዲሣሣቱ አድርጓቸዋል ብሎ ማመን እነርሱን አለመረዳት ነው። እስከዚህ ጊዜ ድረስ፣ አንድ ቀን ርስበርስ የመፋቀራቸውን የነፃነት ተስፋ በማጣፈጥ ያሣድጉታል። በዚህ የደስታ ተስፋቸው ላይ የተጋረጡትን ገደቦች ሁሉ ለማስወገድ ጊዜውን ይጠብቃሉ።

ጆን ባፕቲስት ሰቆንሲሉ ምስጋናውንና አክብሮቱን ለመግለፅ ቀረበ። ቆንሲሉም፣ ለአንደበተ ርቱዕነቱና ለለያስተኛ ስሜቱ እንኳን ደስ ያለህ አለው። በጠረጴዛው ዙሪያ የሚገኙ ተጋባዦችም ተጨማሪ ምስጋናቸውን አከሉ። ከዚህ በማስከተል ይህ አቢሲኒያዊ መልዕክተኛ፣ ቀደም ብሎ የመውጣት ልማድ ስላለው፣ እጅቦት ወደ ቤቱ ሊሄድ ይችል እንደሆነ መድሂኒት ቀማሚው ጠየቀ። ቆንሲሉ፣ ከዚህ ባለማቋረጥ ከሚያሣፍር ሰው ለመላቀቅ ሲል ሣጡን ወዲያውኑ ተቀበለ። ሠረገላውን እንዲጠቀሙበት ቢፈቅድም፣ አላስገደዳቸውም። በእንግዳ መቀበያው ክፍል፣ ሰው በሰቀቀው አንድ ጥግ በኩል፣ አርመናዊው ባለመደገፊያ ወንበር ላይ አጥፍጥፍ ብሏል። የሰበሰው ጃኬት በጥብስ ቅባት ተበክሏል። ምንብ በጣቶቹ ስለሚያነሣ እጆቹ በቅባት ወርዝተዋል። በዚህ ሁሉ የተነሣ አዲሱና ሃር መሣይ ሰማያዊ የመደገፊያ ትራስ ሊነካ ከሚችለው በላይ ተበላሽቷል። ፖንሴ፣ በእግር መንዘሁ የተሻለ እንደሚሆን ገልፆ፣ አምባሣደሩን ጉትቶ ሲያነሣው፣ ሰውዬው በሁሉም አቅጣጫ እየተጥመለመለበት ያልተያያዘ ማጉመትመት አሰማ። በማዕድ ቤት ውስጥ አራታቸውን የበሉትን ሦስቱን አቢሲኒያውያን በመግቢያው በር ደረጃ ላይ አገኟቸው።

«ለተከበሩ አምባሣደር ባትሪ አምጡላቸው» ሲል፣ ሙሴ ዱ ማይሴ አዘዘ።

«በዚህ ትዕይንት ውስጥ ከሚያስፈልገው በላይ መብራት አለማብራት የተሻለ ይሆናል» ሲል፣ ጆን ባፕቲስት ሣጣብ አቀረበ።

ቆንሲሉም፣ የዚህን አስተያየት ትክክለኛነት በመገንዘብ በሽሽት ላይ እንደሚገኝ አንድ አነስተኛ ኮሣ በጭለማ እንዲሄዱ ፈቀደላቸው።

መንገድ ውስጥ ከገቡ በኋላ ለአንድ ሁለት መቶ ሜትሮች ያህል አብረው ተጓዙ። ከዚያ በኋላ ፖንሴ፣ የመራድን ክንድ፣ ጠንካራ ለሆነውና አረቢኛ ለሚናገረው አቢሲኒያዊ ካስያዘው በኋላ ወደ ቬኒስያውያን ቤት ይዞት እንዲሄድ አዘዘው። ጆን ባፕቲስት በበኩሉ ወደ ግራ ታጥፎ በሰፈው የቆንስላው መሬት ዙሪያ ተጉዞ፣ በሁለቱም ጉኖቸው መስኮት በሌላቸው ቤቶች መሃል በሚገኝ አነስተኛ መንገድ ውስጥ ገባ። ከነዚህ ቤቶች አንዱ የሌጋሲዮኑን የማዕድ ቤት ግቢ የሚለይና ለቁሣቁስ አቅራቢዎች መግቢያ በር ያለው ነው። በዚያ በኩል ፍራንቾይዝ ስትጠብቀው አገኛት።

8

ፖንሴ፣ አምክ እምክ በሚሸትት ቀጭን የንሮ ደረጃ፣ ፍራንቾይዝን ተከትሏት ወጣ። ከዚያ በኋላ ብቻውን ወደ አንድ ጨለማ የመልበሻ ክፍል አመራ። ቀጥሎም መስኮቱ የሌሊቱን ከዋክብት በብዛት እንዲያሣይ ተብሎ በስፋት ወደተከፈተ የመኝታ ክፍል ገባ። ቀለል ያለ የሰሜን ነፋስ ከከተማው ዝቅ ብሎ ከሚገኘው የደለል ሥፍራ የአፈር ሽታ ተሸክሞ ያመጣል። ከምድር ቤቱ በኩል፣ ግራ የተጋቡት የእራት ግብዣው እንግዶች ውካታና ጫጫታ ይሰማል። ብዙዎቹ እስከዚህ ሰዓት ድረስ በሣቅ እያውካኩ ቆይተዋል። ጭል፣ ጭል የሚለው ሻማ፣ ከመቅረዙ ላይ ሆኖ፣ ቢጫ ብርሃኑን ፍቅረኛዋን በምትጠብቀው አሲሰ ላይ ይረጫል። ጆን ባፕቲስት፣ በዝግታ ወደርስዋ ተራመደ፣ በእቅፎቹ ውስጥ አስገባት። ልብሶችዋን አልቀየረቻቸውም ነበርና፣ ጆን ባፕቲስት ያንን እንግዳ ፀጉር፣ ጌጣጌጥና በተለይም ያንን በቅርቡ በአዕምሮው ውስጥ አትሞ ያቆየውን ውበት፣ ቀለሙንና የውበቱን ውህደት አጣምሮ የያዘውን አንፀባራቂ መልክ፣ በታላቁ የእንግዳ መቀበያ አዳራሽ ግዙፍ የመብራት ብርሃን ስር ተመለከተ። በአጭሩ፣ ሁለቱ ፍቅረኛሞች አንዳቸው ለሌላኛው በሕይወት ቆይተው ፣ይንኑለት ለነበረው ጊዜ መድረሳቸውን በደስታ ለመገንዘብ ችለው ነበር። እዚህ ደረጃ ለመድረስ ብዙ መሰናክሎች ተደንቅረውባቸው ሰለነበረ፣ በአሁኑ ጊዜ ያገኙትን ደስታ ለአመል ያህል እንኳ የሚያደናቅፍባቸው ነገር ቢኖር የማይቀበሉት ነው። ሁለቱም በስሜት ተውጠው በረሃብም መሣሣም ውስጥ ቀለጡ። በጨለማ ውስጥ በቆየው የኦፔራ አዳራሽ፣ ትዕይንቱ ሲያልቅ ሲል፣ ውብ ጥንዶች በመድረክ ላይ ዳግመኛ ሲገናኙ የሚሰማውን የድጋፍ እልልታ ዓይነት ድምፅ ከምድር ቤቱ በኩል ይሰማል።

ከአጠገባቸው አንድ አልጋ አለ። ብቸኝነታቸው፣ ከማንኛውም ዓይነት ሁከት ነፃ ሆነው፣ ምስጢራቸውም ፍፁም የማላቸውና የተሟላ ነበር። ይሁን እንጂ በዚህ የፍቅር ደረጃ ላይ እርስ በርሣቸው የመፈላለጋቸው ነገር፣ እጅ እንዲሰጡና እንዲሣሣቱ አድርጓቸዋል ብሎ ማመን እነርሱን አለመረዳት ነው። እስከዚህ ጊዜ ድረስ፣ አንድ ቀን ርስበርስ የመፋቀራቸውን የነፃነት ተስፋ በማጣፈጥ ያሣድጉታል። በዚህ የደስታ ተስፋቸው ላይ የተጋረጡትን ገደቦች ሁሉ ለማስወገድ ጊዜውን ይጠብቃሉ።

«ፍቅሬ፣ ፍቅረኛዬ» ስትል፣ የጆን ባፕቲስትን ፊት በመሣም እየሸፈነችው፣ አሲስ አጉተመተመች። «ምን ያህል ደስተኛ እንደሆንኩ ብታውቅ፣ አፈቅርሃለሁ። በዚህ ሁኔታም ሁል ጊዜ መሆንን እፈልጋለሁ»

የጊዜ መጉተት አስቸጋሪነት ሃሣብ በውስጥዋ በመኖሩ፣ ተጀምረውና መልሣም ከጆን ባፕቲስት ራስዋን በመጠኑ ትገታዋለች። በእንባ በሚንፀባረቁ ውብ ዐይኖችዋ ተመለከተችውና ዝቅ ባለ ድምፅ እናገረችው።

«ወደ ቬርሣይለስ መቼ እደምትሄድ ከዚያም ደግሞ መቼ ተመልሰህ መጥተህ፣ ይዘኸኝ እደምትሄድ ንገረኝ»

«እሀ» አለ ጆን ባፕቲስት፣ ፊቱን በመጠኑ ዞር በማድረግ

«ምንድን ነው?»

« ሁሉም ነገር ተወሳስቧል። ወደ ቬርሣይለስ የሚደረገውን ጉዞ ቱርኮች ይቃወሙታል በሚል፣ አባትሽ ወሬው እንዲነሣ አይፈልጉም። በርግጥ፣ እኛም ነገሮች በትክክል እንዲሣኩ ያደረግነው ጥረት የለም። ሙራድንም፣ ምን ዓይነት እንደሆነ አይተሽዋል»

« ይህ ማለት ታዲያ . . . ያ ሁሉ ተስፋችን ስዚሁ ፍሬ ቢስነት ነው?»

« አይደለም!» አለ ጆን ባፕቲስት እጆችዋን ጭምቅ እያደረጋቸው፣ «እኔ ተስፋ ካደረግሁበት ይልቅ አስቸጋሪና ረዘም ያለ ጊዜ ይወስዳል ማለቴ ነው»

ጆን ባፕቲስት፣ ዓላማቸው ሁሉ አለመሣካቱን በቀላሉ ለመቀበል አልፈለገም። ተስፋ የሚያደርግበትን አቅጣጫ ሊለይ ባይችልም፣ በዚያች ሰዓት በአሲስ ፊት ቆሞ ተስፋ ቆርጦ መተው ማለት፣ ከመሸነፍ ይልቅ የባሰ ጥላቻና ተቀባይነትን ማጣት እንደሚሆን ተሰማው።

እነርሱ ካሉበት ቦታ በቱጥታ ከታች ካለው ምድር ቤት መውጫ መድረክ ላይ፣ ጥንዶች በብዙ ቁጥር እየሆኑ በመውጣት ላይ መሆናቸው፣ ደህና ሁኑ እያሉ ከፍ ባለ ድምፅ መሰናበታቸውና የማያቋርጥ የምስጋና ቃላቶቻቸው ድምፅ ይሰማል።

«ስማኝ» አሉት አሲስ። «ብዙ ጊዜ የለንም። የመጨረሻው ስረገላ ተንገኑን ሲያሣፍር አንተም መሄድ ይኖርብሃል»

ይህን ተናግራ እንደገና ሳመችውና ቀጠለች

«አንዳች አጣዳፊ ነገር በዚህ ጉዳይ ላይ እንደገባ ደግሞ እንድታውቅ»

«ምን ማለትሽ ነው?»

«አባቴ . . . አ! ይቅር፣ እንድታውቅ አልፈልግም። ነገሮችን ማወሳሰብ ምንም ፋይዳ የለውም»

«ማዲለም፣ ንገሪኝ»

«ባለፉት ሦስት ቀናት አባቴ ባለማቋረጥ ከፈረንሣይ አንድ ሰው ተልኮለት እንደሚመጣ እየተናገረ ነበር። ስውዱው ዲፕሎማት ሲሆን ሮሴታ ወይም ዳሚየታ ውስጥ እንደሆነ ተረዳኝ አንጂ፣ የቆንሲል ሥልጣን የሚጠሰው ነው»

«እናስ?»

«እናማ፣ አባቴ ስለዚህ ሰው ብዙ ጊዜ ይናገራል። ስለ ትውልዱ ታሳቅነት፣ ስለ አስተዳደጉ፣ ስለ ወደፊት ዕድሉ፣ ወደ እኔ በአትኩሮት እየተመለከተ ያወራል። በርግጥ እስከአሁን በግልፅ የተናገረው ነገር ባይኖርም፣ እናቴ እንደነገረችኝ ከሆነ ግን፣ አባቴ በሆነ ጊዜ ሊድረኝ እያሴረ ነው። አባቴ፣ ዘመዳችን የሆነውን ሚኒስትር፣ እርሱ የሚፈልገውን ዓይነት የሆነ ጨዋ ሰው እንዲልክለትም ጠይቆታል።»

« ታዲያ . . . አንቺ ይህን ሁሉ እንዴት ታስቢዋለሽ?» አለ ፖንሴ።

«እኔ የማስበው፣ ፍቅረኛዬ፣እኔማ አንተንና አንተን ብቻ ነው የምፈልግህ። ስዚህ ለሚባለው እንግዳ ሰው ከአሁኑ ጥላቻ እያደረብኝ ነው»

«ለመሆኑ እዚህ መቼ ይደርሣል ተብሎ ነው የሚጠበቀው?»

«በአሁኑ ጊዜ በጉዞ ላይ እንደሆነ ነው የሚገባኝ»

ጆን ባፕቲስት ፊቱን ቋጠረ።

«ስሚኝ» አለ ስውነቱን ሰብሰብ እያደረገ

«ሁሉንም እስክናስተካክል ድረስ ጥቂት ጊዜ ይወስድብን ይሆናል። ይህ የምትይውም ሰው እኔ፣ አባትሽን ለማግኘት የምችልበትን ነገር በእጄ ከማድረጌ በፊት ሊደርስ ይችላል። እስክዚያው ድረስ ግን ለምንም ነገር ስምምነት አታድርጊ። ለምንም ነገር ቃል አትግቢ። አሻፈረኝ በይ። አንድ ሺህ አንድ ሰበቦችን አትርቢ፣ የታመምሽ አስመስይ፣ ከፈለግሽም በፍራንቾይዝ በኩል እንዲያስልሽ ሊያደርግ፣ ወይም እንዲያስመልስሽ ወይም መልክሽ እንዲገረጣና እንዲያውም በርግጥ ካስፈለገ እንድትታመሚ ሊያደርግሽ የሚችል ፈላሽ መድሃኒት ልልክልሽ እችላለሁ። ምንም አድርጊ ምንም፣ ለምንም ነገር ቃል አትግቢ»

«እስክዛሬ ድረስ ክልቤ ውስጥ መንጭቶ የገባሁት ቃል ቢኖር ሁልጊዜም ያንተ ብቻ መሆኔን ነው። ይህን ደግሞ አታስብ። አንተ የጠየቅሽኝን ሁሉንም ነገር እፈፅማለሁ። ይሁንና፣ አባቴንም በሚገባ አውቀዋለሁ። የምፈልገውን ነገር ሊከለክለኝ ይሞክር ይሆናል እንጂ ትዕዛዙን እንደፈፅም ግን ከቶም ሊያስገድደኝ አይችልም። ከአባቴ ጋር በጭራሽ መስማማት የማንችል ከሆነ፣ ማናችንም አሸናፊ የማንሆንበት ሁኔታ ይፈጠራል። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ተቆራርጠን እንቀራለን»

የመጨረሻው ሠረገላ፣ ተሣፋሪዎችን ሊጭን ሊቀርብ እንደገና ተሣሣሙ። ከምድር ቤቱ አሁንም ጥቂት ድምፆች ይሰማሉ። የሚለዋወጧቸው መልዕክቶች ሁሉ በፍራንቾይዝ በኩል ይተላለፍላቸዋል። ፍራንቾይዝ እንድታስተላልፍላቸው የማያደርጉት ብቸኛው መልዕክታቸው፣ የስሜት ህዋሣቶቻቸውን እርካታ፣ በእጆቻቸውና በከንፈሮቸቸው ላይ ያሉትን ምልልሶች፣ የሁሉን አካላት የመፈላለግ ጨዋታና አንዳቸው ለሌላቸው በከፋይና በሃር ልብሶቻቸው ውስጥ በሹክሹክታ የሚያስተላልፏቸውን መልሶች ይሆናል።

ከመልበሻው ክፍል የጨለማ ቦታ ምናልባት አንድ ሰው በማንኛውም ጊዜ ሊመጣ ይችላል የሚል የፍራንቾይዝ ዝቅ ያለ ድምፅ ተናገረ። አይኖቻቸውን እንባ እንደሞሏቸው ተሰያዩ። በደረጃው ላይ የሚሰማው የእግር ዱካ ድምፅ እስኪጠፋ ድረስ፣ አሊስ ጠበቀች። ከዚያም፣ የመኝታ ክፍሏን በር ቀርቅራ፣ ሙሉ ልብስዋን እንደለበሰች አልጋዋ ላይ በዝግታ ተጋደመች።

ፖንሌ መኖሪያ ቤቱ ሲደርስ፣ ሜትር ዣረሚ አንድ ፋኖስ ከእግሩ ስር አብርቶ፣ ደረጃው ላይ ተቀምጦ በአንድ ትንሽ ብርጭቆ የመንደሪን ጭማቂ ይጠጣ ነበር። ይህ ጭማቂ፣ የመድሃኒት መቀመሚያው በአገልግሎት ላይ ባልነበረበት ወቅት ከረዥም ጊዜ በፊት የተነጠረ ነበር።

«እሺ አቶ አፍቃሪ ፣ መጡ?» አለ ዣረሚ

ጆን ባፕቲስት አንዳችም ቃል ማይወጣው ከንደኖው ባሻገር ተቀመጠ።

«ኧረ... ኧረ... እንዲያው አንዳች ደስ የማይል ዜና ያለም ይመስላል። እስቲ ጨንራህ ሞት እንዲለው ይህን ጠጣ»

ሜትር ዣረሚ፣ለንደኖው አንዲት ትንሽ ብርጭቆ አቀበለው። ፖንሌ ተቀብሎ ሳይቀምሰው በደረጃው መደገፊያ ላይ አስቀመጠው።

«ጠንክር ማለት አልቻልክም ንደኖዬ» አለ ዣረሚ ከተቀመጠበት እየተነሣ።

ቢመሽም እንኳ በጥሩ ስሜት ላይ ነበር። መልካም የምሽት ሰዓት ያሣለፈና ራሱን ለማነቃቃት የንደኖውን መምጣት የሚጠባበቅም ይመስል ነበር። የበረንዳውን ደረጃ በረዥም ርምጃ አቋረጠ።

«ችግሩ ምንድን ነው? ከእንተነትህ የምትቀበልህ አንዳችም ክፍል የላትም?»

«ትቀበላለች» አለ ፖንሌ፣ ሣጣቡ በሌላ ጉዳይ ላይ ሆኖ እንደመጃጃል እያለ።

ሜትር ዣረሚ፣ ያስቀመጣትን ትንሽ አጥንት አንስቶ ድምፅ እስክታሰማ ድረስ ይቆረጣጥማት ጀመር። ከዚያም፣ ይህ በጣም አስፈላጊው ነጥብ እንደሆነ፣ እርሱም ሲበዛ እድለኛ መሆኑን፣ ጋራጣና አንትፋቶችም አልም ብለው እንደሚጠፉና ስሜቱ ሁሉ ውስታ እንዲመልስ እንደሚቀሰቅሰው ነገረው።

«ተስና ሻምላህን ይዘህ ተፋለም! ልታደርገው የሚገባህም ይኸው ነው። እስቲ ያሰህበትን ሁኔታ ተመልከት»

«ወደ ቬርሣይለስ አንሄድም» አለ ጆን ባፕቲስት፣ ትክዝ ብሎ «ንጉሡ የጀብዱ ማዕረግ አይሰጡኝም። በዚህም ሣቢያ እርሷን አላገባትም»

«እናም ምሽቱ ዘለዓለማዊ ይሆናል፣ ውሣውም ዳግም ሽቅብ በመፍለስ ሳይረጭና ሳይምላ ይቀራል፣ በመጨረሻ ላይ ጅቦቹ ሁሳችንንም በመስገብገብ ይበሉናል። በል ተመለስ፣ ተመለስ! አንተ አሮጌ ጨለምተኛ! እስቲ ወኔህን አሣይ»

ሜትር ዠረሚ፣ ደረጃዎቹን በከባድ ርምጃዎች አቋረጣቸውና ወደ ፖንሴ ክፍል ውስጥ ገባ። ከዚያም ሁለት ጉራዴዎችንና የደረት መከላከያዎችን ከተሰቀለበት ሜንጦ ላይ አንስቶ ወደ ጓደኛው ተመለሰ።

«ይኸውልህ፣እንደጥንቱ ቀልጠፍ በል። እስቲ በአምስት ደቂቃ ውስጥ ያ የጥንቱ አንተ መሆንህን ወይም አለመሆንህን አረጋግጥ»

ጆን ባፕቲስት ከወንበሩ ላይ መነሣት ፍላጐት አልነበረውም። በዙሪያው፣ ፀጥ ባለው አየር ውስጥ፣ አሊስ በሰውነቱና በልብሶቹ ላይ የተወቻቸው የመጨረሻዎቹ ጠረኖችዋ እንደተቀቡ ናቸው። ይሁን እንጂ፣ በልቡ ጥልቅ ሥፍራ ውስጥ፣ ጓደኛውን በዚያን ዕለት ምሽት የተወው መለለውና ትንሽም ቢሆን ክፍተቱን ሊያጠብበው ፈለገ። ከወንበሩ ላይ ተነስቶ ቆመ። የቆዳውን ሰገባ ሳበና፣ የተከላካይ ቦታውን ያዘ። ሜትር ዠረሚ በጥቂት ሴኮንዶች ውስጥ በሻምላው ጫፍ ፖንሴን ነካ አደረገው። በድጋሜ በሻምላ ተዋጊነት ቦታ ራሣቸውን አዘጋጁ። ይህ ሁሉ ሲሆን ፖንሴ እንደቀድሞው አይደለም። ለጥቂት ጊዜ ያህል ደካማ መከላከል አደረገ። ሜትር ዠረሚ ለሁለተኛ ጊዜ ዘሎ አፈፍ በማድረግ ነካው።

«በል ነቃ በል፣ ያዝ! እንዲህ ወዙን ያጣውን ሰዛህን ለመመለስ፣ መኮርኮር አለብኝ እንዴ?»

ማንኛውም ሰው የሽንፈት ድምፅ ሲሰማው፣ የተዋጊነትና የጦረኛነት መንፈሱ ከተኛበት ጥልቅ አዘቅት ሆኖ ያስቆጣዋል። አሰምሮው በሌሎች አስጨናቂ ጉዳዮች ፍፁም ተውጥሮ ባለበት ጊዜም እንኳ ቢሆን፣ የመጀመሪያው የሻምላ ጫፍ ሰውነቱን ሲሞረው፣ ጡንቻዎቹ

ተቆጥተውና አይኖቹ ተጉረጥርጠው፣ የፀበኛነት ስሜት የማይቀሰቀስበት ሰው ተሰምቶ አይታወቅም። ሰሰተኛ ጊዜ በጉራዴው ሲገጥመው ፖንሴ ወደ ህሊናው ተመለሰ። ሜትር ዠረሚ በሚገባም ባይሆን፣ በድጋሚ ነካ አደረገው። ከዚህ በኋላ ግን ረዘም ያለ፣ የሚመጣጠን ግጥሚያ አደረጉ። በክንድ ርቀት፣በተሟላ ስልትና ብልሀት፣ በሚያስደንቅ ቅልጥፍና፣ የታፈነ ፖሽትና ጉዳት እስኪሰማ ተፋለሙ። በመጨረሻም፣ ጆን ባፕቲስት በሻምላው ጫፍ ዠረሚን ነካ አደረገውና አሸፈሪ ፖሽት አሰማ።

«ጀስዊቶቹ!»

ሜትር ዠረሚ፣ ትንፋሹ ጠፍቶ፣ ጉራዴውን እንደመጣል አድርጉ፣ ዙሪያውን ግራ በመጋባት ተመለከተ።

«የምን ጀስዊቶች ናቸው? የታሉስ?»

ጆን ባፕቲስት ወደ ኋላው ፈቅ ብሎ ለመከላከያ በተሠራው የብረት አጥር ላይ ደገፍ አለ። ከሃሣቡ ጋር ወዲያና ወዲህ እያለ ጉራዴውን በያዘው እጁ በሃሣቡ የፈጠረውን የአዋጅ ፊደላት በአየር ውስጥ ከተበ።

«ጀስ-ዊ-ቶቹ። እውነቱን ነው ጀስዊቶቹ። በዚህ ጉዳይ ሊረዱን የሚችሉት እነርሱ ብቻ ናቸው»

«እንዴት ያለ ሰይጣናዊ ነገር ነው የምትናገረው?»

«ወደ ቬርሣይለስ ስለሚደረገው ጉዞ ነው። ታዳምጠኛለህ? ሊረዱን የሚችሉት እነርሱ ብቻ ናቸው። ወይኔ! ምነው ፈጠን ብዬ አሳሰበኩትም? አምን፣ቆንሲሉን በጉዳዩ ላይ እንዲቀርብ ሊያደርጉትና እኛም ንጉሡ ዘንድ መድረስ የሚያስችሰንን መንገድ ሊረዱን የሚችሉት፣ ከሁሉም በፊት የንጉሡን ትዕዛዝ እዚህ ድረስ ማስተላለፍ የቻሉት ብቻ ናቸው። ምንም እንኳ የማይታመኑ መሆናቸውን ብናውቅም ሃይላቸውን መዘንጋት የለብንም»

«ነገር ግን» አለ ሜትር ዠረሚ በትካዜ። «አቢሲኒያ ውስጥ ጀስዊቶች ዳግመኛ ተመልሰው አይመጡም በማለት የገባነውን የጨዋ ቃል ኪዳን ረስተሃል። ወደ ቬርሣይለስ መሄድ ከፈለግን፣ እነዚህ የጂስዊት መልካም አባቶች የሚመግቡትን፣ ከንጉሡ ሃሣብ ጋር

በቀጥታ ተፃራሪ የሆነ መግለጫ ማረጋገጥ ብቻ ነው። በገዛአችን ላይ በመጨረሻ ከኛው ጋር እንዲሆኑ የምንፈልጋቸው ሰዎች ደግሞ እነርሱ ናቸው.»

«ትክክል ነህ። ነገር ግን የዚህ ግትር ሃሣብህ መቋጫው ወደ ቬርሣይለስ እንሄድም፣ በቤተመንግስቱም አደባባይ የሚሰማው የጀስዊቶች ትርጉም ብቻ ነው የሚል ነው»

«የዚያን ሃሣብ ትርጉሜ የኛ ስምምነት ሳይኖርበት ብቻቸውን ቢያቀርቡት የሚሻላቸው ነው»

«አይደለም!» አለ ፖንሴ። «ወደ ቬርሣይለስ ለመሄድ ከጀስዊቶች ጋር መቀናጀታችን ከነርሱ ሰበቦች ጋር መስማማታችንን ሳይሆን፣ በንጉሡ ፊት መቅረብ ስንችል በጨዋ ሁኔታ ተቃርናአችንን ለማሳየት ነው። አሁን የምንፈልጋቸው ልንጠቀምባቸው ስንል ብቻ ነው»

«አስከአሁን ድረስ የነርሱን ሃሣብ መርምረህ ሳታይ፣ የነርሱኑ ስልት የተቀበልክ ነው የምትመስለው»

«ታዲያ የጠላትህን ዓይነት የጦር መሣሪያ ከሌለህ እንዴት ትዋጋለህ? ለምሣሌ፣ እኔ በጦራዴ ባጠቃህ አንተ በማንኪያ ትከላከላለህ ወይ?»

«የባላጋራህን ድክመቶች መክረጅ ሽንፈትህን መቀበልና የጠላትህን ድል አድራጊነት ማመን ነው»

«ይህ ካልሆነ የተሻለው ነገር ፍፁም ነፃ ሆኖ መሞት ነው»

«አዎን፣ ከክህደት ይልቅ ሞት ይሻላል። ነገር ግን፣ አለ ሜትር ዣረሚ በዚያ ግዙፍ ቁመናው ዓይኖቹን እያጉረጠረጠ «ሣይረክሱ መቆየትና ማሸነፍም ይቻላል።.

«የውይይታችንን ፍሬ ሃሣብ መሠረት እየሰቀቅን ነው» አለ ጆን ባፕቲስት በብልጣብልጥ ሁኔታ። «የንጉሡን መልዕክት ቬርሣይለስ እንዴት ማድረስ እንችላለን? ጥያቄው ይህ ነው። እውነተኛውም ጥያቄ ይህ ብቻ ነው። እኔ ላስረዳህ የፈለግሁትና እየነገርከህ ያለውም ይህን ተልዕኮአችንን በተአምር ከፍፃሜ ሊያደርሱልን የሚችሉት ጀስዊቶች ብቻ ናቸው»

ሜትር ዣረሚ ወደ ኋላው ሦስት ርምጃ ወደ ግድግዳው ተራመደ። ከዚያም እንደገና ከጎደኛው ፊት ለፊት ሆነ።

«ጆን ባፕቲስት፣ ሁሉንም ነገር እያወሣሰብክ ነው። ይህ ጉዞ ላንተ ግላዊ ምክንያት ሊባል ጉዳይህ ነው። ስለዚህም ግላዊና ፍፁም የራስ ወዳድነት ፍላጐትህን ለማርካት ስትል ቃል ኪዳንህን ለማፍረስ ዝግጁ ነህ።»

«እንዲህ አትበል!» አለ ፖንሴ የመደገፊያውን የብረት አጥር በጉራዴው እጀታ አየገጨ።

«እንግዲያው ተሳስቻለሁ እንዴ?» ሲል ሜትር ዣረሚ በጥላው ጠርዝ ላይ እንደቆመ ጠየቀ።

«ትክክል ነህ፣ ትክክልም አይደለህም። አምን፣ወደ ቬርሣይለስ በመሄድ የራሴን ጉዳይ ላመልክት እፈልጋለሁ። ይሁን እንጂ የአቢሲኒያውን ንጉስ በምንም አይነት አልክድም። ለነዚህ ሁለት ተልዕኮዎች ግን እኩል የሆነ አትሜንና ችሎታዬን በማዋል፣ ሁሉንም በስኬት መፈፀም እፈልጋለሁ»

ሜትር ዣረሚ ራሱን በጥላው ውስጥ ለመሸፈን አንድ ርምጃ ወደ ኋላ ተራመደ። ይህ የመደበቅ ሁኔታ፣ ሃሣቡን ያለ ውዴታ የመቀበል ምልክት እንደሆነ ፖንሴ ያውቃል።

«እስቲ ለኔ ተወው» አለ ጆን ባፕቲስት በተረጋጋ ድምፅ። «አጥብቄ የምጠይቅህ፣ አንተ ከዚህ ሁሉ ነገር ነፃ ሆነህ በኔ ግን እምነት እንዲኖርህ ነው። ለጀስዊቶቹ፣ እኔ ብቻዬን ጉዳዩን እነግራችዋለሁ። ወደዕቅዳችንም ውስጥ የሚመጡበትን ሁኔታና የሚከተሉውን አደጋም ብቻዬን እቀበላለሁ። በመጨረሻም፣ በንጉሡ ፊት እኔው ራሴ ማስተባበሉ የሚያስከትለውን አደጋ እቀበላለሁ»

«በኔ ሃይማኖት፣ የምንስጠክው በምሣሌ ብቻ ነው» አለ ሜትር ዣረሚ ከጨለማው ውስጥ እየወጣ። «በአቅም ወይም በማሣመን ሃሣብህን ላስለውጥህ አልሞክርም። በግሌ ግን ወደ ጀስዊቶች ዘንድ አልሄድም። ሊሞኙ ይችላሉ ብዙ ለመቀበልም ይከብደኛል። አንተን ግን ባቀድከው ዓላማ ላይ እንቅፋት አልሆንብህም። እንዲያውም እንደሚሣካልህ ተስፋ እደርጋለሁ።»

ጆን ባፕቲስት በጓደኛው አስተያየት ተደስቶና እንደማይቃረነው በማወቅ፣ ወደ ሜትር ዝረሚ ራመድ አለ። ጓደኛውም ወደርሱ ተራመደ። ሁለቱም ለወዳጃዊ አለመግባባታቸው ዕዋቸውን አነሱ። ቬጋው እነርሱን ቁልቁል ሲመለከታቸው፣ የካይሮ ውሾች በከፍተኛ ድምፅ ይጮሃሉ።

ፈ

በቆንስላው ግቢ እራቱን ከበላ በኋላ፣ ሙራድ ክፋኛ የራስ ምታት አምሞት ነበር። ይህም በመጠጡ ሳቢያ ቢሆንም፣ እርሱ ግን በምግቡ ላይ ያሳብብ ነበር። ከያንዳንዱ የመጠጥ ዓይነት በዛ ያለ ናሙና በመቅዳት፣ በጠረጴዛው ዙሪያ የተቀመጡት ሁሉ አሣፋሪ ነው አስኪሉት ድረስ የሻምፖኝ፣ የባርጋንዲና የመራራ ቅልቅል በእንድ ብርጭቆ ውስጥ በመሥራት ጠጥቷል።

ከሁሉም ነገር በላይ፣ በየማለዳው ፀጉሩን በሰባራ መስተዋት የሚላጨው ኢትዮጵያዊው ባሪያ፣ የሙራድን አናት በምላጭ ሲላጨው ገሽልጦታል። ሙራድ፣ ለብረት ምላጭ ጥላቻ አለው። የደረቀ የደም ጠብታ በጥምጣሙ ስር ይታያል። ኮሚቱ ሶስት ሰዓት ሲሆን፣ ፖንሴ ወደርሱ መጥቶ፣ የጀስዊቶች ቃል አቀባይ እንዲመጡ እንደላከባቸውና ከጥቂት ጊዜ በኋላም እንደሚደርሱ ነገረው። የንጉሠ ነገስቱን ቃል ያልረሣው ሙራድ በመጀመሪያ ላይ ተበሣጨ። በኋላ ግን ፖንሴ እቅዱን ሊያብራራለት የመፅናናት ስሜት ተሰማውና ስለ ሆድ ህመሙ ይወተውት ጀመር።

አባ ፕላንቱይን፣ ከተባለው ሰዓት ጥቂት ቀደም ብለው ደረሱ። ከሙራድና ከፖንሴ ፊት ደርሰው እንደቆሙ፣ አምባሣደሩ ባመለከታቸው መሠረት፣ ልክ አንድ ግዙፍ በሬ ፍፁም እንክትክት ብሎ እንደሚወድቅ ዓይነት በምንጣፉ ላይ ሰመጡ። ሙራድ፣ በጨዋ የሲቪል ባህርይ ቡናና ኬክ ጋበዟቸው። ጀስዊቱም ተቀበሉ። ግብግቡንም በሰልፍ የቆሙት ሦስቱ ኢትዮጵያውያን ባሮች ከጥቂት ጊዜ በኋላ አቀረቡ።

አባ ፕላንቱይን፣ እነዚህን ሦስት ኢትዮጵያውያን ባሮች እንደተመከሰቷቸው ወዲያውኑ በጉልበታቸው ቆሙ።

«አምላኬ ሆይ! እንዴት ቆንጆዎች ናቸው!»

ሦስቱን ይመራ የነበረው የሁሉም ታላቅና እግረ ቆልማማው ሲሆን፣ እርሱን ተከትሎ በዕድሜው ሁለተኛ የሚሆነውና በሚያስጠላ መልክ ጠንጋራ የነበረው ነበር። ከሦስቱ ወጣት የሆነውና የራስ ፀጉሩ ሁሉ በሞርት ሙልሞ ብሎ ያስቀበት ልጅ በመጨረሻ ነበር።

«እንደዚያ ነው የሚያስቡት?» አለ ሙራድ በረድፍ ያሉትን አሣዛኞች እየተመለከተ።

«መንፈሣቸው ይታየኛል» አሉ ቄሱ፣ ዓይኖቻው ረጥበው። ማርያም ድንግላዊት እንዲባረክ ለመረጠችውና በዋሻ ውስጥ ለነበረ የበግ እረኛ በርህራሄ እንደተገለጠችለት ዓይነት፣ ትኩር ብለው ተመለከቷቸው።

«እንዲህ ከሆነም መልካም። ንጉሱም እንደህ ያለ ዕይታ ስለነበራቸው ዕድለኛ ናቸው። እነዚህ ሦስት አገልጋዮች፣ ለንጉስ ሉዊስ 14ኛ ከታሰቡት ገፀ በረከቶች መሃል ናቸው» አለ ፖንሴ

ሦስቱ ባሮች እያነከሱ ወደ ማድ ቤት እስኪመለሱ ድረስ፣ አባ ፕላንቴይን አይናቸውን ከነርሱ ላይ አልነቀሉም።

«ንጉሠ ነገስቱ፣ ለፈረንሣይ ንጉስ ከሳኪቸው ገፀበረከቶች መሃል ናቸው ነው የምትለኝ? ሰመሆኑ ሌሎችም አሉ?»

«እንዴ፣ አባቴ፣ በርግጥ አሉ እንጂ። ያውም ግዙፍ የሆኑ ናቸዋ» አለ ጆን ባፕቲስት

ቄሱ የተመለከቱትን እንደህ ያለውን ስጦታ ሊያስንቅ የሚችል ገፀበረክት ሰማሰብ ቸገራቸው። ፖንሴ የማወቅ ጉጉቱን እያጠናከረ፣ ቀስ ብሎ ኪሱን ከፈተና ደብዳቤ መዘዘ።

«እንደ ዕድል ሆኖ ይህ መልዕክት ከፓሻው ፖሊሶች ዕይታ አመለጠ»

«መልዕክት? መልዕክት ከፓሻው ፖሊሶች ዕይታ አመለጠ»

«ወራሣቸው ፀሐፊ፣ እራሣቸው በቃላቸው እየነገሩት የተከተበና የታተመ ነው»

በሁለቱ ሰዎች መካከል የሚደረገውን ውይይት ሙራድ ይከታተላል። ፖንሴ፣ ከንጉሡ የተላከውን ደብዳቤ ጉዳይ ሲናገር በመስማቱ፣ ሙራድ ጭንቅላቱን በድንገት ወደርሱ ሲያዞር የራሰ ምታቱን አባባሰው። አባ ፕላንቴይንን ይቅርታ ጠይቆ በመከዳው ላይ ከመዘርጋቱ በፊት፣ የመድሃኒት ቀማሚውን ሴረኛ የአይን ጥቅሻ ለማየት ጊዜ ነበረው። ቄሱ ደብዳቤውን ከፖንሴ እጅ ለመቀበል እጃቸውን ዘርግተዋል።

«ወይኔ» አለ ፖንሴ ወረቀቱን ወደ ኪሱ መልሶ እየከተተው። «ንጉሠ ነገስቱ፣ ይህ መልዕክት ለንጉሥ ሉዊስ 14ኛ በግላቸው ካልሆነ በስተቀር ለማንም ሰው እንዳይሰጥ በጥብቅ አዝዘዋል። ሌላው ቢከፈትም የሹመት ደብዳቤ ነው። ይህኛው ግን በማንም ሊታይ የሚችል አይደለም። እኔም ቃሌን በመሃላ ሰጥቻለሁ።»

«እና . . . መልዕክቱ የሚለው ምንድ ነው?» በማለት የማወቅ ጉጉት እያሰቃያቸው ጀስዊቱ ጠየቁ።

«አባቴ፣ ደብዳቤውና በውስጡ ያለው ሃሣብ አንድ ነው። ሁሉም ለንጉሥ ሉዊስ 14ኛ ናቸው»

«አምን፣ ልክ ነህ፣ ዝርዝሩን አንተወውና መንፈሱን ምንድን ነው ማለቴ ነው?»

«ሙሉ በሙሉ የሚስማማ ነገር ነው። ይህን ያህል ልነግርዎ እችላለሁ። ንጉሠ ነገስቱ፣ ለፈረንሣዩ ንጉሥ ያላቸውን አክብሮት በመግለፅ በማንኛውም የሃይማኖት ጉዳይ ላይ ፈቃደኛ መሆናቸውን ይገልፃሉ»

«ጥሩ፣ በጣም ጥሩ፣ እና ንጉሠ ነገስቱ የክርስቶስን ሁለት ባህርያት እስከመቀበል ድረስ ፈቃደኛ ይሆናሉ?» በማለት ጀስዊቱ ጠየቁ።

አንድ ሰው ስለአንድ ነገር ብዙ ሲያውቅና ስለጉዳዩ የሚያስጨንቀውም ምንም ምክንያት ባለመኖሩ ምንም መናገር እንደማይችል፣ ፖንሴ ዐይኖቹን በግርምት በለጠጣቸው። አባ ፕላንቴይን፣ የተረዱና የተደሰቱ መሆናቸውን የሚገልፅ አይታ አሣዩ።

«አሺ . . . ሌሎቹ ገፀ በረከቶችስ?» ሲሉ ጠየቁ

«አዚሁ አሉ። ወርቅ፣ ዝባድ፣ ቅመማ ቅመም፣ የሃር ሻሾችና ንጉሡ ባሉበት ቦታ ብቻ እንድንከፍታቸው የተፈቀዱልን ሻንጣዎች ናቸው።»

«እጅግ በጣም ጥሩ . . . እጅግ በጣም ጥሩ!። ተልዕኮህ በጣም ጥሩ ነበር»

«ምን ያደርጋል! አባ ብሬቬደንት ግን ይህን ውጤት ማየት አልቻሉም። በታላቅ አክብሮት የምናስታውሣቸው ሰው ናቸው። ተልዕኮአችንን እርሣቸው በመካከላችን ቢሆኑ ኖሮ ግን በተሣካ ሁኔታ አሟልተን ማከናወን እንደማንችል ግን ይመኑኝ»

«ነው እንዴ፣ ገባኝ! የንጉሡ የንስሃ አባት ማህበር፣ ያለ አባ ዴ ላ ቼይዝ ንቁ ተሣትፎ ሊሣካ አይችልም ነበር። የዚህን ታላቅ ሥራ ውጤት ምክንያቶች በርግጥ ለንጉሡ ማቅረብ ይኖርብሃል።.

«እኔም አስቤ ነበር። ነገር ግን እንደማይሣካ እኮ እርስዎም ያወቁታል» አለ ፖንሴ እያጉነበሰ

«አምን፣ቱርኮችን አይደል»

«አባቴ፣ ቱርኮች ቀላል ኢላማም ናቸው»

«ምን ማለትህ ነው ታዲያ?»

ባሮቹ መጥተው፣ መለኪያዎቻቸውን እንዲሞሉላቸው ፖንሴ አጨበጨበላቸው። ቄሱ እንደና የአግራሞት ስሜታቸውን ከፍ እንዲል በማሰብ፣ ባሮቹ በፍጥነት ገብተው እንዲወጡ አደረገ። ባሮቹ እንደወጡ አባ ፕላንቴይን ጥያቄአቸውን ቀጠሉ።

«ስለ ቱርኮች የሆነ ነገር ስትናገር ነበር» አሉት አቋሙን ዳግም ለማረጋገጥ

«አይደለም፣ አባቴ። ስለነርሱ የምትናገሩት እናንተ ናችሁ። እኔ የምገልፀው ዋርጣሬዬን ነው»

«ምን፣ፓሻው ወደ ፈርንሣይ እንዳትጓዝ ሊከለክልህ መቻሉን አታምንም?»

«መሃመት ቤይን አላውቀውም። ከርሱ በፊት ለነበረው ፓሻ ሰብዙ ዓመት ሂጪ ነበርኩ። ምንም ያህል አክራሪ ቢሆኑም፣ በተሰይ ይህኛው ፓሻ በግርዋም አክራሪ ነው። ይሁንና አቶማኖች ግን ከኛ ጋር ባላቸው ግንኙነት ላይ ከተወሰነ መጠን በላይ ሄደው አያውቁም»

«ምን ማለትህ ነው?»

«የምለውማ፣ ቱርኮች የቆንሲሉን የቅድሚያ ይሁንታ ሣያገኙ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኝ ቤት እንዲበረበር ፈፅሞ አያዝዙም»

«ስታስበው . . »

« . . . የቱርኮች ፖሻና መሴ ዴ ማይሌ በዚህ ሥራ ላይ እንግዳና አዲስ የሆነ ህብረት በኛ ላይ ፈጥረዋል።»

ጀስዊቱ በመጀመሪያ ጀሮ ግንዳቸውን የተጮሉ መሰላቸው። የባሰ የማታለያ ማሣሣቻ መግለጫ አሰቡ። ዓይኖቻቸው ከሽፋሽፍቶቻቸውና ከቅንድቦቻቸው አጥንት ጀርባ በጥልቁ ዋሻዎቻቸው ውስጥ እንስቅቃሴ አልባ ሲሆኑ ከንፈሮቻቸውም ተሰበሰቡ።

«ሙሴ ፖንሴ፣ ስሞታህ እጅግ አሳሳቢ ነው። የንጉሡን ፍላጐት ለማገድ አስቀድሞ የታቀደ አቅድ እንዳለ እንዳምንህ የፈለግህ ይመስለኛል»

«አባቴ፣ ንጉሡ አንድ ፍላጐት ብቻ እንዳላቸው ማሰብ የሚፈልጉ ይመስላል። ባልሣሣት፣ ንጉሡ በአቅራቢያቸሁ ባሉ ሰዎች የሚገለፁ ብዙ ፍላጐቶች አሏቸው። አንዱ የንጉሡን ክአደጋ የመጠበቅ ሃላፊነት ያሰባቸው አሉ። ሌላው የንጉሡን ፖለቲካ የሚመሩት ናቸው»

አባ ፕላንቴይን በጥልቅ ተመስጦ ውስጥ ገቡ።

«በኛ በኩል፣ በአባ ቪርግሣው በኩል የመጡትን ትዕዛዞች አብረን ተቀብለናቸዋል። ንጉሡም ከኛ የጠበቁትን ሁሉ በትክክል አከናውነናል። የፈጠርነውን ግንኙነት በወሳኝነት ለመጠበቅና ለንጉሡ ያለንን ተጠያቂነት ለማከናወን፣ የንጉሡም አምባሣደር፣ የንጉሡ መልዕክት ለሉዊስ 14ኛ መድረሱን እንዲያረጋግጥና መልስ ይዞ መመለስ እንደሚገባው አምናለሁ። ነገር ግን ይህ ሃሣብ ፈረንሣይ የክርስትና ተልዕኮዋን ማሟላት ይገባታል ከሚሉት ይልቅ፣ ከቱርኮች ጋር ያለንን ሕብረት ጠብቀን ማቆየት ይገባናል በሚለው አቋም ላይ ይበልጥ አጥብቀው ከሚጠይቁ ጋር በርግጥ ይቃረናል።

ጀስዊቱ በመከራ ተነስተው ቆሙ።

«በፍጥነት የዚህን ጉዳይ ሥረ መሠረት እጀምራለሁ» አሉ።

ሰብዙ ደቂቃዎች ሊያንኳራፋ የነበረውን ሙራድን እንዳይቀሰቅሰው በመምከር፣ ፖንሴን ተሰናብተው፣ በፍጥነት ብድግ ብለው ተንቀሣቀሱ። ሃጢአት ውስጥ ለመዘፈቅ እንደሚዘጋጅና፣ ቢዋጋውም እንኳ መልካም እንደሆነ እንደሚያምን የተደሰተ ሰው መልክ ነበራቸው።

9

ለሦስት ቀናት ያህል ፖንሴ ምንም ወሬ ሳይሰማ ቀየ። በነዚህ ረዥም ሦስት ቀናት ውስጥ ወደውጭም አልወጣም ነበር። ምክንያቱም ለእራት ሊጋብዙት የሚሹ ሁሉ በያንዳንዱ ነጥብ ላይ ትኩረት ነበራቸው። ወቅቱ ደግሞ ሞቃት ነበር። ከሰባይ በኩል የሚነፍሰው ነፋስ ደስ የማይልና ቀፋፊ ሞገድ ከደለሉ አካባቢ ተሸክሞ ይመጣል። ፖንሴ፣ ለምን ጠፋህ እንዳይሉት ታምሜአለሁ ሲል አስታወቀ። ብዙም ሳይቆይ በርግጥ ታመመ። መሳው ሰውነቱ በትኩሣት ተቃጠለ። በአጠቃላይ ሰውነቱም አልፎ አልፎ ድንገተኛ የመሸማቀቅ ሕመም በጉልበቱና በክንዱ ላይ ይሰማው ነበር። ሰውነቱ ልፍስፍስ ስለሚልበት ቀኑን ሙሉ በተንበልጣይ አልጋው ላይ ያልተያያዙ ሕልሞች እየታዩት፣ ሲነቃ እየጠፉበትና የሃዘን ስሜት እያሳደሩበት ተጋድሞ እንዲውል አደረገው። በየዕለቱ ልታየው የምትመጣው ፍራንቾይዝ የፍቅር ሕመም እንደያዘው እየሣቀች ትነግረዋለች። ይህን ንግግር ፖንሴ አውነት ነው ብሎ ለመቀበል ዝግጁ የነበር ቢሆንም ሕመሙ ግን አልተሻለውም። በሁለተኛው ቀን ከአሊስ የተሳከሰትን ደብዳቤ አመጣችለት። ፖንሴም ደብዳቤውን ደግሞ ደጋግሞ ለአንድ መቶ ጊዜ አነበበው።

ደብዳቤው ምንም አልነበረውም። ጥቂት የመውደድ ቃላት፣ ምናልባት በመሣል ሳንካ ቢገጥማቸው እንኳ ብዙም የማያደራድሩ ቢሆኑም ጽፋቸዋለች። የጽሁፉን መስመሮች ተመለከታቸው። ደብዘዝ ያሉ ቢሆኑም፣ ቅጥልጥሎቹ ግን አካላዊ እንቅስቃሴዋን፣ የፃፉትን እጆችዋንና ብዕሯን የመሩትን መሳው አካሏን የሚያሣዩበት ይመስላሉ። በሦስተኛው ዕለትም ሌላ ማስታወሻ መጣ። ይህኛውም የመውደድ ቃላቶችን የያዘ ሲሆን፣ ወደ መጨረሻው ላይ ከርዕሱ ወጣ ያለ ነገር አክላበታለች። ነገሩ ከፍቅራቸው ጉዳይ ወጣ ያለ በመሆኑ ጥረት እንዳደረገች ያረጋግጣል።

አስተውለሽው እንደሆነ እርግጠኛ አይደለሁም። ውድ ፍራንቾይዛችን ልታውቀው ባልቻለችው ፍቅር ውስጥ ጭልጥ ብላ አይገቡ ገብታለች። ከንደናህ ከዝረሚ ጋር በፍቅር ጣፋለች። አመጣጡ ሁሉ አደጋ የበዛበት ስለሆነ ከርሷ ማመንታት ጋር

ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ። በሚገባ ስለምታውቀው ምናልባት እንዲታቀብ ልትነግረው ትችላለህ።

ወደ አዲሲኒያ መንዝ በማንም የማይታወቅበት ሜትር ዣረሚ፣ ወደ ማህበረሰቡ ሰፈርና ወደ ከተማው በነፃ መመላለስ አብዝቷል። ምንም እንኳ እርሱ ራሱ ማንንም ባያክምም ሕመምተኞችን መጥራት ጀምሯል። የፖንሴን ደንበኞችም በቀድሞው ትዕዛዝ መሠረት ትኩስ መድሃኒቶች እንዲሰጣቸው ስለሚለምኑ፣ ፕሮቴስታንቱ፣ ጉንፋን ለሚያስቃያቸውም በስኳር እንዲጣፍጡ የተደረጉ እንክብሎችንና የሆድ ድርቀት ሰሚያስቸግራቸው የካሎሜል መድሃኒት በመስጠት ሥራ ተጠምዶ ነበር። ስጊዜውም ቢሆን በሰላም ሰመሰንበት የሚፈልግ በሚመስለው በሙራድም ላይ ዓይኑን እንደጣለ ነው።

ሜትር ዣረሚ በሰከተኛው ቀን ሲመለስ አብሮት እንዲሆን ጆን ባፕቲስት ጠየቀው። ውስጣዊ የልብ ጉዳዮች በሚሆኑ ነገሮች ላይ ጓደኛው ቁጥብ መሆኑን ስለሚያውቅ፣ ሁኔታውን በማለሳለስ አነሣበት። ሕመሙ መጠነኛ ሃዘን ቢያሣድርበትም፣ ፖንሴ ያለፈውን የአብሮነት ቆይታቸውን በትዝታ ቅላፄ ጀመረው። አብረው ተንዘዋል። ይህ ሁሉ ሆኖ ስለሜትር ዣረሚ ሕይወት ጆን ባፕቲስት የማያውቃቸው ብዙ ነገሮች አሉት።

«አንድ ጊዜ ትዳር ይዘህ እንደነበረ ነግረኸኝ ነበር?» በማለት በትውስታ በሚወያዩበት ዝርዝር ጉዳይ ላይ አግረ መንገዱን ጠየቀው።

«አምን» አለ የፖሊስ መኮንን የነበረው ሰው እንደ መተከዝ ብሎ

«ታዲያ እስከአሁን በስማንያህ እንዳለህ ነህ?»

«ይሆናል»

«ምን? አታውቅም ማለት ነው?»

ፕሮቴስታንቱ እርግጠኛ መሆንን አልወደደም። ጆን ባፕቲስት ደግሞ ጮተጮተው፡

«ያው፣ ያው ነው። በስማንያ ስለመሆንና ስለርሱም አለማወቅን በተመለከተ አስገራሚ ነገር አለ»

«አ፣ አውቃለሁ፣ ግን እኮ ሕይወት . . .»

«በል፣ በል፣ እስቲ እንዴት እንደሆነ ንገረኝ። ምናልባት እጅግ ስለምፈልገው፣ ሕመሜን ያረሣሣኝ ይሆናል።»

«ጉዳዩ በጣም ቀላል ነው። ነገር ግን ሊያስደስትህ የሚችል ነገር በውስጡ የምታገኝበት አይመስለኝም። ከዚህ በፊት እንደነገርኩህ አባቴ ከዩዜሽ ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኝ ቦታ ቀጥቃጭ ነበር። የቤተሰባችን ምንፖ ከኢጣሊያ ነው። ባለፈው ምዕት ዓመት አንድ ጊዜ ቅድመ አያቶቼ ፕሮቴስታንቶች ሆኑ። አስራ ስምንት ዓመት አስኪሆነኝ ድረስ ስለዚህ ጉዳይ ምንም አስተውሎት አልነበረኝም። ምክንያቱም በዙሪያችን በብዛት የሚኖሩት ፕሮቴስታንቶች ብቻ ነበሩ። የአባቴን ሙያ አያወቅሁ ስመጣ፣ እርሱም በዚያ ዘርፍ እንድቀጥል ፅቅድ ነበረው። በሃያ አምስት ዓመቴ እንዲት የአካባቢውን ልጃገረድ አገባሁ። ስሟ ማሪን ይባል ነበር። እነዚያ ዘመናት እንዴት ያሉ እንደነበሩ ብነግርህ ልትገምት እንኳ አትችልም። ይህ ሁሉ ከሃያ አምስት ዓመት በፊት የሆነ ነው። ምንም እንኳ ድሆች ቢሆኑም በአገሬ የነበሩት ሰዎች በጣም ይተሣሰቡ ነበር። እርስ በርሣቸው ይረዳዳሉ፣ በትንሽ ሰበብ ድንቅ በዓል ያከብራሉ። ፕሮስታንቶች ይተባበሩ ነበር። ምናልባት በቁጥራቸው ብዙ ስላልነበሩ መሰባሰባቸው የቡድን አቅማቸውን ስለሚያረጋግጥላቸው ይሆናል። ማሪን እና እኔ በተጋባንበት ዕለት ጧት ከቤተክርስቲያኑ ውጭ መጠነኛ የሕዝብ ክምችት ነበር። የወይን ጠጅ ነበረ። የቫዮሊን ተጫዋቾችም ነበሩ። ከዚያም አንድ ሣምንት ቆይቶ፣ ያሰማጋነን ልክ ከአንድ ሣምንት በኋላ ንጉሡ የናንቴስን አዋጅ ሠረዙ። ይህ ሁኔታ ፕሮቴስታንቶች አምነታቸውን በፈረንሣይ ውስጥ በቃለ ምህላ እንዲያረጋግጡ የሚያስገድድ ነገር ነበር። እጅግ የከፋ ነገር እየመጣ መሆኑን ሁላችንም አወቅን። የንጉሡ የጦር ሚኒስቴር የነበረው ዩቨይስ፣ ፈረሠኛ ወታደሮቹ በዚህ አካባቢ እንዲሰፍሩ ይልካል። በዚያን ሰሞን የኖ እምነት ተከታዮች ስብሰባ ስለነበራቸው፣ ከሣምንት በፊት በኖ ሠርግ ላይ ከተገኘው ሕዝብ የበለጠ ቁጥር ያለው ሰው ነበር። የቤተሰቦች መሪዎች የሆኑ ሁሉ ከበግ ቆዳ የተሠሩ ኮቶቻቸውን ሰብሰው ትልልቅ ጥቋቁር ባርኔጣዎቻቸውን አድርገውና መፅሐፍ ቅዱሶቻቸውን ይዘው ተገኝተው ነበር። እነርሱም ሁኔታው የከፋ አቅጣጫ ከመያዙ በፊት ዕድሜአቸው በሃያና በሠላሣ አምስት መካከል ያሉ ወጣቶች ከቦታው ዞር ብለው እንዲቆዩ ይወስናሉ።

«አንተም ከጋብቻህ አንድ ሣምንት በኋላ ቦታውን ስቀቅህ?»

«በትክክል ከዘጠኝ ቀን በኋላ ነው። ውሣኔው የተላለፈው በቅሬታ አልነበረም። ማህበረሰቡ ደካሞችን ለመከላከል ሣይፈልግ፣ ተዋጊ ሃይሎቻችንን ብቻ ከጠላት ራቅ ለማድረግ ነበር የፈለገው። ሴቶችን፣ ሕፃናትንና ሽማግሌዎችን ባሉበት ተውናቸው። ወጣቶችንና፣ የመዋጋት አቅም የነበራቸውን ብቻ ከጉዳቱ አቅጣጫ እንዲወጡ ተደረገ። የሆነው ሁሉ እንዲህ ነበር። እኔም ተራሮችንና የካውስከስን ሸለቆዎች አቋርጬ በየመንገዱ ላይ እየተደበቅሁ አከይቴይን ደረስኩ። ከዚያም በአንድ አሣ አጥማጅ ጀልባ ላይ ሥራ አገኘሁ። ከዚያ በኋላ በዊሊያም ስር ሆኖ ጠንካራ ይዞታ ወደነበረው የተባበሩት ግዛቶች አቀናሁ። በዊሊያም ሠራዊት ውስጥ ሆኜ እንግሊዝ ውስጥ ተዋጋሁ። ከዚያም ወደ ቅዱስ የሮማ ንጉሠ ነገስት ግዛት ተመልሼ መጣሁ። ካንተም ጋር ቬነስ ውስጥ የፖሊስ መኮንን ሆኜ እያለሁ ተገናኘን።

«ባለቤትህስ?»

«ስለርሷ ዕጣ ፈንታ ምንም የማውቀው ነገር የለም» አለ ፕሮቴስታንቱ ዐይኖቹን ስብር።

«ታፈቅራት ነበር?»

«ሚስቱ እኮ ነች»

«ያው ነው!» አለ ፖንሴ። «ዜጠኝ ቀናት!»

«ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት የተገባ ቃል ኪዳን እስከዘለዓለም ያስርሃል»

«ሞታ ቢሆንስ ምን ይሆናል?»

«ያን ጊዜማ ነፃ እሆናለሁ»

«እንዲያው የሚገፋፋህ ነገር አጋጥሞህ አታውቅም»

«በርግጥ የሚገፋፋ ነገር ገጥሞኝ ነበር» አለ ሜትር ዠረሚ ጭንቅላቱን በመነቅነቅ። «እንደምታውቀው የሥጋ ፈቃድ ያሸንፈኛል። ነገር ግን ሚስት ማግባት ሌላ ጉዳይ ይሆንብኛል። በዚህም ላይ ሰንሰሃ የሚሆን ተገቢው ተቋም የለንም። በዚህ ሣቢያ ይህን ጉዳይ በተመለከተ መሃላዬን አላፈረስኩም»

«ጋርድ ውስጥ ቀበሌህ ማን ይባል ነበር?»

«ሶው ቢይራን»

ከዚህ በኋላ ስለዚህ ጉዳይ አላወሩም። በዚያን ዕለት ምሽት ፖንሴ ለአሊስ ደብዳቤ የፈላት። በደብዳቤውም ውስጥ ሚትር ዠረሚ ነፃ እንዳልሆነና በሆነ ዕድል ፈረንሣይ መድረስ ቢችል፣ ስለጉዳዩ እንደሚያስብበት ገለፆላት ስለዚህ ነገር ለፍራንቾይዝ ምንም እንዳትላት አሳሰባት።

የራሳቸውን ምርመራ ካደረጉ በኋላ በአራተኛው ቀን ላይ አባ ፕላንቴይን ወደ ቆንስላው ሄዱ።

«ከበር ሆይ፣ ዛሬ ጠዋት ክቁስጥንጢንያ በጣም አስቸኳይ ዜና ተቀበልኩ» አሉ ጀስቲቱ ይበልጥ የወታደር በሚመስል ቅላፄ።

ሙሴ ዴ ማይሌ ጆሮዎቹን አቆመ።

«ከአባ ቬርሣው ጋር እንደሚተዋወቁ አምናለሁ» ሲሉ ቁሱ ቀጠሉ።

«ባለፈው ዓመት ካይሮ ነበሩ»

«አዎን፣ ከመርከባቸው መሠባበርና ሌላም ሌላም ብዙ መጥፎ ዕድሎች በኋላ»

«በሚገባ አስታውሳለሁ»

«እንግዲያውማ፣ የአቢሲኒያን ተልዕኮ በሚመለከት፣ የንጉሡን ፍላጐት አርስዎ እንዲያውቁት የማድረጉ ሃላፊነት የርሣቸው እንደነበረም ያስታውሳሉ ማለት ነው»

«በርግጥ»

«የዚያን የኤምባሲ መመሰስ እንዲያውቁት ለማድረግ ጽፈላቸው ነበር»

«በመጀመሪያ የተጠቀሙት ቃል ትክክል ነበር። ማለቱ መልዕክተኛ ነበር እንጂ፣ ኤምባሲ አልነበረም»

«እንደፈለጉት ይበሉት፣ይህ ለውጥ አያመጣም። እኔ ደብዳቤዬን በአስቸኳይ መልዕክት የላክሁት አሁን በንጉሡ መልዕክተኛ ዕጅ የሚገኙትን ንብረቶች እንዲያደርሱ ፓሻው ትዕዛዝ ከሰጠ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነበር። የዚህን ችግር በአጋጣሚ ስጠቅስ፣ የቱርክ ባለሥልጣናትም የኢትዮጵያ አምባሳደር ወደ ቬርሣይለስ እንዳይጓዝ መቃወማቸውንም ገልጨላቸዋለሁ»

«ምን ግንኙነት አለው?» ሙሴ ማይሌ ፊቱ መገርጣት ጀመረ

«አባ ቬርሣው፣ ቁጣቸውን እንድገልፅላቸው ፅፈውልኛል። ምንም እንኳ እኔ በጣም በተለግለሰ ሁኔታ ጉዳዩን ብገልፅላቸውም፣ እርሣቸው ግን እያንዳንዷን ነጥብ ሲሰልቋት ነበር። እንደነፋልኝ ከሆነ፣ ፓሻው አሁን እንዳደረገው በዚህ ጉዳይ ላይ ጣልቃ የመግባት ምንም መብት የለውም። ከዚህም ባሻገር፣ የተከበሩ ሙራድንና የሰር ፖንሴን ወደ ፈረንሣይ መጓዝ መቃወም መብት የለውም። ወደ አቢሲኒያ የተደረገው የመጀመሪያው የተልዕኮ ጉዞ የተከናወነው በንጉሡ ፈቃድ ሲሆን፣ በዚሁ ፈቃድ እማኪይነት የአቢሲኒያው ንጉሥ መልስም፣ ለሱዌስ አሥራ አራተኛ ሊደርሣቸው ይገባል»

ቆንሲሉ በንዴት ሲዘር፣ ጥቅል ፀጉሩ አንገቱ ላይ ወደቀ።

«ስለዚህም» አሉ ጀስቂቱ፣ ልክ ውሣኔ የሚያሰሙ በሚመስል አነጋገር « አባ ቬርሣው ይህን ጉዳይ በተመለከተ እያንዳንዱን ዝርዝር ጉዳይ እንድገልፅላቸው ሲጠይቁኝ ይህን በተመለከተ ተቃውሣቸውን ለሙሴ ፈሪኦል በማስታወሻ ለመፃፍ አስበዋል። ሙሴ ፈሪኦልን እንደማስበው . . . »

«እምን፣ አምን . . . በኦቶማን ዙፋን የፈረንሣይ አምባሣደር ናቸው»

በምሥራቅ ሜዲተራኒያን ዙሪያ ያሉት ቆንስላዎች ሁሉ ሪፖርት የሚያደርጉት ለሙሴ ፈሪኦል ስለሆነ፣ ሙሴ ፈሪኦል፣ የሙሴ ዴ ማይሌ የቅርብ አለቃው ነው።

«የዚህ ማስታወሻ አብይ ጉዳይ ምን ሊሆን ይችላል?» ሲል ቆንሲሉ ጠየቀ።

«የአባ ቬርሣው ታላቅ ተፅዕኖ ያለበት አምባሣደር፣ ይህን ጉዳይ የያዘውን ሱልጣን አስቀድሞ ያሣውቃል ብዬ አምናለሁ። ይህን በመሣሰሉ ጉዳዮች ከፓሻዎች አንዱ ከሱልጣኑ በላይ ከተራመደ፣ ታላቁ ሲኖር ችግር ወደተፈጠረበት ቦታ ምርመራ እንዲያደርግ የቃዲዎች መልዕክተኛ በመላክ አስፈላጊውን ቅጣት ይወስናል። የቱርክ አገረ ገዥዎች፣ እንደ ጥንቱ የፐርሺያ ገዥዎች እንዲሰሩ አልተፈቀደላቸውም። እነዚህ ፓሻዎች ስልጣናቸውን አለአግባብ ከተጠቀሙበት በተገቢው መንገድ ይቀጣሉ»

መጭውን ጊዜ ከማንም ባላነስ አስቀድሞ መገንዘብ የሚችለው ሙሴ ዴ ማይሌ፣ እነዚህ እንደ ታላቅ የማዕበል ደመና የተነሩ የማሰጠንቀቂያ ቃላት በርቀት ላይ እንዳልሆኑ አውቋል።

«የለም፣ የለም፣ የለም፣ አባ ቬርሳው ምንም አይነት ችግር ውስጥ መግባት የለባቸውም» አለ

«ምን? እና ከምዕተ ዓመት በላይ አስተሣስረውን የቆዩትን ስምምነቶች፣ ቱርኮች በእግራቸው ሥር ጥለው እንዲረጋግጡት ሊፈቅዱ ነው። ይህን ከተቀበልንማ ስምምነቱ ምንም ማለት አይደለም። በዚህም፣ በዚህ አገር የሚገኙ ክርስቲያኖች እጅግ የከፋ ደም አፋሳሽ የመከራ አይነት ይቀበላሉ ማለት ነው»

«ልክ ነዎት አባቴ፣ ቢሆንም ይህ ተራ ነገር ስለሆነ መፍትሄው እዚሁ መገኘት ይኖርበታል። ቁስጥንጢንያን እዚህ ውስጥ ባንጨምራት?»

«ወይኔ፣ ተከናወነ እኮ። በተሻለ መልኩ ባስረዳ፣ ፓሻው ከሃይል በስተቀር ሌላ ነገር የማይረዳ ይመስላል።»

«ደህና አድርገው አያውቁትም»

«ከዚህ በተለየ መንገድ ላውቀው አልሻም»

«በርግጥ ቱርካዊ ነው፣ በዚህም ላይ ወታደር ነው። ፀበኛ አይነት ሰው ነው። አንዳንዴ ነክ ያደርገዋል። ቢሆንም ምክንያታዊ ነገሮችን ለመስማት ፈቃደኛ ነው»

«መልካም። እንዲያ ከሆነ ምክንያታዊ ነገሮችን ከሱልጣኑ ለመስማት ፈቃደኛ ይሆናል።»

«ይስሙ፣ ከርሱ ጋር ስምምነት ላይ ለመድረስ፣ እኔ መከራ እንዳደርግ ይፍቀዱልኝ። ለአባ ቬርሣውም ፈጥነው አይፃፉላቸው። ለፓሻው ለራሱ የተቃውሞ አቤቱታዬን አቀርባለሁ» አለ ከመቀመጫው እየተነሣና እየቆመ።

«እንዲያ ከሆነ ሁለታችንም በጋራ እናነጋግረው»

«አብረን ነ»

«አምን፣ ምክንያቱም የተጐጂውን ወገን በአንድ በሆነ ስሜት የምወክለው እኔ ነ
ተልዕኮው በኖ የሃይማኖት ማህበር ላይ የተጣለ ሃላፊነትና እምነት ነበር። እናም ይህ ቱርኮ
ይህን ተልዕኮና ሃላፊነት እንዳንወጣው እንቅፋት እየሆነብን ነው»

«ሆኖም ጠንካራ መስለም መሆኑን ያውቁ የኔ። የማያስደስተንን ነገር ለመፍቶ
ብቻዬን ስሆን ወይም ከርስም ጋር ስሆን በተመሣሣይ ሁኔታ አያየንም»

«እንዲህ ከሆነ ከሱልጣኑ ጋር በቀጥታ እንነጋገር። ቢያንስ እርሱ በሁሰታችንም ሥ
መጥፎ ስሜት የለውም። ለማንኛውም ደብዳቤዬ ዝግጁ ነው። የሚጐድለው ነገር ቢና
ዝርዝሩ ጉዳይ ነው። ይህን ደግሞ እርስም ያክሱበታል። ከዘገየም ነገ እልከዋለሁ»

ሙሴ ዴ ማይሌ ያልበው ጀመር። ከዚህ አጣብቂኝ የሚያመልጥበት መንገድ አልታደ
አለው። ልክ ሁለት አይነት የመሰቃያ ስልቶች ያፈጠጡበት ሰው ይመስል፣ ቀሰለ ያለ ስቃ
ይኖረዋል ብሎ የገመተውን መረጠ።

«እንግዲያው ይሁን። ፓሻውን እናነጋግረው»

«ይህን ከተስማማን ወደ ቆስጥንጢንያ የሚላከው ፖስታ ሊዘገይ ስለማይችል አሁኑ
መሄድ አለብን»

ቆንሲሉ በዚህ በመጨረሻው አማራጭ ሣጣብ ስለተስማማ፣ የከተማውን ጠባ
እንደሚያነጋግር መልዕክት ላከ። የተላከውም ዘበኛ ከግማሽ ሰዓት በኋላ ሳይዘገይ መደረ
ያለበት ከሆነ፣ የስብሰባ አባላት ይጠራሉ የሚል መልስ ይዞ መጣ። በዚሁ መሠረት፣ ሙ
ዴ ማይሌና አባ ፕላንቴይን እንደአስተርጓሚ ሙሴ ማቼን ይዘው፣ በቆንሲሉ ሠረገላ ወጡ
ጀስዊቱ፣ በግልፅ ላለማሣየት ቢችሉም፣ በክፍተኛ ጉጉት ውስጥ ነበሩ። ቆንሲሉ ደግሞ
እጅጌውን ነፋስ እያውለበለበበት በመስኮት ወደ ውጭ ይመለከታል።

ክፍተኛዎቹ መልዕክተኞች ወደ ስብሰባው ቦታ ከደረሱበት ቅፅበት ጀምሮ፣ አንዳች ከባደ
የሥራ ጉዳይ እንደተደቀነ ገመተ። ሥነስርዓታዊውን ሰላምታ በአጭሩ አከናውኖ፣ ቆንሲሉ
ይህን አስቸኳይ ጉብኝት የጠየቀበትን ምክንያት እንዲያብራራለት ጠየቀው።

በጣም ቅር እያለው፣ ጠበቅ ባለና የአስታራቂነት ቃና በተላበሰ፣ ነገር ግን የማመንታትና
የውሽት ዜማ በተቀላቀለበት ድምፅ «ጉዳዩ የሚከተሰው ነው። ከታላቅነትም ዘንድ የመጣሁት
ተቃውሞዬን ላቀርብ ነው»

መሃመት ቤይ መልስ አልሰጠም። አንዴ ጀስዊቱን፣ ቀጥሎም ቆንሲሉን ተመለከተ።
ከዲፕሎማቱ ጋር ባደረጉት ሕብረት ላይ ቅሬታ እየተማሰው እንደነበረ እያሰበ፣ በዚህ
ስምምነታቸው ላይ አንዳች አስቸጋሪ ውጤት መከሰቱን ገመተ። ሙሴ ማቼ ያስተረጉማል።
ቆንሲሉም ንግግሩን ቀጥሏል።

«በሁለቱ አገሮቻችን መካከል በተፈረመው ስምምነት መሠረት፣ እዚህ የሚገኙት
ክርስቲያኖች ሁሉ በፈረንሣይ ንጉሥ ጥበቃ ሥር ናቸው።»

ፓሻው አንደ አነር አይናቹን በዝግታ ክድንና ክፍት እደረጋቸው።

«በዚህም ምክንያት የፈረንሣይ ቆንሲል በቅድሚያ ሳያውቀው በፊት የአንድን ክርስቲያን
መኖሪያ ሊገቡበት አይችሉም፣ ከዚህም በላይ በሕግ በፈረንሣይ ንጉሥ ጥበቃ ሥር የሚገኝ
ሰው ወደ ፈረንሣይ ግዛት የሚያደርገውን ጉዞና ስዚህም ባለመብት የሆነውን ሰው እንቅስቃሴ
ሊያግዱ አይችሉም»

ይህን ተናግሮ ልክ ያቀጣጠለው ባልቦላ ደማሚቱን ሲያነድደው ላለማየት እንደፈለገ ሰው
ሙሴ ማይሌ ዓይኖቹን ጨፈናቸው።

«ማንን በሚመለከት ነው የሚናገሩት?» አለ ፓሻው በመጨረሻ በቁጣ።

«በማህበረሰቡ ውስጥ ካለ ከአንድ ፈረንሣይ ሐኪም ጋር ከአቢሲኒያ ስለመጣው
አርመናዊ»

«እኒህ ከዚህ ሰው ጋር ምን ጉዳይ አሳቸው?» ሲል ፓሻው ወደ አባ ፕላንቴይን
እያመለከተ ጠየቀ።

ቆንሲሉ በሳብ ተጠመቀ። እንዲያውም ሀሲናውን የሣተም መስለው። በሰፊው ክፍል
መሃል ላይ ቆሞ፣ ግድግዳዎቹ በአደገኛ ሁኔታ በዙሪያው የሚሾሩ መሰለው።

«ምንም፣ አባ ፕላንቱይን በቅርቡ ወደ ቁስጥንጢንያ ይሄዳሉ። የምንነጋገርበት ጉዳ ውጤቱ አስደሣች የማይሆን ከሆነ የዚህን ስብሰባ ጉዳይ ለአምባሣደሩ ይገልፃሉ» አለ።

አቋሙን ጥብቅ ለማድረግ በሚመስል ሁኔታ፣ መሃመት ቤይ በጉን በኩል ባለው መከ ላይ እጆቹን አሣረፋቸው።

«የናንተን የፈረንሣውያን ሁኔታ መረዳት አልቻልኩም። ምንም ስለሚያውቁት ነገር ምን ፍለጋ ይመጣሉ? ይቃወማሉ? ስለምን? እነዚያን ደብዳቤዎች የወሰድኳቸው እርስ፣ ስለጠየቁኝ ነኝ። ከዚያም ሰርሰም ሰጠሁም። እርመናዊውን በተመለከተ እርሱ ነፃ ነው ወደፈለጉበት ቦታ ሊወስዱት ይችላሉ። እርሱ ክርስቲያን ስለሆነ ዕጣ ፈንታው የሚያገባ አይደለም። ይሁንና ሰርሰም ማስጠንቀቂያ አለኝ። ቁስጥንጢኒያ ውስጥ የምትናገሩት ታሪ፣ ካላችሁ የራሴን አንድ ወይም ሁለት ቃላት ልጥልላችሁ እችላለሁ። ከተማዋ ልታስተዳድራቸው ከምትችላቸው ጥቂት ካቶሊኮች በላይ፣ በአሁኑ ጊዜ እዚህ የሚገኙት ፈረንሳውያን ሰባኪዎች ቁጥራቸው በጣም ብዙ ሲሆን፣ በጣም በከፍተኛ ሁኔታ የሚንቀሣቀሰ ናቸው። ጊዜያቸውንም ሴራ ሲጐነጉኑ እንደሚያሣልፉ እናውቃለን። ሱልጣኑም ከነዚህ አንዳንዶቹን በዘርዝር ለመስማት በእርግጥ ይፈልጋሉ። ማብራሪያዬ አጥጋቢ ነው?»

«ታላቅነትዎ መሉ በሙሉ እንድንቀበል አድርጐናል» ሲል ሙሴ ዴ ማይሌ ወደፊት ጐንበስ የማለቱን ግዴታ ሳይፈፅም ሞንቅላቱን በጨዋ ሁኔታ ዘንበል አደረገ።

ከዚያም ወጥተው ሄዱ።

ሲመሰሱ በመንገዱ ላይ ይሰማ ከነበረው ሚጫታና ግርግር ጋር ሲነፃፀር፣ የሠረገላው ውስጥ ጉብ በከባድ ዝምታ የተዋጠ ነበረ። ቆንሲሉ፣ በዚህች አነስተኛ የወንጀል ሕብረታቸው የተነሣ እስከ መጨረሻው ድረስ ቀልዳቸውን እንደሚገፉበትና፣ ሁሉንም ተጠያቂነት ፓሻው ይቀበላል የሚል፣ በተሰፋ ላይ ተቃራኒ ተሰፋ ነበረው። ይህ ደግሞ አደጋ ያሰበት ስልት ስለነበረ ከሸፈ። አባ ፕላንቱይን በበኩላቸው የምርመራቸው ውጤት መረጋጠን አይተዋል። ሁሉንም ነገር በሃሰት የፈጠረው ዲፐሎማቱ ነበር። ቁሱ፣ በተቻላቸው ሁሉ ቁጡ ሆነው ሰመታየት ሞክሩ። ውስጣቸው ግን በደስታ ይፈላ ነበር። ምክንያቱም፣ ከእንግዲህ በኋላ ሙሴ ዴ ማይሌ ሊከሰክላቸው የሚችለው አንድም ነገር አይኖረም። ድላቸውን ያገኙት፣

ፓሻው በራሱ ቀስት ላይ ባስወነጨፈው ተኩስ መሆኑ ርግጥ ነው። ይህ እንኳ አርሣቸውን አላሳሰባቸውም። ቆንስላው ግቢ ሲደርሱ፣ ሙሴ ዴ ማይሌ የቢሮውን በር በነርሱ ላይ ዘግቶ ተቀመጠ። ከዚያም ቁሱ ተመልሰው መሄዳቸውን ለመጠየቅ ሳይጨነቅ፣ ሰው ሰራሹን ፀጉሩን አወለቀው።

«ስለጉበኝቱ ማብራሪያ ልሰጥህ ግድ ይሆንብኛል። በእውነቱ፣ የተከበሩ ሙራድን ጉዞ በመቃወም የተነሣብን፣ ፓሻው ሳይሆን፣ የኛው ሚኒስትር ሙሴ ዴ ፖንቻርትሬይን ነው። ስለዚህ ጉዳይ የማያወላውል ማረጋገጫ እዚሁ አለኝ»

ጠረጴዛውን በእመልካች ጣታቸው ጠበጠቡ።

«የፖለቲካ ምክንያቶች ይሆኑ ብዬ አስባለሁ?» አሉ ጀስዊቱ።

«የለም፣ የለም፣ የለም!» በማለት ተማሪው የሚፈፅመውን ተመሣሣይ ስህተት ለማረም ባለማቋረጥ እንደሚያስተካክል መምህር ከፍ ባለ ድምፅ ቆንሲሉ ተናገረ። «ይህ የፖለቲካ ጥያቄ ጉዳይ ሣይሆን ከሕይወት ተሞክሮ የሚገኝ የጥሩ ስሜት ጉዳይ ነው። ሌላው ቀርቶ ተገቢነት የሚኖረው ባህርይ ጉዳይ ነው፣ አባቴ። ይህን ሙራድ የሚባል ሰው ደህና አድርገው አይተውታል? ራሱን እንደ መጨረሻው ዝቅተኛ ወዛደር የሚያደርግ ነው። የሴቶችን አይን አፋርነት ይሣደባል። በገበታ ላይ ይሠክራል። እጆቹን በመጋረጃ ጨርቆች ላይ የሚጠርግ ነው . . . እስቲ በእውነት ክልብህ ይንገሩኝ፣ ይህን አይነት ሰው ለአፍታ እንኳ ቬርሣይለስ ውስጥ እንዲሆን ያስቡታል? ከንጉሡ ፊት ሲቀርብ ሊታይዎት ይችላል?»

ከዘላየቸው ወዳለው የቀለም ቅብ ስዕል አመለከተ።

«በዓለማችን ላይ እጅግ የጠራ የቤተመንግስት ንጉስ፣ ማንም ከዚህ የበለጠ አሣማኝ ሊሆን አይችልም። የሚኒስትሩ መመሪያ ከዚህ የበለጠ ግልፅ ሊሆን አይችልም። ከማን ጋር እንደሚሰሩ አውቀው፣ ሁኔታው ተገቢ ስለመሆኑ የራስዎን ፍርድ ይስጡ። እኔ ግን ልንገርዎ፣ የሚሆን አይደለም»

«ስለዚህ ጥያቄ የሆነው፣ ርዕስ የሆነው ሰው ጉዳይ ነው። በመሠረተ ሃሣቡ ላይ እርስዎም አይቃወሙም።»

«የለም»

«ስዚያ ፖንሴና እኔ ወደ ቬርሣይለስ እንሄዳለን።»

ቆንሲሉ ለስፍታ ያህል አባ ፕላንቱይን በመመርመር አሰበ። ጀስዊቶች በዚህ ጉዳይ ላ በድጋሜ መሣተፋቸው አላስደሰተውም። ንጉሡ፣ የራሱን የጅማሮ ሣጣ እንዲደራደርበ ለማድረግ ተፅዕኗቸውን ሊያሳድሩበት ይችላሉ። ይሁንና ይህ ከሁለት መጥፎ ነገሮች አነስተ ው ነው። ጀስዊቶች፣ ቁስጥንጢኒያ ውስጥ የሰዎችን አመለካከት እንዲያስቆጡ ቢፈቀድላቸ አስፈሪ አሉባልታ ይከተል ነበር። ከዚህም ሌላ፣ ቆንሲሉም፣ ጀስዊቱንና ፖንሴ ከፈረንሣ ከመመለሳቸው በፊት የራሱን የንግድ ድርጅት የመፍጠር ዕድል ይኖረዋል።

«ሃሣቡ እጅግ በጣም ጥሩ ነው» አለ ሙሴ ዴ ማይሴ በመጨረሻ። «ፍሌሀውት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያጅብዎታል» ።

«አርስዎ በፓሻው ላይ ያለዎትን ተፅዕኖ ተጠቅመው ሦስቱ አቢሲኒያውያን ከኛ ጋ መጓዛቸውን ያረጋግጡልናል»

«ይህን ለማድረግ ቃል እገባለሁ»

«አንግዲያውስ ከፈቀዱ፣ ይህንን ሁሉ አሠኑት በጽሁፍ እናስፍረው። በዚህም፣ ቬርሣይለስ እኛን መጠበቅዋን ትረዳለች። ነገ ወደ ቁስጥንጢንያ የሚጉዛሣቀለው መርከብ ይህን መልዕክት እስክ አሌክሣንደሪያ ሊያደርሰው ይችላል። ከዚያም በቤተመንግስቱ የጦር መርከ ተሣፍሮ በአሥራ ሦስት ማርሴይ ይደርሣል። በሚቀጥለው ወር መጀመሪያ ላይ ፖሪስ ይገባል።»

«በትክክል። ነገር ግን፣ ይህ ሁሉ ሲሆን ሁሉም ነገር ከወዲሁ መጠናቀቁን በመግለፅ አባ ቬርሣው በበኩላቸው ምንም እንዳይደክሙ የሚያስረዳ ደብዳቤ ይፃፉላቸው»

«በአንድ ሰዓት ውስጥ እፅፋለሁ፣ ክቡር ሆይ»

ይህ አንድ ስምምነት ይመስላል። ቢያንስ ይህ ደፕሎማሲ ነው። ቆንሲሉ፣ በመጨረሻ ላይ ወደ እውኑ የመመለስ ስሜት ነበረው። ይህን ከመሰለ ጠንካራ የንግድ ሕይወት ሽታናቸ ይዞት ከሄደው የክርክር ጉዳይ መንቃት ጀመረ። ከመሸነፉ በስተቀር ዳግም በሰላም መተንፈስ ጀመረ።

10

ሰዎች የወደፊቱን ዕጣ ፈንታቸውን ለማወቅ የከብብ ቆጠራ ማድረጋቸው የሚያስደንቅ ጉዳይ አይደለም። የሰማይ ክዋክብት፣ ከሰው ልጅ ጉዳይ ጋር በቅርበት የሚመሣሰል፣ ያልታሰበና የተስተካከለ እንቅስቃሴ አላቸው። ቆንሲሉ አንድ ጊዜ ከተጋሰጠ በኋላ፣ ሁሉም ነገር ተሰወጠ። በዚያን ዕለት ምሽትም፣ ፔጋሰስ የሚባለው ከከብ ወደ አንድ ወገን ሲሰምጥና አሪዮን የተባለውን ከከብ ደግሞ ፕሌይዴስና ሌሎች ከዋክብቶች ሁሉ ተከትለውት በሌላው ወገን ከፍ ሲሉ ታየ።

ጆን ባፕቲስት፣ ካልታመመበት ህመሙ በአጭር ጊዜ ውስጥ ዳነ። ከአራት ቀናት በኋላ ይጀመራል ለተባለው የንዞ እንቅስቃሴው ዝግጅት በማድረግ ስራ ላይም ተጠመደ። አስፈላጊ የነበሩ ዝግጅቶች በሙሉ በፍጥነት ተከናወኑ። ሙራድም፣ በቬኔስያውያኑ ቤት ብቻውን ይሰነብታል። ቆንሲሉም፣ መልዕክተኞቹ እስኪመለሱ ድረስ ቀለል ያሉ ወጭዎችን ይሸፍንለታል። ከዚያ በኋላ፣ ከፈረንሣይ ንጉሥ መልስ እንደመጣ ተደርጐ፣ ሙራድ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ ይነገረዋል።

ወደ ቬርሣይለስ በሚሄዱ ገፀበረከቶች ላይ አጠቃላይ ምዝገባ ተደረገ። ከጉንደር በተነሱበት ጊዜ፣ ተጓጉቹ፣ ሃብታሞችና ከባድ ሸክም ያላቸው መስሏቸው ነበር። ይሁን እንጂ የጉዞው ወጭ፣ ኩቴርኮች የዘረፋ ታክስና የአንዳንድ ቁሣቁሶችም መበላሸት ንብረቱን በእጅጉ ቀንሶታል። ፖንሴና ሽሪኩ፣ ንጉሠ ነገስቱ ከሰጧቸው እንቁና አልማዞች ሌላ እያንዳንዳቸው አንዳንድ ከረጢት የወርቅ ዱቄት ነበራቸው። ወደ ፈረንሣይ በሚደረገው ጉዞ መሣካት የተጠመደው ፖንሴ፣ለንጉሡ የሚቀርበው ገፀ በረከት በቂ የማይሆን ቢሆን በሚል የራሱን ከረጢት ሊጨምርበት ዳድቶ ነበር። የሙራድ ሻንጣ በጣም ትንሽ ነበረች። በርግጥ ሦስት አቢሲኒያውያን አሉ። የሙስሊሞቹን በንቃት መጠበቅ በሚገባ ስለሚያውቅ እነዚህን አቢሲኒያውያን ይዞ መንገዝ የሚለው ሣጣ ፖንሴን አላስደሰተውም። ጀስዊቱ ግን፣ ቀሪዎቹ ገፀ በከረቶች የሚያሣዝኑና ተመጣጣኝ ስላልሆኑ በሚል ምንም ክርክር ላይደረግበት ቁርጥ ያለ አቋም ይዘው ነበር። ገፀ በረከቶቹም አራት ፖውንድ የጥርኝ ዝባድ፣ በተሰጣቸው ምክር በኪሣራ ለትምባሆ የለወጡት መጥፎ ሽታ ተቀርቅሧል። ከዚህም ሌላ በወርቁ ዘቦ የተጠለፉ የሃር ሻሾች አሉ። ሻሾቹ፣ ጉንደር ውስጥ ከነጭ ካዊርት ጨርቅ አንዣር ቢታዩ፣ አለም አቀፋዊ

አድናቆትን ያገኙ ነበር። ካይሮ ውስጥ፣ ይበልጥ ደግሞ ቬርሣይለስ ውስጥ፣ በአውሮፖውያን ዕይታ ከአስቀያሚ ቁራጭ ጨርቅ የሚበልጡ አይደሉም። ሲነሱ ይዘዋቸው የነበሩት እንስሳት፣ ፈረሶችና ዝሆኖች በመንገድ ላይ ሞተው አልቀዋል። የቀሪቸው ነገር ቢኖር የደረቀውን የዝሆን ቆዳ የያዘው ትልቅ የእንጨት ሣጥን ብቻ ነው። እነዚህ ነገሮች ይህና ተደርገው መጫናቸውን ፖንሴና ሙራድ አረጋገጡ። በይበልጥም ሙራድ፣ እጁን ልቡ ላይ አሳርፎ ልክ ነው አሉ። የደከሙ ፈረሶች እየገዛ የሚያርደው ሰውዬ፣ የዝሆኑን ሥጋ ቅርጫ ጉትቶ ሲወስደው፣ ሙራድ የእንሰላውን ጀሮ ምን ሊያደርገው እንዳሰበ ስላወቀ በጨው ውሃ ውስጥ ዘፈዘፈው። ከዚህም በኋላ፣ ከተቀመጠበት የርብራብ ሣጥን ውስጥ ሊወጡ በቀላሉ እጥፍጥፍ የሚሉ ለስላሶችና ልክ በሕይወት ባለው አውሬ ላይ ተጣብቀው ያሉ ይመስላሉ።

አሣፋሪ ማብራሪያና፣ በመደጋገማቸው የሚያዋርዱ ይቅርታዎችን በመጠየቅ የጋለ ቃለምልልስ ከፖሻው ጋር በግል ካደረገ በኋላ፣ ቆንሲሉ፣ አቢሲኒያውያኑ ወደ ፈረንሣይ ለመሄድ እንዲችሉ አስፈላጊውን ሥልጣን እንዳገኘ ለአባ ፕላንቴይን ገለፀላቸው። ጥንቃቄ የሚያስፈልገው፣ የአሌክሣንደሪያ መፍቲዎች ስለዚህ ጉዳይ ምንም አለመስማታቸውን ማረጋገጥ ብቻ ነው። እነዚህ ሰዎች አክራሪዎች ስለሆኑ ማንኛውም አፍሪካዊ ወደ ክርስቲያን አገር የሚያደርገውን ጉዞ ይቃወማሉ።

የመሰነባበቻው ጊዜ ደረሰ። ሙሴ ዴ ማይሌ በፈገግታ ተሞልቶ መንገደኞቹን፣ ማለትም ፖንሴን፣ አባ ፕላንቴይን እና ቻንሰለር ፍሌሃውትን በቆንስላው ውስጥ አራት ጋበዛቸው። ጀን ባፕቲስት፣ ፍፁም ድኖ መጣ። ቆንሲሉ፣ በለሁኑ ጊዜ ከፖንሴ ጋር በጥሩ ሁኔታ ላይ ለመቆየት ጥንቃቄ በመውሰድ ላይ ነው። ምክንያቱም ከዚህ በኋላ በከፍተኛዎቹ ደረጃዎች ላይ ችግር ሊፈጥርበት ይችል ይሆናል። የእራት ግብዣው የሥራ ጉዳይ ያለበት ስለነበረ ሴቶችን አላካተተም። ሴቶቹ የተፈቀደላቸው ባለፈው ልዩ በዓል ጊዜ ጀን ባፕቲስት ባየው አነስተኛ የሙዚቃ ክፍል ውስጥ ለቡና ብቻ ነበር። ሙሴ ዴ ማይሌም ይሁን ባለቤቱ፣ በአንዲት በጣም አነስተኛ በሆነች ክፍል ውስጥ አምጥተዋቸው፣ እርስ በእርሣቸው በድንገት እንደሆነ በማስመሰል፣ አስር ጊዜ ሊተሻሹ፣ በሁለቱ ፍቅረኛሞች ልቦች ውስጥ የጫሩትን ሃሴትና ግራ መጋባት በሚመለከት ምንም ዓይነት ፍንጭ አላገኙም ነበር። በአባቷ አስገዳጅነት፣ ማዳሞዜል ዴ ማይሌ፣ በፒያኖው አጠገብ ተቀምጣ ጥቂት ጣዕመ ዜማዎችን ተጫወተች። የክር የሙዚቃ መሣሪያዎች ያላቸውን ሃይል ለማውጣት እንዲችሉ፣ እንደሚቃኙ ሁሉ፣ ልቦችም በሚገባ መቃኘት ይኖርባቸዋል። በዚያ ምሽት፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሚለያዩት ከሁለቱ

ወጣቶች ልቦች በስተቀር በዚያ ክፍል ውስጥ የነበሩት ብዙዎቹ አድማጮች ልቦቻቸው በሚገባ የተቃኙ አልነበሩም። አሲድ፣ የመዳብን ሠሃን አልፎ አልፎ በሰም ባልተሸፈነበት ቦታ ላይ ቅርፅ እንደሚያወጣበት ሁሉ፣ የፒያኖው ጣዕመ ዜማ በጀስዊቱና በሙሴ ዴ ማይሌ፣ ወይም ሰማዳመጥ ፍፁም ፈቃደኛ በነበረው በሙሴ ማቼና በግብዙ ፈሪ በፍሌሃውት፣ መካከል የነበረውን ወሬ አላስተጓጎሰባቸውም። ከዚህ ይልቅ ጣዕመ ዜማው በጥልቀት ዘልቆ የገባው በጨቅላዎቹ የአሲስና የጀን ባፕቲስት ልቦች ውስጥ ነበር። ምክንያቱም እጅግ ጣፋጭ የሆነውና የማይታየው የፍቅር ስቃይ በነርሱ ልቦች ውስጥ ካልሆነ በስተቀር በሌሎች ሊታሰብ የማይችል ነው።

ሁለቱም ስሜቶቻቸውን በዕናት ለመቆጣጠር ችለዋል። ነገር ግን የአርስ በርሣቸው የመፈላለግ ረሃብ እጅግ አደገኛ የሆነ ችልተኝነት እንዲፈፅሙ ሲገፋፋቸው ነበር።

ፖንሴ፣ ወደ ቤት ገና እንደተመለሰ፣ ፍራንቾይዝ፣ በከፍተኛ ጥድፊያ ስትመጣ አያት። የመጣችውም እንደባለፈው ጊዜ፣ አሲስ እክለ ለሊት ጥቂት እንዲለፈ በስትክሉቱ ስፍራ እንደምትጠብቀው የላክችለትን መልዕክት ይዛ ነው። ምሽቱ ጨረቃ ያለችበት ስለሆነ ሲታዩ ይችላሉ። ይህ ደግሞ አደጋውን ከባድ ያደርገዋል። ጀን ባፕቲስት፣ ሀሳቡን ሲቃወመው፣ ስለጨረቃዋ መኖር እንደሚያውቁ ፍራንቾይዝ አስረዳችው። ከዚህ በኋላ፣ ጀግንነት ምኑ ላይ ነው? ሲል ጀን ባፕቲስት አሰበ። ለደህንነታቸው ሲሉ ዕቅዳቸውን መሰረዝ፣ ወይም የድፍረትና የሀሴት ፍላጐታቸውን መምረጥ? እስክ አሁን ድረስ ፍቅራቸው በብዙ እንቅፋቶች የተሞላ ነው። ይህ ደግሞ ተገቢነት በሌለው ማነቆ፣ የማይለሸነት ወይም የስሜት ቀዝቃዛነት ተደርጐ ሲተረጐም ነበር። በርግጥ ጀን ባፕቲስት የሚችለው አንድ ነገር ነበረ። በቀጠሮው ቦታ፣ እንደሚገኝ መልስ ሰጥቷል።

በቀጠሮው ሰዓት፣ እርሱ በአደባባዩ ውስጥ ተደብቆ ሳለ በርቀት የሁለቱ ሴቶች ቅርጽ በጨረቃዋ ብርሃን ደምቆ ወደርሱ ሲጣደፉ ተመለከተ። በፍርሃርጉ የብረት በር ዘንድ ሲደርሱ፣ ሴላ የሰው ጥላ ከአንድ ወጥ ዛፍ ወደሌላው በድንገት ሽው ብሎ ሊያልፍ ጀን ባፕቲስት አስተዋለ። አሲስ ወደ ፍቅርኛዋ መጥታ ተጠመጠመችበት። ደረቱ ላይ ልጥፍ አድርጉ ይዟት፣ ዝም እንድትል አስጠነቀቃት። ዓይኖቹን፣ ሊንቀሳቀስ ወዳየውና ወደተሰወረበት ነገር አትጣጫ በጨለማው ውስጥ ላከቸው። ከዚያም፣ ያ ጥላ፣ በሁለት ዛፎች መካከል ወደ አትክለቱ ሥፍራ ተንሸራትቶ ሲገባ በድጋሚ ተመለከተው።

«የሚከታተሏችሁ ነበሩ» ሲል ጆን ባንቲስት ለአሊስ ሹክ አላት።

እነዚህ ቃላት በልቧ ውስጥ ሽብር ነዙባት። በበሩ አጠገብ ትጠባበቅ የነበረችው ፍራንቾይዝም፣ ያንን ጥላ ተመልክታዋለች። ከዚያም፣ ወደጥንዶቹ ስትቀርብ ጆን ባንቲስት ሲያስጠነቅቅ ሰማችው። ምናልባት ክፉ ነገር ቢያጋጥመኝ አክላከልበታለሁ በማለት አሰበ፣ ፖንሴ ክቤቱ ሲወጣ በቀበቶው ላይ ፖቤ ታጥቆ ነበር። የፖቤውን እጀታ በፍጥነት ይዞ፣ ያቀደውን፣ ለሁለቱ ሴቶች ነገራቸው።

«ሲከታተላችሁ የነበረውን ሰው ተጋፍጩ ማንነቱን አጋልጣለሁ። ሁሰታችሁም ወደ ቆንሰላው በፍጥነት ተመለሱ። ነገር ግን እንዳትታዩ እየተጠነቀቃችሁ እንጂ እየሮጣችሁ እንዳትሄዱ። ለመሆኑ የጓሮውን በር ቁልፍ ይዛችኋል?»

«አዎን» አለች ፍራንቾይዝ

«እንግዲያው በጓሮ በኩል ዞራችሁ ሂዱ። ከዚህ በበለጠ ዋናው ቁምነገር ልክ እቤት ከገባችሁ በኋላ፣ ሞልጥ ያለ እንቅልፍ የወሰዳችሁ ለማስመሰል ሞክሩ። ምናልባት ነገሮች. . .»

«ዚድ፣ ስለሌላው አትጨነቅ» አለች ፍራንቾይዝ

ጆን ባንቲስት፣ አሊስን በችኮላ ሳማት። የከንፈሮችዋን ጣዕም፣ ልስላሴያቸውን፣ በዓይኖችዋ ውሃዎች ውስጥ የነበሩትን ዕይታዎች በጥልቁ ማስታወሻው ውስጥ ጠብቆ ሊያቆያቸው እንዲችል አጥብቆ፣ ቀመሰቸው። ከነገ በኋላ ለሚቀጥሉት ረዥም ወራት ጠብቆ የሚያቆየው፣ ይህን ብቻ ነው። ከዚያም፣ ራሱን ከርስዋ ለይቶ ጨለማው በጣም ክባድ ወደነበረበት የአትክልት ሥፍራ አቅጣጫ ሮጠ። በፍርግርጉ በር ዞሮ በአንድ የእንጨት በር መግቢያ በኩል ዘለቀ። በዝግታ ወደ ሰፊው ጎዳና ጥግ በማምራት፣ በአንድ ነጠላ ዛፍ ጏላ ተደበቀ። የሁለቱ ሴቶች ብርማ ቅርጽ፣ ቆንሰላውን በምታዋስነው በትንሿ የአግር መንገድ ላይ ሊራራጥ በግልጽ ማየት ቻለ። የሚያሳድዳቸው ነገር ጥላ፣ መንገዱን አቋርጦ እንደገና በዛፎቹ ጀርባ ከተሰወረ በኋላ፣ ፖንሴ፣ ይህ ጥላ የፈረንሳውያንን የአሰባበስ ዘዴ የተከተለ፣ መካከለኛ ቁመት ያለውና ግልጽ ባይሆንም መሣሪያ ያልታጠቀ ወንድ ሰው መሆኑን ለመለየት ጊዜ አግኝቷል። ይህን ሰው ለመያዝ ከተደበቀበት መውጣት እንዳለበትም አውቋል። ለዚህ ደግሞ የተሻለው ዘዴ፣ ሰውዬው ላይ ከጏላው በኩል መድረስ ነው። ምክንያቱም የሰውዬው አትኩሮት በመሸሽ ላይ ወደሚገኙት ሴቶች ነው። ፖንሴ በዘኩሉ፣ በርሱና በፊት ለፊቱ ባሉት ሁለት ዛፎች መካከል ያለውን ርቀት በፍጥነት ሸፈነ። ወዲያውኑ ሰውዬው መንገዱን

ከማቋረጡ በፊት ተደብቆበት ከነበረው ዛፍ ሥር ደረሰ። ይህ ማለት ደግሞ ጆን ባንቲስት በትክክል ከሰውዬው ባሻገር በተቃራኒው አቅጣጫ፣ ሰውዬው አትኩሮ ከሚመለከትበት አኳያ ይሆናል።

ሰጥቂት ጊዜ ጠበቀና፣ እንጣጥ ብሎ ዘለሎ መንገዱን በማቋረጥ በጨለማው ውስጥ ሲንቀሳቀስ የነበረውን ቅርጽ አፈፍ አደረገው። ወዲያውኑ የሰውዬውን እንቅስቃሴ በመግታት ፖቤውን እንገቱ ሥር አስጠግቶ ያዘ። ሊነገር የሚችል ትግል አልተካሄደም። በጨለማው ውስጥ እንደተነካኩ ሁሰቱም መሬት ላይ ወድቀው ተንከባለሉ። ጆን ባንቲስት በቀላሉ የበላይነትን አገኘ። በእንፋሩ ባላንጣው ጉልበት ያልነበረው ወይም የፍልሚያ ችሎታ ያልነበረው ስለነበረ ፖቤው እንገቱ ስር እንደተጠጋ ወደብርሃኑ እየተሳቡተ በቀላሉ ተወሰደ።

«ድረሱልኝ፣ ድረሱልኝ፣ ጥበቃዎች፣ ጥቃት እየደረሰብኝ ነው»

በፖንሴ የይቅርታ ፈቃድ ስር የተያዘው ሰው በሀይል መጮኽ ጀመረ

«ማቼ!» አለ ጆን ባንቲስት

ማቼ ይበልጥ በሀይል ጮኸ። ቆንሰላው በርቀት ላይ ስላልሆነ፣ በመግቢያው በኩል የቅጭልጭልታ ድምጽ መሰማት ጀመረ። ይህ፣ ምናልባት የጥበቃ ሠራተኞች መሣሪያዎቻቸውን ሲወስዱ የተፈጠረ ድምጽ ይሆናል። በየመሰኮቶቹ ብርሃን ታየ። ሦስት ሰዎችም መንገዱ ላይ ወጡ። ማቼ አሁንም ይጮሃል። የመጀመሪያው ፖሽት በድንጋጤ ምክንያት እንደተፈጠረ ፖንሴ ያውቃል። የአሁኑ ፖሽት ግን፣ ሊያድኑት የመጡትን የጥበቃ ሰዎች እርዳታ ለመሣብና አጥቂው እንዲያዝለት ለማድረግ ነው። እየጮኸ እያለ፣ ጆን ባንቲስትን ተመለከተው። ፖቤው ጉረሮው ስር በመሆኑ ያለበት ሁኔታ የማያስተማምን ደረጃ ላይ ቢሆንም የፈዝ ሣትና የዝቅተኛነት ፈገግታ አሣየ።

በርግጥ አሁን የያዝከኝ አንተ እንደሆንክ ታስባለህ? ብሎ የሚናገረው መሠለው።

ሦጥበቃ ሠራተኞች በሩጫ እየተቃረቡ ነው። ጆን ባፕቲስት ምርኮኛውን ሰቅቆ አግሬ አውጭኝ አለ። ሦስቱ ተረኛ ዘቦች፣ ማቼ መሬት ላይ ተቀምጦ ጉረሮውን ሲያሻሽ ሲያገኙት፣ የአገራሞትና የመደነቅ ሕምምታ አሰሙ። እርሱ በበኩሉ፣ አጥቂውን እንዳይከታተሉ ትዕዛዝ ሰጣቸው።

የቀረው ለሊት እንደተለመደው በሰላም አለፈ። ይሁን እንጂ፣ እንቅልፍ በአይናቸው ሣይዞር ያደሩ ሦስት ሰዎች ነበሩ። ጆን ባንቲስት፣ በሰላምና በጊዜ አንዳችም ችግር ሳያጋጥማት መመለስ ችላ ፈጥናም አልጋዋ ውስጥ ገበታ ይሆንን እያለ እንደተጋደመ ነቅቶ ስለ ፍቅረኛው አሊስ ሲያስብ አነጋ። አሊስ፣ በክፍሏ ትኑር ወይም አትኑር ብሎ የማጣራት ሃሣብ ያደረበት ሰው አልነበረም። እርሷ በበኩሏ የመጀመሪያውን የፀብ ድምፅና የሰውዬውን ፖኸት ብቻ ስለሰማች ለጆን ባፕቲስት የተሰፋ መቁረጥ ፍርሃት ፊርታስት ነበር። በመጨረሻም፣ እንቅልፍ ሳይተኛ ያነጋው፣ ሙሴ ማቼ ነበር። ሙሉ ልብሱን እንደለበሰ፣ በጠባብዋ የብረት አልጋው ላይ ተንጋልሎ፣ በሚቀጥለው ዕለት ምን ዘዴ ሊፈጥር እንደሚችል ሲያስብ ነበር። በሆነ ሰው፣ ጥቃት እንደደረሰበት ቆንሲሉ ማወቁ አይቀርም። እርሱ ደግሞ፣ ይህን የፈፀመበት ማን እንደሆነ መናገር ይኖርበታል። የፖንሴን ስም ማጥፋት በተሰይ ለርሱ ጣፋጭ ይሆንለታል። አሊስንና ሴት አገልጋይዋን ይጠብቃቸው ከሆነ ደግሞ፣ ሊያደርገው የነበረና ቀደም ሲል በማየቱ፣ ፖንሴን ለማሣሣት ነው ሊል ይችላል። ከዚህ ቀጥሎ ግን በሕይወቱ ላይ የተቃጣውን ጥቃት እንዴት ማስረዳት ይችላል? ፖንሴ ለምን ሊል ጥቃት ይሰነዝርበታል? በጣም በቀላሉ የሁለቱን ፍቅረኛሞች ድብቅ የፍቅር ግንኙነት መናገር ብቻ ነው። በምንም መልኩ ዋናው ቁም ነገር ይህ ሣሣብ ይሆናል። ቆንሲሉ በበኩሉ፣ ልጁ ወደ ውርደትዋ እየተጣደፈች መሆንዋን እስኪያረጋግጥ የተቻኮለ ነገር አይሠራም። ይህን የመሰለ ክባድ ውንጀላ፣ እንዳችም ማስረጃ ሳይኖረው፣ ማቼ እንዴት ሰው ላይ መደፍደፍ ይችላል? ፖንሴም የዋዛ ሰው አይደለም። ብልጣብልጥ ተንኮለኛ ስለሆነ፣ ሁሉንም ነገር በራሱ በማቼ ላይ በማዞር ለውንጀላውና ምናልባትም ነገሩን በግልግል ለመጨረስ ዘዴ ይፈጥር ይሆናል። ፍቅረኛሞቹን በሌላ አጋጣሚ አግኝቷቸው የሚያስደነግጠበት ጊዜና ዕድል ደግሞ አያገኝም። ምክንያቱም በሚቀጥለው ቀን ፖንሴ ወደ ቬርሣይለስ ጉዞ ይጀምራል። በመጨረሻም ከንጋቱ አሥራ አንድ ሰዓት ሊሆን አካባቢ፣ በተሰይ በዚህ ሁኔታ ላይ ሊያከናውን የሚችለውን ጉዳይ ሲወስን፣ እፎይታ አግኝቶ ተኛ።

እንደዚሁም ደግሞ፣ እንቅልፍ ሳይተኛ ያደረው ጆን ባፕቲስት፣ ንጋት ላይ ከአልጋው ወርዶ ሻንጣውን እንደገና ማየት ጀመረ። በተለይም በጉዞው ላይ የማይለየውን የመድሃኒት ሳጥኑን ፈተሸ። ከዚህ በኋላ ጀስዊቱን ሲጠራቸው ወጣ። አባ ፕላንቴይን ገና ቅዳሴአቸውን

መጨረሳቸው ነበርና እስኪያጠናቀቁ ድረስ፣ ጆን ባፕቲስት በመስበኪያው ቦታ ፊት ወዲያና ወዲህ ሲል ቆየ። ቀጥሎ፣ ሁለቱ ሰዎች ቆንሲሉን ሊሰናበቱ ተያይዘው ሄዱ። ፖንሴ፣ በቆንሲሉ ከመጠራቱና ብቻውንም ወደዚያ ከመሄድ ይልቅ አሁን ከቁሉ ጋር መሄዱን በጣም ፈልጉታል።

ሙሴ ዴ ማይሊ፣ ከግማሽ ሰዓት በኋላ በፅህፈት ቤቱ ውስጥ ፒጃማውን እንደለበሰና ሰው ሰራሹን ፀጉሩን ሳያጠልቅ ተቀበላቸው። ማስረጃ ስለሌለው፣ ሲናገረው ባለመቻሉ ቅር እንዳለው፣ ከንፈሮቹን ዘግቶ ፈገግ አለ። በመቀጠልም፣ በተልዕኳቸው ላይ መልካሙን ሁሉ እንዲገጥማቸው ተመኝቶላቸው፣ ጀስዊቱ ምናልባት ክቡር ዴ ፖንቻርትሬይን የማግኘት ዕድልና ክብር ካጋጠማቸው፣ ሰላምታውን እንዲያቀርቡለት ጠየቃቸው። ቻክስር ፍሌሃውት፣ የጉዞ ልምድ የሌላቸው ስለሆኑ ብርቱ ጥንቃቄና እንክብካቤ እንዲያደርጉላቸውም ጠየቃቸው። በመጨረሻም ከሰር ፖንሴ ጋር ጥቂት ጉዳዮችን ለብቻ እንዲነጋገሩ እንዲፈቅዱለት አባ ፕላንቴይንን ጠየቃቸው።

ቆንሲሉ፣ ከመቀመጫው ላይ ተነስቶ መድሃኒት ቀማሚው ወደ ሚቀጥለው ረኸርም ክፍል ተከትሎት እንዲገባ፣ በእንቅስቃሴ አመለከተው። ዝቅ ካለው አድማስ ላይ የተንጠለጠለችው የማለዳ ፀሃይ፣ አቧራ የሞላበትን የጨረር ቀስቷን በጭለማው ክፍል ውስጥ በስላች ስትልከው፣ ግድግዳውን በሚሸፍነውና ቀለሙ በማይለቀቀው ሐምራዊ መጋረጃ አንዣር ሁለቱን ሰዎች የወየበ አይነ ርግብ በመሰለ መልክ ሸፈነቻቸው።

«በምሽት ፀሐፊዬን ማጥቃትህ ተነገረኝ!» አሰው ቆንሲሉ ቀረብ ባለ የማንሾካሸክ ንግግር።

«ይከታተሰኝ ነበር። ማን እንደነበረ አላወቅሁም»

«ይከታተልህ የነበረው፣ ሊያጋልጥህ በማለት ነበር። አንተም እንዲት ወጣት ሴትን ከነከብርዋ ስትቀማ በግልፅ ታይተሃል»

«የማህበረሰቡን ታላላቅ አሴቶች መጠበቅ የርሱ ግዴታ ነው?»

«ይህን ለመከላከል ያንተም ድርሻ አይደለም»

ቆንሲሉ የመለሰው ሞቅ ባለ ድምፅ ነበር። ወደ ጀስዊቱ ተመለከተ። ከአስር እርምጃዎች ርቀት ላይ ሆነው እጆቻቸውን በፍቅር የሚመለከቱት ካህን አልተንቀሣቀቁም።

«እንድም ቤተሰብ የቅፌታ አቤቱታ ቢያቀርብልኝ፣ ሌላው ቀርቶ ከሄድክም በኋላ ቢሆን፣ ማዕቀብ ጥዬብህ ይሆኑ እንዲያስፈፅሙ ወደ ፈረንሣይ እንደምፅፍብህ እመን»

መልክም፣ ምንም አያውቅም ማለት ነው፣ ሲል ጆን ባፕቲስት አሰበ። በአክብሮት ጐንበስ አሰ።

«ከዚህም ሌላ» ሲል ቆንሲሉ በመጠኑም እንደማፈር ብሎ ቀጠለ። «በዚህ ግዛት ውስጥ ያለውን የግንኙነት ደረጃና መጠን ጨርሶ በማለፍ ክሌት ልጄ ጋር ቃለ ምልልስ ለማድረግ ትፈልግ እንደነበረም ተነግሮኛል»

«አ! ጌታዬ፣ ከልጅዎ ጋር፣ ፍፁም የተሰየ ጉዳይ ነው»

«እና ይህ የምትሰው ጉዳይ ምንድን ነው? በፈጠረህ ንገረኝ»

በያንዳንዱ የሃሣብ መነሻ ላይ፣ ለፍቅረኛው በመታሰቢያነት ያስቀመጠውን የድፍረትና የጀግንነት ነገር ለቆንሲሉ ሊነግረው ይገፋፋ ነበር። ሁል ጊዜም ቢሆን፣ እንዲህ ያለው ነገር አስቀድሞ ታስቦበት ሣይሆን በድንገትና ባወጣ ያውጣው ተብሎ የሚፈፀም ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ለመሄድ፣ ካይሮን ሳይለቅ በፊት፣ ቤቱን እርስዋ እንድትጠብቅለት ሃሳብ ነበረው። አሁን ደግሞ በዚያው ተመሣሣይ የሽክሽክታ ድምፅ ሲሰናወን የነበረውን ጭውውት፣ እርሱ ራሱ ሲናገረው በጣም ደነገጠ።

«ደህና፣ ከርስዋማ ጋር በቀላሉ ፍቅር ነው»

ቆንሲሉ፣ በአንድ ቅጥር ነፍሰ ገዳይ ፖቤ ጀርባው ላይ የተወጋ ያህል ስቅጥጥ አለው።

«አፈቅራታለሁ» ሲል ጆን ባፕቲስት አይኖቹን ሳይሰብራቸው ቀጠለ «እርስዋም እንዲሁ ብዬ ለማመን በርግጥ መሞኘት ይሆንብኝ . . . »

«ዝም በል! ደግሞ ይህን ሃሳብህን እርግፍ አድርገህ አሁኑኑ ጣለው» አለው ቆንሲሉ ኮስተር ብሎ።

«ይህ እኮ ሃሣብ አይደለም»

«በቃህ አልኩህ! እንደዚህ ያለ ዕቅድ ኖሮህ ስታንዣብብ እንደነበረ ከረዥም ጊዜ በፊት አወቀአለሁ። ግን እንዲህ ያለውን የማይመስል ህልም ይዘህ፣ ስታጠናክረው ትቆያለህ የሚል ተስፋ አልነበረኝም»

«እኔ አጠናክረዋለሁ፣ እርሱም ያጠናክረኛል»

«ደግ እንግዲያው ስታልም ኑር። ሆኖም ግን ከዚህ በላይ አትውሰደው። ለልጂ፣ እኔ ሌላ እቅድ አለኝ»

«እንግዲያው፣ ለርስዋ ከመንገርም በፊት፣ እኔ ደግሞ የእርስዋን እጅ እንዲሰጡኝ ለመጠየቅ ማሰቢን ማወቅ ይኖርብሎታል»

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ እየደጋገመ ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ በሃይል ሣቀ። ድምፁ፣ በትልቁ ክፍል ውስጥ አስተጋባ። ከዚያ በኋላ በማንሾካሹክ ድምፅ ጭውውታቸውን ቀጠሉ።

«ጉዞ ከመጀመሩ ከአስር ደቂቃዎች ቀደም ብሎ፣ ከእንድ ተራ ቤተሰብ ከተወለደ መድሃኒት ቀማሚ እንዲህ ያለ ነገር በእንድ አና ቤት ውስጥ መስማት፣ እንደእውነቱ ከሆነ ማንም የሚጠብቀው አዋጅ ነው»

ቆንሲሉ በፊቱ ላይ መደበኛውን ፈገግታ ፈገግ በማለት፣ ፊቱን በማጨማደድ፣ የሚያስት ተዋናይ ላይ የሚያፈጥጥ ይመስል በተደናገረ የንቀት እይታ ተመለከተው።

«ይህ አዋጅ አይደለም» አለ ጆን ባፕቲስት ኮስተር ብሎ። «ማስጠንቀቂያ ነው። እኔ የንጉሡን ፍቅርና የክብር ማዕረግ ይገፎ ከርስም ጋር ሊያወዳድሩት እንዲችሉ ተመልሽ አመጣለሁ። ታዲያ ያን ጊዜ፣ ያን ጊዜ ብቻ በይፋ እገልፀዋለሁ። ይሁን እንጂ ከአሁን በኋላ ያ ጊዜ እስኪደርስ ድረስ ዕሰርሷ ተብሎ የሚገባ ቃል ኪዳን አይኖርም»

እነዚህን ቃላት መናገሩ፣ ለጆን ባፕቲስት እፎይታና እርካታ ሰጡት። ብልግናና ተበቃይነት፣ ሁልጊዜም ይሣካላቸዋል። ይህ ሁሉ ሲሆን ደግሞ፣ መጥፎ ርምጃ በመውሰዱ የበደለኛነት ስሜት ተሰማው። ባላሸነፈው ጠላቱ ላይ፣ ራሱን እንደህ ግልፅ አድርጉ ማውጣት፣ የድል አድራጊነትን ትዕግስት ለጠላት ማሣየት፣ ይቅር የማይባል ስህተት ነው። ምክንያቱም፣ ባላጋራው አሁንም ቢሆን ድባቅ ሊመታው የሚችልበት ጊዜ አለው። አንዲሰው፣ ተሞክሮና ብስለት እያገኘ ሲመጣ፣ እንዲህ ያሉ የጅል ስህተቶችን ወዲያውኑ የመለየት ችሎታ አለው። በርግጥ በትዝታ ስለሚያስበው ጊዜ፣ በፍጥነትና በትክክል፣ ስሜት ሊሰ የሚችል ውሣኔ ለመስጠት፣ ተጠንቅቆ ሊፈፅመው ሲችል፣ ይህን የሚያስጥለው የስሜቱ ሃይል ሊያያልበት አይገባም።

«ይህን ማስጠንቀቂያ በሚገባ መስማቴን ርግጠኛ ልትሆን ትችላለህ» አለ ሙሴ ዲ ማይሌ በሰይጣናዊ ፈገግታ። ከዚያም ጆን ባፕቲስት፣ ከጀስዊቱ ጋር እንዲሆን በዐይኑ ጠቀሰው።

❧

በዚያኑ ዕለት ከሰዓት በኋላ፣ ለዚሁ በዓል ሲባል፣ ቆንስላው በተከራየላቸው በአራት ፈረሶች በሚጎተት ሠረገላ ተሣፍረው ሰቀቱ። ከነርሱ በኋላ፣ የጣሪያ ከፈኑ እነርሱን ለመደበቅ ሲባል ዝቅ በተደረገበት ጋሪ፣ ሦስቱ አቢሲኒያውያን ትሕሻ ለትሕሻ ገጥመው፣ ከሸማግሌው አረባዊ ጋሪ ነጅ በስተኋላ ተቀምጠዋል። የጉብው ሰልፍ፣ ሻንጣዎች ከሚጫኑበት ከሙራድ ቤት ፊት ለፊት ተሰበሰበ፤ አርመናዊው፣ ፖንሴን በሃዘን ተሰናበተው። ሙራድ፣ ይህን አደገኛ ጉዞ ባለማድረጉ፣ ካይሮም ውስጥ ምንም የነቃ ተሣትፎ የሚያደርግበት ሃላፊነት ስለሌለው፣ ይህንኑም ስለለመደው፣ ቆይታውም ስለሚራዝምለት ደስተኛ ነው።

ሜትር ዠረሚና ጆን ባፕቲስት እንደተለመደው ከወንድማማችነት መተቃቀፍ በስተቀር የተለየ ስሜታዊነት ላይታይባቸው ተለያዩ። በዚህ ሰዐት፣ ፕሮቴስታንቱ ከካይሮ እንደሚይንቀሣቀስ፣ ጆን ባፕቲስት አርግጠኛ ነው። ሰርሱም ቢሆን፣ በቬርሣይለስ ዙሪያ እንደፖሊቲክ ስደተኛ፣ በንጉሡና በጀስዊቶች ዙሪያ ከሚያንጎራብብ፣ ወደ አቢሲኒያ ያደረገው የአሠሣ ጉዞ አደጋ በጣም አነስተኛ ነው። ሜትር ዠረሚ፣ ሙራድን እንደሚጠብቀው፣ ስለ እሱም የሚያገኘውን ዜና እንደሚልክለት፣ ፖንሴ ሠረገላው ላይ ሲሣፈር ሲል፣ ቃል ገባለት። ከዚያም ጆን ባፕቲስት ጓደኛውን ለብቻው ወሰደው። ማንም ሰው፣ ወደደውም፣ አልወደደውም፣ ጉዞ፣ ተጓዡን ርግጠኛ ባልሆነ ዕጣ ፈንታ ላይ ያደርሰዋል። ሁለት ሰዎችን ለያይቶ የሚያቆይ ሰው፣ ምንም እንኳ በመልካም ባህርይ ቢጠቀስ፣ ለራሱ ይቅርታ አይኖረውም።

«ከፍራንቸይዝ ጋር ጨዋ ሁን፣ እንደማስበው ታፈቅርሃለች» ከሁለቱ አንዳቸውም ለነዲህ አይነቱን በራስ መተማመን ልማድ አድርገው አያውቁም። ግዙፉ ሰውዬ፣ ጆን ባፕቲስትን በጅላጅልነት አመለካከት አይኖቹን ሰብሮ ተመለከተው። በመለያየት ጉዳይ የጥድፊያ እንቅስቀሴ ላይ ባይሆኑ ኖሮ፣ ግዙፉ ሰውዬ ግራ መጋባቱን ለመደበቅ በጣም ይቸግረው ነበር።

«ፖንሴ፣ ምንድን ነው ወደ ኋላ የሚጮኽብህ? ዘገየን እኮ» አሉ ጀስዊቱ።

የሠረገላው በሮች በሚገባ መዘጋታቸውን ለማረጋገጥ ሜትር ዠረሚ ከእንዱ ወገን ወደ ሌላው ተሯሩጠና በመጨረሻም የመልዕክተኛው ቡድን ሲንቀሣቀስ ቆሞ ተመለከተ።

ሠረገላዎቹ በቆንስላው ፊት ለሰፉ። በዚያን ጊዜ ግራጫ የሱፍ ቀሚስ ለብሳ፣ ለባሏ እጇን እያውለበለበችና ቀጥላም በማጨብጨብ ፖቪቷን ለማፈን እጆችዋን በአፏ ላይ ያደረገችው ማዳም ፍሌሃውት ብቻ ነበረች። ለሁለተኛ ጊዜ ወደሚያፈቅራት ሴት ራሱን ይበልጥ ለማቅረብ ጆን ባፕቲስት ተነስቶ ሲሄድ አሁንም ልበ ሙሉነት ነበረበት።

4

የንጉሡ ጀሮ

1

ሊጠቀስ የሚችል የረባ ችግር ሳያጋጥማቸው፣ አሌክሳንደሪያ ደረሱ። ጀስቂቱ፣ የሰኩን አቢሲኒያውያን ተስፋና ምኞታቸውን ሁሉ ይከታተላሉ። እነዚህ ሦስቱ አንዳችም ቃል ባይተነፍሱም፣ ይህ ሰው እንዲህ በድንገት ለምን ባሪያቸው እንደሆነና በእንግሩ ደግሞ፣ እነርሱ የርሱ ጌታ ለምን እንዳልሆኑ እያሰቡ የሚገረሙ ይመስሉ ነበር። ቻንስለር ፍሌሃውትን በተመለከተ ሰውዬው በየዕለቱ በነበራቸው ዕረፍት ላይ ፍፁም አፋቸውን ከፍተው አያውቁም። ይሁን እንጂ፣ የምግብ ሰዓት ትንሽ እንኳ ከዘገየ ሞትኩ እያሉ አንድ ሺህ ጊዜ ይወተውታሉ።

በጉዟቸው ላይ የመጀመሪያው አደጋ ያጋጠማቸው አሌክሳንደሪያ ውስጥ ነበር። ሁለቱ ሰረገላዎች ባህሩ ዳር የደረሱት ከመሸ ስለነበረ፣ ሪጉት በሚባል ፈረንሣዊ ወደ ሆቴልነት የተቀየረው፣ ጥንት የመዝናኛ ቦታ ወደነበረው ፈረሶቻቸውን እየሰቡ ሄዱ። ይህ ቦታ የተመረጠላቸው በሙሴ ዴ ማይሌ ነበር። የሆቴሉም ባለቤት፣ ከቆንሲሉ ስሚያገኘው ድጋፍና ጥበቃ ሲል ሁልጊዜም ሪፖርት ያቀርባል። ሰውዬው፣ መንገደኞቹን ተቀብሎ፣ ራትም አቅርቦላቸው በሁለት የተለያዩ የማረፊያ ክፍሎች ውስጥ እንዲያርፉ በማድረግ፣ ራሱ አስተናገዳቸው። እንደአለመታደልም ሆኖ አቢሲኒያውያኑ የተጫነብትን ሰረገላ ይነዳ የነበረው የአሌክሳንደሪያው ሽማግሌ ሴሊቱን በመኖሪያ ቤቱ ለማሣለፍ ይወስናል። ወደ ቤቱም ሲሄድ የአጐቱን ልጅ በመንገድ ላይ ያገኘዋል። ይህ የአጐት ልጅ፣ በዚህ የሠራተኞች ሠፈር ውስጥ በጣም አክራሪ ከሆኑት ሙፍቲዎች አንዱ ነው። ሽማግሌው ጋሪ ነጅ፣ ስለ አቢሲኒያውያኑና ስለሚያጅቧቸው ፈረንሣውያን ይነግረዋል። ይህ የአጐት ልጅ ተብዬው፣የሰማውን አስደሣች ትንሽ ዜና በጀለቢያው ውስጥ ደብቆ ይዞ ሄደ።

የቤተመንግስቱ ጀልባ በሚቀጥለው ዕለት ከወደብ ይለቅቃል። ወደቡም ደግሞ ሊታመን ከሚችለው በላይ ሽርጉድና ትርምስ የበዛበት ነው። በጭንቅላታቸው ላይ ሚዛኑን ጠብቀው የተሸከሙትን ዕቃ ይዘው በመሸጋገሪያው ላይ የሚወጡና የሚወርዱ ተሸካሚዎች ክምችት ይበዛል። እነዚህ ኩሊዎች ሲጫጫሁ የሚሰማው የገደል ማሚቶ፣ በመርከቡ ወለልና በመርከቡ ማቆሚያ መካከል ይስተጋባል። ለመርከቡ ቀዛፊዎች ከተያዘው ከታችኛው ጨለማ ወለል በኩልም የሰዎች ድምፅ ይሰማል። ፀሐይዋ ቁልቁል በቀጥታ ስለምትመታ፣ ሁሉም ነገር ያንፀባርቃል። ነጭ ቀለም የተቀቡት የወደቡ ሕንፃዎች፣ የፍራፍሬ ሳጥኖችና ሌላው

ቀርቶ በእንጨት ማንጠልጠያዎች ነፋስ ላይ የተዘረሩት ከርዳዳ የጆንያ ጨርቆች ሣይቀሩ ያንፀባርቃሉ። ጆን ባፕቲስትን፣ አባ ፕላንቴይንና ፍሌሃውትን የጫነው ሰረገላ በትርምሱ ውስጥ ቀስ በማለት አለፈ። ሕፃናት ልጆች የሰረገላውን ትልቅ ተሽከርካሪ የእንጨት ጐማ ይዘው በመንጠልጠል ጉማው መሉ ዙር እስኪያስናውን አብረው ይሽከረከራሉ። አንዳንድ ጊዜ ሰረገላው ሲቆም ከሕፃናቱ አንዱ በጭንቅላቱ ሲተከል፣ ሣቅ በሣቅ ይሆናሉ። ከነርሱ በኋላ፣ ብሩህ ሰማያዊ ጣሪያው በፀሐይዋ እየጋመ ያለው የአቢሲኒያውያን ሠረገላ ተከትሏቸዋል። በሕዝብ ከመጨናነቁ የተነሣ ይህ ሁለተኛው ሠረገላ ከቀደመው ጥቂት ርቀት ወደ ኋላ ነው። ጀስቂቱ፣ የመጀመሪያውን ጋሪ የኋላ መስኩት ከፊት አድርገው አክስተኛ የጭንቀትና የድንጋጤ ድምፅ አሰሙ። ነገሮች ሁሉ ሳይታሰቡ ወደ አመፅ ሊቀየሩ የጉዞው አጀብ ከጀልባው ሃምሣ ጫማ ያህል ይርቅ ነበር። ሰፊ ሰማያዊ ካባና የዳንቴል ቆብ የለበሰ አንድ ወፍራም ግብፃዊ፣ እምብዛም ወደ ማይንቀሣቀሰው ሠረገላ በመሄድ የሰረገላውን ሽፋን አንደነገሩ ወደ ኋላ አጠፈው። በዚያ የፀሐይ ብርሃን ውስጥ ሦስት አቢሲኒያውያን በፍርሃትና በጭንቀት ታፍገው ተቀምጠዋል። ወዲያውኑ ከጋሪ ነጅው ቀጥሎ የነበረው ሰው ሰረገላውን እንዲያቆመው አዘዘው። ሽማግሌው አረባዊ፣ የአጐቱን ልጅ ሲመለከተው ትዕዛዙን ወዲያውኑ ተቀበለ። ይህ የአጐት ልጅ፣ ከዚህ በመቀጠል በወደቡ ውስጥ ያሉት ሁሉ ሥራቸውን አቋርጠው እስኪያዳምጡት ድረስ በከፍተኛ የሙኢዚን ድምፅ ጮሆ ተጣራ። በቀጭን የጥጥ ሻሽ ሰውነታቸውን ጠምጥመው ወደ ተቀመጡት ወደ ሦስቱ አቢሲኒያውያንም እያመለከተ፣ የተሰበሰበው ሕዝብ ላይ በሃይለ ቃል ጮኸ። ቀስ በቀስም ሃይለ ቃሉ ወደ መጀመሪያው ሠረገላ አቅጣጫ የከስ ዛቻ እያሰማ ቀጠለ።

«ወደዚያ ተመልሺ መሄዴ ነው» አሉ አባ ፕላንቴይን የሠረገላውን በር እጀታ እየያዙ።

ጆን ባፕቲስት ገታቸው

«ከዚህ ሠረገላ እግርዎ ይወጣና ሞተው ያርፋሉ» አላቸው

ከዚያም ለሠረገላ ነጅው በቀዳዳ በኩል በሚችለው ፍጥነት ሁሉ ፈረሶቹን እንዲያስጋልባቸው፣ ፖንሴ ትዕዛዝ ሰጠው። በፈረንሣይ ማህበረሰብ ውስጥ ነዋሪ የሆነው ጀርመናዊ የሠረገላ ነጂ፣ ሁኔታውን በቅፅበት ተረዳ። ፈረሶቹን እያቻኮላቸው፣ በሚጮኸው የሕዝብ ክምችት መሃል አስፈተለካቸው። ጀልባው አጠገብ ሲደርሱ ሠረገላው ወዲያውኑ

ቆመ። ፖንሴ፣ የሚንቀጠቀጠውን ፍሌሃውትን፣ ከፊት ለፊቱ እየገፈተረውና ከኋላው ሆነው አሁንም አቢሲኒያውያኑን የሚያድኑበትንና ነፃ የሚያወጡበትን ዘዴ የሚያስቡትን ጀስቂት፣ ባለ በሌለ አቅሙ እየጐተታቸው ወደ ጀልባው መሣፈሪያ ሮጠ። መንገደኞቹ ከመጣያፋቸውና ከመፍራታቸው የተነሣ ከዋናው ቃዲ ጋር በጀልባው መግቢያ በር ላይ ሆኖ ይጠብቃቸው ከነበረው የመርከቧ አዛዥ ጋር ተጋጭተው ወደቁበት። ሽማግሌው ቃዲ፣ የፓሻውን ትዕዛዝ ለማስፈፀም ያለ ሰው ቢሆንም፣ ጠቀም ያለ ሣንቲም ካገኘ ውሳኔውን ጠበቅ እንደማያደርግ መንገደኞቹ ባለፈው ምሽት መረጃ አግኝተዋል። ቃዲው ግን፣ ሌላው ቀርቶ የካሊፋው ወኪል እንኳ ቢፈቅዱ፣ አፍሪካዊ ክርስቲያኖች ከአሌክሣንደሪያ ላይ መሣፈር ፈፅሞ እንደማይችሉ አስጠንቅቋቸዋል። ስለዚህ ሌላው ቀርቶ ዝቅተኛው ሙስሊም እንኳ ቢቃወመው ተሰሚነት ስለሚኖረው፣ አቢሲኒያውያኑን የማሣፈሩ ጉዳይ በጣም ደካማ ነው። በዚህም የተነሣ ሊጠገን የማይችል ሁኔታ ተፈጠረ። ባለሥልጣኑ የእጅቱን መዳፎች ወደ ሰማይ ዘርግቶ ሲያደርገው የሚችለው ምንም ነገር አለመኖሩን ተናገረ።

የሠረገላ መኪናው ከዕይታ ተሰወረ። በሰሜት የተንጨረጨሩ ሰዎች አጥቅተውታል። አባ ፕላንቴይን እጀቻቸውን አሻሹ። ፊታቸው በሕመም ተጨማደደ። ውስጣቸው ጨሰ።

ጆን ባፕቲስት፣ ጊዜ ሳያጠፋ፣ ሁለት መርከበኞችን ጠርቶ ሻንጣዎችን እንዲጭኑለት ርዳታቸውን ጠየቃቸው። የመጨረሻዎቹ ሻንጣዎች ብድግ እንደተደረጉ የተሰበሰበው ሕዝብ ከሰረገላው መኪና ውስጥ ሦስቱን አቢሲኒያውያን ይዞ ተፈተለከ። አልፎ አልፎ የነጭ ጨርቅ ቁራጭ ውልብልብታ ካልሆነ በስተቀር ምናቸውም የነዚህ ያልታደሉ ፍጡሮች አይታይም ነበር። ጥቃቱን የመራው ሙፍቲ፣ የቁጣ ዛቻውን በሌላው ሰረገላ ላይ ሲያ�ዘር፣ ከሕዝቡ ከፊሉም ወደዚያው ገሰገሰ። ጀርመናዊው ለመሄድ ነፃ መሆኑን ፖንሴ እጁን በማውሰብሰብ አሣየው። የሠረገላ ነጅው አለንጋውን በማጮህ ፈረሶቹን ሽምጥ እንዲጋልቡ በማስገደድ በፖኸት ትርምሱ መሃል፣ የሁከቡ ፍራፍሬዎችና በመንገዱ ዳር የሚገኙ የቸርቻሪ ነጋዴዎችን ቁቁት እየደፋና እየገለበጡ ተፈተለኩ። በማምለጡ የተቆጣው ሕዝብ ወደ ጀልባዋ ማመልከት ጀመረ። ብዛት ያላቸውና ከደረታቸው በላይ ርቃናቸውን የሆኑ ወንዶች፣ መርከቡ ጠርዝ ላይ ዘልለው በመውጣት ጀልባው ላይ ለመድረስ እጅ በእጅ ላይ እየተነባበረ መከራ አደረጉ።

ሦስቱ ፈረንሳውያን በዋናው ጓደኛቸው አማካይነት በደልባው ኋላ በሚገኝ ጨለማ ክፍል ውስጥ ገብተው ተቆለፈባቸው። ይህ እየሆነ እያለ፣ የደልባዋ አዛዥና ሌሎች መርከበኞች ሕዝቡን አገዱት። ብዙ ሺህ የሚሆኑ ድምፆች በደልባዋ መድረክ ላይ አፍሪካውያንን እየዘረፉ የሚወስዱትን ሰዎች፣ ለበቀል ቅጣት አሳልፈው እንዲሰጧቸው በፖሽት ይጠይቃሉ።

በመጨረሻም የተሰበሰበው ሕዝብ ተበተነ። ጀልባዋም ከወደቡ ጋር የታሠረችበትን ገመድ ፈትታ በባሀሩ ላይ መንሳፈፍ ቻለች። ጀልባዋ፣ በባሀሩ ላይ መሆንዋ ሲረጋገጥ፣ አዛዡ ራሱ መጥቶ መንገደኞቹን ከነበሩበት ሥፍራ በማውጣት አከብሮቱን ገለፀላቸው።

«ለመሆኑ አቢሲኒያውያኑ ምን አጋጠማቸው?» ሲሉ አባ ኘላንቴይን የኔ ልጆች ቢሆኑ ናሮ በሚል ስሜት ሳይሆን ለወሬው ጓጉተው ጠየቁ።

«በእሁኑ ሰዓት ምናልባት ሁሉም ቱርካውያን ሆነዋል» አሰ ካፒቴኑ በትህትና። በርግጥ ለነዚህ ሰዎች ይህ ሁኔታ በጣም መጥፎ እድል ሲሆን ይችላል። የሆነ ሆኖ፣ የፈረንሳይ ንጉሥ ሦስት ዜጎቻቸውን ከማጣት ድነዋልና አሁን ልንደሰት ይገባናል።

የካፒቴኑ ስም፣ ዴ ሁች ሲባል፣ ቤልጂየም ውስጥ ከሚገኙ የፍላንደር ብሔረሰቦች፣ ዲፔ መንደር የተወለደ ነው። ፖንሴንና ጀስዊቱን በፈገግታ እጆቻቸውን ይዘ ከፍሌሀውት ጋር እየመራቸው ወደ ክፍሉ ወሰዳቸው። ሦስቱ መንገደኞች ባሀሩን በሚያቋርጡበት ጊዜ ሁሉ የዚህ ባህረኛ አስደሣች ለዛ፣ ተጭኗቸው የነበረውን ሀዘንና ትካዜ ሊያስወግድላቸው አልቻለም።

ጊዜው ወርሃ ጥቅምት በመሆኑ፣ በወደቡ ዳር የሚጋረፍ የባህር ንፋስ ነበረ። የመርከቧ ቀዛፊ ባሮችም መቅዘፊያቸውን ለማስቀመጥ ችለው ነበር። ከሌሎቹ የደልባዋ ተሣፋሪዎች ፍፁም ተለይተው ከነበሩት ቀዛፊዎች ሌላ፣ መንገደኞቹ በሙሉ ማለት ይቻላል፣ ወታደሮች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ደግሞ ስለራሳቸው የሚናገሩት ምንም የሌላቸው ናቸው። የግብጽ የወደብ መሬት ከአይናቸው እንደተሰወረ፣ ፍሌሀውት በራሣቸው ክፍል ውስጥ ዘግተው በመቀመጥ፣ ጠኔ እስኪጥላቸው ድረስ ምንም አይነት ምግብ አልቀበልም አሉ። ፖንሴ፣ ከሾርባ ውስጥ መድሀኒት በመቀላቀል ምግብ ይልክላቸዋል ቢባልም፣ እንደእውነቱ ግን ምንም ነገር አይጨምርበትም ነበር። ቻንስሉ፣ የዳኑት በምግቡ ሳቢያ መሆኑን ስላልጠረጠሩ ሐኪሙ ለሚያደርግላቸው ጥሩ ጥንቃቄ አመሰገኑት።

ጀስዊቱ ጥሩ የጉዞ ጓደኛ አልነበሩም። ለረጅም ሰዓታት ያለማቋረጥ አጉንበሰው ይፀልያሉ። ክፍሱን የሚወለውለው ልጅ፣ በቁሱ ዙሪያ ያለውን ቦታ እርሣቸውን ላለመረበሽ በሚል ሣይወለውለው ይተወዋል። አባ ኘላንቴይን፣ በአቢሲኒያውያን ባሮች ላይ ለሚፈፀመው በደል እግዚአብሔር ይቅር እንዲል የሚጠይቁ እንደሆነ ፖንሴ ይገምታል። ቄሱ በጣም ስለፈሩ፣ እግዚአብሔርን፣ ስላሰፈው ሳይሆን ለለመጪው እያዩ ይለምኑታል። በባህሩ ውሣ ውስጥ እንዳይሰምጡ ብቻ ይፈልጋሉ።

ጀን ባፕቲስት፣ በነፃነትና በደስታ የሚጫወተው ከካፒቴን ዴ ሁች ጋር ነበር። ካፒቴን ዴ ሁች፣ የአንድ ባህረኛ ልጅ ሲሆን፣ በደች ጦርነት ጊዜ በጀግንነት የተዋጋ ኩሩ ወታደር ነው። በጊዜው የአንድ መርከብ ምክትል አዛዥ በመሆኑ፣ ከኮሞቴ ዴ ቶርቪል ሥር በታላቁ የቤቺ ሄድ ድል ላይ የውጊያ ተካፋይ ነበር። ዴ ሁች ለንጉሥ ሉዊስ 14ኛ ከልብ የመነጨ ፍቅር ነበረው። ይሁንና፣ ንጉሡን፣ ያየው አንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን፣ ለዚያውም ከርቀት ነበር። ስለንጉሡ ብዙ ታሪኮችን ያውቃል። የፈረንሣውያንን ልብ በሚነካው፣ በፍርንዴ ዘመን ስለነበረው የንጉሡ የሕፃንነት ዘመን፣ ስለዝናው፣ ስላደረጋቸው ውጊያዎች፣ ስለጉብኝውና ስላከናወናቸው ስምምነቶች ያውቃል። ከዚህም በተረፈ በየዋህነት ስላከናወነው የተቃራኒ ፆታ ፍቅር፣ ስለቁባቶቹ የቅብ ስዕሎችና ስለዲቃላው ልጁ የሚያወሱ ታሪኮችም ነበሩ። ባለፉት አምስት አመቶች ውስጥ ወደ ምስራቅ ሲያደርጋቸው በነበሩ ጉዞዎች የተነሣ፣ ዴ ሁች ብዙ የትርብ ጊዜ ታሪኮች አምልጠውታል። በርግጥ አሁን አፈታሪክ እየሆኑ ያሉትንና እርሱ የአይን ምስክር በመሆን የመጀመሪያ ማስረጃ የሚሆንባቸው፣ በሉዊስ የመጀመሪያዎቹ የንግስና ጊዜያት ላይ ስፋ ያለ ነገር ያውቃል። ፖንሴ፣ ባለፉት ጥቂት አመታት ውስጥ በአውሮፓ ውስጥ ኖሮ ቢሆን ኖሮ፣ ዴ ሁች ማንኛውም ተራ ፈረንሣዊ ስለንጉሡ ከሚያውቀው የበለጠ እንደማያውቅ ይገነዘብ ነበር። ይሁን እንጂ በዚያ አረንጓዴና ሃምራዊ መዓት መስሎ በከበባቸው ባህርና ከደመናው መሀል በሰያፍ፣ ሸንቁሮ በመጣው ብርሃን ውስጥ፣ በመረከበኛው ለነገር የነበረው የሉዊስ 14ኛ የሕይወት ታሪክ፣ የግሪኮችን አስደናቂና አስገራሚ የሰዎችንና የደርጊቶችን ጉዳይ የሚናገር አስመስሎታል። በሌላ በኩል ይህ ባህረኛ ምሲጋና ይግባውና፣ በንጉሡ ሕይወት ዙሪያ የሚነገሩ በጣም የሚታወቁ ወይም ዝነኛ ድርጊቶችን በዝርዝር ያስተውሣቸዋል። በአቪደስ የትረካ ግጥም ውስጥ ያለው የበግ እረኛ፣ አሸልቦት በነበረበት ሰዓት ከዜውስ የጣኦት አምላክ ጋር በተሰመደው ቋንቋ የሚነጋገር ያህል የተሰማውን ስሜት ሣይነት፣ ጀን ባፕቲስትም፣ ከአማልክት ጋር ይሰተካከላል ተብሎ ከሚነገርለት ሉዊስ 14ኛ

ሕይወት ውስጥ የገባ ያህል ስሜት ተሰማው። በመሆኑም፣ ጀን ባፕቲስት ስለአገሩ ልጅ፣ ስለፀሐፍ ንጉስ ያለው አድናቆት ከዕለት ዕለት እየጨመረ፣ ልክ በልጆቻቸው ፊት በጥምቀተ ባህሩ ውስጥ እንደሚነክሩ አዛውንቶች፣ እርሱም በቤተመንግስት ልማድና ወግ ውስጥ በአንድ ጊዜ ተዘፈቀ። በአጭሩ እንደገና ፊረንሣዊ መሆን ጀመረ።

መርከቡ፣ አግሪጅንቶ ወደብ ላይ ለአምስት ቀናት ቆየ። ከዕለታት አንድ ምሽት ላይ ካፒቴኑ፣ አባ ፕላንቴይንና ፖንሴ በክረብታው ውስጥ በሚገኝ ትንሽ ሆቴል ውስጥ እራታቸውን ለመብላት ሄዱ። በኮረብታው እርከኖች ላይ ተቀምጠው ወደቡን ቁልቁል እንዳያዩት ጊዜው ሞቃት ነበር። የሐረግ አትክልቶችን የደገፉ እንጨቶች በሃይለኛ የመኸር ወቅት ነፋስ ይናወጣሉ። ወደ መርከባቸው ሊመለሱ ሰንሑሥ ከሚቀርቡት ገፀበረከቶች መሃል የሆነው ትምባሆ ተሰርቆ ደረሱ። ከዕቃ ቤቱ ቀጥሎ ባለው ክፍል ውስጥ የተኛው ፍሌሃውት፣ ሚስቱ በማንም ላይ ጣቱን እንዳይቀስር መክራው ካልሆነ በስተቀር፣ ምንም ነገር አልሰማም። ካፒቴኑ፣ ቢዮበታ ላይ የነበሩትን ሰዎች ጠየቃቸው። እነርሱም፣ ሕፃናት በመርከብ መቆሚያው አካባቢ ሲንሸራተቱ እንደነበረ በአንድ ቃል ተናገሩ። እዚህም፣ እዚያም ቅጣት ቢፈፀምም፣ የንጉሥ ሉዊስ 14ኛ ትምባሆ፣ ወደቡን በከበቡት አረንጓዴና ግራጫ ተራሮች ውስጥ አንዱ ዘንድ ተጠሏል።

ከዕለታት አንድ ቀን ከንጋቱ በአሥራ አንድ ሰዓት ላይ ተንቀሣቀሱ። በዚህ ጊዜ ነፋሱ በአንፃራዊነት ስለሚመጣቸው፣ መርከቡ ከማዕበል ጋር ሲጋጭ፣ ቢጫ አረፋ መተፋት ጀመረ። ይዘንብም ስለነበረ፣ የመርከቡ ሸራዎች አልተወጠሩምና ቀዛፊዎችም ለብዙ ሰዓታት ከፍተኛ ሥራ መሥራት ነበረባቸው። እንዲህ ባለው ጊዜ፣ የመርከቧ ቀዛፊዎች በምን ዓይነት መከራ ውስጥ እንደሚቆዩ፣ በምን አይነት አሰቃቂ ሁኔታ ላይ እንደሚሆኑና ይህን ሁልጊዜም ችለውት የመኖራቸውን ነገር ትክክለኛ ሥዕል ለማየት እንዲችል ቢጠይቅ ይሻል ይሆን? ወይስ ደግሞ ሁለት ወሰል ዝቅ ብሎ በሚገኝ ቦታ ላይ የደከመው ሰውነታቸው ከአግዳሚ መቀመጫዎቹ ላይ በሰንሰለት ታስሮ የሚገኘውን አካላቸውን በዓይነ ህሊናው እየተመለከተ እያንዳንዱን የዕረፍት ጊዜውን በጥፋተኝነት ስሜት እንዲጠብጠው ቢያደርግ ይሻል እንደሆነ፣ ፖንሴ በትክክል ማወቅ አልቻለም። ለጊዜውም ቢሆን ከሁለት አጫጭር ሰርጦች በኋላ የመርከቧ ስቃይ አብቅቶ ማርሴይ ወደብ ደረሱ። ከመርከቧ ፊት ላይ ሆኖ ጀን ባፕቲስት አሮጌውን የመርከብ መቆሚያ ቦታ እየቀረበ ሲመጣ በትዕግስት ማጣት ተመለከተው።

መርከቧ፣ ወደቡ ላይ በሚገባ ከታሠረች በኋላ፣ ካፒቴኑን ደህና ሁን ብሎት በዝግታ ወደ ዳርቻው ዘለለ።

ባህሩን በማቋረጥ ላይ በነበሩት ጊዜ ያሣዩት በነበረው ነፃነት እምነት አድሮበት፣ ጀስዊቶቹ በርሱ ላይ ያላቸው ቁጥጥር የላላ ይሆናል ብሎ አስቦ ነበር። አባ ፕላንቴይን፣ ጠንቃቃ ሰው ሲሆኑ፣ በማንኛውም ሁኔታ በባህሩ ላይ በነበራቸው ፍርሃት ተወጥረው ያሉ ናቸው። ነገር ግን በማርሴይ ወደብ እንደደረሱ የሚያጠራጥሩ ነገሮች ተወገዱ። አምስት፣ ጥቋቁር ቀሚሶች የለበሱና ምስት ተመሣሣይ ቀለማት ያላቸው ሠረገላዎች ከመርከብ መቆሚያው ሰፍራ ላይ ቆመው ይጠብቋቸዋል። በአክሲጅንና በአንቅልፍ እጦት ደክምክም በማለት ከክፍሉ በቃሬዛ የወጣው ፍሌሃውት ብቻ ሲሆን፣ ትዕይንቱንም የቀብር ስነስርዓት ነው ተብሎ ቢነገር የሚታመን ዓይነት ነበር። አባ ፕላንቴይን፣ እግራቸው መሬቱን ከነካበት ትዕበት ጀምሮ፣ ሕይወታቸው ለምልሞ ባልደረቦቻቸው የሚያቀርቡላቸውን እንኳን ደስ ያለዎት አቀባበል በመቀበል አንደኛው ሠረገላ ውስጥ ገብተው ተቀመጡ። ፖንሴ፣ ቀዩን ከፋይ ሙሉ ልብሱን እንደለበሰ ውስን ደስታና ነፃነት ይሰማዋል። እርሱም፣ የሬሣ መጫኛ ከሚመስሉት ሠረገላዎች ውስጥ ገብቶ ከሌሎች ጋር እንዲቀመጥ ግድ ሆነበት። ዙሪያውንም አመዳምና የጀንያ ልብስ የመሰለ ፊት ባላቸው አዲስ የጥበቃ ወታደሮች ተከበበ። ወዲያውም፣ ጀስዊቶች ወዳላቸው ማረፊያ፣ ወደ ፋሮስ አቅጣጫ አመሩ። ማረፊያው፣ ሮም ውስጥ በሚገኘው በዝነኛው ኢል ጌሱ ምዬል ከደፍጣጣው ቤተክርስቲያን ቀጥሎ ወደታነፀውና ታላላቅ የነጭ ድንጋይ ደጋኝ ቅርፆች ኖረውት በዝርግ የሮማ የጣሪያ ሸክላ የተሠራ ነው። ጀን ባፕቲስት፣ በሦስተኛው ፎቅ ላይ የምትገኝ ጠባብ ክፍል ተሰጠችው። የክፍሏ መስኮቶች ወደ ክፍላተ ሃገራት ሁሉ ማሣየት የሚችሉ ናቸው።

በአንድ ጉን ወደማርሴይ አቅጣጫ የሚያመሩ ቤቶች ሲኖሩ በሌላው በኩል ደግሞ የሚያማምሩ የባሳገር የእርሻ ሥፍራዎች፣ጥድ መሠል ዛፎች በሰልፍ የተተከሉበትና በየመሃላቸው የጥድና የሰውዝ አይነት ዛፎች የተደባለቁባቸው ይታያል። ራቅ ባለው አድማስ ጠመልማላ ነጭ መስመር፣ የአልኘስ የበረዶ ቁንጮ የመጀመሪያው ጉብታ፣ ደመና ካንገላታው ፃፀም ቢኒ መሬትና ዝናብ ካጠበው ሰማይ ለይቷቸው ይታያል። በዚህ ጊዜ ራሱን በክፍሉ ውስጥ ለይቶ ያቆየው ፖንሴ ነበር። ይህን ያደረገው ከጀስዊት ካህናቱ ጋር በመሆን ከሌሎች ጋዜ የመጫወቱን ጉዳይ ለማምለጥ ሲል ነበር።

ከሁለት ቀናት በኋላ ተጓዦቹ በሌላ ጥቁር ሠረገላ ላይ ተሳፈሩ። ይህ ሠረገላ ለመንቀሳቀስ እንኳ ደካማ የነበረ ሲሆን፣ ጋሪ ነጂውም እጅግ ዝቅተኛ ክፍያ የሚያገኝ ተቀጣሪ መሆኑ የማያጠራጥር፣ ለቀጣሪ ጌቶቹ አውጥቶ ሊገልፅላቸው ያልቻለውን ተስፋ መቁረጥና ብስጭት ለተሳፋሪዎች የሚውተውት ነበር። ይህ ምስኪን፣ በመንገዱ ላይ በሚገኙት የተቦረቦሩ ቦታዎች ሁሉ ላይ ሆን ብሎ ፈረሶቹን በሙሉ ሀይላቸው እንዲጋልቡ በማድረግ ተሳፋሪዎቹ ከአንድ ጊዜ በላይ እንዳቸው በሌላኛው ላይ እንዲወድቁ የሚያደርግ ይመስላል። በዚህ የተነሳ ያገኙትን ሁሉ በመጨበጥ ሲዋከቡ ተጉድተውና ከፍቷቸው ስለነበረ፣ በመንገዳቸው ላይ ምንም ነገር ማየት ሳይችሉ፣ ሶሱቱ የመንግስት መልዕክተኞች እንዲቆዩበት በማለት ጀስዊት ካህናት ወዳዘጋጁላቸው ቻቴ ዴ ሲሚአኔ በድቅድቅ ጨለማ ደረሱ።

ከበርቴው ዴ ሲሚአኔ፣ ግዙፍና ደስ የሚል ጨዋ ሰው ሲሆን፣ የሚያስደስት የክፍለ ሃገር ቅላፄ ይናገራል። ይህ ከበርቴ እንግዶቹን እስከሚቀጥለው ሁለት ቀን ድረስ ይመጣሉ ብሎ አይጠብቃቸውም ነበር። በተፈጠረው አለመግባባት በጣም ቅር ቢለውም የአደን ልብሱን እንደለበሰና በሚያደርገው ተግባር እንግዶቹ እንዳያዝኑበት በቀላል አቀራረብ ሰላምታ ሰጥቶ ከተቀበላቸው በኋላ ባለቤቱንና ሁለት ወንዶች ልጆቹን አስተዋወቃቸው። ልጆቹ በሚደንቅ ሁኔታ ቁርጥ እናታቸውን ናቸው። ረዣዥምና ሹል አፍንጫ፣ ጥቁር ፀጉርና ክብ ፊት ያላቸው ናቸው። በትዳር ብዙ በመቆየት ብዙ ያተጉዳችና ድቅቅ ያሰችው ይህች ሴት በሰጠቻቸው ወጣትነትና ቁንጅና ሳቢያ በነዚህ ሁለት ጠንካራ ልጆችዋ ተደግፋ፣ ባልተቋረጠ ሁኔታ በሚሰጧት አትኩሮት እየታደሰች ያለች መሆኗ ሲታይ ያከራል። በዚያን ዕለት ምሽት ከአደን የተገኘ ምግብ በቢጫ ሰማያዊ የሸክላ ገበታ ላይ ቀርቦላቸው ተመገቡ።

«አያችሁ፣ እንዲህ የተደረገው ልክ እንደቤታችሁ እንዲሰማችሁ ነው» አለ አስተናጋጃቸው እየሳቀ።

ክብ፣ ግዙፍና በጣም በሚያብረቀርቀው ሳህን ጀርባ ላይ የቱርካውያንን ሁኔታ የሚገልፀውን የጌጥ ቅርፅ አሳያቸው። በዚህ ቅርፅ ላይ ሰጉን የሚያድኑ ቱርኮች፣ በአንድ የፏፏቴ ምንጭ አጠገብ ቁርአን ሲቀሩና በረዥም ረድፍ ገብተው ፈረስ ሲጋልቡ የሚያሳይ አለበት።

በሚቀጥለው ዕለት ያሀንኑ ከበርቴ ለአደን አብሮት ሊወጣ ይችል እንደሆነ ፖንሴ ጠየቀው። የአስተናጋጁ ልጆችም ተጨመሩና አራት ሆኑ። ደኑ፣ በሞቃት ጭጋግ ተሸፍኖ፣

ወርቃማ ቅጠሎችም ውሃ ያንጠባጥባሉ። በዚህ ወቅት እሾሃማ ቅርፊት ባለው የሰውዝ አይነት የተሸፈነው ወፍራም ብስባሽ፣ የፈረሶቻቸውን የኮቴ ድምፅ ያፍነዋል። ከኤልኘስ ተራራ በረዷማ ነፋስ አፍንጫዎቻቸውን ሲወጋው የጥድ ደንና የጥድ ሽታ መዓዛ ይደርሳቸዋል።

ከመሸ በኋላ ደረሱ። ማዳም ዴ ሲሚአኔን ከጨፍጋጋዎቹ ከፍሌሀውትና ከአባ ኘላንቴይን ጋር የእራት ሰዓት እስኪያልፍ ድረስ ሰብቻዋ ትተዋት በመሄዳቸው አፈሩ። ይሁንና በአደናቸው ተደስተው፣ ደክሟቸው ነበር የተመለሱት። ምንም እንኳ ሰዓት ቃላት እንኳ በመነጋገር ባይሰዋወጡም፣ በአደናቸው ላይ አርሰ በርሳቸው ጣዕማቸውን የተዋወቁ ወዳጆች ሆነው በመቆየታቸውም ተደስተው ነበር።

አዳኞቹ ልብሶቻቸውን ሰውጠው ቀሰል ያለ ዕራት በሉ። የቀሩት ቀደም ሲል ወደየመኝታቸው ሄደዋል። ፖንሴ በሚቀጥለው ቀን በዚሁ መንገድ፣ በዚያው ጥቁር የወፍ ጉጆና የቁራ አሞራ ያለበትን ቦታ ተከትሎ የመሄዱ ሃሳብ ስጋት ቢያሳድርበትም፣ ሙሴ ዴ ሲሚአኔ፣ ፈረስ ከነኮርቻው ቢሸጥሰትና በዚያ ሊጓዝ ይችል እንደሆነ ጠየቀው። በርግጥ በዚያ መንገድ በቀን ብርሃን በሠረገላ ሊጓዝ ይችላል።

«ሙሉ በሙሉ እገነዘባሰሁ። ወደ ፈረንሳይ ገና መመለስህ ነው። ስለዚህም በታሳቅ ደስታ ልትሰማመደውና በነፋሱ ውስጥ ልትንሸራሸር ፈልገሃል። እኔ ራሴም ብሆን በቤት ውስጥ መዋል በጭራሽ አልችልም ነበር። ለዚህም ነው በየአደባባዩ የማልገኘው። አሁን ሰሸርሸርህ ፈረስ ያስፈልግሃል። ይህንንም ነገ ታገኘዋለህ። ወርቅህን ስሌላ ጉዳይ ስለምትጠቀምበት ያዘው። አግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ስትመለስ ይህን ፈረስ መልስህ ታመጣልኛለህ። ወይም ሌላ ወይም ሰራሽም አታመጣልኝም። አንተን አዚህ ቤት ሁልጊዜም ልንተበልህ ዝግጁ ነን» አለው ከበርቴው።

አራቱም ሰዎች በእሳት ማንደጃው ዙሪያ በአንድ ትልቅ ባለመክዳ መቀመጫ ላይ ተቀምጠው ሳሉ፣ ሙሴ ዴ ሲሚአኔ፣ ስለአቢሲኒያ ጥቂት ነገር እንዲነግራቸው ፖንሴን ጠየቀው። ፖንሴም ሊተርክላቸው ከሚችላቸው ሁሉ አቢሲኒያውያን ዝሆንን እንዴት እንደሚያድኑ ሊነግራቸው መረጠ።

የፖንሴ ትረካ ማረካቸው። ሙሴ ዴ ሲሚአኔ፣ ሴላ ታሪክ እንዲነግራቸውም ለመነው። በመጨረሻም የአቢሲኒያ ጉዞው ታሪክ ከሰሊቱ ረዥሙን ጊዜ ነቅተው እንዲቀዩ አደረጋቸው። እንዲያውም ፖንሴ የግድ መተኛት እንዳለበት ባይናገር ኖሮ እነርሱ እስከ ንጋት ድረስ ሊያዳምጡት ዝግጁ ነበሩ።

የትረካው ስኬት የጥሩ ገድ ምልክት እንደሆነ ሀኪሙ ታየው። ስሰንዞው ሲተርክ ይህ የመጀመሪያው ሲሆን በሰዎች ላይ ባሳደረውም ጥሩ ስሜት ተደፋፈረ። ንጉሡም ተመሳሳይ ስሜት ካሳቸው ያለችግር እማርካቸዋለሁ ሲል አሰበ።

በማግስቱ ጧት ጆን ባፕቲስት በቁንጥንጥ ሽክላ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ከቻቲው ዴ ሲሚአኔ ወጣ። ወደ ቫሌንስ በሚወስደው ጉዳና ላይ ከሠረገላዎች ፍጥነት ጋር በዝግታ ሲሰገር ተሳፋሪዎቹ ሲንጫጫበጉ አይቶ እጅግ ተደሰተ። ሰማዩ፣ ቱርካዊ የማይታይበት፣ ለማያዊና ግራጫ በይት የተቀባ ሳህን ይመስላል ሲል ጆን ባፕቲስት አሰበ።

2

ከጆን ባፕቲስት ጋር ለመጨረሻ ጊዜ በሴሊት ከተገናኙ በኋላ፣ አለስ ስለርሱ በጣም ትሰጋ ነበር። በማግስቱ ጠዋት ግን፣ ደህና መሆኑን ፍራንቾይዝ አረጋገጠችላት። ከሰዓት በኋላ በወይን ተክሉ ውስጥ ከሚያገለግለው ሠራተኛ፣ እናቷ «ምስኪን ሙሴ ማቼ» ብላ የምትጠራው ሰው በሴሊት ጥቃት እንደደረሰበት ሰማች። ሁሉንም ነገር ስላወቀች ተናደደች። ነገር ግን ቁጣዋን ብዙም ሃዘኔታ በማይሰማት «በምስኪኑ ሙሴ ማቼ» ላይ አላነጣጠረችም። ቀደም ባለው ጊዜ ይህን ከመሰለው ሰው ጋር እንዴት ጓደኛ ለመሆን እንደበቃች ስታስብ ይገርማታል። አሁን ግን በሚገባ እያየችውና እንደምታምነውም በሚገባ እየመዘነችው ነው። እርሱን ከጆን ባፕቲስት ጋር ማወዳደሩም ፍርደገምድልነት ነው። በርግጥ በአሁኑ ሰዓት የዚህ ሰው አድርባይነት፣ ወኔ ቢስነት፣ ተፈጥሮአዊ ቅሌቱ፣ ምንም እንኳ በርሱ ላይ ሙሉ በሙሉ ባትደፈፍፍበትም፣ ቁልጭ ብሎ ታያት። የቁጣዋን ነበልባል ሙሉ በሙሉ ያሳረፈችው በአባቷ ላይ ሆነ። በጣም በርግጠኝነት ሙሴ ማቼ ትዕዛዝ በመቀበል እርሷን ለቆንሲሉ እንደሚሰልላት አውቃለች።

አሁን በቅርቡ የተገነዘበችው እውነታ ቢሆንም፣ አለስ በአስተሳሰብዋና በተግባርዋ፣ ምክንያታዊና ፅንፈኛ ሰው አልነበረችም ማለት አይደለም። ሳቅ፣ ጨዋታና ቀልዶችን ላለማወቅዋና ላለማሟላትዋ ሃላፊነቱን በሙሉ በአባትዋ ላይ ከመረችበት። በአሁኑ ጊዜ ከጆን ባፕቲስት ጋር የመለያየትዋንና የግል አስተሳሰብዋንም በአባቷ ላይ አመካኘች። ፍቅረኛዋን ለመጀመሪያ ጊዜ ስታውቀው እርሱ አስቀድሞ ወደ አቢሲኒያ ለመጓዝ ውል ፈፅሞ ነበር። ያ የማንም ጥፋት አልነበረም። በአሁኑ ጊዜ ግን ጆን ባፕቲስት የሄደው በአባቷ ምክንያት ነው። ይህ ሁሉ የሆነው በአባቷ ሃሳበ ግትርነት፣ ሀሳበ ውሱንነትና ለሌሎች ሰዎች በተለይም ለሴት ልጁ ሕይወት ባለው ግዴለሽነት የተነሳ በጋብቻዋ ሂደት ላይ ደንቃራ እያስቀመጠበት ነው። በተጨማሪም፣ ከጆን ባፕቲስት ጋር ሊኖራት የነበረውን የመጨረሻ ጊዜ ለማበላሸት፣ ቆንሲሉ አባትዋ ተከታታይ ሰላይ ስለላክባት ክነነችው። እርሷና ፍራንቾይዝ ልቦቻቸው እየጋለቡባቸው በጠባቦቹ ታክ ጫማዎቻቸው ያንን የተረገመ ሰላይ ለማምለጥ ሲያደርጉት የነበረውን የሚያዋርድ ጊዜ መልሳ መላልሳ በዓይነ ህሊናዋ ሥዕሱን ተመለከተችው። የአደን ትርዒት ነበር። ልክ ነው፣ አባቷ እንዲያድኗትና እንዲያሳድዷት እንደ አደን እንስሳ ይቆጥራት ነበር።

ይህ ደግሞ አውነተኛውን የሃይል ሚዛን የሚያንፀባርቅ ነበር። እርሷና ጆን ባኽቲስት የሚያነፈንፏቸውንና የሚያድኗቸውን ውሾች ለማምለጥ በበቆሎ ማሳ ውስጥ እንደሚደበቁና እንደሚሸሹ ጥንቸሎች አይነት ነበሩ።

እንደለውዝ ቅርፊት ልቧን ከሰበረባት ከዚህ ትዕይንት ተነስታ፣ አሊስ የሕፃንነት ዘመንዋን በሙሉና በትምህርቷ ላይ ስላለፈው ጊዜ መልሳ አሰበች። በርግጥ ያ ዘመንዋ በዚያን ጊዜ በአጠቃላይ ለሴት ልጆች ከተወሰነው የዐዛም፣ ያነሰም አልነበረም። በሕፃንነትዋ፣ አብይ ሃሳፊነትዋና ተግባርዋ በነበረው በሞግዚቷ እጅ፣ አልፎ አልፎ ወላጅ እናትዋ በምትገኝበት ቦታ በሳምንት መጨረሻዎች ላይ እንድትገኝ ትደረግ ነበር። ከዚያ በኋላ አሊስ ወደ እመምኔቶች ትምህርት ቤት ገባች።ይህ ያደገችበት ቦታ በዙሪያዋ እንዳሉት እንደሌሎቹ፣ በሩ ለዓለም ክፍት የሆነ፣ ቅልጥፍናና አዲስነት ያነበረው አልነበረም። ከዚህ ይልቅ በባላገር ጨለማ ሕይወት ውስጥ ከሥልጣኔ ርቃ እንድታድግ ነበር የተደረገው።

እንዲህ ዓይነቶቹ የተገለሉ ሕፃናት የነበራቸው ብቸኛው ተስፋ፣በተቻለ ፍጥነት ወደሌላ የጥገኝነት ግንኙነት ማለፍ ነበር። ይህ ማለት ወደ ማያውቁትና ወዳልመረጡት ባል ቤት ጉዞተው የቤት እመቤቶች መሆን ነው። ተጀምሮ እስኪጨረስ ድረስ ለዚሁ ዕጣ ፈንታ የሚያዘጋጃቸው ይመስል፣ ሕብረተሰቡ በፈረስ ጭራና በብረት ኩቴዎች የታጨቁ ትራሶችን በክብረ በዓላት ጊዜ እንዲለብሷቸው በማስገደድ ትምህርት ይሰጣቸዋል። ካይሮ በሚገኘው በቆንሲሉ መኖሪያ ቤት፣ እነዚህ የአለባበስ ወጐች የተለመዱ መሆናቸውን እንድታውቅ የሚያደርጋት ሰው በዙሪያዋ አልነበረም። እርሷ ግን ክልምድ በመነሣት ትፈፅማቸው ነበር። ነገር ግን ያጠለቀችውን ታኮ ጫማ እንዳደረገች በታደነችበት ምሽት ይህ ልምድ ተበጠሰ። ከዚህ በኋላ ተፈጥሯዊ የሆነው ምን እንደሆነ በብልሃት ግንዛቤ አገኘችበት። ያለችበት የመረብ ድር እንዴት እንደሆነ አወቀች።

ፍቅረኛዋ በመጀመሪያ ባደረገው ጉዞ ወቅት ስሜቷን በጥንቃቄ በመደበቅ አባቷን ዋሽታው ነበር። ይህን በማድረጓ አዝናለች። ለወላጆችዋ የነበራት የአክብሮት ስሜትም በምንም ዓይነት አልቀነሰም ነበር። የሆነ ሆኖ፣ በአሁኑ ሰዓት ግን ሁሉም ነገር ተለውጧል። አባቷ፣ በሚያስነውር ሁኔታ ስላሣደጋት ከዚህ በኋላ ጠንካራ የማመፅ አዝማሚያ ታሰባት። ምንም ዓይነት አግባብነት ያለው የጨዋታ አስተሣሰብ ስልቷን ሊያውክባት አይችልም።

ከአንግዲህ በኋላ ዋጋ ቢስ በሆነ መሣሪያም እኳ ቢሆን ራስዋን ትከላከላለች። እንዲያውም አዲስና ይበልጥ ሃያል የሆኑ መከላከያዎችንም ለማግኘት ጥረት ታደርጋለች።

ከአባቷ ጥሪ እስኪደርሳት ጠበቀች።

ፖንሴ ከሄደ ከሁለት ቀናት በኋላ አባቷ ወደ ቢሮው ጠራት። ቆንሲሉ፣ በሴት ልጁ ላይ አንዳችም ጥርጣሬ የለውም። ራሱን እጅግ የሚወድድ ሰው ስለነበረ፣ በዙሪያው ስላሉት ሰዎች እምብዛም ፍቅር አልነበረውም። የጥላቻ ባህርይም አልነበረውም። በርግጥም በዙሪያው ስላሉት ሰዎች በነፃነት ለማሰብ ችሎታውም አልነበረውም። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ወጣቷን ልጁን፣ ፀሐፊው በማድባት እንዲጠጋት ትዕዛዝ አልሰጠም። ነገር ግን፣ የሙሴ ማቼ በቆንሲሉ ስሜት ላይ ተፅዕኖ ማሣደር መቻልና የፖንሴ የብልግና የጋበቻ ጥያቄ፣ ስለሴት ልጁ አንዳች ነገር እንዲያውቅና በጥበቃ ውስጥ እንድትሆን ገፋፋው።

«ለመሆኑ ሰር ፖንሴ ስለሚባለው መድሃኒት ቀማሚ ያስተዋልሽው ነገር ነበረሽ?» ሲል የጥላቻ ምልክት ሣያሣይ ጠየቃት። ሴት ልጁን ያነጋገረበት የማይለዋወጠው ጨዋነቱ፣ እንደሚያፈቀራት ራሱን አማመነው።

«በርግጥ፣ አዎን አባባ፣ አንተው ነበርክ እኮ ያስተዋወቅኸኝ» አለችው ምንም የተለየ ስሜት በማይታይበት ሁኔታ

በአዳኙ የመጀመሪያ ርምጃ፣ ቆቋ በርግጋ እንድትበርር ማድረግን ካሰበ ተሳስቷል ስትል አሰበች።

«አንግዲህ አሁን ሄጃል። ከዚህ በኋላም ጨርሶ እንደማናየው ተስፋ አደርጋለሁ። ግን እንድትመልሺልኝ የምፈልገው ጥያቄ አለኝ። ምናልባት፣ ከቶም ወደዚህ አካባቢ የመመለስ ጥረት ቢያደርግ ልወስዳቸው የሚገቡኝ እርምጃዎች ይኖራሉ። ለመሆኑ ተገቢነት የሌለው አቀራረብ ቀርቦሽ ያውቅ ነበር?»

አሊስ፣ ጥቁር ለማያዊ ቀሚሷ ላይ የነበረውን እጥፋት፣ የሆነ አስጠሊታ ነገር የምታስወግድበት ይመስል በጭኗ ላይ አስተካክለችው። ምናልባት፣ ከቶም ወደዚህ አካባቢ

የመመለስ ጥረት ቢያደረግ? ስትል አሰበች። አባቴ እንዳይመለስ ለማድረግ ይሞክራል። ነገ ግን ንጉሡ ቢሸልሙት፣ ጆን ባፕቲስት ይህን አባባልም እንዲሁ ያሽንፋል . . .

«ታቅማሚያሰሽ?» አላት ቆንሲሉ

«ያሰፈውን አያሰብኩ ነው። እውነቴን ነው፣ አባባ፣ እንዲህ ያለ ነገር ማለ አልችልም። ስውዱውን ያየሁት ለጥቂት ጊዜያት ብቻ ነበር። እርሱም ቢሆን በነዚህ ጊዜያ ሁሉ በከፍተኛ ስነስርዓት ነበር ራሱን ሲመራ የነበረው።»

አያምነኝም፣ ስትል ለራስዋ አሰበች። ካቺ፣ ካቺ፣ ካቺ፣

«የሚያጠራጥር ቃል ድንገት አፈትልኮብሽ እንዳልተናገርሽ እርግጠኛ ነሽ። አንዳንዴ ባለጌ ግሰሰብ፣ በትህትናሽ ላይ ፍንጭ ያገኘ መስሎት ሥርዐት ይጥስ ይሆናል»

«እኔን፣ አባባ?» አለች ሰማያዊ አይኖችዋን በልጥጣ

የዓይኖችዋ ብሌኖች በቋጥኝ መሃል ያለ ኩሬ ወይም ሐይቅ ያህል ሲሰፉ እንደሚችሉ በዚያም ባለው ኩል የመሰለ የጠራ ውሃ፣ ጠጣሩ ልቧ የምት ሃይሉን እንዲጨምር ማድረግ እንደምትችል ራስዋን በሚገባ ታውቀዋለች።

አባቴም ምንም ካላወቀ፣ በአይኖቼ ውስጥ ከንፅህና በስተቀር ምንም አያይባቸውም፡ ማየት ከቻለ ደግሞ፣ የሚያየው ፖቤ ነው ስትል አሰበች።

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ተንጠራራና ወደ አሊስ ቀርቦ፣ አንድ ትንሽ እንሰላን እንደሚያሻሽ አይነት እጆችዋን ይዞ ያሻሽ ጀመር።

«እርግጥ ነው፣ ጥያቄዎቼ በጣም ግርድፍ ናቸው። ነገር ግን ይህ ግለሰብ የተናገራቸው ነገሮች ስላሉና ምናልባት የሰሚ ሰሚ ትሰሚያለሽ ብዬ ስለምፈራ፣ በተቻለኝ መጠን ሁሉ ልክላከልሽ እሞክራለሁ።?» አላት።

«ምን ነገሮች፣ አባባ?» አለችው እጆችዋን ከእጆቹ እያላቀቀች

«ምንም አይደል። የስካራም ንግግር ነበር። ስውዱው እዚህ ማህበረሰብ ውስጥ እንደተጠራቀሙት ጀብደኞች ሁሉ ወሮበላ ነገር ነው። ማንንም እንዳታይ በተቻለኝ መጠን የምከላከለውም ለዚሁ ነው»

«እመሠግንሃለሁ፣ አባባ» በማለት የመጀመሪያውን ድንገተኛ ጥቃት መፈረካከሷን ርግጠኛ ሆነችና፣ ለመልሶ ማጥቃት ጊዜው የደረሰ መሆኑን አመነች። «ላንተ ባለኝ ውሲታ፣ ከብሬ እስክዛሬ ድረስ አንዲትም ሲጋት ተደርጐበት አያውቅም። የሚያሣዝነው . . . »

«እሺ?»

« . . . እዚህ ፍፁም ተሰላችቼ መኖሬ ነው»

«እውቃለሁ» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ

ከአገጠንብዋ ሄድ አለና፣ እንደገና በተረከዙ ላይ እንደመሽከርከር ብሎ ወደ ልጁ ተመለሰ

«እስከአሁን ድረስ ዜናውን ለመናገር አላቀድኩም ነበረ። እንግዲያውስ ልናገረው። በበኩሌ አስፈላጊውን ዝግጅት ስላደረግሁ በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ አዎን፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከመሰላቸት ትገላገያለሽ»

«እንዴት፣ አባባ?»

«አድርሻለሁ»

አፍቃሪዎች ልብ የላቸውም። አባቷ፣ ወዲያውኑ ለጆን ባፕቲስት እንደሚድራት ሊነግራት እንደሆነ አሰበች።

«ዜናው አስቸጋሪ እንደሚሆንብሽ መረዳት እችላለሁ» አለ ቆንሲሉ። «ሆኖም ግን ይህን ለማከናወን አለመፍጠናችንን ግን ተገንዘቢው»

«ለማን እንዳሰብከኝ ማወቅ እችላለሁ?» ስትል አሊስ በትህትና ጠየቀች

«በቅርቡ ከምታገኚው ሰው ጋር ነው። ሰውዬው፣ ላንቺ ሲል ከፈረንሣይ ድረስ ተጉዟ ብዙ ሙሉ በሙሉ ባልናገርም፣ ግን እውነት ነው። ሰውዬው፣ ሲበዛ ከታላቅ ዘር የተወ ነው። የአጐታችን ልጅ ፖንቻርትሬይን ራሱ፣ ስለሰውዬው ስለተናገረ ይህ በጣም ጥሩ እው ነው»

አሊስ፣ በድጋሚ እጅ ነሣችና ተጨማሪ ጥያቄ ሳታቀርብ ቀረች። ይህ አባ እንዲስደነቀውና እፎይታም የሰጠው መሰለ። እምቢታ ይኖራል ብሎ በርግጥ አልፈራ ሰዚህ፣ ስዚህ፣ ሥልጣኑ እጅግ ታላቅ ነው። ይሁን እንጂ፣ አንዳችም የማቋረጥ ኑ ካልተፈጠረ፣ ጥያቄዎችና የውስጣዊ ስሜት ሁኔታ ካልታወቀ፣ ውስብሰብ ነገር ሳይናገ እንደማይቀር ማስጠንቀቂያ ነው። ማንም ሰው ቢሆን፣ የወጣት ልጃገድ ልብ፣ መሀ ከሚገባው በላይ ረቂቅ ነው ብሎ ሁልጊዜም ሊገምት ይችላል። ሆኖም ግን፣ ማንም ሰው ልጅን በሚገባና በትክክል ካሣደገ፣ ይህ ሁሉ ቀላል ነው ሲል አሰበ። ሙሴ ዲ ማይሌ፣ እንከ በሌለው የቤተሰብ ሥርዓትና ስምምነት አሊስን በፍቅር አያት።

«አባባ፣ አሁን የተናገርከውን ሰው ለማየት ጓጉቻለሁ። ሆኖም፣ ላንተም ይህን ያህ ጠንክር ተደርጐ የተሰጠህን ሃሣብ፣ በዚሁ ሰው ውስጥ ጥሩነቱን አገኝዋለሁ ብዬ ስማሰብ ትን እጠራጠራለሁ።»

ሙሴ ዲ ማይሌ በፍቅር ፈገገ

«ይሁን እንጂ፣ ጋብቻዬ ነገውኑ ይፈፀማል ብዬ አላስብምና እስክዚያው ድረስ አንድ ነገ እንድትፈቅድልኝ አሰምንሃለሁ»

«ንገሪኝ» አላት ቆንሲሉ

«እንዲህ ነው። የካይሮ የአየር ጠባይ አያፈነኝ ነው። እስቲ እንዴት እንደገረጣሁ ተመልከት። ሌላው ቀርቶ እጮኛ የሚሆነኝን ሰው ለመማረክ . . »

«ምን ማለትሽ ነው። ስመለከተሽ ሙሉ በሙሉ ታንፀባርቂያለሽ»

«አዎን፣ ፊቴን ተቀባብቼዋለኋ። ደግሞ ማንም ሰው ስለሰርጉ ያሰውን ስጋት በየዕለቱ አይማረውም። በአሁኑ ጊዜ ጉንጮቼ በተፈጥሮ ይቀላሉ። ግን አባባ፣ እመነኝ ጊዜ እያጠፋሁ ነው»

«ካይሮ ውስጥ ገና ብዙ አመታት እንኖራለንና ልትለማመጂው ይገባሻል» አላት ሙሴ ዲ ማይሌ በማይጣስ የትዕዛዝ ቅላፄ። «እኛ የመረጥንልሽን ሰው ካገባሽ፣ ተከትለሽው ወደሌሎች ቦታዎች ልትሄጂ ትችያለሽ። ሰውዬው፣ በምስራቅ ሜዲቴራኒያን እንዲያገለግል የተወሰነ ዲፕሎማት ነውና፣ አንድ ቀን ከዚህ የባሰ ቦታ ራስሽን ልታገኝው እንደምትችይ ሳስጠነቅቅሽ ይገባኛል። ለምሣሌ ደማስቀስ ወይም ባግዳድ፣ በሌጋሲዮኑ ውስጥ ብቻሽን ተዘግቶብሽ እንደምትቀመጪ ማሰብ ትችያለሽ? እነዚህ ከተሞች ምን እንደሚመስሉ በርግጥ ምንም ዕውቀቱ የለሽም! እዚህ እኮ ቢያንስ የአባይ ለስላሣ ነፋስ አለ»

«ትክክል ነው አባባ። የምፈልገውም በትክክል ያንን ነው። እዚህ ካይሮ ውስጥ ያለውን ማህበራዊ ህይወት ስለማልፈልገው አልወደውም። የምፈልገው ከተፈጥሮ ጋር ብቻ ንክኪ እንዲኖረኝ እና ንፁህ አየር እንዳገኝ ነው። አንተ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ላይ የባላገር ቤት አለህ። እዚያ ከእናቴና ከጥቂት አገልጋዮች ጋር እንድሰነብት ፍቀድልኝ»

«ያ ቤት ለጤና ጥሩ አይደለም። በወንዙም ላይ መርዛም ቢምቢዎች ስላሉ ትታመሚያለሽ» አላት ቆንሲሉ ተናድዶ።

«በዚጋው ጊዜ አዎን። በክረምቱ ግን ጤናማ ቦታ ነው። ካንተ በፊት የነበረው ቆንሲል በየዓመቱ ሁለት ወሮችን እዚያ ያሣልፍ ነበር»

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ በጣም ዋናው ነገር ስለጋብቻው ምንም ተቃውሞ አለማንሳቷ ነው ሲል፣ ቆንሲሉ ለራሱ ተናገረ። በዚህ ጉዳይ ላይ ውለታ ሊዋልላት ተገቢ ነው። እስከ አሁን ድረስ መልካም ፈቃድ ስለሚታይ፣ በዚህ ላይ ተቃውሞን የሚያነሣሣ ነገር አለመስራት ጥሩ ነው።

«እናትሽ ከካይሮ ውጭታ እንድትሄድ አልፈቅድም። ቆንስላውም፣ እርሷን ለረዥም ጊዜ ማጣት አይችልም»

ይህ ግራ የሚያጋባ ቢሆንም እውነተኛ ሃሣብ ነው።

«ቆንስላው» ብሎ ሲናገር ስለቆንሲሉ እያሰበ መሆኑ ግልፅ ነው።

«እንግዲያው ከአገልጋዮቼ ጋር ብቻ እሄዳለሁ» አለች አሊስ

«የትኞቹ አገልጋዮች? ያች ሁልጊዜም ከጉንሽ የማትለየውና መጥፎ ሪፖርት የሰማሁባት ልብስ አጣቢ ነች?»

የሙሴ ማቼ መራራ ሃሞት በርስዋም ላይ ተደፍቶባታል፣ ስትል አሊስ አሰበች።

«ለመሆኑ እስከዛሬ ምን ጥፋት ፈፀመች፣ አባባ?» አለች ትልልቆቹን ዓይኖችዋን በቆንሲሉ ፊት ላይ በዝግታ እንዲሽከረከሩ በማድረግ።

«ያም ሆነ ይህ» አለ ዓይኖችዋን እየሸሸ « ሁለት ሴቶች አብረው ብቻቸውን እዚያ መቆየት አይችሉም። ከቆንስላው ሁለት ዘበኞች ያስፈልጉሻል፣ ከመናፈሻው ራቅ ካለው ዳርቻ ላይ የጥበቃ አዛዡ ጥቂት ሚሊሺያዎችን እንዲመድብልኝ ጠይቀዋለሁ።

«አ! እንዲህ ከሆነ ፈቃድህን አግኝቻለሁ?»

«ለመልካም ባህሪሽ ስል ነው» አለ በሻካራ ድምፅ። «አናም እንደቅድመ ሁኔታ፣ እኔ እንድትመጪ ስጠራሽ ወዲያውኑ ለመመለስ ቃል ስትገቢ ነው። ምክንያቱም ስለማንነቱ የተናገርኩለት ሰው ብዙም አይቆይም»

አሊስ፣ በዚህ ቅድመ ሁኔታ ተስማማችና በጦርነት ድል እንዳደረገች ያህል ራሷን አሣምና ሄደች።

ሙሴ ዴ ማይሌ በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ትዕዛዙን ሰጠ። ከዚያም፣ እርሱ ራሱ በውይይቱ የረካ ስለሆነ ቀረውን የማለዳ ሰዓት ለሚያውቃቸው ሰዎች ሦስት ደብዳቤዎችን ሲፅፍ ቆየ። ከነዚህ አንዱ በፖንሴ ላይ የጥቃት በትሩን እንዲያሣርፍለት የመረጠው፣ ሚኒስትሩ ፖንቻርትሬይን ነው። ቆንሲሉ፣ ፖንሴን ሲገልፀው ሠካራም እንደሆነ፣ አንዳችም የአውነት ጠብታ የሌለባቸውን ታሪኮች እንደሚፈጥር፣ በምኞት የሚነዳና የባለጌነት ባህርይ

ያለው ነው ይሰዋል። ቆንሲሉ፣ ፖንሴ ወደ አቢሲኒያ መጓዙን በሚገልፀው ትረካውም ላይ፣ ትልቅ ጥርጣሬ አለው። እንዲያውም ይህ የማጋነንና የመዋሸት አባዜና ዝንባሌ ያለው ግለሰብ ምናልባት ከሲናር አልፎ እንዳልሄደም ሲል ሃሳቡን አስፍሯል። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ይደግፋቸልና ማሽነፈያም ይሆኑኛል ያላቸው የመከራከሪያ ነጥቦች ደካሞች ቢሆኑም፣ እግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነ በሚቀጥሉት ተጨማሪ ቀናት የሚደርሱት ሌሎች መረጃዎች ቢኖሩ እንደሚያክል ገልጿል።

የመጀመሪያው የመልዕክተኛ ቡድን ከሄደ በኋላ እንደ ሆነው ሁሉ፣ የካፑቺኖች አለቃ የሆኑት ፒማሙና ግዙፉ መነኩሴ ወንድም ፖስኳል፣ ቅሬታቸውን በቁጣ ሊገልፁ ወደ ቆንሲሉ መጡ። መነኩሴው አባ ፕላንቴይን፣ ከአቢሲኒያውያን ጋር ወደ ቤርማይሰስ መጓዛቸውን አውቀው ስለነበር «ፈረንሣይ፣ በተሰየ ላሉት የስብከት ሥርዓት አራማጆች የምታሣየው አድልዎ» በማለት፣ በሚጠቅሱት ጉዳይ ላይ ተቃውሞአቸውን ያቀርባሉ። ለዚህ ቅሬታ ሙሴ ዴ ማይሌ ደስ በሚልና በወዳጃዊ መንፈስ ማንንም በተሰይ እንደማይደግፍና እንዲያውም በሌላ ምክንያት ሳይሆን በወንድም ፖስኳል ወዳጅነት ሣቢያ የርሣቸውን የእምነት ሥርዓት ጥረት፣ አትሙ በፈቀደው መጠን እንደሚደግፍ መለሰላቸው።

«ስለትም የደረሰው በጥሩ ሰዐት ነው። አሁን በቅርቡ ወደ አቢሲኒያ አንድ የጉዞ ዘመቻ ለማድረግ አቅደናል» አሉ ኢጣሊያዊው ካህን

«ሌላ ዘመቻ ልታደርጉ?»

«ለጊዜው ሲናር እንሰነብታለን። ከዚያም አልፎ የሄደ ሰው የለም» ካሉ በኋላ በአታላይ ፈገግታ «ሌላው ቀርቶ የርስም ተረጂና ተመፅዋችም ቢሆን አላስፈም»

«የኔ ተረጂና ተመፅዋች?»

«አምን፣ ሲኞር ፖንሴ!»

ቆንሲሉ፣ይህን ዜና ለመስማት የመጓጉት ስሜት አሣየ። ወንድም ፖስኳል የተናገሩትን እንዲደግሙለትም ጠየቃቸው።

እጅግ በሚታመኑትና፣ ሲናር ከሚኖሩት ወንድሞች በደረሳቸው መረጃ መሠረት፣ ፖንሴ፣ ከሲናር፣ ከሸሸ በኋላ አንድ ሃምሳ ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ድረስ ከወሰኑ አልፎ እንደተጓዘና በአንድ የአቢሲኒያውያን መንደር ውስጥ በቀረጥ ኬላ ላይ ሲያገለግል እንደቆየ፣ ከዚያም አልፎ መጓዝ እንዳልተፈቀደለት፣ በዚያው መንደር ውስጥ ብዙ ወራት ሲጠብቅ እንደከረመ፣ በአገሩ ባህል መሠረት በቀላሉ ሊያደርገው የሚችለውን፣ አንዲት የአካባቢውን ተወላጅ ሴት አግብቶ እንደነበረና ጨርሶ ስላላገኘው ንጉሠ ነገስት ብዙ ታሪኮችን ሰብስቦ እንደተመለሰ በማረጋገጥ ቁሱ ተናገሩ።

በዚህ ንግግር ቆንሲሉ ከመጠን በላይ ተደሰተ። እንዲያውም ይህን ሁሉ ከሰሙ በኋላ ለምን ፈጥነው መጥተው እንዳልነገሩት ካፑቺኑን ጠየቃቸው። እርሳቸውም በበኩላቸው፣ ፈረንሣውያን፣ አንድ አርመናዊ የቀድሞ የወጥ ቤት ሠራተኛ የነበረን ሰው፣ እንደ አምባሣደር አድርገው ተቀብለው ራሣቸውን ሲያዋርዱ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ አርሣቸው ጣልቃ የሚገቡበት ሰበብ ስለሌላቸው እንደሆነ በሽሙጥ ተናገሩ። ይሁን እንጂ ዝርዝር ታሪኩን ወደ ሮም እንደላኩና ሁሉም ካፑቺኖች ሌላው ቀርቶ ፖሪስ የሚገኙትም ጭምር እውነቱን እንደሚያውቁ አብራሩ።

«የሚነግሩኝ ሁሉ ታሳቅ ጉዳይ ነው» አለ ቆንሲሉ። «ሲናር ከሚገኙት አባቶች ሪፖረት ማግኘት ይችላሉ? ሪፖርቱስ በጽሁፍ ነው?»

«ሲናር ከሚገኙት የመነኮሣት አለቃ የተፃፈ ረዥም ደብዳቤ በገዳሙ ውስጥ አለኝ»

«የደብዳቤውን ቅጅ እንዲሰጡኝ በማክበር አጠይቅዎታለሁ። ሁሉንም ነገር እንዲቋረጥ ለማድረግ አሁንም በቂ ጊዜ አለ»

ካፑቺኑ ምንም ማይናገሩ ረዘም ላለ ጊዜ ጠበቁ።

ቆንሲሉ ወጥመዱ ውስጥ ከገባ በኋላ፣ ቁጣውንና ብስጭቱን በወረቀት ላይ ማስፈር ጀመረ።

«የተሰማማን ስለሆነ ፈቃዴን ሰጥቼዎታለሁ። ያቀዱትን ተልዕኮ ለማገዝ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ»

«ቃል ነው?»

«ቃል ነው»

«ጥሩ። ደብዳቤው ዛሬ ማታ በእጅዎ ውስጥ ይገባል» አሉ፣ የመጡበት ጉዳይ የተሣካላቸው አባ ፖስኳል። «ወሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ በእቅዳችን ላይ እንዴት ሊረዱን እንደሚችሉ ላነጋግርዎ አመጣለሁ»

ይህን ከተናገሩ በኋላ፣ ኢጣሊያዊው ካህን፣ ሳይታሰብ በድንገት እንደመጡ ሁሉ ወዲያውኑ ቆንስላውን ለቀው ሄዱ ። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ የካህኑን አጠቃላይ ግልፅነት፣ ጨዋ መሰለው በምስጢርና በድብቅ ከሚሠሩት ከአንኖጢዮሣውያን ጋር በማነፃፀር በጣም እደነቃቸው።

❧

ጊዛ ውስጥ አና ሆኖ የከረመውን ቤት ለማደስና ለማዘጋጀት፣ አገልጋዮች የጥቂት ሣምንት ጊዜ ወስደባቸው። መስኩቶቹን ሁሉ ክፍተው ንፁህ አየር በየማረፊያው እንዲገባ አደረጉ። ከዚያም በመቀጠል ሁሉንም ክፍሎች ከትኩሣት ሕመም ነፃ ለማድረግ በመድሃኒት አጠኑ። በመጨረሻም በሁለት ሠረገላዎች ጭነው ያመጧቸውን ዝርግና ጉድጓዳ ሳህኖች፣ኩባያዎችና ሌሎችም ከሸክላ የተሠሩ የቤት ቁሳቁሶችን በክፍሎቹ ውስጥ ሞሏቸው። በአልጋዎቹም ላይ አዳዲስ አንሶላዎችን አንጥፈው አስጌጧቸው።

ቤቱ ተስተካክሎ ካበቃ ከአንድ ቀን በኋላ፣ አሊስ ከፍራንቾይዝ ጋር መጣች። እንደተገመተው፣ የአሊስ እናት ካይሮ ለመሰንበት ወሰነች። የተከተሏቸው ሦስት አገልጋዮች፣ ሙሉ በሙሉ ሁለቱን ሴቶች ለማገልገል የሚታመንባቸው ናቸው። በርግጥ፣ ሁለቱን ሴቶች ተከትለው ለመምጣት መመሪያ የሚችሉ ብዙ ነበሩ። ምክንያቱም በአጠቃላይ የቤት አገልጋዮች በቆንሲሉ ንፉግነትና ለበታቾቹ ባለው ጥላቻ ላይ አቋም ወስደው ነበር። የሚሊሺያዎች አዛዥ የመደባቸውን ጥቂት ቁርኳውያን ጠባቂዎችን በተመለከተ የተሰጣቸው መመሪያ፣ ከመኖሪያ ቤቱ ራቅ ባለ ሥፍራ ላይ እንዲሰፍሩና ንብረቱን ብቻ ከውጭ ሆነው እንዲጠብቁ የሚል ነበር።

ማዳሞዜል ዴ ማይሌ፣ በሠረገላ ተሣፍራ ከቀትር በኋላ በዘጠኝ ሰዓት ላይ ደረሰች። የለበሰችው ተራ ስማያዊ ጥብቅ የሚያደርግ ልብስና ጥቁር ከፋይ ቀሚስ ሲሆን፣ ጥቅል ፀጉሮችንም በአንድ ነጠላ ሪበን ሸብ አድርጋዋለች። ስለቤቱ ገለባ ሲደረግ ከመስማቷ በስተቀር በአይኗ አይታው አታውቅም። አሁን ስትመለከተው በውሃ ሙላት ጊዜ ዙሪያውን በውሃ በሚከበብ ከፍ ያለ ቦታ ላይ የተሠራ መሰላት። ሕንፃው ራሱ የቱርካውያን ቤተመንግስት የነበረ ሲሆን፣ በአንጨት ቅስቶች በሹል ቅርፅ የተሠራ ነው። መስኮቶችም የአንጨት ርብራብ መከላከያ ያላቸው ክፍት የጥድ ጣውላዎች ናቸው። ባለስምንት ማዕዘን ረዥም ጉልላት ሆኖ፣ የኦቶማኖችን የራስ ቁር የመሰለ ጣሪያ አሰው። በአሁኑ ጊዜ የማይታይበት በጣሪያው አናት ላይ የነበረው የአስልምና ግማሽ ጨረቃ ነው። ይህ ምልክት በአንድ ዘመን ነበረ። በኋላ ግን ገዥው ፓሻ ቤቱን ለፈረንሣይ ቆንሲል ከአንድ ሃምሳ ዓመት በፊት ሲሰጥ፣ ይህን ምልክት አስነሣው።

ሕንፃው፣ የአባይ የተለመደ ሙላት ከማይደርስበት ከፍ ብሎ በጉብታ ላይ የተሠራ በመሆኑ፣ የወንዙን ግራና ቀኝ ዳርቻዎች ቁልቁል ወለል አድርጉ ያሣያል። በሦስቱም ማዕዘንና ቤቱን ከብቦ የሚታየው የደለል አፈር ሜዳ፣ ለም መሆኑ ባያጠራጥርም ቆንሲሉ ስራ ላይ አላዋለውም። በዚህ የተነሣ ለፊ የሣር ምድር ግቢ በመሆኑ፣ ቤቱ፣ ባልተቆራረጠና እጅግ ሠፊ የሣር መስክ ተከብቧል። የቤቱ አራተኛው ጉኑ ወደ ወንዙ የሚያቆለቁል ሲሆን በትላልቅ ዛፎች ተክል የተሸፈነ ነው። የነዚህ ዛፎች ቅርንጫፎቻቸው የተጠጋጉና የተቀራረቡ በመሆናቸው ሌሎች ተክሎች ከስራቸው እንዳይበቅሉ ያግዳሉ። ከዚህ ይልቅ የደረቁ ቅጠሎች እንደ ስጋጃ በጥላው ውስጥ ተነጥፈው እስከ ወንዙ ጠርዝ ድረስ እስካሉት የቁጤማ ተክሎች ተዘርግተዋል። በአባይ ላይ የሚንሳፈፉት ነጫጮቹ ትናንሽ የጠረፍ ጀልባዎች፣ ከቆንሲሉ ንብረት አካባቢ እንዳይቀርቡ የሚከለክለው ቃል፣ ለጀልባ ቀዛፊዎች ሁሉ የተላለፈ ይመስል በርቀት ናቸው። አንድ የእንጨት የመዝናኛና የመሻጋገሪያ ድልድይ፣ ያረጀና ጥቅም የሌለው ተንሣፋፊ ጀልባ ወዳለበት ሃያ ጫማ ያህል ወደ ውሃው መሃል ተዘርግቷል።

አሊስ፣ ቤቱን ተዘዋውራ አየች። በአንግዳ መቀበያ የእንጨት በረንዳ ላይ ቆም ብላ፣ የወንዙን መረር የሚል ነፋስ ወደ ውስጥ በሃይል ሣበች። ይሁንና በዚህ ደስታ ውስጥ ራሷን ብዙም አላቀየችውም።

ፍራንቾይዝን «ነይ» አለቻት። «አቅዳችንን ለመጀመር ሌኮንድ ማባከን የለብንም»

3

የህዳር ወር ቀዘቃዛ ነበር። እጆቹን በተቻለው መጠን በፈረሶቹ ጫንቃ ላይ በማሸሽት ያሚሟቀው ጀን ባፕቲስት፣ ኬላው ላይ ሲደርስ በረዶ ሆኖ ነበር። በራሱ ፍጥነት እየጋለበ ሊሄድና በያንዳንዱ ታላቅ ከተማ መግቢያ ላይ ለመገናኘት ከጉዞ ጓደኞቹ ጋር ተስማምተው ነበር። በመጨረሻም፣ ነፃነትና በራሱ የመመራት ስሜት አድሮበት መንዝ ጀመረ። ወደ መንደሮች እየገባ ከባላገሮች ጋር ይነጋገራል። በየመስኩም፣ ሥራ ፈትተው ከተቀመጡ አዛውንቶች የሚነገረውን ይሰማል። ሊዮንስ ከተማ ውስጥ፣ አንድ የፖስታ ቤት ሰራተኛ መሎጭ ቀይ ላባ ያለበት ሰፊ ባርኔጣ ገዛ። አግረ መንገዱንም የአስፖኝ ንጉስ መሞታቸውን ተረዳ።

ከሶስት ቀናት ጉዞ በኋላ፣ ባለሰረገላዎችና ባለፈረሶች፣ የጀስዊቶች መኖሪያ ቤት ወደሚገኝበት ፎንቴይን ብሉ፣ በውድቀት ሌሊት ደረሱ። ሃይለኛ ነፋስ የሠረገላውን የነሃስ ፋኖስ መብራት በተደጋጋሚ ያጠፋው ነበር። በመንገዱ ግራና ቀኝ በመደዳ የተተከሉት ጥቋቁር ዛፎችም ወደፊትና ወደ ኋላ በሃይል ይወዛወዛሉ። ጀን ባፕቲስት፣ የሚወርደውን ቀዝቃዛ ዝናብ ለመጉረስ በሚል አፉን ሲከፍት፣ ከት ብሎ ሣቀ። የተለየ በሆነው በሀሩር አውራጃ ምድር ለአመታት በመቆየቱ፣ እዚህ ያለውን የአየር ጠባይ መዘንጋቱን ተገነዘበ። በሚቀጥለው ቀን የቀረጥ ተቀባዮችን የከላ ዳስ በደቡባዊ መግቢያ በር አልፈው ፖሪስ ደረሱ። ከዚያም ወደ ዮቭሬ አቀኑ። በጉናቸው በኩል ዝናቡ እንደገና ከመጣሉ በፊት መጠለያ ወዳለበት ለመድረስ ሲገሰግሱ ጥቋቁር ጥላዎችም እንዲሁ ይጣደፋሉ።

የሉዊስ ሌ ግራንዴ ትምህርት ቤት በሆነው የተለየ ሕንፃ ውስጥ ሠፈሩ። በአቅራቢያው በሚገኘው የአውቱኦል መንደር ቤተሰብ ያለው ፍሌሃው፣ በመጀመሪያው ዕለት ተሰያቸው።

ጲፖሎማቱ፣ ያሳደዱት ያህል በጋሪው ተጣድፎ ከሄደ በኋላ፣ «ለፖንቻርትሬይን ራፖርቱን ሊሰጥ ነው» አሉ አባ ፕላንቱይን ክፉት በተሞላበት አነጋገር።

በዚያን ጊዜ ይነገር የነበረው ታላቅ ዜና፣ የስፔይን ንጉሥ ያደረጉትን የጉዛዜ ቃል ሉዊስ 14ኛ የመቀበላቸው ጉዳይ ነበር። ከአብራካቸው የተገኘ ልጅ የሌላቸው የአስፔይኑ ነጋሲ፣ ዘመዳቸውን ለሉዊስ የልጅ ልጅ፣ ለአንጁ ዱክ ተናዘውለታል። በዚህም የተነሣ ታዋቂው የንጉሡ የልጅ ልጅ፣ የማድሪድን ዙፋን ሊይዝ ስለሆነ፣ የፈረንሣይ ንጉሥ ሁለቱንም ግዛተ

ዘውዶች ሊገዙና፣ በአውሮፖና በመላውም ዓለም እጅግ ሃያሉ ሰው ሊሆኑ ነው። ስለዚህም ጦርነት የማይቀር ነገር ነው። ጀስዊቶቹ ይህን ታላቅ ጉዳይ በደስታ ተወያዩበት። በክርስቲያኑ ዓለም ውስጥ እጅግ ታላቁ የሆነው ንጉሥ፣ ክዚህ በፊት ሲያከናውነው ከነበረው ባላነስ፣ የካቶሊክ ተልዕኮውን፣ በተለይም በምስራቁ ዓለምና በአቢሲኒያም ውስጥ የጠባቂነት ሚናውን በግድ ይወጣዋል ሲሉ አባ ፕላንቴይን ያስባሉ። ምንም አዲስ ነገር ባይፈፀምም፣ አባ ፕላንቴይን በሕይወታቸው ውስጥ እጅግ ታላቅ ከሚሉት ተግባር ጋር ይህን ሃሣብ አቆራኙት። ይህ ታላቅ ተግባር ደግሞ፣ የተዳከመውን የቅዱስ ሮማና የሃዋርያትን ቤተክርስቲያን እርሳቸው ወደማያውቋትና ከርሣቸውም ምንም ወዳልጠየቀችው አገር ማምጣት ነበር።

ጆን ባፕቲስት፣ ክዚህ ቀደም ጨርሶ ፖሪስ መጥቶ አያውቅም። እዚያ በገባ በመጀመሪያው ምሽት ወደ ሲየን ወረደ። ፈረሱንም በመርከቦች ማቆሚያ ዳር፣ በተቀዛፊ ጀልባዎችና በማጠቢያ ቤቶች መካከል ውሃ እንዲጠጣ አደረገው። በመጀመሪያ ላይ አዲስ የሕንፃ ግንባታ በሚከናወንበት ሰፊ ሜዳ ላይ ቆየ። ከዚያም ኢንቫሊድን አቋርጦ፣ በመርከብ ማቆሚያው አድርጉ፣ ራቅ ብሎ እስካለው እስከ ፖንትኑዩፍ ተጓዘ። ከዚያም በሰሜናዊው ሰፊ የከተማው ጐዳና ረዥም ዙሪያ ክብ መንገድ ላይ እስከ ባስቲል ድረስ ተጓዘ። እርሱ አገሩን ለቅቆ ከሄደ ወዲህ፣ ሰዎች በልብስ ፋሽናቸው ላይ በጣም ትልቅ ለውጥ እንዳደረጉም ተገነዘበ። ይህን በተመለከተ፣ ካይሮ የሚገኙት ፈረንሣውያን በጣም ኋላ ቀር ሆነዋል። የለበሰውን ምርጥ ሙሉ ልብስ ከዋና ከተማው ነዋሪዎች አለባበስ ጋር ሲያነፃፅረው፣ የሚያሣፍር ሆነበት። በሚቀጥለው ቀን ወደ ሴንት ጃክይስ ሄዶ የብር ጉንጉን ጌጥ ያለበት አረንጓዴ ከፋይ ኮት፣ የሃር ሰደርያ፣ ጥቁር ቦላሌና የእግር ሹራቦችን ገዛ። ይህን የአዘቦት የሥራ ልብስ ለብሶ፣ የከተማዋን አምብርት ዘልቆ ለመግባት ወኔ ተሰማው። ይህን ለብሶ በከተማዋ መሃል ባሉ ጠባብ መንገዶች ላይ የሚንቀሳቀስ ሰው፣ ሌሎች ተጓገዦችና ባለሱቆች የሚናገሩትን አርቲ ቡርቲ አስተያየቶች ሁሉ ሊሰማ ይችላል። አቂሙ ደስ የሚል ነው። ጉራዴ ታጥቋል። አይኖቹም የሚያባብሉ ናቸው። አንድም ሰው አንዳችም ማጉረምረም አያደርግበትም።

በከተማው ውስጥ በራሱ ወጭ ማረፊያ ቦታ ለማግኘት ቁርጠኛ ውሣኔ አደረገ። ጀስዊቶቹ፣ እዚህ ድረስ አምጥተውት በቤተመንግስት ስብሰባ ላይ እንዲገኝም ሁኔታዎችን እያመቻቹ ነው። ይህ ደግሞ በቂ ነው። ክዚህ ባሻገር የነርሱ ሽክምና ዕዳ መሆን አልፈለገም። ይሁን እንጂ ራሱን ለመቻል ሃብታም አልነበረም። የዋና ከተማው ኑሮም ከፍተኛና ውድ ነው።

የያዝኩትን የወርቅ ዱቄት ለንጉሡ በገፀበረከትነት ከማቀርብላቸው ይልቅ፣ የራሴን ነፃነት የማውጅበት ይሆነኛል ሲል ጆን ባፕቲስት አሰበ። ንጉሠ ነገስቱም ይህችን ታህል ትንሽ ነገር በስጦታ ስትቀርብላቸው እንደስድብ ሊቆጥሯት ይችላሉ።

ወርቁንም ወደ አንድ በገንዘብ ሊለውጥለት ወደሚችል ሰው ዘንድ አመጣው። ምንም እንኳ ከረዥም ርቀት ቦታ የመጣ ወርቅ ቢሆንም በዚያን ጊዜ ሊለወጥ ከሚችለው በላይ አያወጣም። ባለገንዘቡም በጥርጣሬ ካየውና ከረዥም ዝምታ በኋላ ቀለል ያለ የኢኩስ ከረጢት ሰጠው። ይህ መጠን ከምንም የተሻለ ነው። ለጥሩ ማረፊያም በቂ ነው ሲል ጆን ባፕቲስት አሰበ።

የማረፊያ ክፍል ለማግኘት ባደረገው እንቅስቃሴ፣ በመጀመሪያ በኢል ዴ ላ ሲቲ ዙሪያና ቀጥሎም በሆቴል ዴ ቪሌ አካባቢ ተዟዟረ። በመጨረሻም የሚፈልገውና የሚስማማውን በቅዱስ ኢዩስታች ቤተክርስቲያን አጠገብ አገኘ። ዓይኖቹን የማረከው የመጠጥ ቤት ምልክት ሰርሶ ሁኔታ ፍፁም የሚስማማ ነበር። ምልክቱም በአንድ የብረት ንጣፍ ላይ ከወገቡ በታች ግልድም ታጥቆ ጦር የያዘ የግዙፍ አፍሪካዊ ቅርፅ የተሣለበት ነበር። ጆን ባፕቲስት፣ ወደዚህ ሱ ቢዩ ኖይር ተብሎ ወደሚታወቀው ቤት ገባ። አስተናጋጁ ባለቤት፣ ረዥም፣ ጐንጮቹ ወደ ውስጥ የተጣበቁበትና አመዳም ፊት ያለው ሲሆን፣ ክራሱ ይልቅ ለደንቆሮቹ የተሻለ ጥንቃቄ የሚያደርግላቸው ይመስላል። ወደ መንገዱ አቅጣጫ ካለው ክፍል ውስጥ ሞቅ ያለ እውነተኛ የሣቅ ድምፅ ይሰማል።

«መጋዘኑን የገዛሁት ከአንድ ልብስ አቅላሚ ላይ ነበር» ሲል ሰውዬው ሞቅ ባለ ፈገግታ ይናገራል፡ «እርሱ የፈለገው ያንን ያልተሰመደ ምልክት ሲሆን እኔም ልጠቅሰት ወሰንኩ»

ጆን ባፕቲስት ወደ ውስጥ ዘልቆ አንድ የተሰቀቀ ክፍል ያገኘ እንደሆነና ዋጋውም ምን ያህል እንደሚሆን ጠየቀ። ሊገኝ የቻለው ከጉረኖ የማይሻል ትንሽ ክፍል ነው። ሰዚያውም ክራዩ ውድ ነው። ይሁንና የራሱ የሆነ የእሣት ማንደጃ ቦታ ያለው ሲሆን፣ ባለቤቱም፣ እንግዳው የሚፈልገውን ያህል ማገዶ ሊያቀርብለት እንደሚችል አረጋገጠለት። ወጣቱ ሰው ከሠሽት እስከ ንጋት ድረስ በቁር ሊቆራመድ የቆየ በመሆኑ፣ የትዝታ ስሜቱም እየዘቀዘቀ ስለነበረ፣ የተነገረውን ዋጋ ተስማምቶ የአራት ቀን ሂሣብ በቅድሚያ ከፈለ። ባለሁለት ክፍል የሆነውን ሻንጣውንና የመድሃኒት ሳጥኑን ለመውሰድ ወደ ጀስዊቶች መኖሪያ ተመልሶ ሄደ። እዚያም፣ ከነርሱ ዘንድ እንደሚወጣ፣ ነገር ግን ፈረሱን ብቻ እንዲጠብቁለት ነገራቸው። አባ

ፕላንቴይን፣ እንዳይወጣና እንዳይሄድ እጅግ አጥብቀው ሞከሩ። ፖንሴ ግን በየዕለቱ ማለዳ በትምህርት ቤቱ አካባቢ በመቆየት ከንጉሡ ጋር ለሚኖራቸው ስብሰባ ይጠሩ እንደሆነ ወሬ እያዳመጠ እንደሚቆይ ቃል በመግባት ጥያቄአቸውን ሳይቀበለው ቀረ። ከዚያም ወደ ሴ ብዙ ኖይሬ በመመለስ አስኪጠግብ ድረስ በቂ እራት በልቶ ውስጥ አካሉን በጣም በሚደነቀው የባርጋንዲ ወይን አሞቀው። የማወቅ ጉጉት ያለው የሆቴሉ ባለቤት፣ ጨዋታ ፈልጎ ቀረበው። ጆን ባፕቲስትም፣ ከካይሮ እንደመጣና የፈውስ ሃይል ባላቸው አዕዋት እየተጠቀመ ሰዎችን የማዳን ሥራ እንደሚሠራ ነገረው።

«ሐኪም ነሃ፣ እንግዲያው!» አለ የመጠጥ ቤቱ ባለቤት በአክብሮት ጉንበስ እያለ።

«ከሞላ ጎደል።» አለ ፖንሴ፣ ሕጋዊ የምስክር ወረቀት ጥያቄን ጉዳይ ሳለመቀስቀስ አስቦ

«አ! ጌታዬ ሙሉ በሙሉ እንጂ! ያለ ስህተት ሙሉ በሙሉ። ክሕክምና ትምህርት ቤት የሚወጡትን እነዚያን ጨካኞችማ አውቃቸዋለሁ። ሊገድሉን እንኳ ባሉ በሌሰን ላይ ይደራደሩናል። ወዳጄ፣ እኔ በዕፅዋት ተአምራዊ ሃይል በተሰይም ክምስራቅ በሚመጡት ላይ እምነት አለኝ»

ጆን ባፕቲስት ነገሩ እንዳይሰፋ ወይም ሰውዬውም ወሬውን እንዳይቀጥል ለማድረግ ተጠንቅቆ፣ ጨዋታውን አልቀጠለም። ወደ ፎቁ እየወጣ ሣለ፣ የሆቴል ቤቱ ባለቤት ሙያውን ከአንዱ ጠረጴዛ ወደ ሌላው እያደነቀ ሲነዛ ሰማው። የአክብሮት አይኖችም ዱካውን ተከተሉት።

ይህ ሥራ ደንበኞችን ይስባል ብለን ተስፋ አናድርግ፣ ሲል አሰበ። እዚህ ከተማ በሚታየው የገንዘብ አወጣጥ፣ የያዝኩት ክረጢት ሙሉ የወርቅ ብናኝ በአጭር ጊዜ ውስጥ ቀልጦ ይጠፋል። ለዚያውስ እዚህ ምን ያህል እንደምንቆይ ማን ያውቃል? ሲል አሰበ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ጀስዊቶች እጆቻቸውን አጣጥፈው አልተቀመጡም። አስፒይን ውስጥ ያጋጠመው ታላቅ ጉዳይ ቤተመንግስቱን ግርግር ውስጥ ስለከተተው፣ የንጉሡን ስሜት ሙሉ በሙሉ ይዘባታል። ይሁን እንጂ ቀሣውስቱ፣ የኢትዮጵያን ጉዳይ በክፍተኛዎቹ መሪዎቻቸው በኩል የማሰማት ዕድል ለማግኘት ጊዜአቸውን ሁሉ በማሣወቅ ስራ ላይ እያዋሉት ነበር። በፈረንሣይ ውስጥ ለሚገኙት ስብዙዎቹ ታላላቅ ሰዎች የንስሃ አባቶች የሚሆኑት የእየሱስ ማህበረሰቦች ንጉሡንም ይጠቀልላሉ። በዚህም የተነሣ፣ በተረት የተሰበጠው የአቢሲኒያ የተልዕኮ ቡድን የጀግንነት ጉዞና ዘመቻ ወሬ፣ በመቶዎች በሚቆጠሩ ታላላቅ ቤቶች ውስጥ

እንዲሰራጭ አደረጉ። ለነዚህ ታማኞች ብዙ የእራት ግብዣዎች በየታላላቁ ሰው ቤት ተዘጋጅቶላቸዋል። ፖንሴ ግን፣ የራሱን ታሪክ ከሁሉ በፊት ለንጉሡ ማሰማት አለብኝ በሚል አቋም የእራት ግብዣዎችን ሣይቀበል ቀረ። ይህን ጠባዩን፣ አባ ፕላንቴይን ደስም ባለ ወቀሣ ይነግሩታል። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን፣ ቄሱ፣ ወደነዚህ ስመጥር ቤቶች ብቻቸውን በመሄዳቸው ታላቅ ክብር ይሰማቸው ነበር። በተመስጦ በሚያዳምጧቸው ሃብታሞች፣ ባለማዕረግ ሰዎችና በውብ ወይዛዝርት መሃል፣ በአጭሩ በሚያንፀባርቁ የሕብረተሰቡ አባላት መሃል መገኘታቸውን፣እንዲህ ባልተቋረጠ ሁኔታ ሲጋበዙ፣ ፊረስ ነጋዴዎች የነበሩት ቅድመ አያቶቻቸው ቢያዩዋቸው ኖሮ እጅግ ይኮሩ ነበር። ቀሣውስት በአጠቃላይ የሚደነቁበት ነገር ቢኖር፣ በተአምር ላይ ብዙ ማለት መቻላቸው ነው። ከፖንሴና ከአባ ዴ ብሬቬደንት የጉዞ ታሪክ ከሚያውቁት ትናንሽ የታሪክ ቃርሚያዎች፣ አባ ፕላንቴይን የሚያቁነጠጥ ታሪክ ይሰሩበታል። በትረካቸው ጊዜ የሚዘልሏቸው ጉዳዮች የራሣቸው ሌላ ድንቅ ተአምር ይሆኑና በድል እድራጊነት ሣጣብ ሲቋጥ፣ሐቀኛ አማንያን ከሆኑ መላው መኪንንት ጋር ያቆራኙታል። ታሪክች፣ ደግመውና ተደጋግመው በመሣፍንቱ ዙሪያ በመነገራቸው የተአምርነትን ክብር ሲይዙ፣ ፖንሴ ከዕይታ ውጭ ሆኖ ቆየ።

ይህ ሁሉ ሲከናወን ጀን ባፕቲስት፣ ሌ ቢደ ኖይሬ ሆቴል ውስጥ አብረውት አራት ከሚበሉ ሰዎች ጋር እግሮቹን በእሣት ማንደጃው አጠገብ አድርጐ ካርታ ይጫወታል። ይህም ካልሆነ፣ በቱ ኢሌሪየስ መናፈሻ ውስጥ ለመንሸራሸር ፀሐይዋ ብልጭ ስትልለት ይወጣል። ከዚያም መስኮቱ ላይ ያለውንና የዘራውን የቆንጥር ፍሬ ውሃ ለማጠጣት ይመለሳል። ወደዚህ ሆቴል የገባ ዕለት የመጀመሪያው ታካሚ ህመምተኛ መጣለት። ሕመምተኛው፣ የአንዲት ምግብ አሣላፊ ሴት ልጅ ሲሆን፣ ያመጣውም የሆቴሉ ባለቤት ሙሴ ራኦል ራሱ ነበር። ሕፃኑ ክባድ የጉሪሮ ምርቀዛ አለበት። ጆን ባፕቲስት፣ ትንሽ መድሃኒት ሰጥቶት ካከመው በኋላ ክፍያ ሳይቀበል ቀረ። ከሁለት ቀን በኋላ፣ ሕመምተኛው ህፃን፣ ተፈጥሮ በራስዋ መስመር ያለድጋፍ እንደምታደርገው ሁሉ፣ በእግሮቹ ቆመ። ሐኪሙ፣ ይህን ጉዳይ ለራሱ ውለታ እንዲሆንለት ለማድረግ ቻለ። ዝናው ወዲያውኑ ናኘና ከዚህ ሥራ ጥቂት ትርፍ ማግኘት ጀመረ።

በዚህ ዓይነት በዋና ከተማው ውስጥ በቆየበት በመጀመሪያው ሣምንት ውስጥ፣ ጆን ባፕቲስት ሁለት በጣም የተራራቁ ዝናዎችን አተረፈ። በማያውቁት መሣፍንትና መኪንንት አካባቢ አምባሣደር ነው ተብሎ ተመሰገነ። ሁለተኛም፣ ጊዜውን በሚያሣልፍበት የድሆች

መኖሪያ አካባቢ ፈዋሽ ተባለ። እንደ እውነቱ ከሆነ ሦስተኛም የሚገባው ዝና ነበረው። ይህኛውን ግን እርሱም አያውቀውም ነበር። ቢያውቀው ኖሮ ግን ቅር ይሰኝበት ነበር። የቤተመንግስቱ ስብሰባ በመዘግየቱ የተነሣ በሙሴ ዴ ማይሌና በካፑቺኖዎች የተሣፈው ደብዳቤ፣ የመንገደኞችን እግር ተከትሎ በመድረሱ የነርሱን ዝና መናድ ጀመረ። ሚኒስትሩ ዴ ፖንቻርትሬይን፣ እዚህን ሰዎች በተመለከተ ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ስለደረሰውና ግንኘ ነታቸውን ከጀስዊቶች ይልቅ ለሮማ በሆኑ ካህናት፣ እስካሁን የተከናወነው የኤምባሲ ጉዳይ የፈጠራ ሥራ እንደሆነና ፖንሴም አስመሣይ አጭበርባሪ ነው የሚል ወሬ አናፈሰ።

ምንም እንኳ እስከአሁን በጣም ጠንካራ መሠረት ባይዝም፣ ይህ አስከፊ አንቅስቃሴ መቀጨት ይገባዋል ሲሉ አባ ፕላንቴይን አሰቡ። ከንጉሡ ጋር ሊኖር የሚችለው የስብሰባ ግንኙነት ለጥቂት ጊዜ ሊከናወን ባይችል፣ አስከዚያው ድረስ መጠበቁ ግን ጀልነት ይሆናል። ግርማዊ ንጉሠ ነገስት፣ የልጅ ልጃቸው ወደ አስፒይን እንዲንዝ ዝግጅት እያደረጉ ሲሆን ምናልባትም ጥቂት መሠረታዊ የአገዛዝ ሐሣቦችንም እየመገቡት ይሆናል። ስለዚህም አባ ፕላንቴይን በትምህርት ቤቱ አጠገብ ወደ ሚገኘው መኖሪያቸው ፖንሴን ጠሩት። ሐኪሙም፣ በአንድ ማለዳ ሁለት ህመምተኞች ትቶ ደረሰ። ጐንጮቹ በቅዝቃዜው የተነሣ ገርጥተዋል።

«ውድ ወዳጀ» አሉ አባ ፕላንቴይን ከአንገት በላይ በሆነ አነጋገር፣ «የሆኑ ቅናት ያንገበገባቸው ቡድኖች፣ አንተ ወደ አቢሲኒያ ያደረግኸው ጉዞ ሙሉ በሙሉ የፈጠራ ነው ብለው ለመናገር ወኔ አግኝተዋል። እኛ እንኳ በጥላቻ የተሞላውን ትችታቸውን በሃይማኖታዊ መስመራችን በሚገባ እናውቃቸዋለን። ይህን ስህተታቸውን አሁኑኑና በማያጨቃጭቅ መልኩ ማጋለጥ ይኖርብናል። ስለሆነም መልካም ፈቃድህ ከሆነ እንግዲህ እዚህ ደርሰናልና ንጉሡ የሰጡህን ደብዳቤ ስጠኝ፣ በአስቸኳይ ላስተረጉመውና የተረጋገጠ ላስደርገው። ከዚያም በኋላ በጋዜጦች ላይ እንዲታተም በማድረግ ለእንዴና ለመጪረሻ ጊዜ የዓላማችን እውነተኛነት እንዲሰራጭ እናደርገው»

የፖሊስ ግርግርና ሁካታ፣ ጆን ባፕቲስትን ሁሉም እንዲምታታበት አድርጐታል። ለመገናኘት ወደተቃጠረበት ወደ ቅዱስ ጄኩይስ ሲያመራ በፍጥነት እየሰገሩ የሚያልፉትን ሰረገላዎች፣ ግራጫ የለበሱ የንጉሡ የክበር ዘበኞችን ስኳድሮንና ተኳክሰው የወጡ ወይዛዝርትን ፈዝዞ ሲመለከት፣ ከጀስዊቶች ጋር ያለውን ተልዕኮ፣ በተለይም ሊይዘው ይገባው የነበረውን ደብዳቤ ፊፅሞ ረስቶታል። በርግጥ ይህ ደብዳቤ የሚባለው ከአንድ ቁራጭ ወረቀት

የማይበልጥ፣ ለዚያውም አርሱ ራሱ የፃፈው ሆኖ በእማት መቆስቆሻ ሰም አቅልጦ እንደማህተም የሠራው ነው።

«የንጉሡ ደብዳቤ?» አለ አይኖቹ ቡዝዝ እንዳሉ። ከዚያም ትዝ አለው። «አ! አዎን። ይቅርታ ያድርጉልኝ። ይህ ቅዝቃዜ አዕምሮዬንም አደንዝዞታል። አዩ አባቴ፣ ይህ የማይቻል ነው»

«ለምን ቢሉ?»

«ጠፍቶብኛል»

መብረቅ ወርዶ ክፍሱን ቢመታውና ኮርኒሱንም ለሁለት ቢክፍለው ኖሮ ይህን ያህል አባ ፕላንቴይን የሚናገሩትና የሚሉት አያጡም ነበር።

«እንዲህ በቀላሉ! ጠፋ ነው የምትለው። ለመሆኑ የምትናገረው ምን ሊሆን እንደሚችል ትገነዘባለህ?»

ከዚያም፣ ጥቁር ዘርፋፋ ቀሚስ የለበሱት ሰው፣ ራሣቸውን ከተቆጣጠሩ በኋላ ከፍ ባለ ድምፅ ተናገሩ። «ና፣ ና፣ ና! ልታገኘው ይገባሃል። የምትለው ሁሉ ሊሆን አይችልም፣ በቃ ሊሆን አይችልም። በሁሉም ፅቃ ውስጥ ፈልገው። መመለስ ካለብህም አይኖችህን መሬቱ ላይ ተክለህ እስከማርሴይ ድረስ ትሄዳለህ»

«አይሆንም» አለ ፖንሴ፣ በትንሿ ታሪኩ ላይ ጉዳዩን ሊዘጋ ፈልጐ። «ይመኑኝ፣ ምንም አያደርግልንም። የጠፋብኝ ደግሞ በጀልባው ላይ ነው»

«ወደ ማርሴይ አንድ መልዕክተኛ እንላክ። ጀልባው እስከአሁን ድረስም ምናልባት እዚያው ሊሆን ይችላል። ወይም እንዲያቆመው ሊያደርግ የሚችል ሌላ ፈጣን ጀልባ ልንልክ እንችላለን»

ጆን ባፕቲስት ጭንቅላቱን አነቃነቀ

«አየነገርኩዎት፣ ጥቅም የለውም»

አንድ ወንበር ሳብ አደረገና በጐን በኩል አንዱን ክርኑን በጀርባው በኩል አሣርፎ፣ መጠጥ ቤት ውስጥ ያለችግር እንደሚዝናና ሰው ተቀመጠበትና የሚከተለውን ታሪክ ነገራቸው

«ሣርዲኒያን ሀሪን ልንጨርስ ስንል ነበር። እርስዎ እንደተሰመደው በመርከቡ ፊት ባለው ክፍል ውስጥ እንደነበሩ በሚገባ አስታውሣለሁ። እንደሚመስለኝ ይፀልዩ ነበር።

የለም፣ ምሣሌዎችን ያነብቡ ነበር። አዎን ልክ ነኝ። ምሣሌዎችን ያነብቡ ነበር። የባህሩ ወሰል ቢያንስ ሦስት ጫማ ርዝመት ያህል ባለው ትልቅ አሣ እንቅስቃሴ መስመር ያበጃል፡ ስንመለከታቸው የሚከተሉን ይመስል ነበር። ወደ ምግብ ማብሰያው ክፍል ወርጀ የደራረፃ የዳቦ ቅርፊቶች በማምጣት አቅጣጫቸውን ላስለውጣቸው እችል እንደሆነ ለማየት ወረወርኩላቸው»

«እናስ?» ሲሉ ጀስዊቱ ይበልጥ እየከፋቸው

«እንደገመትኩት ሠራልኝ! አሦቹ አቅጣጫቸውን ለወጡ! ወደ ዳቦው ቀጥ ያለ መስመ ሰሩ»

«ከአሣህ ጋር ዲያብሎስ ይውሰድህ» አሉ አባ ፕላንቴይን «እና ደብዳቤው ምን ሆነ»

«ከኪሴ ወደቀብኝ»

«መርከቡ ወሰል ላይ»

«አይደለም ውሃው ውስጥ»

ካህኑ ራሣቸውን ለማረጋጋት እጀቻቸውን በሾላው ጣውላ ጠረጴዛ ላይ አሣረፉ

«እናም ከነዚያ ውስጥ ሶስት የሚሆኑ ጭራቆች ወረቀቱ ላይ ሲራኩቱና ወረቀቱ ብጭቅጭቅ ሲያደርጉት አየሁኝ ብልዎ ያምኑኛል፣ አባቴ» አላቸው ፖንሴ እየተሚሚቀ

ጀስዊቱ እጃቸውን ልባቸው ላይ አሣረፉ። የሚተነፍሱ አይመስሉም።

«እና ምን ገጠመዎት አባቴ፣ አመምዎት እንደ» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቃቸው።

ጀስዊቱን በራሱ ወንበር ላይ እንዲቀመጡ ካደረጋቸው በኋላ፣ አንድ አገልጋይ ከስኪር የሚዘጋጅ አንድ ብርጭቆ ጠንካራ የአልኮል መጠጥ እንዲያመጣ አዘዘ።

አባ ፕላንቴን፣ ወዲያውኑ ጠንካራ ጣውላ ሆነው ከደንገተኛው ሕመማቸው ተሻላቸው። ፕላንቴይንን ሊረዷቸው የመጡ ሌላ ቄስ፣ ሕመምተኛው አርሱን ሲያዩት የስሜት መረበሽና ቁጣ የሚፈጠርባቸው መስሏቸው፣ ፖንሴ ለቅቆ እንዲወጣ ምልክት ሰጡት።

አስከዚህ ጊዜ ድረስ፣ ጆን ባፕቲስት የሚመርጣቸው ታካሚዎቹ ቤት የለሾችና ሥራ አጥ በመሆን በሉ ቢዩ ኖይሬ ውስጥ አጣቢዎች ከሆኑት መካከል ነበር። የሆቴሉ ጥቂት ክፍሎች የተከራዩት ለአነስተኛ ነጋዴዎችና በማይታወቅ ሥራ ላይ ለሚዞሩ የውጭ አገር ሰዎች ነው። መጠጥ ቤቱ ቢጋሪ ነጂዎች፣ በወታደሮችና በአቅራቢያው ባለው ቦታ ላይ የሚሠሩ ወዝ አደሮች ባለማቋረጥ እንደተሞላ ነው። ሙሴ ራኦል፣ በወዳጃዊ ሁኔታ ሰላምታ ያቀርብላቸዋል። ጆን ባፕቲስት፣ ከፕላንቴይን ጋር ከነበረው ግንኙነት በተመለሰ ምሽት፣ የሆቴሉ ባለቤት ይጠብቀው ነበር። ወደ አንድ ተለምረኛ የሆነ ሕመምተኛ ቤት ሊወስደው ስለፈለገ ስለህመምተኛው ሲናገር እንኳ በአክብሮት እሸሽ ይላል።

የሰውዬው መኖሪያ በዚያው መንገድ ላይ ነበር። እንዲያውም ከመጠጥ ቤቱ በቀጥታ ባሻገር ነው። የመኖሪያ ቤቱ ፊት ለፊት የድንጋይ ሕንፃ ከፍታ፣ ግልብጥ የሚል ከሚመስለው ግማሽ የጣውላ ስሪት ከሆነው ክሌ ቢዩ ኖይሬና በዙሪያው ካሉ ደሣሣ ጉጀዎች ጋር ተቃራኒ ነው።

«ከግማሽ ምዕተ አመት በፊት» ሲል ባለ ሆቴሉ ቀጠለ «ንጉሡ በጠመንጃም ይሁን በጉራዴ መፋለምን ህገወጥ ከማድረጋቸው በፊት፣አሁን የምወስድህ ቤት ፖሪስ ውስጥ ታላቅ የሻቦላ ግጥሚያ ማዕከል ነበር።»

«ኧረ! እንዲህ ከሆነማ ጉራዴዬን ማምጣት ነበረብኝ!»

«በዛሬው ዘመን አንዳችም የሚያስፈራ ነገር የለም» አለ ሙሴ ራውል ወደ ሕመምተኛው ቤት ከመድረሳቸው በፊት፣ ለፖንሴ ጥቂት መረጃዎች ለመስጠት እያሰቆመው፣ «ቤቱ አጅግ ለተከበረና በፖርሳማው ውስጥ ለረዥም ዘመናት ሕግ አውጭ ሆኖ ይሠራ ለነበረ ከበርቴ ነበር የተሸጠው። ባለቤቱ፣ ከሃያ ዓመቶች በፊት በወረርሽኝ ሳቢያ ሞታበታለች። ይህ አጋጣሚ ሰውዬውን በአግዚአብሔር እንዳያምን አድርጐታል ብለው ያወሩበታል፣እኔ ግን አላምንም። በጣም እርግጠኛ የሆነው ግን ሁለቱን ልጆቹን በሚገባ ማሣደጉ ነው። ልጆቹ በአሁኑ ጊዜ ያደጉ ስለሆኑ እዚህ የሚመጡት አልፎ አልፎ ነው። ሴት ልጁ፣ የውጭ ተወላጅ ስላገባች፣ የምትኖረውም ውጭ አገር ነው። ወንድ ልጁ በኢስት ኢንዲስ ክፍለ ጦር ውስጥ በማገልገል ላይ ነው። ሰውዬው አሁን የሚኖረው ብቻውን ቢሆንም፣ ፍልቅልቅ ፀባይ ስላለው በመኖሪያ ቤቱ ውስጥና አልፎ አልፎም ወጣ እያለ መዝናናት ይወዳል። ባለፉት ስድስት

ወሮች ግን ብዙውን ጊዜ ታማሚ ሆኖ ቆይቷል። የሕመሙ ስቃይ በጣም ከባድ ስለሆነ አንዳንድ ጊዜ ስቃዩ ያስጮኸዋል። የስቃይ ድምፁ ሌሎች አላፊ አግዳሚዎችን እንዳይረብሽ በማሰት በቤቱ ሌላኛው በኩል መኝታውን እስከለወጠበት ጊዜ ድረስ እስከ ሆቴሉ ይሰማ ነበር። ሐኪሞች፣ እርሱንም ገንዘቡንም በሚያላፍር ሁኔታ ነው የያዟቸው። በእውነቱ ገድለው ገንዘቡን ሊወስዱበት የሚንቀሣቀሱ ይመስላሉ። ሕጋዊውን መንገድ ተከትሰው አስቀድመው ሊያጠፉት እንደሆኑ ርግጠኛ መሆን ትችላለህ። በአሁኑ ጊዜ የምትጠብቀው አንዲት የቤት ሠራተኛ ብቻ አለችው። እንደ ዕድል ሆኖ ሴትዮዋ ደህንነቱን የምትከታተልለት ቅድስት ሰው ነች። ስላንተ ነግሬው ነበር። ባለፈው ምሽት በጣም አስፈሪ ድንገተኛ ሕመም ገጥሞት ነበር። ዛሬ ጧት ይህችው የቤት ሠራተኛው መጥታ አንተ እንድታክመው የሚፈልግ መሆኑን ተናገረች።»

ይህን ተናግሮ፣ ሙሴ ራኦል ወደ በሩ ተጠግቶ የብረት ስንሰለት ሣበ። በጣም በርቀት፣ ከአናው አዳራሽ ባሻገር ደወል ሲንቃጨል ሰሙ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሠራተኛይቱ መጣች። ፊትዋ ሙሉ በሙሉ የተሸበሸበ ሲሆን አይኖችዋ ግን እንደወጣት ይንቦገቦጋሉ። ወገቢ ላይ የታሠረ ሽርጥ ለብሳ ፀጉርዋ ላይም ሻሽ ሸብ አድርጋለች።

«ፍራንቾይዝ፣ እሱ አሳዳሪሽን ሰማየት መጥቷል» አላት ባለ ሆቴሉ

ስሟ ሲጠራ፣ ጆን ባፕቲስት ደነገጠ። የአሊስ ሃሣብም መላ አካሉን እንደ ፖቤ ሰነጠቀው። ወዲያውኑ ግን መለስ አለ። ሠራተኛዋ፣በሸላ ጣውላ የተሠሩ ሣጥኖች በተደረደሩበት ረዥም ጨለማ መተላለፊያ እየመራች ወሰደቻቸው። በአሁኑ ጊዜ እና ቢሆኑም፣ አዳራሾቹ በሙሉ አንድ ዘመን ላይ በቤተሰብ የተሞሉና በሕፃናት ጫጫታ የደመቁ እንደነበሩ ለመገመት የሚቻልባቸው ናቸው። የሚንሣጠጥ ደረጃ ወጥተው፣ ሃምራዊ የቀለም ንድፍ የተጌጠበትና ቀይ ከፋይ መጋረጃ የተጋረደበት መኝታ ክፍል ውስጥ ገቡ።

ሰውዬው፣ የናይለን አንሶላ በተነጠፈበት አልጋ ላይ ተጋድመው ይጠብቋቸዋል። ረጅም ሰው ናቸው። ፊታቸው ክብና ፀጉራቸውም በአጭሩ የተቆረጠ ሽበቶ ነው። በሕመም ስቃይ በተጨማደደ ፊታቸው ላይ ደካማ ፈገግታቸውን በግድ አሣዩ።

ባለሆቴሉና ሠራተኛዋ ሴት ወጣ እንዳሉለት፣ ፖንሴ ጠየቃቸው። ሕመምተኛውን መረመራቸው። ታማሚው ስቃዩ የት ላይ እንደሚበረታ ላለመጮህ ጥረት እያደረጉ ያመለክቱት ጀመር። ረዘም ላለ ጊዜ አዎን ወይም አይደለም በማለት በሞንቅላት ማወዛወዝ

ብቻ እንዲነግሩት በማድረግ ጠየቃቸው። በመጨረሻም የሕመሙን ምንነት የተገነዘበ መሆኑን በሃሣቡ ካረጋገጠ በኋላ፣ በሚቀጥለው ማለዳ እንደሚመለስ ቃል ገብቶ ተሰናብቷቸው ወጣ።

የሌሊቱን አኩሌታ በላይ፣ በማቀጥለው ቀን ስለመምተኛው የሚሰጣቸውን መድሃኒት ሊያዘጋጅ አመሸ። ይሁን እንጂ የህመምተኛው ስቃይ አልነቀሰም። በዚህም የተነሣ ቀጣዩን ከሰዓት በኋላ ሁሉ ሌላ አዲስ መድሃኒት ሊያዘጋጅ ቆይቶ አመጣ። ይህኛውም መድሃኒት ከመጀመሪያው የተሻለ ውጤት አላመጣም። በሚቀጥለው ምሽት ጥረቱን ወደ ሌላ አቅጣጫ አዞረ። ሜትር ዠረሚ አዚህ ሆኖ፣ ግሩም መድሃኒት በማዘጋጀት ሊያግዘው ባለመቻሉ አዘነ። በመጨረሻም፣ በሚቀጥለው ማለዳ ለህመምተኛው ከሲስተስ ቁጥቋጦ ወተት የተዘጋጀውን ሦስተኛውን መድሃኒት አመጣላቸው። ይህ መድሃኒት ከግማሽ ሰዓት ባነሰ ጊዜ ውስጥ የማረጋጋት ውጤት አሣየ። የስቃዩ መቀነስ በሕመምተኛው አይኖች ውስጥ በሚስተዋሉት መርካቶች ፊታቸው ላይ ሊነበቡ ይስተዋላሉ። እፎይታው፣ በፈንታው ሕመምተኛው እንዲያንቀላፉ ረዳቸው። የዚያን እለት ማታ ሕመምተኛው ጆን ባፕቲስትን እንደገና አስጠሩት። ወጣቱ ሰው ሲደርስ ሕመምተኛው ልብሶቻቸውን ለብሰውና ተቀምጠው አገኛቸው።

«እባክህ ተቀመጥ» አሉት ሰውዬው፣ በወዳጃዊ አነጋገር። «ራሴን እንዳስተዋውቅህ ፍቀድልኝ። ስሜን የምታውቀው አይመስለኝም። ሮበርት ዱ ሣንግራይ እባላለሁ።»

4

አሊስን ወደ ጊዛ ተከትለዋት ከሄዱት አሽከሮች አንዱ ሚካኤል ነበር። ይህ ከሱክሶር የመጣ ሽበቶ የኮፕቲክ አማኝ፣ ተቀያያሪዎች የፊረንሣይ ዲፕሎማት ቤተሰቦችን ላለፉት ሃያ አመታት በፈረስ አጣቢነትና በግልቢያ አስተማሪነት ቆንስላው ውስጥ ሲያገለግል የኖረ ነው። ግብፃውያን፣ ለጌቶቻቸው ያላቸውን በተለይም እመቤታቸው ሴትና የደስ ደስ ያላት ከሆነች የሚያሣዩትን የፍርሃት አድናቆት ለአሊስ ያሣያታል። በመጀመሪያ ላይ ምን እንደምትፈልግ ሊረዳት አልቻለም። በኋላ ግን የግልቢያ ትምህርት እንደምትፈልግ ጠየቀችው። እንደገመተው ሁለቱንም እግሮችዋን በፈረሱ አንድ ጐን በማድረግ በአጥር ግቢው ዙሪያ ለመዟዟር የፈለገች መሰለው። ለዚህም የሚስማማውን ከቤቱ በታች ሣር የለበሰ ሰፊ የመጋለቢያ ቅጥር ቦታን መረጠ። በሁለተኛው ቀን ልምምድዋን እንድትደግመው ፈረሱን አዘጋጀላት። አሊስ ግን ችሎታዋን በፍጥነት ማሻሻል እንደምትሻ ነገረችው። አስንጋውን ሲያስጮህበት ፈረሱ የዝግታ ስግሪያ ጀመረ። ሰስተኛውን የልምምድ ግልቢያ ለማድረግ ዝግጅት እያደረገችና ሽማግሌው ፈረስ አጣቢ ቅጥሩን እያጠባበቀ ሣለ አሊስ ቀረበችው። በቀጥታና በማያወላውል አይነት ተመለከተችው። ከዚያም በወጣት ሴት ልጅ ላይ ሊያስፈራ በሚችል ቁርጠኝነት ለስለስ ባለ ቋንቋ አቋሟን ገለፀችለት።

«ሚካኤል፣ አየህ፣ ብዙ ጊዜ የለንም። አባቴ በማንኛውም ቀን ወደ ካይሮ ሊጠራኝ ይችላል። እስክዚያው ድረስ ግን ግልቢያ መማር እፈልጋለሁ። ግልፅ ነው? በኮርቻው ላይ ሁለት እግሮቼን በአንድ ላይ አድርጌ በጐን የመቀመጡንና በተወሰነው ክበብ ውስጥ የመዘሩን ነገር ከእንግዲህ እንርግው። የወንዶችን ኮርቻና ጥንድ መኮርኮሪያዎችን ጫንልኝ። ማንኛ ውንም ነገር ሊቋቋም የሚችል ወፍራም ቦላሌ አሰብግለሁ። ልዩ ልዩ አይነት የፈረስ እርምጃዎችን፣ ስግሪያዎችን፣ ግልቢያዎችን፣ እንዴት እንደሚዘለል፣ እንዴት በፍጥነት ወደፈለግሁበት ቦታ መጋለብ እንደምችል አስተምረኝ።»

ሽማግሌው ሰውዬ ቢገርመውም፣ ትዕዛዝዋን ተግባር ላይ አዋለው። ከፈረስ ላይ ሳትወድቅ ግልቢያ መማር አትችልም ብሎ ሰጋ። በርሱ ስሀተት የተነሣ ብትወድቅና አንድ አጥንትዋ ቢሰበርስ? ቆንሲሉን አይወደውም። ነገር ግን ይፈራዋል። ይህን የስጋት ችግሩን፣

አሊስ አስወገደችለት። ምንም አይነት አደጋ ቢገጥማት ሙሉ በሙሉ ተጠያቂነቱ የራስዋ እንደሆነና ፈረሱንም ሙሉ በሙሉ በራስዋ ፍላጐት እንደመራችው እንደምትገልፅ ነገረችው።

ርግጠኛ ቃሏን ሲቀበል፣ ሚካኤል ሥራውን በፈቃደኝነት ገባበት

በአንድ ሣምንት ውስጥ ፍርሃቱና ስጋቱ ወደ ኩራት ተለወጡ። ውጣቷ ተማሪው እጅግ ድንቅና ፈጣን አካላዊ እንቅስቀሴ ማድረግና አጀማመሯም በሚያስደስት የአቀማመጥ ችሎታ መሆኑን ተገነዘበ። ለተፈጥሯዊ ሞገስዋና ለማያጠራጥረው ድፍረትዋ ምስጋና ይግባውና፣ ፈረስዋን ጠበቅ፣ ነገር ግን ሰስለስ ባለ አዛዥነት መቆጣጠር ቻለች።

በአጭር ጊዜ በአግር መንገዶች ላይ መጋለብ ጀመረች። ርዳታ የምትጠይቀው ብቻዋን ለትወጣ ስትል ብቻ ነው። ምክንያቱም ያዘጋጀላት አንድ ፈረስና አንድ ኮርቻ ብቻ ነው፣ ከዚህም ባሻገር ለጋላቢዎች ሁሉ ምክርና ትምህርት የሚሰጠው አዛውንት ባለበት የቁርጥማት ሕመም ሳቢያ እርሱ አይጋልብም። እንደ ጥንቃቄ ቤቱንና ንብረቱን ለመጠበቅ ተመድቡው በመግቢያው አጠገብ የሠፈሩት ሚሊሺያዎች፣ የአሊስን ግልቢያ በንቃት ይከታተላሉ። በየዕለቱ ማለዳ አንድ ጋላቢ ከግቢው ወጥቶ ሜዳውን ሁሉ አቋርጦ ገበሬዎች በቀይ አፈር የሰሩትን የግድብ ቦይ አልፎ ሲሄድ ይመለከታሉ። ሚሊሺያዎቹ ይህን የሚያደርገው ወንድ ሰው ነው ሲሉ ያስባሉ። ምክንያቱም፣ አሊስ ፀጉርዋን በሰፊ ባርኔጣ ስር ስለደበቀችውና ቅርፅዋን ሊደብቅላት የሚችል ሰፊ ሸሚዝ ስለለበሰች በሚገባ ሊለዩዋት አይችሉም።

የግልቢያ ልምምዱ ፍፁም ሊያደክማቸው ቢችልም፣ ውጣቷ ወይዘሪት ግን ልታቋርጠው አልፈለገችም። በርሷ ጥያቄ መሠረት እነርሱ ከደረሱ አንድ ቀን በኋላ፣ ሜትር ዠረሚ በጀልባ መጥቶ ተቀላቅሏቸዋል። ወደ ወደቡ ዳርቻ በውድቀት ለሊት ያለ አንዳች ረዳት ረዥም የእንጨት ሣጥን ተሸክሞ እስከቤቱ ድረስ ዘለቀ። ይህ ረዥም የእንጨት ሣጥን ከመሬቱ ጋር በተጋጨ ቁጥር የብረት ቅልጭልጭታ ድምፅ ይሰማበታል። ከዚህ ረዥም ሣጥን ውስጥ እጅግ ብዙ የተቋጠሩ ገመዶችን፣ ሁለት የደረት መከላከያ የቆዳ ጋሻዎችንና ሁለት የሸቦላ ጭምብሎችንም አወጣ።

በዚያኑ ዕለት ማታ፣ ወደ አባይ አቅጣጫ በሚወስደው የእንጨት መተላለፊያ መድረክ ላይ፣ አሊስ የመጀመሪያውን የሸቦላ ግጥሚያ ትምህርቷን ወሰደች። በዚህ አይነት ግጥሚያ ላይ ከሜትር ዠረሚ ጋር እኩል ለእኩል የሚሆንበት ነጥብ የለም። ውጣቷ ተማሪ የምትፈልገውን ከተገነዘበ በኋላ እንደ ወንድ ክስተርና ጠበቅ ባለ ሁኔታ ያዛት።

ከዚህ በመቀጠል፣ ፍራንቾይዝንም እንዲያስተምራት አሊስ ጠየቀችው። እንዲህ ከሆነና እርሱ ከዚያ ቦታ እንዲሰቅቅ የሚገደድ እንኳ ቢሆን፣ ሁለቱ ሴቶች ልምምዳቸውን በጋራ ሊቀጥሉ ይችላሉ። በሁለተኛው ትምህርታ ላይ ባጋጠማት ግራ መጋባት የተነሳ፣ አሊስ በውስጧ ፈገግ አለች። ፍራንቾይዝም፣ የአጀማመርዋን ገልጃጃነት አጋነነችባት። እኔ የለሁበትም፣ የሚል ማስተባበያ ለማቅረብ የማይችሰው ሜትር ዝርሚ ስሜቱን ሰርቆበት በነበረ ጉዳይ ሣቢያ ሁለት ጊዜ በሻቦላው ተነካ።

ሁሉንም ከፈፀሙ በኋላ፣ የሻቦላውን ጠቢብ፣ ፎቅ ላይ ወደ ሚገኘው ክፍሉ፣ አሊስ ራሷ መብራት አብርታለት መራችው። ፍራንቾይዝ፣ ክልብ በመነጨ ስሜት ውስጣዊ ምስጢሯን ለዚህች ወጣት ጓደኛዋ ልትገልፅላት ፈለገች። ወጣቷ ግን ሁለመናዋን ድካም ሙጥጥ ስላደረገው፣ እንደደረሰች አልጋዋ ላይ ወድቃ እንቅልፍ ወሰዳት።

ያልተቋረጠውን አካላዊ የልምምድ ሥርዓት በማከናወን ቀናት አለፉ። አንድ ጊዜ በአካባቢው ያሉትን ተልከስካሽ ተዘዋዋሪ ውሾችን፣ አሽከሮች ለማደን እቅድ አውጥተዋል ተብሎ ለሚሊሺያዎች ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸውና ምሽቱን የሽጉጥ ተኩስ ልምምድ ሊያደርጉ አደሩ። አሊስ መሣሪያውን ጥይት ማጉረስ ካወቀች በኋላ፣ ሣትንቀጠቀጥ አንድ ደርዘን ጥይት ተኮሰች።

ምሽቱ ከብጿቸዋል። ሦስቱም፣ በበረንዳው ላይ አብረው እራታቸውን በሉ። የጨዋታው ሞቅ ማለት ያሣደረባትን ውስጣዊ መቃጠል፣ አሊሰ መቻል ነበረባት። ሁለቱ ደግሞ፣ እንዲህ ፊት ለፊት መገናኘት መቻላቸው አሣፍሯቸዋል። ምግባቸውን በሚመገቡበት ጊዜ በመካከላቸው ረዘም ላለ ጊዜ የቆየው ፀጥታ በወንዙ ዳርቻ ባሉት ቀጤማዎች ውስጥ በሚኖሩት እንቁራሪቶች ማንቋረር በአንድ አፍታ ተሞላ።

ስለአረም እጅግ ብዙ ተሞክሮ ያላቸውን ይህንን ሰውዬና ይህችን ሴት በማየት ልጃገረዲቱ ተደሰተች። ሁለቱም ሰዎች በተፈጥሯቸው ፍልቅልቅ ፀባይ ያላቸው ቢሆኑም በሚገባ ባልተዘጋጁበት የፍትር ጉዳይ ግራ የተጋቡ ናቸው።

የምሽቱ የለየር ፀባይ ይጫጫን ጀምሯል። ለፍራንቾይዝ ምንም ባትነግራትም፣ አንዳች ነገር በተፈፀመ በማለት አሊስ ተሰፋ ታደርጋለች። ከዕለታት አንድ ቀን ምሽት ላይ ለሽርሽር ከሄዱበት ሲመለሱ በሙሉ ሃይላቸው ጋልበው ነበርና ራሣቸውን ስተው ሣለ፣ ወጣቷ ሴት ሁኔታው በሙሉ መጨረሻ ላይ የተሰወጠ ነው የሚል ግምት አደረባት። ከእራት በኋላ፣ በተለይ ፀጥ ባለበት ጊዜ ሜትር ዝርሚ ተናገረ። ወፍራሙ ድምፅ፣ ጨለማውን ሞላው።

« ይቅርታ ወይዘሪት፣ እነዚያን ዕፅዋቶቻችንን አደራ የሰጠሁት ለእንድ ጐረቤት ነው። እፅዋቱ ለኛ ምን ማለት እንደሆኑም በሚገባ ታውቂያለሽ። ስለዚህ ነገ ጧት ወደ ካይሮ እንድመለስ ፈቃድሽን እጠይቃለሁ።»

«እንዴ? ትምህርታችንስ . . » ካለች በኋላ፣ አሊስ በራስ ወዳድነቷ ወዲያውኑ አዘነች።

«ማንም ቢሆን መጣደፍ የለበትም። መሠረታዊዎቹን ተምራችኋል። ማሻሻል የሚቻለው በልምምድ ነው። ሽምላዎቹንና ሌሎችን መሣሪያዎች አተውልሻለሁ። ስለዚህ ከፍራንቾይዝ ጋር መለማመድ ትችያለሽ። እውነቱን ለመናገር በዚህ ረገድ እኔ ከእንግዲህ አላስፈልጋችሁም።

ፍራንቾይዝ፣ በተሰፋ መቁረጥ ሁኔታ የታችኛው ከንፈርዋ እየተንቀጠቀጠ ሜትር ዝርሚን ተመለከተችው። ብድግ አለችና ራሷን አረጋግታ፣ የቡናውን ማቅረቢያ ይዛ ወደ ማዕድ ቤት ሄደች። የሻቦላ አለቃውም፣ ከመቀመጫው በመነሣት፣ ለአሊስ ጉንበስ ብሎ ቀዝቃዛ ሰላምታ ከሰጣት በኋላ፣ ፋኖሱን ይዞ በተቃራኒው አቅጣጫ ወጥቶ ሄደ። ጭር ባለውና በባዶው የደረጃ መወጣጫ ላይ የእርምጃው ድምፅ ሲያስተጋባ ሰማች።

ሜትር ዝርሚ በሚቀጥለው ቀን ንጋት ላይ ሄደ። ሁለቱም ሴቶች እስከወደቡ ድረስ ተከተሉት። ጀልባዋ በማዕበሉ ተንፍታ በመንሣፈፍ ነጐደች። የጉዞዋ መስመርም ጠፋ። የፀሐይዋ ቅርፅ በጭጋግ ምክንያት ተዛብቶ በርቀት በሚገኙት የውሃው ዳርቻ የተምር ዛፎች ውስጥ አራት ማዕዘን ቅርፅ ይዛ ወጥታለች። ሽራ ያልተወጠረባት ጀልባ እንጨት ተሸክማ ሳይታወቅ በውሃው ላይ አለፈች። ቀጭኑ መንጠቆዋ እንደ አንቴና መወጠሪያ ከምሰሶው ላይ ተመሣቅሎ ወርዷል። ሁለት ትላልቅ ሃምራዊ ቀለም ያላቸው ወፎች ብቅ ጥልቅ እያሉ መንቆራቸውን ወደ ፀሐይ አቅጣጫ ያመላክታሉ። ከርቀት ሲመለከቷቸው የጋመችውን ከብ ነገር ከውሃው ውስጥ ቀስ እያሉ እየሳቡ በማውጣት የያዟት ይመስላል። ፍራንቾይዝ ታለቅሣለች።

«ምን ሆንሽ?» ስትል አሊስ ጠየቀቻት፣ ክንዷን ይዛ

ፍራንቾይዝ አይኖችዋን ጠራረገች፣ በአፍንጫዋም አየር ማጎትና ትክሻዋን ነቀነቀች። ወዲያውም አሊስን ተመለከተቻት።

«በጣም አዝናለሁ። በአጭር ጊዜ ውስጥ ይሻለኛል፣ ተመልከቺው። በቁጥጥሩ ሥር ነው። በኛ ዕድሜ እንዴት ጅሎች ነን?»

«አነጋግረሽው ነበር?» አሰች አሊስ፣ ወደቡ ዳር ተቀምጣና ከጉንዋ ያለችውን ጓደኛዋን እንድትቀመጥ እያደረገቻት።

«አዎን አነጋግሬዋለሁ። ሁሉንም ነገር አስከአሁን ድረስ ገምተሽ ቢሆንም እነግርሻለሁ። እዚህ ወደብ ላይ አሣ የሚያጠምድ በመምሰል ቀኑን ሙሉ ወደኔ ለመምጣት ሳይችል እንዴት እንደሚውል ባየሽው። ትናንት ከሰዓት ቡኋላ ስሄድ፣ ሁልጊዜም ለቁርጥማት ሕመሙ በማለት የአባትሽን አንድ ጠርሙስ ብራንዲ ከእጁ የማያጣውን ሚካኤልን አግኝቼው ነበር። እኔም ሁለት ዋንጫ ሙሉ ጠጥቼ ወደዚሁ መጣሁ። እኔ መድረሴን አስከሰማበት ድረስ፣ ዣረሚ ፍፁም አንድም ነገር አይሠራም ነበር። ከዚያ በኋላ የማጥመጃ ገመዱን መሣብና ከመንጠቆው ጋር መታገል ጀመረ። ሄጄ ከጉኑ ተቀመጥኩ። አጉረመረመ። እመኚኝ፣ ፈራሁ። መዋኘት ባልችልም ውሃው ውስጥ ዘልዬ ልገባ ነበር። ቡኋላ ተናገረ። ያ ድምፁ እንዴት እንደሆነ ታውቂው የለ? አንዴት ጭንቀት እንደተሰማኝ ቢገባሽ? አንዳች ነገር ልናገር ስል ያ ከበሮ ድምፅ ጀሮ ግንዱ ላይ ይደልቅ ጀመር።»

«አርሱስ ምን አለ?»

ፀሐይዋ ከፍ ብላለች። የወንዙ ዳርቻዎች ብሩህ መሆን ሲጀምሩ፣ ውሃውም ጠቆር ብሏል። የውሃ ዳር ወፎችም በርረው ሄደዋል።

«ፍራንቾይዝ ሲል ጀመረ። ስሜን ሲጠራው የተሰማኝን ሁኔታ ልነግርሽ አልችልም። «ፍራንቾይዝ፣ ልትነግሪኝ የመጣሽበትን ጉዳይ አውቀዋለሁ። መነጋገሩ ፋይዳ የለውም። አየሽ፣ ወላጆቼ እምነታቸውን በመለዋወጣቸው አሊቃቂ መከራ ተቀብለዋል። ይህንን አንዳችንም አላደረግንም። ይህ ደግሞ የሃይማኖት ጥያቄ ጉዳይ አልነበረም። ሐቁ ተመልሰን ያለፈውን ሕይወታችንን ለመጀመር አቅሙ አልነበረንም። አየሽ፣ እኔ በበኩሌ የራሴን ሰጥቻለሁ» ለአፍታ ያህል ንግግሩን ገታ አደረገው። የማጥመጃ ገመዱንም አስቀመጠውና እጆቹን በእጆቼን ላይ ጫናቸው። ከዚያም «ሕይወት ከቃል ኪዳኔ ልትፈታኝ ትችላለች ብዬ አስባለሁ። ያን ጊዜም ነፃ እሆናለሁ። ያን ጊዜ ቀሪውን ሕይወቴን በሙሉ አንቺ ፈቃደኛ ሆነሽ ልትቀበይኝ ከቻልሽ ቃልኪዳኔን የምሰጠው ላንቺው ነው።»

ፍራንቾይዝ ልቅሶዋን ሰቀቀተው። አሊስ፣ እጆችዋን በእጆችዋ ውስጥ ይዛ ልታበረታታት ሞከረች። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሁለቱም ተያይዘው ወደ ቤት ወጡ።

ይህ ማለት ለርስዋ ደስታ ማለት መሆን አለበት። ግን ምን አይነት ያልታደሉ ፍቅረኛ ሞች ናቸው፣ ስትል አሊስ አሰበች።

ከጀን ባፕቲስት ጋር ያሣለፈቻቸውን አጭር ጊዜያት መለስ ብላ ተመለከተች። እርሷም ብትሆን ባልተለመደ ሁኔታ ደካማና የማያስደስት የሚመስል ስዕል ነበራት።

ቬርሣይለስ ውስጥ በብዙ የሚወደዱ ወይዛዝርት መሃል ሆኖ፣ ከቶውንም እንዴት ሊያስታውሰኝ ይችላል ስትል አሰበች።

ይህ ሣጣብ በሌላ ጊዜ ቢሆን ኖሮ እንድትረታ ሊያደርጋት ሲችል፣ አሁን ግን ፈጣን ግልቢያ እንድታደርግ ቀሰቀሳት።

የሆቴሉ ባለቤት፣ ስለምክር ቤቱ አባል ሮበት ፖሞት ዱ ሣንግራይ የሰጠው አጭር መግለጫ ትክክል ነው። ሰውዬው በተፈጥሯቸው ፍልቅልቅ ከመሆናቸውም በላይ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲሆኑ ደስተኛ ናቸው። በተሰይም ሕመሙ ከለቀቃቸው በኋላ የርሣቸው መገለጫ የሆኑት መልካም ባህርያቶች ሁሉ ጐልተው መውጣት ጀምረዋል። ለጀን ባፕቲስት ምስጋና ይግባውና ይኸው ለመጀመሪያ ጊዜ የሕመማቸውን ስቃይ የሚከላከሉበት መሣሪያ አግኝተዋል። ይህም ሳይሆን ቢቀርና የአጭር ጊዜ ከስቃይ የመዳን ዕድል ቢሆንላቸውም እንኳ፣ ለጀን ባፕቲስት ታላቅ ውለታ አለባቸው። የተሰጣቸው ሕክምና የሕመሙን ምልክቶች ረዘም ላለ ጊዜ አስታገሰላቸው። ጊዜ ባለፈ ቁጥር የመዳን ስሜታቸው እርግጠኛ እየሆነ መጣ። በዚህ ምክንያት ለምስጋናቸውም ወሰን አልነበራቸውም። ከዚያም፣ መድሃኒት ቀማሚው፣ ፖሪስ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ መክረሙ እንደማይቀር በማሰብ፣ የዚህን ቆይታውን ወጭ በሙሉ እንደሚሸፍኑለት አረጋግጠው ሠላሣ የወርቅ ኤኩስ ሰጡት።

አንዳንድ ጊዜ፣ ታላቅ ርህራሄ በለምች ውስጥ ያለውን ጥርጣሬ ሁሉ ያስወግዳል። የሃብታሙ ሰውዬ ወዳጅነት፣ በጀን ባፕቲስት አይኖች ሲታይ ለአገልግሎቱ በቂ ክፍያ ነበር። ያንሰኛል ብሎ ቢጠይቅ እንኳ የራሱ ስሜት ይገሥፀዋል። በዚህ ሳቢያ የተሰጠውን የገንዘብ ቦርሣ ተቀብሎ ከዚህ በኋላ ምንም እንደማይቀበል አረጋገጠ።

ጆን ባፕቲስት፣ በየዕለቱ ከሰዓት በኋላ እየመጣ ሕመምተኛውን ይጎበኛቸዋል፡ የመንቀሣቀስ ነፃነታቸው የተመለሰላቸው ዱ ሣንግራይ፣ በክተማው ውስጥ ሲዞሩ እየዋሉ ወደ ቤት የሚመለሱት በየዕለቱ ላላቸው ውይይት ሲሉ ብቻ ሆነ። በዚህ ሳቢያ እንደእውነቱ ከሆነ ማን ማንን እንደሚጎበኝም ግልፅ አልነበረም ማለት ይቻላል። አንዳንዴ ሐኪሙና ሕመምተኛው ከተለያየ አቅጣጫ በመምጣት በሩ ላይ የሚገናኙበትም ጊዜ ነበረ። ውይይታቸውና ጭውውታቸውም ከሕመም ጉዳይ አልፎ፣ በሁለት ጓደኛሞች መካከል እንደሚኖር ነፃና የፈለጉትን ጉዳይ እያነሱ ወደ መነጋገር ደረጃ ዓይነት ደረሰ።

«እንዲያው ልጠይቅህና፣ ለምን እዚህ ቤት ውስጥ አትኖርም? ሌ ቢዩ ኖይር ጥሩ መጠጥ ቤት ቢሆንም፣ ከሁሉም አቅጣጫ እንደሚሰማው ደስ የማይል ሆቴል ነው» ሲሉ በአንድ የሣምንት ማብቂያ ዕለት አማካሪው ጠየቁት።

«በመጀመሪያ ነገር ሁለታችን እንድንገናኝ ያደረገንን የሆቴሉን ባለቤት ውለታ መርሣት ይሆናል»

«ክርሱ ጋር ያለውን እኔ አስተካክለዋለሁ። በርግጥ ምግብህን ማቅረቡን ይቀጥላል። እኔም ብሆን፣ የፍራንቾይዝን መረቅ የመፈለጌና የመጋቴ ነገር እያበቃ ስለሆነ፣ ለኔም ጭምር ምግብ እንዲያመጣ እነግረዋለሁ። በዚህ ሳቢያ ጥሩ ደንበኞቹ ሆነን እንቀጥላለን። በሴላ በኩል፣ በዚህ ወቅት ባሉት ትርኢቶች ሳቢያ ያንተን ክፍል ወዲያውኑ ያከራየዋል።»

ጆን ባፕቲስት ተስማማ። አማካሪውም፣ አንድ የመኝታ ክፍል በፎቁ ላይ እንዲዘጋጅለት አዘዙ። ክፍሉ፣ ሙሉ ዕቃ የነባለትና ቀለል የሚል ነበር። በፊት ለፊቱ በኩል፣ ሥራ ብዙ ወደሆነው መንገድ የሚያሣዩ ሁለት ረዣዥም መስኮቶች አሉት። ከዚህም በላይ፣ አማኒያን በየበረንዳው ስር ወደ ቅዱስ ኢዩስታች ቤተክርስቲያን ሲመጡና ሲመለሱ ይታይበታል። በኢጣሊያ እምነበረድ የተሰራው ትልቅ የጤስ ማውጫ ባለመደፈኑ፣ እሣት ግር አድርጐ በማንደድ ራሱን ማሞቅ እንደሚችል በማወቁ ጆን ባፕቲስት ተደሰተ። ቤቱ በጀርባ በኩል የመኝታ ክፍል፣ ሁለት ትንንሽ ክፍሎችና ለስሙ ያለውን ሻንጣውን፣ የመድሃኒት ቦርሣውንና የገዘሁኑን ጀሮዎች የያዘበትን ሳጥን ሊያስቀምጥ የሚችል ቁምሣጥን አለው።

«ይህን የከተማ ቤት ስገዛው፣ ለአስር ዓመት ያህል ተዘግቶ የኖረና ለባለቤቶቹም እጅግ የሚጠላ ነገር ሆናባቸው የነበረ ቤት ነበር።» ሲሉ እንግዳቸውን ለማየት የመጡት ሳንግራይ ተናገሩ።

«ሰዎች እዚህ ይፋለሙ ነበር መሰለኝ?»

«ክፍለ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ የጠራ ክብር አለን ለሚሉ ሰዎች የመገናኛ ቦታቸው ነበረ። በኩበሯቸው ላይ ማንም ሰው ጥርጣሬ አልነበረውም። ነገር ግን የጥራቱ ጉዳይ፣ የማያላውሱ ሕጐች ነበሩበት። ሕጐቹንም እነርሱ ለሚያከናውኑት የግፍ ግድያ ሲሉ ራሣቸው ያወጡት ነበር። እዚህ ያለውን ተራ ጭሰኛ አስበው። ዴ ሞንት ሞሬንቺያ ቡቴቪል የተባለው ባለስልጣን፣ በሃያ ሰባት ዓመት ዕድሜው ሃያ ሁለት ጊዜ ፍልሚያ አድርጐ ነበር። የመጨረሻው ፍልሚያውን ያደረገው በሪቼሊዩ የከተማ ትልቅ ቤት ውስጥ ነበር። በዚህ ዕለት ማለትም ልክ በበጋው አጋማሽ ዕለት ሐምሌ 24 ቀን በዚሁ ፍልሚያ ላይ ታረደ»

«አስኮሪ ገድል ነው» ሲል ፖንሴ ተቁነጠነጠ

«እንደዚያ ታስባለህ?»

«አምን፣እነዚያ ሰዎች በዕውነት የኖሩ ነበሩ? ብዬ አስባለሁ»

«ብዙ ጊዜ ግን ይሞታሉ። ሌሎችንም ይገድላሉ። ሁሉንም ነገር እስከዛሬ ድረስ በሚገባ አስታውሣለሁ። የፍሮንዴ አሰቃቂ ግድያ ትዝ ይለኛል። በሕዝባዊው ንቅናቄ ጊዜ ገና ሕፃን ነበርኩ። ሆኖም ግን፣ በወቅቱ፣ ሃይል ሕዝቦችን ይገዛ የነበረበትን ትርምስ ፈፅሞ አልረሣውም። የለም፣ አየህ ዶክተር፣ እኔ የሕግ ሰው ነኝ። የሚዛን ሰው ነኝ። ራሴን ሳስበው የነዚያ አውሬ መናፍስት ጠባቂያቸው ሳልሆን አሣሪያቸው እንደሆንኩ ነው»

ከመጀመሪያ ጀምሮ እነሀን በትዕግስት የተሞሉና ሁሉንም ነገር በነፃ አዕምሮ የሚቀበሉ ጨዋ ሰው፣ ጆን ባፕቲስት ትልቅ እምነት አሣድሮባቸዋል። ወደ አቢሲኒያ ያደረገውን የጉዞ ታሪክ ነግሯቸዋል። ትረካውን ሁለቱም ሰዎች የድመት የመሰለ የአግር ቅርፅ ባለው ባለመደገፊያ ወንበር ላይ ሆነው፣ እግሮቻቸውን ወደ ነሐሱ የእሣት ማንደጃ ዘርግተው ለብዙ አስደሳች ምሽቶች ዘልቋል።

እነዚህ ምሽቶች ካበቁ በኋላ ራሣቸውን በዕሁፍ ሥራ ላይ ለማሰማራት ወሰኑ። ሣንግሪይ ያምረውት የነበረውን የተለያዩ የሰው ልጆች ሕገ-ች ለማጠናቀቅ ተዘጋጀ። በሣንግራይ ማግባባት፣ ጆን ባፕቲስትም የጉዞውን ታሪክ በጽሁፍ ለማስፈር ወሰነ። ሥራቸውንም በሁለተኛው ቀን ጀመሩ።

አማካሪው፣ ከመፅሐፍት አዋኚ በላይ ናቸው። ሕመማቸው ፈፅሞ ከተዋቸው በኋላ ሕይወትን ሁሉ መፈተሽ ጀመሩ። በዚህም ያልጻሰሱት የደስታ መስመር አልነበራቸውም። በፖሳስ ሮያሌ በተዘጋጀው የደመራ ምሽት ላይ የቻርትራሱ መስፍን ያውቋቸው ስለነበረ ተጋብዘዋል። ሣንግራይ ይህን የደስታ ምሽት ለመካፈል በጣም ደስ ስላላቸው፣ ጆን ባፕቲስትም አብሯቸው እንዲሆን በፈንታቸው ጋበዙት።

ሁለቱ ሰዎች በሰውነታቸው አቋም ቢለያዩም፣ ቁመታቸው ተመሣሣይ ነበር። አማካሪው፣ ለእንግዳው፣ በወርቅ ጥልፍ ያማረ ሙሉ ልብስና ያሸበረቀ የእንገት ፎጣ አዋሱት። ጋሪ ጭምር የሚያከራየው የሆቴሉ ባለቤት ሙሴ ራእል፣ አንድ ሠረገላ ከነኔጂው ላከላቸው። በጊዜ ለዕራት ለመድረስ ሄዱ።

5

በዚያን ዘመን የቤተመንግስቱን ሕይወት የሚያሣየውና፣ ፖሪስ ውስጥ በብቸኝነት የቀረው ፖላስ ሮያሌ ነበር። የተቀሩት የቤተመንግስት ተግባራት ሁሉ፣ በንጉሡ ዙሪያ እንዲሆኑ ተብሎ ወደ ቬርሣይለስ ተዛውረዋል። ፖላስ ሮያሌ ውስጥ እጅግ የደመቀ በዓል ቢደረግም፣ የሚያስፈራ አምባገነን የሌለበት ስነስርዓት ነበር። የቻርትራሱ መስፍን፣ የንጉሡ የእጮት ልጅ ሲሆኑ በዙሪያቸው ለሚገኙት ሰዎች ሁሉ ፍቅርና ወዳጅነትን የሚያሣዩ ሰው ነበሩ። በዚህም የተነሣ በበዓሉ ላይ የነፃነት መንፈስ ሰፍኖ ነበር። እንዲህ ባለው ሞቅ ያለ የወዳጅነት ቦታ፣ እጅግ ውብ የሆኑ ዕፅዋት ከቬርሣይለስ ይልቅ እዚህ ይበልጥ ይደምቃሉ። እንደልብ በአንድ ላይ ሆነው የሚገኙት ውበት፣ ወጣትነትና ሰዛ በዚያ ቦታ በብዙ ድንቅ ሰዎች ዘንድ፣ በተሰይም በሌቶች ውስጥ ተዋህደው ይኖሩ። ሣንግራይ፣ አጃቢውን ከቻርትራሏ ልዕልት ጋር አስተዋወቁት። ባለቤታቸው የቻርትራሱ መስፍን ግን፣ የዚያኑ ዕለት ጥቂት ቀደም ብሎ፣ እነርሱ ከመድረሳቸው በፊት ወደ ቬርሣይለስ ተጠርተው ስለሄዱ ሊያስተዋውቋቸው አልቻሉም።

በእራት ሰዓትና ከዕራት በኋላ የነበሩት ጥቂት እንግዶች፣ በግሎን ውስጥ ተሰብስበው በነበረበት ጊዜ፣ ፖንሴ ጥንቃቄውን በመጠኑም ቢሆን ላላ አደረገው። ውብ ሴቶች ያሉባት አንድ ቡድን በጥግ በኩል በዙሪያው ተክለክሉ። ስለነዚህ ወይዛዝርት ማንነት የሚያውቀው አንዳችም ነገር ባይኖርም፣ ከሁሉም ታላቅ የሚሆኑትን አንዷን ሴት ግን፣ ማዳም ማርኩስ ብለው ሌሎች ሲጠሯቸው ሰማ። የጆን ባፕቲስት ድንቅ አቀራረብና የትንግርቶች መፍለቂያ ስለሆነው ስለዚህ ቦታ ማስረዳት በመቻሉ፣ አንዳች ተአምር የሆነ ነገር የተደበቀበትን ማሽተት የሚችሉበትን ልዩ ተሰጥኦና፣ ባላቸው የማወቅ ጉጉት የተነሣ ይህን አዲስና ያልተደመደ ነገር ሰብረው ለመውጣት ስለንጉ፣ ሴቶቹ ፖንሴን መሃላቸው አስገቡት። እርሱም፣ እውነቱን ተናጋሪው እርሱ ብቻ ስለሆነ እነዚህ ድንት የቤተመንግስት ሰዎች ባሉበት፣ አክብሮታዊ ፍርሃትን ለማስወገድ ሲል በወጥመዳቸው ውስጥ ሆን ብሎ ገባላቸው። አቢሲኒያን ሲገልፃት ለራሱ ፍፁም ሥልጣን ሰጠው። የተነገረውም ነገር ብዙ ሺህ የአግራሞት ጥያቄዎችን አስነሣ። አንዱን እያነሣ ሌላውን እየጣለ በሚገለባበጠው ማህበራዊ ጭውውት፣ ጆን ባፕቲስት ይህን ውብና ማራኪ ነገር ከሚያስፈልገው በላይ በማስፋት ስህተት ሠራ። አቢሲኒያውያን

እጅግ ታላቅ በሚሆነው ግብግቦቸው ላይ፣ በራ በቁመ እንዴት እንደሚበሉ፣ በበዓሉ ቦታ የሚስተናገዱ እንግዶችም በበራው አዘርካሪ በኩል ጣቶቻቸውን እያሳለፉ የሚንዘፈዘፈውን ሥጋ እየቦጨቁ የሚወስዱ አድርጉ ያስማቸውን ዝርዝር ተረክላቸው።

የትረካው መጨረሻ የቀዘቀዘ የዝምታ ስንብት ገጠመው። አርጊቷ ማርኩስ፣ የነፋስ ማራገቢያቸውን በትንሹ እያማቱ የቁጣ ግልምጫ አሣረፋብትና ወደ በረንዳው ተቆናጥረው ሄዱ። በዚያ የነበሩት ፈንጠዝያ ወዳዶቹ ውጣት ወይዛዝርት በሙሉ፣ አብረቅራቂውን ከወፍ ላባ የተሠራውን ልብሳቸውን እያንሿሹ ተከትለዋቸው አብስ አሉ።

በረኸሙ መቀመጫ ላይ ብቻውን የነበረው ውጣት፣ ከሴቶቹ ሰውነት ላይ በልብሶቻቸው ውስጥ ተጀቡኖ የነበረውን ጠረን ማገው። የሴቶቹ ጡቶቻቸው፣ የገባኖ ሽቱ፣ የበርበሬና ግሩም መዓዛ ያለው ጠረን ይረጫሉ። ፊቶቻቸው በነሮ የወበት ዱቄትና በአደስ ፍሚል። ይህን የመሰለ ደስ የሚል ነገር ከዚህ በፊት አይቶ አያውቅም። ስነዚህ ሴቶች እያንዳንዷ፣ ከወጣትም ሆነ ከአሮጊት ክፉኛ የሚያስጮኹ ነበሩ። ከአንድ ዕፅ ላይ ጥቂት የፈሣሽ ጠብታዎች ቢነበር መድሃኒቱ እንደማያድን ወይም እንደማይገድል ዓይነት፣ እነዚህም ሴቶች ሴትነታቸውን ፍፁም በንፅህና አጠንክረው የያዙ ናቸው።

ይህ ሁሉ ሆኖ የቸገረው ነገር ነበር። ይህ የሚታየው ሁሉ በርግጥ በሰው ሰራሹ አቋማቸው ይሆን? እውነት ነው፣ በነዚህ በመቶዎች በሚቆጠሩ የሽማዎች ብርሃን ውስጥ፣ የክት ልብሶቻቸው ከተዘጋጁ በኋላና መልሰውም መመንቸክ ከመጀመራቸው በፊት በነበሩት ጥቂት ሰዓታት ውስጥ፣ እንዲህ ያለ ነገር በቤተመንግስት ውስጥ ተገዚ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ሴቶች ራሣቸውን በሌላው ዓለም ውስጥ፣ ማለትም በእውነተኛው ዓለም ውስጥ ቢያገኙት ምን ሊሆኑ ይችላሉ? አካላቸው ሣይፈርስ እንደሚቆዩ አስከሬኖች ደርቀው ይገኙ ይሆን? ወይስ ደግሞ በዚህ የሩዝ ዱቄት በሞላው አየር ውስጥ ብቻ ነው መተንፈስ የሚችሉት። እናም፣ አንድ ሰው ለመደሰት ሲፈልግ ተመሣሣይ ጊዜያትን መከተል፣ በተመሣሣይ አካባቢ መንቀሳቀስንና ተመሣሣይ ባህርያትን ማሣየት ይኖርበታል። አስቲ ሁሉንም ተመልከቷቸው።

ጆን ባፕቲስት፣ ትንሽ ብልግና በተቀላቀለበት ሁኔታ፣ የሣያ አመቶቹ የሠራዊት አለቆችንና፣ ሰገባው ውስጥ ያልገባ ጐራዴ የሚያስደነግጣቸውን ጨዋዎቹን ጓዳሳት ቃኖቸው። የሰው ልጅ ልብ፣ አምነቱና የመሣሪያ አጠቃቀም ዝናውም ተገርቷል። ይሁን እንጂ፣ እነዚህ

ሁሉ ደስታዎች ምርኮኛ ያደርጋሉ እንጂ ምንም ማለት አይደሉም፣ ሲል ለራሱ ተናገረ። ይህን እያውጠነጠነ ሣለ ሁለት ውጣት ቆነጃጅት በአጠገቡ እያለፉ ዐይኖቻቸውን ቢወረውሩበት ውስጡ ተረበሸበት።

በሣጣ ጭልጥ ብሎ መጓዙን የተረዱት ሣንግራይ አጠገቡ መጥተው ተቀመጡ።

«አሸ, ወዳጄ፣ የምሥራች። አንተን በሚመለከት ከሁሉም አቅጣጫ ድንቅ መረጃዎች ደርሰውኛል። እዚህም ይገርህ ስለመጣሁ ምስጋናው ለእኔም ተርፎኛል»

«ይቀልዱብኛል አይደል? እኔ ደግሞ የተገላቢጦሽ ተንገላጅጃለሁ።»

ስላልታደለው የበሬ ታሪክ ያወራላቸውንና ሁሉም አድማጮቹ ትተውት መሄዳቸውን አክሎ ነገራቸው።

«አርሱን አርሣው። አርባና የሌለው ነገር ነው። ይልቁንስ በአቃ ማስቀመጫ ውስጥ ድንገት የተገኘ ዕቃ ላይ ለመሸማት የሚተራመሱ እስኪመስሉ ነበር ወይዛዝርቱን ያደረግሃቸውና፣ ከሚጠበቀው በላይ ነበር የሠራኸው። እስከአሁን ድረስ ይህን የምትነግረኝን ሁሉ ረስተውት፣ በልባቸው ያለው፣ ደስ የሚል ሰው ማግኘታቸው ብቻ ነው»

የሳንግራይን ንግግር ለማረጋገጥ ይመስል፣ ጥቂት ወይዛዝርትና ብዙ የማርኩስ ወጣት አሻቢዎች በአጠገባቸው ሲያልፉ ሞቅ ያለ ፈገግታ ወደነርሱ አቅጣጫ ለቀቁ።

«በነገራችን ላይ፣ ካንተ ጉዳይ ጋር የተያያዘ ወሬ ሰምቻለሁ። ውጣቱ የስፔይን ንጉሥ ነገ ወደ ቬርሣይለስ ይሄዳሉ። ንጉሡ ነገስታችን፣ እንደ ቤተመንግስት ሕግ አውጭና አስፈፃሚ መሆናቸው ከእንግዲህ አብቅቷል። ስለዚህም አሁን ተከታዮቻቸውን መቀበል ይጀምራሉና ያንተም ረኸም ገዜ አይወስድም» አሉት፣ ጠቢቃው።

በእንግዳ መቀበያ ክፍሎች ሁሉ ውስጥ ገበጣና የመጫወቻ ጠጠሮች ባሉባቸው ጠረጴዛዎች ዙሪያ እንግዶች እጅብ ብለዋል። ጆን ባፕቲስትና ሣንግራይ፣ አስተናጋጃቸውን በተናጠል ካመሰገኗቸው በኋላ፣ ሹልክ ብለው ለመውጣት ዕድል አገኙ። ወደ ቤታቸውም በግልፅ ሠረገላ ተጓዙ። በመኝታ ክፍሎች ውስጥ ፍሪንቾይዝ የሚንተገተግ እሣት አንድጳላቸዋለች። ጆን ባፕቲስት፣ ልዕልቲቱ በዝባድ ሽቱ እጃቸው በወደጅነት ዓይን ተመልክተው የጨበጡትን የራሱን አምባር ማስሪያ ወደፊቱ አስጠግቶ በማሽተት ወዲያውኑ ተኛ።

በማግስቱ፣ ራእል፣ ለጆን ባፕቲስት መልዕክት ይዘለት መጣ። መልዕክቱ፣ ከአባ ፕላንቴይን የተላከ ነው። ካህኑ፣ እስከአሁን ድረስ ጆን ባፕቲስት፣ ሌ ቢዩ ኖይር የሚኖር መስሏቸው በዚያ አድራሻ ነበር የፃፉለት። ሐኪሙ ግን በአሁኑ ጊዜ በአማካሪው ቤት የሚኖር መሆኑን እንዲያውቁ ማድረግ ሞኝነት ይሆናል በሚል አሳስታወቃቸውም ነበር። የደብዳቤው መልዕክት እንዲህ ይላል።

ተዘጋጅ። ተነገ ወዲያ ወደ ቬርግይለስ እንሄዳለን። እኛ እንድንቀርብ ፕሮግራም የተያዘልን ረቡዕ ዕለት ከሰዓት በኋላ በአስር ሰዓት ላይ ነው ።

አባ ጂ ፕላንቴይን ሰኛ

ከምሣ በኋላ፣ ጆን ባፕቲስት ስለአቀራረባቸው ጉዳይ በዝርዝር ለመወያየት፣ ወደ ሉዊስ ሌ ግራንዱ ትምህርት ቤት ሄደ።

ወደ ቤት ሲመለሱ በሎው ቭሬ በኩል ዞሮ ሄደ። በጭምጭምታ እንደሚናፈሰው ከሆነ በቅርቡ የአንጀው መስፍን ተብለው ሹመት የተቀበሉት የስፖኑ ንጉሥ ፊሊፕ አምስተኛ ፈረሰኞች፣ በሚቀጥለው ቀን ለሚደረገው ደማቅ ሰልፍ በዚያ በኩል ልምምድ ያደርጋሉ። በመርከብ ማቆሚያው ስፍራ ላይ፣ ጆን ባፕቲስት፣ የንጉሡን አንደኛና ሁለተኛ ፈረስ አጣቢዎች ውብ ልብሣቸውን ለብሰውና ሽክ ብለው በድንገት አያቸው። እነርሱን ተከትለው ሃያ አራት ረድፍ የሚሆኑ ከሃር የተሠራ ጠባቃ ጃኬትና የእግር ሹራብ የለበሱ፣ በብርማ ጌጥ ተሠርተው የሚያብለጨልፖ ተንጠልጣይ አበባዎችን ያሠሩ፣የአንገት ፎጣዎችን የጠመጠሙ ፈረሰኞች፣ የአበባ ጉንጉን በተደረገላቸው ፈረሶች ላይ ተቀምጠዋል። እነዚህን ተከትለው በእጅ የሚጐተቱ አሥራ ሁለት የስፔይን ፈረሶች አሉ። እነዚህኞቹ፣ የሰውነታቸውን ውብትና የጋማቸውን መዘናፈል፣ የተሸለሟቸው የወርቅ ልብሶች፣ በማዕከላዊው የሰውነታቸው ክፍሎች ላይ የተበጃጁላቸው ጌጣጌጦችን፣እርካቦቻቸውን፣ በወርቅና በብር የተጠለፉትን ግላሶቻቸውን ለማሣየት የወጡ ናቸው። ጆን ባፕቲስት፣ ከዚህ የበለጠ ሊመለከት አልቻለም። ምክንያቱም፣ ግራጫ ልብስ የለበሱና መስኩቶ ጠመንጃቸውን የያዙ ወታደሮች፣ የንጉ ሰዎች ወደ ሎውቭሬ ቤተመንግስት በጣም እንዳይቀርቡ ይከላከሉ ነበር።

ወደ አማካሪው ቤት ተመልሶ ሲመጣ፣ እኒህ አስተናጋጁ፣ ሣሎኑ ውስጥ አግቱ አጠገብ ተቀመጠው አገኛቸው። ጆን ባፕቲስትም እጃቸን ወደ ሙቀቱ እያቀረበ እዚያው ተቀመጠ። ጊዜው ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ሆኗል። ፍራንቾይዝ፣ እራታቸውን በዚያው በእሣቱ ጫር

አቀረበችላቸው። ስለ ቤተመንግስቱ ሰልፍና ፖንሴን ስለሚጠብቀው የቤተመንግስት አዳማቂ አወሩ።

«ለመሆኑ ምን ለማድረግ አቅደሃል?»

«መቼም እውነቱን እናገራለሁ» አለ ጆን ባፕቲስት በቀላሉ።

«ይህማ ደካማ አጀማመር ሊሆን ነው። ለንጉስ እኮ እውነት ማለት በቀላሉ እርሱ ሊሰማው የሚወደውን መንገር ማለት እኮ ነው። ታዲያ ይህን እታውቅም ማለት ነው?»

«ንጉሡ ሊሰሙት የሚወዱትና የሚያስደስታቸው ምን እንደሆነ አላውቅም። ነገር ግን ጥቂቶች ምን ሊነግሯቸው እንደሚፈልጉ አውቃለሁ። ያ ደግሞ ሐሰት ነው»

«ይህን ስትል ማንን እየጠቀስክ ነው?»

«ጀስዊቶችን»

«ይህን፣ ወደ ቤተመንግስት መቅረብህን ያዘጋጁልህ ጀስዊቶች አይደሉም እንዴ?»

«እነርሱ ናቸው። ነገር ግን ይህ ማለት እነርሱና እኔ፣ ለንጉሡ በምንነግራቸው ጉዳይ ላይ የተለያየ አመለካከት ያለን መሆኑን አያግደውም»

አማካሪው፣ በጣቶቻቸው ይዘው ሲቆረጥሟት የነበረችውን ትንሽ አጥንት ትሪው ላይ አስቀመጡና ከሚያብረቀርቀው ወይን በረጅሙ ተጉነጭተው፣ ጆን ባፕቲስትን በአግራሞት ተመለከቱት።

«ጀስዊቶቹን የሚቃረን ነገር በንጉሡ ፊት ለማቅረብ ማቀድህን ነው የምትነግረኝ? መቼም የመጨረሻችን ይሆናል ብዬ ስለምፈራ እራት አብሬህ መብላት በመቻሌ ደስ ብሎኛል። ነገር ግን በትክክል ፍላጐትህና ግብህ ምንድን ነው?»

«እርግጠን ንገረኝ ካሉኝ ሁለት ናቸው»

«ይህ ጥሩ አቋም አይደለም።»

«ይሁን እንጂ በኔ አዕምሮ ውስጥ ሁለቱ አንድ ነገር ይሆናሉ»

ፖንሴ፣ በንግግሩ ሞቅ እያለ ቀጠለ□ «ንጉሡ፣ ወደ አቪኒዮን አምባሣደራቸው አድርገው ሾመው እንዲልኩኝ፣ ይህን ሃላፊነት ለመወጣት ማንኛውንም የአጋጣሚ መብት ሳይቀር እንድጠቀም እንዲሰጡኝና የመኳንንትነት ማዕረግም እንዲያጐናፅፉኝ እፈልጋለሁ»

«አነጋገርህ በጣም የምኞታም ቢሆንም፣ አይደረግም ሊባል እንኳ የሚችል አይደለም»

«እርስዎም ታይቶዎታል»

«ይሁን እንጂ፣ ለምንድን ነው ወደዚያ ተመልሰህ መሄድ የምትፈልገው?»

«ለመሄድ እንኳ በጣም ቁርጠኛ ከመሆኔ የተነሣ አይደለም። ነገር ግን፣ ንጉሡ እነዚህን ሁሉ ሊሰጡኝ ፍላጐቱ ካላቸው፣ የፈፀምኳቸውን ሁለት ቃልኪዳኖችን ላሟላ እንድችል ዕድል አገኛለሁ።»

«ደኅ ክርስቶስ! ሰማን ነው ቃል የገባኸው?»

«የመጀመሪያው ለእንዲት ወጣት ሴት ነው። በዘርዋ ከኔ ይልቅ ከፍተኛ ማዕረግ ካላቸው የምትወለድ ነች። ላገባት ቃል ኪዳን ገብቼላታለሁ። ይህን ማድረግ የምችለው ደግሞ፣ ንጉሡ የመኳንንት አባል ሊያደርጉኝ ብቻ ነው»

«ይገባኛል። እንዲህ ያሉ ነገሮችን ባንተ ዕድሜ የሚገኝ ሰው የሚያደርጋቸው ናቸው። እሺ፣ ሌላው ቃል ኪዳንስ?»

«ሌላው ቃልኪዳን፣ ለአቢሲኒያው ንጉሠ ነገስት የገባሁላቸው ነው። ለንጉሠ ነገሰቱ፣ ጀስዊቶች ወደ አገራቸው እንደማይመለሱና፣ እርሳቸው፣ ፈረንሣይ አምባሣደር እንድትልክ የሚጠይቁ ከሆነ ቦታውን እኔው ተሹሜበት እንደምመለስ ምዬላቸዋለሁ።»

«ይህ ማለት የምትጠይቀው ወደዚያው እንድትላክና ጀስዊቶች የማይወደዱ መሆናቸውን ንጉሡ እንዲረዱት ማድረግ ነው። የሚገርመው እስከዚህ ድረስ ያመጡህ ግን ጀስዊቶች መሆናቸው ነው»

«ሌላ አማራጭ አልነበረኝም። ያለነርሱ፣ ለዘለዓለም ከካይሮ አልፍ እንኳ ማለት አልችልም ነበር»

«እኔም የምነግርህ ይህንኑ እኮ ነው»

«ቢሆንም እነርሱ ስለፅቅዱ የሚያውቁት ነገር የለም»

«ልቀበለው እችላለሁ። ማለትም በመጨረሻም ሰዓት ላይ በንጉሡ ፊት ትቃረናቸዋለህ። ምን ልታደርግ እንደሚገባህስ አስበህበታል? ደግሞ ትስቃለህ እንደ?»

«የምስቅበት ምክንያትማ፣ ካለኝ ማስረጃ ባሻገር ልብ ሙሉነት ይለማኛል»

«እንዲህ ግልብልብ የሚያደርግህ ወጣትነትህ ነው። የቤተመንግስቱ ግቢ የሴራ ቦታ ነው። ትንሿ ነገር በውኔና በጀግንነት የምትቀጣጠልበት ነው። ስለዚህ፣ እንዳችም ነገር እንዲህ በቀላሉ ድል የሚደረግበት ቦታ አይደለም። እንደኛ ብዛት አሳቸው። ከየተሸጉጡበት ሆነው ከኋላህ ይወጉሃል። ያን ጊዜም ያሸንፉሃል»

«በጭራሽ፣ ክቡር አማካሪ» አለ ጆን ባፕቲስት በጨዋነት «ራሴን አብድ ነኝ ብዬ አላስብም። ልበ ሙሉነቴ የሚመነጨው ግዴሰሽ በመሆን ሣይሆን፣ ይልቁንም በተቃራኒው ካየሁት ሁሉ የሚነሣ ነው። ይህን የት እንዳየሁት ያውቃሉ? ፈረስ እየጋለብኩ ወደ ፖሪስ ስመጣ፣ በንጉሡ ግዛቶች አቋርጬ ስንዝ፣በገጠርና በከተማ ውስጥ ያሉ ሰዎችን ሣነጋግር ነው። ይህን ሁሉ አገር የሚገዙት ሰው ታላቅ ንጉሥ ናቸው» እያልኩ ስራሴ አወራ ነበር።

«ይመስልሃል?»

«ቆይ፣ አይደለም። ሰውዬው ታላቅ ንጉሥ ናቸው። ምክንያቱም በዚህ አገር እኖር በነበረበት ዘመን፣ ስለፍሮንዴ ይነገሩ የነበሩትን የጥንት አፈታሪኮች፣ ስለ አስፈሪው የሕዝብ ሁከት፣ ስለ ሃይማኖት ጦርነቶች፣ ደርሶ ስለነበረው ስለታላቁ የወረርሽኝና የረሃብ መቅሰፍት የሰማኋቸውን አስታውሣቸዋለሁ። እናም በአባቶቻቸውና በአያቶቻቸው አልጋ የተተኩት እኒህ ንጉስ ይህን ሁሉ መከራ ከፍሣሜ አድርሰዋል። ታላላቆቹን ሁሉ አሸንፈው፣ መኳንንቱም እጅ እንዲሰጡ አድርገዋቸዋል። መኳንንቱ፣ ወደ ቤተመንግስት ግቢ በመምጣታቸው የተነሣ በአገር ቤት የነበሯቸው ታላላቆቹ ግንቦቻቸው ዛሬ አና ናቸው። በዚህ ሳበያ፣ በአገር ቤት የቀሩት ሁሉ የንጉሡ ታማኞች ናቸው። ቤተክርስቲያንን በተመለከተ ከሆነ እርሷም ፕሮቴስታንቶችን በምትዋጋበት ጊዜ፣ ንጉሡ ስላደረጉላት ድጋፍ ውለታ ስትል ሥልጣናቸውን አሜን ብላ ተቀብላለች። ንጉሡ፣ የፈረንሣይን ወታደራዊ ሃይል አጠናክረዋል። በውጭ አገር የሚገኙ ጠላቶቻቸውንም ድል አድርገው መልሰዋቸዋል። በክዚህ ሁሉ ምክንያቶች ወደር የለሽን ስልጣንና ሃይል በእጃቸው አስገብተዋል»

«እነዚህ ሁሉ ያስከፈሉትን ዋጋ አትረሣም አይደል? የአውሮፖ ህብረት የተፈፀመው የኛን ተቃውሞ ጥሶ ነው። ሕዝቡ በግብር ጫና ተደቆሰ። ፕሮቴስታንቶችና ኧንሴናውያን እንደተባይ ነበረ የታደኑት። እኔ በፖርላማ ውስጥ ስላሣ ዓመት ነበር የቆየሁት። እናም በፖለቲካ ውስጥ ከንጉሡ ከራሳቸው በስተቀር የሌሎች ድምፅ አይሰማም። ይህን ደግሞ እመነኝ።»

«ነጥቡ እሱ አይደለም» ሲል የጨዋታውን መስመር ለመቆጣጠር በመፈለግ፣ ጀን ባፕቲስት እጁን አወዛውዞ ቀጠለ። «አሁን እያደረግሁት ያለሁት፣ ታሪካዊ ፍርድ እየሰጠሁ አይደለም። የገለፅኩት ታሳቅ ንጉሥ መሆን ፈልገው፣ መሆን የተቻላቸውን ሰው ሥራ ነው። እናም እንዲህ ያለ ሌላ ሰው ደግሞ የአቢሲኒያው ንጉሥ ነው»

«አያወዳደርክ እንዳይሆን . . . »

«አዎን። አንድ አይነት ፍላጐት አላቸው። ሁሉንም በስልጣናቸው ሥር ሰማድረግ አንድ አይነት ቁርጠኝነት አሏቸው። አንድ አይነት ወደር የለሽ ሥልጣንና ሃይል አዚያም አይቻለሁ። እያሱ፣ የሚያከናውኑት ተመሣሣዩን ተግባር ነበር። በዚህ ዓለም ላይ ሁለት ሰዎች ኖረው አንዱ ሌላውን መረዳት ይችላል ከተባለ እነዚህ ሁለት ሰዎች ይሆናሉ።»

«እናም ለፈረንሣይ ንጉስ በዚህ ዓይነት ስሜት ልትናገር ነው የምታስበው?»

«እንደሚረዱኝ በጣም እርግጠኛ ነኝ። ጀስዊቶች ሊነግሯቸው የሚችሉት 'አቢሲኒያውያን ወደ ካቶሊክ እምነት ሊቀየሩ ይፈልጋሉ' ብለው ነው። እኔ የምነግራቸው ደግሞ፣ ግርማዊ ሆይ የምስራቁን ታላቅ ንጉስ ወጃጅነት ይቀበሉ። ወደርሣቸውም ዘንድ ኤምባሲ ይላኩ። ከርሣቸውም ጋር ይነግዱ። ወርቃቸውን ይግዙ። በርስም በኩል የፋብሪካ ውጤቶችዎን ይሸጡሳቸው። ነገር ግን፣ ግርማዊ ሆይ፣ የአገራቸውን አቋም፣ሃይማኖት በመለወጥ ፍላጐት ለማወክ ፍላጐት አይደርብዎ። ልክ እርስዎ በዚህ መልክ የራስዎ መንግስት አቋም እንዲታወክ እንደማይፈቅዱ ሁሉ፣ የአቢሲኒያውንም አይንኩ»

«ጀን ባፕቲስት፣አንተ እብድ ሰው ነህ» አሉት ሣንግራይ፣ ከተቀመጡበት እየተነሱ። «ለራስህ ባዘጋጀኸው እንዲህ ባለ ወጥመድ ውስጥ ገብተህ እንዳትወድቅ ጓደኝነታችን ያሳስበኛ ል»

በክፍሉ ውስጥ ሁለት ረገጭነም ርምጃዎችን ተራመዱና ተመልሰው ወደ አሣት ማንደጃው በመምጣት ከዶክተሩ ፊት ለፊት ቆሙ።

«ፖንሴ፣ ለመሆኑ አቢሲኒያ ምንድነው?»

«አገር ነው»

«የለም። አቢሲኒያ ምንም ነገር አይደለም። ይልቁንስ በአፍሪካ ቀንድ ዳርቻ ያልለሙት አረማውያን ያሉበት ነው። ምንም ነገር አይደለም። ትሰማኛለህ? እና ፈረንሣይ ማለትስ ምንድ ነው? ፈረንሣይ ማለት ሁሉም ነገር ነው»

«ይህ በርስም አስተሣሰብ ነው፣ ክቡር አማካሪ? ስለአቢሲኒያ ብዙ ጉዳዮችን ሰምተዋል። ነገር ግን በአኳያው ደግሞ ስለነርሱ እንድፅፍ የገፋፋኝና የነገሩኝ እርስዎ ሲሆኑ፣ በሁለት የተለያዩ አገሮች ባህሎች መካከል ንፅፅር ይጀምራሉ። ገና ከመታወቃቸው በፊትም ይፈርጇቸዋል።»

«እንድትፅፍ፣ አዎን ነግሬሃለሁ። ነገር ግን ስለነርሱ እንድትናገር አላልኩም። ይባስ ብሎም በርግጠኝነት ስለነርሱ ለንጉሡ እንድትነግራቸው አላልኩም። የኔ እምነት የሚገባቸውና የሚሰማቸው ሰዎች ጥቂቶች ናቸው። ለዚህም ስል ነው ሃሣቤን በታሳቁ የፅሁፍ ጀረት ውስጥ እንዲፈስስ የምሻው። ይህን በማድረጌም ምናልባት አንድ ቀን አንድ እንደእኔው የሚያስብና መስማትም የሚፈልግ ሌላ ሰው በራስ መተማመንና ወኔ ኖሮት፣ ይህን አስቸጋሪና አስፈሪ ነገር ይፋ ያደርገው ይሆናል። አሁን ግን ማናችንም ልናረጋግጥ የሚገባን፣ሁሉም ሰዎች የሚያስቡትን ነው። ሁሉም ሰዎች የሚያስቡት ደግሞ ንጉሡ የሚያስቡትን ነው። ንጉሡ፣ ሃያል መሆናቸውን በሕይወታቸው ውስጥ የሚያስቡት ከሌሎች ጋር በማወዳደር አይደለም። በርግጥም ደግሞ እርሣቸው ሥልጣኔ ፈፅሞ አልደረሰባቸውም ከሚሏቸው ሰዎች ጋር ራሣቸውን እንዲወዳደሩም አይፈቅዱም። ፖንሴ፣ በወዳጅነታችን አምላክ፣ ላንተ ያለኝ ፍቅር፣ አባት ለልጁ ያለውን ፍቅር ዓይነት ነው። እናም በንጉሡ ፊት ስትቀርብ፣ በርሣቸው ሥልጣንና በአንድ ተራ የአገሬው ተወላጅ መሰፍን መካከል፣ ሌላው ቀርቶ ክርስቲያን እንኳ ቢሆን፣ አንዳች የሆነ ማወዳደር ብታደርግ እንደስድብ ወንጀል ይቆጠርብሃል። በዚህም የተነሣ የምትፈልገውን ነገር ወዲያውኑ በቅጣት ካሣ መልክ፣ ሌላው ቀርቶ ከዚህ አገር በነፃነት መውጣትንም እንድታጣ ትደረጋለህ።»

ወዳጁ በሃቀኝነትና በታማኝነት አጠንክረው በነገሩት ማስጠንቀቂያ፣ ጀን ባፕቲስት መቦረቅ የመታው ያህል ሆነ።

«እንግዲያውስ ምን ማድረግ አለብኝ» ሲል እየከፋው ጠየቃቸው።

«ሃሣብህን በፅሁፍ አስፍረው። እኔ እስከአሁን አጥብቄ እየሠራሁ ነኝ። ጽፈህ ስትጨርስ እንዴት እንደምናሣትመውና ለየትኞቹ አርቆ ተመልካች ግለሰቦች እንደምናሣይ የራሣችንን

ሥራ እንሰራለን። አሁን ለጊዜው ግን በንጉሡ ፊት በጀስዊቶቹ ላይ አንዳችም የተቃውሞ ነገር እንዳታሰማ። ምንም የሚያግዳቸው ነገር ሊኖር ባይችልም፣ ጉዟቸው ሊያጋጥመው የሚችለውን አደጋና ችግር አጋንነህ ታቀርብባቸው ይሆናል። እነርሱ በራሣቸው አነጋገር፣ ንጉሡ ሃይማኖታቸውን መለወጥ ይፈልጋሉ ካሉም አትቃወማቸው። እንዲያውም፣ እንዳላችሁ ብለህ ተቀበላቸው። ለንጉሡ አስተሣሰብ ካልተሸነፍክ በስተቀር፣ ክርሣቸው አንዳችም ድጋፍ አገኛለሁ ብለህ አትገምት። መኳንንት መሆን ትፈልጋለህ? ይህ ሙሉ በሙሉ ሊሆን የሚችል ስለሆነ እኔ ልረዳህ እችላለሁ። ነገር ግን አስቀድመህ ሰዎችን ማስደሰትን ማወቅ ይኖርብሃል። ለንጉሡ ታማኝነትህን አረጋግጥላቸው። የርሣቸውን ታላቅነት እስክ መሬት ዳርቻ፣ እስከምስራቅ አገር ነገስታት ዘንድ ዜናቸውን ማሠራጨትህንና ማስደንገጥህን ንገራቸው። ይህን የሰሙት ሁሉ ዝቅ ብለው አክብሮታቸውን ያቀረቡ መሆናቸውን ንገራቸው። እውነተኛው እምነት ግን፣ ለርሣቸው ምስጋና ይግባቸውና ይህንኑ ማበልፀግ ሲቻል መሆኑን አስረዳቸው። እናም ወደዚያ አገር አንድ ጀስዊት ይዘህ ሄደህ እንደነበረና የእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን ቀርቶ ካህኑ በመንገድ ላይ ማረፋቸውን፣ አሁን ግን ሌሎች ብዙዎችን መርተህ ለመውሰድ ተስፋ እንዳለህ ንገራቸው»

«ወደዚያ አገር ሌሎች ብዙዎችን መርቼ ልሄድ?» ሲል ጆን ባፕቲስት ተቆጣ። «እነዚህ ሰዎች ለዘለዓለም ተመልሰው እንዳይመጡ አደርጋቸዋለሁ ብዬ ለንጉሠ ነገስቱ ቃል ገብቼላቸዋለሁ።»

«ለቃል ኪዳን ክብርህ ልንም አብጅለት፣ ወጣቱ ወዳጄ። ጀስዊቶች፣ እምነታቸውን የሚከተል እጅግ ታላቅ የክርስቲያን ግዛት ንጉሥ እያላቸው፣ ብቻህን በነርሱ ላይ አንዳችም የማገጃ ግድግዳ መሥራት አትችልም። ይህ ቃል ኪዳንህ በጣም መጥፎ ነው። በአሁኑ ጊዜ የጠራ ክብር በሚባለው ዘመን ውስጥ አይደለንም። አንዳንዶች ይህ በመቅረቱ ያዝኑ ይሆናል። ከዚያ ታች ያሉት ባዶ ግርግምና ባዶ የእንጨት ገንዳዎችን እይተሣቸዋል? ልለምንህና፣ ስለምንኖርበት ዘመን ሣታውቅ አትሣሣት»

ጆን ባፕቲስት ወደ እሣቱ አቅጣጫ ተሸከረከረና ክንዶቹን አመሣቀላቸው

«አስቲ እናያለን» ሲል በጥርሶቹ መሃል ተናገረ።

6

በዚህ ሁሉ መሃል፣ ሙሴ ሌ ኖይር ዱ ሮውሌ፣ ካይሮ ውስጥ ብቅ ሲል አልቻለም። ቆንሲሉ፣ ሌላ የመርከብ መስመጥ ደርሶ እንደሆነ በሚል ፈራ። በአንድ የዛፍ ግንድ ላይ ተጣብቀው እንደቀሩት እንደ አባ ቬርሣው፣ የወደፊቱ አማቹም በአንድ የባህር ዳርቻ ውሃው ተፍቶት ይሆናል። አውነታው ይህን ያህል የሚያሳዝን አይደለም። ወጣቱ ዲፐሎማት በጉዞው ላይ ጊዜውን እየተዝናናበት ነው። ሌ ቪታቬቺያ ውስጥ ሰንብቶ፣ ወደሮም በሠረገላ ተንዘፍ፣ ከተማዋንም እስኪደሰትባት ጐብኝቶ፣ በሮማውያን ማህበረሰብ ውስጥ ከአንድ ወይም ሁለት ሴቶች ጋር ግንኙነት ፈጥሮ ቆይቷል። ከዚያም ወደባሪ በመሄድ ወደ ኮሪንዝ ተሻግሯል። በመጨረሻም አሌክሣንደሪያ ውስጥ ከታየ በኋላ ብዙም ሣይቆይ ካይሮ ደርሷል።

ምንም እንኳ ዱ ሮውሌ የበታቹ ቢሆንም፣ በቆንሳላው ውስጥ እንዲሰነበት ለማድረግ ሙሴ ዴ ማይሌ ወስኗል። ደረጃውንም እንደጨዋ ሰው ለማክበርና ይበልጥም የቤተሰቡ አካል አድርጐ እንዲሰማው ለማድረግ ፈልጓል። የልጁን የአሸታ ቃል በማግኘቱ እፎይታ የተሰማው ቆንሲል፣ የእጮኛዋን ሃሣብ ለማወቅ ጓጓ። አሊስን የምትፈቀር ሆና ያገኛት ይሆን? ቆንሲሉ፣ ለልጁ ልቡ እስኪጠፋ ድረስ ፍቅር ያለው አባት አይነት አልነበረም። ልጁን የሚፈርጃትም በአቋሟ ሣይሆን ተቀባይነት ባለው ልማድ መሠረት ስለሆነ፣ ያስፈልጋታል ሲል ገመተ። በትዕዛዙ መሠረት ባለፈው ሣምንት ከጊዛ አልተመለሰችም። ስለዚህም በፀሐይ ምክንያት ፊትዋ ይጠቁራል። የትም ቦታ በባዶ እግሯ ስለምትጓዝ ያልለሰለሰነች ሴት ትመስላለች። የተለሣለሰ ፍላጐት ያለውና የፖሪስ የውበት አዳራሾችን የለመደ ሰው እንዲህች ካለች ሴት ጋር ለድርድር መቅረብ አይፈልግም ይሆናል።

ዱ ሮውሌ በመጣበት ዕለትና ሻንጣ ወደ ግቢው በሚገባበት ጊዜ፣ አሊስ በአዳራሹ መግቢያ ላይ ብቅ ብላ ስለነበረ፣ ልብሷን እንድትለውጥ ወደ ፎቅ መልሶ ለመላክ እንኳ በጣም የዘገየ ነበር። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ጉንጮችዋ ምንም መጋጊያጪያ እንዳልተደረገባቸውና ፀጉርዋም እንደ ዝቅተኛዋ የቤት አገልጋይ ወደ ኋላዋ ተንጨሩርር መውረዱን በድንጋጤ አስተዋለ። ለርስዋ በጣም ትልቅ የሚሆንባትን የአናትዋን ቀሚስ ስብሳለች። ልብሱ አስቂኝ መሆኑ ብቻ ሣይሆን፣ የተቀዳደደና ጥቁር ቡኒ ቀለሙም፣ ካይሮ ውስጥ እንኳ ከአስራ አምስት አመት በፊት የቀረ ፋሽን ነው። በቆንስላው ውስጥ የነበሩት አገልጋዮች በሙሉ በአዳራሹ

መግቢያ ላይ ከማይሌዎች ኋላ ተሰልፈው ቆመው ስለነበረ በዚህ ሁሉ ሰው ፊት ለመገርመም አስቸጋሪ ነበር። ከዚህም ባሻገር፣ እንግዳ ደራሹ የሠረገላውን በር እየከፈተና አንድ አረባዊ እግረኛ ተከታይ መውረጃውን እያዘጋጀለት ነበር። ቆንሲሉ፣ ደረጃውን ጠብቆ መድረኩ ድረስ ሊቆይ አቀደ። ይህ የፕሮቶኮል ጉዳይ ስለሆነ ባለፈው ምሽት ከሙሌ ማቼ ጋር ተነጋግሮበታል። ይሁን እንጂ በወቅቱ በነበረው ሙቀት ተቻኩሎ ደረጃዎቹን በመውረድ እንግዳውን ከሰረገላው ግርጌ ቀርቦ ሰላምታ ሰጠው።

ሙሌ ሌ ኖይር ዱ ሮውሌ፣ ረዥምና ጥሩ ቁመና፣ ሽንቁጥ ያለ ወገብና ቀጥ ያሉ እግሮች ያሉት ነው። ይህ ቁመናው የሚያሣድረውን ተፅዕኖ በሚገባ ስለሚያውቅ፣ በዚያው ሁኔታ መውረዱ በግልፅ ያስታውቅ ነበር። ቀጥሎ ሊያገኘው የሚችለው ጠቀሜታ ካልታየው በስተቀር ፣ክንዶቹን ንቅንቅ አያደርግም። በተቻለው መጠን ተፈጥሮአዊ ሞገስን ጠብቋል። አንገቱን አቅንቷል፣ ተረከዞቹን እኩል ወጥሯቸዋል፣ ትከሻውን አስተካክሏል። ሊያዩት እጥፍ ዘርጋ የሚል ሰው ይመስላል። እንዲያውም የዳንስኛ ቅርፅ ያለው ያስመሰለዋል። ነገር ግን በውስጡ አንዳችም ሃይል የሌለውና ሞራውን የሚቆላ፣ በትልቁ ቁመናው ትልቅ ሞካኔውን የደበቀ፣ ትልቅ አዳኝ አውሬ ይመስላል።

አሊስ ፊቱን ስትመለከተው ተንቀጠቀጠች። ፊቱ እንደምላጭ ስል ነው። ጠባብ ቀዳዳዎች ያሉት ረጅሙ አፍንጫው፣ በወፍራሙ ከተጣጠፈው ግንባሩ ሥር ይነሣል። ጉንጮቹ የሰረጉዱ ናቸው። ከንፈሮቹ ስስ መስመር ሊመስሉ አንፖ ሹል ነው። ቆንሲሉ እያቀረበለት ለነበረው ትህትና የተመላ አቀባበል ምላሹን እየሠጠ፣ ሌ ኖይር ዱ ሮውሌ አይኖቹን ሆን ብሎ በተሰበሰቡት ተቀባዮቹ ላይ ወረወረ። አንደኛው የአይን ሽፋሽፍቱ፣ ወዝ ላይ የተሰበረ ደጋን መስሎ በስላች ይታያል። ከሌሎች ሰዎች ሁሉ ሊረዝም፣ ቅንድቦቹ እንደ መጋረጃ ባሰበት ድርቅ ብለው ስለሚቆዩ፣ ጥቋቁር ዓይናቹን ይከላከሉሰታል። በዚያ ከነበሩት ሁሉ ይልቅ አዚያው የነበረችውን ወጣት ሴት አጥብቆ አተኩሮና ልብ ብሎ አስተውሏታል። እርስዋም ብትሆን፣ እንዲህ ካለ ሰው፣ ውበቷን ፈፅሞ በቀላሉ ቸለል ብላ ልትደብቅ እንደማትችል ወዲያውኑ አወቀች።

እንግዳ ደራሹ፣ በዜተመንግስት ወግ መሠረት ለወይዛዝርቱ ሰላምታ አቀረበላቸው። ይህ የሠላምታ አቀራረብ ለነርሱ እንግዳ ቢሆንም አዲሱ ባህል ይሆናል በሚል ሁሉም ተቀበሉት። ከዚያም፣ እንግዳው ከቆንሲሉና ከሙሌ ማቼ ጋር ወደ ሕንፃው ውስጥ ገቡ። ለጥቂት ጊዜ ከተነጋገሩ በኋላ መንገደኛው ወደተዘጋጀለት ክፍል ሄደ። ሰዕራት ተመልሶ

ሲመጣ፣ ከቅድሙ ይልቅ በጣም ሽክ ብሎ ሰብሶ መጣ። ረቂቅ ብሩህ ሰማያዊ መስመሮች ያሉበትና በወርቅ የተጠለፈ ሰማያዊ ሰማይ የመሰለ ክፋይ ኮትና ከሱሪው ጋር የሚመሳሰል ነጣ ያለ ሃምራዊ ሰደርያ ለብሷል። በእራት ክፍሉ ውስጥ እርሱን የሚመስል አልነበረም። አንግዳውም፣ እሁን በቅርቡ ከቪርሣይለስ የመጣ ተራ ሰው ለመምሰል ይጥራል። ሴሎቹ፣ ከሁሉም በላይ ቆንሲሉ፣ ያረደ ቡትት የሰበሰ ይመስላል። ከአባቷ በስተግራ የተቀመጠችው አሊስ፣ የሚማርክ ቀሚስ ለብሳለች። ቀደም ሲል እንደማሳሳቻ ለብሳው፣ አባቷን ያናደደውን አይነት ግን አልነበረም። በማንኛውም ሁኔታ ግን፣ የዚህን ሰው እይታ ከርሷ ላይ ሊነቅልላት የሚችል ነገር እንደሌለ ተሰምቷታል። አንድ ነብር፣ ጥቅጥቅ ባለ ደን ውስጥ ድኩላ ያለችበትን ቦታ መለየት እንደሚችል ሁሉ፣ ይህም ሰው ውበቷን በትክክል አውቋል። የሌ ኖይር ዱ ሮውሌ አስተሣሰብ የሚጠቁመው፣ እርሱ ሰርሷ የመሆን መብት እንዳለው ሲሆን፣ እርስዋ ግን በዚህ ዓይነት አልገመቶችም ነበር። ይሁንና፣ አባቷና ፖንቻርትሬይን ስለጋብቻው አቅድ ሳይነጋገሩበት እንዳልቀሩ አያጠራጥርም። እርሷም ይህንኑ ገምታለች። በራሱ ርግጠኛ የሆነ፣ በውበቱና በጮሌነቱ የሚተማመንና ምንም ይሁን ምን፣ ሌላው ቀርቶ በተገቢው መንገድ ከተሰጠችውም በታላቅ ደስታ፣ በተገቢው መንገድ ባትሰጠውም እንኳ ሊወስዳት እንደሚችል የሚያመለክት የባሰኔ አተያይ አለው።

ሙሌ ሌ ኖይር ዱ ሮውሌ፣ በሚጥም ጨዋታው ዝበታውን አደመቀው። የሥነ ጥበብ ሥራዎችን ያፈቅራል። ገና ያላያቸውን፣ ነገር ግን ብዙ የሚያውቁ ሰዎች የሣፉትን አንብቦ፣ ስለግብዣውያን ሃውልቶች አስረዳቸው። እንደሞተር እየተንጣጣ ስለሚናገር የፊቱ ገፅታ ከአንድ ዓይነት መልክ ወደ ሌላው ይለዋወጣል። የጊታር ተጫዋች የግራ እጅ፣ ከአንድ ክር ወደ ሌላው በፍጥነት ዘልሎ ሲንቀሣቀስ እንደማይታይ ሁሉ፣ በሚለዋወጠው የፊቱ ገፅታ መካከል ልዩነቱን ለመገንዘብ የለውጥ ሽግግር ጊዜ እንኳ የለውም። የአይኑ ሽፋኖች ብቻ አይንቀሣቀሱም። ፍራፍሬ በቀረበ ጊዜ ግን በቀጥታ ወደ አሊስ ተመለከተ።

«እናም አንቺስ ማዳሞዜል፣ ለመሆኑ ስፊኒክስን አይተሽው ታውቂያለሽ?»

«የለም» አለችው ቆጣ ብላ

ገና በቅርቡ ከጊዛ ተመልሳ መምጣቷን አባቷ ሊናገር ሲል፣ የቃለ አጋኖ ድምፅ ሰማ። አሊስ ከገበታው ብድግ ብላ ገና አንድ ርምጃ እንደተራመደች አቅሏን ስታ ወለሉ ላይ ወደቀች።

ማዳም ዴ ማይሌ፣ ደውላ የጠራቻቸው ፍራንቾይዝና አንዲት የወጥ ቤት ሠራተኛ፣ ወጣቷን ሴት ተሸክመዋት ወደ ክፍሏ ወሰዷት። ወላጆችዋ በጣም ግራ ተጋብተው ተከተሏት።

«አየሽ፣ እዚያ ቤት ውስጥ የትኩሳት ሕመም ሊይዛት እንደሚችል እርግጠኛ ነበርኩ።» አሳት ቆንሲሉ ለባለቤቱ፣ የፎቁን ደረጃ በመውጣት ላይ እያሉ።

«አታተኩስም» አለች ማዳም ዴ ማይሌ

«ተይው ግዴለም። ቀኑን ሙሉ ተቀምጣ በማረፍ ሃሣቧን ሁሉ በልብ ወለዶች ስታደስደንቅ ስለምትውል እንፋሎት እየወጣት ልታልቅ ተወስና ስለነበረ ነው»

ይህ በዚህ እንዳለ፣ በእንግዳ መቀበያው ክፍል ውስጥ፣ ሙሴ ማቼ የወጣቱን ዲፕሎማት ሃሣብ ለማዛባት ሲል አጋጣሚውን በይቅርታ እንዲያልፈው ይለምነው ጀመር።

«መቼም ተላላፊ አይደለም፣ ነው እንዴ?» ሲል አፍንጫውን በዳንቴል መሃረብ ውስጥ ቀብሮ ሌ ናይር ዱ ሮውሌ ጠየቀ።

ጊዜው ወርሃ ታህሳስ ነበር። ቬርሣይለስ፣ አዲሱ ንጉስ ለቀዋት መሄዳቸውን ምክንያት በማድረግ ከተዘጋጀው ታላቅ ፌስታ በኋላ ክባድ ሃዘን አጥልቶባት ግውዝ ሆናለች። መናፈሻዎች በቢጫ ቅጠሎች ተሞልተውና በጭጋግ ታጥረው ወደ ጭለማው ደን ውስጥ የተዘረጉ የማንጣፊያ ቦኖች መረብ ይመስላሉ። ጥቂት ቅዝቅዝ ያሉ ጥላዎች ይታያሉ። ጥቂት አትክልተኞች በአንድ ዛፍ ሥር ዙሪያ ወይም ሜዳውን ወደፊትና ወደ ኋላ እንደ አራሽ ሰው በመጥረግ ሥራ ተጠምደዋል። በቀላሉ በሚሰባበረው የቦረቦር ግራጫ ድንጋይ ጣሪያ ስር፣ ቤተመንግስቱ አሣዛኙን የፊት ለፊቱን ገፅታውን እርጥበት ወዳለው ነፋስ አቅጣጫ አሰግንል። በመስተዋት መስኮቶች ጀርባ ቀኑን ሙሉ ሲበሩ የሚውሉ የያኮማ ፋናዎች ብርሃን ይታያል። ዋናውን አደባባይ ያቋረጠ ሠረገላ የለም። ነገር ግን የሠረገላውን ተሽከርካሪ ወጥሮ የሚይዘው የብረት ዘንግ በበሃ ድንጋይ ንጣፍ ላይ ሊንገጫገጭ የሚፈጠረው ስቅጣጭ ድምፅ፣ አንድ የተጫነ ጋሪ ወደ ሰው መግደያው ቦታ እየሄደ እንደሆነ ያስታውቃል። ከየእንጨት አጥሩ በስተጀርባ፣ የሠራተኞች የእንጨት መደሽዎች ድምፅ ከማይታየበት ሆነው ከአንድ ከፍተኛና ሰፊ የመውጫ መስመር ላይ ሲሰሩ ይሰማል።

ጆን ባፕቲስት፣ አባ ፕላንቴይንና አባ ፍሌኦሪአ፣ የቤተመንግስት ሹማምንት ከመሰብሰባቸው በፊት ሌሊቱኑ ገብተው ቬርሣይለስ ውስጥ በኢየሱስ ማህበረሰቦች በተሠራውና ወደ ራይን ወንዝ በሚያሣየው ቤት ምሽቱን አሣለፉ። በመጨረሻ ላይ፣ አባ ፍሌሃውት፣ ፖሪስ ውስጥ አልተቀላቀሏቸውም። እርሣቸው በቀጥታ በስብሰባው ቦታ ላይ እንደሚያገኟቸው ግን መልዕክት ትተዋል።

«ይህ ማለት እርሣቸው የሃይማኖት አባሎቻቸው አሉላቸው። በዚህም ላይ ፖንቻርትሬይንም ከጐኑ እንዲሆኑለት ይፈልጋል» አሉ አባ ፕላንቴይን።

ሌ ቢአው ኖይር ውስጥ፣ ጆን ባፕቲስት የለመደው የዶሮ አሮስቶ አራት ላይ በተከታታይ ቀረበ። እርሱ ግን የተኩሩ ጉመንና ንፁህ የአይብ ሾርባ ብቻ ተመገበ። ፍሌኦሪአ፣ እነዚህን አረንጓዴና የመነመኑ ነገሮች ተሰጥተውት ሊያመነዥካቸው ቆየና ሲጠግብ፣ ግብጣ ላይ የተመገበ ያህል ተደሰተ። በምድጃው ውስጥ፣ ነቀርሣ የመሰለ እሣት ለአጭር ጊዜ ቆየ። ፖንሴ፣ እራት የበላው ወፍራም ካባውን ለብሶ ነበር። ነገር ግን ጥርሶቹ ሁሉ ስሰተንጫገፖበት፣ አስቀድሞ በሚሞቀው መጥበሻ ቅዝቃዜውን እንዲሚማ የማድረግ ጥንቃቄ ወስዶ ወደ መኝታው ሄዶ እንዲተኛ ጠየቀ። በመንቀጥቀጥ ውስጥ ፍፁም ሰጥሞ የያዘውን ሙቀት ከአንድ ጐኑ ወደ ሌላው በማሸጋገር ለማቆየት ይችል እንዳሆነ ብቻ በማሰብ በበረዶ ውሃ ላይ እንደተጋደመ እንሰሳ ደንዝዞ ተኛ።

ማሰዳ፣ በሁለት ሰዓት ላይ፣ አንድ አጃቢ መጥቶ መጋረጃዎችን ሰበሰባቸው። እሣትም አነደደና ቁርስ እንዲበላ ካህናቱ እየጠበቁት መሆኑን ነገረው። ምግቡ እንደማታው ሁሉ የማያስደስት ነው። ከዚህም በላይ፣ በዚያን አይነት ሰዓት ላይ ለዶሮ ሾርባ ግድ የሌለው ፖንሴ፣ እየከፋውም ቢሆን በዚያ ቤት ውስጥ ሻይ፣ ቡና ወይም ቸኮሌት የሚባል ነገር እንደሌለ አወቀ። በአንድ ትልቅ ብርጭቆ ማልምሴይ እንዲሰጠው ጠይቆ፣ በአንድ ረዥም ትንፋሽ ጨለጠው። በዚህ መሃል አባ ፍሌኦሪአ መታመማቸውንና በዚሁ ዕለት ቀኑን ሙሉ ተኝተው ስለሚውሉ ወደ ቤተመንግስቱ ስብሰባ አብረዋቸው ሊሄዱ እንደማይችሉ አባ ፕላንቴይን ገለፁ። ያመማቸው ምናልባት ከትናንት በስቲያ ማታ የበሉት በርከት ያለ እራት ውጤት ሳይሆን አይቀርም።

አራት ሰዓት ላይ፣ አባ ዴ ላ ቾይዝ የላኩላቸው ሠረገላ ሲሽከረከር በር ድረስ መጣ። የአየሩም ፀባይ ከባለፈው ቀን ይልቅ ይበልጥ ጠቆርቀር ያለ ሰማይ ይታይበታል። ቢጫ

አብረቅራቂ ያለበት ትልቅ ጥቁር ደመና፣ በረዶ ለመጣል እያንገበገበ ሲሆን ብርሃኑን ሁሉ ውጦታል። በቤተመንግስቱ መግቢያ ግንብ የሚጠብቁት ስዊሳዊ ዘበኞች፣ ሦስት እጥፍ በሆነ ኮት ተጠቅልለዋል። በቤተመንግስቱ ጣሪያ ላይ የሚገኙት ጭስ ማውጫዎች ሁሉ ጢስ ቢትጮስጮልባቸውም፣ እነዚህ እንግዶች በቅጥር ግቢው ውስጥ ማንንም አላገኙም።

የአየሩ ጠባይ ለጆን ባፕቲስት ተስማምቶታል። እንዲህ ባለ ውብ ቀን፣ አብረቅራቂ የወርቅ ቅቦችና ጌጣጌጦች፣ የመናፈሻ ስፍራዎች ህብር፣ የሕንፃዎች ሽብረቃ የድል ብስራታቸውን የሚጭነብት ይሆኑ ነበር። ቢሆንም፣ ይህ ጢስ የሞላው ዋሻ አንዳች ትህትና ያለው ይመስላል። ንጉሡ፣ ያላቸው የሚመስላቸው ታላቅነት ሁሉ፣ እርሣቸውም ለወቅቶች ሃይል ተገዥ ስለሆኑ ራሣቸውንና በጐጀአቸው ውስጥ ያሉትን ነፍሳት ሁሉ ከዚህ ከሚለዋወጥ ባለጌ ዝናብና ቅዝቃዜ መከላከል ይኖርባቸዋል። በክረምት የቆፈን እጅ ውስጥ ያሰችው ሼርሣይስ፣ ለደስታና ለፈንጠዝያ የምትሆን ሳትሆን፣ ዜጐችዋ ሁሉ ለዘብ ባለው እሣት ዙሪያ በተራ የድንጋይና የሸክላ መጠለያዎች ውስጥ፣ ክረምቱ እንዲያልፍ ጀርባቸውን አጉብጠው የሚጠባበቁባት ከተማ ነች።

በታላቁ የእምነበረድ መወጣጫ ደረጃ በኩል ገቡ። አድርጉ የተባሉትን ለማድረግ ፈቃደኞች የሆኑት ሰዎች፣ ቀለል ያለ ልዩ ልብስ ለብሰዋል። እጆቻቸው በቅዝቃዜው ሰማያዊ ሆነውባቸዋል። ትልቁና ረዥሙ የመወጣጫ ደረጃ፣ ሲራመዱበት የበረዶ ርጥበትና የሠምና የእስክሬን ሣጥን ሽታ ሲሸትት፣ ከበላዩ የታፈነ የገደል ማሚቶ ድምፅ ይመጣበታል። ጉብኘ ዎቹ፣ ደረጃውን ጥብቅ በሆነ ሥርዓት ሽቅብ ይራመዱታል። ከነርሱ መካከል አንድም እንኳ የወርቅ ቅብ የተቀባውንና የፅጌሬዳ ቅርፅ ያለውን የብረት መደገፊያ የደረሰ የለም። ላይኛው ማረፊያ ላይ እንደ አጋጣሚ የሚያንሸካሸኩ አጃቢዎች አሉ። የሚቀሰቅሣቸው ማንም ይሁን ማን፣ የጉብኚዎቹን መድረስ ግን፣ አንድም ያስተዋለው ያለ አይመስልም። የመጨረሻውን ደረጃ ከወጡ በኋላ፣ ይህ ጥቂቶች ያስብት ቡድን የሚቀጥለውን ደረጃ ሳያስቡት ሽቅብ ተመለከቱት። አሁንም ገና በነርሱና በጣሪያው ኮርኒስ መካከል ብዙ ርቀት እየቀረ፣ የደረሱ የመሰላቸው ግራ የሚያጋባ ነው። ልክ በዚህን ጊዜ፣ አባ ዴ ላ ቾይዝ እነርሱ ካሳስተዋሉት መጋረጃ ውጥተው ተቀላቀሏቸው። የማይማርክ የካህን ልብስ ለብሰው፣ ክጥቁር አብረቅራቂ ሃር የተሠራ ቆብ በጭንቅላታቸው ላይ ደፍተዋል። ሰውዬው ባለማቋረጥ ፈገግ ይሉ። የማይለዋወጠው የፊት ገፅታቸው በመጀመሪያ ላይ የስኬት ሁኔታ መስሏቸው ነበር። በኋላ ላይ ግን ፍርሃት ሰቀቀባቸው። ከአኳኋናቸውና ከአግባ ንግግራቸው፣ ሰውዬው በነገሮች

የመጨረሻ ሰዓት ላይ ታላቅ መሆናቸውን ለማሣወቅ የሚጥሩ መሆናቸው ይታወቅባቸው ነበር። ለንቋሳው ቁመናቸው ከታላቁ ሕንፃ አኳያ ሲታይ አንክትክት ማለታቸው የማይቀር መሆኑን ያጋልጥባቸዋል። ፖንሴን በአይናቸው ቂጥ በፍርሃት ይመለከቱታል። ከሠረገላው ውስጥ ገና የሚወርዱና የሚመጡ ሁለት ሣጥኖች መኖራቸውን አባ ፕሳንቱይን ለፖንሴ ሲነግሩት፣ አባ ዴላ ቾይዝ ደግሞ ሁለት ምን ልታዘዝ የሚሉ ሰዎችን ጠሩ። ወዲያውም ክሳተርና ቁርጥ ያለ ምልክት ሰጧቸው። ይህ ድርጊታቸው በለውጹው ውጫዊ የርጋታ ሰውነት ስር ዘልቆ ያለውን ጥሳቻና ወዳጅነት አለመፈለግን ያመለክታል። አባ ፕሳንቱይንን ወደ ዳር ወስዷቸውና ወደ አንድ ትልቅ የጌጥ ቅርፅ ማውጫ በመዞር፣ በዝቅተኛ ድምፅ የሆነ ነገር ነገሯቸው።

የንጉሡን የንስሃ አባት ተከትለው፣ የዘቦች ወደ ሆነው ወደ መጀመሪያው ክፍል አመሩ። አባ ዴ ላ ቾይዝ፣ የመስኬቶ ጠመንጃ ሳንገተው ተረኛ መኮንን ሁለት ሰዎች ተሸክመው የሚያመጡት ሣጥን አለ ብለው ሲነግሩት ሳጥኑም ወዲያውኑ ደረሰ።

በመቀጠልም ወደ መጀመሪያው የእንግዳ መቀበያ ክፍል ገቡ። ይህ ሰፊ ክፍል፣ ንጉሱ በአብዛኛው አራት የሚበሉበት ነው። የነሐሱ ግድግዳ ብርሃን ይተፋል። መስኮቶቹ፣ በመስተዋቱ ውስጥ ምንም ባያንፀባርቁም፣ እየባሰ የሚጠቁር ብርቱካንማ ሰማይ ይታይባቸዋል። ኒየርት የተባለው ድንክ፣ አጭርና ሰው ሰራሽ ፀጉር ያጠለቀው የንጉሡ ቀደማይ የልፍኝ አስከልካይ፣ እንግዶቹን ለመቀበል በሩ አጠገብ ቆሟል። ተከትለውትም ወደ ሌላ ክፍል ሄዱ። ይህኛው ክፍል መብራት ባይበራበትም፣ ደብዘዝ ባለ ግራጫ ብርሃን የተሞላ ነበር። በተቃራኒው ጐን፣ ገርበብ ያለና የሠላሣ ሻማዎች ክባድ ብርሃን እየተንበገበገበት ያለውን ራቅ ያለ ክፍል የሚያሣይ ባለሁለት ተከፋች በር አለ። የልፍኝ አስከልካዩ፣ ከዙፋን ፊት የሚቀርቡትን ሰዎች በለልፍ ካዘጋጃቸው በኋላ፣ በሩን ወለል አድርጐ ከፍቶ ለንጉሡ አቀረባቸው።

7

የንጉሡ ክፍል ምንም ዓይነት የተለየ ነገር የለበትም። ምናልባትም፣ ሉዊስ 14ኛ ሊለውጡት የፈለጉትም ለዚሁ ይሆናል። ክፍሉ የእንግዳ ማረፊያ እንዳይሆን በጣም ትንሽ ነው። በተለይም ሦስት ታላላቅ የመግቢያ በሮች ያሉት ስለሆነ የግል ዕህፈት ቤት እንዳይሆንም እጅግ ከሚለፋው ከጋለሪ ዴስ ግላሴስ ጋር ሲነፃፀር በጣም ትንሽ ነው። ሽጋ ነው የሚለው አባባልም ክፍሉ ለጉራ ያመቻል ለማለት ነው። ይህ ሁሉ ሆኖ የሚጋነን ግርማ የለውም። ንጉሡ ትንሽ ራቅ ብለው ተቀምጠዋል። በተመለሙ ከሚያስፀሯት ጉዳይ አንፃር ሲታዩ፣ በደስታ የተሞሉ ወይም እንደ ስመጥር ገናና ሰው በዚያች ትንሽ ቦታ ሊሆን እንደሚችለው፣ እጅግ ጠንክራውና ሃያሉ፣ በርግቸው እዚያ መኖርም በዙሪያቸው ያለው ሁሉ በጉጉት እንዲደመጥ የሚያደርግ አይነት አይደለም። ንጉሡ እዚያ የተገኙት አንድ ሃብታም፣ በአንድ አነስተኛ የለምች ሰብሰብ ውስጥ ሲኖር ከሚታየው መደነቅ በማይልቅ መልኩ ነበር። ይሁን እንጂ፣ ከርግቸው፣ ባለሦስት ጠርዝ የሆነውና ነጫጭ ላባዎች ባሉት ባርኔጣቸው በቀላሉ ይለያሉ። ሌሎች ሰው ሰራሽ ፀጉራቸውን አጥልቀዋል።

ንጉሡ የታቀመጡበት ወንበር የመኖሪያ ቤት መቀመጫ መልክ ያለው ባለመደገፊያ ሲሆን፣ ሻር ጫሩ ግን በሚያብረቀርቅ የጌጥ ምስማር የተከፈፈ፣ ጥቁር ቆዳ ሆኖ ባሦስት ተሸከርካሪ እግር ላይ ጉብ ያለ ነበር። በመቀመጫው ኋላ ያሉት ሁለቱ ትላልቅ ተሽከርካሪዎች፣ ለንጉሡ ነፍስ ለማራገብ ለቆሙት ጥንድ የስዊዝ ዘበኞች አመች ሲሆኑ በፊት ለፊት ያለው አነዱ ተሽከርካሪ፣ ንጉሡ ራሣቸው ወደፈለጉት አቅጣጫ ሊያንቀሳቅሱት እንዲችሉ ተደርጉ እጅታ ተበጅቶለት በብረት ንጣፍ ላይ የተያያዘ ነው። ከዚህ እንዲያግዛቸው ተብሎ ከተዘጋጀላቸው መሣሪያ የበለጠ የንጉሡን አካለ ደካማነት፣ የሚያሣጣው፣ ሌላ ነገር የለም። አንድ እንደጣሦት የሚታሰብ ሰው በሃይሉ ብቻ ልዕለ ሰው ተደርጉ እየታሰበ ሣለ፣ ንጉሥ አንግዳና ውስብስብ የሆነ ባለሦስት ተሽከርካሪ እግር ላይ ሆኖ ደካማነቱ ሲታይ ሩጂያውኑ ያ የሣሰት እምነት በንኖ ይጠፋል።

ንጉሡ ቅዝቅዝ፣ ምንችክ ያሉና በድን ባለግርማ መስለው ቀርበዋል። የአኗኗናቸው ቀልል ማለት የተብሣፖ፣ ያልተደሰቱና ስሜታቸው የተጉዳ መሆኑን ይናገራል። ለጀን ጥፐቲስት እንዲህ ባሰ በክሩት ስብሰባ ውስጥ መግባት የመጀመሪያው አግራሞቱ ነበር።

ንጉሡ፣ በተለይም ካይሮ፣ የቆንስላውን ጽህፈት ቤት በማድመቅ የሚገኘውን የቀለም ቅብ ስዕላቸውን ግልፅ ባልሆነ መልክ ይመለከሉ። ጀን ባፕቲስት አሁን ከፊት ለፊቱ የሚያየውንና ያንን ስዕል አነፃፀረ። በርሱ ግንዛቤም፣ ሠዓሊው፣ የንጉሡን አምሣያ ስዕል ሣይሆን፣ መንፈስንና ልብን ሊማርክ የሚችል የነፃዱን ዓለም ነፀብራቅ ነበር የሣለው። ምክንያቱም፣ በስዕሉ ላይ ፈንጣጣ የወጋጋው፣ የቀላው አፍንጫቸውና በአንገታቸው ላይ ያለው የተንጠለጠለ ቋት የመሰለ ትርፍ ነገር ተዘልሏል። በአጭሩ፣ ስዕሉን እንዲታደስ ያደረገው ሙሉ ዴ ማይሌ ስህተት ሠርቷል። ምክንያቱም ተፈጥሮ ራስዋ፣ ከሰዓሊው ይልቅ የተሻለ አድርጋ ባስቀመጠችው አካል ላይ አስጠሊታ የቀለም ጠብታዎች እንዲያርፍበት ተደርጓል። በንጉሡ ዙሪያ ከተሰበሰቡት መካከል፣ ፍሌሃውት በጠርዝ በኩል መቆሙን ጀን ባፕቲስት አስተዋለ። ሰላ ረዥም ሰው ከነሱ፣ ነገር ግን ለንጉሡ ቀረብ ብሎ ቆሟል። ምናልባትም ቻንሰለር ፖንቻርትሬይን ሣይሆን አይቀርም። በዚያ ቦታ ተገኝተው የነበሩት፣ ከዝቅተኛው ወንበር ጐታች ስዊሣዊ ድረስ የነበሩት ሁሉ፣ ንጉሡን በመኮረጅ የባለስልጣንነት ስሜትን ተላብሰዋል። ሁሉ አኳኋኖች ቡጣም ስለሚመሣሰሉ፣ ሌላው ቀርቶ በፍትህ መዘበት የተቆጡ፣ በሃፍረተ ቢሱ የአዲሶቹ መጪዎች ጣልቃ ገብነት የተናደዱ ይመስላሉ።

ጀስዊቶቹ በተለየ የትህትና መልክ ጉንበስ አሉ። እንዲህ ያደረጉት የሰው ልጆች ሙሉ በሙሉ መሸነፍንና መስገድ የሚገባቸው ተጠቃሚ ለሚያደርጋቸው ለእግዚአብሔር ብቻ ነው ከሚል አሳቤ ነው። ጀን ባፕቲስት፣ የሰላምታ አትርቦቱ በቅዕበት የሚከናወንና የሚያልፍ መሆኑን በማስታወስ ወለሉ ላይ እስኪነበፍ ድረስ ዝት አለ። ይህ አይነቱ የሰላምታ አቀራረብ የጊዜው ፋሽን ሣይሆንም ከልብ የመነጨ ስለነበረ፣ በንጉሡ ነገስቱ ፊት እንዲያ ዘመንብጡ የሚያናርበትና የማይፀፀትበት መሆኑን የሚያሣይለት ነበረ።

ሥነስርዐቱ ካበቃ በኋላ ለጥቂት ጊዜ ያህል አጠቃላይ የማመንታት ሁኔታ ነበር። ጀን ባፕቲስትም በበኩሉ በክፍሉ ውስጥ በጉልህ የሚታይ ውጥረት እንዳለ አስተዋለ። ይህ ውጥረት ካህናቱንና ፖንሲን፣ በንጉሡ ዙሪያ ካለው ቡድን በጥቂት ሜማዎች ርቀት በሚለየው ቦታ ላይ በክፍተኛ ሁኔታ ይስተዋላል። ወዲያውኑ ህማህምታው በክፍሉ ውስጥ ያለውን አየር ልክ በአንድ የበጋ ቀትር ላይ በነጮድጓድ ውስጥ ሊፈጠር እንደሚከማች የመብረቅ ሃይል ሊሰማ በሚችል መጠን ሞላው።

«ጃንሠይ» በማለት ወደ ሚያስፈራው ስብስብ፣ አባ ቾይዝ ብቻቸውን በድፍረት ተራመዱ። «ወደ ምሥራቅ ላለን ተልዕኮ ሃላፊ የሆኑትን አባ ፍሌኦሪአን ታውቂቸዋላችሁ።

በዛሬው ዕለት እጅግ በመታመማቸው ምክንያት በመካከላችሁ ሊገኙ ባለመቻላቸው አዝነዋል። ይሁን እንጂ የቱርካውያን አገዛዝ ውስጥ ከሚገኙት አገሮች መካከል በተለይም በግብፅ፣ እኛን በመወከል ከባድ ሃላፊነት ተሸክመው ያሉትን አባ ፕላንቱይንን ሳቀርባቸው ታላቅ ክብር ይሰማኛል»

አባ ፕላንቱይንም ሰፊውን ግንባራቸውን እንደገና አንድ ጊዜ ዝቅ አደረጉና እጃቸውን ልባቸው ላይ አሣረፉ።

«እናም ግርማዊነትዎ በአርቆ አሣቢነትዎ፣ ወደ አቢሲኒያ የሚደረገው ተልዕኮ እንዲንቀሣቀስ ያዘዙትና የረዱትም ከዚህ አገር የተንቀሳቀሰ ነበር» ሲሉ የንጉሡ የንስሃ አባት ቀጠሉ። «በዚህች ያልታደለች የክርስቲያን አገር ውስጥም ጥሩ መሠረት ለመያዝ ድጋሜ ሙከራ ተደርጓል። አንዳሰመታደል ሆኖ በምዕተ ዓመቱ መጀመሪያ ላይ፣በተግሣተ አስተሣሰብ፣መናፍቃን በሚል ሰበብ ብዙ ወንድሞቻችን ተጨፍጭፈውበት ነበር። ልዑላን ሆይ፣ሕዝቦች ከስህተትና ከማይምነት ካልተላቀቁ በስተቀር ለዘለዓለሙ ተፈርዶባቸው፣ ተከንነው፣ እንደሚቀሩ በማወቅ የኛ የሃይማኖት ሥርዓት ያከናወናቸውን እጅግ ከባድ ጥረቶች ታውቃላችሁ። መልካም ፈቃዳችሁ ቢሆን ስትመኙት የነበረውን ተልዕኮ በተመለከተ አባ ፕላንቱይን ጥቂት መግለጫ ይሰጣሉ»

ንጉሡ፣ የአረንጓዴውን ጃኬታቸውን እጅጌ ሰብሰብ አድርገው በመዳፋቸው መሃል በትንሹ አሣሉ። ምንም እንኳ እንቅስቃሴው በጣም ፈጣንና አይን የማይገባ ቢሆንም፣ ንጉሡ የአፋቸውን የቀኝ ዳርቻ በእጅጌአቸው ጨርቅ ጠርዝ ሊጠርጉት ተመለከተ። ከንፈራቸውም በዚያ አቅጣጫ ጣል በማለቱ አፋቸው ሙሉ በሙሉ አልተከደነም።

«አባ፣ ይናገሩ። በዚህ ጉዳይ ላይ ትልቅ ፍላጉት አለን።» አሉ ንጉሡ

«ጃንሆይ» አሉ አባ ፕላንቱይን ግንባራቸው እየቀላ። «ይህን ጀግንነት የሚጠይቅ የሃይማኖታችንን ተስፋ ወደዚያ እሩቅ አገር ለማድረስ የወጡት በእሁኑ ሰዓት በዚህ ዓለም የሌሉ መሆናቸውን በሐዘን መግለፅ ይገባኛል። በዚያ ፈታኝ ጉዟቸው ላይ እግዚአብሔር ወደራሱ ጠራቸው። መስዋዕትነታቸው ግን እንደመታደል ሆኖ በከንቱ አልቀረም። የአቢሲኒያው ንጉሠ ነገስት ቀሪዎቹን መልዕክተኞች በታላቅ አክብሮት ተቀብለዋቸዋል። ንጉሠ ነገስቱ ለካቶሊክ እምነት በሚገባ ዝንባሌ እንደነበራቸው ገልፀው፣ አሁን ግን ሊቀላቀሉ እንደማይፈልጉ አጥብቀው ተናግረዋል። ከዚህም በላይ በግርማዊነትዎ መማረካቸውንና በዓለም

ላይ ሃያሉ የክርስቲያን መሪ መሆንዎን ተቀብለዋል። አክብሮታቸውን ለመግለፅም እስከ ካይሮ ድረስ አንድ የመልዕክተኛ ቡድንና በራሱ ሕዝብ መካከል ደረጃው ባይታወቅም አምባሣደር ሊባል የሚችል ሰው ልከው ነበር»

«እንግዲያውስ ሰውዬው አሁን እዚህ ለምን የለም» አሉ ሉዊስ 14ኛ

«ጃንሆይ፣ እኛም ልናመጣቸው ከልባችን ፈልገን ነበር። ነገር ግን ግርማዊነትዎ እንደሚያውቀው፣ አውሮፖዊ ተወላጅ ያልሆነ ሰው፣ ወደ አውሮፖ እንዳይንገዝ ቱርኮች ብዙ እንቅፋቶችን ይፈጥራሉ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ አምባሣደሩ የመጡት ብቻቸውን አልነበረም። አጀቧቸው የመጣውና አሁን እፊትዎ የሚያዩት ሙሴ ፖንሴ ነበር»

አባ ፕላንቱይን ወደ ጆን ባፕቲስት ዞር አሉ። በክፍሉ ውስጥ ቀደም ሲል ሰፍኖ የነበረው ውጥረት እንደገና አገረሸበት። የዚህ ሁሉ ማዕከላዊ አትኩሮት እርሱ እንደሆነ ጆን ባፕቲስት ተገነዘበ።

«ሙሴ ፖንሴ፣ በምስራቅ ሜዲቴራኒያን ጣቢያዎች የመድሃኒት ቅመማ ሥራ ይሠራል። በአሁኑ ጊዜ መኖሪያው ካይሮ ውስጥ ነው። ለግርማዊነትዎ ቀደም ሲል የገለፅኳቸው ነፍሣቸውን ይማረውና አባ ዴ ብሬቬደንት፣ ወደ አቢሲኒያ ጉዟቸውን ያደረጉት ከርሱ ጋር ነበር። ያን ጊዜ ንጉሠ ነገስቱ ታምመው ስለነበር አውሮፖዊ የመድሃኒት አዋቂ እንዲያያቸው ጠይቀው ነበር። በዚህም መሠረት በሙሴ ፖንሴ አማካይነት አቢሲኒያውያን፣ ንጉሥ እያሱ ወደሚጠሯቸው መሪያቸው ዘንድ የመድረስ ዕድል አገኙ። ከዚያም፣ ከዚሁ ከሙሴ ፖንሴ ጋር የአቢሲኒያውያን መልዕክተኞች የመልስ ጉዞ አደረጉ»

ይህን ተናግረው አባ ፕላንቱይን ወደ ኋላ ተራመዱና ጆን ባፕቲስትን ተመለከቱ። ሉዊስ 14ኛም በተራቸው ዐይኖቻቸውን ወደ ሐኪሙ መረመሩ። የንጉሡ ከፍተኛ ባለስልጣን አጃቢዎችም እንደመሪያቸው አደረጉ። ጊዜው ደረሰ።

ጆን ባፕቲስት፣ ለአመል ያህል ወደፊት ተራምዶ ከወገቡ ጐንበስ ካለ በኋላ ቀጠሉ።

«ጃንሆይ፣ የአቢሲኒያው ንጉሠ ነገስት ለግርማዊነትዎ እንዲያደርሱት የላኩትን መልዕክት፣ አምባሣደሩ እዚህ ሊገኙ ባለመቻላቸው እኒያ ከፍተኛ ገዥ፣ በዚህ ቤተመንግስት እንዲሰማላቸው የፈለጉትን መልዕክት የማቅረብ ሃላፊነት በኔ ላይ ወድቋል። በዚህም ላይ ማከል የምፈልገው፣ ንጉሠ ነገስቱ፣ ግርማዊነትዎ መልስ እንደሚልኩላቸውም ትልቅ ተስፋ

እንዳላቸው ነው። እኔም ሕይወቴን እንደገና አደጋ ላይ የሚጥል እንኳ ቢሆን፣ የግርማዊነትዎን መልስ ይዤ ሰመሄድ ሙሉ በሙሉ ለመታዘዝ ከፊትዎ እገኛለሁ።

«የተሰጠህ መልዕክት ምን ነበር?» ሲሉ ንጉሡ ጠየቁ

«ጃንሆይ። የተሰጠኝን መልዕክት አናገራለሁ። ነገር ግን ግርማዊ ንጉሠ ነገስት መልካም ፈቃድዎ ከሆነ የአቢሲኒያው ንጉስ ባዶ እጅን እንዳልሰደዱኝ ሰመናገር እፈልጋለሁ። የንጉሡ ግዛት እጅግ ሃብታም ነው። ምድራቸው ማዕድናትና እንቁ የሞሉበት ነው። እንሰሣት የሞሉበት ደናቸው ሊታመን ከሚችለው በላይ እጅግ ሰም ነው። ንጉሡ፣ ወዳጅነታቸውን ሊገልፅላቸው የሚችል ከሆነ በማለት ለፈረንሣይ ንጉሥ የላኩላቸውን ስጦታ . . . »

በዚያ ቦታ በነበሩ ሰዎች መካከል ጉርምርምታ ተፈጠረ። የንጉሡ ዓይን ግን ትክ እንዳሉ ነበሩ።

« . . . ያላቸውንም አድናቆት እንድገልፅ ጠይቀውኛል» ካለ በኋላ ጆን ባፕቲስት በጣም ፈጠን ብሎ «የዚህን ሃብት እጅግ ውብ ናሙናዎችንም እንዲቀበሉ ልከውኛል»

«መልካም» አሉ ሉዊስ 14ኛ «ገፀ በረከቶቹ የታሉ?»

ዓይኖቹ በአስተናጋጆቹ እግሮች ስር በነበረው ሣጥን ላይ አረፈ።

«ጃንሆይ፣ ንጉሠ ነገስቱ አምስት በቅሎዎች ላይ የተጫነ የወርቅ ዱቄት ስጥተውን ነበር። ከዚያም በሌሎች አራት በቅሎዎች ላይ የተጫነ ዝባድና እጣንም ጨምረው ነበር። ከዚያም በላይ ዛሎችና በአስም ላይ በሌላ ቦታ የማይገኝ አሥር ክረጢት ሙሉ ድንቅ ጣዕም ያለውን ቡና ልከው ነበር። ይህ የመጀመሪያው ጭነት ነው። ይህን ተከትሎ ሙሉ በሙሉ ያልተዳቀሉ፣ ግርማዊነትዎን በእጅጉ ሊያስደስቱ የሚችሉ ቁመናቸው የሚያምር ድንገላዎች ነበሩ። እነዚህ ፈረሶች በማንኛውም አይነት መልክአ ምድር ላይ እንደልባቸው መንዝ የሚችሉ ነበሩ። ንጉሠ ነገስቱ፣ እነዚህ ፈረሶች በውብ ኮርቻዎች እንዲጫኑና እንዲለመሙ ይፈልጉ ነበር። ከእነዚህ ፈረሶች ጐን፣ ከንጉሡ ዘቦች መካከል እጅግ ጠንካሮችና በዚያ ክፍተኛ አምባ ምድር ላይ ማንኛውንም ዓይነት ነገር መቋቋም ይችላሉ የተባሉ ስምንት ምርጥ አቢሲኒያውያን ወታደሮች ይራመዳሉ»

ጀስዊቶቹ ቀስ በቀስና ሳይታወቃቸው ጆን ባፕቲስት እየተናገር ሣለ እርሱን ላለማየት ወደኋላቸው አፈገፈጉ። ቀጥ ብሎ ቆሞ አንዳንድ ጊዜ የሁሉም የበላይ የሆኑትን ንጉሠ ነገስት፣ አንዳንዴም በዙሪያቸው የሚገኙትን አዳማጮች ላይ ዐይኖቹ ያርፋሉ። በልበ ሙሉነት ድምፅ ስለሚናገር ለአፍታ ያህል በክፍሉ ውስጥ የነበረው ሹክሹክታ ረጭ አለ። ወርቅ የተጫኑት በቅሎዎች፣ አሸብርቀው የተዘጋጁት ፈረሶችና የወጣት አቢሲኒያውያን ወታደሮች ለልፍ ክፍሉን ከአንድ ዳርቻ ጀምሮ እየተጓዘ በመሙላት ወደ ሌላው ዳርቻ ዘልቆ ወደ ጋለሪ ዴስ ግላሴስ በመግባት ከአይናቸው የተሰወረባቸው መሰላቸው።

«ከበስተጀላችን» በማለት ጆን ባፕቲስት ቀጠሉ።

«ለልፋን በማጀብ የጀርባ ጠባቂዎቻችን በመሆን የታሰሩበት ሰንሰለት የብር ቃጭል ታስሮለት ሊከተሉን የነበሩት ዝሆኖች ተብለው የሚታወቁት ግዙፋን እንሰሳት ነበሩ። የነዚህ ዝሆኖች ጥርሶች የአንድ ሙሉ ሰውን ሃውልት ማሠራት የሚያስችል ርዝማኔም ነበራቸው።»

ፖንቻርትሬይን ወደ ንጉሠ ነገስቱ ጆሮ ዝቅ ብሎ የሆነ ቃል ሹክ አላቸው። ይህ አስተኛ እንቅስቃሴ በዚያ ክፍል ውስጥ የነበረውን የተመስጦ ማዳመጥ አወከውና ንግግሩ ተቋረጠ።

«በአሜሩ» ሲሉ ንጉሡ አቋረጡና «የተናገርከው ሁሉ በዚህ ሣጥን ውስጥ ነው እንዴ?»

ምፀታዊ ጉርምርምታ ከአጃቢዎች አካባቢ ተቀሰቀሰ። በፊቶቻቸውም ላይ ሰይጣናዊ ፈገግታ ብቅ አለ።

«በሞትኩት፣ ጃንሆይ፣ በተወሰነ መልኩ አዎን»

እያደገ የነበረው ጉርምርምታ ፈነዳ። ውሃ በአሣት ላይ ሲፈስስ የሚፈጠረውን የጭስስታ ድምፅ አይነት ሣቅ ተከተለ።

«አዎን» ሲል ጆን ባፕቲስት ትልቆቹንና ቅን ዓይኖቹን ወደ ሉዊስ 14ኛ በማቅናት ደገመው። «ጉዞው የያዝናቸውን ብዙ ድንቅ ነገሮች ወስዶብናል። የአየር ጠባዩ ድንገላሞቹን ገደላቸው። አብረውን የመጡትን አቢሲኒያውያን ቱርኮች ወረሷቸው። ወርቁ፣ዛሎቹና እጣኑ ተሰረቁብን»

ወደ ሣጥኑ አንድ ርምጃ ተጠጋ

«ጃንሆይ፣ ይህን ለመቀበል ያጠራጥር ይሆናል። ነገር ግን የአቢሲኒያው የበላይ ገዥ እርስዎን ለማክበር የፈለጉበት ይህ አፀብ ድንቅ ነገርና የኔን ትረካ የሚያረጋግጠው ይህን ነው»

አስቀድሞ አጃቢዎቹን የብረት መፈልቀቂያ አስይዟቸው ነበረ። ጆን ባፕቲስት፣ በፊቱ ምልክት በመስጠት ሣጥኑን እንዲከፍቱት አዘዛቸው። ንጉሡ፣ ስዊሳውያን ዘቦቹ ወደፊት ጥቂት ርምጃዎች ወንበራቸውን እንዲያሽከረክሩላቸው ምልክት ሰጡ። የማንቀሣቀሻ ዘንጋቸውን በመጠቀም በግራ በኩል ሊታይ የሚችለውን ለማየት፣ራሣቸውን በስያፍ አስቀመጡ። ሁለቱ አጃቢዎች ሣጥኑን ለመክፈት በሚጥሩበት ጊዜ በክፍሉ ውስጥ የሚጠበቀው ፀጥታ ሰፈነ። በዚያን ሰዐት ይሰሙ የነበሩት ድምፆች በምድጃው ላይ ይንተገተግ የነበረው የግንዲላ እሣት ነበልባልና ሣጥኑ ሲፈለቀቅ በሚሰማሮች ላይ የሚሰማው መንሣጠጥ ብቻ ነበር። በመጨረሻም የሣጥኑ ክዳን ተከፈተ። ጆን ባፕቲስት፣ አጃቢዎቹ ወደ ኋላ እንዲሉ ካመለከታቸው በኋላ የሣጥኑን ክዳን በአንድ በኩል አስቀመጠው። ይታይ የነበረው አንድ ቀለሙ ቡኒ የሆነ የረጠበ የናይለን ጨርቅ፣ የሆነ የተወጠረ ነገር ሽፍኖ ነው። ጆን ባፕቲስት ጨርቁን አንስቶ ሲጥለው የቀረው ሁሉ ቁልጭ አለ።

ለእፍታ ያህል ቆም አለና በመቀጠልም በሁለት እጆቹ የሣጥኑን ስፋት ያህል ነገር ጨበጠ። ከፍ አድርጐ ሲይዘው ክባዱ ነገር በስበት ሃይል ድጋፍ ተዘረጋጋ። አረንጓዴ፣ ፈዛዛና አስጠሊታ ነገር ነበር። የዝሆኑ ጆሮ በሻጋታ ቅርፅ የማይታወቅ ነገር መስሏል። ሲዘረጋ፣ ነጣ ያለ ደቃቅ፣ የተበላሸ ዱቄት የመሰለ መርዛማ የደመና ብናኝ ፈሰሰበት። አስጠሊታ መልክ ያላቸው ነፍሣት በገጠማቸው ድንገተኛ ድንጋጤ በየአቅጣጫው እግሮቻቸው፣ ክንፎቻቸውና አንቴናዎቻቸው የረዷቸውን ያህል እየዘለሉ ተፈተለኩ። በዚያ ክፍል ሁሉ ውስጥ፣ በሚያስፈራ የመንጋ ብዛት ተፈተለኩ።

በነገሩ የመበስበስ ሁኔታ ጆን ባፕቲስት ነፍሱን ሣተ። ዙሪያውን ሁሉ በተስፋ መቁረጥ መልክ ተመለከተ። የሚያደርገው ቢያጣ ከፊት ለፊቱ የሚገኘውን ብል ያከተውን ጨርቅ ማራገፍ ሲጀምር ታምኮ የከረመውን ቆሻሻ ወደ አየር ውስጥ ናኘው።

ለእፍታ ያህል የመደነቅ ሁኔታ የነበረበት የቤተመንግስቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናት አጀብ በሁካታ ተተረማመሠ።

«ንጉሡን! ንጉሡን! ያገር ያለህ!» ሲል አንድ ድምፅ ጮኸ። ፖንቻርትሬይን ይመስላል። «በዚህ ውስጥ ፊፅሞ እንዲተነፍሱ እንዳታደርጓቸው»

ስዊሣውያኑ ዘበኞች የንጉሡን ወንበር አሽከርክረው ወዲያውኑ ወደ ሰገነቱ በሚያደርሰው በር በኩል ይዘዋቸው ወጡ።

«ዘብ! ዘብ! ዘብ ጥሩ!» ሲል ሌላ ድምፅ ጮኸ

«ሐኪም»

በዚያ የተሰበሰበው አጀብ ሁሉ ጆን ባፕቲስትን ትቶ ሸሸ። እርሱ ግን ብቻውን ቅርንጫፈ ብዙ በሆነው ተንጠልጣይ የሸማ መብራት ሥራ ተንተሮ ቀረ። ሌሎቹ በየጥጋጥጉ አራት ትንንሽ ስብስብ ሰርተው ይታያሉ።

የሆነ አንድ ሰው «መርዝ» ሲል ተናገረ። ይህ ቃል እነደተሰማ በቤተመንግስቱ አጃቢ አባላት ዘንድ የማይረሳ ድንጋጤን በመፍጠሩ፣ እያንዳንዱ አፍንጫ ወዲያውኑ በመሃረብ ወይም እጅጌ ላይ በተንጠለጠለ ጨርቅ ውስጥ ተቀበረ። ዘቦቹ በሩን በርግደው ወደ ክፍሉ ውስጥ ገቡ። ስድስት የሚሆኑ ሰዎች በያዙት የመስኬቶ ጠመንጃ ስደፍ ጆን ባፕቲስት በእጁ ላይ የነበረውን ደስ የማይል ሽታ ያለበትን ገዳይ ነገር እንዲጥል እጆቹን በመምታታ ተረባረቡበት። ግርግዳው ላይ የነበረውን መጋረጃ በጥሰው ጥለው ሣጥኑንና ሌላውንም ሁሉ ነገር ጠቅልለውበት ወደ እሣቱ ውስጥ ጣሉት። ቤቱም እንዲናፈስ ተደረገ። በስብሰባው ላይ የነበሩትም አርቆ አሳቢ የሚባሉ አጃቢዎች፣ ጀስዊቶች ከቆይታ በኋላ እንዲወጡበት በተፈቀደላቸው ጋለሪ ዬስ ግላሴስ በኩል አለፉ።

ንጉሡን ለማየት ክፉኛ ተጨንቀው የነበሩት አባ ዴ ላ ቾይዝ፣ ንጉሠ ነገስቱ ለደህንነታቸው ሲባል በመጨረሻ ላይ ወደ ተወሰዱበት ክፍል ገቡ። ፋጉን የተባለው የንጉሡ ሐኪም፣ በተነነው ነገር ሣቢያ ምንም የመርዝ ምልክት እንደሌለ አስረዳ። ለጥንቃቄ ሲባል ግን አንድ ጉድጓዳ ሣህን የፈላ የአሀያ ወተት አዘዘ። ጀስዊቱ ሲደርሱ፣ ፖንቻርትሬይን ከማማከሪያው ክፍል አስቀድሞ ሄዶ ነበር። ላ ቾይዝ፣ ከንጉሠ ነገስቱ እግር ስር ወድቀው ይቅርታ መለመን ጀመሩ።

«ይተዉ» አሉ ሉዊስ 14ኛ «ይነሱ አባቴ። ይህ ምንም ማለት እንዳልሆነ ያረጋግጣል። ከኔ ይልቅ ስዊሳውያን ጠባቂዎቼ ቡጣም ፈርተው ነበር። እኔ ግን በዚህ ወንበር ላይ እስረኛ ቸው ሆኜ . . . »

«ጃንሆይ በሆነው ነገር ሁሉ በጣም አዝናለሁ»

«የሚያመጡልኝን ገፀበረከት ለኔ ከማቅረብም በፊት ይመልከቱት» አሉ ንጉሡ በትህትና በመጠኑም የምፀት ቅላፄ ባለው አነጋገር።

«ማየትማ . . . »

«ይህን አጋጣሚ እዚሁ ላይ እናቁመው።» አሉ ንጉሡ አቋርጠውው። «ያውቃሉ፣ ክፉ ነገር ይመጣል ብዬ አስቤ ነበር። ሰውዬው የሚታመን አይመስልም። ከየአቅጣጫው ጠንካራ ጥርጣሬዎችን ስምቻለሁ። እንደ እውነቱ ከሆነ ሰውዬው አስመሣይ አጭበርባሪ ነው ብለው ብዙዎች ፈርተው ነበር። እርስዎንም የነገሩኝን ሁሉ ሰምቼ ነው ልቀበለው የተስማማሁት»

«ጃንሆይ፣ ድርጊቱ ጥሩ እንዳልሆነ እኔም እስማማለሁ። ነገር ግን በኛ በኩል ስለሰጠው መግለጫ ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ እንኳ አልነበረንም»

«አባ፣ እርስዎ ቅዱስ ሰው ነዎት። የዚህን ጋኔን ማንነት በሚጋልጥም፣ከፊት ለፊትዎ ከሚቆም ሥጋ ከለበሰ ወስላታ ይልቅ እርስዎ ይበልጥ የለለጠኑ ይሆናሉ።»

ንጉሡ፣ ጋኔን የሚለውን ቃል ሲጠቅሱ፣ ለንስሃ አባታቸው እየተናገሩ ነበርና ድንገተኛ የሆነ እንቅጥቃጤ ያጋጠማቸው ጊዜ ትዝ አላቸው። እናም አሁን በአፄው አትኩሪት ላይ የፍርሃት ጥላ ለአመል ያህል ሲያጠላባቸው፣ አባ ዴ ላ ቾይዝ ተመለከቱ

«ንግግርዎ ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥሪት እንዳደርግ ያደርገኛል» አሉ ጀስዊቱ በትህትና

«አያስፈልግም። በርስዎ ላይ ያለኝ እምነት ይቀጥላል። የርስዎን የሃይማኖት ሥርዓት እንደማደንቅና ከመቸውም የበለጠ አምኜ መቀበሌን እንዲያውቁ። ቻይናን በሚመለከት፣ ጌኪንግ የሚገኘው መልዕክተኛችሁ ሙሉ ድጋፍ እንዲያገኝ አዝዣለሁ።»

«የተቀደስ ተግባር ነው»

«አቢሲኒያን ቡተመለከተ፣ ስድስት ሰዎች ግን ወደዚያው ለመላክ ዕርዳታዬን ጠይቀዋል። ልክ ነኝ?»

«አዎን፣ ጃዝሆይ»

«ፈቅጂልዎታለሁ። ነገር ግን ሕዝባዊ ጉዳይ እንዳያደርጉት»

«ዕድሜ ይስጥልኝ ግርማዊ ሆይ»

«ይህን ተጓዥ የተባለ ሰው በተመለከተ ግን» ሲሉ ንጉሡ ቀጠሉ። «አስቀድሞውኑ ሊወሰድ ይገባው የነበረውን እርምጃ አሁን ወስጃለሁ። ሰውዬው፣ በዕውቅ ምሁራን እወያዮች፣ እውነቱን ይናገር እንደሆነና እንዳልሆነ ይፈተሻል። እነዚህ ምሁራን፣ ሰውዬው አታላይና አስመሳይ አለመሆኑን ከተስማሙ በኋላ የሚሰውን እንሰማለን።»

«የአካሄድ ሥነ ስርዓቱ በጣም ተገቢ ነው፣ ጃንሆይ። እኔ ግን፣ ይህ የምሁራን አወያይ የሰውዬውን ጉዞ እውነተኛነት እንደሚመሰክርለት ርግጠኛ ነኝ»

«አስቲ እናያለን» አሉ ንጉሡ

«አንግዲያው፣ አባቶቻችን ሳይዘገዩ ወደ አቢሲኒያ መንገዝ ይችላሉ»

«ደስ ካለዎት ነገ ይችላሉ» አሉ ንጉሡ። ጀስዊቱ፣ ለመውጣት ነፃ መሆናቸውን ለመግለፅ ከጠረጴዛቸው ላይ ምልክት የሚሰጡበትን የቆዳ ማህደር እያነሡ።

አባ ዴ ላ ቾይዝ፣ በረዥሙ የመተላለፊያ ክፍል አድርገው ተመለሱ። አብረቅራቂው የሸማ ማብሪያ የጠርሙስ ድንጋይ፣ ጥቁር ነፀብራቅ ይታይበታል። በውጭ በኩል ቀኑ ቀለል ብሏል። ፀሐይ በሞጥለቅ ላይ ስለሆነች ከሰዓት በኋላ የነበረውን ደመና ነፋሱ ጠራርጐታል።

አጃቢ አድማጮችን እንዲህ ባለ የተቀናበረ ዘዴ፣ የሰውየውን ዕቅድ እንዲቋረጥና ዓላማው እንዳይሳካ ማድረግ ብልህነት ነው ሲል ፖንቻርትሬይን አሰቦ ነበር ሲሉ ጥቁር ቀሚስ የለበሱት ሰው እየተጣደፉ ሲሄዱ አሰቡ። ንጉሡ እኛን እንዲጠነቀቁን እንዳሰባቸው ሁሉ ደካማ የሆነ አጋጣሚ ሲደርስም፣ እንዲሁ ሌሎችን አስጠንቅቂቸው ነበር። በመጨረሻ ግን ተሸናፊ ሆነ። ግርማዊነታቸው ስላላዘኑን ይቅርታ ጠይቀው፣ የጠየቅነውን ሁሉ ፈቅደውልናል።

ወደዘቦቹ ክፍል ቡር ሲደርሱ፣ ይህ ፖንሱ የተባለ ሰው ጥሩ አድርጐ ቢያገለግለንም እንደ ጅል ነበር ሲሠራ የነበረው። ከዚህ በኋላ በርሱ ላይ የምንተማመን ባንሆንም በእርሱ ዝና ላይ የሚፈፀም ማንኛውም ጥፋት በኛ ላይ ሊንፀባረቅ ስለሚችል ልንከላከልለት ይገባናል።

8

የመጨረሻው የአምስት ሰዓት ደወል ከመደወሱ በፊት፣ ሰረገላው በቅዱስ ኢዩስታቼ ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ቆመ። ሌ ቢዩ ኖሬ አጠገብ፣ ባልፀዱ መስኩቶች ዘልቆ ከሚታየው ደብዛዛ የሻማ ብርሃን በስተቀር ጉዳናው ድቅድቅ ባለ ጨለማ ውስጥ ነበር።

ጀን ባፕቲስት ወጥቶ በሩን ዘጋው። በቀጥታ ወደመዝናኛው በማምራት ፈንታ የአማካሪውን በር ለመቆርቆር ቢጋሪው በኩል ዞሮ ሄደ።

«ምን?» ሲሉ፣ አባ ፕላንቴይን የሰረገላውን በር በከፊል እየከፈቱ አንሾካሸኩ። «እዚያ ትንሽ ሆቴል ውስጥ አትኖርም ማለት ነው?»

«እንደሚያዩት» አለ ጀን ባፕቲስት በሩን በመቆርቆሪያው ሁለት ጊዜ እየመታው።

በመጨረሻም በሩ ተከፈተ። አማካሪው ራሣቸው ባትሪ ይዘው መጡ። አባ ፕላንቴይን ደነገጡ። በራሣቸው ጋሪ ዋሳ ውስጥ ራሣቸውን ደበቁና ነጂው ፈረሶቹን እንዲገርፋቸው ምልክት ሰጡት። ከሁለተኛው ጋሪ ውስጥ ሁለት ዘቦች ወረዱ። ከጨርቅ በተሰራ ባርኔጣ ተሸፍነው መስኬቶ ጠመንጃ ይዘዋል።

«ፈጠን ብለሀ ግባ» ሲሉ የተከተሰውን አጃቢ ያላዩት ሣንግራይ አንሾካሸኩለት።

«ብቻዬን አይደለሁም» ሲል ወደተከተሉት ሁለት ወታደሮች እያመለከተ ጀን ባፕቲስት ተናገረ።

«በንጉሡ ትዕዛዝ መሠረት።» አለ አንደኛው ለአማካሪው «ከዚህ ሰው ጉን አንለይም። ለመሆኑ ከርስም ጋር ነው የሚኖረው?»

«እኔ እስከማውቀው ድረስ» አሉ ሳንግራይ

«እንግዲያውማ ለኛም ጭምር አንድ ትንሽ ከፍል ሊያዘጋጁልን ይገባል»

አማካሪው፣ ፖንሴ እንዲያልፍና ዘበኞቹም እንዲከተሉት ካደረጉ በኋላ በራቸውን ቀረቀሩ። የአዳራሹ መተላለፊያ በረዶ ሆኗል። ነገር ግን፣ ሣንግራይ ለወታደራዊ ሰዎች ብዙም ደንታ ሣይኖራቸው የሌሊቱን ማረፊያቸውን በዚያ እንዲያደርጉ ጋበዟቸው። ከዚያም ጀን

ባፕቲስት በእግቱ ዳር ሆኖ ወደሚጠብቃቸው የእንግዳ መቀበያ ክፍል ገቡ። ሁለት ትላልቅ ግንዶች ደስ በሚል ሁኔታ እየተንጣጡ ይንለበለባሉ።

«በአንድ ሰዓት አካባቢ ትመለሣለህ ብዬ ገምቼ ስጠብቅህ ነበር» አሉ አማካሪው ዝቅ ባለ ድምፅ። «ይሁን እንጂ ድጋሜ አላይህም በሚል ተስፋ መቁረጥም ጀምሬ ነበር። ነገ ወደ ፖላስ ሮያሌ ወይም ወደ ቅዱስ ክላውድ ሄጀ ስላንተ ዜና ለማግኘት እሞክራለሁ እያልኩ ነበርኩ»

ጀን ባፕቲስት ባለመደገፊያው ወንበር ውስጥ ዝልፍልፍ ብሎ ወደቀ። እጆቹንና እግሮቹን ወደ እሣቱ ዘረጋቸው። አይኖቹ ባዶ ነበሩ። ሣንግራይ ካዩት ጊዜ ሁሉ አሁን እጅግ በትንሹ ላይ መሆኑ ይታወቃል። ወዳጁ ስላስገደዱት ምንም አንኳ በፊቱ ላይ የሚነበብ ነገር ባይኖርም፣ ወጣቱ ሰው ከንጉሡና ከአጃቢዎቻቸው ጋር የነበረውን ታሪክ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው ተረከላቸው። ከዚያም ወደ እስር ቤት መወሰዱን ገለፀላቸው። በተሰይም ራሱን መድሃኒት ቀማሚ ነኝ ብሎ ስለተናገረ መስኬቶ ጠመንጃ ያነገቱት አስረኛ ነው ብለው አምነዋል። ሙሉ በሙሉ እንዲናዝዝም መደብደብ ጀምረውት ነበር። «ለንጉሡ ያመጣሁላቸውን ገፀበረከት እንዲመረመር አምጡት፣ እናም እናንተ የምትገምቱት ነገር ጨርሶ እንዳልሆነ ታያላችሁ» በማለት ጀን ባፕቲስት ነግሯቸው ነበር።

ይህን ከሰሙ በኋላ፣ የዘቦቹ አለቃ፣ ሣጥኑን እሣቱ ውስጥ በመወርወራቸው የወንጀሉ ማስረጃ መጥፋቱን ተገነዘበ። አንዳች የቀረ ነገር ቢኖር አንድ በአንድ ከእሳቱ ውስጥ ተለቅሞ እንዲወጣ አዘዘ። የሣጥኑ እንጨት ነድዶ አልቋል። ይሁን እንጂ በአመዱ ስር ብዙ ጥበቅብቅ ያሉ የጀሮ ቁርጥራጮችን ለማግኘት ቻሉ። አንድ ለስላሳ ፀጉር ያለው ውሻ ይህንን ቁራጭ እንዲቀምሰውም አመጡ። ውሻው የተጠበሰውን ስጋ ተንገብግቦ ዋጠው። እንዲያውም ድጋሚ የሚፈልግም መሰላቸው። ሙራድ ሁልጊዜም እንደሚያደርገው በማጣፈጫ ቢሠራ ምግቡ ለጤና አዋኪ አይደለም።

በመጨረሻም ጀስዊቶቹ ከአንድ ፀሐፊ ጋር ተመለሱ። ጠመንጃ አንጋቾቹ ተጠርጣሪውን እንዲለቅቁትና በተማሩ ሰዎች እስኪመረመር በአይነቁራኛ እንዲጠብቁት መመሪያ ሰጧቸው። ከዚህ በኋላ የሚታዩ ብዙ ሥርዓቶች አሉ። ዘቦቹ አንድ ጊዜ ከተመረጡ፣እስኪዘጋጁ ድረስ መጠበቅ ነበረባቸው። በመጨረሻም ሁሉቱ ጋሪዎች በዚያ ቀዝቃዛና ጨለማ ሌሊት ከፖሪስ ወደ ቬርሣይለስ ተጓዙ።

«ኧረ! እንግዲያው ከዚህ ያለፈ የለም ማለት አኮ ነው» አሉ ሣንግራይ፣ ታሪኩን ሰምተው ሲያበቁ እየሳቁ።

ጆን ባፕቲስት ትከሻውን ሰበቀ

«ይህ በቂ ይመስለኛል»

«አዎን እንዳልከው በቂ ነው። ያጋጠመውም ጥፋት በጣም መጥፎ አይደለም። ያንን የሻገተ የዘሆን ጀሮ ይዘህ ቆመህ በነበረበት ጊዜ የነበረውን ሁኔታ እንደገና ንገረኝ እስቲ . . . »

መሣቅ ጀመረ። ሲጀምር፣ ወዳጁን ላለማስቆጣት በጥንቃቄ ነበር የጀመረው። በኋላ ግን ያለፉት ሰዓታት በሣንግራይ ላይ ያሣደሩት ስጋትና ሰቅዞ የመያዝ ሃይላቸው እየሰቀቃቸው መጣ። የመመጠን ችሎታው ጠፍቶባቸው ጣሪያ እስኪሰነጠቅ ድረስ ከልባቸው ሣቁ። መላ ሰውነታቸው በውቅያኖስ ማዕበል እየተርገፈገፈ ያለ እስኪመስል ድረስ ሣቁ። ዘቦቹ ጀሮአቸውን በሩ ላይ ሰጥፈው ያዳምጣሉ። ጆን ባፕቲስት ራሱ ተደንቆ በግልፅነታቸው አውካካ። ብዙ ካወሩና ከብዙ ድግግሞሽ በኋላ፣ እንባዎቻቸውን ከአይኖቻቸው ላይ በመጥረግ ተረጋጉ።

«ያው ያው ነው። ሁሉንም ነገር አጥቻለሁ» አለ ጆን ባፕቲስት እንደገና ወደ ቁምነገሩ እየተመለሰ።

«አይመስለኝም።» አሉ ሳንግራይ፣ ተንፈስ ለማለት የሰደሪያቸውን ቁልፍ እየፈቱ። «እንዲያውም እንደ እውነቱ ከሆነ በተቃራኒው ነው። የዚያ ዝሆን ጀሮ ሕይወትህን አድኗታል። ለአጭር ጊዜም ቢሆን ወህኒ እንድትወርድ ወይም በነዚያ ረጋሾም ጀልባዎች ላይ ቀዛፊ እንድትሆን በባርነት ስትገላ ይታየኝ ነበር»

አማካሪው በድጋሜ ሣዘንና ትካዜ ውስጥ የገባውን ጆን ባፕቲስትን ሲያስተውሉት «ሆኖም ግን» ቀጠሉ። «ሳስናውነው አስቤ የተንተማቀስኩበትን ነገር ሁሉ አጣሁት»

«ኦ! ውድ ወዳጄ፣ ነገም ሌላ ቀን ነው። እንዲህ ያለውን ማላዘንህን ሰመስማት ስሜቱ ዝግጁ አይደለም። ምክንያቱም ሲበዛ ታጋንነዋለህ። የምመክርህ፣ከዚህ ስሜታዊ የመከራ ዕለት ጉዳይ በኋላ፣ ዛሬ ማታ ለሁሰታችንም እጅግ አስደሣች ስሜትን ከፈጠረልን ከዚህ ሣቅ ያለ ሣቅ አለመሸሽ ብቻ ነው። ወደ መኝታህ ሄደህ በሕይወት መኖርህን ብቻ አስበው። ይህ እውነታ ደግሞ በተሰይም የሚፈትን ጉዳይ በገበመን ዕለት፣ መጨረሻ ላይ ሲሆን የመደነቅና የአርካታ ምንጭ ሊሆንን ይገባል»

ይህን ካሉ በኋላ ጆን ባፕቲስትን እንደ አባት አቀፉት። ሣፉን ይዘው ወደ መኝታ ቤቱ በመምራት መልካም ለሊት ለእንግዳቸው ተመኙለት።

የሚቀጥሉት ቀናት የባሱና የሚያስፈሩ ተከታታይ መጥፎ ወሬዎች የሚመጡባቸው ሆኑ። በመጀመሪያ የቤተመንግስቱ ሹማምንት በዚያው በቤተመንግስቱ ውስጥ እናፈሱት። ከዚያም ጋዜጦቹ በከተማው ውስጥ ዝቱት። የዚያን ደስ የማይል ሽታ የነበረውን ነገር ትክክለኛ ምንነት የሚያውቅ ማንም ስላልነበረ፣ ሪንሴ፣ ንጉሡ ፊት ቀርቦ ለመታየት ድፍረቱ ነበረው። ወሬው እንደ አስቂኝ ጉዳይ ሣይሆን፣ አንድ ተንኮለኛ እንዳከናወነውና በንጉሡ ሕይወት ላይ አውነተኛ ሙከራም ሊፈፀም ይችል እንደነበረ ተደርጐ ተነዛ። እጅግ መጥፎው አሉባልታም፣ በጆን ባፕቲስት ላይ ተሠራጨ። በግልፅ አስመሣይ፣ አታላይ፣ ተብሉም ተወነጀለ። ሴራውም፣ በጀስዊቶች ጠላቶች በምስጢር ተራገበ። የነዚህ ሴረኞች ዓላማ ወጣቱን ተንኙ በትንሹ ለመከነንና የተባባሪዎችን ዝናና ክብር ግን ለመንዳት የታሰበ ነበር። ነገር ግን፣ የጀስዊቶቹ ደረጃ ከፍ ያለና የማይደረስበት ስለሆነ በጭቃው ውስጥ እንዲጐተት የተፈረደበት እርሱ ሆነ።

ጆን ባፕቲስት በፍጥነት ይጀመራል ብሎ ተስፋ ያደረገበት የፍርድ ሂደት፣ከብዙ ሣምንታት በኋላ እንደሚሆን ፕሮግራም ወጣለት። ጉዳዩን ለመስማት ብቃት ያላቸው ከሕዝብ የተመረጡ ምሁራን መሰብሰባና፣ ሥረ-ነገሩንም ለማጥናት ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። አዝማሚያዎች ሁሉ የሚያመላክቱት፣ምርመራው ሊጀምር የሚችለው ከጥምቀት ዓመት በዓል በኋላ ነው።

በመጨረሻም፣ ንጉሡ ጥያቄአቸውን ተቀብለው እንደፈቀዱላቸው፣ ጀስዊቶቹ፣ ለጆን ባፕቲስት ነገሩት። ይህ እውነታ፣ እርሱ በዋና ከተማው ውስጥ ከታሰረበት ጉዳይ የተለየ መልክ ተሰጥቶት ነበር። ስድስት ጀስዊት ካህናትን የያዘ አንድ የመልዕክተኛ ቡድን በሚቀጥለው ሣምንት መጀመሪያ ላይ ጉዞውን ይጀምራል። በዚህ ቡድን ውስጥ አንድ ሐኪም፣ አንድ የአፅዋት ሊቅ፣አንድ ፕላን ነዳፊና አንድ የሥነ ከዋክብት ተመራማሪ አሰብት። ከነዚህ መካከል ሦስቱ መልዕክተኞች የመጡት በክፍላተ ሃገራት ከሚገኙ ገዳማት ሲሆን፣ ሁሰቱ ከፍልስጤም እና የቀረው አንዱ ከአስቱሪየስ ናቸው። የአየሱስ ማህበረሰብ እነዚህን ሚሲዮናውያን ሁሉ ከያሉበት ቦታ በቀጥታ በማጓጓዝ አስክንድሪያ ውስጥ እንዲገናኙ

ያደርጋቸዋል። ይህ ማለት እነዚህ ሚሲዮናውያን፣ ፈረንሣይ ውስጥ አይሰባሰቡም ማለት ነው። ይህ መጥፎ እድል እንደሆነ ካህናት አባቶች ይገምታሉ። ምክንያቱም፣ አስቀድመው ከፖንሴ ሊያገኙት የሚችሉትን ጠቃሚ ምክር አያገኙም ማለት ነው። ይሁንና ካይሮ ከደረሱ በኋላ ግን፣ ፖንሴን ባለማግኘታቸው ያጡትን ሁሉ በንዛው ላይ አብሯቸው እንዲመለስ ከሚያደርጉት ከሙራድ ያገኙታል።

ያስርሱ ፈቃድ አርመናዊውን ሊገለገሉበት እንደማይችሉ፣ ጆን ባፕቲስት ሊቃወም ፈልጐ ነበር። ይሁንና እነዚህን ሰዎች ከዚህ እንቅስቃሴአቸው የሚገታበት ምንም መንገድ እንደሌለው ወዲያውኑ ተገነዘበ።

የታህሳስ ወር እየተጋመስ ነው። የክረምቱ የቀን ርዝመት አጭርና ጨለማ ሆኖ፣ ክለሊቱ የማይለይበት ወቅት ደረሰ። ሽማዎችና ጣፎች ባለማቋረጥ ይበራሉ። የፖሪስ ከተማ ነዋሪዎች ከምድጃቸው አጠገብ በስንለስት የታሰሩ ይመስል እዚያው ይውላሉ። የርሱ ጉዳይ በተጀመረበት አዲስ አቅጣጫ ላቢያ፣ ጆን ባፕቲስት ስሜቱ በጣም ስለተጐዳ ያለበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ጭራሽ አጨልሞ ተመለከተው። ለንጉሡ የገባላቸውን ቃል ኪዳን ለማክበር እየፈለገ ሣለ፣ ይኸው በግማሽ ምዕተ ዓመት ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የጀስዊቶች ወረራ ወደ አቢሲኒያ ሊንቀሣቀስ፣ ለዚህም ሣላፊነት ተሰማው። በአሊስ ልብ ውስጥ ፍቅርና ተስፋ እንዲያብበም ተደፋፍሮ ነበር። ይሁን እንጂ አሁን ካለበት ሁኔታ የሚወጣበት ምንም ተስፋ ስለሌለው በርዕ. ውስጥ ለማይፋቅ ስቃይና ቅሬታ መነሻ ይሆናል። እንዲያውም ስሙን አጭበርባሪና ሰዎችን የሚያሳዝን ምትሃተኛ አድርገው ስለበከሉበት ከበፊቱም የባሰ መከራ ውስጥ የወደቀ መሰለው።

ሣንግራይ በበኩላቸው፣ የቻርትሬሱን መስፍን፣ በፖላስ ሮያሌ ውስጥ እንዳገኟቸውና ስለጆን ባፕቲስት ሽንጣቸውን ገትረው ሊሟገቱ እንደሰሟቸው በመንገር ሊያስደስቱት ሞከሩ። ሞውውታቸው፣ ጆን ባፕቲስት፣ በንጉሡ ህይወት ላይ ስለቃጣው ሙከራ፣ ንጉሡ ባሉበት ቦታ ያልታወቀ ስይጣናዊ ነገር እያወዛወዘ ከውስጡ መርዛም ትናጓ እንዲወጣ ስለማድረጉ ወደሚሰው ርዕስ ዞረ። «እንደተሰመደው አሞቱ በማያስፈራ ነገር ሁሉ ይፈራል» አሉ መስፍኑ እየሳቁ። «ከአቢሲኒያ ምን ሊቀበል ነበር የጠበቀው? የስፔስ የጊዜ መለኪያ ሰዓት እንደሆነ አይጠረጠርም» ይህን ድንገተኛ መልካም አስተያየት ከሰሙ በኋላ አማካሪው፣ መስፍኑን ወደ አንድ ጥግ በመውሰድ፣ ፖንሴ የርማቸው እንግዳቸው መሆኑን ነገሯቸው። መስፍኑም፣ ጆን

ባፕቲስትን ለማግኘት የንጉሡ መሰሉ። ይህን አይነቱን ቅርርብ ምን መልካም ነገር ሊያስገኝ እንደሚችል አሁን ፈጥኖ ለመናገር ቢያስቸግርም ቅሉ፣ ቢያንስ የተስፋ ጨረር ፈንጥቆላቸዋል።

ከዚህ ታሪክ ጆን ባፕቲስት ምንም አይነት ማፅናኛ ያገኘ አልመስለ አለው። ባለማቋረጥ በአፖርታማው ውስጥ ባለው የእግት ማንደጃ አጠገብ ቅር እንደተሰኘ ይቆያል።

«እንግዲያው ለምን አትፅፍም» አሉት ሣንግራይ በመጨረሻ ላይ ትዕግስታቸው እያለቀ። «አዎን፣ ፃፍ፣ አንድ ሰው የትም ለመሄድ ሳይሆን፣ ብቻ እንዲሁ ወደፊትና ወደኋላ በመራመድ እየተንቀሣቀሰ ብርድ እንዳይገድለው ሊያደርግ ይችላል። አንድ ጊዜ ትውስታዎችህን ሁሉ ሰብስብ አድርገህ፣ ያየኸውንና ያከናወንከውን ሁሉ ታሪክ ብትናገር ለዳኞችህ የምትመልስላቸውን ሁሉ በእርግጠኝነት ልትነግራቸው ትችላለህ።»

ጆን ባፕቲስት ይህን ምክር ተቀበለ። ሲጀምር ትጋቱ እምብዛም ነበር። እያደር ግን የራሱን ትውስታዎች በመፃፍ ውጥኑ ውስጥ ይበልጥ እየተማረከ መጣ። በክረምቱ፣ በከተማዋ የመከራ ሣጥኖች ውስጥ ከመዋኘት ይልቅ፣በአቢሲኒያውያን አምባ ምድር ላይ የቆየባቸውን ብሩህ ቀናት፣ በፈረስ ላይ ሆኖ ድኩላን መከተል፣ የንጉሡ ጠባቂዎች የወርቅ ጋሻቸውን አንግተውና የነብር ቆዳቸውን በትከሻቸው ላይ ለብሰው ማየት ጭንቀቱን አቀለለለት። ጉንደር በቅመማት ገበያ ውስጥ መዘዋወር ጀመረ። ቀረፋውንና ቀዩን በርበሬ ማሽተት ቀጠለ። ምሽቱ ገና ስዓይን ያዝ በሚያደርግበት ድንግዝግዝ ሰዓት፣ ጀቦች ሲጮሁ መስማት ቻለ። ሴቶች በጉጉ ሲያልፉ ረዘም ላለ ጊዜ ኦስተር ያለ አይታ ሲወረውሩበት፣ ዐይኖቻቸውም በቅፅበት ነጭና ጥቁር እየሆኑ ሲያንፀባርቁበት ታየው።

በአፖርታማው ቤቱ ውስጥ ባለው በእግቱ ጫር ተቀምጦ ከንጋት እስከ ምሽት ይፅፋል። ዘቦቹ በመኖሪያ ቤቱ በር ላይ ያለባቸውን ጥበቃ ተራ በተራ በመግባት ሥራቸውን አቀለሉት። አንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ቀኑን ሙሉ ሳያዩት ይውላሉ። ከዚያች ከተጐግቆለች ሻንጣው ውስጥ አቢሲኒያውያን የሚለብሱትን ከጥጥ የተሠራ ልብስ ከነጠባብ ሱሪውና ቦጥንት ዘመን ሮማውያን በትከሻቸው ላይ ጣል የሚያደርጉት የነብረውን አይነት በቀጭኑ በባለቀለማት ክሮች የተጠለፈ የአንገት ልብሱን አወጣ። እነዚህን ልብሶች ከኢትዮጵያ በርግጠኝነት ለምን እንዳመጣቸው ባያውቅም ሰሆነ ሰው በስጦታ ለማቅረብ አስቦ ነበር። አሁን ግን እርሱ ራሱ በክፍሉ ውስጥ ስለለበሳቸው ተደሰተባቸው። በወገቡ ላይ ለፈረንሳዩ ንጉሥ እንዲሰጥ ታስቦ

የነበረውንና፣ ጀሰዊቶች እንዳይሰዋ የከለከሉትን ቀበቶ ታጠቀ። እንደ አቢሲኒያውያን ከለበሰ በኋላ ጀን ባፕቲስት ለጉዳዩ ይበልጥ መቅረቡ ተሰማው። አሰባበሱን፣ ንጉስ እያሱ ሲለያቸው የሰጡትን የወርቅ ሰንሰለትና በእንገቱ ላይ የሚያንጠለጥለውን አልማዝ በማጥለቅ የተሟላ አደረገው። እኒያ ፀርቀት ቦታና በአጠራጣሪ ሁኔታ ላይ የሚገኙት ንጉስ፣ የወዳጅነታቸውን ማረጋገጫ እንዲሆኑ የሰጡትን እነዚህን ዕቃዎች ያዘና ሁሉም ነገር በሕይወቱ ላይ ጥርጣሬን ለማጫር ቡተነባበት ጊዜ፣ ጀን ባፕቲስት በትጋት የመንቀሳቀስ ነገር ተሰማው። የቀን ህልሙንም ቡተማ የትረካ ዘዴ ስላስፈረው፣ ከስበሰው ነጭ ልብስ ጋር የተጣጣመ ነበር። ለንግሪይም፣ ከእንግዳቸው ጋር ምግባቸውን አብረው ሲበሉ በዚህ ዓይነት የተሟላ ትጥቅ ሆኖ ማየትን እየለመዱት መጡ።

ከዕለታት አንድ ቀን፣ ሙሴ ራኦል፣ አንድ በድንገተኛ የሚጥል ሕመም የተያዘን እንግዳ፣ በአስቸኳይ አይቶ እንዲመረምር ጀን ባፕቲስትን ጠራው። የጠቅላይ ሚኒስትሩ ትዕዛዝ፣ ጀን ባፕቲስት ከንጉሣውያን ቤተሰብ አስከራቀ ድረስ በጠባቂዎች እየታጀበ እንዳይወጣ የሚከለክል አልነበረም። በመጠየ ቤቱ ውስጥ የነበሩት ሁሉ ይህን ነጭ ሰብሶ የወርቅ ቀበቶ ታጥቆ፣ በሁለት ጠመንጃ አንጋቾች ታጅቦ የመጣውን ወጣት ሰው እንደተመለከቱ፣ ሁሉም እንደ አንድ ሰው ከመቀመጫቸው ላይ ብድግ አሉ። ግራ የተጋቡት ጠፈኞች፣ ላይታሰብ አንድ ልዑል ከምሥራቅ በበራሪ ምንጣፍ ላይ ሆኖ የመጣና ንጉሡም ለክብሩ ሲሉ በንቁ ወታደሮች እንዲታጀብ ያደረጉት ማይሆን አይቀርም ሲሉ አሰቡ። በሆቴሉ ውስጥ እራታቸውን በመብላት ላይ የነበሩ ነጋዴዎች ይህን የመሰለ ድንቅ ሰልፍ፣ ባረጀው የደረጃ መውጫ ላይ ደርሶ ከነርሱ አንዱን ለመገብኘት መምጣቱን ሲመለከቱ ይበልጥ ተገርመዋል። በኋላ እንደታየው፣ ጀን ባፕቲስት ለሰውዬው የሚያደርግለት ምንም ነገር የለም። ነጋዴዎች ወደነበሩበት ክፍል ሲገባ፣ ሕመምተኛው በጣዕረ ሞት ሲንፈራገጥ አገኘው። ሐኪሙ ሰቅቆ ሲወጣ፣ አስከሬኑ ከዮቂት ጊዜ በኋላ ወደታችኛው ፎቅ ተወሰደ። ተመልካቾች ሊሆን የሚችለውን ሁሉ ገቅ ባለ ድምፅ ይወያያሉ። ብዙዎች የታበሰሱን የወይን ገበሬ በመደገፍ ቆሙ። ይህ የወይን ገበሬ፣የነጋዴዎቹ ጓደኛ በጉዞው ዘመን በአንድ ራቅ ባለ ፀታ ሃይማኖቱን እንደለወጠ ስለሚታመን፣ ለሚቹ የመጨረሻውን ፀሎተ ፍትሃት ለማድረግ ሙሉ በሙሉ ነጭ የለበሰ አንድ አንግዳ ቄስ ተገኝቷል ሲሉ አወሩ።

የለበሰውን ለብሶ አንድ ጊዜ ከቤት ወጣ ስላለ ይሆንን አለባበስ ዳግመኛ የማያደርግበት ምክንያት እንደሌለው ጀን ባፕቲስት አሰበ። መሴ ራኦል፣ ውይይት ለማድረግ የሚቀርብለት

ጥያቄ በረከተ። እርሱም ጥያቄዎችን ለማርካታ በመቻሉ ደስተኛ ሆነ። ጀን ባፕቲስትም ድሆችን ብቻ ለማየትና ምንም ክፍያ ሳለመቀበል ተስማማ። ስለርሱ ያለውን እውነታ በዚያ አካባቢ ቀስ በቀስ እየታወቀ መጣ። ሕዝቡም፣ እርሱ በአጠገባቸው ሲያልፍ፣ ሁልጊዜም ከሰዓት በኋላ ቀደም ይልና ከፅሁፉ ላይ አረፍ ለማለት ፣ ረዥም ቁመናው በነጭ የአንገት ልብስ ተሸልሞና በሁለት የንጉሡ ወታደሮች ታጅቦ በየሰርጡ መንገድ ባሉ ደሣሣና ጉስቁላ ቤቶች ውስጥ በሕመም የሚያለቃይ ልጅ ለማየት ሲወጣ ሲያዩት መደነቃቸውን ተው።

የርሱ ጉብኝት በሚወስደው በማንኛውም የፖሪስ ክፍል ውስጥ፣ ነዋሪዎች በቀላሉ «አቢሲኒያዊ» እያሉ በመጥራት በመንገድ ላይ ባገኙት ቁጥር በወዳጃዊ መንፈስ ሰላምታ ይሰጡታል።

9

"ባንተ አስተማሰብ ቅብዐ ቅዱስ ምን ይመስላል?" በማለት በአንድ ትልቅ ባለመደገፊያ ወንበር ላይ እግሮቹን በአንዳሩ ከተቀመጠው ከሙሴ ማቼ እግሮች ላይ አመሳቅሎ የተቀመጠው ሙሴ ዴ ማይሌ አስቸጋሪውን ጥያቄ ያቀረበው ዝቅ ባለ ድምፅ ነበር።

"ክቡር ሆይ፣ ማለት የምችለው ... እርግጠኛ ሆኜ ባላውቀውም ... ሳስበው ያው ዘይት ይመስላል" .

"ደህና" አለ ቆንስሉ ትንሽ እንደመቆጣት ብሎ "ግን ምን አይነት ነው ፣ መጠኑስ ፣ በምን አይነት ጠርሙስ ውስጥ ነው የሚቀመጠው"

"እ፣ ጥቂት ብቻ ነው የሚወሰደው፣ ግንባር ላይ መቀባት ... ጥቂት ደግሞ እጆችን መቀባት"

"በእግሩ፣ አንተም እንደኔው በአንድ ጀልባ ውስጥ ነን ማቼ" አለ ሙሴ ዴ ማይሌ ከተቀመጠበት ተሰይቶት እየተነሣ "ምንም የምታውቀው የለህም"

"ምንነቱን ለማወቅ አጠያይቃለሁ" አለ ፀሐፊው በሚያስቆጣ ሁኔታ

"ምንም አልክ፣ ምንም ለውጥ አያመጣም፣ ካፑቺኖች ያውቁታል። አስቲ ለመሆኑ ሌላ ልጠይቅህ። ለመሆኑ ለነርሱ ይህን ነገር ማነው የሚያቀርብላቸው?"

"ወንድም ኢብራሂም የሚባሉ ሶሪያዊ መነኩሴ ናቸው። ሰውዬው፣ የኮንቲኩ ፖትሪያሪክ ስለሚያውቋቸው ይህን ቅብዓ ሜሮን ከርሣቸው እንደሚያገኙት ይናገራሉ"

"መቼ"

"ካፑቺኖች ተዘጋጅተው ሲያበቁ"

ሙሴ ዴ ማይሌ ብድግ ብሎ ቆመና ከባድ ባርኔጣ አጠለቀ። የታህሳስ ወር፣ ካይሮ ውስጥ ቀዝቃዛ ሊሆን ይችላል። ምድረበዳው ርቀት ባይኖረውም፣ ደሣቃዎቹ ቤቶች የተሠሩት የበጋውን ተናካሽ የአየር ጠባይ እንዲቋቋሙ ብቻ ተደርገው ነው። ቆንሲሉ፣ አሁን አሁን ሰው ሰራሽ ወኑሩን አውልቆ እያውቅም። እንዲያውም ቁልቁል የወረደውን ረዥም ጫፉን በደረቱ ላይ በማሳለፍ ቅዝቃዜውን ይከላከልበታል።

"እንዲህ ከሆነ፣ እኔ እንደሚገባኝ ካፑቺኖች፣ ለአቢሲኒያው ንጉሠ ነገስት፣ ለንግስና በዓሉ ቅብዓ ሜሮን ሊያቀርቡለት ነው። የዚህን ዓይነት ሁኔታ የተከናወነው ደግሞ ከአስራ አምስት ዓመታት በፊት ነበር።። ልክ ነው?»

«አባ ፖሰኪል፣ ምንም ልዩነት አያመጣም ይላሉ። አቢሲኒያውያን ከቀረው አለም ራሣቸውን አግልለው ስለሚኖሩ፣ ግልፅ የሆነ ዕቅድና ዘዴ ወይም ተስማሚ መሣሪያ የላቸውምና የራሣቸውን ይጠቀማሉ። ይሁን እንጂ፣ ቅብዓ ሜሮን ስለሌላቸው ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ቅር እንደተሰኙ ናቸው። የሆነ ሰው ይህን የንግስና ሥርዓት ማስፈፀሚያ ዘይት ቢያቀርብላቸው ባለታላቅ ውለተኞች ይሆናሉ። ከአስራ አምስት አመት በኋላም እንኳ ቢሆን ለላ የሥርዓተ ንግስ በዓል በጋለ ስሜት ያደርጋሉ»

ይህችን አነስተኛ ንግግር ካደረገ በኋላ፣ ሙሴ ማቼ ከፍ ባለ ድምፅ አሣለ።

«ጭቅጭቃችንን ለመቋጨት ስንል እንለፈው፣ ለመሆኑ አባ ፖሰኪልን ላያቸው አለመቻሌን ምን ብለህ ነበር ያስረዳሃቸው?» አለው ቆንሲሉ።

«ክቡር ሆይ፣ እርስዎ ይሻላል ብለው እንደነገሩኝ ጤና እንዳልሆኑ ነው የነገርኳቸው»

«አመኑህ ታዲያ?»

«እጠራጠራለሁ። ሆኖም ግን ነገ ተመልሰው ይመጣሉ። ክቡርነትዎ እንድነግርዎ ከፈቀደልኝ ሰውዬው የሚተው አይመስለኝም። እንዲያውም እርስዎ በገንዘብ ሊረዷቸው ቃል እንደገቡላቸው ይናገራሉ»

«ይህ የሚያበሳጭ ነገር ነው። ካፑቺኖች ቅብዓ ሜሮን እንዲያደርሱ በማለት ሰንዷቸው የምሰጣቸው የገንዘብ ድጉማ ለበቂ የለኝም። ይህንኑ ገልጬ ወደ ቬርሣይለስ መፃፍ አለብኝ» አለ ቆንሲሉ በንዴት

ትክሻውን ነቀነቀ

«እውነቴን ነው። ሁሉም ነገር ባልተለመደ መልኩ አሣሣቢ እየሆነ ነው። እነዚህ ቀሣውስት ሰላማቸውን ይዘው ቢቀመጡ ይሻላቸው ነበር። በሌ ኖይር ዱ ሮኡሌ የሚመራውና እኔ እስከማምነው ድረስ ትንሽም እንኳ ቢሆን ጥቅም ያለውን የራሣችንን ኤምባሲ ስኬት ስጋት ላይ እየጣሉት ነው»

«ምናልባት ከነርሱ ዘመቻ ጋር የኛንም ቀላቅለን አንድ ኤምባሲ ማድረግ ከቻልን?»

«ምነው! ጨርሶ የማስቢያህን ነገር ጥለኸዋል?» አለው ቆንሲሉ።

የተቆጣበትን ምክንያት ሊያብራራ ሲል በጽህፈት ቤቱ በር ላይ በሚገባ የማይሰማ እኩለ-ኛ ማንኳኳት ተደረገ። ፀሐፊው በሩን ለመክፈት ፈጥኖ ሄደና አንድ ትንሽ ጥቅል ይዞ ተመለሰ።

«ከእስክንድሪያ የመጣ ፖስታ ነው፣ ክቡር ሆይ»

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ደብዳቤውን ከሙሴ ማቹ እጅ በጉጉት ወሰደበት። ፖስታው የታሸገበትን ሲያገ በሚንቀጠቀጠው ጣቶች በጠለውና ይዘቱን ማንበብ ጀመረ። ከፖንቻርትሬይን የተሳፈ ምንም ነገር የለበትም። ይልቁንም ከፍሌሄውት አጭር ደብዳቤ አለ። ቆንስሉ፣ ፖስታውን ከፍቶ በመጣደፍ ሊያነብበው አሁንም አሁንም፣ ድምፅ ያስማል። ፖንሌ፣ ከንጉሡና ከአጃቢዎቻቸው ጋር የመገናኘቱን፣ ውጤቱንና የሚጠብቀውን ፍርድ ፍሌሀውት ተርኮለታል። ከዚህም በተጨማሪ በሚስጢር መጠበቅ ያለበት መሆኑን ጠቅም በማድረግ፣ የስድስቱን ጀስዊቶች መምጣትም ገልያለታል።

«ርገ-ም!» አለ ቆንሲሉ «ሊሆንስ ይችላል? የመጨረሻዎቹን ነበር አይተናል ብለን ስናስብ የነበረው። ግን አሁንም ገና ሌሎች ስድስቶች ሊመጡ ነው»

የደብዳቤው ቀሪው ክፍል እጅግ ታላቅ ደስታ ስለ ሰጠው፣ ለሙሴ ማቹ ከፍ ባለ ድምፅ ማንበቡን ሊገታው አልቻለም።

«ይልቅስ ይህንን አዳምጥ... የጀስዊቶች ተልዕኮ ከቆንስላው ሙሉ በሙሉ ነፃ እንዲሆን ሚኒስትሩ አዝዘዋል። በተጨማሪም ለክብርነትም ያላቸውን አድናቆት የሚገልፁበት በቂ ቃል ማግኘት ያልቻሉት ሙሴ ዴ ፖንቻርትሬይን ለአገሪቱ የፖለቲካና የንግድ ግብ ሲባል የራሳችንን ኤምባሲ መላክ ብንችል ስላለው ጠቀሜታ ንጉሡን አሳምነዋል... እንዲህ ነው ትልቅ ሰው! እንዲህ ነው የወንድ ልጅ! ... ለዚህ ተልዕኮም፣ ሙሴ ሌ ኖይር ሮውሌ ተስማሚ መሆኑን ሚኒስትሩ ያረጋገጡ ይመስላል። ስለዚህም ሳይውል ሣያድር መሄድ ይችላል። የተጣዩ ቆንሲል ሻንጣ፣ ይህን ጉዞ ለማሣካት የሚያስፈልገ መሳሪያዎችን ለማሟላት አስፈላጊውን ገንዘብ ይይዛል። ፈርማ ፍሌሀውት»

ባርኔጣውን አራግፎ፣ ሰው ሰራሽ ፀጉሩን አንጋድዶ ቆንሲሉ ወንበሩ ላይ ዘጭ አለ።

«አየህ ማቹ ... ውሉ አድሮ ነገር ሁሉ ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ ተመለሰ። ኤምባሲ ... ተነስ ሂድና ሌ ኖይር ዱ ሮውሌን ፈልግልኝ»

«አሁን ቤት ውስጥ ያሉ አይመስለኝም» አለ ሙሴ ማቹ

« ፈልገው»

መፈለጉ አስቸጋሪ ነገር አይደለም። ወጣቱ ዲኘሎማት ቁማር ወዳድ ስለሆነ ሁል ቀን ከሰዓት በኋላ ነጋዴ ባሳ የሞተባት ሴት ቤት በመሄድ ካርታ ይጫወታል። ዱ ሮውሌን ከማግኘቱ በፊት፣ ሰውዬው አንድ ዘመን ላይ ሀብታም ነበር። ሙሴ ማቹ ወጣቱን ዲኘሎማት ክቱማር ጨዋታው ላይ በመከራ አስነስቶ ቆንሲሉ ዘንድ አመጣው።

«መጀጀ የምነግርህ መልካም ዜና አለኝ» አለ ቆንሲሉ ፍልቅልቅ እያለ

እውነት፣ እንኳንም ጥሩ ሆነ፣ ከምጫወትበትና አንድ ሺ ሊቭሬ በቀላሉ ላሸንፍ ከምችልበት ቦታ ነው ያስጠራኝ ሲል ዱ ሮውሌ አሰበና በትህትና ጮንዘስ አለ።

«እባክህ ተቀመጥ። ዜናው እንኳ ግራ የሚያጋባ ነው። ሚኒስትሩ አንተን በአቢሲኒያ አምባሳደራቸን እንድትሆን ሾመውሃል»

በወጣቱ ዲኘሎማት ፊት ላይ አራት ወይም አምስት አይነት ስሜቶች ሲለዋወጡበት ውስጡ ግን ይጨፍር ነበር። እንደተሰመደው ምን እያሰበ እንደሆነ መናገር አስቸጋሪ ነው።

«እንደ እውነቱ ከሆነ ሲበዛ የሚያስደነግጥ ነው» አለ በፈገግታ።

ይህ ለአለባበሱና ለቁንጮ የሚጨነቅ ሽሙንሙን፣ ስሜቱ በጣም የተነካ ከመምሰሉ በስተቀር ሌላ የለም። በርግጥ ወደቆንስላው ሰመድረስ ሊጣደፍ ያቋረጠው ጭቃማ ጮዳና በስተቀር በካልሲው ላይ እንኳ የሚታይ ነገር የለበትም።

«መቹ ነው ከዚህ የምነሣው?» ሲል ጠየቀ

«አ! እንዲህ ያለ ትጋት፣ እንዲህ ያለ ጥድፊያ ! ከፈለገህ ደስ ብሎህ ጥቂት ጊዜ ሰንበት። ገንዘብ የሚደርሰው በሚቀጥለው የገንዘብ መላኪያ ጊዜ ነው። ሁሉም ነገር በጥንቃቄ መዘጋጀት ይኖርበታል» አለው ቆንሲሉ በደስታ፣ አንዳችም እንከን የሌለበት መሆኑን በማሰብ፣

«ጥቂት ቀናት?»

«ከዚያም በላይ፣ ጥቂት ሣምንታት። ሁሉም ነገር በሰላም ከተከናወነ፣ ምናልባት እንበልና ስድስት ሣምንት ወይም ስምንት ሣምንት»

«ድንቅ ነው! አለ ዱ ሮውሌ፣

«ዝም ብለን በጭፍን እንድትሄድ አንፈልግም ። ስላንተ ብዙ እናስባለን ውድ ወዳጄ። መንገዱን ለሚያደምቁ ደብደኞች ትንሽ ልምምድ ማድረጉ ጥሩ ነው። ከዚህም በላይ እውነተኛው ኤምባሲ ሌሎች እጅግ አስፈላጊ ነገሮች ያስፈልጉታል። ለምሣሌ የክበሩ ገፀበረክቶች ፣ ጠባቂዎች ... »

በንዘው ጉዳይ ላይ ጥቂት ዝርዝር ነገሮችን ተነጋገሩ። ሰዓቱም በቆንስላው ውስጥ ቀደም ብሎ የሚቀርበው የእራት ጊዜ ነበር። ሙሴ ዱ ማይሌ፣ ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ሁለቱ ብቻቸውን እንዲሆኑ በማለት ፀሐፈውን እንዲወጣ ጠየቀው።

«ከዚህ ከመነሣትህ በፊት ልታከናውናቸው ወይም ልታዘጋጃቸው የምትፈልጋቸውን ግላዊ ጉዳዮች የለህም?» በማለት ከዱ ሮውሌ ጋር ብቻቸውን መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ቆንሲሉ ጠየቀ።

ይህ ወጣት ዲኘሎማት ይህን ወቅታዊ ሁኔታ በመጠቀም ለሴት ልጁ ያለውን ፍላጐት ይገልፅ ይሆናል ሲል ቆንሲሉ አሰቦ ነበር። በሞውውታቸው ወቅት በእያንዳንዱ ዕድል ላይ ቆንሲሉ ሳይሣሣት በተዘዋዋሪ መንገድ ጉዳዩን ደጋግሞ ይጠቅስለት ነበር። ይሁን እንጂ፣ አንድም የዱ ሮውሌ አስተዳድግ ባልተለመደ አኳኋን ቁጥብ ስላደረገው (ቆንሲሉ እንደፈራው) ይሁን፣ ወይም ወጣቷ ሴት ልታስደስተው ባለመቻሏና ራሷን ማራኪ አድርጋ ባለማቅረቧ፣ አንዳችም ውጤት ሳያገኝበት ቀረ።

«የለም፣ ክቡር ሆይ፣ አሳሰብኩበትም» አለ ዱ ሮውሌ በፊቱ ላይ የመገረም ሁኔታ እየታየበት በእርጋታ።

ፈረሰኛው ሄክቶር ሌ ኖይሬ ዱ ሮውሌ፣ በወራሾች መካከል ሊከፋፈሉት የሚችሉት አንዳችም ነገር ላይኖር፣ ለረዥም ዘመናትም ምንም ማይኖራቸው፣ ነገር ግን የብዙርና ወራሽ ነው ተብሎ፣ ሥርዓተ ሕጉን በጥብቅ ሥራ ላይ ያዋለ የቤተሰቡ ሶስተኛ ልጅ ነበረ። ያደገውም፣ ሴንሊስ አጠገብ በሚገኘው በቤተሰቡ መኖሪያ ግንብ ውስጥ ቸል ተብሎ ነበር። በቤቱ ውስጥ ከግርግዳ ጫፍ እስከ ጥግ አስጨሊታና አስቀያሚ ሆኖ ያለው ሁሉ፣ ከቅድመ አያቶቹ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው። በዚያ ሕንፃ ግንብ ውስጥ ሊዘነጉ ከቶም የማይችሉት

የባህል መገለጫ መሣሪያዎች፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የነበሩት የከፍተኛ መደቦች ማዕረጐችና ስነ-ጥበቦች በሕፃኑ አዕምሮ ውስጥ ጥንድ መልክ ይዘው እንዲከዳችው አድርገውታል። ምንም እንኳ ለረዥም ጊዜ በፍቅር ያደገበት ቦታ ቢሆንም፣ እነዚህ ነገሮች ቤተሰቡን ጉዳት ላይ የጣሉ ናቸው። ወጣቱ ዱ ሮውሌ፣ እያንዳንዱን ጌጥና እያንዳንዱን የውበት መግለጫ ቁሣቁስ የማየት ልምድ አዳብር ነበር። በታሳቅ ማስተር የተሠራን የሸራ ስዕል፣ በግድግዳ ላይ ለሻማ ወይም መብራት ማስቀመጫ ተብለው የሚሰሩ የነሐስ ጌጦች፣ ሥጋጃዎችን ፣ የፈረሰኛ ጉራዴዎችን ሁሉ እንደሸቀጥ በግድግዳ ወይም በሆነ ቁሣቁስ ላይ ሲቀመጡ፣ የግድግዳውን ወይም የእቃውን ስንጣቂ ለመደበቅ፣ የእይጥ ጉድጓዶችን ወይም የሻገቱ ቦታዎችን ከአይታ ለመሰወር ሲባል ነው። ገበሬዎች፣ ፈረሰኛው እያሉ ይጠሩታል። ምክንያቱም ከታሳቁ ልጅ በስተቀር ከቤተሰቦቹ ሊሰጠው የሚችል ምንም ዓይነት የሹመት ስም የለም። ስለዚህ ፈረሰኛው፣ ከሕፃናት የገበሬ ልጆች ጋር እንደልቡ በነፃነት ለመንቀሣቀስና በየአደን ቦታው ሁሉ ለመዟዟር ይፈቀድለት ነበር። ወጣቱ የመሣፍንት ዘር፣ እነዚህ ዋጋ የለሽ የሚባሉ ወጣቶች ከርሱ ይልቅ የተሻሉ መሆናቸውን አወቀ። በአጭር ጊዜ ውስጥም የሁለቱ ዓለሞች ጥበበኛ ሆነ። በውጭ ተንኮለኛ ፣ ጨካኝና አጭበርባሪ ነው። ይህ ደግሞ የመኖሪያው መሣሪያ ሆነለት። በመኖሪያው ግንብ ውስጥ ደግሞ ጥሩ የግርማ ሞገስና የትህትና ምሣሌ ሊሆን የሚችል ሆነ። በዚህም የተነሣ በዚያ ቤተሰብ ውስጥ ሊያገኝ ከሚገባው መብት ባለፈ ጥቂት ልብስና ምግብ ከሴቶች በበለጠ ይሰጠው ጀመረ። ከዚህም በላይ ገና ከልጅነቱ ለስላሳ ንፁና ለሽቶ ዓለማዊ ፍቅር ስላዳበረ በሴቶች መዳበስንም ይሻ ነበር።

የግል አስተማሪ የነበረው ታላቅ ወንድሙ ብቻ ቢሆንም፣ እርሱ የወንድሙን ደብተሮችና ትምህርቶች በመገልበጥና በመኮረጅ በቂ ዕውቀት አግኖቶ ለመስፍኑ ዱክ ዴ ቬንደሚ፣ ዐሃፊያቸው ሆነ። ለዚህ ቦታ ብቁ መሆኑም በዚህ ትንሽ በር ወደ ሰፊው ዓለም ገባ። ነገር ግን በህብረተሰቡ ውስጥ እንዲህ ያለ ዕውቅና ያለገኘለትን ባለሚልነት በቁማርና በአስረሽ ምችው ያበላሸው ጀመረ። እንዴት ባለ የማታለያና የማጭበርበር ዘዴ ተጠቅሞ እንደሆነ ባይታወቅም፣ ለማገልገልና ማንኛውንም መጥፎ ተግባር ለማከናወን በማመልከቱ፣ በፖለቲካ መሪው በሙሴ ቶርሲ ትዕዛዝ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ ተቀጠረ። የዚህን ቅጥር ምስጢር አለማወቁ ግን ይመረጣል። ከዚህ በኋላ ሮዉሌ ለጥቂት ጊዜ በዲፕሎማሲው ሥራ ላይ ዓይኑን እንዲገልጥ ተደረገ። ባህሪውን ቢያሻሽል እንደሚጠቀምበት፣ በውጭ አገር የመኖር ዕድል ደግሞ ትርፍ ገንዘብ ለማግኘት ላለው ጠንካራ ፍላጐት እንደሚረዳው አመነ።

በቆንሲል ማዕረግ ወደ ሮዜታ ተሳከ። ሮዜታ ወደብ በመሆንዋ ክበቂ በሳይ የንግድ እንቅስቃሴ ቢታይባትም በምስራቅ ሚዲተራኒያን ከሚገኙት ጣቢያዎች ሁሉ፣ አነስተኛ ክፍያ የሚደረግባት ነች። እርሱ ግን ደመወዙን በቀላሉ እጥፍ ማድረግ እንደሚችል ስራሱ ነገርው። ያሰበውንም ወዲያውኑ ጀመረ። እንደ ደረሰ ምንም ሳይቆይ፣ በእንክን የለሽ ጥሩ ስሙ ሳቢያ፣ ሚስትና ለመሥሪያ ቤቱ የሚሆን ሕንፃ ተሰጠው። ለማንኛውም ዓይነት ዓላማና ተግባር ሁለት ነገሮችን ታደሰ።

የሚያጋጥሙ ነገሮችን ስርዓት ሳያጠብቁ ከማከናወን አስቀድሞ፣ በበቂ ሁኔታ ማሰብ ጠቃሚ ነው። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ የተከበረ እኩያና የሚመጥን ሰው ስለሆነለት፣ ለሴት ልጁ የሚጠይቀው የጥሎሽ ጉዳይ ላይ ሊጣደፍ ይችላል። ዱ ሮውሌ ደግሞ ፈጥኖ ለመታሰር አይቸኩልም። በአሁኑ ሰዓት የርሱ ትልቁ ፍላጐት አቪሲኒያ ነች። ሰለ አቪሲኒያ የሚያውቀው ትንሽ ቢሆንም፣ በተደጋጋሚ ወርቅ፣ የከበሩ ድንጋዮችና ቅመማ ቅመም እንደሏት ተነገሯል። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ባልተለመደ ከፍተኛ ጉጉት የፈረንሣይን ኢስት ኢንዲያ ካምፓኒ፣ ወደ አቪሲኒያ ለማስፋፋት አቅድ አወጥቷል። ይሀን ያደረገው ዱ ሮውሌ ከርሱ ይልቅ ለሌላ ሰው ለማገልገል ይሄድብኝ ይሆናል ከሚል የተሣሣተ ሀሣብ በመነሣት ነው። ይህ ፈረሰኛ ግን ይህን የሚያደርግ አይደለም። ምክንያቱም እርሱ በዘኩሉ የራሱን ሀብት ማግኘቱን እንጂ፣ ትክክለኛ ነገር በመስራት በራሱ ላይ መሰናክል እንዲፈጠርበት ሀሳቡም የለውም። ወዲያውም በውስጡ የተፈጠረውን ጥርጣሬ ሊገነዘብ፣ በርሱነቱ ኮራ። ይሁን እንጂ በራሱ መንገድም እንኳ ቢሆን፣ ይህ አስተዋይ ሰው ሀልመኛ ነው። አገኘዋለሁ ብሎ ስለሚያሰበው ሀብት የሚታወቅ ነገር የለም። ነገር ግን ልክ የመጀመሪያዎቹ አሰሪኒያውያን አሜሪካ ውስጥ እንዳደረጉት ወይም ፈረንሣዊው ኻሮኒስ፣ በማላሬኔ ደሴቶች ላይ እንዳደረገው የርሱ የግሉ የሆነ ግዛተ ዘውድ ይመሠርታል። እርሱም፣ መጠነ ሰፊ በሆነ ሀብት ላይ ንጉስ ይሆናል። በዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ደግሞ ማዳሞዜል ዴ ማይሌ ልትመጥነው ስለማትችል ፈራ። ስለዚህም የንግስታትን ልዕልቶች አሰመ። በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ፈጣን ውሣኔ ላይ ለመድረስ ምንም አልተቸገረም። መጀመሪያ ጉዞው ይደረግ። ከዚያ በኋላ ጥያቄው የሚቀጥል ከሆነ ጋብቻውን ማድረግ፣ ሲል ደመደመ።

ይሁን እንጂ ይህ እቅዱ፣ አሊስ በውስጡ ቀስቅሳበት የነበረውን ጠንካራ ስሜት ሊያሸንፍ አልቻልም። ከአንድ ሣምንት በኋላ እንዲህ ሲል ለራሱ ተናገረ። እርግጥ ነው፣ ጋብቻው የሚማርከኝ አይደለም። ሆኖም ግን ከዚህች እርጠትብት ሕፃን ጋር ለመደሰት ማንኛውንም ነገር አክፍላለሁ።

እንዳለመታደል ሆኖ አሁን እርሱም ያለው በቤተሰቦቹ የአገር ቤት ግንብ ውስጥ አይደለም።የቆንሲሉም ሴት ልጅ፣ እንዳፈቀደው ሊያንከባልላት እንደሚችላት የገበሬ ልጅ አይደለችም። አስቀድሞ በሕግ ሊያገባት ይገባል፣ ይህን ደግሞ አይፈልገውም። ቆንሲሉ በተዘዋዋሪ ያቀረበለትን ያልተነገረ ስጦታ እርሱም አድበስብሶ ለማለፍ ስላልፈለገ ከመውጣቱ በፊት ከልጅቷ ጋር ወሲባዊ ስሜትን የሚቀሰቅስና ምንም ዓይነት ቃል ኪዳን የሌለበት የጨዋታ ጊዜ የሚያገኝበትን ዘዴ ፈለገ። ሲከታተላት ቆይቶ፣ ቀስ በቀስ አንድ ዕቅድ ነደፈ። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ የርሱን እምባሲ መክፈት እንዳረጋገጠለት፣ ወጣቷ ወይዘሪት የሆነ ቦታ ላይ አንድ ምስጢራዊ ፍቅር እንዳዳበረች ድ ሮዉሌ ርግጠኛ ስለሆነ የታሰበውን ጋብቻ እንደርሱ ሁሉ፣ በእርስዋም ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም ይሆናል። ለዚህ ባለጌ ሰው ይህ መፅናኛው ሆነለት። ለሌላ ሰው ያላትን ፍቅር፣ ተባባሪዬ ነው ብሎ ዱ ሮውሌ የመዘገበው ሙሴ ማቼ፣ ፈጥኖ ስሙን ነገረው። ይህ ለሌላ ሰው ያላት ፍቅር፣ እርሱ እንደተገነዘበው በጣም ጠንካራ ስለሆነ፣ ምናልባት የራሷን ስሜት እንድትከተል ያስገድዳት ይሆናል። እርሱ ደግሞ ልምድ ያለው ሰው በመሆኑ፣ ይህን ጉዳይ በብልሀት ወደራሱ አቅጣጫ መመለስ ይኖርበታል።

ከገበታው ላይ ብድግ ብላ ነፍሷን ስታ በመውደቋ፣ ከእይታ ከተሰወረች ከብዙ ቀናት በኋላ፣ አሊስ ተመልሣ ብቅ አለች። ዱ ሮውሌ፣ በሄደችበት ሁሉ በዓይኑ ይከተላታል። ሙሴ ዴ ማይሌ ምንም እንዳላስተዋለ እያስመሰለ ውስጡ በደስታ ሞላ። ልጁን ግን፣ ንፅህናዋን ባለመጠበቋና እንግዳቸውንም ባለማስተናገዷ መውቀሱን ተያያዘው። ታዲያ አሊስ የአባቷን ውቀሣ ተቀበለች? ወይስ ደግሞ ተፈጥሮአዊው ውበቷ ፣ ላላ ተደርጐ የተሠራው ፀጉርዋ፣ ተራው ልብስዋና ሆን ብላና ምክንያት ፈጥራ ታምሚአለሁ ከማለቷ በስተቀር፣ የተሟላው ጤንነትዋ፣ የጀግኖችን ስሜት አላነሣሣም ይሆን? አይናፋርነትዋና ፍርሃትዋ እውነተኛውን የዱ ሮውሌን ስሜት አጋግሎ ምንም ዘንድ ለመድረስ እንደንፋፋው፣ ማለትም ይህን ባህርይ ብወሲባዊ ግንኙነት ፍላጐት ለመለወጥ አላነሣሣውም?

ከቆንሲሉ ፅህፈት ቤት የእምባሲ ሹመቱን ገና ተቀብሎ ሲወጣ፣ ፊረሰኛው፣ አሊስን በየረጃው ላይ ስትወርድ አያት። ወደ ሙዚቃው ክፍልም በፍጥነት ተከተላት። እርስዋ ግን ዞር ያለችውና ላይ የነበረ አንድ የሙዚቃ ድርሰት ዕሑፍ በፍጥነት አነሣች።

ዱ ሮውሌ፣ ይህን ተግባር በማስመሰል እንኳ ቢሆን ሊያረጋግጥ አልቻለም። በቀጥታ ወደ ውጣታ ዘንድ በመሄድ ፊት ለፊትዋ ሙሉ በሙሉ ተጋርጦ ተገተረ።

«ላንቺ የሚሆን መልካም ዜና አለኝ» አለ። የትንፋሹ ሙቀት ግንባሯ ላይ እስኪሰማት ድረስ አፉን ወደርስዋ በጣም አስጠግቶ

«ተነስቼ ልሄድ ነው»

«ግን ... እንዴት ያለ በጣም መጥፎ ዕድል ነው»

ከዚህ በፊት ፊዕሞ ተነጋግረው አያውቁም

«እውነትሽን ነው? ስለይሽ እያየሽ ሀዘን አይሰማሽም?»

አሊስ መልስ አልሰጠችም። በዚያ የዝምታ ቅፅበት ውስጥ ግን እጅግ ፈጣንና ጥልቅ የሆነ ለውጥ ተሰማት። ይህ ሰው፣ በሩ በጣም አሩቅ በሆነበት በዚህ የእንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ እንዲህ ሲቀርባት፣ ፊቷ መቅላትና ትንፋሽዋ ቁርጥ፣ ቁርጥ፣ ቁርጥ ማለት ጀመረ። ወዲያውኑም እንደገና በምሽት ያደባ ሰው እንዳገጣት፣ እንደተከታተላት፣ ቁርጭምጭሚቷ እንደተሰበረባት፣ ውሾችም መጮህ እንደ ጀመሩ ታያት። በዚህ መሀል የኒዛው ነፃነትዋ ወዲያውኑ ትዝ ሲላት የሻምላው ብርታት፣ የፈርስዋ ኃይል፣ የሽጉጥዋ የፍንዳታ ድምፅ በአንድ ላይ ተሰማት። ብድግ አለችና ፊት ለፊት ተጋፈጠችው።

«ምን ትፈልጋለህ?» አለችው በሰማያዊዎቹ አይኖችዋ አጠንክራ እያየችው።

«እኔ በጭራሽ ሳልፈልግ ሌሎች እኔን ወክለው ይፈልጉልኛል። አንቺ ከምታስቢው የተለየ አላስብም፣ አንጋባም» አላት ዱ ሮውሌ

«ለመወሰን በመቻልህ በጣም የተደሰትክ ትመስላለህ»

ቀረባት። እርሷም ወደኋላ አላፈገፍገችም ሲቀርባት በውስጧ የተቀሰቀሰው ጥልቅ ስሜት የፍርሃት አልነበረም።

«እየወሰንክ አይደለም፣ አውቃለሁ» አለ።

«ምንድነው የምታውቀው»

«ሣልነካ መቆየት እፈልጋለሁ። አንቺ ግን ሣትነኪ የቆየሽ አይደለሽም»

«እና ምን ይሁን?»

«እናማ ጋብቻ የሚሉትን ነገር እንርሳውና፣ እንዲሁ አንቺ እንደምታደርጊው፣ ፍቅራችን ይቀጥል። እናም ደግሞ እንራራት ...»

አይኖችዋ በፍርሃት አልተቁለጨለጮም

« . . . ለመደሰት» አላት ክንፈሮችዋን በክንፈሮቹ እየቆለፋቸው። እርስዋም ልታደርገው በምትችለው ፍጥነት አላመሰጠችውም።

በኮሪደሩ በኩል የእግር ዱካ ይሰማል። አሊስ ረጋ ብላ የሙዚቃ መሣሪያው አጠገብ ተቀመጠች። ዱ ሮውሌ፣ ወንበር ይዞ በሌላኛው አነስተኛ የእንግዳ መቀበያ ክፍል ጥግ ተቀመጠ። ማዳም ዱ ማይሌ፣ ሽር ብትን እያሰኝ ስትገባ፣ ሁሉቱንም በፍቅር የጠፋ ወፎች ስትመለከታቸው፣ ሙሉ በሙሉ በባሏ ሀሣብ ውስጥ በመሆን ተደሰተች። አራት አብረዋት እንዲበሉም ወደገበታው ጋበዘቻቸው።

በገበታው ላይ ቆንሲሉ፣ ጨዋታው እንዳይቀዘቅዝ በማድረግ ሲያቆየው፣ በቅርቡ ከተዓፋት ጋዜጠኞች ላይ ያሰውን ዜና ነገራቸው።

« ፖንሴን በተመለከተ» አለ ሰባለቤቱ፣ «መቼም በደንብ ታውቂዋለሽ፣ ያ መድሃኒት ቀማሚ . . . » ማቼና ዱ ሮውሌ በማንኪያቸው ላይ አሻግረው አሊሰን ተመለከቷት

« . . . ይህ አሰልቺ ሰው ንቱሱን ሊያያቸው ይፈልጋል። እንዳሰበውም አገኛቸው። ግርማዊነታቸው ግን እጅግ ብልህ ስለሆኑ በርሱ የሚታለሉ አልሆኑም። ታዲያ ይህ ቀን ያነሣው፣ ታስሮ ፍርድ እየጠበቀ ነው»

በአሊስ በኩል እንዳችም እንቅስቃሴ የለም። አንዳችም የማጉረምረም ድምፅ፣ ወይም ሊያጋልጣት የሚችል በሀይል አየር የመሣብ ነገር የለባትም። ይህ ሁሉ ሲሆን፣ አሊስ፣ ጊዛ ውስጥ፣ በወንዙ አጠገብ፣ በረገዥሞቹ የሰንበሌጥ አጥሮች ስር ነበረች። በነዚያ ጥቂት ቀናት ያገኘችው ጥንካሬ በውስጧ ተደብቆ አለ። ከተመለሰችበት ጊዜ ጀምሮ የዚያን ያህል በታላቅ ነፃነት እንዳልኖረች ሁሉ፣ ነገሮች በትክክል እየተከናወኑ ናቸው። የታመመች ወይም የደነገጠች ትንሽ ልጃገረድ እንደምታደርገው ከዱ ሮውሌ አምልጣለች። ይህን ሁሉ ያደረገችው፣ ጀን ባንቲስትን በመጠበቅና የወደፊቱን ሕይወታቸውን በአደጋ ላይ ላለመጣል ብላ ነበር። አሁን ግን መታሰሩን ሰማች። እንግዲህ ለመንቀሳቀስ ተራ ድርሻው የርስዋ ነው። ነፃነትዋን ወደ ሕግ መጣስ መለወጥ ያለባት እርስዋ ነች። ፍላጐቶዋን ወደ ሃይል መለወጥ ያለባት እርስዋ ነች። ስለሆነም ከዚህ በኋላ እንዳችም ነገር ከራስዋም ይሁን ከሌሎች የምትፈራው ነገር አይኖርም። እናም ሁሉንም መሰናክል በጣጥሣ ታልፋለች።

ፈረሰኛው ዱ ሮውሌ፣ ትመጣለች ብሎ ይጠብቃት ስለነበረ፣ ከአስሶ ሌሊት ትንሽ አለፍ አንዳለ ተሸልካ ወደ መኝታ ክፍሉ ገባች።

10

ጆን ባፕቲስትን ለመመርመር ከምሁራን የተመረጡት ሰዎች፣ ሣንሣራይ ከገመቱበትና ከአዲሱ ዓመትም ጥቂት ቀደም ብለው ተሰበሰቡ። ቬርሳይለስ ውስጥ የዚህ እጅግ ልዩ የሆነ ታሪክ የሚነገርለት የውጭ አገር አሰረኛ ቆይታ መራዘም፣ እየዋለ እያደር አስቸጋሪ መሆኑ ይታወቅ ጀመር። ጉዳዩ እስከመንግስት ምክር ቤት ድረስ ሲቀርብ ፣ንጉሡ ራሣቸው የተፋጠነ ርምጃ እንዲወሰድ አዝዘዋል። ፖንሲ፣ በርግጥም አታላይና አጭበርባሪ ከሆነ በፍጥነት ቢቀጣ ጥሩ ነው። ነገር ግን መልካም ሰው ሆኖ፣ በርግጥም የንጉሡ መልዕክተኛ ከሆነ እንደስድብ ሊቆጠር የሚችለውን ጉዳይ በጣም በአጭሩ ማድረጉ የተሻለ ነው።

ከሕዝብ መካከል የተመረጡ አራት ምሁራን ዳኞች አሉ። ሁለቱ የዩኒቨርሲቲ ሰዎች ሲሆኑ፣ ሁለቱ ደግሞ ከክህናት መካከል ናቸው። አራቱም ሰዎች በጥንታዊ ታሪክ፣ በቋንቋዎች ትምህርትና ጥናት የዕውቀት ዘርፍ የታወቁ ምሁራን ስለሆኑ ትምህርታቸውን ሊፈታተን የሚችል አንድም ሰው የለም።ምንም ይሁን ምን እነርሱ የሚሉት ታምኖ ተቀባይነትን ያገኛል። እነርሱ ብዙም አይናገሩም። ቢናገሩም በተቻለ መጠን ኮስተር ባለ ድምፅ ነው። በሌላ መልክ፣ በነርሱ አስተያየትና ትምህርት ውስጥ ባልተካተተ ወይም በተለየ አስተያየትና ትምህርት ላይ መርዛቸውን ይተፋሉ።

እነዚህ ከሕዝብ መካከል የተመረጡ ዳኞች፣ ለፖንሲ ጉዳይ ጠላቶች ናቸው ማለት ጉዳዩን ማጣጣል ይሆናል። እውነተኛው ነጥብ፣ ፖንሲ፣ ንጉሡን ያስቀየማቸው መሆኑንና፣እነርሱ ደግሞ ንጉሡን ለማስደሰት መፈለጋቸው ነው። ከዚህም በላይ፣ ስለዚህ ተጓዥ ሰለተባለው ሰው ያዳመጡት ፐሮፖጋንዳ፣ አስተሣሰባቸው በርሱ ላይ ተቃራኒ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። ይሁን እንጂ በታዋቂነታቸውና በዝነኛነታቸው ምክንያት በቀላሉ ተፅዕኖአቸውን ያሣድራሉ።

በመጀመሪያው ችሎት ላይ ሊቀርብ፣ ጆን ባፕቲስት ንጉሡ ነበር። ሣንሣራይ፣ ከነጭ ጥጥ የተሠራውን ልብስ እንደ ትንሣኤ ሊቆጠርበት ስለሚችል፣ እንዳይለብስ መክረውት ነበር። በዚህም የተነሣ የተለመደውንና ተቀባይነት ያለውን የሱፍ ልብስ ለብሶ ሄደ። የፊት ለፊቱ ተቃውሞ በሶርቦኔ ውስጥ በሚገኝ አንድ ትልቅ ክፍል ውስጥ ተጀመረ። የክፍሉ ግድግዳ በተቀረፀና በወርቅ በተለበጠ እንጨት ያጌጠ ነው። ተመራጭ ዳኞች የተቀመጡት ከእንጨት

በተሠራ መድረክ ላይ ሲሆን፣ ፕሮፌሰሮች የመምህርነት መለያቸውን፣ ቀላውስቱም የክህነት ካባቸውን ለብሰዋል። ተጠርጣሪው፣ ከፊት ለፊት ከመድረኩ በታች ተቀምጧል። ጠባቂዎቹ፣ በግራና በቀኝ በኩል ሆነው ይከታተሉታል። ከበስተኋላው ባሉት ሁለት ተርታ መቀመጫዎች ላይ፣ አነስተኛ ቁጥር ያለው የችሎት ታዳሚ ሲገኝ፣ ከዚህ መካከል ዓይኑ እየሸሸው ያለውን ፍሌሀውትን፣ ከሶስት ሌሎች ጀስዊቶች ጋር ታጅቦው አባ ኘላንቴይንንና ሌሎች እንግዶችን ጆን ባፕቲስት ተመለከተ። ክረምት በመሆኑ ምክንያት ክፍሉ ቀዝቃዛ ነበርና አድማጮች ሊያስላቸው ይቃጣል።

ሁሉንም ሰው ያስጨነቀው ሥርዓት፣ የፍርድ ቤት ያልሆነውን ሥራ የፍርድ ቤት ማስመሰል ነበር። ሂደቱ፣የአንድ ሰው እውቀት መገመቻ የባለሙያ ሥራ ነበር። ጥያቄው ጆን ባፕቲስት በርግጥ ወንጀል መፈፀሙን ለማረጋገጥ ሳይሆን፣ ጆን ባፕቲስት አከናውኜው ተመልሻለሁ የሚለውን ጉዞ፣ በርግጥ አከናውኖታል ወይ የሚል ነው። እንደዚሁም ደግሞ ግልፅና ያልተደበላለቀ የእውነታ ምርመራው፣ ሌላ ገፅታ ቢኖረውስ የሚለው ነው። ጆን ባፕቲስት ሐሰተኛ ሆኖ ከተገኘ፣ ይኸው ተመልከቶ በፍርድ እንዲወሰንበት ወደ ማሪፈያ ቤት ይተላለፍና እዚያ ሰዎች እውነቱን እንዲናገሩ የሚደረግበት ሌላ ዘዴ አለ።

የምርመራው ሂደት እየተከናወነ እያለ አጠራጣሪ ነገሮች ግልፅ ነበሩ። የምርመራው አጣሪዎች «ተከሣሽ» ስሙን፣ ትውልዱንና ሥራውን «ፈቃደኛ ከሆነ» እንዲገልፅ ጠየቁት። ይሁን እንጂ የምርመራ አጣሪዎች ፕሬዚዳንት፣ ይህን ጥያቄ ባይመልስ አዳጋች እንደሚሆንበት በራሱ አገላለፅ አስረዳው።

«ስሜ ጆን ባፕቲስት ፖንሴ ይባላል። ወላጆቼን አላውቃቸውም። የተወለድኩት ግሬናብል ውስጥ ሰኔ 17 ቀን 1672 ዓ.ም ላይ ነበር። ላለፉት ሦስት ዓመቶች ያህል ካይሮ ውስጥ አዕዋት በመሰብሰብ ስራ ላይ በመሠማራት ኖሬአለሁ»

ፕሬዚዳንቱ፣ ከፊት ለፊት ያሉትን ወረቀቶች ፈተሸቸው። የፍርድ ሂደቱ ፀሐፊ፣ በመድረኩ ጠርዝ ላይ በብዕሩ ፃጨረ።

«እንዲህ ከሆነ ወደ አቢሲኒያ ተጉዣለሁ ብለህ እየገለፅክ አይደለም እንዴ?»

«እየገለፅኩ ሣይሆን እያረጋገጥኩ ነው»

«እንዲህ ከመሰለ ጉዞ ተመልሰናል እያሉ በጉራ የሚናገሩ ጥቂት ክርስቲያኖች በዛሬው ዘመን እንዳሉ ታውቃለህ?»

«አውቃለሁ፣ እኔ ግን ጉራ አልናገርም» አለ ጀን ባፕቲስት

«ታዲያ እስከዚያ ድረስ የተገነከው ንጉሡ ፈት ለመቅረብ ነበራ።» አለ ሌላው በጣም ሽማግሌ ሆኖ ፊቱ የገረጣውና የአስቀያሚ አሮጌት የሚንቋቋ ድምፅ ያለው መምህር።

«ለዚህ ተልዕኮ ሀላፊነቱን የሰጡኝና ያዘዙኝ የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገስት ራሣቸው ናቸው»

«እናውቃለን፣ እናውቃለን» ሲል ፕሬዚዳንቱ አንድ እብድ የሆነን ሰው በምናብ ከሚፈጠሩ የቅዠት ሀሳቦች ስቃይ የሚያፅናናው ይመስል። «አስቲ ከዚህ አጠቃላይ ሀሣብ ወደሌላ ሀሣብ እንሻገር። የምንጠይቅህን የተለያዩ ጥያቄዎችን ለመመለስ ፈቃደኛ ሁንልን። አባ ዝሌት ሊጀምሩ ይፈልጋሉ ይመስለኛል»

«ጌታዬ» አሉ ክሉላው ጋር ሲታዩ ወጣት የሚመስሉ፣ አጥንታም ፊትና በአፋቸው ግራና ቀኝ ጥልቅ መስመር ያላቸው ቄስ «የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገስት የሚኖሩበት ከተማ ስሙ ማነ ይባላል?»

«ጐንደር ይባላል፣ አባቴ»

«ፊደላቱን መጥራት ትችላለህ?»

ፖንሴ፣ የከተማውን ስም ፊደላት ለይቶ ጠራ። በክህኑ ጥያቄ መሠረትም ስለከተማው መጠነኛ ገለፃ ሰጠ። አራቱ ሰዎች፣ ፖንሴ የሚናገረውን አሁንም፣ አሁንም በዓይኖቻቸው እየተጠቃቀሱና በቃላቶቹ ላይ አሽሙራዊ አስተያየት እየተለዋወጡ በጥንቃቄ ያደምጣሉ።

«ለመሆኑ ዶን አልቫሬዝን ታውቀዋለህ?»

«የለም፣ የትም ቦታ አግኝቼው አላውቅም?» አለ ጀን ባፕቲስት፣ ስሙን ለማስታወስ እየሞከረ

«ዶን አልቫሬዝ ሞቷል» አለ ፕሬዚዳንቱ በንቀት ፈገግታ «የተከበረ ጀስዊት፣ ታላቅና የሚታመን ምሁር ነበር። የአቢሲኒያውያንን ሕይወትና አኗኗር በውስጣቸው ሆኖ ለአስር ዓመታት ስለቆየ፣ መረጃ ትቶልን አልፏል»

«ባነብበው በጣም እደሰት ነበር» አለ ፖንሴ።

«ብታነብበው ትጠቀምበታለህ» አለው ቢጫው ምሁር «የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አንተ እንዳልከው ጐንደር ሣይሆን አክሱም መባሉንም ትማር ነበር»

«ከዚህም በተጨማሪ» ሲሉ ወጣቱ ካህን ቀጠሉ። «በአገሪቱ ሌሎች ከተሞች አለመኖራቸውን፣ ሕዝቡ ሁሉ በየመሬቱ ላይ እያረሰ እንደሚኖርና ንጉሡ ራሣቸውም ከአንዱ ሰፈር ወደ ሌላው ሲጓዙ እንደሚኖሩም ታውቅ ነበር»

«ይቅርታ፣ ይህ የተፃፈው የቅርብ ጊዜ መግለጫው አይደለም። አገሪቱ መንደሮችና ከተሞች የሞሉባት ነች። ጐንደር የተመሠረተችው ጀስዊቶች ከሰቀቁ በኋላ ነው። ምክንያቱም ንጉሠ ነገስቱ አንድ ቦታ የፀና ቤተመንግስት ስለፈለጉና አክሱሞችን ስላላመኗቸው ነበር። በመጀመሪያ ላይ እርግጥ ነው፣ የኛ የፈረንሣይ ነገስታት ይከተሉት የነበረውን ዓይነት ሥርዓት ነበራቸው። በቀዳማዊ ፍራንሲስ ጊዜ ቤተመንግስቱ ከቦታ ቦታ ይዘዋወር ነበር። በኋላ ፖሪስ ላይ ረጋ። አሁን በመጨረሻም ቬርሣይለስ ሆነ። ይህ የመጨረሻው ሰውጥ በጣም በቅርብ ጊዜ የተከናወነ በመሆኑ ለምሣሌ ከአስር ዓመት በኋላ ወደ ፈረንሣይ የተመለሰ መልዕክተኛ የከተማውን ስም ላይጠቅስ ይችላል»

«ማብራሪያህ የሚያጓጓ ነው» አለ ምሁሩ «በኛ በራሳችን አገር ታሪክ ላይ ተመስርተህ ተጉዘ አይቼዋለሁ የምትለውን አገር መልክ ለመገንባትና ለመቀባባት ካደረግኸው ይልቅ እኛ የተሻለ እናሳምር ነበር»

ጀን ባፕቲስት መቃወም ጀመረ። ፕሬዚዳንቱ አሰመግባባታቸውን አቋርጠ ሌላ ጥያቄ ጠየቀ። ከዚህ አጭር ምልልስ፣ የምርመራው አጠቃላይ መንፈስና አዝማሚያ ምን እንደሚመስል መለካት ይቻላል። ዝርዝሩን አሁን ማስፈር ፋይዳ የለው። ምክንያቱም ምርመራው ከሁለት ሰዓት በላይ ጊዜ ፈጅቷል።

ተጠርጣሪው፣ በጠባቂዎች ግራና ቀኝ ተከብቦ፣ ምሽት ላይ ወደቤት ተመለሰ። ሣንግራይ፣ ትዕግስታቸው ተሟጦ ይጠብቁት ነበር። ክሌ ቢዩ ኖይር የመጣው ትኩስ መጠጥ ጠረጴዛው ላይ ሆኖ እንፋሎቱን ያወጣል።

«እናስ?» አሉ አማካሪው።

«የምናገረውን አንዱንም ቃል አያምኑም። አነርሱ የሚያውቁት ነገር ሁሉ፣ አቢሲኒያን ከስልሣ ዓመት በፊት ትተዋት ከወጡት ጀስዊቶች የተገኘ ነው። በጀስዊቶች አገላለጽ ላይ ተመስርተው ስለሆነ በዚያች አገር ከንግስት ሣባ ጊዜ ጀምሮ አንዳችም የተለወጠ ነገር የለም። እነዚህ የአዕምሮ ዘገምተኞች፣ ግማሽ ምዕተ አመት ምንም አይደለም በማለት ድርቅ ይላሉ። በነርሱ መዛህፍት ውስጥ ያልተጠቀሰውን ነገር ሁሉ የፈጠራ ነው ይላሉ።»

ጆን ባፕቲስት የዕለቱን ውሎ ሰወዳጁ እጥር ምጥን ባለ ሁኔታ ነገራቸው።

«ከዚህም በተጨማሪ የአቢሲኒያውያንን ሀይማኖት አውቀው እንደሆነም ጠየቁኝ። ስለዚህ ነገር የማውቀው እንደሌለኝ ነገርኳቸው። ይህን በተመለከተ እንደኛው በነዚህ ሕዝቦች ካህናት መሠረት የክርስቶስ ባህሪያት ስንት ነው? ሲል ጠየቁኝ። እዚያም በቀጥታ ይህን አይነት ጥያቄ ቀርቦልኝ እንደነበረ ነገርኳቸው። እንዲህ ከሆነና ከኛ ሀይማኖት ጋር አረጋግጠህ ከመለስክላቸው ይገድሉህ ነበር ሲል ፕሬዚዳንቱ ተቃወሙ። «እኔም፣ ቁርጥ ያለ መልስ አልሰጠኋቸውም። ይህም ምክንያት አለው። ምክንያቱም መልሱን አላውቀውም። በስነ መለኮት ትምህርት ላይ ዕውቀቴ አናሣ ስለሆነ ይቅርታ እንዲያደርጉልኝ ጠየቅኋቸው። ያዳነኝም ይሽው ማይምነቱ ነው። ስል መለስኩለት»

«ጥሩ፣ እጅግ በጣም ጥሩ፣ አንበሣ ሆነህ ነው የተፋለምካቸው» አሉ ሣንግራይ

«ጉድጓድ ውስጥ ሆኖ በሁሉም አቅጣጫ በተመረዘ ጦር እየተወጋ እንዳለ አንበሳ ማለት ነው። የሚገርምም፣ የሙራድን ስም የአቢሲኒያውያን ስም ሣይሆን የቱርካውያን ስም ነው የሚለውን መሠረት በማድረግ የርሱን ሕጋዊነትም ጠይቀውኛል። እውነት ነው፣ ሰውዬው አርመናዊ ነው። ታዲያ አርመናዊ ሆኖ ነው ንጉሡ ዲፕሎማታቸው እንዲሆን የሾሙት አለኝ፣አንደኛው አላዋቂ ቂስ። ለመሆኑ ነገስታት ከመች ወዲህ ነው ከጠላታቸው አገር አምባሣደር መምረጥ የጀመሩት? አለኝ። ሳስረዳው ሞክርኩ። የማቀርባቸውን ነጥቦች ሁሉ ማዳመጥ አልፈለገም»

«ተስፋ መቁረጥ የለብህም» አሉት ሣንግራይ። «የመከራከሪያ ነጥቦችህ ላይ በርታ። ባይስማማህም እንኳ የተሻለ ዳኝነት አግኝ። እኛም ከበስተጀርባ ስላንተ ጉዳይ እያወራን ነው። እንዲያውም እውነቱን ልንገርህና አንድ ጥሩ ዜና አግኝቻለሁ። የቻርትሬሱ መስፍን፣ አንተ ከሰሰት ቀናት በፊት የሰጠሽኝን የእጅ ፅሁፍህን ለማንበብ አሺ ብለዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ የሚኖራቸው አቋም በሚቀጥለው ሣምንት መጀመሪያ ላይ ይደርሰኛል። ሰውዬው፣ በንጉሡ ላይ ያላቸው ተፅዕኖ አነስተኛ ቢሆንም አምነው ለሚነሰቡበት ጉዳይ የሕዝብን አስተያየት ለማሰባሰብ ከፍተኛ ችሎታ አላቸው»

«እንደሚመስለኝ በእኔ ጉዳይ ላይ ተቀጣጥሎ እየነደደ ያለው እሣት፣ የመጨረሻው ሃይሉ ላይ የደረሰ ይመስለኛል» አለ ጆን ባፕቲስት ምርር ብሎት።

የሚቀጥለው ዕለት እሁድ ነው። የምርመራው ጥያቄ ረቡዕ ይቀጥላል። ጆን ባፕቲስትን ለማየት፣ ሳንግራይ በአስር ሰዓት ላይ መጡ

«ለአንድ መንፈሣዊ ሰባኪ ሚና፣ ምንም ያህል መውደድ እንደሌለኝ ታውቃለህ» አሉት ዝቅ ባለ ድምፅ «እነዚህ ሁለት ጠባቂ መላዕክቶችህም ባንተ ላይ ሳያቋርጡ ሪፖርት እንደሚያደርጉ አይጠረጠርም። በርግጥ ከኔ ጋር በመኖርህ አንዳንድ ነገሮች አይስማሙህም። ነገር ግን ወደ ቤተክርስቲያን ባለመሄድ፣ ጥፋቶቹን ሁሉ ከዚያ ጋር አታያይዝ»

ጆን ባፕቲስት፣ ያስወነጅሉትን ተንከባካቢውን ምክር ተቀብሎ፣ አጃቢዎቹን መርቶ፣ ለአስራ አንዱ ሰዓት የፀሎት ስነ ሥርዓት ወደ ቅዱስ ኢዮስታቹ ቤተክርስቲያን ሄደ። ስለቅዳሴ ምንም የሚያውቀው ነገር ስለሌለው ማይም ነው። በጥቁር ሰማያዊው ባለቀስት ቅርፅ ጣሪያ ላይ በሚታየው የታህሣስ ወር ደካማ ብርሃን፣ እፎይታና መደመም አገኘ እንጂ የሚሰማውን መዝሙር እንኳ፣ረጋ ያለ ድምፅ አድርጐ ነበር የሚያስበው። የዚያን ወቅት የአየር ሁኔታው፣ የልጅነት ጊዜውን አስታወሰው። አላውቃትም የሚሉትን፣ ነገር ግን ምስኪን የቤት ሠራተኛ የነበረችና ዲቃላ ልጅዋን እንዳታሳድግ፣ አሳዳሪዋ የከለከላትን እናቱ፣ ትዝ አለችው። የወላጅ ጉዳዩ ሲነሣ ለመሆኑ የማን ዲቃላ ነበር?

ይህን ጨርሶውንም ሣያውቅ ይኖራል። በርግጥ አንድ ህፃን ቤተሰቡን ማወቅ ካልቻለ ዓይኖቹ ሁልጊዜም ወደ አንድ የታላላቅ ሰዎች ግንብ መመልከቱ አይቀርም። በዚህም የተነሣ ፖንሴ፣ የአንድ ንጉስ ወይም መስፍን ዝርያ እንደሆነ እንጂ የማንም ምስኪን ልጅ እንዳልሆነ ያምናል። ነገር ግን በትክክል አባቱ ቤሣቤስቲን የሉለው፣ ጭራሽ ከሁሉም የባሰ መናጢ ድሃ ነው። ምናልባትም የክፉ ወንጀለኞችና ነፍሰ ገዳዮች መሪ ይሆናል። ምናልባትም የመጨረሻው ለጋስ ሰው ይሆናል። ወይም ማንኛውንም አደገኛ ተግባር ለማከናወን ፍርሃት የሚሉት ነገር ያልፈጠረበት ሰው ይሆናል። ምናልባትም ጨርሶ ሊሸነፍ የማይችል ሽፍታ የነበረ ሰው ይሆናል። የሰማዩ አባታችን ሆይ፣ አንተ ማነህ? እነዚህ ቃላት ለጆን ባፕቲስት በእውነቱ ምንም መልክና ቅርፅ አያሣዩትም። እንዲያው አንድ ልዩሰብአዊ ፍጡርን ብቻ ያሳስቡታል። እርሱ የሚታየው፣ አንድ ባህርያቱን በያንዳንዱ አንቅስቃሴው ላይ እንዳሻው መለወጥ የሚችል አይነት ሰው አድርጎ ነው። ሰማያት፣ ለአባት የለሽ ልጆች እና ናቸው። ወይም ደግሞ በአባት የለሽ ልጆች ከመጠን በላይ የተሞሉ ስለሆኑ፣ ለተጨማሪ ልጅ ቦታ የላቸውም።

ፖንሴ፣ ገና ከጨቅላነቱ ጀምሮ አስራ ሁለት ዓመት እስኪሞላው ድረስ ያሳደጉት በዝጠር የሚኖሩት ሴት አያቱ ነበሩ። አዛውንቲቱ ኑሯቸውን የሚደጉሙት ቅርጫት እየሠሩ ነበር። በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉት የሴቶች ስዕሎች ሁሉ ክርሱ የተዋሱትን ብርሃን መልሰው ያንፀባርቁበት ነበር። ወንድ አምላክን በማምለክ ፈንታ ሴት ጣኦትን ቢያመልክ ኖሮ፣ ጳጳስ ሊሆን የሚችልበትን ሃይል ያገኝ ነበር። ይህን በተመለከተ ክርሱ ሊሸል የሚችል ማንም እንዳልነበረ ትዝ ሲለው ሰራሱ ፈገግ አለ።

የቅዳሴ ስነስርዓቱ ሲካሄድ እንደ አስፈላጊነቱ ጆን ባፕቲስት ይቀመጣል፣ ይቆማል፣ ወይም ይንበረከክል። በያንዳንዱ የአንቅስቃሴ አቅጣጫ ለውጥ፣ በቀዝቃዛው የድንጋይ ወለል ላይ ያረፉት ወንበሮች ይንሣጠጣሉ። በቁርባን ጊዜ፣ በካህኑ አጠገብ ቆሞ የነበረው ዲያቆን አንዲት ትንሽ ቃጭል ሲያንቃጭል ድምፁ በቀዝቃዛው አየር ውስጥ የደወል ያህል ተስተጋባ። ተንበርክኮ የነበረው ጆን ባፕቲስት፣ ከአፋ ውስጥ ጭጋግ የመሰለ እንፋሎት ሲወጣ ይመለከታል። ጭንቅላቱን ትንሽ ቀና ሲያደርግ አንዱ ገጨው። እንዲህ ያሉ ሰዎች ማን መሆናቸውን እንኳ ሳታጣራ በፊት ወዲያውኑ፣ ለዘለዓለም ሳትሰወሩ እንድትኖሩ የሚፈልጉ ዓይነት ሰዎች ናቸው።

ዓይናቸ አንድ ታላቅ ነገርን ያገኙ ይመስል ብልጥጥ ብለው ሣለ፣ ተንበርክኬአለሁ ሲል አሰቡ። አምነ ወደ ኢትዮጵያ ስመጓዝ ይህን ኃላፊነት ከተቀበልኩበት ጊዜ ጀምሮ እንደተንበረከክሁ ነኝ። ወይም ደግሞ ምናልባት አሊስን ካየኋት ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ ሊሆን ይችላል። ያም ሆነ ይህ፣ አንድ ነው። ነፃ ሰው ነበርኩ። በላዬ ላይ ስተጫነብኝ አንድም ባለስልጣን ተሸንፈ አላውቅም ነበር። ቆንሲሉም ቢሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ማየው፣ ወደኔ የመጣው እርሱ ነበር እንጂ፣ እኔ ወደርሱ አልሄድኩም። በአንድ ዛፍ ስር አረፍ ብዬ አቤቱታውን በማዳመጥ ውለታ ነበር የሠራሁለት። እንዲያ ላደረግሁለት ሰው አሁን ተንበርክኬ እገኛለሁ።

ቁሱ ምልክት ሲሰጡ፣ ተንበርክኮ የነበረው ሁሉ ብድግ ብሎ ቆመ። ከበስተኋላው ጠመንጃ አንጋች አጃቢዎቹም ብድግ ሲሉ መሣሪያቸው ሲንጫነጭ፣ ጆን ባፕቲስት ሰማ። እርሱም እንደሚመቻቸው ሆነላቸው።

ይኸው አሁን ደግሞ ተነስቼ ቆሜአለሁ። ይህንንም ያደረግሁት ስለታዘዝኩ ነው። ተቀመጥኩም፣ ቆምኩም ሁልጊዜም እንደተንበረከክሁ ነኝ። ይህ ደግሞ ሽንፈት ነው። ቆንሲሉ

ራርቶልኝ ሴት ልጁን ይሰጠኛል ብዬ እጠብቃለሁ። ንጉሡም የመሣፍንት ዘር ብለው እንዲመርቁኝ እጠብቃለሁ። እነዚህ ምሁራኖችም አስተያየታቸውን እንዲሰጡ እየጠበቅሁ ነኝ። እነዚህ ደግሞ ሊወነጅሉኝ ነው። ንጉሡም ሲረዱኝ የሚያደርጉት አንዳችም ነገር የለም። ቆንሲሉም ሴት ልጁን ይከለክለኛል። ይህ ሁሉ ሲሆን የምንበረከከው በሚያፈቅረኝ ሕዝብ ፊት ሳይሆን፣ በነዚህ እጅግ መጥፎ ባለሥልጣናት ፊት ነው። ከዚህ ሁሉ የሚከፋው ግን፣ እኔ ይህን አለማመኔ ነው። የመሣፍንት ወገን ተብሎ በአንድ ንጉስ ውዳሴ ማግኘት ሌሎችን ለመጫን ከሆነ፣ ይህን ክብር ነው ብዬ አልቀበለውም። ይህም ሃይማኖት ከሌለው የተሻለ ነው ብዬ አላምንም። ማንም ሰው እምነቱን በራሱ ፍላጐት ሊመራ መቻሉን ባምንም፣ ቤተክርስቲያን በሰዎች አስተሣሰብ ላይ፣ በተሰይም በኔ ላይ ሥልጣንዋን እንድሸከም እንድታስገድደኝ ፈፅሞ አልቀበልም። ይህም ሆኖ ግን ይኸው ተንበርክኬ እኖራለሁ።

ካህኑ ቡራኬ ሰጥተው ካሳረጉ በኋላ፣ ምዕመኑ እጆቹን በየኪሱ ውስጥ እየወሸቀ ተጣድፎ ወጣ። ምእመናኑ ሲወጡ ግን በሃሣብ ጭልጥ ብሎ፣ በሁለት ታጣቂዎች ይጠበቅ የነበረውን ወጣት ተመለከቱት።

ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው፣ ቆንሲሉ ፊት ስለተንበረከክሁ ነው። ያለጥርጥር ሁሉም ነገር ከዚሁ የሚመነጭ መሆኑ ግልፅ ነው። ጥፍቀቱ የጀመረው ያን ጊዜ ነው። ነፃነቴን አግልፈ የሰጠሁበትና የካድኩበት ጊዜ በትክክል ያን ጊዜ ነበር። አባት፣ የሴት ልጁን ፍላጐት ተቀብሎ፣ አይዞሽ ግፊበት ይላታል ብዬ ሳስብ ነበር። አንዲት ሴት አፈቀርኩ ብዬ ለራሴ እያረጋገጥኩ እያለሁ፣ የርሷን መኖርና ነፃነቶዋንም እየካድኩ እንቀማቀማለሁ። የአሊስንና የኔን ሕይወት፣ በዚያ ክብር በሌለው አባቷ እጅ ውስጥ ጥዬዋለሁ። ስለዚህም ተዋርጃለሁ። ተንበርክኬአለሁ።

«የሰም» አለ አንዱ ታጣቂ ወዲያውኑ

ጆን ባፕቲስት እንደማፈር ብሎ ይህን የመጨረሻ ቃል ጮክ ብሎ መናገሩን ተገነዘበ።

ወደ አቅሉ ከተመለሰ በኋላ «ኑ ጌቶቼ፣ ማንም ሰው በእግዚአብሔር ፊቃድ ፊት ሁልጊዜም ዝቅ ማለት አለበት» አላቸው።

ከዚያም ከክብር ተከታዮቹ ጋር እብስ አለ።

ይህ ሃሣቡ የሚያስከፋ ቢመስልም፣ በጆን ባፕቲስት ላይ ግን ከባድ ተፅዕኖ አሣደረበት። እዚህ ውስጥ ከተዘራች ሀዋስ የሚበቅልና መላውን መላኢ ተግባራቱን ሁሉ የሚቀይርበት አዲስ መንገድ፣ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ራሱን ያሣውቃል።

«ነፃነት ሊጠየቅ የሚችል ነገር ሳይሆን የሚወሰድ ነው» ሲል በዚያን ዕለት ምሽት ለሣንግራይ ነግሯቸዋል።

ከሚቀጥለው ዕለት ጀምሮ ይህን ውሣኔውን ሊተገብረው ተዘጋጀ።

ከሦስት ቀናት በፊት ተከናውኖ የነበረ ሁኔታ ዛሬ ታላቅ ሆነ። ጆን ባፕቲስት፣ የምርመራ ሰዓቱ ደርሰበት እያለ እንኳ ሕመምተኞችን መታገሥቱን ቀጥሏል። በርግጥም፣ ውጣ ሊያስብሉት የሚችሉት ሰበቦቹ እነዚህ ብቻ ናቸው። ዘበኞቹ፣ እርሱ ሕመምተኞቹን ለማከም እስከሚዘጋጅበት ቤት መግቢያ ድረስ ይከተሉትና ወደ ውስጥ ግን ሳይገቡ ይቀራሉ። በአንዳንድ ሕመሞች ላይ የሚነገረው ነገርና እርሱም ሕመሞቹን አጣርቶ እንደክብደታቸው አስቸኳይ ሊሆኑበት መሌ ራኦል እንደ ፀሐፊ ያገለገለዋል። በተለይ በዚያ ዕለት፣ ማለትም ምርመራው ከመለማቱ ከሦስት ቀናት በፊት፣ ጆን ባፕቲስት የሚሠራውን ሁሉ፣ ሙሉ በሙሉ ጥንቃቄና እርቆ አስተዋይነት ባለው መልክ እንዲያከናውን የሚጠይቅ አስተያየት ያለበት ወረቀት፣ በመሌ ራኦል በኩል ደረሰው። ሲናገርም የፊቱ ገፅታ አዲስ አመለካከት ነበረው።

ሐኪሙ ባለበት የጨለመ ቆሻሻ ጉጅ ውስጥ፣ አራት ሰዎች ይኖራሉ። ዕድሜዋን ለመለየት የምታስቸግር ሴት፣ ቡትት የለበሰችና ፀጉርዋ ያልተበጠረ፣ ከሁለት ሕፃናቶችዋና ከበሽተኛው ጋር በጥግ በኩል ተኩራምታ ትታያለች። የሰውዬው ስም ሞርቲየር ይባላል። በመጀመሪያ ላይ ኪጋሪ ጋር ተጋጭቶ እንደነበረ ለመናገር ሞክረ። ይሁንና በቡቱ ላይ የደረሰበት ሁለት ቁሰሉት በቀስት ምክንያት መሆኑን ጆን ባፕቲስት ሲነግረው፣ ሰውዬውም እውነቱን ገለፀ። የመጣውም በሚደክስ መግቢያ በኩል፣ ቀስተኞቹ ጠባቂዎች እያዩት በእህል ሜዳነት ላይ ተሣፍሮ ነው። ይሁን እንጂ ይህን ተደብቆ የነባ ሰው በሚመለከት፣ ጆን ባፕቲስት ለማንም ትንፍሽ እንደማይልበት አረጋገጠለት። ከዚያም በቁስሉ ላይ ሃይለኛ መድሃኒት አድርጉበት በፋሻ ጠቀለለለትና ሌላ ጠንካራ መድሃኒት ሰጠው። የሕመምተኛው አጥንቱ አልተነካም። የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር የቁሰሉን ማመርቀዝ በቁጥጥር ስር ማድረግ ነው። በሚቀጥለው ዕለት ሕመምተኛው ከመጠን በላይ ቢያልበውም ግን እንደገና መመገብ ጀመረ።

11

ጆን ባፕቲስት፣ ከሕዝብ መካከል ከተመረጡ ዳኞች ጋር ክርክር በገጠመበት በሁለተኛው ችሎት ላይ ታዳሚዎች የነበሩ ሰዎች በሙሉ በመጀመሪያ ላይ ከነበራቸው አመለካከት በቅፅበት የተሰየ ሃሣብ ያዙ። ከነዚህ ታዳሚዎች መካከል የተማሩ ናቸው የሚባሉት፣ ይህ ወደ አቢሲኒያ ተጉዟል የተባለው ሰው፣ ጥያቄዎቻቸውን ጥሩ አድርጉ አልመለሰውም በሚል በሙሉ ድምፅ ቢሰማሙም፣ ተንገፍ ያቀረባቸውን የመከራከሪያ ነጥቦች ብርታትና በዚህ ላይ እነርሱ ድክመቱን ሊያጋልጡበት የሚችለበት ማስረጃ እንደሌላቸው ግንዛቤ ነበራቸው። በሁለቱ ችሎቶች መካከል የነበሩትን ቀናት በመጠቀም፣ ራሣቸውን ሰፋ ባለ ጥናቶችና ትክክልም መጥፎም በሆኑ ጥያቄዎች ሲያዘጋጁ ሰነበቱ። ጆን ባፕቲስት በዘኩሉ በቅርቡ በደረሰበት የግል ቁርጠኛ ውሣኔው ተደሰቶ፣ ችሎቱ ወደሚሰማበት ቦታ በፈገግታ ደረሰ። ወደዚያ ያደረገው ጉዞም አስፈነደቀው። የታናሽና የታላቅ ልጆች የሆኑት ከፐካርዲ አካባቢ የመጡ ጠባቂዎቹ ጋር ያደረጋቸው ጭውውቶች ሁሉ አስደሣቾች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች በሥራ ላይ ተረኛ ሲሆኑ አብረው እንዲመደቡ በማለት ከቅርብ አለቃቸው ጋር ፕሮግራማቸውን አስተካክለዋል።

ችሎቱ ሲሰየም አስከዛሬ ድረስ አፋቸውን ከፍተው በማያቁት ቁስ ጥያቄ ተጀመረ። ሰውዬው ግዙፍ፣በጣም ሩቅ ማየት የማይችሉ በመሆናቸው የፃፉትን ወረቀት እንኳ ለማንበብ አፍንጫቸው ሥር አቅርበው የሚይዙና ክፍሉን ሲቃኙት አይኖቻቸውን ጭጋግ መሠል ውሃ የሚሞሳቸው ናቸው። ሰውዬው፣ አቢሲኒያውያን የሚመገቡትን የምግብ አይነት ማወቅ ስለፈለጉ ውስብስብነት ያላቸውን የቃላት ሣረጋት ትተው በጣም ቀላልና ተራ በሆነ መልክ ጠየቁት። ጆን ባፕቲስትም፣ ትህትና በተሞላበት ሳያስዘው እንደመጣለት መልስ ሰጡ። ከዚህ በኋላ እነዚህ ምሁራን ሊያገኙ በቻሏቸው መረጃዎች ሁሉ ላይ ምን ያህል በትጋት ሲሰሩ እንደሰነበቱ የሚያመለክቱ ዝርዝር ጥያቄዎችን ማቅረብ ጀመሩ። አዳራሹ ውስጥ የነበረው ተመልካችና ተከታታይ፣ ደንዝዘት እያንቀላፋ ነበር። ይህን የመሰለው ድባብ፣ በንጉሡ ነገስቱ ግዛት የመዋቅር ሕግጋት ላይ በቀረበው ጥያቄ ሳቢያ እንደገና ተነቃቃ።

«በዚያ ያለው ሕግ፣ልክ እዚህ እንዳለው የብኩርና ወራሽነት ደንብ ነው። የንጉሡ ወንድሞች፣ የአጎት ወይም የአክስት ልጆች ምናልባት አመፅ ሊመሩ የሚችሉ ስለሚሆኑ፣

አስቀድሞውኑ አቅመ ቢስ እንዲሆኑ ይደረጋል። በሌሎች ቦታዎች እንዲህ ዓይነቶቹን ሰዎች በወሲብ፣ በአልኮል መጠጦችና በአደንዛዥ ዕፆች ብላሾችና ሞራላቸው የወደቀ እንዲሆን አድርጉ ከመተው ይልቅ አቢሲኒያ ውስጥ በተራራ አምባ ላይ ያስሯቸዋል።» አለ ጆን ባፕቲስት

«እና ንጉሦች፣ ወንድሞቻቸውን በጠቀስካቸው የሞራል ውድቀት ውስጥ የሚጥሉበት ቦታ የት እንደሆነ ስለአግዚአብሔር ልትነግረን ትችላለህ?» ሲሉ ፕሬዝዳንቱ ጠየቁት።

የኦርሊየንሱን መስፍን በተዘዋዋሪ መንገድ መንካቱ በጣም ግልፅ ስለሆነ ምንም ተጨማሪ ማብራሪያ የማይጠይቅ ጥያቄ ነበረ። ጆን ባፕቲስት ግን ፈገግ አለ።

«እንደኔ . . . በአዜቲክች መካከል እንደሚሆን አስባለሁ»

እነዚህ ከሀዘብ መካከል የተመረጡ ዳኞች በመደነጋገር እርስ በርሳቸው ተያዩ። ይህን የመሰለ ፀያፍ መገፋፋት በሞራሽ ደስ የማይል ቢሆንም፣ለነርሱ ግን ያልጠበቁት ነገር ነበር። እንዲህ ያለው ሁኔታ ከቀጠለ፣ ሣይንስና የቋንቋ ጥናት እየተቀየሩ ያሉበትን እውነታ ትተው፣በመንግስት ላይ መነሣሣትን የሚጋብዝ ጠንካራ የክስ ማስረጃ ለመፈለግ ሊነሱ ሆነ። ስለዚህም ሁሉም ጥያቄዎች በፖሊስ ዳኝነት ሊቋሞ ስለሚችል ክትትል ያስፈልገዋል።

«ደስ የሚልህ ከሆነ ስለአቢሲኒያ ንጉሥ ጥቂት ተጨማሪ ጉዳዮችን ንገረን» አለው ተጉዝኛ ፈጣንታ ያለው ከምሁራኑ አንዱ

«ስለ ንጉሡ ልናገር የሚገባኝን ብዙውን ነገር ተናግሬአለሁ። ከዚህ የበለጠ የማስታውሰው በእውነቱ የለኝም»

«ልብ ብለህ አስብበት። እንዴት ነው የሚኖሩት። በዙሪያቸው የሚደነቅ ነገር ምን ምን ይኖራል?»

«ሁሉንም በዝርዝር እንደነገርኳችሁ አምናለሁ። ዙፋኑን፣ ቤተመንግስቱን . . . እ ግን አንድ ታሪክ አለ። አሁን ትዝ አለኝ። በቤተመንግስቱ ውስጥ የንጉሡ ክፍል መስኮቶች በሁለት አቅጣጫ ወደ ግቢው ያሣያሉ። በአንደኛው ግቢ አንበሶች አሉበት»

«ይህንንማ ነግረኽናል»

«አም አውቃለሁ። ያልተገነዘባችሁት ከሁለተኛው ግቢ የማያቋርጥ ልቅሶ መሰማቱን ነው። ድምፁ በጭራሽ አይቋረጥም። አልፎ አልፎ፣ እንዲያውም ጮሌ ስለሚል፣ ልቅሶና ዋይታ ለይታችሁ ትሰማላችሁ። ከዕለታት አንድ ቀን ይህን ድምፅ የሚያሰሙት በጦርነት ላይ

የተማረኩ እስረኞች ይሆኑ ወይ ብዬ ጠየቅሁ። የተነገረኝ መልስ ግን በተገላቢጦሽ፣ እነዚህ አሪታቸውን የሚያሰሙት በጥሩ ሁኔታ የሚከፈላቸውና ንጉሡ የሚወዷቸው አሽከሮች ናቸው ተባልኩ። እነዚህ ሰዎች የሚያሰሟቸው ድምፆች አንድ ንጉሰ ነገስት ሁልጊዜም ሊሰማው ይገባዋል ብለው አቢሲኒያውያን የሚወዱትን የሙዚቃ ቅላፄ መያዝ ይኖርበታል። ያ ድምፅ፣ሕዝቡ በስቃይ ውስጥ ስለሆነ ንጉሡን ድረስልን፣ እርዳን እያሉ የሚጠሩበት ድምፅ ነው»

«አሺ፣ ታዲያ ከዚህ ምን ነገር ተገነዘብክ?» አሉት ፕሬዝዳንቱ

«እናንተ ለራሣችሁ ግንዛቤ ውሰዱ። ንጉሶች፣የሕዝባቸው መከራና ስቃይ ለጆሮአቸው እንዲደርስ መመከር አለባቸው ወይም የሰባቸውም የማስቱ ጉዳይ የኔ ተግባር አይደለም» አለ ጆን ባፕቲስት።

«አሃ!» አሉ ፕሬዝዳንቱ፣ ባልደረባዎቻቸውን በደስታ እያማተሩ። «ፀሐፊው እነዚህን ነገሮች በሚገባ ከትቧቸዋል? ትክክል!»

ሰዎች ሊሰግዱለትና ጭራቸውንም ሊቆሰሰት የሚገባቸውን ነገር የሚክድ ኩሩ ሰውን የማየት ያህል የክብር ባለሟሎችን ልብ የሚያሞቅ ነገር የለም።

ከዚህ በኋላ ሽንፈት በቅድሚያ የሚታወቅ ውጤት እንደሆነ በማመን፣ ሥልጣን ርህራሄ እንደሚያጣና የነርሱም ፍርሃት ትርጉም ባለው ምክንያት ሣቢያ መሆኑን ይመለከታሉ።

«አ! አወቃለሁ» አለ ጆን ባፕቲስት ወደ ችሎቱ የሊደት መንፈስ እየተመለሰ። «በንጉሡ ጉዳይ ላይ ከፍ ያለ ስሜት ስላላችሁ ሌላም ነገር ልጨምርላችሁ። በምሽት፣ ከንጉሡ ታላላቅ ሰዎች አንዱ ከመኝታ ክፍሉ በር ባሻገር በሚገኝ መስክ ላይ ይተኛል። ይህ ሰው በማግስቱ ጧት መሬቱን እየገረፈ ንጉሡን ከእንቅልፋቸው ይቀሰቅሣቸዋል? ታዲያ ጅራፉ ለምን ያስፈልጋል? ጅራፉማ የሚያስፈልገበት ምክንያት አለው። ንጉሡ አጠቃላይ ጓዛቸውን ይዘው በየዕለቱ በየጥሻው እየተጓዙ ስለሚሰፍሩ የዱር አውሬዎች፣ ሥጋ በል አውሬዎች፣ ብዙ ጊዜ ጅቦች በምሽት ተሸልለው ወደ ድንኳኖች ይደርሣሉ። አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም እስከ ንጉሡ ድንኳን መግቢያ ይቀርባሉ። ስለዚህ ጅራፉን ማጮህ እንዲህ ያሉ አስፈሪ አራዊት በምሽት ወደርሣቸው አጠገብ እንዳይደርሱ ለማባረር ሲባል ነው። ንጉሡ፣ ቤተመንግስት መስርተውና ግንቦችን አንፀው በዚያው መኖርና ማደር ከጀመሩም በኋላ፣አሁንም በደን ውስጥ፣ዙሪያቸውን በአደገኛ አራዊት ተከብበው የሚኖሩ ይመስል ልምዱን ቀጥለውበት ይታያሉ። አውነቱን

ለመናገር፣ ከቡራን እንዲህ ያለው ድርጊት ጥሩ ምሣሌ ሊሆን ስለሚችል በሌሎች ቦታዎችስ ቢኮረጅ ድንቅ አይመስላችሁም?»

«ጅቦችን ከቤተመንግስት ለማባረር ማለትህ ነው! ለምሣሌ ባለሟሎችን መግረፍ ማለትህ ነው? ያውም ንጉሡ ባሉበት ቦታ፣ ንብቶኝ ይሆን ያልከው?» ሲሉ ፕሬዝዳንቱ ጠየቁት።

«አዎን ልክ ነው። ፀሐፊ ይህንም ሃሣብ በፅሁፍ አስፍርልን እባክህ። ታሪኮችህ በጣም ድንቅ ናቸው። በነዚህ እፀብ ድንቅ ጉዳዮች ቀደም ብለህ እንድንደሰት አስማድረግህ ያሣዝናል»

ዳኞቹ አሁን ተዝናንተው በይፋ ፈገግ ይላሉ። አድማጮ ሕዝብ ፀጥ ብሏል።

«ምናልባት ሌሎች ተጨማሪ ነገሮችንም ትነግረን ይሆን?» አሉት ፕሬዝዳንቱ በመጓጓት።

«አንድ የመጨረሻ ልንገራችሁ፣ በቆይታዬ ጊዜ በብዙ ግድያ ቦታዎች አገኝ ነበር። አሁን ልገልፅላችሁ የምወድደው አንድ የቅጣት ዓይነትን ነው። አንዱን አስረኛ አመጡትና ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ድረስ በነጭ ጨርቅ ጠቀለሉት። ከዚያ በኋላ በትኩስ የፈላ የሰም ፈሣሽ ውስጥ ነከሩት። ሰሙ ከመድረቁ፣ ሰውዬው በተጠቀለለበት ጨርቅ ተመጠጠና በሕይወት ያለ ትልቅ ሟፍ ወይም ሻማ አደረጉት። ከዚያ በኋላ ልታደርጉት የምትችሉትን ያንን ነገር መሰክሰ ብቻ ነው። እንደችቦ ይንቀለቀላል። የአማቱ ነበልባል ድምፅ እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ የሰውዬው አሪታ አይሰማም» አለ ፖንሴ ፈገግ ብሎ።

ዳኞቹ ፖንሴን በፍርሃት ተመለከቱት። የችሎት ፀሃፊው ብዕር በአየር ላይ ተንጠልጥሎ ቀረ።

«ሁሉም ነገር ሊያበቃ፣ ጥቁር ቅርፅ ያለው ያረረ አስከሬን ይቀራል። ልባም ሆኖ ነገሩን መገንዘብ የሚገባው እዚህ ላይ ነው። አስከሬኑን ወደዚህና ወደዚያ አያላሰጣችሁ በጥንቃቄ ብትመለከቱት፣ አሁንም ነጭ ሆኖ ባለው ጨርቅ ስር የአስረኛው ያልፈሰሰ አይኖች ብዙውን ጊዜ በእንባዎቹ ተጠበቀው ታያላችሁ።»

ጀን ባፕቲስት ከመቀመጫው ላይ ብድግ አለ።

«የሚበቃችሁን ያህል ሰምታችኋል። በአሁኑ ሰዓት ከዚህ የበለጠ ልነግራችሁ የምችለው ይኖራል ብዬ አላስብም። ተስማሚ ነው በምትሉት መልክ ፍረዱኝ። በርግጥ አንድ ኑዛዜ አለኝ። ለኔም፣ አካሌን አጥፍቶ፣ በሚገባ ያገለገሉኝን ሁሉንም ዓይናቸን ሊያተርፍልኝ

የሚችለውን ዓይነት ቅጣት እንዳገኝ ፍረዱበኝ። ስለጉዞዬ የገለፅኳቸውን ታሪኮች ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ። ደህና ሁኑ ጌቶቼ» አለ።

ፀጥ ያለውና በረዶ የሆነው አየር፣ በጀን ባፕቲስት የጫማ ርምጃ ድምፅ ተሞላ። ሁለቱ የፒካርድ ሰዎችም ተከተሉት። ክፍሉን አቋርጠው ወደታላቁ በር የሚያደርሰውን የእንጨት ደረጃ ወጥተው እብስ አሉ።

«ወዳጄ ሆይ፣ የሰራኸው ስህተት ነበር። ሁሉንም ነገር በመልክ በመልኩ ለማድረግ እንችል ነበር። ከሁሉ በፊት የቻርትሬሱ መስፍን፣ አንተ ባሰባሰብካቸው ጉዳዮች ላይ ፍፁም ተመስጠው ነበር። በነዚህ ጉዳዮች ላይ ተመስርተው ያዘጋጇቸውን ድንቅ ጉዳዮች ሊያሣዩህ በመፈለግ፣ ሊያዩህም ወስነው ነበር። ይኸውልህ ይህንን አስር ሺህ ሊብሬ በመላክ ድርሰትህን ለማሣተም ይችሉ እንደሆነ ጠይቀዋል። አየህ፣ ዳኞችን አጉል መገፋፋት እንዴት ስህተት እንደሆነስ ይታይሃል» አሉት ሣንግራይ

አማካሪው ከጀን ባፕቲስት ፊት ለፊት ቆመው ነበር። እንደተለመደው አዛውንቱ ምንም ዓይነት ሰው ሰራሽ ፀጉር አላጠለቁም። ገመሞው ጭንቅላታቸው፣ አጭር ሆኖ ባልተበጠረው ሽበታቸው የተሸበበ ነው። ክንዳቸውን ዘርግተው ሃኪሙን ጠበቅ አድርገው ያዙት።

«አ! አዎን ልክም ነህ፣ ልክም አይደለህም፣ እኔም ይህን በሚገባ አውቃለሁ። በሚገባ የማውቅልህ መሆኔን ስለማለፅ ይህንንም በመስፍኑ ወርቅ ላይ ጨምርበት፣ ከኔ የተሰጠህ ነው። ልለምንህ»

ትልቅ የሃር ከረጢት በጀን ባፕቲስት እጅ ውስጥ አስቀመጡ

«እናም ከእንግዲህ ጊዜ አታጥፋ። አንዳች ልዩ ስሜት ልትፈጥር ፈልገሃል። በዚህ ላይ እንዳትሞክረው ልመክርህ ባስብም፣ እዚህ ሁሉም ነገር የሚከናወነው በጥድፊያ ነው። ላ ሬይኒ ከዚህ በኋላ ዋናው ኃላፊ አይደለም። ከዚህ በኋላ እጅግ ሃይለኛው የፖሊሱ ክፍል ነው። ሌላው ቀርቶ፣ ዳኞቹ ውሣኔ ከማሣለፋቸው በፊት ንጉሡ ሁሉንም ነገር ያውቃሉ»

«ዛሬ ማታ የራሴን ትያትር መጫወት አስቤአለሁ።»

«ድንቅ፣ እንግዲያውስ እኔ ምን ልረዳህ እንደምችል ንገረኝ»

ጆን ባፕቲስት ነገራቸው።

«ያገር ያለህ!» አሉ አማካሪው። «የቻርትሬሱ መስፍን ካንተ ጋር መገናኘት ባለመቻላቸው የሚያዕናናቸውም ነገር አይኖርም። ሊጠይቁህ የሚፈልጉዋቸው ብዙ ነገሮች ነበሩዋቸው»

ከዚህ በኋላ፣ ሣንግራይ ዐይኖቻቸው በእንባ ተሞልተው፣ ወጣቱን ጓደኞቸውን አቀፉት።

«እኔም ልጄን ላጣው ነው» አሉ

«አያጡት አይደለም፣ አያዳኑት እንጂ»

«ይህም አንድ መፅናኛ ነው። ይሁን እንጂ ምንም እንኳ አንተ ከዳኞቹ ብታመልጥም፣በኔ ላይ የሚጣለው ቅጣት ግን ከባድ እንደሆነም እመን»

ይህ የስንብት ቃል ወጣቱን ሰው በጥልቀት ተሰማው። ሙሴ ራኦል፣ ከአንድ ባላገር ጋር መጣና ሁሉቱ ሰዎች ለመጨረሻ ጊዜ በሁሉቱ ሃሣቦች ላይ የመወያየት መብታቸውን እንዲጠቀሙ በማሰብ አንድ ጠርሙስ ባርጋንዲ ለመግዛት ወጣ።

በሰባት ሰዓት ላይ፣ ጆን ባፕቲስት ወደ መኝታ ክፍሉ ሄደ። ሁለቱ ፒካርዳውያን ፖሊሶች፣ በአክብሮት ከራሣቸው ዝቅ አሉለት። ከግማሽ ሰዓት በኋላ በቤቱ ውስጥ የነበረው ሁሉ በእንቅልፍ ውስጥ ወደቀ።

ሣንግራይ የሚኖሩበት የከተማው ቤት ጓሮ፣ ወደ አንድ አነስተኛ የተነጠፈ ግቢ ያመራል። በዚህ ግቢ ውስጥ በያንስ ስድስት ጫማ ያህል ርዝመት ባለው አጥር የተከበቡ የውሃ ጉድጓድና ሁለት የከብት ጋጣዎች አሉ። የጆን ባፕቲስት የመኝታ ክፍል፣በተከፋፈለ የመስኮት መስተዋት ወደዚህ ወደቤቱ ጀርባ ያሣያል። የእድል ይሁን የአጋጣሚ እንደሚሆን ሁሉ፣የጋጣው ጣሪያ ውቅር ሰፊ አሸንዳ ያለው ሆኖ፣ ከዚህ መስኮት ስር ያልፋል። ጆን ባፕቲስት የሚያሞቁ ልብሶቹን ለብሶ፣ በወፍራም ካባርት ተጀቡኖ፣ በዚህ መስኮት በኩል በመውጣት የጋጣው ጣሪያ ላይ ሲረግጥ፣ የቅዱስ ኢዮስታች ቤተክርስቲያን ከምሽቱ አራት ሰዓት መሆኑን የሚያመለክተውን ደወል አሰማ። ትከሻው ላይ ጆንያ ተሸክሟል። በጣም በጥንቃቄ በጥቁሩ ድንጋይ ጠርዝ ተራምዶ ጣሪያው ላይ ወጣ። ከዚያም በጉረቤቱ ግቢ ውስጥ ባለ የደቃቅ ጥራጊ ክምር ላይ ድምፅ ሳያሰማ ወረደ።

ጊዜው ጨለማና እጅግ ብርዳም ነበር። ከዋክብት በጥቁሩ የሰማይ በረዶ ውስጥ ያበራሉ። ጆን ባፕቲስት፣ ጥንቃቄ በተሞላው ሁኔታ አንድ ወይም ሁለት ርምጃ እንደተራመደ አንድ እጅ አፈፍ አደረገው።

«ሞርቲየር ነህ?» ሲል ደንግጦ ጠየቀው

«ሽሽ፣ ዝም ብለህ ተከተለኝ»

ኮንትሮባንዲስቱ፣ ሙሉ በሙሉ ባይድንም ትኩሣት የሚባል ነገር ጨርሶ የለበትም። ቁስሉም ፀድቶ በሚገባ ከተበጀለት የመከላከያ ፋሻ ውስጥ እየዳነ ነው። ስለዚህ ሰው፣ ይህ የመጀመሪያው ቁስሉ አልነበረም። አሁንም ድረስ የሚያነክስ ቢሆንም፣ ወደዚያ በሞኝነት ወደሚያከናውነው ተግባሩ መመለሱ አይቀርም። ፖሪስን ደግሞ ከርሱ ቡተሻለ የሚያውቃትም የለም። ከመተማመናቸው የተነሣ፣ ፖንሴ ሚስጥሩን ነገረው። ሞርቲየር በበኩሉ፣ይህን ሕይወቱን ሳተረፈለት ሰው ማንኛውንም ተግባር በመፈፀም ውለታ ለመክፈል በጣም ደስተኛ ነበር።

ጉዟቸውን በየጠመዝማዛው መንገድና አደባባይ እያደረጉ ሄዱ። የክረምቱ ነፋስ በመንገድ ላይ የነበሩትን መብራቶች በሙሉ አጥፍቷቸዋል። ነገር ግን ሞርቲየር፣ውሾች ያሉበትን ቦታና እንደመተላለፊያ ሊጠቀመባቸው የሚችሏቸውን የአደባባይ በሮች ጠንቅቆ ያውቃቸዋል። የሌሊት ተረኛ ጠባቂዎች የሚሄዱባቸውን መንገዶች ስለሚያውቅ ከወሬ አቀባዮች በስተቀር የሚፈራው አንዳችም ነገር የለውም። እርሱ አጥብቆ እንደሚያምነው፣ ቀደም ሲል ላጋጠመው አደጋ ተጠያቂዎቹ እነዚሁ ወሬ አቀባዮች ናቸው። አንድ ባህረኛ ከፊት ለፊቱ የሚኖረውን ማዕበልና ሞገድ ለመለካት ባህሩን እንደሚመለከት ሁሉ ሞርቲየርም መንገዱን አሻግሮ ተመለከተው። በግማሽ ሰዓት ውስጥ የቴምፕልን አውራ ጐዳና ደረሱ። ይህ ጐዳና በየምሰሶው ላይ በተንጠለጠሉ ትላልቅ የመዳብ መብራቶች ይንቦገቦጋል።

«ተጠንቀቅ፣ ከሃምሣ ያርድ ርቀት ላይ የዘብ ስንተሪያ አለ። የጨለማውን ጠርዝ ይዘህ ተጓዝ። አንዳች የሆነ እሪታ ብታዳምጥ በሩጫ ማምለጥ ይኖርብሃል።» ሲል ሞርቲየር ሹክ አለው።

ሞርቲየር፣አስተድሞ በሚገባ መብራት ባለው ሰፊ ጐዳና ላይ እያነከሰ ተሻገረ። ወዲያውኑ በጥላዎች ውስጥ ገብቶ እንደተሰወረ፣ ጆን ባፕቲስትም እንዲሁ መንገዱን በፍጥነት ዘሎ በማቋረጥ ዱካው ሳይሰማ ደረሰበት። ራቅ ባለው ጐን ረጃጅም ዛፎችና ጥቁት ቤቶች

ያሉበት የመናፈሻ ስፍራ አለ። ከሆነ አጠር ያለ አጥር በስተጀርባ ይጮሁ የነበሩትን የጥበቃ ተረኞችን ውሾች፣ በጥንቃቄ አለፏቸው። ወዲያውኑ ይህን አጥር አልፈው ወደ ቻሮኔ በመውጣት ባዶ፣ ነፋና ንላጣ በሆነው አካባቢ ውስጥ ገቡ። ጉዟቸውን በረባዳው የአግር መንገድ ላይ በማድረግ በደን ውስጥ በማቆራረጥ ግራና ቀኟን የደረቁ ቅጠሎች የተንዘራዘሩባትን ትንሽ ምንጭ ዘልሰው አብስ አሱ።

እስከአሁን ድረስ ጨረቃዋ ስላልወጣች ከሰማይ የሚመጣ ምንም ብርሃን አልነበረም። በአንድ ስፊ መንገድ ውስጥ ገብተው ወደ አንድ አጥር ዘንድ ሲቃረቡ፣ በአንቅልፍ ላይ ያለች ላም አልፎ አልፎ ስትጮህ ይሰማሉ። የቻሮኔን መንደር ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው ወደ ቀኝ አጥፍ አሱ። አርጥበት አዘል ከሆነው አየርና ከሚንሸሸሸው የቅጠላቅጠል ድምፅ በመነሣት በደን ውስጥ እየተንዙ መሆናቸውን፣ ጆን ባፕቲስት አወቀ። አንድ መስክ ላይ ፈረስ ሲያናፋ ተሰማቸው። ሞርቲየር ምልክት ሲያሰማ በጭለማው ውስጥ ያለ ሌላ ሰው በፉጨት መልስ ሰጠው።

«አንተ ወስላታ፣ አንተነህ እንዴ?»

«ሌላ ማን ይሆናል የኔ ወሮበላ?»

የሰውዬው፣ ስልል ያለችና ቀጭን፣የምትንቀጠቀጥ፣ምናልባትም ሽማግሌ ሣይሆን እንደማይቀር የምታጋልጠው ድምፁ፣ በቅርብ ካለው ጨለማ ውስጥ ትሰማለች።

«አውሬውንስ አምጥተኸዋል?»

«አውሬስ አንተው ነህ፣ ጆሮ የለህም እንዴ? አጅህን ወደዚህ አቅርብ። ይህ የምትዳስሰው ቆት ይመስልሃል እንዴ?»

«አንተ ቀልደኛ ሽማግሌ። ልጓሙን አቀበለኝ። ዶክተር፣ ይኸውልህ። ፈረሱ ተጭኖልሃል። መሄድ ትችላለህ።»

ጆን ባፕቲስት፣ የቆዳ ርካቡን በዳሰሳ ካስተካከለው በኋላ ኮርቻው ላይ ዘልሎ ወጣ። ሞርቲየር፣ ዳብ አግኝቶ ፈረሱ ላይ ሊወጣ እንዲችል በማለት መንገዱን ይዞ ወደፊት ሄድ አለ። ኮንትሮባንዲስቱ፣ ምንም ዓይነት ገንዘብ ላለመቀበል አሻፈረኝ ቢልም፣ ጆን ባፕቲስት የሙጢኝ ሳይለው፣ ነገር ግን ሰውዬው ሳያስተውል አንድ ገንዘብ ያለበት ቦርሳ በኩቱ ውስጥ በዘግታ ጣል አደረገለት።

ድምፅ ሳይሰዋወጡ ተጨባበጡ። ከዚያም ከልብ በመነጨ ስሜት ተመሰጋገኑ። ፖንሴ፣ የፈረሱን ጉን በእርካቡ ኮረኮረውና መንገዱ ውስጥ ገባ። በመጀመሪያው መስቀልኛ መንገድ ላይ ሲደርስ፣ ከቀደሞው ውሣኔው ፈፅሞ ላለማፈንገጥ ሲል ወደ ደቡብ ታጠፈ። ገና ጉዞውን እንደጀመረ እጅግ ጨለማ ስለነበረ ግልቢያውን ቀዝቀዝ ሊያደርግ ዳድቶት ነበር። በኋላ ግን ብርማዋ ጨረቃ በሰማይ ላይ ብቅ ስትል፣ ከፊት ለፊቱ ያለውን የመሬት አቀማመጥ ልታሣየው በቂ ሃይል ነበራት። ፈረሱ፣ረጋ ብሎ ደስ የሚያሰኝ ግልቢያ ያደርጋል። ጆን ባፕቲስት፣ ከዚህ በፊት እንዲህ ለአስር የተቃረበበት ጊዜ ፈፅሞ አልነበረውም። አሁን ግን የነገስታት ሁሉ ሃያል የሆኑትን ንጉሥ አሻፈረኝ ስላለ ይፈልጉታል፣ ያሣድዱታል። በእንዛሩ አርሱ ደግሞ በዛፍ ቅርንጫፍ ቢገረፍና ዓይኖቹም በእንባ ጅረት ቢሞሉም፣ በዚህ ቀዝቃዛ ምሽት የተሰማውን ነፃነትና በራስ መተማመን ስሜት መቼውንም ቢሆን ተሰምቶት አያውቅም ነበር።

5

የቁጥቋጦው ሠደድ

1

አሊስን ከምንም ነገር በላይ የሚያሳስባት፣ የርስዋ የራስዋ ውስጣዊ ንፅህና፣ የስሜቶችዋ መልካም ስምምነትና ሙሉ በሙሉና በታማኝነት ለማፍቀር የመቻልዋ ጉዳይ ነበር። እነዚህን ግላዊ ስጦታዎችዋን መጠበቅ በራስዋ ፈቃድ ላይ ብቻ የተወሰኑ ናቸው። አንዳች አጋጣሚ በሰውነቷ ላይ ቢደርስ እንደማይበላሽባት ስታስብ በውስጧ ጤነኛ ትምክህት ተሰማት። በልቧም ውስጥ እውነተኛ ልዝገረድነትዋ ሃያልና ጠንካራ ሆኖ ቆየ።

ሕብረተሰብ፣ የራሱን ውጣት ትውልድ ነፃነት በመፍራት፣የሚያከብረውን ቁሣዊ ድንግልና ጠብቃ በማቆየት ራስዋን ባሪያ የምታደርግበት አስፈላጊነት የለም። በአንፃሩ፣ እስከዛሬ ድረስ ጠብቀው ያቆየችውን ቅድስናዋን በረባሽየሞቹ የመሰንከያ ቀሚሶችና ቀፈትን መሰብሰቢያ ባሰብረት ቀበቶ ሙታንታዎችን መልበስ፣ በእንግዳ ሰዎች ፊት አይኖችዋን መስበርና ሲ,መሽ እንደደነገጠች የምትታደን አንሰላ እንድትሮጥ የሚያደርጋት ያንን አሰቂኝ ነገር ለመከላከል ነው፣ ስትል በስጨት ብላ አሰበች።

አሁን ግን እግርጠኛነትን፣ ብርታትንና ክህሎትን፣ ጊዛ ውስጥ ተምራለች። ስለዚህም ይህንን የሚያስራትን ገመድ ወዲያ ጥላ፣ራስዋን ነፃ ማድረግ ይኖርባታል። በዚህ ረገድ፣ ጆን ባፕቲስት ያለ አንዳች ማወላወል መንገዱን እንዲቀድድላት ትመርጥ ነበር። ይሁንና አሁን የሚቻል አይደለም። ከዚህ ይልቅ በተቃራኒው፣ አርሱን ላይዘገይ ነፃ ሊያደርገው የሚችለውን ነገር ለማከናወን ያለ የሌለ ሃይሏንና ጉልበትዋን ሁሉ ለማዋል እንድትችል፣ ያገኘችውን ማንኛውንም ወንድ ልትጠቀም ፈለገች። ፈረሰኛው ሮውሌ፣ እንደተማረከችለትና የግሉም ሊያደርጋት እንደሚችል አምኗል። አርሷ እራስዋ የቋመጠችለትን ጉዳይም፣ ለመፈፀም እያዘነ ፈቀደ። ምንም እንኳ የረዥም ጊዜ ልምድ ቢኖረውም ይህ ቅንዝረኛ ፈራ። ይህ የሆነው ምናልባት አብሯት ባሳለፈው ምሽት፣ የአሊስ ቅዝቅዝ ማለትና የውሣኔዋ ሁኔታ የፈጠረበት ይሆናል። ለማንኛውም የዚህን ግጥሚያ አስፈሪ ውጤት ለማሳካት ፈረሠኛው ነፃ ሆኖ ሊያስብ ቆየ።

በመጀመሪያ ደረጃ ተፈጥሮአዊ ሁለንተናዋን ከወሲባዊ መስህብ፣ ከትልቅነት፣ ከጋለ ስሜትና ከነፃነት ጋር አደበላልቃ ማከናወን በቻለችው በዚህች ውብና ሃፍረተቢስ ልጃገረድ

ፍቅር ተማረከ። ሁሉንም ነገር ቀጥሎ ደግሞ፣ድል አድራጊነቱ፣ የሆኑ መብቶች የሰጡት መስሎት አመነ። ለምሣሌ ከርስዋ ጋር እንዳሻው ለመዳራት መብት እንዳለው አመነ። ይሁን እንጂ ቆየት ብሎ በርስዋ የምህረት ፊቃድ ሥር መሆኑን ተገነዘበ። በሁለተኛው ዕለት ምሽት አግፍራ መለሰችው። መፍራት የጀመረውም ያን ጊዜ ነበር። ይህችን ደፋር ሴት እንዲህ ያነቃቃት ምን እንደነበረ ሊገባው አልቻለም። ራሱን ጠላ። ልጅቱም ምን ሊከተል እንደሚችል ሳታስብ የምትንቀሣቀስ ችኩል፣ በቀላሉ የምትረካ፣ ያልተገራ ተግባር የምታከናውን፣ ሌላው ቀርቶ ግንኙነታቸውን ይፋ የምታደርግ አድርጉ ንመታት። ለደስታ የነበረውን ፍላጉት ከተዝዚው መስመር እንዲወጣ እንዳደረገውም ተረዳ። ምንም እንኳ የከፋ ነገር ይመጣል ብሎ ቢፈራም፣ አሊስ ያሳደረችበት ስሜት ጠንካራ ስለነበረ ፀፀት አልገባውም። በሚቀጥሉት ምሽቶችም እሺ እንድትሰው ለመናት። እርስዋም ቅዝቅዝ ባለው ስሜትዋ እምቢታዋን ገለፀችለት። እሺ እንድትሰው እየተለማመጣት፣ በፍላጉት ሰክሮ፣ በመጀመሪያው ግንኙ ነታቸው ላይ አጭር ጊዜ የፈቀደችለትን ዳግመኛ፣ለዘለዓለም ላይቀምሰውና እስከ ዘለዓለም እንደቋመጠ መቅሬቱን እያሰበ በረንዳው ደረጃ ላይ ብቻውን ቀረ።

ሁሉንም ታሪክ ለፍራንቾይዝ እንዳለ ተናዘዘችላት። በችሎታዋ የፅዳት ሠራተኛ የሆነችውም ሴት፣ ያጋጠማትን ነገር ሁሉ ደምስሳ አጠፋችላት። ስለዚህ ጉዳይ ቀደም ተደርጉ ተነግሯት ቢሆን ኖሮ፣ ፍሪንቾይዝ ምናልባት ጭራሽም እንዳትሞክረው በማለት ታግዳት ነበር። አሁን ግን ለማልቀስና ለማንባት እጅግ በጣም የዘገየ ነው። አሊስ ከዚህ በኋላ ዕቅዷን ለፍራንቾይዝ በዝርዝር አስረዳቸች። ፍራንቾይዝም፣ አንድ ሺህ አንድ መቃወሚያ ነጥቦችን አነሣችባት። ምክንያቱም ወጣቷ ሴት ሊያጋጥማትና ልትጋፈጣቸው የምትችላቸው ስፍር ቁጥር የሌላቸው መሰናክሎች በመንገዷ ላይ እንዳሉ ነግራታለች። በመጨረሻ ግን እያጉመተመቱቸም ቢሆን፣ አሊስ የነፃነትዋን ጉዳና ለመምረጥ የነበራትን ጥንካሬና ትጋት፣ሠራተኛዋ አደነቀች። በዝርክሩ ከተሸነፈችና ሣጣቡንም ከተቀበለች በኋላ ወጣቷን ሴት በሁሉም መንገድ ለመርዳት ቃል ገባችላት።

በአራተኛው ቀን ማታ፣ ዴ ሮውሌ፣ የማዳሞዜል ዴ ማይሌን በር እንደ ድመት ወይም እንደ ውሻ ሊፀጥጥ መጣ። ሊከተለው የሚችለውን አስፈሪ ቅሌት እያሰበ፣ በሩን ቢገፋው መሸጉሪያው ስላልተቆለፈ፣ ዴ ሮውሌ በጥፊ የተመታ ያህል ደነዘዘ። በሩን ከፍቶ ወደ ውስጥ ዘለቀ። አሊስ፣ ፊት ሰፊቱ ተገተረች። የሚጠለቅ ረዥም ሽሚዝ፣ ከጥጥ የተሠራ ከንልበት እስከ ዳሌ የሚደርስ ሱሪ፣ የበት ጫማዎች፣ ጊዛ ውስጥ ፊረስ ስትለማመድ ትጠቀምበት

የነበረውን ልብስ ለብሣለች። እጅግ የተቆጣች ትመስል ስለነበረ ፈረሰኛው እጅግ ቢቆምጥም ሊስማት ግን ወኔ አልነበረውም።

«በሩን ልትቆልፈው ብትችል እባክህ?» አለችው

ታዘዘት። ብዙ ዝዜ ተቀምጣ ምኞቷንና ሕልሟን ወደምታሰላስልበት፣ ከቀጭኑ የጣውላ አግዳሚ ፊት ለፊት ያለውን ወንበር አመለከተችው። ወንበሩ እንክትክት የሚል ስለሚመስል፣ ዴ ሮውሌ በጥንቃቄ ተቀመጠበት።

«ጌታዬ፣ በየምሽቱ ወደ ክፍሌ በመምጣት የምታገኘው ምንም ነገር የለም። ዳግመኛ አልከፍትልህም። ደግሞም አንድ ሰው ምናልባት ሊያይህ ይችላል» አለችው

«ግን ምን እጠፋሁ?» ሲል በጥሞና ጠየቃት። «ምን አድርጌ አስቀየምኩሽ?»

«ጉዳዩ ካንተ ጋር አይደለም። ላረጋግጥልህ የምችለው፣ አንተ የተሰጠህን ተግባር በብቃት መግለፅ ችለሃል።»

«በብቃት? ተግባር! ወይኔ፣ ምነው ትቀልጅብኛለሽ» አለ፣ ዴ ሮውሌ በቀና መንፈስ፣ እዝን ብሎ

«በጭራሽ። ጥያቄው ነገሮችን እንዴት ወይም እንደነበሩ አድርጉ የማየት ጉዳይ ነው። አንተ ልታከናውነው የሚገባህ ሥራ አለህ። ይህንን ደግሞ በቅልጥፍና አከናውነኸዋል። ለዚህም አመሰግንሃለሁ።»

«ማዳሞዜል፣ አያዋረድሽኝ ነው»

ሕይወቱን ሙሉ ውርደት የሚባለው ነገር ጫፉን ደርሶበት የማያውቀው ዴ ሮውሌ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ሊተኛት ባተዳት ሴት ሃይል ስር ሙሉ በሙሉ መውደቁን አወቀ። የተሻለና መልካም ከሆነ፣ ከእግሯ ስር ወድቆ ሊለምናት ተዘጋጅቶ ነበር። ነገር ግን ራሱን ከዚህ ባለፈ ሳለማሪስስ ሞከረ። የመጀነን ትዕቢቷ የሚያመለክተው፣ እርሷም ከርሱ ትንሽ ክብር መፈለንን ነው።

«ከፈለግህ አመዛዝነው። ያንተና የኔ ፍላጉቶች ፍፁም የተለያዩ ናቸው። አንተ ነውርን ስትሸሽ፣ እኔ እፈልገዋለሁ»

ስሙን ልታጠፋበት በርግጠኝነት የተዘጋጀች መስሎት፣ ዴ ሮውሌ በጣም ደነገጠ።

«ይሁን እንጂ አትስጋ። እኔ የራሴን ስምና ክብር ለማጉደፍ የምጥረውን ያህል፣ ያንተን የተከበረ ስምና ዝና ለመጠበቅ በቁርጠኛነት ወስኛለሁ። ስለዚህ ስጋት አይግባህ»

ሁኔታው ሁሉ፣ ዱ ሮውሌን አልገባህ አለው። ሊገባው የቻለው ነገር ቢኖር፣ ይህች ሴት፣ በሆነ ዘዴ ተስገብግባ ከተመገበችው በኋላ የወንድ ስሜቱ መዋፋቱን ነው።

«እባክሽ ግልፅ ሆነሽ ንገሪኝ» አላት በደከመ ድምፅ

«እሺ። ተግባብተን ልንዘልቅ እንደምንችል አስባለሁ። አንተም ባሰፈው ጊዜ እንደጠየቅሁህ ከፍተኛ ፍላጐት እንዳለህ ሆነህ ትንቀሳቀሳለህ። በዚህ ሁኔታ፣ አባቴ፣ እጅን ላንት በጋብቻ እንዲሰጥህ እንዲፈቅድ ነገ ትጠይቀዋለህ።»

ዱ ሮውሌ፣ ወዲያውኑ ይቆጣጠረው እንጂ፣ ከተቀመጠበት ላይ በደስታ አንርቶ ብድግ አለ።

«ማዳሞዜል፣ ከዚህ የበለጠ ቅንነት እንዳገኝ አምላኬን አላስቸግረውም»

ይህ አባባሉ እውነት ነበር። በመጀመሪያ ላይ ጋብቻው በርሱ ፈቃድ እንዳልሆነ ያስብ ነበር። ነገር ግን፣ አሊስ ከጦሸኘችው ምሽት ጀምሮ የወደፊት ሰጣ ፈገታውን የሚወስንበት በመሆኑ ሁሉም ነገር ተሰዋወጠ። ለዚህም ሲል የሁለቱን በእንድነት መጣመር እውን ሊያደርግለት፣ ክርስዋም ጋር በመሆን ሊያገኘው የሚችለውን ደስታ ሊያስገኝለት ለሚችል ነገር ያለውን ሁሉ በዋጋነት ይከፍላል። በዚህ ዙሉል በርግጥ ታውሯል። ነገር ግን ስሜቱን ይበልጥ ያነደደው የአሊስ ነፃነት ነው። የሆነ ሆኖ፣በዚህ ሰዓት ላይ ሙሉ በሙሉ ራሱን እያታለለ ይኖራል።

«አንተም ሆንክ እኔ፣ ይህ ጋብቻ እንዲፈፀም ቅንጣት ታህል ፍላጐት አልነበረንምና ምንም አይነት ስህተት እንዳትፈፅም» ስትል ክስተር ብላ ተናገረች።

«ለምን አይፈፀምም?» ሲል ተነጫነጨ

«ይህንንማ፣ አባቴ ገና ከመጀመሪያው፣ እኔን ላንተ ሲያቀርበኝ ራስህ ነበርክ የተናገርከው። አሁን ደግሞ ሃሣብህ ተቀይሮ ከሆነ፣ስሜቶችህ የሚነጫነፖት እነርሱ ለቀመሱት ናሙና ምርጫ ሲሉ ነው። እምቢታዬ ሊያስቆጣህ ይችል ይሆናል። ነገር ግን አንተ እጅግ ሰፊ ተሞክሮ ያለህ ሰው ስለሆንክ፣ ስሜቶችህና ፍላጐትህ አይምታቱብህም»

«የለም፣ የለም፣ በጭራሽ፣ እመኚኝ» አለ ዱ ሮውሌ ለማልቀስ እየቃጣው።

«ይህን በተመለከተ ጊዜ እናጠፋም። እንደ ስሜትህ የተናገርከውን ቃል ጉዳዩም ባይሆን አምኜ እቀበልሃለሁ። በኔ ዘንድ ቢያንስ ቢያንስ ጋብቻ የሚባለው ጉዳይ ጨርሶ የለም። የምፈልገው፣ ጥያቄህን ለአባቴ እንድታቀርብለት ብቻ ነው። ይህን አሻፈረኝ የምትል ከሆነ ግን ሁሉንም ነገር አፍረጠርጠዋለሁ»

ዱ ሮውሌ ግራ ገብቶት ወንበሩ ላይ የመውደቅ ያህል ዘጭ አለበት

«አንዲህ ከሆነ ለአባትሽ ይህን የመሰለ ጥያቄ እንዳቀርብላቸው ለምን ፈለግሽ? ሊገባኝ አይችልም»

አሊስ ወደ በሩ ሄደችና መሸጕሪያውን በዝግታ ወደ ኋላ ሳበችው።

«ጌታዬ! የምታደርገውን ለምን እንደምታደርገው ሳትረዳው ስትፈፅመው ይህ የመጀመሪያህ አይደለም። የተስማማን መሰለኝ? ነገ፣ አባቴ እጅን እንዲሰጥህ እንደምትጠይቀው እጠብቃለሁ። ይህ ካልሆነ መናገሩ የኔ ተራ ይሆንና ውጤቱ እጅግ የከፋ ይሆናል»

«አሁን ጨክነሽ ልታባርሪኝ ነው?» ሲል ዱ ሮውሌ ጠየቃት

ይህች ሴት ፍፁም ድንግርግር የሚል ሁኔታ ውስጥ ጣለችው። ይህ ደግሞ በሁለት ምክንያት ነው። አንዱ በውበትዋ ሲሆን ሁለተኛው በሰጠችው ደስታ ትውስታ ነው።

በሩን ወለል አድርጋ ከፈተችው።

ዱ ሮውሌ፣ በጨለማው ውስጥ እግሩን የሚያሣርፍበትን መሬት በፍርሃት ተመለከተ። ሳይወድ በግዱ ከተቀመጠበት ላይ በመነሣት ወጣ። በሩ ዘንድ ሲደርስ፣ ምናልባት የከንፈር መሣም ለማግኘት ወይም የመጨረሻውን የፀፀት የፊት ገፅታ ለማሣየት ወይም ደግሞ ሴቶች በጭካኔያቸው የመጨረሻው ደረጃ ላይ ሲደርሱ የሚፈጥሩትን ሽንፈት ለመግለፅ ይሁን፣ መለስ ብሎ አያት። አሊስ ግን በሩን ፈቱ ላይ ዘጋጅቦት።

በሚቀጥለው ዕለት ከስዓት በኋላ ከመንገዱ መጨረሻ ላይ ወደሚገኘው የሕዝብ መናፈሻ በእግርዋ ተንዘች። ወደዚህ ቦታ እንድትሄድ የተፈቀደላት በቅርቡ ነበር። ይህን ለማድረግም ራስዋን የምትሸፍንበትና ትከሻዋም ላይ ጣል የምታደርገው ስካርፕ መልበስና ከማንም ጋር ሳለመነጋገር ቃል መግባት ይኖርባታል። በዚህ ጉዞ ላይ ፍራንቾይዝ አጀበቻት። ሁለቱ ሴቶች

ሲጓዙ ካዩቸዋው ከአንድ በላይ ነጋዴዎች መነጩል፣ ቆንሲሉ አባቷ በመሆኑና ዱ ሮውሌም በሁሉም ረገድ ይሁንታ በማግኘት የወደፊት አማቹ በመሆኑ ቀኑ።

የዘንድሮው ክረምት እጅግም ቀዝቃዛ አይደለም። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ልክ እንደዛሬው ከሰዓት በኋላ ዓይነት የምሥራቅ ነፋስ ከአርቢያ ፔትሪያ በኩል ቀዝቃዛ አየር ያመጣል። በዚህም ውስጥ በመጠኑ ጨዋማ የሆነ ርጥበት ከስዊዝ ሸለቆ ስለሚኖር ተስማሚ ያደርገዋል።

«ለመሆኑ ሚትር ዝረሚን አይተሽዋል?» ስትል በአይነ ርግቧ ውስጥ ሆና አሊስ ጠየቀቻት።

«አምን። እንዲያውም ሁለት ጊዜ ነበር የሄድኩት። ስሄድ ሁሉ ከሰዎች ጋር ይወያያል። በተቻለው መጠን የሸሪኩን ቦታ ለመያዝ እየሞከረ ነው» ስትል ፍራንቾይዝ መለሰችላት።

«የጠየቅነውን ነገር ተቀብሎ እሺ ብሏል?»

ይህንን የሴራ ጨዋታ በአግር በሚንዘዙበት ሰዓት ተስማሚ ለማድረግ፣ የሆነ አበባ ወይም በርቀት ያለች ወፍ እያመለከተች አሊስ ቀዝቀዝ ብላ አጣፍጣ አቀረበች።

«አንቺ አድርግ ብለሽ የምትጠይቂውን ሁሉ ያደርጋል።» አለች ፍራንቾይዝ «እናንም ደግሞ ጆን ባፕቲስትን እንደገና የማየት ሃሣብም . . »

«አደገኛ እንደሚሆን አልደበቅሽውም አይደል?»

«አንዲህ እንዲህ ያሉትን ነገሮች ሰውዬው በሚገባ ያውቃል። ነገር ግን ለአደጋ የተጋለጠ ነው»

«ለመሆኑ . . . አነጋግሮሻል» ስትል አሊስ ጠየቀቻት

ፍራንቾይዝ ቀና ብላ ወደ ሰማይ ከተመለከተች በኋላ፣ውብ ጥርሶችዋን ሊያሣይ የሚችል መጠነኛ ሣቅ ሣቀች።

«ለኔ ምን ይነግረኛል ብለሽ ነው? ሁሉታችንም ብንሆን በሁኔታዎች ተገድደው በሚደረጉ ጉዳዮች ላይ፣ እኛን ለድርድር የማያደርሱን እስከሆኑ ድረስ ስንነጋገርባቸው መቀየት በራሱ ያስደስተናል። ታውቂያለሽ፣ ሁሉንም ነገር ተነጋግረናል . . . በኛ ዕድሜ እንደመታደል ሆኖ የጊዜው ማለፍ እምብዛም አይሰማንም። ሁሉታችንም እንጠበቃለን። በቃ ይኸው ነው»

«ይህን መረዳት እችላለሁ። ነገር ግን ያው፣ ያው ነው ቢባልም፣ ትንሽ ቅር ይለኛል። ላለመለያየት ጥሩ ዕድል እያላችሁ . . . »

ጨዋታው ሁሉቱንም እንዲያዝኑ አደረጋቸው። ጥቂት ርምጃዎችንም በፀጥታ ተራመዱ። ከዚህ በኋላ አሊስ ተግባራዊ የሚሆኑ ርዕሶችን ጀመረች። ሁሉቱም በመተጋገዝ ዝርዝሩን ሥራ አከናወኑ።

ወደ ቆንስላው ጥቂት ቀደም ብለው እንደደረሱ፣ አንድ ዘበኛ መጥቶ፣ ከቡር ቆንሲሉ፣ ማዳሞዜል ዴ ማይሴን አሁኑኑ ሊያዩዋት እንደሚፈልጓት ነገራት። ምድር ቤት ወደሚገኘው ሰፊ የእንግዳ መቀበያ ክፍል ገቡ። አባቷ፣ ጥቋቁር መስመሮች ያሉብት ቀይ ደማቅ መሉ ልብስ ለብሰ፣ ረዥሙን ሰው ሠራሽ ፀጉሩን አጥልቆ፣ በእግር ሹራቡ ላይ ጥብጣቦችን አስር ቆሟል። እርሷ ሰራሷ፣ አባቷ በሽቶ የተነከረ ትልቅ አሻንጉሊት ይመስላል እያለች ታስባለች። አራት ማዕዘን ተረከዝ በሆነው ጫማው እየተሞናደሰ ወደርስዋ ተራመደ። ጀመረ እንግዲህ፣ እንደልማዱ ሁሉቱንም እጆቼን በእጆቹ ውስጥ ሊይዛቸው ነው። ይኸው ብዬ የለ? ስትል አሰበች።

«ውድ ልጄ . . . . » ሲል ቆንሲሉ ጀመረ። ድምፁ በሕመም እንደሚንቀጠቀጥ እየተቆራረጠ።

የጀመረውን አረፍተ ነገር የመጨረስ አቅም ስላጣ አቀፋት። ከኪሱ ውስጥ መሃረቡን አወጥቶ ፊቱን ጠረገና ቀጠለ።

«የምነግርሽ ታላቅና ድንቅ ዜና አለ። ከዜናዎች ሁሉ የበለጠ ዜና ነው። እንደማምነው ሴት ልጅ በሕይወት ዘመኗ የምታገኘው ታላቅ ዜና ነው»

«ሁለመናዬ ጆሮ ሆኖ ይሰማሃል፣ አባዬ» አለች አሊስ።

«አሺ እንግዲያውስ። ይህ አዚህ የምታይው የተከበረ ሰው እንቺን እንድሰጠው ጠይቆኛ ል።»

በዚህ ጊዜ፣ በክፍሉ ውስጥ ጥላ ባለበት ቦታ፣ የለበሰውን የሚመስል ጠባቃ ልብስ ከተሰቀለበት ፊት ለፊት ዱ ሮውሌ እስከት መስሎ ቆሟል። ወደ ክፍሉ ውስጥ ስትገባ ያለየችው አሊስ፣ አሁን ጭንቅላቷን ወደርሱ አዞረች። አንገቱን ከተቀላ በኋላ በሁለት እግሮቹ ቀጥ ብሎ የቆመውን ሰማዕቱን ቅዱስ ዴኒስን መስሏል። ደም የሌለውን የሰማዕቱን ፊት

የመሰለ ፊትና፣ መቅሰፍት ሲመጣ ለመስማት እንጂ እርሱ ላይ እንዳይወድቅበት የሚሻ ይመስል አይኖቹን ጨፍኗቸዋል። አሊስ እጅግ ሲበዛ ለዱ ሮውሴ አዘነችለት።

«አባዬ፣» አለች በርጋታ «ለብቻህ ልነግርህ የምፈልገው ነገር አለኝ»

በቅዕበት የሚከናወኑ ጥቂት የትዕዛዝ ዓይነቶች አሉ። ምልክት ይጠብቅ የነበረው ዱ ሮውሴ፣ ወዲያውኑ ተሰወረ። ብቻቸውን እንደሆኑ፣ ሙሴ ዴ ማይሌ፣ምናልባት ሆን ብሎ ጥፋትና ጉዳት እንዲደርስ የመጨረሻውን እንቅስቃሴ ታደርግ ይሆናል እያለ እየፈራ ወደልጁ ዞረ።

«ስሜትሽ ተረብሿል። ነገሮችን ሁሉ በጣም ቀላልና ተራ አድርገን ለመያዝ በርግጥም ምስጢራዊ የሆነውን ነገር ውብት ላለማደፍረስ እንሞክር። እናም፣ ታዲያ የወደፊቱ የትዳር ጓደኛሽ እንዳይሰማ በማለት ልትነግሪኝ የፈለግሽው ጉዳይ ምንድን ነው?»

«አባዬ፣ ነገሮችን ሁሉ ቀለል እንዳደርጋቸው ጠይቀኸኛል። እኔም ቀለል አደርጋቸዋለሁ። ይህ ሰው በፍፁም ባሌ አይሆንም»

«አንተው አድነኝ አምላኬ! አምላኬ! » አለ ሙሴ ዴ ማይሌ። ወደ ሰማይ እያንጋጠጠ። «ለምን ቢባል?»

«ምክንያቱም ለዘለዓለም አላገባምና»

«እንዲህ ነው። እንዴት እንዲህ በድንገትና ሳይታሰብ የሣጣብ ለውጥ ታደርጊያለሽ። ያውም ያለ በቂ ምክንያት?» አለ ቆንሲሉ በሃይለ ቃል

«ድንገትና ሳይታሰብ የተደረገ የሣጣብ ለውጥ አይደለም። በቂ ምክንያትም አለው። የማይቻል ስለሆነ ነው»

«ለምን እንደሆነ ላውቀው እችላለሁ?»

«ከፈለግህ፣ አባዬ እነግርሃለሁ»

«ከፈለግህ አልሽኝ? አምን እፈልጋለሁ እንጂ። በዚህም ላይ ጋብቻ የሚከለክል ነገር ምን እንደሆነ የማወቅ መብት ያለኝ ይመስለኛል።»

ስፖርተኛ ውድድሩን ከመጀመሩ በፊት እንደሚያደርገው፣ አሊስ አየር በሃይል ሣበች።

«ለዘለዓለም የማላገባው ክብሬ ስለተገሠሠ ነው»

«ክብሬ ተገሠሠ ስትይ ምን ማለትሽ ነው?» አለ ቆንሲሉ ትዕግስቱ እያለቀበት።

«ማለቴ ነዋ። በተፈጥሮ እንዳለሁት ከነክብረ ንፅህናዬ አይደለሁም። ወይም እንዲት ሴት ከባሏ ጋር ልትሆን በሚያስችላት ደረጃ ላይ አይደለሁም»

የከንች እንጨት አናቱ ላይ ቢወድቅ ኖሮ፣እንዲህ ሲያንዳግደው አይታይም ነበር። ወደ ኋላው አንድ ርምጃ ከተራመደ በኋላ ጠረጴዛውን ጠንክር አድርጐ ይዞ ቆመ።

«ልጅ፣ ይህማ ቀልድ ነው . . .»

አሊስ፣ ርህራሄ ላይስማትና ዓይናችዋን ሳትሰብር ቀጠለች

«ምናልባት ቁስ፣ወይም አንዲት አዋላጅ ካለች፣ወይም ይህን እኔ ያልኩትን የሚያረጋግጥና ኦፊሴል መግለጫ ሊያዘጋጅ የሚችል ማንኛውንም ሰው ከመረጥክ አሁንም ፈቃድህን ለመፈፀም ዝግጁ ነኝ»

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ልጁን በጥሬ ሰማጮል በጣም ቋምጦ ሳለ፣ በጥላቻ የተሞላው አተያይዋ ገታው። ራሱን ካረጋጋ በኋላ በያንዳንዱ ርምጃው ወሰኑን በሃይል እየደቃ ክፍሉን በስፋው ዞረው። በንጉሡ ሥዕል ፊት ሲያልፍ አይኖቹን ሰበራቸው። ከዚያም አንድ ሣጣብ ብልጭ ሲልለት፣ ወደ አሊስ ተመልሶ ዞረ።

«ይህ ሁሉ የሆነው ከዚህ መድሃኒተኛ፣ ከዚህ አስመሣይ፣ ያ ፖንሴ ከሚሉት ጋር እንደሆነ ብቻ እንዳትነግሪኝ» አላት አይኖቹን አጥበቦ እየተመለከታት

«የለም አባቴ፣ እርሱ አይደለም»

«እንግዲያው ማነው?» አለ ቆንሲሉ የሸላውን ጣውላ ጠረጴዛ በመሣል እጁ እየደበደበ።

«አንተ የምታውቀው አይደለም» አለች በትህትና

«እንዴት ሊሆን ይችላል? ከዚህ ውጥተሽ ሄደሽ አታውቂም። የሚመጣውም እንግዳ ሁሉ ይነግረኛል። የለም፣ የለም፣ እየተከላከልሽው ነው እንጂ፣ ሊሆን የሚችለው ፖንሴ ብቻ ነው»

«እውነተኛውን ቃሌን ነው የነገርኩህ»

«ምን ቀርቶታል? እንግዲያውስ ማነው?» አለ ቆንሲሉ ጥርሶን ነክሶ

«ቱርካዊ ነው»

«አምሳኬ!» አለ ቆንሲሉ በዚህ የመጨረሻ ጦር ሲወጋ

«ምን ለውጥ ያመጣል።» ስትል በትህትና ተከራከረችው

«ዋናው ነገር እውነታው ብቻ ነው። ለዚህ ሃላፊ የሚሆነው ሰው ይህን ያህልም የሚያስጨንቅ አይደለም»

«ያው፣ ያው ነው! ቱርካዊ!»

አንድ አዳኝ፣የሞተች ዋንቸልን በድን መሬት ለመሬት እንደሚጉተት ሁሉ፣ ቆንሲሉም፣ሰው ሰራሽ ፀጉሩን ስርዓት በሌለው ሁኔታ ካወለቀው በኋላ ወለሉ ላይ እያወዛወዘው ወደፊትና ወደኋላ መራመድ ጀመረ።

«እንዳህ ያለው የተረገመ ሰው፣ የት በታ ነው አግኝቶ የለከፈሽ?»

«ጊዛ ውስጥ ነው»

«አውቄአለሁ! እዚያ እንድትሄጂ በጭራሽ አልፈለግሁም ነበር። ያቺ ሴት አገልጋይ ደግሞ አሻቢሽ ነበረች፣ ወይም አታጣሪሽ ልትሆን ትችላለች»

«ስለዚህ ጉዳይ ፍራንቾይዝ የምታውቀው ነገር የላትም። የዚያን ዕለት እሷ ከፈረስ አጣቢው ከሚካኤል ጋር እንቁላላ ለመግዛት ወደ ገበያ ሄዳ ነበር። አንድ ሰው ከወደ ወንዙ በኩል መጣ። አግ አስጋሪ ነው። ወደ መድረሱ ወሰደኝ»

«ያለ ፈቃድሽ? ይህ የሃይል ስራ ነው? ወይኔ! ምርመራ እንዲደረግ ፓሻውን እጠይቀዋለሁ። ምርመራ የሚያከናውኑ ቡድኖችም ይኖራሉ። ያገኛታል!»

«አይሆንም አባዬ፣ አቅጄ ነው። ምናልባት ፀሐዩም ይሁን ወይም የቦታው ፍፁም ጭር ማለት፣ ብቻ ለወሲብ የሚያነሣሣ ነበር። ልጄ ገና ብቅ ሲል እኔ ፍላጐት አደረብኝ---»

«በቃኝ!» ሲል ሙሴ ዴ ማይሌ አቋረጣት።

«ከዚህ በላይ መስማት አልፈልግም። ይህ የሚያስፈራ ነው! ይህ ርግማን ነው። ብቸኛዋ ልጄ፣ ብቸኛዋ ተስፋዬ፣ ብቸኛዋ ወራሼ!»

ከተበላሸችው ልጁ ሣጣብ ይልቅ፣ ልጁ የተጫወተቻቸውን ማስቂያ የሌላቸውን ትዝታዎቹን በደስታና በብልፅግና ራዕይ ተሞልቶ ሲያወጣና ሲያወርድ በርግጥም ቆንሲሉ ተረብሾ ነበር።

«ፖንቻርትሬይን . . . ነፍስ ያለው ፖርቲ . . . አምባሣደር ሲሆን ምንም ያልቀረው . . . »

በወንበሩ ላይ እግሮቹን አመሣቅሎ ተቀምጦ፣ ጉንጮን በትልቁ ትከሻው ላይ አስደግፎ፣ ሰራሱ ያወራ ነበር።

«በዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ ከመግባታችን በፊት ይህን ጉዳይ ለምን ቀደም ብለሽ አልነገርሽኝም ነበር?» ሲል ጮኸባት

«ችግሩ ውስጥ ገብተህ ነበራ። ከዚያም በተጨማሪ አባዬ፣ ካንተና ከአማዬ ጋር ልናገር የምችለውን ያህል ጊዜ መኖር ስለምፈልግ ከመነገር ተቆጠብኩ። የኔ ሁኔታ እንዳሳሰበህ ወዲያውኑ . . . »

«ያንቺ ሁኔታ! ወንሻለሁ ብለሽ ብቻ እንዳትነግሪኝ!»

«ዕድለኛ ነኝ። እንዳልወነስኩ ማረጋገጫ አለኝ»

«ቢያንስ ይህ አንድ ስጋት ይቀንሳል»

«እንዳልከህ፣ የተለወጠውን ሁኔታዬን አንተ ስትገነዘብ፣ ሁሉም ነገር ተለወጠ እንበል። ይህ ከሆነ፣ ላንተ ፈቃድ ተሸንፌ በፈረንሣይ ጠቅላይ ግዛት በአንድ ጨለማ ገጸም ውስጥ ቀሪውን ዘመኔን ራሴን ቀብሬ እኖራለሁ።»

«ትክክል! ይኸው ነው፣ ሴላ አማራጭ የለም፣ ወይኔ ሰውዬው! »

«እኔም ይህና አድርጌ አውቀዋለሁ። አባዬ» አለች

አሊስ፣ ትንሽ እንባ በጉንጮችዋ ላይ እንዲፈስስና ፊትዋን እንዲያርሰው በማድረግ። «ይህን ታዲያ በተቻለ ፍጥነት ማከናወን ይኖርብናል። ከዚህ በኋላ አንተ ባለህበት ይህን ውርደቴን ተሸክሜ ልኖር አልችልም። ይገድሰኛል»

«እኔም አንቺን ማየቱ እንዲሁ ይገድለኛል» አለ ቆንሲሉ ትዕግስት አጥቶ

ይህ ሁሉ ሲሆን እርሱ ሴላ ሣጣብ ውስጥ ገቢደል። ፈረሰኛው ዱ ሮውሊ፣ ሊነገረው ይገባል።

«ፀጉርሽን አሣምሪው። ጉንጮችሽም ላይ እንዳንድ መዋቢያዎችን አድርጊ። ወጣቱን ሰው እጠራዋለሁ»

አሊስ በፍጥነት ራስዋን ሰብስብ አደረገች። ዱ ሮውሴ፣ ቄንቅላቱን በትከሻዎቹ መሃል ቀብሮ እንደሚታደን አጋዘን በሁሉም አቅጣጫ በፍርሃት እየተቁለጨለጨ ገባ።

«ቀድሞውንም ባልሆነ ነበር፣ ውድ ጌታዬ» አለ ቆንሲሉ፣ ግርማ ባለው ቃና። «ልጄን አማክርኪት። በዚህ ዓለም ላይ በታላቅ ደስታ ልትቀበልህ የምትችለው አንተን ሆኖ ግለ፣ ነገር ግን አንተ ልትታገለው የማትችለው ተፎካካሪ አለብህ። ሳትደብቅ የነገረችኝ፣ልጄ ለዚህ ዛያል ሕይወቷን ሁሉ ለመስጠት ተስላለች። የምናገረው ስለአግዚአብሔር አምላክ ነው። ልጄ አሊስ፣የመንፈሣዊ ሕይወት ጥሪ ደርሷታል። እኔም ይህን ለመከልከል ከቶም አቅም የለኝም»

«እረ!» አለ ዱ ሮውሴ፣ በድንጋጤ አግራሞት። ዓይኖቹን ወደ ውጣቷ ሴት ወረወራቸው። ለአፍታ ያህል በዚህ በሚያስታውሰው ስጋዊ ውበትዋ ላይ፣ ሴላ ከላይ የተጫናት አንዳች መልክ ታየውና ቆንሲሉ የገለፃት አይነት እመምኔት አልታይህ አሰኘው።

«እናም» አለ ቆንሲሉ፣ በማዘን «አግዚአብሔር ይሰጣል፣ አግዚአብሔር ይነሣል። አንዳንድ ጊዜ ከመሣሳትን እርሱ የፈለገውን ብቃት ያለውን ይጠራል። ይህ የርሱ ፈቃድ ስለሆነ እንደፈቃዱ ይሁን። አንተም ለአምባሳደርነቱ የመጨረሻውን ዝግጅትህን ስታደርግ፣ ልጀም የአሌክሳንደሪያን ጉዳና ትጀምረዋለች። በሚቀጥለው የሮያል መርከብ ላይ በመሣፈር ፈረንሣይ ውስጥ ወደ ሚገኘው ገዳሟ ታቀናለች።

2

አንዳንድ የመሬት ገፅታዎች ስምንታቸው ጠፍቶ፣ ሁለመናቸው በጭራሮና በእሾሃማ ዳዋ ተሞልቶ፣ ዕጣ ፈንታቸው በዚሁ የሚቀር ቢመስልም፣ የሰው ልጅ በሚያስኖውነው ተግባር፣ በተፈጥሮ ላይ አንዳች ውበትና ሲላው ቀርቶ ብልፅግናን ለማምጣት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ይሳካሉታል። እዚህ አካባቢ ያለው የመሬት ገፅታ ፍፁም የተገላቢጦሽ ነው። ተፈጥሮ ራስዋ፣ መሬቱን፣ አየር እንደልቡ የሚመሳለስበትና ምንም ዓይነት ማዳበሪያ ሳይስጠው የፈለገው ነገር የሚበቅልበት ጥቁር ለም አፈር ነው። ከበሳዩ የሚታየው ሰማይ በርህራሄ የተመላ በመሆኑ፣ ፀሃይንና ዝናብን በስምምነት አያፈራረቀ ይመግበዋል። ምድሩ እጅግ ንፁህ የምንጭ ውሃዎች፣ ተንጠባጥበው ከሚገኙት ኮረበታዎች ውስጥ እየተንሳፈፉ የሚወርዱበት ነው። ተፋስሱ እጅግም አቀበት በመሆን የእርሻን ሥራ የሚያውክ ሣይሆን፣ ይልቁንም ተስማሚና አመች ነው። ይሁን እንጂ፣ ይህ ዓይነቱን የተፈጥሮ ስጦታ ሰዎች በሚችሉት ሁሉ አጥፍተውታል። እርስ በርሣቸው በሚያደርጓቸው ፀቦችና ጦርነቶች፣ ወንድም ወንድሙን እያጠፋው፣ ደካሞችንም በማስወገድ አገሩን ሰረሃብ አጋልጠዋል። የባለጉ አካባቢ፣ ወፍ ዘራሽ እሾሃማ ቁጥቋጦ የለበሰ ስለሆነ፣ አልፎ ተርፎ መንገዱን ይሸፍነዋል። በዚህ ውስጥ የሚጓዝ ፈረሰኛ መንገዱን አንዳይስት ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል። ሰፋፊዎቹ ጉዳናዎችም፣ ተገልጋይ ችሳ ስላላቸው በቁጥቋጦው ውስጥ ያሉ የአገር መንገድ መሰለዋል። ከቤት ቤት ያለው ሁሉ ወድሟል። በጫካው ውስጥ የሚጓዝ ሰው ቂማቸውን ለመቅረፍ ሣይሆን፣ በደመነፍስ ሰውን ከሚተናኩሉ ልቅ ውሾች ራሱን ለመጠበቅ መሣሪያ መያዝ ይኖርበታል።

ፈረሰኛው፣ በአንድ ኮርብታ ላይ ከተመሠረቱች መንደር ድረስ ጋለበ። ከርቀት ሲያዩዋት ትልቅና ምናልባትም አዳጊ መንደር ትመስላለች።

እየተጠጋ ሲመጣ የተገለበጡ ጉተራዎችን፣ የተቃጠሉ የሣር ክዳን ቤት ጣሪያዎችንና የቤቶች ቅርፆች ብቻ ተርፈው ተመለከተ። እንደ ሸቦ የቀጠኑና ግራጫ የለበሱ፣ አጥንቶቻቸው የሚቆጠሩትን ፍየሎቻቸውን በፍርስራሹ ውስጥ የሚጠብቁ ጥቂት አሮጊቶች አሉ። ፈረሰኛው፣ በአንድ የወደቀ ግድግዳ አጠገብ የተቆለለ ድንጋይ ያለበትና ሣር በየቦታው ከበቀለበት የመንደሩ አደባባይ ሲደርስ ቆመ።

«ማክሀ እዚያ!» ሲል አንድ ወጣት አረኛን ተጣራ «አስቲ ወዲህ ቀረብ በል»

ሕፃኑ ልጅ የተፈጨመሳለቀ ፊቱን ወደ ሰውዬው ቀና በማድረግ፣ በባለማመን አተያይ ከተመለከተው በኋላ፣ በባዶ እግሩ በአዚያ ሹል ድንጋዮች ላይ እግሬ አውጭን ብሎ ተፈተለከ። መንገደኛው፣ ከዚህ በኋላ አንድ ሽማግሌ ሰው ተመለከተ። ሰውዬው፣ ቆልማማው ክዳኑ ከተወገደበት ከአንድ የውሃ ጉድጓድ አጠገብ የመሸሸግ ያህል ቆመዋል። ፈረሰኛው፣ ከፈረሱ ላይ ወረደና ልጓሙን በአንድ ክሰሩ ተንትለሙ በፍርስራሽ ላይ በወደቀ ዛፍ ቅርንጫፍ ላይ አሰረ። የለበሰው ኮት ከመንገዱ ላይ የተነሣውን የአቧራ ብናኝ ዱቄት ለብሷል። ዓይኖቹ ጉድጓዳቸው ውስጥ የተቀረቀሩ ናቸው። ጉንጮቹ በማምጠት የቆረጎ ለቀማ ምርቅ ተሸፍነዋል። እረማመዱ፣ ለጥቂት ጊዜያት በረጋ መሬት ላይ እንዳልቆመ መርከበኛ፣ እርግጠኛነት የለውም። ዓይኖቹ ወዳቀኑበት ሽማግሌ ተራመደ።

«ሰዎች ሰውዬይራን ብለው የሚጠሩት መንደር ይህ እንደሆነ ሊነግሩኝ ይችላሉ?» አሳቸው የደከመውና ከጆን ባፕቲስት በስተቀር ሌላ ሊሆን የማይችለው ፈረሰኛ

ፊጣን ግልቢያ ያደርግ በነበረበት ጊዜ ባርኔጣውን ስለጣለው፣ ግንባሩ በላብ ወርዝቶና ፀጉሩም በአቧራ ብናኝ ተያይዟል።

«ለዚህ ቦታ ስም የሚሰጡት ብዙ ሰዎች የሉም» አሉ ሽማግሌው ሰውዬ

ድምፃቸው መጠነኛ የጉሪምሃ ዓይነት ቅላፄ ቢሰማበትም ግልፅና ክሰል ያለ ነበር።

«ግን አውነትህን ነው» ሲሉ ቀጠሉ «ክሰውብራይን የተረፈው ያህ ነው»

«እዚህ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ወዴት አሉ?» ሲል ዙሪያውን እየተመለከተ ጆን ባፕቲስት ጠየቀ

የሰሚን ምስራቅ ነፋስ፣ ላለፉት ብዙ ቀናት እንደቢላዋ ጠርዝ ቀዝቅዞና ስሎ ሲነፍስ ሰንብቷል። በዚህም የተነሣ ክሰማዩ ላይ ደመናውን ሙልጭ አድርጐ ስለወሰደበት፣ ክክሰሉት የመንደሯ ድንጋዮች በላይ በጣም ግልፅ ስማያዊ ሰማይ ብቻ ይታያል።

«መልሱን እያወቅህ ልታጠምደኝ የምትሞክር ከሆንክ ግን» አሉ ሽማግሌው ሰውዬው፣ «እኔንም ከምትፈልጋቸው ሰዎች አንዱ መሆኔ እርግጥ ስለሆነ፣ አሁኑኑ ልትወስደኝ ወይም እዚሁ ልትገድለኝ ትችላለህ። ነገር ግን እንደምትናገረው አገሩን የማታውቅ ሰው ከሆንክ ከሩት ቦታ የመጣህ መሆን አለብህ»

«አጅግ ክሩቅ ቦታ ነው የመጣሁት»

«አንግዲያው እዚህ ድረስ እንድትመጣ ያደረገህ፣ አንዳች የሆነ የምትፈልገው ነገር ወይም የምትፈልገው ሰው አለህ ማለት ነው። በየትኛውም መልክ ብትመጣም ልነግርህ የምችለው መጥፎ ዜና ነው»

«አንዲት ሴት እፈልጋለሁ»

«ወንድ ሰው የምትፈልግ ቢሆን ኖሮ ወዲያውኑ በቃህ አልህ ነበር። ምክንያቱም በሕይወት አንዳሉት አድርገህ እኔንም መቁጠር ከፈለግህ እዚህ ያለነው ሁለት ብቻ ነን። በርግጥ ጥቂት ሴቶች አሉ። አንተ የምትፈልጋት ማን ትባላለች?»

«ማሪኔ ትባላለች»

ሽማግሌው ሰውዬ ቀና አሉ።

«የቤተሰቧን ስምስ ታውቀዋለህ?»

«አግብታ፣ ቢበዛ አንድ ሣምንት የቆየች ነበረች። ባሏ አገር ጥሎ ጠፋ። ስሙ ሜትር ዠረሚ ይባላል»

«እህ! ዠረሚ! እውነት ነው። ጥሩ ቁመና የነበረው ጉበል ነበር። ለቅርብ ጐረቤቶቼ ሁለተኛው ልጃቸው ነበር። ይኸውልህ እዚያ ከጐተራው በስተጀርባ። ሰመሆኑ በህይወት አለ?»

«የሥራ ሽሪኬና ጓደኛዬ ነው። ካይሮ ውስጥ ይኖራል»

«ካይሮ ውስጥ፣ ግብፅ ማለት ነው። የመፅሐፍ ቅዱሱ ግብፅ። እግዚአብሔር ታላቅ ነው! ምን ዐይነት አድል ነው! እንዲህ ያለው ዜና ቤቴ እድሜ ምን ያህል ድንቅ እንደሆነ አይገባህም። አንተ ከዚህ ከሄድክም በኋላ ቢሆን ይህን ዜና ሳስበው አናራለሁ። አውነት፣ ልንገርህ፣ ዠረሚ አስክአሁን በሕይወት በመኖሩ ደስተኛ ነኝ»

«ባለቤቱስ ግን?» ሲል ጆን ባፕቲስት ጥበሰ።

«አ! እንዲህ ባለ ነገርስ ሊተሳቀየው፣ ያለፈው አልፏል። እርሱ ብቻ ክፉ አይንክው በሰላም ይኑር»

«ግን እኮ አልተረዱኝም» አለ ጆን ባፕቲስት ጉልበቱን መሬቱ ላይ አሣርፎና ፊቱን ወደ ሽማግሌው ቀረብ አድርጐ። «የሳክኝ እሱ ራሱ ነው። እስከዛሬ ድረስ ይህን ሁሉ አመት ለርስዋ ታማኝ ሆኖ ይኖራል። ተደስቶ እንዲኖር የሚመኙለት ከሆነ እርሱም ይህን ማወቅ ይኖርበታል።»

«አዎ» አሉ ሽማግሌው በሃዘን ሰጥመው «እርሱ እንዲህ አይነት ሰው ነው። በቃ! እርሱ እንዲህ ዓይነት ሰው ነው። የርሱ ቤተሰቦች የሆኑት ሁሉ የርሱ ዓይነቶች ነበሩ። ምናልባትም የዚህች መንደር ሕዝብም በሙሉ እንደዚሁ እንደሆነ አስባለሁ። ለዚህም ነው እንዳንተርፍ ያደረጉን»

ዓይኖቻውን ቀና አደረጉ። የሆነ የፉጨት ድምፅ ከበላያቸው ላይ አስተጋባ።

«እርሱ የሄደ የዕለቱ ዕለት አረፈች»

በዚህ የባላገር አካባቢ የነበረው ወጥታ ከጥቁር ድንጋይም ይከብዳል። ሌላው ቀርቶ ነፋሱ ከድንጋዮች በላይ ድምፁን አጥፍቶ ይንቀሣቀሣል።

«እንዴት ሆነ?» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቀ

«ወዳጄ» አሉ ሽማግሌው፣ ረጋ ባለ ሁኔታ አሻግረው ወደሀዋ እየተመለከቱ። «ጠቀሜታ ባይኖረውም ታሪኩን ለመናገር ያህል ሁለት ብቻ ቀርተናል። መከራዎችና አሣፋሪ ተግባራትን ለመቀበል የተፈጠረን ይመስላል። ግን ይህን ታሪክ መናገር ምን ይጠቅማል? በርግጥ ይህ መጥፎ ስምና ታሪክ ለትውልድ ሲተላለፍ ይኖራል። የለም፣ የለም፣ ስለጨካኝ ገዳዮቻችን ያለንን መጥፎ ትዝታ ከምንወዳቸው ሟቾቻችን ጋር በአንድ ጉድጓድ ውስጥ ቀብረናቸዋል። ይህን ያደረግነው ለፍቅር፣ ለሰላምና ለደስታ ስንል ነው። ለዚህም ደግሞ የመታሰቢያ ሣውልት ልናቆምላቸው ይገባናል። ምክንያቱም የነርሱም ታሪክ ካለኛ መኖር አይችልም።

«ቢሆንም ግን ይህቺ ሴት፣ ይህች ወጣት ሴት፣ ገርሪሚ ያገባት ሙሽራ . . .»

«አዎን፣ ታፈቅረው ነበር። ለርሱ የነበራትን ፍቅር፣ ጊዜ ወይም ሰው የሚያበላሸባት አልነበረችም። ስሙን እየጠራች ነው የሞተችው»

ሽማግሌው ሰውዬ፣ በጣቶቻቸው በመፈተግ ያለሰለሱትን ትንሽ ጭራሮ ይዘው በሚያሣዝን ሁኔታ ተነስተው ቆሙ። በክሳማናው ሰውነታቸው ላይ የደረቡትን ያረጀ ወፍራም ካፖርት ጠራረጉ።

«ለጥቂት ጊዜ ትቆያለህ?» ሲሉ ጠየቁት

«ያለም፣ አልቆይም። በፍጥነት መሄድ ይኖርብኛል። በርግጥ . . .»

ጆን ባፕቲስት፣ ሽማግሌው እንዲያጅቡት በመፈለግ ክንዱን ዘረጋላቸው።

«. . . ማንም ሰው ቢጠይቅም አላዩኝም»

«ከኛ አንዱ ነህ?»

«አይደለሁም፣ ነገር ግን የጋራ ጠላቶች ያሉን ነን»

«እንግዲያው ተጠንቀቅ።» አሉ ሽማግሌው

ሰውዬው፣ የወጣትነት ወኔአቸውን በተመሣሣይ ሁኔታ እየተሰለቡ፣ የቀሩትን ሁሉ እያሰቡ፣ ከጐናቸው ያለውን ጠንካራና የደስደስ ያለውን ወጣት ሰው መረመሩ።

«ለመሆኑ ከወይኔት ነው የመጣኸው? ፈረስህም የደከመው ይመስላል»

«ይህኛው የመጣው በራይን ወንዝ አጠገብ ካለችው ከተሮን መንደር ነው። ከዚህ በኋላ ብዙ ሊጓዝ የሚችል ስለማይሆን አሰጋለሁ። ፖሪስን ከለቀቅሁ በኋላ ሰድስት ያህል ለውጫለሁ»

«ፖሪስ!» አሉ ሽማግሌው በመደነቅ «እና ወዴት ለመሄድ ነው አቅድህ?»

«ወደ ሲየቱ፣ በዛሬው ምሽት እቀጥላለሁ»

«በዚህ አካባቢ ያሉት ወታደራዊ ቦታዎች በመሉ በነዚያ ጭራቆች እየተጠበቁ ናቸው» አሉ ሽማግሌው።

ከዚያም ዘወር አሉና በፍርሰራሾች መሃል የገደል ማሚቶ መፍጠር በቻለ ድምፅ ተጣሩ።

«ዳንኤል!»

ጆን ባፕቲስት፣ ቀደም ሲል አይቶት የነበረውና ፊቱን ሁሉ ጥላሸት ያጠቆረበት ልጅ፣በአቅራቢያው ካለው ግርግዳ ውስጥ ጭንቅላቱን ብቅ አደረገ።

«ወዲህ፡ ና» አሉ ሰውዬው።

ወደ መንገደኛው ዞሩ።

«ይህን ልጅ አፈናጥጠህ ውሰደው። በቁጥቋጦዎች መሃል አድርጐ፣ የኛ ሰዎች ወዳሉበት አካባቢ እስክሄዱ የሚኖሩ ከሆነ፣ ሳስበው ግን ይኖራሉ፣ መርቶ ይወስድሃል።

በእሥሩ ጊዜ በየገደሉና በየሸንተረሩ ከፍተኛ እንቅስቃሴ አለ። አንዳች ታላቅ ሁኔታም እየቀረበ እንደሆነ ይታየኛል። ሰምቼን ስታገኛቸው ከሶውቤይራን እንደመጣህና ጆን እንደላከህ ንገራቸው። ጆን ማለት እኔ ነኝ»

ጆን ባፕቲስት ፈረሱ ላይ ወጥቶ፣ ሕፃኑን ልጅ ከኋላው ለማፈናጠጥ ይዞ አነሣው።

«ይህ ከመንገድህ ወጣ አድርጉህ ይወስድህ ይሆናል። ቢሆንም አትቆጭበትም። እዚያ ስትደርስ አዲስ ፈረስ ይሰጡህና ነገ ጧት ሲየቴ ትገባለህ» አሉት ሽማግሌው

«እግዚአብሔር ይስዋልኝ» አለ ጆን ባፕቲስት

የገንዘብ ቦርሳውን ወዳስቀመጠበት ወደ አንደኛው የኮርቻ ኪስ እጁን ሰደደ።

«ትንሽ ዕርዳታ ባደርግልዎ?» ሲል እየፈራ ጠየቃቸው

ሽማግሌው የፊቱን ገፅታ ተመልክተው አስቆሙት

«ከኔ ይበልጥ አንተ ያስፈልግሃል። በዝህ ቤቶች ሁሉ ውስጥ፣ ጭራቆቹ ሲያገኟቸው የማይችሏቸው የተቀበሩ ሣንቲሞች አሉ። ገንዘብ ይዘን ካዩን ተመልሰው ይመጣሉ»

«እንግዲያውስ ደህና ይሁኑ ጆን። ሰላምታዎን ለገርሪሚ አደርሳለሁ።» አለና ጆን ባፕቲስት ተንቀሳቀሰ።

ፈረሱን በእርካቡ ከረከረው። በዛሬጋማው ቁጥቋጦ ውስጥ ጭንቅላቱን የተከለው ምስኪን ፈረስ ግን አልተንቀሣቀሰም። በመጨረሻ ግን በወደመው ቦታ ላይ፣ ወድቀው በቀሩ ለማዕታት አፅም ላይ፣ በጥንቃቄ በመራመድ ተገዘ።

ጆን ባፕቲስትና ልጁ እየጋለቡ ሲሄዱ «ዝቅ ብለህ ተመልከት» አሉት ጆን። «ያቆሟቸውን የመታሰቢያ ሃውልቶች ታያቸዋለህ? ድላቸውን የሚዘክሩበት መስቀል! . . . ይህን ታምናለህ?»

ይህ ሁሉ ሲነገር ፈረሰኛው ግን ሊሰማ ከሚችልበት ርቋል።

ከሶውቤይራን አልፎ ያለውን የቁልቁለት መንገድ ጥለው ሲገዙ፣ ርግቦት ያለበትና ጥላ የሚያጠላበት ሸለቆ ውስጥ ገቡ። በምንፖ ዳር ዳር፣ አልፎ አልፎ ዳገታማው መንገድ

በየቅጠሉና በየአንጨት ሽቡቱ ተሸፍኖ ተዘርግቷል። ጊዜው እየመሸና ከበላይ ያለውም ጥላ ይበልጥ እየጨለመ መጣ። በፈረሱ ኮቴ ስር ጭራሮዎች ሲሰባበሩ በስተቀር ምንም ሳይሰሙ ዳገቱን ተያያዙት። በአረንጓዴ የድንጋይ ላይ ኅር የተሸፈነ የመጨረሻው ቁጥኝ ከፊት ለፊታቸው እንደተጋረጠባቸው፣ ልጁ ወደ ቀኝ አቅጣጫ አመለከተ። ልጁ፣ ሙሉ በሙሉ ግንኙነት የሚያደርገው በምልክት ብቻ ነው። አሁን ግን በድንገት በመጮሁ ቀደም ሲል ድምፁን ያልሰማው ጆን ባፕቲስት ደነገጠ። ፖኾቱ፣ ታሳት የለሰበት የእንሰሳ ዓይነት ድምፅ ነበር። እንዲያውም፣ የሚቆራረጥ የጉተት ወፍ ዓይነት ማቃሰት የመሰለ ሦስት ጊዜ አሰማ። ጉሟቸውን ግን በአንድ ወድቆ በተሰበረ ግዙፍ ያረጀ ባፍ ስር በማለፍ ተጠሉ። በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ አነስተኛ የቅጠላቅጠል መንኩሻ ተሰማ። ወዲያውም አምስት ሰዎች ከየቁጥኙና ከየባፋ ላይ የበቀሉ ይመስል ብቅ አሉ። ሰዎቹ፣ ጥቁር ያሉ፣ የየርጣሬ ስሜት ያለባቸውና እንደዲያብሎስ ፊታቸውን ያጨለገጉ ነበሩ። ቀስቶቻቸውን በፈረሰኛው ላይ አነጣጠሩ።

«ከሶውቤይራን ጆን ናቸው የሳኩ» አለ ጆን ባፕቲስት ረጋ ብሎ።

በባርኔጣዎችና ባጐፈሩ ፂሞች ኋላ ካሉት ከነዚህ ፊቶች ለየትኛው እየተናገረ እንደሆነ አላወቀም።

«እውነት ነው!» አለ ሕፃኑ

«ውሪዱ!» ሲል ከሰዎቹ አንዱ ለስለስ ባለ አነጋገር አዘዘ።

ጆን ባፕቲስት፣ ከኮርቻው ላይ ወርዶ መሬት እንደረገጠ እጆቹን ወደ ላይ ሰቀላቸው። አስቀድሞ የተናገረው ሰው ወደ ፈረሱ ተጠግቶ ሻንጣዎቹን ተመለከታቸው።

«በኮርቻው የግራ ቦርሣ ውስጥ ሽጉጥ አለ። በታዘልክት ሻንጣ ውስጥ ፖቤና የምትመለከቱት ጐራዴ አለ። ይሁን አንጂ ወዳጃችሁ ስለሆንክ አንዳቸውንም የመጠቀም ሃሣቡ በውስጤ የለም»

ሰውዬው የሆነ ነገር አገተመተመና ከጓደኞቹ አንዱ የፈረሱን ልጓም እንዲይዝ ምልክት ሰጥቶ፣ ከኪሱ መሣሪያ በማውጣት የጆን ባፕቲስትን ዐይኖች አሰራቸው። መንገዱን ይዘው ሽቅብ ተራመዱ። ልጁ ግን አስክአሁን ፈረሱ ላይ ሆኖ የኮርቻውን ቀዳማይ አጥብቆ ይዟል። ጆን ባፕቲስት፣ አይኖቹን እንደታሰረ በአንደኛው ሽፍታ ትከሻ ላይ እጁን በማሳረፍ እየተመራ ይራመዳል። በዚህ ዓይነት በአይኖቹ ላይ የታሠረው መሣሪያ ሳይፈታለት ለማማሽ ሰዓት ያህል ተጓዙ። መሣሪያው ከአይኖቹ ላይ ሲፈታለት፣ ጆን ባፕቲስት ዙሪያውን በቁጥኞችና በሰው ሰራሽ

ዋሻዎች መሣል መሆኑን ተመለከተ። ጊዜው መሸቶ ስለነበረ በደረሱበት ወታደራዊ ሠፈር ላይ ሰባት ወይም ስምንት በሚሆን ቦታ እሳት በርቶበታል። ጥላ የመሣሰሉ ሰዎች፣ ክስልስል ባሉት ባለሦስት እግር የማብሰያ ምንቸቶች ዙሪያ ተፍ ተፍ ይላሉ። ራቅ ብሎ ባለው አነስተኛ እሳት አጠገብ የተቀመጠው ሰው፣ ጆን ባፕቲስትን ከርሱ ፊት ለፊቶ ባለው ቦታ ላይ እንዲቀመጥ ጋበዘው።

«እና» አለ ሰውዬው «ከሰውቢይራን መምጣትህ ነው? ለመሆኑ ከኛ አንዱ ነህ?»

ሰውዬው፣እየተናገረ፣ ጭራሮ አንስቶ በመሰባበር አንድ በአንድ ወደሚንጣጣው እሳት ይወረውራል። ሰውዬው፣ረዥም አጥንታም ፊትና ብሩህ ዐይኖች አሉት። ከረሃብ፣ ከድካምና መከራን ከመሸከም ልማድና መልሰውም በለሉች ላይ ጉዳት በማድረስ በዚህ አካባቢ ያሉት ሰዎች ሁሉ ተመሣሣይ ሁኔታ ይታይባቸዋል። ሰዎቹ፣ እንደ ፍጡር መኖር ሊችሉ ነገር ግን እንደማለሰብ የመቆጠር ዕድል በመነፈጋቸው እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ሕይወት ውስጥ ኖረዋል።

ወደዚህ አካባቢ ምን እንዳመጣው ጆን ባፕቲስት ገለፀላቸው። ምንም እንኳ የርሱ ታሪክ ረዥም ቢሆንም ከዚህ ሁሉ ውስጥ ዝርሚና እርሱ በቅርቡ ከካይሮ መመለሳቸውን የሚያመለክተውን ክፍል በአጭሩ ተረከላቸው።

«ስሜ ካቲናት ይባላል» አለ ሰውዬው

«በዚህ አካባቢ የምታወቀው ቢያንስ በዚህ ስም ነው። ዝርሚ ከኔ ይልቅ ትልቅ ስለሆነ አላውቀውም። ይሁን እንጂ ከረዥም ጊዜ በፊት ስለርሱ ሰምቻለሁ። አስከዛሬ በሕይወት በመኖሩ ዕድለኛ ነው። አባቶቻችን ምንም ምርጫ ስላልነበራቸው ሕይወታቸውን ማዳን ከፈለጉ ወደ ሩቅ ቦታ መሰደድ ግድ ነበረባቸው። እኛ ግን አሁን መዋጋቱን መርጠናል። ጊዜውም እየተለወጠ ነው። ንጉሡ እያረጀ ነው። አገሩም ሁሉ በርሱ ላይ እያጉረመረመና እየተበታተነም ነው። በአሁኑ ጊዜ ከውጭ ሃይል ጋር ህብረት ለመፍጠር ጊዜው ስላይደለ ለነሳነታችን እዚሁ ሆነን እንታገላለን»

እንደ ጭስማው ጥቁር ያለና ከአማሚያኑ አንዱ የሆነው ሰው፣ ለያንዳንዳቸው ቀጭን አጥሚት በእንጨት ወጭት አመጣላቸው።

የየድርሻቸውን ፉት እያሉ ስለካይሮና ስለቬርሚይስስ ማውራት ጀመሩ። ላለፉት ሁለት ዓመታት እዚህ በጫካው ውስጥ በመኖሩ ከዓለም ዜናዎች ሁሉ መገለሉን ካቲናት ገለፀ። የርሱ

ትግል ዓለምን ለማጥፋት ሣይሆን፣ በውስጧ እያንዳንዱ ሰው ሊኖርበት የሚችልበትን ቦታ ማዘጋጀት ነው። አስቸጋሪው ሕይወቱም ለሰው ዘር ፍፁም የሚስማማ አገልግሎት ማበርከት ነው።

«ካገ ሚት የማድ ሲየቴ ክተማ ውስጥ መድረስ ይገባኛል» አለ ጆን ባፕቲስት። ያለበትን ሁኔታና ያከናወነው ረዥም ጉዞ አላለበት

«አዚያ ደርሰህ በመርከብ ለመሣፈር አቅደሃል?»

«አዎን። ወደ ጀኖአ የሚሄድ የአሣ አጥማጅ ጀልባ ላይ እሣፈራለሁ።» አለ ጆን ባፕቲስት

«አንተን በሚመለከት የንጉሡ መልዕክተኞች ለየአካባቢው ባለሥልጣኖች ሳያስታውቁ ይቀራሉ ትላለህ? እየፈለጉህ መሆን አለባቸው»

«መልዕክተኞቹ ከኔ በተሻለ ፍጥነት የሚጓዙ አይመስለኝም። የመጥፋቴም ነገር ወዲያውኑ የሚታወቅ አይሆንም። ከአንግዲህም በኋላ አራት ሰዓት ጊዜ አለኝ»

«አዎም፣ ይህ አደጋ ያለበት ዕቅድ ነው። አሁን ከምትለው ቦታ ጀልባዎች በየቀኑ አይንቀሣቀሱም። እንበልና መርከበኞቹን በጉቦ ልትደልላቸው እየሞከርክ ሳለህ ትዕዛዙ ቢደርስስ? ወዲያውኑ ውሣዘት ይደርስብሃል።»

«አውቃለሁ» አለ ጆን ባፕቲስት በሃዘን፣ «ፖሪስን ከለቀቅሁበት ጊዜ ጀምሮ ሳስብ የነበረው ይህንኑ ነበር። ዳሩ ግን ምንም ምርጫ የለኝም»

ካቲናት አጥሚቱን ጠጥቶ ከጨረሰ በኋላ፣ ወጭቱን በጣቱ መፋቅ ጀመረ።

«እኔ የምመክርህ ግን ጥቂት ሰዓታት እንድትተኛ ነው። እስቲ ራስህን ተመልከተው። በሚገባ ዕረፍት አላደረግህም። በእንዲህ ያለ ሁኔታ ላይ የሚገኝ ሰው ደግሞ ጥሩ አይሆንም። ከነዚያ ዋሻዎች ወደ አንደኛው ሂድና አጉላ ደራርበህ ለብስህ ጥቂት ተኛ። ሠፈራችንን የምናፈርሰው ከሰሊቱ አሥር ሰዓት ላይ ነው። እስከዚያ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ አንዳች ነገር ላሰናዳልህ እችል ይሆናል።»

ትኩሱን ሾርባ ከጠጣና በእሣቱ ጻር ዕረፍት ካደረገ በኋላ፣ ጆን ባፕቲስት ከባድ የመጫጫን ሁኔታ አጋጠመው። ሽሽት ከጀመረ ወዲህ የተኛው በጣም ለአጭር ጊዜ ሲሆን፣ በዚያም ሁኔታ ላይ እንኳ ንቁ ስለነበረ እንቅልፉ በከፊል ነበር። የካቲናትን ምክር ለመቀበል

ወስኑ። ገና ጋደም ከማለቱ ካልተፋቀው አጭሣ በሚወጣው የሚሰነፍጥ ሽታ በስተቀር፣ እንቅልፍ ጭልጥ አድርጐ ወሰደው።

ካቲናት በገባለት ቃል መሠረት ክለሊቱ አሥር ሰዓት ላይ ቀስቀሶ አነቃው። የሆኑ ልብሶች አመጣለትና የለበሰውን አውልቆ እንዲቀይር ነገረው። አሁንም ገና እንደተጫጫነውና ንቃቱ በከፊል ቢሆንም፣ መንገደኛው አሮጌ ልብሶቹን አውልቆ ከሣር የተሠራና እጅጌው በጥልፍ ያጌጠ ለርሱ ግን በሚገባ የተስማማው ልብስ ለበሰ። ከዚያም በትንሽ የሚሰፋበት ሁለት የበት ጫማዎችን አጠለቀ። በዚህ ላይ ሰፊ የሱፍ ኮፍያና ባለ ሶስት ማዕዘን ባርኔጣ አደረገ። በዚህ በሚያንፀባርቅ አለባበሱ በቅርብ ባለው እሣት ዙሪያ ወደ ቆሙት የሰዎች አጀብ፣ ጀን ባፕቲስት ሄደ። በነዚያ ሰዎች መሃል ካቲናት አለ። የማለዳው ፀሎት አጭርና ክልብ ሲሆን፣ ሁሉም እናታቸው ባዶ ነበር። ከዚህ በኋላ እያንዳንዳቸው ከማታው ሾርባ አንዳንድ ወጭት ተቀበሉ። ሾርባው ዛሬ የበሰ ውሃ ሆኗል። ካቲናት፣ ፖንሴን ጠርቶት ከጐኑ እንዲቀመጥ ጠየቀው።

«ከሶስት ቀናት በፊት በአዚየስ ጉዳና ላይ ተዋጊዎቻችን እንድ ወጣት የመሣፍንት ዘር ተኩለው ጥለው ነበር። ሰውዬው፣ አለ አንዳች አጀብ መጓዙ ትክክል አልነበረም። ሰዎቻችን እጅግ በጥንቃቄ የፈፀሙት ሥራ ስለነበረ በልብሶችህ ላይ አንዳችም የደም ምልክት የለበትም። የሰውዬው ሰነዶች እኒሁልህ»

አንዲት ትንሽ፣ቀይ፣ የሥራ ድርሻን የምትገልፅና ሀ. ቭ የሚል የወርቅ ማህተም ያለባትን ወረቀት ለጀን ባፕቲስት ሰጠው።

«ሰውዬው፣ ጦር ሠራዊቱን በመቀላቀል መከራችንን የሚያሣጥን ጀብደኛ ወጣት ነበር። የሃይማኖታቸውን ደህንነት በመጠበቅ ሽፋን ስም አንዳችም ነገር ላይዙ፣ ለዘረፋና ለዝናቸው መገንቢያ ሃብት ለመሰብሰብ ይመጣሉ። ከነርሱ አንዱ ነህ ተብለህ ባለመጠርጠርህም ዕድለኛ ነህ። እርግጥ ነው፣ አንተ ሁለመናህ በጭታ ዐከቷል። እነርሱ ግን በአጠቃላይ ለልብሶቻቸው ይጨነቃሉ። እነዚህ ሰዎች ለኛ ታላቅ ክብር የሚያደርጉልን ይመስልሃል? ሊገድሉን ሲመጡ ውድና ያጌጡ የክት ልብሶቻቸውን ለብሰው ነው»

ጀን ባፕቲስት የቆዳውን እሽግ ከፈተው። በውስጡም የሚቹ ሰው ሰነዶች አሉበት። ስመም ሁፈስ ዴ ቫውዴሶሬስ ይባላል። ሰውዬው፣ የልዑል ዴ ኮንቲ ቤተሰብ ሲሆን፣ ልዑሉም፣ የኒየም ጠቅላይ አገር ገዥ እንዲሆን የድጋፍ ደብዳቤ ዕፎሰታል። ሰውዬው፣

ከፖንሴ ጋር ቢበዛ ጥቂት ወራት ታላቅ ወይም ታናሽ ቢሆን እንጂ ዕድሜው ተመሣሣይ ነበር።

«ፈረስህን ልትጠቀምበት ትችላለህ። እዚህ ያሉ ፈረሶች ጋሪ ጉታቾች ስለሆኑ ከአዲሱ ደረጃህና ሕይወትህ ጋር አይመጣጠኑም። በሌላ በኩል እነዚህ ሰነዶች አስካለህ ድረስ ማንም ቢሆን ችግር አይፈጥርብህም። የመጀመሪያውን የጉዞ ምዕራፍህን፣ ከአዚያስ በስተምስራቅ በኩል ሄደህ አጭር ርቀት የተጓዝክ በማስመሰል ፈረስህን ቀይረው። ፈረሰኞቹ ተወዳዳሪዎችህ በዚህ መንገድ አይሄዱም፣ አንተንም ለመጠርጠር ምንም ምክንያት አይኖራቸውም። ከዚያም ወደ ማርሴይ ተሸገር። ማርሴይ ትልቅ ወደብ ነው። እዚያ ማንም ልብ ሳይልህ በርግጠኝነት ጀልባ ታገኛለህ። ጥይቶቻችን በጀሮ ግንዶቻቸው ላይ ማፏጨታቸውን ሲሰሙ፣ እነዚህ ትንንሾቹ ጀግኖች የመርከቦቻቸውን ፊት ወደ ምስራቅ ሜዲተራኒያን በማዞር፣ ዕድል ሃብታቸውን እዚያ ለመፈለግ መሞከራቸው የተለመደ ነገር ነው።»

ቀኑ እየደበዘዘ፣ ብርሃንም ጭራሯቸው ከሚታዩ ቅርንጫፎች ላይ እየነጠሠ ነው። ሰዎቹ፣ እሣቶቹን ሁሉ በመረጋገጥ ካጠፉ በኋላ፣ ሻንጣዎቻቸውን በየትከሻዎቻቸው ላይ ተሸክመው፣ እንደደረጃቸው ቅደም ተከተል ተሰልፈው፣ መሣሪያዎቻቸውን አቀባብለው ተነሱ። ጀን ባፕቲስትም፣ ፈረሱን እየሣበ አንድ በተፈጥሮ አርከን መሰል ሰጥ ያለ ጉብታ አስኪደርሱ ድረስ አብሯቸው ተጓዘ። ከዚህ ጉብታ ላይ ሆኖ፣ ማንም ሰው ከርቀት የሚታየውን ትልቅ ጥቁር ደንና በስሱ የገረጣ የሚመስለውን የሸለቆውን መስመር ይመለከታል። በፖንሴና በካቲናት መካከል ረዘም ያለ መተቃቀፍ ከተከናወነ በኋላ የየራሣቸውን የተለያየ መንገድ ጀመሩ። ጀን ባፕቲስት፣ ፈረሱ ላይ ከወጣ በኋላ በለማያዊው የንጋት ብርሃን ውስጥ፣ ይህንን ወደፊት የሰው ልጅ የነፃነት ምልክት የሆነውን ጢማም፣ ጉስቁሳና የሚንቀጠቀጥ ጓድ ለመጨረሻ ጊዜ ተመለከተው። ከእነዚህ የደፈጣ ተዋጊዎች ብዙዎቹ በነተቡት ልብሶቻቸው ላይ ዘርፈፍ ያለ ሽሚዝ ለብሰዋል። ይህ ደግሞ ምናልባት እርስ በርሣቸው ለመተዋወቅ እንዲረዳቸው ተብሎ ሣይሆን አይቀርም። ለሚለያቸው ጀን ባፕቲስት፣ ጦሮቻቸውንና ጉራዴዎቻቸውን ከፍ አድርገው በማንሣት ሰላምታ ሰጡት። የአገር መንገዱን ይዞ ቁልቁል ሲንዝ፣ ከትናንት በስቲያ ገድለውት ዛሬ ደግሞ በሕይወት እንዲኖር ያመጡትን ሰው ቅርፅ የተዋጊዎቹ ዐይኖች ተከተሉት።

3

ወንድም ፖስኳልና ከኢጣሊያ በቅርቡ የመጣው ባርቶሎሚዎ የተባለው የተጠመቀ ክርስቲያን፣አዋር ግቢው ውስጥ ሆነው ይጠብቁ ነበር። ከዚህ ባለፈ መጻፈር ግን አግባብነት አይኖረውም። ቂማሙ ካፑቺን፣ ብቻውን እንደጅብራ በተንተረ አንድ የተምር ዛፍ ዙሪያ ሆሩ። በዚህ አና የሆነ የተጠረገና የመታከሻ ቀዳዳዎች ካሉት ረዥም ግድግዳዎቹ አጠገብ ሆነው የሚገርም ነገር አሰቡ። ይህ የመህኒ ቤት ያህል ነው። በተለይም ወደ ኮፕቲክ ቤተክርስቲያን በኩል ያሉት መስኩቶቹ ሁሉ በጠንካራ የብረት ፍርግርግ የታጠሩ በመሆናቸው ይበልጥ አስር ቤት ያስመስላቸዋል፣ አያሉ ያስባሉ። በከፊል በተከፈተው በር በኩል ባለፉ ቁጥር፣ በወፍራም ድምፅ የሚዜሙ የዳዊት መዝሙሮች ወደ ጆሮአቸው ሲደርሱ፣የለመዱት የአጣን ሽታ ወፍራሙን አፍንጫቸውን ይወጋዋል።

በካቶሊካውያን ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው ድባብ ፍፁም የተለየ ዓይነት ነበር። በእያንዳንዱ መስኮት ላይ ከዳር እስከ ዳር ለተገጠሙት የጣውላ መከለያዎች፣ ውስብስብ ሆነው ለተሠሩት የመስኮት መጋረጃዎች፣ መከለያዎችና ተከፋይ ግድግዳዎች ምስጋና ይድረሳቸውና የቤተክርስያኑ ቅድስተ ቅዱሣን ሙሉ በሙሉ በጨለማ ተውጣል። ይሁን እንጂ ደብዘዛው ቀይ የሻማ መብራት፣ በሰላም ተስብስበው እዚህም እዚያም በተቀመጡ ምዕመናንና ዕቃዎች ላይ እንዲሁም በጥላው ውስጥ በተንተን ብለው ባሉና በአጻኝ የሴባ አይኖች በሚታዩ የወርቅ፣ የዘሆን ጥርሶችና የሉል ዕቃዎች ላይ በስስት ያበራሉ። ኢብራሂም የሚባሉት ሶሪያዊ መነኩሴ ረዥም ሰዐት በሚፈጀው የቅብዓ ሜሮን ዝማጅት ላይ፣ ፖትርያርኩንና የተመረጡ ዋቂት ተሣውስትን በመርዳት ላይ ናቸው። ቅድመ ሁኔታ ከሚጠይቁ የተንዛዙ የፀሎት ሥነስርዓቶች በኋላ፣ ፖትርያርኩ ባለ ሁለት ጆሮ የእብነበረድ ገንባውን ከፅላተ ሙሴው ላይ አነሱ። ከዚህ ተከትሎ ትክክለኛው ቡራኬ ቀጠለ። በመጨረሻም ከቅብዓ ሜሮኑ የተመሰነ መጠን እጅታ ባለው የሸክላ ብልቃጥ ውስጥ ተጨምሮ በዙሽ ታሸገ። ሥራው ያበቃው አመሻሽ ላይ ነበር። ፖትርያርኩ፣ የአምነበረዱን ገንባ ይዘው፣ ወደዋናው ካቴድራል ወደ ሚያስገባው ቦታ ድረስ ሌሎቹ በስልፍ ተከትለዋቸው ሄዱ። እዚያ ሲደርሱ፣ ጭንቅላታቸው ሣያቋርጥ የሚንቀጠቀጥባቸው የጥንታዊት ኮፕቲክ ካህን በሩን ከፈቱላቸው። ብዙ እንዲጠብቁ የተደረጉት ወንድም ፖስኳል ቢናደዱም፣ ለኮፕቲኩ ጳጳስ ጥሩ ገፅታ አሳዩዋቸው። እጅግ

ከፍተኛ የትህትና ታዛዥነት ባለው አገላለፅም ይህን የተከበረ ገንባ ተቀብለው እውነተኛነቱን ለማረጋገጥ በብራና ጠቅልለው አተመብት። ከዚያም በቁንጮኛ ዘዴ ተንበረከኩ።

«ይህ ቅብዓ ሜሮን በሚቀጥሉት ሦስት ቀናት ውስጥ ወደ አቢሲኒያ ይጓዛል፣ ብፁዕ አባታችን» አሉ በእረቢኛ

ጳጳሱም፣ በደምበኛኑ ላይ ለመጫረሻ ጊዜ የቡራኬ የመስቀል ምልክት አማረቆ። አብራሂምም ከካፑቺኑ ጋር ትርጉም ያለው አተያይ ተሰዋወጡ። ወንድም ፖስኳል ጉንበስ አሉና፣ከባርቶሎሚዎ ጋር እየተጓተቱ ግቢውን ቀስ ብለው በማቋረጥ ሁካታና ጫጫታ ወዳለበት ከተማ ዘልቀው ገቡ።

የኮፕቲኮች ቅዱስ ስፍራ በረዛዥም ቤቶች አዋሳኝ በሆነ ቀጭን መንገድ በኩል ያሣያል። ከሞላ ጐደል በሁሉም ቤቶች ደጃፍ ፊት ለፊት፣ በነዳጅ የሚበሩ የፋኖሶች መስቀያዎች በአንስተኛ ኑጋዴዎች ተሠርተው ቆመዋል። መንገዱ እስከ አሁን ድረስ በሕዝብ የተጨናነቀ ሲሆን አሳፊ አግዳሚው በጨለማው ምክንያት እርስ በእርሱ ይላተማል።

«ይሁን ደምበኛን ያዘው። ከኔ ይልቅ ያንተ ዓይኖች ይሻላሉ» አሉ ወንድም ፖስኳል ለአዲሱ ተጠማቂ።

ወጣቱ ወንድም፣ ይህን ብርቅ ጠርሙስ በፍርሃት ስሜት ተቀበለ። በውፃ ከተከበበው ከኢስትራያን የመጣው አገጫሙ ትልቅ ልጅ፣ ለመቀሰስ የመጣ ሲሆን፣ የአካል ጥንካሬ ግን አልነበረውም። እጅግ አጥብቆ የሚፈራው ወላጅ አባቱ፣ ከልጆቹ አንዱን ለአግዚአብሔር አገልጋይነት ለመስጠት ፈልጐ ስለነበረ፣ ይህንኑ ልጁን መረጠው። አባትዬው ይህን ልጁን የመረጠው ከልጆቹ ሁሉ ስስታም ስለሆነና ለመቀሰብ ግን ብዙ የሚያስወጣው ስለነበረ ነው። ከዚያም ወዲህ፣ ባርቶሎሚዎ፣የዕለቱ መቁነን የተትረፈረፈ በመሆኑ በጀግንነት እንደሚዋጋ ወታደር ጌታን በታማኝነት አገልግሏል።

«ልጄ፣ ያ መጥፎ ፖትርያርክ በወርቅ በተጠለፈው ካባው እንዴት ለመታየት እንደሚራመድ አየኸው» ሲሉ እጀቻቸው ነፃ በመሆናቸው በሕዝቡ መሃል በትክሻቸው በዘረፈዱ እየተጋፉ ለመራመድና ቀልጠፍ ለማለት ያልበዛኑት ካህን በመነጫነጭ ተናገሩ። «ይህ ችጋራም፣ የቆንሲሉን የወርቅ ሣንቲም ልስጠው ባልንቀሣቀስ ኖሮ . . .»

ባርቶሎሚዎ፣ ከሽማግሌው ዱካ ላለመራቅ ከኋላቸው በቅርበት ሆኖ በመሮጥ ይከተላቸዋል።

«ስማኝ እስኪ» አሉ ወንድም ፖስኳል። «በርቶሎሚዎ? አንተ ወጣት ነህ። እነዚህ ኮፐቲኮች ዋጋ ቢሶች መሆናቸውን መማር አለብህ። ፍፁም ዋጋ ቢሶች ናቸው። አየህ? እነዚህን ሰዎች በልብሰ ተክህኗቸው ላይ ተመስርተህ የምትገምታቸው ከሆነ፣ በቀይ ክፋይ የማጠንት ዕቃዎቻቸው ላይ ተመስርተህ የምትመዝናቸው ከሆንክ፣ አንዳች ድንቅ ዕውቀትና ቁም ነገር ያላቸው ናቸው ብለህ ማመን ትጀምራለህ። በእውነቱ ይህ ስህተት ነው። የሁሉም ነገር ባለቤት ፓሻው ነው። እንዲጠቀሙበት እንኳ የሚፈቅድላቸው ፓሻው ነው። እነርሱ የሰማኝ ያህል ምስኪን ድሆች ናቸው»

«እኛስ እንዲሁ ድሆች አይደለንም እንዴ?» ሲል ወጣቱ ካፑቺን እያስከለከለ ጠየቀ። የምንኩስና ማዕረግ ለማግኘት ሲፈቀድለት፣ የዕለት ምግባቸውን ለማግኘት እንደሚለምኑ ስዕለት ማድረጋቸውን ሲያውቅ በጣም ተደንቋል።

«ቢሆንም፣ እኛ እኮ ጳጳሳችን አሉልን። ይህ እንኳ አይታይህም?» አሉት ፖስኳል። «እውነት ነው፣ እኛም ድሆች ነን። ይሁን እንጂ፣ ይህ እኛ በአለም ውስጥ ላለን የተለየ ሥፍራ ዋናው መሣሪያችን ነው። እኛ እስካውቶች ነን። እኛን ተስትለው ፈረሰኞች፣ ባለ ጠመንጃዎችና ታላቁ ሠራዊት ይመጣሉ። ኮፐቶች ግን ከኋላቸው ምንም የላቸውም። እንዲያውም የቱርኮች ጦራዴ እንገቶቻቸውን ይቀላዋል። ይህ ሁሉ እያለ ለማስመሰል ሲሉ ቡራኬአቸውን እያቃሰቱ ሲያዝንቡ ለአራት ረዥም ሰዓቶች እንድንጠብቃቸው ያደርገናል»

ከመጀመሪያውም የባሰ ጠባብ የቁልቁለት መንገድ ውስጥ ገቡ። ጭለማው ድቅድቅ ሆኗል። ማንም ሌላ የሚጓዝ ሰው የለም። የከተማውን የጥበቃ ምሽግ ለማለፍና ወደ ገዳሙ በተቻለ ፍጥነት የሚያደርሳቸው አቋራጭ መንገድ ነው።

«አባቴ እባክም ይጠብቁኝ። ምንም ነገር አይታየኝም» አለ በርቶሎሚዎ።

«እንዳን እግርህን ከሌላው እያስቀደምክ በማፈራረቅ ተራመድ፣ አንተ ደደብ ዝሆን። ለመሆኑ በመንፈሣዊው ትምህርት ቤት ምንም አላስተማሩህም እንዴ?»

ወንድም በርቶሎሚዎ የሚችለውን ሁሉ አደረገ። ይሁን እንጂ በድንገት ቆሞ የመታፈን አረታውን ለቀቀውና በፍርሃት መቀበጣጠር ጀመረ።

«ደኮ አምላኬ! አቤቱ ፈጣሪዬ! ምን በደል ፈፀምኩ። እኔስ ጠፋሁ። አቤቱ ይቅርታህን ስጠኝ። አምላኬ አድነኝ። አምላኬ፣ አምላኬ . . . »

ወንድም ፖስኳል በጭለማው ውስጥ እርምጃቸውን እንደገና ወደ ኋላ መለሱት

«አሁን እንግዲህ ምን ሆንክ?»

«ሰኔ ይዘኑልኝ፣ ስለክርስቶስ ሲሉ ይራሩልኝ!» አለ አዲሱ ተጠማቂ፣ ሰውርበጥባጣው መሬት ላይ ተንበርክኮ። «ገንዘው ወደቀብኝ»

«ታዲያ ተስበረ እንዴ?»

«ወይኔ ጉዴ! አምን፣ ወይኔኬኔ በጠፋሁ»

ወንድም ፖስኳል በራሣቸው የቋንቋ ዘዬ ተራገሙ። ይህ ደግሞ ግልፅ ካልሆነውና ሊቋረጥ ካልቻለው መሣላው ጋር ሆኖ በርቶሎሚዎን ይበልጥ አስፈራው

«ለመሆኑ ከዚህ የባሰ ቀርፋፋና ጅላጅል ተፈጥሮ ያውቅ ይሆን?» ሲሉ ደመደሙ ። ከቁጣ ይልቅ ይበልጥ ተናድደው

ልጁ ግን አሁንም ተንበርክኮ እየጮኸ ነው።

«ለዚያው ላይ ተደፍተህ በመጮህህ አሁንም የበለጠ ጊዜ እያጠፋህ ነው። ይህን ያህል ቁም ነገር ስላልሆነ ተነስተህ ና። ስለዚህ ይቅር ብልህ፣ ሰው አይደለህም። አሁንም ላስጠንቅቅህ፣ ሰፅራት እንዳንደርስ ካዘገየኸን ደግሞ ከዚህ የባሰ እጣላሃለሁ»

«ግን እኮ ስለዚህ ቅዱስ ገንዘ ምን ሊያደርጉ ይችላሉ» አለ የማታ አራት ነገር ሲነሣ አንባውን እያደረቀ በመበረታታት።

«አጅግ በጣም ቀላል ነው። ነገ ጧት ከገዳሙ ባሻገር ካሰው መንገድ፣ ከአረብ ግሮሰሪ ሄደህ ከሁለት አብረቀራቂ አዝራር በላይ የማያወጣ የአጌቭ በይት ትገዛለህ»

«አናም እንዲባረክ ወደ ፖትርያርኩ እንወስደዋለን»

«እንዲባረክ!» አሉ ወንድም ፖስኳል የመንፈሣዊውን ተማሪ ጆሮ ሊቀም አድርገው እየጠመዘዙት። «ለመሆኑ ይህን የመሰለ ደደብ ተፈጥሮ ያውቅ ይሆን እንዴ! እንዲባረክ ይለኛ ል! ጣኦት ወደ ማምለክ እየተሸጋገርክ ነው እንዴ?»

«የለም! የለም!» ሲል በርቶሎሚዎ ተነጫነጨ

«ታዲያ የነዚያ የተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች ቡራኬ ምን ይፈይዳል ብለህ ነው? ንገረኝ እንጂ? ከነርሱ ጋር የምንገዘው ወደ አቢሲኒያ ሠርገን ለመግባት ስንል ነው። በመሠረቱ

መለወጥ ያለብን እነርሱን ነው። የተገላቢጦሽ አይደለም። ገዛህ? ቅብዓ ሜሮኑን የተረጋገጠና እውንተኛ ነው ለማለት ብራናው አለን፣ የግሮሰሪውም ዘይት እያንዳንዷን ተፈላጊ ነገር ያሟላል» ይህን ተናግረው የቅብዓ ሜርኑ መያዣ የነበረውን ገንቦ ስብረባሪ ለመከታተን ወንድም ፖስካል በነጠላ ጫማቸው መራቱን ጠራረጉት። ከዚህ በኋላ ስለበርቶሎሚዎ እምብዛም ሳይጨነቁ ጉዟቸውን ቀጠሉ። በርቶሎሚዎም አንድ እጁን ጀሮው ላይ አድርጐ አየተንፋረቀ ተከተላቸው።

ጀን ባፖቲስት ከዜደ በኋላ መሰላቸት የሚገድል ቢሆን፣ መራድ ይሞት ነበር። በፊረንሣውያን ማህበረሰብ ሰፊር መጨረሻ ጥግ ላይ ባለው ቤቱ በብቸኝነት ኖረ። ለመኖሪያው የሚሆነውን በአብዛኛው የሚያገኘው ከፈረንሣይ ቆንስላ ቢሆንም አቪሲኒያውያኑ ባሮቹ ስለተወሰዱበት፣ በግብሣውያንና በአውሮፖውያን ነጋዴዎችም ገሸሽ ስለተደረገ፣ ብቸኛው ጠያቂው ሜትር ዠሪሚ ነበረ። በሜትር ዠሪሚ በኩል አንዲት አረባዊት አገልጋይ መቅጠር ችሎ ነበር። ሴትዮዋ ከድኃ የምትባል በጣም አሮጊት፣ ከሞላ ጐደል ለመኖር ስትል በግድዋ የምትሠራ ነበረች። መራድ ዘንድ በተቀጠረች በሁለተኛው ቀን አንድ ወደል እጅ በሰፊው የናይለን ቀሚሷ ስር ሲነካት ተሰማት። እንዲህ ባለው ከስነስርዓት ውጭ በሆነ ድርጊት ስብዙ ሴኮንዶች ተገርማ ከቆየች በኋላ ወዲያውኑ ወደ ደፋሩ ሰው መለስ ብላ አይመቱ ምት ጥፊ፣ ፊቱ ላይ አሳረፈችበት። ከዚያም ተፋችበትና የርግማን መዐት አከታትላ ወረወረችበት። ሰላም ከሰፈነ በኋላ፣ አሷም ዳግመኛ ትንክሳ ሳይገጥማት ስራዋን ቀጠለች። በዚህ ጉዳይ የተነሣ መራድ በዚህች አሮጊት ሴት ላይ አንዳች የቅድስና ፍርሃት አደረበት። ከድጃን በተመለከተ ግን ይህን የመሰለ የሚያስቆጣ ተግባር ተፈፅሞባት ዝም ማለቷ ባለውለታ ያደርጋታል። ከዚህ ጊዜ በኋላ ግን የሰውዬውን የመንካት ስሜት ከቁብ ሳትቆጥረው ቀረች። ይህ ምናልባት ሰውዬው፣ እርስዋን እንደሚፈልገው ፅቃ አይቶኝ ይሆናል በሚል መራድን ትታ ሳትሄድ ቀረች።

በነዚህ ረኻቦም ሣምንታት አርመናዊው ሌላ ጓደኛ አልነበረውም። ብዙ ጊዜ በካይሮ ጠባብ ጉዳናዎች ላይ ስርሱ ሲባል ከሚደረግ ደስታ በኋላ በመዝናናት መልክ በዘንቱ ሲራመድ ይታይ ነበር። ክረምት ሲገባ፣ በቤቱ ውስጥ ታሽጐ፣ በመስኮት ወደ ውጭ እየተመለከተ

የእንጨት ዶቃዎችን በጣቱ ሲቆጥር ይውላል። አልፎ አልፎ፣ ሜትር ዠሪሚ ጥቂት ቴምር ያመጣለታል። መራድ፣ ቴምሮቹ የውስጥ ጠንካራ ፍሬአቸው እስኪለለስ ድረስ ሲመጣቸው ይቆይና በመጨረሻም በቅፌታ ስሜት ይውጣቸዋል።

መራድ፣ ካይሮ ውስጥ ተስፋ ቆርጠው ከሚኖሩትና ስለ ፖንሴ ስመስማት ውሬ ከሚናፍቁ ቡድኖች ውስጥ ነበር።

ከዕለታት አንድ ቀን፣ ሦስቱ አቢሲኒያውያን ሲመለሱ እጅግ ተደንቆ ተመለከተ። አሌክሣንደሪያ ውስጥ የደረሰባቸውን መጥፎ ዕድል ሰምቶ ስለነበረ፣ ዳግመኛ እንደሚያያቸው ጨርሶ አስቦ አያውቅም። ነገር ግን ሦስቱ ምስኪን ጥቁቁር ሰዎች፣ አንድ ጊዜ ለአስልምና ሃይማኖት ቃለ መሃላ ከፈፀሙ በኋላ፣ ለነፍሣቸው ያን ያህል ከባድ ሃላፊነት አለብኝ ይል በነበረው ሕዝባዊ ቡድን እንደ ዕድላቸው ተብለው ተለቅቀዋል። ለብዙ ቀናት ያመባቸውን ለማግኘት እየለመኑ ሲንከራተቱ ከቆዩ በኋላ፣ ከሁሉም ታሳቅ የነበረው ባሪያ፣ ወደ ካይሮ ተመልሰው መራድን ለማግኘት ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው ያግባባቸዋል። ይህ የቀድሞው ኔታቸው ቢያንስ ቋንቋቸውን የሚናገርና በታማኝነትም የሚያስተዳድራቸው ነው። በመሆኑም ሥርዓት ባለው ሁኔታ ጉዟቸውን ጀመሩ። በቀን አምስት ጊዜ ፀሎት ስለሚያደርሱ ማንም ያስቸገራቸው አልነበረምና በአጭር ጉዞ ካይሮ ደረሱ። ከዚህ በኋላ በቀድሞው ቦታቸው የነበራቸውን ሥራ ቀጠሉ። አሮጊቷም እዚያው ለመቆየት ወሰኑ። ሜትር ዠሪሚም ያገኙ ቸው እዚሁ ሲሆን እንዳያቸው በጣም ተደንቆ ነበር።

«ቱርካውያን እንዲሆኑ ተገድደው ነበር ሲባል የሰማሁ መስሎኝ ነበር» አለው ለመራድ

«ልክ ነው»

«ምስኪናቹ እንሰሶች ክፉኛ መበሳጨት አለባቸው»

«እንደ አውነቱ ግን አልተበሳጇም። ሙስሊም ሲሆኑ ይህ ሁለተኛ ጊዜያቸው ነው»

«ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?»

«እነዚህ ሰዎች የንጉሡ የጦር አስረኞች እንደነበሩ አትዘንጋ። በምርኮ የተያዙት ከአቢሲኒያ ካሉት ሃይማኖት የለሽ ጐሣዎች ነው። የሚያመልኩት ሳሞንን፣ ዛፎችንና ተራሮችን ነው። ከውጭ የሚመጣ ሠራዊት ሲወርራቸው ሁልጊዜም የአሸናፊውን ወራሪ ሃይል ሃይማኖት ይቀበላሉ። እነዚህ ሰዎች በመጀመሪያ ጊዜ የሲናር ሕዝቦች ነበሩ። የሲናሩ

ንጉስ፣ ለአላህ እንዲሰግዱ አስገደዳቸው። ከዚያ በኋላ በኛ ንጉሠ ነገስት ተያዙና የእየሱስ አማኞች ሆኑ። ይሽው አሁን ደግሞ ከመጀመሪያው እምነታቸው በፊት ወደነበሩበት ቦታ ተመልሰዋል። ይሁን እንጂ በልባቸው እነዚያኑ ተራራዎቻቸውን ወይም እኛ ምንነታቸውን የማናውቃቸውን ነገሮች ማመናቸውን እንደቀጠሉበት ርግጠኛ ነኝ»

ሜትር ዝረሚ ሦስቱን አቢሊኒያውያን ተመለከታቸው። በመመለሳቸው ደስተኞች ናቸው። በሩ አጠገብ ቁጢጥ ብለዋል። አሁንም ክስተር እንዳሉና ለመረዳት አዳጋች እንደሆኑ ናቸው። ትክክለኛውና ለራስ ከፍተኛ ክብር የመስጠትን ጉዳይ ልታስቆመው የማትችለው የተቃውሞ መግለጫ ነው። ለዚህም ደግሞ እነርሱ ሀያው ምስክሮች ናቸው።

ከየቂት ቀናት በኋላ፣ የፓንሴን የውርደትና በቅርቡ ለፍርድ እንደሚቀርብ የሚገልፅ ዜና ሙሴ ደ ማይሌ ተቀበለ። ወዲያውም ከዚህ ወር መጨረሻ በኋላ የሚያደርግለትን ድጕማ ሁሉ እንደሚያቋርጥበት ለመራድ አስታወቀው። የዚህን ውሣኔ ለማስታወቅ፣ ሙሴ ማቼ ወደ አርመናዊው ዘንድ መጥቶ ጥቂት ተጨማሪ አስተያየቶችንም አከለበት። የዚህ ብልግና የተቀላቀለበት አስተያየት ዓላማም መራድ ወደ አገሩ ከመመለስ ሌላ ጥሩ ነገር እንደሌለው የሚገልፅና ክርሱ ባህርይ አኒያ ይህ መግለጫ አንዳች ትርጓሜ ይኖረዋል የሚል ነበር።

መራድ፣ በቀጥታ ወደ ሜትር ዝረሚ ቤት ሲገሰግስ ደርሶ፣ አደጋ ላይ መውደቁን እያስቀሰ ነገረው። የመጀመሪያው ሣጥኑም በማህበረሰቡ ውስጥ በሚገኝ አንድ ኒጋዴ ዘንድ በምግብ አዘጋጅነት መቀጠር ሆነ። በዚህ ችሎታው አሌፖ ውስጥ ሠርቷልና ካይሮ ውስጥ ለምን አይሠራም?

ይህ አስተሣሰቡ ከንጉሠ ነገስቱ የተተበለውን የአክብሮት ተልዕኮ እንደማንኪስስ እንደሚሆንበት ዝረሚ አስረዳው። በሌላ በኩል ጆን ባፕቲስትን ማዳን የሚቻልበት ዕድል እንኳ ቢኖር፣ ይህ ሊሆን የሚችለው የታሪኩን አውነታ በተቻለ መጠን ጠብቆ በማቆየት ነው። ሲመለስ አምባሳደር ይዞ እንደሚመጣ ቃል ገብቷል። ስለሆነም የተባሉው ሰው፣ወጥ ውስጥ ተዘፍቆ ሊገኝ አልቻለም ከማለት የተሻለ ይሆናል።

በርግጥ ዝረሚ ለመራድ ብልህ ምክር ለመስጠት የሚችል አይደለም። እርሱም ቢሆን ቬርማይለስ ውስጥ በርግጥ ምን እንደተከናወነ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ አይደለም።

በሌላ በኩል፣ ሁኔታዎች አዲስ መስመር የመያዛቸውን፣ ማለትም ዱ ሮውሌና ብዙት ያለው ሀጋዊ ኤምባሲ መሄዱ እንደማይቀር በመግለፅ የሚረብሽ ዜና ፍራንቾይዝ ነግራዋለች። ምስኪኑ ዝረሚ ከዚህ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለበት አላወቀም። ፖንሴን የሚከላከል ቢሆንም ጓደኛው ውርርዱን እንደተሸነፈ በፍፁም አምኗል። ሙራድ ክብር ያለው የንጉሡ መልዕክተኛ ሆኖ እንዲቆይ አደፋፍሮታል። በሌላ በኩል ቆንስላው ለአርመናዊው ምንም ተቀባይነትን ስላልሰጠው የራሱን ተልዕኮ አያደራጀበት ነው። በአጭሩ ቁርጥ ያለ ውሣኔ ለመስጠት ያልቻለበት ትልቅ ፈተና ውስጥ ወድቋል።

ይህ ሁሉ እየሆነ ግን የመድሃኒት ቅመማና ዝግጅት ሥራውን ባለማቋረጥ፣ በፖንሴ የተፃፉትን የህክምና ትዕዛዞች እየሞላ ይጠቀምባቸዋል። እንዲያውም ከሙፍቲዎች ፍላጐት ውጭ፣ አስፈሪው አዲሱ ጋሻ መሃመት ቤይ፣ ተቀብሎት በምስጢር የርሱ መድሃኒት አዘጋጅ አድርጐታል።

ሌላው አስቸጋሪ ነገር ደግሞ ፍራንቾይዝ በርሱና በቆንስላው መካከል ባለማቋረጥ እንደ መልዕክተኛው ጥልቅ ትላለች። ስለርስዋ ያለው ሰሜት ከቀን ወደ ቀን እያየለና እየበረታ ቢመጣም፣ ይህንኑ በግልፅና በታማኝት ሊገልፅላት መቻል አለመቻሉን ርግጠኛ አይደለም። አሊስ፣ ፖንሴን ለማግኘትና ለማዳን ስትል፣ ገዳም እንባለሁ በሚል ሰበብ ወደ ፈረንሣይ ለመሄድ ያቀደችውን ስትነግረው፣ ወጣቷን ሴት ነፃ በማድረጉ ጉዳይ ላይ እንዲረዳትና በጉዞዋም ላይ እንዲያጅባት ስትጠይቀው፣ ሊጥም የሚችለውን ችግር ሁሉ ቢገምትም በመጨረሻ ፀሐይ የምትወጣ ያህል ስሜት ዝረሚ ተሰማው።

በመጨረሻም ሊንዝዘብ፣ ሊንቀሣቀስና ሊታገል ብቁ ሆነ። እንደርሱ በመከራ የተገረፈን ሰው ከዚህ ካለመንቀሣቀስና ከመደበቅ የባሰ የሚከፋና ሊሰማማው የማይችል ነገር የለም። ከዚህ በኋላ ጫማዎቹን ወለወላቸው፣ ጕራዴውንና ሽጉጡንም አፀዳቸው። በደስታም ዘመረ።

አዲሱ አቅድ፣ አንዱን ሰው ከጨዋታው ውጭ አደረገ። ይህም ሰው መራድ ነበር። ዝረሚ ትዕግስትን እንዳልሰበከው ሁሉ፣ በጣም በችኮላና ትህትና እንኳ በጐደለው ሁኔታ ሣጥኑን ቀይሮ፣ ልክ ቆንሲሉ እንዳደረገው ሁሉ ወደ አቢሲኒያ እንዲመለስ መከረው። ይህንንም ሰማሣክት የሚያስችለውን ሁሉ ለማድረግ፣ ጥቂት የጭነት አጋሰሶችን ሊገዛለትና ጥቂት ገንዘብ ሊሰጠው እንደሚችል ሁሉ ሃሣብ አቀረበለት።

ነገሮች ሁሉ በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉና ሙራድም የቱን መንገድ መያዝ እንዳለበት ሣይወስን በፊት፣ ከዕለታት አንድ ቀን ማለዳ ሁለት እንግዶች ሰዎች ወደ ቤቱ መጡ።

ሁለቱም ሰዎች ፈረንሣውያን ሲሆኑ፣ ከዚህ በፊት ማንም ሰው በማህበረሰቡ ሰፈር እይቷቸው አያውቅም። ሰዎቹ ባለፈው ቀን መምጣታቸውን ይናገራሉ።

«ክቡር ወእም ክቡራን ጌታ ሙራድ፣ የኢትዮጵያ አምባሣደር እርስዎ ነዎትን?» ሲል ከሁለቱ ጐብኚዎች ረዥሙ ተናገረ። ሰውዬው፣ አርባ አመት የሚሆነው ቀጭንና ሌላው ቀርቶ ሲናገር እንኳ መልኩን ሰይቶ ይህን ይመስላል ሊሉት የማይችሉት ነው።

«መቼም ሌላ ሰው የለም» አለ ሙራድ ከተቀመጠበት እየተነሣ። እንዲህ ባለ ደስ የሚል አክብሮት ማንም ሰው ሣይጠራው ረዥም ጊዜ አልፎታል። «እሺ የሆነ ሆኖ ምን ልርዳችሁ?»

«የመጣነው ከፖለስታይን፣ ማለትም በርግጥ ከእየሩሳሌም ነው። እኔ ሀብርት ዴ ሞኔሃውት ስባል ይህ የሥራ ባልደረባዬ ደግሞ ግሪጐሪ ሪፋው ይባላል። ሁለታችንም የሣይንስ ሊቃውንት ነን። እርሱ ባልደረባዬ የጂአግራፊ ሊቅ ሲሆን እኔ የስነ ሕንፃ ንድፍ ጠቢብ ነኝ» አለ ቀለል የሚለው ሰው በተረጋጋ ሁኔታ

ከመጀመሪያው ጉብኚ ይልቅ ወጣት የሚሆነው ሁለተኛው ሰው፣ በባልደረባው ንግግር መስማማቱን ለማሣወቅ ቄንቅሳቱን በአምንታ አነቃነቀ። ይህ ሰው እጅግ ያልተለመዱ ከሚመስሉት፣ የገረጡና ከሞላ ጐደል ነጭ ከሆነው በሙራድ ላይ እንደ ሁለት የሚያብረቀርቁ የሸክላ ዝርግ ሣህኖች ካነጣጠሩት አይኖቹ በስተቀር ሊታወስ የሚችል ምንም ነገር የለበትም።

«ከአቢሲኒያ ቤተመንግስት የተላኩት ባለሙሉ ሥልጣን አምባሣደር መኖሪያቸውን ካይሮ ውስጥ መመስረታቸውን ሰማን። ስለዚህም የክቡርነትዎን ድጋፍ እናገኛለን በሚል ተስፋ ወደዚሁ መጣን»

«አቅሜ የፈቀደውን ሁሉ አደርጋለሁ» አለ ሙራድ፣ግብዝነቱ አገርሽቶበትና አውነት ተነግሮ ከሆነ በስብሰባ ላይ እንኳ ሳይቀር ጀርባውን ሲያዞርበትና አንጉቱን ሲመልስበት የነበረውን የሙሴ ዴ ማይሴ ሁኔታ አየታሰበው።

«አስቀድመን ከፍ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን። በጣም እናመሰግናለን ክቡር ሆይ» አለና የቻይና ዓይን ያለው ሰውዬ እንዳደረገው ጥቂት ዘግየት ብሎ ጉንበስ ብሎ ተናገረ።

«በአስፖኘ የሮያል የሣይንስ አካዳሚ ድጋፍ ተሰባስበን የመጣን የአሣሽ ቡድን አባላት ነን» አለ ቃል አቀባዩ። «ከሣምንቱ ማብቂያ በፊት ሌሎች አራት ሳይንቲስቶች እዚህ ደርሰው ይቀላቀሉናል። እነርሱ የተነሱት ከአውሮፖ ነው። ሆኖም አሌክሣንደሪያ መድረሣቸውን የሚገልፅ መልዕክት ልከውልናል። ስድስታችንም እርስዎ ወደሚወክሏት አገርዎ ወደ አቢሲኒያ እንሄዳለን። ስለዚህም ክቡርነትዎ ስለአገርዎ ንጉሠ ነገስት ልናውቅ የሚገባንን ሁሉ እንዲያሣውቁን በአክብሮት እንጠይቃለን»

ሙራድ፣ በግራ እጁ ይዟት የነበረችውን የትንሽ አበባ አንጓ ጭምቅ አደረገ። አምላኬ ሆይ በመጨረሻ ደረስክልኝ ሲል አሰበ።

«ጌቶቼ፣ በተልዕኳችሁ ላይ እናንተን መርዳት ለኔ ታላቅ ደስታ ነው» ሆኖም ዓላማችሁን ልትነግሩኝ ይገባል። ምናልባት ንጉሴ፣ ጌታዬ የውጭ አገር ሰዎች ወደ ግዛታቸው እንዳይገቡ ያወጁትን አገዳ አታውቁም ይሆናል» አለ በሃዘን።

«ክቡር ሆይ እናውቃለን። የኛ ተልዕኮ ሰዕውቀቱ ሲሉ በመንገት እንደሚጓዙ ሰዎች ዓይነት ብቻ ነው። ለምሳሌ የጂአግራፊው ሊቅ፣የዋናዎቹን ወንዞች መነሻ ያጠኛል፣ ደክተሩ፣ ማለቱ በመሣክላችን አንድ ሣኪም አለን፣ እርሱ በዚያ አገር ያለውን ሰብይ የሕመም ዓይነት ይገልፃል። አያንዳንዳችን በተፈጥሮ በአዕምሯችን ያሰውን የማወቅ ጉጉት ለማርካት በአዲስ አገር ውስጥ የምናገኘውን ለመረዳት እንጥራለን»

«ወርቅ ፍለጋ መቼም አትሄዱም፣ አይደለም እንዴ?» ሲል ሙራድ ገሳ ባለ ድምፅ ጠየቀ።

«እውነቱን ለመናገር፣ ይህ የዘመቻ ጉዞ እኛ ልናገኝ ከምንፈልገው ነገር በላይ ወጭ ይጠይቀናል። ክቡር ሆይ። ስለዚህ ወርቅ አንፈልግም። ወርቅማ የራሣችን አለን»

ይህ የአነጋገር ቅላፄ ደስ የሚል ነው! ሲል ሙራድ አሰበ።

«ጌቶቼ፣ ወደ ንጉሡ መምጣታችሁን ብቻ ሣይሆን፣ ከዚያም በላይ ቢሆን አስታውቃለሁ።» አላቸው

«ድንቅ ነው፣ ክቡር ሆይ?»

«እንዲያውም አጀቤአችሁ አደርሣችኋለሁ»

«ይቻላል እንዴ?» ሲል ሞኔሀውት ጠየቀ

«በአጋጣሚ እኔ ልመለስ በተዘጋጀሁበት ዋዜማ ላይ ነው የመጣችሁት። አምን ነገ ወደ ጌታዬ የሚያደርሰኝን መንገድ እጀምራለሁ።»

«ነገ! ታዲያ እኛ በቀረን ጊዜ ውስጥ መዘጋጀት ፈፅሞ አንችልም። »

«ጉድ ነው! እኔ ደግሞ ልጠብቃችሁ አልችልም» አለ ሙራድ በንርማ ሞገስ አነጋገር።

«የሥራ ባልደረባዎቻችን ሁሉ እስኪሰበሰቡና ለዘመቻው የሚያስፈልጉንን ቁሣቁሶች በሙሉ እስክናዘጋጅ አንድ ሣምንት ያህል ገዜ ይወስድብናል»

«ጌቶቼ ፣ ጉዞዬን ለማቆየት መሉ በሙሉ ዝግጁ ልሆን ብችል እንኳ፣ አመኑኝ የሚሆን ነገር አይደለም»

«ምናልባት ምክንያቱን ብጠይቅዎትና እኛ ልንረዳ . . . »

«አ ጌቶቼ፣ ምክንያቱ ቀላል ነው። ተልዕኮዬን እንድፈፅም ንጉሠ ነገስቱ የተወሰነ መጠን ገንዘብ ሰጥተውኝ ነበር። ያ ገንዘብ አሁን ተሟጥጧል። ከውጭ አገር ሣይል ደግሞ የመጨረሻዋን ትንሽ የገንዘብ መጠን የመቀበል ጥያቄ ላነሣ አልችልም። የፊረንሣይ ቆንሲል ሊረዳኝ ፈቃደኛ ሆኖ ቀረቦ ነበር። ነገር ግን እንደ ዲፕሎማት ሰክብረ ስል እምቢ አልኳቸው። ስለዚህም መሄድ ይኖብርኛል»

«ይገባናል» አለ ረጋ ያለው ጉብኚ። «ነገር ግን ክቡርነትዎ ለኛ አገልግሎት ሲሉ ጥቂት ቢቆዩልን፣ ይህ እንዲሆን ያደረገው ቡድን ደግሞ የመሰንበቻዎን ወጭዎች ለመደጉም ግዴታ ይኖርበታል። እርስዎም ቢሆኑ በርስዎ ላይ የጣልንብዎትን ዕዳ እንደተነነልዎ አድርገው ሊወስዱት ይችላሉ።»

«እንዲህ ከሆነ ምንም ችግር የለም» አለ ሙራድ።

ቀሰል የሚሰው ስውዬ ዘጣም ዉሚገርም ፍጥነት፣ በራስ የመወሰን ነፃነትና ብልሀት ቀልጠፍጠፍ በማለት፣ እጅን ወደ ልብሱ በመሳክ አንድ የቆዳ ቦርሣ በማውጣት በአምባሣደሩ እግር ስር አስቀመጠ።

ከዚህ በኋላ ተጨማሪ ቆይታ የሚደረግ ከሆነ ተጨማሪና እንደቆይታው መጠን ለረኽም ጊዜ የሚከፈል ክፍያ እንደሚኖር ስምምነት ተደረገ። ይሁን እንጂ ሣይንቲስቱ፣ዝግጅታቸውን ከአንድ ሣምንት በላይ ላለማቆየት ቃል ገቡ።

«ክቡር ሆይ፣አንደ የመጨረሻ ጉዳይ ግን አለ። ስለዝግጅታችንና ስለዕቅዳችን ቆንሲሉ በጭራሽ እንዲያውቅ ባይደረግ እንወዳለን። ምንም እንኳ አስፖንና ፊረንሣይ በአሁኑ ገዜ ወዳጆች ቢሆኑም፣ ነገ ግን . . . »

«ስጋት አይግባችሁ» አለ ሙራድ

ሁለቱ ሰዎች በድጋሜ ጉንበስ በማለት፣ አንደ ሺህ አንድ ጊዜ አመሰገኑት። ሰዎቹ ወዲያውኑ እንደሄዱ ሙራድ ቦርሣውን ለቀም አደረገው። ሲቆጥረውም አሥራ ሁለት አቡኬል ኤክስ ሆነለት። በዚህም በደስታ ጮቤ ረገጠ።

የዚያን እለት ምሽት ራሱንም በአመፀኛነት እያዘናና በካራቫን ሴራይ ውስጥ ስድስቱን ጨረሰ።

4

ፊረሰኛው ሌ ኖይር ዱ ሮውሌ፣ በቆንስላው ውስጥ በተፈጠረው ሁኔታ ክፉኛ ተጨንቋል። በመጀመሪያ ላይ በአንድ አማፋሪ ነገር ውስጥ የገባ መስሎት ሰውነቱ ሁሉ ሽባ ሆኖበት ነበር። በኋላ ምንም ነገር ሳይነገርበት መቅረቱን ሲያውቅ ጭንቀቱ ሁሉ እንደ ማዕበል ከሳዩ ላይ ተጠርጎ ጠፋለት። ነገር ግን፣ ለአሲስ ያለው ፍላጐት ግን እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ አሁንም ጠንካራ እንደሆነ መሆኑን አወቀ። አሁንም እንኳ የወደፊቷ እመምኔት ፍቅሯን እንድትሰጠው ለመለመን፣እንዳለፈው ጊዜ የበሯን መዝጊያ ለመሚጠጥ አጉል የብልግና ድፍረት ይሰማዋል። አዕምሮው ሙሉ በሙሉ በቆንሲሉ ሴት ልጅ ስለተያዘበት ወደ ውጭ መውጣት ተው። ራሱን ፣በርሷ ቦታ አድርጐ ለማሰብ ቢሞክርም ከንቱ ሆነበት። ምክንያቱም እርሷ ክፍሏንም ገጿም አድርጋው ዘግታ ቀርታለች። በአጭሩ፣ ምልክቶቹ የተለመዱ ዓይነቶች ነበሩ። በፍቅር መያዙን ለንደኛቹ በፈዝ መልክ እየሣቀ ነግሯቸዋል። ሆኖም ግን የራሱ ድክመት አስጠላው። ማንኛውም አይነት ድክመት ይቅር ሊባል እንደሚችል ቢያምንም፣ ይህኛው ግን እኩያህ ባልሆነ ሰው ላይ ጥገኛ የመሆን የደደብነት አባዜና፣ሌላው ቀርቶ የዚሁ ሰው ትግል ያንተን ፍላጐት ጨርሶ የማያግዝ ሲሆን ፣ይቅር የማይባል ነው።

ቆንሲሉ፣ ሴት ልጁን እንዲሰጠው የጠየቀውን ሰው ልመና ባለመቀበሉ፣ ለዱ ሮውሌ ቅሬታ በከፍተኛ ደረጃ ተጠያቂው ራሱ እንደሆነ ሰለተሰማው፣ ለይስሙላ ያህል ለፈረሰኛው ወሰን የለሽ ወዳጅነትን ማሣየት ጀመረ። ምስኪኑ ወጣት ግን ስለኤምባሲው ያለው ጉጉት እንኳ የጠፋበት መስሰ። ቆንሲሉም፣ ስለቀጣይ ዕቅዱ ከመግለፅ ራሱን ቆጠብ በማድረግ፣ ውስጥ ውስጡን ግን ለቅፍስቱ የሚያስፈልጉ ቁሣቁሶችን ማሰናዳትና፣ በሚያቋርጠባቸው መስመሮች ላይ ለሚገኙ ገቸሮች የሚሰጡ ገፀ በረከቶችን በመግዛት ማዘጋጀቱን ቀጠለ። በአጭሩ፣ ዱ ሮውሌ ከትካዜው ሲመለስ ሁሉንም ነገር ተዘጋጅቶ እንዲጠብቀው በማድረግ እየሠራ ነው። ይህ ሁሉ እየተከናወነ ወጣቱን ሰው ጠዋትና ማታ በቢሮው ውስጥ እየተቀበለ በማፅናናት ሁኔታ ያጋግረዋል።

ማንኛውንም ሰው፣ ሃዘኑን ለሌሎች ሰዎች የማካፈልን ያህል የሚያፅናናው ነገር የለም። የአግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ለልበ ስውዎች የሚላክውን ታላቁን የፍርደ ጉዳይ፣ ቆንሲሉ በየዕለቱ ባለማቋረጥ ሲናገር በመስማቱ፣ ዱ ሮውሌ ለራሱ ይበልጥ ማዘን ጀመረ። የሙሴ

ዴ ማይሌ የተዋበ ንግግር የጥንቱን ጊዜ የሚመስል ነው። በመጨረሻ ላይ ግን ይህ አማኝ ሊሆን ትንሽ ቀርቶት የነበረው ወጣት፣ ቆንሲሉ፣ አንድ ጨዋ ሰው ድክመት ይኖርበታል በሚል ስለሚያምን ብቻ፣ ስለተከበረው ፍቅር የሚናገራቸውን የክብሩና የጸድቅ ሰው ንግግሮች ለመስማት ትዕግስት እያጣ መጣ። ዱ ሮውሌ በበኩሉ፣ የሰውዬውን ወዮመድ ለማዝሸፍ ልጅህን በሚመለከት የምመኘው ሁለት ነገሮችን ብቻ ነው፣ አንድም ለአንድ ለሊት እንደገና አብራኝ እንድታድር፣ ሁለተኛም ከዚህ ሰቅቆ የመሄዱ የኔ ቢሆን ብሎ ለመናገር እጅግ በጣም ተገፋፍቶ ነበር።

ይህን ሃሣቡን ግን የበላዩ ለሆነው ሰው አውጥቶ ከመግለፅ ተቆጠበ። ይሁን እንጂ ለራሱ ሲናገራቸው በመጀመሪያ ላይ እንዳሰበው የፍቅሩ ጉዳይ ይህን ያህል ተስፋ የሚያስቆርጥ ሳይሆን ይችላል ሲል አሰበ። ይልቁንም ቀደም ሲል የተጉዳው የርሱ ፍላጐትና የርሱ የራስ ማክበር ስሜቶች ናቸው። የቆሰለ ሰው በመጀመሪያ የሚሰማው ስቃይ ያሰደነግጠዋል። በኋላ ግን ስለደረሰበት ቁስል ቀላልነት ግልፅ የሆነ ግምት ለራሱ ሲሰጥ፣ በመበረታታት እኖራለሁ ብሎ ያምናል። እንደዚሁም ሁሉ ዱ ሮውሌ ሙሉ በሙሉ በፍቅር እንዳልተሸነፈ ሲገነዘብ፣ ራሱን በማድነቅ ተዕናና። በመቀጠልም ወደ ቀድሞው እርሱነቱ ለመመለስ ደፈረ። በሚቀጥለው ዕለት በአንድ ነጋዴ ቤት የካርታ ቁማር ጨዋታውን ቀጥሎ ብዙ ተበላ። በመበላት፣ ብዙ በመጠጣትና ሌሊቱን በቱርካውያን አገናኞቹ ሳቢያ ቤቱን ከሞሉ ወጣት ቆነጃጅት መካከል ከሁለቱ ዳንሰኞች ጋር አግለፈ። ብአጭሩ ራሱን ወደ አልሆነ አቅጣጫ ከመውሰድ ገታው።

የግል አስተያየቱ ብኽ ባይልበት ኖሮ፣ ለአፍታ ያህል እንኳ ሣያያት ሊቆይ እንደማይሆንለት ሁሉ፣ አሊስን በሚገባ ሊያያት ይችል ነበር። የግል አስተያየቱ ብኽ ስላለበት፣ ሊያያት በከፊል ያበደች፣ በሌቶች ገጸም ውስጥ ጥሩ ሆና መገኘት የምትችልና ዕድሜዋን በሙሉ ከርሱ ጋር በርህራሄ የተጋራችውን አጭር የደስታ ጊዜ በትዝታ እያስታወሰች የምትኖር ሌት አድርጉ አስባት።

ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሣ የሚታይበትን የክህደይ ሰውጥ፣ ሙሌ ማይሌ ወዲያውኑ እንዳያውቅ ዱ ሮውሌ ተጨነቀ። በአጭር ጊዜ ውስጥ ጤንነቱ እንደሚመለስ ስማስመሰል ቢሞክርም፣ ቆንሲሉ ግን ከምን ጊዜውም በበለጠ መሻሻሉን ለማጠናከር ተጨነቀ። የዱ ሮውሌን አምባሲ ወደ አቢሲኒያ መንገዝ ያፀደቀው መሆኑን የሚያረጋግጥ የሚኒስትሩ ደብዳቤ ከፈረንሣይ ደረሰ። ሙሌ ዴ ማይሌም፣ ከቆንስላው ሣጥን ውስጥ አስቀድሞ በገፍ ዝቆ

ለመውሰድና ተንገርቹም ምንም ነገር እንዳማይቸግራቸው ለማድረግ ሥልጣን እንዳሰው አመነ። ይህ ተልዕኮ ደግሞ ይፋዊ ማንነቱን በማያወላውል መልክ ለሁሉም፣ በተሰይም ለኢትዮጵያውያን ግልፅ ሊያደርገው ነው። ይህ ተልዕኮ ቀደም ሲል በፖንሲ መሪነትና አገልጋዩ ናቸው ተብለው አብረውት ከተጓዙት ከዮሴፍ ከርፋፋ ዝግጅት ፍፁም የተለየ ይሆናል።

የዱ ሮውሌ ኤምባሲ ቅፍለት፣ የተንቆጠቆጠ ኮርቻ የተጫኑ ሃያ ሰስት ምርጥ የግመል ዝርያዎች ያሉበት ይሆናል። የቅፍለቱ መሪ በላክ ተብሎ የሚጠራና የሲናር ንጉስ ወኪል የሆነ ቱርካዊ ነው። ቆንሲሉ ቅር ቢሰውም፣ ዋናው አስተርጓሚም ይህን ዘመቻ በአስተርጓሚነት ለማገልገል እንዲችል እንዲቀላቀል ስለተደረገ ይለያያሉ። ዱ ሮውሌ፣ ሙሉ በሙሉ ራሱን ከገዛ በኋላ፣ ቀሪዎቹን ተንገሮች የመምረጡ ሃላፊነት ሙሉ በሙሉ ለርሱ እንዲተውለት ጠየቀ። ለቆንሲሉ ማይነግረው፣ ባለፈው ዓመት ካይሮ የገባና ራሱን በመጥፎ ምግባሮች ለይቶ ያሣወቀ አንድ ወጣት ፈረንሣዊን እንደ ዋና ረዳቱ አድርጉ መረጠ። ዱ ሮውሌ፣ በካርታው መጫወቻ ቦታ፣ ሩሚላክ ተብሎ የሚጠራ ሰውም ተዋውቋል። ወጣቱ ሩሚላክ ተሰማማጅ የሆኑትን የኬይሬኔ ሃብታሞችን በጫወታው ላይ በማታለል የሚበልጣቸው ነበር። ማንም ሰው፣ ዱ ሮውሌ በቁማር ጨዋታው ላይ ማጭበርበር እንዲደረግ አመራር ይሰጣል ብሎ የሚጠረጥረው ስለሌለ፣ ሩሚላክን ለይቶ አወቀው። ከዚህ በኋላ የሩሚላክን ስም ከማጉደፍ ይልቅ በሽርክና ተወዳጀው። እነዚህ በቅርብ የተሣሰሩ ሰዎች ስማቸውና ዝናቸው ተሰራጨ። እንዲያውም በከንቱ ውዳሴ ይኩራሩ የነበሩት አንሏቸው፣ ጥንዶቹ ሊሸነፉ የማይችሉ ጠንካሮች ናቸው ተብሎ ተፈሩ። ሩሚላክ ለመጠጥ ጠንክር ያለ ፍላጐት ያለው ከመሆኑ በስተቀር ገና ልጅነትም ያለው ስለሆነ ሽንቃጣና ደስ የሚያሰኝ ቁመና አለው። በጉንጮቹ ላይ ግን ወደፊት ፊቱን የሚሸፍኑት ነገሮች እጅግ ጥቃቅን ቀያይ መስመሮች ብቅ ብቅ እያሉ ነው።

ዱ ሮውሌ፣ ከዚህ በተጨማሪ ተመሣሣይ ዓይነት የሆኑ ሁለት ሌሎች ሰዎችንም መረጠ። እነዚህኞቹ ያለባቸው ችግር ከበራተኞቹ ይልቅ አነስ ያለ ነው። አንደኛው፣ ቀደም ሲል ፖሪስ የነበረ ሲሆን፣ ሥራውን ግልፅ ባልሆነ ምክንያት ሰቅቆ በአሁኑ ዘዜ ካይሮ ውስጥ ያለሥራ የተቀመጠ ሰው ነው። ከአርሌስ የሆነው ወርቅና ብር አንጥረኛው፣ ምናልባትም የሸምላ ተዋጊና የሃሰት ሰነድ የሚያዘጋጅ ሆኖ በውጭ አገር መኖርን የመረጠ ነው። እነዚህ ሰዎች በብላሽ ጠባያቸው ስማቸው የሚጠቀስ ናቸው። ሁለቱም ሰዎች የሚጋሩት ጠባያቸው

ስድነትና እጅግ ሲበዛ ራሣቸውን ያለመቆጣጠር ባህርያቸው ነው። ከዚህ ቀደም ሁለቴን ሰዎች ፊፅሞ አግኝቷቸው የማያውቀው ሙሴ ዲ ማይሌ፣ በምርጫው ደስተኛ አልነበረም። ይሁን እንጂ ቁመናቸው የሚያምርና የሚያስደስት ስለሆነ አምኖ መቀበል ነበረበት። ዱ ሮውሌ፣ ስማሃመንና ራሱንም የበለጠ ነፃ ለማድረግ በማሰብ «እንዲህ ያለ ብዙ አደጋና ፈተና ባለበት ተግባር ውስጥ ፈታዴኛ ሆኖ የሚሣተፍ ንፁህ ሰው ማግኘት ፊፅሞ አስቸጋሪ ነው» ሲል ነገረው።

በዚህ ቡድን ውስጥ ያለው አያንዳንዱ ሰው ሹመት ባይኖረውም፣ ስም አለውና አሥር ወይም አስራ ሁለት የሚሆኑ ከማህበረሰቡ ውስጥ ዝቃጭ የሆኑት ምስኪኖች ተመረጡ። እነዚህ ከወታደራዊ ሙያ የከዱ፣ ከሕግ በመደበቅ የሚሸሹ፣ የሁሉም አይነት ቅጥረኞች የሆኑትን ሰዎች ዱ ሮውሌ ሲመርጣቸው እንደተዋጊ ኃይልም አስቧቸው ነው።

የተጓዥ ሠራዊት ሁለት መሪዎች በመጀመሪያ ያጋጠማቸው ሥራ፣ ከቆንስላው የተሰጣቸውን ድንጋጤ ቅፍለቱ ተሸክሞ ሊያንገላቸው በሚችላቸው ፅቃዎች ላይ ወጭ ማድረግ ነበር።

የዱ ሮውሌ ሃላፊነት በጣም ቀላል ነበር። ሽሬክቹም ይህንኑ ወዲያውኑ ተገንዘቡ። አምባሲው የማስመሰያ ስበባቸው አንጅ እውነተኛ ተግባራቸው ንግድ ነበር። በተቻለ መጠን ገፀ በረክቶቹ በአነስተኛ መጠን ይሆኑና ጭነቱ ሊሸጡም ወይም ሊለወጡ በሚችሉ ሽቀጦች ይተካል። እግረ መንገዳቸውን ለመጠቀምና አቢሲኒያ ውስጥ እጅግ ከፍ ባለ ልዋጭ ሃብት ለማከማቸት የራሣቸውን ሽቀጦች በአንድ ላይ አደረጉ። በርግጥ እቢያ በሚሄዱበት ቦታ ሁኔታዎች አላስበዋቸው ሃብታቸው ሌላ ከፍ ያለ ምኞት ውስጥ በክትታቸውስ? የጦር ሠራዊት ቢዝና፣ ከሌላ ሃይል ጋር የተሣካ ግንኙነት ፈጥረው ምናልባትም ሥልጣን መንጠቅ ቢችሉ? ለምን አይሆንም? በተጓዥ ሠራዊቱ መሣል ጤናማ ወዳጅነት ዳበረ። ዱ ሮውሌም የአደናቆታቸው ማዕከል ሆነ። የመሪያቸው ከመጠን በላይ አስተዋይ የመሆን፣ የድፍረቱ፣ የተጠራጣሪነት ባህርይው ታክሎበት፣ እርሱን የምድር ገዥ፣ ራቸውን ደግሞ አስከ ግዛቱ ድረስ አጅበውት የሚጓዙ ሠራዊቱ መሆናቸውን አንድም የሚጠራጠር አልነበረም።

ዘመቻው የሚገጥመውን አደጋ በተመለከተ ሰዎቹ በመጠኑ ለየት ያለ አስተያየት ፈጥረዋል። እያንዳንዱ ባለፈው በጀብድ የተሞላ ሕይወቱ፣ የተለያየና ያልተመጣጠነ አደጋን አምልጧል። ረሃብንና ጥምን ለመከላከል፣ ማንም ሰው የሚያስፈልገው በበቂ መጠን ሥንቅ ሊሰጠው ይገባል። የአገሬውን ተወላጆች በሚመለከት፣ እነዚህ በምሥራቅ ሚዲተራኒያን የሚገኙ ልምድ ያላቸው ሰዎች ከብዙዎቹ ነብያውያን፣ ሱዳናውያንና፣ ሌሎች ከመካከለኛው አፍሪካ የመጡ አገልጋይ የአገሬውን ተወላጆች በተመለከተ የሚደራደሩባቸው ቀላል ፖሊሲዎች አሏቸው። ከነዚህ ሰዎች ጋር በጥሩ ብልጠት ሊፈታ የማይችል ምንም ዓይነት ችግር የለም። ሰዎቹ ብዙ ጉራዴዎች፣ ሽጉጦችና ቀስቶች ታድሏቸዋል። ይህ ሁሉ ላልለለመነት ሕዝቦች ለመሸጥ ወይም ራሣቸውን አንዳከላከሉበት ተብሎ ሣይሆን፣ በየዋህ ስሜት አንድ ያልተለመደ ነገር በመውደድ፣ እርስ በርሣቸው አንዳጨራረሱ ሲባል መሆኑን በሚገባ ያውቃሉ።

ከዚህም ባሻገር ከአገሬው ተወላጆች ጋር በሚኖር ግንኙት፣ ማንም ቢሆን አስቀድሞ መሥራት ያለበት ከሴቶች ጋር ነው። ምክንያቱም ሴቶቹ ከወንዶቹ ይልቅ ደፋሮችና በማይለዋወጥ ፅኑ አቋም ውሣኔ ሆነው የሚኖሩ ስለሆነ ነው። ስለዚህም ዘማቹ፣ ርካሽ የሆኑ ቀለማት የበዙባቸው ጨርቆችን፣ የሚንሿሹ ጌጣጌጦችና ሌላው ቀርቶ በአንደ ቪኔሲያዊ ኒጋዴ በቅርቡ ወደ ካይሮ የገቡትና በአውሮፖ ትያትሮች የሚገኙት መልክን አጣምመው የሚያሣዩ መስተዋቶች ሳይቀሩ ተገዝተዋል።

እነዚህ ዝግጅቶች እየተከናወኑ ባሉበት ጊዜ ውስጥ፣ አሊሰም የራስዋን መብነኛና በጣም ጥንቃቄ የሌለባቸውን ዝግጅቶች ታደርግ ነበር። ከአባቷ ፊት ርቃ በክፍሏ ለመቆየት ስለለመነችው፣ እርሱም በእፎይታ ስሜት ፈቅዶላታል። በሌላ በኩል ባለፉት ቀናት ሥራዎቹን ሲያጎበጥጡ የከረማቸውን የኤጊኩቲስ ሣጥኖችን በማውጠንጠን አዕምሮው ተይዟል። ይሁን እንጂ ምንም ማይጨነቅ ሁሉንም ለመቀበል በመቻሉ፣ ከዘመምናና ከሃፍረት እንደተገላገለ አመነ። በሌላ በኩል ይህ አስተያየቱ ጠንክሯ አልነበረም። ስለዚህም ወደ በሩ በመሄድ በክበራው መራቱን እየደቀደቀ ሣጥኑን ያመነጭከዋል። ይህ ታዲያ ከመጦፎው ሁኔታ በኋላ በቶሎ ሊለቅቀው ያልቻለው ስሜት ጣጣ ነው። ሆኖም እርሱን በተመለከተ ከዚህ በኋላ ሴት ልጅ የምትባል የለችውም። ማዳም ዲ ማይሌም፣የባሏን የወኔ ቆራጥነት አጥታበታለች ይሁን እንጂ በርሱ ብሶ ይወቅሳታል። እስከዚህ ሰዓት ግን ሙሴ ዲ ማይሌ፣ አሊሰ የተናዘዘችውን አለቃቂ ወንጀል አልነገራትም። አናትየውም ልጇ ወደ መንፈሣዊው ሕይወት በመጠራቷ ብቻ እርር ኩምትር በማለት ላይ ነች። የልጇን ክብር ማጣት በማወቅ ብታስቅስስ ምን ሊመስል ይችል ይሆን? አሊስ፣ ምስኪኗን ሴትዮ፣ በየዕለቱ ቀትር ካለፈ በኋላ ትቀበላትና አንድ ጊዜ አሊስ ተቀምጣ ታነብብበት የነበረውንና በሀምራዊ ሃር የተሸፈነውን ባለመደገፊያ ወንበር እስኪርስ ድረስ አልቅሣ፣ በልቧ ያለውን ሁሉ እንድትተነፍስው ታደርጋት ነበር። በተረፈ በቀረው ጊዜዋ በሯን የምትከፍተው ለፍራንቾይዝ ብቻ ነበር። ሙሴ ዲ ማይሌ፣ ምስጢረኛ

ዋና የልብስ አጣቢዋ በሆነችው ሴት ንፅህና ፈፅሞ እምነት ስለሌለው፣ እስክፊረንሣይ ድረስ ሴት ልጁን ተከትላ አደባ እንዳትሄድ ከለከለ። ሆኖም ግን ልጁ እስክምትሄድበት ጊዜ ድረስ እንድታገለግላት ፈቀደ።

ሁለቱ ሴቶች ለአሊስ የገዳም ሕይወት የሚሆናትን ያልተለመደ ዕቃ አዘገጃጁ። አሊስ አገር ለቅቃ፣ ስትሄድ፣ረኽርም የጥቁር ቬዥ ቀለም ያለው፣ምኞት የማይሰጥና ለሴቶች ገዳም ተስማሚ ሆኖ ምንም ዓይነት ጥርጣሬን የማያጭር ቀሚስ እንደምትለብስ ተሰማሙ። ከዚህ ከላይ ከሚታየው ልብሷ ሥር ግን ወፍራም የጥጥ ሱሪ፣ ሰፋ ያለ ሸሚዝ ትለብስና ለሽንጥቸዋ መያዣ የሚሆን የቆዳ ቀበቶ ትታጠቃለች። በወገቧ ላይ ደብዘዝ ባለውና ለዕድሜ ሙሉ ፀሎት ተስማሚ በሆነው ልብሷ ስር፣በአረቦች ለፈር ውስጥ ፍራንቾይዝ የሠራችላትን ጥንድና በቀላሉ እጥፍጥፍ የሚል የቆዳ ቦት ጫማ ሸሽጋ ትይዛለች። የልብስ አጣቢዋ እግር፣ በትክክል ከወጣቷ ሴት እግር ጋር እኩል ስለሆነ ጫማውን የሠራችው በራሷ እግር መጠን ነበር። ከነዚህ ቀጥሎ ጥንድ መክርኮሪያዎችና የዝሆን ጥርስ እጀታ ያለው ፖቤ አለ። በመጨረሻም፣ዣረሚ ለዚሁ ሲል አሹሎና ስል አድርጐ ያዘጋጀውን ቀላል ሻምላ፣ ፍራንቾይዝ በቀሚሷ ስር ደበቃ አመጣች። ከዚህ በማስከተል መያዝ የነበረባቸው ሽጉጦች፣ ባሩድና የጥይት አርሣሶች ሲሆኑ እነዚህም በነጭ የናይለን ቅርጫት ውስጥ ተደርገው ደረሱ።

ሁለቱ ሴቶች ከፍተኛ ጥንቃቄ ባለው ሁኔታ መስራት ስለነበረባቸው ዝግጅቱ አስር ቀን ያህል ጊዜ ወሰደ። በመጨረሻ ግን አሊስ ዝግጁ ሆነች። የወጥ ቤቱ ሠራተኛ፣ በትሬይ ላይ አድርጐ ያመጣላትን ምግብ እየተመገበች በመስኩቱ ወደ ውጭ በትካዜ ተመለከተች። ጉዞ የምትጀምረው መቼ ይሆን? ጀልባዋስ ምን እየሠራች ነው? ዓመቱ ቀስ እያለ መንጐድ ጀምሯል። የካቲት እየተገባደደና በማብፅ ውስጥ ሙቀት ቀስ በቀስ እየተመለሰ ነው። አፅዋት እየፋፉ ነው። ከዕለታት አንድ ቀን በአትክልቱ ሥፍራ ውስጥ በመድረቅ ላይ የነበረ ቁጥቋጦ፣እንደገና ትናንሽ ቀያይ ቅጠሎች አቆጥቁጦ ተመልክተዋል። ከዚያም ብዙ ሣይቆይ፣ ሙሉ በሙሉ አብበና አበባዎቹም ተንሻርርገው፣ ሳር ቅጠሉን በተሰያዩ ቀለማት አሸብርቋቸዋል። ይህን ትዕይንት፣ አሊስ፣ በቅርቡ ከጀን ባፕቲስት ጋር እንደምትሆን ምልክት እንደሆናት አድርጋ አነበበችው። የፊሊጋትን ያህል ራሷን በጥልቀት ብትመለከተውም፣ከዚህ በፀለጠ በቅሬታዋና በመከራዋ የተነሣ የምታፈሰሰው እምባ ስለሌላት የሚታያት ሁሉ ትዕግስት ማጣት ነው።

በዚህን ጊዜ ካደሮ ውስጥ ራሣቸውን በሥራ የጠመዱ ብዙ መንገደኞች ቢኖሩም፣ ከከተማዋ ለመልቀቅ የመጀመሪያው ግን ሙራድ ነበር። አስቀድሞ ግን አክብሮቱን ለመግለፅ ወደ ሙሴ ዲ ማይሌ ሄደ። ሙሴ ዲ ማይሌም በደስታ ተቀበለው። የቆንሲሉ ሰላዮች በከተማው ውስጥ ስድስት እንግዳ መንገደኞች መግባታቸውን ሪፖርት አድርገውለት ስለነበረ፣ እነዚህ ፍሌሃውት የነገሩት ጀስዊቶች ናቸው፣ ሲል መርምሮ ውሣኔ ላይ ደረሰ። እነዚህን ሰዎች በተመለከተ ሚኒስትሩ የሰጠው መመሪያ፣ በጉዳዩ ላይ ዝምታ እንዲጠበቅ ስለነበረ፣ ሙሴ ዲ ማይሌም በጣም በጥንቃቄ ይከታተላቸዋል። በማንኛውም መልኩ የርሱ ኤምባሲ ከሃይማኖታዊው ዘመቻ ተለይቶ እንዲቆይ ይፈልጋል። ሙራድ፣ ጉዞው በድል ተጣጥቶለት በጥላቻ አላየው ከሆነ፣ የፈረንሣይን ንጉሥ ሰላምታ ለአቢሲኒያው ንጉሠ ነገስት በቃል እንዲያስተላልፍለት ተመኘ።

«ወደ ኢትዮጵያ ስትመለስ በየትኛው መንገድ ትሄዳለህ?» ሲል ቆንሲሉ ሙራድን ጠየቀው

«ክቡር ሆይ አስቀድመን ወደ ጂዳ እንሄዳለን። ከዚያም ወደ ምፅዋ እናመራለን። ከዚያ ተነስተን የጐንደርን መንገድ እንይዛለን»

«ይህ ማለት በባህር ላይ ለመጓዝ ወስነሃል ማለት ነው»

ይህ ጥሩ ዜና ነው። ምክንያቱም ቢያንስ በዱ ሮውሌ መንገድ ላይ አይሆኑም። ከዚህም በላይ ትንሽ ዕድል ኖሯቸው ከተሳኩላቸው ከርሱ በኋላ ይደርሣሉ።

ሜትር ዣረሚ ሙራድን ከልብ በመነጨ ሰላምታ ተሰናበተው። ይህ ማለት ቢያንስ በአስቸጋሪና በመጥፎ ሁኔታ ውስጥ ጥሎት ስላልሄደ የሚሰጋው ነገር የለውም። በመጨረሻ ላይ የእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ እየደረሰ ነው። ለአፍታ ያህል የጥርጣሬ ስሜት በአዕምሮው ብልጭ ቢልበትም፣ ፕሮቴስታንቱ፣ ሙራድን የሚያጅቡትን የሣይንስ ሰዎች አያውቃቸውም። የዚህን ምስጢር በግልፅ እንዲነገረው ሜትር ዣረሚ ምንም ጥረት አላደረገም። በአርመናዊው ሁኔታ እፎይታን ከማግኘቱም በላይ፣ አሊስ በሰጠችውና የባሰ ውስብስብነት የሌለውን ተልዕኮ ለማሣካት በሥራ በጣም ተይዟል። ሙራድ፣ በገንዘብና በሌላም ነገር ድጋፍ ከሚያደርጉለት ሰዎች ጋር በፈረስ ላይ ሆነው በአንድ ውብ ፀሐያማ ማለዳ ወደ ስዊዝ ተነሱ። ሦስቱ አቢሲኒያውያን አሁንም እንደና በሰረገላ ውስጥ ሆነው ተከተሉት።

ከሁለት ቀናት በኋላ የአሊስን ዕቅድ የሚያበላሽ ድንገተኛ ነገር አጋጠመ። ከቬርማይሰስ የመጣ መልዕክተኛ ቆንስላው ግቢ ደርሶ፣ አንዲት መርከብ ጥቂት ቀደም ብላ አሌክሣንደሪያ ላይ ማረፍዋን በመግለፁ የአሊስ መጓዝ የማይቀር ሆነ። በመጨረሻው ሰዓት ላይ ጥርጣሬ ያደረባት አሊስ፣ ይህ በቅርቡ የመጣው ፖስታ የጀን ባፕቲስትን ጉዳይ የሚናገር ነገር እንዳለበት ስማወቅ ፈለገች። እንዲህ ተለያይተው ሣሉ ለተመሣሣይ ግብ እየሠሩ፣ ነገር ግን እንዳቸው የሌላውን ዕቅድ ባለመገንዘብ ለነገሮች መፍትሔ በማግኘት ፈንታ ውስብስብ እንዳያደርጓቸው ሰጋች።

እንደተለመደው ሙሴ ማቼ ደብዳቤውን ለቆንሲሉ አመጣለት። እርሱም ደብዳቤውን ለማንበብ ቢሮውን በላዩ ላይ ዘጋ። ለምሣ በመጣበት ጊዜ ፀሐፊው በገበታ ላይ አብሮት እንዲሆን ጠየቀው። አሊስና ፍራንቾይዝም ቀልጠፍ ብሰው ቆንሲሉ ከምሣ በኋላ ወደ ፎት ዘመውጣት አጭር ሽለላታ በሚያደርግበት ጊዜ፣ ዕድሉን በመጠቀም ታላቂቱ ሴት ወደ ቢሮው በፍጥነት ገብታ ደብዳቤዎችን ታያቸዋለች። ይህን ዕቅድ በድፍረት በመከወን የመጀመያውን ደብዳቤ ማንበብ ጀመረች። ምስኪኗ ሴት የሚኒስትሩን የአጅ ዕሁፍ ለማንበብ ይቸግራታል። አልፎ አልፎም እየቸገራት ማንበባዋን ቆም ታደርገዋለች። የአያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር መልዕክት በመጀመሪያው ንባቢ ላይ አትረዳውም። በዚህ የተነሣ ጊዜ እያለፈ ሲሄድ፣ ስለጀን ባፕቲስት ግን አንዳችም ነገር አላገኘችም።

ዘአዳራሹ መተላለፊያ በኩል አንግዳ መምጣቱን የሚያስታውቅ የሚመስል ድምፅ በድንገት ሰማች። በፊት ለፊቱ የመግቢያ በር በኩል ምንም ዓይነት የሠረገላ ድምፅ ስላልተሰማ አንግዳው በእግሩ ተጉዞ የመጣ ማይሆን አይቀርም። ፍራንቾይዝ ስታነብበው የነበረውን ወረቀት ጥላ ወደ ትንሿ የመዝፈቻ ክፍል ሮጠች። በሩን ከፍታ ስትገባም፣ ማዳም ዴ ማይሰ ጀርባዋን ሰርስዋ ሰዮታት ብቻዋን ተቀምጣ ስታሰቅስ አየቻት። ፍራንቾይዝ በሩን ስትዘጋውና የሙሴ ማቼን ድምፅ ስትሰማ አንድ ሆነ። ከመደንገጥዋ የተነሣ ከአንድ መጋረጃ ጀርባ ውሽቅ ብላ ተደበቀች። ፀሐፊው፣ ቂንቋውን በባዕድ አገር ሰው ቅላፄ የሚናገር አንድ ሰው አስከትሎ ገባ።

«አቡቴ፣ ቅር ባይልዎ አዚሁ ይጠብቁ። ሙሴ ዴ ማይሴ በአጭር ጊዜ ውስጥ አብሮዎት ይሆናሉ» አለ ማቼ

ሙሴ ማቼ፣ እንግዳውን በክፍሉ ውስጥ እንዲጐራደዱ በመተው ወደ ፎቁ ሲወጣ ፍራንቾይዝ ሰማች። ወዲያውኑም ቆንሲሉ መጣ። በሐሩር ምድር አረፍት በመካሣቱ በመበሣጨት እየተናገረ ደረሰ።

«አሺ ወንድም ፖስኒል፣ ምን አይነት አስቸኳይ ጉዳይ ነው ባጣዳፊ እንዲመጡ ያደረገዎ?»

«እ፣ ይቅርታ ክቡር ቆንሲሉ። በእንቅልፍ ላይ መሆንዎን አላወቅሁም። የመጣሁት ዜና ልነግርዎ ነው። ዘይቱን አገኘነው»

«ዘይቱን?»

«ምነው? አዎን ዘይቱን፣ የጉማስናውን ዘይት»

«አ! ዘይቱ» አለ ቆንሲሉ እንደመመራመር «እናስ?»

«መቼም ፖትርያርኩ በጣም ንቢጋባ ናቸው። እርስዎ የሰጠንን ሁሉ ልንሰጣቸው ተገደድን»

«ይህማ የራሣችሁ ጉዳይ ነው ወንድም ፖስኒል። የተስማማነው በተወሰነ የገንዘብ መጠን ነው፡ ከዚህ በኋላ ምንም ነገር አልጨምርበትም»

«ግን እኮ ወንድሞቻችን ነገ ስለሚሄዱ እሰምንዎታለሁ ቆንሲል ሆይ። ሌላው ቀርቶ የሚጓዝባቸው በቅሎዎች የላቸውም። በእግራቸው! ወደ አቢሲኒያ በእግራቸው ሊሄዱ ነው?»

«እባክዎን፣ ወንድም፣ ግድ አይበሉች። ቀደም ሲልም ተናግሬአለሁ። ይህ የናንተው ጉዳይ ነው»

ካፑቺኑ ለአፍታ ያህል ዝም አለ። ፍራንቾይዝ በተደበቀችበት ቦታ ሆና ትንፋሽ አጥታለች።

«በአምባሳደርዎ ቅፍለት ውስጥ ያሉትን ግመሎች ሁሉ ሳስባቸው ...»

«ያ ከዚህ ርዕስ ውጭ ነው»

«ወይኔ! እነርሱም ቢሆኑ በሲናር ውስጥ ነው አቋርጠው የሚያልፉት። ወንድሞቻችንንና ዘይቱን ይዘው ሊሄዱ ይችላሉ።»

«ይህ ከጥያቄ ውጪ ነው። ሁለቱ ጉዞዎች እንደተለያዩ መቆየት ይኖርባቸዋል። ይህ የንጉሡ ትዕዛዝ ነው።»

«የፈረንሣይ ንጉሥ ማለትዎ ይሆናል። መቼም የሲናር ንጉሥ አያደርጉትም»

«ምን ማለትዎ ነው?»

«ምንም፣ የሲናርን ንጉስ በሚገባ እናውቃቸዋለን፣ ይኸው ነው»

በነዚህ ቃላት ውስጥ ምንም የለባቸውም። ይሁን እንጂ ኪቃላቱ ጥልቅ ፍቺ ውስጥ፣ አንድ ሰው ኩል በመሰለ ውሃ ሥር ሆን ብሎ ለማስፈራራት ፊልጮ እንደሚዋኝ አባብ የመሰለ አሣ፣ በግልፅ እንደሚመለከት ሁሉ፣ አነጋገሩም በአዕምሮ ውስጥ የተጠነሰሰ ነገር እንዳለ ያሣያል። ሙሴ ዴ ማይሌም ይህን ስሜት ወዲያውኑ ተረዳው። ምንም ዓይነት አደጋ ሊያስከትል የሚችል ነገር አይመስድም። የፊለገው እንኳ ቢሆን መከሠቱ ምንም ጉዝ ስለሌላቸው ጉዟቸውን ይጀምራሉ። ሌላም ስለሆኑ ፊጥነው መጓዝ ይችላሉ። ስለዚህ ዱ ሮውሌ ሌላው ቀርቶ ሲናር እንኳ ማይደርስ በፊት ማንኛውንም ዋጋ ተከፍሎ ምንም ዓይነት የፖለቲካ የበላይነትን እንዳይዘዙት መታገድ ይኖርባቸዋል።

«አሺ፣ ታዲያ ምን ይፊልጋሉ?»

ወደፊትና ወደ ኋላ ሊወዛወዙ ክቆዩ በኋላ፣ ካፑቺኑ ተገቢነት በሌለው ዘዴ እንድ ግመል ሁለት በቅሎዎችና ጥቂት መጠን ወርቅ አገኙ። ለቆንሲሉ ዝቅ ብለው ለላምታ በማቅረብ አመስግነው ሄዱ።

«መቼም በዚህ ድርጊታችን ተሸናፊ አንሆንም። ቢያንስ አሁን ባለዕዳዬ ናቸው» አለ ቆንሲሉ ለሙሴ ማቼ፣ የእጅ መስጠቱን ተገቢነት ለማሣመን እየጣረ። ከዚህ በኋላ ሁለቱ ቢሮውን ለቅቀው ሄዱ። ቆንሲሉ ወደ መኝታ ክፍሉ ለመሄድ ፎቁን ሊውጣና ሙሴ ማቼም በመጥረጊያ ማስቀመጫ ክፍሉ ውስጥ ገብቶ በራሱ ላይ በሩን እስኪዘጋ ድረስ ጠበቀችና ፍራንችይዝ፣ ክተደበቀችበት ወጥታ ወደ አሊስ ክፍል ተመለሰች።

5

ሙራድና ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ደማቅ በዓል አድርገው ከተለያዩ ከአንድ ሣምንት በኋላ የኤምባሲው ቅፍለት ሰንዞው ተነሣ። በፈረንሣውያን ማህበረሰብ ውስጥ የተከበሩ ሰዎች፣ የዱ ሮውሌ ሠራዊት ሲንቀሣቀስ ለማየት በዝርዝር ተጠርተዋል። ብዙዎቹ ሸኚዎች ለዚህ ጉዞ የሚሰጡት ምንም ዓይነት ስም አልነበራቸውም። ቆንሲሉ፣ ባለፊው ዘመቻ ጊዜ የባከነውን ገንዘብ በከፊል ለማካካስና ክብሩን ለመጠቀም ችሏል። ፓሻው፣ ለዚህ ተጓዥ ቡድን አስፈላጊ የሚሆኑትን መብቶች ፈቅዶ ለመስጠት ችግር የፈጠረ ቢሆንም፣ ቆንሲሉ ግን ጉዞውን በጥንቃቄና በስልት ለመያዝ ሃሣብ አላደረበትም። ይልቁንም ለዚህ እጅግ ክባድና ሲሆን ለማይችል ዕቅድ፣ ፈረንሣይ የሰጠችውን ክፍተኛ ግምት ለማሣየት ፈለገ። ምንም እንኳ፣ ቱርኮች እዚህ ጌቶች ነን በማለት ለማስመሰል ቢሞክሩም፣ መቼም ሁልጊዜም ለነሱ ሲሰግድ የሚኖር የለም ይላል።

ፈረሰኛው ዱ ሮውሌና በኩራት የሚወጣጠሩት አጭበርባሪዎቹ የቡድን አባላቱ፣ በግመሎቻቸው ላይ ተቀምጠው ሲታዩ ድንቅ ናቸው። ቤላክ፣ ብቃት ያለው የቅፍለት መሪ ነው። ግመሎቹንም በአንድ ላይ አስደሳች እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ አሰልጥኗቸዋል። እንዲያውም በአግሮቻቸው ላይ የብር ቃጭል አንጠልጥሎላቸዋል።

ይህ አነስተኛ የቅፍለት ጓዝ ቀደም ሲል ፖንሴ፣ አስዩት ውስጥ የተቀላቀለውን ትልቅ ቅፍለት መገናኘት አልቻለም። በመጨረሻም ተጓዦቹ ቁጥራቸው ብዙ ሰለሆነና በበቂም ስለታጠቁ፣ ቤላክ ደህና አድርጉ የሚያውቀውንና በአባይ ሰከተኛው ፏፏቴ ላይ ሊያደርሣቸው የሚችለውን መንገድ ለመከተል ወሰኑ።

ይህ የተንቆጠቆጠ ሰልፍ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ሊያቀና፣ ካይሮ ውስጥ የሚገኙ ፈረንሣውያን ባለሥልጣናትና ሃብታሞች ከርቀት ሊያዩት እያነሰባቸው ሲሄድ ልበ ሙሉ ሆኑ። ይህ በዚህ አንዳለ ሌላ ተጓዥ ደግሞ ከቆንስላው ለመልቀቅ ሽር ጉድ እያለ ነው።

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ሴት ልጁ በዚህ ጊዜ ለቅቃ እንድትሄድ ይፈልጋል። ምክንያቱም የመታየቷና የመሄዷ አስባልታ አይጉላም። ስለዚህም፣ አንድ አርማ እንኳ በሌለበት ጥቁር ሰረገላ ውስጥ ሆና፣ ሁለት ዘበኞች በፈረስ ላይ ተቀምጠው አጅበዋት ብቻዋን ጉዞዋን ጀመረች። ማዳም ዴ ማይሌ፣ ለአግዚአብሔር አገልጋይነት የሰጠቻትን መነኩሲት በመሳም ፣ደህና ሁኚ

«ይህ ከጥያቄ ውጪ ነው። ሁለቱ ጉዞዎች እንደተለያዩ መቆየት ይኖርባቸዋል። ይህ የንጉሡ ትዕዛዝ ነው።»

«የፊረንሣይ ንጉሥ ማለትም ይሆናል። መቼም የሲናር ንጉሥ አያደርጉትም»

«ምን ማለትም ነው?»

«ምንም! የሲናርን ንጉስ በሚገባ እናውቃቸዋለን፣ ይኸው ነው»

በነዚህ ቃላት ውስጥ ምንም የሰባቸውም። ይሁን እንጂ ከቃላቱ ጥልቅ ፍቺ ውስጥ፣ አንድ ሰው ኩል በመሰለ ውሃ ሥር ሆን ብሎ ለማስፈራራት ፈልጎ እንደሚዋኝ አባብ የመሰለ አሣ፣ በግልፅ እንደሚመለከት ሁሉ፣ አነጋገሩም በአዕምሮ ውስጥ የተጠነሰሰ ነገር እንዳለ ያሣያል። ሙሴ ዴ ማይሌም ይህን ስሜት ወዲያውኑ ተረዳው። ምንም ዓይነት አደጋ ሊያስከትል የሚችል ነገር አይወስድም። የፊለገው እንኳ ቢሆን መከሠቱ ምንም ጉዝ ስለሌለቸው ጉዟቸውን ይጀምራሉ። ሌላም ስለሆኑ ፈጥነው መንዝ ይችላሉ። ስለዚህ ዱ ሮውሌ ሌላው ቀርቶ ሲናር እንኳ ማይደርስ በፊት ማንኛውንም ዋጋ ተከፍሎ ምንም ዓይነት የፖለቲካ የበላይነትን እንዳይዙበት መታገድ ይኖርባቸዋል።

«እሺ፣ ታዲያ ምን ይፈልጋሉ?»

ወደፊትና ወደ ኋላ ሊወዛወዙ ከቆዩ በኋላ፣ ካቦቺኑ ተገዚነት በሌለው ዘዴ እንድ ግመል ሁለት በቅሎዎችና ጥቂት መጠን ወርቅ አገኙ። ለቆንሲሉ ዝቅ ብለው ሰላምታ በማቅረብ አመስግነው ሄዱ።

«መቼም በዚህ ድርጊታችን ተሸናፊ እንሆንም። ቢያንስ አሁን ባለዕዳዬ ናቸው» አለ ቆንሲሉ ለሙሴ ማቼ፣ የእጅ መስጠቱን ተገዚነት ለማሣመን እየጣረ። ከዚህ በኋላ ሁለቱ ቢሮውን ለቅቀው ሄዱ። ቆንሲሉ ወደ መኝታ ክፍሉ ለመሄድ ፎቁን ሲወጣና ሙሴ ማቼም በመጥረጊያ ማስቀመጫ ክፍሉ ውስጥ ጉበቱ በራሱ ላይ በሩን እስኪዘጋ ድረስ ጠበቀችና ፍራንቾይዝ፣ ከተደበቀችበት ወጥታ ወደ አሊስ ክፍል ተመለሰች።

5

ሙራድና ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ደማቅ በዓል አድርገው ከተለያዩ ከአንድ ሣምንት በኋላ የኤምባሲው ቅፍለት ሰንዞው ተነሣ። በፊረንሣውያን ማህበረሰብ ውስጥ የተከበሩ ሰዎች፣ የዱ ሮውሌ ሠራዊት ሲንቀሣቀስ ለማየት በዝርዝር ተጠርተዋል። ብዙዎቹ ሽኚዎች ለዚህ ጉዞ የሚሰጡት ምንም ዓይነት ስም አልነበራቸውም። ቆንሲሉ፣ ባለፈው ዘመቻ ጊዜ የባከነውን ገንዘብ በከፊል ለማካካስና ክብሩን ለመጠቀም ችሏል። ፓሻው፣ ለዚህ ተጓዥ ቡድን አስፈላጊ የሚሆኑትን መብቶች ፈቅዶ ለመሰጠት ችግር የፊጠረ ቢሆንም፣ ቆንሲሉ ግን ጉዞውን በጥንቃቄና በስልት ለመያዝ ሣጣብ አላደረበትም። ይልቁንም ለዚህ እጅግ ከባድና ሲሆን ለማይችል ዕቅድ፣ ፊረንሣይ የሰጠችውን ከፍተኛ ግምት ለማሣየት ፈለገ። ምንም እንኳ፣ ቱርኮች እዚህ ጌቶች ነን በማለት ለማስመሰል ቢሞክሩም፣ መቼም ሁልጊዜም ለነርሱ ሲሰግድ የሚኖር የሰም ይላል።

ፈረሰኛው ዱ ሮውሌና በኩራት የሚወጣጠሩት አጭበርባሪዎቹ የቡድን አባላቱ፣ በግመሎቻቸው ላይ ተቀምጠው ሲታዩ ድንቅ ናቸው። ቤላክ፣ ብቃት ያለው የቅፍለት መሪ ነው። ግመሎቹንም በእንድ ላይ አስደሳች እንቅሰቃሴ እንዲያደርጉ አሰልጥኗቸዋል። እንዲያውም በእግሮቻቸው ላይ የብር ቃጭል አንጠልጥሎላቸዋል።

ይህ አነስተኛ የቅፍለት ጉዝ ቀደም ሲል ፖንሴ፣ አስዩት ውስጥ የተቀላቀለውን ትልቅ ቅፍለት መገናኘት አልቻለም። በመጨረሻም ተጓጉቹ ቁጥራቸው ብዙ ሰለሆነና በበቂም ስለታጠቁ፣ ቤላክ ደህና አድርጐ የሚያውቀውንና በአባይ ሶስተኛው ፏፏቴ ላይ ሊያደርሣቸው የሚችለውን መንገድ ለመከተል ወሰኑ።

ይህ የተንቆጠቆጠ ሰልፍ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ሲያቀና፣ ካይሮ ውስጥ የሚገኙ ፊረንሣውያን ባለሥልጣናትና ሃብታሞች ከርቀት ሲያዩት እምነሰባቸው ሲሄድ ልበ ሙሉ ሆኑ። ይህ በዚህ እንዳለ ሌላ ተጓዥ ደግሞ ከቆንስላው ለመልቀቅ ሽር ጉድ እያለ ነው።

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ሴት ልጁ በዚህ ጊዜ ለቅቃ እንድትሄድ ይፈልጋል። ምክንያቱም የመታየቷና የመሄዷ አሰባልታ አይገመም። ስለዚህም፣ አንድ አርማ እንኳ በሌለበት ጥቁር ሰረገላ ውስጥ ሆና፣ ሁለት ዘበኞች በፈረስ ላይ ተቀምጠው እጅበዋት ብቻዋን ጉዞዋን ጀመረች። ማዳም ዴ ማይሌ፣ ለእግዚአብሔር አገልጋይነት የሰጠቻትን መከሩሲት በመሳም ፣ደህና ሁኚ

ካለቻት በኋላ፣ በመግቢያው መተላለፊያ ላይ ሀሊናዋን ስታ ወደቀች፡ ፍራንቾይዝ፣ ወደ ክፍሏ ተሸክማት መውሰድ ስለነበረባት ጎደኛዋ ስትሄድ በወጉ ልታያት እንኳ ዕድል አልነበራትም።

የልብስ አጣቢዋን በዜቱ ውስጥ መቆየት ታግሶ ችሎ የነበረው ቆንሲል፣ አሊስ ቆንስላውን በሉቀቻበት ዕለት ከፊቱ እንዳትደርስ ስማድረግ ወደ ዕዳት ሥራ አዛወራት። ያንኑ ዕለት ማታ፣ ፍሪንቾይዝ ጓሏን ጠቅልላ ተሸክማ ወደ ቤቷ በእግርዋ ተመለሰች።

በመስኮታ አሻግራ ስትመለከት ሜትር ዝረሚ በመድረኩ ላይ ስለነበረ ሄዳ አገኘችው። የአሊስን መልቀቅም ነገረች። በሚቀጥሉት ቀናት ስለሚያከናውኗቸው ጉዳዮች ተመካከሩ። ከዚህ በኋላ በመካከላቸው ፀጥታና ፍርሃት ነገሠ።

ከምሹቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ነበር። ከመድረኩ በላይ የሚታየው የሰማይ ሜዳ፣ ደማቅ ሰማያዊ እየሆነ ነው። የብርቱካን ዛፎች አሁንም ገና እረንጓዴነታቸው ሲታወቅ ጥቂት ከዋክብትም ያንዘባርቃሉ። ይህ ሰዓት፣ አብረትራቂው ምሽትና የቀኑ የብርሃን ቀለማት ሲለዋወጡ፣ ሰላምታ የሚሰጣጠቡት ጊዜ ይመስላል። በቤቱ ውስጥ ያሉት ዕፅዋቶች ደን፣ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ጥቅጥቅ እያለ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሜትር ዝረሚ እንክብካቤ አላደረገላቸውም። ከጏላቸው ባሉ ብዙ ዕፅዋት ግፊት ላቢያ ትላልቅ ቅጠሎች በመስኮቱ መስተዋት ላይ ተደፍጥጠዋል።

«እፅዋቶችሀ ካንተ እየራቁ ነው» አለች ፍራንቾይዝ

«ከትናንት ጀምሮ ምን ለውጥ አለ . . . »

ለምንጊዜውም ላይመለሱ፣ከሁለት ቀናት በኋላ ከካይሮ ለቅተው የመጌዳቸው ሃማብ ሁለቱንም በተመሣሣይ የትዝታ ማዕበል ውስጥ እንዲዋልሉ አደረጋቸው። እውነት ነው ሊሄዱ ነው። የሚሄዱትም አብረው ነው። አብረው በአንድ ጉዳና ይጓዛሉ። ሊያጋጥማቸው የሚችለውንም አደጋ አብረው ይጋፈጣሉ። ባለፉት ሁለት ዓመቶች አንዳችም ነገር ማይፈፅሙ ቢቆዩም፣ አሁንም ድረስ ፍፁም እርስ በርሣቸው አልተተራረቡም። ይህ ሃማብ ዝረሚን ተስፋ የለሽ ያደረገውና ጉዳዩም እንዳሳሰበው ፍራንቾይዝ ተሰማት።

«እባክህ ገሸሽ አታድርገኝ። ሁለታችን አብረን መሆናችን የማይቀር ነው። አሁን ባለንበት ሁኔታ ግን መደሰት ይገባናል። እኔ ሌላ የምጠይቅሽ ነገር የለኝም።»

እርስ በእርሣቸው ፊት ለፊት ተያዩ፣ ተቀራረቡ።

«ጆን ባፕቲስት የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ። አሊስም ትታን ሄደች። አ! ዝረሚ፣ ሁለታችንንም ያጣናቸው ነገሮች ናቸው ይቀራረቡን» አለች።

በክፊል ጢም የሸፈነውን ጭንቅላቱን ቀና አደረገና እነዚያን ሩሀሩህ አይኖቹን አሣረፈባት። እርሷም ፊትዋን በሰፊው ደረቱ ላይ ስታደርግ በክንዶቹ ውስጥ አቀፋት። ጊዜው ሙሱ በሙሉ ሲመሽ፣ በመስኮቱ ውስጥ ክፍ እያሉ የሚወጡ እየመሰሳቸው ወደ ፍራንቾይዝ ቤት ሄዱ። በሁለቱ ማዕዘናት ላይ በሸክላ ድጋፍ የተሠራ ሰፊ አልጋ አሳት። ይህ አልጋ በደስታ ማዕበል ውስጥ፣ በደስታ፣ በፍቅርና በነፃነት እንደሚጋጭ ታሳቅ የመርከብ ተንሣፋፊ አካል ለሊቱን ሙሉ በዙሪያቸው ሲንሳጠጥ አደረ።

በማግስቱ ጠዋት፣ ሜትር ዝረሚ ወደ ቤቱ ተመልሰ፣ ሻንጣወቹን ማዘጋጀት ዕቅዱ ነበርና ሥራውን ጀመረ። ይሁን እንጂ እንዴ ወደ ፎቅ ቀጥሱም ወደ ምድር ቤት በመመላለስ ሰዚህን ያህል ረዥም ጊዜ በጓደኝነት ያቆዩትን ዕፅዋት አየተቀመጠና እንደገናም እየተነሳ፣ ባለማቋረጥ በዙሪያቸው እየተንዘ ይመለከታቸው ጀመር። ዝረሚ የፀሎት እማራጭ አልነበረውም። ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ለእግዚአብሔር ምን እንደሚነግረውም አላወቀም።

ፍራንቾይዝ አስተዋይ ስለሆነች መጥታ ልታስቸግረው አልፈለገችም። ነገ ማለዳ ግን አብረው ጉዟቸውን እንደሚጀምሩና ልጂን ሲያሰደስተው ከጉኗ እንደሚናሩት እርግጠኛ ነች።

ከሰዓት በኋላ በአሥራ አንድ ሰዓት ላይ በምድር ቤቱ ጥላ የተንሣ መጨላለም ጀመረ። ያንቀላፋ፣ በመብራት እንደሚነቃ ሁሉ፣ በህልም ውስጥ ያለ ሰውም ብዙውን ጊዜ ከማላዊ ዓለሙ በጨለማ ጥቃት ብቻ ይንቀሳቀሣል። ሜትር ዝረሚ ፋኖሱን ሲያበራ ለቅቆ ሰለመሄዱ ምንም ዝግጅት አለማድረጉን በድንጋጤ ተገነዘበ። ከዚያም ከአቢሲኒያ ከተመለሰ በኋላ በቁምሣጥኑ ውስጥ ክርችት ብለው ደርቀው የተቀመጡትን ሁለት የከርቾ ሻንጣወች አገኘና ለሚጠብቀው ጉዞ የሚያስፈልጉትን ሁሉ መሰብሰብ ጀመረ።

በአንድ ሰዓት ላይ በሩ ተንኳኳ። ፍራንቾይዝ ትሆናለች ብሎ ስላሰበ ዝረሚ በሰጨት አለ። ማንኳኳቱ ተደጋመ። ይህን ያህል ከሚጣደፈው በር አንኳኪ ማን ምንም ድምፅ አልተሰማም። እርምጃውን ዝግ አድርጎ ወደ በሩ እየተደናበረ ተራመደ፣ የዛነውን አጮልቆ መመልከቻ ቀዳዳ ከፈተው።

«ምንድነው?» አለ ጮርነን ባለ ድምፅ፣ በቀዳዳው እያጮለቀ

በመተላለፊያው በኩል ባለው የብርሃን ፍካት ጀርባ የአንድ ወንድ ሰው ቅርፅ ታየው።

«ምን ትፈልጋለህ?» አለ ሜትር ዠረሚ፣ ምናልባት ሃኪም ፍለጋ የመጣ ሰው ይሆናል በሚል ሃሣብ

«ክፊት» አለ ሰውዬው።

«አ! ቀስ በል ወዳጄ፣ መጀመሪያ ነገር እዚህ ማንም የለም።»

እንግዳው ሰው አፉ የማጮለቱያውን ቀዳዳ እስኪነካው ድረስ ተጠጋ።

«እንዲህ ደደብ አትሁን፣ በሩን ክፈተው»

ሜትር ዠረሚ አመዱ ቡን ሲል ተሰማው

«አንተ ነህ እንዴ?»

«ፍጠን፣ ሁሉም ሊያየኝ በሚችልበት በዚህ ቦታ ላይ በግላጭ አታቆየኝ»

በሰከንድ ጊዜ ውስጥ ፕሮቴስታንቱ መቀርቀሪያውን አወለቀውና በሩ ተከፈተ። ጆን ባፕቲስት ወደ ውስጥ ዘለቀ። ሁለቱም ተቃቅፈው ድምፅ ሳያወጡ እንባቸውን አፈሰሱ

በመጨረሻ ተነስቶ በመቆም ወደ ኋላ ራመድ ብሎ ፋኖሱን ከፍ አደረገና «እስቲ ልይህ» አለው ሜትር ዠረሚ።

ጓደኛው የሚለይ አይደለም። በርግጥ አንፀባራቂዎቹ ጥቋቁር ዓይኖቹ በቦታቸው ናቸው። በርግጥ እርሱ ነው ብሎ ለመናገር የሚያስችለው፣ ቢትክክል የሚታወቀው የፊቱ ቅርፅ እንዳለ ነው። «አዎ፣ ምናልባትም እሱ ነው» ግን እኮ ሁለመናው ተሰዋውጧል። ፀጉሩ በአጭሩ ተከርክሞ፣ አልፎ አልፎ ግራጫ ሆኗል። ግራና ቀኝ ሾል ብሎ የሚታየው ሪዙ፣ የአፍንጫውን ቅርፅ ለውጦታል። በሰዊስ 13ኛ ዘይቤ አገፖ ላይ ያለው ቀጭን ሂም፣ ለታችኛው ከንፈሩ የኩራትና የቁጣ መልክ ፈጥሮለታል። ከዚህም በተጨማሪ ራሱን ሊከበር በሚችል የጨዋ ሰው ግርማ ሞገስ ጠብቋል። በሱል የተጠሰፈ እጅጌው፣ ከውብ ጨርቅ የተሠራ ግራጫ ቡኒ ልብስና የሐር ሰደሪያ ለብሷል። ነጫጭ ላባዎች ያሉበት ባለሦስት ማዕዘን ባርኔጣ በእጁ አንጠልጥሏል።

«ለመሆኑ ልተለየኝ ትችል ነበር?» ሲል ጆን ባፕቲስት እየማቀ ጠየቀው

«ይህ አማሳክህ ስህተት የለበትም» አለው ፕሮቴስታንቱ፣ጓደኛውን እንደገና ጭምቅ አድርጐ እያቀፈው።

«እንግዲህ ጊዜ አናጥፋ። ፈረሴ በመተላለፊያው ፊት ለፊት ባለ አንድ ቀለበት ላይ ታስሯል። ወጣ ብለህ በጓሮ በኩል ወደ ቤኖቹ ጋጣ ውሰደው» አለው ጆን ባፕቲስት

ከነርሱ ቤት በስተጀርባ፣ በቤኖቹ የንግድ ተቋም የሚመራ የማሰልጠኛ ሜዳ አለ። አንድ ዘመን ላይ ይህ ቦታ በጣም የበለፀገ እንደነበረው ሳይሆን፣ ዛሬ ብዙ ሰፋፊ ባዶ ሥፍራዎች ስላሉት ጉረቤቶች ሁሉ በነፃነት ሊጠቀሙበት የሚችሉት ሆኗል። ሜትር ዠረሚ ፈረሱን ወደ ጋጣው ለማድረስ ወጣ። ሲመለስ የጆን ባፕቲስትን ከባድ ኮርቻ በአንድ ክንዱ ላይ ተሸክሞ፣ አራት ማዕዘን የሆነውን ሻንጣውን በሌላው ትከሻው ላይ አድርጐ መጣ።

ጆን ባፕቲስት በላይኛው ፎቅ ከእዕዋቱ ጋር ነበር። እዚያም፣ ልክ ክፍል ሙሉ እንዳሉ ወላጅ አልባ ህፃናት፣ አያንዳንዱን ተክል በቅጠሎቻቸው ላይ እጆቹን እያሣረፈ ሰላምታ ይሰጣቸዋል።

«መረን ሆነው እያደጉ ነው» አሰው ለሜትር ዠረሚ። በድምፁ ውስጥ ምንም ዓይነት ዘለፋ አልነበረበትም። ይልቁንም ተማሪዎቹ አንታዘዝ ያሉት የትምህረት ቤት መምህር የፍቅር ምፀት ይመስላል።

«አህ! የተረገመ!» አለ ሜትር ዠረሚ ወዲያና ወዲህ ከተራመዳት እንቅሰቃሴው ረጋ ካለ በኋላ። «ፖሪስ ውስጥ ለፍርድ ቀርበሃል ብለው ነበር ሲነግሩን የነበረው። እንዲያውም በተግባርም አስረውሃል ብለን ስናስብ ነበርን»

«ታስሬ ነበር። ይሁንና ያ ሁሉ አይመለከተኝም። ምክንያቱም፣ ያ ያጋጠመው ሌላ ሰውን ነው። አሁን ከፊትህ ያለው ሰው ከልዑል ዴ ኮንቲ ቤተሰብ የሆነው ፈረሰኛው ሁፈስ ዴ ቫ ው ዴ ሶሬስ እንጂ ሌላ ሰው አይደለም»

ዝቅ ብሎ የአክብሮት ሰላምታ አቅርቦ ፈገግ አለ።

«አሊስ እንዴት ነች?» ሲል ሰውጥ ባለ የድምፅ ቅላፄ ጠየቀው። ሜትር ዠረሚም ሁኔታውን ሁሉ በአንድ ጊዜ አስታወሰ።

«እስክ አሁን ፖሪስ ነህ በሚል ታስብ ነበረና ትናንት ጠዋት ከዚህ ለቀቀች።»

«ለቀቀች? እንዴት? ማነው ይህን .. . . » አለ ጆን ባፕቲስት

«በሁለት ጦራዴ ታጣቂዎች ታጅባ ነው የወጣችው። የጉዞዋ አቅጣጫ ወደ አሌክሣንደሪያ ሲሆን እዚያም ወደ ፈረንሣይ በሚያደርሣት መርከብ ላይ ትሣፈራለች። እዚያ ከደረሰች በኋላ ደግሞ ወደ ገዳም ትወሰዳለች»

ጆን ባፕቲስት በመገረምና በቁጣ ጮኸ።

ሜትር ዠረሚ በበኩሉ ጓደኛው ምንም ዓይነት ወሬ አስቀድሞ ባለመሣኩ፣ በመውቀስ ቆጣ ብሎ መለስለስ። ሁለቱም እርስ በእርሣቸው መጠያየቅ ጀመሩ። በዚህ መሣል እንዳቸውም ጊዜ ወስደው መልስ ለመስጠት ፍላጐት አልነበራቸውም።

ድምፁን የሰማችው ፍራንቾይዝ በመስኮቷ በኩል ዘላ ብቅ አለች። ሁለቱ ሰዎች በደረጃው ላይ ዱካዋን ስለሰሙ መናገራቸውን አቋረጡ። ጆን ባፕቲስትም ሰመሸሽ በመዘጋጀት ወደ ፎቁ መውጫ ደረጃ ዳኸ።

«ቆይ፣ ፍራንቾይዝ ነች» አለ ሜትር ዠረሚ በሃፍረት ዐይኖቹን እያሻሻ።

«ወደ ሶውቢይራን ሄጀ ነበር። ማሪኔ ከአሰራ አምስት አመታት በፊት አርፋለች» ሲል ጆን ባፕቲስት ራሱን አረጋግቶ ፍራንቾይዝን ከማቀፉ በፊት ሹክ አለ።

በመመለሱ የተሰማትን አግራሞትና ደስታ በነግነት ገለፀች። ይሁንና ተፈጥሯዊ ባህርይዋ ወዲያውኑ አጭሮ፣ ጆን ባፕቲስት ምግብ በልቶ እንደሆነ ጠየቀችው። በርግጥ ጠኔ ጥሎታል። በጠረጴዛው አጠገብ ለሁለቱ የሚሆን ቦታ አዘጋጀ። ሜትር ዠረሚ ክሎሬው ውስጥ ሲያመሳቅል ቆይቶ፣ አንድ ጠርሙስ ይዞ እስኪመለስ ፍራንቾይዝ ወደ ክፍሏ ወጥታ የተቀቀለ ጐመን፣ የስጋ ወጥና ትልቅ የዳቦ ቁራጭ አመጣች። ጆን ባፕቲስት ምግቡን እየተስገበገበ ሲበላ ሜትር ዠረሚ አስቀድሞ ተናገረ።

ፍራንቾይዝ፣ የወጣቷን እመቤትዋን ምስጢር አሣልፋ ስላልነገረችው፣ስለ አሊስ መሄድ በይፋ የሚያውቀውን ታሪክ ነገረው። ከዚህም በመቀጠልም እርስዋን ለመከተል ስለታቀደው ሃሣብና በዚህም መሠረት በሚቀጥለው ዕለት ጉዞ ሲቀድ ሊንቀሳቀሱ እንደነበረ አስረዳው። ጆን ባፕቲስት ለሣጡም፣ ለዕቅዱም አጨብጭቦ፣ ይሣካ ዘንድ ዕዋቸውን አነሱ። ይህ ሁኔታ ይበልጥ ሃይል ሰጣቸው። ከዚህ በኋላ የወጣ ውሪድ ገድሉን መግለፅ፣ የጆን ባፕቲስት ተራ ነበረ። በተቆራረጠ ሁኔታ ስለጉዞው፣ ከንጉሡ ጋር ስላጋጠመው ስብሰባ፣ ከዚያም ስለተከተሉት ችግሮች፣ ስለማምለጡና ፕሮቴስታንቶቹን ስለማግኘቱ ተራ በተራ ዘረዘረ። በዚህም ለሁለተኛ ጊዜ ዋንጫቸውን ከፍ አደረጉ።

«የሆነ ሆኖ መራድስ?» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቀው

«ለጉዞው የሚያስፈልገውን ወጭ የሚከፍሉት ጥቂት በጐ አድራጊዎችን ስላገኘና፣ ሊሆን የሚገባውም ድንቅ ውሳኔ ነበርና በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ።

«ስድስት ሰዎች ናቸው አይደል?»

«እምን፣ ግን እንዴት አወቅህ?»

«በፈረንሣይ ቤተመንግስት የተላኩ ጀስዊቶች ናቸው» አለ ጆን ባፕቲስት ዳቦውን እየገመጠ። «እኔ ከንጉሡ ጋር የነበረኝ ግንኙነት ከተበላሸ በኋላ፣ ንጉሡ ለነፍስ አባታቸው ይህንን ቃል ገብላቸው። ይህን አዲሱን ተልዕኮ ለነፍስ አባታቸው እንደ ስጦታ፣ ላለፈውም እንደውለታ አድርገው ነው ትዕዛዝ የሰጡት»

«አንዲህ ከሆነ የንጉሡ ነገስቱን መልዕክት ልታቀርብ አልቻልክም ማለት ነው?» አለ ሜትር ዠረሚ።

«ይህን በተመለከተ ጊዜ አልነበረኝም። ከዚህም በላይ መልዕክቱን ለመሰማትም ፈቃደኛ የሚሆን፣ ነበረ ብዬ አላምንም»

«ኦ! አየህ ጆን ባፕቲስት፣ እነዚህ ጀስዊቶች እንደሚያሽንፉ ርግጠኛ ነበርክ፣ አንተ ግን ከነርሱ ጋር ህብረት የምትፈጥር መስሎህ አስበህ ነበር» አሰው ፕሮቴስታንቱ ፊቱን ከስክሶ።

«ወደ ቬርሣይለስ መሄድ ከተገባኝ ሌላ ምርጫ አልነበረኝም»

«ለመሆኑ ወደዚያ ለመሄድ ያን ያህል የቆረጥከው ለምንድን ነበር?» ሲል፣ዐይኖቹ ክአምላኩ ጋር ሲከራከር እንደሚሆኑ አስፈሪ ሆነው ጠየቀው። «የራስህን ጉዳይ በግንባር ቀርበህ ልታስረዳና የአሊስን እጅ ለማግኘት መከራ ከማድረግ ሌላ ምክንያት አልነበረህም»

«አንተ ጉዳዩን በጣም አጠንክረህ እየገለፅከው ነው። ከዚያ ባሻገር ንጉሡን ለማግባባትና ላገለግላቸውም እችላለሁ የሚል እምነት ነበረኝ» ሲል ጆን ባፕቲስት በደስታ ተናገረ።

«ቀስ፣ ቀዝቀዝ በሉ» አለች ፍራንቾይዝ፣ የሁለቱ ሰዎች ድምፅ አሣስቧት። «የሆነ ለው ሊሰማችሁ ይችላል። አሁን ይህን ለመነጋገር ጊዜውም አይደለም»

«ያም ሆነ ይህ» ሲል ሜትር ዠረሚ ለስለስ ባለ ሁኔታ ቀጠለ። «ውጤቱ በግልፅ የሚታይ ነው። ያንተን ተልዕኮ ተከትሎ በአቪሲኒያ ላይ ድንገተኛ ጥቃት የሚጥሉ ሁለት ቅኝሰቶች እየገሰገሱ ናቸው። የሚከፍላቸውም የፈረንሣይ ንጉሥ ነው። ምንም ዓይነት ጀስዊቶች እንደማይኖሩ ምለን ተገዝተን ማለን፣ አሁን ደግሞ የመራድን ጭራ ተከትለው

የሚሄዱ ስደስት መጥተዋል። ንጉሠ ነገስቱ የፈለጉት አንተን እንደ አምባሣደራቸው ነበር። ነገር ግን ባንተ ፈንታ ዱ ሮውሌን መርጠውታል። በሚደርሱን መረጃዎች አማካኙ መኮንን በአገር ውስጥ ባለው መዋፎ ሁኔታ ከትልቅ ቤተሰብ የተወለደ ውዳቂ ሰው ነው።»

ፍራንቾይዝ በመፍራት ጮረሮዋን አጠራች

«ይቅርታ አድርጉልኝ። ከሁሉም በላይ እኔ የምሻው በመሣከላችሁ ሰላምን እንድትፈጥሩ ነው። ስለአቢሲኒያ ስለምታወሩ፣ ቆንስላው ግቢ በነበርክበት ጊዜ የሰማሁትን ጥቂት ነገር ልንገራችሁ»

ከዚህ ቡኋላ በሙሴ ዱ ማይሴና በወንድም ፖስኒል መካከል የነበረውን ቃለ መጠይቅ ዘረዘረችላቸው።

«ይህማ ሦስት ያደርጋቸዋል ማለት ነው» አለ ሜትር ዠረሚ። «አሁን ያልተካተቱት ካቮቺኖች ብቻ ናቸው። እነርሱ ደግሞ ቅብዓ ሜርኑ አላቸው። ይህም ቢሆን የኮፕቲኩን ፖትርያርክ የጋለ ስሜት ያነሣሣ አልነበረም። ይገርማል! የሠራነው ሁሉ ያሣፍረኛል»

«እኔንም ያሣፍረኛል ዠረሚ» አለ ጆን ባፕቲስት፣ ዓይኖቹን ሰብሮ። «የማትተቸኝ ከሆነ ልንገርህ። እኔ የሠራሁትን ሁሉ ያከናወንኩት በንፁህ ልብ ነው። ይህም ሆኖ አልተሣካልኝም። ስመለስም በጉዞዬ ላይ እንዳችም ሌላ ነገር አላሰብኩም»

ሜትር ዠረሚ የብርጭቆውን ውስጥ አጮልቆ ተመለከተና የሆነ ነገር አጉተመተመ

«አየህ» ሲል ጆን ባፕቲስት ቀጠለ። «ወደዚህ በመጓዝ ሰይ እያለሁ እኔም የራሴን እቅድ አውጥቼ ነበር። በዚህ ዕቅድ ውስጥ የአሊስን መሄድ አስመልክቶ አንድም ነገር አላሰብኩም። ምክንያቱም መሄድዋን አላውቅም። ስመኘው የነበረው ማንም እንደሚያደርገው ላያት መጓጓት ብቻ ነው። ከዚህም በላይ ሌሎች ልከታተላቸው የሚገቡኝ ሥራዎች ነበሩኝ።»

ጆን ባፕቲስት፣በረዙና በትንሹ ጠሙ ሆኖ ሲታይ፣ ባለፈው ክፍለ ዘመን እንደሚታወቀው ገና ብዙ ትግልና ጦርነት እንዳለበትና፣ ማንግራይ እንዳሉት ክብሩን የማያስነካና ለዚህም ሲል ማንኑቱን በሕይወቱ ስመጠበቅ እንደሚዘጋጅ ሰው አስፈሪ ነው።

«እናንተ ልታከናውኑት ባቀዳችሁት ዓላማችሁ ትቀጥላላችሁ። ስለኔ ከእንግዲህ መጨነቅ የለባችሁም። ነገር ግን በጠረፍ አካባቢ ዜዳችሁ መርከብ ላይ ከምትሳፈሩ ወደ ምስራቅ ማለትም ወደ ስዊዝና ወደ ሲና ተራራ ትሄዳላችሁ። ዠረሚ? ስመሆኑ ወደ ግብፅ ለመጀመሪያ ጊዜ ስንመጣ አንድ ወር ያህል የከረምንበትን ገዳም ታስታውሰዋለህ?» አለው

«የወንድ መኳሣቱን አለቃ በትከሣታቸው ምክንያት ያከምካቸው ቦታ ነው?»

«በትክክል። እዚያ ዜዳችሁ ትደበቃላችሁ። እንዳይከታተሏችሁ ጥንቃቄ ካደረጋችሁ ማንም ሊያገኛችሁ አይችልም። እኔ የማከናውነውን ሥራ እንደጨረስኩ እዚያ መጥቼ እንገናኛ ለን።»

ሜትር ዠረሚ በድንገት ፀፀት ተሰማው

«ጆን ባፕቲስት፣ እስቲ ተከተለን። ስላለፈው ብቻ ሣወራህ ቆየሁ። ነገሮች ሁሉ እንደነበሩ ናቸው። ይህ ደግሞ ምንም አይደለም። አቢሲኒያውያኑ ለዘመናት እንዳደረጉት ሁሉ ራሣቸውን ይጠብቃሉ»

«የለም፣ አይደለም ዠረሚ። ያለፈው የሚቋጨውና የሚቀረው ከኛ ሞት በኋላ ነው። እኔ አሁንም ገና እዚህ የማከናውነው ጉዳይ አለኝ። ቃላቸውን የሚጠበቁ አይደሉም ሊለን የሚችልም ሰው አይኖርም»

ካይሮ፣ በስላሮችና በጆሮ ጠቢዎች የተሞላች ስለሆነች፣ምናልባት ለይተው ቢያውቁት ስሙን እንደሚያጠፉበት በመናገር ፍራንቾይዝ አስጠነቀቀችው። ሜትር ዠረሚ፣የደረስባቸውን ተፅዕኖ ማየት ስለቻለ፣ ቀደም ሲል ያደረበትን ፀፀት የሚያስወግድበትን ዘዴ ማሰብ አልቻለም። ጆን ባፕቲስት፣ ተቃውሞአቸውን ድርቅ ብሎ አልቀበልም በማለት ዝም አሰኛቸው። ከአንድ ሰዓት ስበለጠ ጊዜ ያህል አርሰ ከዜደ ቡኋላ በማህበረሰቡ ውስጥ ስለነበረው ሕይወት፣ ስለመድሃኒት ቅመማው የንግድ ሥራቸው፣ ስለ ዱ ሮውሊ ቅፍለት ሲጠይቃቸው ቆየ። ሜትር ዠረሚም ጥንቃቄ ሲያደርግላቸውና ሲንከባከባቸው የነበሩትን ሕመማን የስም ዝርዝር ሰጠው።

በመጨረሻም ዕረፍት ለማድረግ ሦስቱም ተሰያዩ። ከማሰዳው አስራ ሁለት ላይ ገና የመጀመሪያው የንጋት ብርሃን ሲወጣ ሜትር ዠረሚና ፍራንቾይዝ ሻንጣዎቻቸውን ሰብስበው ከትናንት በስትያ ምሽት ጆን ባፕቲስት ፈረሱን ካሰረበት ጋጣ፣ የራሣቸውን ፈረሶች አውጥተው አዘጋጇቸው። ፍራንቾይዝ እንደ ወንድ ለብሣለች። የቦት ጫማ ተጫምታ ሰፊ ክፈፍ ያለው ባርኔጣም አድርጋለች። ሜትር ዠረሚም ትንሽ ረዘም ከማሉቱ በስተቀር ተመሣሣይ ቁመና አለው።

ደህና ሁኑ፣ ብሎ በመልካም ምኞት ሲሰናበታቸው፣ ጆን ባፕቲስት ጥልቅ የስሜት ማዕበል ተሰማው። ከእንግዲህ በኋላ ለመገናኘት ርግጠኛ ላይሆኑ፣ ስመጨረሻ ጊዜ ተሰያዩ። ግማሽ ሰዓት ያህል ቆይቶ፣ በአትክልቶቹ መሣል ሰመጨረሻ ጊዜ ከተመላለሰ በኋላ ጥቂት ዘሮች ወስዶ በኪሱ ውስጥ ከተተ። ሜትር ዠረሚ የተወለትን ትንሽ የመድሃኒት ሣጥን ትክሻው ላይ አድርጐ ወጣ። ከአንድ ቀን በፊት እንደመጣ ወዳረፈበት፣ ወደ ከተማው የድሮ ሰፈር፣ ባዝራውን ወዳሰረበት ቦታ በቀላሉ እጥፍ ብሎ ተራመደ።

6

በመጀመሪያው ዕቅዳቸው መሠረት አሊስና ግብረአበሮችዋ ከአሌክሣንደሪያ ጥቂት ራቅ ባለ ቦታ ጠባቂዎችዋን አስወግደው በሴራናይካን ጠረፍ ወዳሰ ወደብ በመሸሽ በመርከብ ሆነው ፈረንሣይ ይደርሣሉ። ፍራንቾይዝና ሜትር ዠረሚ አርስዋ ገዞ ከጀመረች ከሶስተኛው ቀን በኋላ ጠባቂዎችዋ ላይ የደፈጣ ጥቃት ካደረሱ በኋላ ያገኙአትና አብረው ይሆናሉ።

አሁን ሁሉም ነገር ተለውጧል። እነርሱ አቅጣጫቸውን በምሥራቅ በኩል ወደ ስዊዝ አድርገዋል። እርስዋን ለመድረስ መዘግየታቸው አይቀርምና ይህ ደግሞ ከባድ ችግር ይፈጥራል። ምክንያቱም እነርሱ አቅጣጫቸውን እንደገና በደለሉ ምድር በኩል እስከ ማቋረጫው በመሄድ፣ወደ አልማንሱራ አቋርጠው ከዚያ ወደ አስማኢሊያ መሄድ ይኖርባቸዋል። ከፍራንቾይዝ ጐን ሆኖ በመጋለብ ላይ እያለ አዲሱ ዕቅድ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ አሰበ፣ ነገር ግን ፀሐይዋ ከአድማስ በላይ ወጥታ የአባይን ሜዳማ አገር እንደብርድ ልብስ ያፈነውን ጭጋግ ስትጸሰስው፣ብቸኝነትን ለምዶት የነበረው የኘሮቴስታንቱ መንፈስ መጠናከርና ለግልቢያውም ስሜቱን ነፃ ማድረግ ጀመረ። አልፎ አልፎ ፍራንቾይዝ እየተመለከተቸው ፈገግ ትላለች። እንቅስቃሴውና በወንዙ ዙሪያ ያለው የነፋሱ ሽውታ ጉንጮችዋን ማቅላት ጀምረዋል። ፀጉርዋ በባርኔጣዋ ሥር ሲሸፈን፣ በአንገቷ ዙሪያ ያለው ፀጉር ምን ያህል ለስላሳ እንደሆነ ሲገነዘበው በግልጽ የሚታይ መሆኑን ሜትር ዠረሚ አወቀ። እነዚህን ሁለት ግለሰቦች ማየት አስደሣች ነገር ነው። ሁለቱንም ዕጣ ፈንታ ፈትኗቸዋል፣የሕይወት መከራና ጊዜም ክፉኛ አደድሯቸዋል። አሁን ደግሞ በትኩስ ስሜት እያበቡ፣ ፍፁም ልስልስ ያሉና ከወደመ ከተማ ውስጥ ምንም ሳይሆኑ በመትረፍ የወርቅ ሣህናቸውን ከተደበቀበት እንደሚያወጡ ለዛ ያላቸው ሰዎች ይመስላሉ።

ወደ ጠረፍ እየወረዱ ሲሄዱ፣ብዛታቸው የሚጨምር የባህር ወፎች በውሃው ላይ ግራጫና ነጭ እየሆኑ ይንሸራተታሉ። መንደሩ ውስጥ ከዙ በኋላ ጥምጣም ያላቸው ብዙ ሽማግሌ ወንዶች አጋጠሟቸው። እጅግ ሰፊ የሆነው የባላገር መሬት በሸክላ የመሰሩ ቦዮች መረብ ተሸፍኖ፣ ተራ ግራጫ ሸሚዝ የለበሱና እነርሱን በፊርአናች ዐይን የሚመሰክቱ ሠራተኞች ተወርሯል። በጨዋማው ነፋስ የተበታተነውና በዘንባባ ዛፎች አጠገብ ያለውን ግር

የደለቡ በሬዎች ይግጣሉ። እነርሱ ራሣቸው መልሰው ያገኙት የወጣትነት፣ስሜታቸው በዙሪያቸው ያለውን የተለመደና ቀላል የሆነውን የዓለምን ወጣትነት እየተመገበ ይመስላል።

የአሊስ ክባድ ጉዝ ከሁለት ቀናት ጉዞ በኋላ አዳር ያደረገበትን፣ ደማንሱር ከተማ በአንድ ቀን ደረሱ። የቆንሲሉ ሴት ልጅ፣ ከአንዲት ባሏ ከሞተባት ሴት ጋር ትቀያየሸች። የዚህች ሴት ሟች ባል፣ ቤኑሎራት ይባል የነበረ ፈረንሳዊ ነጋዴ ነበር። ይህ ሰው እስከሞተበት ዕለት ድረስ በዚያች ትንሽ ከተማ የቆንሲሉ ቃል አቀባይ ሆኖ ሲያገለግል ነበር። ፍራንቾይዝና ሜትር ዠረሚ ጥራት በሌላትና ኮንቶች በሚያስተዳድሯት ደረቅ ጣቢያ አደሩ። ጋብቻቸውን ማረጋገጥ ስላልቻሉ ሁለቱም ሁለት የድርቆሽ ፍራሽ ተሰጥቷቸው፣ ከዘንባባ ስሌን በተሠራ መጋረጃ በተከፈለ ቦታ ሆኑ። ይህ ዝግጅት ቁመናቸው እንዳይጋለጥ ረዳቸው። የተትረፈረፈ የዶሮ አሮስቶና ቢጫ ሩዝ ከበሉ በኋላ፣ ሽማግሌው ኮንት፣ በጥርስ የለሹ ድዳቸው በመተባበር ዓይነት ፈገግታ ደህና እደሩ ብለዋቸው ሄዱ። ከእራት በኋላ ወገብ ለወገብ ተቃቅፈው ከተማዋን በሙሉ ዞሯት። ከርቀት የአሊስን ስረገላና የጠባቂዎችዋን ፈረሶች በከተማዋ ውስጥ ካሉት ጥቂት የደንጋይ ቤቶች አጥር ግቢ ውስጥ ተመለከቱ። ይህን እርግጠኛ ከሆኑ በኋላ፣ ወደማረፊያቸው ተመለሱ። ሜትር ዠረሚም አስተዳዳሪው ከንጋት በፊት እንዲቀሰቅሷቸው አደራ አሏቸው። የመጀመሪያው የቀን ብርሀን ከመፈንጠቁ በፊት ማረፊያቸውን ትተው ወደተመረጠው ቦታ አቀኑ።

የአሊስ ጉዝ በዝግታ ተንቀሣቀሰ። የቆንሲሉ ፈረስ አጣቢ ሚካኤል፣ ከሰረገላው ልንም አጠንብ ነው። ሙሉ ታሪኩ አልተነገረውም እንጂ የሆነ ነገር መጠንሰሱ ገብቶታል። በመሆኑም እንቅፋት መሆን አልፈለገም። አሊስን እንደራሱ ልጅ ስለሚያፈቅራት ወደ ገጸም ሲወስዳት ልቡ ተሰብሯል። በሌላ ወገን ሁለቱ ዘበኞች ተግባራቸውን ክልብ ተቀብለው ሌሊቱን ሙሉ በአሊስ በር ፊት እንዳወሩ ነበር ያደሩት። ሁለቱም ወሮበላዎች ሙሉ በሙሉ የሚያመሰግኑት ሙሴ ማቼን ነበር። አንዱ ፈረንሣዊ ነው። ይህ ሰው ከሶስት ዓመት በፊት ከጦር መርከብ ላይ ነፃ ተለቅቆ ያለምንም የሰነድ ማስረጃ አበክር ውስጥ ይኖራል። በቱርኮች ቡተያዘበት ጊዜም እንዲያድነው የቆንሰሉን ፀሐፊ ተማጠነው። ከዚያም ወዲህ በማያጠያይቅ ሁኔታ ታማኝነቱን አረጋገጠ። ሁለተኛው ሰው፣ ከካይሬን የመጣ፣ ከሕግ ውጭ በኢጣሊያዊና ቤኮፕት መካከል በተደረገ የፍቅር ግንኙነት የተወለደ ዲቃላ ነው። ይህ ሰው በአባይ የጭነት ወደቦች ላይ ዘበኛ ሆኖ ሰርቷል። ሙሴ ማቼ፣ የዜግነት ወረቀት እሰጥሃለሁ በማለት ከረዥም

ጊዜ በፊት ቃል ገብቶለት ነበር። ለዚህ እርግጠኝነት ስሌለው ተስፋ፣ በምላሹ ለማንኛውም ድንገተኛ ሥራ ሊጠራው እንደሚችል ነግሮታል።

ሠረገላው ጉዞ ሊጀምር ሲል አዲስ ችግር ተፈጠረ። አሊስን ያስተናገደችውና ባሏ የሞተባት ቤኡሎራት፣ ጉዞውን አቀላቀላለሁ ስትል ወሰነች። አሌክሣንደሪያ ውስጥ የምትሠራው ስራ ስላላት በቆንሲሉ ሠረገላ መጓዝ ፈለገች። ወዲያውኑ የጠባቂዎቹ ነገር ከፊቷ ድቅን አለባት። ይህም ቢሆን በጥቂት ሣንቲሞች እሽታ ሊያስገኝ ይችላልና ችግር አይደለም ስትል አሰበች። ለርስዋ የሚሆን ቦታም ተዘጋጀላትና ጉዟቸውን ቀጠሉ። ጎደኞችዋ፣በትርኢቱ ላይ በማንኛውም ጊዜ በድንገት ፀቡን እንደሚጀምሩ ስላወቀች ፖቤውና ሽኑጡ ያለበትን ሻንጣዋን እግሯ ስር አደረገችው። ይሁንና ለአደጋው ለመዘጋጀት ጊዜ ከመግዛት ይልቅ በቅናት ላይ ለነበረው ጭውውት ምላሽ በመስጠት መቀበጣጠር ጀመረች።

«ውይ፣ የኔ ኮረዳ» አለች ወይዘሮ ቤኡሎራት፣ ማር ማር በሚል ቅላፄ። «በመስኩቱ አሻግረሽ እንደዚህ ማየትሽን ተይው! ራስሽን ትጮሻለች። ይህን የምትመለከችውን የመሬት ገፅታ መልክ ትተሽው የምትሄጅው ነው። ይልቅስ ከእንግዲህ በኋላ እስክዘለሰዓለሙ ስለምታመልኪው ስለ ሰማያዊው ውበት ብታስቢ ይሻልሻል»

«ማዳም፣ አውቀውልኝ ከሆነ እኔም ስለመሣኪው ተስፋ ነው የማስበው»

«ገባኝ። አየሽ፣ እኔም ሙሉ በሙሉ ቀናተኛ መሆኔን ስትገነዘቢ ትደነቂ ይሆናል። ሕይወቴ በርግጥ የተለየ ዓይነት ነበር። ዕድሜዬን በሙሉ ለባሌና ለልጆቼ በታማኝነት ነበርኩ። ይሁንና አንዳንድ ጊዜ ለመሆኑ እኔ ለአግዚአብሔር አገልጋይነት አልተፈጠርኩም ይሆን? እያልኩ ራሴን አጠይቀዋለሁ።»

«የሚደንቅ ነው» አለች አሊስ አሁንም በመስኩቱ በኩል እየተመለከተች።

«ሕይደለም እንዴ? ሕይወቴን ሙሉ ላገኘው የምንጓጓለትን ሰላም፣ ሃይማኖታዊው ሕይወት ያስገኝልኛል ብዬ አምናለሁ።»

ሃር የመሰለውን ልብሷን ለብሣ፣ በባለፈው ክፍለ ዘመን ዘይቤ ፀጉርዋን ጠቅልላ ያለችው የተጨማደደችው አሮጊት እመቤት፣ የእግዚአብሔር አገልጋይ ብትሆን ኖሮ ምን ያህል ትወደድ እንደነበረ ለመግለፅ የድንግልና ስሜት ታሰባት።

«ታወቂያለሽ፣ ራሴን ለእግዚአብሔር አገልጋይነት አሳልፌ በሰጠሁበት ጊዜ ባለቤቴ ቀንቶ እንደነበረ?»

«ይህ እውነት ሊሆን ይችላል እንዴ?» ስትል አሊስ በትህትና ጠየቀች

ለግማሽ ሰዓት ያህል አሰልቺ ከነበረው ውይይት በኋላ፣ ሠረገላው ክፉኛ በሚታጠፍ መንገድ ላይ ዝግ ሲል ሁለት ፈንጂዎች በርጥበት አዘሉ አየር ውስጥ ተንጸዱ። አሊስ፣ ወደ መስኩቱ ፈጥና ብትንቀሣቀስም ምንም ማየት አልቻሉም። በኋለኛው መስኮት ላይ ፈትዋን አስጠግታ ተመለከተች። ከአጃቢ ጠባቂዎቹ አንዱ ተመትቶ ኖሮ መሬት ላይ ወደቀ። ሚካኤል ሠረገላውን አቆመው። ሁለተኛው ታጣቂ ፈረሱ ላይ እንጣጥ ብሎ ለመውጣት ስለቻለ ወደ ሠረገላ ነጂው ደረሰ። ፈረሶቹን በሃይል እየገረፈ እንዲያስጋልባቸው አዘዘው። በዚያኑ ጊዜ ከአትክልቱ ሥፍራ በስተደርባ፣ ከደረቁ የድንጋይ አጥር በኋላ በፈረስ ላይ ሆኖ ሲያሣድደው የነበረው ሜትር ዝረሚ፣ ዘበኛው ላይ ተወርውሮ ደርሶበት የታጠቀውን ጉራዴ መዘዘበት። ዘበኛውም፣ ጉራዴውን ከሰገባው ፈጥኖ በመምዘዝ መፋለም ጀመረ።

የመጀመሪያ ስሜቷ ድንጋጤ የነበረ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር በአዲስ ፈተና ውስጥ እየከተተኝ ነው ስትል ማዳም ቤኡሎራት ገመቱት። ምርር ብሳም እንደ እንሰሳ በማላዘን አለቀሰች። በመሰኮቷ በኩል ጦርነቱን በከፍተኛ ጉጉት ትከታተል የነበረችው አሊስ፣ ዞር ብላ፣ አሮጊቷ ዝም እንድትል ነገረቻት። ሴትዮዋ ግን የባሰውኑ በከፍተኛ ድምፅ አምባረቀች። ለዘለዓለም በማይረሣት ሁኔታ፣ ወጣቷ ሴት ወደ አሮጊቷ በቀጥታ ዞራ፣ ምንም ሣትናገር ሁለት ጊዜ ፊቷን በጥፊ አጮለቸው።

«ዝም ትይ እንደሆነ ዝም በይ፣ አንቺ ጨርቄሳ አሮጊት!»

እጆችዋን በነደዱት ጉንጮችዋ ላይ አድርጋ፣ በሠረገላው ዙሪያ እየተከናወነ ያለውን ድርጊት ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ በፍርሃት መመልከት ጀመረች። ከጥቂት ጊዜያት በፊት በከባድ ፀሎት ውስጥ የነበረችውና የክርስቶስ እጮኛ የሆነችው መነኩሲት፣ የለበሰችውን ምኞት የሰሸ ልብስ አውልቃ የፈረሰኛ ልብስ ለብሳ ተመለከተቻት። ልጃገረዲቱ በመቀጠልም ወለሉ ላይ ያለውን የቆዳ ቦርሣ ከፈተችው። የተጫማችውን አውልቃ በመወርወር እንደቸነኳት ቡኒ የሆኑ ባለዘለበት ቦት ጫማዎችዋን አጠለቀች። ከውጭ የጉራዴዎች መጋጨት አሁንም ይሰማል። ሜትር ዝረሚ የሚያይል ቢመስልም ሌላኛው ሰው ራሱን በሃይል ይከላከላል። በቅፅበት የሁኔታዎች አቅጣጫ ተሰወጠባቸው። ፈረሰኛ የቱርክ ወታደር በዚህ ጠመዝማዛ

መንገድ ላይ እየጋለበ ሲደርስ፣ እንዲቆም የተደረገውን ሠረገላ ተመለከተ። ጥቃት አድራሹ ማን እንደሆነ ለመለየት ብዙም ጊዜ አልወሰደበትም። ይህ ወታደር፣ የደንብ ልበስ ለብሶ የቀረውን፣ የማቼን የቤት ሠራተኛ ለመርዳት ቆልማማውን ጉራዴውን ይዞ ተጣድፎ ገባ። ሜትር ዝረሚ ወደ ኋላው ፈንጠር አሉ። ፍራንቾይዝ ከአሞሩ አጥር በስተጀርባ መሆንዋን በግርግሩና በትርምሱ መሃልም ሽጉጧን እንዳትጠቀም በርቀት ላይ እንደሆነች፣ አሊስ ተመለከተች። አሁንም በሰረገላው ውስጥ ሆና በመነፋረቅ ላይ ወዳለችው አሮጊት ዘንድ ተመልሳ በመግባት አትናንት ምሽት በፊት አቀባብላው የነበረውን ሽጉጥ አሊስ ያዘች። አነጣጥራም የባሩድ ማቀጣጠያውን አስተካክለችው። ተዋጊዎቹ ከርሷ ራቅ የሚሉት ጥቂት ርምጃዎችን ብቻ ነው። ብቸኛው የቱርክ ወታደር በአይታዋ ውስጥ እስኪገባላት ጠብቃ ተኩሰች። የቱርካዊው የጦራዴ እጁታ ሽቅብ ጮነ። ጥይቱም በቀጥታ ደረቱን በጥርቀ በሌላው በኩል ውጣ። ወዲያውኑ እጥፍጥፍ አሉ። ተባባሪ ጓደኛው መመታቱን በመመልከት፣ ከቆንስላው የመጣው ጠባቂ፣ በዝረሚ ፊት ለአፍታ ያህል ፈዝዞ እንደቆመ፣ የዝረሚ ጉራዴ ፊቱን ለሁለት ሰንጠቀው። ሁለተኛው እንቅስቃሴው ልቡን በጠረቀው። ጠባቂውም ከፈረሱ ላይ ወደ ኋላ ዘፍ ብሎ ወደቀ።

አሊስ በደስታ ጮኸች። ይሁንና ልታጠፋው የምትችለው ጊዜ አልነበራትም። ፍራንቾይዝ የወደቁትን አስከሬኖች ከመንገዱ ወደ ዳር በመጎተት ከግድግዳው ኋላ ደበቀቻቸው። ሚካኤልም ሠረገላውን ወደ ኋላ ዞር አድርጎ በዘንባባ ዛፎች አጠገብ ደበቀው። ሜትር ዝረሚ፣ ሽማግሌውን የጋሪ ነጂ ወንጀሉ ሲፈፀም በቦታው እንዳልነበረ ለማረጋገጥ እንዲቻል ጠበቅ አድርጎ አሰረው። አሊስ ራሷ የአሮጊቲን ቤአሎራትን አፍ ለጉመች።

«ያየሽውን ሁሉ በሚገባ አስታውሺ» አለቻት እያዘዘች። «እኔ ራሴ በሁለት ቱርካውያን ሽፍታዎች ታፍኜ ነበረ። ከዚህ የተለየ ብትናገሪ ጓደኞቼ ተመልሰው መጥተው ነፍስሽን ወደ ሰማይ ቤት እንድትቀርብ ያደርጓታል»

ከዚህ በኋላ ሣቀች

«እና በገዳሙ ውስጥ አሁንም የኔን ቦታ የምትፈልጊው ከሆነ ነፃ ነው»

ከዚህ በኋላ በእንደኛው ዘበኛ ፈረስ ላይ ዘልላ ወጣች። ፍራንቾይዝ ማሠሪያውን አላልታው ነበርና ሦስቱ ጓደኞሞች ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመጋለብ ነጐዱ።

ከኋላቸው በቂ ርቀት መኖሩን ሲያውቅ ሜትር ዝረሚ ከመንገዱ ወጣ አድርጓቸው በአንድ ጉብታ ላይ በሚገኝ ፍርስራሽ በኩል ወሰዳቸው።

ከፈረሶቻቸው ላይ በመውረድ እንሰሳቱን እንዲያርፉ አደረጓቸው። ካይሮ ውስጥ ምን እንደተፈፀመ፣ ፕሮቴስታንቱ ለአሊስ ተረከላት።

«ጆን ባፕቲስት ተመልሷል» ስትል በመደነቅ ተናገረች።

ከብዙ ጭቅጭቅ በኋላ ወደ ከተማ ሊመለሱ ነገሯት። የምታፈቅረው ሰው ከነርሱ የግማሽ ቀን የግልቢያ ርቀት ላይ በተቃራኒው አቅጣጫ መሆኑን ቢነግሯትም ይህ በራሱ ቢቃይ ነው። ፅጣ ፈንታ፣ ፍቅረኛሞች ፍቅራቸው በደስታ ከከብ ስር የመሆኑን ምልክት ሲያመለክታቸው፣ እነርሱ ራሣቸው ይበልጥ በድፍረት ሊቋቋሙት ይሞክራሉ። ጆን ባፕቲስት፣ ከቬርሣይለስ ማምለጥ ችሎ ከሆነና ከንጉሡም ካፈተለከ አይፈራም። ምክንያቱም እርሷ ተመልሳ ካይሮ ውስጥ ትታያለች። ሜትር ዝረሚና ፍራንቾይዝ ትዕግስት እንድታደርግ በመጮትጮት ራሱ ጆን ባፕቲስት የሰጣቸውን መመሪያ ደግመው ነገሯት። በመጨረሻም አመነቻቸውና ወደ ሲና ለመድረስ ፅቅድ ነደፉ።

«ለጊዜው አሁን በዚህ ብቸኛና ምንም በሌለበት ቦታ እንተኛና መንገዳችንን እንደገና ማታውኑ እንቀጥላለን» አለ ሜትር ዝረሚ

እንቅልፍ ሊወስዳቸው ባይችልም፣ አውላላው መሬት ላይ ለሽለብታ ያህል ዝርግትግት ብለው ዕረፍት አደረጉ።

ከማታው አስራ ሁለት ሰዓት ሲሆን፣ ፈረሶቻቸውን ጫጭነው እንደገና ጉዟቸውን ቀጠሉ። ምሽቱ ንፁህ ሰማይ ስለነበረው፣ የጨረቃዋ የወተት አረፋ የመሰሉ አንድ ሺህ አንድ ነፀብራቆች በወንዙና በየበዩ ውሃ ላይ ስለተፀቱ በደለሉ መሬት ላይ በቀላሉ መጋለብ ቻሉ።

ሊነጋጋ ሲል የኢስማኢሊያን ከተማ ለማየት የሚችሉበት ቦታ ደረሱ። በአስራ አንድ ሰዓት አካባቢ ሲዘልቁ፣ ከተማዋ ገና በፀጥታ እንቅልፍ ላይ ነበረች። የሱቆች የእንጨት መከለያዎች እና መስኮቶቻቸውም እንዲሁ እንደተዘጉ ነበሩ። በሮቻቸው በተሰይ በጥብቅ የተዘጉ ነበሩ። በመንገዶች ላይ ነፍስ አይታይም። የጠለፋው ዜና አስቀድሞ ካይሮ ሳይነገር አዚህ ሊደርስ ስለማይችል ሜትር ዝረሚ አልሰጋም። ይሁን እንጂ እርሱም ቢሆን እንደ ሁለቱ ሴቶች በዚህች ያልጠፋች ወይም ነዋሪዋ ፊጽሞ ትድት ያልሄደችና የሞተች የምትመስል ከተማ ፀጥታ ስጋት አሣድሮበታል።

ግራና ቀኙን በሁለት የኦቶማን መስኪዶች የሀውልት መግቢያ በረንዳዎች ከሚዋሰነው ሠፊ ጐዳና ሊደርሱ በአንድ ቤት ሦስተኛው መከለያ በድንገት ሲከፈት ሰሙ። ወዲያውኑም አንዲት ወጣት ሴት መስኩቱ አጠገብ ብቅ ሰትል ተመለከቱ። ዐይኖችዋን በአጀቧዋ እንደማከለከል አድርጋ እንደ አይነ ስውር ዐይናችዋን ጨፈነቻቸው። በዚያው ቅፅበት ከመንገዱ ባሻገር የሚገኝ ቤት መስኮትም ቀንሦጥጦ ተከፈተና አንድ ሽማግሌ አጮንበሰ በመንገዱ ላይ መንገዝ ጀመረ። ያደረገው ኮፊያ በጨርማታው ግንባሩ ላይ ተንጋዷል። ሌሎች መጋረጃዎችም መከፈት ጀመሩ። የአንድ ሱቅ መዝጊያም አፋሽክ።

«ለምንድነው ለመኮማተ እንዲህ የምትዘገየው?» አለ ሜትር ዣሪሚ ከበላያቸው ባለው መስኮት ውስጥ ለነበረው ሽማግሌው ሰው፣ በአረቢኛ

ሰውዬው የሚያናግረው ማን እንደሆነ ለማየት ዙሪያውን ቃኘ። እርሱም እንደሌትዮዋ ዐይኖቹ ጨፍኖ የማየት ችግር ያለበት ነበር።

«እዚህ መንገዱ መሣል ነው ያለሁት፣ ሃሎ! » አለ ሜትር ዣሪሚ

«አሃ፣ እንግዳ መሆን አለብህ!» አለው ሽማግሌው

«ዛሬ ማለዳ መድረሴ ነው»

«እናም በተሰበ መኮዳታችንን አታውቅም ማለት ነው»

ፕሮቴስታንቱ ነገሩ ትዝ አለው። ካይሮ ውስጥ ማለ፣ በስዊዝ የባህር ወሽመጥ በኩል ራቅ ብሎና በአንዳንድ ከተሞች ውስጥ ወረርሽኝ ተከስቶ እንደነበረ ሲወራ ሰምቷል። በውቅቱ በዚያ አቅጣጫ የመሄድ ዕቅድ ስላልነበረው የሰማው ነገር ከአዕምሮው ጠፍቷል።

«ዛሬ ተገልለን የመሰንበታችን የመጨረሻው ቀን ነው። ለመሆኑ በመንገዱ ላይ ብዙ አስከሬኖች ተመለከትክ? አለው ሽማግሌው ግብፃዊ

«እስከ አሁን አላየሁም። ሁሉም ሰው በጣም ጤነኛ ይመስላል» አለ ሜትር ዣሪሚ

ከዚህ በኋላ መስኮቶች ሁሉ ተከፈቱ። ሰዎች ከወዳህ ማዶ ወደዚያ ማዶ ቃላትን በደስታ መለዋወጥ ቀጠሉ። መንገዱ በደስታ ሁካታና ዋካታ ተሞላ። በሮች ሁሉ ተበረገዱ። ወንዶች፣ ሴቶችና ሕፃናት በጭለማው ግራ ቢጋቡም እየተጠባበቁ በመሰብሰብ መንገዱ ላይ መደነስ፣ መዋከብና አይነ ስውር የሆኑ ይመስል እርስ በርሣቸው እየተንቀራፈፉ መጋጨትና ከልባቸው በመሣቅ መደሰት ጀመሩ።

በሁካታውና በጫጫታው መሃል ሶስቱ መንገደኞች ሳይስተዋሉ አለፉ። ለፈረሶቻቸው ድርቆሽና ለራሣቸውም የደራረቁ ፍራፍሬዎችን አገኙ። ባለመደብሮቹም ለረኃየም ጊዜ ሥራ ፈትተው ቆይተው ስነለበረ በጥሩ ዋጋ ሸጡላቸው።

ቅድመ ጥንቃቄ ካለማድረግ የተነሣ የምግብ ሽቀጣሽቀጦችን ለሚሸጥላቸው ሰው ሜትር ዣሪሚ በተደጋጋሚ ወደ ስዊዝ እንደሚጓዙ ነገረው። ከከተማዋም ወጥተው ወደ ባህረ ሰላጤው አቅጣጫ ጉዟቸውን ጀመሩ። ከመንገዱ ጥቂት ርቀት ወጣ በማለታቸውና ቀኑም ገና ስለሆነ ከአንድ ትንሽ የአሸዋ ቁልል ተራራ ግርጌ እጅብ ብሎ በበቀለ የዘንባባ ጥሻ ውስጥ አረፍ ብለው ድብን ያለ እንቅልፍ ወሰዳቸው። በምሽቱ ቅዝቃዜ ደግሞ እንደገና ጉዟቸውን ቀጠሉ። መንገዱን በቀጥታ ተከትለው ከመንገዝ ይልቅ ወደ ኋላ ተመልሰው በምስራቅ አቅጣጫ ወደ ሲና ተራራ የሚያመራውን አቧራማውን የአግር መንገድ በመያዝ ወደ ምድረ በዳው አቀኑ። ብዙም ማይቆዩ አረንጓዴ እዕዋት ሁሉ ከኋላቸው ቀሩ። በዙሪያቸውም በምድረ በዳው አሸዋማ አልጋቸው ላይ እንደ ሃውልት ሽቅብ ከተመዘዙት ድንጋዮች ሰማያዊ ጥላ በስተቀር አንዳችም ነገር የለም። እንዲህ ባለ የምድር ገፅታ ገዞ ላይ፣ ግመሎች የበለጠ ተመራጭ ይሆኑ ነበር። ይሁን እንጂ ፈረሶቻቸው እዝህ የአካባቢውን ምድር ያቆሸሹ፣ሹልና ስለታም ድንጋዮችን በድፍረት ተቋቋሚቸው። እኩለ ለሊት ላይ የመጀመሪያውን የምድረ በዳ ገነት አካባቢ ሲያቋርጡ ላለማረፍ ወሰኑ።

በሰማዩ ውስጥ በተረፖት ከዋክብት እየተበራቱ ጉዟቸውን አጋጋሉት። ሜትር ዣሪሚ ብዙ ጊዜ ወደ ፍራንቹይዝ ይመለከታል። ይሁን እንጂ የአሊሰን ቅር መሰኘትና ሃዘን በመፍራት ስሜታንም ላለማቁሰል በማሰብ ወደ ጓደኛው አብዝቶ ፈገግ ከማለት ተቆጠበ።

7

የካይሮ ፓሻ ከሚኖርበት ምሽግ በስተጀርባ፣ ከቤተመንግስቱ ረዥም ግንብ በታች፣ አንድ ጭር ያለ መንገድ አለ። ወደዚህ መንገድ ምንም አይነት ነገር ማለትም በርም ይሁን መስኮት እንዲከፈት አይፈቀድም። በዚህም የቱኒሣ የቤተመንግስቱ ጀርባ በአንድ በኩል እና እንዲሁም ግድግዳ ብቻ የሆኑት የከተማው ቤቶች በሌላው ወገን ሆነው ሲያዩት፣ መንገዱ በሁለት በማይቋረጡ ግድግዳዎች መሃል እንደ አባብ እየተጥመለመለ ያለ የመስኖ ቦይ ወይም ተራ ቦይ ይመስላል። ጠባቂዎች ቀንና ሌሊት ይቃኙታል። ይህን የምስጢር መንገድ አንድም ሰው አይደፍረውም። ይህም ሆኖ ፍፁም ከሌላው በጣም ቡተነጠሰው የጠባቡ መንገድ መሃል አካባቢ፣ አንድ በብረት ቁልፎች የተቆለፈ፣ ነገር ግን በፊት ለፊቱ በኩል የመክፈቻው ቀዳዳ የሌለበት መግቢያ አለ። የዚህን ታላቅና ሰፊ ግንብ በሽነቆረው በዚህ መግቢያ በኩል፣ ማንም ሰው ወደ ቤተመንግስቱ አደባባይ መዝለቅ ይችላል። በዘመናት ውስጥ የተሰዋወጡት ፓሻዎች በዚህ መግቢያ ላይ የያንዳንዳቸውን ባህርይ ሊገልፅ ለሚችል ለተለያየ አገልግሎት ተጠቅመውታል። ፖንሴ፣ ወደ አቢሲኒያ ለመንገዝ ከከተማው እንደለቀቀ፣ ከፊረስ ላይ ወድቆ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሞተው እንደ ሁሣይን ያሉት፣ ይህን መሸሸቢያ የከፈቱት ማንነታቸው ሣይታወቅ ወደ ከተማው ዘልቀው ለመግባትና በጉዟቸውም ላይ ሰዎች ምን እንደሚሉ ለመስማት፣ በሃሩን አልረሺድ ስልት ሌረኞችንና ተንኮለኞችን ለማሣደድ ይጠቀምበት ነበር። ሌሎቹ ደግሞ ባልተቋረጠ ቅኝት ውስጥ ተቆልፎ እንዲቆይ አድርገውታል። እንዲህ የሚያደርጉት ለነፍሣቸው በጣም የሚፈሩት ናቸው። እንግዲህ የሰዎችን ውስጣዊ ስሜትና ፍላጉት፣ ሁልጊዜም የሚያረካቸውን ነገር የሚያውቀው አሳህ ሲሆን፣ እነዚህ ለሕይወታቸው የሚሰጉት ፓሻዎች፣ ብዙ ጊዜ የሚሞቱት በቅጥር ነፍሰ ገዳዮች እጅ ነው። አንዳንዶቹ ደግሞ ይህን የጓሮ በር በአፈሌል የማይቀበሏቸውን ሰዎች የሚያስገቡበት አደረጉት። የመሃመት ቤይም የዚህን በር አጠቃቀም ይህን ይመስላል። ዙሪያውን በፀሎት፣ በተስፋ፣ በግብፅ ውስጥ በሚገኙ ወግ አጥባቂ ሙፍቲዎችና ኢማሞች የማዕናኛ ቃላት ቢታጀብም እርሱም ቢሆን አልፎ አልፎ ሃሣብ ግትርነቱን ለሰለስ ያደርግና፣ ጠንቃቃ የውጭ ጉብኚዎችን በዚህ በር በኩል እንዲገቡ ይፈቅድላቸው ነበር። እነዚህ ጠያቂዎች እንዲገቡ የሚደረጉት በመሸሎኪያው በኩል ነው።

መሃመት ቤይ፣ በእስልምና ሕግ አራት ሚስቶች አሉት። ከነርሱም አሥራ ሁለት ልጆችን አግኝቷል። እነዚህ የተቆጠሩት ልጆች በሕይወት ያሉት ብቻ ናቸው። እንዳለመታደል ሆኖ ታዲያ መሃመት ቤይ ሊገታ የማይችል የውጭ አገር ሴቶችን የማደን ስሜት አለው። ይህን አይነት ፍላጉት ያደረበት፣ አውሮፖ ውስጥ በዘመቻ ላይ ሣለ ነበር። እነዚያ የተባረኩና ከረዥም ዘመናት በፊት የነበሩ ጊዜያት ቀላል ነበሩ። በነዚያ ጊዜያት አረማውያን ቆነጃጅትን በምርኮ ይቀበላቸዋል። ይህን ድርጊት አይሆንም ብሎ የሚቃወምና የሚያጠቃም አልነበረም። ሁለም ዓይነት ቁመናና ዕድሜ ያላቸውን ፈረንሣውያን ሴቶች ንብረቱ አድርጓቸው ነበር። እውነቱ ይነገር ከተባለ፣ ሰርሱ ሁሉም ምንም ልዩነት የላቸውም። መሃመት ቤይ ደስ ይለው የነበረው፣ የሌላ እምነት ተከታዮች የሆኑ ካቶሊኮች፣ አይሁዶች፣ ኦርቶዶክሶች ወይም እምነት የለሾችም ቢሆኑ አግሮቻቸውን አንፈራጥጠው ሲቀመጡ የሚሰማው ስሜት ነው። ይህን ሲያከናውን የራሱን እምነት በመተው አይደለም። በእምነቱ በኩል አይታማም። የራሱን እውነተኛ አማኒያን ፍሬያቸው፣ ቀደም ሲል ሌሎች ኦርሰውና አሰስለሰው ያዘጋጁትን ትልም በመንጠቅ በዚያ ላይ መትከል ለነብዩ ትሁት አገልጋይ የሆነ ያህል ይሰማዋል። ሙፍቲዎችም፣ ፓሻው የሣይማኖት መልዕክተኛ ያህል የሚያከናውነውን የጋለ ፍቅር ስለተቀበሉት ሌላውን ተግባሩን የተመለከቱት በሌላ መልክ ነው። ይሁን እንጂ በዚህ የቱርካውያን ግዛተ ዘውድ አካበቢ ያለውን የሞራል ትክክለኛነት፣ ተገዢነትና በተለያዩ እምነቶች መካከል ያለው ሚዛናዊ የመንፈስ አርካታ ስላለ፣ በተቻለ መጠን የፓሻውን የተለያየ ስሜትና ዝንባሌ ለማስደሰት ይሞክራል። ትንሿ የስርቆሽ በር የምታገለግለውም ለዚሁ ነው።

በውትድርና ዘመኑ ከቦታ ቦታ ያደረጋቸው እንቅስቃሴዎች፣ በአካሉ ላይ ከባድ ጉዳት ጥለውበት አልፈዋል። በዚህም የተነሣ ካለፉት ወራት ጀምሮ በሚሰማው ስቃይ ምክንያት፣ ሌላው ቀርቶ መኖፎ ወንጀል የፈፀመ ሰው እንኳ ቢቀርብለት ለመቅጣት ብርታቱና ፍላጉቱ አልነበረውም። እንደዚሁም ሁሉ የፈለገውን ያህል ቆንጆ፣ ወጣትና በሃይማኖታም የተጠላች ሆና ብትቀርብለት ብርታቱና ፍላጉቱ አልነበረውም። ባለፉት ሦስት ወራት በዚህ የጓሮ በር ተጠርተው የሚመጡት ሐኪሞች ብቻ ነበሩ። ከነርሱም መካከል ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ዝረሚ ነበር።

ዝረሚም ከግምጉቱ በተወሰኑ ሰዓት ቀናት ውስጥ እኩለ ሌሊት ላይ ይመጣል። የክላ ዘበኞችም ይህን ስለሚያውቁ «ሄሌቦሬ» የሚሰውን የይለፍ ቃል ሲለሙ ያስገኙታል። የዚያን ዕለት ምሽትም እንደተለመደው በትልቅ ክት ተጀቡኖ፣ ሰፊ ባርኔጣ አድርጉ መጣ። የይለፍ

ቃሉን ተናግሮ በስርቆሹ በር ገባ። በባዶ እግሩ ሆኖ፣ ነጭ የለበሰ ሰው ሃኪሙን በእምነ በረድ ደረጃዎች በኩል ወደ አንዲት አነስተኛ የቤተመንግስት ቅጥር ግቢ መርቶ ወሰደው። በቱርካውያን ዘይቤ በተሰናዳ ሽምል የቅስት ማለፊያ በር አልፎ፣ ግድግዳው በሰማያዊ ሴራሚክ በተጌጠ ባለ ስምንት ማዕዘን ክፍል ውስጥ አስቀመጠው።

በረዥም ሰንሰለት በጣሪያው የጥድ ከንች ላይ ከታሰረ መብራት፣ አራት ሻማዎቹ ብቻ የሚበሩበትና የተለያዩ ቀለማት ያሉት የመስተዋት አምፑል ተንጠልጥሏል። ፓሻው፣ በጥግ በኩል በአንድ የአራት መብያ ጠረጴዛ አጠገብ ተቀምጧል። እግሮቹን ወደ አንድ የነሃስ ምድጃ ዘርግታቸዋል። ምድጃው ባለሦስት እግር ሲሆን የጢስ ማውጫው በቀጭን ቱቦ ወደ ውጭ እንዲወጣ ተደርጓል። እግረኛው ሰውዬ ተመልሶ ሄደ።

«ወደዚህ ቀረብ በል። ዶክተር» አለ መሃመት ቤይ በአረቢኛ

ጉብኚው፣ ከአንጨትና ከዝሆን ጥርስ በተሠራ በርፖማ ላይ ተቀምጦ የለበሰውን ኮት ሲያወልቅ ቱርካዊው በፍርሃት ወደ ኋላ ካለ በኋላ፣ እጅታው እንቁ ሆኖ የታጠቀውን ቢላዋ አፈፍ አደረገ።

«ለመሆኑ አንተ ማነህ?» ሲል ጠየቀው።

ዘበኞቹን ሊጠራቸው ምንም አልቀረውም ነበር። ጆን ባፕቲስት ፈጥኖ ገታው።

«ጌታዬ፣ ስጋት አይግባህ። የተሳክሁት በሜትር ዝረሚ በራሱ ነው። እኔ ሽሪኩ ነኝ። ስለኔ እስክሣሬ ድረስ ምንም አልነገረዎትም?»

«የኢትዮጵያውን ንጉሥ ያከምከው ሰውዬ ነህ?»

«በትክክል እኔ ነኝ ጌታዬ»

ጆን ባፕቲስት ዝቅ ብሎ እጅ ነሣ

«ስስቀድሞም እንድታየኝ አጥብቄ የፈለግህህ አንተን ነበር። ሆኖም ሽሪክህ ወደ አውሮፓ መሄድህን ነገረኝ» አለ መሃመት ቤይ

«ይኸው አሁን ገና መድረሴ ነው»

«እንግዲያው ዝረሚ ለምን አብሮህ አልመጣም። ከዚህ አይነቱ አስፈሪ ስጋት ያድነኝ ነበር»

«እርሱ ራሱ አሁን ጤነኛ አይደለም። ይቅርታ እንዲያደርጉለትም እንድነግርዎ ጠይቆኛ ል»

ፓሻው በምድጃው አጠገብ ተመልሶ ተቀመጠ።

«እጅግ በጣም ጥንቃቄ ሲያደርግልኝ ነበር። ሁልጊዜም ቢሆን እርሱ እንደማይስተካከልህ በመግለፅ፣ አንተ እዚህ ብትኖር ኖሮ ምንኛ ጥሩ እንደነበረ ሲመኝ ነበር»

«ይህን ዓይነት የሚናገር የልብ ጓደኛ ነው። እውነቱ ግን፣ሁለታችንም እንደጋገፋለን። እኔ መድሃኒቶችን ሣዘዝ፣ እርሱ ቀምሞ ያዘጋጃቸዋል። የመድሃኒት ቅመማው ለኔ ባዕድ ነው»

«እንዲህ ከሆነ እንግዲያው መርምረኝና የሚያስፈልገኝን የህክምና ጉዳይ ወስንልኝ» አለው ፓሻው በድካም።

ጆን ባፕቲስት፣ ሕመሙ ምን ያህል ጊዜ እንደቆየበት፣ መነሻ ስበቡ ምን እንደሆኑና በትክክል ምኑ ላይ እንደሚያመው ሽማግሌውን በስፋት ጠየቀው። ከዚህ በኋላ ስለራሱ የሕይወት ታሪክ፣ ስለሚበላውና ስለሚጠጣው፣ እንዴት እንደሚተኛ፣ ስለሴቶች ያለውን ስሜት እንዲነግረውም ጠየቀው። በዚህ ዘዴ ጆን ባፕቲስት ከፊት ለፊቱ ያለውን ሰው ውስጣዊ ማንነትና ስሜት ይረዳል። የሰውዬውን ተፈጥሮአዊ ሥረ መሠረት በማመዛዘን ከሌሎች ነገሮች ጋር ማለትም ከሌሎች ሕይወት ያላቸው ነገሮችና ከዝሁ ነገሮች ቅጠሎችና ፍሬዎች ጋር ያለውን ምስጢራዊ ግንኙነት በመመልከት ጤንነት እንዲመለስለት ሊያደርግ ይችላል።

«የመዳን ዕድል እንዲኖረኝ ልታደርግ ትችላለህ?» ሲል ፓሻው ጠየቀው።

«ይህ የሚወሰነው እንደ ጥያቄው ዓይነት ነው። መዳን ማለት እንደገና የሃያ አመት ጉረምሣ መሆን ማለት ከሆነ የሚቻል አይደለም። ጌታዬ፣ የዚህን ዓይነት ነገር የሰም። ነገር ግን ሰላማዊ ጥንካሬና አሁን ባሉበት ዕድሜዎ ላይ የሚያስፈልግዎትና ተዝዎ የሚሆነውን ደስታ ማለትዎ ከሆነ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሊያገኟቸው እንደሚችሉ ላረጋግጥልዎ እችላለሁ።»

ቱርካዊው ተደሰተ።

«መድሃኒቶቹን ለማዘጋጀት ወደ ሥራ ቦታዬ መመለስ ይኖርብኛል። እናም ነገ እኔው ራሴ ይዤልዎ እመጣለሁ» አለ ጆን ባፕቲስት።

«እንግዲያው እንዳትዘገይ» አለው ፓሻው፣ ትዕግስት እንዳጣ በሚያመለክት ሁኔታ። «በነገራችን ላይ ዝረሚ ማይነገርህ እንደማይቀር ባውቅም፣ እኔም በደንቡ መሠረት ልነግርህ ይገባኛል። ይህን ሁሉ ነገር በተመለከተ አንድም ቃል ትንፍሽ አትልም። በተለይም ለፈረንሳዮች»

«ጌታዬ፣ እኔም እርስዎ ተመሣሣዩን ውለታ እንዲያደርጉልኝ መጠየቅ አወዳለሁ። በፈረንሣውያን ማህበረሰብ ውስጥ የኔን መመሰስ የሚያውቅ አንድም ሰው የለም። በተለይም ቆንሲሉ አያውቁም። እኔም ብሆን መመሰሉ እንዲታወቅ አልሻም። በርግጥ ሽሪክን የምጐበኘው ማታ ማታ ሲሆን፣ቀን ቀን፣በጥንቱ የአረቦች መኖሪያ ውስጥ በሚገኝ ፔንሲዮን ስኒዜው እየኖርኩ ነው»

«እውነትህን ነው? በጣም ይገርማል» አለ ፓሻው «ንጉሥህን ልታያቸው እንደሄድክና በተልዕኮህም እምነት የተጣለብህ ነበር የመሰለኝ»

«አይ ጌታዬ፣ ታሪኩ ክፉና የሚያም ነው።» ሲል የራሱን መጥፎ ዕድል ሌሎች እንዲሸከሙለት በማይፈልግ ሰው የአነጋገር ቅላፄ «እናም ረዥም፣ እጅግ ብዙ አስገራሚ ውጣ ውረዶች የነበሩበትና በአጭሩ ሊያያዝምዎ የሚችል ታሪክ ነው»

«አስተ ታሪክህን ንገረኝ» አለው ፓሻው። በአፈ ታሪክ እንደሚታወቀው እንደ ሱልጣን ሻህርያር፣ ልብ አንጠልጥል እንደሆነ ወግ የሚያስደስተው ሌላ ምንም ነገር እንደሌለ ሁሉ

«ደግ እንግዲያው» አለ ጆን ባፕቲስት «ወደ አቢሲኒያ ሄድኩ»

የገዛውን ትረካ በረዥሙ ገለፀለት። ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር መገናኘቱን፣ ከክንፈሮቹ እንደ ውብ ምንጭ ውሃ እየፈሰሱ በሚወጡ ቃላት ሲናገር፣ ፓሻው ዐይኖቹን በከፊል ጨፈን በማድረግ ትረካውን በመስማቱ መደሰቱን የሚያመላክት ምልክት አሣየ። ደስታውን ይበልጥ ለማጣፈጥ ስለፈለገ ጥሩ መዓዛ ያለው ተክል ሻይና ኬክ እንዲቀርብ አዘዘ።

ጆን ባፕቲስት በትረካው ውስጥ ንጉሡ አንድም የውጭ አገር ቄስ እንደማይፈልግ፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም በቋሚነት ከግብፅ ፖትርያርኪን እንድታገኝ ፓሻው መብት መስጠታቸውንና እንደሚያከብሯቸው ዘረዘረለት።

«ቡተራሮቻቸው ላይ በሰላም መኖር ይፈልጋሉ» በማለት ፖንሴ አጠቃለለ።

«በእሳህ፣ ትክክል ነው? ላስበው ምክንያታዊነታቸው ዝቅ ያለ ይመስለኝ ነበር። አሁን አንተ የምትነግረኝ በጣም ጥሩ ቤና ነው። ነገር ግን፣ ይህ ሁሉ፣ አንተ አሁን ለምን መደበቅ እንዳለብህ የሚያስረዳ አይደለም።» ሲል መሣመት ቢይ ገለፀ።

«ወደዚሁ እያመራሁ ነው ጌታዬ። ከዚያ በኋላ ደግሞ ወደ ቬርሣይለስ ተጓዝኩ . . . »

ጆን ባፕቲስት ከዚህ በኋላ ቬርሣይለስ ስላሉት ሰለፀሐዩ ንጉስ ቤተመንግስት ረዥም ገለፃውን ቀጠለ። ፓሻውም በደስታ ያዳምጠው ጀመር። ፓሻው፣ አውሮፖ ውስጥ በውትድርና ላይ በነበረበት ዘመን ወደ አንዱ የአውሮፖ ዋና ከተማ የመግባት ተስፋ ብዙ ጊዜ ነበረው። የሚያሣዝነው ግን ብዙውን ጊዜውን በሚዳ መካከል በሚከተም ቦታ ላይ ነበር ያሣለፈው። በሌላ በኩል አንድ ከተማን የመያዝ ዕድል የነበረው ጊዜም ቢሆን ከተማውን የሚያገኘው ከወደመ በኋላ ነበር። ጆን ባፕቲስት፣ ቬርሣይለስ ስለሚገኙ ሴቶች፣ ስለፀጉር አሠራር ዘይቤአቸው፣ ስለሽቷቸው በሰጠው ገለፃ ላይ ሆን ብሎ በተንኮል ቀስ እያለ ተናገረ። ምስኪኑ ሽማግሌ ወታደር በደስታ አቅሉን ሣተ።

ከዚህ በኋላ ጆን ባፕቲስት ከንጉሱ ዘንድ ያጋጠመውን የሽንገላ ግንኙነት ገለፀ። በዚህ ትረካው ውስጥ አጣርቶ የሚያዳምጥ ጆሮ እንደሌለ፣ የፈረንሣዩ ንጉሥ ደስ ብሏቸው የሚቀበሉት በምስራቅ ሜድቴራኒያን ስላለው ጉዳይ ብቻ ነው ሲል አስረዳ።

በመጨረሻም የፈረንሣዩ ንጉስ፣ ታላቅ ንጉሥ መሆናቸውን ተስማሙ። ይሁን እንጂ፣ ሉዊስ፣ ሙስሊም ባለመሆናቸው መሣመት ቢይ አዘነ። ሆኖም ካለው የጋለ ስሜት በመነሣት፣ ንጉሡ ቢሰልሙ ጥሩ ሙስሊም ሊሆኑ እንደሚችሉ ተናገረ።

«ይህ ሁሉ ነገርህ፣ለምን መደበቅ እንዳለብህ የሚነግረኝ ነገር የለም» ሲል ፓሻው ጐተጐተው።

ምሽቱ እየተገፋደደ ነው። አሽከሮች ሁለት ጊዜ በምድጃው ላይ አዳዲስ ጊንዲላ ጨምረዋል። ፓሻው፣ የውሃ ፒፖው እንዲቀጣጠልለትና ከጆን ባፕቲስት ጋር እንዲጋራው ትዕዛዝ ሰጥቷል። በዚህ ሞቅ ባለ ጭውውታቸው በመሃከላቸው ያለውን የደረጃ ልዩነትም አላገናዘቡትም።

«ወይኔ» አለ ጆን ባፕቲስት «ታላቁ ንጉሣችን፣ ያው ንጉሥ ናቸው። ከእግዚአብሔር ጋር ሲነፃፀሩ በጣም ደካማ ንጉሥ ናቸው። በሰማይ ያለው ጌታችን ግን ሁሉንም ነገር ያያል . . »

ባልተቋረጠ የጣአት እምነት ቁጥጥር ስር የኖረው ቱርካዊ በተሸናፊነት ወደ ሰማይ አንጋጥጦ ተመለከተ።

«አንድም ጣአት ብሎ ነገር የለም። ያለው ፈጣሪ እግዚአብሔር ብቻ ነው» ሲል በመግሪያ እንደተፈጠረ የሙዚቃ ድምፅ ተናገረ።

«. . . ምድራዊ ገዥዎች በሚያውቁት ነገር ውስን ናቸው»

«ይህ እውነት ነው»

«አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በዙሪያቸው ምን እየተከናወነ እንደሆነ አይጠነቀቁም»

ጨዋታው ከመቀጠሉ በፊት፣ ፓሻው ያቀበለውን የእንጨት ፒፖ ተቀብሎ ሁለት ጊዜ ሳብ ሳብ አደረገ።

«እኔ በቤተመንግስታቸው ውስጥ ሊካሄድ የደረስኩበትን ሴራ፣ እርግጠኛ ነኝ፣ ንጉስ ሉዊስ 14ኛ አይፈቅዱም ነበር»

«ሴራ!» ሲል ጊዜው በጣም ቢመሽም ፓሻው በደከተሩ ታሪክ ይዘልኖ እየተመሰጠ መጣ።

«ሊገልፀው የሚችለው ቁቸኛው ቃል ይኸው ነው። ለምን እንደምደበቅ ለማወቅ ይፈልጋሉ አይደለ? አዩ፣ ምክንያቱ እኔ ራሴን ለነዚህ ሴረኞች አቅድ ተባባሪ ማድረግ ስላልፈለግሁ ነው»

«ይህ ሁሉ ስለምን ጉዳይ ነበር?» ሲል ፓሻው በመቁነጥነጥ ጠየቀው።

«ስለርስዎ ነበር ጌታዬ»

«ስለኔ!»

«አዎን፣ ስለርስዎ፣ ስለግብፅና ስለአቢሲኒያ። ይህ ሁሉ የሚጠነሰሰውና የሚፈለፈለው እርስዎ እዚህ በመልካም ሁኔታ ተቀብለዎቸው የዲፕሎማሲ ከለላ በሚሰጧቸው ሰዎች ነው»

«የነብዩ ያለህ፣ እስቲ ንገረኝ በሞቱ!» ሲል ፓሻው ብድግ ብሎ ቆመ። ለማወቅ ያለው ጉጉትም የሥጋት ስሜት አሣደረበት።

«ረጋ ይበሉ ጌታዬ። እያንዳንዱን ዝርዝር ጉዳይ አነግርዎታለሁ። ነገር ግን ምንም ዓይነት መጥፎ ምኞት እንደሌለኝ እንዲገነዘቡልኝ አወድዳለሁ። እኔን በተመለከተ ግን የዚህ ሴራ ሰለባ ሆኜ ቀይቻለሁ»

«በል፣ በል»

«እንግዲያው እሺ። ይዝውልዎ፣ የእኔ ወደ አቢሲኒያ ተልዕኮ፣ ለንጉሡ የሕክምና ዕርዳታ ከመስጠት ሌላ ምንም ዓይነት ተጨማሪ ወይም የተለየ አላማ አልነበረውም። ከዚያም፣ ቢያንስ የምስጋና ውለታ አለብኝ ብለው ያሰቡት ንጉሥ፣ ምስጋናቸውን ለፈረንሣዩ ንጉስ እንዳቀርብላቸው ላኩኝ»

«ይህንን ታሪክ አስቀድመህም ነግረኸኛል»

«አምን አውቃለሁ። እናም ፈረንሣይ ውስጥ፣ አቢሲኒያውያን ለፈረንሣይ ንጉሥ ያቀረቡት አክብሮት በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ የተለየ ሞገስ አሣደረ»

«እነማን ናቸው?»

«የንጉሡ ነገስቱ አጃቢዎች ልንላቸው እንችላለን»

«ቀሣውስቱ ናቸው?»

«በርግጥ እነርሱ ናቸው። ይህ ደግሞ የሚደንቅ አይደለም። ምክንያቱም ወደ አቢሲኒያ ዘልቀው ለመግባት የመፈለጋቸውን ተስፋ ፈፅሞ አልተዉትም። በዚህ ጉዳይ ላይ ይበልጥ የሚጠቀሱትና ሙሉ በሙሉ የሚመለከታቸውም እነርሱ ብቻ አይደሉም»

«ከነርሱ ሰዎች፣ የባሰ መጥፎ ነገር መኖሩን ለማሰብ አልችልምና ክፉኛ እያሳሰበኸኝ ነው

«ጌታዬ፣ እርስዎ ነገሮችን ሁሉ በቀናነት ስለሚመለከቱ ነው። ሌሎች ግን አዕምሯቸውን ሁሉ ለክፋትና ለተንኮል ዕቅድ ሲያዘጋጁ የሚኖሩ መሆናቸውን ይመኑኝ። ከዚህ ከቱርካውያን መደሰቻ ጥቂት ሳብ ሳብ በማድረግ እራሴን አንድጋብዝ ይፈቅዱልኛል ጌታዬ»

«የቱርካውያኑን መደሰቻ ለጊዜው ርሣውና የምትነግረኝን ቀጥልልኝ»

«ሃሣባቸው እንዲህ ነው። አቢሲኒያ ሃብታም ነች። ወርቅ፣ አልማዝና እንደልብ የሚገኙ የእንጨት ዓይነቶች ሞልተውባታል። ምንም እንኳ አቢሲኒያ የክርስቲያን አገር ብትሆንም፣ በአንዳንድ የሃይማኖቱ ሕግጋት ላይ የተለየ መስመር አላት። በዚህም የተነሣ ስርጣ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን አክብሮቷን አትገልፅም። እንደዚሁም ደግሞ አቢሲኒያ፣ ከቱርኮች አልፋ ማለትም ከርስቃም አልፋ በሩቅ ቦታ ላይ ነው የምትገኘው»

«እና?»

«እናማ ስለዚህ በቀጥጥር ስር መደረግ ይኖርበታል»

«ይኸው ብቻ ነው»

«ይበቃል ካሉ ይኸው ነው። ይህ ደግሞ የተወሰነ ጉዳይ ነው። ነገር ግን እንዴት ዕቅዱ ይሣካል? አቢሲኒያን እምነቷን በማስለወጥ ነው? ይህ ደግሞ ብቻውን በቂ አይደለም። ምናልባትም የተገላቢጦሽ ቢፈፀም የተሻለ ይሆናል። ይኸውም አስቀድሞ በሃይል ማሸነፍና መቆጣጠር። ከዚያ በኋላ ሃይማኖቷን ማስለወጥ። የተመረጠው ዕቅድ ይኸው ነበር»

«ፈረንሣውያን አቢሲኒያን ለመግዛት ይፈልጋሉ ብለህ ነው ሣጣብህን የምትነግረኝ?»

«ሣጣቤን አይደለም የምነግርም ጌታዬ፣ እውነቱን ነው የምገልፅልም። እኔ በየዋህነት አስቤው ስለኢትዮጵያ ሰላማዊ ንጉሥ የሰጠሁትን ገለፃ፣ ሌረኞቹ በሚገባ የታጠቀ፣ ወርቅና የገፀ በረከት ዕቃዎች ይዞ የተንቀሣቀሰ ሠራዊት፣ ይህችን ኋላ ቀር የሆነች ሀገር ለመቆጣጠርና ለመያዝ በቂ ነው የሚል ሃሣብና እቅድ እንዲያሪምዱ ነው የመራቸው። ከአንድ ምዕተ አመት በፊት፣ ጀስዊቶች፣ ንጉሡን ብቻ ለመለወጥ በመቻላቸው፣ አገሪቱን በሞላ ለመቆጣጠር ምንም አልቀራቸውም ነበር። ይሁንና እነርሱ ድላቸውን በጦርነት ለማረጋገጥ መሣሪያ አልነበራቸውም። አሁን ግን አስቀድሞ መሣሪያው ይለሰፋል።»

በመደገፊያው ዙሪያ ባሉ ትራሶች ተከበቦ የተቀመጠው ፓሻ፣ ጆን ባፕቲስትን በጭንቀት ተመለከተው።

«አሁን የምትነግረኝ፣ ይኸ አሁን በመጓዝ ላይ ያለው ኤምባሲ . . . »

«. . . የተወሰኑ ሰዎች አቢሲኒያን እንቆጣጠራለን ብለው ተስፋ ያደረጉበት መገልገያቸው ነው»

«እነዚህ እኮ ሃያ እንኳ አይሞሉም! ይህ ሊሆን የማይችል ቀልድ ነው!»

«ጌታዬ፣ እኔ ወደዚያች አገር ተጉዣለሁ። አገሪቱ፣ በተቀናቃኝ ሃይሎች ፍላጐት የተዳከመች ነች። ገንዘብና ጠመንጃ ያላቸው ሃያ ሰዎች ሠራዊት ሊመሰርቱ ይችላሉ። አለመረጋጋት ሊፈጥሩ ይችላሉ። በዙፋኑም ላይ አሻንጉሊት ንጉሰ ሊያነግሰብት ይችላሉ። ወይም ልክ ስፖኒያውያን፣ አሜሪካ ውስጥ ባሉ ኢንካዎች ላይ ባለፈው ክፍለ ዘመን እንዳደረጉት ከራሳቸውም ሰዎች አንዱን ሊያነግሱት ይችላሉ።

«እህህህ!» አለ ፓሻው የመሞላቀቅ ፈገግታ ፈገግ እያለ «ይህ ነዋ ሲከበር የነበረው ሴራችሁ?»

«እኔን ራሴን ፍርሃትና ስጋት ውስጥ የከተተኝም ይኸው ነበር። ምክንያቱም እኔ የዚህ ሴራ ተካፋይ ለመሆን አሻፈረኝ ብያቸዋለሁ። ፈረንሣይንም ለመልቀቅ ተገደድሁ። በዚሁ ሳቢያ በተመሣሣይ ምክንያት ስለፈራሁ እዚህ መኖሬን ሸሸኔ አገኛለሁ»

«ወዳጄ ሆይ፣ እውነቱን ልንገርህና አላምንህም። ይህን ሁሉ ያልከኝ እዚያ በነበርክበት ጊዜ ምናልባት አሳሳቢና አስቸጋሪ አለመግባባቶች ኢጋጥሞህ ይሆናል። ከዚህም ሌላ፣ አንተ በነበርክበት ቦታ ላይ፣ አንዱ ይህን የማይጨበጥ ዕቅድ አንተ አየሰማኸው ተንፍሶ ይሆናል። ይህ ማለት ታዲያ፣ እኔ ራሴው ሰላማዊ የይለፍ የሰጠሁት ቅፍለት፣ መሪውን የአቢሲኒያ ንጉሠ ነገስት ለማድረግ ያቀደ ነው ማለትህ ከእውነታው ፍፁም የተለየና የማይታመን ነው»

«ጌታዬ፣ የአርስቃ ማህተም ለዚህ ሰዎች ፍፁም አስፈላጊያቸው ነበር። የእንቅስቃሴያቸውን መልክ በሚያሣምንና ግልፅ በሆነ መንገድ ካላረጋገጡ እንዴት ሊያገኙ ይችላሉ። እቅዳቸውንም በአንድ ጊዜ ይፋ ማውጣት ጅልነት ነው የሚሆንባቸው። ለምሣሌ የሚያንስ ሰዎችን ብቻ ያቀፈ ጓድ ስለሚባሰውስ ምንም ነገር አልሰሙም?»

«አዎን ሰምቻለሁ እንጂ። የምሁራን ስብስብ የሆነ አንድ ቡድን ወደ ስዊዝ በማቅናት ከዚያ ወደ አረቢያ ይሄዳል የሚባል ሰምቻለሁ።»

«እና ከዚያም ወደ አቢሲኒያ ይሄዳል። ያጀባቸው ሰው የአቢሲኒያው ንጉሠ ነገስት እንደወኪላቸው አድርገው ከኔ ጋር የላኩጥ ሰው ነው»

«ያ ውሻ ኩርዳዊ»

«አርመናዊ ነው»

«ያው፣ ያው ነው» አለ ፓሻው። «አርሱ አብሯቸው ሄደ? ይህ አልተነገረኝም ነበር»

«ያልተነገረም ሆን ተብሎ ነው። እንግዲህ አሁን ይታይም ከሆነ፣ ሰዎቹ ሃያ ያህል ሳይሆኑ ወደ ሠላሳው የሚጠጉ ናቸው። ከነርሱ መካከል ጥቂቶቹ ወርቅና መሣሪያ የያዙ ናቸው። ሌሎቹ የንጉሡን መልዕክተኛና የተከማቸውን የምዕራባውያን ዕውቀት ይዘው ይገባሉ»

ፓሻው፣ ሃሣቡን ሊቆርጥ ያልቻለበትና ግራ የተጋባበት ሁኔታ ላይ ስለሆነ በጣም ተጨነቀ። ጀን ባፕቲስት፣ ርህራሄ ተሰምቶት ሊረዳውና ክውሣኔ ላይ እንዲደርስ ለማድረግ አንድ የመጨረሻ መረጃ ሊሰጠው ወሰነ።

«ሌላም አለ»

«ተጨማሪ?»

ጀን ባፕቲስት ፓሻውን በቀጥታ አይኖቹ ውስጥ አየው።

«አምን ጌታዬ፣ ከዚህ ቅፍለት በፊት አንድ የካፑቺኖች ቡድን ለምን ቀደም ብሎ እንደሄደ ራስዎን ጠይቀው ያውቃሉ? ይህ የተደረገው ሲናር ውስጥ ሊጠብቋቸው አቅደው ነው። በዚህም ላይ በኮፕቲኩ ፖትርያርክ የተሰጣቸውን የቅብዓ ሜሮን ዕዋ ለምን ይዘው ሄዱ?»

«ቅብዓ ሜሮን፣ ቅብዓ ሜሮን ደግሞ ምንድ ነው?» አለ ፓሻው በሃይለ ቃል።

«በኮፕቲክ ሃይማኖት፣ ሥልጣንና ሃይል ከአንዱ ንጉሥ ወደ ሚቀጥለው ንጉሠ ነገስት እንዲተላለፍ የሚያደርግ ቅዱስ ዘይት ነው»

«ይህን ያደረጉት ፖትርያርኩ ናቸው?»

«አሁን እተየነጋገርን ባለንበት ጊዜ ካፑቺኖች በጉዞ ላይ ናቸው»

«ለኔ ሣይነግሩኝ? በአሊ ጐራዴ!»

ከፖንሴ ጋር ስሊቱን ለረዥም ሰዓታት ስላወሩ፣ ፓሻው ደክመው። ይሁንና ከንጋት በፊት ይህን ሳይታሰብ የተነገረውን ታሪክ አምኖ ተቀበለ። ከመከዳው ተነስቶ በክፍሉ ውስጥ ወዲያና ወዲህ ተራመደ። የዕለቱ የመጀመሪያዎቹ የፀሐይ ብርሃን ጨረሮች በሰማያዊው የመስኮት መስተዋት አልፈው በግድግዳው የግርጌ ጠርዝ ላይ የወለሉን ምንጣፍ በሰማያዊ ብርሃናቸው ሞሉት። ድንገት በጀን ባፕቲስት ፊት እንደመፍዘዝ ብሎ ቆመና አመሰገነው። ቀጥሎም፣ በሚቀጥለው ዕለት ማታ መድሃኒቱን ይዞ እንደሚመጣ ቃል ካስገባው በኋላ የሚያብረቀርቅ ንፁህ ውሃ ወዳለው ገንዳ ሄደ ። ሃኪሙ፣ በጀርባው የስርቆሽ በር እንደወጣ፣ መሃመት ቤይ ዘበኛውን ጠርቶ የኮፕቲክ ፖትርያርኩን ከመኝታቸው ላይ ቀሰቅሰ፣ በዚያውም ኢማሞችንም ጭምር ከየቤታቸው ጠርቶ እንዲያመጣቸው አዘዘው።

8

በሚቀጥለው ቀን ማታ ጀን ባፕቲስት ተመልሶ በተለመደው የስርቆሽ በር ገባ። አንዲት አነስተኛ ቦርሣ ይዟል። ፓሻው፣ ባለፈው ጊዜ በነበረበት ክፍል ውስጥ ሆኖ ሲቀበለው፣ መድሃኒቱን ስላመጣለት ወዲያውኑ አቅፍ አደረገው። ጀን ባፕቲስት ብዙ ብልቃጦችን አወጣ። ዱቄት የተሞሉ የሱሪት ብልቃጦችና የደረቁ ሥራስሮችን የያዘ ክሪጢት ነበሩበት። ፓሻው ሁሉንም መድሃኒቶች በአንድ ጊዜ እንዳይጠቀማቸው መከላከል፣ የጀን ባፕቲስት ግዴታው ነበር። ቱርኮች መድሃኒት ይዳፈራሉ ብሎ፣ ሜትር ዠረሚ የነገረው ቢሆንም እንዲህ ይስገበገባሉ ብሎ አልገመተም።

«መድሃኒቶችን የሚያዘጋጅልም የተለየ አሽከር እንዳለዎት አምናለሁ። እርሱ ቢጠራና እነዚህን መድሃኒቶች እንዴት እንደሚያዘጋጃቸው በቀጥታ ከኔ ሰምቶ ሃላፊነቱን ቢወሰድ የተሻለ ይሆናል» አለ ጀን ባፕቲስት

ፓሻው አጨብጭቦ፣ አንድ የሆነ ስም ጮሆ ተጣራ። የቤት ውስጥ ተላላኪው ወዲያውኑ ደረሰ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሸምገል ያሉ አሽከር ገባና ለሁለቱ ሰዎች በአክብሮት ጐንበስ አሉ። አዛውንቱ፣ አጭርና ቀጭን ሲሆን ባለቤቶቹ ያባረሩት፣ ረዣዥም ቅልጥሞች ኖረውት ለመሮጥ ፈጣን የሆነ፣ ዓይናቸ ማተኮር የሚችሉና የአዳኝ ውሻ የመሠሉ ሾጠጥ ያሉ ፊት ያለው ነው።

«አብዱል መጅድ። አዳዲሶቹ መድሃኒቶች እኒሁና። እንዴት መጠቀም እንዳለብህ በሚገባ በጥንቃቄ አጽምጥ» አለው ፓሻው።

ጀን ባፕቲስት ሁሉንም ነገር በስፋት ተንትኖ ከነገረው በኋላ፣ ቦርሣውን ሳያስረክበው በፊት የተነገረውን በሚገባ መረዳቱን ለማረጋገጥ፣ አሽከሩ ሁሉንም ነገር መልሶ እንዲደግምለት አደረገው። ፓሻውም የመጀመሪያውን መጠን አዚያው በዚያ ሰዓት ለመውሰድ የሙጢኝ አሉ።

«እስክ ብዙ ሣምንቶች እፎይታ አገኛለሁ ብለው አያስቡ» አለ ጀን ባፕቲስት

ይሁን እንጂ፣ ፈሣሽ መድሃኒት የመውሰዱ ጉዳይ በፓሻው ላይ አንዳች ሃይል ማሣደሩ አልቀረም። ኪኒን ከሚሠራበት የሲንቾና ዛፍ ቅርፊት የተዘጋጀለትን መድሃኒት ሲወሰደው፣ ፊቱን እንደማጨማደድ አድርጐ ዕርካታ ካገኘ በኋላ፣ ባገኘው ነገር ሙሉ ደስታን እንዳገኘ

ሙሽራ ባል፣ በመከዳው ላይ ዝርግትግት አለ። ይሁን እንጂ አዕምሮው ሰላም ሲያገኝለትና የዕለቱን ሁኔታዎች ሲያስታውሳቸው ግንባሩን ቋጠረና ፊታ ሲያደርግ ፈር ማሣየት ጀመረ።

«ያን ውሻ ፓትርያርክ አስጠራሁት» ሲል ጀመረ «ስሰዘይቱ አንተ ትክክል ነበርክ። ሰውዬውም ተናዘዘልኝ። ዘይቱን ምን ማለት እንደሆነ ልነግረው ግድ ነበረ። ጅሉ፣ ከከፈሉት ወርቅ ባሻገር ማየት አልቻለም። እንዲያውም ከነገሠ አስራ አምስት ዓመት የሆነውን ንጉሠ ነገስት፣ ዘውድ ለማስጫን፣ ካቦቺኖች ይህን ያህል የሚያገባቸው ምን እንደሆነ ዝርሞት ነበር። የዚህን ጉዳይ ሥረ-ነገር ፊፅሞ አላየውም። በኔው ጠያቂነት ዘበኞቹ በካልቾ እየመታው አዋርዶ ባያባርረው ኖሮ እስካሁን ሲያወሩ እንሰማቸው ነበር»

ፓሻው የሚያስተጋባ ግሳት ሲያጋላ ይህን ያደረገለትን እግዚአብሔር አመሰገነና ቀጠለ።

«እንዲሁም ደግሞ የፊንሣዩን ቆንሲልም አየኋቸው። አምባሣደሩን መጥራት አላስፈለገኝም። ምክንያቱም ከሁለት ቀናት በፊት ወደ አሌክሣንደሪያ በሚወስደው ጉዳና ላይ ሴት ልጃቸው ስለተጠለፈች ለዚህ ሲሉ አቤት ለማለት መምጣታቸው አይቀርም»

ጆን ባፕቲስት የደነገጠ መሆኑን ለማሣየት ሞከረ።

«ታውቃት ነበር?» ሲል ፓሻው ጠየቀው።

«በዓይን ብቻ ነው። ለዚያውም ቆንስላው ግቢ ውስጥ ነው። በጣም ውብ ልጃገረድ ነበረች።»

«እንዲህ ሆነ ብለው ነገሩኝ። ለአምባሣደሩ ልነግራቸው የምችለው እጅግ አሳፋሪ ነገር እንደገጠመኝ ብቻ ነው። ምናልባትም ጠላፊዎቹ ዘራፊዎች ሊሆኑ ይችላሉ። መንገዱን የሞሉት እነርሱ ናቸው። ጠላፊዎች ያልወሰዷት፣ግን በሰረገላው ውስጥ የነበረች ሌላ ሴት በኋላ ላይ ስለድንገተኛ አደጋ አድራሽቹ ገለፃ ሰጥታለች። ሴትዮዋን ያልወሰዷት ልጅነት ስለሌላት ይሆናል። በሴትዮዋ አገላለፅ ሰዎቹ ማንንም ሊመስሉ የሚችሉ ናቸው። ሁለት ግዙፍ ወንዶች ናቸው። ሁለቱም ጥምጣም አስረዋል። ሪዛቸው ጥቁር ነው። የሚምሉት በአላህ ነበር። ልጅገረዲቱን፣ አንደኛው በፈረሱ ላይ አፈናጥጧት፣ በስሜን ምዕራብ አቅጣጫ ሄዱ፣ ስትል አስረድታለች። ምናልባት በድብቅ በጀልባ ወደ ቆጵሮስ ሊያሻግሯትና ከዚያም በባልካን አገሮች ወይም ሌላ ቦታ በሴትኛ አዳሪነት ሕይወቷን ትቀጥላለች» አለ ፓሻው

«ምስኪን ልጅ» አለ ጆን ባፕቲስት ፈጠን ብሎ።

«አዎን፣ ግን ምንም ባያጋጥማትም ኖሮ በቀሪው ዘመኗ የደስታ ሕይወት አይኖራትም ነበር»

«ለምን ቢባል?»

«ወደ ሴቶች ገጸም እንደምትገባ አባቷ ነግረውኛል። ዶክተር፣ ላንተ በሁሉም ረገድ አክብሮት አለኝ። ነገር ግን ክርስቲያን ስለሆንክ በናንተ እምነት በኩል ሊገቡኝ የማይችሉ ነገሮች አሉ። ይህን ሁሉ ሴት፣ ለአግዚአብሔር አገልጋይ ይሁን በማለት ብቻ ለምን ዘግታችሁ ታኖሩታላችሁ። በርግጥ እግዚአብሔር ይፈልጋቸዋል ብላችሁ በእውነት ታምናላችሁ? ሁለቱን ፆታዎች ሲፈጥራቸው እንዲዋሃዱ አይደለም? ስለሁኔታው ቆንሲሉ ሲገልፁልኝ በማዝናናውም መልክ ተዘግቶባት የምትቀረው ይህች ልጅ በዙሪያዋ አሁን ላሉት የሰው ልጆች እንዳች መልካም ነገር ልታደርግላቸው ትችል ነበር ብዬ ልነግራቸው ዳድቶኝ ነበር፣ እና፣ተወው ይልቅስ ጨዋታችንን እንቀጥል። የዚህ ሁሉ ፍጥጫው ታዲያ፣ ሙሴ ዴ ማይሴ በክፍተኛ የመንፈስ መረበሽ ውስጥ መውደቃቸው ነው። እንዲያውም ኢምባሲያቸውንም ፈፅሞ የረሱት ይመስላል። ይመስላል ያልኩበት ምክንያት፣ እኔ ስለጉዳዩ አንዳች ነገር እንዲነግሩኝ ስጠይቃቸው፣ እርሳቸው ጉዳዩን ሙጭሙጭ ይሉብታል። አንተ ሁሉንም ነገር ግልጥልጥ አድርገህ ካማኸኝ ወዲህ፣ ሰውዬው ለዚህ ስራ ያሳቸውን ጠንካራ ፍላጐት በተሻለ መረዳት ችያለሁ»

ጆን ባፕቲስት የተረጋጋ ስሜት ይዞ ቆየ። የቤት ውስጥ ተሳላኪው፣የሚበላ ኬክና ሻይ ይዞ ከተፍ አለ።

«ቀትር ላይ ጋደም በማለት ለመተኛት ብሞክርም አምቢ አለኝ። ይህን አታምንም ይሆናል።» ሲል ፓሻው ቀጠለ። «አየተካሄደ ያለው ነገር ሁሉ በአዕምሮዬ ውስጥ እየተሽከረከረ ነው። ዶክተር? አንድ ነገር ልናዘዘልህ። ከዚያ በኋላ የራሴንም ማንነት በሚገባ አሳውቃለሁ። ጠላቴን ማየት ስለቻልክ አንተን አመሰግንሃለሁ። ይህ ደግሞ በራሱ ታላቅ ነገር ነው። ይሁንና ጠላቴን እንዴት አድርጌ ነው መምታት ያለብኝ? በአሁኑ ጊዜ በጦርነት ሜዳ ውስጥ አይደለንም። ታዲያ ምን ላደርግ እችላለሁ? የአገራችን ከፍተኛው የአመራር አካል፣ ከፈረንሣዮች ጋር እንዴት እንደሚሠራ ታውቃለህ። ሁልጊዜም ድርድር ነው የሚያደርገው። የነመደ ጉተታ አይነት፣ አንዱ ሌላውን በመቃረን ብቻ፣ ውጤት አልባ ነው። ታዲያ ይህ ሁሉ ወዴት እያመራ እንደሆነ አሁን እያየን ነው።»

ሲናር ወደ ጆን ባፕቲስት እየተመለከተ አልነበረም። ጆን ባፕቲስትም መናገር የሚገባው ጊዜ እስኪደርስ በትዕግስት ጠበቀ።

«ለታላቁ መሪያችን ሁኔታውን ሪፖርት ባደርግ ምን ሊሆን እንደሚችል አውቃለሁ። ማረጋገጫ ማስረጃ ይጠይቁኛል። እኔ ላቀርብ የምችለው ማንኛውም ማስረጃ በቂ አይደለም ተብሎ ይፈረጃል። ስለዚህ ተጨማሪ ይጠይቁኛል። በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ ቀኑ ቀንን እየወለደ ጊዜው ይገፋና እነርሱም ያንን የተረገመ ዘይት በዱ ሮውሌ ግንባር ላይ በማፍሰስ ንጉሠ ነገስት ብለው ዘውድ ይጭኑለት ይሆናል»

ጆን ባፕቲስት ባይፈልግም ራሱን በመነትነት ተስማማ

«በሌላ በኩል በራሴ ውሳኔ በፈረንሣውያኑ ላይ እርምጃ ብወስድ፣ ቆንሲሉ አስፈሪ ምሬት ሊያሰሙ ይችላሉ። ቁስጥንጢንያ ደግሞ እኔን መርዳቷን መናገር አይቻልም። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ለረዥም ጊዜያት አጥብቄ አስቤበት ነበር። የበቀል ጥቃትን ሳልፈራ፣ልይዛቸው የምችላቸው፣ ካፑቺኖች ብቻ ናቸው። በዚህ ውሳኔዬ ረክቼ ቀጣዩን ስሊት በሰላም ለማደር ወታደሮቼን ወደ ሲናር እልካለሁ። ከዚያም በማስቴ ወታደሮች አስረው እንዲያመጧቸው በዚያውም ቅብዓ ሜርኑንና የፖትርያርኩን የምስክር ወረቀተ መልሰው ያመጣሉ። ለመባረር በሚገባ የተመቻቹ ስለሆነ፣ ማንም ጠንካራ ተቃውሞ የሚያነሣ የለም። ግን የፈረንሣዮችን ቅናሰት ምን ላደርገው ነው? ዶክተር፣ አንተ የታላቅ ጥበብና ብልሀት ባለቤት ነህ፣ እንዲያው ስለዚህ ጉዳይ ምን ትሰኛለህ?»

ጆን ባፕቲስት ይጠብቀው የነበረው ሰዐት ይህን ነበር። ሁለት ጊዜ ከሻዩ በዛ አድርጎ ከተኮነጨ በኋላ መልሱን ለማቀናበር ወይም የሚያቀናብር ለመምሰል ጊዜ ወሰደ። እንደ እውነቱ ከሆነ መልሱን ቀደም ሲል አዘጋጅቶ ነበር። እናም ጥያቄ አስመስሎ በጥንቃቄ ጣል አደረገ።

«ምናልባት የሲናር ንጉስ እንደ ዓይነት ርምጃ ይወስዱ ይሆናል?»

«የለም፣ አፊሴላዊ የሆነን የፈረንሣይ ኤምባሲ በማጥቃት አደጋ እንዲጥሞው ፈፅሞ አይፈልግም።»

«ሕዝባቸው በራሱ ፈቃድ ካላደረገው በስተቀር . . . »

«ምን ማለትህ ነው?»

«እኔ ሲናር በነበርኩበት ጊዜ፣ ካፑቺኖች ህዝቡን በኔ ላይ ለማነሣሣት ማስፈራራት አስበው ነበር። ማድረግ የነበረባቸው፣ እኔን አስማተኛ ነው የሚል ጥላሸት መቀባት ብቻ ነበር። የሲናር ሰዎች አስማተኞን በጣም ስለሚፈሩ፣ ሊያምኑ ምንም አልቀራቸውም ነበር። በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ስጋት ያደረበት ሕዝብ፣ በራሱ ተነሣሽነት በማያውቀው የተጓዥ ቡድን ላይ ቁጣ ሊቀሰቅስና ማንም ሰው፣ ሌላው ቀርቶ ንጉሡ እንኳ ቢሆኑ ሊቆጣጠሩት የማይችሉት ረብሻ ሊያነሳ ይችል ነበር»

በፈረሰኛ ወራጅ ወንዝ ውስጥ ሆኖ፣ነፍሱን ለማዳን ሲል ያገኘውን ሀረግ ሁሉ ለመያዝና ወደዳር ለመውጣት እጀቹን እያወናጨፈ እንደሚጥር ሰው፣ ፓሻው ይህን የሃሣብ ሰንሰለት ተከተለው። ሣህቡን ሰብሰብ አድርጎ አዕምሮን ከገዛ በኋላ፣ እንዲህ ያለ ግልፅ ፈረንሣዊ በማግኘቱ ራሱን በራሱ የምስራች አለው።

ከዚህ በኋላ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ተከታታይ ጥያቄዎችን ጠየቀው። ጆን ባፕቲስትም በቀላሉና ግልፅ በሆነ መልክ መለሰለት።

«ልክ አስቀድመህ መልሱን ያዘጋጀኸው ነው የሚመስለው» ሲል ፓሻው በጥርጣሬ ሳይሆን በታላቅ የአድናቆት ስሜት ተናገረ

የሚያጨሰው ፒፖ እንዲመጣለት በማዘዝ፣ ያንን እየማገ በደስታ ተነፈሰ። ጆን ባፕቲስት፣ ቀጥሎ የሚሆነውን ጠበቀ። ፓሻው ሊናገር ሲል፣ የፒፖው ጭስ በተሣሣተ መተንፈሻ አካሉ በማለፉ በድንገተኛ መረበሽ ሳሉ ተቀሰቀሰበት።

«ከዚያ ኩርድ ጋር በመንገዝ ላይ ስላሉት ምሁራንስ ምን ትላለህ?»

«አነርሱን ለኔ ይተዋቸው ጌታዬ፣ እኔ እከታተላቸዋለሁ።» አለ ጆን ባፕቲስት

ፓሻው በስግራሞት ተንቀሣቀሰ

«እስክ ጂዳ ድረስ የሚያጅቡኝን ሰዎች፣ግብፅ ውስጥ እስካለሁ ድረስ ምናልባት ለቆንሲሉ ስሜን የሚያሳጣብኝ እንዳይኖር መከላከያ ይሆነኝ ዘንድ የርስዎን ከለላ ይስጡኝ። በአሁኑ ጊዜ በይፋ እኔ ፊረሰኛው ዱ ቫውዴ ሶርኔስ ነኝ። እርስዎ፣አፊሴላዊ ዋሴ ቢሆኑኝ፣ ያለ አንዳች ፍርሃት የትም መሄድ እችላለሁ። ስድስቱንም ሰዎች ፍፁም ኢትዮጵያ ማይደርሱ በፊት እንደማገኛቸው ይመኑኝ»

ከረዥም የማቅማማት ጊዜ በኋላ ቱርካዊው ተናገረ

«ይህ ከጥያቄ ውጪ ነው»

ጆን ባፕቲስት ዓይናቸን በሽማግሌው ጦረኛ ላይ ተክሎ ተንቀሳቀሰ

«አየሀ፣ እኔ ያለነዚም መቆየት አልችልም» አለ ፓሻው።

ግንዲላው ቀስ እያለ በመንጣጣት እየነደደ ምድጃውን በአመድ ዱቄት እየሞላው ነው።

«ጌታዬ፣ እጅግ ቢበዛ አራት ሣምንታት ቢወስድ ነው። ስርስም የሚሆን ቢያንስ ለሦስት ወራት ሊያገለግልም የሚችል መድሃኒት አዘጋጅቼ አኑራልዎታለሁ። ምንም እንኳ አሁን የታመመ ቢሆንም፣ አስፈላጊ ከሆነ ሜትር ዝረሚ ይከታተልዎታል»

«በምስራቅ በኩል ወረርሽኝ የመነሣቱ ነገር ይወራል። የኢስማኢሊያ ከተማ ተገልላ እንድትቆይ ተደርጋ ነበር። አንተም ብትሆን ታመህ ልትተኛ ትችላለህ»

«ይህ አዚህም ሊደርስ ይችላል። ሁላችንም ብንሆን በአግዚአብሔር እጅ ውስጥ ነን» አለ ጆን ባፕቲስት ካንጀቱ ሳይሆን ካንገቱ

«እውነቱ ይህ ነው።» ብሎ ፓሻው በረዥሙ ተነፈሰ። ከዚህ በኋላ ፖንሰ ያቀረበውን ሣጣብ በአማራጭ ካሉት ሣጣቦች ጋር ካመዛዘነ በኋላ የትኛውም ባያስጨንቀውም ተስማማ።

አሁን ሁሉም ነገር መፍትሄ አግኝቷል፣ወይም በቅርቡ ውሣኔ ያገኛል። ትምባሆው ከሰጠው የርካታ ስሜት፣ የመክዳው ልስላሴና ምናልባትም ደግሞ ከመድሃኒቱ የተነሣ የሸማግሌውን ቱርካዊ ሰውነት ባለፉት ሁለት ቀናት ከነበረው የከረረ ሁኔታ ጋር ሆኖ የድካም ማዕበል መታው።

ጆን ባፕቲስት ቀደም ብሎ ተሰናበተ። ፓሻው ወደ አልጋው ከመሄዱ አስቀድሞ ሲናርን በተመለከተና ዶክተሩን እስከ ጧዳ ድረስ አጅቦ ስለሚሄደው ሠራዊት ትዕዛዝ ሰጠ።

ፉ

ፈረሰኛው ዴ ቫውዴ ሶርንስ በሸክላው የአረብ ፈረሱ ላይ ተሽሞንሙኖ ተቀምጦ፣ በካይሮ ክተማ ውስጥ አለፈ። በየፎቅ ቤቶቻቸው መስኮቶች ላይ ሆነው እርሱንና የክብር አጃቢዎቹ የሆኑትን የጠመጠሙና ጉራዴዎቻቸውን የታጠቁ ወታደሮቹን በአድናቆት ቁልቁል የሚመለከቱትን የቤት እመቤቶች፣ ፊቱን ወደነርሱ ቀና በማድረግ ባርኔጣውን ያነሣላቸዋል። ዕለቱ ሞቃት ሲሆን፣ አዕዋፍት በብዛት በሰማዩ ውስጥ ይበርራሉ። በተለያዩ የሲጋጃ ምንጣፎች፣ የመዳብ ቁሣቁሶችና የስፌት ዕቃዎች ቀለማት በሚያብረቀርቁበት የንግድ ሱቆች

መሃል ሠራዊቱ አለፈ። እነዚህን ከየመደብሩ ወጥተው በጉዳናው ዳር የተደረደሩ ቁሳቁሶችን፣ ረዣዥም ሰማያዊ ጥቁር ካባ ለብሰው፣ ጠርዙሽና አይነርግብ ያደረጉ አላፊ አግዳሚዎች በእጆቻቸው ይነካኳቸዋል።

እነዚህ ተንገቦች እስከ ስዊስ ሲሄዱ አንዳችም ቃል ሳይተነፋፈሱ ነበር። ሌላው ቀርቶ፣ ከፍተኛዎቹ አጃቢ ወታደሮች፣ ይህን እጅግ የተከበረ በማለት የተከተሉትን ሰው በመፍራት፣ ፀጥታውን ሊሰብሩት አልደፈሩም። ጆን ባፕቲስት ወደፊት የሚጠብቀውን ስራ በአዕምሮው እያውጠነጠነ ሊያናግራቸው አልቻለም። አዕምሮው ዕረፍት እንዳገኘ ግን አሊሰንና በዚያ ምድረበዳ ውስጥ የምታደርገውን ሽሽት አሰበ። ጆን ባፕቲስት፣ በርስዋ፣ በዝረሚና በፍራንቸይዝ ላይ መተማመን ነበረው። ከሁሉም በላይ ግን በራሱ እጣ ፈንታ ላይ ከፍተኛ መተማመን ነበረው።

በመጨረሻም መራራውን ሐይቅ አልፈው፣ ሴራፒየምን ከርቀት ተመለከቱ። ሁለተኛውን የጉዞ ዕለት ሊያጠናቅቁ ጥቂት ሲቀራቸው፣ ትንሿን የስዊዝ የወደብ ከተማ ከባሩ ጠርዝ ላይ ተመለከቱ። በዚህ አካባቢ ያለው የስዊዝ ወደብ፣ የኢጣሊያ ሐይቆችን ያህል ጥብብ ያለ ነው። ወደቡ፣ ነጫጭና ግራጫ መልክ ባላቸው ጀልባዎች የተሞላ ሲሆን ከሰሜን ምስራቅ በኩል ለስላሣ ነፋስ ይነፍሳል።

በአጃቢ ወታደሮቹ ጥያቄ መሠረት፣ የወደቡ አዣዥ የሆነው ጢማሙ፣ ፍልቅልቅ ሊባኖሳዊ፣ ሊጠቀመባቸው የሚችሏቸው ባለሁለት ሸራ ጀልባዎችን ሰጣቸው። ቀድሞ የንግድ መርከብ የነበረችው ይህችው ጀልባ፣ ሁለት መድፎች ተጨምረውላት ወታደራዊ አገልግሎት እንድትሰጥ ተደርጋለች። የዚህችው መርከብ ሠራተኞች ቱርካውያን ወታደሮች ሲሆኑ፣ በአፈታሪክ እንደሚነገሩት የባህር ላይ ባለችሎታ ሰዎች፣ የተዋጣላቸው ናቸው። የኢጋጣሚ ሆኖ ሰወታደሮቹ አስፈላጊውን ስንቅና ትጥቅ የሚያቀርበው ክፍል አዛዥና ብዙዎቹ ሰዎች በቀን አምስት ጊዜ እየፀለዩ ፣በመሃመድ አምላክ የሚያምኑ ቢሆኑም እስከ አሁን ድረስ የአሪስቶፈነስን ቋንቋ የሚናገሩ ናቸው።

መርከቧ፣ በባህረሰላጤው ዳር ምንም አይነት ድንገተኛ ነፋስ ወይም ፍፁም ፀጥ ያለም ነፋስ ሳይገጥማት በሰላም ተጉዛ የሲናን ተራራ አለፈች። በአካባ ባህረ ሰላጤ ዳር ሆኖ አካሏ በሞጋማ ውስጥ ተሰይቶ ይታወቃል።

በአካባ ባህረ ሰላጤ ጠርዝ ላይ፣ የባህሩ ውሃ እንቅስቃሴ የሞገደ ሰውጥ ይታይበታል። ቀን ላይ ርጥቡ የጀልባዋ ክፈፍና ጠርዝ፣ የመርከበኞቹ ፊትም በፀሐይዋ ብርሃን ውስጥ ያብረቀርቃሉ። ምሽቱ አሁንም ቀዝቃዛና ሃይለኛ የነፋስ ማዕበል አለው። መንገደኞቹ፣ በጉዟቸው ላይ አንድ ጊዜ ብቻ በወደብ ዳር ከማረፋቸው በስተቀር በአምስተኛው ቀናቸው ንጋት ላይ ጂዳ ደረሱ።

የካይሮው ፓሻ፣ አድራሻው ለመካው ሸሪፍ የሆነ የይለፍ ወረቀት ሰጥቶት ስለነበረ፣ ፈረሰኛው የአክብሮት አቀባበል አገኘ። ከዚያም ማርቆስ በሚባል ሶሪያዊ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ንብረት በሆነ ትንሽ ሆቴል ውስጥ እንዲያርፍ ተደረገ። ቦታው ከቀሪው የከተማው አካል ትንሽ ራቅ ብሎ ከአሸዋው መሬት ጠርዝ ላይ በሚገኙ ጥቂት የዘንባባ ዛፎች አጠገብ የተመሠረተ ነው። ይህ ቦታ ክርስቲያኖች እንዲሰነብቱበት የሚፈቀድ አካባቢ ነው።

የዚህ ትንሽ ሆቴል ጓሮ፣ በአጥር ወደ ተከበበ የአትክልት ቦታ መግቢያ አለው። ወደ አትክልቱ የሚወስደው መንገድ በጡብ የተሠራ ሲሆን፣የብርቱካንና የሮዝ አበባ ተክል ያላቸው አፅዋት በሚያምር መስመር ተተክለውበታል። በዚህ ቦታ ላይ፣ ጆን ባፕቲስት፣ ይሆን ይሆናል ብሎ የጥርጣሬ ስሜት ይዞ ነበርና ይህ ሃሳቡ ስህተት አልነበረም። ወደ አትክልት ሥፍራው ውስጥ ብዙም ሳይራመድ በፊት ሙራድ በአንድ መከዳ ላይ ተቀምጦ የውሃ ጋያውን ሲያጨስ ተመለከተው። ከርሱ ባሻገር ስድስቱ ምሁራን ፀጥ ብለው በክብ ቅርፅ ተቀምጠዋል። እያንዳንዳቸውም መፅሃፍ ይዘዋል

ጆን ባፕቲስት፣ በፈረሰኛው ዴ ቫውዴ ሶርገስ ሚና፣ ራሱን በኩራት ጉንበስ በማድረግ አሰተዋወቀና ጀርባውን ለሙራድ ሰጥቶ ተቀመጠ። ወዲያውም የሚጣፍጥ የቱርክ ቡና አዘዘ። በርሱ ጥያቄ መሠረት አጃቢ ወታደሮቹ የሉም። እርሱ ከሚፈልገው ቦታ በመድረሱ ሳቢያ ስለማይፈልጋቸው፣ ወታደሮቹ በከተማዋ ውስጥ የየራሣቸውን ክፍሎች ተከራይተዋል። ጂዳ፣ የቅዱሱን ቦታ ተሣላሚዎች መጓጓዣ መንገድ ላይ ስለሆነች እንቅስቃሴ የሞላባት፣ በጥብቅ ሥርዓት ውስጥ ሁሉንም ዓይነት ምቾት የያዘች ከተማ ነች። ጆን ባፕቲስት፣ ለአጃቢ ወታደሮቹ አሰቃ፣ ሁለት ሴኩይንስና ለሌሎቹ ደግሞ አንዳንድ ሰጣቸው። ይህ ገንዘብ ሁለት ክሩሳደስ ማለትም ሃምሣ ስድስት ሴሪፊንስ ይሆናል። ወይም በሌላ አገላለፅ አንድ መቶ አሥራ ሁለት ፖርዳይስ ወይም ሁለት ሺህ ሁለት መቶ አርባ ታንጋ ወይም ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ባሩክስ ይሆናል። ይህ በወቅቱ በቀይ ባህር ዙሪያ በማገልገል ላይ የነበረ ገንዘብ ከብረታ ብረት የተሠራ ሣይሆን፣ በቬኔስያ መስታወት ስብርባሪ የተሠራ ነበር። በእጭሩ፣ ጆን

ባፕቲስት እነዚህን ሰዎች በአንድ ጊዜ ባለፀጋ አድርጓቸዋል። ወደ ከተማውም በኩራትና በጥድፊያ አየተሣደኑ ወጡ። እግዚአብሔር በዚህ ገራገር ሰው ላይ አድሮ፣ ሕይወት የምትክፍላቸውን ውሰታ እንዲቀምሱት ፈቃዱ ሆኗል።

በዚያን ዕለት ምሽት፣በትንሿ ሆቴል ቤት ውስጥ የነበሩት እንግዶች በሙሉ ነጭ ቀለም በተቀባ በአንድ ትልቅ የምግብ አዳራሽ ውስጥ ራታቸውን በፀጥታ ተመገቡ። በዚህ አዳራሽ ውስጥ ይታይ የነበረው ብቸኛው ጌጥ፣ ዝገት የበላው የጥንት የፈረሰኛ ጉራዴ፣ በሁለት ሚስማሮች ላይ ተንጠልጥሎ ነው። ዕራት ተመጋቢዎቹ፣ ሻማዎቻቸውን ይዘው ወደየክፍላቸው ሲሄዱ፣ ከበላያቸው ያለው ወሰል ሲንሳጠጥ ድምፁ ይሰማል። ሙራድ፣ ሁልጊዜም እንደሚያደርገው ልማዱ፣ ሌሎች ተመጋቢዎች ያስተረፉትን ምግብ እስኪያፀዳ ድረስ ከገበታ ሳይነሳ ስለሚቆይ ብቻውን እስኪሆን ድረስ ጆን ባፕቲስት ጠበቀ። ወዲያውም ከአርመናዊው አንዣር ተቀመጠ።

«ጌታዬ!» አለ ጆን ባፕቲስት፣ በአረቢኛ

ሙራድ የትርቡን ብቻ እንደሚያይ ዓይኑን አንሸዋርሮ እንደመገንጥ አይነት ጉንበስ አለ።

«ባልሣሣት አምባሣደር ሙራድ ነዎት» አለ ጆን ባፕቲስት

«አህ!ይህን እንዴት ሊያውቁ ቻሉ?»

አርመናዊው ሻማውን አንስቶ ወደሚያዋራው ሰው ፊት ጠጋ አድርጐ ያዘው።

«እንዴ . . . ፍፁም አሰን ይመስላሉ . . . ለመሆኑ አንተ ጆን ባፕቲስት ነህ እንዴ?»

«አሸሽ! እኔ ፈረሰኛው ዴ ቫውዴ ሶርገስ ነኝ»

«አ! ይቅርታ» አለ ሙራድ ተስፋ ቆርጦ «ሳስብም»

«የሰም፣ አንተ ደደብ፣ እኔው ነኝ። ነገር ግን በዚህ ሁሉ ሰው ፊት እንደምታምባርቅ፣ በተለይም በአዲሶቹ ጓደኞችህ ፊት»

«ጓደኞቼ አይደሉም። ስላንተ ምንም ወሬ አጣሁ። እነርሱ ደግሞ ስለአቢሲኒያ ማወቅ ይፈልጋሉ . . . »

«ካይሮን ስቀህ በመውጣትህ ትክክል ነገር ሠርተሃል ሙራድ» አለው ጆን ባፕቲስት ፈገግ እያለ

አንዲት የተከደነች የመዳብ ኮዳ አውጥቶ ንፁህ ፈሳሽ በሙራድ ባዶ ስኒ ውስጥ ከጨመረ በኋላ ለራሱም ቀዳ።

«ብራንዲ ነው!» አለ አርመናዊው። «አረቢያ ውስጥ ያውም በነብዩ ምድር ላይ! አትፈራም እንዴ?»

ብርጭቆዎቻቸውን በዝግታ አጋጭተው ወደ ጣሪያው አፈሰሱ።

«አምን፣ አፈራለሁ፣ ስላንተ ስል አፈራለሁ» አለ ጆን ባፕቲስት

«ምን ማለትህ ነው?»

«ወደ ምዕዋ ልትሻገር ነው አይደል?»

«የሜካ ሸሪፍ የነዚህን ክቡራን ሰነዶች ማህተም እስኪመቱበት ድረስ ሁለት ሦስት ቀን ይፈጃል»

«ናኢቡን ካየሃቸው ረዥም ጊዜ ነው?»

«አምን፣ ድንቅ ሽማግሌ ናቸው»

«በእሁኑ ጊዜ እዚያ የሉም»

«እውነት ነው። መቼም ጨካኙ ሙሃመድ እንዳይሆን»

«የለም፣ ሙሃመድ ሞቷል። ከእንግዲህ ግኝትህ ከወንድሙ ልጅ ከሃሰን ጋር ነው። ሃሰን የባሰ ጨካኝ ሲሆን፣ ለፈረንሣውያን ካህናት ያለው ጥላቻ ወሰን የለውም»

«እና ይህ ታዲያ ለኛ ምናችንም አይደለም። ንጉሡ ራሣቸው፣ ፈቃደኛ ሆኖ የሚመጣ ከተገኘ ምሁር ይዤላቸው እንድመለስ ነግረውኛል»

«ምሁራን? ልክ ነው። ነገር ግን ጀስዊቶችስ?»

«ምን? ምን እያልክ ነው?» አለ ሙራድ

ጆን ባፕቲስት፣ የአርመናዊውን ኮሌታ ጨምድዶ ፊቱን ወደ ፊቱ አስጠጋ።

«የምልህማ፣ስድስት ንፁህ የጀስዊት ደም ያላቸውን ሰዎች ወደ ምዕዋ እየመራህ ነው። ይህን ለማስተዋል እንዳትችል አንተ ተንኮል የሌለብህ ሰው ነህ። በዚህ የተነሣ ናኢቡም

አይጠነክሩም። ንጉሡ ነገስቱም ቢሆኑ ስድስት ሰዎችን ይዘህላቸው ስትመለስ፣ ሃይማኖታቸውን እንዳያስለወጧቸው እንጂ ሌላ የሚጠረጥሩት ነገር አይኖራቸውም። ታስታውስ እንደሆነ አንድም ጀስዊት ወደ አገራቸው እንዳናመጣባቸው አስምለውን ነበር። አንተ ግን ግማሽ ደርዘን የሚሆኑትን በሻንጣህ ተሸክመህ እየተመለስክ ነው»

ሙራድን ሲለቅቀው የተመታና የደነዘዘ ያህል ተመልሶ ወንበሩ ላይ ወደቀ።

«እኔ ጠፋሁ» አለ አርመናዊው

እንደ ህፃን ልጅ በገመታ ማንባት ጀመረ።

«ቢቃህ» አለው ጆን ባፕቲስት፣ ብርጭቆ ሙሉ ሌላ ብራንዲ እየቀዳለት።

ሙራድ በአንድ ትንፋሽ ጨለጣትና ብርጭቆውን አስቀምጦ ከበፊቱም የባሰ ያዘነ መሰሰ።

«ወይኔ! ራሴን በራሴ መክሬው፣ ካይሮ ውስጥ የወጥ ቤት ሰራተኛነት ሥራ ብጀምር ይሻለኝ ነበር። የሚገባኝም ነገር ይኸው ነበር። ይህ የሃይማኖትና የፖለቲካ ነገራችሁ ግራ ያጋባኛል»

«ስማ ሙራድ። የምነግርህን ከፊፀምክ የምትፈራው አንዳችም ነገር የለም። ንጉሡ ነገስቱም ባንተ ላይ ያላቸውን እምነት ስለሚያረጋግጡ ሌላው ቀርቶ ከፈለግህ አንተው ራስህ የወጥ ቤታቸው ልትሆን ትችላለህ»

ሙራድ፣ምንም ሣይናገር አየር ወደ ሣንባው ከሣበ በኋላ፣ ቀስ ብሎ ብርጭቆውን ጠረጴዛው ስር አስቀመጠው። ጆን ባፕቲስት ወደ ማዕድ ቤቱ ከተመለከተ በኋላ ሌላ ማደፋፈሪያ ቀዳለት።

«ነገ ጧት ከንጋት በፊት ወደ ወደቡ ውረድ።» አለው ሃኪሙ። «የምትፈልገውን አይነት ጀልባ ከነካፒቴኑና ከሠራተኞቹ ጋር ልትከራይ እንድትችል አንድ ወቄት ወርቅ አሰጥሃለሁ። ቀይ ባህርን አቋርጠህ ወደ ናኢቡ ሒድ። እዚያም ደርሰህ፣ ስድስት ጀስዊቶች ወደ አገራቸው ሊገቡ እንዳቀዱና አንተ ግን ዕድለኛ ሆነህ ልታመልጣቸው እንደቻልክ ንገራቸው። ከዚያም ወደ ጐንደር ተጓዝ። ለንጉሡ ነገስቱ ሰላምታዬን አድርስልኝ። የፈረንሣዮች ንጉስ፣ ኤምባሲያቸውን እንደተቀበሉና ምርቃታቸውን መሳካቸውንም ንገራቸው።

ያንተም ተልዕኮ እዚያ ላይ ያበቃል። ከዚያ በኋላ ወደ አጐትህና ወደ ወንድሞችህ ልጆች ዘንድ መሄድ ትችላለህ። በቀሪው ዘመንህም ደስተኛ ሆነህ እንደምትኖር ተስፋ አደርጋለሁ»

«ጀስዊቶችስ?» ሲል በሰማቸው ቃላትና በሶስቱ ብርጭቆ ብራንዲ የተደሰተው ሙራድ ጠየቀ።

«የነርሱን ሃላፊነት እኔ እወስደዋለሁ»

«እና . . . እንተስ?»

«እኔ ደስተኛ ሰው ነኝ፣ ወዳጀ። ከዚህም በኋላ እጅግ በጣም በቅርቡ ደስተኛ እንደምሆን ተስፋ አለኝ»

«እፈቅኛህስ?»

«አብራሌት ለመሆን እየተንቀሣቀስክ ነው። ማን ያውቃል? አንድ ቀን ጐንደር ውስጥ ታየን ይሆናል»

ለሁለተኛ ጊዜ መልካም ምኞታቸውን ተለዋወጡ። ጀን ባፕቲስት፣ ከአነስተኛዋ ነጥብ ጀምሮ ቀደም ሲል የነገረውን መመሪያ በዝርዝር ደገመለት። እኩለ ለሊት አካባቢ ሞቅ ባለ መተቃቀፍ ሰላምታቸውን ተለዋውጠው ተለያዩ።

9

በሚቀጥለው ቀን፣ ጀን ባፕቲስት፣ በትንሿ ሆቴል ውስጥ ባሉት በስድስቱ እንግዶች ላይ የቅርብ ክትትል ሊያደርግ ዋለ። ሙራድ ከመኝታው ዘግይቶ የሚነሣ በመሆኑ፣ ሰዎቹ ይህንን ለምደዋልና ጨርሶ አለመኖሩን ያስታውሱት እኩለ ቀን አካባቢ ነው። ከመካከላቸው አንዱ የሙራድን ክፍል በር ለማንኳኳት ሄዶ፣ በክፍተኛ ጭንቀት በረዳውን እየወረደ ተመልሶ መጣ። ባለፈው ምሽት በጀን ባፕቲስት የተሰጠውን መመሪያ በመከተል ሙራድ የቃል ማስታወሻ ለባለሆቴሉ ነግሮታል። በዚህ ማስታወሻውም ከተማ ውስጥ ሥራ እንዳለው፣ ማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ የተለየ መብት ካልተሰጠው በስተቀር ወደ ከተማ መግባት እንደማይፈቀድለት በመግለፁ፣ ስድስቱ ጀስዊቶች በትዕግስት በመጠበቅ ተጉላሉ። በአትክልቱ ስፍራ ውስጥና ወደ ወደቡ በሚወስደው አቧራማ መንገድ በተፈቀደላቸው አምስት መቶ ያርድ ርቀት ውስጥ ሲናፈሱ ዋሉ።

ቀኑ መሸ። ጀስዊቶቹ እንደገና ተመካክሩና አራታቸውን በፀጥታ ተመገቡ። የዚያን ዕለት ምሽት ከፖንሴ በስተቀር ሌሎች ደንበኞች በሆቴሉ ውስጥ አልነበሩም። ምግቡን በተቻለ መጠን በፀጥታ ከተመገበ በኋላ፣ ሊጨርስ ሲል፣ ጀን ባፕቲስት ወንዘሩን ጐትቶ ወደ ምሁራኑ ጠረጴዛ በመሄድ የሚጉት ሻይና ኬክ ሊጋብዟቸው ይችል እንደሆነ ፈቃዳቸውን ጠየቀ። ከአነስተኛው ውይይታቸው የተረዳው የአገሩ ልጆች መሆናቸውን እንደሆነ ሳይደብቅ ነገራቸው።

«ትችላለህ» አለው፣ ከስድስቱ ጨፍጋጋዎች አንዱ

«እሺ እንግዲያው።» አለ ጀን ባፕቲስት፣ እንፋሎታማውን ብርጭቆውን ብድግ በማድረግ፣ «በዚህ አካባቢ ለጤናችን ብለን ጽዋችንን የምናነሳበት ሌላ ዘዴ ስለሌለ ሻዩን አነሳሳችኋለሁ። እንደምታዩት ቀለሙ በጣም ወደ ክኹነ የሚጠጋ ስለሆነ እንደ መጠጥ አስቡት። ለጤናችሁ፣ ክቡራን ጌቶች»

እነርሱም ብርጭቆቻቸውን አነሱ። ጀን ባፕቲስት ለሰባታቸውም ተገቢ የሆነውን ቢገልጸም ከነርሱ አንዱም ደስተኛ አልነበረም

«እባካችሁ ይቅርታ አድርጉልኝ ራሴን አላስተዋወቅኋችሁም፣ ፈረሰኛው ሁሳስ ዴ ቫውዴ ሶርገስ እባላለሁ። ላገለግላችሁም ዝግጁ ነኝ»

ይህን ካለ በኋላ፣ አስመሣዩ ፈረስኛ ከወንበሩ ላይ ጥቂት ኢንቾች ብድግ በማለት በተለይ ተለይቶ ባልተገለፀ መልክ በመጠኑ ጮንበስ አለ።

«እኛ ምሁራን ስንሆን፣ ለስፖኒሽ የሮያል አካዳሚ እና ሣይንስ መረጃዎችን ለመስብሰብ የተላክን ነን» ሲል ከእንግዶቹ ሽምገል የሚለው ጨፍጋጋ ተናገረ።

«እና ጉዟችሁ ወደየት የሚወስዳችሁ ነው?» ሲል ጆን ባፕቲስት በየዋህነት ጠየቀ።

ስድስቱ ሰዎች እርስ በርሳቸው በጭንቀት ተያዩ

«ወደ አቢሲኒያ» ሲል ቃል አቀባያቸው በመጨረሻም ተናገረ።

ፈረሰኛው የአድናቆት ፖንት አሰማ።

«የማይታወቅ አገር ነው፣ ክቡራን፣ ለድፍረታችሁን እጅ እነሳለሁ።»

ለፍላፊው፣ የማይታመነውን አነጋጋሪያቸውንና መንገድ መሪያቸውን ያጡ ስለሆኑ በዚያች ቅጽበት ከስድስት የተከፉ መንገደኞች ያነሰ ጀግንነት የሚታይበት አልነበረም።

«ምስጢር ካልሆነ አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፣ ጌቶቼ?» ሲል ጆን ባፕቲስት ዝቅ ባለ ድምፅ ጠየቀ።

«መጠየቅ ካለብህ»

«አሺ እንግዲያው፣ ግን ጥያቄዬን ላለመመለስ ከፈለጋችሁ አትገደዱምና ልትተዉ ትችላላችሁ። ለመሆኑ አግብታችኋል?»

የስድስቱንም እንግዶች ስሜት ምቾት የሚነሳ ድንጋጤ ወረረው። ለአፍታ ያህል ፀጥ ካሉ በኋላ ያው ሰው በመጨረሻ ላይ ተናገረ።

«የለም፣ አላገባንም፣ ባልደራስ»

«ይህ ድንቅ ነገር ነው። በጣም ድንቅ ነው» አለ ጆን ባፕቲስት

«ለምን ቢሉ ብሎ ቢጠየቅስ?» ሲል ከተንገቦቹ አንዱ ቆጣ ብሎ ጠየቀ። ከጠረጴዛው በስተግራ በኩል የተቀመጠው ይህ ሰው ጣልቃ ገቡን ሰው ከሌሎች ይልቅ በርጋታ ይመረምረው ነበር።

«ምክንያቱም፣ ወደዚያ የምትሄዱት የአገሪቱን ሃይማኖት ለማስለወጥ እንደማይሆን ትንጣት ታህል ጥርጣሬ በአዕምሮዬ አይኖርም»

ስድስቱም በአንድ ጊዜ የመደነቅ ቃል ተናግረው ሲያበቁ፣ በጭንቀት ወደ ማዕድ ቤቱ በር ተመለከቱ። እንደ ዕድል ሆኖ የጆን ባፕቲስትን የድፍረት ንግግር ያዳመጠ አንድም ሰው አልነበረም።

ከተንገቦቹ መካከል ይበልጥ ለፍላፊ የሆነው ሰው «ማንነትህን ግለፅልን» ሲል ዝቅ ባለ ድምፅ ጠየቀው

«አንዳችም ቀላል የሚሆን ነገር የለም። አንዲት ትንሽ ታሪክ እነግራችኋለሁ። ያን ጊዜ ይገባችኋል። ታሪኩን የለማሁት በሰናር ኗሪ የነበረና በጥቂት ራት ብሎ ወደ ኋላ ካለችው ወደ አቢሲኒያ አቅጣጫ ተጉዞ ከነበረ የካፑቺን ሚሲዮናዊ ነው። ነገር ግን ከሁሉ በፊት፣ ማነህ የኔ፣ አስተናጋጅ! ሻማዎች አምጣልን። ደግሞም አትሰስት፣ የምንከፍልህ ለዚሁ ሁሉ በቂ ነው»

ማርቆስ እያነከሰ ደረሰ። እንግዶቹ ጥያቄአቸውን ግልፅ አስካደረጉና ጮክ ብለው አስከተናገሩ ድረስ ለማስተናገዱ ሙሉ በሙሉ ዝግጁ ነው። ምክንያቱም ጀሮው እያስቸገረው ነው። ሶስት አዳዲስ ሻማዎችን እስኪያቀርብላቸው ጠበቁትና ተመልሶ ሲሄድ ፈረሰኛው ታሪኩን ቀጠሉ።

«ታሪኩን ልቀጥልላችሁና፣ ይህ ሚሲዮናዊ ከዕለታት አንድ ቀን ጥቂት ጐጀዎች ያሉበትና ዙሪያውን በረጣኸም ግሮች በተከበበ አንድ የግር ምድር መንደር ደረሰ። እዚያም የመንደሩ ሽበቶ ጉምቱዎች በድንክ በርፖማዎቻቸው ላይ በአንድ ትልቅ የዋርካ ዛፍ ሥር ተቀምጠው ያገኛቸዋል። ራሱንም በአረቢኛ ቋንቋ ያስተዋውቃል። የአገሬው ሰዎች በመጠኑ ቋንቋው ይገባቸዋል። የመንደሩ ሹም አንግዳውን ወደደው። የመንደሩም ሕዝብ ተቀበለው። ሁለት ቀናት ያህል ከቆየ በኋላ ስለራሱ ሃይማኖት መናገር ይጀምራል። ይህም ስገምተው ስለኛ ሃይማኖት ይመስለኛል»

ተንገቦቹ በታሪኩ በመስማማት ላይሆን ጭንቅላታቸውን አነቃነቁ

«ሹመ፣ ብዙ ተአምራቶችን በሠራው በኢየሱስ ታሪክ ክፍተኛ ስሜት አደረበት። የካፑቺኖችን ወዳጅነት እንደተደሰተበትና ስለሃይማኖቱም የበለጠ ለመማር እንደሚፈልግ ይነግረዋል። በዚህ መልክ ሁሉም ነገር በሰላም የሚዘልቅ መሰለ። ከዚያም ምሽት ሆነ። ምስኪኑ መነኩሴም ሊተኛ ሲዘጋጅ፣ የሹመ ሴት ልጅ፣ በማደሪያ ጐጆው ውስጥ ሆና ስትጠብቀው አገኛት። ምንም ሳይናገርና ሳይነካት በአልጋው ግርጌ ሄዶ ተኛ። በማግስቱ በሌሊቱ ሁኔታ ያልተደሰተችው ልጃገረድ ለአባቷ ትነግረዋለች። «ምን?» ይላል ሹመ።

«ልጅን ሳለመቀበል ምን አይነት ሃሞት ቢኖርህ ነው ሳትቀበላት የቀረኸው? ካህኑ እፍረት እየተሰማው ሃይማኖቱ ሁሉንም ዓይነት ዝሙት እንደሚከለክል ለማስረዳት ይሞክራል።»

ስድስቱ ጀስዊቶች ጭንቀታቸው እየጨመረ አዳመጡ። ጆን ባፕቲስት፣ ጊዜ ወስዶ ትረካውን ከመቀጠሉ በፊት ተጨማሪ ሻይ አዘዘ።

«ሹሙ ክፋኛ ተቆጣ! አስፈራውን ንዴቱንም በጉብኙው ላይ ተወጣበት። «ይህን ዓይነት ትዕዛዝ የሚሰጥ አምላክ ምን አይነት አምላክ ነው? የሰዎች ደስታና ምኞት በልቡ ቢኖር ኖሮ፣ እርሱን እጅግ አድርገው እንደሚወድዱት የሚገልፁትን ሰዎች፣ በሕይወታቸው ውስጥ በፍፁም ሌት እንዳይኑ እንዴት ያስገድዳቸዋል? በአጭሩ ያንተ አምላክ ወንጀለኛ ነው። ተፈጥሮን እንዲህ የሚሰድብ ከሆነ፣ ሊፈጥረውም ባልተገባ ነበር። የዚያን ዕለት ምሽት፣ ሹሙ፣ ሴት ልጁን ከካፑቺኑ ጋር እንደገና እንድታድር በሩን ዘጋባቸው። በዚህ ጊዜ የመንደሩ ሰዎች በሙሉ በጉጀው ዙሪያ ተሰለሰሉ። መነኩሴውም ከዚያች ውብ ድንግል ልጃገረድ ጋር መርፈና ክር ሆኖ ሕጋዊ ጋብቻ መፈፀሙ ካልተረጋገጠ በስተቀር በሕይወት እንደማይወጣ አስጠነቀቁት»

«ይህ እጅግ ዘግናኝ ታሪክ ነው ባልደራስ፣ እባክህ ይብቃህ፣ አትንገረኝ» አለው የተጓጉቹ መሪ ስሜት ባጣ ሁኔታ።

ይሁንና ጀስዊቱ ተቃውሞውን አጠንክሮ አልገፋበትም። እንደ እውነቱ ከሆነ ሁሉም ቢሆኑ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ለማወቅ የነደደ ጉጉት ነበራቸው።

«ታሪኩን ከሞላ ጐደል ጨርሻለሁ።» አለ ጆን ባፕቲስት። «ወዳጄ ቅዱስ አይደለም ወይም ደግሞ በተግባሩም ቅዱስ ሊሆን የሚችል አልነበረም። ታዲያ በማንኛውም መመዘኛ መሥራት የነበረበትን ሠራ። ሹሙ፣ አንዳችም ሃፍረት ሳይሰማው ማረጋገጫውን ለማወቅ በሚቀጥለው ማሰዳ ሊመረምር፣ ወዳጅ! ዛሬ ኮራሁብህ። አሁን ስላንተው እየሱስ ለመሰማት ዝግጁ ነኝ። ከዚህ በኋላ መላውን አገር ሃይማኖቱን ማስለወጥ ትችላለህ። በዚህም አቅምህ አስቀፈቀደልህ ድረስ ብዙ ትንንሽ ሕፃናትን የሚያስገኘልህ ዘር ልትዘራ ትችላለህ። ማንም ቢሆን ሃይማኖቱን ለማስፋፋት ጥሩው ዘዴ ይሸው ነው' ሲል ሹሙ ንግግሩን ቋጨ። በአጭሩ ብዙ ሕፃናትን ማፍራት እንጂ የሌሎችን መስረቅ አይደለም፣ መስረቁ ጥሩ አይደለም»

ጆን ባፕቲስት ታሪኩን ሲጨርስ፣ ዝምታው ውስጥ ከባድ ፀጥታ ሰፈነ። ደንታ ቢስ በመሆን ሻዩን እፍ ብሎ ሃይለኛ ድምፅ አስኪያሰማ ድረስ ሳበው።

ከሁሉም ደፋሩና ነገሩን በአትኩረት ሲከታተል የነበረው ጀስዊት በመጨረሻ ላይ፣ «የምትነግረን እኛ ስድስታችን አቢሲኒያውያንን በሙሉ ማስረገዝ ያለብን መሆኑን ነው?»

ይህን ከተናገረ በኋላ በጊዜ ርዝመት የደበዘዘውን ትውስታውን ለማጥራትና ሃሳቡንም ለማቅለል ፈረሰኛውን አተኩሮ ተመለከተው። የዚህ ሰውዬ ፊት ለጆን ባፕቲስትም ቢሆን ፍፁም የማይታወቅ አይደለም። የሰውዬውን ጥያቄ በሚመልስበት ጊዜ፣ ፖንሴ የማጃጃል አቀራረቡን ፍፁም በመለወጡ፣ አድማጮቹን ይበልጥ ፍርሃት ያርዳቸው ጀመር።

«አቢሲኒያ፣ የሲናር ገጠር አይደለችም። አቢሲኒያ ኩሩ ጥንታዊ የክርስቲያን አገር ነች። እኛ ግን ይህንን ጥንታዊነት፣ እንጭጭና ብስለት የሌለው ነው በሚል በመገመት በዚህ የምትተዳደር አድርገን እንሰድባታለን»

ዙሪያውን የተቀመጡትን ሰዎች በጥንቃቄ ተመለከታቸው።

«አባቶቼ፣ እኔ የምሰጣችሁ ምንም ነገር የለም። በፍፁም አስፈላጊም አይደለም። በአጭሩ ግን እናንተ ማን እንደሆናችሁና ምን ልታደርጉ እንደሆነ ከአውነተኛ ምንጭ ተረድቻለሁ»

የእነጋገሩ ቅላፄ የርግጠኛነት ድምፀት ስላለበት ማስተባበል የሚቻልበት አይመስልም ነበር። ከመጀመሪያው ድንጋጤአቸው በኋላ በሌላ አቅጣጫ ተፋለሙት።

«አሺ እንግዲህ እኛ ማን መሆናችንን አወቅህ?» ሲል የመጀመሪያው ቃል አቀባይ ቀጠለ። «እንግዲያው በኛ ዕቅድ ላይ ሲናርህ የሚችለውና ልንቀበለው የምንችለው ተቃውሞ ሊኖርህ ከቻለ ንገረን። ለመሆኑ የወንጌልን መስፋፋት ትቃወማለህ?»

ሙራድ፣ ስለጉዞው ድጋፍ አድራጊዎች ከሰጠው መግለጫ በመነሣት፣ የራሱን ግንዛቤ ወስዶ በደረሰበት ውሳኔ መሠረት «እርስዎ መቼም አባ ዴ ሞኔሃውት መሆን አለብዎት?» አለ ጆን ባፕቲስት

«ልክ ነህ»

«አሺ እንግዲያው፣ አባቴ፣ ተቃውሞ ከሆነ በጣም ብዙ ተቃውሞ አለኝ። ያቺ አገር ወንጌልን፣ እኛ ያወቅነውን ያህል ዘመን ስለምታውቅ፣ አሁን ወንጌል አያስፈልጋትም። እኔ እስከማውቀው ድረስ እነርሱ የሚከተሉት የሃይማኖት ህግ ከካቶሊክ ቀኖና ጋር ልዩነት አለው። እውነቱን ለመናገር የጉዳዩ ሥር መሠረት ያለው ሌላ ቦታ ነው»

«የት ነው ያለው?» ሲሉ አባ ዴ ሞኔሃውት ለስለስ ብሎው ጠየቁት።

ጀን ባፕቲስት ለአፍታ ያህል ካመነታ በኋላ ቀጠለ።

«ጊዜው ረዥም ነው። እኔም ብዙ ተለውጫለሁ። አምና በዚህ ጊዜ ቢሆን ኖሮ፣ ባለኝ ታሪካዊ መረጃ፣ ሰብዓዊና ሃይማኖታዊ የመከራከሪያ ነጥቦች ይዤ በዚህች አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንዳትገቡ በማቀርባቸው የመከራከሪያ ነጥቦች ላሳምናችሁ እችል ነበር። በዚህ ዓላማ መሠረት ጉዳዩን ለማስረዳት ወደ ቬርሣይለስ ድረስ ተጉዤ ነበር። »

«ፖንሴ» አሉት ማንኑቱን በጣም ሲመረምሩት የነበሩት ጄስዊት

እኒህ ካህን፣ ጀን ባፕቲስት ከአባ ኘላንቱይን ጋር ሆኖ ማርሲይለስ ሲገባ፣ በጀስዊቶች መኖሪያ የነበሩት ቂስ እንደሆኑ አስታወሳቸው።

«አምን፣ አባቴ ባለፈው ዓመት ባዞኝ ጊዜ ሰዎች እንዲያዳምጡኝና እንዲረዱኝ በጣም እጣደፍ ነበር። አሁን ግን ሁሉንም ነገር የተረዳሁት እኔ ነኝ»

የሆነ ወፈፌ ሰውን የሚያረጋጉ ይመስል «አስቲ ምን እንደተረዳህ ትነሽ ንገረን» አሉት አባ ዴ ሞኔሃውት በተረጋጋ ስሜት።

«በጣም ቀላል በሆነ አገላለፅ፣ አናንተ ለአንድ አስገዳጅ ሃይል የተደራጃችሁ መሆናችሁን ነው» ክርስቶስን እንደ ባንዲራችሁ በመያዝ፣ ሌላውም ባንዲራ እንዲሁ እንደናንተ ተመሣሣዩን መሠረታዊ ጉዳይ ሸፋፍኖ ያቀርባል። መሠረታዊው ጉዳይ ሥልጣን ነው»

«አናስ?» አሉ፣ እኒያው ለትችት የተፈጠሩ የሚመስሉ ቂስ

«አናማ፣ የሚገታችሁ ሃይል ነው። በጣም ለረዥም ጊዜ፣ ከነገ ዛሬ ሁኔታውን ትረዱታላችሁ የሚል ገራገር እምነት ነበረኝ»

ለአፍታ ያህል ፀጥታ ሆነ። ይህ በሽማግሎች ብርሃን የደመቀው ክፍል በአረቢያን ባህረ-ሰላጤ አሸዋማ ምድር ጠርዝ ላይ ጠፍቶ የቀረ ነው ብሎ ለመዘንጋት ቀላል ነው። የት እንዳለ ጀን ባፕቲስት በድንገት ትዝ አለው። ይህ ቦታ እንዴት በቀላሉ ወህኒ ቤት ሊሆን እንደሚችልም ተገነዘበ።

«ሙራድን ለማግኘት አትብዝኑ። ሙራድ ሄዷል። እንዲያውም በዚህ ቅፅበት ከሚፈልግበት ቦታ ይደርሣል የሚል ተስፋ አለኝ። ስለናንተ አመጣጥ የምፅዋው ናኢብ ማስጠንቀቂያ ደርሷቸዋል። የኒህ ናኢብ ቅድመ አያት፣ የአገሪቱ በር በሚገባ መጠበቁን

ሰማረጋገጥ የናንተን ቀደምት መሳክሰት ጭንቅላቶች፣ ለንሡ ነስቱ ለክፉላቸው ነበር። እኒህ የልጅ ልጅ የሆኑት ናኢብም፣ የአያቶቻቸውን ባህርያት ሁሉ የወረሱ ናቸው። እኒህ ናኢብ ቱርካዊ አይደሉም። የቱርክን የበላይ መሪ የሚታዘዙት ክርቀት ነው። እኒህ ሰው ምንም አይነት የተንኮል ሴራ፣ ምንም ዓይነት ውሸትና ምንም ዓይነት አቤቱታና ተማፅኖ ከአላማቸው ንቅንቅ አያደርጋቸውም። ይህን ባህር ስታቋርጡ ሊገጥማችሁ የሚችለውን አደጋ እንቀበላለን እንኳ ብትሉ ወደ አቢሲኒያ ግን ለዘለዓለም አትደርሱም።»

ይህን ቀይ ፍም የመሰለ ሙሉ ልብስና የተስተካከለ የአንገት ፎጣ ሰብሰ፣ እጅግ ክብደ ምት ያሣረፈባቸውን ግርማ ሞገስ ያለውን ወጣት ሰው፣ በፍርሃት ተመለከቱት።

«ታዲያ ምን ማድረግ አለብን?» ሲሉ አባ ዴ ሞኔሃውት እያዘኑ ጠየቁ።

«በጣም ደካማ አቀባበል ሊያጋጥማችሁ ወደሚችለው ወደ ካይሮ አትሂዱ ወይም አቢሲኒያ ለመድረስ በየብስ ለመጓዝም አትሞክሩ። ምክንያቱም በየአቅጣጫው ሳሉ የአካባቢ ገዥዎች በናንተ ላይ እንዲነሱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል። በአሁኑ ጊዜ ነሣና ክፍት ሆኖ የምታገኙት መንገድ፣ በጀልባ ተሣፍራችሁ ወደ ስዊዝ የምትመለሱበት ብቻ ነው። ከዚያም ወደ ቅዱስ ምድራችሁ ወይም ወደ ፈረንሣይ ወይም በርግጥም ወደ ምትመርጡት ማንኛውም ቦታ መሄድ ነው። በብዙ ቦታዎች ራሣችሁን ቤተኛ ሰላደረጋችሁ ልትሄዱበት የምትችሉበት አገር እጥረት አይኖርባችሁም»

ጀን ባፕቲስት ብድግ ብሎ ከቆመ በኋላ በሚያስፈራ ሁኔታ በመራመድ ሁሉንም በይቅርታ ዓይነት አተያይ ተመለከታቸው።

«እመኑኝ፣ ለያንዳንዳችሁ አክብሮት አለኝ። አናንተን የሚጋለጥ ሣጣብ ቢኖረኝ ኖሮ፣ ጉዳዩን በተለየ መልክ እንቀሳቀስበት ነበር። ይልቁንስ እኔ በተቃራኒው ሕይወታችሁን እየታደግሁላችሁ ነው። ይህን የሚደርገው የእምነት ቃሌን ለስጠሁት ንጉስ ታማኝ ስለሆንኩ ነው»

ስድስቱ ጀስዊቶች ዕቅዳቸው መቀልበሱን በዝምታ አሰቡት። ፖንሴም ቢሆን፣ ከነርሱ የባሰ የተጨነቀ መሆኑ ተሰማው። ይህ ሁሉ የሚሆነው፣ እኔ፣ ነፃ ለውጥ አምጭ ስለሆንኩ፣ የምሠራውና የምንቀሣቀሰው በሙሉ ሃላፊነት ነው። እነርሱ ግን የራሳቸው ምኞትና ፍላጐት ጌቶች ሣይሆኑ፣ የሚባሉትን በአሽታ የሚቀበሉ ናቸው፣ ሲል አሰበ።

በትህትና ጮንበስ ብሎ ሰላምታ ከሰጣቸው በኋላ፣ በሩን ከመድረሱ በፊት መለስ አለና ወጥቶ ሄደ።

«በርግጥ የመካውን ሽሪፍ የምናስጠነቅቅበት ምንም ሰበብ የለም። እስካሁን ስለ እውነተኛ ው ማንነታችሁ የሚያውቁት ምንም ነገር የለም። ይሁን እንጂ በአጠቃላይ እውነተኛው ማንነታችሁ መጋለጥ የሚገባው ሁኔታ ከተፈጠረ እጅግ የከፋ ሁኔታ ይሆንባችኋል። እንግዲህ በጣም ስለመሸ ጥቂት ዕረፍት አድርጉ። ደህና እደሩ። አባቶች»

ወደ ፎቁ ወጥቶ የራሱን ክፍል በር ዘጋ

ከንጋቱ አሥራ አንድ ሰዓት ላይ፣ መስተዋት የመሰለውን የባህር ውሃ የሚያወራጨው አንዳችም የነፋስ ሽውታ ሳይኖር፣ ጀን ባፕቲስት ከወደቡ በተከራያት አነስተኛ ጀልባ ሹልክ ብሎ ወጣ። ስምንት የጀልባ ቀዛፊዎች በተባበረ ሙሉ ሃይላቸው በሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ፣ ካሲዮፒያን ተከትለው መቅዘፍ ጀመሩ።

❦

በዚያው ሣምንት ውስጥ ፓሻው የላካቸው ቱርካውያን ፈረሰኞች በአባይ ወንዝ ሦስተኛ ው ፏፏቴ ላይ ሁለት ካፑቺኖችን አስሩ። ከታሣሪዎቹ አንደኛው በያዙት ከረጢት ውስጥ ለአቢሲኒያው አቡን የተሣፈ ሰነድና አንድ ብልቃጥ ዘይት ይገኛል። እነዚህ የተያዙ ዕቃዎች ወደ ካይሮ ተወስደው የኮፕቲኩ ፖትርያርክ እንዲያዩዋቸው ሲደረግ፣ ደብዳቤውን ሲያረጋግጡ ብልቃጡንም ሆነ ዘይቱን ከዚህ በፊት አይተው እንደማያውቁ በመሣላ ገለፁ። ወንድም ፖስኳል ግን በግትር አቋማቸው ሳቢያ፣ እውነተኛው ቅብዓ ሜሮን የት እንደተደበቀ ለመግለፅ አሻፈረኝ አሉ። ይህን በግልፅ የታየውን አስነዋሪ የአምነት ጉዳይ፣ ፓሻው ወደ ቁስጥንጢንያ በላከው ደብዳቤ ላይ ጠንከር ያለ አፅንኦት ሰጥቶ ስለገለፀ፣ ከማማሽ በላይ የሚሆኑት የካፑቺን ወንድማማቾች አባላት ከአገር እንዲወጡና ወደ ኢጣሊያ እንዲሄዱ ተደረገ። ወደ አቢሲኒያ የተንቀሳቀሰውም የዚህ የሃያማኖት ሥርዓት ሚሲዮናዊ ጓድም ከዚህ መስናከል አላመለጠም።

❦

የዱ ሮውሌ አንዱ ጭንቀት በተክታዮቹ መካከል ሥነ ስርዓትን የማስጠበቅ ጉዳይ ነበር። የሰበሰባቸው ጋጠ ወጦችና ምላሳም የሆኑ ክቡሌዎች፣ ሀብት ለማግኘትና ለወረራም በጣም

የሚጓጉ ስለነበሩ፣ ይህን ስሜታቸውን ለማርገብ ያልተቋረጠ ጥረት ማድረግ ነበረበት። እነዚህ ቁርጠኛ ጀግኖች የሆኑ ሰዎች ይህንን የሚይበረግ የጀግንነት ወኔአቸውን፣ አንዲት የዋህ ኮረዳ ብን ብላ ስትጠፋ ያሣዩትን ያህል ድፍረት ሌላ ጊዜ አሣይተው አያውቁም። ይሁን እንጂ በሙስሊም ግዛት ውስጥ እስካሉ ድረስ ይህ ባህርያቸው መገታት ነበረበት። አቢሲኒያ ውስጥ ግን ታሪክ ልዩ ይሆናል። ከዚህም በላይ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ከፍተኛ የወሲብ ፍላጐት ስላሳቸው የሚጠመዱት አነርሱ እንደሚሆኑ ስለተነገራቸው፣ ይህን ዘገባ እውነት ነው ብለው ሰማመን በቅተዋል።

በሚገባ ተደራጅቶ፣ በሚገባ ታጥቆ፣ በሚገባ ስንቱ ይዞ የሚጓዘው ይህ ቅፍለት አንዳችም አይነት ያልተጠበቀ መንተት ሳይገጥመው ደንቡሎ ደረሰ። የዚያች ከተማ መስፍንም በሚቸለው ሁሉ በመልካም መስተንግዶ ተቀበለው። ይህ መስፍን ለክበራቸው ሲል ባዘጋጀው ጉስቁሳና ደካማ የአራት ግብዣ ሁኔታ በመገረም ሣቃቸውን እንዳይለቅቁት ዱ ሮውሌና ሩሚላክ ራሳቸውን በጣም መቆጣጠር ነበረባቸው።

«ያልሰለጠነ ሰው መሆን ወይም ካልሰለጠነ ሰው ያልተሻለ መሆን እንዴት ድንቅ ነገር መሰለህ። እነዚህ ሰዎች የነፃነትንና ተፈጥሮአዊ የሆነውን የጭውውት ዕድል ሊደሰቱበት ይገባቸው ነበር። እነዚህ ሰዎች እንዲህ ያለውን ነገር አያደርጉም። በድሮ ዘመን በአገራችን ከነበሩት መሣፍንቶችና መኳንንቶች በባሰ መልክ፣ የህብረተሰብ ሕግ ትክክል ካልሆነ ብለው መጭጭ የሚሉ ናቸው» አለ ዱ ሮውሌ።

ዱ ሮውሌና ሩሚላክ፣ በዋናው አስተርጓሚያቸው በፍሬሴቲ ሁኔታ ላይ ቅሬታቸውን ይነጋገራሉ። ይህ አስተርጓሚ የአገሬው ተወላጆችን ድርጊትና ተግባሮች ተገቢ አድርጐ ሲቀበል፣ የነርሱን ባህርይ ግን እንደማይስማማበት የሚያሣይ ሥራ ያከናውናል። ይህ ደግሞ እንደ እውነቱ ከሆነ ከሚገባው በላይ ነው። ዘሩ ሊነገር ከማይችል የጥቁር ሕዝብ መሣል የተገኘ ካልሆነ በስተቀር፣ ከመሣፍንትና ከመኳንንት ዘር ለሚወለዱ ሰዎች ስለ ትክክለኛው ባህርይ ትምህርት ለመስጠት መዳፈር ያበዛል።

በዚህች ከተማ ውስጥ ሊከናወን የሚችል የንግድ ጉዳይ ስለሌለ፣ አንድ ቀን ብቻ አርፈው ወደ ሲናር ተንቀሣቀሱ።

የመጀመሪያዎቹን ሁለት የበረሃ ንነት ሰፈሮች በቀላሉ ደረሱ። በሦስተኛው የበረሃ ንነት መንደር ሲደርሱ የቅፍለቱ መሪ ቤላክ፣በጣም ተጨንቆ፣ ዱ ሮውሌን ለማግኘትና ለማነጋገር መጣ። ሦስት ግመል ነጂዎች ጉዟቸውን ለመቀጠል አሻፈረኝ ብለዋል። ለዚህም

ምክንያታቸውን ለመግለፅ አልፈቀዱም። የየበረሃው ገነት ነዋሪዎች ሊገለፅ የማይችል እምነት ማጣት በነጮች ላይ እያሣዩ ነው። እነዚህ ሕዝቦች፣ ነጭ ነጋዴዎች በወሰጣቸው እየተዘዋወሩ ሊነግዱና ከነርሱ ጋር ሊሠሩ ያውቃሉ። ከሠራተኞቹ አንዱ የሆነ፣አንድ ወደል የዳልማቲያ ጉሪምላ፣ እንደአጋጣሚ ሆኖ የአሥራ ሁለት ዓመት ዕድሜ የሚሆናትን ኮረዳ ሰውነት በጣም እንደተላመዳት አይነት እጅቹን በማሣረፍ አሻሽታታል። ልጅቷ አፍንጫዋ በንፍጥ የተሰቀሰቀ፣ ባዶ እግሯን ያለች ጮሌ ስትሆን ተወላጁ ህዝብ ክብሯ በመነካቱ ተደፈርን በሚል ስሜት በተጋነነ ቅናት ለመከራከረ ተነሣ። ሁኔታውን ለማለሣለስና ለማብረድ ሲል፣ ዱ ሮውሌ ለዚህች ተደፈርኩ ላለች የፊጠራ ሰው፣ የሼኒሲያውያንን የመስተዋት ሃብል ይሰጣታል። ለአባቷም ያረጁ ጫማዎችን ይሰጣል። ይሁንና እነዚህ ያልስለጠኑ ሕዝቦች በዚህ የረኩ አይመስልም። የሚታየው አጠቃላይ ጥረት ሁሉ ሙሉ በሙሉ ስምምነት የማይታይበትና የአካባቢውን ጉሣ የጥላቻ ስሜት የሚያመላክት ሆነ። ይህ ሁሉ፣ ጉብኚዎች በሚያደርጉት የተሰየና ያልተሰመደ ችሮታ ሳቢያ ነው ሲል ሩሚላክ አሰበ።

በሚቀጥለው ሠፈር የተሻለ አቀባበል እናገኛለን በሚል ተስፋ ይህኛውን መንደር ትተው ወጡ። ይሁን እንጂ ወደ ሲናር በተጓዙ ቁጥር ሁኔታዎች ከዕለት ዕለት እየተበላሹ ሄዱ። በየደረሱበት ሁሉ፣ ፀጥታ የሚታይበት የጥላቻ ስሜት ያለው የሕዝብ ስብሰብ አለ። እንደ ዕድል ሆኖ ግን፣ንጉሡ ፣የሕዝቦቹን የቀዘቀዘ የአቀባበል ስሜት ለመቀየር ሲል ያሰቡትን ሃሳፊነት በልዩ ሁኔታ ተወጣው። መንገደኞቹን በመጀመሪያው ዕለት አብረውት እራት እንዲበሉ ጋበዛቸው። ምንም እንኳ ለቅመማ ቅመማትና ቅባት ለበዛበት ምግብ ጥሩ ፍላጉት ባይኖራቸውም፣ ዱ ሮውሌ፣ ሩሚላክና ባለስልጣናች ናቸው የተባሉ ሌሎች ሁለት ሰዎች በግብጣው ላይ ተገኙ። ፍሬሌቲ ታምሜአለሁ በሚል የማስመሰያ ሰበብ፣ ካምፕ አጠብቃለሁ ብሎ ቀረ። ፈረንሣውያኑ፣ ሁሉም ሰው የሚያውቀውንና የሚቀበለውን ባህል ቢከተሉም፣በየኪሶቻቸው ውስጥ ትናንሽ ብልቃጦች ይዘዋል። ከነዚሁ ብልቃጦቻቸው መጠጦቻቸውን ይጉነጫሉ። የአራት ግብጣው በሚጠናቀቅበት ጊዜ እነዚህ ተጋባዦች በሚገባ ሞቅ ብሏቸው ነበር። ይህን የመሰለ ሞቅ ያለ ስሜታቸው ምን እንደሆነ ንጉሡ የማያውቅ መስሎም ተሰማቸው። ይህም ንጉሡን የታወረ አድርጎ የመገመት ያህል ነው። በርግጥ ንጉሡም እንደክብሩ ምንም ያላስተዋለ መሰለ። ሌላው ቀርቶ የቀድሞው ወታደር፣ በተከታይ አሽከሩ ረዥም ጀለቢያ ኪስ ውስጥ እጁን ሲሰድድ፣ እንዲህ ባለ ረዥም ካባ ውስጥ ምን ሊፈስግ እንደሚችል እንኳ እንዳላየ ሆነ። በመጨረሻም ወደቅፍለታቸው ሰፈር ተመለሱ።

ማረፊያቸውም ከከተማዋ መግቢያ በአንዱ አጠገብ ተደርጉላቸው ነበር። እነዚህ ሰዎች ደስ እንዳላቸው ሰዎች ሆነው ወደየመኝታቸው ሄዱ። በዚያም ዝናና ሃብት ሲያልሙ አደሩ።

በሚቀጥለው ቀን በነርሱ ላይ የተቀሰቀሰው ጥላቻና ተቃውሞ ከመቼውም በበለጠ እየጐላ መጣ። ከሰዎቹ መሃል ሁለቱ በከተማው ውስጥ እየተዘዋወሩ ላሉ ድንጋይ ተወርውሮባቸዋል። በየገበያው ስፍራ ለመሸጥ የሞከሯቸው ሽቀጣ ሽቀጦች ከአውሮፓ የሚመጣ ማንኛውም ነገር መጥፎ ዕድል ይዞ የሚመጣ ይመስል ተቀባይ አጡ።

ዱ ሮውሌ በበኩሉ ተቀባይነት የማግኘታቸውን ዕድል በተገቢ አክብሮት ለመቀበል ከሚፈቅዱ ሰዎች ማለትም፣ ከንጉሡና በዙሪያው ከሚገኙ መኳንንቱ ጋር ለማጠናከር ወሰነ። ባሰፈው ምሽት ለአገሪቱ የበላይ መሪ ካቀረበው የገፀ በረከት ስጦታ በተጨማሪ፣ ልዕልቲቱንና ከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን ወይዛዝርቶችዋን ከአውሮፓ ባመጣቸው ማራኪ ቁሣቁሶች ማስደሰት እንደሚፈልግና ዕድል ቢሰጠው ይህ ለርሱ ከፍተኛ ክብር እንደሚሆን መልዕክት ላከ። በማግስቱም አንድ ደርዘን ያህል የሚቆጠሩ ሴቶች ከቤተመንግስቱ መጡ። ይሁን እንጂ፣ ንግስቲቱ በመጀመሪያው ቀን ላለመታየት ፈልጋ ነበር። እነዚህ ግዙፍ ኑቢያውያን ሴቶች፣ ቀለመ ደማቅ አይነ ርግቦቻቸውን እንዳደረጉና ፊቶቻቸውን ሳይሸፍኑ በነፃነት ደብረክ ደብረክ ሲሉ በማየቱ ሩሚላክ በሰቅ ፈነዳ።

ከመጀመሪያው ጀምሮ ለእንግዶቹ ፈገግ ብሎ «ምን አይነቶቹ ያስፈበትን ፋሽን የሚለብሱ ማስጠሉዎች ናቸው?» ሲል ዱ ሮውሌ በፈረንሳይኛ ነገረው።«እባካችሁ ወይዛዝርት ወደ ውስጥ ዝለቁና የልዕልታት ምርጫዎች የሆኑትን፣ የተከበሩ የቫሲየሬ ወይዛዝርት የሚወዷቸውን ተመለከቱ»

ራሷ ላይ ሁለት አጫጭር ጉንጉን ያለባት፣ የምታነክስ ወፍራም ሴት ላይ ጣቱን አመለከተ።

«ውድ ፍራንቾይዝ ዳውቢኜ እኒሁና። እባክዎ ማዳም ላ ማርኩይስ ይግቡ»

ሴትየዋ፣ ተስፋ የቆረጠ ፊት የሚታይባት አሮጊት ነበረች። በሰፈሩ ውስጥ ወዳሰው ትልቅ ድንኳን እንዲገቡ ካደረጋቸው በኋላ ዱ ሮውሌ፣ ቃል የገባቸውን ማስደሰቻ ማሳየት ጀመረ። ከነዚህም መካከል መልክን አጣምሞ የሚያሳየው የቬነስ መስተዋት ይገኝበታል።

መስተዋቶቹ ሁሉ በግድግዳው ዙሪያ ተሰቅለው ሳሉ፣ ወይዛዝሮቹ በድንኳኑ መሃል ነበሩ። መስተዋቶቹ የተሸፈኑባቸው ጨርቆች ሲነሱ፣ ወይዛዝሮቹ ንቅንቅ ሳይሉ፣ በየራሳቸው ስብስብ ቆዩ። ፈረንሳውያኑ ወንዶች፣ ወይዛዝሮቹ ገና የመልኮቻቸውን ነውበራቅ እንዳላዩ አመኑ። ዱ ሮውሌና ሩሚላክ እነዚህን አመቤቶች ተራ በተራ እየያዙና በፈረንሳይኛ እየቀሰዱ፣ ሴቶቹ የፊቶቻቸውን ምስል በቅርበት እንዲያዩ ያመጧቸዋል።

«ይህች ወይዘሮ፣ ራስዋን እንዲህ ሽንቃጣ ሆና ፈፅሞ አይታ አታውቅም፣ እየልኝ የኔን ቆንጆ! ሲያዩሽ የግመሰ ቅርፅ ነው ያለሽ ሁለመናሽ እግር ብቻ ሲሆን ጭንቅላትሽ የፍየል ነው»

«ነይ ጠጋ በይና ጎደኛሽን ተመልከቻት፣ እንዴት ክስታራ እንደሆነችም እያት። ከቁመትዋ መርዘም ይልቅ ወደጉን ትሰፋለች። እዚህ ያሉት ወንዶች ደግሞ እንደርስዋ ያሉትን ይመርጣሉ»

ዋናው አስተርጓሚ ፍሬሴቲ፣ ሴቶቹ የሚያትረመርሙበትን ምክንያት ስለተረዳ አይስቅም ነበር። ሴቶቹ፣ በነዚህ ምስሎቻቸው የደነገጡና የተገረሙ መሆናቸውን ተረድቷል። ሴቶቹ፣ ራሳቸውን ሲመለከቱ፣ የሚያስጠላ መልክ፣ የሰውነታቸው ቅርፅ ተወለጋግዶ፣ አካላቸው ወደ ርክሰ መንፈስ የተቀየረባቸው መስሎ ታያቸው። የአስልምና ሃይማኖት እየተነካ ባለበት አገር፣ የአስማትን ሥራ ህጋዊ ማድረግ ምትሃት ነው ተብሎ ብቻ የሚታሰብ ሳይሆን የከረረ ስሜት አለበት። ዱ ሮውሌ፣ ሲያሽሟጥጣቸው፣ ለነርሱ ይታያቸው የነበረው፣ ልክ የገሃነም በሮች በድንገት ተከፍተው፣ የተረገሙባቸውን ዘለዓለማዊ ሥቃይ እንዲመለከቱ የተደረጉ መስሏቸው፣ የወደፊቱ ዕጣ ፈንታቸው ታያቸው።

በመጀመሪያ እሪታዋን የለቀቀችው ወይዘሮ፣ ሰሌሎቹ ምልክት በመስጠት ተሰቀሰቻቸው። ከድንኳኑ ውስጥ በመውጣት ዓይነ ርግቦቻቸው ሩጫቸውን እንዳያሰናክሉባቸው ከፊቶቻቸው ላይ አያነሷቸው፣ አይኖቻቸውን ጦልጉሰው በነዚያ ሽለቆ በሚመስሉ የአግር መንገዶች እስከ ቤተመንግስቱ ድረስ እያለከለኩና ፖኩቶቻቸውና እሪታዎቻቸው ከኋላቸው ኒያስተጋቡባቸው ሮጡ።

ዱ ሮውሌ፣ ሁሉም ነገር ካለፈ በኋላ ነገሩን ተረድቶ፣ ሁሉም መሣሪያ እንዲያዘጋጅና የመከላከያ ቦታውን እንዲይዝ ትዕዛዝ ሰጠ። አሥር ደቂቃ ያህል የፍርሃት ፀጥታ ከሆነ በኋላ ጥቅጥቅ ያለ የሰዎች ክምችት በሶስት አቅጣጫ ሲመጣና ዝግ ያለው የአግር እርምጃቸውም የአቧራ ደመና ሲያስነሣ ተመለከቱ። እያንዳንዱ ፈረንሣላዊ ጠመንጃውን በመተከ

ያነጣጠረበትን ሰው ገደለ። ነገር ግን የወደቀውን ሰው የሚተካ ተጨማሪ ሰው ቦታውን እየሞላው፣ መጭው የውጭ ሃይል ለመፀለይ እንኳ ፋታና ጊዜ አሳገኘም። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ መላው የቅፍለቱ መንደር በአደጋ ጣዮቹ ቁጥጥር ሥር ሆነ። በኑቢያውያኑ እምነት፣ አንድን አስማተኛ በባዶ እጅ መግደል ርግማን ያስከትላል። በዚህ ሳቢያ የጦር አስረኞቹ ስቃይ በቀጥታ በስቅላት ተፈፅሞ ቢሆን ኖሮ ሊቀልል ከሚችለው በላይ ተራዘመ።

የንጉሡ ፈረሰኛ ጦር ሁሉም ነገር ካበቃ በኋላ ጣልቃ በመግባት፣ በቅፍለቱ ላይ ተጭነው የነበሩትን ንብረቶችና ግመሎችን በመያዝ ወደ ንጉሡ አመጣ። ንጉሡም፣ የዚያውኑ ዕለት ሰፓሻው ደብዳቤ ፃፈ። ጥርጥር በሌለው ሁኔታ፣ ካፑቺኖች የነዙት የተንኮል ወሬ፣ ተጓዦቹ ወደ አገሩ ከመግባታቸው በፊት መሠራጨቱን በማማረር ገለፀ። እርሱ ራሱ፣ ፈረንሣውያንን በተቻለው መጠን በትህትና ያስተናገደ ቢሆንም፣ ሕዝቡ ግን በመጨረሻ ላይ እንደያዛቸው ፃፈ። እንግዲህ ሕዝብ ተቆጥቶ ለግድያ ከወጣ፣ ንጉሡ ምን ሊያደርግ ይችላል? የሚል ትህትና ያለበት ጥያቄ ያዘለ ደብዳቤ ፃፈ።

10

ሁለቱ የባህር ሰላጤዎች በሚለያዩበት ቦታ ላይ በጀልባዋ ሰፊ ክፍል ውስጥ አዲስ ነፋስ ሽው አለ። ሸራዎቹ ተወጥረው ጀልባዋ ወደ ሲና በጥሩ ፍጥነት ተጉዛፈች። የተራራው ቀይ አፈር አናት፣ ከግራጫው ሰማያዊ የሚያዘያ ወር ሰማይ አንፃር ከፍ ብሎ አድጓል። ጆን ባፕቲስት በፊቱና በእጆቹ ላይ የባህሩ ሃይለኛ ጣዕም ነበረው። በሰውነቱ ላይ የተረጨው ውሃ የጨው መስመር ምልክቶችን በመተው ፀሐይዋ አደረቀችው።

ሁሉም ነገር ማብቂያና መነሻ እየሆነ ነው። ወደ አቢሲኒያ የተጓቀሳቀሱት ሦስቱም ተልዕኮዎች ተገትተዋል። አሊስም፣ አሁን በእይታ ውስጥ ባለው ተራራ ትከሻ ላይ ሆና ትጠብቀዋለች። ከእንግዲህ በኋላም ርግጠኝነት የሌለባቸው ብዙ ነገሮች ስላሉ፣ ጆን ባፕቲስት ወደፊት ስላለው ሁኔታ ይጨነቃል። በርግጥ ከእስከ አሁኑ የበለጠ አስደናቂ ነገር በልቡ ውስጥ አያስብም። የተናወጠው ነፋስና ማዕበል የወረወረው ውሃ፣ በአስገራሚው የባህሩ ወለል ላይ ሲሳተሙ የሚያሣዩትን ስላማዊ ትርኢት መላ አካሱ ሲሰማው፣ የሰውን ዕድል ፈንታና ሁኔታ የሚወክሉ ይመስላሉ። ይህን ትርዒት ጆን ባፕቲስት በተደበላለቀና ተቃውሞ በሌለው ምርኮ፣ ልክ በገደል ጠርዝ ላይ ቆሞ በመጨረሻው ሰዓት ላይ ከሚያፈቅራት ሴት ጋር ዳግም የሚዋሀድበትን ጊዜ እንደሚጠብቅ ሰው በርጋታ ተመለከተው።

በፀሃይና በጨው፣ ቀለሙ ለቅቆ በወየበው የመርከብ ወለል ላይ፣ አረባውያኑ መርከበኞች ባዶ እግራቸውን በዙሪያው ቆሙ። ረዣዥሞቹ ሸሚዞቻቸው በንፋሱ ይውለበለባሉ። መርከበኞቹ ሙቀት በማግኘታቸውና ጀልባቸውንም በሰላም ወደ አገራቸው መልሰው ማምጣት በመቻላቸው ደስተኞች ነበሩ። ተራራውን ፊት ለፊታቸው እንደተገተረ እንደ አንድ ትልቅ ተራ ነገር ተመለከቱት።

እንደነርሱ ለመሆን እንሞክር ሲል፣ ጆን ባፕቲስት ለራሱ ተናገረ። ሊሰማን የሚገባው፣ እየሆነ ያለው ብቻ እንጂ፣ አዕምሯችንን በሰላም ላይ ማስታጠቅ የለብንም።

እኩለ ቀን ሊሆን ሲል፣ አል ቱር ወደብ ደርሰው ወረዱ። ጆን ባፕቲስት፣ የአውሮፖዊ ልብሶቹን በከረጢት ውስጥ አድርጐ እንደ አረቦች ለበሰ። የቻርትራሱ መስፍን የሰጡትን አስር ሴኩንስ ሊሆን የሚችል ትንሽ ወርቅ እስክአሁን ስላለው፣ አንድ ያረጀና በግላሱ ውስጥ ጭዳ

ወጥቶ የሚታይበት ኮርቻ ከአንድ በቅሎ ጋር መግዛት ይችል ነበር። በአንድ እጁ የአጋሰሱን ጉን መታ መታ የሚያደርግበት እርፖሜ በሌላው እጁ የእንሰላውን አቅጣጫ የሚቆጣጠርበትን የልጓም ገመድ ይዞ በአብዛኛው በውሃ ወደተከበበው አገር ሄደ።

በዚህኛው የባህር ጠረፍ ቦታ ላይ፣ የሲና ተራራ ከወደሚዳው እጅግ ቀስ እያለ የሚያድግ በመሆኑ መንገደኛ ሰው ወደ ተራራው ሰንሰለት በዝግታ እየወጣ ሊገዝበት ይችላል። ምድረበዳው፣ ከወደቡ የመጨረሻው የአትክልት ሥፍራ በኋላ ወዲያውኑ ይጀምራል። ምድሩ፣ ሁሉም ነገረ የተሰያየበት የአሸዋ ምድረ በዳ ሳይሆን፣ ይልቁንም እርቃኑን ባለ የምድር ገፅ ላይ ድንጋዮች በቁጥኝ ላይ የተገተሩበት ነው። ሲመለከቱት፣ እጅግ ሰፊና ገላጣ በሆነ ቦታ ላይ፣ በማይበከለው ማዕድኑ የሚታይ የሐውልቶች ፍርስራሽ መስሎ፣ ከራሱ ዘለዓለማዊና የተወሰነ መኖር በስተቀር የሌሎችን መኖር የሚያከስስ ይመስላል። ከአረቢያ ፔትራኤ እምብርት በሚጥመለመል የአውሎ ነፋስ ሃይል ተገፍቶ የመጣው የነጭ አፈር ንብርብር፣ አይን የሚያርፍበትን ሁሉ የሸፈነ ስለሆነ፣ የመጨረሻው አገልጋይ ለቅቆ ከሄደ በኋላ የሚታይ የቤተመንግሰት ሁኔታ በሃሣብ ውስጥ ይመጣል። ዘመን ከቶም ሊያከሰምነው ስላልቻለ፣ ይልቁንም መለኩታዊ የጊዜ መቀመሪያ፣ ውብ የአሸዋ ዱቄቱን ያፈሰሰበት ይመስላል።

ጆን ባፕቲስት፣ አንድም ሰው ሳያይ ሁለት ሰዓት ሙሉ በበቅሎው ሰገረ። ምሽቱ በጣም እየተቃረበ ነበር። በቅሎዋ በተቻለ መጠን ቀሪውን ርቀት እንድትፈጥንለት የሚችለውን ሁሉ ቢያደረግም ከንቱ ሆነበት። ምስኪኒቱ እንሰሳ የነበራት የአረማመድ ሁኔታ ሁለት ዓይነት ብቻ ነበር። አንደኛው ፍፁም መቆም ሲሆን ሁለተኛው የድንዛዜ ዓይነት ነበር። ከዚህ በኋላ ያለው መንገድ ሽቅብ እየተጠማዘዘ የሚያድግ፣ ጠቁሮ የሚታይ ገደል ነው። ጆን ባፕቲሰት ዳንቱን ወጥቶ ሲያጠናቅቅ ሰማዩ የጥቁር ቀለም መልክ ይዟል። ጥቁርቁር ያለ ቅርፅ የያዙት ቋጥኞች፣ በዚህ የሰማይ ቀለም ፊት እንደ ጭራቅ ተገትረዋል። የሲናን ተራራ ጫፍ በጠረቡት በሁለቱ ታላላቅ ሸለቆዎች መገናኛ ላይ፣ በጣም ተመሣሣይ በሆኑ ድንጋዮች መሃል አንድ የተጠረበ ቋጥኝ ተመለከተ። ይህ፣ አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለው የገዳሙ ግድግዳዎች ቁልል ቋጥኝ ነው።

የእነዚህን አመድማ ግድግዳዎች ወለል ሰንኖቀው ሽቅበ ያሰገጉ አሥራ ሁለት ክብ ማማዎች አሉ። የጦር ጫፍ የመሰሉት የቡተክርስቲያኑ ሁለት ጣሪያዎች ባይኖሩ ኖሮ በምድረበዳ ውስጥ ያሉ ምሽጐች ይመስላሉ። በጣም ቅርብ ቢሆንም፣ የመከላከያውን በሮች ለመድረስ ግን ከአንድ ሰዓት በላይ ይወስዳል። በዚህ የመከላከያ ቦታ ላይ ዘቦቹ ራሣቸው

መኰሣቱ ነበሩ። ሰውነታቸው እንደ ነሣ ትግል ታጋይ በሚገባ ፈርጥሞ የተገነባና ቁጥ ያሉ ስለታም ጕራዴዎቻቸውን በክባዎቻቸው ላይ ባሉት ሰፋፊ ቀበቶዎቻቸው ላይ የታጠቁ ሁሉት መኰሳት መንገደኛውን ካስቆሙት በኋላ፣ ስሙን ለገዳሙ አበምኔት ላኩ። መግባት እንደሚችል የሚፈቅደው መልስ ከመጣ በኋላ እንዲገባ ተደረገ።

በአጥሮቹ ውስጥ ያለው የቅድስት ካተረን ገዳም እንደአውነቱ ከሆነ አንድ ከተማ ነበር። በተከርስቲያኑ የሚገኘው መሣል ላይ ሲሆን ሌሎች ህንፃዎችና አዳራሾች፣ ተመሣሣይ መልክ ያላቸው መኖሪያዎችና ትናንሽ የፀሎት ቤቶች መጠነኛ ክፍተት በመሣላቸው እየተተመ ዙሪያውን ተገንብተዋል። የግድግዳዎች፣ የመንገዶችና ተራ የመተላለፊያ ጕዳናዎች በምስራቅ ሜዲተራኒያን ከተሞች የሚታዩትን ዓይነት ናቸው። እንደ መስቀል ጦር ተዋጊ፣ ስስና ወርቃማ የራስ ፀጉር ቀለም ያላቸው ወጣት መነኩሴ፣ ጆን ባፕቲስትን እየመሩት ወደ አበምኔቱ መኖሪያ ወሰዱት። መኩሴው፣ የጆን ባፕቲስትን ኻንጣ ሲይዙለት፣ በቅሎውን ግን በመግቢያው በር ላይ ከሚገኙት መነኮሣት ዘንድ እንዲተወው መከሩት።

የቅድስት ካተረን ገዳም የተመሠረተው በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ በጀስቲኒያውያን ነበር። ከዚያ እስክ ዛሬ ድረስ መቆየት የቻለው በነዚሁ አኖሮቹ ነው። ከዚህም በላይ ምናልባትም ሲወርድ ሲዋረድ በመጡት የሙሴ ዘሮች ዘንድ እጅግ ከፍተኛ ግምት ባላቸው በነዚህ የተቀደሱ ተራሮች መከላከያነት ይሆናል። በዚህ ቅድስተ ቅዱሣን ሥፍራ የሚኖሩት የአርቶዶክስ መነኮሣት፣ የሚመሩት በቀጥታ በኢየሩሣሌም ፓትርያርክ ሥልጣን ሥር ነው። ይሁን እንጂ ለአንድ የተለየ የሃይማኖት መስመር መሣሪያ ከመሆን በማለት፣ በገዳሙ የሚኖሩ መነኮሣት የራሣቸው የሆነና ራሣቸውንም የሚያስተዳድር ሥልጣን ያለው ጠባቂ በዚህ አስፈሪና ምስጢራዊ በሆነ ቦታ ላይ መሠረቱ። ወደዚህ ገዳም ሽሽተው የሚመጡና ከለላም የሚሹ ሰዎች፣ ከየትም ይምጡ ከየት ወይም ምንም ዓይነት ወንጀልም ፈፅመው ይምጡ፣ ደህንነታቸው የተረጋገጠ ነበር። ጥቂቶቹ በዚህ ቦታ ላይ ለአጭር ጊዜ ሲሰንብቱበት፣ ሌሎች ብዙዎች ደግሞ በቋሚነት ስለሚቀሩ፣ የኗሪው ቁጥር እንዲያድግ አድርገዋል። ከብዙ ጊዜ ሃይማኖታዊ የደረጃ ዕድገት በኋላ ከዚህ ሰዎች አንዳንዶቹ የገዳሙን ማህበረሰብ ለመምራት ጭምር ተሰፋ ይኖራቸው ነበር።

በገዳሙ አበምኔት መኖሪያ ውስጥ የነበረው ሁኔታ፣ ጆን ባፕቲስት ከዚህ በፊት በመጀመሪያ ጉብኙቱ ወቅት ከሚያውቀው እጅግ አዲስና የተለየ ነበር። መኰሣቱ የሚነጋገሩት

እየተንሸካሸኩ ነበር። የብርጉድና የክርቤ ሽታ፣ የድንጋይ ንጣፍ፣ ባለባቸው መተላለፊያዎች በአየሩ ውስጥ ተበትኗል።

«የገዳማችን አስተዳዳሪ በጣም ታምመዋል» ሲሉ አበምኔቱ ለጆን ባፕቲስት ነገሩት። ከሶስት ሣምንት በፊት ቅዳሴ ሥርዓት ላይ እያሉ ወድቀው ህሊናቸውን ስለሣቱ አንስተን ወስድናቸው። ይህ ሁኔታ ከገጠማቸው ወዲህ ቃላት አነጣጥመው ለመናገር ያቅታቸዋል። በምሽት የህመሙ ስቃይ ይበረታባቸዋል። ሲያቃስቱና አንዳንዴም ሲጮሁ እንሰማቸዋለን። ባልደረባህ የሚጠጣ መድሃኒት ስለሰጣቸው እፎይታን የሚሰጣቸው ቢሆንም እኛ ግን አስካሁን እንደተጨነቅን ነን»

ጆን ባፕቲስት የገዳሙን አሰቃ ለመመርመር እንዲችል ሃሣብ አቀረበ። ይሁን እንጂ ከዚህ አስቀድሞ ውስጡን ሲበላው የነበረ ጥያቄ ነበረው።

«ጓደኞቼ፣ ሜትር ዝረሚና ሁለቱ ሴቶች የት እንዳሉ ይንገሩኝ»

«ስለነርሱ አትጨነቅ።» አሉት አበምኔቱ። «እዚህ ከመጡ ሁለት ሣምንት አልፏቸዋል። አስካሁንም አንተኑ ነው የሚጠብቁህ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ግን ትናንትና የኛው ወንድሞች በተራራው ጫፍ ላይ ባንዷት አንዲት የፀሎት ቤት አጠገብ ሆነው የማለዳዋ ፀሐይ ስትወጣ ለማየት ሄዱ። እዚህ ምንም የሚሠራ ነገር ባለመኖሩ ሣይሰላቹ እንዳልቀሩ ነው። ወጣ እንዲሉ ሃሣቡን የሰጠኋቸው እኔ ስለነበርኩ አዝናለሁ። ይሁን እንጂ በማንኛውም ሁኔታ ነገ ጧት ተመልሰው እዚሁ ይደርሣሉ።»

ጆን ባፕቲስት ለጊዜው ተስፋ እንደመቁረጥ ካለው ቦኋላ፣ መልካም የዕረፍት ለሊት ሊያገኝ፣ ልብሶቹንም ለመቀየር እንደሚችል ሰራሱ በመንገር፣ በአካልና በአዕምሮ ብርታት አግኝቶ፣ በማግስቱ ጧት ሊያነሯቸው እንዲችል ለመሄድ ወሰነ።

የገዳሙ አበምኔት፣ ጆን ባፕቲስትን ወደ አስተዳዳሪው መኝታ ክፍል አስገቡት። የመኝታ ክፍሉ ሰፊ ሲሆን፣ ረገቸሞቹ መስኩቶቹ ለምለም ሣርና የደመል ቅርፅ ያላቸው አበቦች ፈንድተው ወደሚታዩበት ሰገነት ይከፈታሉ። በአንደኛው ግድግዳ ላይ የባቢሎንን ግንብ የሚወክል የሰጋጃ ጥልፍ ተሰቅሏል። የገዳሙ አስተዳዳሪ የጎድፍ ሥራ ባለሞያ ሆነው ደማስቆስ ውስጥ ለብዙ ዓመታት ኖረው ነበር። ነገር ግን ከባለቤታቸውና ከሁለት ወንዶች ልጆቻቸው ድንገተኛ ሞት ቦኋላ እግራቸው እንደመራቸው ወደፊት ተጉዘው የሲና ተራራን

ጐዳና ገቡበት። ሲና ከገቡ ወዲህ፣ ቅድስት ካተሪንን ለቅቀው ወጥተው አያውቁም። ከአስር ዓመት ባነሰ ጊዜም ውስጥ ከፍተኛው መሪዋ ለመሆን በቅተዋል። ጆን ባፕቲስት፣ ሲና ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በሰነበተበት ሰሞን እኒህ ሰው ገዳሙን ለማስፋፋት የሚያስችላቸውን ንድፍ ለማዘጋጀት የፕላን መሥሪያ ኮምፖሳቸውን፣ ማዕዘን ማውጫዎችንና ማስመሪያዎቻቸውን በመገልገል ላይ ነበሩ። በአንድ ጠርዝ አጠገብ የተቆለሉ የወረቀት ጥቅሎች ይታያሉ። እነዚህ ያለጥርጥር ያልተገደዱ ሥራዎቻቸው ይሆናሉ።

ምስኪኑ ሰው፣ ሊለዩ በማይችሉበት ደረጃ ከስተዋል። ፊታቸው እንቅልፍ በማጣትና በጭንቀት ተሸብሽቧል፣ ቆዳቸው እንደለም ገርጥቷል። አፋቸውም የስቃዩ መጠን ስላየለባቸው ተጣምሟል።

«ሁሉም ነገር ከመፈፀሙ በፊት በድጋሚ አንተን የማየት ዕድል ስላገኘሁ በጣም ደስ ብሎኛል» አሉት በመከራ።

አንዳች ቃል ለመተንፈስ አቅም የሌላቸውን ሰው የደረቀ እጅ፣ ጆን ባፕቲስት ጠበቅ አድርጐ ያዘ። ሽማግሌው ወዲያውኑ አሸለቡ። ዶክተሩ ከክፍሉ ውስጥ ሹልክ ብሎ ወጥቶ አበፃኤቱን አገኛቸው። ስቃዩን እያስታገሱላቸው ሊያቆዩዋቸው ብርቱ ተስፋ የነበራቸው ቢሆንም፣ መሞታቸው የማይቀር መሆኑን አረዳቸው።

«እጅግ የተለየ የሚሆነው ነገር» አሉ አበምኔቱ። «እርሳቸው ይህንንም ወይም ያኛውን ፈፅሞ አይፈሩም። ይበልጥ የምንጐዳው ግን እኛ ነን»

«እንደማስበው በሁለት ቀናት ውስጥ . . . »

አበምኔቱ የመስቀል ቅርፅ አመላክተው አማተቡ። እንባቸውንም ጠራርገው፣ ለጆን ባፕቲስት ወደ ተያዘለት ክፍል ይዘውት ሄዱ።



የፀሐይዋን አወጣጥ ከሚመለከቱበት የማረፊያ ቦታ ወርደው፣ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ሲሆን በመምጣት ላይ ሣሉ፣ ፍራንቸይዝና ገረሚ፣ ጆን ባፕቲስት ከገዳሙ ወጥቶ ሽቅብ ሲመጣ አገኙት። ሞቅ ባለ ሁኔታ አቅፈውት ሰላምታ ከሰጡት በኋላ ስለጉዞውና ስለአመጣጡ ጠየቁት። እርሱ ግን ስለአሊስ ተጨንቆ ነበር።

«ሰዋቂት ወደ ኋላ ቀረት ብላ ነው። ለአጭር ጊዜ ያህል ብቻዋን መሆን ስለፈለገች ነው። ከዚህ ብዙም በማይርቀው ከቤተመቅደሱ ባሻገር፣ በትልቁ ማህበረሰብ መሬት ላይ ታገኛታለህ» አሉቸው ፍራንቸይዝ።

እነርሱን ትቶ በመሄዱ ይቅርታ ጠይቆ፣ ጆን ባፕቲስት የአግር መንገዱን ተከትሎ ሽቅብ ቀጠለ። ጊዜው ሞቃት ስለነበረ ጃኬቱን አውልቆ ትከሻው ላይ አደረገው። አነስተኛዋ ቅድስተ ቅዱሳን በመንገድ መጠማዘዣ አጠገብ በድንገት ታየች። ቤተክርስቲያኗ ተራ የድንጋይ ጉጆ ናት። ጣሪያዋም በቅርፅ የለሽ የድንጋይ ቁርጥራጮች የተሠራ ነው። መከማቱ፣ ሌላው ቀርቶ የመስቀል ቅርፅ እንኳ በላይዋ ላይ አሳቆመም። ይህን ያደረጉት የተለያየ እምነት ኖሯቸው ሃማባቸውን ሰብስበ አድርገው ራሣቸውን መማዛት ለሚፈልጉ ጉብኚዎች ክላቸው አክብሮት የተነሣ ነው። ሕንፃውን፣ ከአንድ ባህረገብ መሬቱ ላይ ካለ ቋጥኝ ጋር የሚያገናኝ አነስተኛ ደልዳላ መሬት ሲኖር፣ ቀጥ ብሎ የሚታየው ቋጥኝ አንድ የተንጠለጠለ አካል ይመስላል። በዚህ ቦታ መሬቱ በሦስቱ ማዕዘኖቹ የሰመጠ ስለሆነ፣ የፀሐይዋን አወጣጥ ለማየት የሚጋርድ እንቅፋት የለም። በነዚህ የድንጋይ ቅርፆች መካከል ጆን ባፕቲስት፣ አሊስን ለይቶ አወቃት። ወይም መኖርዋን ተገነዘበ። እርስዋም ብትሆን እንደተመለከተቸው ተመሣሣይ ሃሣብ አድርባት ባለችበት ቆመች። ወደርስዋ ሮጠ። አሥር እምጃዎች ያህል ሲቀረው ሆን ብሎ ርምጃውን አንቀረፈፈው። ምን ያህል ተለውጣለች! ፊትዋ፣ ሰውነትዋና አቋቋምዋ በአጠቃላይ የጉመራ ነው። ውበትዋም ይበልጥ ያሸበረቀና የሚያበራ ሆኗል። የለበሰችው የፈረስ ግልቢያ ልብስ ነው። ጥብቅ በሚያደርጋት ጠባብ ልብስ የታሠረች አይደለችም። ፀጉርዋን ለቃዋለች። በርስዋ ላይ ከሚታየው የግርማ ሞገስ ድባብ ጋር ሲታይና ማንም ሊቆጣጠራት የማይችል መሆኑ ሲታወቅ፣ ይህ ሁሉ ነገር ኢምንት ነው። እርስዋም በበኩልዋ፣ እርሱ ባልነበረባቸው ጊዜያት፣ አብሯት ያኖረችውን የደከመ ቅርፅ፣ ይበልጥ የደቀቀ ሆኖ ሲታያት እንዳልነበረ ሁሉ፣ አሁን ብርቱና ሃያል ቁመናው ጐልቶ ወጣ። ብሩህ ዓይኖቹና ተዋህደው የሚታዩት የብርታትና የቁመና ዛላው የርሱን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ እንደነበረ አድርጐ አሣያት።

ሁሉም ነገር እንግዲህ ይኸው ነው። ሁሉም እንቅፋት ተሸንፏል። ጠጠራማ ከሆኑ አሥር እርምጃዎች ያህል ከሚሆን ስፋት በስተቀር ሁሉን የሚለያቸው አንዳችም ነገር የለም። የደምና የዘር ልዩነት፣ የአባቷ ተቃውሞ፣ የንጉሡ ግዴለሽነትና የብዙ ሰዎች ምቀኝነት፣ በአግራቸው ሥር ሆኖ ከሚንከባለለውና ቀልጦ ከቀዘቀዘው የእሣተ ገሞራ ፍርክስካሽ የበለጠ ጉዟቸውን ሊያደናቅፈው የሚችል አይደለም።

ለመነካካት በተቃረቡበት ጊዜ እርስ በእርሣቸውን በሃፍረት ተመለከቱ። እስከዚህ ሰዓት ድረስ ሁለቱም ያከናወኑት ተግባር፣ ራሳቸውን ለዕውነተኛና ፍፁም ትኩረትን ለሚሻው የመጀመሪያው ግንኙነታቸው መንገዱን ማዘጋጀት ነበር። በሙን የመተያየቱና ዓይን የመስበሩ አስቂኝ ጨዋታ አብቅቷል። ከዚህ በኋላ ሁለቱም ነፃ ናቸው። ሁለቱም አንዳቸው ሌላውን ሙሉ በሙሉ በነፃነት ለማየት ነፃ ነው። ከዚህ በኋላ አይን አፋርነትን አሸቀንጥረው በመጣል ምን መሆን እንደቻሉ ያያሉ።

አሊስ፣ እጇን በዘግታ ወደ ጆን ባፕቲስት ክንፈሮች አሰጠጋች። የጣቶችዋን ጫፎች ሳማቸው። እነዚህ ጣቶች ነፃ ስለነበሩ ደስታቸውን የድብብቆሽ የሚያደርጉበት ሁኔታ ከእንግዲህ በኋላ የለም። ወይም ደግሞ በችኮላ ምክንያት ንክኪያቸውን በማጣደፍ የሚሰጡትን ደስታ መቀነስ ከእንግዲህ በኋላ የለም።

ሰማየ ትሳልቅ የጥጥ ባዘቶ በመሰሉ ደመናዎች ተሞልቶ ፀጥታ የሰፈነበት ነው። ጆን ባፕቲስት፣ ጃኬቱን በአንድ ቋጥኝ ላይ ጥሎ አሊስን አቀፋት። ሁለቱም ነፃ ስለነበሩ ስሜታቸውንና መፈላለጋቸውን የሚገልፁበት አንዳችም ምክንያት የለም። ይህን ማድረጋቸው ደግሞ ተገቢም ነው። ተሣሣሙ። ከንፍሮቻቸው በፍቅር ተደጋስሰው፣ በጋራ ቀለጡ። በሕይወታቸው ውስጥ እንዲህ ባማረና ትክክለኛ በሆነ መልክ ለአፍታም ያህል እንኳ መደሰትን አስበው ስማያውቁ ጭምር፣ ስለዚህ ጉዳይ የሚነገር የለም።

አንዳቸው ሌላው ላይ ልጥፍ ብለው በመተቃቀፍ አየተራመዱና የመሣሣማቸውን ዕድገት መቋረጥ ለመቀጠል ቆም አያሉ፣ ማለዳውን በሙሉ በተራራው ላይ ቆዩ። ግዙፍ የጥቁር ድንጋይ ቋጥኞች፣ እንደ ታላቅ መፅሐፍ ገፆች እርስ በርሳቸው ተሰድረዋል። የተሰያዩ የምድሩ ገፅታዎችም በተከታታይ ልዩ ልዩ ስማያዊ ቀለማት ይታያሉ። ራቅ ብሎ ወደ ቀይ ባህር አካባቢ እነዚህ ቀለማት ወደ ሃምራዊ ጥላነት ያደላሉ። በምድር ላይ ከሲና ተራራ ከፍታ በበለጠ የተስታየ ቦታ የለም። ይህ የተራራ ከፍታ ከቀለጠው የምድር ማህፀን ውስጥ ተመዝዞ በመውጣት፣ በማዕበል በሚተራመሰውና በዝናብ ደመናዎች ተሸፍኖ በሚወራጨው አውሎ ነፋስ ተጠምዝዞ ሽቅብ የተመዘዘ ይመስላል። ፀጉራቸውን እንዲደበላለቅና በነፋሱ ሀይል እንዲውለበለብ በሚያደርገው በሞቃቱ ነፋስ ውስጥ ተንዘ።

«ምን አይነት አስማታም ቦታ ነው። እንዲያው እግዚአብሔር በማንኛውም ቅጽበት በደመና ውስጥ ሆኖ ሊመጣ የሚችልበት አካባቢ አይመስልም?» አለ ጆን ባፕቲስት

«እግዚአብሔር እዚህ እፊት ሰፊታችን ዱብ ቢል ምን ታደርጋለህ?» ስትል አሊስ እየሣቀች ጠየቀችው።

«ደግ፣ በመጀመሪያ አረፍ እንዲል አጠይቀዋለሁ። ያውም በዚህ ትልቅ ቋጥኝ ላይ፣ ምክንያቱም ሳስበው እጅግ በጣም የሸመገለና የደከመው ሰው አደርጌ ነው የማስበው»

«እና ከዚያስ?» በማለት በፍቅረኛዋ ግንባር ላይ የተሰጠፈውን ፀጉር ወደጐን እያነሳችለት።

«እና ከዚያም እንዲባርክን እጠይቀዋለሁ። ከዚያም ስለርሱና ስለኛ ሕይወት እንጨዋወታለን»

«እንበልና አሥርቱን ትዕዛዛት ቢሰጥህስ?»

«ሕይወት ባላቸው ፍጥረታት ሁሉ ዘንድ ተጽፈው መገኘታቸውን እነግረውና ደስታ ቢስነትን የሚያስከትሉት ቀሣውስትን፣ ነገስታትና አባቶችን ለማግኘት ካልሆነ በስተቀር በተለይ ለማንም እንዳይሰጥ አለምነዋለሁ።»

«ይህማ እጅግ በጣም ብልግናና ድፍረትም ይሆንብሃል። ስለዚህም የቁጣውን መብረቅ ሊልክብህ ይችላል»

«ለምን ይልክብኛል።» አለ ጂን ባፕቲስት እንደማዘን ብሎ «በርግጥ እግዚአብሔር እኮ ደስተኞችን ሰዎች የሚያፈቅር ነው»

እነዚህን ፍፁም የደስታ ሰዓታት፣ በየመካከሉ በሚኖሩ በማቅ በተሞሉ ጭውውቶችና የእርስ በርስ መደባበስ አሣለፉ።

የቁልቁሰቱን የእግር መንገድ ተስትለው ወደ ገዳሙ ሲመለሱ፣ ተለያይተው በቆዩባቸው ጊዜያት በነበሩት ሁኔታዎች ላይ በዝርዝር መነጋገር ጀመሩ። ይህን ርዕሰ ለረዥም ጊዜ ያህል ሊጨርሱት እንኳን አልቻሉም። ምስጢሩን ይዛ መቆየት ስላስጨነቃት፣ ራሲን ለሌላ ሰው ገልፃ መስጠቷን አውጥታ ልትነግረው ወሰነች። ማን እንደሆነና ለምንስ እንዳይረገች በአጭሩ ነገረችው።

«ታፈቅረዋለሽ?» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቃት

«ሀሳቤ ሁሉ አንተ ነበርክ። አንተን ማፍቀሬን ለአፍታ ያህል እንኳ አቋርጪ አላውቅም»

«እንዲህ ከሆነ ታዲያ ምን ይፈይዳል? እኔ ጌታሽ አይደለሁም። እንደዚህ እንዳንቺና እንደኔ ባለ አንድነት ላይ ግዴታዎች የሉም»

ለመናገር የፈለገውን ወይም የተመኘውን ሳይል፣ የበቀል ስሜቱን መወጣቱን በማስብ፣ ጆን ባኘቲስት በውስጡ ፈገግ አለ።

ገዳሙ ውስጥ ምሳቸውን ከፍራንቾይዝና ከሜትር ዣርሚ ጋር ተመገቡ። ደስታውን በጥሩ መንፈስ የተቀበለው ኻርቴስታንቱ የቀድሞው ፈገግታውንና ወሬኛነቱ ተመልሶለታል። ከእንግዲህ በኋላ ዋናው ቁም ነገር ወዴት ይሂዱ ነው። ምንም እንኳ በቅድስት ካተሪን ገዳም ጥላ ከለላ ውስጥ ቢሆኑም፣ አሁንም የሚገኙት በታሳቁ የቱርክ መሪ አገር ውስጥ ነው። በመሆኑም እነርሱን የመፈለጉ ጉዳይ መቀጠሉ እንደማይቀር እርግጥ ነው።

«ፍራንቾይዝና እኔ ወደፈረንሣይ እንሄዳለን» አለ ሜትር ዣርሚ

«ወደ ፈረንሣይ? ረሣህ እንዴ? አንተ እኮ ኻርቴስታንት ነህ»

«እኔ ከረሣሁም እነርሱ ያሰታውሱኛል» አለ ሜትር ዣርሚ እየሣቀ «ቁም ነገር እንጨዋወት። ከማህበረሰቡ ተገልሎ በዚህ በምስራቃዊ የዓለም ክፍል መኖር ይሻላል? ወይስ በራስ አገር መኖር ይሻላል? የሕሀይወት መራራው ክፍሉ ሁሉ ወደ መንከራተት ሕይወት እንደሚያመራ የምናነናዝብበት ዕድሜ ላይ ደርሰናል። ስለዚህ በምንም ዓይነት መልክ የሚያደርጉልንን አቀባበል እንቀበላለን»

በዚህ ጉዳይ ላይ ፍፁም አምነውና አቋምም ይዘው ስለነበረ፣ ጉዳዩን እንደገና እንዲያስቡበት የማስደረግ ተስፋ የለም። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ካይሮ ውስጥ ስለአሊስ መጠለፍ በመግለጽ ያናፈሰውን ወሬ ለማቀዝቀዝና ለማርገብ ሲሉ ሁለቱ ለአንድ ወር ያህል በገዳሙ ውስጥ በመቆየት ይስነብታሉ። ከዚያም ወደ ፖለስታይን በመሄድ ወደ ቆጵሮስ፣ ወደ ግሪክ፣ ወደ ቤነስና በመጨረሻም ፈረንሣይ የሚያደርሣቸውን መርከብ ይሣፈራሉ።

ሁለቱን በጥንካሬአቸው፣ በመንፈስ እርጋታቸው፣ በተሞክሯቸው ብርታትና ፍፁም ጥልቅ በሆነ ፍቅር መዋሀዳቸው ሲታይ፣ ለጋራ ፈቃዳቸው የማይዝ አንዳችም ነገር የሌለ ይመስላል።

አሊስ፣ ስለ አቢሲኒያ አብዝታ ታልማለች። ጆን ባኘቲስትም የማወቅ ፍላጐትዋን ይበልጥ በመቀስቀስ፣ ሰሰዓታት ስለአቢሲኒያ ያወራላታል። አጭር ጊዜም ቢሆን ወደዚያው ለመሄድ አቅደው ነበር። ይሁን እንጂ ለአንዳንድ ከአልቱር ለመጡ ባህረኞች ምስጋና

ይግባቸውና፣ ገዳሙ ውስጥ በሰነበቱበት ጊዜ ከሙራድ የተላከ ደብዳቤ ደርሷቸዋል። ሙራድ፣ ምጽዋ ደርሶ ተልዕኮውን ከዚያ ላይ አጠናቅቋል። በደብዳቤው ላይ ስለኢትዮጵያ አንዳንድ ዜና ገልያላቸዋል። ንጉሠ ነገስቱ እያሱ፣ ከጥቂት ወራት በፊት አርፈዋል። ምናልባትም ጆን ባኘቲስት እንደሚታመሙበት አውቆ በነገራቸው ሕመም ሳቢያ ሳይሆን አይቀርም። በካሀናቱ ተጽዕኖ ሥር ያደገው ልጃቸው ሰውጭ አገር ሰዎች መጥፎ አመለካከት አለው። ሌላው ቀርቶ ሙራድም እንኳ ወደዚያው ተመልሶ በመሄድ ስለተልዕኮው ሪፖርት የማቅረቡን ሀሣብ ፊጽሞ ትቶታል። ከዚህ ይልቅ ወደ አሌፖ ወይም ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ እንደወጉ ቤት እየሠራ ካይሮ ውስጥ በሚኖሩ ፈረንሳውያን አጠገብ የመኖር ዕድሉን ለመሞከር መርጧል።

ከሙራድ ዘንድ የመጣው ዜና፣ ከአደጋ ሊጠብቃቸው ስሚችሉትና በከፊል ጆን ባኘቲስት፣ ለንጉሠ ነገስቱ በነበረው ወዳጅነት ተነሳስቶ ሊያደርገው አስቦት የነበረውን ጉዞ እንዳይሞክረው የሚመክር ነበር። የውጭ አገር ሰዎች በዚያች አገር ጉዳይ ጨርሶ ጣልቃ እንዳይገቡ እጥብቆ ያስብ የነበረው ጆን ባኘቲስት፣ አሁን አሁን ምዕራቡና ምዕራባዊያኑ ያልተሳተፉበትን፣ አቢሲኒያ የራሷን ታሪክዊ ፈለግ መከተሏ የሚያሳዝነው ሊሆን አልቻለም።

በዚህ የተነሳ ፍራንቾይዝና ሜትር ዣርሚን በማጅብ ወደ ሰሜን እስከ ኤክሬ ድረስ ለመንገዝ ወሰኑ። ከዚያ በኋላ የየራሣቸውን ምርጫ ያደርጋሉ።

የገዳሙ አስተዳዳሪ ህመም እየጠናባቸው ሄዶ ከአንድ ሣምንት በኋላ አረፉ። ቀብራቸውም በብርታትና በፍቅር ስሜት ተከናወነ። መነኩሳቱም የሚተኪቸውን ሰው መረጡ። አሊስና ጆን ባኘቲስትም ወደ ተራራው የሚያደርጉትን ረዥም ጉዞ ልምድ እያደረጉት መጡ። ነገር ግን በገዳሙ ውስጥ በሚገኙት ስርንጉጥ የጨለማ መንገዶችም ውስጥ መሸጉሸት ሲልና ቀኑን አንቆ የያዘው ሙቀት ቀዝቀዝ ሲል፣ ከቤተክርስቲያኑ በስተምስራቅ በኩል የሚገኘውንና የሚወዱትን አንድ አነስተኛ የዕረፍት ቦታ ለመዱት። ይህ ቦታ በሚያስገርም መልኩ ሁል ጊዜም ባዶ ሆኖ ቢታይም ማንም የማያስተውላትና ከማንም ምንም አይነት እንክብካቤ የማታገኝ ቁጥቋጦ በቅላቢታለች። ከዚህም በላይ ይህ ቦታ የገዳሙ የህልውና መሠረት ነው። የሕንፃው የተቀደሰና ዓብይ ነገር ሁሉ የሚሸከረከርበትም ነው። ይሁን እንጂ ይህቺ ተክል በመጀመሪያ በተገናኙበት ቦታ ላይ ከነበረችው ወይም ደግሞ ጆን ባኘቲስት አል ዋህ አጠገብ ካገኛት ተክል ጋር ተመሣሣይ ዝርያ ያላት አይደለችም። በመጠኑም ቢሆን ሁለቱንም ቅር ቢያሰኛቸውም፣ እንደተነገራቸው ግን ይህች አየነደደች ያለች የምትመስለው ቁጥቋጦ እውነተኛዋ ዕፀ ሙሴ ነበረች።

ተጨማሪ መረጃ

ጆን ባፕቲስት፣ ከፕሮቴስታንት አማኒያን ጋር በፈረንሣይ ፕሮቬንስ ውስጥ መገናኘቱን ከሰማበት ዕለት አንስቶ ሜትር ዝረሚ የሚያልመው ሌላ ምንም ነገር ሳይሆን እነዚሁኑ አማኒያን መቀላቀል ነበር። ሁለቱም ፈረንሣይ እንደገቡ በተቀማጭ ገንዘባቸው አንዲት አነስተኛ ሆቴል ወዲያውኑ ተከራዩ። እርስዋ የካቶሊክ እምነት ተከታይ ስለነበረች ማንም የተቃወመ አልነበረም። ቀን ቀን ይህችው አነስተኛ ሆቴል ለመንገደኞች፣ ከአገር ቤት ለሚመጡ ባላገሮችና ለወታደሮች የመጠጥ ሽያጭ አገልግሎት ትሰጣለች። ሲመሽ ደግሞ ሜትር ዝረሚ ከተቀላቀላቸው አድመኞች ጋር ከተራራው ወርዶ ይመጣል። ስድስት ወር ባልሞላው ጊዜ ውስጥ አማኒያኑ ግልፅና አደገኛ የርስ በርስ ጦርነት በክልሉ ቀሰቀሱ። እነዚህን በታሪክ «ቀምጣ ለባሽ» ሆነው ብቅ ያሉትን ሽፍታዎች ለማሸነፍ፣ በማርሻል ዱ ቬላርስ የሚመራ ሠራዊት በሙሉ አሰፈልጉ ነበር። ሜትር ዝረሚ በጓደኞቹ ዘንድ ራቭኔል ተብሎ ሲታወቅ ከመሪዎቻቸው አንዱ ነበር። ሕዝባዊው አመፅ ከተደመሰሰ በኋላ ዝረሚ ለማምለጥ ሲችል ፍራንቾይዝም ተከተለችው። የሁለቱ ሰዎች ዱካ እዚህ ላይ ጠፋብን። ይሁን እንጂ ኢንግላንድ ውስጥ ጥገኝነት የማግኘታቸው ምልክት ነገር ነበር።

ጆን ባፕቲስት፣ አክሬ ውስጥ የአገሪቱን ታዋቂ ሃብታሞች በማከም በቂ ገንዘብ አግኝቶ ወደ ሲሪያ ተሻገረ። ከአሊስ ጋር ወደ ፖልሚራ ሄደው፣ ከዚያም ምድረ በዳውን ሁሉ አቋርጠው፣ በኢፍራጠስ አካባቢ ባለ ረግረጋማ አገር ደረሱ። ከዚያም ወደ ፋርስ በመሄድ በዚያ ያለስጋት ኖሩ። ይሀን ሁሉ አገር ሲጓዙ መንፈሳቸው እንደመራቸውና እነርሱም ደስ እንዳላቸው ነበር። ኢሰፋሃን ውስጥ ጆን ባፕቲስት የተሰመደውን ጥበቡን በመቀጠል ዝነኛ ስኬት አግኝቶ ነበር። ፋርሳውያንና የውጭ አገር ኒጋዴዎች በሙሉ፣ ዲፕሎማቶች፣ የሕዝብ መሪዎችና ሌላው ቀርቶ የከተማዎቹ ቁጡዎቹ ኢማሞች ሳይቀሩ የበኒንትን ጉዳይ በተመለከተ ያማክሩት ነበር። በአጭር ጊዜ ውስጥ በሰማያዊው መስጊድ አጠገብ አንድ ትልቅ ቤት ለመግዛት በቂ ወርቅ አገኘ። በዚህ ቦታ የአየር ጠባዩም ሁሉንም አይነት ተክል ለማብቀልና ለማሣደግ ተስማሚ ነበር። በሕክምና የአትክልት ሥፍራው ውስጥ በጉዞዎቹ ዘመናት ሰለበስባቸው የነበሩትን የተክሎች ፍሬዎች አበቀላቸው። አሊስ፣ ጽጌረዳዎችን ማሳደግ ጀመረች። ከዚህ ቦታ ወደ ሌላ መሄድ ፈፅሞ አልፈለጉም።

ሱዊስ 14ኛ ሲሞቱ፣ የኦርሊያንስን መስፍን እንደራሴ መሆን ቆይተው ሰሙ። እኒህ መስፍን የቻርትሬስ ገዥ ማሉ ጆን ባፕቲስት አግኝቷቸው ነበር። ጆን ባፕቲስት ሰዓፈላቸው ደብዳቤ፣ እንደራሴው፣ ፖንሴ፣ ፖሪስን ቢጉበኝ አጅግ የሚደሰቱ መሆናቸውን የሚገልፅ በራሣቸው እጅ ጽፈው መልስ ላከሉት። ጆን ባፕቲስት ይህን መልዕክት ከአሊስ ጋር ተመካክረበት። በመጨረሻም የሚወዷቸውን ተራሮችና ዕጌሬዳዎቻቸውን ላለመተው ወሰኑ።

አቪሲኒያን በተመለከ፣ ኩዱ ሮውሌ ሞት በኋላ እጅግ ለረዥም ጊዜ ባለማቋረጥ በስፋት ሲነገርና፣ ከጀስዊቶች አሣዛኝ ውድቀትና ከካፑቺኖች ከአገር መባረር በኋላ፣ ለአንድ ተኩል ምዕተ ዓመት ያህል አገሪቱ ከማንኛውም ዓይነት የውጭ አገር ወረራ ተጠብቃ ቆይታለች። ይህም ሲባል ጥቂት በእንግሊዛውያን የጂአግራፊ ሊቃውንት የተደረጉት ሰላማዊ ጉዞዎች ሳይዘነጉ ነው። ከአሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያውም የስዊዝ ካናል ከተጠናቀቀ በኋላ፣ የቅኝ ገዥዎች መስገብገብ እንደገና ወደ ቀይ ባህር አቅጣጫ ዞረ። አቢሲኒያም አንድ ጊዜ ፖንሴ ያስጠነቀቃትን የአነዚህን ሃይሎች እንደገና መመለስ ተመለከተች። ይህ ሲሆን የቻለው ምናልባትም አገሪቱ፣ ነባሩ እምነትዋ፣ ራስዋን በራስዋ የመምራትዋና ባህልዋ እነዚህን ሃይሎች ለመቋቋም የሚችል ስለሆነ ይሆናል።

በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ፣ በኢጣሊያ ኤርትራ ዜና ታሪክ ውስጥ፣ ፖንሴ የሚለው ስም እንደገና ብቅ ይላል። ይህኛውም ፖንሴ፣ አስመራ ውስጥ መድሃኒት ቀማሚ ነበር። ምናልባትም ከአሊስና ከጆን ባፕቲስት አራት ልጆች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ሊሆን ይችላል። ልክ በደስታ ስለኖሩ ሰዎች ብዙም ሳይታወቅ እንደሚቀር ሁሉ፣ ይህን የሚያፈርስ ታሪክ የለም። በርግጥም የሚያረጋግጠውም መረጃ የለም። ደስተኞች ኖረዋል። ደስታቸውም ታሪክ ይሆናል።